# የኢትዮጵያ የ5 ሺ ዓመት ታሪክ

## ከኖኅ እስከ ኢህአዴግ

**መጽሐፍ ፩**

ፍስሐ ያዜ ካሣ

2003
አዲስ አበባ

© መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው

የመጀመሪያ ሕትመት 2003 ዓ.ም.
ሁለተኛ ሕትመት 2004 ዓ.ም.
ሶስተኛ ሕትመት 2004 ዓ.ም.
አራተኛ ሕትመት 2005 ዓ.ም.

**መታሰቢያነቱ :-**

ለክቡር አቶ ተክለሃይማኖት መኩሪያ እና ለሌሎች ሳሉ ቀደምት ኢትዮጵያዊ የታሪክ ፀሐፍት፡፡

**ማስወሻነቱ፡-**

ለፍቅርተ ሁሴን አብዲ እና ለቤተሰቦቿ፤
እንዲሁም ለዳዊት እውቀ እና ለቤተሰቦቹ
ይሁንልኝ፡፡

**ምስጋና፡-**

ለወ/ሮ እታፈራሁ አበበ
እና
ለወ/ት አለምነሽ ታከለ
እንዲሁም አስቸጋሪውን የመተየብ ሥራ
ያለመታከት ላከናወነችው ለወ/ት ትዝታ ላቀው
ምስጋናዬንም አክብሮቴንም ገለጽኩ፡፡

ለአስተያየትዎ:- Fiseha Yaze@yahoo.com
Only text:- 0921797053

## ማውጫ

| | | |
|---|---|---|
| 1 | መግቢያ | 8 |
| 2 | መግባቢያ | 11 |
| 3 | ምዕራፍ 1 ኖኅ እና ኢትዮጵያ | 21 |
| 4 | ምዕራፍ 2<br>የነገደ ካም ዘመነ መንግስት ከ3500 እስከ 1985 ቅ.ል.ክ | 30 |
| 5 | ምዕራፍ 3<br>ኢትዮጵያና ባቢሎን | 34 |
| 6 | ምዕራፍ 4<br>አሮጌው ስልጣኔ ከኢትዮጵያ ወደ ግብፅ | 44 |
| 7 | ምዕራፍ 5<br>የአጋዝያን ዘመነ መንግስት | 55 |
| 8 | ምዕራፍ 6<br>የኢትዮጵያ ትክክለኛ መጠሪያ ስም | 70 |
| 9 | ምዕራፍ 7<br>የአክሱም ኢትዮጵያና የኑብያ ኢትዮጵያ ልዩነትና አንድነት | 79 |
| 10 | ምዕራፍ 8<br>ኢትዮጵያ በታላቁ መፅሃፍ | 82 |
| 11 | ምዕራፍ 9<br>የግብፅ ስልጣኔ | 85 |
| 12 | ምዕራፍ 10<br>የግብፅ ግዛት በኢትዮጵያ | 91 |
| 13 | ምዕራፍ 11<br>ከንግስተ ሣባ እስከ ንጉስ ባዚን የነበሩት የኢትዮጵያ ነገስታት ዝርዝር | 95 |
| 14 | ምዕራፍ 12<br>የንግስተ ሣባ ታሪክ | 99 |
| 15 | ምዕራፍ 13<br>የቀዳማዊ ምኒልክ ዘመነ መንግስት | 104 |
| 16 | ምዕራፍ 14<br>ከንጉስ ሐንድዮን እስከ ንጉስ ተዋስያ2ኛ | 108 |
| 17 | ምዕራፍ 15<br>የኢትዮጵያ ግዛት በግብፅ ላይ፤ በንጉስ ፒያንኪ 2ኛ ዘመነ መንግስት | 110 |
| 18 | ምዕራፍ 16<br>የአክሱማይ ወረደ ፀሐይእና የካስታህ ሐን ድዮን ዘመነ መንግስት | 118 |
| 19 | ምዕራፍ 17<br>የንጉስ ሻባካ ዘመነ መንግስት | 120 |
| 20 | ምዕራፍ 18 | 122 |

የንግስት ኒካንታ ህንዳኬ ዘመነ መንግስት
21 ምዕራፍ 19 123
የንጉስ ተሃርቃ ዘመነ መንግስት
22 ምዕራፍ 20 128
የንጉስ ታንታሙን ዘመነ መንግስት
23 ምዕራፍ 21 132
የመናገሻ ከተማ ለውጥ ከናፓታ ወደ መርዌ
24 ምዕራፍ 22 134
የንጉስ ናስቶሰኔን ዘመነ መንግስት
25 ምዕራፍ 23 136
የንጉስ ሐንዲው አብራ ዘመነ መንግስት
26 ምዕራፍ 24 140
የመርዌ መጻከም
27 ምዕራፍ 25 142
የአክሱም አነሳስና አመሠራረት
28 ምዕራፍ 26 151
የአክሱማውያን /የኢትዮጵያውያን/ የፊደል አመጣጥ
29 ምዕራፍ 27 155
የአክሱማውያን ቀደምት አምልኮና የክርስትና ወደ
ኢትዮጵያ መግባት
30 ምዕራፍ 28 159
የአክሱማውያን ገንዘቦችና በላያቸው ላይ የሰፈረው ጽሁፍ
31 ምዕራፍ 29 161
የንጉስ ዒዛና እና ሲዛና /የአብርሃ ወ አፅባሃ/ ዘመነ
መንግስት
32 ምዕራፍ 30 173
የንጉስ እለዓሚዳ ዘመነ መንግስት
33 ምዕራፍ 31 175
የአፄ ካሌብ ዘመነ መንግስት
34 ምዕራፍ 32 181
የአፄ ገብረመስቀል ዘመነ መንግስት
35 ምዕራፍ 34 187
የንጉስ አርማህ 2ኛ ዘመነ መንግስት
36 ምዕራፍ 33 189
የእስልምና መስፋፋት
37 ምዕራፍ 35 194
የዮዲት ጉዲት ዘመነ መንግስት
38 ምዕራፍ 36 198
አክሱምና በአካባቢዋ የሚገኙ ቅርሶች
39 ምዕራፍ 37 201
የዛግዌ ስርወ መንግስት አመሠራረትና የመስራቹ የንጉስ
መራ ተክለሐይማኖት ዘመነ መንግስት
40 ምዕራፍ 38 204
ከአፄ ጠጠውድም እስከ አፄ ይምርሐነ ክርስቶስ
41 ምዕራፍ 39 207
የቅዱስ ሐርቤ 2ኛ ዘመነ መንግስት
42 ምዕራፍ 40 210
የአፄ ላሊበላ ዘመነ መንግስት
43 ምዕራፍ 41 218
የስልጣን ሽግግር ከላስታ ወደ ሸዋ፤ በአፄ ነአኩቶለአብ
ዘመነ መንግስት
44 ምዕራፍ 42 222
የደቡብና የደቡብ ምስራቅ ማኅበረሰቦች
45 ምዕራፍ 43 224
የሸዋ ነገስታት
46 ምዕራፍ 44 228
የአፄ አምደጽዮን ዘመነ መንግስት
47 ምዕራፍ 45 239
የአፄ ሠይፈ አርዕድ ዘመነ መንግስት
48 ምዕራፍ 46 241
የአፄ ዳዊት ዘመነ መንግስት
49 ምዕራፍ 47 246
የአፄ ቴዎድሮስ 1ኛ ዘመነ መንግስት
50 ምዕራፍ 48 249
የአፄ ይስሐቅ ዘመነ መንግስት
51 ምዕራፍ 49 252
የአፄ ዘርዓያዕቆብ ዘመነ መንግስት
52 ምዕራፍ 50 264
የአፄ በእደ ማርያም ዘመነ መንግስት
53 ምዕራፍ 51 268
የአፄ እስክንድር ዘመነ መንግስት
54 ምዕራፍ 52 271
ቱርክ፣ ፖርቱጋልና ኢትዮጵያ
55 ምዕራፍ 53 274
የአፄ ናእድ ዘመነ መንግስት
56 ምዕራፍ 54 280
የአፄ ልብነድንግል ዘመነ መንግስት
57 ምዕራፍ 55 284
የግራኝ አህመድ የበላይነት

58 ምዕራፍ 56 291
የአፄ ገላውዴዎስ ዘመነ መንግስት
59 ምዕራፍ 57 299
የአፄ ሚናስ ዘመነ መንግስት

60 ምዕራፍ 58 302
የጎንደር ነገስታት ዘመን
61 ምዕራፍ 59 304
የአፄ ሠርፀድንግል ዘመነ መንግስት
62 ምዕራፍ 60 311
የአፄ ያዕቆብ ዘመነ መንግስት
63 ምዕራፍ 61 313
የአፄ ዘድንግል ዘመነ መንግስት
64 ምዕራፍ 62 315
የአፄ ሱስኒዮስ ዘመነ መንግስት
65 ምዕራፍ 63 319
የአፄ ፋሲል ዘመነ መንግስት
66 ምዕራፍ 64 332
የአፄ ዮሐንስ 1ኛ ዘመነ መንግስት
67 ምዕራፍ 65 336
የአፄ እያሱ 1ኛ ዘመነ መንግስት
68 ምዕራፍ 66 344
የአፄ /ርጉም/ ተክለሐይማኖት ዘመነ መንግስት
69 ምዕራፍ 67 348
የአፄ ቴዎፍሎስ ዘመነ መንግስት
70 ምዕራፍ 68 350
የአፄ ዮስጦስ ዘመነ መንግስት
71 ምዕራፍ 69 351
የአፄ ዳዊት 3ኛ ዘመነ መንግስት
72 ምዕራፍ 70 355
የአፄ በካፋ ዘመነ መንግስት
73 ምዕራፍ 71 357
የአፄ እያሱ 2ኛ ዘመነ መንግስት
74 ምዕራፍ 72 364
የአፄ ኢዮአስ ዘመነ መንግስት
75 ምዕራፍ 73 366
የአፄ ዮሐንስ 2ኛ ዘመነ መንግስት
76 ምዕራፍ 74 369
የአፄ ተክለሐይማኖት 2ኛ ዘመነ መንግስት
77 ምዕራፍ 75 371
የአፄ ሰሎሞን ዘመነ መንግስት

78 ምዕራፍ 76 372
የአፄ ተክለጊዎርጊስ ዘመነ መንግስት
79 ምዕራፍ 77 374
ዘመነ መሳፍንት፤ ከትልቁ ራስ ዓሊ እስከ ትንሹ ራስ ዓሊ
80 ምዕራፍ 78 376
የአፄ ቴዎድሮስ 2ኛ ዘመነ መንግስት
81 ምዕራፍ 79 401
የአፄ ተክለጊዎርጊስ 2ኛ ዘመነ መንግስት
82 ምዕራፍ 80 404
የአፄ ዮሐንስ 4ኛ ዘመነ መንግስት
83 ምዕራፍ 81 424
የአፄ ምኒልክ 2ኛ ዘመነ መንግስት
84 ዋቢ መፃሕፍት 454

## መግቢያ

ከሳይንሱ አንፃር የዓለምና የህዝቦቿ ታሪክ የሚጀምረው ከሚሊዮኖችና ከቢሊዮኖች አመታት በፊት ነው።

ከመንፈሣዊ ትንታኔ አንፃር ደግሞ የዓለምና የሠው ልጆች ታሪክ የሚጀምረው ከአዳም መፈጠር በኋላ ነው። ዘመኑም ከክርስቶስ ልደት በፊት 5500 ዓመት ተብሎ ይሰላል። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ እስከ ክርስቶስ መወለድ ድረስ ከላይ ወደታች ወደ ኋላ እየተቆጠረ ኖሮ፤ ከክርስቶስ ውልደት በኋላ ደግሞ እንደ አዲስ "አንድ" ተብሎ ወደፊት መቆጠር ጀምሮዋል። ስለዚህም በዚህ መፅሃፍ የተካተቱት ታሪኮች የሚታወሱትም ሆነ የሚያጠነጥኑት "የሠው ልጆች የፍጥረት መጀመሪያ አዳም ነው" በሚለው መነሻ ይሆናል።

ሣይንስ መነሻችን ሲነግረን ቢዳዳም መድረሻችን እስካሳጠቀን ድረስ ሁሉም ከጥያቄ አይድንም። ስለዚህ ሠው ከ"ዱዳሌብ አፈር፣ ከኮሬብ እሣት፣ ከአዜብ ነፋስና ከናጌብ ውሐ ተውጣጥቶ ተፈጠረ፤ ከፈጣሪው ነባቢነትን፣ ልባዊነትን፣ ህያውነትን አገኘ፣ የፍጥረታት የበላይ እንዲሆንም ተደረገ። ህግ ተሠጠው፣ ያንን ህግ ተላለፈ፣ ቅጣቱ ሞት ሆነ። "አፈር ነህና ወደ አፈር ትመለሣለህ ሞትንም ትሞታለህ.."ተባለ። ይሄው ዛሬ ድረስ እየሞትን ነው። ሳይንስ ሞትን እስኪያስቀር ድረስ የትኛውን መነሻ መምረጥ እንዳለብን መድረሻችን በራሡ ስለሚነግረን ብዙ ማለት አያስፈልገንም።

ምንም ቢሆን ግን የኢትዮጵያን ታሪክ በተመለከተ መፈናፈኛ የለም። በክርሠ ምድር ጥናት ቢባል በምን.. ያው የሠው ዘር መገኛነቷ የተረጋገጠ ነው።

ለማንኛውም ግን በዚህ መፅሃፍ የኢትዮጵያ ዘመን ሲቆጠር የ5844 አመታት እድሜ ያላት አገር ሆና ነው የምናገኘው። ይህም ሲባል የኢትዮጵያ ታሪክ ከ "ኖኅ" ስለሚጀምር ከክርስቶስ ልደት በፊት 3844፣ ከክርስቶስ ልደት በኋላ 2ሺ አመት ስላለ በድምሩ 5844 ዓመታት ይሆናል።

የዘመን አቆጣጠርን በተመለከተ ከወዲሁ ግልፅ መሆን ያለበት ጉዳይ አለ። "ዓመተ ዓለም" ሲባል ዓለም ከተፈጠረ ጊዜ ጀምሮ ወደ ኋላ እየተቆጠረ ሲመጣ ነው። ከክርስቶስ ልደት በፊት ሲባል ግን ከውልደቱ



ዋዜማ ተነስተን ወደ ላይ እየቆጠርን ስንሄድ የምንደርስበት ነው። ስለዚህ ዓ.ዓለምና ቅ.ል.ክ ሠፊ ልዩነት አላቸው። በጥንታዊ ታሪኮች ላይ በተደጋጋሚ በብዙዎች ዘንድ ውዝግብ ሲፈጥር እንደመኖሩ መጠን በአንድ ምሣሌ ገልፀነው እንለፍ።

ለምሳሌ በምድር ላይ የጥፋት ውሃ ሲደርስና ኖኅና ቤተሠቦቹ ብቻ የተረፉበት ዘመን ከክርስቶስ ልደት በፊት 3844 ላይ ነበር። ይህ በዓመተ ዓለም ሲሠላ 1656 ዓ.ዓለም ተብሎ ይገለፃል። በድምሩ 5500 አመት ይሆናል። ዓለም በተፈጠረ በ1656 ዓ.ዓ ላይ የጥፋት ውሃ ተከሠተ እንደማለት። ከዚሁ ጋር በተያያዘም "አንድ አመት" የሚባለው በጨረቃ አቆጣጠር 254 ቀናትን ስለሚሸፍንና በፀሃይ አቆጣጠር "አንድ አመት" 365 ቀናትን ስለሚሸፍን በተለይ የፀሐይ አቆጣጠሩ ግኝት ከሠው ልጆች አስኪመንጭ ድረስ የነበረው ጊዜ በመጠኑ ሲያወዛግብ ቢችል ቅር ልንሰኝ አይገባም። ያም ቢሆን ከክ.ል በፊት 3ሺ አመታት ቀደም በሚለው ታሪክ እንጂ ከዚያ በኋላ ባለው ጊዜ አያጋጥምም። ይህንኑም ቢሆን ለማስተካከል ተሞክሯል። በታሪኩ ውስጥ ከክ.ል በፊት እየተባለ ስለተገለፀም ብዙ ችግር አይኖርም። በዋናነት ቀድሞ መግለፅ ያስፈለገበት ምክንያት የሌሎች ፀሃፍትን የዘመን አገላለፅ እንደወረደ በምናይበት ጊዜ ግር እንዳይለን ነው። በተረፈ እንደተለመደው (እ. ኤ. አ) ከሚሉት በቀር ሌሎች ሁሉ በፀ አቆጣጠር ናቸው።

የኢትዮጵያን የብዙ ዘመንና ተዘርዝሮ የማያልቀውን ታሪካ በአንድ መፅሃፍ ብቻ መፈፀሙ አስገራሚ ሊመስል ይችላል። ምክንያቱ የአንድ ኢትዮጵያዊ ንጉሠ ነገስት ታሪክ እንኳን ብቻውን ከዚህ መፅሃፍ ገፆች በላይ እንደሚወስድ ይታወቃልና ነው። ቢሆንም የረዘመውን በማሣጠር፣ የተዘበራረቀውን በማደራጀት፣ የሚምታታውን አመሣክሮ በማስማማትና አሣማኝ ማስረጃ የተገኘለትን መርጦና አሣጥሮ ይዘቱን ሣይለቅ ለማቅረብ ተሞክሯል። ለነገሩ እንዲህ ለማለት የሚያስችል የመረጃ ክምር የለም። ቀደምት ፀሃፍትም ቢሆኑ የአንድ፣ የሁለት፣ የሦስት ሚሊኒየምን ታሪክ ሲፅፉ የነገስታቱን ስም ዝርዝርና የገዙበትን ዘመን አስፍሮ ከማለፍ ውጪ ዝርዝር ታሪኩን ለማተት የቻሉበት ሁኔታ በስፋት የለም። የመረጃ እጥረት ይገድባል። የዚህ መፅሐፍ ዓላማ ደግሞ በተቻለ መጠን ጎደለውን መሙላት፣ ሊፈርስ የተቃረበውን ከ3 ሺ አመት በፊት የነበረውን የኢትዮጵያን የታሪክ አጥር መጠጋገን ነው።

"የኢትዮጵያ የ5 ሺ አመት ታሪክ - ከኖኅ እስከ ኢሕአዴግ" በሚል ርእስ የቀረበው ይህ መጽሐፍ በዚህ ጥራዙ እስከ አፄ ምኒልክ ድረስ

ያለውን ታሪክ ያካተተ ሲሆን፤ በቅርቡ የልጅ እያሱ፣ የንግስተ ነገስታት ዘውዲቱ፣ የአፄ ሀይለስላሴ ፣ የደርግና የኢሕአዴግ ዘመን ታሪኮችን ያካተተው ተከታይ ክፍል ይከተለዋል። የ100 ዓመት ታሪክ አስተርፈናል ማለት ነው። በግልጽና በጠራ መንገድ መተንተንና ሰፋ ተደርጎ መዳሰስ ያለበትም ነው። ስለዚህ ካልተዘመረለት እያሱ እስከተዘመረለት ኢሕአዴግ ድረስ የነበረውን ታሪክ በሌላ ጥራዝ እናገኘዋለን።

በዚህ መፅሃፍ ውስጥ በአንድ ምዕራፍ ስር የምዕራፉ ባለቤት የሆኑ ነሲገስታት በዘመናቸው የፈፀሟቸውና በዘመናቸው የተፈፀሙ ታሪካዊ ክንውኖች ተጣምረው ስለሚገኙ "የንጉስ እገሌ ዘመነ መንግስት" እያልን ይሆናል የምንቀጥለው። ለምሳሌ "የአፄ ገብረመስቀል ዘመነ መንግስት" በሚለው ምዕራፍ ውስጥ የቅዱስ ያሬድ ታሪክም አብሮ ተካቶ ይገኛል፣ የንጉስ ሐንዲው አብራ ዘመነ መንግስት በሚለው ምዕራፍ ውስጥ ኢትዮጵያ ኑርስን በጦርነት ድል ያደረገችበት ታሪክ ተካቶ ይገኛል ወዘተ...። ይህ ማለት ግን አንዳንድ ጉዳዮች ለብቻቸው ምዕራፍና ርዕስ ተሰጥቷቸው አይገኙም ማለት አይደለም።

የነገስታቱን ታሪክ በተመለከተ ሙሉ ታሪካቸው የተገኘውንና ሠፋ ያለ ታሪክ የተፃፈላቸውን ሠፋ ባለሁኔታ፣ መጠነኛ ታሪክ ያላቸውን ከነመጠነኛ ታሪካቸው የአጭር ታሪክ ባለቤቶችንም ከነአጭር ታሪካቸው፣ የ "በጣም አጭር" ታሪክ ባለቤቶችንም ከነ "በጣም" አጭር" ታሪካቸው፣ ከስማቸው በቀር ታሪካቸው ያልተገኘውን ወይም የጠፋውን ደግሞ ዝርዝራቸውን ብቻ አስፍሮ ለማለፍ ግድ የሚልበት ሁኔታ ይኖራል። መጥፎ እድል ሆኖ በስም ተዘርዛሪዎች ይበዛሉ።

"ያለፈ ታሪክን አለማወቅ አሁን ያለብትን ሁኔታ ከማዘንጋት ባለፈ የወደፊቱን አትጣጫና አካሄድም እንዳናውቅ ይከለክለናል" ይባላል። እውነት ነው። ስለዚህ የትናንቷን ኢትዮጵያ ሁኔታ በመጠኑም ቢሆን መረዳት የዛሬይቱን ኢትዮጵያ ለማወቅ፣ የወደፊቷን ኢትዮጵያም ለማየት ያስችለናል።

የሠው ልጅ ባለፈታሪኩ መማር እንጂ መማረር እንደማይገባው ይታወቃል። ከዚህ አንፃር ይህ መፅሃፍ ከታሪክ የሚገኘውን ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ለማስገኘት እንጂ ለሌላ ለምንም ሊሄፍ አይችልም። ከዚህ ክብ በወጣ አካሄድና አተረጓጎም እየተረጎመ የሚቆጭ አንባቢ ይኖራል ብዬም አላስብም።

በተረፈ የሚጠቀሱ የታሪክ ምንጮች በየዕሁፉ ጣልቃ የሚገኙ ሲሆን፣ በስተመጨረሻ በጥቅል ሠፍረው ይገኛሉ።



## መግቢያ

የምንግባው በብዙ ነገር ነው። በዋናነት ግን በአንድ፣ በሁለት፣ ወይም በሶስት ነጥቦች ላይ መግባባት ይኖርብናል። ስለኢትዮጵያ ታሪክ የሚያትቱ የተለያዩ ዓለማዊ እና መንፈሳዊ ይዘት ያላቸው ሰነዶች አሉ። ይሁን እንጂ የኢትዮጵያን ታሪክ በሚመለከት አንድአይነትና ወጥ የሆነ ድምዳሜ ላይ ሊያደርሱን ሳይችሉ ቆይተዋል፤ይህም ሲባል በተለያዩ ፀሀፍት እይታ የኢትዮጵያ የታሪክ መነሻ ዘመን የተለያየ ሆኖ ተጽፎ ስለሚገኝ ነው። ከዚህ አንፃር አንዱን የታሪክ ሰነድ ከሌላው ጋር እያገጣጠምን መቀጠል የግድ ይሆናል። ለአብነት ያህል ይቺን ሀገር በሚመለከት ከሰፈሩ ፅሁፎች ከብዙ በጥቂቱ ስናይ በምን አይነት ሁኔታ ከወዲሁ መግባባት እንዳለብን እንረዳለን።

"..... እግዚአብሔርም በምስራቅ በዔድን ገነትን ተከለ። የፈጠረውንም ሠው ከዚያው አኖረው... ለማየት ደስ የሚያሰኘውን፣ ለመብላትም መልካም የሆነውን ዛፍ ሁሉ ከምድር አበቀለ። ወንዝም ገነትን ያጠጣ ዘንድ ከዔድን ይወጣ ነበር። ከዚያም ለአራት ክፍል ይከፈል ነበር። የአንደኛው ወንዝ ስም ፊሶን ነው። እርሱም ወርቅ የሚገኝበትን የኤውላጥ ምድርን ይከብባል። የዚያም ምድር ወርቅ ጥሩ ነው። ከዚያም ሉልና የከበረ ድንጋይ ይገኛል።

- የሁለተኛው ወንዝ ስም ግዮን ነው፡ እርሱም የኢትዮጵያን ምድር ሁሉ ይከብባል። የሶስተኛውም ወንዝ ስም ጤግሮስ ነው። እርሱም በአሦር ምስራቅ የሚሄድ ነው። አራተኛውም ወንዝ ኤፍራጥስ ነው። እግዚአብሔርም ሠውን ወስዶ ያበጃትም ይጠብቃትም ዘንድ በዔድን ገነት አኖረው..."/ መፅሐፍ ቅዱስ ኦሪት ዘፍጥረት ም.2 ከቁ 8-16/

ነገር ግን የሠው ልጅ ሣተ። ትዕዛዝ በመተላለፉም ከምቹ መኖሪያው ሊፈናቀል ግድ ሆነ። ፈጣሪውንም አሣዘነ ማለት ነው። ስለዚህ ፈጣሪ ለአዳም እንዲህ ይለዋል።

"... ምድር ካንተ የተነሣ የተረገመች ትሁን። በህይወት ዘመንህም ሁሉ በድካም ከእርሷ ትበላለህ።... የምድርንም ቡቃያ ትበላለህ። ወደመጣህባት ምድር እስክትመለስ ድረስ በፊትህ ወዝ እንጀራን ትበላለህ። አፈር ነህና ወደ አፈርም ትመለሳለህና..." /ም.ዕ. 3 ከቁ16-20/

"...የተገኘበትን መሬት ያርስ ዘንድ አዳምንም አስወጣው። ወደ ህይወት ዛፍ የሚወስደውንም መንገድ ለመጠበቅ ኪሩቤልንና

የምትገለባበጥ የነበልባል ሠይፍን በዔድን ገነት ምስራቅ አስቀመጠ።"/ ምዕ 3 ከቁ 23-24/
ወደ ዓለማዊ የታሪክ መፃህፍት ስንመጣ፡-

"... ኦፊር የአፍሪካውያን አባት ለሣፊዎቹ አፋሮች አባት ነው። በኦፊር ስም በሣፊው አውጣ የሚገኘው ወርቅ ኦፊር ይባል ነበር። ዋና ከተማው ተርሲስ ነው። እርሡም በሠለሞን ዘመነ መንግስት የታወቀ ወርቅ ስለነበረ የኦፊር ወርቅ ክቡር ነበር። በኦፊር አገሩን/አህጉሩን/ አፍሪቃ፣ ህዝቦችን አፍሪካኖ ይሉዋቸዋል።."/ መፅሃፍ አብርሃት በመሪ ራስ አማን በላይ/

"... ኢት ስጦታ፣ ዮጵ ብጫ ወርቅ ወይም እንቁ፣ ግዮን ፈሳሽ ወንዝ፣ በጥቅል ኢትዮጵግዮን፣ የግዮን ወርቅ ስጦታ ተብሎ በሱባ ይተረጎማል.."/ "መፅሃፈ አብርሂት" በመሪ ራስ አማን በላይ/

"... ይች አገር በሠሜን ከግብፅ፣ በምዕራብ ከኒል አባይ፣ በምስራቅ ከዓረብ አገር፣ በደቡብ ከህንዳዊው ውቅያኖስ ትዋሠን ነበረች። ከእየሱስ ክርስቶስ ልደት ብዙ አመታት በፊት በዚች አገር የኩሽ ዘሮች የሚባሉ የካም ወገን የሆኑ ተወላጆች ይቀመጡባት ነበር። እነዚህ የኩሽ ዘሮች ባላገሮችና ዘላኖች ስለነበሩ የእነርሡ አኗኗርና ዋና ስራቸው ከብት ማርባት ብቻ ነበር።... የማዕድኖችን ስራ ገና አላወቁም ነበርና መሣሪያቸው ሁሉ ከድንጋይ አይነት የተሠራ ነበር። ቆይቶ ግን እየሠለጠኑ ከሄዱ በኋላ ይህንን ለመሣሪያቸው የሚሆነውን ድንጊያ መጥረቡና ማለዘብ ጀመሩ።... እንዲህ ሆኖ ስራቸው እየተስፋፋ ከሄደ በኋላም የስልጣኔ ኑሯቸው ከፍ እያለና እየተራመደ ሄደ። ለኑሯቸው የሚጠቅሙ ማዕድኖችንም ማግኘት ጀመሩ። ስጊዜው ያገኟቸው ማዕድኖችም ነሃስና መዳብ፣ ብረት፣ ወርቅና ብር ይህን የመሣሰሉ ሌሎችም ማዕድኖች አግኝተው መስራት ጀምረዋል። እኒህ ማዕድኖች አልፎው አልፎው በሙሉ ኢትዮጵያ ይገኙ ነበር። በተለይ ግን በኦጋዴንና በሱማሊ አገር ይገኙ ነበር። እንዲሁም ማለት መጽሃፍ ቅዱስ /3 ዘነገስት ም 1 ቁ 11፣ 2ኛ ዜና መዋዕል ም9 ቁ 10/ በብዙ ስፍራ የኦፊር ወርቅ ብሎ በሚያነሣው በተለይ ይገኙ ነበር ማለት ነው።

ሠው በየጊዜውና በየዘመኑ እየተለዋወጠ መሄዱ የታወቀ ነው። እንኳን ሠው መሬት እንኳ በአንዳንድ ጎመራ ዋዕይ ምክንያት ተራራ የነበረው ሜዳ ፣ ሜዳ የነበረው ተራራ ሆኖ፤ ያ ሜዳ የነበረው ቦታ ገደልና ሸንተረር ስለተገኘበት የወርቅና የብር የነሃስና የመዳብ፣ የብረትም የሌላም ልዩ ልዩ ማዕድን መገኛ ሆኖ ይታያል......" / "የኢትዮጵያ ታሪክ" አባጋስፖረኒ ገ/ም/

"..... ግብፃውያን ከ2500 አመት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በፊት ጀምረው ወርቅና ሌላ ክቡር እቃ ለመፈለግ በኒል አባይና



በአትባራ አድርገው ወደ ኢትዮጵያ ይገቡ ነበር ። እነሱ የመጡበት ዘመን ኦሪት ከመፃፉ በፊት ስለሆነ የአገሪቱን ስም ኩሽ ብለው ጠርተዋት ሄዱ። ኋላም ሙሴ በግብፅ በስደት አገሩ ያደገና የተማረ ስለሆነ ከግብፅ አገር ሊቃውንቶች የሠማውን የኩሽ አገር ብሎ ኢትዮጵያን በኦሪት መፅሃፍ ላይ ፃፉት።

ግብፃውያን ወርቁን እየቆፈሩ ወስደው እኩሌቶቹ በኒል አባይና በአትባራ፣ እኩሌቶች በቀይ ባህር አድርገው ወደ አገራቸው ተመልሠው ከኢትዮጵያ በወሠዱት ወርቅ የአምላኮቻቸውን የነገስታቶቻቸውን ምስሎች ይሠሩ ነበር። እስካሁን ድረስ በግብፅ የሚገኙት የቀድሞ ዘመን ምስሎች ብዙዎቹ ከኢትዮጵያ በወሠዱት ወርቅ የተሠሩ ምስሎች ናቸው። የቀድሞዎቹ ኢትዮጵያውያን (የኩሽ ዘሮች) ግብፃውያን ከአገራቸው እየተሠደዱ መጥተው በኢትዮጵያ ውስጥ ወርቅ የሚገኙባቸውን ቦታዎች እየፈለጉ በነቀምት፣በሌቃ፣በማጂ፣ በጉባ፣ በሸንጎሌ እስከ ኦጋዴን ድረስ የሚገኘውን የወርቅ ማዕድን እየፈለጉ ቆፍረው መውሠዳቸውን ካዩ በኋላ የወርቅ ማዕድንን ጥቅም አወቁ። እንደዚሁም እየሠለጠኑ ከድንጋይ ዘመን ወደ ወርቅ ማዕድን ዘመን ደረሡ። ከዚህም በኋላ ጥቂት በጥቂት ወደ ነሃስና ወደ መዳብ ወደ ብረትም ዘመን ደረሡ። /"የኢትዮጵያ ታሪክ" አባ ጋስፖረኒ ገ/ም/

"... አንዳንድ ታሪክ ፀሃፊዎች ኦሪ ወይም ኣራም የተባለው የአዳም ልጅ ዓለም በተፈጠረ በ970 ዓመት በኢትዮጵያ ነግሶ ነበርና የእርሡ ነገድ እስከ ጥፋት ውሃ (ማየ አይኅ) ድረስ 21 ነገስታት ነግሠው ኢትዮጵያን ገዝተዋል ብለው ፅፈዋል።"/"ዋዜማ" ብላቴንጌታ ህሩይ ወልደስላሴ/

"... የአዳም መኖሪያ የነበረችው ገነት በአርማንያ.አገር አጠገብ ናት።.. የእነዚህም ያራቱ ወንዞች ምንጫቸው በአርማንያ አገር ካለው አራራት ከሚባለው ተራራ እንደሆነ በጂዎግራፊ መፅሃፍ የታወቀ ነውና ገነት በአርማንያ አገር አጠገብ መሆንዋን ያስረዳል።... ነገር ግን ኖን ከጥፋት ውሃ በኋላ ከመርከብ ወጥቶ ምድርን ከሶስት ከፍሎ መካከሉን እስያን ለሴም፣ ግራውን አፍሪቃን ለካም፣ ቀኙን አውሮጳን ለያፌት አከፋፍሎ ሠጥቷቸው ነበርና በዚያ ዘመን ካም ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ባይነግስና ባይገዛ እንኳ አፍሪካ የካም ክፍል ከሆነ ካም በኢትዮጵያ ነግሶ ነበር ቢባል ተቃዋሚ የለበትም።... ከጥፋት ውሃ አስቀድሞ የአዳም ልጅ ኦሪ፣ ከጥፋት ውሃም በኋላ የኖህ ልጅ ካም፣ በኢትዮጵያ ነግሠው ነበር ብለን ብንፅፍ አንባቢዎችና ታሪክ መርማሪዎች እውነት ብለው አይቀበሉንምና፤ የነገደ ኦሪንና የካምን መንግስት ታሪክ ትተን ከካም የልጅ

ልጅ ከሰብታህ ጀምረን በኢትዮጵያ የነገሡትን ነገሥታት ስምና ቁጥር እንፅፋለን።"/ ብላቴን ጌታ ህሩይ ወልደ ስላሴ "ዋዜማ"/

"... በመጀመሪያ ከንሰም ክፍል ሠው የነበረበት እስያ ነበር። ሁለተኛው አፍሪካ ነው፤ ከዚያ ቀጥሎ አውሮጳ፤ በመጨረሻ አሜሪካ ነው።... አዳምና ሄዋን በእስያ በዔድን (ገነት) ተክል መኻከል ተቀመጡ። ይህም ስፍራ በእስያ ምዕራብ ወገን ካለው ከኤፍራጠስ ወንዝ ሩቅ አልነበረም። ነገር ግን እግዚአብሔርን በድለው በሃጢያት ከወደቁ በኋላ ያንን ደስ የሚያሠኝ ስፍራ ለቀቁ። በዚች ሠፊ ዓለም ለጊዜው የነበሩባት ከሠው ወገን አዳምና ሄዋን ብቻ ነበሩ። ይህም ስለሆነ እግዚአብሔር አልተለያቸውም ነበርና ብቻኝነታቸው አይሠማቸውም ነበር። ወዲያው ልጆች እየተወለዱላቸው ዘራቸው እየተባዛ ሄደ። እነዚህም በኤፍራጠስ ዙሪያ ያለውን አገር ሁሉ መኖሪያቸው አደረጉት። በዚያም ከተሞችንና መንደሮችን ሠሩ። ነገር ግን ክፋታቸው እየበዛ ስለሄደ አምላካቸውን ማምለክ ረስተው ክፋትንና አውሬነትን ተከተሉ። ስለዚህ እግዚአብሔር አምላክ ለማይታዘዙ እምቢተተኞች ቅጣት፤ ወደ ፊት ለሚመጡት ነገዶች ጥንቃቄ እንዲሆናቸው ብሎ ከኖኅና ከልጆቹ በቀር የሠውን ወገን ሁሉ ለማጥፋት ቁርጥ ሃሣብ አደረገ።" ("የዓለም ታሪክ" አቶ ዮሃንስ ወልደማርያም)።

"... ከጥፋት ውሃ በፊት የነበሩት ህዝብ አንቲዴሉቭያን ይባላሉ። ከጥፋት ውሃ በፊት የነበሩ ማለት ነው። ስለእነርሁም በመፅሃፍ ቅዱስ ከተነገረው በቀር ሌላ አናውቅም። ምናልባት በእስያ ውስጥ በትንሽ ስፍራ ተበትነው ይሆናል እንጂ ከጥፋት ውሃ በፊት በአፍሪካ፣ በአውሮፓና በአሜሪካ ከቶ ምንም ሠው አልነበረበትም። የጥፋት ውሃ መግባቱን በህዳር ጀምሮ በመጋቢት እንደቆመ ይታሠባል። ወዲያው ከጥቂት ጊዜ በኋላ ውሃው እየጎደለ ሄደ። የኖኅም መርከብ በአርመን አገር በአንድ ረጅም ተራራ ጫፍ ላይ አረፈ። ይህም ተራራ አራራት ይባላል። እስከ ዛሬም ድረስ ይታያል።

... ምናልባት ከጥፋት ውሃ በፊት የነበሩ ሠዎች (ሁብዓ ትካት) የሠፈሩት በዚህ በኤፍራጠስ ወንዝ ዳር ሳይሆን አይቀርም። የቀድሞ ወገኖች መጀመሪያ ነገድ የሆኑበት በዚህ ስፍራ ነው..." (አቶ ዮሃንስ ወ/ም "የዓለም ታሪክ")

"... ፈጣሪም በኖኅ መስዋዕት እጅግ ተደስቶ ለአዳምና ለሄዋን የነገራቸውን ምድር እንዲወርስ ስለወደደ "የሠው ልጆችን ከእንግዲህ አላጠፋም" ሲል ቃል ኪዳን ገብቶ ለቃሉ ማረጋገጫ በደመና ቀስቱን አኑሮ በማመልከት ወደ ግዮን ዘአበ ሜስክ መነሻ ባና ሃይቅ (አዳምና ሄዋን ባጠፉት ጥፋት ተባረው ኢየሩሳሌም ከመኖራቸው ቀደም ብሎ ይኖሩበት



የነበረ ቦታ እንደሆነ ይታመናል።) እንዲሄድ አዘዘው። ኖኅም ሴምንና ያፌትን ትቶ ካምን ይዞ ወደ አፍሪካ ኢትዮጵያ ምድር መጣ።" ("የጎንደር ታሪክ" ያሬድ ግርማ ሃይሌ)

"... የካም ዘሮች ያልሠፈሩበት ቦታ አልነበረም። ሔሮዱተስ የግሪክ ቀደምት ነዋሪዎች የካም ዘሮች ነበሩ ብሏል። ("የኢትዮጵያ አንድነትና ኢጣሊያ" ዶ/ር ተወልደ ትኩእ)

"... አንዳንድ ስለሠው ዘር የሚያጠኑ ጠበብት የመጀመሪያው የሠው ዘር ብቅ ያለው በዓባይ፣ በኤፍራጠስና ጤግሮስ ወንዝ ሸለቆዎች ነው። ይላሉ። ሌሎች ደግሞ የሚያምኑት የመካከለኛው ምስራቅ የመጀመሪያዎቹ ሠፋሪዎች ከአባይ ሸለቆ በቀይ ባህር በኩል ወደ ሠሜን የፈለሡ ጥቁር ኑብያንስ ናቸው በሚል ነው። የሚመስለው ግን ህይወት በእነዚህ አካባቢዎች በተመሣሣይ ጊዜ ተከሠተና የመካከለኛው ምስራቅ የመሬት ሠላጤ የእነዚህ ሁሉ ህዝቦች መገናኛ ሆነች የሚለው ነው።... በዚህ በኤፍራጠስና ጤግሮስ ወንዝ ሸለቆዎች የመጀመሪያውን የሠው ልጅ ስልጣኔ ፈጠሩ..." (David Lamb "the Arbs" እ.ኤ.አ 1987)

"... ኢትዮጵያውያን ገነት የምትባለው የራሣቸው አገር የኒል ምንጭ መሆኗን አያምኑም። ይደነግጣሉና።... ደግሞም የሩቅ አገር ሠው ዕሁፍ ይጠብቃሉ። በዚያ ላይ ስለራሣቸው ማውራት አይወዱም። ሃጢያት ነው ይላሉ።... (Fredric T.Bolton "Plant and planiet" እ.ኤ.አ 1982)

"... በ9ነኛው መቶ ዓመት የነበረው ሆሜርና ይልቁንም በ6ኛው መቶ አመት የነበረው ሄሮዱት የፃፉት ነው። እነርሡም ከብዙዎቹ ውስጥ እንደዚህ ይላሉ። ኢትዮጵያውያን ታላላቆች መልካቸው ያማረ፣ የሠውነታቸው ቅርፅ ደንበኛ የሆነ ባድቆች፣ በጎ አድራጊዎች፣ ለስራ የማይደክሙ፣ ጥበበኞች፣ በሩቅ ስፍራ የሚኖሩ አማልክት የሚወዷቸው፣ ባንደበታቸው ሃሠት የማይገባ፣ በጦርነትና በእርጅና ካልሆነ በስተቀር በበሽታ የማይሞቱ ናቸው። ("የኢትዮጵያ ታሪክ ኑብያ/ናፓታ መርዌ/" ተክለፃድቅ መኩሪያ)

ከላይ የተጠቃቀሡት ሐተታዎች ሁሉ ከተጠቀሡት መፃህፍት የወጡ ናቸው። በርካታ ፀሃፍት ስለዚች አገር ብዙ ብዙ ብለዋል። በመጨረሻ የሚደርሡበት ድምዳሜ ግን "ይች አገር ሚስጥር ናት" የሚል ነው።

ስለኢትዮጵያ ቀደምት ታሪክ ብዙዎች ብዙ ይበሉ እንጂ አንዱ ፀሁፍ ካንዱ ሲስማማ የምናየው በጣም በውስን ነጥቦች ብቻ ነው። በስም ቢስማሙ በዘመን ይጣረሣሉ። በነገድ ቢስማሙ በመቸት ይጣላሉ... ወዘተ።

ይህም ነው ትልቅ ችግር ፈጥሮ ሲያወዛግብ የኖረው። ስለኢትዮጵያ የተፃፉና በደንብ ተደራጅተው ያልተቀመጡ ሙሉዕነት ያላቸው መረጃዎች ካለመኖራቸው ጋር ተደማምሮ ሁኔታውን ከባድ አድርጎታል። ስለዚህ የጎደለውን ከመፅሃፍ ቅዱስ እየቆነጠርን ለመሙላት እንሞክራለን።

ምንም እንኳ ለታሪክ ዋቢነት ተብሎ ያልተፃፈ ቢሆንም በአግባቡና በጥቂቱ ብንጠቀምበት ተከፋ ወገን ሊኖር አይገባም። ይህም ሲባል በጥንቱ ታሪክ ላይ መሠረቱን እስክንይዝ ድረስ ባሉት ጥቂት ገፆች ላይ ነው። ቡተረፈ ከሌሎች አገራት ታሪክ ነገስት፣ ዜና መዋዕል፣ የሃውልት ላይ ፅሁፎች... ወዘተ.. ተነስተው የተፃፉትን እየመረጥን ትውፊታዊ መረጃዎችንም እያከተትን አንዱን ከአንዱ እያስማማን እንቀጥላለን። የአንዱን ዓረፍተነገር ከሌላው፤ የሌላውን ሐተታ ካንዱ አስማምተን እያዋሃድን፣ ያንዱን እያነሳን ያንዱን እየጣልን፣ መንፈሣዊውን ፅሁፍ ከአለማዊው እያጣመርን የሩቁን ዘመን ታሪክ እንረዳና ሁሉም የተስማሙበት ወጥ የሆነ ታሪክ የምናይበት ዘመን ላይ እንደርሣለን። ያን ካላደረግን ወደ እውነታው መድረስ ስለማንችል እንደማለት። ይህ በእንዲህ እንዳለም ከወዲሁ መነሳት ያለበት ጥያቄ አለ፤ ይኸውም ፦

1ኛው ገነት የት ነበረች? የሚለው ሲሆን፤ 2ኛው የኖኅ መርከብ የት አረፈች? የሚለው ነው። በተለይ በ2ኛው ጥያቄ ላይ ጥቂት ነጥቦችን ማንሳት የግድ ይሆናል።

ብዙዎች የውጭ አገር ጸሃፊዎች ገነትን አርማንያ ውስጥ ያደርጓታል። ሁሚ ያሉ የሚመስሉ ጥቂት የአገር ውስጥ ፀሃፍት ደግሞ ጣና ላይ ነው ይላሉ። እርግጥ ነው ከሁለቱ አገራት ውጪ እንዳልሆነች ግልጽ ነው።

ንግሥ ዔድን ገነት ኢትዮጵያ መሆኗን እርግጠኛ ይሆንና፤ ነገሩ ሁሉ ምስቅልቅሉ በወጣ ጊዜ እነ ጢግሮስ ተቆርሠው ሽሹ ይላል። የቀረው በእግተ ገሞራ ግቢያ ነገሩ ሁሉ ተለዋወጠ እንጂ ገነትማ ኢትዮጵያ ለመሆኑ ምን ጥርጥር አለው? ይለናል። አንዳንዱ አዳም ገነትን ለቆ ተባሯል። ከተባረረ በኋላም ኢትዮጵያን ለቆ አምላክ ወዳዘጋጀለት ሌላ ስፍራ ተወስዷል። ስለዚህ በኋለኛው ዘመን የጥፋት ውሃ ሲከሠትና ኖኅ ፃድቅ ሆኖ ሲተርፍ ለአዳም የነሣውን ምድር ለኖኅ መልሶ አውርሶታል ይላል።

ትውፊቱማ ጉድ የሚያሠኝ ነው። "የምትገለባበጥ የነበልባል ሠይፍን በዔድን ገነት ምስራቅ አስቀመጠ.." የሚለውን ነገር በማመልከትማ አንዳንድ ትውፊታዊ መረጃዎች መነሻቸውን ጣና ያደርጉና "ምስራቅ" የሚለውን ወደ አፋር አካባቢ ያመላክቱና ኤርታሌን ሲጠቁሙን የሚሞክሩ አሉ። ቀደም ሲል እንደተመለከትነው የወርቁንና የማዕድኑን ጉዳይ እያመሣከሩ ይተነትኑልናል። ኤርታሌን ከኤደን ባህረ ሠላጤ ጋር እያስማሙ ሠይፉን ተክለው እያብለጨለጩ ያሣዩናል።

ምናልባት ከግማሽ በላይ የሆኑ የአገር ውስጥና የውጭ አገር ሀሃፍት ገነት አርማንያ መሆኑን ይስማሙበታል። ከግማሽ በታች የሆኑት ደግሞ በኢትዮጵያ መሆኑን ያምናሉ። ዛሬ ድረስ በስፋት ተቀባይነት አግኝቶ ያለውም የአርማንያው ነው። ምክንያቱም ከኛ ቀድመው "ዘመናዊ" ትምህርት የተማሩት ነጮች ስለሆኑ በሚመቻቸው መንገድ ቀድመው ታሪኩን ሁሉ ወደራሣቸው ወስደው ስለጨረሡት ነው።

ከአገር ውስጡ የብራና ፅሁፍ ይልቅም የነጮችን መርጠው የሚቀበሉ ምሁራን ስለ ሚበረክቱ ቀደምት አባቶች ቆዳ ፍቀው የፃፉት ተቀባይነት እያጣ ተረተረት እየተባለ እዚህ ተደርሷል።

ቀደም ሲል በብላቴን ጌታ ህሩይ ወ/ሴ "ዋዜማ" መፃህፍ ላይ አንድ አስገራሚ ሃተታ አይተናል። "... የአዳም ልጅ አሪ ከጥፋት ውሃ በፊት፣ የኖኅ ልጅ ካም ከጥፋት ውሃ በኋላ በኢትዮጵያ ነግሶ ነበር ብለን ብንፅፍ የሚያምነን አይኖርምና.." በሚል መነሻ "ትተነዋል" ብለውናል። እንጂ የተፃፈ ሠነድ አግኝተው ነበር። እንዲህ ነው እንግዲህ የኢትዮጵያ ታሪክ! እንደነግጣለን፤ አይመስለንም፤ ሽምቅቅ እንላለን።

መረጃ፣ መረጃ፣ መረጃ ይባላል። መረጃውንማ ወስደውታል። ምንም የለንም'ኮ በዘረፋም፣ በጎብኚዎችም፣ በጦርነትም፣ በስጦታም አልቋል፡፡ እኛ ስለ ፅሁፍና ስለመፃህፍ ምንነት ከመረዳታችን በፊት ነው የወሠዱት። አሁንም ቢሆን እነሡ የፃፉትን ተቀብለው ከፃፉ የአገራችን ሊቃውንት እየቆረስን እንጂ ከየትም አናመጣም።

ጥንታዊውን የታሪክ ሠነድ ወሠዱትና አደራጅተው ፃፉት። አንዳንዱን መለሡት። የቀረውን አስቀሩት። እነ ተክለፃድቅ መኩሪያን የመሣሠሉ ሊቃውንት በዲፕሎማትነት ዘመናቸው በየአውሮፓ አገሩ ቤተመፃህፍት ተቀምጠው ያሉትን ከኢትዮጵያ የተወሠዱትን ፅሁፎች አስፈቅደው እየገቡ መርምረው ታሪክ ፃፉ። እነ አለቃ ታዬን የመሣሠሉ የቤተክህነት ቀደምት ሊቃውንት ደግሞ በምኒልክ ጊዜ ወደ ጀርመንና ወደ ሌሎች የአውሮፓ አገራት እየተጓዙ ግዕዝን አስተማሩ። እነሡ ያስተማሯቸው አውሮፓውያን ዛሬ ከፍተኛውን የግዕዝ ት/ት ለኢትዮጵያ ምሁራን... ያስተምራሉ። ከዚያም እነዚህኞቹ እነዚያኞቹ የፃፉትን ተረተረት ነው ይላሉ። እንዴት? ስንል "ዘመናዊ የአጠናን ዘዴን ያልተከተለ፣ እንዲሁ መረጃ አልባ የሆነ ፅሁፍ ነው" ይላሉ።... ታዲያ በዘመናዊው የአጠናን ዘዴ አጥኑና አስተምሩን እንጂ፤ አለበለዚያኮ በትውፊት ተታለን መቅረታችን ነው ከማለት ውጪ ምንም አይባልም።

ስልጣኔ ከኢትዮጵያ ወደ ግብፅ ብቻ ሳይሆን ወደ መላው ዓለም ሄደ። ሁሉንም አይነት ስልጣኔ ቀደምት ኢትዮጵያውያን አሣልፈው ሠጡ። ከዚያም ባዶአቸውን ቀሩ። እንደገና ተመልሠው እስኪያሠለጥኗቸው መጠበቅ ግዴታ ነበር። መለማመጥንም ይጨምራል። የታሪክ ሠንድ ከኢትዮጵያ ተወስዶ በመላው ዓለም ተሠራጨ። ከዚያም ባዶዋችንን ቀረን። እንደገና መልሠው እስኪሠጡን መጠበቅ ግዴታችን ነበር። መለማመጥንም ይጨምራል።

"ቀደምት ነን" ስንል "ምን መረጃ አላችሁ"? ይሉናል። መረጃችን እንደወሠዱት ስለሚያውቁ አጠያየቃቸው ልብ ሙሉነት የሚንፀባረቅበት ነው። ጥቂት ነገር ቆንጥረው (እሡንም አበባርቀው) ይሠጡንና ስንወዛገብ እንድንኖር ያደርጋሉ። እንዲህ ነው'ጂ መወዛገብ!

ወደ ዋናውና ወደ ሁለተኛው ነጥባችን እንለፍ፤ አንደኛው ጥያቄ ከሁለተኛው ጥያቄ ጋር ተያያዥነት ስላለው አብረን ልናየው እንችላለን። ከጥፋት ውሃ በኋላ የኖኅ መርከብ የት አረፈች? ስንል፤ ታላቁ መፅሃፍ "በአራራት ተራሮች" ይለናል። ከዚህ ያለፈ ነገር አይነግረንም፤ መንገርም አይጠበቅበትም። ስለዚህ አራራት ተራራ የት ነው? ብለን ስንጠይቅ ነጮች "አርማንያ" ወይም ቱርክ ይላሉ። ከነጮች ተቀብለው የፃፉ ሀበሾችም አርማንያ ብለው መልሠው ይነግሩናል። የአገር ውስጥ ጥቂት ሊቃውንት ደግሞ "አራራት ተራራ ጣና ላይ ነው" ይሉናል። አሁንም በተመሣሣይ አራራት ተራራ የሚባሉ በሁለት የተለያዩ የዓለም አገሮች ይገኛል። በአርማንያ እና በኢትዮጵያ። አይገርምም?

"አራራት ተራራ በደቡባዊ ጣና ሃይቅ በዘጌ ባህረ ገብ ጥቅጥቅ ባለ ደን ውስጥ ከአንድ ሠዓት የእግር ጉዞ በኋላ የሚገኝ የአካባቢውን ዙሪያና የጣና ሃይቅን ለመመልከት የሚያስችል፤ ሲሆን በዙሪያው ላይ ይጋንዳ ተክለሃይማኖት በአድያም ሠገድ እያሡ የተተከለ፤ ቅድስት ስላሴና በተራራው ስር ኡራ ኪዳነምህረት አብያተ ክርስቲያናት ይገኛሉ" ይላል ያሬድ ግርማ ሃይሌ የተሻለ አማራጭ አቅርቦ ክፍት አድርጎት ሲያልፍ። በሌላ በኩል አራራት ተራራ በአርማንያ ውስጥ የሚገኝ የከፍታ መጠኑ 5165 ሜትር ሲሆን፤ በዓለም ካሉ ተራሮች 27ኛ ተራ ረድፍ ላይ ይገኛል። አርማንያ ቱርክ፣ ጆርጂያ፣ አዘርባጃንና፣ ኢራን የሚያዋስኗት እስያዊት አገር ናት።"

የኛው አራራት ተራራ አልተለካም። ያን ያህል ቁመትም የለውም። ከፍታ ደግሞ ምንን ይገልፃል? የኖኅ መርከብ ከሁለቱ አራራት ተራራዎች በአንደኛው አርፋለች። የብዙሃኑ ምልከታ በእስያው አራራት ተራራ አረፈች የሚል ነው። ይህም ሲሆን ኖኅ ከጥፋት ውሃ በኋላ ሲያምንና ያፌትን ትቶ ካምን ይዞ ወደ ኢትዮጵያ መጣ ልንል ነው።



መርከቧ ያረፈችው በዚህኛው አራራት ተራራ ከሆነ ደግሞ ሴምና ያፌት ከዚህ ተነስተው ሄደው በእስያና በአውሮፓ ሲስፋፉ፤ ካም እዚሁ ቀርቶ በአፍሪካ ተስፋፋ ልንል ነው። የዚህን ምርጫ ለአንባቢያን ክፍት አድርጎ ማለፍ ይቻል ይሆናል። ምክንያቱም እርግጠኛ ሆኖ መናገር የማይቻለው የመርከቧን ማረፊያ ቦታ እንጂ ኖኅ ካምን ይዞ ለመምጣቱ ወይም በዚች ምድር ለመኖሩ በዋናው ታሪክ ውስጥ ስለምናገኘው በታሪካችን ላይ ተፅእኖ አይፈጥርም። የትኛው ተራራ ላይ አረፈች? እዚህ ወይስ እዚያ? የሚለውን "እዚህ ነው" ብዬ ድምዳሜ ከወዲሁ ደምድሜ ለማለት የሚያስችል ከትውፊት በስተቀር በቂ መረጃ ለጊዜው ስለሌለኝ ክፍት አድርጌው ልለፍ እንጂ ግላዊ እምነቴ አርማንያ አይደለም። ስለዚህ ሊሆንም ላይሆንም ይችላል በሚለው ለጊዜው ተግባብተን እንቆይና የታሪኩ ሂደት በራሡ የበለጠ ወደ አንዱ ድምዳሜ ሊያደርሣችሁ ከቻለ አብረን እንይ። ካላደረሳችሁ ብቻዬን እደርሣለሁ ማለቴ ነው። ይህን ለማለት ያስፈለገው በአንዳንድ ፀሐፍትና አንባብያን ዘንድ ትውፊት ሲጣልና ሲናቅ ስለሚስተዋል ነው። ስለዚህ ትውፊትን በተመለከተ አንድ ነገር ላንሳ። ይህ መፅሃፍ ተፅፎ ከመጠናቀቁና ከመታተሙ በፊት "ከኖኅ እስከ ኢህአዴግ የኢትዮጵያን ዘመናት ቆጠራ" በሚል ርዕስ ሠለሞን አበበ ቸኮል (ሰ.አ.ቸ) የዚህን መፅሃፍ አጠቃላይ ሁኔታ በሚመለከት መጠነኛ ዳሠሳ ቢጤ እያደረገ ለጥቂት ሣምንታት ከህዳር 19 2002 ዓ.ም ጀምሮ ብጋዜጣ አስነብቦ ነበር። እናም ትውፊትን በተመለከተ ካሠፈረው ፅሁፍ ጥቂት ዓረፍተነገሮችን ቆንጥሬ ላስፍር። እርሡ እንዲህ አለ፦

"... ለብዙዎች ትውፊት ማለት እውነት ያልሆነ ነገር ይመስላቸዋል። ትውፊት ማለት በውርስ የተገኘ በቅብብሎሽ የመጣ፣ የወረደ ማለት እንጂ ውሸት ወይም ተረተረት አይነት ማለት አይደለም። በትውፊት የተገኘ ታሪክን ሣይንስ በገዛ ራሡ መንገድ ለመከተትና ለማውጣት እስካልቻለ ድረስ ለዘመናት የኖረ ማህበረሠብና ሃገር የኖረበትን ማንነቱን መግለጫነታቸውን ማስተሃቀር ትልቅ ውድቀት እና ጥፋት መፈፀም እንደሚሆን ከኛው ወዲያ ጥሩ አስረጅ ማቅረብ አይቻልም። ይህም ቢሆን ሊታወቅ የሚቻለው ኖኅን ከመሠሉ የሡው ልጅ የጋራ ቤቶችና አባቶች ከነበሩበት ጀምሮ ታሪክን በዘመን መንገድ ላይ እያሽከረከሩ ያመጡት እንደሆን ነው...።" ስለዚህ ትውፊት መጣል፣ መናቅ የለበትም። በዚህም ልንግባባ ይገባል።

ትውፊት ከተባለውም በላይ ነው። በትውፊት ያልታገዘ ጥንት ታሪክ አለ ብሎ ለማለት አይቻልም። ታሪክን ጠብቆ የማቆየ አንድ መንገድ ነው። ስለ ትውፊት እንዲህ ሲባል መነሻና መድረሻችን ትውፊት

ነው ማለት አይደለም። ትውፊትን መጣል ተገቢ አለመሆኑን ለመግለፅ እንጂ።

እኔ እንዲህ እላለሁ፡- የኢትዮጵያ ታሪክ መነሻ አጼ ቴዎድሮስ ቢሆን ኖሮ ከቴዎድሮስ እጀምር ነበር። ሌላ ንጉስም ቢሆን ከሌላ እነሣ ነበር። ያሉትን አነስተኛ የኢትዮጵያ የታሪክ ሠነዶች ተጠቅሞ የኢትዮጵያን ታሪክ ከስር ጀምሮ ለመፃፍ የተነሣ ፀሃፊ የግድ መነሻውን ይመረምራል። ፍለጋውን ሲጨርስ መነሻ ብሎ ከወሠነው ቦታ ጊዜና ንጉስ ጀምሮ ይፅፋል። ከቴዎድሮስ ከሆነ ከቴዎድሮስ፣ ከኖኅ ከሆነ ከኖኅ ይጀምራል። ከመሃል እስከልጅመሬ ድረስ። ባጠቃላይ ኖኅን መነሻ ያደረግሁት ታሪኩ አስገድዶኝ እንጂ፤ ኖኅ ከጥፋት ውሃ የተረፈ የመጀመሪያው ግንድ ስለሆነ አይደለም ወደ ኢትዮጵያ ያመጣሁት። መነሻ እንዳደርገው ያስገደደኝ ታሪክም እኔን ብቻ ሣይሆን ሌሎች ቀደምት ፀሃፍትንም ያስገደደ ነውና በምናየው መልኩ በመጠቃቀስ ኖኅን መነሻ አድርጌያለሁ።

በዚህ መሰረት ከአዳም ጀምሮ 10 ትውልድ ወይም የዘር ግንድ ይቆጠራል። አዳም፣ ሴት፣ ሄኖስ፣ ቃይናን፣ መላልኤል፣ ያሬድ፣ ሔኖክ፣ ማቱሳላ ላሜህ፣ ኖኅ ተብለው ይቆጠራሉ። በኖኅ ዘመን የጥፋት ውሃ ይሆንና ኖኅና ቤተሠቦች ብቻ ይተርፋሉ። ከዚያም ከጥፋት ውሃ ከተረፈው ከኖኅና ከቤተሠቦቹ ጀምሮ "አዲስ" የዓለምና የህዝቦቿ የታሪክ ምዕራፍ ይከፈታል። ወይም ሁሉም የሠው ልጆች በጥፋት ውሃ ጠፍተው ኖኅና ቤተሠቦቹ ከተረፉ በኋላ በእነርሡ አማካኝነት ዓለም በሠው ልጆች ተሞልታለች። በዚህ ብንግባባ ምርጫዬ ነው። በዚህ ካልተግባባን በሙሉው መፅሃፍም ስለማንግባባ፤ ከዚህ እምነት ውጪ የሆነ አንባቢ ካለ ከውዲ[illegible] [illegible]ን እንዲያቋርጥልኝ በትህትና "ዝቅ" ብዬ ሣይሆን "ቀና" ብዬ [illegible]

[illegible]



## ምዕራፍ ፩
## ኖኅ እና ኢትዮጵያ

ኖኅ የ500 አመት እድሜ ላይ እያለ ነበር ሴምን፣ ካምንና፣ ያፌትን የወለደው። በኖኅ የህይወት ዘመን የሠው ልጆች በክፉ ስራቸው አማካኝነት አምላካቸውን በእጅጉ ሲያስከፉት ከምድረ ገፅ ሲያጠፋቸው ተገደደ። ነገር ግን ኖኅ ፍፁም ጥሩ ሠው ሆኖ ተገኝቶ ነበርና ከጥፋት ውሃ ይድን ዘንድ የፈጣሪ መልካም ፈቃድ ሆኖ መርከብ እንዲሠራ ታዘዘ።

መርከቢም 300 ክንድ ርዝመት፣ 50 ክንድ ወርድና፣ 30 ክንድ ከፍታ ያላት ሆና፣ በሮች እና መስኮቶች ያሏት ባለ 3 ደርብ የነበረች ስትሆን፤ ኖኅ ሚስቱን፣ ልጆቹንና የልጆቹን ሚስቶች እንዲሁም ከሁሉም አይነት ጥንድ ጥንድ እንስሣትን ይዞ በመርከቢ ተጠለለ።

ከዚህ በኋላ የምድር ቀላያት ፈንድተው፣ የሠማይ መስኮቶች ተከፍተው ለ40 ቀንና ለ40 ሌሊት በወረደ ውሃ ምድር ስትጥለቀለቅና ፍጥረቶች ሁሉ ሲጠፉ፣ የኖኅ መርከብ ወዲያ ወዲህ እያለች ስትንሣፈፍ ቆይታ ውሐው ሁሉን አጥፍቶ ሲጨርስ ከምድር ላይ እየነጠፈ በመሔዱ መርከቢ "አራራት" በተባለ ተራራ ላይ አረፈች። ኖኅና ባለቤቱ እሜቴ አይከል፤ እንዲሁም ሦስቱ ልጆቹ ሴም፣ካም፣ ያፌት ከነሚስቶቻቸው እንስሶችን ጨምሮ ከመርከቢ ወጡ። ኖኅ ከነቤተሠቦቹ በመትረፉ እጅግ ተደስቶ ለአምላኩ ምስጋናና መስዋዕት አቀረበ። ፈጣሪም በኖኅ መስዋዕት ደስ ተሠኘ።

ከዚህ የጥፋት ውሃ በኋላም አምላክ በድጋሚ የጥፋት ውሃ የሠው ልጆችን ላለማጥፋት ወሠነ። ለዚህም ቃል ኪዳኑን በሠማይ ላይ የደመናውን ሁበረ ቀስት ዘረጋ። ማለትም በእርሡና በሠው ልጆች መካከል ስላደረገው የምህረት ቃል የቃል ኪዳን ምልክቱን በሠማይ ላይ አኖረ።

ከላይ የሠፈሩትን እውነታዎች ቅዱሣት መፃህፍት ሲያረጋግጧቸው የተለያዩ የአገራችን ፀሃፍት ደግሞ መፅሃፍ ቅዱሡንም፣ ትውፊቱንም፣ በተለያዩ ጊዜያቶች የተገኙ ታሪካዊ ሠነዶችንና በዙሪያችን ያሉትን ማህበረሠቦች፣ ቋንቋ፣ ባህል እምነት፣ እንዲሁም ዛሬ ድረስ የሚገኙ ታሪካዊ ቦታዎችን መሠረት በማድረግ ሁሉም የየበኩላቸውን እያሉ በመቀጠል የኖኅን ጉዳይ ዳር ያደርሡታል።

እነዚህን ነጥቦች በውል እሡናስለን ስንቀጥልም ነው የታሪካችን መነሻ መንገድ ለደብተን የምናውቀው። "የቃል ኪዳን ምልክቱን በሠማይ ላይ አኖረ" ይላል ቅዱስ መፅሃፉ። ያሬድ ግርማ ሃይሌ "የጎንደር ታሪክ" ብሎ በሠየመውና በ1999 ዓ.ም ባሣተመው መፅሀፉ ደግሞ ሌሎች ዋቢዎችን ጠቅሶ ይቀጥለዋል።

" ኖኅ ከነቤተሠቦቹ በመትረፉ ተደስቶ ለፈጣሪው መስዋዕት አቀረበ። ፈጣሪም በኖኅ መስዋዕት ተደስቶ ለአዳምና ለዜዋን የነሣቸውን ምድር

እንዲወርስ ወደደ። "የሰው ልጆችን ከእንግዲህ አላጠፋም" የሚል ቃል ኪዳኑን ጉብቶ ለቃሉ ማረጋገጫ ቢደመና ቀስቱን አኑሮ በማመልከት ወደ ግዮን መንሻ " አበሜሌክ" ማለትም ጣና ሐይቅ አዳምና ሄዋን ባጠፉት ጥፋት ተባርረው እየሩሣሌም ከመኖራቸው ቀደም ብሎ ይኖሩበት እንደነበር በሚታመነው ቦታ እንዲሔድ አዘዘው። ኖህም ሴምንና ያፌትን ትቶ ካምን ይዞ ወደ ኢትዮጵያ /አፍሪካ/ መጣ።" ይላል።

ኖኅ በመፅሃፍ ቅዱሱ መረጃ መሠረት ሶስት ልጆቹን ሲወልድ እድሜው 500 ዓመት የነበረ መሆኑ እንዳለ ሆኖ፣ ምድር በጥፋት ውሃ ስትጥለቀለቅ ደግሞ ኖኅ እድሜው 600 ሞልቶ ነበር። በዚህ መሠረት በ"መግቢያችን" ላይ እንዳየነው የሰው ልጅ ታሪክ 5500 ዓመት ተብሎ የተወሰነው ከአዳም ጀምሮ ነው። በ"መግቢያችን" ላይ እንዳየነውም ከአዳም እስከ ኖኅ 10 ትውልድ ይቆጠራል ብለናል። 9ኛው ላሜህ ነው። ስለዚህ ከአዳም እስከ ላሜህ ድረስ 1656 አመታት አልፈዋል። ከዚህ ውስጥም ኖኅ ከጥፋት ውሃ ሲተርፍ 600 አመት ሞልቶታልና ህይወት እንደ አዲስ የቀጠለው ከ3844 ቅ.ል.ክ. ጀምሮ ነው።

ኖኅ የመርከብ ስራውን ለማጠናቀቅ 100 አመት ፈጅቶበታል። (120 አመት የሚያደርሱትም አሉ) ሶስቱ ልጆቹ የተወለዱት ከጥፋት ውሃ በፊት ኖኅ የ500 አመት ጎልማሣ በነበረበት ጊዜ ስለሆነና፣ "የልጆቹ ሚስቶችም አብረው ወደ መርከብ ገቡ" ስለተባለ ለአቅመ አዳም የደረሱ ልጆች እንደነበሩ እንረዳለን።

ከጥፋት ውሃ በኋላ ኖኅና ባለቤቱ፤ እንዲሁም ሶስቱ ልጆቹ ከነሚስቶቻቸው ከመርከብ ሲወጡ ሴም የ130 አመት ጉብል ወጣት ነበር። ጠይም ልጁ ካም የ120 አመት ልጅ እግር ነበር። ትንሹ ልጁ ያፌት የ100 አመት እምቦቀቅላ እንደነበር ይታመናል። ኖኅ ከ3844 ቅ.ል.ክ እስከ 3500 ቅ.ል.ክ ድረስ ለ350 አመታት ያህል የቤተሰቡ አለቃ ሆኖ ኖረ። መተዳደሪያውም ግብርና ነበር።

ከጥፋት ውሃ በኋላ ኖኅና ቤተሰቦቹ ምድርን ይሞሏት ዘንድ ፈጣሪ ሲፈቅድም ሴምና ያፌት ሁለት እህቶቻቸውን ይዘው ሲባዙ፤ ኖኅ ባለቤቱንና አንድ ልጁን ካምን ይዞ እንደመጣ ነው የሚታመነው። ይህም ሲባል "መርከቧ እዚያኛው አራራት ተራራ አረፈች" ብለው በሚያምኑ ፀሃፍት ዘንድ ሲታሰብ ነው። ወደፊት ባሉ ተከታታይ ምዕራፎች አንድ ድምዳሜ ላይ እስክንደርስ ይህንኑ እምነት ይዘን እንቀጥላለን። ምክንያቱም ኖኅ ካምን ይዞ ወደዚህ ሲመጣ የሚችለው መርከቧ በእስያው አራራት ተራራ ካረፈች ነው። በኢትዮጵያው አራራት ተራራ ካረፈች ግን ሴምና ያፌት ከዚህ ተመርቀው ተሸኙትው ካምና ኖኅ እዚሁ ሲቀሩ ልናይ ስለምንችል ነው። ለማንኛውም ግን ለጊዜው ሴምና ያፌትን ትቶ ካምን ይዞ መጣ የሚለውን ይዘን እንጓዝ።



ኖኅ በዚች አገር እየኖረ ሳለ ባለቤቱ እሜቴ አይክል ሞተበት። የሞተችም ከጎንደር በስተምዕራብ በኩል በምትገኘውና ከከተማው 37 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ባለችው "ጭልጋ" ተብላ በምትጠራው ምድር ነበር።

ጭልጋ ውስጥ እሜቴ አይክል የተቀበሩበት መቃብር እንደሆነ በሚታወቀው ቦታ ላይም ትልቅ ዛፍ በቅሎበት እስከ ዛሬ ድረስ የ"ቅማንት" ብሔረሰቦች ፀሎታቸውን ያደርሱበታል። የመቃብራቸው ሃውልትም ዛሬ ድረስ ጭልጋ/አይክል/ ውስጥ ይገኛል።

በዚህ ታሪክ መነሻነትም የጭልጋ ዋና ከተማ በስማቸው "አይክል" ተብሎ እንደተሰየመ ዛሬ ድረስ ይጠራል። አቶ ዮሃንስ ወልደማርያም "የዓለም ታሪክ" በተሰኘውና በ1936 ዓ.ም በታተመው መፃሀፋቸው " በኢትዮጵያ 25 የካም ልጆች (ነገዶች) ተከታትለው መንገሣቸውን ይገልፁና "የቅማንት ብሔረሰብ ምንጭም ከካም መውረዱንና ተወራርሶ መቆየቱን፣ ቅማንት የሚለው ቃል መሠረታዊ አመጣጡ "ክም" "ክንት" ማለትም "አንተ ካም" ከሚለው የመጣ እንደሆነ" ይገልፃሉ።

በመሆኑም እነዚህ በጭልጋ /በአይክል/ እና በዙሪያው የሚኖሩ ህዝቦች የካምን ባህል፣ እምነት፣ ቋንቋ... ወዘተ.. ሳይበርዙና ሳይከልሱ ይዘው ይገኛሉ። የሠንበት ቀናቸውም ቅዳሜ ነው።

ወደ ኖኅ ታሪክ ስንመለስና ቀደም ሲል የጠቀስነው "የጎንደር ታሪክ" የሚለው መፅሃፍ ደግሞ እንዲህ ይለናል "ኖኅ ባለቤቱ ከሞተችና ከቀበራት በኋላ የቀረችውን ጥቂት ዘመን ኖሮ (እንደሁሉ አገላለፅ በ850 አመቱ፣ እንደዚህ መፅሃፍ በ950 አመቱ) በአሁኗ የጎንደር ከተማ ሲሞት በመቃብሩ ላይ ምንጭ ፈልቆ በርካታ ሰዎችን ይፈውስ ነበር። ከዚያም ለኖኅ መታሰቢያ ይሆን ዘንድ አምላክ በቤተመንግስት አጣቦ የኖኅ የመቃብር ሃውልት እንዲታነፅ ፈቀደ። ይህም በኋለኛው ዘመን በንጉሥ ፋሲለደስ የታነፀው የፋሲል ግንብ ነው።" (የፋሲል ግንብን ታዓምራዊ አሠራር ዘመኑ ላይ ስንደርስ እናየዋለን)

ኖኅ ከ3844-3500 ቅ.ል.ክ ለ350 አመታታ ቤተሰቡን ሲመራ፣ በተመሣሣይ አገላለፅ ኢትዮጵያን ሲያስተዳድር ኖሮ ሲሞትም ልጁ ካም ተተክቶ ቤተሰቡንና አገሩን መምራት፣ መግዛት ቀጠለ።

የኖኅ ልጅ ካም ከ3500 ቅ.ል.ክ ጀምሮ ሲያስተዳድር ቆይቶ ሲሞት ልጁ ኩሽ ተተክቶ ከ2787-2545 ቅ.ል.ክ ድረስ የማስተዳደር ተግባሩን ተወጥቷል። ከኖኅ ሶስት ልጆች አንዱ የሆነው የካም ነገድ በአፍሪካ ምድር እየተባዛና እየተስፋፋ ሄዷል።

"ኖኅ"ሲባል የቃል ኪዳኑ ምልክት አብሮ ይነሣል። "የጥንቷ ኢትዮጵያ ትንሳኤ ታሪክ" የሚል ርዕስ ያለውና በመሪ ራስ አማን በላይ በ1986 ዓ.ም የተፃፈው መፅሃፍ ውስጥ እንዲህ የሚል ነገር የተካተተ ሲሆን፣ የቃል ኪዳኑንና የቀስተደመናውን ሁኔታ ከሠንደቅ ዓላማችን ጋር አመሣክሮ ከማስረዳት ጎን ለጎን እነ ኖኅ ስለ ፈለጡት ምድርና ስለጠጡት

ውሃ... ወዘተ የማስረዳት ብቃት ስላለው እንጠቀምበታለን። ፀሐፊው በደርግ ዘመን በጥንቷ የኢትዮጵያ መናገሻ ከተማ በ"ደንጎላ" በድንጋይ ግግር ውስጥ የተቀመጠና በኋለኛው ዘመን በ"ሰብ" ቋንቋ የተፃፈ ሰነድ አግኝተው ወደ አማርኛ ወስደው እየዘገኑ በመተርጎም ከ6 በላይ ትልልቅ መፃህፍት ሊፅፉ የቻሉ ናቸው። እናም ከጉዳያችን ጋር የሚሄደውን መርጠን ስናይ፦

“በ4000 ዓ.ዓ የኢትዮጵያን ግዛቶችና አፍሪካን በሙሉ እስያን ጨምሮ ይገዛ የነበረው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገስት ይገዛቸው ለነበሩ ህዝቦችና አገሮች ሁሉ መተዳደሪያ የሚሆናቸው ህግ ደንግጎ በሶስት ክፍል የተከፈሉና ሃያ ስምንት አንቀፆች ያሉት አዋጅ አውጥቶ በብራና ላይ በ"ሰብ" ቋንቋ ፊደል አፅፎ ለሁሉም እንዲታደል አድርጓል።

በዚህ አዋጅ በአዋጁ ሶስተኛ ክፍል ስለሠንደቅ ዓላማ የተደነገገው እንዲህ ይላል።

አንቀፅ 22 "ህያው አምላካችን ለአባታችን ለኖኅና ለልጆቹ፣ለኛ፣ እንዲሁም ለፍጥረቶች ሁሉ እንዲህ አለ። "በእኔና በእናንተ መካከል ለዘላለም የማደርገው የቃል ኪዳን ምልክት ይህ ነው። ቀስቴን በደመና አድርጌያለሁ። የቃል ኪዳኑም ምልክት በእኔና በምድር መካከል ይሆናል። ከምድር ላይ ደመናን በጋረድሁ ጊዜ ቀስቲቱ በደመና ትታያለች" እኔም ዛሬ በህያው አምላኬ ፈቃድ፣ በአባቶቼ ዙፋን፣ በረገጡዋት ምድር፣ ባረፉባት መሬት፣ በቀመሡትና በተጠቀሙበት ውሐ ድንበር ሆኘ ይህን ለዘላለም የሚሆን በህዝቡና በመንግስት መካከል ያለውን የፍቅር ምልክት ዓላማ በከፍታ ቦታ ላይ ሠቅዬ አውለበልብላችኋለሁ። አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ሠማያዊ ቀለም መሆኑ፤ አረንጓዴው ምድራዊ፣ ቢጫው የፍቅር አበባ፣ ሠማያዊው ደግሞ የሠማያውያን መንፈሣዊ አካል እንዳለን የሚገልፅ ምልክት ነው። ይህን ዓላማ አይቶም ሆነ ሠምቶ ያላከበረና ያላመነን ባሪያ ሆኖ እንዲኖር በህግ ተደንግጓል።

አንቀፅ 23 “ማንኛውም ንጉሠነገስቱን የሚገልፅ ሠንደቅ ዓላማ በፊቱም ሆነ በኋላው ሊሠቀል ይችላል። ነገር ግን ከማድረጉ በፊት ለንጉሠ ነገስቱ ቀለሙን ማሳየትና ማስመረጥ አለበት። ይህን ሳያሣውቅ ቢሠቅል ከመንግስቱ እንዲወርድ ማድረግ፤ ባይወርድ እንዲገደል በህጋችሁ ተደንግጓል።

አንቀፅ 24 “የአጼው/የንጉሡ/ የሠላም ሠራዊትና የጦር ሠራዊት ዓላማ ከንጉሠ ነገስቱ በታች ስንት ንጉሶች እንዳሉት የሚገልፅ የተሸነሸነ ዓላማ በፊትና በኋላቸው አስይዘው እንዲሄዱ በህጋችሁ ተደንግጓል።

አንቀፅ 25 "በሠንደቅ ዓላማው አምድ ላይ ከወርቅ፣ ከብር፣ ከነሃስም የተሠራ የኮከብ ቅርፅ ማስቀመጥ አለበት። ይህንን ሳያደርግ ሠንደቅ ዓላማ የሠቀለ በአደባባይ እንዲሠቀል በህግ ተደንግጓል።"የሚሉት ይገኛሉ።

ኖኅን በሚመለከት ቋንቋን፣ ባህልን፣ ብሔረሠቦችን፣ ታሪካዊ ቦታዎችን፣ በፅሁፍ የተገኙ ሠነዶችን፣ ትውፊታዊ መረጃዎችን... መሠረት



ባደረገ መነሻ ይሄን ያህል ተንደርድረናል። “አይበቃም” ካልን ወደ ራሣችን ተጨማሪ ጥረት እንሄድና የማይገናኙ የማይተዋወቁ የሚመስሉ፤ ነገር ግን ተስማሚ የሆኑ ዓለማዊና መንፈሣዊ ፅሁፎችን አገጣጥመን አጠንክረነው እናልፋለን።

ኖኅ የመርከብ ስራውን ካጠናቀቀ በኋላ ከፈጣሪው ዘርዘርና ሠፋ ያሉ ትዕዛዞች ደርሠውታል። ከእነዚህ ውስጥም “... ከንፁህ እንስሳት ሠባት ሠባት ተባትና እንስት፣ ንፁህ ካልሆነ እንስሳም ሁለት ሁለት ተባትና እንስት፣ ከሠማይ ወፍ ደግሞ ሠባት ሠባት ተባትና እንስት እያደረግህ በምድር ላይ ለዘር ይቀር ዘንድ ለአንተ ትወስዳለህ..” (ዘፍጥረት ም.ዕ. 7 ከቁ 1-4) ይህ ሃተታ ሠፍሮ ሲገኝ፤ በሌላ በኩል ደግሞ በኢትዮጵያ ብሔረሠቦች ጥናት ኢንስቲቲዩት ዋና የታሪክ ኤክስፐርት የሆኑት/የነበሩት/ የያኔው ዶ/ር የአሁኑ ፕ/ር ላጲሶ ጌድሌቦ “Ethiopia a credil of History” ብለው በሠየሙት ጥናታዊ መፃህፋቸው እንዳሠፈሩት... “በሌላው ዓለም በየትኛውም ቅስፍራ ወይም "ምድር" በተባለችው ኘላኔት ላይ በየትኛውም ገርና አህጉር የማይገኙ ሠባት አጥቢ እንስሣት በኢትዮጵያ ምድር ይገኛሉ" ። በትክክል እንደዚያ ነው። እነዋሊያ፣ እነ ቀይ ቀበሮ፣ እነ ቆርኪ፣ እ ጭላዳ ዝንጀሮ.. እዚህ ናቸው። (... መቸም ዋሊያ ያንን የሚያክል ቀንድ ይዞ.. ቀይ ባህርን ዋኝቶ መሄድም፣ መምጣትም የማከብደው ይመስላል። ሠው ይዟቸው መጣ እንዳይባል ጭላዳ ዝንጀሮ እየነዳ የሚመጣ ነገድ አይኖርም...) ሌሎች ከሀገር መውጣት የማይችሉ እንስሶችም የሚገኙት በዚች ምድር ነው። ይሄው የዶ/ር ላጲሶ የ1983 ዓ.ም ጥናት "ኢትዮጵያ 239 አይነት አጥቢ እንስሣትና 832 የወፍ ዝርያዎች ሲኖሯት፤ ከእነዚህ መካከል ሠባት አጥቢ እንስሣትና 24 ወፎች በኢትዮጵያ ምድር ብቻ የሚገኙ ናቸው።" ይበል እንጂ ከዚያ ጊዜ በኋላ ደግሞ አዳዲስ እንስሶች፣ አእዋፍትና እፅዋት እየተገኙ ባሁኑ ሠዓት በአገር አቀፍ ስታትስቲክስ መረጃዎች መሠረት 31 ጡት አጥቢ የዱር እንስሣት በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ መሆኑ ሲረጋገጥ፤ ከእነዚህ ውስጥ 7ቱ በሠሜን ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ ውስጥ ይገኛሉ። ከ24ቱ 13ቱ አእዋፍትም በዚያው የነዋሊያ መኖሪያ በሆነውና ከኢትዮጵያ 1ኛ ከአፍሪካ 4ተኛ ደረጃ ላይ በተቀመጠው የከፍታ መጠኑ 4620 ሜትር በሆነው በራስ ደጀን ተራራ ሠፍረው ይገኛሉ።

ከሠሜን ተራሮች ውስጥ ከፍተኛው ተራራ የሆነውን ራስ ደጀንን ፀሃፍት ሲገልፁት "የተራሮች ራስ፣ ቁንጮ፣ የራሶች ደጀን፣ ጋሻ፣ በተፈጥሮ የታነፀ፣ ያለ፣ የነበረ፣ የሚኖር፣ ማንም የማይገሰሠው የማይከልሠው፣ ህያው ሆኖ ፀንቶ የሚኖር" በማለት ነው።

ምናለ የተራራው ስም አራራት ቢሆን ልንል አይገባም። የጣናው አራራት ተራራ በቂ ነው። ታላቁ መፅሃፍም ቢሆንኮ ውሃው ወደ ላይ 15 ክንድ ከፍ ከፍ አለ ተራሮችም ተሸፈኑ አለ እንጂ ሌላ አልወጣውም።

ለማንኛውም ግን ሁኔታዎቹ ባየነው መልኩ በደንብ የሚገናኙ እንጂ እንዲሁ የሚታለፉ አይደሉም። እነዚህን የመሣሠሉ ነባራዊ ሁኔታዎችም ናቸው ይችን አገር "ሚስጥር" እያሠኟት ያሉት። ኖኅን የሙጥኝ ብለው የቀሩ እንስሶች ናቸው ከማለት ውጪ ሌላ ምን ሊባል ይችላል?

እኔና እናንተ ችግር የለብንም። ለየብቻቸው ምዕራፍ ተሠጥቷቸው ባጭር ባጭሩ የሠፈሩ ታሪኮች ከጥቂት ገፆች በኋላ ተለቃልቀው ወደ አንድ እቃ ሲገለበጡ የኖኅ መርከብ በየትኛው አራራት ተራራ እንዳረፈች ለስምንረዳ ግድ የለም። አሁንም ገና አልወሠንንም። ታሪኩ እስኪያስወስነን እንጠብቃለን። ነገር ግን የታሪክ ሽሚያ በባዕዳኑ ዘንድ (ሁሉንም አንልም ብዙዎች ዘንድ) በእጅጉ ይንፀባረቃል። የኖኅ መርከብ በእስያው አራራት ተራራ እንዳረፈች ለማሣመን ብዙ ተጥሯል። ዛሬ ድረስ "የመርከቧን ስብርባሪ አገኘን" የሚል ዜና ይደመጣል። ቀደም ካለው ጊዜ ጀምሮ ሲባል የኖረ ነው። ሁለተኛው ማስረጃቸው የተራራው ስም እና ከፍተኛነቱ ብቻ ነው። ሌላ ነገር ቆጥረው ሊያሣምኑን አይችሉም። እኛ ግን እየቆጠርን ያለነው የጣውላ እድሜ አይደለም። የእንጨት እድሜ አይደለም። የነበረን፣ ያለን፣ የሚኖርን ነገር ነው። ከኖኅ ታሪክ ጋር የሚገናኝ ሆኖ እነሡ ጋ ኖሮ እኛ ጋ የሌለ አንድም ነገር የለም። እኛ ጋ ያለ እነሡ ጋ የሌለ ካልሆነ በቀር። ዓለማችን ካየቻቸው ግዙፍ የታሪክ ሽሚያዎች ቁጥር አንዱም ይኼ ነው።

ከኖኅ ታሪክ ጋር በተያያዘ መንደርደሪያችን እንደቀጠለ ነው። በተንደረደርን ቁጥር እየገፈተርናቸው ብንቀጥል በጥላቻ ሊተረጎም አይገባም። መንገዳችንን እያስለቀቅን ነው። በእነርሡ ዘንድ የኖኅ መርከብ በጥቁሮች አገር አታርፍም፤ ልታርፍም አትችልም ተብሎ ይታሠባል። በእነሡ ዘንድ ጥቁር ምንጊዜም ጥቁር ነው። ጨለማ። የችግርና የሠቆቃ ምንጭ ብቻ ነው። የመልካም ታሪክ ባለቤት ሆኖ ሲያዩ አይናቸው ደም ይለብሣል። ከኖኅ ልጆች አንዱ የሆነው ካም ጠይም የቀዳ ቀለም እንደነበረው ግን ያምናሉ። ያም ቢሆን ጥቁር ሆኖ እስከተገኘ ድረስ የምንም አይነት ነገር ባለቤት ቢሆን ምንም ሆኖ እንዲቀር ይፈልጋሉ። ነገሩን ሁሉ ከቀለም ጋር ያያይዙታል። ስለቀለም ካነሣን አይቀር እንዴት እንዳቀለሙን አይተን እንለፍ።

ስለ ኖኅ ታሪክ በሚተረክበት በቅዱስ መፅሃፉ በዘፍጥረት ምዕ5 ከቁ 8 ጀምሮ እስከ 11 "... ርግብንም ውሃው ከምድር ፊት ቀልሎ እንደ ሆነ እንድታይ ከእርሡ ዘንድ ሠደዳት። ነገር ግን ርግብ እግሯን የምታሣርፍበት ስፍራ አላገኘችም። ወደ እርሡም ወደ መርከብ ተመለሠች፤ ውሃ በምድር ላይ ሁሉ ስለነበር እጁን ዘረጋና ተቀበላት፤ ወደ እርሡም ወደ መርከብ ውስጥ አስገባት። ከዚያም በኋላ ደግሞ እስከ 7 ቀን ቆዬ፤ እርግብንም እንደገና ከመርከብ ሠደደ። እርግብም በማታ ጊዜ ወደ እርሡ ተመለሠች፤ በአፏዋም እነሆ የለመለመ የወይራ ቅጠል ይዛ ነበር"። ይላል።

ከዚህ ታሪክ ጋር በተያየዘ ነው እርግብ የሠላም ተምሣሌት የሆነችው። ይህንንም ይዘው እነ ፖብሎ ፒካሶ እርግብን አሣምረውና



የለመለመ የወይራ ቅጠል አስነክሰው በመሣል የሠላም አርማነቷን አፀደቁ። ስለዚህ ቀደምት ሠዓሊያን በዚህ ታሪክ ያምናሉ ማለት ነው። ነገር ግን መሣሎቻቸው ቀደምት ሠዓሊያን እነ ማይክል አንጀሎን የመሣሠሉ ካለፉ ጥቂት ምዕተ አመታት ያለፉቸው እንጋፋ የቀለም ሠዎች የታላላቅ ነገስታትን ቤተ መንግስትና የየአገሩን ቤተመቅደስ በመንፈሣዊ ስዕሎች ሲያሽበርቁ የሌለን ነገር ፈጥረው ነጭን የፈጣሪና የመላዕክት አምሣያ ጥቁርን የሠይጣን አምሣያ፤ አድርገው ስለው አፀደቁ። "ሠይጣን በጨለማ ስለሚመላለስ፣ ፈጣሪ ብርሃን ስለሚመሠል ነው" ብለው ሊከራከሩ ሞከሩ። "ጨለማም ብርሃንም "ይሁን" ተብሎ የሆነ ነው። ሠይጣን በጭለማ ብቻ ሣይሆን በቀንም ይመላለሣል። አስተሣሠቡ ነው ጭለማ፣ ብለው ሞገቷቸው። "የተገፈፈው ክብሩ እንጂ መልኩ አይደለም፤ መልኩና ቀለሙ የያኔው ሣጥናኤል ይባል በነበረበት ዘመን የነበረው አይነት ነው" አሏቸው። "ስለዚህ የግድ ፊቱን በጥቁር ከመመሠል ለምን እንደማንኛውም አይነት መልክ ያለው አድርጋችሁ ስላችሁ ስታበቁ ያንኑ መልክ እንደያዘ በጭለማ ሲመላለስ አትስሉትም?" ተባሉ፤ በጥቂት ጥቁር ተሟጋቾች። አልቻሉም ወይም አልፈቀዱም። ስለዚህ ነጮች በምንም መልኩ ቢሆን ጥቁር የበላይ እንዲሆን አይፈልጉም። በስዕልም ቢሆን! ከጥንት ጀምሮ የነበረ ታሪክ ቢሆንም፤ በተለይ በመካከለኛው ዘመን ተባብሶ ቀጠለና ጥቁር ላይ በህብረት ተዘመተ። የምንም ነገር ምንጭም፣ ፋንጭም ሆኖ እንዳይታይና እንዳይገኝ በጣም ይጠነቀቃሉ። ከግራ ከቀኝ ታሪኮችን ሲዘርፉ ኖረዋል። ከዚህ አንፃር የታሪክ ሽሚያው መጧጧፉና የኖኅን የመርከብ እንጨት መስቃቀማቸው ሊገርመን አይገባም ነው ጉዳዩ። እንጂ... ከሆነ ይውሠዱት።

"... በኖኅ እድሜ በስድስት መቶ አንድ አመት፣ በመጀመሪያው ወር ከወሩም በመጀመሪያው ቀን ውሃው ከምድር ላይ ደረቀ። ኖኅም የመርከቢቱን ክዳን አነሣ። እነሆም ውሃው ከምድር ፊት እንደደረቀ አዬ።" ቁ 13

የኢትዮጵያ የዘመን መለወጫ ወይም አዲስ አመት መነሻው ይኼ ነው። መድረሻውም ጭምር። "መድረሻው" ሲባል ቋሚነቱን ለማመልከት ነው። በሌሎች ጃንዋሪ 1 በኛ መስከረም አንድ መባሉና ይኼ የኋለኛው ዘመን የ7/8 አመት እንቅደም ግኝትን መሠረት አድርገን አይደለም ኢትዮጵያ የራሷ የዘመን አቆጣጠር አላት የምንለው። ነገር ግን ዋናው ምንጩ ቅ.ል.ክ ከ3 ሺ. አመት በፊት በነበረው ጊዜ ዓለም ገና ከጨረቃ አቆጣጠር ሣይወጣ፣ ግብፃውያን የፀሃዩን አቆጣጠር ሣኙት (365 ቀን) አገኙ ከመባሉ በፊት ኢትዮጵያውያኑ ይጠቀሙበት የነበረ ነው። ይህ አቆጣጠር ከኢትዮጵያ ወደ ግብፅ የሄደ መሆኑን ወደፊት እናያለን።

በእርግጥ የፀሃይ አቆጣጠር በዘመናዊ መንገድ ተሠልቶና ተከትቦ ለዓለም ይፋ የሆነው በግብፅ አማካይነት ነው። ኢትዮጵያውያኑ ግን በባህላዊ መንገድ ይጠቀሙበት ነበር። የተለየ ነገር የለውም፤ የፀሃይ አቆጣጠር ሲባል አመቱን በ4 በመክፈል ክረምት፣ በጋ፣ በልግ፣ ፀደይ ማለት ነው። እነ ኖኅ

ለግብርና ብቻ ይጠቀሙበት ነበር። "... በምድር ዘመን ሁሉ መዝራትና ማጨድ፣ ብርድና ሙቀት፣ በጋና ክረምት፣ ቀንና ሌሊት አያቋርጡም።" ይላል ዘፍ 8 ቁ 22። ከጥፋት ውሃ በኋላ ኖኅ ለፈጣሪው መስዋት ሲያቀርብ ፈጣሪ ያለው ነው። ከዚሀ ቃል በኋላ ነው ህይወት እንደ አዲስ የሚጀምረው። "በእጃችሁ ተሠጥተዋል.." ይባላሉ ኖኅና ልጆቹ" ሁሉንም ነገር። ከዚህ ቃል በኋላ ነው ኖኅ ገበሬ መሆን የጀመረው። ይህ ከፍልፋይ ነው ወደ ቁጥር ተሰውጦ የምናየው። እናም የነ ኖኅ ማሪፊያ በነበረችው ቦታ የዘመን መቁጠሪያ ቢኖር ባይኖር ለውጥ አልነበረውም። የዓመት መቁጠሪያ ጫፉ የመጀመሪያው ዓመት፣ የመጀመሪያው ወር፣ የመጀመሪያው ቀን መስከረም አንድ ተጨብጧል። እሡ (ብራው) ከታወቀ ሁሉም ቀላል ነው። እሡን ጊዜ መሠረት ባደረገ መልኩ መቁጠር ነው። ማረስ፣ መዝራት፣ማጨድ፣ መከመር መውቃት ነው። መስከረም መግባቱን ለማወቅ ከዚህም በላይ ጥርት ያለ የማወቂያ መንገድ ነበራቸው። አሁንም አለ። መነሻውም መድረሻውም ለማለት የተደፈረው ከዚህ በመነሣት ሲሆን፤ እሡም አደይ አበባ ነው።

ዓለም እቀፍ የስነእፅዋት ተመራማሪዎች ሁሉ ያመኑበት እውነት፣ ግራ የተጋቡበት፣ ሊደብቁት የማይችሉት የሆነ ጉዳይ ነው። ኢትዮጵያ የሚበቅለው የአደይ አበባ ዝርያ በየትኛውም የዓለም ክፍል አይበቅልም። በአየር ብክለት የተፈጥሮ ሚዛን እስካልተዛባ ድረስ አደይ አበባ ኢትዮጵያን ቀጥሯት አይጠፋም። ሀዓቱንም አያዛንፍም። እርግጥ ቀጠሮ ነው ያላቸው። የኢትዮጵያ ቀደምት ካላንደር ይሄ ነው። የራሷ የዘመን አቆጣጠር ይሄ ነው። ስሙም መስከረም ነው። መጀመሪያ ማለት ነው። መደቡ ነጭ በሆነ ወረቀት የተፃፈ የዘመን መቁጠሪያ አይደለም። መደቡ ቢጫ ነው፤ "የፍቅር አበባ" ይሏል ይሄ ነው።

ይችን ሀገር በሚመለከት ከዚህም ያለፈ ብዙ ብዙ የሚባል ነገር አለ። እንደተባለውም ይሄን የሚሣሠለው እውነታ ነው ኢትዮጵያን "ሚስጥር፣ እንቆቅልሽ፣ እረቂቂ አገር እያሰኛት ያለው። በርግጥም ያስብላል። ቢሆንም በየገጹ "ሚስጥር ናት" እያልን መቀጠል ይከብዳል። ጊዜውም ቦታውም አይኖረንም። ብዙ ሚስጥር ነዋ ያለው። ስለዚህ ልዩ አገር በመሆኗ ለመስማማት ያህል ከኖኅ ታሪክ ወጣ እንበልና ጥቂት ነገሮችን በዚህ ምዕራፍ ጠቀስ ጠቀስ አድርገን ወደን ካም ኩሽ ዘመን እንሄዳለን።

በፈጣሪ እጅ ተፅፎበት ለሙሴ የተሠጠው ፅላት እዚህ ነው። የኢየሱስ ግማደ መስቀል አንድ አካል እዚህ ነው። በአፍሪካ የመጀመሪያው መስጊድ እዚህ ነው፣ የመጀመሪያው መንፈሣዊ ዜማና ሽብሸባ የሄደው ከዚህ ነው፣ ነብዩ መሐመድ ወገኖቻቸውን የላኩባት አገር ናት፣ የራሷ ብቻ የሆነ ጤፍ የተባለ ምግብ የሚሆን ሠብል የሚበቅልባት፣ እንጀራ በወጥ የሚበላባት ልበል ይሆን?

እንደ ፕ/ር ላጲሶ ጥናት ኢትዮጵያ የግሏ ከሆኑ የተፈጥሮ ቅርሶቿ ውስጥ አፅም የማያበሠብሡ የአፈር አይነቶች፣ የተፈጥሮ ድልድዮች፣ 13ቱ



ፀሃያማ ወራት፣ ካመት እመት አረንጓዴ ለብሶ የሚታየው ልምላሜ፣ ጤናማ የአየር ጠባይና ፍቱን የተፈጥሮ ፍል ውሃዎች፣ ነፋሻማ ኮረብታዎቿ፣ አይን የሚማርኩና መንፈስን የሚመስጡ ሸለቆዎቿ ኢትዮጵያን የመልክዓ ምድር እንቆቅልሽ አድርገዋታል። ከራስ ደጀን ከፍተኛ ተራራ ጫፍ ጀምሮ ከባህር በታች እስከ ዳሉል የእሣተ ገሞራ አዘቅት መካከል የሚገኘው የመልክዓ ምድር ገፅታዎቿ "የአፍሪካ ጣቤት "(እኛ የዓለም እንላለን) ወይም የአፍሪካ ሲዊትዘርላንድ" አሠኝተዋታል። የኢትዮጵያ ስምጥ ሸለቆ ሐይቆች የልዩ ልዩ አእዋፍና የዱር እንስሳት መናህሪያዎች ናቸው። የአፍሪካ ጣራ /roof of Africa/ በሚል ስም ያስጠራትና እንደሠንሠለት የተቆላለፉ የሠሜንና ባሌ ተራራዎች "የአፍሪካ የውሃ ምንጭ" ወይም "የምስራቅ አፍሪካ የዝናም መጋዚ" እየተባለች በልምላሜ እንድትደነቅ አድርገዋታል።

"የኢትዮጵያ ህዝብ አብይ መተዳደሪያ እርሻ ሲሆን በአፍሪካ አህጉር በቀንድ ከብት ብዛት ተወዳዳሪ የማይገኝለት ምናልባትም በሬ ጠምዶ የማረስን ስልት ለሌሎች ያስተዋዋቀ ቀዳሚ ህዝብ እንደሆነ ይታመናል።... ለእርሻ ተስማሚ የሆነ ለም አፈር፣ ልዩ ልዩ አዝርዕትን ለማብቀል ምቹ የሆነ የአየር ፀባይ፣ የተለያዩ የከበሩ ማዕድናት የሚገኙባት ምድር ናት" ( ፕ/ር ላጵሶ 1983 ዓ.ም) ።

ለማንኛውም የእሜቱ አደከል የመቃብር ሃውልት፣ በሰባ ቋንቋ ተፅፎ የተገኘው ዓጥጅና የአዋጁ ቃላቶች፣ የኖኅን ልጅ የካምን ባህል ይዘው በጭልጋ የሚኖሩ ብሔረሠቦች መኖር፣ በየታሪክ ነገስቱ የነገደ ካም ነገስታት ተዘርዝረው መገኘታቸው፣ በአፍሪካ ምድር ተስፋፍተው ዛሬ ድረስ እየኖሩ ያሉት ህዝቦች የካም ልጅ በሆነው በኩሽ መጠሪታቸው ወዘተ.. ግንቡ፣ እንስሶቹ አእዋፍቱ፣ እፅዋቱ፣ ሁሉም "ኖኅና ኢትዮጵያ" ያላቸውን ቁርኝት ከመግለፅ ባለፈ፤ ወደዚች ምድር ለመምጣቱ ጠቋሚ ወይም አረጋጋጭ ናቸው።

# ምዕራፍ ፪
# የነገደ ካም ዘመነ መንግስት
# ከ3500-1985 ቅ.ል.ክ

ቀጥሎ የተዘረዘሩት ከኖህ በኋላ "የነገደ ካም ነገስታት" ተብለው የሚታወቁት ናቸው። በጣም ጥቂት ቀደምት ፀሃፍት ከኖህ ጀምረው ይዘረዝራሉ። ጥቂቶች ከካም ጀምረው ይዘረዝራሉ። ብዙዎች ከኩሽ ጀምረው ይዘረዝሯቸዋል። በጣም ብዙዎች ከሰብታህ ጀምረው ይዘረዝራሉ። ከዚያ ዝቅ የሚል የለም።

| ተ.ቁ | የነገስታቱ ስም | በስልጣን ላይ የቆዩበት ጊዜ በዓመት | የነገሱበት ዘመን ከክ.ል.በፊት |
|---|---|---|---|
| 1 | ኖህ | 344 | 3844 - 3500 |
| 2 | ካም | - | 3500 - 2787 |
| 3 | ኩሽ | 242 | 2787 - 2545 |
| 4 | ሰብታ | 30 | 2545 - 2515 |
| 5 | ኤሌክትሮን | 30 | 2515 - 2485 |
| 6 | ነቢር | 30 | 2485 - 2455 |
| 7 | አሜን 1ኛ | 21 | 2455 - 2434 |
| 8 | ነህሴ (አቢስ) | 30 | 2434 - 2404 |
| 9 | ታርኬም | 29 | 2404 - 2375 |
| 10 | ሳባ 1ኛ(ሳባኖባ) | 30 | 2375 - 2345 |
| 11 | ሳፎሪድ | 30 | 2345 - 2315 |
| 12 | እስከንዲ | 25 | 2315 - 2290 |
| 13 | ሆህይ ስዋእ | 35 | 2290 - 2255 |
| 14 | አህያጥ | 20 | 2255 - 2235 |
| 15 | አድጋስ | 30 | 2235 - 2205 |
| 16 | ባኬንደን መሊስ | 25 | 2205 - 2180 |
| 17 | ማንተራይ ሐቃቤ | 35 | 2180 - 2145 |
| 18 | ራክሁ ድድሚ | 30 | 2145 - 2115 |
| 19 | ሰቢ | 30 | 2115 - 2085 |
| 20 | አዜጋን ፈርአን | 30 | 2085 - 2055 |
| 21 | ሱስሐል አቶባኢዝ | 20 | 2055 - 2035 |
| 22 | አሚን ዳዊዛ 2ኛ | 15 | 2035 - 2020 |
| 23 | ራሚን ፀሃቲ መስልኔ | 20 | 2020 - 2000 |
| 24 | ዋኔና | 3 ቀን | 2000 - 2000 |
| 25 | ጲአሪ 1ኛ | 15 | 2000 - 1985 |



ያሬድ ግርማ 1999 ዓ.ም
መክሪያ 1965 ዓ.ም
ጌታ ሀሩይ ወልደ ስላሴ

ከኖህ በኋላ ያሉት ተከታታይ ነገስታት የነገደ ካም ነገስታት በሚል ስያሜያቸው እየተፈራረቁ እስከ ጲአሪ 1ኛ ድረስ ቆይተዋል። ከነዚህ 25 ነገስታቶች የግዛት ዘመን ጀምሮ አሁን እስካለንበት ዘመን ድረስም በርከት ያሉ አ[illegible]ች የነገስታቱ መቀመጫ ሆነው አገልግለዋል። ረጅም ዘመን ባስቆጠረው የኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የነገስታቱ መቀመጫ ወይም ዋና ከተማ የነበሩ ተብለው በውል የሚታወቁና ተደጋግመው የሚጠሩት ቦታዎች ጥቂት ይምሁሉ እንጂ በርከት አድርገን ስንዘረዝራቸው የሚከተሉትን ይመስላሉ።

ጎንደር/ጣና/ ማንኩሽ /ቤንሻንጉል ውስጥ/ ቱብ (ሳእላይ ግብፅ) ናፓታ፣ ደንጎላ (በናፓታና በመርዌ መካከል) የሳባ ከተማ፣ መርዌ፣ አትባራ (አልፋ ገዳማ) አፈረዋ ናት (ወንድ በሽር ጣና) ኢሉፋንቲን (ደቡባዊ ግብፅ) መረብ (ከሰንና በስተምዕራብ) ባፋር (ደቡባዊ ኢራቅ) መቋድሽ፣ ዳጋ እስጢፋኖስ (ጣና) የሃ፣ ሃውዜን፣ መጠራ፣ ከስክስ፣ አዶሊስ፣ ግሎማክዳ (ተሆንዶ ባልአንበሳ) አክሱም፣ አክሱምና ጎሃፅዮን በጥምረት፣ አክሱም፣ ስቅንቅን፣ አክሱም፣ ሮሐ (ላስታ) ተጉለት፣ ደብረ ብርሃን፣ ሐረር፣ የረር፣ እንፍራዝ፣ ጎርጎራ፣ ጎመንጌ አዘዞ፣ ጎንደር፣ ደብረታቦር፣ መቅደላ፣ ላስታ፣ መቀሌ፣ እንጦጦ፣ (አዲስ አበባ) ተብለው ሲዘረዘሩ፣ እነዚህ ሁሉ ቦታዎች በተለያየ ዘመን የነገስታት መቀመጫ ሆነው ያገለገሉ ሲሆን፣ በዚህም የጥንቱን የኢትዮጵያ ግዛት ስፋት መረዳት እንችላለን።

ሁሉም ነገስታት በመረጡትና አመች በመሰለው ቦታ መቀመጫቸውን ሲያደርጉም የየራሱ መነሻ ምክንያት ይኖረዋል።

ለምሳሌ ኖህ በኢትዮጵያ ምድር ቆይቶ ሲሞትና ልጁ ካም ተተክቶ ሲመራ ካም ከሞተ በኋላ ልጁ ኩሽ ተተክቷል። የኩሽ ልጅ ሰብታህ ደግሞ በአባቶቹ ምድር በኢትዮጵያ ንጉስ ሆኖ ከ 2545-2515 ቅ.ል.ክ. ኢትዮጵያን አስተዳድሯል።

"ንጉስ ሰብታህ አብታላይ የሚገዛውን ምድር እየተዟዟረ እየጎበኘ በነበረበት ጊዜ የዓባይን ወንዝ ሲቃኝ ጉዞውን ወደ ወንዙ መነሻ ያደርጋል። ከምንጩ እንደደረሠም በአንድ ኮረብታ ላይ ድንኳን አስተክሎ አካባቢውን ሲቃኝ የአካባቢው የተፈጥሮ ውበት እጅግ አስደነቀው። ይህም 32 የተለያዩ ወንዞች የሚገብሩለት የጣና ሃይቅ ለንጉሡ ተስማሚ እንደሚሆን በመገንዘብ በጉብታው ላይ ካለው አፈረዋናት ከተባለው ቦታ ላይ ሐይቁንና ወንዙን ሲመለከት እጅግ በመማረኩ በዚያው ቦታ 9 በሮች የነበሩት ታላቅ ግንብ አስገንብቶ "ወንድ በሽር" በሉ ሠየመው" ( ያሬድ ግርማ 1999 ዓ.ም)

ሌሎች የተዘረዘሩት ነገስታትም በየአውራጃው ተበታትና /ተሰራጭተ/ ይኖር የነበረውን ህዝብ ጠቅልለው ያስተዳድሩ የነበሩት ከቦታ ቦታ እየተዘዋወሩና በየጊዜው መቀመጫቸውን እየለዋወጡ ነበር። ነገር ግን በዋናነትና በሰፊው የሚታወቁት መናገሻዎች ናፓታ፣ የሳባ ከተማ፣ መርዌ፣ አክሱም፣ ላስታ፣ ሸዋና ጎንደር ናቸው።

ይህም ሲሆን በጥንቱ ዘመን የቀድሞዋ ሀሬዋ ኢትዮጵያ አንድ ራሱን የቻለ አሐዳዊ መንግስት ነበራት ማለት ነው። የተጠቀሱት ቦታዎችም የ"ንጉሰ ነገስት" መቀመጫ ሆነው ያገለገሉ እንጂ የ"ንጉሶች" አይደሉም። በየቦታው ከንጉሡ ነገስቱ በታች የሆኑ የየግዛቱ ንጉሶች ይሾማሉ።

የዘመናዊት ኢትዮጵያ የታሪክ አባት የሚባሉት ፕ/ር ባህሩ ዘውዴ "እውነተኛውን የኢትዮጵያ ታሪክ አጀማመር ለማወቅ የፅሁፍ መረጃዎች ብቻቸውን ብዙም አያራምዱንም ..." ይላሉ።

በእርግጥም እንደዚያ ነው። ምክንያቱም በአገራችን ተጠብቆ ለትውልድ የተላለፈው ታሪክ የነገስታቱ ስም ዝርዝርና የገዙበት ዘመን ብቻ እንጂ ዝርዝር ስራቸው በተለይ የጥንቶቹ ተፅፎ ስላልተገኘ ነው። ይህም ብቻ ሣይሆን መነሻቸውን ታሪክነገስት ያደረጉ ቀደምት ፀሃፍት "መነሻ" ብለው በጋራ የወሆኑትና የተስማሙበት መዳረሻ የለም። እንደተባለው አንዳንዱ ከኖኅ፣ ሌላው ከካም፣ የቀረው ከኩሽ፣ ሲጀምር፣ በርከት ያሉት ከሰብታ ይነሣሉ።

በተጨማሪም የአንዱ መነሻ ንግስተ ሣባ ትሆንና 3 ሺ አመት ተብሎ ሲወሰን፤ ሌሎቹ የባቢሎኑ ግንብ ግንባታና የቋንቋ ድብልቁን እንዲሁም የህዝቦች ብተና በተከሠተ ጊዜ ከመካከለኛው ምስራቅ ፈልሠው የመጡ የኩሽ ዘሮች ኢትዮጵያን ቆረቆሩት ብለው ታሪኩን ወደ 4ሺ ዓመት አስጠግተው ይነሣሉ። ይህን አቋም የያዙት ቀላል ቁጥር የላቸውም።



ሌሎቹ ደግሞ ከግብፅና ከሌሎች ቀደምት ታሪክ ካላቸው አገሮች በየጊዜው የነገደ ኩሽ ዘሮች ወደ ኢትዮጵያ እንደገቡ ለመገመት ይዳዳሉ፤ ሌላውም ሌላ።

ጥቂቶቹ እንዳየነው ከኖኅ ጀምረዋል። የሚያሳምነውም፣ የሚያስኬደውም፣ እውነታውም ያለው ከኖኅ ጀምረው በጻፉ ፀሃፍት ዘንድ ነው። ይህንኑ እውነታ እያጠነከሩና እያሀኑ ለመቀጠል ያመች ዘንድም ስለባቢሎንና ስለግብፅ የሚመለከቱ ታሪኮችን ራሣቸውን የቻሉ አንድ አንድ ምዕራፍ በመሥጠት ለማየት እንሞክራለን።

ያን ስናደርግም ሌላ ምዕራፍ ስለተሠጣቸው ብቻ ከነገደ ካም ዘመነ መንግስት ታሪክ ወጥተን ሌላ ታሪክ ጀመርን ማለት አይደለም። ለየብቻ መስፈር ስላለባቸው ነው።

# ምዕራፍ ፫

## ኢትዮጵያና ባቢሎን

በርካታ ቀደምት የታሪክ ፀሃፍት ኢትዮጵያ በካም ኩሽ ነገድ መመስረቷን ያምናሉ። ከአዳም ጀምሮ በሚቆጠረው የሠው ዘር አመጣጥ የሚያምኑ ፀሃፍት በዚህ መነሻ ይስማማሉ። "የነገደ ካም ነገስታ " ብለውም ይዘረዝራሉ። ነገር ግን የኢትዮጵያ መስራቾች የሆኑ የካም ኩሽ ነገዶች ወደዚች አገር የመጡት ከባቢሎን ግንብ ጋር በተያያዘ በተከሠተው የቋንቋ መደባለቅና የህዝቦች ብተና አማካኝነት የመጡ ህዝቦች ያደርጓቸዋል። እንደገና ደግሞ መልሠው የነገደ ካም ነገስታት ብለው ከዚያ ዘመን በፊት እዚህ እንደነገሡ ይነግሩናል። ሁሉም ነገድ ቋንቋው ተደባልቆበት ሲበተን የኩሽ ዘሮች ወደ ኢትዮጵያ መጡና ይችን አገር ቆረቆሯት ይሉናል። ምናልባት ይህ ስህተት ለኛ የጠራ እውነትን ሣያስጨብጠን አይቀርም። መቅደም ያለበትን እናስቀድምና እሡኑ እንቀጥላለን።

ኖኅ ከጥፋት ውሃ በኋላ ከነቤተሠቦቹ ፈጣሪው ቃል ይገባለታል። "እነሆ ቃል ኪዳኔን ከእናንተና በኋላ ከሚመጣው ከዘራችሁ ጋር አቆማለሁ..." በሚል ለኖኅና ለቤተሠቦቹ ይነገራቸዋል። አዲስ ኑሮ መጀመሩን ያሣየንና ኖኅ ልጆቹን ሲባርክ ሲመርቅ ያስነበበናል። ኖኅም ገበሬ መሆን ጀመረ ወይንም ተከለ.. በማለት 350 አመት እንደኖረና እንደሞተ፣ ምድርም በልጆቹ እንተሞላች ገልፆልን ምዕራፍ 9ን ይደመድማል።

የብላቴን ጌታ ህሩይ "ዋዜማ" እስያን ለሴም፣ አውሮፓጳን ለያፌት፣ አፍሪካን ለካም እንዳካፈለ ይነግረናል። በርካታ ፀሃፍት የሚስማሙት በዚህ ነው። "የዓለም ታሪክ" ተብሎ የተተረጎመው መፅሃፍ ደግሞ በምዕራፍ 7 ቁ 7 "... እንዲህ ሆኖ የሠው ወገን ሁሉ ጠፋና እንደገና በምድር ላይ የአንድ ሠው ቤተሠብ ብቻ ቀረ። ይህም የሆነው 1656 ዓመት ከዓለም ፍጥረት በኋላ ነው።" ይላል። ማለትም ከክ.ል.በፊት 3844 ላይ ማለቱ ነው። ይሄው የዓለም ታሪክ በምዕራፍ 8 ከቁ 3-4 ባለው "ኖኅ ከቤተሠቦቹና ከእንስሶቹ ጋር ከመርከብ ወጣ። በዚህም እንደገና ዓለም በህዝብ ተሞላች። እንስሶችም በገዛ ራሣቸው ወደ ሩቅ እየሄዱ ተናኙ። ከብዙ መቶ ዓመታት በኋላ በየአገሩ ገቡበት። ለኖኅ ሶስት ልጆች ነበሩት። እነርሡም ሴም፣ ካም፣ ያፌት ናቸው። እነዚህ ከቤተሠቦቻቸው ጋር ሰናኦር ወደተባለው አገር ገቡ።" ይልና ከቁ 6-10 ድረስ "... ህዝቡ በፍጥነት እየበዙ ይሄዱ ጀመር። ከጥፋት ውሃ ጀምሮ መቶው አመት እስኪፈፀም ድረስ ያለ ልክ ቁጥራቸው በዛ። ትውልዳቸውንም ለልጆቻቸው ይነግሯቸው ነበር። ወደ መርከብ ከገቡት በቀር የጥፋት ውሃ መጥቶ ሠውንና እንስሣን ሁሉ እንዳጠፋ ይተርኩላቸው ነበር። በጥፋት ውሃ የሆነውን ሁሉ የሚያስታውሡ ወይም ወሬውን የሠሙ ሁሉ የሠው ክፋት ያንኑ የመሠለ ቅጣት እንደገና መልሶ ያመጣብናል እያሉ ይሠጉ ነበር። ስለዚህ ታላቅ ግንብ ለመስራት ተማከሩ። በዚያም ውስጥ ገብተው ሊሠወሩ ነበር። ይህም ግንብ ባብል ይባላል። በኤፍራጠስ ወንዝ ዳር በስተምዕራብ ወገን የህንፃውን መሠረት ቆረቆሩ። ወደ ሠማይ ለመድረስ እንዲመቻቸው ግንቡን ከፍ አድርገው ለመስራት አስበው ነበር። ግንቡን የሚሠሩት ፀሃይ ባደረቀው ጡብ ነበር። ጡቡንም ሲገነቡ ጭራና አሸዋ በመሠለ ነገር እያያያዙ ነው። ሠራተኞቹ በትጋት ይሠሩ ነበርና ጡቡን አንዱን በአንዱ ላይ እያደራረቡ ሲገነቡ ከላይ ሆነው ምድርን ቁልቁል ሲመለከቱት እጅግ ሩቅ ሆኖ እስኪታይ ድረስ ያጣድፉት ነበር። ነገር ግን ሠማዩና ፀሃዩ ከዋክብቱም ርቀታቸው ግንቡ ሲጀመር እንደነበሩ ናቸው እንጂ ያራራቃቸው ሁኔታ አልተለወጠም።" በማለት አሠራሩን ይተርካል። ይህ መፅሃፍ (የአለም ታሪክ) መፅሃፍ ቅዱሡ ዘርዝሮ የማይነግረንን የባቢሎንን ታሪክ ዘርዝሮ ስለሚነግረን ወሣኝ መንደርደሪያችን እናድርገውና ወደ መፅሃፍ ቅዱሡ እናልፋለን።

ስለዚህ በዚሁ በዓለም ታሪክ መፅሃፍ በምዕራፍ 9 ከቁ 1-7 ድረስ ያለውን ሃተታ እንደወረደ እንየው። "እንድቀን እነዚሁ እብዶች የሆኑ ህዝብ በስራቸው ላይ ሣሉ ታላቅ የሚያስገርም ነገር ሆነ። እንዲሁ እንደልማዳቸው ሲነጋገሩ ሣሉ በድንገት ቋንቋቸው ተለዋወጠና አንዱ ሲናገር ሌላው የሚለውን አላስተውል አለው። ማንኛውም ሠራተኛ ከላይ ሆኖ የታችኛውን ጡብ አቀብለኝ እያለ በጣቱ ሲያመለክተው የታችኛው ሠራተኛ የማያውቀው ቋንቋ ስለሆነ ሌላ ነገር አንስቶ ይሠጠው ጀመር። እንዲሁም ሠራተኞች አንድ ነገር ሲጠይቁ ሌሎች ደግሞ ሌላ ያልተባለውን ይሠጧቸዋል። ድምፅ ብቻ ይሠማቸዋል እንጂ አንዱ የተናገረውን ሌላው አይሠማውም ነበር። የሚለው እንደማይታወቅ ለመናገር እንደሚንተባተብ እንደ ትንሽ ህፃን ሆኑ። እንደዚህ ያለ የቋንቋ መለያየት ሲሆንባቸው ጊዜ የግንቡን ስራ ወደፊት ለመግፋት የማይሆንላቸው ስለሆነ ወደ ሠማይ እንደርሣለን የማለታቸው ተስፋ ተቆረጠና በዓለም ላይ ወደ ልዩ ልዩ ስፍራ ለመንከራተት ግድ ሆነባቸው። ከዚህ በኋላ በብዙ ክፍል ሆነው በብልሃት ለመነጋገር እየፈተኑ ወደ ልዩ ልዩ ስፍራ ለመሄድ ወጥተው የተበታተኑ ይመስላል። በእያንዳንዱ ክፍል ሲሄዱ ከኋላቸው ገልመጥ እያሉ ወደ ባብል ግንብ እያዩ ምናልባት ሣያዝኑ አይቀርም.....።

የሴም ልጆች በኤፍራጠስ አውራጃ ያለውን አገር እንደተካፈሉ ይመስላል። የካም ልጆች በምዕራብ አውራጃ ያለውን አገር ይዘው ወደ አፍሪካ ፈቀቅ አሉ። ከዚያ ምስርን/ግብፅን/ ያዙና ታላቅ ነገድ ለመሆን በቁ። የያፌት ልጆች ወደ ግሪክ አገር ፈቀቅ አሉና ከዚያ አያሎችን የአውሮጳን አገር መሠረቱ። በባሬው ዘመን አያሌ መንገደኞች (በርካታ ጎብኚዎች አጥኚዎች) በኤፍራጠስ ወንዝ ዳር ሠፋፊ ኮረፍቶች አግኝተዋል። የተሠሩበት በዝፍትና በሚያጣብቅ ነገር ባንድነት ተቦክቶ በፀሃይ በተተኮሠ ጡብ ነው። እነዚህም ኮረፍቶች ከ 4ሺ ዓመት በፊት ተሠርቶ የነበረ የባብል ግንብ ፍራሽ እንደሆኑ ተረዱት።" ይላል። ከ4ሺ አመት በፊት የሚለው ከዚህ ዘመን ተነስቶ ወደ ላይ ተቆጥሮ ነው። ማለትም ከክ.ል.በፊት 2ሺ ዓመት ላይ መሆኑ ነው።

የጥፋት ውሃ ከደረሠ ከብዙ ዘመን በኋላ ነው የባቢሎን ግንብ የተጀመረው። እናም እንደዚህ ሐተታና እንደ ሌሎች በርካታ ፀሃፍት እይታ ከሆነ ከ2ሺ ቅ.ል.ክ በፊት የካም ልጆች ወደ አፍሪካ ጠጋ እያሉ ከመጡ ከዚህ ጊዜ በፊት በአፍሪካ ምድር ሠው አልነበረም ማለት ነው። በአፍሪካ ምድር ሠው ከነበረ ደግሞ በባቢሎኑ ግንብ የተሣተፉ የካም፣ ኩሽ ነገዶች አይኖሩም ማለት ይሆናል። መሪ ራስ ኤም.ሌ በላይ ቀደም ሲል እንዳየነው በጥንቷ የኢትዮጵያ መናገሻ ከተማ በነበረችው በናፓታና በመርዌ መካከል በምትገኝ "ደንጎላ" በተባለች ከተማ በአንድ ዋሻ የድንጋይ ሣጥን ውስጥ በርከት ያሉ ሠነዶች አገኙ ብለናል። የተገኘው በኋላኛው ዘመን በመጡ የሴም ዘሮች ነበር። እናም የደንጎላው ሠነድ የሚያስረዳው በባቢሎኑ ግንብ የተሣተፉት 72 የቤተ ሤም፣ የቤተ ካምና የቤተ ያፌት ነገዶች መሆናቸውን ነው። የተደባለቀውን የቋንቋ ዝርዝርም የተጠቀሠው መፅሃፍ ይዘረዝራል።

እነዚህን ነገሮች ይዘን ወደ መፅሃፍ ቅዱሱ እንምጣ። በመፅሃፍ ቅዱስ በዘፍጥረት በምዕራፍ 10 ቁ 1 ጀምሮ "የኖኅ ልጆች የሴም የካም የያፌት ትውልድ ይህ ነው። ከጥፋት ውሃም በኋላ ልጆች ተወለዱላቸው።" ብሎ ይጀምርና የያፌትን ነገድ በስም ዘርዝሮ ከቁጥር 6 ጀምሮ እስከ 20 ድረስ ባለው ደግሞ ስለ ካም ይዘረዝራል።

"የካምም ልጆች ኩሽ፣ ምጽራይም፣ ፉጥ፣ ከነዓን ናቸው። የኩሽም ልጆች ሳባ፣ ኤውላጥ፣ ሰብታህ፣ ራዕማ፣ ሰበቃታ ናቸው። የራዕማ ልጆችም ሳባ ድዳን ናቸው።" ይልና መልሶ "ኩሽም" ብሎ ይቀጥለዋል።

"ኩሽም ናምሩድን ወለደ። እርሡም በእግዚአብሄር ፊት ሃያል አዳኝ ነበር፣ ስለዚህም በእግዚአብሔር ፊት ሃያል አዳኝ እንደ ናምሩድ ተባለ። የግዛቱም መጀመሪያ በሰናኦር አገር ባቢሎን፣ ኦሬክ፣ አርካድ፣ ካልኔ ናቸው። አሶርም ከዚያች አገር ወጣ። ነነዌን፣ የረሆቦትን ከተማ፣ ካለህን፣ በነነዌና በካለህ መካከልም ሬሴንን፣ ሠራ። እርሷም ታላቂቱ ከተማ ናት።

ምጽራይምም ሉዲምን ዐናሚምን፣ ላህቢምን፣ ነፍታሌምን፣ ፈትሩሲንም ከእርሡ የፍልስጤም ሠዎች የወጡባቸውን ከስሊሁምን፣ ቀፍቶሪምንም ወለደ። ከነዓንም የበኩር ልጁን ሲዶንን (ሜዶን፣ መቄዶንያ ይሆኛል ወደ በኋላ) ኬጤያውያንንም፣ ኢያቡሳውያንንም፣ አሞራውያንንም፣ ጌርጌሣውያንንም አማቲንም ወለደ። ከዚህም በኋላ የከነዓናውያን ነገድ ተበተኑ።" ይለናል። ወደ የት ተበተኑ? ብለን ስንጠይቅ እዚያው በሚቀጥል ዓረፍተነገር አማካይነት እንዲህ የሚል ምላሽ ይሠጠናል "የከነዓናውያንም ወሠን ከሲዶን አንስቶ ወደ ጌራራ በኩል ሲል እስከ ጋዛ ድረስ ነው። ወደ ሰዶምና ወደ ገሞራ ወደ አዳማና ወደ ሰቦይም በኩል ሲል እስከ ላሣ ድረስ ነው። የካም ልጆች በየነገዳቸውና በየቋንቋቸው በየምድራቸውና በየህዝባቸው እነዚህ ናቸው።" ብሎ በቁ 20 ይዘጋውና በቁጥር 21 የሴምን ትውልድ ይዘረዝራል። የያፌቱን መዘርዘር አያጠበቅብንም። የሴሙን በስፋት እናገኘዋለን። አሁን ማተኮር ያለብን በካም ላይ ነው።

ከላይኛው ታሪክ ስንነሣ የካም ልጆች ኩሽ፣ ሚጽራይ፣ ፉጥ፣ ከነዓን ሲሆኑ፤ የካም የመጀመሪያው ልጅ ኩሽ ደግሞ ሳባ፣ ኤውላጥ "ሠብታ"፣ ራዕማንና ሰበቃታን፣ እንዲሁም ናምሩድን ወልዷል። የአገራችን ታሪክነገስትም ሆነ ክብረነገስት የአገር ውስጥ ፀሃፍትም ሆኑ የውጭ፣ የብራናው ወዘተ... ባጠቃላይ የኢትዮጵያ የመጀመሪያ ንጉስ ብለው የሚጀምሩበት ዝርዝር "ሠብታ"ህን ነው። በዚህ መፅሃፍና በሌሎች ጥቂት መፅሃፎችም ቢሆን ኖህ፣ ካም፣ ኩሽ፣ ተብሎ ሠብታ ብሎ ነው የተጠሰው። ባጭር አገላለፅ ከፍ ሲል "ኖኅ" ዝቅ ሲል "ሠብታ" አራት ነጥብ።

ይህ ከኩሽ ልጆች አንዱ የሆነው የኢትዮጵያ ንጉስ የናምሩድ ወንድም ነው። ናምሩድም የኩሽ ልጅ ነውና። ነገር ግን ከሠብታህ ቀጥሎ በነገደ ካም ነገስታት ዝርዝር ውስጥ እንዳየነው ተከታዩ ንጉስ ኤሌክትሮን ነው። ይህም የሠብታ ልጅ ነው። ከዚያ ነቢር፣ አሚን 1ኛ... እያለ ይቀጥላል፤ እንጂ ናምሩድ በኢትዮጵያ የነገደ ካም ነገስታት ዝርዝር ውስጥ የለም ሊኖርም አይችልም። እንግዲህ ናምሩድ የኩሽ ልጅ ሆኖ ግለ ነገር ግን ከወንድሞቹ ተለይቶ ምናልባትም የዓባይን ወንዝ እየደነ ተከታትሎ በዚያው ወደ ባቢሎን ሄዶ ግዛት መስርቷል፣ ሃያል ተብሏል ከማለት ውጪ ሌላ እድል የለም!

የጎንደር ታሪክ የሚለው መፅሃፍ ቀደም ሲል እንዳየነው "... ካም በኢትዮጵያ ምድር ቆይቶ ሲሞት ልጁ ኩሽ የቤተሠቡ መሪ ሆነ።

እርሡም እንደ አባቱ ብዙ ዘመን ኑሮ ሲሞት ልጁ ሰብታህ/የናምሩድ ተከታይ/ በአባቶቹ ምድር በኢትዮጵያ ንጉስ ሆኖ ከክ.ል.በፊት ከ 2545-2515 ነገሠ" ይላል።

"የናምሩድ ተከታይ" ሲልም ሆነ፣ በመፅሃፍ ቅዱሡ የኩሽ ልጆች ተብለው ከተዘረዘሩ በኋላ እንደገና "ኩሽም" ብሎ በመጀመር "ናምሩድን ወለደ" ብሎ ስለሚቀጥለው ምናልባት የሚነሣ ጥያቄ ካለ አንድ ጥያቄ ብቻ ነው። እሡም ማነው ታናሽ ማነው ታላቅ? በተረፈ ወንድማማች መሆናቸው ከግልፅም በላይ ግልፅ ነው። ስለዚህ ማነው ታላቅ ማነው፣ ታናሽ የሚል ጥያቄ ሣይነሣ የሠብታህ ወንድም መሆኑን በመረዳትና ናምሩድ በኢትየጵያ አለመንገሡን በመገንዘብ ብቻ ሁለት የኩሽ ዘሮች ተነጣጥለው መቀመጣቸውን እንወስዳለን። በአንድ አይነት ዘመን። ማን ወደዚህ መጣ? ማን ወደ ዚያ ሄደ? ናምሩድ ሃያል አዳኝ ሲባል (የአውሬ አደን አይደለም፤ የአገር አደን ነው፤ ምክንያቱም ".. ሃያል አዳኝ እንደ ናምሩድ ተባለ፣ የግዛቱም መጀመሪያ በሰናኦር አገር..." እያለ ስለሚቀጥል ግልፅ ነው።) ልክ በዚያው ዘመን ከወዲህ በኩል ከክ.ል.በፊት ከ2545-2515 ሡብታ በኢትዮጵያ ለመንገሡ ጥርጥር የለውም። ዘመኑ ከፍም ዝቅም ቢል አንድ ቡድን እዚያ አንድ ቡድን እዚህ ነበር የሚለውን እውነታ ሊያፋልስብን የሚችል ምንም ሃይል የለም። ነገሩን በደንብ ለማስረገጥ ያህል አንድ የኩሽ ሃያል ልጅ (ናምሩድ) ከኢትዮጵያ ወደ ባቢሎን ሔዶ ሌላ የኩሽ ልጅ (ሡብታህ) በኢትዮጵያ ነገሠ። ልጅ ሲባልም ነገድ መሆኑ ነው። ናምሩድ ብቻውን አልሄደም። ለዘመናት የተባዛ ህዝብ አለ። በተናጠል የምንጠቅሠው መሪ ነገስታቶችን ነው። ልክ በዚሁ መጠንም ወንድም የሚለው በታላቅና በታናሽ የሚገለፀው እንኳን መሆን ቢያቅተው ሁለቱም ከኩሽ እስከ ተገኙ ድረስ ለጊዜው (ለዚህ ሃተታ) በቂያችን ነው።

ስንቀጥል የካም ልጆች ኩሽ ሚጽራይ ፉጥ ከነዓን ናቸው ተብሏል። በዚህ መሠረት ከነዓን የኩሽ ወንድም ነው። የእርሡም ነገድ ቀደም ሲል እንዳየነው.. ሲዶንን፣ ኬጤያዊያንን ወዘተ ወለደ። የከነዓናውያንም ነገድ ተበተኑ የሚል ነገር አይተናል። ወዴት? ብለንም ጠይቀን ቦታዎቹ ተዘርዝረውልናል። የተጠቃቀሡት ቦታዎች (በነገድ ስም የተሠየሙትን ጨምሮ) በየጊዜው ስማቸው ሊለዋወጥ ይቻል እንጂ ወደ ጥንቷ ኑብያ ኢትዮጵያም ሆነ ወደ አሁኗ ኢትዮጵያ እልፍ አላሉም።

ኢትዮጵያ ከቋንቋ መደባለቅ በኋላ የፈለሡ የኩሽ ዘሮች የመሠረቷት አገር አለመሆኗን በዚህ እንረዳለን።

የካም ኩሽ ነገድ የአፍሪካውያን መሠረቶች መሆናቸው ይታወቃል። እስካሁን ድረስ ባለው ጊዜ ማለትም ቋንቋ ከመደባለቁና



የባቢሎኑ ግንብ ግንባታ ከመጀመሩ በፊት፤ ከዚሁም ጋር ተያይዞ የሁዎች ፍልሡት ከመከሠቱ በፊት ወደ ኢትዮጵያ የመጣ ሠው ሳይኖር መሆኑ ነው። ስለዚህ በእነዚያ ዘመናት ወደ ኢትዮጵያ የመጣ የኩሽ ዘር ከሌለ ለዘመናት ታምኖበት የመጣው የነገደ ካም የነገስታት ዝርዝር ስምና ዝሁበት የተባለው ዘመንም ውድቅ ይሆናል ማለት ነው። ይሄ ደግሞ ሙሉውን የኢትዮጵያን ታሪክ መናድ ይባላል።

ሰብታ ከክ.ል. በፊት ከ2545-2515 በኢትዮጵያ መንገሡ እየታወቀ፤ ነገር ግን የኢትዮጵያ መስራች የሆኑት ነገደ ካም ኩሽ ከባቢሎኑ ግንብ መፍረስ ጋር ተያይዞ ቋንቋ ሲደባለቅና የሠው ልጆች ሲበተኑ ከመጡና ከሠፈሩ የባቢሎን ሙከራና ክሽፈት እንዲሁም የቋንቋ መደባለቅና የነገዶች ፍልሠት ከክ.ል.በፊት በ2300 እና በ 2200 መካከል ነው። ይህም ሲሆን አይደለም ከሰብታ ከ "ባኤንደን መሊስ" እንኳ ብንነሣ ልክ አይመጣም። ስለዚህ ያለጥርጥር በኢትዮጵያ ያንኑ አንድ ቋንቋ ይዞ የነበረ የነገደ ካም ኩሽ ህዝብ ነበረ። ናምሩድ ከዚህ ገስግሶ ሄዶ እዚያው ሃያል ተብሎ እዚያው ተስፋፍቶ፣ እዚያው ቀርቷል። በትክክለኛው የመፅሃፍ ቅዱስ ያዘመን አቆጣጠር መሠረት የባቢሎን ግንብ ታሪክ 2247 ቅ.ል.ክ. መሆኑ ታውቋል። ነገር ግን መፅሃፍ ቅዱስ ዝርዝር ነገሮችን ሙተንተን ስለማይጠበቅበት ዘመኑ አልሠፈረም። ይሁን እንጂ በምዕራፍ 10 ከላይ ያየናቸውን የነገድ ተዋረዶች እንደየወገኑ ከዘረዘረልን በኋላ ነው ዝቅ ብሎ በምዕራፍ 11 ስለባቢሎን የሚተርክልን። የባቢሎኑ ስራ ወይም ሴራ በምዕራፍ 11 ከሠፈረ ደግሞ የዘመን ተዋረዱን እንደጠበቀ በቀላሉ እንረዳለን።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በፍልሠት መጡ ልንል ብንችል እንኳን ከወዲያኛው አገር ወደዚህኛው አገራችን ፈልሶ የመጣ የነገደ ካም ኩሽ ዘር የለም፤ ግብፅን ያለፈ የለም። ፈልሶ የመጣው ወደፊት እንደምናገኘው የሴም ዘር እንጂ የኩሽ ዘር የሚል በየትኛውም የታሪክ ሠነድ ተፈልጎ አይገኝም። ነገር ግን ተስፋፍቷል፤ ከሌላው ጋር ተዋልዷል፣ ተዳቅሏል፤ ተቀላቅሏል። ይሄ አንዱ ነው። ሌላው ቀሪ አማራጮችን ነገደ ካም ኩሽ በዚሁ በአፍሪካ ምድር ቀረ እንጂ ወደየትም አልተንቀሳቀም የሚል ነው። ይሄ የማይሆን ብቻ ሣይሆን አስቂኝ ቀልድ ይሆናል። በባቢሎኑ ግንብ የተሣተፈ ነገደ ካም ኩሽ ነበረ፤ ግንቡ በተገነባበትም ወቅት እዚህም ንጉስ ነበር። በጥቅሉ 1ኛ የኩሽ ልጅ የሆነው ናምሩድ የትም አልሄደም ብሎ መካድ፣ 2ኛ በአሁኑ ሠዓት የኩሽ ነገድ በአሁኗ ኢትዮጵያና በቀደሞዋ ኢትዮጵያ/ኑብያ/ እንዲሁም በመላው አፍሪካ ፈፅሞ የለም ብሎ መካድ። እነዚህ ናቸው አማራጮቻችን። ይህን ምርጫ ማንም ስለማይቀበለው 3ኛውን ምርጫ እንይዛለን። "ግማሹ ነገደ ካም እዚያ፤ ግማሹ እዚህ።"

ነገድን በማመለከት በኖህ ሶስት ልጆች መነሻነት ሴም፣ ካም ያፌት ተብለው ተገልፀዋል። በመፅሃፍ ቅዱስ እንዲህ ሲረጋገጥ፣ ሣይንስ በገዛ ራሡ መንገድ ደግሞ በተመሣሣይ በሶስት ከፍሎ 1ኛ የኒግሮይድ ሠው ዘር፡- ጥቁር የቆዳ ቀለም ያለው ሲሆን የአፍሪካ ጥቁሮች፣ ቡሽሜን፣ ሆቴንቶ፣ ማሌዥያ... ወዘተ ወዘተ... 2ኛ የሞንጎሎይድ ሰው ዘር፡- ቢጫ የቆዳ ቀለም ያለው ሲሆን ቻይናውያን፣ ጃፓናውያን ሞንጎሊያ.. ወዘተ... ወዘተ... 3ኛ የካውካስያን ሠው ዘር፡- ነጭ የቆዳ ቀለም ያለው ሲሆን የኖርዲክ ቅርንጫፍ፣ የአልፓንያን ቅርንጫፍ ወዘተ... ወዘተ... እያለ ይተነትነዋል። ይህ አይነቱን ትንታኔ ከዚህ በላይ መዘርዘር ስለማያስፈልገን ወደ ጉዳያችን እንመለስ።

በምዕራፍ 10 ትንታኔ መሠረት ከላይ እንዳየነው የያፌትንና የካምን የዘር ሃረግ እንደሚተነትነው፤ ከዚያው ምዕራፍ ሣይወጣ "ለሴምም ደግሞ ልጆች ተወለዱለት..." ብሎ ይጀምርና የነገድን ተዋረድ በስም እየዘረዘረ ቀጥሎ... "ስፍራቸውም ከማሴ እንስቶ ወደ ስፋር፤ ሲል እስከ ምስራቅ ተራራ ድረስ ነው።..." የሚል ገለፃ ያስከትልና በመጨረሻው ዓረፍተ ነገር "የኖኅ የልጆቹ ነገዶች እንደ ትውልዳቸው በየህዝባቸው እነዚህ ናቸው። ህዝቡም ከጥፋት ውሃ በኋላ በምድር ላይ ከእነዚህ ተከፋፈሉ።" ብሎ ምዕራፍ 10ን ይዘጋና ምዕራፍ 11 ከቁ.1 ጀምሮ "ምድርም ሁሉ በአንድ ቋንቋና በአንድ ንግግር ነበረች። ከምስራቅም ተንስተው በሄዱ ጊዜ በሰናኦር ምድር አንድ ሜዳ አገኙ። በዚያም ተቀምጠው..." ያው... ዶሉ፡ ማለት ነው። ወደ ሠማይ ግንብ ሊገነቡ ስራውን ጀመሩት።

እነማን ናቸው? ብለን መጠየቅ ካለብን ምናልባት "ከምስራቅ ተነስተው.." ስለሚል የሴም ወገን "ሊበረክቱ" እንደሚችሉ እያሠብን መቀጠል እንችላለን፤ የካም ወገኖችም እንደነበሩበት አይተናል። ዞሮ ዞሮ የደረሡበት ቦታ "በሠናኦር ምድር አንድ ሜዳ አግኝተው.." ስለሚልና ሠናኦር ማለት ደግሞ ቀደም ሲል ከናምሩድ ታሪክ ጋር በተያያዘ "ሃያል አዳኝ እንደ ናምሩድ ተባለ፣ የግዛቱም መጀመሪያ በሰናኦር አገር ባቢሎን አሬክ አርካድ ካልኔ [illegible]ው።" ስለተባለ እዚያ ሆነው እንደዶሉ፡ ግልፅ ነው። ሠናኦር ማለት [illegible]ን ነው። በኋላ ላይ የአሶር መንግስት ተመስርቶበታል። መፅሃፍ ቅ[illegible]ስ "አሶርም ከዚያች አገር ወጣ" የሚለን በኋላ ላይ የአሶር ገናና መንግስት ስለተመሠ[illegible] ነው። ከናምሩድ በኋላ። በዚህ ጊዜ ፈጣሪያቸው ተቆጣ ማለ[illegible] [illegible]ንቋቸውን ደባለቀው። " እግዚአብሔር [illegible]ዚያ የም[illegible] [illegible]ልና ከዚያም እግዚአብሔር በምድር ሁሉ ላይ [illegible] [illegible]ነዋል" ዘፍጥረት 11 ከ ቁ 9-10 ያለው ዓረፍተ ነገር።

[illegible]ዓለም ቀደምት ታሪክ ውስጥ በግልፅ የሚታወቁ ሶስት አይነት [illegible]ሉ። 1ኛ ከኖህ ሞት በፊትና በኋላ ሠዎች ተበትነዋል። 2ኛ ከባቢሎኑ ግንብ መፍረስ በኋላ ሠዎች ተበትነዋል። 3ኛ ክርስት እጣ መውጣት በሚባለው ሠዎች ተበትነዋል። ያም ሆኖ ብተና ሲባል ሌሎች ንዑስ ብተናዎች ይኖራሉ። ይህም ሲባል ፍልሠት፣ ስደት፣ የጦርነት ሽሽት... ወዘተ ለማለት ነው። ከእነዚህ ውጭ የሆኑ ብተናዎችም አሉ። ለምሣሌ "የከነዓናውያንም ነገድ ተበተኑ።" የሚል ነገር አይተናል። ወደየት? ብለን ስንጠይቅ ግን በቀደመው ዘመን የቦታ እንጂ የአህጉር (ወይም የአገር ርቀቱ እጅግ ሣይሠፋ ወደተቀራራቢ አዋሣኝ ግዛቶች) ሲበተኑ ነው የምናየው። ይህም ከንዑስ ብተናዎች የሚካተት አይነት ነው።

የባቢሎኑ ብተና ግን ዋና ከሚባሉት ውስጥ ነው። ስለዚህም የኛ ዋነኛው ነጥባችንም ከዚሁ ጉዳይ ጋር የተያየዘ ይሆናል ማለት ነው።

ተደጋግሞ እንደተገለፀው የኢትዮጵያ እንደ አገር የመቆርቆር ታሪክ የሚጀምር ተብሎ (በስፋት) የተወሠነው ከባቢሎኑ ብተና በኋላ መሆኑ ነው። በጣም በሚገርም ሁኔታ ደግሞ የሠው ልጆች ሁሉ እስከ ባቢሎኑ ግንብ ድረስ በአንድ ላይ በአንድ ቦታ ነበሩ ማለት ነው። ከዚያ በኋላ ቋንቋቸው ተደባልቆ እነሡም ተበትነው የየራሣቸውን አገር መሠረቱ መሆኑ ነው።

የግብፅ OLD KINGDOM ግን ወደፊት እንደምናየው ከክ.ል.በፊት ከ3200 ዓመት ቀደም ብሎ በነበረው ጊዜ በኢትዮጵያውያኑ ተመስርቶ ነበር። በኢትዮጵያውያኑ ሲባልም ከዚህ ተነስተው በሄዱ በጥቁር ኑብያንስ ለማለት ነው። የቋንቋ ድብልቁ ግን 2247 ቅ.ል.ክ ነበር።

በባቢሎን ታሪክ ውስጥ ከወደ ግብፅ የወረዱና በባቢሎን የሠፈሩ ነገዶች እንደነበሩ ተፅፏል። ሌሎች ደግሞ አካድያን የሚባሉ ዘራቸው ሴማዊ የሆኑ በአካባቢው ይኖሩ ነበር። እነዚህ ህዝቦች ከዋነኛው ንጉስ ከሐሙራቢ በፊት የየራሣቸውን ትንንሽ መንግስት አቁመው በነገስታት መመራት ጀምረው ነበር።

ናምሩድ ባቢሎንን እና አሶርን፣ ኑኒስ የነነዌን ከተማ፣ ሴሚራሚስ የተባለችው የባቢሎንን ከተማ ያስጌጠች ንግስት፣ ሠርዳናፓል የነነዌ ከተማ በጠላት ሲከበብበት ሃብት ንብረት ቤተሠቡን ሠብስቦ በፈቃዱ እሣት ውስጥ ገብቶ የሞተ ንጉስ... እንደተከታተሉ ተፅፏል።

ሱሜርና አካድ በተባሉት ነገዶች ላይ ሌሎች የሴም ዘሮች በየጊዜው እየተደባለቁ የከለዳውያንንና የባቢሎንን የመጀመሪያውን መንግስት ከቀድሞው የበለጠ አድርገው አቋቋሙ። በመፅሃፍ ቅዱስ ተደጋግማ የተነሣችው የባቢሎን ከተማ በ2500 እና በ2000 ቅ.ል.ክ መካከል ተመስርታ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየደመቀች ሔዳለች። ከአሶር፤ ከሜዶን፣ ከህንድ፣ ከፋርስ፣ ከአርመን፤ ከግብፅ ለሚመጡ ነጋዴዎች ዋና መገናኛና የሸቀጥ መገበያያ መደብር ሆነች። እንዲህ ሆኖ በደመቀችበት ጊዜ ሐሙራቢ የሚባል

ሃይለኛ አዋቂና ህግ አጋጊነትን አጣምሮ የያዘ ንጉስ ተነሣላቸው። እርሡም ለባቢሎን መንግስት ለመጀመሪያው ዳይናስቲ /ስርወመንግስት/ 6ኛ ንጉስ ነው። ይህ ንጉስ የነበረበት ዘመን ከ1792-1750 ቅ.ል.ክ እንደሆነም ታውቋል።

ሐሙራቢ በነገሠ ጊዜ እንደ ሁለት የተለያዩ ነገድ የሚቆጠሩትን አካድንና ሱሜርን በአንድነት አዋህዶ የአሶርን፣ የኤላምን አገሮች ሁሉ እየወጋ የባቢሎን ወይም የከለዳውያን መንግስት የሚባለውን አገነነው።

ከእርሡ መነሣት በፊት ግን ናምሩድ በአካባቢው ታላቅ ሆኖ ቤተጣኦትም ገንብቶ ነበር። "ቤሉስ" የሚባለውን የወርቅ ምስል አሠርቶ አስገብቶበታል። ይህም የሆነው ከቋንቋ ድብልቅ በፊት ነው። ከድብልቁ በኋላ ሁሉም በየነገዱ ተከፍሎ የየራሡን ቋንቋ እየፈጠረ፣ እያዳበረ፣ በየአገሩ ግዛት እየመሠረተ የኖረው በርካታ ነበር። ስለዚህ ከቋንቋ ድብልቅ በፊት ያንኑ አንድ ቋንቋ የያዘ ህዝብ በኢትዮጵያ ብቻ ሣይሆን በግብፅም ይኖር ነበር። በባቢሎንና በሱሪያውም እንዲሁ። እነዚህን አገሮች ቀድመው ያሰለጠኑት ከወደ ግብፅ ወረዱ የተባሉት ናቸው። በኑብያ፣ በግብፅ አድርገው የሄዱት እነናምሩድ!

ከኖኅ ሞት በኋላና በፊት በነበሩት ብዙ መቶ አመታት የሠው ልጆች እጅግ በርክተው በዓለም ላይ ተሠራጭተዋል።

ምንም እንኳ የካምን ትክክለኛ እድሜ ለማወቅ ባይቻልም መፅሃፍ ቅዱስ ሴም 600 ዓመት ሲኖር ያሳየናል። ስለዚህም በዚያ ዘመን አንድ ሠው አንድ ሙሉ ወይም ግማሽ ሚሊኒየም ይኖር ስለነበር የህዝቡ ብዛትም በዚያው መጠን ሲሠላ መበርከቱ አይገርምም።

የኖኅ የልጅ ልጆችና ተከታይ ትውልዶች ልባቸው የፈቀደውን አምልኮ ማምለክ ጀመሩ እንጂ ያባታቸውን የኖኅን አምላክ በማምለክ አልቀጠሉም።

ከባቢሎን ግንብ በፊት በነበረው ታሪክ በመፅሃፍ ቅዱስ ስለነገዶች፣ ስለትውልዱ አወራረድ ተዘርዝሮ ተጠናቆ ነበር። ነገር ግን በምዕራፍ 11 ቁ 9 የባቢሎኑን ታሪክ ከደመደመ በኋላ ለመጨረሻ ጊዜ ወደ ኋላ ተመልሶ የሴምን ሁኔታ ያነሣና በቁ 10 "የሴም ትውልድ ይህ ነው።" እያለ በመቀጠል ብዙ የሴም ተዋረዶችን ይዘረዝርና አብርሃም ሲወለድ ያሳየናል።

የሴምን ተዋረድ መልሶ ያነሣበት ምክንያት አብራም/በኋላ አብርሃም/ የተባለው ፃድቅ ሠው ተወራርሶ መምጣቱን ሊገልፅን ነው። አገሩ ሁሉ ጣኦት ሲያመልክ አብራም እውነተኛውን አምላክ ይዞ የሚቀጥል የእብራውያን ነገድ መስራች ሲሆን እናያለን። ከአሶራውያን መንግስት በስተደቡብ በኩል ካለው ከላውዲዎን (ካልዲያ) (ከለዳውያን) በተባለው አገር ከታራ ሲወለድ ነው የምናየው። የተወለደበትን አገር ለቆ በምዕራብ በኩል



ከነዓን ወደ ተባለው አገር ፈጣሪው እንዲሄድ ያዘዋል። ይህም ሲሆን አምላክ ለኖኅ የገባውን ቃል ኪዳን ሲተገበረው እንመለከታለን። በም. 12 ከቁ 1 ጀምሮ "…. ከአገርህ ከዘመዶችህም ከአባትህም ቤት ተለይተህ እኔ ወደማሣይ ምድር ውጣ። ታላቅ ህዝብም አደርጋሃለሁ፤ እባርክሃለሁ።… የምድር ነገዶች ሁሉ ባንተ ይባረካሉ።" ይለዋል። አብራሃም ከዑር ከለዳውያን ወጥቶ ወደ ተባለው ምድር ወደ ከነዓን ሚስቱን /ሦራን/ ሣራን ይዞ ይሄዳል። እዚያም ሲደርስ "ይችን ምድር ለዘርህ እሠጣለሁ" ተብሎ ይነገረዋል። የሄደባት አገር ከነዓን በኋላ ላይ ፓለስታይን የተባለቸው ናት።

አብራም በዚያው ሆኖ በአምላኩ ትዕዛዝ ወዲያ ወዲህ እያለ ጥቂት ዘመን ይኖርና በምድሩ ረሃብ ተከስቶ ወደ ግብፅ በእንግድነት የሚሄደውና ከፈርኦኑም የሚገናኘው፣ ከዚያም ወጥቶ ወደ ከነዓን የሚመለሠው.. ወዘተ በዘፍጥረት ም. 12 ላይ ይተረካል። በምዕ 14 ቁ 14 ጀምሮ ደግሞ " አይንህን አንሣና አንተ ካለህበት ስፍራ ወደ ሠሜን እና ወደ ደቡብ፤ ወደ ምስራቅና ወደ ምዕራብ፤ እይ፤ የምታያትን ምድር ሁሉ ለአንተና ለዘርህ ለዘላለም እሠጣለሁና…" ይባላል (ደቡብ ወደ ቀይ ባህር አቅጣጫ ነው) በምዕ 15 ቁ 13 ላይም አምላኩ አብራምን ሲያነጋግረው "ዘርህ ለእርሡ ባልሆነች ምድር ስደተኞች እንዲሆኑ በእርግጥ እወቅ፤ ባሪያዎች አድርገው አራት መቶ አመት ያስጨንቋቸዋል።…" ይለዋል።

በዚሁ ምዕራፍ ሌላ ቃል ኪዳን ይገባለታል። "… ከግብፅ ወንዝ ጀምሮ እስከ ጥልቁ እስከ ኤፍራጠስ ወንዝ ድረስ ይችን ምድር ለዘርህ ሠጥቻለሁ።" ብሎ ምዕ 15ን ይዘጋል። በምዕ 17 አብራም "አብርሐም" ይባላል። "…. ቃል ኪዳኔ ካንተ ጋር ነው። ለብዙ አህዛብም አባት ትሆናለህ። እጅግም አበዛሃለሁ። ህዝብ አደርጋሃለሁ። ነገስታትም ካንተ ይወጣሉ። ቃል ኪዳኔንም በእኔና በአንተ መካከል፤ ከአንተም በኋላ ከዘርህ ጋር በትውልዳቸው ለዘላለም ኪዳን አቆማለሁ። ለአንተና ካንተ በኋላ ለዘርህ አምላክ እሆን ዘንድ በእንግድነት የምትኖርባትን ምድር የከነዓንን ምድር ሁሉ ለዘላለም ግዛት ይሆንህ ዘንድ ለአንተና ከአንተ በኋላ ለዘርህ እሠጣለሁ። አምላክም እሆናቸዋለሁ።" (ምዕ 17 ከቁ 1-8)

አብርሃም ለዓረቦችም ለአይሁዶችም አባት መሆኑ ይታወቃል። ከዚህ በኋላ ነው አብርሃም፣ ይስሃቅ፣ ያዕቆብ…. እየተባለ ዳዊት የሚነሣው። ዳዊት ሠለሞንን ይወልድና አዜብ (ደቡብ ማለት ነው በግዕዝ) ንግስተ አዜብ፣ ወይም የሣባ ንግስት /ንግስተ ሣባ/ ማክዳ ከምትባለዋ ንግስት ጋር አቀራኝቶ ምኒልክን ሲወልድ የምናየውና ኢትዮጵያ የ3 ሺ አመት ታሪክ ያላት የምንባለው። ነገር ግን ከአብርሃም ዘመን በፊትም ሆነ ከባቢሎኑ የቋንቋ ድብልቅ ዘመን በፊት በኢትዮጵያ የመጀመሪያዎቹ ህዝቦች ይኖሩ የነበረ መሆኑን ከላይ ካየነው ሀተታ በቀላሉ እንረዳለን።

# ምዕራፍ ፩

## አሮጌው ስልጣኔ ከኢትዮጵያ ወደ ግብፅ

በዓለም አቀፍ ደረጃ ጠንከር ያለ እውቅና የተሠጠው ታሪክ ፀሃፊ ግሪካዊው ሄሮዱተስ ነው። ዓባይን "የግብፅ ህይወት ነው" እያለ ደጋግሞ የማያነሣውም እሡ ነበር። "የግብፃውያንን የቀደመ ታሪክ ለመፃፍ መነሻዬ የናይል ዴልታ (ድፍድፍ) ነው" ይላል ሄሮዱተስ። (ሄሮዱተስ የተወለደበት ዘመን ቅ.ል.ክ 490 ላይ ነው)

እርሡን ጠቅሠው የኢትዮጵያን ታሪክ የፃፉትም በእውነታው ያምናሉ። የ1985ቱ የነጋ ወልደ ስላሴ "ባለታሪክ ኢትዮጵያ" የተሠኘው መፃህፍ አንዱ ነው። በዚህ መፃሃፍ በምዕራፍ ሶስት "ቀደምቶቹ ግብፃውያን ይህን የናይል ወንዝ ዴልታ የሚል ስም ሠጥተውት ነበር።" ይለናል። ዓረቦቹ ደግሞ የጥንቱን የናይል ስም ይዘው ናይል ወይም ናይል ምስር ብለው ይጠሩታል። ከ 6ሺ ዓመታት በፊት ታላቁ የናይል ወንዝ ለግብፆች ህይወት እንደበረ ሁሉ አሁንም ህይወት እንደሠጠ ነው።

የናይል ውሃ ግብፅ ከመድረሡ በፊት 3ሺ ተራሮችንና አረንቋማውን ክፍል የኑብያን ግዛት አቋርጦ ይጓዛል።

ሸለቆዎቹ ውስጥ የሚገኙትን ህዝቦች በአንድ መንግስት ጥላ ስር እንዲዋሃዱ የናይል ወንዝ አስተዋዕኦ ማድረጉን ፀሃፍት ሁሉ በአንድ ድምፅ ይስማሙበታል። ኢትዮጵያውያን ከግብፅ ጋር ስለነበራቸው ግንኙነት ሄሮዱተስ ልዩ ጥናት ከማድረጉም በላይ ዲሞክሪቲየስ የተባለው የግሪክ ፈላስፋም እስከ መርዌ ድረስ ተጉዞ "ሂዬሮግላፊ" ስለሚባለው ስዕላዊ ፊደል አጥንቶ የምርምር ዘገባውን አቅርቧል።

እርሱ እንዲህ ይላል፡- "ኢትዮጵያውያን የስልጣኔ እርሾ ስለሰጧቸው ግብፃውያን የኢትዮጵያውያን ውለታ አለባቸው።

ከክ.ል.በፊት 3 ሺ አመታት ቀደም ብሎ በናይል ወንዝ ሸለቆ ይኖሩ የነበሩ የተለያየ እምነት፣ አስተሣሠብና ባህል የነበራቸው ህዝቦች በአንድ የገጠር መንግስት ሲኖሩ ከሌሎች በገጠር መንግስት ከሚተዳደሩ ህዝቦች ጋር ተባምረው አንድ ሌላ ላቅ ያለ መንግስት ማቋቋም ነበረባቸው። እነዚህም መንግስታት ከሌሎች ጋር በመዋሃድ በጊዜ ሂደት "የላይኛውና የታችኛው ግብፅ" በሚል ስያሜ የሚጠሩ ሁለት መንግስታትን መፍጠር ቻሉ።

በቀደመው ዘመን ጥቁር ኑብያንስ የተባሉት ኢትዮጵያውያን አሮጌውን ስልጣኔ በግብፅ ከመሠረቱ በኋላ ነው ከመካከለኛው ምስራቅ አጎራባች አገሮች የመጡ ነገዶች ተባብረው በኋለኛው ዘመን የተባበረ መንግስት መመስረት የቻሉትና እየገነኑ የሄዱት። "ፈርኦን" ማለት "የተባበረ" ወይም "ትብብር" ማለት ነው በእነሡ ቋንቋ። ከላይ የተጠቀሠው መፅሃፍ "በጥንት ጊዜ የናይል ፈሠስ ሸለቆ የመጀመሪያው የስልጣኔ አንቀልባ ሆኖ



ያገለገለ ምድር ነው። በዚህ በስሙ የናይል ሸለቆ አካባቢ የሠፈሩ አያሌ ጎሣዎች ነበሩ። ይህም ዘመኑ ከ5ሺ አመት በፊት ነበር። እነዚህም ጎሣዎች ኑሮዋቸውን በዚህ ሸለቆ አካባቢ በማድረግ አንድ ላይ ሆነው መቀመጥ ጀመሩ። በዚያ ዘመን በዚህ አካባቢ የሚገኙ የነበሩ ነገስታት አካባቢውን በአጠቃላይ ለመግዛት ፍላጎት ስለነበራቸው በመካከላቸው ጦርነት ያካሂዱ ነበር። እነዚህም ጎሣዎች "ነገደ ኩሽ" የሚባሉት ኢትዮጵያውያን ነበሩ" ይለናል።

ወደሌላው የመረጃ ምንጫችን ስናልፍ የ1951 ዓ.ም ቱ የተከለፃድቅ መኩሪያ "የኢትዮጵያ ታሪክ ኑብያ /ናፓታ መርዌ/ 1ኛ መፅሃፍ በምዕራፍ 5 እንዲህ የሚል ሃተታ እናገኛለን። "...የታሪክ አባት የሚባለው ስመጥሩው ሄሮዱተስ ወደ ግብፅ መጥቶ ዐባይንም ጎብኝቶ በፃፈው የታሪክ መፃህፍ፣ እንደዚሁም ዲዮዶር የሚባለው የሮማ ፀሃፊ ከግብፅ በፊት ስልጡንና ገናና የነበረችው ኢትዮጵያ መሆኗን፣ ህዝቦቿም ደግ፣ እንግዳ ተቀባይ፣ ሠላማዊ፣ በጦርነት ጊዜ ጀግና ጎበዝ መሆናቸውን እያጋነኑ ፅፈዋል። ኢትዮጵያም በአገር (በጂዎግራፊ) አቀማመጧ ከፍተኛ (ላዕላይ)፣ ግብፅ ግን ወደ ታች (ታህታይ) ስለሆነች ዓባይም ከላይ ከኢትዮጵያ ወደ ታች ወደ ግብፅ እየፈሠሠ እንደሚያጠጣት፣ አፈርም እያቀበለ እንደሚመግባት እንደዚሁ እንደውሃው አወራረድ ስልጣኔን ለግብፅ መጀመሪያ የሠጠች ኢትዮጵያ መሆንዋን እነዚሁ የታወቁት የጥንት ፀሃፊዎች እነሡንም የተከተሉት ሁሉ አስፋፍተው ፅፈዋል። በኋላ ግን ግብፅ ደግሞ ከኢትዮጵያ ያገኘችውን ስልጣኔ ይበልጥ አስፋፍታ እንደገና የ18ኛውና የ19ኛው ዳይናስቲ ነገስታት ኢትዮጵያን መልሠው እንደገዙ፣ ከዚያ ወዲህ ደግሞ ኢትዮጵያውያኖች አይለው እንደገና ግብፅን ይዘው የ25ኛውን ዳይናስቲ እንደመሠረቱና እንደገዙ ተፅፏል..." ይሉናል።

አንድ ሌላ ተቃራኒ መነሻ እንጨምር። የዴቪድ ላምብ The Arabs (በነብዩ እያሁ "አረቦችና እስራኤል" ተብሎ ተተርጉሟል) "... በግብፅ ምድር ጊዛ የሚገኙት ፒራሚዶች ከመሠራታቸው አንድ ሺ አመት ቀደም ብሎ በ3500 ቅ.ል.ክ ወደ አረቢያ በመምጣት የተዳቀለውና የተዋሃደው ህዝብ በተከታታይ በቡድን በቡድን እየፈለሡ ከሠላጤው ምድር በመውጣት እንደ አዲስ ዘር ወደ ሰሜን ሠፈሩ። በዚህ በኤፍራጠስና ጥግሪስ ወንዝ ሸለቆዎች የመጀመሪያውን የሠው ልጅ ስልጣኔ ፈጠሩ።

"እውሮፓ" ዘላን ጎሣዎች በጭቃ ጎጆዎች የሚኖሩበት አካባቢ በነበረበት ጊዜ ግብፃውያን ታሪካቸውን በራሣቸው ፊደል ይፅፉ ነበር። ለመስኖ ልማት ቦዮችንና ፈሠሶችን በመዘርጋት የቅየሣ ስልትን ፈጠሩ። ፒራሚድን በመገንባት ምህንድስናን አስተዋወቁ። የዓለም የመጀመሪያዎቹ የህዋ ጠበብት በመሆን 365 ቀኖች ያሉት ቀን መቁጠሪያ በማበጀት አንድን ቀን በ24 ሠአታት ከፈሉት። በዓባይ ሸለቆ ከሀቀሉ ፓፒረስ ከተባሉ እፅዋት የመጀመሪያውን ወረቀት ሠሩ። ከእህል የመጀመሪያውን ጠላ፣ ከወይን

የመጀመሪያውን ወይን ጠጅ ጠምቀው በጭቃ ምርግ በተከደኑ ማሠሮዎች አቀረቡ።

"የዓባይ የየዓመቱ ውሃ ሙላት ከሚያስከትለው ጥፋት ለመዳንና ወንዙ የሚያመጣውን ደቡሽት አፈር እህል ለማብቀል ለመጠቀም ግብፃውያን መተባበርና መደራጀት ነበረባቸው። ለዚህም መንግስት አቋቋሙ። እንደ ውሃው ጥልቀት መጠንም ግብር መክፈል ጀመሩ። የወንዙ ውሃ ከፍታ በጨመረ መጠን የበለጠ ደቡሽት አፈር ያመጣል፤ ያ ማለት ደግሞ የበለጠ ምርትና የላቀ ግብር ማለት ነው..." ይላል። ሌላው "የአለም የድንጋይ ዘመን ብቻም አይደለም የሁሉም ቀደምት ስልጣኔ ብርሃን ፈንጣቂ ህዝቦች ጥቁር ኑብያንስ ናቸው" ብለው ያለጥርጥር አስረግጠው የሚገልፁት ተጓዥ ፀሃፊና የስነ ዕፅዋት ተመራማሪ የሆኑት Fredric T.Bolton በ"Plant and Planiet ጥናታዊ መፃህፋቸው (እ.ኤ.አ በ1982) ያሠፈሩት ነው። ዲሞክሪቲየስንና ሄሮዱተስን እንዲሁም ሆሜርን ይጠቅሣሉ። "... ጥቁር ኑብያንስ በላይኛው ግብፅ መንግስታቸውን መስርተው በነበረ ጊዜ በጨረታ ዘመን 5ሺ. ቅ.ል.ክ የመካከለኛው ምስራቅ ቅልቅል ጎሣዎች በታችኛው ግብፅ መስፈር ጀመሩ። በየነገዳቸው እየተመሩ የበርሃ እንስሶችን ያረቡ ነበር። ምናልባትም በኋላ የቴምር ዛፎችን በእንስሶቻቸው እየለወጡ /እየገዙ/ ከላይኛቹ ጋር ሣይስማሙ አይቀርም። የመጀመሪያው ግብር ታችኞቹ ገባሪ፣ ላይኞቹ አስገባሪ ሆነው የተጀመረው በዚያን ጊዜ ይመስላል። ኑብያንሶችም/የኑቢያ ኢትዮጵያውያን/ ወረድ እያሉ ምርታቸውን ያዩ እንደነበር በብዙ ተፅፏል። በእርግጥ አንድ አይደሉም። አማልክቶቻቸው የታችኞቹ ጥጃ/ኮርማ/ ነበር። የላይኞቹ ብዙ አይነት ነበር። ኣሞራና እባብ ይዘወተራል። ኒል /ዓባይ/ የጋራ አምላካቸው እንዲሆንም ተስማምተው ነበር ይባለል።..." ይሉናል።

ካየናቸው ሁተታዎች የምንረዳው የመጀመሪያዎቹ የኑብያ ኢትዮጵያውያን ከዛሬው ኢትዮጵያ አልፈው እስከ ላዕላይ ግብፅ ግዛታቸውን አስፍተው ሲኖሩ፤ ከመካከለኛው ምስራቅ አገሮች በየራሣቸው ነገድ እየተመሩ ልዩ ልዩ ግዛቶች ላይ ህዝቦች ሲሠፍሩ የኋለኛዋን ስልጡን ግብፅን የመሠረቷት ነገዶችም ወደ ጋዛ እና ወደ ላሣ እየተጠጉ በመጨረሻም በታህታይ ግብፅ (መምፊስ) እንደሠፈሩና የአማልክት መቅደሣችውን በመምፊስ ሠርተው ባልሠለጠነ የጎሣ አለቃ ሲመሩ እንደቆዩና የላዕላይ ግብፅ መስራቾች (ቡቴብ) የአማልክታቸውን መቅደስ አቋቁመው በዓባይ ላይ የበላይነትን ይዘው መጤዎቹን ሲያስገብሩ እንደቆዩ፣ ታችኞቹ ከላይኞቹ ግብርናን እንደተማሩ፣ እየቆዩ ሲሄዱም ከጥገኝነት ለመላቀቅ መሠልጠን እንዳለባቸው በመረዳት ለዚህም የአካባቢው ትንንሽ መንግስታት መተባበር እንደሚኖርባቸው በመገንዘብና ተግባራዊ በማድረግ ላዕላይ ግብፅን መጠቅለል መቻላቸውን ነው።

ከድንጋይ ዘመን ወደ ወርቅ ዘመን እስኪሸጋገሩ ድረስ ብርቱ ሆነው መደራጀታቸውንም በቀላሉ እንረዳለን።



ቀደም ሲል "18 ኢትዮጵያዊ ነገስታት ግብፅን ገዝተዋል" የሚል ነገር አይተናል። ይህ ሲባል ግን በ"ዳይናስቲ" ከሚሠላው ውስጥ የሚካተት አይደለም። የመጀመሪያው ዳይናስቲ እና የመጀመሪያው ፈርኦን ፍፁም ተደራጅቶ ከመመስረቱ በፊት የነበሩ ታሪኮች ናቸው። እነዚህን "ሁለት የግብፅ መንግስታት" ተብለው በላይና በታች የተከፈሉትን ጥቂት ፀሃፍት "ሁለቱ ተባብረው ታላቋን ግብፅ መሠረቱ" ይሉናል። ነገር ግን የበርካቶች አገላለፅ ከዚህ የተለየ ሲሆን፤ ይኸውም ታችኞች በራሣቸው ላይና ታች ሠሜንና ደቡብ በሚል የተከፋፈለ አሠፋፈር ሠፍረው በባላባቶቻቸው ሲመሩ እንደኖሩና ዋናው የበላይ ንጉሠነገስትና አስገባሪያቸው የላዕላዩ ግብፅ የጥቁር ኑብያንስ ነባር መንግስት የነበረ መሆኑን ነው። እነዚያን ባላባቶች አስተባብሮ ነው "ማኔስ" የተባለው የመጀመሪያው ንጉስ የግብፅን መንግስት ለመመስረት የቻለው። ግብፆች በአንድ በተባበረ መንግስት ከተጠቀለሉ በኋላ ነው ተደራጅተውና አይለው ኢትዮጵያውያንን ከላዕላይ ግብፅ (ከቴብ) በሃይል ያባረሩዋቸውና ነፃ መንግስት መስርተው ታላቅ መባል የጀመሩት።

ማኔስ የመጀመሪያውን መንግስት መስርቶ ንጉስ የሆነበትን ጊዜ የግብፅን ጥንታዊ የሂዩሮግላፊ ፅሁፍ በመተርጎም የታወቁት ጆሴፍ ፍላቭየስ፣ ማኔቶን ሻምፖሊዮን፣ ሙሴ ማርዮት፣ ወደ ቅ.ል.ክ 5 ሺ. ዓመት ሲያደርሡት ቆይተው ነበር። በመጨረሻ አሜሪካዊው ሚስተር ብሪስትድ ጠለቅ ያለ ምርምር አድርጎ ቅ.ል.ክ 3400 አደረገው። በመጨረሻው መጨረሻ ስቴይንዶርፍ የተባለው የጀርመን ሊቅ የጨረቃውን የዓመት አቆጣጠር /354 ቀኑን/ እና የፀሃይ አቆጣጠሩን ግኝት /364 ቀን ከ6 ሠዓቱን/አመሣክሮ ቅ.ል.ክ 3200 ዓመት ላይ ወሠነው። ዛሬ ድረስ እዚህ ላይ እንደቆመ ይገኛል። ስለዚህ ከሣማሽ ሚሊኒየም በላይ በሆነ እድሜ የተባዛው የነገድ ካም ህዝብ አሮጌውን ስልጣኔ በላዕላይ ግብፅ መስርቶ ነበር ማለት ነው።

አሮጌውን ስልጣኔ በፀባይ የተቀበሉት የኋለኞቹ የታህታይ ግብፅ መስራቾች ደግሞ አሮጌውን አድሠው በሃይል ላዕላይ ግብፅንም ሲጠቀልሉ የአሮጌው መስራቾች ወደ ኑብያ ኢትዮጵያ ማለትም ወደ ናፓታ ተሸጋሽገዋል። ናፓታ የኢትዮጵያ የመናገሻ ከተማ የሆነችው ለመጀመሪያ ጊዜ ቅ.ል.ክ 3200 ላይ እንደሆነ በሂዩሮግላፊ ፅሁፍ ያለአንዳች አወዛጋቢ ሁኔታ የተረጋገጠ ነው። ምናልባት የውጪ አገር ፀሃፍት 3200 B.C ብለው ስለፃፉትና የአገር ውስጥ ፃሃፍትም በተመሣሣይ 3200 ቅ.ል.ክ ብለው በመፃፋቸው በዘመናችን አቆጣጠር የ7 ወይም የ8 አመት ልዩነት ካልኖረ በቀር ትክክለኛው ጊዜ የተጠቀሠው ነው። ከዚህ ዘመን በፊት ግን ቴብ መናገሻቸው ነበረች። የመጀመሪያው ፈርኦን እነዚያን ሁሉ ነገዶች አደራጅቶ ኢትዮጵያውያኑን ከቴብ አባረረ። ስለዚህ ወደ ናፓታ መጡ። በዚህ መሠረት ከ3200 B.C በፊት የነበረው ስልጣኔ ሁሉ ምንም እንኳ አሮጌ ቢሆን የኑብያንሁ ነው። የፈርኦኑ ምስረታ መምፊስ ስለነበር እንደማለት።

በርካቶች ይህን ዘመን ያሠፍሩና "ግን እንዴት? በማን ዘመን?" ብለው በመጠየቅ ይመስላል ቁጥሩን አስቀምጠው ብቻ ያልፋታል። ለምን ቢባል በ3200 ናፓታ መናገሻ ከሆነች ይህ ዘመን በነገስታቱ ዝርዝር ላይ እንደሚታየው የካም (የኖህ ልጅ) አስተዳደረ ተብሎ የተቀመጠበት ዘመን ነው። ከዚህም በላይ የህዝብ ብዛት የለም፣ በዚህም ላይ ከካም ቀጥሎ የነገሠው ኩሽ ነው፣ እሁም ተከታዩ ሠብታህም ከዚህ በኋላ ነው ወይ የመጡት? እንዴት እነ ጣና ይጠቀሟሉ?.. ወዘተ.. የሚል ጥያቄ ስለሚያስነሣ ነው።

ኖኅ ከመሞቱ በፊት በነበረው 350 አመታት ካም፣ ሴምና ያፌት ምን ያህል ሊስፋፉ እንደሚችሉ ግልፅ ነው።

ካም እዚህ በነበረ ጊዜ በዓለማዊውም፣ በመንፈሣዊውም ፅሁፍ እንደምንረዳው፣ ወይም ሶስቱ የኖኅ ልጆች ከመሞታቸው በፊት ዓለም በሚሊዮኖች በሚቆጠሩ ህዝቦች መጥለቅለቋን ነው። ስለዚህም ካም፣ ኩሽ፣ ሰብታህ... እየተባሉ በተከታተሉ ቁጥር ዋና ዋና ግንዱ ሲፃፉ እንጂ በውስጣቸው ያሉት ትውልዶች አንዳንድ ግዛት ለየብቻቸው እየያዙ አገር መስርተዋል፣ ነግሠውበታልም። ገንን ካሉ አገር በእነሡ ስም ትሠየማለች። የኩሽ ልጅ የሆነው ናምሩድ ወደ ሠናአር ከሄደ በኋላ የራሡ የናምሩድ ልጅ አቢስ ከነ ነገዱ በዚች ምድር ይኖር ስለነበር ኩሽ /የኩሽ ነገድ ምድር፣/ አቢስ /የአቢስ ነገድ ምድር/፣ አገሩን አቢሲኒያ ብለው ሠይመውት እንደነበረ ወደፊት የምናየው ነው። አንድ የትውልድ አለቃ ቢነገስም ባይነግስም ነገዱን ይዞ የሠፈረበት ቦታ፣ አካባቢ ወይም አገር በስሙ ይጠራል። ወይም ሊጠራ ይችላል፣ የራሡን ነገድ በደንብ ካደራጀና ካጠነከረ ሌላውን ነገድ ወግቶ ሊያስገብር ይችላል.. ወዘተ። ቋንቋውን ሊያዘምን ይችላል... ወዘተ። በኋላቀርነቱም ሊቀጥል፣ ሊሠለጥን ይችላል ወዘተ። በሌላ አገላለፅ ዋናው ግንድ እንዳለ ሆኖ ቅርንጫፎች ይኖራሉ። የካም የልጁ ልጅ ናምሩድ ባቢሎንን መስርቶ ታላቅ ንጉስ ሆኖ ተመልሶ መጥቶ ወንድሙን ሰብታህን ሊወጋው ቢችል (ነገዱን) ሊገርመን አይገባም ነው ለማለት የተፈለገው። እዚያው ከቀረ ታሪኩ እዚያው ይፃፍለታል። የሆነውም ያ ነው። በሌላ በኩል የልጅ ልጅ አያቱን ተመልሶ መጥቶ ሊወጋውም ይችላል። የአንድ ሠው እድሜ ከ200 በታች ሆኖ የምናየው ከባቢሎኑ ሴራ በኋላ ባለው ጊዜ ነው። ለማንኛውም ግን ትልቁ ጥያቄ ወጥ ግዛት ነው ወይ? የሚለው ነው። ከኢትዮጵያ እስከ ባቢሎን ወጥ አልነበረም። ከኢትዮጵያ እስከ ቴብ ግን ወጥ ግዛት ነበር። ለምሣሌ ናምሩድ በኢትዮጵያ የነገስታት ዝርዝር የለም። በባቢሎኑ ግን አለ። የሡ ወንድሞች መናገሻቸውን ጣና ያደረጉትም፣ ቴብ ያደረጉትም በኛ ታሪክ ነገስት ተዘርዝረዋል። ወጥ ግዛት ስለሆነ። ናምሩድ በባቢሎን ሆኖ ኢትዮጵያን ልግዛ ቢል ግን ከኢትዮጵያ እስከ ባቢሎን ወጥ ግዛት ሊሆን ይገባል።



እንግዲህ... የሠው ልጅ የፍጥረት መጀመሪያ አዳም /አደም/ ነው በሚለው አይደል አምነን እዚህ ድረስ የመጣነው? ጥሩ ነው። ልክ ነን። ስለዚህ አዳምና ፈጣሪው የተነጋገሩበት ቋንቋ ነበረ። እብራይስጥኛ እንደሆነ ብዙዎች ያምናሉ። ግዕዝ ነው የሚሉ ብዙዎችም አሉ። ዓረብኛ ነው የሚሉም በርካታ ናቸው። ምንም ይሁን። ብቻ ግን የሚነጋገሩበት ቋንቋ ነበራቸው። ኖኅም ከአዳም 10ኛ ግንድ እንደመሆኑ መጠን ያው የድሮውን ቋንቋ ነበር የሚናገረው። ከፈጣሪው ጋርም በዚያው በሚሠማው ቋንቋ ይነጋገሩ እንደነበር ግልፅ ነው። ፊደል ግን የለም። ፊደል ያለመኖሩም ሌላ እውነት ያስጨብጠናል።

ከቋንቋ መደባለቅ በፊት በነበረው ጊዜ በሐይማኖታዊውም ሆነ በሣይንሣዊው ምርምር የተረጋገጠው ስዕል እንጂ የመፃፊያ ፊደል አልነበረም። እስከ ቅ.ል.ክ 2000 ዓመት ድረስ የሠው ልጆች ወጥ ሆኖ በሚነበብ ተከታታይ ሆሄ /ፊደል/ የፃፉት ነገር የለም። የግብፅ ሂዩሮግሳፊ፣ የግራክ ፒክቶግራም ብቻ ከልደት በፊት 3 ሺ ዓመት ድረስ ይታወቃሉ። እነሡም በአንድ ስዕል ብዙ መልዕክቶችን የሚገልፁ ሆነው የተዘጋጁ ናቸው። ግሪክ ስንል የኋለኛዋን አይደለም። "ሲዶን" በምትባል ጊዜ ነው። አቴናውያን፣ ስፓርታውያን ገና ሣይታወቁ፣ የካም ነገድ በሆነው በከነዓን የበኩር ልጅ የተመሠረተውን ከተማ ነው። ስለግሪክ አመሠራረት ከተክለፃድቅ መኩሪያ ሐተታ እንረዳና ወደ ፊደሉ ስንመለስ ነገሩ ግልፅ ይሆናል።

"ባሬ ግሪክ በሚባለው ስም የተጠቀሰው ህዝብ ያን ጊዜ ግን ዘሩም ቋንቋውም የተለየያ ነበር። የኑሮውም ጊዜ በግምት የሚታወቀው ከክ.ል.በ1600 ዓመት ጀምሮ ነው። ግሪኮች የሚባሉት በምዕራብ በኩል ባለው አገር ተቀምጠው ሳለ ደግሞ ከምስራቅ የመጡት የዮኒክ ቋንቋ የሚናገሩ ዛሬ አቴና ባለበት አቲካና፣ አውቢያ፣ በሚባለው በምስራቅ ወገን ተቀመጡ። እነዚህም የአቴናን ከተማ የመሠረቱ ናቸው። ደግሞ ግማሾቹ ከላይ ከሠሜን ከቴሳሊያን፣ ከትራችያ መጥተው እስከ ቆረንቦስ ድረስ ያለውን አገር ያዙ። እነዚህም ለየግላቸው ሶስት ቋንቋ (ዲያሌክት) ለየራሣቸው የሚናገሩ ህዝቦች በያሉበት ተቀምጠው ጥቂት መቶ ዓመታት እንደኖሩ ከሠሜን ዶሪክ ከሚባለው ስፍራ ቋንቋቸውም የራሣቸው የሆነ የዶርያ ህዝቦች አገራቸውን ትተው በተሣልያ አልፈው የዛሬውን ደቡብ አገር የፔሎፒኒን የላቆኒን አገር ያዙ። ከዚያም አብረዋቸው ከተደባለቋቸው ግሪኮች ጋር ያለፉት ክራችና ኸሮን የሚባለውን አገር እቀኑ። የስፓርታንም ከተማ ከተሙ።..." ( ተክለፃዲቅ መኩሪያ 1965 ዓ.ም)

ይህ ሁሉ ከቋንቋ መደባለቅ በኋላ የሆነ ነው። ስለዚህ በይፋ የሚታወቀው የነገድ ምስረታ በመካከለኛው ምስራቅ የተጀመረው ከህዝቦች ብተናና ከቋንቋ መፋለስ በኋላ ነው። ለምሣሌ አብርሃም የእብራውያን ነገድ መስራች መሆኑ ይታወቃል። አብርሃም ይስሃቅን ይስሃቅ ያዕቆብን ከወለዱ በኋላ ነው ያዕቆብ የሚለው ስም እስራኤል በሚል ተለውጦ ነገደ እስራኤል

የሚባሉ አንድ ሆነው ነገር ግን የተከፋፈሉ ዘሮች የምናየው። ከነገድ ምስረታ በኋላ ቀስ በቀስ ሁሉም ነገድ ወይም አገር የየራሱ ፊደል ሲኖረው ችሏል። (አብርሃም የኖረው ከ2ሺ. - 1800 ቅ.ል.ክ ነው) የሁሉም ነገድ የመፃፊያ ፊደል ከየት መጣ? ካልን ወይም መሠረቱን ከጠየቅን ሁለት ቀደምት አገራት ስለሚነሡ ነው የግሪክን አመሠራረት ከላይ ለማየት የተገደድነው። እናም ከግብፅ፣ ከግሪክ፣ ከባቢሎንና ከሌሎች አጎራባች ቀደምት አገራት ክብ ውስጥ አንወጣም። ሙሴ በሲና ተራራ የተፃፈ ህግ የተሠጠው ቅ.ል.ክ. 1300-1200 ባለው ጊዜ መካከል ነው። እስራኤላውያን በግብፅ በባርነት ያሣለፉት ከ1700-1300 ቅ.ል.ክ ድረስ ለ400 አመታት ያህል ነው። ግብፅ ስዕላዊ ፊደል ያገኘችው 3200 ቅ.ል.ክ ላይ ነው። ቴብን የራሷ ያደረገችውም በዚህ ዘመን ነው።ቴብ ማለት የአማልክት ቤት ማለት ሲሆን በጥንታዊው ስዕላዊ ፊደል ቤት ብለው ፅፈውበት ነበር። ግብፅ አገር ከመሆኗ በፊት።

የመጀመሪያው ስዕላዊ ፊደል መስራቾች ግብፃውያን መሆናቸው በይፋ ይታወቃል ተብሏል። ሃይሮግላፊ አሉት። ከዚያ ግሪኮች ፒክቶግራም አሉትና ቀጥለው ቅዱስ የፊደል ቅርፅ የሚል ስያሜ ሠጥተው ከዚያው ከስዕል ያልወጣ ፊደል ቁጥራቸውን በርክት አድርገው አሣደጉት። ግብፆች 3 ሺ. ዓመት ላይ "ሂዮራቲክ-የቀሣውስት ፊደል" አሉና አሁንም አሣደጉት። በጥቅሉ ከ4ሺ. -2ሺ. ዓመት ቅ.ል.ክ በቤተመንግስትና በካህናት አለቆች ብቻ ይታወቅ የነበረውን ስዕላዊ ፊደል ለአፃፃፍ እንዲመች ሆኖ ነገር ግን ያው ስዕልነቱን ሣይለቅ እስከነሙሴ ዘመን ድረስ ቆይቶ ወደፊት ታሪኩን እንደምናገኘው በመጨረሻ በኑብያ ኢትዮጵያ በናፓታ ቆይቶ በንገሡው በቴሃርቃ ጊዜ "ዲሞቲክ-የህዝብ ፊደል" ተብሎ ተሻሽሎ ይሠራበት ጀመር። ይህ ኢትዮጵያዊ ንጉስ ግብፅንም ሊቢያንም መካከለኛው ምስራቅንም የገዛ ንጉስ ነበርና ዲሞቲክን በደንብ እንዲስፋፋ አድርጎ ነበር። በኋላ ላይ ታላቁ እስክንድር ታላቅ ተብሎ ግብፅን ሲይዝ የግሪክና የዲሞቲክ ተቀላቅሎ ኮፕት የሚባለው ፊደል ይሠራበት ጀመር። ይህም ቅ.ል.ክ 300 ላይ ተጀምሮ ለ1ሺ. አመታታ ያህል ቆየና በ700 ዓ.ምህረት ከእስልምና መፈጠር በኋላ ግብፅ በዐረቦች ስትያዝ የአረበኛ ፊደልና ጽሁፍ ተተካ። በኑብያና በግብፅ ሀንቶ ቀረ።

ወደነጥባችን ስንመጣ በጥንቱ በፓፒረስ/በልጥ ብራና/ ይፃፍ የነበረው ስዕላዊ ፊደል ምንም እንኳ ለብዙ ሺ. ዓመታት ተለዋወጠ ቢባልም መነሻውንም፣ ይዘቱንም፣ እምብዛም አልለወጠም፣ ከጥቂት መከረባበት በስተቀር።::: እሡ ይቆየንና ግን ፊደላቱ ሁሉ መነሐ የተባሉት ከግብፅ፣ ከግሪክ አልፍ ሲል ባቢሉን። እነዚህ አገራት ቀደምት ታላላቅ መንግስታት የተመሠረተባቸው አገራት ናቸው። እነዚህ ሁሉ አገራት ቋንቋ ከመደባለቁ በፊት ያንኑ አንድ ቋንቋ የያዘ ህዝብ የሠፈረባቸው ናቸው። እነዚህ ሁሉ አገራት ከኢትዮጵያ በሄዱ ጥቁር ህዝቦች የተመሠረቱ ናቸው። እነዚህ ሁሉ አገራት ከቋንቋ መደባለቅና ከህዝብ ብተና ጋር በተያያዘ ልዩ ልዩ በተለይ የሴም ነገዶች ሄደው የታጨቁባቸው አገራት ናቸው። ታላላቅና አዳዲስ



መንግስት መስርተው ከመግነናቸው በፊት ግን ነገደ ካም ኩሽ በጣም ያልሠለጠነና አሮጌ ስልጣኔ የሚባለውን መስርተዋል። የገጠር መንግስት የሚባለውን አቋቁመዋል። ፊደልንም ሣይቀር መስርተዋል። ቀደም ሲል በ"መግባቢያችን" ላይ ካትትትናቸው የልዩ ልዩ ፀሃፍት ሃተታዎች ውስጥ የዶክተር ተፀልደ ትኩዕን መፃህፍ ጠቅሠን እንዲህ ሲሉ አንብበን እንደነበር የሚታወስ ነው። "…. የካም ዘሮች ያልሠፈሩበት ቦታ አልነበረም። ሔሮዱተስ የግሪክ ቀደምት ነዋሪዎች የካም ዘሮች ነበሩ ብሏል።" የሚል ነገር አይተን ነበር። ስንቀጥል "የጥንት ግብፃውያን ስልጣኔ የነጮች ስልጣኔ እንዳልሆነ የሚከራከሩ ወገኖች የሲፊንክስን ሃውልት ፊት ማየት በቂ ነው ይላሉ። ያ ፊት ደግሞ የጥቁር ፊት ነው። አሜሪካ በሚገኘው አፍሮ ሴንተሪዝም ማዕከል እንዳውም በግሪካዊነት የሚታወቁት ሶቅራጠስ፣ ሆሜር፣ የሂሣቡ ሊቅ ፓይታጎረስና ኢኩሊድ ሁሉ ጥቁሮች እንደነበሩ ያስረዳሉ። በስነ ፅሁፍ ረገድም ቢሆን የግዕዝ ሳብዕ ፊደላት የተለየ ድምፅ ተሠጥቷቸው በቁማቸው ከኢትዮጵያ ፊደላት የተቀዱ ናቸው። ይህ በተጠየቅ ወይም በሎጂክ ያለ እውነታ ነው፣ እንደዚሁም በዚህ በኢትዮጵያችን ሳላው ሃይልና ለተሠሩት ትልልቅ ስራዎች ተጠያቂ የሆነ ትውልድ ነበረ፣ አለም፣ ይኖራልም። ይህ እሣተ ነበልባል ትውልድ ነው። ጥበብንና እውቀትን ከመጀመሪያው ጀምሮ ለዓለም ህዝብ በግብፅ አድርጎ ወደ ግሪክ በመላክ የታላቅ ስልጣኔ ባለቤት አስማተሪና መሪ የሆነው።" የሚል ነገር እናደምጣለን ወይም እናነባለን።

ይህ ስለተባለ ብቻ ሣይሆን የመጀመሪያውን ስዕላዊ ፊደልን ጥቁር ኑብያንስ ባሠሯቸው መቅደሶች ላይ "ቤት" የሚል ዛሬ የ"በ"ፊደል ቅርፅ ያለው ፅሁፍ ከግብፅ ምስረታ በፊት ተፅፎበት የነበረ በቁፋሮ ተገኝቷል።

አንባብያን ከመፅሃፍ ቅዱሡ ወጥቶ የተዘረዘረውን የካም ኩሽ ነገድን መለስ ብላችሁ ብታዩ ታሪካችን ፍሠቱን ጠብቆ ከላአሳይ ወደ ታህታይ መፍሠሡን በቀላሉ ታረጋግጣላችሁ እላለሁ። ግልጽ ነው "ፈገግ"ም ያሠኛል።

የኖኅ መርከብ በጣናው/በኢትዮጵያው/ አራራት ተራራ አረፈች። ማንም "እረፍ!" ሊለኝ አይችልም እዚህ ላይ፤ ብትሉኝም አላርፍም። ተግባብተን እንደመጣነው እዚህኛው ትረካ እዚያኛው ትረካ በታሪካችን ላይ ቀንጣት ተፅእኖ አያሳድርም። አንባብያን በመሠላችሁ ልትወስኑ ትችላላችሁ። ምክንያቱም ከሶስት ነገር አያልፍም ታሪኩ። ዋናው የጥፋት ውሃ መከሠቱን አለመካድ እንጂ መስማማታችን አይቀርም። ለነገሩ በሣይንስም በቅዱስ ቁርዓንም በመፅሃፍ ቅዱስም ተረጋግጧል። ስለዚህ፦

1ኛ ከጥፋት ውሃ በኋላ የኖኅ መርከብ በአርማንያው አራራት ተራራ አርፋ ኖኅና ቤተሰቡ፤ ሲተርፉ ሴምንና ያፌትን ትቶ ወደ ኢትዮጵያ ካምን ይዞ መጥቷል። ሁለቱ ልጆቹ እውሮፓንና እስያን ይዘው ሲስፋፉ አንደኛው ልጁ ካም በአፍሪካ ተስፋፍቷል፣ የካም ልጆች እስከ ኑብያ ድረስ አልፈው ሔደው ሃያላን ሆነዋል፤

2ኛ ከጥፋት ውሃ በኋላ ኖኅና ቤተሠቦቹ ሲተርፉ የቀድሞ ኑሯቸውም እዚያው መካከለኛው ምስራቅ ነበርና አሁንም መርከቧ እዚያው አካባቢ አርፋ ኖኅም እዚያው ቀርቶ እንደተባለው ለሶስቱ ልጆቹ ግዛት ሲያካፍል አፍሪካን ለካም ሠጥቶት ወደዚህ መጥቶ ተስፋፍቷል፤

3ኛ ከጥፋት ውሃ በኋላ የኖኅ መርከብ በጣናው አራራት ተራራ አረፈችና ቤተሠቡ ጥቂት ዘመን ቆይቶ ሲምና ያፌት ከኢትዮጵያ ተነስተው ወደ እስያና ወደ አውሮፓ ሔደው ካም እዚሁ ቀረ። እናም ተስፋፋ። በመሃል እነ ናምሩድ እነከነዓን ወደ ሠው ርስት ዘለቀው ገቡ።

ሁለተኛው ላይ ልንወያይብ አይገባም። ከጥፋት ውሃ በኋላ ኖኅና ቤተሠቦቹ ሲተርፉ የቀድሞ ኑሯቸውም እዚህ ስለነበር አሁንም መርከቧ እዚሁ ስላረፈች ኖኅም እዚሁ ቀርቶ እንደተባለው ለሶስቱ ልጆቹ ግዛት ሲያካፍል አፍሪካን ለካም ሠጥቶታል ልንል እንደምንችል መታሠብ አለበት። ልክ በዚሁ መጠንም ኖኅ የዓዳምን መኖሪያ እንዲወርስ ተፈቅዶለት ከሆነ ገነት እዚህ ነበረች፤ ገነት እዚህ ካልነበረችና በአርማንያው ከነበረች ደግሞ ብሎቱን ጌታ ሀሩዩ " ትተነዋል" ያሉትን "ነገዩ አሪን" እናስነሣለን። ያኔ የ7ሺ አመት ታሪክ ይኖራታል ማለት ነው። አዳም ተባሮ የተሸኘባት ምድር ከሆነች የግድ ነው። ግዮንስ የት ሊወድቅ? "ሚስጥር ኖት" እያልን ለማለፍ እስካልተዘጋጀን ድረስ እየተፈላሠፍን አይሆንም። አይደለምም።

የኖኅ መርከብ በጣናው አራራት ተራራ ካረፈች በኋላ ባለቤቱና ልጆቹ እንዲሁም አብረዋቸው የነበሩት እንስሣ አራዊትና ነፍሣት ሁሉ ይወጣሉ። ኖኅም እስከመጨረሻው እውነተኛውን አምላክ ሲያመልክና በግብርና ሲተዳደር ኖረ። የቤተሠቡ ሁሉ ቋንቋም አንድ ነበር። ኖህ ከመሞቱ በፊትና በኋላም ነገዶች እየበረከቱ ነበር። በየመሠረቱት ግዛት በየዋሻው የእንስሣና የአውሬ ስዕሎችን እስመስለው ይስሉ ነበር። የተባዙት ነገዶች በያሉበት ሆነው የመሠላቸውን ማምለክ ጀመሩ፤ በአጠቃላይ ከ3844 ቅ.ል.ክ እስከ 3200 አካባቢ አርጌው ስልጣኔ በአፍሪካ እየተስፋፋ መሔድ ጀምሮ ነበር። በዓለምም ጭምር።

በዓባይ ሸለቆዎች ድንበር የሚበቅለው ፓፒረስ የተባለው ተክል (አሁንም በጣና ሃይቅ ደሴቶች በብዛዎቹ ይበቅላል) በልጡ ላይ የመጀመሪያውን ስዕላዊ ፊደል የኖኅ ልጆች ፈጠሩት ወይም ጀመሩት አሌፍ፣ ቤት፣ ጊሜል፣ ዳሌት… እያለ  የሚከታተለው የሂብሩ ፊደል ወይም አ በ ገ ደ እየተባለ የሚነበበው፣ በአርበኛም መነሻ የሆነው፣ በግዕዝም የፊደል መነሻ የሆነው በአማርኛም "ሀ" ተብሎ የሚነበበው በላቲንም " a" (ኤ) ተብሎ የሚነበበው የመጀመሪያው የስዕላዊ ፊደልም፣ የሠለጠነው ተከታታይ ፊደልም ምንጩ ይሄው ሆኑ። ቤት!



ይህንንም ይዘው እነ ናምሩድ አባታቸው ባልፈቀደላቸው (ከኖኅ ምርቃትና በርኮት ውጪ በሆነ አካሄድ) ሔደው በመካከለኛው ምስራቅና በአጎራባች አገራት መንግስት መሠረቱ። ከዚች ምድር ይዘውት የሄዱት ስልጣኔ አለ። የመጀመሪያው የጥጥ ፈትል ውጤት የሆነው ሸማ፣ ጠላ፣ ከወይን የሚሠራ ጠጅ፣ በበሬ የማረስን ግብርና፣ ዝናምን ጠብቆ ከማረስ ጋር በተያያዘ ክረምት፣ በጋ፣ ፀደይ… የሚባሉትን የወራት ክፍልፋዮች ለይቶ የማወቅን ጥበብና ከዚሁም ጋር ተያይዞ የጨረቃውን አቆጣጠር ወደ ፀሃይ አቆጣጠር ለመለወጥ የሚያስችል ዘዴን፣ በጠብታዎች ልኬት ቀንን በሠዓት መከፋፈል መቻልን፣ ንብን በቀፎ ማከማቸትንና ማርን ማግኘት መቻልን፣ ለመድሃኒት የሚሆኑ እፅዋትን ለይቶ ማወቅን፣ ሁሉንም ነገሮች ልጆች ከአባታቸው ከኖኅ ተምረው ነበር። አባታቸውም ከጥፋት ውሃ በፊት የነበረውን የአኗኗር ዘዴ ዘርዝሮ ያውቀዋልና፣ ከእነርሡ በፊት በዙ ኖሯልና፣ የቀድሞውን ስልጣኔ በዚች ምድር አስተምሮ ነበር መርቆ የሸኛቸው። እነ ናምሩድ ግን ፈጠኑ። የፈጠኑት በስልጣኔ ብቻ አልነበረም። ያን ጊዜ እንደ ስልጣኔ በሚቆጠረው በጣኦት አምልኮም ፈጣን ነበሩ። እዚያ ሄደው አጥለቀለቁት። የሠፈሩባት ምድር ሁሉ ለሌላ ነገድ ትሠጥና መንግስትም ይመሠረትና ስልጣኔው ሁሉ ይጠረስና ይዘቱን ሳይለቅ መልሶ በሚበቱኑ ነገዶች አማካኝነት ይሠራጫል። በራሷ በኢትዮጵያም ይህ መሠሉ ክስተት ሲከናውን እናያለን። ከእነዚህ ውስጥ በኋለኛው ዘመን ውርርሡን በደንብ የምናየው ቋንቋ አንዱ ነው። ፊደልም ጭምር።

እናም አርጌው ስልጣኔ የሚባለው ሁሉ ምንጩም ፍንጩም ከዚህ ተለኩሶ እየነደደ እዚያ የደረሠ እንጂ ሌላ አይደለም። ግን የሌላውን ሲለኩሡ የራሣቸው ጠፋባቸው። ባጠቃላይ ቀደምት ስልጡን አገር ግብፅ ነች ተብሎ እስከተወሰነ ድረስ የግብፅ ስልጣኔ ከኢትዮጵያ ስለተወሠደ፣ ሚስጥሩ ሁሉ ይፍታታል።

"የለም የግብፅ መስራቾች ስልጣኔን ከምስራቅና ከባቢሉን ይዘውት የመጡት ነው!" የሚል ተከራካሪ ከተነሣብንም "ያንንስ የመሠረቱት እነማን ሆኑና?" ብለን በመጠየቅ እንገት እናስደፋለን። የነናምሩድ ጉዳይ በመፅሃፍ ቅዱሡም በዓለማዊ ፅሁፉም በደንብ ስለሚታወቅና የኖሩበት ዘመንም ገሐድ ስለሆነ፣ እንዲሁም እነርሡ እዚያ በኖሩበት ዘመን ወንድሞቻቸው ኢትዮጵያ ላይ ነግሠው ስለነበር መፈናፈኛ የለም። እንዲያው ጠንከር ያለ ተከራካሪ አጋጠመን እንበልና " ከግብፅ ወደ ኑቢያ ኢትዮጵያ የካም ዘሮች ፈልሠው መጡ እንጂ እዚህ ሰብታህ የሚባለው የናምሩድ ወንድም የምትሉት አልነገሠም ነበር" ቢሉን እኛ "ያማ ከሆን በዚያ ዘመን እዚህ ንጉስ ከሌለ ግብፃውያን ሃያል የሆኑበት ዘመን ነበርና፣

ሠው እንደመሆናቸው መጠን የሁሣን ጥቅም ያውቃሉና ንጉስ የሌለበትን አገር ይይዙ ነበር እንጂ ግብፅን የሙጥኝ ብለው ተወስነው የሚቀሩበት ምን ምክንያት ይኖራል? ለድፍን 1ሺ ዓመት ከኢትዮጵያውያኑ ጋር ሲዋጉ፣ ሲታረቁ ኖረው አይደለም እንዴ በመጨረሻ ቅ.ል.ክ 1500 ላይ ተማክቶላቸው ኢትዮጵያን ማስገበር የቻሉት? ምን የሚሉት መከራከሪያ ነው?" ብለን እንከፌግለን። ለነገሩ በ "ሰባታሁ" የኢትዮጵያ ንጉሰነገስትነት ያልተስማማ "ቀደምት" ፃሃፍት የለምና ቢከራከሩን ብለን የተመኘነው ባእዳኑን ነው። ስለዚህ ዝግ ነው። ምናልባት ያልደፈንነው ቀዳዳ ካለ "የዘመን አቆጣጠሩ የኛንተ ዝቅ ያለ ነው፣ እኛ ከእናንተ በፊት ገናና ነበርን" ብለው ቢሞግቱንና የመንፈሳዊውን አቆጣጠር አንቀበለውም ቢሉን እነ ሉሲን፣ ሠላምን፣ አርዲን፣ ካዳሙን፣ እናስነሣለን። "በጥፋት ውሃ የነፈሩ ፖስቸሪይዝድ አጥንቶች ናቸው" ቢሉን ደግሞ እሡም የተገኘው እኛ ጋ ነው እንላለን።

ከዚህ የበለጠ ማጠሪያ ቢገኝ የኢትዮጵያን የታሪክ አጥር በደንብ እናጥረው ነበር። ልክ ናምሩድ የባቢሎኑን ቅጥር እንዳጠረውና በኋላ የነገሠችው ንግስት ሴሚራሚስ ጠግባ ህንድን እወጋለሁ ብላ ዘምታ ጦሯ ተሸንፎ የህንዱ ንጉስ ግዛቷን ዘልቆ ገብቶ ቅጥሩን እንዳፈረሠበት ሁሉ የኢትዮጵያ ታሪክም በደንብ የታጠረ የነበረና በኋላ የፈረሠ ነው። የባቢሎን አጥር በኋላ ላይ እንደነገሩ ታጠረ። የኛ ግን ዛሬ ድረስ ሳይታጠር ቆይቷልና በዚህ መሰሉ እውነታ በተቻለ መጠን ፈርሶ ከመቅረት እንታደገዋለን። ሳሁኑ ግን የዓለም ቀደምት ስልጣኔ ከኢትዮጵያ መሄዱን አፅድቀን እንለፍ። በሙሉ ድምፅ። ግልፅ ነዋ!

# ምዕራፍ ፭

## የአጋዚያን ዘመነ መንግስት

እነዚያ ያየናቸው ታሪኮች ሁሉ ይከናወኑ የነበሩት ኢትዮጵያ ውስጥ የነገደ ካም ነገስታት እየተባሉ እየተከታተሉ ይነግሡ በነበረበት ዘመን ነው። ምንም እንኳ የኢትዮጵያን ታሪክ የያዙ ቀደምት ዕሁፎችና ፀሃፍት (ዋና መነሻቸውን ታሪክ ነገስት ያደረጉ) ስማቸውንና የገዙበትን ዘመን ሳይዘረዝሩ ባያልፉም የፈፀሙትን ታሪክ አብሮ ለማተት የተቻለበት ሁኔታ የለም። ስለዚህ የአገር ውስጥ መነሻችን እንዳለ ሆኖ በየሠው አገሩ ብናማትርና ብንቀሳውጥ አግባብነት ይኖረዋል።

እናም የነገስታት መነሻ ሆነው እስኪተዘረዘሩና ስማቸውና የገዙበት ዘመን እስከሠፈረ ድረስ ማን በዘመኑ ምን እንደፈፀመ ገና ለገና በዝርዝር አልታወቀም በሚል መነሻ ምንም ሣይፈፅሙ እንደኖሩ መቁጠር አይቻልም። በዘመናቸው ምን እንደፈፀሙ ካልታወቀ እድሉ ካለ በዘመናቸው ምን እንደተፈፀመ ማወቅ መጠነኛ ግንዛቤ ያስይዛል።

እንግዲህ ቀደም ሲል ያየናቸው እንደ አንዳንዶቹ ከኖኅ፣ እንደ አንዳንዶቹ ከካም፣ እንደ አንዳንዶቹ ከኩሽ፣ እንደብዙዎቹ ከሠብታህ ጀምረው እስከ ጲኦሪ1ኛ ድረስ ነገስታቱ ከተዘረዘሩ በኋላ የጲኦሪ ዘመን ላይ የተለየ ነገር ያከሥታል።

"ነገደ አጋዚያን" የሚባሉት ይተካሉ። ይህ የብዙዎች ድምዳሜ ነው። የነማን? ከተባለ "የነገደ ካም ነገስታትን የሚዘረዝሩ ፀሃፍት ሁሉ" ነው መልሡ። በውጭ አገር ፀሃፊ ለሚያምን እነ ሽንሞሪዎ፣ በአገር ውስጥ ፀሃፊ ለሚስማማ እነ አለቃ ታዬ፣ እነብላቴን ጌታ ህሩይ፣ እነተክለፃድቅ መኩሪያ ወዘተ....።

*ታሪኩ ባጭሩ ይሄ ነው። እስከ ጲኦሪ 1ኛ ድረስ የተዘረዘሩት የነገደ ካም ነገስታት ናቸው። እንዲሁም የካም ወንድም ሴም ዘጠኝ ልጆችን ይወልዳል። ከዘጠኙ አንዱ አርፋክሲስ ይባላል። እርሡም ሳባህን፣ሳባ ሔቦርን፣ ፋሌትንና ዮቅጣንን ይወልዳል። ዮቅጣን ደግሞ 13 ልጆች ይወልዳል። ከእነዚህም ከ13 ነገዶች አምስቱ ማለትም ሳባ፣ አባል፣ ኦፊር፣ አቢማኤል፣ ሐዊላ የሚባሉት ከወንድሞቻቸው ተለይተው ራቅ ያለውን የመካከለኛው ምስራቅን አገር ትተው ወደ የመን ተጠግተው ተቀመጡ። በየመን ሲኖሩም የህንድ ነገስታት እየወጉ ሲያስቸግሯቸው እላይ የተዘረዘረው የነገስታት ዝርዝር እንደሚያመለክተው የካሙ ዘር ጲኦሪ 1ኛ በነገሠበት ዘመን በ1980 ቅ.ል.ክ የመንን ለቀው ወደ ኢትዮጵያ ተሻግረው መጡና ስቱ ነገዶች ሳባ በትግሬ፣ አባል በአዳል፣ኦፊር በአጋዜን ተቀመጡ። እንደመጡም የመጀመሪያውን አምስቱን አመት ለካሙ ነገድ ለጲኦሪ 1ኛ ሲገብሩ ኖሩ።*

በዚህ መካከል የህንድ ንጉስ ራማ /ብርሃማ/ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ጲኦሬን ወግቶ አሸንፎ መንግስቱን በመቀማት ህዝቡን እንደ ባሪያ መግዛት ጀመረ። በዚህ ጊዜ እነዚህ የዮቅጣን ልጆች ተላልከው ከየስፍራው ተሰባስበው ራማን ወግተው ሠራዊቱን አሸንፈው እርሱን ገደሉና ህዝቡን የባሙን ነገድ ነፃ አወጡት። ተመካከረውና ተስማምተውም የሳባውን ነገድ አክናሁስን አነገሱት። እናም ነፃ ያወጡትን አገር ያዙት፤ መንግስቱንም ተረከቡት። በዚህ ምክንያት አጋዚያን ተባሉ። ይሉናል። ነፃ አውጪ ማለት ነው፤ በዕግዝ።

ፀሃፊቱ በዚህ ይስማማሉ። ትንሽ ግር የሚላቸው "የህንድ ንጉስ..." የሚለው ነው። ይህም ቢሆን የህንድ ንጉስ እንዴት መጣ? እንዴት ገነነ?... አይነት ጥየቄ ከጠተሰናቸው ፀሃፊት ጥቂቶቹ ያነሡና በዚያ ሠዓት የገነኑ መንግስታ ባቢሎን...? በሚል ክፍት አድርገውልን ያልፋሉ። ባጠቃላይ እንዴት የሚለውን በዝርዝር ሊነግሩን ባይችሉም የስልጣን ሹርርሆን ያምኑበታል።

ስለዚህ የህንዱን ክፍተት ለሌላ ዓላማ ማለትም ስለሌሎች አገራት ሁኔታ ሊተረኩበት ታቅዶ ከሠፈረው ፅሁፍ (ከዓለም ታሪክ መፅሃፍ) ቀርሆን ጥያቄውን እንመልስና በዚህ ፋንታ ሌላ ያልተመለሠ ጥያቄ ተከተንበት እናልፋለን። ቀጣይ ፀሃፊት እንዲሞሉት ለማለት ነው። ጥያቄውን እናቆይና መልሡን እናስቀድም።

የዓለም ታሪክ የባቢሎኑን ታሪክ ከተረከ በኋላ ሠዎች ቢበተኑም በዙሪያው የቀሩ እንደነበሩ ያወጋናል። እናም የባቢሎን ከተማ ከቀድሞው የበለጠ እየደመቀች መሄዷን በሚተርክ ጊዜ ዙሪያዋን አሣምረው እንዳጠሯትም ይገልፃል። ቅ.ል.ክ 2229 ላይ ነው የአሶር መንግስት አሹር በተባለው ንጉስ ሲጀመር የሚያሣየን። ለማለት የፈለገው የመጀመሪያውን ዳይናስቲ ነው። ከናምሩድ በኋላ።

ብዙ ጊዜ ይሄ አገር ሲጠቀስ ግር ልንሆኝ አይገባም። የመጀመሪያ ስሙ ሠናአር ነው። ከዚያ ባቢሎን፣ ቀጥሎ አሶር፣ እንደገና ባቢሎን፣ ፋርስ፣ ጨዘተ እያለ ዋና ከተማው እየተለዋወጠ የሚቆይና፤ አንዳንድ ጊዜ አንድ አገር ሆኖ በአንድ መንግስት ሲጠቀስል፣ ሌላ ጊዜ ከሁለት በላይ አገር ሆኖ ባቢሎን፣ አሶር፣ ፋርስ ተብሎእየተከፋፈለ በተለያዩ ነገስታት ሲመራ የኖረ ነው። ምንም ቢባል ቦታው በፋርስ ባህር በስተሠሜን በኤፍራጠስና ጤግሮስ ወንዞች መካከል የሚገኝ ነው። ሞሶፖታሚያ (በወንዞች መካከል)የሚገኙ ተብለውም ይጠራሉ አሶር እና ባቢሎን።. ለማንኛውም ወደ ጉዳያችን ስንመለስ ፊገን በሚያሆኝ አተራረክ ከምዕራፍ 10 ቁ 5 ጀምሮ እንዲህ የሚል ነገር እናገኛለን።

"... በዚህ ከተማ ውስጥ ደምቆ የሚታይ ቤተ መንግስትና አታክልት ነበረበት፤ ሳሥራሩም እንዲህ ያለ ሁኔታ ነበረው። ከምድር ላይ ሣያርፍ አየር ላይ የተንጠለጠለ ይመስል ነበር። ፍሬ የሚያፈሩ ዛፎችና ብዙ አይነት አበቦች



ነበሩበት። (አጥሩን ወይም ቅጥሩን ማለት ነው) ደግሞ አሶራውያን ለዋናው ጣኦታቸው ለቤሉስ (ቤል) ወይም ለበአል የተሠራ እጅግ ያማረ ቤተጣኦት ነበር። ይህ ቤተ ጣኦት ወደ ላይ ቁመቱ 680 ፊት ነበር። በዚሁም ውስጥ ከፍታው 40 ፊት የሚሆን የጣኦቱ የቤሉስ የወርቅ ምስል ነበረበት። ይህንንም የነገርኳችሁን የባቢሎንን ከተማ ቀድሞ የሠራው ናምሩድ ነው። ስለእርሁም ያ ሃይለኛው አዳኝ ብሎ መፅሃፍ ቅደስ ነግሮናል።

ነገር ግን አትክልቱንና ቤተመንግስቱን ያሠራችው ሴሚራሚስ የተባለች ሴት ነች። የኑኒስ የአሶር ንጉስ ሚስት ነበረች። ነገር ግን ንጉሡ ኑኒስ በሞተ ጊዜ ንግስት ሴሚራሚስ ዋና የመንግስቱ ገዥ ሆነች። ክብርን ፈላጊ ሴት ስለነበረች ባቢሎንን እጅግ ያማረች ከተማ ልታደረጋት ፈለገች እንጂ ዝም ብላ መኖር አልበቃትም። በዓለም ያሉትን ነገዶች ሁሉ አሸንፋለሁ ብላ በክፉ ምኞት ተሠቃየች። ልክ የሌለው ጦር ሠበሠበችና ስመጥሩውን እጅግም ሃብታም የተባለውን የህንድን ንጉስ ለመውጋት ተነሣች። እርሡም ዛሬ ሂንዱስታን በምንለው አገር ይኖር ነበር። ይህም አገር በእሶርያ ደቡብ ምስራቅ በኩል ያለው አገር ነው።. እጅግ ባለፀጋና ሃይለኛ የነበረ የህንድ ንጉስ አገሩን ለመውረር ሴሚራሚስ እንደመጣችበት በሠማ ጊዜ መክቶ አገሩን ለማዳን ልክ የሌለው ጦር ሠራዊት ሰበሠበ። ካርበኞችም ሌላ ደግሞ እያሌ ትላልቅ ዝሆኖች ነበሩት። የእነዚህም የታላላቆች ዝሆኖች የያንዳንዳቸው ሃይል የመላውን ወታደር ሃይል ያህላል። ጠላት ወደተሠለፈበት ገስግሶ ጠላትን በኩምቢው እያንጠለጠለ ለማምዘግዘግና በዚያም አንዳች በማያህለው እግሩ ለመዳጥ ደህና አድርጎ ተምሯል።

- ንግስት ሴሚራሚስ ዝሆን አልነበራትምና የህንድ ንጉስ ማያሸንፈኝ አይቀርም በማለት ስለፈራች ይህን የመጣባትን መከራ ካሁን ቀደም ባልተደረገ ነገር ለመከላከል አስባ አስቀድማ 3ሺ በሮች አሣረደች። ቆዳቸው ተገፎ ዝሆን እየመሠሉ እንዲሠሩ አዘዘች። ይህም ከሆነ በኋላ በግመል እየተጫኑ ወደ ጦርነቱ ቀርበው በተደረደሩ ጊዜ በእውነት የተሠሰፉ ዝሆኖች መሠሉ። ያለጥርጥር ሴሚራሚስ ይህን ሁሉ ዝሆን ከየት ለፍራ አገኘችው ብሎ የህንድ ንጉስ ተደነቀ።

ጦርነቱ እንደተጀመረ የህንድ ንጉስ እውነተኞች ዝሆኖቹን ባንድ ወገን ይዞ በቀረበ ጊዜ ንግስት ሴሚራሚስም በቆዳ የተሠሩ ዝሆኖቿን በግመል አስጭና ባንድ ወገን ፊት ለፊት በጀግንነት ተጋፈጠችው። የህንድ የጦር አርበኞች ወደ አሶራውያን ሠልፈኞች ፊት በተቃረቡ ጊዜ አንድ እንኳ የነሡን ዝሆን የሚመስል አላዩም። ከዚህ ወዲያ ፍርሃትን ወዲያ አስወግደው ወደ ንግስት ሴሚራሚስና ወደ አርበኞቿ በመናደድ ገሠገሡባቸው።

የህንድ እውነተኞቹ ዝሆኖች ግን የአሶራውያኑን ወታደሮች በኩምቢያቸው እያንጠለጠሉ ወደ አየር ያጓኗቸው ጀመር። መቶ መቶውን እየጨበጡ በእግራቸው ይደፈጥጧቸው ጀመር። እንዲህ ሁነው ያሶራውያን ጭፍሮች ከስራቸው ተነቀሉና የህንድ ንጉስ ፈፅሞ ድል አደረጋቸው። ንግስት

ሴሚራሚስ ክፉኛ ቆስላ ስለነበረ ወዲያው ከሠረገላዋ ገብታ ከመዋጊያው ስፍራ ተነስታ ሸሸች። ወደ ኋላም ሸመጠጠች። ነገር ግን በመጨረሻ በታላቅ ሃዘን አምልጣ ወደ ግዛቷ ደረሠች።

ከዚህ በኋላ መኖሪያዋን በባቢሎን ቤተመንግስት አደረገች። ዳሩ ግን ከአየር የተንጠለጠለ በሚመስለው እጅግ ያምር በነበረው አታክልትዋ መታጣት ደስታ አላገኘችም። በኋላም ዙፋንዋን ለመውረስና በህዝቡ ላይ ለመንገስ ብሎ ኒንያስ የተባለው ልጅዋ ገደላት ይባላል።

የታላቂቱ ንግስት የሴሚራሚስ ፍፃሜ እንዲህ የሚያሣዝን ሆኖ ቀረ። የገዛ ህዝቧን ደስ ከማሠኘት ችላ ብላ የሌላውን አገር ድል አድርጌ ህዝቡን እገዛለሁ እያለች ዘመንዋን ሙሉ ስትመኝ መኖርዋ እንዴት ያለ ስንፍና ነው? ነገር ግን ሌላው ሊያደርግልህ እንደምትወደው አንተም እንዲሁ አድርግለት የተባለውን አልተማረችም ኑራለች።" በማለት ምዕ 11ን ይዘጋል።
(ዮሐንስ ወልደ ማርያም1936 ዓ.ም)

በ...ጣም በፈገግታ እንደደመቃችሁ ተስፋ አደርጋለሁ። ምርጥ አተራረክ ነው በእውነት። "ሙቶ መቶውን እየጨረሱ..."እሱ ስለዚህ እዚህም መጥተው ጨፍደዋል ማለት ነው። እናም ስልጣኑን እንዲሁ በፈገግታ እንደደመቅን ደስ እያለን እናስረክባለን። ሠላማዊ የስልጣን ሽግግር ይሏል ይሄ ነው። ይች የማትረባ እንዴት ያለች ሠነፍ ነች? እሱ....

ወደ ጉዳያችን እንምጣ። ከላይ የተጠቀሠው ታሪክ በባቢሎናውያን ዜና መዋዕሎችም የተረጋገጠ ነው። እነ ሴሚራሚስ ነበሩ። ተከታዮች አነሠርዳናፓልም ከባቢሎን ጋር በኋላኛው ዘመን በተነሡ ነብያት ሲወገሡ ነበር። ጥቂት የዘመን ክፍና ዝቆች ይኖራሉ እንጂ የህንድ ነገስታት ቅ.ል.ክ 2100-2000 ድረስ በነበረው ዘመን ገናና ነበሩ።

በእነዚያ ዘመናት የህንድ ነገስታት ብርሃማ ብቻ ሣይሆን /ራማ/ በሚል /የማዕረግ ስም/ ተከታትለው የነገሡበት ዘመን ሲሆን ብዙ አገሮችን እየወጉ ማስገበር መቻላቸውም የታወቀ ነው። በዚህ መሰሉ የህንድ ጥቃት ከመካከለኛው ምስራቅ እየሸሹ ወደ የመን ተጠግተው የሚኖሩ ህዝቦች መኖራቸው የሚታመን ነው። ምክንያቱም ያች የማትረባ ሴሚራሚስ እርፎ የተቀመጠውን የህንድ ንጉስ ነካክታ ከተሸነፈች በኋላ ህንድም የባቢሎንን ትምህርት ፍርስርሡን ማውጣቷ ይታወቃልና ሃያል የነበረችው ባቢሎን ከተሸነፈች ሌላው ሁሉ ለህንድ ቀላል ነበር ማለት ነው። ብዙዎችን ያስገበረው በርቀት እንደነበር የሚሩም አሉ። ይህ ጦርነት ቅ.ል.ክ 2200-2100 (እንደ ሌሎች 2000 ቅ.ል.ክ) ሊደርስ አቅራቢያ የተካሄደ ነው። ሃሙራቢ ከመነሣቱ በፊት።

ስለዚህ ተወራሪዎቹ ነገደ ዮቅጣኖች በወረራው ማግስት ባይመጡም በሽሽት ወደ ያዙብ አረብ ተጠግተው ጥቂት ዘመን ኖረው ወደ ኢትዮጵያ ባህር ተሻግረው ኑሮ የመሠረቱ ነበሩ። የባቢሎንን ስልጣኔም ቋንቋም የያዙ ናቸው። ይህ እውነታ ግልፅ መሆኑ እንዳለ ሆኖ፤ የነገስታቱን ዝርዝር



ከማስከተላችን በፊት ለምናነሣው ጥያቄ መንደርደሪያ ይሆነን ዘንድ እንዴ እንድገመው።

የብላቱን ጌታ ህሩይ "ዋዜማ" የሚለው መፃህፍ "... ከነገደ ካም ወገን በኢትዮጵያ ነግሶ የነበረው ጲኦሪ 1ኛ እነዚህን ሶስቱን ነገደ ዮቅጣንን 5 አመት አስገብሯቸዋል። በኋላ ግን ራማ የሚባል የህንድ ንጉስ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ጲኦሪን ወግቶ መንግስቱን በወሰደበት ጊዜ እነዚህ ሶስቱ ነገደ ዮቅጣን ከውጋዴን፤ ከአዳል፤ ከትግሬ ተላልከውና ተስማምተው በትግሬ ላይ ከነበረው ከሳባ ዘር አክናሁስን "ሳባ 2ኛ" ብለው አንግሠው ከህንድ ንጉስ ከራማ ጋር ተዋግተው ደል አድርገው ገደሉት። እነርሡም አገራቱን ኢትዮጵያን ከመግዛት ህዝቡን ከባርነት ነፃ ስላወጡ አጋዚያን ተባሉ። በግዕዝ ቋንቋ አጋዘ ማለት ነፃ አወጣ ማለት ነው። አጋዝያን ማለት ግን ነፃ የሚያወጡ ማለት ነው። አገራቱም ብሔረ አግዓዚ ተባለች። ቋንቋቸውም ግዕዝ ተባለ" ይሉና ምንጭ ሲጠቅሡ "የሞሪዎን የመጀመሪያውን መፅሃፉን 237 ገፅ ተመልከቱ" በማለት ይመሩናል። ሲቀጥሉ "የነዚሁም አጋዓዚያን የተባሉ የነገደ ዮቅጣን ነገስታት ስማቸውና ቁጥራቸው ከዚህ ቀጥሎ የተፃፈው ነው" በሚል ሠንጠረዡን ያስከትላሉ። ሻንፃሪዮ ኩልቦ፤ ኮንቲሮሲኒ፤ ሌልቤር ካሚረር ወዘተ ወደፊት ለምናገኛቸው ታሪኮች ሁሉ ዋና መሠረት የሚሆኑን ቀደምት ፀሃፍት ናቸው። የኢትዮጵያን ታሪክ በሠፊው የፃፉ ናቸው። የቀደመውን የኢትዮጵያን ታሪክ የሚፅፍ ፀሃፊ ሁሉ ከእነዚህ ታላላቅ ፀሃፍት ውጭ ሊገዝ አይችልም። የፃፉት ከአገር ተወላጅ የብራና ፅሁፍና ከሌሎች አገራት ታሪክነገስትና ዜና መዋዕል፤ ከሃውልቱ.. ወዘተ በመነሣት ነው።"ስለዚህ ልናመሠግናቸው ይገባል።..... ወደ ጉዳያችን ስንመጣ ጥያቄው ቋንቋን መሠረት ያደረገ ሆኖ እናገኘዋለን።

አጋዓዚያን ተባሉ። የግዕዙ ትርጓሜ ነፃ አውጪ የሚል ነው በአማርኛ። ነገዳቸው ዮቅጣን ነው። ዮቅጣን በአማርኛ ነው። በግዕዝ ዮቃጤን ይባላል። በእንግሊዝኛ የካታን ይባላል። ይህ የነገድ ስም ነው። ወይም ከሴም ዘር የወረደ አንድ ግንድ የሆነው ልም። ስለዚህ ችግር የለውም። አጋዓዚያን ያላቸው ማነው? ነዋሪው ህዝብ? ወይስ ራሣቸው "አጋዓዝያን በሉን" ብለው ነገሯቸው? ማነው በዚያን ጊዜ (ክ.ል.ክ 1985) ግዕዝ ተናጋሪ የነበረው? ከዚያ የመጡት ከሆኑ፤ እዚህ የነበሩትስ ቋንቋቸው ምን ነበር? ነው ጥያቄው።

የጥንቱ የኢትዮጵያ ታሪክ የሠፈረባቸው የታሪክ መዛግብት ሁሉ በአማርኛ የተተረጎሙትም፤ በግዕዝ የተፃፉትም ግዕዝ የመጣው ከሳባ ቋንቋ እንደሆነ ነው የሚነግሩን። ለምሣሌ የመጀመሪያው የግዕዝ አባት ሣባ ይሆንና ሣባ ግዕዝን ይወልዳል፤ ግዕዝ እሮጌና አዲስ ተብሎ የሠለጠነና ያልሠለጠነ ተብሎ ይከፋፈልና እንደገና አማርኛን ሲወልድ ነው የምናየው። አማርኛም በየጊዜው እየተሻሻለና እየደገ ሄዶ እንጂ አሮጌ አዲስ የሚባል እንደነበረው ወደፊት እናገኘዋለን። ከዓጋዝያን/ከነገደ ዮቅጣን/ መምጣት በፊት የነበረው የነገደ ካም ኩሽ ዘር የሚናገረው ቋንቋ ምን ነበር? የሚፅፍበት ፊደልስ? ስንል

ፊደልን ከስልጡን አገሮች ይዘው የመጡት ሣባውያን እንሆኑ እንረዳለን። እነዚህም ብቻ ሣይሆን በኋላኛው ዘመን በየጊዜው ወደ ኢትዮጵያ የገቡና ነገደ ሣባ የሆኑ ከደቡብ አረብ የሚነሡ ስልጡን የሴም ነገዶች ተከታትለዋል። በዚህ ዘመን የመጡት የቅጣኖች ፊደል ላይኖራቸው ይችላል። ታሪኩ የተፃፈው በኋላኛው ዘመን ስለሆነ። ቋንቋቸው ግን ልዩነት ነበረው ከነዋሪው ህዝብ ጋር። ይህን ስያሜ ማንም ይስጣቸው ማን እነሡ በነበሩበት ዘመን የተሠጠ ስያሜ እንጂ የኋለኛው ዘመን ፀሃፊ "ቢቃ አጋዝያን እንበላቸው" ብሎ ታሪካቸውን አይፅፍም። ከዚህ አንፃር ከዚያው ከነበሩበት አገር ይዘውት የመጡት ነው ማለት ይሆናል። ቀደምት ፀሃፍትም ይሄንን ነው የሚሉን።

በኋለኛው ዘመን በመጡ የሴም ነገዶች ተከትሎ የተገኘ በርካታ የታሪክ ሀገድ እንደበረ አይተናል። እነሡ ከመምጣታቸው በፊት የነበረው የኢትዮጵያውያን ታሪክ ደግሞ በጥንቱ በግብፃውያን ፊደል የተከተበ ነው ተብሏል። እነዚህን የመሠሉ ሌሎች ነገዶች ከሠለጠኑት አገሮች ከባቢሎን፣ ከአሶር፣ ከፊንቂ (ጢሮስ) ከእብራውያን... ወዘተ ሲገቡ አማልክቶቻቸውም፣ ባህላቸውም፣ ቋንቋቸውም፣ ፊደላቸውም መሠረቱ ከተዘረዘሩት አገሮች ይሆንና ወደ ደቡብ አረብ ወደ የመን፣ ከዚያም ባህር ተሻግረው ወደ አሁኗ ኢትዮጵያ እንደገቡ ግልፅ የመሆኑን ያህል፤ ነገዶቸው ሴማዊ መሆኑ የመታወቁን ያህል፤ ስልጣኔ ቋንቋና ፊደሉም አብሯቸው እንደገባ /ይዘውት እንደገቡ/ ታምኖበታል።

የኢትዮጵያ መጠሪያ ስምና የግዛት ስፋት በአፍ ሲጠራም ሆነ ሲፃፍ ከቀይ ባህር ወዲያና ወዲህ፣ ከግብፅ ደቡብ እስከ አሁኑ ሠሜናዊ ሡዳን ያለውንና የዛሬውን ምስራቃዊና ምዕራባዊ ድንበር የሚያካትት ሆኖ፤ በሁሉም አይነት ፅሁፍ "ኢትዮጵያ" ተብሏል። በእብራይስጥ ኩሽ ሲባል፤ ኦሪት ሲተረጎም ወደፊት እንደምናገኘው ኩሽ የሚለውን በፅርዕ /በግሪክ/ አይቶፒያ ተብሎ ተተርጉሞ፣ ከግሪክ ወደ ግዕዝ ሲተረጎም ኢትዮጵያ፣ ከግዕዝ ወደ አማርኛም ኢትዮጵያ ተብሏል።

"በኋለኛው ዘመን የመጡ" የሚባል ቃል፣ ታሪክ፣ ንግግር አቃም ይሁን ቋንቋ ፊደልም ይሁን ምን ከኢትዮጵያ ጋር ሲቀራኝ ሁሌም ጥያቄ ያስነሣል፣ ሁሌም ውዝግብ ይኖራል።። ምክንያቱም ከዚህ ሄዶ ተመልሶ ስለመጣ ነው። የተባለውን ጥያቄ እናንሳና ከሡንጠረዡ በኋላ ሌላውን እንደርስበታለን።

ጥንታዊው የሳባ ቋንቋና ፊደል ለግዕዝ አባት ነው። ግዕዙ ለአማርኛ አባት ነው። የግዕዝ አያት ማነው? አያት ነው የተባለው። ወይም ሳባ /ሱባ/ን ማን ወለደው? ይሄን በተጠየቅ እንያዘውና እንቀጥል። ሌላው የትም አይሄድም። ኩሽቲክ፣ ሴሜቲክ የሚለውንም እናየዋለን። ሣባውያን ከፊንቂ፣ ከእብራውያን አመጡት የሚለውም ቢሆን የሚያራምድ አይደለም።



<u>የዓጋዝያን ዘመን መንግስት የነገስታት ዝርዝር</u>

<u>ከአክናሁስ ሳባ 2ኛ እስከ ማክዳ ንግስት (ከ1985-1013 ቅ.ል.ክ.)</u>

| ተ.ቁ | የነገስታቱ ስም ዝርዝር | በስልጣን ላይ የቆዩበት ጊዜ በዓመት | የገዙበት ዘመን ከክ.ልደት በፊት |
|---|---|---|---|
| 1 | አክናሁስ ሳባ 2ኛ | 45 | ከ1985-1930 |
| 2 | ነክሁቲ ካሊስ | 40 | 1930-1890 |
| 3 | ካስዮጲ | 19 | 1890-1871 |
| 4 | ሳባ 2ኛ (ሳባ ሻባ) | 15 | 1871-1856 |
| 5 | ኢትኦጲስ 1ኛ | 56 | 1856-1800 |
| 6 | ላክንዱን ኒዎር ኦሪ | 30 | 1800-1770 |
| 7 | ቱት ኢምሐብ | 20 | 1770-1750 |
| 8 | ሐርሒተር ሸኒ | 20 | 1750-1730 |
| 9 | ኢትኦጲስ 2ኛ | 30 | 1730-1700 |
| 10 | በኑካ | 17 | 1700-1683 |
| 11 | ቦኑ 1ኛ | 8 | 1683-1675 |
| 12 | ሙማዚስ | 4 | 1675-1671 |
| 13 | አሩአሣ | 7ወር | 1671-1671 |
| 14 | አሚን አሣሮ | 30 | 12711641 |
| 15 | ኦሪ (2ኛ) | 30 | 1641-1611 |
| 16 | ጲኦሪ 2ኛ | 15 | 1611-1596 |
| 17 | አሚን አምሐት 1ኛ | 40 | 1596-1556 |
| 18 | ፃውዕ | 15 | 1556-1541 |
| 19 | አክቲሳኒስ | 10 | 1541-1531 |
| 20 | ማንዲስ | 17 | 1531-1514 |
| 21 | ፕሮቶውስ | 33 | 1514-1481 |
| 22 | አሞይ | 21 | 1481-1460 |
| 23 | አንኪ | 5 | 1460-1455 |
| 24 | ቦኑ 2ኛ | 2 | 1455-1453 |
| 25 | ሳቢ 3ኛ | 15 | 1453-1438 |
| 26 | ጃጎንስ | 20 | 1438-1418 |
| 27 | ሰኑካ 3ኛ | 10 | 1418-1408 |
| 28 | አንጋቦ 1ኛ | 50 | 1408-1358 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 29 | ማሕመር | 2ቀን | 1358-1358 |
| 30 | ክሌና (ንግስት ሳዶኒ) | 11 | 1358-1347 |
| 31 | ዘግዱር 1ኛ | 40 | 1347-1307 |
| 32 | ሐርሐቶር 2ኛ | 30 | 1307-1277 |
| 33 | ሐርቶር 3ኛ | 1 | 1277-1276 |
| 34 | ኔክቲ 4ኛ | 20 | 1276-1256 |
| 35 | ቲቶን ስትዩ | 10 | 1256-1246 |
| 36 | ሐርመንተ 1ኛ | 1ወር | 1246-1246 |
| 37 | አሚን አምሐት 2ኛ | 5 | 1246-1241 |
| 38 | ኮንሳብ 1ኛ | 5 | 1241-1236 |
| 39 | ኮንሣብ 2ኛ | 5 | 1236-1231 |
| 40 | ስኑካ 4ኛ | 5 | 1231-1226 |
| 41 | አንጋቦ /ህዝባይ/ | 40 | 1226-1186 |
| 42 | አሜን ሀስቶት | 30 | 1186-1156 |
| 43 | ሖርሐር | 16 | 1156-1140 |
| 44 | ፒያንኪያ 1ኛ | 9 | 1140-1131 |
| 45 | ጥኖት ሴም 1ኛ | 17 | 1131-1114 |
| 46 | ጥኖት ሴም 2ኛ | 41 | 1114-1073 |
| 47 | ማስሐርታ | 16 | 1073-1057 |
| 48 | ራሜን ኮበርም | 14 | 1057-1043 |
| 49 | ጥኖት ሴም 3ኛ | 7 | 1043-1036 |
| 50 | ሣቢ 4ኛ | 10 | 1036-1026 |
| 51 | ተዋስያ ዴውስ /አጋቦስ/ | 13 | 1026-1013 |
| 52 | ማክዳ ንግስት | 31 | 1013-982 |

(ብላቴን ጌታ ሁሩይ ወልደ ስላሴ1921ዓ.ም)

በአገራችን ቀደምት አፃፃፍ መሠረት በአጋዚያን ዘመነ መንግስት ስር የነገሡት የነገስታት ስም እና የገዙበት ዘመን ከአክናሁስ ሳባ 2ኛ እስከ ማክዳ ንግስት ያሉት ያየናቸው ናቸው፡፡ ወደ ሌላ ጉዳይ ከመግባታችን በፊት አንድ ነገር ልጠቁማችሁ፡፡ ሁሉም ፀሃፍት እነዚህን ነገስታት ሲዘረዝሩ በተራ ቁጥር 15 ላይ የሠፈረውን "ኦሬ" ብለው ነው የሚያልፉት፡፡ የብላቴን ጌታ ሁሩይ ወልደ ስላሴ ጥዜማ ላይ ግን " ኦሬ 2ኛ" ተብሎ ነው የሠፈረው፡፡

እንደሚታወቀው "2ኛ" ሲባል ያው በዚህ ስም ቀድሞ የነገሠ ካለ ለመለየት ነው፡፡ "ኦሬ" ብለው 2ኛ ያሉበት ምክንያት ግልፅ ነው፡፡ በነገደ ካም ነገስታት ዝርዝር "ኦሬ" የሚል የለም፡፡ በራሣቸው ዝርዝር ላይ እንኳ 22 ነገስታትን ከሰብታ ጀምሮ እስከ ጲአሬ ሲዘረዝሩ ኦሬ የሚል አላስገቡም፡፡ ይሄን ግን 2ኛ ብለውታል፡፡ በትንና ያስገባሁትም ይህንኑ አግራሞቴን ላካፍላችሁ



ነው፡፡ "ኦሬ" ማለት ከአዳም የዘር ግንዶች አንዱ ነው፡፡ አዳም ሴትን ወለደ፣ ሴት ሄኖስን እያለ 9 የዘር ግንድ ዘርዝሮ 10ኛ ላይ ኖኅን እንደምናገኘው ሁሉ፣ የሁለተኛው ግንድ የሴት ቅርንጫፍ ውስጥ የሚገኝ ንዑስ የነገድ አባት ነው፡፡ ኦሬ፡፡

ስለዚህ በመግቢያችን ላይ እንዳየነው የነገደ ኦሬ አባት የሆነው ራሡ ኦሬ ከጥፋት ውሃ በፊት በኢትዮጵያ ነግሶ ነበር ስለተባለ ነው፡፡ እሡን መረጃ ሳገኘው አልቻልኩም፡፡ እማቾውም ማንም አያምንም ብለው እንዳልፃፉት ነግረውናል፡፡ እናም ኦሬ ከጥፋት ውሃ በፊት አዳም በተፈጠረ በ970 አመት በኢትዮጵያ ነግሶ ነበር ተብሎ ስለተፃፈ ምንም እንኳ ባያምኑበትና ባያትቱት ከዚህኛው ኦሬ በፊት ሌላ ኦሬ መንገሡን ማይገልፁ ማለፍ ከብዷቸው ይሄኛውን ኦሬ 2ኛ ብለውታል ማለት ነው፡፡

ይሄን ሁሉ ትተን ነው ከኖኅ ከትናንቱ ታሪክ የጀመርነው፡፡ ስንቀጥል በኢትዮጵያ ታሪክ የግዛት ዘመን ክፍልፋይ መሠረት ተፀስኖ የተቀመጠ ነገር እናገኛለን፡፡

1. የነገደ (ኖኅ ካም-ኩሽ) ዘመነ መንግስት
2. የአጋዚያን ዘመነ መንግስት ከክ.ል.በፊት
3. የአጋዚያን ዘመነ መንግስት ከክ.ል. በኋላ
4. የነገደ ዛጉዬ ዘመነ መንግስት
5. የሸዋ ነገስታት
6. የጎንደር ዘመነ መንግስት
7. የሸዋ ዘመነ መንግስት ተብሎ ይከፋፈላል፡፡

የመጀመሪያውን የነገደ ካም ዘመነ መንግስት የነገስታት ስም ዝርዝር ቀደም ሲል ያየነው ነው፡፡ አሁን ደግሞ ተተኪዎችን የአጋዚያን /ከዮቅጣን ዘር/ የወረዱትን እይተናል፣ ሌሎችንም ወደ ፊት እናገኛቸዋለን፡፡

በብዙዎች እይታ ነገደ አጋዚያን ከገዙ በኋላ ስልጣኑ /መንግስቱ/ ከእነሁ ዘር አልወጣም፡፡ በዚህ መፅሃፍ ደግሞ የምንቆጥረው የነገድ ተዋረድ አይደለም፡፡ አሁን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ታሪኩን ከስሩ ለማምጣት የግድ ሲሆን (በእርግጥም አስፈላጊ ሆኖ የሚገኝበት አጋጣሚ ይበረክታል) ያኔ እንቆጥራለን፡፡ በተረፈ የኢትዮጵያን ታሪክ ነው የምናየውም፣ የምንቆጥረውም፡፡ የኢትዮጵያን ብቻም አይደለም የአፍሪካን፡፡ የአፍሪካን ብቻም አይደለም የጥቁሮችን፣ የጥቁሮችን ብቻም አይደለም ዛሬ ጥቁር ህዝቦች የሠፈሩባትን ምድር ወይም መሬት ነው፡፡ ለማለት የተፈለገው ጥቁር ህዝቦች መሠልጠን የጀመሩት ስልጣኔን ከነሙች ይዘው በየጊዜው በገዙ ነገዶች መሆኑ ተደምድሟል፡፡ በዚህ መፅሃፍ ግን ያ ሃሠት ነው፡፡ ከዚህ የሄደው ነው ተመልሶ የመጣው የሚለውን ለማሣየት ነው የሚጣረው፡፡ ይሄንን እውነታ በደንብ የምንረዳው 1ኛ እስካሁን ባየናቸው ታሪኮች መነሻነት፣ 2ኛ በዚህ ምዕራፍ ስር በምናየው፣ 3ኛ በቀጣዩ ምዕራፍ በምናነበው፣ 4ኛ በቀጣዩ ቀጣይ

ምዕራፎች በምንመለከተው ይሆንና ከዚያ በኋላ መደበኛውን የኢትዮጵያ ታሪክ በመደዳ መቀበል ነው። ያኔ ምንም የምንገረምበት ነገር አይኖርም። እንትን መጣ፣ እንትን ሄደ፣ እዚያ ነገሠ፣ እዚህ ነገሠ፣ እየተባለ ቢተረክ እንገዳ እንዳንሆን እንደማለት።

"አግዓዚያን ተባሉ" ቋንቋቸውም ግዕዝ ተባለ። ማን አለው? የሚለውን ጥቂት ነክክተነው እናልፋለን።

"ግዕዝ" "ግዕዝ" የሚባለውን ስም አገኘ ማለት ነው? ያ ከሆነ ቋንቋው ነበረ ማለት ነው። የሳባውያኑ ቋንቋ "ሳባ" ይባል ስለነበር ከሳባ ወደ ግዕዝ ተሸጋገረ ከተባለ ደግሞ፤ ግዕዝና ኢትዮጵያ ትውውቃቸው ቅ.ል.ክ 1985 ጀምሮ ሊሆን ነው። ይህም ሲሆን የነገደ ካም ነገስታት ከግዕዝ የተለየ ቋንቋ ነበር የሚናገሩት ማለት ይሆናል። እሡ ከሆነ ደግሞ በሁለቱም ዝርዝር ላይ እንዳየነው ጺአሪ የሚሉ ስሞች አሉ።

የነገደ ካሙም፣ የነገደ ሴሙም የነገስታት ዝርዝር የሠፈረው በአማርኛ ባየነው መልኩ ነው። "God" አምላክ ነው በእንግሊዝኛ። "እግዚአብሔር" አምላክ ነው በግዕዙም በአማርኛውም። የቋንቋው ጭብጥ አንድ ነው። ሲነገርና ሲፃፍ ይለያያል። ጺአሪ በአማርኛ በተፃፈ የነገደካም ነገስታት ዝርዝር ከሠፈረና ጺአሪ በነገደ አጋዚያኑ ዝርዝር በዚያው በአማርኛ ከሠፈረ ምን መሆን ይችላል? ነው ጉዳዩ። ይሄም ብቻ ሣይሆን ሌሎችም ብዙ አሉ።

በነጮች ፀሃፍት እይታ እነሡንም ተከትለው በፃፉ ምሁራን አመለካከት የአሁኗ ኢትዮጵያ መስራቾች እነሡማውያን ስልጣኔን ብቻ ሣይሆን ፊደልንም ከሠለጠኑት አገሮች ከባቢሎን፣ አሶር፣ ከለዳውያን፣ አካድያን... ወዘተ እየፈለሡ ወደ ደቡብ አረብ እየተጠጉ በየጊዜው ባህር ተሻግረው በገቡ ጊዜ ያመጡት ነው። የአሁኗን ኢትዮጵያ በተመለከተ ጉዳዩን በዚህ ሲደመድሙ፤ የቀድሞዋ ኢትዮጵያ ኑብያውያን ደግሞ ስልጣኔን ከግብፅ እንደወረሡ አድርገው በመደምደም ያገጣጥሙታል። ስለዚህ ከዚያ ወደዚህ እንጂ ከዚህ ወደዚያ የሚሄድ ነገር እንደሌለ ያሣምኑናል። "እጣንና ከርቤ ብቻ ከዚህ ይሄድ ነበር" በማለት። እነሡማውያን ለምሣሌ ፊደልን በኋላኛው ዘመን ከግሪክ ሲወርሡ እናያለን። የግሪኩ ፊደል (ስሌጡኑ) ኤ.ቢ.ሲ.ዲ የኛ የአሃዝ ቁጥር መሆኑን ከደው የኛ አሃዝ ቁጥር ከእነሡ እንግሊዝኛ ሲወሠድ ይነግሩናል ያሣዩናልም። ይሄ እንግዲህ ቢ.. ኋላ ላይ ነው። ቁጥር የመጣው በኋላ ግዕዝ የነበረው በፊት ሊሉን አይችሉም።

በጥቅሉ የኑብያ ኢትዮጵያ ታሪክ በግብፅ ተውጦ ሲገኝ የአክሡሙ ደግሞ በግሪክ ተውጦ ይገኛል። ምክንያቱም ሁለቱ አገሮች ግራና ቀኝ ያለውን ታሪክ በየራሣቸው ፊደል እንደልባቸው ፅፈውት ስለሚገኝ ነው። ይህ የሆነው ከኢትዮጵያ የሄደውን የመጀመሪያ ፊደልና ቋንቋ የበለጠ አሻሽለው አሠልጥነው በመገኘታቸው ነው። የራሣቸውን ታሪክ አዳብረው ከፃፉ በኋላ ነው የኛን ታሪክ መፃፍ የጀመሩት። ስለዚህ እኛ የነገስታቱን ዝርዝር ስምና



የገዙበትን ዘመን ብቻ ይዘን ልንቀር ግድ ሆኗል። የግብፅን ቀደምት ታሪክ ማንም ሊክደው አይችልም። በደንብ የተፃፈ ታሪክ አላት። በዚህም ላይ አህጉሯ አፍሪካ ቢሆንም ነጮች ናቸው። እንደገናም መፅሃፍ ቅዱሱን ሊክዱት አይችሉም። ጉዳዩ የቀለም ስለሆነ ነው።

ለዚህም ነው የኛ ብቸኛ አማራጭ መፅሃፍ ቅዱሱ ብቻ ሆኖ የምናገኘው። ምክንያቱም ሌላው ነገር ሁሉ በኋለኛው ዘመን መንጋደድ ስለነበረበት ነው።

ግዕዝ አባቱ ሳባ ከሆነ ሳባ የመጣው በኋለኛው ዘመን ነው። ግዕዝ የመጣው ከእብራይስጥ/ከሂብሩ/ ከሆነ በኋለኛው ዘመን ነው። ከአብራሃም በኋላ። እምላክ ህዝቤ እስራኤል እያለ የሚነግረን ከአብርሃም በኋላ ነው። አብርሃም የኖረበት ዘመን ግልፅ ነው፤ ቅ.ል.ክ 1800። ፊደል የመጣው ከሲናው በርሐ ታሪክ ጀምሮ ከሆነ የሙሴ እድሜና የኖረበት ዘመን ይታወቃል። ቅ.ል.ክ 1300። ግዕዝ የመጣው ከባቢሎን ከአሶር፣ ከፊንቄ (ጢሮስ ወይም ሶሪያ) ከሆነ የእነዚህ አገሮች ምስረታ ግልፅ ነው። ቅ.ል.ክ 2500-2000። ግዕዝ ከግሪክ ከመጣ ቅ.ል.ክ 1500 እንዲያውም ከዚያ በታች!

ቋንቋን መናገርና መፃፍ በእርግጥ ይለያያሉ። ነገር ግን በየጊዜው የሚሻሻልና የሚታደስ እንጂ ቋንቋ ከስተት አይደለም። ስጦታ ነው፤ ይሉታል ራሣቸው። ባለፉት ምዕራፎች ያየናቸውና ስለቋንቋ ድብልቅ የሚያትቱ ታሪኮች አሁን ለምንለው ነገር ጥሩ ይሆኑልናል። (በነገራችን ላይ ይህን መሆሉን ሐተታ ማስገባት ግድ የሚለው የዚያ ሁሉ ነገስታት ታሪክ ተፅፎ ስለማይገኝና ከስማቸው በቀር ያስታቀፉን ሌላ ነገር ስለሌለ ነው። ስለዚህ ለምን? በሚለው ጥያቄ ውስጥ ፍሬ ነገር ካገኘን በሚል ነው)።

እናም ባለፉት ምዕራፎች ስናይ ገና ቋንቋ ከመደባለቁ በፊት ታላቁ መፅሃፍ "የሴም ነገዶች በየህዝባቸው፣በየነገዳቸው፣ በየቋንቋቸው እነዚህ ናቸው" "የካም ነገዶች በየህዝባቸው.." ብሎ ከነገረን በኋላ ነው "ምድርም ሁሉ በአንድ ቋንቋ ነበረች" በማለት እንደገና ቋንቋቸው እንደተደባለቀ የሚነግረን። ለዚህም ነው እናት ቋንቋቸው አንድ ነበር ለማለት የተደፈረው። ሲበተኑ የሠፈሩባቸው ቦታዎች ሁሉ ከዚህ የሄዱ ጥቁሮች በመሠረቱት አገር ነበር። እነሡም ናቸው በባቢሎንና በዙሪያው የሚሠፍሩት። ለዚህ ነው ሄሮዱተስ "የቀድሞ ግሪካውያን ጥቁሮች ነበሩ" ያለው። ለዚህ ነው የአለም ታሪክ "እርስ በርሣቸው ለመነጋገር እየፈተኑ /እየሞከሩ/ ወደየአገሩ ጠጋ ጠጋ አሉ" የሚለን። ሲዶንን፣ ኬጢያውያንን፣ ኢያቡሣውያንን.. እየተባለ የሚዘረዘረው የነገድ አባት ነው። ግሪክ ሲዶን ነበረች። ሲዶን ማለት ዘረግንዱ ጥቁር ነው። ሜዶን፣ መቄዶንያ እየተባለ ነው እነቢሮስ ተከፍለው እየወጡ በዘመን ብዛት የተለያዩ አገሮች እየሆኑ ያኔ አንድ ግዛት የነበረው ዛሬ አንድ አገር የሆነው። እንደ ሁዳንና እንደ ኢትዮጵያ። አጠቃላይ ስልጣኔው ምንጩ ዛሬ ነጮች የሠፈሩበት አገር ተደርጎ እንዲታይ በሚል እንትኖች እንትን ይዘው በላይ ገቡ፣ እንትኖች እንትን ይዘው በታች ገቡ በማለት አፍሪካን ባዶ ያደርጓታል።


እንደገና ነገስታቶቻችሁ እነዚህ ናቸው ብለው ስም ይጠረውሩልናል። ግዕዝ በኋላ መጣም ይሉናል። ግዕዝ ግን በኋላ የመጣ ቋንቋ አይደለም፣ ሊሆንም አይችልም።

የኖኅ አንዱ ልጅ ከነገዱ የኤርትራን ባህር ተሻግሮ ሲሄድ ሌላው ልጁ በኤደን ባህረሰላጤ ሲወጣ፣ የቀረው ልጁ የዓባይን ተፋሠስ ይዟል። የካም የልጅ ልጅ የሆነው ናምሩድ ከዓባይ ተፋሠስ አልፎ ሄደ። ከነዓንም በሴም ድንኳን ሊያድር። ኖኅ እዚሁ ቀረ። ሞተም። ሁሉም በየነገዱ ፊደሉን አበጀ። የሁሉም ቋንቋ አንድ ነበር ግዕዝ። ስሩ ይሄ ነው። የግዕዝ አባት ሳባ ነው ልክ ናቸው። ያማርኛ አባት ግዕዝ ነው። ልክ ናቸው። የግዕዝ አያት ግን ግዕዝ ነው። ልክ ነን። የዛሬው እንግሊዝኛ የኛ የአሃዝ ቁጥር ነው። ሃይሮግላፊ ቢባል፣ ፒክቶግራም ቢባል፣ ላቲን ቢባል፣ ምንም ቢባል ስሩ ያው ያዳም ቋንቋ ግዕዝ ። ስለዚህ ሲመጡም ያንኑ እናት ቋንቋው/ስሩ/ አንድ የነበረውን በኋላ የተሰዋወጠውን የተደበላለቀውን፣ የተገለባበጠውን ምንም ምንም የሆነውን ብቻ ግን ከዚች ምድር የወጣውን ዋናውን ነው። ነገር ግን ስልጣኔም ከዚያ መምጣቱን ለማረጋገጥ ያመች ዘንድ ፊደልንም ከዚያ ሲመጣ ያሣዩናል። በቋንቋችን የተፃፈ ታሪክ እንደሌለ ነግረው ያዝኑልናል።

እንግዲህ በዙሪያችን ያሉት ሂብሩ፣ አረብኛ፣ ግዕዝ ናቸው። ከታሪካችን ጋር የሚገናኙት ስስቱ ቋንቋዎች የሚለዩበትን ነገር ማጤን እውነታውን ለማረጋገጥ ይረዳል። ስሩ አንድ ነው። መስከታዊ የተባሉ ቋንቋና ፊደሎች እነዚህ ናቸው። በዚህ አንጋጭም። ከእነግሪክ ጋር ግን እንጋጫለን። እስቲ እንዳው አሁን ማን ይሙት የትኛው ከየትኛው ተኮረጀ ቢባል ይታመናል? ቀደምቱስ የትኛው ነው? እንግዲህ ይሄ ቀጥለን የምናየው በኋለኛው ዘመን፣ አክሡሞች ሊሠለጥኑ አቅራቢያ መጣ የተባለው ነው። ምናልባትም ወደፊት ዘመኑ ላይ ስንደርስ ከታሪኩ ጋር በተያያዘ "ከግሪክ ፊደል ተኮርጆ የተሠራው የአሃዝ ቁጥራችን" በሚል ከሌሎች ፊደላት ጋር ደግመን ልናየው እንችላለን። አተራረካችንም የእውነት እንደመጣ አድርጎ ሊያሣየን ቢችል ግር መሠኘት የለብንም። እውነታውን ከወዲሁ እንይና በኋላ ሳይም "መጣ" እያልን እናውራው። ከተክለፃድቅ መኩሪያ መፅሃፍ ያገኘሁትን ነው። የእጅ ፅሁፉም የራሣቸው ነው። እሣቸው ለማሣየት የፈለጉት ከግሪክ መምጣቱን ለአንባብያን ለማመልከት ነው። የዚህ መፅሃፍ አበናቃሪ ደግሞ ተቃራኒ ነው። ከሠንጠረዡ በላይ የሠፈረችው ቁንፅል ሃተታም ማን ምን ተረድቶ ምን እያስረዳን እንዳለ ታስረዳናለች!

አያችሁ? ይሄ እንግዲህ ገና ገና በኋላ ላይ ተወረሠ የተባለው ነው። እንጂ እነዚህኞቹ ነገደ አጋዝያን ያመጡት የወረሡት አይደለም። በየጊዜው የገቡ ሌሎች አሉ። ነገደ ሃበሳን.... ወዘተ እየተባሉ ከደቡብ አረብ የገቡ። የፊንቂን፣ የአራማይክ፣ የእብራውያን.. የወዘተ ስልጣኔ ይዘው መጡ የሚባሉ።





| የግሪክ ፊደል | [illegible] | [illegible] |
|---|---|---|
| Α | ፩ | አንድ |
| Β | ፪ | ሁለት |
| Γ | ፫ | ሦስት |
| Δ | ፬ | አራት |
| Ε | ፭ | አምስት |
| Ϛ | ፮ | ስድስት |
| Ζ | ፯ | ሰባት |
| Η | ፰ | ስምንት |
| Θ | ፱ | ዘጠኝ |
| Ι | ፲ | አሥር |
| Κ | ፳ | ሀያ |
| Λ | ፴ | ሠላሳ |
| Μ | ፵ | አርባ |
| Ν | ፶ | ሃምሳ |
| Ξ | ፷ | ስልሳ |
| Ο | ፸ | ሰባ |
| Π | ፹ | ሰማንያ |
| Ϙ | ፺ | ዘጠና |
| Ρ | ፻ | መቶ |

የእብራውያን.. የወዘተ ስልጣኔ ይዘው መጡ የሚባሉ።

ለማንኛውም ነገደ ዮቅጣን ወይም አጋዝያን የተባሉት የገቡበት ዘመን ያየነው ሲሆን፣ ከዚህ ዘመን በፊት ወደ ኢትዮጵያ የገባ ነገደ ሴም አልነበረም። ከተጠቀሠው ጊዜ በኋላ ግን በየጊዜው አዳዲስ ስልጣኔ እየያዙ ይመጡ ነበር።

ቋንቋ፣ፊደል፣ የአሃዝ ቁጥርን... ወዘተ በሚመለከት ወደፊት የምናገኛቸው እንዳሉ ሆነው፣ ነገር ግን ከወዲሁ መገንዘብ የምንችለው ወይም የሚኖርብን ቀደም ሲል በሌላ ምዕራፍ ስዕላዊውን ፊደል መሠረት ያደረገው ግኝት እንዴት ወደ ክግት እንደተለወጠና ከግሪክ እንደተቀላቀለ፣ ከዚያም በምን እንደተተካ፣ እንደገና ደግሞ በኋለኛው ዘመን ያ የግሪክ ፊደል ተመልሶ በሌላ አቅጣጫ እንዴት ሊመጣ እንደሚችል ነው።

በተረፈ.. ለምሣሌ በሂብሩ ቁጥር ሲቆጠር "ኤሐድ" አንድ ማለት ነው "አሀዱ" በኛ በግዕዝ አንድ ማለት ነው። "አንድ" በኛ አማርኛ "አንድ" ማለት ነው። በትርግኛም ያው ነው። ይሄ ሁሉ በሴማዊ ስሌት ነው። በኩሽቲክስ? ስንል አሁንም በኋለኛው ዘመን ፊደሉ ላቲን ሆኖ ይገኝና

ምንጩ ከወደ አፍሪካ ቀንድ አገሮች የፈለቀ ያደርጉታል። ስለዚህ አሁን የኩሽ ቋንቋ ተናጋሪ ከሆኑት ውስጥ ቋንቋቸውን ሲፅፉ በላቲን/ባሁኑ እንግሊዝኛ/ ቢፅፉ ያው የግሪኩ ፊደል መሆኑ ነው። ይህም ሲሆን የኩሽ ነገዶች ፊደል ሁሉ ከነጭ የመነጨ ይሆናል ሊባል ነው። አህዱ፣ክሌቱ.. የሚለው ኤ.ቢ.ሲ.ዲ ከሆነ ብዙ ነገር ማለት ይቻላል። እኔ የቋንቋ ሊቅ አይደለሁም። ዓለማዬ መጠየቅ ነው። የኢትዮጵያ ታሪክ በቋንቋና በፊደል ሚስጥራት ታጅሎ ያለ ነውና እሡኑ ከወገንተኝነት በፀዳ መልኩ በዘመናዊና በሣይንሣዊ የአጠናን ዘዴ "ያገራችን ሊቃውንት" ለማጥናት ቢሞክሩ ለማለት ነው።

በተረፈ "ዞሮ ዞሮ መግቢያው ጭራሮ" እንደሚባለው ዓለም አቀፍና አገር አቀፍ የቋንቋ ሊቃውንት ወይም የቋንቋ ጠበብት "ኩሽቲክ፣ ሴሜቲክ".. እያሉ ከፍለውታል። "ያፌቲክ" ለምን አይሉም ታዲያ?

ከዚህ በላይ ጥያቄ የለም። ከዚህ በላይ መልስም የለም።

በጣም በሚገርም ሁኔታ "ባለታሪክ ኢትዮጵያ" የተሠኘው የነጋ ወልደ ስላሴ መፅሃፍ በገፅ 43 እንዲህ የሚል ነገር ተካቶበታል። "... የግሪክ አፈ ታሪክ እንደሚለው ከሆነ "የተቃጠለ ፊት ያላቸው ሠዎች አገር" ለሚለው አነጋገር ትርጉም ሲሠጥ "ወራሪ ጠላት ገብቶ አገሩንና ንብረቱን ከመውሠዱ በፊት በአካባቢው ያለውን ንብረት ሁሉ ማውደም" ማለት ነው ይላል። የዚህ ትርጉም ስሜት የቀድሞዎቹ ግሪካውያን ስለ ኢትዮጵያ ከሚያውቁት ግንዛቤ ጋር ሲነፃፀር ፍችውን ይበልጥ ውስብስብ ከማድረጉም በላይ እንዲደራሲ እንዳስቀመጠው ጥንታዊያን ግሪኮች ስለዚህ አገር /ኢትዮጵያ/ የነበራቸው ግንዛቤ ጥልቅ ካለመሆኑም በላይ በተረታዊ ዘይቤዎች ላይ የተመሠረተ ነበር። ዘመናዊ የታሪክ ምርምር ዋና ዋናዎቹን የኢትዮጵያ ታሪክ ርዕሶች ሊያስጨብጠን የሚችል ቢሆንም ዞሮ ዞሮ ወሠንና መጨረሻ ወደ ሌለው ወደ ግብፅ ታሪክ ማምራቱ አይቀርም።..." ፀሀፊው ማኔቶን ይጠቅሳሉ። ማኔቶ የሄሮዱተስን ፅሁፍ ለማሻሻል የሞከረ ቅ.ል.ክ 300 ላይ የነበረ ነው።

በእርግጥም እነሄሮዱተስ፣ ሆሜር... ወዘተ ቀደምት የግሪክ ባለቅኔዎችና ታሪክ ፀሃፊዎች "ኢትዮጵያውያን መልካቸው ያማረ ቅኖች.." እያሉ የማወደሣቸውን ያህል በልዩ ልዩ ነገድ ተከፍሎ የሚገኘውን ህዝብ "በዋሻ የሚኖሩ፣ ውሻ የሚያረቡ፣ አራት ማዕዘን ፊት ያላቸው፣ ያሞራ ጭንቅላት..." እያሉ ያካተቱበት ሁኔታ አለ። ነገር ግን የኒለኞቹ ታሪክ አጥማሪዎች በሃቀኛ ፀሃፊዎች በእንሄሮዱተስ ፅሁፍ ላይ ሌላ ነገር ሳስሙጨመራቸው ምን ማስረጃ አለ? ምንም። እንዲህ የሚያወዛግቡን ያለነገር አይደለም።



እንዲያውም ከዚሁ መፅሃፍ አንድ ነገር ጨምረን እንለፍ "ስለጥንታዊ የኢትዮጵያ ስልጣኔ ለማጥናት እንቅፋቱ ችግር ስለዚህ ጉዳይ የሚያብራሩ ደንበኛና ማስረጃ የጨበጡ ፅሁፎች በቅርብ አለመገኘታቸው ሲሆን ቢገኙም አብዛኞቹ በግብፃውያን፣በእስራኤላውያንና በሶርያውያን የተዘገቡ ናቸው" ( ነጋ ወልደ ስላሲ1985 ዓ.ም) የሁሉም ብሶት ይሄ ነው። የት ሄደ ያ ሁሉ ታሪክ? ያሁኛል። ታሪኩን ሁሉ አውድመው መልሠው የተቃጠለ ፊት እያሉ በሚስጥር ማንነታችን ይነግሩናል ማለት ይሆን?

"... ሱማ! አካ ሱማ፣ የተባልከው እንደ አግሡማ... ለካ አንተ ነህ..." ይላል የሎሬት ፀጋየ ገብረ መድህን ቅኔ። በአፍሪካ ቀንድ ብትሄዱ በአፍሪካ ጅራት በኒለኛው ዘመን የተተበተበ ሴራ እንጂ ነገርየው ሁሉ ከዚህ ወደዚያ፣ከዚያ በኋላ ከዚያ ወደዚህ ነው። ዛሬ አንዳንዱ ያወቀ እየመሠለው "የኔ ቋንቋ ላቲን ነው" ይላል። ልክ ይሄን ሲል ታሪኩን ከነቫስኮ ደጋማና ከእነ ፈርናንዶ ምንትስ ቅብጥርስ ጉዞ ጋር በተያያዘ የተገኘሁ ነኝ ማለቱ ሲሆን ነው። እነሡም ከዚያ ፊልሣችሁ ስትመጡ የኛን ቋንቋ ይዛችሁ ገባችሁ ይላሉ። እኛ ደግሞ የኛን አሻሽላችሁ መለሣችሁት እንላለን። ቀጣዩን ምዕራፍ ስንቀጥል ተቀጣጥሎ እናገኘዋለን።

# ምዕራፍ ፮
# የኢትዮጵያ ትክክለኛ መጠሪያ ስም

እንባቢያን የመሠላችሁን መርጣችሁ ትይዙ ዘንድ ስለኢትዮጵያ መጠሪያ ስም የተለያዩ ፀሃፍት ያሉትን አሠፍራለሁ። ከዚያ ወደ ዋናው ጉዳይ እናልፋለን።

ዛሬ በአንድ ኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊ ስም የሚታወቀው የአገራችንና የህዝቦቿ/የነገዶቿ/ ስያሜ የቀድሞ መጠሪያዎች በርካታ ነበሩ።

በኦሪት ዘፍጥረት እንደተቀመጠው የኖህ ልጆች ሴም ካም ያፌት መሆናቸውን፤ የካም ልጆች ኩሽ ሚዕራይም፣ ፋጥ፣ ከነዓን መሆናቸውን እንደሚገልፀው፤ የኩሽም ዘር ተራብተውና በርክተው ከዛሬው ሡዳን ጀምሮ እስከኤርትራ ባህር ድረስ ያለውን አገር ይዘው ይኖሩ ነበር። ስለዚህም ቅ.ል.ክ ከ3000-1000 ዓመታት መካከል ካሉት ጊዜያቶች ጀምሮ ግብፆች በሐውልታቸውና በፓፒረስ/በልጥ ብራና/ ፅሁፋቸው ላይ እንደፃፉት ኢትዮጵያን ብዙ ጊዜ የኩሽ አገር፣ አንዳንድ ጊዜ የፑንት አገር እያሉ ይጠሩት ነበር።

ኩሽ ሲሉ ያው የነገድ አባትን ስያሜና የዘሮቹን መኖሪያ ምድር መሠረት አድርገው ነው። አባ ጋስፓሪኒ ደግሞ ፋጥ የሚለውን ጽጥ ካሉ በኋላ ፑንት አሉት ይሉናል። አንዳንድ ጊዜም የደቡብ ምድር ወይም የነህሴ አገር እያሉ ሲጠሩት ኖረዋል። ፑንት የሚባለው አገር ከሠሜናዊ ኢትዮጵያችን ጀምሮ እስከ (ኤልማንደብ) የየመንንም ግዛት የሚጨምር ነበር። የሚሉን ደግሞ ተክለፃድቅ መኩሪያ ናቸው። ነህሴ ማለት ደግሞ ከነገደ ካም 8ኛው ንጉስ ተብሎ የተመደበ ስለሆነ በመሪው ስም የነህሴ አገር ማለታቸው ነው።

በማቴዎስ ወንጌል በምዕራፍ 12 ቁ 42 ላይ እንደሚገኘው ደግሞ "... ንግስተ አዜብ ይህን ህዝብ ለመፋረድ ትነሣለች ... የሰለሞንን ጥበብ ለማየት ከምድር ዳር መጥታለችና ..." የሚለውን በኛ በግዕዝ ቋንቋ አዜብ ማለት ደቡብ (በደቡብና በምዕራብ መካከል የሚገኝ) ማለት ነው። ይህም ጥንታዊ ግብፆች "የደቡብ አገር" ከሚሉት ጋር ይገናኛል።

የሆነ ሆኖ ግብፆች የኩሽ ህዝብ የሰፈረበትን አገር የደቡብ አገር፣ የኩሽ አገር፣ የፑንት አገር እያሉ ጠርተውታል። የሴም ዘሮች መጥተው ከተቀላቀሉ በኋላም የሰፈሩብትን የኢትዮጵያን ሰሜናዊ ክፍል በቀድሞ መጠሪያው ፑንት እያሉ ነበር የሚጠሩት። ሌሎች ደግሞ እንደዛሬው አጠራራችን ኢትዮጵያ በማለት ሲጠሯት እንደኖሩ እናያለን።

አቢሲኒያ የሚለው ደግሞ የኩሽ የልጅ ልጅ በነበረው (በናምሩድ ልጅ) በአቢስ ስም የተሰየመ ነው።



ግሪካዊው ሊቅ ሆሜር (ቅ.ል.ክ. ከ1000-900 የነበረው) በኤልያድ (ስ) በምዕራፍ 5 በተለይ ኢትዮጵያ እያለ ደጋግሞ ይጠራል። የታሪክ አባት የተባለው ሄሮዱተስ (ቅ.ል.ክ. 500-400) ኢትዮጵያ ይላታል።

ከእስራኤሎችም ወገን ተመሣሣይ አጠራር እናገኛለን። ቅ.ል.ክ. 1100 ላይ የነበረው ዳዊት በመዝሙሩ ኢትዮጵያ ሲል በ700ኛው ቅ.ል.ክ. የነበረው ኢሣያስ ደግሞ በትንቢቱ በምዕራፍ 18 እና 11፣ ሶፎንያስ በምዕ.3 ቁ. 10 "የኩሽ አገር እያሉ ነው የጠሯት። መሠላቸው እምባቆም ደግሞ በምዕ.3 ቁ. 7 ላይ መልሶ ኢትዮጵያ ይላታል። እነዚህ ሁሉ ቀደምት ነብያትና ፀሃፍት ለእስራኤል ልጆች ተግሣፅና ምክር ወይም ለአምላካቸው የፀሎትና የምስጋና ቃል ሲያቀርቡ እግረ መንገዳቸውን የአገራችን ጉዳይ ሲያጋጥማቸው አንዳንድ ጊዜ ኢትዮጵያ በሌላ ጊዜ የኩሽ አገር እያሉ ሲጠሩት ኖረዋል።
በኋለኛው ዘመን ደግሞ የሴም ዘሮች ነገደ ሳባና ነገደ ዮቅጣን ከደቡብ አረብ የኤርትራን ባህር እየተሻገሩ ከካምና ከኩሽ ዘር ጋር ተደባልቀው ቡተቀመጡ ጊዜ በስም ላይ ስም እየበረከተ ሄዷል።

ምንም እንኳን የቀድሞዎቹ እስከ ኑብያ መንግስታቸውን /ግዛታቸውን/ አስፍተው የኩሽ አገር እየተባሉ ቢቀመጡ የተቀላቀሉት የሴም ዘሮችም በዚያው መጠሪያ ሲጠሩ ቢኖሩም፤ በስልጣኔ፣ በዕሁፍ፣ በልማድና በጥበብ ሁሉቱም ነገዶች የሚለያዩበት ሁኔታ ቢፈጠርም፣ መደባለቃቸው ግን ግድ ነበርና አንድነትም ልዩነትም ነበራቸው ይሉናል።

‹‹በኋላ ግን ነገደ ዮቅጣን ነገደ አግአዚ አጋዝያን፣ አገሩን ብሄረ እግዓዚ፣ ቋንቋቸውን ልሣነ ግዕዝ ብለው ከኩሽ ዘር ለመለየት ሞክረዋል።›› ( ተክለፃድቅ መኩሪያ 1951 ዓ.ም )

ዓረብ መታወቅ ከጀመረ በኋላ ደግሞ በንግግሩም በጽሑፉም ሐበሻ /ድብልቅ/ ብሎ ይጠራናል። መደባለቆችን ለማመልከት ነው ተብሏል።

ሐበሻ ሲሉን የቻሉበት ሌላው ምክንያት ደግሞ በዛሬው ምዕራብ የመን የሚገኘው የአገሩ ስም ሀበሳት፤ ሠዎችን ሀበሳን የተባሉት "ሃበሳ" ከሚባል የነገድ አባት ሃወረዱና ከአገራቸው ተሻግረው በኢትዮጵያ ሠሜን ስለተቀመጡ ሃበሳ የሚለው መጠሪያቸው ሆነ፤ በማለት በሳባውያን ፊደል "ሳ" የነበረው በአረብኛ "ሳ"በ"ሻ" ተለውጣ "ሃበሻ" የሚለውን መጠሪያ አገኙ ይሉናል።

በሌላ በኩል በብሉይ ኪዳን በዘፍጥረት ምዕ. 10 በኖኅ ዘር ውስጥ ሁለት ሳባ እንዳለ እንረዳለን። አንደኛው የኖህ የልጅ ልጅ ኩሽ የወለደው ሳባ ነው። ነገር ግን ከሌላው ለመለየት ሳባኖባ ይሉታል። ይህ የካሙ ነገድ የኑብያው ኢትዮጵያ የነገድ አባት መሆኑ ነው። እናም ሳባኖባ ሲገዛ ግዛቱን በስሙ ኑብያ ብሎ እንደሰየመ ይነገራል። ይህም በነገደ ካም የነገስታት ዝርዝር ውስጥ 10ኛ ተራ ቁጥር ላይ ያየነው ነው።

ሁለተኛው የሳባ ትውልድ ደግሞ ኖኅ የካምን ወንድም ሴምን፣ ሴም አርፋክስድን አርፋክስድ ሳላህን፣ ሳላህ ኤቦርን፣ ኤቦር ዮቅጣንን፣ ዮቅጣን ሳባን ይወልዳል።

ይህን የዮቅጣንን ልጅ ሳባ ሻባ ይሉታል። እርሱም በነገደ አጋዝያን የነገስታት ዝርዝር ውስጥ ተራ ቁጥር 4 ላይ ሰፍሮ ያየነው ነው።

ሳባሻባ ወይም የሴም ዘር ግንድ የሆነው የኢትዮጵያ ገዥ ከገዛ በኋላ በእርሱ እግር የተተካው በዝርዝሩ 5ኛ ላይ የሰፈረው ኢትኦጵስ 1ኛ ደግሞ ግዛቱን ኢትዮጵያ ብሎ ሰየመ ይባላል።

በእነዚያ ዘመናት በአሁኒቷ ኢትዮጵያ የሚገኙት አግዓዚ ወይም ሃበሳን የሚባሉት የአሁኗን ኢትዮጵያ ሰሜናዊ ክፍል ይዘውና ጠብቀው ሲኖሩ ቀደም ሲል የነበሩት ነገደ ካም /ኩሽ/ የሚባሉትም በኑብያ ኢትዮጵያና በአሁኗ ኢትዮጵያ መኖራቸውን ቀጠሉ።

በዚህና በዚህ መሰል መልኩ የኢትዮጵያ መጠሪያ ስም የተለያየ እንደነበር እንረዳለን። ባጠቃላይ በመጀመሪያ በኩሽ፣ ቀጥሎ በናምሩድ ልጅ አቢስ አቢስኒያ ከዚያም በሳባ ኖባ ስያሜ ኑብያ ... ወዘተ... እየተባሉ ሲጠሩ ቆይተው የሴም ዘሮች ውስጥ ነገደ አጋዝያን ከመጡ በኋላ ደግሞ ከእነሱ አንዱ በሆነው በኢትዮጲስ 1ኛ ኢትዮጵያ ተብላ መሰየሟና በየጊዜው ወደ ኢትዮጵያ በገቡት ነገደ ሃበሳን... ወዘተ ሲባሉ ሃበሻ የሚለው መጠሪያ እንደመጣ ነው የሚታመነው።

በዚህ መፅሃፍ አጠናቃሪ እይታ ከላይ የተዘረዘሩት የተለያዩ የኢትዮጵያ መጠሪያ ስሞች (ከሁለቱ ውጪ) መጤ ናቸው። ወይም መሰረት የላቸውም። ስራቸው በሚገባ የተጠና አይደለም።

ይህ ማለት ግን ለምሳሌ "ፑንት" በሚለው ስም አንድ ታሪክ ተፅፎ ቢገኝ ኢትዮጵያን ለመግለፅ ተብሎ የተፃፈ መሆኑን እንክድም። "ኑብያ" ተብሎ በተጠራና በተፃፈ ጊዜ የኢትዮጵያን ግዛት እየገለፀ እንደሚገኝ እንክድም። "ሃበሻ" በሚል ቃል ታሪካችን በሆነ ቦታ ሰፍሮ ቢገኝም እኛን እንደሆነ አንክድም። አቢሲኒያ ቢሉንም እንሰማቸዋለን።

የኛ ጉዳይ ሌላ ነው። የኢትዮጵያ የመጀመሪያው መጠሪያ ስም፣ ስሩ፣ ምንጩ የቱ ነው? የሚለው ነው። ምክንያቱም ያየነው ስያሜ ሁሉ፣ ሁሉም የየራሱን አገር መስርቶ መሰልጠን፣ መፃፍ፣ ማዬል ከጀመረ በኋላ ነው የተኘናገደጎደው።

ኢትዮጵያ በተለያዩ ፀሃፍት ዘንድ በተለያየ አጠራርና ስም ስትጠራ መኖሯ እንዳለ ሆኖ በዋናነት በኦሪት ላይ "ኩሽ" ተብላ ሰፍራ እናገኛለን። ከዚህ በኋላ 70 ሊቃውንት በጋራ ሆነው ብሉይን ከእብራይስጥ ወደ ፅርዕ /ግሪክ/ ሲተረጉሙ "ኩሽ" የሚለውን ቃል/ከግብፅ በስተደቡብ ያለውን አገር ሁሉ ለመጠቆም" ይጠቀሙበት የነበረውን የነገድ አባት ስም/ "አይቶ ፒያ" ወይም "Aithio - Pia" ብለው ተረጎሙት።



ይህንኑ ወደ ግዕዝ ሲተረጉሙትም ቃሉን ብቻ እንደወረደ "ኢትዮጵያ" ብለው አስፈሩትና ከግዕዝ ወደ አማርኛ ሲተረጎምም እንደገና ያሰፍሩቺ ሆኄውን ብቻ "ኢትዮጵያ" አገሪቷን፤ ህዝቡን "ኢትዮጵያዊ" አሉት።

የቃሉ ስረ መሰረት የት ነው? ሲባል ግሪክ ሆነና ትርጓሜውስ? ተብለው ሲጠየቁ "በፀሃይ የጠቆረ፣ በፀሃይ የተቃጠለ ፊት ያላቸው ..." ብለው የነገሯቸው ወይም የዋሹዋቸው ብሉይ ከሂብሩ ወደ ፅርዕ በተተረጎመበት ዘመን ቅ.ል.ክ. 282 ላይ ነበር። Aithio — Pia የሚሉት እነዚህ ሁለቱ ቃላቶች "አይቶ" ጥቁር፣ አደረገ፣ አቃጠለ፣ የሚል ትርጉም ሲሰጥ "ኦፕያ" ወይም "አጵስ" ፊት የሚል ትርጉም ይይዝና ነዋሪዎች ፊታቸውን ፀሃይ ያቃጠለው በሚል ሆና። አንዳንዶችም ሲራሩልን ጠይም ለማለት ነው ይሉናል።

በዚህ ምዕራፍ ይህን ቀልማዳነት አፍርሰነው እናልፋለን።

በዚያ ባልሰለጠነው የግሪክ ፒክቶግራም ሆሜር በኤልያድ/Iliad/እና በodyssey ላይ "በኢትዮጵያ የሚኖሩ ህዝቦች እጅግ ሃያላን እጅግ የሚያምሩና የተከበሩ ናቸው። ..." ይላል፤ በመዝሙሩ ቁ 423 ላይ። "የአማልክት አባት ዜውስ ሃያላኑን ኢትዮጵያውያንን ለማየትና አብሯቸው ምግብ ለመብላት/ማዕድ ለመሳተፍ/ ወደ ታላቁ ወንዝ ይወርዳል..." እያለ የተረከው ቅ.ል.ክ. ከ1000-900 ባለው ጊዜ መካከል ነበር። ያኔ "አይኦቶፒያ" "Aiotopia" ተብሎ የሚነበብ ያልሰለጠነ ፊደል ነበር የነበራቸው።

የኋለኛው ዘመን ግሪካዊ ሊቅ ሄሮዱተስም ቅ.ል.ክ. 490 ላይ የተወለደው "ኢትዮጵያውያን ወይም የኢትዮጵያ ነዋሪዎች ከሰዎች ሁሉ የተዋቡና ታላላቆች፣ ቁመናቸው ያማረ ሃያላን ናቸው ..." ይላል 3ኛ መፃህፍ ም.20 ቁ. 114

ይሄ ሁሉ በቀድሞው ባልሰለጠነው ፊደልና ቋንቋ ውበትን ለመግለፅ ሲጠቀሙበት የኖሩት ቃል ነው።

ቀደም ሲል የነጋ ወልደስላሴ ባለታሪክ ኢትዮጵያ ገፅ 45 ላይ ያየነውን አንድ አንቀፅ እንድገመው፡- "የግሪክ አፈ ታሪክ እንደሚለው ከሆነ "የተቃጠለ ፊት ያላቸው ሰዎች" ለሚለው አነጋገር ትርጉም ሲሰጥ "ወራሪ ጠላት ገብቶ አገሩንና ንብረቱን ከመውሰዱ በፊት በአካባቢው ያለውን ንብረት ሁሉ ማውደም" ማለት ነው ይላል" በማለት የሄሮዱተስ ፅሁፍ ላይ የራሱን ፅሁፍ ጨመረ የተባለውን ማኔቶን ጠቅሰው ጠቁመውናል። ማኔቶ ቅ.ል.ክ. 300 ላይ እንደነበረም አይተናል። ምንም እንኳ ይህ መፅሃፍ ከዚህ ያለፈ ነገር ሊነግረን ባይችልም ለኛ በቂ ነው።

ይህ ወቅት ማለትም ቅ.ል.ክ. 300 ማለት አስገራሚ ዘመን ነበር። ታላቁ እስክንድር ታላቅ የተባለበት ዘመን፤ ግብፅን ያስዋበበት ዘመን፤ የእስክንድርያን ከተማ በስሙ ሰይሞ 24 ሰአት መብራት የሚበራባት ከተማ አድርጎ ያሸበረቀበት ዘመን... ነበር። እስክንድር ያልያዘው ኢትዮጵያንና ህንድን ብቻ ነበር። ነገር ግን እሱ የሞተው በ323 ነበርና የጦር አለቆቹ

ግዛቱን ሲከፋፈሉ /ጎድለውታልም ይባላል/ ከእሱ ዓላማና እቅድ ውጪ የሆነ ተግባራትን እንደፈፀሙ ታሪክ ይነግረናል።

እስክንድር የሆሜር ፍፁም አድናቂ እንደነበርም ይታወቃል። ኢትዮጵያንም የሚያውቃት እነሆሜር በፃፏትና ባዩባት አይን መሰረት መሆኑ ግልፅ ነው። በጥቅሉ እስከእርሱ ዘመን ድረስ ኢትዮጵያ የተዛባ ትርጉም አልነበራትም።

የሆነ ሆኖ ከእርሱ ሞት በኋላ ታሪክ ተለዋውጧል። እናም ያ ዘመን የኑብያ ኢትዮጵያው ፊደል ከዲሞቲክ የህዝብ ፊደል የተቀላቀለበት፤የአዶሊስ ወደብ የተሰራበት፣ ወደቡ ከእስክንድር ተከታዩች አንዱ በሆነው በፕቶሎሚ /በጥሊሞስ/ ስም የተሰየመበት፣ አክሱማውያን መግነን መታወቅ የጀመሩበት፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ዘመናዊ ወደብ የተሰራበት፣ በግብፅ ጥንታዊው ፅሁፍ ቀርቶ "ኮፕት" ተግባራዊ የተደረገበት፣ የአሃዝ ቁጥርን ለመጀመሪያ ጊዜ ከግሪክ ፊደል ወረሱ የተባለበት/እንደ እውነቱ ከሆነ ዳግም የተፈጠሩበት/ ታሪካቸውን በግሪክ ቋንቋ መፃፍ የጀመሩበት፣ በደቡብ አረብ በየመን የእን ዜውስ ጣኦት የተተከለበት ... ዘመን ነበር።

ማኔቶ ግሪካዊ ሆኖ ሣለ የግብፅ ካህን የሆነበት ዘመን ነው። ደራሲም ነው፣ ፈላስፋም ነው፣ ታሪክ ፀሃፊም ነው፤ አፈታሪክ የሆነውን ነገር... ያውቃል። የእነሄሮዱተስን ፅሁፍ የማሻሻል፣ የመጨመር ብቃትም እውቀትም ስልጣንም ነበረው። የግሪክ አዲሱ መዝገብ ቃላት የተዘጋጀበት ዘመን ነው። ኑብያም የተያዘችበት ዘመን ነው።

እስክንድር ግን "የአማልክት መቀመጫ፣ የእነዜውስ አገር" እየተባለች በእነ ሆሜር የተነገረችውን አገር በጦር መያዝ አልፈለገም። ግብፅን ከያዘ በኋላ እንኳ ኑብያን አልነካም። ይልቁንም ከልጅነቱ ጀምሮ ያስተማረው አርስቶትል በመከረው ምክር መሰረት የዓባይን ምንጭ አስመረመረ እንጂ። በኋላም መጥቶ ለኢትዮጵያዊቷ ንግስት የአክብሮት ሰላምታውን አቀረበ እንጂ። ስለዚህ ... የትርጉም ለውጥ ... ማለትም ማውደም ማቃጠል ... የሚለው እግረ መንገዱን ... የተቃጠለ ፊት ... ወዘተ እየተሰኘ ተሻሽለ እንጂ ጥንትማ ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ ነበረች። አፈታሪኩን ይዘን አይደለም ይህን ያምነለው። እሱን እንደ አንድ ተጨማሪ ማዳበሪያነት እየተገለገልንበት ነው። ገና አልጨረስንም።

"ኢትዮጲስ 1ኛ" "ኢትዮጲስ 2ኛ" የሚለው ስም ግሪክ ከመታወቋ ሺ አመት ቀድሞ እዚህ የነገስታት መጠሪያ ስም የነበረ ነው። "ኢትዮጲስ" በአማርኛም፣ በግዕዝም፣ በሱባም በእንግሊዝኛም፣ በምንም ቢለዋወጥ ያው ኢትኦፒስ ነው። ያው ነዋ! የአገሪቱ ስም ትርጉሙ በግሪክ ብቻ ከተገኘ ንጉስ ኢትኦጲስ ከግሪክ የወሰደው ስም ነው? በአማርኛ በኋለኛው ዘመን ተለውጦ ነውንጂ የንጉስ ኢትኦጲስ ስም ትርጉሙ "የተቃጠለ ፊት ያላቸው ህዝቦች ንጉስ" ሊባል ነው?



የአክሱም ታሪክ ወደ ፊት እንደምናገኘው በየሃውልቱ ላይ ግሪክኛ ፊደል ተፅፎባቸውና እነሱው መረጃ ሆነው ስለተገኙ ብቻ የኢትዮጵያን ታሪክ፣ ፊደል አወራረስንም ሆነ፤ ቁጥር አከራረድን ሊወስኑ አይችሉም። ያ ከሆነ ኢትዮጵያ የ1600 አመት ታሪክ ይኖራታል።

የግዕዝ ቋንቋ ግን በአጋዝያን ዘመን ነበረ፤ በግዕዝ የተፃፈ ሰነድም ሞልቷል። የአሃዝ ቁጥርም ነበራቸው፤ አሪትም ገብቷል ... ወዘተ። ኢትዮጵያም ቋሚ ስም፤ ትርጉም ያለው ስም ነበራት።

"ኢት– ስጦታ፣ ዮጵ ብጫ ወርቅ ወይም እንቁ፣ ግዮን ፈሣሽ ወንዝ፣ በጥቅል ኢትኦጵግዮን "የግዮን ወርቅ ስጦታ ተብሎ በሱባ/በሳባ/ ይተረጎማል" ለመሪ ራስ አማን በላይ እናጨበጭባለን። /መፅሃፈ አብርሂት 1999 ዓ.ም/

እኛ ጥሩ ጥሩውን ወደኛ እያመጣን አይደለም። በእውነቱ ከላይ የታተቱት ሃተታዎች ሁሉ ግዴታ ሆነው አይደለም። "ኢትኦጵ" የሚለውን ብቻ አስፍሮ "ሃግሪኩን እርሱት" ብሎ ተክቶ ማለፍ ይቻላል። ነገር ግን ይህቺ ሀገር በራስዋ ቋንቋ ትርጉም የሚሰጥ ስም የነበራት አገር መሆኗንና ኢትዮጵያ የሚለው ቃል ምንጩም ፍንጩም ከግሪክ አለመሆኑን ገልጾ ለማለፍ ሲባል ነው። መፍረስም ይኖርበታል።

"ኢትዮጵያ ማለት" ብለን በመጀመር ተወራርሶ ሲቀመጥ እንዴት እንደሚሆን ማደራጀት ሳይኖርብን አይቀርም። ኢትዮጵያ ማለት በትክክለኛው፤ ፍፁም በጠራው አገላለፅ ባሁኑ "ኢት–ዮጵ" የአማርኛ አባት በሆነው በግዕዝ "ኢትዮጳግዩን" የግዕዝ አባት በተባለው በሳባ "እንቅዮጳገዮን" ቋንቋ ከመከፋፈሉ በፊት በኖኅና በቤተሰቦቹ ዘመን ኩሽቲክ ሴሜቲክ ተብሎ ከመከፋፈሉ በፊት በነበራት ስያሜ "እንትዮጳገዮን" የተባለች አገር ናት።

የመፅሀፈ አብርሂትን አገላለፅ እንደወረደ ሳስፍርና አብረን በደንብ እናፀድቀዋለን።

"ኢት–ስጦታ፤ ዮጵ–ብጫ ወርቅ ወይም እንቁ፤ ግዮን • ፈሳሽ ወንዝ፣ በጥቅ ል ኢትኦጵግዮን፤ የግዮን ወርቅ ስጦታ ተብሎ በሱባ ይተረጎማል። እንቅዮጳግዮን የሚለውን እንቅዮጳገዮን ብለውታል" ይሉናል። ደህና ሁኑ! በሏቸው። የእነርሱን የተወላገደ ትርጉም እዚያው ለራሳቸው!

አሁን እኛ ማስረጃችን ብዙ ነው። እንግዲህ ያ ፅሁፍ ከደንጎላው ሰነድ አንዱ መሆኑ ነው። በኋለኛው ዘመን በመጣ ሴማውያን የተከተበና በሱባ ቋንቋ ትርጉም የሚሰጥ ስም ነው።

አለቃ አያሌው ታምሩ በ1995 ዓ.ም በአንድ ያገራችን ጋዜጣ ያስቀመጡት እውነታ አለ፡ "ግዕዝ የዓለም ቋንቋ ነው፤ የዓለም ህዝብ በዚህ ቋንቋ ዛሬ ባይጠቀምበትም የዓለምን ድምፅ አጠቃሎ የያዘ ግዕዝ ነው። ግዕዝ ለዓለም ቋንቋ መሰረት ነው። ልዑል እግዚአብሄርና ሰው ለመጀመሪያ ጊዜ የተነጋገሩበት ቋንቋ ግዕዝ ነው። ሰባት የድምፅ ንብረት ያለው ብቸኛ ቋንቋ ግዕዝ ነው። ይህ ድምፅ በመላው አለም እየሆረ ነው። በአገሩ ግን የተናቀ ሆኗል፤ በተለይ ዛሬ።" ብለዋል።

"ኢትዮጵያ ማለት ምን ማለት ነው?" ሕ … በግሪክ የተቃጠለ ፊት ማለት ነው ቲቸርዬ" "ብራቮ በትክክል ተመልሷል። የተቃጠለ ፊት ወይም በፀሃይ የጠቆረ ፊት ያላቸው… ጎበዝ ልጅ!" ትምህርት ቤት ነ ነው። ኢትዮጵያዊ መምህርና ኢትዮጵያዊ ተማሪ። ፈተና ላይ ሳይቀር ይቀርባል።

ወዲያው ደግሞ እዚያው ክፍል ውስጥ "ኢትዮጵያ የ3 ሺ አመት ታሪክ ያላት፣ የራሷ ፊደልና ቋንቋ ያላት፤ ዓለም ባልሰለጠነበት ዘመን የወጪ ንግዷ እጣን፣ ብርጉድ፣ ክርቤ፣ የዋሊያ ቀንድ፣ ያውራሪስ ቀንድ፣ በታችኛው ሽለቆ፣ በላይኛው ሽለቆ፣ የኩሽቲክ ተናጋሪዎች በሰፈሩበት፣ ሴሚቲኮች ከመግባታቸው በፊት፣ ኒሎ ሰሃራ ከመሰልጠኑ በፊት፣ በኦሞቲክ ተፋሰስ … ምንትስ ቅብርጥስ" እየተባለ ይሸነጎዳል።

ኪርኩለሙ የነሱ ከሆነ መቸስ ምን ይደረጋል?

ለማንኛውም መቀበል ካለብን ራሳችን ለማሞኘስ ሳይሆን፣ በግሪክ የሚጠክሰን ትርጉም ስለሌለው ሳይሆን በቂ ማስረጃ ስለሌላቸውና እኛ ግን ስላለን ነው። ምነው መረጃ መረጃ ይባል የለ? እነሱ እኛን የሚያስፈራሩን በመረጃ የተደገፈ በሚል ውሽክታ ነው። ስለዚህ ይብራሩልን።

ከዚህ የበለጠ ማስረጃ ከየት ይመጣል? ዓባይ መቸም ትርጉም አለው። በአማርኛ ዓባይ፣ በግዕዝ ፈለገ ግዮን፣ በጥንት ግብፃውያን ዲልታ፣ በቅዱስ መፃህፍ "የኣር" በአዲሱ ላይ ግዮን፣ በአረቦች ምስር፣ ፈደል አልባ በነበሩ አገሮች ኒል ኧረ ብዙ ብዙ እየተባለ ተገለባብጦ ትርጉም ሲሰጥ የኖረ ወንዝ ነው።!

ስለዚህ በአማርኛ ኢትዮጵያ እያልነው ያለነው በዘመን ብዛት ተወራርሶ እዚህ ደረሰ እንጂ በጥንታዊ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አንድ አይነትና ተመሳሳይ፣ ቢገለባበጥ ይዘቱን የማይለቅ፣ በራሱ በፈጣሪ የተሰየመ፣ ከነወንዙ የተሰጠ ስያሜ ነው። የምድር ሁሉ ቋንቋ አንድ በነበረች ጊዜ፣ በቋንቋዎች ሁሉ እናት ቋንቋ፣ ፈጣሪ ከፍጡሮቹ ጋር በተነጋገረበት ቋንቋ "እንቅዮጳዝዮን" ስትባል ቆየችና ቀስ በቀስ "ኢትዮጵግዮን" መባል ጀመረችና በመሐል ቤት ተሰረቀች። ከዚያ በኋላ ለሌላ ግልጋሎት ሲጠቀሙበት ኖረው ብንፈልግ፣ ብንፈልግ፣ ብንዳብስ፣ ብንዳበስ አጣነው። በመጨረሻ "ኢትዮጵ" ሆኖ አገኘነው። ኢት፤ ስጦታ ዮጵ፤ ብሩሬ ወርቅ፤ ኢት ዮጵ-አሃ ብለን ስንመረምር ፍርፍርው ወጥቶ ቁጭ። ስሟ ተገኘ!

"ኢት" ምንድነው? "ስጦታ" ዮጵ? "ብሩሬ ወርቅ ወይም እንቁ" ግዮን? "ፈሳሽ ወንዝ" በጥቅል? "ኢትዮጵግዮን" አጠቃላይ ምን ይሆናል? "የግዮን ወርቅ ስጦታ" በድሮው የኢትዮጵያ ቋንቋ ምን ትባል ነበር? "ኢትኦጵግዮን" ከዚያ በፊትስ ያች ምድር ማን ትባል ነበር? "እንቅዮጳዝዮን" ባጭሩ የአገራቱ ስያሜ ምን ተብሎ ይገለፃል? "የግዮን ምንጭ" ጎበዝ ልጆች በትክክል ተመልሷል። በሁሉም ቋንቋ ትርጉሙ ይሄ ነው። ወደፊት ልጅ ስወልድ የማስተምራቸውን እየተለማመድኩ ነው። እንዳይንዛዘባቸው "ኢትዮጵ" እላቸዋለሁ። ክፍ ሲሉ "ኢትኦጵግዮን" እላቸዋለሁ። ለአቅመ አዳምና ለአቅመ



ሄዋን ሲደርሱ "እንቅዮጳዝዮን" መሆኑን እነግራቸዋለሁ። ፀሃይ ለፀሃይ እንዲንከራተቱ ሳይሆን በነፋሻማ አየር ዘና ብለው ወርቅ እንዲፈልጉ!

ለማንኛውም እኔና እናንተም በዚህ መልኩ ብንቀበለውና በደንብ ብናፀድቀው ደስ ይለኛል። ጥልቅ ምርምሩንም ሆነ አወራረዱን አሰፋፈሩንም ሆነ አጠቃላይ ሁኔታውን ለምሁራን እንተዋለን።

እውነቱ ደግሞ ይሄ እና ይሄ ብቻ ነው።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ከ "ኢትዮጵያ ታሪክ ኑብያ/ናፓታመረዌ/" መፅሃፍ ስለዚያ ዘመን ሁኔታ የተወሰኑ ነጥቦችን ቀርሰን አውጥተን ጥቂት ነገሮችን እንዲያው ለትዝብት ያህል … ስለ አክሱምና ስለግሪኮች ግንኙነት እንመልከት። ከወዲሁ ጠርጥረን ካላለፍን እዚያ ዘመን ላይ ስንደርስኮ… የግል ሃተታ አናስገባም። የተባለውን ማለት ብቻ ነው።

"… እስክንድር ሊሞት ሲል ግዛቱን በደፈናው "የሚገባው ሰው ይውሰድ" ብሎ የማንንም ስም ሳያነሳ ሞተ ይባላል። የጦር አለቆቹ ግን "እኔን ይሆናል" በማለት በአሳብ ተንሸ ተተራመሱ። ተዋጉም። ከሞተ በኋላ ከ ሮክሳን የተወለደው አሌክሳንደር ኤጎ የሚባለው ልጁ በመቄዶንያ ዙፋን በሞግዚት የሁሉ የበላይ ሆኖ እንዲገዛ ተደርጎ ነበር። ዳሩ ግን የገዛ ሞግዚቱ ካሳንድር ከነእናቱ ጋር ገድሎ መቄዶንያን ያዘ። የቀረውንም ሰፊ ግዛቱን "ዲያዶክ – ተከታይ" የተባሉት የጦር አለቆቹ በክፍፍልና እኔ የበላይ ልሁን በማለት እርስ በርሳቸው ብዙ ጊዜ ሲዋጉ ቆይተው የመጨረሻው ጦርነታቸው በ301 ቅ.ል.ክ. በ ኢፕሰስ ከተደረገ በኋላ እርቅና ሰላም ሆኖ ከዚህ እንደሚቀጥለው በስምምነት ክሶስት ላይ ተከፋፈሉት።

1ኛ፡- ግብፅና አካባቢው ለፕቶሎሚ/በጥሊሞስ/ የላጎስ ልጅ

2ኛ፡- ሶርያና አካባቢው ለሴለውኩስ

3ኛ፡- መቄዶንያ ከካሳንድር በፊት ለአንቲገን በኋላ ለካሳንድር።

እንግዲህ ከዚህ ጊዜ ቀጥሎ እስከ ሮማውያን መነሳትና እስከ ክሊዮፓትራ ድረስ የበጥሊሞስ ዘር እየተከታተለ በግብፅ ዙፋን ተቀመጠ። የመርዌና ያክሱም መንግስታትም … ግንኙነት አድርገው የግሪክን ስልጣኔ በመጠኑ ማስገባት የቻሉት ሽቀጥ ለሸቀጥ የተለዋወጡት ከነዚሁ ከነበጥሊሞስ ጋር ነው።" ይሉናል በገፅ 173።

በምዕራፍ 29 በገፅ 178 ደግሞ "… እርሷንና (የመርዌዋን ህንዳኬን) አገሯን ለመሰለል ክግብፅ ሰላዮች በላከ ጊዜ ራሱ ትልቁ እስክንድር ከሰላዮቹ ጋር እንደ አንድ ተራ ሰው መስሎ መጥቶ እንደነበርና አውቃው "አንተ ዓለምን የያዝከው እስክንድር ንጉስ ዛሬ ደግሞ ባንዲት ሴት ተያዝህ" እንዳለችውና እርሱ ደግሞ "አንችንም ልጆችሽንም በደግነት አጠብቃችዋለሁ፤ አንችንም ሚስት አደርግሻለሁ" እንዳላት… የዮሃንስ መደብርን መፃህፍ ጠቅሰው አስፍረዋል። ወረድ ስንል፡-

"… የሆነ ሆኖ እስክንድር ባለፈው ባመለከትነው አይነት ሞቶ ግዛቱን የጦር አለቆች ሲካፈሉት የግብፅ ግዛት ለፕቶሎሚ ሶተር ደርሶ ይኸው

ኘቶሎሚ በግብፅ ላይ ንግሶ በሚያስተዳድርበት ዘመን በመርዌም ንግስት ህንድኬ ሞታ አስተርክ አሚን ገነሰ። (ሶስት መቶ አመት ከክርስትና በፊት) በዚህም ጊዜ የግብፅ ገዥዎች ኘቶሎሚ ሶተርና ከእርሱ የቀጠለው ኘቶሎሚ ፊላደልፍ በኢትዮጵያ የሰሜን ጠረፍ ወታደርና ሰው መላክ ጀመሩ። በተለይ ኘቶሎሚ ፊላደልፍ በምጥዋ ወደብ አንድ የባህር ወደብ አሰርቶ በስሙ ኘቶሎማይስ ብሎ ሰየመው። እንደዚሁም ከቀድሞ ኸምሮ የነበረው የአዶሊስ ከተማ ወደብ ከጊዜ ወደ ጊዜ ይበልጥ ተሟሙቆ የግብፅና የኢትዮጵያ ዋና የሸቀጥ ማመላለሻ ሆኖ ነበር።

ይኸም ኘቶሎሚ ፊላደልፍ በ282 ቅ.ል.ክ. ላይ ከእስራኤል ሊቃውንት ውስጥ ሰብአ (70) ሊቃውንት ራሱ መርጦ አምጥቶ ብሉይን ከእብራይስጥ ወደ ፅርዕ ለመጀመሪያ ጊዜ ስላስተረጎመ በትርጉሜው ስራ ራሱ አብሮ ስለሰራ ስመጥርነትን አግኟል።

ከህንደኬ ንግስት ይኸውም ከ300 አመት ቅ.ል.ክ. ወዲህ በመርዌ ምንም ያህል ሃይለኛና ታሪካዊ ስራ የሰራ ንጉስ አልተነሳም። አስተርክ አሜን፣ አርካሜን፣ አሩአሞን፣ ሐርሲኦተው የሚባሉ ነገስታት በዙፋን አልፈዋል። እነዚህም ምናልባት በዘመናቸው ብዙ ስራ የሰሩ ይኖርባቸው ይኖራል። ዳሩ ግን ከእነዚህ ውስጥ የአርክአሜን በመጠኑ ሲገኝ የቀሩት ስራቸው በታሪክ ውስጥ ሽፍን ነው።..."

እንግዲህ ... በግልፅ እንዳየነው "ኢትዮጵያ" የሚለው ስም በዚሁ ጊዜ ነው መሰረቱን የያዘው ማለት ነው። ስመ ጥርነትን ... እሱ...

"ኩሽ" የሚለውን ወደ ፅርዕ /ግሪክ/ ሲተረጉሙ "ኢትዮጵያ" እሉት አይደለም የተባለው? በዚህ ጊዜ ነው በፀሃይ መቃጠላችን የነገሩን፤ መክሰላችን ያረዱን፤ መጥቆራችን ያበሰሩን፤ ከዚህ ጊዜ በፊትስ? እነ ሆሜር፣ እነ ሄሮዱተስ ማን ይሉን ነበር? "አይቶፒያ" ምን ለማለት? "ታላላቆች፣ መልካቸው ያማረ፣ ቅኖች፣ በጎ አድራጊዎች፣ ሸበላዎች..." እያሉ የዚችን ምድር ነዋሪዎች ሲገልጿቸው ነዋ። ታዲያ ከምኔው ጠቆርን ጎበዝ? ከዚህ በፊት ስሟ ማን ሆነና!

"አሯል ሆዴ ጨሷል ሆዴ

ቢቸግረኝ እንጂ ጠላቴን መውደዴ!" አለ ያገሬ ሰው! "ዘራፍ!" አትልም ... እንዳባቶችህ!



## ምዕራፍ ፺

## የአክሱም ኢትዮጵያና የኑብያ ኢትዮጵያ ልዩነትና አንድነት

የአክሱሙ ኢትዮጵያና የኑብያው ኢትዮጵያ ልዩነትና አንድነት ስንል ከታሪክ አንፃር እንደመሆኑ መጠን የአዲስ አበባ ኢትዮጵያና የድሬዳዋ ኢትዮጵያ እያልን እንጂ ሌላ አይደለም። በዚህ ግ--ር ወይም ቅ--ር የሚሆኝ ካለ «እሽ በቃ የአስመራው ኢትዮጵያና የአዲስ አበባው ኢትዮጵያ እያልን ነው» ብለን እናረጋጋዋለን። በዚህ ምሣሌ ካልተግባባን ኢትዮጵያ የ20 አመት ታሪክ ያላት ናት ልንል ስለሆነ ይቅርብን።

ቀደም ሲል እንዳየነው በኢትዮጵያ በነበሩ የካም ኩሽ ነገድ ላይ ነገደ ዮቅጣናች ከተቀላቀሉ በኋላ የአሁኗን ሠሜናዊ የኢትዮጵያ ክፍል ይዘው ሲኖሩ፤ ነባሩ ህዝብ ደግሞ ወደ ኑብያ እየተስፋፋ ሔዷል። ያም ቢሆን በቀደመው ዘመን በጣም የገነነው መንግስት መቀመጫው በኑብያ ኢትዮጵያ የነበረና ነገስታቱ መቀመጫቸውን እየለዋወጡ በየግዛቱም በንጉሰነገስቱ ስር የሆኑ ንጉሶች እየተሾሙ በጋራ ያስተዳድሯት የነበረች አገር ናት። «በመላ አፍሪካ ከሚታወቁት የቋንቋ ቤተሠቦች መካከል አፍሮ እስያዊና አባይ ሠሃራዊ የተሠኙ ሁለቱ በኢትዮጵያ ይነገራሉ። ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚነገሩት ከ70 የሚበልጡ ልዩ ልዩ ቋንቋዎች ሁሉ ከተጠቀሡት እናት ቋንቋዎች እንደመነጩም ይታወቃል። የኢትዮጵያ ህዝብ ተሠባጥሮና ተቀላቅሎ መስፈር ከቋንቋዎች ስርጭትም አኳያ ሊገለፅ ይችላል። በጥቅል ሲታይ የኢትዮጵያ ህዝብ ተወራርሷል፣ ተጋብቷል፣ ተዛምዷል። በጋራም የረጅም ታሪክ ባለቤትነቱን በጦርነትና በሠላም ጊዜ ተጋርቶአል።» (ፕ/ር ላጵሶ1983 ዓ.ም)

ከዚህ አንፃር በኑብያ ኢትዮጵያም ሆነ በአክሡሙ ኢትዮጵያ የነገስታቱ የዘር ሃረግ አመዛዘዝ ወጥ የሆነና ተዋረዱን ጠብቆ የተከታተለ አንጋገስ ነበረ ብሎ ማሠቡ ብዙ አያስኬድም። ይህ ምናልባት በኋለኛው የአክሡም ዘመን ተግባራዊ የተደረገ ቢሆን እንጂ በጥንቱ ዘመን ሆኖ ነበር ለማለት አይቻልም። የአሁኗ ኢትዮጵያ መስራቾች አክሡማውያን መሆናቸው ይታወቃል። ነገር ግን ታሪክ የሚነግረን ከጎናቸው ያለው መንግስት እየደከመ ሲሄድ (የናፓታና የመርዌው) አክሡማውያን አክሡምን እያቀኑ፣ እያገነኑ መነሳታቸውን ነው።

ዛሬ በካርታ ተከልለው ሁለት የጎረቤት አገራት የሆኑት እነዚህ ህዝቦችና መንግስታት በጥንቱ ዘመን አንድ በነበረው ግዛታቸው በአንድ አይነት ስም ሲጠሩ ያሳለፉ ናቸው። ልዩነታቸው በኑብያ በኩል ኩሾች መበርከታቸው፤ በአክሡሙ በኩል ሴማውያን መበርከታቸው ሲሆን፤ በባህል፣ በልማድ፣ በቋንቋና በአምልኮ ላይ የተመሠረተ ሆኖ እናገኘዋለን። ይህም ሲባል የናፓታና የመርዌዎቹ ከግብፅ እንደመዋሃዳቸው መጠን

ቋንቋና ባህል ወግና ልማድ አምልኮና መሠል ነገሮቻቸው ከግብፅ ጋር የተወራረሠ ነው። በአክሡም በኩል ደግሞ ከደቡብ አረብ እንደመዋሠናቸው መጠን የተጠቀሡት ነገሮች ከደቡብ አረብ የሚወራረሡ ናቸው። ደቡብ ዓረብ ስንልም

በየመን አድርገው ቀይ ባህርን ተሻግረው የገቡ ያልናቸውን የሴም ዘሮችን መሆኑ ነው። ይህ በእንዲህ እንዳለም ዓረብ ስንል ከእስልምና በፊት ቦታን፣ ከእስልምና በኋላ የሀይማኖቱ ተከታዮች የሰፈሩበትን ቦታ መወከል መጀመሩን አንዘንጋም። በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ የሚነገሩ ቋንቋዎች በምሁራኑ እይታ በ3 የተከፈሉ መሆናቸው ይታወቃል።

1. የኩሽ ቋንቋዎች፦ አገውኛ፣ ቤጂኛ፣ ብሌን፣ ሀድያኛ፣ ከምባትኛ፣ ደራሲኛ፣ ኮንሶኛ፣ ሲዳምኛ፣ ሳሆኛ፣ አፋርኛ፣ ሱማሊኛና በሠፊው ኦሮምኛ የሚገኙበት ሲሆን፣ በጠቅላላው 23 ያህል የኢትዮጵያ ብሄረሠቦች የኩሽ ቋንቋ ተናጋሪዎች ናቸው።
2. የኦሞ ቋንቋዎች፦ 16 ያህሉ የኢትዮጵያ ብሔረሠቦች የሚናገሩበት ቋንቋ ሲሆን፣ ከነዚህ መካከል ከፋኛ፣ ጃንጀሮኛ፣ ወላይትኛ፣ሽናሽኛ፣ ጊሚርኛ፣ ኮሉኛ (ኮንታ)፣ ማጂኛ፣ ዶርዜኛ ይገኙባቸዋል።
3. የሴም ቋንቋዎች፦ አማርኛ፣ ትግረ፣ ትግርኛ፣ አርጎብኛ፣ ጉራግኛ፣ ጋፋትኛ፣ ሐረርኛን ጨምሮ አስራ ሠባት ብሔረሠቦች የሴም ቋንቋ ተናጋሪዎች ናቸው ተብሎ ተዘርዝሯል። በዚህ መሰረት ስለ ልዩነት እና ስለአንድነት ስናነሳ ለምሣሌ በአፄ ዮሃንስ 4ኛ ዘመን "ንጉሠ ነገስት ዘኢትዮጵያ" ተብለው የነገሡትና የሚታወቁት ራሣቸው አፄ ዮሐንስ ነበሩ። መቀመጫቸውም መቀሌ አድዋ ነበር። ልክ በዚያው ዘመንም አፄ ምኒልክ የሸዋ "ንጉስ" ነበሩ። አፄ ምኒልክ የሸዋ ንጉስ ቢሆኑም ግን ለማእከላዊው መንግስት መገበራቸው አልቀረም።

የንጉስ እና የንጉሠነገስትን ልዩነት ሳንዘነጋ፤ እነዚህ ሁለት ነገስታት የሚያስተዳድሩት ህዝብ በቋንቋ፣ በባህል፣ በጂኦግራፊ፣ እንዲሁም በሌሎች ዘርፈ ብዙ ነገሮች የተለያየ ህዝብ ነበር።.. በብሔርም እንዲሁ።

ሁለቱም የየራሣቸው ሠራዊት ነበራቸው። ሁለቱ ነገስታት እንዲሁም የሚያስተዳድሩት ህዝብ ግን በአንድ ኢትዮጵያ ስር የሚካተቱ ናቸው። የሚገናኙት በአመትም በሁለት አመትም፣ ወይም ጦርነት ሲኖር፣ አሊያም በሌላ ጉዳይ ብቻ ነበር። ሊሳው ቀርቶ ምኒልክና ዮሃንስ በብሄርም/እናት ቋንቋቸው አንድ መሆኑን ሣንዘነጋ/ በሚናገሩት ቋንቋም ልዩነት ነበራቸው። ከመሐላቸው አንዱ ከገነነ የበላይነቱን በሃይል ይይዛል። ሊላውም ተነስቶ የንጉሠነገስትነቱን ስልጣን ሊነጥቅ ይችላል፣ የመናገሻ ከተማውንም ሊለውጥ ይችላል.. ወዘተ። ነገር ግን ግዛቱ አንድ



ወጥ ሆኖ በኢትዮጵያ ስም የሚጠቃለል ነው። በዚህ መሠሉ ቀላል ምሣሌ በቀላሉ አንድነታቸውን እያሠብን መቀበል እንችላለን። በአንድነታቸው ውስጥም ልዩነታቸውን። ይህ እውነታ በዛርታ ተከልሎ እስኪለያዩ ድረስ የቆየ መሆኑንም እንዲሁ።

በጥቅሉ የናፓታና የአክሡም አገሮች በአገር ጉርብትናም በዘርም የሚገናኙ በየተራ ገናና መሆን የቻሉ ወንድማማቾች ናቸው። ‹‹ሁለቱ አገሮች በመጀመሪያ ናፓታ፣ ቀጥሎ መርዌ በገነኑ ጊዜ በአክሡም ዙሪያ የሚገኘው አገር ለእነርሡ መገበሩ፤ አክሡም በገነነ ጊዜ ደግሞ አብርሃ/ኢዛና/ ከነተከታዮቹ ኑብያን/ /ናፓታንና መርዌን/ መግዛታቸው የተረጋገጠ ነውና ይህን መሠሉ የእርስ በርስ መገዛዛት አንድነታቸውንም ጭምር ያሣያል።›› ( ተክለፃድቅ መኩሪያ 1965 ዓ.ም)

ኢትዮጵያ ሲባል ደግሞ በጥንቱ ዘመን ከግብፅ በደቡብ፣ ከኤርትራ ባህር ወደ ምዕራብ እስከ አትላንቲክ ድረስ ያለውን ግዛት ያጠቃልል ነበር። በአንዳንድ ፀሃፍት ዘንድም ምስራቁ ኢትዮጵያ ምዕራቡ ኢትዮጵያ ተብሎ ተገልፆ ይገኛል።

ምንም ቢባል ግን ከኑብያ እስከ ላዕላይ ግብፅ፣ ከኤርትራ ባህር ወዲህና ወዲያ እስከ አሁኑ የመን ድረስ የሚያጠቃልለው ግዛት ኢትዮጵያ ተብሎ የሚጠራ ወጥ የሆነ ግዛት ነበር...። በአጭር አነጋገር የአሁኗ ኢትዮጵያ ላይ ኤርትራን፣ ሱዳንንና የመንን መጨመር ማለት ነው።.... ስለዚህ ልዩነታቸውንና አንድነታቸውን ስናይ፤ ልዩነታቸው ጠባብ፣ አንድነታቸው ሰፊ ሆኖ እናገኛቸዋለን።

## ምዕራፍ ፫

## ኢትዮጵያ በታላቁ መፃህፍ

በዚህ ምዕራፍ አባ ጋስፓሪኒ ገብረማርያም ጥቂት ያግዙናል።

"በኦሪት ዘፍጥረት ምዕ 2 ቁ 13 ለመጀመሪያ ጊዜ ኩሽ የሚለውን ቃል የኢትዮጵያን ምድር የከበበው የትልቁ ዠማ የግዮን ነገር በሚነገርበት ላይ እናገኘዋለን" ይሉናል። "... የሁለተኛውም ስም ግዮን ነው እርሡም የኢትዮጵያን ምድር ሁሉ ይከብባል" የሚለውን ማስታቸው ነው።

- በኦሪት ዘፍጥረት ም10 ቁ 7 ላይ የካም ልጆች ኩሽ፣ ሚዝራም ፋጥና ከነዓን ተጠርተዋል"ም ይሉናል።
- "በኦሪት ዘኁልቁ ም12 ቁ 1 ማርያምና አሮን በሙሴ ሚስት በኢትዮጵያዊቷ ላይ መናገራቸው ይገኛል "ሙሴም ኢትዮጵያይቱን አግብቶአልና።" ይላል።
- መዝሙረ ዳዊት ም67 ቁ 31 " መኳንንት ከግብፅ ይመጣሉ፣ ኢትዮጵያ ወደ እግዚአብሔር እጆቿን ትዘረጋለች።"
- መዝሙረ ዳዊት ም86 ቁ 4 "እነሆ ፍልስጤማውያን ጢሮስም የኢትዮጵያም ህዝብ እነዚህ በዚያ ተወለዱ"
- 2ኛ ዜና መዋዕል ምዕ. 12 ቁ 3 የሠለሞን ልጅ ሮብዓም ታማኝነቱን አጉድሎ በአምልኮ ባእድ ወደቀ የሚል ቃል ይተርካል። በዚያን ጊዜ አምላክ የግብፅን ንጉስ ሴሳቂምን አስነስቶ እርሡም የልብያን የትሮግሎዲትንና የኢትዮጵያ ወታደሮችን ጨምሮ አስከትሎ እየሩሣሌምን ይዟታል። "የኢትዮጵያ ሠዎችም ነበሩ" ይላል።
- በዚሁ መፅሃፈ ዜና ም21 ቁ 16 የዓረብ ወሠንተኞች የሆኑ ኢትዮጵያውያን ዝና ባጭሩ ይተረካል "የፍልስጤማውያንና በኢትዮጵያውያን አጠገብ የሚኖሩትን የዓረባውያንን መንፈስ በኢዮራም ላይ አስነሣ።"
- ትንቢተ አሞፅ ምዕ 9 ቁ 7 "የእስራኤል ልጆች ሆይ እናንተ ለኔ እንደ ኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁምን? ይላል እግዚአብሔር" ይላል። እዚህ ላይ የአባ ጋስፓሪኒን ትንታኔ እንስማ። "በአሞፅ ትንቢት ላይ ስለ ኢትዮጵያ የሚናገር እጅግ የሚያስደንቅ ነገር እናገኛለን። ክክ.ል በፊት 750 ላይ ቀድሞ ትንቢት የተናገረው አሞፅ "እናንተ የእስራኤል ልጆች ለኔ እንደ ኢትዮጵያውያን ናችሁ" ይላል እዚህ ላይ የተናገረው የመለኮታዊ ቃል አነጋገር በጣም ግልፅ ነው። እግዚአብሔር ኢትዮጵያውያንንና የተመረጠውን ህዝብ እስራኤልን በአንድ አይነት ፍቅር አፈቅራቸዋለሁ ይላል። ይህም ደግሞ ኢትዮጵያ በእምላካዊው ፍቅር ለመወደዷ የሚመሠክር ፅኑ የሆነ ምስክር ነው።" ይሉታል።



ስለ ኢትዮጵያ ደጋግሞ የሚያነሣው ኢሳያስ ነው። ኢሳያስ በትንቢቱ ኢትዮጵያን ሲያነሣ የጠራቸው የኢትዮጵያ ነገስታት በኑብያ ናፓታ የነገሡ መሆናቸውን ስናስብ የኑብያና የአክሡም ኢትዮጵያ ተጠቃለው በአንድነት መጠራታቸውን እናረጋግጣለን።

ኢሳያስ የነበረበት ዘመን ቅ.ል.ክ 730-690 ባሉት ጊዜያቶች ነው። ይህ ታላቅ ነብይና ትንቢተኛ ምድር ላይ በነበረ ጊዜ ደግሞ የኢትዮጵያ ነገስታት መቀመጫ ናፓታ ነበረ።

- ትንቢተ ኢሣያስ ም 45 ቁ 14 "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። የግብፅ ድካምና የኢትዮጵያ ንግድ ቁመተ ረጅሞችም የሳባ ሠዎች ወደ አንተ ያልፋሉ ለአንተም ይሆናሉ..."

የአባ ጋስፖሪኒ መፅሃፍ እንዲህ ይላል" የግብፅ ስራዎች የኢትዮጵያ የንግድ እቃዎችና ረጅም ቁመት ያላቸው ሳባውያን ወደ አንቺ/እየሩሣሌም/ ያልፋሉ ያንችም ይሆናሉ። እጃቸውን አጣምረው ይከተሉሻል፣ እጅ ይነሡሻል፣ ልመናቸውንም ያቀርቡልሻል፣ ስለምን? ባንቺ ብቻ አምላክ ስላለ፣ ካንችም ውጪ ስለሌለ ነው" ይላል ይሉናል።

- በምዕ 43 ቁ 3 "ግብፅን ላንተ ቤዛ አድርጌ ኢትዮጵያንና ሣባንም ለአንተ ፋንታ ሠጥቻለሁ..።" ይላል።
- ትንቢተ ሶፎንያስ ም2 ቁ 12 "እናንተ ኢትዮጵያውያን ደግሞ..." ሲል ያነሣናል። ም3 ቁ 10 ላይ " ከኢትዮጵያ ወንዞች ማዶ" ተብሎ ተጠቅሷል።

ሌላው ቅ.ል.ክ ከ626-587 የነበረው ኤርሚያስ ኢትዮጵያን ሁለት ጊዜ ይጠራል። ትንቢተ ኤርሚያስ ምዕ 13 ቁ 23 "በእውኑ ኢትዮጵያዊ መልኩን ወይስ ነብር ዝንጉርጉርነትን ይለውጥ ዘንድ ይችላልን?"

- አሁንም ኤርሚያስ በትንቢቱ ምዕ 38 ቁ 7 "በንጉሡም ቤት የነበረው ጃንደረባ ኢትዮጵያዊው አቤሜሌክ ኤርሚያስን በጉድጓድ ውስጥ እንዳኖሩት ሠማ።... ንጉሡም ኢትዮጵያዊውን አቤሜሌክን ከአንተ ጋር ሠላሣ ሠዎች ከዚህ ውሠድ፤ ነቢዩም ኤርሚያስ ሳይሞት ከጉድጓድ አውጣው ብሎ አዘዘው.." የሚል ሁተታ ሰፍሯል በትንቢተ ህዝቅኤል በምዕ. 30 ደግሞ "ኢትዮጵያና ፋጥ" ተብሎ ሠፍሯል። (ቅ.ል.ክ 590)
- ትንቢተ ኢሣያስ ምዕ 18 "በኢትዮጵያ ወንዞች ማዶ ላለች፤ ክንፍ ያላቸው መርከቦች ላሉባት፤ መልዕክተኞችንም በባህር ላይ፤ የደንገል መርከቦችንም በውሃ ላይ ለምትልክ ምድር ወዮላት! እናንተ ፈጣኖች መልእክተኞች ሆይ፤ ወደ ረጅምና ወደ ለስላሣ ህዝብ፤ ከመጀመሪያው አስደንጋጭ ወደ ሆነ ወገን፤ ወደሚሠፍርና ወደሚረግጥ፤ ወንዞችም ምድራቸውን ወደ

ሚከፍሉት ህዝብ ሂዱ። በንሏም የምትኖሩ ሁሉና በምድር የምትቀመጡ ሆይ፤ ምልክት በተራሮች ላይ በተነሣ ጊዜ እዩ፤ መለከትም በተነፋ ጊዜ ስሙ።" ይላል።

በአባ ጋስፖሪኒ የኢትዮጵያ ታሪክ መፃህፍ በገፅ 13 እንዲህ ይብራራል። ከአብራይስጡ እንዳለ ተርጉመው ያሠፈሩት ነው።

"የአክናፍ ጨኸት የሚሠማባትና (ግብፅ) ከኩሽ ኸሮች ወዲያ ያለች (ኢትዮጵያ) አገር፤ ከፓፒሩስ በተሠራ ታንኳዋ መልዕክተኞቿን በባህር ውሃ ላይ የምትልክ ምድር፤ ወዮላት! ፈጣኖች መልእክተኞች ሆይ ቁመተ ረዣዥም፣ መልክ ጠይም፣ (ቆዳቸው ወደሚያብለጨልጩ) ወደ ሆኑት፤ እጅግ በጣም ሩቅ የሆኑትን አገሮች ሁሉ ወደሚያስፈሩት፤ ሃያላን በመሆናቸው ሁሉን በእግራቸው ወደሚረግጡት፤ አገራቸውን ዥሮች (ወንዞች) ወደተለሟት (ወደፈረፈሯት) ህዝብ ተመለሱ ይላል። ይህ በነቢዩ አፍ የተነገረው ሁናቴዋን የሚያስታውቀው የአምላክ ቃል ለኛ ክብሯን፣ ሃይሏንና፤ ስልጣኗን የኢትዮጵያንም ስመ ጥርነት ያስረዳናል" ይሉናል። ይህ ምክር ለኢትዮጵያዊው ንጉስ ለሻባካ የተነገረ ነበር። በአሶር ንጉስ ላይ ተባባሪ እንዳይሆን ለማስታወቅ።

በምፅ 37 ቁ 9 ደግሞ "ትልቁ የኢትዮጵያ ንጉስ ቲርሃካ በአሶር ንጉስ በሰናክሬብ ላይ ሊዘምት ነበር" ይላል።

ዳንኤልም በትንቢቱ ንጉስ አንጥያኮስን "በግብፅ፣በሊቢያና በኢትዮጵያ ላይ መዝመቱን" ይናገራል።

ከግብፅ፣ ከአሶር፣ ከኢየሩሳሌም፣ከጢሮስ.. ወዘተ በዚያ ዘመን ሃያል ከተባሉ አገሮች ተርታ ኢትዮጵያ ከነንግስታቷ ስም ስትጠራ በደንብ እናያለን። በተለይ በነፒያንኪ፣ ሻባካ፣ ቲርሃካ፣ታንታሙን ጊዜ በተደጋጋሚ ተነስታለች። ወደፊት እንደምናየውም እነዚህ ታላላቅ ነገስታት በታላቁ መፃህፍ ስለተጠቀሱ ብቻ ስራቸውን በቁፋሮ ከተገኙ ሐውልቶችና የሃውልት ላይ ፅሁፎች በመተርጎም ተመራማሪዎች ይፋ አድርገውታል። በታላቁ መፃህፍ አገላለፅ እነ ሻባካ፣እነቲርሃካ "የኢትዮጵያ ነገስታት" ተብለው በግልፅ ተቀምጠዋል። የኋለኞቹ የታሪክ ተመራማሪዎች ቢያንስ "የቀድሞ የኢትዮጵያ ነገስታት" ብለው ለመጥቀስ አልደፈሩም። አገር በስዕልና በካርታ በተከለለ ቁጥር ታሪክ መካፈል ይቻል ይሆን?



# ምዕራፍ ፱

## የግብፅ ስልጣኔ

ማኔስ የተባለው የግብፅ የመጀመሪያው ፈርኦን ቅ.ል.ክ 3200 ላይ ተበታትኖ የሠፈረውን ህዝብ ገሚሡን በማስተባበር፣ የቀረውን በሃይል በመጠቅለል ከሁለት የተከፈለውን ህዝብ አንድ በማድረግ የመጀመሪያውን ዳይናስቲ መሠረተ።

ከኑብያ ኢትዮጵያ የሚዋሡኑት በአሞንና በአባብ ሲያመልኩ፤ በታህታይ ግብፅ የሠፈሩት ደግሞ "አዚት" በምትባል በሴት አንቀፅ በምትጠራ አባብ ያመልኩ ነበር። የእነዚህ አማልክት ካህናት አንድነት መስርተው እንደተለመደው ህዝቡን ማስተዳደር ጀመሩ። በቀደመው ዘመን የግብፅ ፈርኦኖች ተጠሪነታቸው ለአማልክቱ ካህናት ነበር። ማኔስ "አማት" ላይ መቀመጫውን አድርጎ በግብፅ በሠፈሩ ህዝቦች ላይ ከነገሠ በኋላም ተከታታይ ዘሮቹ እየተተኩ ጥቂት ዘመን ገዙ።

በኋላም "የወንዶቹ ወንድ" የሚል ትርጓሜ ያለው "ካካኡ" የተባለ የጦር አለቃ ዙፋኑን ከማኔስ ዘር ቀምቶ ሁለተኛውን ስርወመንግስት መሠረተ። በካካኡ ዘመን ብዙ አይነት አምልኮ ተስፋፋ። ዋናው በሠው አምሣያ የሚቀረፀው "ኘታህ" እና የእርሡ ማደሪያ የሆነው "አፒስ" ወይም ሐፒ የሚባለው ኮርማ ነው።

ለጥጃ በላይ ከበሬ በታች የሆነ ኮርማ ይፈለጋል። ጥቁር ቦታ የሆነ፣ ግንባሩ አካባቢ ነጭ ሆኖ ነጩ ክፍል ሶስት ማዕዘን ያለው፣ደረቱ ላይ የሩብ ጨረቃ አይነት ቅርፅ ኖሮት ነጭ ቢሆን፣ ከወደ አፉ የጢንዚዛ ቅርፅ ከያዘ እሡ አምላክ ነው ይባላል። መረጣውን የሚያከናውኑት ካህናቱ ናቸው። የተጠቀሠውንና ያልተጠቀሡትን አይነት መመዘኛዎች ያሟላ ጥጃ ከውልደቱ ጀምሮ ይታደንና ከተገኘ "ኘታህ አድሮበታል" ተብሎ ስለሚታመን ጥጃውን ወስደው ያሣድጉታል። አድጎ ኮርማ ሲሆን የተቀደሠ ውሃ በሚባለው ቦታ ወስደው ይነክሩታል ወይም ያጠምቁታል። የአምላክነት ክብር ሠጥተው ይቀድሡታል። በቤተመቅደስ አስቀምጠው ይሠግዱለታል። በህይወት ዘመኑ ሁሉ ዓመታዊ ክብረበዓላቶች ይከናወኑለታል። ሲሞት በታላቅ የቀብር ስነስርዓት ከመሠል አምላክ ወንድሞቹና ከነገስታቱ ጎን ይቀበራል። እንደገና ሌላ ይመረጣል።

የዚህን አይነቱን ኮርማ ምስል በተለያዩ በድንጋይ፣ በብረት፣ በነሃስ፣ በብር፣ በወርቅ ተቀርፆ ይሠራና ደስ የሚል አብረቅራቂ ጨርቅ ደርበው ላይ ይለብሣል... ወዘተ።

ይሄ የጥጃ አምላክ ለረጅም ሦስት አመት በግብፅ ሆኖ የቆየ ነበር።ነገር ግን የቀድሞዎቹ የአሮጌው ስልጣኔ ፀሐፊዎች እንስሣውን፣ዛፉን

ወይም አሞራውን እባቡን እንዲሁ ራሁን ብቻ ያመልኩትና ይቀርፁት እንዲሁም ይሠግዱለት ነበር እንጂ ማደሪያው የሆነውን "ሥውን" አሳዘጋጁም ነበር።

በኋላ ግን የሥው ማደሪያ ያለውን አሞንን በላእላይ ግብፅ በቴብ ቤተመቅደሡን ሠርተው ማምለክ ከጀመሩ በኋላ ግብፅ ራሷን የቻለች አገር ሆና ስትመሠረትና ላእላይ ግብፅን ስትጠቀልል የአሞንን ቤተ መቅደስና አምልኮውንም ልትወርስ ችላለች።

በኋለኛው ዘመን ከ1700-1300 ቅ.ል.ክ እስራኤሎች በግብፅ በተገዙ ጊዜና ከ400 አመት በኋላ በሙሴና በአሮን እየተመሩ ወደ አገራቸው ሲሄዱ እስራኤላውያን ጥጃ ቀርፀው ያመለኩትና ሙሴን ያበሣጩት፣አምላካቸውንም ያስቆጡት በፕታህ/በኮርማው/ አምሣል እንደነበር ይታወቃል።

ከዚህም ባለፈ በጥንቱ ዘመን በግብፅ ተዘርዝረው የማያልቁ ልዩ ልዩ አማልክት ነበሩ። እስከዚህ ዘመን ድረስም አሞን እጅግ አልገነነም ነበር። ፕታህ ከኋላው ተነስቶ በልጦት ነበር ማለት ነው። "ከ2ኛው ስርወ መንግስት በኋላ እስከ 10ኛው ስርወ መንግስት ድረስ ከ2980-2060 ቅ.ል.ክ ድረስ ብዙ ነገስታት ሲያልፉ የውስጥ አስተዳደራቸውን ከማደራጀት ጥበባቸውን ከማስፋፋት በቀር ግዛት ለማስፋፋት ገና አልተቀሰቀሡም፤ ትንሽ በምስራቅ በኩል እስከ ሲና ተራራ ድረስ ሄደው አስገብረዋል" (ተክለፃድቅ መኩሪያ 1965 ዓ.ም)

ግብፃውያን ግዛት ማስፋፋት ሳይጀምሩ ገና የሠሯቸው ስራዎችም በተለይ ከ3ሺ. አመት ጀምሮ የቀን ቀጠራውን ካላንደር ከማዘጋጀት ጀምሮ የተለያዩ የቤተመንግስት አደረጃጀቶችን፣ የግብር አሠባሠብ ስልትን፣ የጦር አደረጃጀትን፣ ቢሮክራሲውንና መሠል ነገሮችን ሲያደራጁ ቆይተዋል።
በተለይ በ4ኛው ዳይናስቲ የፒራሚድ ግንባታውን ጨምሮ በርከት ያሉ የምህንድስና ጥበቦች ሊታዩ ችለዋል።

በግብፆች አጠራር "ኩው" /khouwou/ በግሪኮች "ቼዮፕስ" (CHEOPS)የተባለው የ4ኛው ዳይናስቲ አንዱ ንጉስ በሕይወቱ እያለ ያሠራው መቃብር ቤት ከሁሉ የበለጠ መሆኑን ፀሃፍት አረጋግጠዋል።

ይህ ፒራሚድ 2 ሚሊዮን 300 ሺ. ድንጋይ በሥው ትከሻ እየተጋዘ የተሠራ ሲሆን፤ ከመሠረቱ ውጪ ቁመቱ 146 ሜትር እንደሚደርስ የፖልፒዬሪ መዝገበ ቃላት ያሣያል።

100 ሺ. የሚደርሱ ባሮች በምሬት እንዳያመልጡ አንገታቸው በገመድና በሠንሠለት ተሳስሮ ራቁታቸውን ሆነው ከኋላ ገራፊ ተዘጋጅቶ በጅራፍ እየተገረፉ ያቀላጠፉት ግዙፍ ህንፃ ነው። አንድ ሠው አንድ



ሜትር ኩብ ድንጋይ ባንድ ጊዜ ይሸከም ነበር። ስራው 20 አመት እንደሌሎች 40 አመት ፈጅቷል።

ነገስታቱ ሞተው ሲነሡ ሲኖሩበት የፈለጉት ቤት እንደመሆኑ መጠንም ተቀብረውበትም በዘበኞች ይጠበቃል፤ አገልጋዮችም ተመድበው ንብረቱ ሁሉ ተቀምጦበት ይገኝ ነበር።

ከ1ኛ እስከ 10ኛው ዳይናስቲ ድረስ የነበሩት ዋና መቀመጫ ከተማ መምፌስ/ታህታይ ግብፅ/ ነበረች። አምላካቸውም ፕታህ ነበር። ከ11ኛው ዳይናስቲ ጀምሮ ግን መምፊስ ጣል ጣል እየተደረገች ቆይታ ከ13ኛው ዳይናስቲ በኋላ የመምፊስ ገናናነት ወደ ላዕላይ ግብፅ ወደ ቴብ ዞረና የፓታህ አምላክነትና ገናናነትም ወደ አሞን እየዞረ ሄደ።

የቀድሞውን የአሞን ቤተመቅደስም አፍርሠው ሌላ እጅግ ያማረ መቅደስ ገንብተው "የሠማይና የምድር ፈጣሪ፣ዘላለማዊ የሆነ አንድ አምላክ" ብለው እነ ሴት 1ኛ፣ እነ አሚኖፊስ 3ኛ መቅደሡን ገንብተው መንበረ አሞን/የአሞን መቀመጫ/ አደረጉና ፕታህ ምክትል አምላክ ሆነ።

141 ክፍሎች ያሉት 102 X51 ሜትር የሆነውና ዛሬ ድረስ ፈራርሶም ቢሆን የሚታየው ይህ መቅደስ የተሠራው ቅ.ል.ክ 1400-1300 ባለው ጊዜ ነበር። ይህ ዘመን ማለት ደግሞ ወደ ፊት እንደምናየው ግብፅ የኑብያ ኢትዮጵያን ቅኝ አድርጋ በሃይል የያዘችበት ዘመን ነበር።

በ12ኛው ዳይናስቲ ሳኑስትሪ (በግብፆች አጠራር) በግሪኮች ሴሶስትሪ የሚባሉት በየተራ በነገሡ ጊዜ ነበር አብርሃም ከዑር ከለዳውያን ወደ ግብፅ የተሠደደው። (ቅ.ል.ክ 2000-1800) በእነዚያ በ12ኛው ዳይናስቲ በተከታተሉ የግብፅ ፈርኦናት ጊዜም ግብፅ ከነበረው የበለጠ የሃውልት፣የቤተመቅደስ፣ የመንገድ፣ የዘመናዊ የውሃ ቦይ... ስራዎች ተስፋፍተው እየተሠሩ በምዕራብ ሊቢያን፣በምስራቅ የሲናን አገር እየወጉ አስገበሩ። ወደ ደቡብም ዘልቀው እስከ ኑቢያ ሁሜን ደረሁ። እስከ 1700 ቅ.ል.ክ የ13ኛው ዳይናስቲ ነገስታት ቴብን የመናገሻ ከተማ ሲያደርጉ ነው ሁለት ታላላቅ ከተማ ሲኖራቸው የቻለው። ቴብ እና መምፊስ። ነገር ግን እንዲህ በገነኑ ጊዜ ቅ.ል.ክ 1680 "ሂክሶስ" በሚል መጠሪያ የሚታወቁ ነገዶች መጥተው የግብፆችን ነገስታት ገልብጠው አገር ያዙ። እነዚህ ሂክሶሥ የተባሉት እነማን እንደሆኑ ውሣኔ ላይ ባይደረስም" ኢትዮጵያውያን መሆናቸው በብዙ ቦታ ተጠቅሶ ይገኛል። ግዛታቸውም ለድፍን 100 አመት የቆየ ነበር። የሠሜኖቹ ኢትዮጵያውያን ናቸው ከሚሉት ውስጥም ጀምስ ብሩስ ይገኝበታል። ይህ ሰው "ወደ ኑብያና ወደ ሐበሻ ጉዞ" በተሠኘ ፅሑፉ "የሂክሶስ ዘሮች በኢትዮጵያ ነገደ ዮቅጣን የተባሉት ናቸው" በማለት አስረግጦ ይገልፃል።

አንዳንድ ያገራችን ፀሃፍትም ሠሜኑ ኢትዮጵያ ለ100 አመት የሀል ባዶና ሠው አልባ ሆኖ ቀይቶ ነበር በማለት ህዝቡ ከ1680-1580 የት ሄዶ ነበር? በማለት ይጠይቃሉ። የሆነ ሆኖ ሂክሶሶች ለ100 አመት ግብፅን ገዝተው በ14ኛው ዳይናስቲ ተካተው ይገኛል። ብዙ የስልጣኔ ስራ እንደሠሩም ይነገራል። ስማቸውም (የነገስታቱ) የብዙዎቹ በሃውልት ላይ ተገኝቷል። "አፒፒ" ይባላል።

የአብርሃም የልጅ ልጅ የያዕቆብ ልጅ ዮሴፍ ወንደሞቹ ሸጠውት የመጣውና የታሠረው፣ በህልም አፈታት ምክንያት ተፈትቶ እንደራሴ የሆነውም፣ አባቱን ያዕቆብንም ከነቤተሠቡ ከከነዓን ወደ ግብፅ ያስመጣው በነዚሁ በሂክሶሶች ነገስታት ዘመነ መንግስት ጊዜ መሆኑ የተረጋገጠ ነው።

ታላቁ መፃህፍ በሃዋርያት ስራ ም7 ቁ 17-19 "የእስራኤል ህዝብ በምስር/በግብፅ/ በረከተ፣ ሌላ ንጉስ ዮሴፍን የማያውቅ እስኪነሣ ድረስ ይህ በዘመዶቻችን እየደረሠ ያለው ስለዚህ ነው.."የሚለውም ቀደምት ፈርኦኖች በሌላ ነገስታት መባረራቸውን ያስረዳል። የግብፅ ህዝብ ምንም እንኳ የሂክሶሥ ነገስታት በርካታ ስራዎችን ቢሠሩም በፀጥታ ሲገዛ አልፈለገም። አመፅ በረከተ።

ስለዚህ የቴብ የአሞን ካህናት ከላዕላይ ግብፅ ሹማምንት ጋር ተስማምተው ሳቅኑሪ 1ኛ የተባለውን ግብፃዊ መሪ አድርገው "አፒፒ 3ኛ" የተባለውን ከሂክሶሥ ወገን የሆነ ፈርኦን በነገሠበት ዘመን ውጊያ ጀመሩ። ሳቅኑሪ1ኛ ተሸንፎ ተባረረ። አሁንም ውጊያው ቀጠለ። እናም ከ1680-1580 ድረስ የቆዩትን ነገስታት በአህሞሲሥ መሪነት ከግብፃውያን ተወላጆች ጋር በመተባበር በሽሽት ያለው ሠራዊት ተደራጅቶ በመግጠም ሂክሶሶችን ማሸነፍ ተቻለ። እነርሡም ከነህዝባቸው ተበተኑ። ግማሹ ወደ ምስራቅ የቀረው በየመንገዱ በከነዓን አገር ተበተኑ።

ቀዳማዊ አህሞሲሥ ድል አድርጎ ስልጣን ከያዘ በኋላ ሂክሶሶች የመሠረቷቸውን አዳዲስ አምልኮ ጣኦቶችን እያፈራረሠ የቀድሞዎችን እየተካና እያደሠ በደንብ አሠራው። ከዚህ በኋላ ነው ግብፃውያን እንደአዲስ ተደራጅተው አገር መውረርና ግዛት ማስፋፋት የቻሉት።

የግብፅ ጦር ሠራዊት የሞዓባውያንን፣ የኢዶማውያንን፣ የፍልስጤማውያንን፣ የሂቲትን (ፓለስታይንን)፣ የዓረባውያንን ሠሜናው ክፍል ሁሉ፣ ከአሶርና ከባቢሎን በስተቀር ታናሽ እስያን/ቱርክን/ የኑብያ ሠሜኑን በሙሉ ወግተው እያስገበሩ በየአገሩ የሚገኘውን ወርቅ፣ ብር፣ መዣሪያና ልዩ ልዩ ሀብት በዘረፋም፣ በግብርም እየሠበሠቡ የግብፅን ቤተ መንግስት በሃብት አጥለቀለቁት። ነገስታቱ ሁሉ ነገራቸውን በወርቅ ማሠራት የጀመሩበት ዘመንም ይህ የአህሞሲስ ዘመን ነበር። ከአህሞሲስ በኋላም "ቱትሞሲስ" በሚለው ስም 3 ነገስታት የተከታተሉ ሲሆን፣



በቱትሞሲስ 3ኛ ጊዜ ግብፅ የዓለም አገሮች የበላይ የሆነችበት ዘመን ነበር።

"ባለታሪክ ኢትዮጵያ" የተሠኘው መፅሃፍ "ቀዳማዊ ቱትሞሲስ በነበረበት ዘመን በሞሶፖታሚያ ውስጥ የነበሩትን አሶራውያንን ባቢሎንን ድል በመምታቱ ስሙና ዝናው የገነነ ነበር" ይለናል። እናም "አቢዶ" በተባለው ታላቅ ቤተ መቅደሡ ውስጥ የተገኘው ዕሁፍ "የሌሎችን ውጤት ጨምሬያለሁ፤ ከኔ በፊት በነበሩት ነገስታት ጊዜ የነበሩት አማልክት በደንብ ተመልክባቸዋል፤ መቅደሣቸውም በጥሩ ሁኔታ አሸብርቀው ታይተውላቸዋል። የግብፅን ዳር ድንበር ፀሃይ እስከምትደርስበት ድረስ ከማስፋቴ በላይ ግብፅን ከሌላ አገር የላቀች አገር አድርጌያታለሁ" ይላል።

ስለዚህም ግብፃውያን ከድንጋይ ዘመን ወደ ወርቅ ዘመን የተሸጋገሩት ከ16-15ኛው መቶ አመት ቅ.ል.ክ ሲሆን፤ እስከዚህ ዘመን ድረስ ኢትዮጵያውያንን ለማስገበር ደፋ ቀና ሲሉ ነበር እንጂ ተሣክቶላቸው አልያዟትም። ከዚህ ዘመን በኋላ ግን ለ300 አመት ያህል ልንገብርላቸው ግንገደድ አንቀርም። ከዚያ በፊት ግን ስለወንዛችን ስለ ዓባይ ቀደምት ፀሃፍት ካሉት ተነስተን፣ ዛሬ ያለበትን ሁኔታም ጨምረን ጥቂት ነገሮችን እንይ።

<u>ዓባይ</u>

ከሚያምር አዳራሹ ወጥቶ በሠረገላ ተቀምጦ እየተንማለለ ግራና ቀኙ የደስታ ድምፅ ለሚያሠማው ህዝብ ፈገግታ እያሣዩ ለረጅም ዘመን እንደሚጓዝ መስፍን የዓባይም ውሃ ከአዳራሹ ከጣና ወጥቶ ለኑብያና ለግብፅ መሬት ህይወት እየሠጠ ከረጅም ጉዞ በኋላ ከቤተዘመዱ ከሜዲትራኒያን ባህር ይገባልና አረፍ ይላል። ይተኛልም። በጉዞው ወቅት ሁልጊዜ እግረ መንገዱን ለአሸዋማው ለግብፅ አገር የአፈር ስጦታ እንዳቀበለ ይኖራል። ለዚህ ውለታ ግብፃውያኑም፣ ኑብያዎችም ሣይቀሩ ለዓባይ የአምላክነት ደረጃ ሰጥተው በህይወት ላይ ህይወት ከምትጨምርላቸው ከፀሃይ እኩል እያመለኩ የንጭ በሬ መስዋዕት ሲያቀርቡለት ኖረዋል። ጥንታውያን ግብፆች ከኛ ይበልጥ ዓባይን በመውደድና በማክበር ያመልኩታል። ስሙን የአማልክቶቻቸው ካህናት ይኸውም ማለት የቀለም ሠዎች የሆኑት /የተማሩት/ "ሐፒ ቅዱስ ወንዝ" ሲሉት ያልተማሩት ህዝቦች ደግሞ "ኢቱር" ወይም እዑር ወንዝ ብለውት ይገኛል።

የግብፅ አገር ራሡ የደቡብና የሠሜን አገር እንደሚባለው፤ ንጉሡም የደቡብና የሠሜን ንጉስ እንደሚባለው፤ ዓባይንም የደቡብና የሠሜን ዓባይ ብለው ምስሉን ለምለም ነገር በራሣቸው ባሠሩ፣ በእጃቸው ለአማልክት የሚሠጥ የፍራፍሬ ስጦታ በያዙ ሠዎች ተስሎ ይታያል። አንዳንድ ጊዜም ብቻውን ይሣላል። (ከምስሉ 2ቱ በሉቨር ሙዝየም

የተቀመጡትን ተመልክቻለሁ ይሉናል የዚህ መፅሃፍ ዋነኛ ምንጫችን ክቡር ተክለፃድቅ መኩሪያ) እናም የአማልክቱ ካህናት ዓባይ ከአስረስ (በጎ አድራጊው አምላክ) ከንድ እየፈሠሠ ለፍጥረት ሁሉ ህይወትን የሚሠጥ ራሡ ከፀሃይ የሚወዳደር አምላክ ነው ብለው ለዚሁ ለበጎው ተግባሩና ለአምላክነቱ የሚገባ መዝሙር ያርሠውለት መዝሙሩን "ማስፒር" የተባለው ፈረንሣዊ ፀሃፊ ወደ ፈረንሣይኛ ተርጉሞታል።

የአማልክት አገር ከሚባለው ከኢትዮጵያ ከሚመነጨው ዓባይ ህይወታቸውን ደጅ የሚጠኑ የጥንት ከተሞች መርዌ፣ናፓታ፣ቴብ፣ሔሬክሊዮፖሊስ፣መምፊስ... በሚያልፍበት መንገድ ላይ ተኮልኩለው ይታያሉ። ከእነዚህ ውስጥ መርዌና ናፓታ የኑቢያ ኢትዮጵያ፣ሔሬክሊዮፖሊስ/ሄሌዎፖሊስ/ መምፊስ፣ የግብፅ ከተሞች ናቸው። "ባለመቶው በር ከተማ" ብሎ ሄሮዱተስ የሠየማት የቴብ ከተማ ግን በሁለቱ አገሮች መካከል ሆና የደከመ ግብፃዊ ፈርኦን ሲለቃት፣የበረታ ኢትዮጵያዊ ንጉስ ሲይዛት፣ እንደ ካምቤዝ /የሶርያ ንጉስ/ ጨካኝ የሆነ ወራሪ ሲያፈርሳት፣ከወረራ በኋላ በኢትዮጵያውያኑ ወይም በግብፃውያኑ ነገስታት መልሳ ስትሠራ የኖረች ናት። ቴብ መከረኛ ከተማ ነበረች። ለማንኛውም ግን ዓባይንና ምንጩን ለመያዝ ያላሠፈሠፈ ነገስታት አልነበረም። ዓባይ ያኔ አምላክ ተብሎ ይሠግድለታል፣ መስዋዕትም ይቀርብለታል፣ ይመለካል፣ በኋለኛው ዘመን ደግሞ የኢትዮጵያውያን ነገስታት ማስፈራሪያ ሆኖ በማገልገል "ዋ! ዓባይን ገድቤ ጉድ ሳላደርግህ ቶሎ ብለህ ጳጳስ ላክ!" እያሉ ጳጳስ ያስመጡበት ነበር።

*ዛሬ ደግሞ ዓባይ ከጳጳስ ማስመጫነት ወደ ሃይል ማመንጫነት እየተዛወረ ነው። ዓባይ.. ብዙ ነገር ነበር፣ ነውም፣ይሆናልም።*



## ምዕራፍ ፲

## የግብፅ ግዛት በኢትዮጵያ

ቅ.ል.ክ. ከ 2ሺ. ዓመት ጀምሮ በኢትዮጵያውያንና በግብፃውያን መካከል ፀብም፣ ፍቅርም ሲስተናነድ ኖሯል። ከ 1580 ወዲህ ግን ግብፆች እየገነኑ በመጣው ስልጣኔያቸው አማካኝነት ግዛት የማስፋፋት ፍላጎት አደረባቸው።

በቱትሞሲሥ 3ኛና በሌሎች ከእርሱ በፊት በነበሩት ፈርኦኖች ጊዜ ደግሞ የኢትዮጵያ ነገስታት የነበሩት እነ አሜንምሒት፣ እነ ጻውዕ በሰንጠረዡ ዝርዝር 17ኛና 18ኛ ላይ የሰፈሩት የኢትዮጵያ ነገስታቶች በዚያ ጊዜ የነበራቸው ሃይልና ጎናናነት ከግብፅ አንፃር ሲታይ ደካማ ነበር። እናም መመከት አልቻሉም።

ስለዚህ ከቱትሞሲስ 3ኛ በፊት የነበረው ፈርኦን /አህሞሲሥ/ የተባለው ከ 1580 እስከ 1557 ቅ.ል.ክ መካከል ባለው ጊዜ የኢትዮጵያን ወሰን እያለፈ መውጋትና መዝረፍ ጀመረ። ተከታዩ ፈርኦንም እንዲሁ ይበልጥ እየገፋ አገር ያዘ። ቀጥሎ የነገሰው ቱትሞሲሥ 3ኛ የተባለው ፈርኦን ደግሞ ከ 1500-1480 የነገሰው ማለት ነው ከእነርሱ በበለጠ ጦር እየላከ ኢትዮጵያን /ኑብያን/ አስያዘ።

በምስራቅ በኩል ብዙ አገሮች አስገብሮ ግብዕን አገነነ። በዘረፋና በግብር የሚገኘው እቃ፣ ብርና ወርቅ የግብፅን መንግስት አከበረው። "ወርቅ ባንተ ዘንድ እንደ አሸዋ ነውና እባክህን ላክልን" እያሉ የባቢሎን ነገስታት ይለምኑት ጀመር።

ሻምፖሊዮን የተባለው የፈረንሳይ ሊቅ የጥንቱን የግብፆችን ፊደል የአፈታት ሚስጢር እስኪገልጠው ድረስም እነዚህ የግብፅ ነገስታት በአገራቸው ውስጥና ከአገራቸው ውጭ የሠሩት በርካታ ታሪክ ተደብቆ ይኖር ነበር።ነገር ግን የፊደሉ ሚስጢር ከተፈታ በኋላ የጀርመን፣ የእንግሊዝ፣ የፈረንሳይና የአሜሪካ ሊቃውንት በቡድን በቡድን እየሆኑ ወደ ጥንታዊቷ ከተማ ወደ መምፊስ፣ ቴብ፣ ሉክሶር ፣ ካርናቅ እየሄዱ በየሃውልቱና በየቤተመቅደሱ፣ በየቤተመንግስቱ አዳራሽ ግድግዳ ላይ፣ የፈርኦኖች አፅም በሚሸፈንበት የእንጨትና የድንጋይ ልባሥ በውስጥም በውጭም እንደ ስዕል ተስሎ ከሚገኘው ፅሑፍ ላይ ተገልብጦና ተተርጉሞ የብዙ ፈርኦኖች የጦርነት፣ የመንግስትና የነገስታት፣ የአማልክትና የካህናቱ ታሪክ ከነስርዓቱ ተገኘ። በዚህም ውስጥ ፈርኦኖች እነራምሲስ፣ እነቱትሞሲሥ 3ኛ ኑብያን ያስገበሩበት ታሪክ አብሮ ተገኝቷል።

ቱትሞሲሥ 3ኛ በግብፅ በ18ኛው ስርወ መንግስት / ዳይናስቲ/ ውስጥ ከነገሱት ዋና ዋና ፈርኦኖች ውስጥ አንዱ ነበር። በካርናቅ

ቤተመቅደስ ግድግዳ ላይ ተገኝቶ የተተረጎመው ታሪክም በምስራቅ አገር አሶራውያንን፣ ፊኒቃውያንን፣ በደቡብ በኩል የኑብያን አገር ማስገበሩን እንዲሁም የእርሱ እህት የሆነችው ሐታሱ የተባለችው የስልጣን ተካፋይ ሆና ሰብቻዋ ጦር አዘጋጅታ ፑንት የሚባለውን ሀገር ወግታ ልዩ ልዩ የከበሩ እቃዎችን እንዳስመጣች ታውቀ።

ፑንት የሚባለው አገር ደግሞ ቀደም ሲል እንዳየነው ከሰሜናዊ ኢትዮጵያችን እስከ ኤልማንደብ የሚያጠቃልልና የየመንንም ግዛት የሚያካትት ነው። በዚህ በተገኘው ፅሁፍም የወረራ ምክር የሰገሷቸው ጣኦታቱ እንደሆኑ የሚገልፅ ሲሆን፤ ቱትሞሲሥ 3ኛም በጦር መሳሪያና በበርካታ ሠራዊት የኑብያ ኢትዮጵያን መውጋቱን ይገልፃል።

ቀደም ባሉት ጊዜያቶች ለግብፅ አንገዛም ብለው የፈርኦኖቹን ሃይል ይመልሱ የነበሩት ኢትዮጵያውያን በቱትሞሲሥ 3ኛ ጊዜ ሙሉ ለሙሉ ተሸንፈው ገበሩ። የቀሩትም ውጊያውንና ዘረፋውን መቋቋም ተስኗቸው ወደ አትባራና ወደ ተከዜ ሸሹ። ቀጥሎ ባለው ጊዜ የግብፅ ጦር ወደዚሁ ሸሽተው ወደመጡበት አገር ዘልቆ በመርከብ መጥቶ ወግቶና ባላባቶችን ማርኮ ተመለሰ እንጅ በሰሜኑ ኢትዮጵያችን ጦሩን አላሰፈረም።

በቴብ ከተማ በካርናቅ የአሞን ቤተ መቅደስ ውስጠኛ ግድግዳ ላይ "ቱትሞሲሥ 3ኛ ራ-ሜን- ኬፐር /ደጉ አምላክ/ የሁለቱ አገራት /የደቡብና የሠሜን፣ የግብፅና የኩሽ/ ንጉስ፣ ለዘላለም የሚኖረው በጦር ያስገበራቸው አገሮች" ተብሎ የ15 አገሮች ስም በዝርዝር ተፅፎ ይገኛል። ከእነዚህ ውስጥ በመጀመሪያው መስመር የሚገኘው የኛው የኩሽ አገር ነው። በተዘረዘሩት አውራጃዎች ውስጥ ኡትሊት፣ ታካሩ፣ ሐማሱ፣ ታና የሚል ቃል ስላለበት አዱሊስ፣ ትግሬ፣ አማሴን፣ ጣና ማለቱ ሳይሆን አይቀርም የሚል ድምዳሜ ላይ ተደርሷል።

ከዝርዝሩ ጎን ደግሞ የፑንት አገር ሰዎች የገበሩበት ስዕል ይታያል። እንግዲህ ግብፆች የቀድሞ ኢትዮጵያ የሚባለውን የዛሬውን ሱዳን ከያዙ በኋላ ከአትባራ ወዲህ ሠሜኑንና ምስራቁን የዛሬውን ኢትዮጵያ ጦር እየላኩ አስገብሩ እንጂ ቋሚ ጦር አስቀምጠው አልገዙትም ማለት ነው። የኑብያን ግን ግዛቱን በሙሉ ወደራሳቸው ግዛት ደባልቀው ሹም ሽር እያደረጉ በገዥነታቸው ሲቀጥሉ ችለዋል።

ለዚህ ግዛት የበላይ አስተዳዳሪም የፈርኦኑ የበኩር ልጅ አልጋ ወራሹ ሆነ። የማእረግ ስሙም "የኩሽ ንጉሳዊ ገዥ" ተባለ። በስሩም ከቀድሞዎቹ ከኢትዮጵያ ነጋሲዎች ውስጥ ታማኝ የተባለው እየተመረጠ የበታች ሆኖ ይገዛ ጀመር። እነዚህ የኑብያ ኢትዮጵያ ነገስታትና ህዝቦችም በተመቻቸው ጊዜ የግብፅን ገዥዎች አባረው የራሳቸውን መንግስት ለማቋቋም ደፋ ቀና ማለታቸውን ገፋበት። ነገር ግን ከቱትሞሲስ 3ኛ በኋላ



የተነሱ ፈርኦኖች የበለጠ እየገነኑ ስለሔዱ የነፃነት ተስፋቸው እየመነመነ ሔደ።

ከቱትሞሲሥ 3ኛ በኋላ ከተነሱት ከሀይለኞቹ ፈርኦኖች መካከል ደግሞ ይበልጥ ገናናና ስመጥር የሆነው ራምሲሥ 2ኛ ሲሆን፤ እርሱም ኑብያን መግዛቱን ቀጥሏል። በ18 አመቱ እንደነገሰና ኑብያውያን ሸፍተውበት በድጋሚ ድል እንዳደረጋቸውም ታውቋል።

ታላቁ ራምሲሥ ዳግማዊ የግዛት ዘመኑ ከ1292-1225 ቅ.ል.ክ ሲሆን በዚህ የግዛት ዘመኑም ግብፃውያንን፣ የኑብያ ኢትዮጵያውያንን ፣ ሊቢያን፣ የከነዓንንና የሶርያን፣ የሞሶፖታሚያን አገሮች 67 አመት ገዝቶና አስገብሮ በ85 አመቱ ሞቷል። እስከዚህ ጊዜ ድረስም የኑብያ ኢትዮጵያውያን በተገዥነት ላይ ነበሩ። ከታላቁ ራምሲስ ቀጥሎ ሜኔፕታህ የተባለው ልጁ ሲነግስ ልክ በዚያው ወቅት እስራኤሎች በሙሴና በአሮን እየተመሩ ግብፅን ለቀው ወደምድራቸው የተጓዙበት ዘመን ነው።

ሙሴ በነበረበት ዘመን የግብፅ ንጉስ/ፈርኦን/ የነበረው መጠሪያ ስሙ ራምሴስ እንደሆነና፤ ሜኔፕታህ እንደተካው፤ በዚህ በሻምፖሊዮን ጥናት ይፋ ተደርጓል። ራምሲሥ ማለት ደግሞ የሀሀይ ልጅ የሚል ትርጓሜ አለው። ይህ ንጉስ የእስራኤሎች መብዛት ባሰጋው ጊዜ "የበኩር ወንድ ይገደል" የሚል ትዕዛዝ ያስተላለፈው ነው። ይህ ንጉስ ከንጉስ ሰለሞን የበለጠ ሚስትና

እቁባት እንደነበረው፤ ከሚስቶቹ ውስጥ ደግሞ ሶስቱ የራሱ ልጆች እንደነበሩና ባጠቃላይ 111 ወንድ ልጆችና 51 ሴት ልጆች ነበሩት ተብሏል። ሌላው ደግሞ እስራኤሎችን አልለቅም ያለውና በኋላ ላይ ለቆ እነርሱን ሲያሳድድ በኤርትራ ባህር ሰጠመ በማለት መፅሐፍ ቅዱስ ፈርኦን ብሎ የጠራው ንጉስ ስሙ ሜኔፕታህ እንደሆነና /የፕታህ ወዳጅ/ የሚል ትርጉም እንዳለው ተረጋግጧል።

እርሱም የገዛበት ዘመን ከ1225-1215 ድረስ እንደነበር ታውቋል። የኑብያ ኢትዮጵያን ለመጀመሪያ ጊዜ ሙሉ ለሙሉ ገዛ ያልነው የቱትሞሲሥ 3ኛ የግዛት ዘመን በ18ኛው ዳይናስቲ የሚካተት ነው ብለናል። የራምሲሥ 2ኛና የሜኔፕታህ የነጋሲነት የዘር ሃረግ /ዳይናስቲ/ 19ኛው ሲሆን፤ የ20ኛው ዳይናስቲ ደግሞ እንደርሱ የቴብ ዘር የሆነው ከገዛ በኋላ፤ የ21ኛው ዳይናስቲ የተመሰረተውም የታኒትና የቴብ ድብልቅ ከሆነ የዘር ሃረግ ነው።

22ኛው ደግሞ የነጋሲ ዘር የሆኑት የሊቢያና የቡባስቲ ነገድ ተብለው በየተራ ከገዙ በኋላ 23ኛው ዳይናስቲ የታኒት ዘር፤ 24ኛው የሳይስ ዘር ተብሎ ተዘርዝሯል።

ከዚህ በኋላ ግን የግብፅን 25ኛውን ስርወ መንግስት /ዳይናስቲ/ ኢትዮጵያውያን እንደመሰረቱት ነው የተረጋገጠው። ይህንንም ቀጥለን በስፋት የምናየው ይሆናል።

በእነዚህ በተዘረዘሩት ፈርኦኖች የግዛት ዘመን ጊዜ የኑብያ ኢትዮጵያ ለግብፅ እየገበሩ መኖራቸው በበርካታ ማስረጃ የተረጋገጠ ነው። (National Geography feb,2008) ይህም ሲሆን በኑብያ ያሉ ነገስታቶች ሃይማኖታቸው ከእነርሱ ጋር እየጠነከረ፣ እነርሱ የሚያመልኩትን እያመለኩ፣ ቋንቋቸውን እየተናገሩና በአጠቃላይ በሁለነገራቸው ከእነርሱ ጋር ተመሳስለው ከመኖራቸውም በላይ፤ በጣም ጥልቅ ትስስር ከመፈጠሩ የተነሳም የጣኦታቱ የነአሞን አገልጋይ ካህናት እስከመሆንና ልዩ ልዩ መንፈሳዊና ሲጋዊ መስተዳድሮች ላይ በታማኝነት ሊሾሙ ችለዋል። እዚህ ላይ አንባብያን በድጋሚ ሊገነዘቡት የሚገባ ጉዳይ አለ። ይኸውም ይህ ሁሉ በኑብያ ኢትዮጵያ ሲከወን የአሁኗ ኢትዮጵያ መስራቾች አክሱማውያን በዚያው በኢትዮጵያችን ሠሜናዊ ክፍል እንደሰፈሩና በራሳቸው ነገስታት እየተዳደሩ፤ እንዲሁም ኑብያን የገዙትና ያስገበሩት ግብፃውያን ድንበር ዘልቀው ገብተው ሲያስገብሯቸው እንኳ በሙሉ ሃይላቸው መጥተው ሠፍረው ቋንቋቸውን አልበረዙም፣ ባህልና ልማዳቸውም አልተቀየረም። እዚያው በሰፈረ የግብፅ ሃይል ተገዙ የሚል ማስረጃም የለም። ነገር ግን የኑብያ ኢትዮጵያና የአክሱም ኢትዮጵያ አንድ አገር ነበሩና፤ ልንል የምንችለው ግብፆች ከፊሉን ኢትዮጵያ ገዙ፣ ከፊሉን ደግሞ በርቀት ሆነው አስገበሯቸው ነው።

በእነዚያ ዘመናት በኑብያ ያሉት ኢትዮጵያውያን ውስጥ ለውስጥ የነፃነት እንቅስቃሴ ሲያደርጉና ያገኙትን የመንፈሳዊና ስጋዊ አስተዳደር ስልጣን ተጠቅመው የግብፅን ግዛት ነቅለው ለመጣል ሲሞክሩ ቆይተዋል። ከረጅም ጊዜ በኋላም ተሳክቶላቸው የግብፅን ሰራዊት ጠራርገው ለማስወጣትና ነፃነታቸውን ለመቀዳጀት ችለዋል። በአጠቃላይ የግብፅ ግዛት በኢትዮጵያ የቆየው ከ1500-1200 ቅ.ል.ክ እንደነበር ታውቋል። ይህም ማለት ለ300 አመታት ያህል መሆኑ ነው። የኢትዮጵያውያን ሐብት በከፍተኛ ሁኔታ የተዘረፈበት ዘመን መሆኑም የታወቀ ነውና ናፓታ ለጊዜው ቀዝቀዝ ብትል አይገርም



## ምዕራፍ ፲፩

## ከንግስት ሳባ እስከ ንጉስ ባዚን ያሉት የኢትዮጵያ ነገስታት ዝርዝር

የግብፅ ግዛት በኢትዮጵያ በቆየበት ወቅት ግብፆች ሲመጡ መመከት አቃታቸው ካልናቸው ከአሚን አምሃት 1ኛና ከባውእ በኋላ እንዲሁም ግብፆች እስከወጡበት እስከ 1200 ድረስ የነበሩት የኢትዮጵያ ነገስታትና ከእነርሱ በኋላ እስከተዘረዘሩት እስከ ተዋስያ ዴውስ፤ ማለትም ከንግስተ ሣባ በፊት እስካለውና ከ1026 እስከ 1013 ድረስ እስከነገሰው ያሉት የኢትዮጵያ ነገስታቶች በግዛት ዘመናቸው ምን እንደፈፀሙም ሆነ ስለ ሌላ ተያያዥ ታሪካቸው የሚገልፅ ማስረጃ ከስም ዝርዝራቸው በቀር አልተገኘም። ምናልባትም የኑብያ ኢትዮጵያ ከግብፅ ቀንበር ከተላቀቀ በኋላ እየቀዘቀዘ ሄዶ ከኤርትራ ባህር ወዲህና ወዲያ ያለው ግዛት ጎን እያለ ሣይሄድ አልቀረም። ለማንኛውም እስካሁን ያየናቸው ታሪኮች ሁሉ የተከናወኑት ከንግስተ ሣባ በፊት በነበረው ዘመን ነው። ቀጥለን ከምናየው የነገስታት ዝርዝር በኋላም ከንግስት ሣባ ጀምሮ ያለውን ታሪክ ይሆናል የምንመለከተው። እነዚህን ነገስታት ስናይም በሠሜኑ ኢትዮጵያችን በኋላ የገነነውና እሁን ድረስ ገናናነቱን በሃውልቱና በፅሑፉ ያወቅነው የአክሱም መንግስት እስካሁን ማለትም ቢያንስ ከ1ሺ ቅ.ል.ክ ጀምሮ እስከ ክርስቶስ መወለድ ጊዜ ድረስ ጥቂት ቀደም ብሎ ባለው ዘመን እጅግ አለመግነኑንና አለመታወቁን ስንረዳ፤ ነገር ግን ከዚህ ዘመን በፊት በክልሉ በአክሱምና አካባቢው እንደነበረ በብዙ መረጃ የተረጋገጠ ነው። በመጀመሪያ ናፓታ፣ ቀጥሎ መርዌ፣ ከዚያም አክሱም የኢትዮጵያ ነገስታቶች መናገሻ መሆናቸው እንዳለ ሆኖ፤ ንግስተ ሣባ ግን በጥንቱ አጠራር ሣባ በምትባለውና በአክሱም አቅራቢያ በምትገኘው ከተማ መንገሷን ቀጥለን የምንረዳው ይሆናል።

| ተ.ቁ | የነገስታቱ ስም | በስልጣን ላይ የቆዩበት ጊዜ በዓመት | የገዙበት ዘመን ከ.ክ.ልደት በፊት |
|---|---|---|---|
| 1 | ንግስተ ሳባ | 31 | 1013 -982 |
| 2 | ሚኒልክ 1ኛ | 25 | 982-957 |
| 3 | ሐንድዮን | 1 | 957 -956 |
| 4 | ሲራህ 1ኛ | 26 | 956 -930 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 5 | አሜን ሆቴብ /ዘማዱር/ | 41 | 930 -889 |
| 6 | አክሱማይ ራሚሱ | 20 | 889 -869 |
| 7 | ሲራህ 2ኛ | 38 | 869 -831 |
| 8 | ቱዋስያ 2ኛ | 21 | 831 -810 |
| 9 | ፒያንኪ 2ኛ /አብራሊዮስ/ | 32 | 810 -778 |
| 10 | አክሱማይ ወረደ ፀሀይ | 23 | 778 -755 |
| 11 | ካሲታህ ሐንዲዮን | 13 | 755 -742 |
| 12 | ሻባካ | 12 | 742 -730 |
| 13 | ኒካንታ ሀንዳኬ | 10 | 730 -720 |
| 14 | ቲሃርቃ /ወረደ ነጋሽ/ | 49 | 720 -671 |
| 15 | አርድአሜን አውስያ | 6 | 671 -665 |
| 16 | ገሰዮ | 6 ሰዓት | 665 -665 |
| 17 | ታንታሙን | 4 | 665 -661 |
| 18 | ቶማድዮን ፒያንኪያ 3ኛ | 12 | 661 -649 |
| 19 | አሚን አሳሮ 2ኛ | 16 | 649 -633 |
| 20 | ፒያንኪያ አውጥዮ 4ኛ | 34 | 633 -599 |
| 21 | ዝዋሬንብረት አስፑርታ | 41 | 599 -558 |
| 22 | ሰይፋይ ሐርሲኦተው | 12 | 558 -546 |
| 23 | ራምሃይ ናስቶሰኔን | 14 | 546 -532 |
| 24 | ሐንዲው አብራ | 11 | 532 -521 |
| 25 | ሰፎሊያ ኒኮቦን | 31 | 521 -490 |
| 26 | አግልቡል ሰዩክስ | 21 | 490 -469 |
| 27 | ጽዕመረት /ወረደ ነጋሽ/ | 21 | 469 -448 |
| 28 | አውስያ ብራክስ | 12 | 448 -436 |
| 29 | ቀኒዝ ጽስሜዝ | 13 | 436 -423 |
| 30 | አጽራስ | 10 | 423 -413 |
| 31 | ካሲታህ ወልደ እሁህ | 20 | 413 -393 |
| 32 | ኤላልዮን ቲአንኪ | 10 | 393 -383 |
| 33 | አርቲስክ አሚን 3ኛ | 10 | 383 -373 |
| 34 | አርቲስክ አሚን 4ኛ | 10 | 373 -363 |
| 35 | ሐዲና | 10 | 363 -353 |
| 36 | አርቲስክ አሚን 5ኛ | 10 | 353 -343 |
| 37 | አርቲስክ አሚን 6ኛ | 10 | 343 -333 |



| | | | |
|---|---|---|---|
| 38 | ኒካውሳ ሀንዳኬ 3ኛ | 10 | 333 -323 |
| 39 | ባስኡ | 7 | 323 -316 |
| 40 | ኒካውሳ ሀንዳኬ 4ኛ | 10 | 316 -306 |
| 41 | አውጥዋ አራውራ | 10 | 306 -296 |
| 42 | አርካሚን 2ኛ | 10 | 296 -286 |
| 43 | ክልአስ 2ኛ | 10 | 286 -276 |
| 44 | ዙዋሬ ንብረት | 16 | 276 -260 |
| 45 | ስትዮ | 14 | 260 --246 |
| 46 | ሰይፋይ | 13 | 246 -233 |
| 47 | ኒኮሲስ ሀንዳኬ 5ኛ | 10 | 233 -223 |
| 48 | ራምሐይ አርሚን 4ኛ | 10 | 223 -213 |
| 49 | ፊልያ ሁርኒክሐት | 15 | 213 -198 |
| 50 | ሃንዲ አውኪራራ | 20 | 198 -178 |
| 51 | አግሐቡ ብሴሀራን | 10 | 178 -168 |
| 52 | ሱላይ ክዋውማኑን | 20 | 168 -148 |
| 53 | መስልኒ ቁራርሜር | 8 | 148 -140 |
| 54 | ነክሳይ ብስንቲ | 10 | 140 -130 |
| 55 | ኤትቢኑ ካውር | 10 | 130 -120 |
| 56 | ሰፈልያስ አብራሚን | 20 | 120 -1 0 |
| 57 | ሠናይ | 10 | 100 -90 |
| 58 | አውሲና ንግስት | 11 | 90 -79 |
| 59 | ዳዊት 2ኛ | 10 | 79 -69 |
| 60 | አግልቡስ | 8 | 69 -61 |
| 61 | በዋውል | 10 | 61 -51 |
| 62 | ባሬዋስ | 10 | 51 -41 |
| 63 | ዲኒዳድ | 10 | 41 -31 |
| 64 | ኣሞይ መሐሲ | 5 | 31 -26 |
| 65 | ኒክትራስሀንዳኬ 6ኛ | 10 | 26 -16 |
| 66 | ሞልኪ | 2 | 16 -14 |
| 67 | ሱዛይ | 8 | 14 -6 |
| 68 | ባዚን | 6 | 6-1 ዓ.ምህረት |

(አጭር የኢትዮጵያ ህዝብ ታሪክ በአለቃ ታዬ)

ባዚን በኢትዮጵያ በነገሠ በ6ኛ ዓመቱ ኢየሱስ በቤተልሔም ተወለደና የዘመን አቆጣጠሩም እንደ አዲስ ወደፊት እንድ ተብሎ መቆጠር ጀመረ።

ከንግስተ ሣባ የሚነሳው የኢትዮጵያ የነገስታት ዝርዝር ዶክተር ሬይዝነርና ሌሎች የአገራችን ፀሃፍት፣ እንዲሁም መንፈሳዊ ይዘት ያላቸው የታሪክ መዛግብት ባየነው መልኩ ነው የሚዘረዝሩቸው። የሁሉም መነሻ የአገራችን ክብረ ነገስትና ታሪክ ነገስት መሆኑም ይታወቃል።



## ምዕራፍ ፲፪
## የንግስተ ሳባ ታሪክ


ንግስተ ሳባ የነገሠችው በአክሱም አቅራቢያ በጥንቱ አጠራር ሳባ በምትባለው ከተማ ነበር።ንግስተ ሳባ በአባቷ በአጋቦሥ /ተዋስያ/ እግር ተተክታ ኢትዮጵያን መግዛትና ማስተዳደር የጀመረችው ከክ.ልደት በፊት ከ 1ሺ 13 ጀምሮ ነው።

ንግስተ ሳባ የሚለውም ስሟ ሳይሆን የሳባውያን ንግስት ማለት ነው።

የንግስተ ሳባ መጠሪያ ስሟ በክብረ ነገስት ማክዳ፣ በመጽሐፈ ነገስት በቀዳማዊና ካልዕ፣ በዜና መዋዕል ንግስተ ሳባ፣ በወንጌል ንግስተ አዜብ ትባላለች።

በዚያ ዘመን የኢትዮጵያ ወሰን ወይም የንግስተ ሳባ ግዛት ስፋቱ በምስራቅ እስከ ማዳጋስካር፣ እስከ ፋርስ ባህር፣ በምዕራብ እስከ ኑብያ፣ እስከ ምስር/ግብፅ/ ጠረፍ፣ በደቡብ እስከ ኒያንዛ የቪክቶሪያ ባህር ድረስ ነው ይባላል። በእርሷ ዘመን በኢትዮጵያ የዓረብ፣ የግብፅ፣ የህንድ፣ የእየሩሳሌም ሰዎች የዘመኑን ሽቀጣሽቀጥ ልብስ፣ ሽቶ፣ እጣን፣ ወርቅና ሌሎች አስፈላጊ ነገሮችን ይነግዱ ነበር። በዚሁ ዘመን ደግሞ በእየሩሳሌም የነገሰው የዳዊት ልጅ ሠሰሞን ነበር።





Solomon embraced and
311 x 318 - 36ቤ. - jpg
mythencyclopedia.com

ንግሥተ ሳባ በኢትዮጵያ፣ ሰለሞን በእየሩሳሌም ነግሰው በነበረበት ዘመንም ታምሪን የሚባል ነጋዴ ከኢትዮጵያ ወደ እየሩሳሌም እየተመላለሰ ይነግድ ነበር።

እርሡም ለንጉሥ ሰለሞን የሚሆኑ ጥሩ ጥሩ እቃዎች ከኢትዮጵያ ገዝቶ ወስዶ ለሠለሞን ካስረከበ በኋላ፤ ሲመለስ የሰለሞንን የቤተ መንግስት ስነ ስርዓትና ጥበቡንም፣ ክብሩንም ሁሉ ለንግስተ ሳባ ነገራት።

በታምሪን አማካኝነት የተጀመረው ግንኙነትም እየቀጠለ ሔደ። በዚህ ነጋዴ አማካኝነትም በሁለቱ ነገስታቶች አገር የማይገኙ እቃዎችን በስጦታ መልክ ይላላኩ ጀመር። ንግስተ ሳባ የንጉስ ሠለሞንን ጥበብ፣ የቤተመንግስቱንና የስርዓቱን ሕግ እና አደረጃጀት በደምብ ከሚያውቀው ከታምሪን እንደበት ብዙ ጊዜ እየጠየቀች ከሰማች በኋላ በመጨረሻ በጆሮዋ የሰማችውን በአይኗ ለማረጋገጥ በብዙ ወታደሮቿና ደንገጡሮቿ ታጅባ ለሠለሞን የምታበረክተውን ልዩ ልዩ ስጦታ አስጭና በነጋዴው መሪነት ወደ እየሩሳሊም ተጓዘች።

በደረሰችም ጊዜ ንጉስ ሠለሞን በታላቅ ክብርና በደስታ ተቀበላት። እርሷም ከኢትዮጵያ ይዛለት የሄደችውን የከበረ እንቁና ወርቅ፣ ሽቶና ሌሎች ስጦታዎችን አበረከተችለት።



ንጉስ ሰለሞንም ስጦታውን በክብር ተቀብሎ ልዩ ማረፊያ ቦታ መርጦ ለእርሷና ለአጃቢዎቿ አዘጋጀላቸው። በየቀኑም በእርሱ ትዕዛዝ በሬ፣ በግና ፍየል እንዲሁም መጠጥ ለአጃቢዎቿም ለራሷም እንደ ደንቡ ሲያቀርብላቸው ቆይቶ፤ አንድ ቀን ንጉስ ሠለሞን ለንግስተ ሣባ ክብር ትልቅ ግብር/ግብዣ/ አዘጋጅቶ ጠራት።

ከዚህ ግብዣ ቀደም ብሎም ቤተመንግስቱንና ቤተመቅደሱን ሲያስጎበኛት ነበር። በዚህ እለት ደግሞ ስለ እርሷ ክብር በተዘጋጀው ግብዣ የአዳራሹን አይነት፣ የመሳፍንቱንና የመኳንንቱን አገባብና አቀማመጥ ለማሳየት በራሱ ዙፋን አቅራቢያ ለእርሷ ልዩ ዙፋን አዘጋጅቶ ዙፋኑንም እሷ ከውስጥ ሆና ማናቸውንም ነገር ለማየት እንድትችል፣ ከውጭ በኩል ግን እሷን ማንም እንዳያያት ተደርጎ በተሠራ መስታዎት መሠል ነገር አስጋርዶ አስቀመጣት። በዚህ ባማረ ዙፋን ተቀምጣ የመሳፍንቱን፣ የመኳንንቱን፣ የወታደሩን አገባብና አቀማመጥ፤ በየክፍሉ የሚያገለግሉትን የወይን ጠጅ አሳላፊዎችንና ሠራተኞችን አሰባበርና የስራቸውን ቅልጥፍና እየተመለከተች ተደነቀች።

ግብዣው ሲጠናቀቅም ንጉስ ሠለሞን ንግስተ ሣባን ሊያነጋግራት እርሷ ወዳለችበት ዙፋን አመራ። እርሷም፦ "የጥበብህንና የስራህን ነገር እዚህ ሆኜ በአይኔ ተመለከትኩት፤ በአገሬ ሳለሁ ከሰማሁት እጅግ ይበልጣል" በማለት አድናቆቷን ገለፀች።

ከዚያም ወደተዘጋጀላት ሠፈሯ ለመሄድ ስትጠይቀው "መሸቷልና እዚህ እደሪ" አላት። በዚህ ጊዜ ሌሊት ላይ ንጉስ ሰለሞን ንግስተ ሳባን ተገናኝቷት አደረ፤ እናም ፀነሰች። በዚህ ጊዜ ንግስተ ሳባ "ልጅህ መሆኑን የምትረዳበት ምልክት ስጠኝ" በማለት ከሠለሞን የጣቱን ቀለበት ተቀብላ በቶሎ ወደ አገሯ ተመለሰች። /እዚህ ላይ ታሪክ ነገስትና ክብረ ነገስት ሠፋ ያለ ሐተታ በመስጠት እግሯ ላይ ሸሆና እንደነበርና እየሩሳሌም ስትደርስ እንደወለቀላት፤ ጨው የበዛበት ምግብ አብልቶ በውሃ ጥም ወደ እሱ መኝታ ውሃ ፍለጋ እንደሄደችና በዚያ ዘዴ እንደተገናኛት.... ወዘተ የሚል ነገር አስፍሮ ይገኛል/። የሆነ ሆኖ ንግስተ ሳባ ፀንሳ ልትመለስ ስትነሳ በእየሩሳሌም ርስት ይሆናት ዘንድ ቦታ ሠጥቷት አብያተ ክርስቲያናት ታንፀውበት ዛሬ ድረስ መንፈሳዊ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል። /የዶር ሱልጣን ኀዳም'ን/

ንግስት ሳባ ከነአጃቢዎቿ ወደ አገሩዋ ስትመለስ የኤርትራን ባህር ተሻግራ በሐማሴን አውራጃ ማይበላ ከተባለው ቦታ /አገር/ ስትደርስ ወንድ ልጅ ወለደች።

ንግስተ ሳባም የወለደችውን ልጅ ስሙን እብነ መለክ የሚል ስም አወጣችለት። ትርጉሙም የንጉስ ወይም የገዥ ልጅ ማለት ነው። እብነ ሐኪምም ተብሏል። ይህም የብልህ ልጅ ማለት ነው።

የመጀመሪያውም ሁለተኛውም የስም ስያሜ የጥንቱ የሳባውያን አነጋገር ሲሆን፤ ታሪኩ የሰፈረበት ክብረ ነገስት በሣባውያን ቋንቋ ተፅፎ ስለነበርና በኋላ ላይ እንንበረእድ ይስሐቅ ወደ ግዕዝ ሲተረጉሙ የአረብኛውን ስም እንዳለ ወስደው እንደተረጎሙት ይነገራል።

ምኒልክም አድጎ ሐያ አመት እንደሞላው "አባቴ ማነው ንገሪኝ" ብሎ እናቱን ሲጠይቅ እርሷም "የእየሩሳሌሙ ንጉስ ሠለሞን ነው" ብላ ነገረችው። አባቱን ሠለሞንን ለመገናኘትም የእናቱን ፈቃድ ጠይቆ ወደ እየሩሳሌም ሔደ።

አባቱ ንጉስ ሠለሞንም ልጁን በደስታ ተቀበለው፤ ባየውም ጊዜ ለሞ ባረከው። ምኒልክ ለ3 ዓመታት ያህል በእየሩሳሌም የኦሪት ህግ፣ የመንግስት አስተዳደር በእብራይስጥ ቋንቋ ተምሮ ሲጨርስ፤ ወደ እናቱ ወደ ንግስተ ሣባ ተመለሰ። ሲመለሱም ንጉስ ሠለሞን ልብሰ መንግስት አልብሶ ከ12ቱ ነገደ እስራኤል 12ሺ የእብራዊ የበኩር ወንድ ልጆች /ከእያንዳንዱ ነገድ አንድ አንድ ሺ ማለት ነው።/ የዳዊትን ልጅ ወንድሙን ጨምሮ ብልሆችንና አዋቂዎችን መርጦ፤ ከተማሩትም ካህናት እንዲሁም ከመሳፍንቱ ልጆች 22 ታላላቅ ሹማምንት ጋር የኢትዮጵያ ንጉሰነገስት ይሆን ዘንድ ልብሰ መንግስቱን አሠፍቶ፣ ቅብዓ ሜሮንን በሊቀ ካህናቱ በሳዶቅ አስቀብቶ፣ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ982 ወደ ኢትዮጵያ ሸኘው።

ንግስተ ሣባ ልጇ ምኒልክ ከእየሩሳሌም ሲመለስ በታላቅ ክብር ሠልፍ አድርጋ ተቀበለችው። ምኒልክና ሰዎቹ ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ አዛርያስ በሚባለው ሊቀ ካህን አማካኝነት በልዑል እግዚአብሔር ጣቶች ተቀርፆ ለሙሴ የተሰጠው እውነተኛ ፅላት ወደ ኢትዮጵያ አብሮ መጣ።

ይህን ጉዳይ በተመለከተ ገሚሱ አባቱ ንጉስ ሠለሞን ፈቅዶለት እንደሰጠው፤ ሌላው በድብቅ ይዞት እንደመጣ ይገልፃል። ያም ሆነ ይህ ፅላቱ/ታቦተ ፅዮን/ ወደ ኢትዮጵያ እንደመጣ በግልፅ የሚታወቅ ሲሆን፤ በአክሱም ፅዮን ቤተክርስቲያን አምላክ በመረጣቸው ሠዎች እየተጠበቀ እንደሚገኝ ነው የሚታወቀው።

ከዚያም ንግስተ ሣባ ምኒልክን ተቀብላ በሕይወት እያሏት በኢትዮጵያ አነገሰችው። ንግስተ ሳባ በኢትዮጵያ ለመንገሷ ከመፅሐፍ ቅዱስ ጀምሮ በሁሉምታሪ ካዊና መንፈሳዊ ፅሁፎች ውስጥ የተረጋገጠ መሆኑ እንዳለ ሆኖ ፤ ገናና ንግስትና በጥበብ የተሞላች እንደነበረችም ይታወቃል።

ከዚህም በላይ የኢትዮጵያን አጠቃላይ ገፅታ መለወጧን ልብ ይሉታል። ይህም የንግስናውን ዘር ከእየሩሳሌሙ ጥበበኛ ንጉስ ጋር



በማስተሳሰሯ ሙሉ ለሙሉ ባይሆንም ብዙሃኑ በጣኦት ማምለኩን ትቶ በኦሪተ ህግእየተመራ እውነተ ኛውን አምላክእንዲያውቅ የተደረገው/ በፍላጎት/ በእርሡዋና በልጇ ዘመን ነው።

ጤፍ ለምግብነት የዋለው በእርሷ ዘመን እንደሆነ ስለሚነገርላት ስለዚች ንግስት በርካታ ፀሃፍት የፃፉላት ሲሆን፤ ከግሪክ ሊቃውንት እንደ ሔሮዱተስ፣ መልዚ፣ ሆሜር...... ከኢጣልያ ሊቃውንትም ሆነ ከሌሎች የአውሮፓና ጀስያ ታሪክ መርማሪዎች ብዙ ብለውላታል። ሞሪዮ የተባለው የፈረንሳይ ሊቅም ስለ ንግስተ ሳባ ሲገልፅ «በአክሱም አጠገብ በምትገኝ ሳባ በምትባል ከተማ ተቀበረች። ከመቃብሯ ላይም 24 ሐውልቶች አሉበት። አሁን ግን ተሠባብሮ አልቋል» ይላል።

ከንግስተ ሳባ ጋር በተያያዘ ተደጋግሞ የሚነሳው ጥያቄ ንግስተ ሳባ የዓረብ ንግስት ወይስ የኢትዮጵያ? የሚል ነው። ከአምስት በላይ የሆኑ አገራትም የኛ ናት እያሉ ይሻሟታል። ነገር ግን የተነሳችው ከቀድሞዋ የኢትዮጵያ ግዛትእስከሆነ ድረስ ፤ የዛሬውን ክፍፍል መነሻ አድርጎ መወዛገብ አይገባም። ያም ቢሆን ግን በዛሬው የካርታ ክለሳም ብንሄድ ሣባ የኢትዮጵያ ነች። የተቀበረችውም በአሁኗ ኢትዮጵያ እንደሆነ በርካታ ፀሃፍት የተስማሙበት ነው። በተረፈ ..... ሣባ የመጣችው ከዘንዶ ነው ...... ወዘተ ... የሚል ሐተታ ይገኛል። በብዙዎቹ የዛሬ ሊቃውንት አይታ ይሄ መሰሉ ሃተታ ተረት ተረት ተብሏል። ነገር ግን ሚስጥራዊ አገላለፅ ይመስላል።

ለማንኛውም ንግስተ ሳባ /ማክዳ/ በኢትዮጵያ 31 ዓመት ገዝታ ልጇን ምኒልክን በሕይወቷ እያለች ተክታ አልፋለች

## ምዕራፍ ፲፫
## የቀዳማዊ ምኒልክ ዘመነ መንግስት
## ከ982-957 ቅ.ል.ክ

ከክ.ልደት በፊት በ982 በኢትዮጵያ የነገሰውና ከእየሩሳሌሙ ንጉስ ከሰለሞንና ከሳባውያን ንግስት ከንግስተ ሳባ የተወለደው፤ እንዲሁም ኢትዮጵያን ለ25 ዓመታት በንጉሰነገስትነት ያስተዳደረው ቀዳማዊ ምኒልክ ነው።

የቀዳማዊ ምኒልክ በኢትዮጵያ መንገስ የኢትዮጵያን ታሪክ የተለየ መልክ አስይዞታል። ይኸውም የኢትዮጵያን ንግስና /የነገስታት ታሪክ/ እንዲሁም አወቃቀር ከሠለሞናዊው ስርወ መንግስት ጋር አቆራኝቶታል።

ከእርሱ ጋር የመጡ የ12ቱ ነገዶች 12ሺ የበኩር ወንዶችም በኢትዮጵያ ምድር ህገ ኦሪትን እያስተማሩ ሐይማኖታዊ የሆነ ህዝብ እንዲበረክትና ባእት ማምለክን እንዲተው በር ከፍተዋል።

ስጋዊ አስተዳደሩና ህግ አወጣጡም ከቀድሞዋ ስልጡንና ቀደምት አገር ጋር የተመሳሰለ መሆኑ ጠቀሜታ ነበረው።

ከእየሩሳሌም የመጡትና በኢትዮጵያ መኖር የጀመሩት ከኢትዮጵያ ህዝቦች ጋር እየተጋቡ፣ እየተዋለዱ በህላም ለመኖር ከመቻላቸውም በላይ፤ በተለያዩ ተፈላጊ ሙያዎች የተካኑ ነበሩና በእጅ ሙያቸው ለህዝቡ የሚጠቅመውን የመገልገያ እቃ ሠርተው በማቅረብና ህዝቦችንም በማስተማር ረገድ የማይናቅ አስተዋፅኦ አበርክተዋል።

በተጨማሪም ከቀዳማዊ ምኒልክ ጀምሮ ባህላዊውን የንግስና ስርዓትም ሆነ የህዝብ አመራር በተመለከተ ከጥበበኛው ከእየሩሳሌም ንጉስ በተቀሠመውና በዚያ ዘመን ዘመናዊ የተባለውን አይነት ስርዓትና ዘዴ በተከተለ አካሔድ የህግና የስርአት ደንቡን በዕኑ መሰረት ላይ ለመጣል ተሞክሯል።

ምንም እንኳን ከእርሱ በኋላ የተከታተሉት ነገስታት ቀጥለን እንደምናየው ኦሪተ ህግን ትተው በጣኦት ማምለካቸውን ቢቀጥሉም፤ በእውነተኛው አምላክ በማመን በኦሪተ ህግ የፀኑ ህዝቦች ግን በርካታ ነበሩ። ነገስታቱም እንዲሁ። ይህ በእንዲህ እንዳለም ከሌሎቹ ቀደምት ሐያል አገራት ጋር የተፈጠረው ዲፕሎማሲያዊ ትስስር በንግድም ሆነ በሌሎች መስል ዘርፎች የራሱ የሆነ አዎንታዊ ገፅታ ማስገኘቱን መገንዘብ አይከብድም።

በኋለኛው ዘመንም ስልጡን ከነበሩ ክርስቲያናዊ አገሮች ጋር የጠበቀና ተፈላጊ የነበረ ግንኙነት መፈጠሩ አልቀረም። ይህም መሰረቱ



ቀደም ባለው ዘመን ከኦሪተ ህግ ጋር የተዋወቁና ለአምላካዊው ሐይማኖት እንግዳ ያልነበሩት ህዝቦች በኋለኛው ዘመንም ክርስትናን ለመቀበል አልከበዳቸውምና ነው።

በምኒልክ ንግስና ጊዜ የተለያዩ በርካታ ሠራፊና ጥቃቅን ግዛቶችን የሚያስተዳድሩ ንጉሶችና ሹሞች ተሾመው፤ አገራቱን በበላይነት የሚመራው ንጉስ ነገስቱ ቀዳማዊ ምኒልክ ነበር።

ንግስናው የተፈፀመው እናቱ በነገሰችበት ሳባ በተባለችው ጥንታዊት ከተማ እንደነበር ይነገራል። ይህም ሲባል የምኒልክ የግዛት ወሠን ያንኑ እናቱ ትገዛው የነበረውን ሠፊ ግዛት መሆኑ እንዳለ ሆኖ፤ ያኔ ከ 15 እስከ 12ኛው መቶ አመት በግብፅ ይገዛ የነበረውን ኑብያንም እንደሚያጠቃልል ይነገራል። ምክንያቱም ግብፆች ለቀው ከወጡ 2 መቶ አመት ካለፈ በኋላ ነው ንግስተ ሳባ የነገሰችውና እርሡም የተካት።

እናም የኢትዮጵያ ታሪክ አንድ አይነት መሠረት ይዞ ነገስታቶች ከሠለሞናዊው ስርወ መንግስት እየተመዘዙ ሲነግሱና ኢትዮጵያን ሲያስተዳድሩ፤ ጠላት ሲነሣም ከግዛቷ ህዝብ /ከኑብያ ኢትዮጵያም ከአክሱም ኢትዮጵያም/ ጋር ተባብረው እየመለሱ ሙሉ ለሙሉ የተለያዩ አገራት እስኪሆኑ ድረስ የራሳቸውን ግዛት አስከብረው ሊቆዩ ችለዋል።

ቀዳማዊ ምኒልክ ሚስቱን ያመጣት ከእየሩሳሌም የነበረ ሲሆን፤ ከእርሷ በስተቀር ሌሎች አብረውት የመጡት ሁሉ ወንዶች ነበሩ። ሆኖም በተለያዩ ጊዜያቶች ከሌሎች አገሮች ወደ ኢትዮጵያ በተለያየ ችግር የገቡ ህዝቦች የመኖራቸውን ያህል፤ ከእየሩሳሌምም በተመሳሳይ መልኩ በርካታ እስራኤላውያን ወደ ኢትዮጵያ ይገቡ ነበር።

እንግዲህ እነዚህ ህዝቦች ናቸው ተራብተው ከቆዩ በኋላ ክርስትና ሲገባ ክርስትናን ሳይቀበሉ በኦሪተ ህጋቸው ፀንተው የኖሩት። በዚህም ምክንያት በኋለኛው ዘመን ክርስቲያኖች ይደርስባቸው በነበረው ጥቃት እየሸሹ፣ እየተዋጉ፣ እየተከላከሉ ሲኖሩ የቆዩት።

በዚህ ሽሽታቸውም ፈላሲ ወይም ፈላሻ የሚለውን ስያሜያቸውን ይዘው ዛሬ ድረስ በኢትዮጵያ የሚገኙና በየጊዜው ወደ ቀድሞ አገራቸው ወደ እስራኤል የሚጓዙት።

ቀዳማዊ ምኒልክ በእናቱ እግር ተተክቶ የኢትዮጵያን የንጉሰነገስትነት ስልጣን ሲረከብ አባቱ ንጉስ ሠለሞን ለእርሱና አብረውት ለመጡት ሠዎች የእርሱን አነጋገስና የሌሎችን የስልጣን ክፍፍል ምን መምሰል እንዳለበት ገለፃ /ምክር/ ለግሶ ሲሸኛቸው እንደሚችል ማሰብ ይቻላል። ይህንኑ የአባቱን ምክር ያማከለ መንግስታዊ አወቃቀር መዘርጋቱም ይታወቃል።

ስለዚህም በቀዳማዊ ምኒልክ ጊዜ ምን አይነት የመንግስት አወቃቀር እንደነበረ ባጭሩ ለመረዳት ያሀል ቀደምት ፀሃፍት ያሠፈሩትን ስናይ፡-

1. ቀዳማዊ ምኒልክ ንጉሰነገስት፤ በፍርድ ጊዜ ሲቀመጥ ወንበሩ ባአዳ፣ ባህረ ልብሱም ልብሰ ፀሃይ፣ ዙፋኑም የእንቁ፣ መታጠቢያውና የሚጠጣበት የእንቁ ዳንታ ነበር።
2. ሊቀ ካህን አዛርያስ። የአክሱምን ግብዝና በመያዝ በታላቅ ክብር ሆኖ በእርሱ ፈቃድ ግብር ያስገባ ነበር። በተጨማሪም የአክሱም ንቡረዕድ፣ የተድባበ ፅዮን ፓትርያሪክ፣ የመርጡለ ፅዮን ርዕሠ ርዕሣን፣ የጣና ቅዱስ ቂርቆስ ሊቀ ካህን በመሆን መንፈሳዊ አገልግሎት ይሠጥ ነበር።
3. ጌዴዎን ከዳዊት ልጅ ከአቢያጥ የተወለደ፤ ዙፋኑ የወርቅ ሲሆን በንጉሠ ነገስት ምኒልክ ስር ሆኖ የሚገዛው ግዛትም ሽሬ፣ ሠሜን መደባይ፣ አደይ አቦ፣ መረብ፣ ወልቃይት ጠገዴ ፣ወገራ፣ ጃኖራ፣ ሰቀልት፣ በጌምድር፣ ጭልጋ ነበር። መቀመጫው ከንጉሠ ነገስቱ አቅራቢያ ነበር። በተጨማሪም ሠራዊቱን ያዛል፣ ከንጉሰነገስቱ ጋር ይመካከራል፣ ህዝቡን፣ መኳንንቱንና መሳፍንቱን እያስጠራ ልዩ ልዩ ጉዳዮችን ያስፈፅማል። በዚህም የሠሜን አጋፋሪ የሚል ስያሜ ተሠጥቶት ነበር።
4. ኤልያብ የእሴይ ልጅ የሠለሞን እኅት፤ ከንጉሰነገስቱ በስተግራ ይቀመጣል። ንጉስ ነው። ዙፋኑ፣ የመታጠቢያው ዳታኑና ወንበሩ የወርቅ ነበር። ከንጉሰነገስቱ በታች ሆኖ ስዩመ ተንቤን ተብሎ ከባህረ ተከዜ እስከ ሃገረ ናግራን/የመን/ ድረስ ያስተዳድር ነበር።
5. ሔት፤ የዳዊት የልጅ ልጅ የአምኖን ልጅ ነው። ዙፋኑ ወንበሩና ዳታኑ የወርቅ ነበር። ከንጉሰነገስቱ በታች ይቀመጣል። የአስተዳደር ወሠኑም ከተከዜ እስከ ወንበራ፣ ነጭ አባይ ማዴ፣ እናርያ /ከፋ/ ፣ስናር፣ ቋራ፣ አቸፈር፣ ወለጋ፣ ጎንደሳ .... ነበር። ንጉስ ነገስቱን ወክሎም ይዘምታል።
6. ኢዩኤል፤ ዙፋኑ ወንበሩም ዳታኑም የወርቅ ነበር። ከንጉሰነገስቱ በግራ በኩል ይቀመጣል። ከዝቋላ ድራሬ እስከ በሽሎ ወንዝ ይደርስ ነበር።
7. አብሔል፤ ከነገደ ብንያም የተወለደ። ዙፋኑ የብር ሲሆን፤ ታጥቆ ይቆማል። የግዛት ወሠኑም ሉቅማጅ፤ ሴቃ፤ ትቤ ከተማው /መቀመጫው/ እናርያ ነበር።
8. በልዳድ፤ ከከነዓን የተወለደ። ዙፋኑ የብር ሲሆን የግዛት ቦታው ገዝዋ ጃፋር የተባለ ቦታ ነበር። የአብሔል ታዛዥም ነበር።



9. አሴር፤ ከነገደ ይሁዳ የተወለደ። ዙፋኑ የብር ነው። የግዛት ወሠኑ ኩሉ ጋታ፣ አሩሲ፤ጅንካ ፤ ሮቸሉሚ ነበር።
10. ሳቤቅ፤ የቤተልሔም ተወላጅ የአሚናዳብ ዘር ነው። ዙፋኑ የብረት ሲሆን ከተማው ሳይንት ነበር።
11. ሱርባ፤ ከመሳፍንት ወገን የሆነ፤
12. ጉርባ፤ ከመሳፍንት ወገን የተወለደ ሲሆን፤ ሱርባና ጉርባ በአንድ አይነት ስልጣን በተሠጣቸው ግዛት ንጉስ ሆነው ያስተዳድሩ ነበር። ዙፋናቸውም የብር ነው።

ከላይ የተዘረዘሩት ለየሹሞቹ የተሰጡት ግዛቶች /ቦታዎች/ አንዳንዶቹ በዚህ ዘመን መጠሪያ ስማቸው መቀየሩ እንዳለ ሆኖ፤ በጥንቱ ስያሜያቸው ዛሬ ድረስ የሚጠሩ የኢትዮጵያ ከተሞች አሉ። ስለዚህም በርካታ ግዛቶች በአሁኗ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ግዛቶች ናቸው። ነገር ግን ቀዳማዊ ምኒልክ የቢሁች ሹሞችን ወደ ሩቅ አገር ሲያስማራ አናይም። የኢትዮጵያ የግዛት ወሠን ግን በእርሡም ዘመን ያው እንደ እናቱ ግዛት ግዙፍ እንደነበር የታወቀ ነው።

በእርሱ ጊዜም ሆነ በንግስተ ሳባ ጊዜ በናፓታ ቀደም ሲል በንጉሰነገስትነት የነበሩና አሁን በንጉስነት የተወሰኑ ገዥዎች እንደነበሩ እንረዳለን።

የሆነ ሆኖ በዚህ መሠል ሐይማኖታዊ ይዘት ባለው ፤ ማለትም የኦሪት ህግን መሠረት ያደረገ የአነጋገስና የአሿሿም ስልት ያየነውን አይነት ቅርፁን እንደያዘ የቀጠለው በጥቂት ተከታታይ ነገስታት እንጅ እስከመጨረሻው ሊዘልቅ አልቻለም። ምክንያቱም ከቀዳማዊ ምኒልክ በኋላ በናፓታና በመርዌ የነገሱት ንጉሰነገስቶች የግብፆችን አማልክት ማምለክ ጀምረዋልና ነው።

ይሁን እንጂ በጥንታዊው አክሱምና አካባቢው የሚኖሩ ህዝቦች በግለሰብ ደረጃ ማለትም የመንግስት ሐይማኖት መሆኑ በቀረበት ጊዜ ኦሪት ህግን የሚያራምዱ ህዝቦች እንደነበሩ ይታወቃል።

በተመሳሳይ ከምኒልክ መምጣት በፊት ኦሪት ህግ ስለማይውቅና ባእታት ይመለኩ ስለነበር ምኒልክና ተከታዮቹ ኦሪት ህግን ይዘው ከገቡና ካስተማሩም በኋላ በቀድሞው የጣኦት አምልኮ የቀጠሉ ህዝቦች መኖራቸው ግልፅ ነው።

በአጠቃላይ አክሱምና አካባቢው ከቀዳማዊ ምኒልክና ከእናቱ ማክዳ ጀምሮ ቢታወቅም ፤ እንዲሁም ከእርሱ በኋላ ጥቂት ጊዜ ቆይቶ እንደገና መናገሻው ወደ ናፓታ በመዛሩ አክሱምና አካባቢው ለሁለተኛ ጊዜ ወይም እንደገና መናገሻ እስኪሆን ድረስ ለብዙ ምዕተ ዓመታት ደብዝዞ ቆይቶ በኋለኛው ዘመን እንደገና ሊገን ችሏል።

# ምዕራፍ ፲፬
# ከንጉስ ሐንድዮን እስከ ንጉስ ተዋስያ 2ኛ
# ከ 957-810 ቅ.ል.ክ

ከቀዳማዊ ምኒልክ ቀጥሎ በኢትዮጵያ የነገሰው በነገስታቱ ዝርዝር ማለትም ከንግስተ ሳባ ጀምሮ ባለው ቁጥር 3 ላይ የሠፈረው ንጉስ ሐንድዮን ነው። ንጉስ ሐንድዮን ከ957 እስከ 956 ቅ.ል.ክ ድረስ ለአንድ ዓመት ያህል ብቻ በንግስና ቆይቷል። እንደ አገር ውስጥ የታሪክ ሠነድ ማስረጃነትም የቀዳማዊ ምኒልክ ልጅ እና አሪታዊ ንጉስ ነገስት እንደነበር ይነገራል። ከዚህ ያለፈ ነገር የለውም።

## ንጉስ ሲራህ 1ኛ ከ956 -930

ከሐንድዮን ቀጥሎ በኢትዮጵያ የነገሰው በዝርዝሩ 4ኛ ላይ የሠፈረው ሲራህ 1ኛ ሲሆን፤ ኢትዮጵያን ለ26 ዓመታት አስተዳድሯል።

ሲራህ 1ኛ የተባለው የኢትዮጵያ ንጉስ በነገሰ በ10ኛው ዓመት አንድ ሚሊዮን የእግረኛ ጦር ከመላው የኢትዮጵያ ግዛት ሠብስቦ በ300 ሠረገላ የተቀመጡ ሠራዊቶችን ይዞ ግብፅን ወረረ። ከዚያም የግብፅን ምርኮ ይዞ ወደ ፓለስታይን ዘምቶ ተሸነፈ። በዚህ ሽንፈቱም ከግብፅ ድሉ ያገኘውን የምርኮ ሐብት ሳይቀር አስረክቦ፣ ብዙ ወታደሮቹንም አስጨርሶ ተመለሠ። /2ኛ ዜና መዋ. ምዕ 14 ቁ-9-13 የሠፈረው ዕሁፍም ይህንኑ ነው የሚገልፀው።/

## ንጉስ አሜን ሖቴቭ ዘግዱር ከ930-889

ከሲራህ 1ኛ ቀጥሎ አሜን ሖቴቭ ዘግዱር ነው የነገሰው። ከ930-889 የነገሰውና በዝርዝሩ 5ኛ ላይ ያየነው ንጉስ ዘግዱር ኢትዮጵያን ለ41 ዓመታት ገዝቷል። ቶማፅዮን በሚል ቅዕል ስሙም ይታወቃል። ቶማፅዮን ማለት ደግሞ የፅዮን ፀሃይ ወይም የፅዮን ንጉስ ማለት ስለሆነ፤ አሪታዊ ንጉሰነገስትነቱን ያመለክታል። በተጨማሪም ዘግዱር የሚለው የስሙ ስያሜ ግዕዝኛውን የግዱር ስለሚመስል ስያሜው ወደ ሳባዊነት እንደሚጠጋ ያሳያል።

ዘግዱር ማለት በግዕዝ ገፊ ማለት ሲሆን፤ የዚህ ንጉስ እናት እርሱን በወለደች በአንድ ወሯ ስለሞተች ስሙ ከወጣለት በኋላ ዘግዱር የሚለውን ቅዕል ስም እንዳገኘ ይነገራል። እርሱ ከሞተ በኋላም አክሡማይ ራሚሱ የተባለው ንጉስ ተተካ።



## ንጉስ አክሱማይ ራሚሱ ከ889-969

አክሱማይ ራሚሱ 20 አመት በቆየ የግዛት ዘመኑ ምን እንደፈፀመ ባይታወቅም ከእርሱ ቀጥሎ የነገሰው በዝርዝሩ 7ኛ ላይ የሠፈረው ሲራህ 2ኛ ግን መጠነኛ ታሪክ አለው።

## ንጉስ ሲራህ 2ኛ ከ869-831

ንጉስ ሲራህ 2ኛ ወረደ ፀሃይ የሚል ስመ መንግስት የመሰለ ቅዕል ስም አለው። ይህ በዝርዝሩ 7ኛ ላይ የተቀመጠው ንጉስ ኢትዮጵያን ለ 38 ዓመታት ያህል አስተዳድሯል። በዘመኑ ከፈፀማቸው ታሪኮች ውስጥም ከላይ ያየነውን የሲራህ 1ኛን ወደ ፓለስታይን ዘምቶ ተሸንፎና ብዙ ወታደሮች አልቀውበት ስለነበር፤ የእርሡን ደም ለመበቀል እንቅስቃሴ አድርጓል።

በዚህ እንቅስቃሴም ጦሩን አደራጅቶ ወደ ፓለስታይን በማምራት ዮራም ከተባለው ከእስራኤል ንጉስ ጋር ተዋግቶ አገሩን አጠፋፍቶ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሷል። 2ኛ ዜና መዋዕል ምዕ 21 ከቁ. 16-17 ያለውም ይህንኑ ያረጋግጣል።

## ንጉስ ተዋስያ ከ831-810

ከሲራህ 2ኛ ቀጥሎ የነገሰው ተዋስያ ወይም አውስያ የተባለው ነው። እርሱም ኢትዮጵያን ለ21 ዓመታት ገዝቷል። የንግስና ስሙም ልክ እንደ ሲራህ 2ኛ ወረደ ፀሃይ የተሠኘ ነው። በዝርዝሩ 8ኛ ላይ ተቀምጧል። ትውልዱም ከቀዳማዊ ምኒልክ የወረደ እንደሆነ ይነገራል። የዘር ተዋረዱም ምኒልክ አትራምን፣ አትራም አብራልዮስን ሲወለድ፤ አብራልዮስ ደግሞ ከኑብያ ኢትዮጵያ ከሚገኙ ከአሞን ሊቀ ካህናት ዘር አንዲት ሴት አግብቶ ተዋስያን ወለደ። ተዋስያ በንግስና ዘመኑ የአሪትን ካህናትና የአሞንን ካህናት አከራክሮ በክርክሩ የአሞን ካህናት ስላሸነፉ እርሡ ራሱ ከክርክሩ በኋላ አሪታዊነቱን ክዶ ወደ እናቱ ሐይማኖት ወደ አሞን . አምልኮ ዞሮ አሪታውያኑን እንደተጫናቸው ወይም እንዳጠቃቸው በሙሴ ጃን ሞሪዮ መፅሐፍ ተጠቅሷል።

እንግዲህ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የመንግስት ሐይማኖት ከኦሪተ ህግ ወደ አሞን /የግብፆች አምላክ/ን ማምለክ እንደተጀመረ መረዳት እንችላለን።

እንደተባለውም የጋብቻ ትስስር ተፈጥሮ፣ የሐይማኖት ለውጥ ተደርጎ፣ የመናገሻ ከተማ ለውጥም ሲደረግ የምናየው ከዚሁ ከንጉስ አውስያ ጀምሮ ነው። ከዚህ አንፃር ጥንታዊቷ የሳባ ከተማ የመናገሻ ከተማ ሆና የቆየችው ከንግስተ ሳባ እስከ ንጉስ አውስያ ድረስ ነበር ማለት ነው። ከዚህ በኋላ ባለው ጊዜ ነገስታቶቻችን መቀመጫቸውን መልሰው በናፓታ ሲያደርጉ እናያለን።

## ምዕራፍ ፲፫
## የኢትዮጵያ ግዛት በግብፅ ላይ
## በንጉስ ፒያንኪ 2ኛ ዘመነ መንግስት
## ከ810-778 ቅ.ል.ክ

በኢትዮጵያ የነገስታት ታሪክ እጅግ ስመጥር ከተባሉት ውስጥ ፒያንኪ 2ኛ አንዱ ነው። የፒያንኪ 2ኛ መናገሻ ናፓታ ነው። እርሱም የተዋስያ /የአውስያ/ ልጅ እንደሆነ ይነገራል። ሐይማኖቱም በአሞን ጣኦት መሆኑ በደንብ ያታወቃል።
ፒያንኪ 2ኛን ሜሪአሙን በሚል ስምም ይጠሩታል። ትርጓሜውም ካህኑ ንጉስ ማለት ሲሆን፤ የህይወት መቅደስ በእርሱ ላይ ነው ይሉታል። ፒያንኪ ፍቅሩ ለአሞንም ይባባል።

በዚያ ዘመኑ የግብፃዊ አፃፃፍ በሃይሮግላፊ ስሙ ሲፃፍና ሲነበብ ፒያንኪ የሚል ሲሆን፤ በኛ ታሪክ ነገስት ላይ ደግሞ ፒያንኪያ ወይም ህዝባይ እንደገናም አብራልዮስ ተብሎ ሠፍሮዋል።

ከአምላኩ ከአሞን ጋር የነበረውን ጥልቅ ፍቅር ቀጥለን ስናይም ሊያመሠግነውና ሲምልበት እግረ መንገዳችንም ስለአማልክቱ የነበረውን ሁኔታ እንገነዘባለን። ፒያንኪ 2ኛ በናፓታ መቀመጫውን አድርጎ ኢትዮጵያን በሚገዛበት ጊዜ በግብፅ የነበረው ንጉስ ተፍንክታ የተባለው ፈርኦን ነበር። ይህ ፈርኦን በከፊል ግብፃውያን ዘንድ ተቀባይነት አልነበረውም። እነዚሁ ለተፍንክታ አንገዛም ብለው ለጦርነት የተሠለፉ ግብፃውያንም ፒያንኪን እንዲረዳቸው ጠይቀውት /ልከውበት/ ነበር። ፒያንኪም ፑአርማና ሉአሜርስኪን በሚባሉ በሁለት የጦር አለቆቹ የሚታዘዝ ጦር ከናፓታ ወደ ላእላይ ግብፅ ልኮ እርሱ ደግሞ በከተማው ተቀምጦ ሌላኛውን ዋናውን ጦሩን ማደራጀት ጀመረ።

ፒያንኪ 2ኛ በምን አይነት ሁኔታ ግብፅን ድል እንዳደረገ የሚያስረዳው በርካታ የታሪክ ሠነድ ከመኖሩም በላይ፤ በጥንቱ አጠራር ናፓታ ዛሬ ጀበል ባርካ በሚባለው ስፍራ እራሱ ባሰራው ሐውልት ላይ የሚገኘው ፅሁፍም ተጨማሪ ማስረጃ ነው።

ሙሴ ማርዮት የሐውልቱን መጠን ለክተው ፅሁፉን እንደገለበጡትና ሙሴ ደ. ሩጂ ወደ ፈረንሳይ ቋንቋ እንደተረጎሙት፤ እንዲሁም ታላቁ የአገራችን ታሪክ ፀሐፊ ተክለፃድቅ መኩሪያ ወደ አማርኛ እንደተረጎሙት የሐውልቱ ርዝመት አንድ ሜትር ከሠማንያ፣ ስፋቱ ደግሞ አንድ ሜትር ከሠማኒያ አራት፣ ውፍረቱ አርባ ሶስት ሴ.ሜ መሆኑ ታውቋል።

በላዩ ላይ በሁለቱም በኩል በቱ-አብ /ንፁህ ተራራ/ የሚቀመጠው የዓለም ዙፋኖች ጌታ የአሞን ምስል ፣ከፊት ለፊቱ የንጉስ ፒያንኪ ምስል ሲታይ፤ ሶስት የግብፅ ነገስታት ተንበርክከው ሲሠግዱለት፤ ሌላኛው ንጉስ



ደግሞ በግራ እጁ ለግብር ያመጣለትን የራሱን ፈረስ፣ በቀኝ እጁ ፀናፅል ይዞ ሚስቱን እንድታማልደው ከፊት አስቀድሞ ይታያል።

ከእነዚህ ምስሎች በታች ደግሞ በሐውልቱ በሁለቱም በኩል 150 በሚሆኑ መስመሮች ላይ በዚያው በጥንቱ የግብፃውያን አፃፃፍ የተፃፈውን ታሪኩን ይዘረዝራል።

በዚህ ፅሁፍ የመጀመሪያው መስመር ላይ እንዲህ የሚል ፅሑፍ ሰፍሯል። "ዘለዓለም ህያው የሆነው ፒያንኪ የታህታይና የላእላይ ግብፅ ንጉስ በነገሰ በ21ኛው ዓመት በቶት ወር ግርማዊነቱ እንዲህ አለ።

"ከአባቶቼ ይበልጥ የሠራሁትን ስሙ፤ በቱም /በማታ ፀሃይ የሚመሰል አምላክ/ አምሳል ከአማልክት የሠረፅኩ ንጉስ ነኝ።"

ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ "ከእናቱ ማህፀን ለንጉስነት የተመረጠ .... መሳፍንት ያከበሩት፣ በአማልክት ዘንድ የተወደደ፣ ራሱ ደግ አምላክ፣ የፀሃይ ልጅ፣ ፀሃይ በገዛ እጆቿ የፈጠረችው ፒያንኪ ሜሪአሙን" የሚለው ፅሁፍ ይገኛል።

ቀጥሎ ደግሞ ቀደም ሲል የላካቸው ሁለት የጦር አለቆቹ የግብፅ ፈርኦን የተፍንክታ ሠራዊት የማይደፈር መሆኑን የሚገልፅ መልዕክት ልከውለት ስጋታቸው ይነበብና፤ የእርሁ ምላሽ ይቀጥላል።

ፒያንኪ 2ኛ መልዕክቱን ከሠማ በኋላ ለጦር አለቆቹ ለፑአርማና ለሉአሜርስኪን እንዲህ ብሎ ላከባቸው። "ወደ ሔሬክሊዮፖሊስ ሒዱ። ተዋጉ፤ ሰውንም፣ ከብቱንም፣ በወንዝ ላይ የሚገኙትን ጀልባዎች ሁሉ ማርኩ። ማንም ሠው ወደ አደባባይ ወጥቶ አይስራ። ገበሬም አይረስ። ከተማዋን ክበቡ። ያለስንፍናም ውጉት።

ይህን መልዕክት ቴብ ላሉት የጦር አለቆቹ ከላከ በኋላ ለእንርሱ የሚሆን ሌላ ተጨማሪ ጦር ከናፓታ ለመላክ አዘጋጀ። ለጦር ሠራዊቱም ጉዞ ከመጀመራቸው በፊት ከዚህ ቀጥሎ ያለውን የምክር ቃል ነገራቸው።

"እንደ ጨዋታ በሌሊት አትውጉ። ነገር ግን ወታደሩን ሰብስቦ ወደ እናንተ ሲጓዝ ተዋጉት። ...ጦርነቱም ሲጀመር ሲል አምላካችን አሞን እንደላከን አስቡ። በቴብ ከተማ ስትደርሱ ቀስትና ጦራችሁን አስቀምጣችሁ በአፒ /ሐፒ ኮርማው አምላክ/ ትይዩ ባለው ወንዝ ተንከራችሁ፣ ታጥባችሁ በጥምቀት ሠውነታችሁን አንፁ።

ከመካከላችሁ ማናቸውም ሹም የጌታን /የአሞንን/ ቃል አይጣስ፣ ያለ እርሱ ማንም ወታደር ዋጋ የለውም። የተሠበረውን ክንድ አሸናፊ ሊያደርገው ይችላል።

ብዙዎችን ያደክማል፣ አንዱን ሠው ከብዙ ሺ ሠው እኩል ያደርጋል።.... በመሠዊያው ፊት ባለው ውሃ ታጠቡ። በፊቱም ተደፍታችሁ እንደዚህ በሉት።

"በሠይፍህ ጥላ ውስጥ ለመዋጋት የምንችልበትን መንገድ ምራን። የምትልከው ልጅ ብዙዎችን ያስፈራውን ተፍኝክታን ያስደነብራል"። ፒያንኪ ይህን ተናግሮ ሲጨርስ ወታደሮቹ ሁሉ እንዲህ በማለት በፊቱ ተደፉ።
"ለኛ ሀይፋችን ስምህ ነው። ጥበብህ ሠራዊትህን ትመራለች። ህብስትህ በአካላችን ውስጥ ሆኖ ለጉዟችን ስንቅ ነው። ወይንህም ጥማችንን ያረካል... ድል አድራጊ ንጉስ ነህ። ...."

ከዚህ በኋላ ወታደሩ ወደ ሠሜን ጉዞውን ጀመረ። በመርከብ /በጀልባ/ የአባይን ወንዝ እየተከታተሉ ሲጓዙ የፒያንኪን ጦር ለመዋጋት በመርከብ ሆነው ከሠሜን ወደ ደቡብ ከሚመጡት ጋር ድንገት ተገናኝተው ውጊያ ተጀመረ።

ከሁለቱም ወገን በርካቶች ካለቁ በኋላ የፒያንኪ ወታደሮች አሸነፉ። የማረኩትን ሠራዊትና መሳሪያም ወደ ጌታቸው ልከው ጉዟቸውን ቀጥለው ሔሬክሊዎፓሊስ ከተማ ደረሡ። ተፍኝክታም በበኩሉ ጦሩን ይዞ ተዘጋጅና ገጠማቸው። ነገር ግን እንደማይችል ሲረዳ የፓፒካን ወንዝ ተሻግሮ ወደ ታህታይ ግብፅ ሸሸ። የሸሸውም በርካታ ሠራዊቶቹ በቅፅበት ሲያልቁበት ስላየ ነው።

የፒያንኪ ጦርም የግብፅን ከተሞች አንድባንድ እየተቆጣጠሩ የየከተሞችን ነገስታት ከነሠራዊታቸው እያሸነፉ ከተማዋን ከበቡዋት። እንደከበቧትም ለንጉሳቸው ለፒያንኪ 2ኛ ደስ እንዲለው የሆነውን ሁሉ ላኩበት። ሆኖም ድሉ ሙሉ አልነበረም።

ፒያንኪ ግን በዚህ ድል ከመደሰት ይልቅ የተፍኝክታን ማምለጥና የሔሬክሊዮፖሊስ ከተማ ንጉስ የነበረው የኒምሩድን ከነሠራዊቱ መሸጎ መቀመጥ በሠማ ጊዜ፤ እጅግ ተቆጥቶ ለመልዕክተኛው "ለወሬ ነጋሪ እንኳን ከታህታይ ግብፅ አንድ ወታደር ከተረፈና ሁሉንም ድል አድርገው ማምታት ካቃታቸው እኔው ራሴ እንደምሄድ በህይወቴ በፀሃይ አምላክ ፍቅር የሆነው አባቴ አሞን ባደረገልኝ ቸርነት እምላለሁ።

"ሔጄም የሠራውን ሁሉ አፈራርሰዋለሁ። ጦርነቱንም በቃኝ እንዲል አደርገዋለሁ። በዓመቱ መጀመሪያ ላይ ስርዓተ ክህነቴን ፈፅሜ በዓሉ በሚውልበት ጊዜ ለአባቴ ለአሞን ስለቴን በሚያምረው በዓሉ ቀን አቀርብለታለሁ።

"በደመቀ በዓልም ወደ ቴብ ገብቶ በቤተ መቅደሱ ዙፋን ላይ እንዲቀመጥ አደርገዋለሁ። በዚያን ጊዜ የታህታይ ግብፅ ቅጣቱን እንዲያጣጥም አደርገዋለሁ"። የሚል መልዕክት ላከ። የጦር አለቆቹም የንጉሳቸውን ቁጣ በሠሙ ጊዜ በስጋትና በአዲስ ወኔ ተነሳስተው እንደገና በመዋጋት ብዙ ጀብድ ፈፅመው፤ የቀሩ አንዳንድ ከተሞችን መያዛቸውን በድጋሚ ላኩበት። ፒያንኪ ግን በዚህ ድልም ቁጣው አልበረደም።

ስለዚህም እርሱ ራሱ ሄዶ በሠራዊቱ መካከል ተገኝቶ አመራር እየሠጠ ካልተዋጋ በፍጥነት ሙሉ ድል እንደማይገኝ ተረዳ።



ስለዚህ የቶት ወር በገባ በ9ኛው ቀን ሠራዊቱን ይዞ ከናፓታ ተነስቶ በመርከብ ተጉዞ ወደ ቴብ ከተማ በደረሰ ጊዜ ዘውዱን እንደደፋ ከመርከብ ወረደ። ተዘጋጅቶ በተቀመጠለት በሚያምር ሠረገላ ተቀምጦ ወደ ሔሬክሊዮፖሊስ ሄደ።

እንደደረሰም በፊቱ ለቆሙት ሹሞቹ "በዚህ አይነት እየተዋጋችሁ የትዕዛዜን ፍፃሜ የምታዘገዩት ከሆነ የማደርገውን ሹበር ለታህታይ ግብፅ አሣያታለሁ።" ካለ በኋላ በእርሱ መሪነት የሚደረገው ውጊያ ተጀመረ። በሶስተኛው ቀን ነምሩድና ተከታዮቹ በመሸጉበት ምሽግ ውስጥ እንዳሉ ብዙ ጥቃት ደረሠባቸው። ወዲያውም ከምሽጉ እየወጡ የከበሩ ገፀበረከቶችን የያዙ መልዕክተኞች እየመጡ የይቅር በለን ጥያቄ አቀረቡ።

ንጉስ ነምሩድም ሚስቱን ለአማላጅነት ወደ ፒያንኪ ላካት። እርሷም ወደፒያንኪ ሴት ልጆችና እህቶቹ ሠፈር ሔዳ "ንጉስ ፒያንኪን አራሩልኝ፤ መንፈሱ ከፍ ያለ ፍርዱም ታላቅ ናትና ...." በማለት ተማፀነች። በእነዚህ ሴቶች አማላጅነትም ፒያንኪ ልቡን አለሠለሰ።

ንጉስ ነምሩድም ዘውዱን እንዳደረገ ወደ ፒያንኪ መጥቶ፡- "የህይወትን መንገድ ዘጋህ፤ እንደ ፍላፃ ወደ ሠማይ ብበር እንኳ ትደርስብኛለህ ። የደቡብ አገሮች ተሸነፉ፤ የሰሜኖቹም አጎነበሡ። በጥላህ ስር መኖር እንቻል። ሌሎች የግብፅ ከተሞች ነገስታት የገበሩልህ ይቆጠርና እኔ ከእነርሱ የበለጠ እሠጣለሁ።" አለው

ከዚያም ወርቅ፣ ብር፣ እንቁ፣ መሳሪያና ሌሎች የዘመኑ ተፈላጊ እቃዎች ሁሉ ለፒያንኪ ተሠጡና ጊዜያዊ ግምጃ ቤቱ ሞላ። ቀጥሎም እርሱ ራሱ በቀኝ እጁ በሠማያዊ እንቁና በወርቅ የተሠራ ፀናዕል ይዞ መጥቶ ለንጉስ ፒያንኪ አቀረበ።

ሌሎችም በተመሳሳይ ገፀ በረከት እየያዙ ወደ ፒያንኪ እየመጡ መግባታቸውን ቀጠሉ።ብዙዎቹ ድል ከተደረጉ በኋላም ሮህን የምትባል አነስተኛ ከተማ ቀርታ ነበርና፤ ፒያንኪ ወደዚች ከተማ ተጓዘ። በዚች ከተማ በርካታ የታህታይ ግብፅ ወታደሮች መሽገው ነበር።
ትልልቆቹ ከተማዎች ያልመለሱትን የኢትዮጵያ ሠራዊት ይች ትንሽ ከተማ አመክታለሁ ብላ ማሰቧ ፒያንኪን ከማስገረም አልፎ በውስጧ ለመሸጉት ወታሮች እንዲያዝንላቸው አደረገው። እናም እንዲህ የሚል መልዕክት ላከባቸው።

"የጥንት ፈርኦኖች ኢትዮጵያውያንን አስገበርን በማለት ፋንታ "ምስኪኖችን አስገበርን" ብለው ነበር። አሁን ያ የማከሠሥ ቃል በፒያንኪ 2ኛ ተለውጧል። እናም እናንተ በሞት የምትኖሩ ደካሞች፣ ምስኪኖች ፣ የምሽጋችሁን መዝጊያ ሳትከፍቱ ጥቂት ጊዜ ያለፈ እንደሆነ በማደርሠው አልቂት ሐላፊዎች ትሆናላችሁ /ሃላፊነት ትወስዳላችሁ/ ለህይወት የከፈትኩላችሁን መዝጊያ አትዝጉ .... ሞትን አትምረጡ፣ በአገር ፊት ህይወትንም አትናቁ"።

ይህን ቃል ሲሠሙ ሳያመነቱ በፍጥነት እንዲህ የሚል መልዕክት ላኩ።

"የእምላክ ጥላ በራስህ ስላለ፣ ክንዱን ከሠጠህ፣ ቃልህ ከአምላክ እንደበት እንደወጣ ተቆጥሮ ወዲያው ይፈፀማል። አምላክ እንደወለደህ በስራህ ሁሉ ይታወቃል። ከተማዋና መዝጊያዎቿ ከስልጣንህ በታች ናቸው። እንደልባችን አስወጣን አስገባን።" ይህ ቃል በደረሰው ጊዜ ፒያንኪ ጦርነቱን ትቶ ለመናኞቻቸውን ሠምቶ በሠላም እንዲወጡ ፈቀደላቸው።
ፒያንኪ በሠላም ለሚማረክ ጠላት ሩህሩህ እንደነበረ ነው የሚነገረው። በጦርነት ላይ ካልተገደደ በቀር ነብስ በከንቱ ማጥፋት አይወድም ነበር ይባልለታል። የሚዋጋውንም አገር ቀድሞ ሳያ ስጠነቀቅና ሳይመክር ውጊያ አይጀምርም። የጦር አለቆቹም በዚህ አይነት መመሪያ እንዲዋጉ ነው የሚነግራቸው።

ትዕዛዝና ምክር ሲሠጥም ንግግሩ በምሳሌና በሚደነቅ ፍልስፍና የታጀበ ሆኖ፣ ግልፅና አጭር እንደነበር ነው የሚታወቀው።
የሮህን ከተማ ከያዘ በኋላም ሜሪቱም ወደምትባለው ከተማ በመምራት የመሸጉትን ሠራዊቶች ከነመሪዎቻቸው የተለመደውን አይነት ቅድመ ማስጠንቀቂያና ምክር አስቀደመ። እንዲህም ብሎ ላከ።

"በፊታችሁ ሁለት የመንገድ መስመር አስቀምጡ። እንደፍላጎታችሁም ምረጡ። ምሽጋችሁን /ቀጥራችሁን/ ብትከፍቱ ህይወትን፣ ብትዘጉ ሞትን ታገኛላችሁ። ግርማዊነቴ በተዘጋ ከተማ ላይ ማለፍ አይችልም።" ሲል እነርሱም በፍጥነት "አባትህ የውርሱን ቅርስ ላንተ አዘጋጅቶልሃል። የሁለቱ ዓለሞች የኢትዮጵያና የግብፅ ጌታ እንደመሆንህ፤ እነሆ ገንዘቦችህ ናቸው። ዓለምን የምትገዛ ጌታ ነህ።" የሚል ምላሽ ሠጡት።

ፒያንኪም ከዚህ በፊት እንዳደረገው ሁሉ እጃቸውን በሠጡ ከተሞች ላይ እየዞረ ቤተመንግስታቸውን እየጎበኘና ለአማልክቱ በየቤተመቅደሡ የ[illegible]ን እያደረገ፤ እሺ ያሉትን በሠላም፣ እምቢ ያሉትን በጦርነት እያሸነፈ ብዙዎቹን በስሩ አደረገ። በርካቶቹም "የአሞን ልጅ ፒያንኪ የኢትዮጵያው ንጉስ መጥቷል" የሚለውን ወሬ እስከፈፀመው ጅብድ ሲሠሙ እጃቸውን ሲሠጡ ተገደዋል። አካሄዱ ሁሉ ልክ እንደ ታላቁ እስክንድር እንደነበርም ይነገርለታል። ሒደቱ በዚሁ ቀጥሎ ብዙ ከተሞች በፒያንኪ ስር መሆን ቢችሉም፤ ቀደም ሲል ሸሽቶ አመለጠ ያልነው የግብፅ ዋና ፈርኦን ተፍነክታ ገና አልተያዘም። ይልቁንም ለውጊያ ዝግጅት አድርጎ ሉካሪስ እና አስርኮን የሚባሉትን ሁለት ንጉሶች ከጎኑ አድርጎ በመጠባበቅ ላይ ነው።

በተጨማሪም ታላቋና የፈርኦኖቹ መቀመጫ ከተማ የሆነችው መምፊስ ገና አልተያዘችም። ተፍነክታም ከነተከታዮቹ የመሸገው በታላቂቱ ከተማ በመምፊስ ነበር። እናም ፒያንኪ ወደ መምፊስ ተጓዘና እንዲህ የሚል መልዕክት ላከ።



"በዚች ከተማ ውስጥ የምትኖሩ መዝጊያችሁን አትዝጉ፣ አትዋጉ።.... እርምጃዬን ያልገፋችሁ እንደሆነ በመምፊስ ለሚገኙ አማልክት መስዋዕቴን አቀርባለሁ። የነበረውን ስርዓት ሁሉ
እፈፅማለሁ። ከተማዋን በመልካም እይዛታለሁ፤ ትደነግማለች። የህፃናት ዋይታ አይሰማም። ተመልከቱ የደቡብን ከተሞች፤ የአምላክን ቃል ካልሠሙት በቀር አንድ ሠው እንኳ አልተገደለም። ስቃይ የተሠራው ለሃጥአን ነው"

በዚህ ጊዜ ፈርኦን ተፍነክታ ከሠሜን ወደ መምፊስ መጥቶ "የመምፊስ ከተማ ሃይለኛ ናት። ወታደሮቹም ጎበዞች ናቸው። በምስራቅም በኩል በባህር የተከበበች ስለሆነች ጠላትን አታስገባም።" ያለው ከመምፊስ መጥቶ ወደ ሠሜን አቅጣጫ ከሄደበት ሆኖ ነው።

"ገንዘብ፣ ዘይት በሠሜን ላሉት ወታደሮቼ ስጥቼ ከሠሜን ተመልሼ እስክመጣ ድረስ ተከላከሉ" ብሎ ስላዘዛቸው በፒያንኪ ማስጠንቀቂያ መሠረት የተፍነክታ ሹሞች ቀጥሩን ሊከፍቱ አልቻሉም።
ፒያንኪ ይህን ሁኔታ ካረጋገጠ በኋላ ወደ ከተማዋ ተጠግቶ በምስራቅ በኩል የወንዙ ውሃ መሙላቱንና ከተማዋ ከቀድሞው የበለጠ በደንብ መመሸጓን እየዞረ ተመለከተ።

የፒያንኪ ሹማምንትም ሁኔታውን አይተው ፍርሐት የሚያሳድር አስተያየታቸውን ሠጡ። ፒያንኪ ግን የሹሞቹ አስተያየት አስቆጣውና እንዲህ የሚል ምላሽ ሰጣቸው።

"በሕይወቴ ፍቅር በአባቴ በአሞን ቸርነትና ፀጋ ይሄን ሁሉ ያደረኩት በአሞን ትዕዛዝ ነው። አሞንን በልባቸው አላስቀመጡትም። ትዕዛዙንም አላወቁም። ይህንንም ሁሉ አሞን ያደረገው ልባቸውን ያፀናው የሹበሩን ሐይል ለማሠማት ሲል አውቆ ነው። እንግዲህ ይችን ከተማ እንደ ማዕበል ሆኜ እንዳነሳት አባቴ አሞን አዟል።"

ከዚህ በኋላ "ጀልባዎችን፣ ታንኳዎችን፣ መርከቦችንም ሁሉ ሰብስቡ" ብሎ አዘዘ። በባህሩ በኩል አድርገው ወደ ከተማው ውስጥ ሲገቡ ለተዘጋጁት ወታደሮቹ እርሱ ራሱ አዛዥ ሆኖ ወደ መርከቡ ከገባ በኋላ ተከታዩን ትዕዛዝ ሰጣቸው።

"ግማሻችሁ ከተማዋን ውጉ። ግማሻችሁ ደግሞ በበር በኩል ወደ ውስጥ ግቡ። የሚማረክ ሹም ስታገኙ አይገባምና እንዳትገፉት። ደቡብንና ሠሜንን ከያዝን በኋላ በሁለቱ አገሮች መካከል ባለችው በዚች በመምፊስ እረፍት እናደርጋለን።"

ይሄን ከተናገረ በኋላ የፒያንኪ ወታደሮች ወደ ከተማዋ ገብተው ብዙ ሠው ጨረሱ። ቀጥሎም ራሱ ፒያንኪ ከነሠራዊቱ ገብቶ ትልቋን ከተማ መምፊስን ያዛት።

ዜና መዋዕሉ እንደሚለው በድሉ ማግስት ብዙ ሹማምንት ከነሕይወታቸው ተማርከው እፊቱ እንደቀረቡ፤ ፒያንኪም ቤተመቅደሶች

እንዲከበሩ አገዘ የገባላቸውን ቃል ተግባራዊ እንዳደረገ የደንቡን መሰዋዕትም እንዳቀረበ ነው።

ይህ ሁሉ ከተማ ከተያዘና ንግስታቱ ሁሉ ለኢትዮጵያዊው ንጉስ ለፒያንኪ ከገቡለት በኋላም፤ ይልቁንም ታላቋ የመምፊስ ከተማ ከተያዘችና ተስፋ እንደሌለው ከተረዳ በኋላ ባለበት በሠሜናዊ ስፍራ ሆኖ የግብፁ ፈርኦን ተፍንክታ አሳዛኝ መልዕክቱን ለፒያንኪ 2ኛ ላከ። መልዕክቱም ከብዙ በጥቂቱ ይህን ይመስላል።

"ክቁጣህ ታገስ..... በነበልባል ፊት መቆም አልችልም። በግለትህ ተሸንፌአለሁ። ወደ ባህር ደሴት ሸሸሁ፤ ከዛች የግለት ቃል የተነሳ መንፈስህን ተጠራጠርኩ። ..... በኔ ላይ የተነሳው ልብህ አሁንስ አልቀዘቀዘምን? አሁን ግን በእውነቱ ምስኪን ነኝ። በወንጀሌ ጥፋት ውስጥ አትጣለኝ። የሚዛን ልክ ትናንሽ ሰብርባሪዎችን ያውቃል። እነዚህን ለኔ በይቅርታህ አብዛቸው።

ዘር ብትዘራ በጊዜው ፍሬውን ታገኛለህ። ፍሬ የሚያፈራውን ዛፍ ገና በአበባው አታጥፋው። ፍርሃትን በልቤ አሳደርክ፣ ሽብርም በአካሌ ውስጥ ተገኘ። በመጠጥ ቤት ውስጥ አልቆምም፤ በገናዬንም ለጨዋታ አያመጡልኝም፤ በራበኝ ጊዜ ከደረቅ ዳቦ በቀር አልበላም። ሲጠማኝም የምጠጣው ውሃ ብቻ ነው።

ስምህን ከሰማሁበት ቀን ጀምሮ ፍርሐት በአጥንቶቼ ውስጥ ዘለቀ። አእምሮዬ ተቃጥሏል። ልብሶቼ ተበጣጥሰዋል። ወደ ኔይት /የራሱ አገር የማይስ ሴት አምላክ ቤተመቅደስ/ ሸሸቼ ተደብቄያለሁ። ና ወደኔ ፊትህን እኔ ወዳለሁበት መልስ። አገልጋይ /ወንጀለኛ/ በይቅርታ አይነሳምን? ያለኝ ሁሉ ወርቅና የከበረ ድንጋይ፣ በመልካም እቃ ያጌጡት ፈረሶቼ ሁሉ ይወሰዱ። ወደ ግምጃ ቤትህም ይግቡ። ፍርሃትን ከልቤ የሚያጠፋ መልዕክተኛ ይላክልኝ። ከእርሱም ጋር ወደ ቤተ መቅደስ ሄጄ ቅዱስ መሐላዬን ልፈፅም።"

ይህን መልዕክት የሠማው ፒያንኪ እንደእርሱ ታላቅ የሆነና የነበረ ንጉስ እንዲህ ያለ አሳዛኝ መማፀኛ ማቅረቡ አሳዝኖት ጠላትነቱን ፍቆ ታላላቅ ካህናትን ልኮ አስመጥቶ ክፉ ነገር ሳያደርግበት ወደ ቤተመቅደስ ሔዶ የአምላኩን ስም ጠርቶ "ለኢትዮጵያ እገብራለሁ" ብሎ እንዲምል አስደረገ። ተፍንክታም

"የንጉሱን የፒያንኪን ትዕዛዝ አልጥስም፤ ከቃሉም እልፍ አልልም። እሱም ሳይፈቅድ ማናቸውንም ሹም አልሾምም። እንደንጉሡ ቃልና ትዕዛዝ እፈፅማለሁ።" በማለት ማለ።

ከዚህ መሃላ የምንረዳው ፒያንኪ ግዛቱን ሠጥቶ እንዳስቀመጠው ነው። ለሌሎች ለገቡለትም ተመሳሳይ ሹም ሽር አድርጎ ፒያንኪ በግብፅ ያለውን ወርቅና ብር ሌሎች ጌጣጌጦችንና መሳሪያዎችን በአጠቃላይ ብዙ ሃብት በመርከብ አስጭኖ ጉዞውን በባህር ላይ ጀመረ።

ልቡ በደስታ ተሞልቶ ወደ መናገሻው ወደ ናፓታ ሲመለስ ግብጽን ድል አድርጎ ያስገበረ ጀግና ኢትዮጵያዊ ንጉስ እንደመሆኑ መጠን፤ ልዩ



አቀባባል ጠበቀው። ተቀባዮቹም ፡- "ድል አድራጊው ንጉስ መጣህ፤ ግዛትህ በታህታይ ግብፅ ተዘረጋ። ወንዶችን እንደ ሴት አደረካቸው። እሞን ሕይወትን ሠጠህ፤ ክብርም ያንተ ነው። ስልጣንህና ሃይልህ ለዘላለም ነው፤ አንተም እስከ ብዙ ዓመት ትኖራለህ።" በማለት እያሞገሡ ተቀበሉት።

እናም 300 ዓመት ኢትዮጵያን የገዙትን የሃያላኑ ፈርኦኖች የእነ ቱትሞሲስ 3ኛና የእነ ራምሲስ 2ኛን አገር ታላቋን ግብፅ ኢትዮጵያዊው ንጉስ ፒያንኪ 2ኛ ባየነው መልኩ አስገብሮ ተመለሠ።
የታላላቆቹ የግብፅ ከተሞች የመምፊስና የቴብ ክብር ወደ ናፓታ ዞረ። የፈርኦኖችን ልጆችም ለእርሱና ለተከታዮቹ ኢትዮጵያዊ ነገስታት እንዲገብሩ አደረጋቸው።

እዚህ ላይ መገንዘብ ያለብን ጉዳይ ፒያንኪ ግብፅን በግዛቱ ስር አድርጎ አስገበራት እንጂ፤ በግብፅ ላይ ከዚህ ድል በኋላ ባለፈው ታሪክ ያየነውን 25ኛውን ስርወ መንግስት አልመሠረተም። ነገር ግን በመሐላው እማካኝነት ተፍንክታም ልጁም ለኢትዮጵያውያን ነገስታት ሲገብሩ ኖረው በመጨረሻ መሃላውን ያፈረሠ ንጉስ በግብፅ ሲነሳ ወደፊት የምናየው ሻባካ የተባለው ንጉስ ተነስቶ 25ኛውን የግብፅ ዳይናስቲ እንደመሠረተ እንረዳለን።

ሆኖም የመጀመሪያው መሠረት የተጣለውና ኢትዮጵያውያን ግብፅን ያስገበሩት በፒያንኪ 2ኛ ጊዜ መሆኑ ግልፅ ነው።

ፒያንኪ ደግነት በተላበሰ ጀግንነቱ ግብፅን አስገብሮ ከተመለሰ በኋላ 10 ዓመት፣ ግብፅን ከመውረሩ በፊት 21 አመት፣ በዘመቻው የቆየበት ጊዜ 1 ዓመት፣ በድምሩ 32 አመታትን ኢትዮጵያን በንጉሰነገስትነት አስተዳድሮና አገሩን አስከብሮ፤ እንዲሁም የአባቶቹን ደም ተበቅሎ ከዚህ ዓለም በሞት የተለየው በነገስታቱ የሠንጠረዥ ዝርዝር ባየነው መሠረት በ778 ቅ.ል.ክ ነው።



King Piye

# ምዕራፍ ፲፮

# የአክሱማይ ወረደ ፀሃይና የካስታህ ሃንድዮን ዘመነ መንግስት

## ከ 778-742 ቅ.ል.ክ

ፒያንኪ 2ኛ ከመሞቱ ቀደም ብሎ ዙፋኑን የሚወርስ ወንድ ልጅ ስላልነበረውና ሚስቱ እርጉዝ ስለነበረች በታመመ ጊዜ ለሴት ልጁ ባል ለሆነው ለካስታህ እንዲህ የሚል ኑዛዜ አስተላለፈ።
"ሚስቴ ወንድ ልጅ የወለደች እንደሆነ ልጄ ዙፋኑን ባንተ ሞግዚትነት ይውረስ፤ ወንድ ልጅ ካልወለደች ግን አንተ ከሴት ልጄ የምትወልዳቸው ልጆች ልጆቼ ናቸውና መንግስቴን ላንተ ሰጥቼሃለሁ።"

ከዚህ ኑዛዜ በኋላ ፒያንኪ በሞተ በ15ኛው ቀን ሚስቱ ወንድ ልጅ ወለደችለትና ስሙ አክሱማይ ተብሎ በህፃንነቱ ነገሰና በካስታህ ሞግዚትነት ሲገዛ ቆይቶ በወጣትነቱ በድንገት ስለሞተ የፒያንኪ የልጁ ባል ካስታህ በመንግስቱ ሊተካ ችሏል።

የፒያንኪ ብቸኛ ወንድ ልጅ አክሱማይ /ወረደ ፀሃይ/ በተወለደ በ23ኛ አመቱ በነገሰ በ 23ኛ አመቱ ኢትዮጵያን ከግብፅ ግዛት ጋር በሞግዚት ሲያስተዳድር መቆየቱ ሲታወቅ፤ በሂዩሮግላፊ በሃውልት ላይም ሆነ በሌላ ቦታ ዝርዝር ታሪኩ አይገኝም።

ከእርሱ የተከተለው የፒያንኪ 2ኛ አማች ንጉስ ካስታህ ሐንዲዮን ግን ታሪኩ ረዘም ያለ ባይሆንም በትክክል በሒዩሮግላፊም በሌሎችም ተፅፎለት ይገኛል።

### የካስታህ ሐንድዮን ዘመነ መንግስት ከ755-742 ቅ.ል.ክ

ካስታህ ሐንድዮን የፒያንኪ የሴት ልጅ ባል ነበር። በፒያንኪ 2ኛ ልጅ በአክሱማይ ዘመነ መንግስት በፒያንኪ ኑዛዜ አማካኝነት በሞግዚትነቱ ፀንቶ ቆይቷል። ከአክሱማይ ሞት በኋላ መንግስቱን ሲረከብም በታህታይ ግብፅ ለኢትዮጵያ እየገበረ ያለውና የፈርኦንነቱን ስልጣን የያዘውን የአሶርኮን 3ኛን ልጅ ሻፒ ናፒት የምትባለውን አግብቶ ነበር። ሆኖም ይች ሁለተኛ ሚስቱ ናት እንጂ፤ ዋናዋ ባለቤቱ የፒያንኪ 2ኛ ልጅ ነበረች።

የጆሴፍ ካታዊ ፓሻ የታሪክ መፃህፍም ከገፅ 54 ጀምሮ ያለው ይህንኑ ነው የሚያረጋግጠው። ካስታህ ወይም ካሽታ የዋና ሚስቱ አባት ፒያንኪ ስለሞተ በግብፅ ቀድሞ ለፒያንኪ የተገዙለትና የገበሩለት አሁን ግን ለካስታህ አንገዛልህም ብለው ተዋግተዋል።

ከሁሉ በላይም የተፍነክታ ልጅ ኮንራፍ ሌሎችን ሁሉ መሳፍንቶች ደምስሶ እርሱ "በታህታይ ግብፅ የፈርኦንነቱን ዙፋን ያገዘኩ" ብሎ አወጀ።



ሌሎችም የእርሱ ተባባሪ ሆነው ስለተነሱ ካስታህ የግዛት ዘመኑ የተረጋጋ አልነበረም። ይሁንና ካስታህ በላእላይ ግብፅ፤ የተፍነክታ ልጅ ደግሞ "24ኛውን ስርወ መንግስት በታህታይ ግብፅ መስርቼ ፈርኦንነቱን የያዝኩት እኔ ነኝ" እያለ ኮንራፍ እና ካስታህ በእኔ ነኝ እኔ ነኝ ግጭት ሲባሉ ቆይተው፤ በመጨረሻ የፒያንኪ 2ኛ የልጅ ልጅ ማለትም ከፒያንኪ ሴት ልጅ እና ከካስታህ ሐንድዮን የተወለደው ሻባካ ኮንራፍን ገድሎ ዋናውን የፈርኦንነት ቦታ እና ስልጣን ይዞ ቀጥለን እንደምናየው በግብፅ 25ተኛውን የግብፅ ስርወ መንግስት /ዳይናስቲ/ ሊመሰርት ችሏል። እናም ካስታህ ሐንድዮን 12 አመት ባልተረጋጋ ሁኔታ የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት ሆኖ ቆይቷል።

# ምዕራፍ ፲፯

## የንጉስ ሻባካ ዘመነ መንግስት

### ከ 742-730 ቅ.ል.ክ

ሻባካ የፒያንኪ 2ኛ የልጅ ልጅ መሆኑን አይተናል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ የሚጠራበት ስሙም ይሄው ሻባካ የሚለው ሲሆን፤ በጥንታዊው ግብፅ አጠራር ሻባካ የሚለው "ካ" ሳይጨመር ሻባ ወይም ሳባ ማለት ነው፡፡ በግብፆች አጠራር "ካ" ሲጨመር ግን የሻባው /የሳባው/ ለማለት ሻባካ እንደተሠኘ ይነገራል፡፡ ይህንንም የሳባ ወገን መሆኑን ለመግለፅ ነው የሚሉ አሉ፡፡

በተጨማሪም በስሙ ላይ እንደ አባቶቹ ሜይ አሙን፤ የአሙን ወዳጅ ይሉታል፡፡ ይህን ንጉስ የግሪክ ፀሃፊዎች እነ ማኔቶን፣ ሄሮዱተስ፣ ዲዮዶር "ሳባኮስ" ወይም "ሳባኮን" ይሉታል፡፡

የኒቅዬ ኤጲስ ቆጶስ ዮሃንስ ደግሞ በስሙ በሠየመው "የዮሃንስ መደብር" በተሠኘው መፅሃፍ ሰዋኤን ብሎታል፡፡ በመፅሃፍ ቅዱስ ላይ ደግሞ በአማርኛው "ሶዋኤን" በግዕዙ "ሰጎል" የሚለው እርሱን ነው፡፡ /2ኛ ነገስት ምዕ 17 ቁ 14/ በአጠቃላይ ስለ ሻባካ ዶ/ር ሬይዝነር፣ ዋላስ ባጅ፣ የሄሮዱተስ 2ኛ መፅሃፍ፣ የካታዊ ፓሻንና ሌሎች መፅሃፍትን የዮሃንስ መደብርን ጨምሮ በመጥቀስ ተክለፃዲቅ መኩሪያ በናፓታ መርዌ 1ኛ መፅሃፋቸው ብዙ ብለውለታል፡፡

ሻባካ ወደ ዙፋን ከመውጣቱ ቀደም ብሎ አባቱ ካስታህ ላእላይ ግብፅን ጨምሮ በሚያስተዳድርበት ጊዜ ለአያቱ ለፒያንኪ 2ኛ እገዛልሃለሁ ብሎ ምሎ የነበረው የተፍነክታ ልጅ ፒያንኪ ከሞተ በኋላ ለአማቹ ለካስታህ አልገዛም ብሎ የታህታይ ግብፅን ነጻነት ለማወጅ ሞክሮ ነበር፡፡

ስልጣኑን ከአባቱ የተረከበው የተፍነክታ ልጅ ኮንራፍ ፈርኦንነቱ በውል ሳይረጋገጥ እራሱን በራሱ ፈርኦን ነኝ እያለ በታህታይ ግብፅ እያስተዳደረ እያለም ሻባካ ሊዘምትበት ተገዷል፡፡

ሻባካ ከናፓታ ወደ ታህታይ ግብፅ ሲዘምትም የግብፅ መሳፍንት እና ሹሞች በኮንራፍ ቂም ይዘውበት ነበርና /አማልክቱን እያንቋሸሸባቸው/ ለሻባካ አበሩለት፡፡ በዘመቻውም የሙሉ ድል ባለቤት መሆን ችሎ የኮንራፍን ሠራዊት ደምስሶ፤ እራሱን ኮንራፍን በመማረክ "አባትህ ተፍነክታ ለአያቴ ለንጉስ ፒያንኪ 2ኛ ሊገዛለት በመሐላ ያረጋገጠውን ቃል ሽረህ አልገዛም ብለሀልና ..." በማለት እስከነህይወቱ በእሳት አቃጠለው፡፡

ከዚያም ኢትዮጵያዊው ንጉስ ሻባካ የታህታይና የላእላይ ግብፅን፤ እንዲሁም ሊቢያን ወደ ራሱ ግዛት አጠቃሎ ከደረበ በኋላ ልክ እንደ አያቱ ወደ ናፓታ በመመለስ ፋንታ በዚያው በግብፅ ሆኖ ማስተዳደር ጀመረ፡፡



የግብፅን የዋና ፈርኦንነት ስልጣንንም ያዘ፡፡ እህቱንም ሙሉ ስልጣን ሠጥቶ ከእርሱ በታች በላእላይ ግብፅ በቴብ አነገሳት፡፡

እርሷም ብልህና ሃይለኛ ስለነበረች ከሻባካ ቀጥለው በነገሱት 3 ነገስታት ዘመን እንደሞግዚት ሆና መላውን ግብፅ ለማስተዳደር ችላለች፡፡

እስከ ሻባካ ዘመነ መንግስት ድረስ በግብፅ ዙፋን የተለያዩ ነገስታቶች በፈርኦንነት እየተቀመጡ እስከ 24ኛው ዳይናስቲ ድረስ ቆይተው የነበረ ሲሆን፤ አሁን በሻባካ ዘመነ መንግስት ጊዜ ግን በንጉስ ሻባካ አማካኝነት ኢትዮጵያውያን በግብፅ ላይ 25ኛውን ስርወ መንግስት መስርተው ማስተዳደር ችለዋል፡፡

ንጉስ ሻባካም ኢትዮጵያን ባስተዳደረበት የግዛት ዘመኑ በ12 አመት ቆይታው ይህን የመሰለ ግዙፍ ድርጊት ፈፅሞ እንደ አያቱ ኢትዮጵያን አግንኖ ነው ያለፈው፡፡ እርሱ ሲሞትም በሙሉ ስልጣን አነገሳት ያልናት እህቱ መንግስቱን ተረክባለች፡፡ እርሷም በዝርዝሩ ላይ ከሻባካ ቀጥላ የሠፈረችው ኒካንታ ቅንዳኬ ወይም ህንዳኬ የተባለችው ናት፡፡

## ምዕራፍ ፲፰
## የንግስት ኒካንታ ህንዳኬ ዘመነ መንግስት
## ከ730-720 ቅ.ል.ክ

ንግስት ኒካንታ ቅንዳኬ የሻባካ እህት እንደሆነች አይተናል። ወንድሟ ሻባካ የላእላይና የታህታይ ግብፅ ዋና ፈርኦን በነበረ ጊዜ እርሷ ከእርሱ በታች በላእላይ ግብፅና በናፓታ ነግሳ መቀመጫዋን በቴብ አድርጋ ትገዛ ነበር። በዚያም ሳለች ‹የላእላይ ግብፅ ንግስት ለአሞን የምትሰግድ የአሞን ታላቂቱ ካህን› እየተባለች የቤተመንግስቱንና የቤተክህነቱን ስልጣን ደርባ ይዛ ስትገዛ የቆየች ናት።

ሲጠሯትም ግብፆቹ አሜኒሪትስ፣ ግሪኮች ክንዳኬ የኛ የግዕዙ መፅሃፍ ህንዳኬ በማለ ነው። ይች ንግስት በሁሉም ዘንድ ተፈሪና ተከባሪ እንደነበረችም ታውቋል። ከሁሉ በላይ ተከባሪ ያደረጋትም በአሞን ቤተመቅደስ የነበራት የመንፈሳዊ ስልጣን ነው። ኒካንታ ህንዳኬ ቀደም ባለው በወንድሟ የግዛት ዘመን የናፓታንና የላእላይ ግብፅን ዘውድ ብቻ ነበር ያደረገችው።

በኋላ ግን የላእላይንም የታህታይንም ግብፅ ዘውድ ለመድፋት ችላለች። በዘመኗ ሁሉም ለኢትዮጵያውያን ነገስታቶች ሚስትም፣ እህትም፣ ሞግዚትም እየሆነች በትልቅ ስልጣንና መፈራት ያሳለፈች የሴት ንግስት ሆና ቆይታለች።

ከግብፃውያን የመሳፍንትና የነገስታት ዘር ካላቸው፤ እንዲሁም ከኢትዮጵያ ነገስታቶች ጋር በመጋባትም ልጅ ወልዳለች። ከእነዚህም ውስጥ የግብፅን ንጉስ ፕሳሜቲክስ 1ኛ ይባል የነበረውን ከኢትዮጵያውያን በኋላ ለተተካው 26ኛው ዳይናስቲ ተከታይ ለመስጠትና ከግብፅ ግዛት የኢትዮጵያ ዘር እንዳይጠፋ ሴት ልጇን ከፕሳሜቲክስ 1ኛ ጋር /ሻፕ አን አፕ/ን አጋብታለች።

ህንዳኬ ሻፕ አን አፕን የወለደችው ከአንድ የኢትዮጵያ ንጉስ እንደነበረም ይነገራል። ገናናነቷም በቴብ ከተማ በካርናቅ የእብነ በረድ ሐውልቷ ከነፅሁፉ ከተገኘውና ሙሴ ማርዮት የተባሉት የፈረንሳይ ሊቅ በተረጐሙት ፅሁፍ ላይ ለፈጋገጥ ችሏል። በእርሷ የግዛት ጊዜም አሶራውያን እየገነኑ ወደ ግብፅም እየመጡ ጥቃት ለመሠንዘር እንደሚፈልጉ የሚያሳይ ፍንጭ የሚታይበት ወቅት ሆነና 10 አመት ያህል በንግስትነት ከገዛች በኋላ ቲሃርቃ የተባለውን በእርሷ ስር እንዲተካ አደረገች።



## ምዕራፍ ፲፱
## የንጉስ ቲሃርቃ ዘመነ መንግስት
## ከ720-671 ቅ.ል.ክ

ቲሃርቃ ወይም ቲርሃቅ ከሻባካ ዘመነ መንግስት ጀምሮ በቤተመንግስት ያደገና በመንግስት አስተደደርና በጦርነት ውስጥ ሲሳተፍ በመቆየቱ የሚመሰገንና ተቀባይነት የነበረው የነጋሲ ዘር ነው። ከሻባካ እቁባት የተወለደ እንደሆነም ብዙዎቹ ተስማምተዋል።
መጠሪያ ስሙም በመፅሃፈ ነገስተ ካልዕ ምዕ. 19 ቁ 9 ላይ ተጠቅሶ ይታያል። በዚሁ ላይም ቲሃርቃን ‹ቲርሃቅ የኢትዮጵያ ንጉስ› ብሎ ነው ያሰፈረው። ቲርሃቅ የሚለውም በእስራኤላውያኑ በእብራይስጥ አነጋገር ነው።

የኑብያን ነገስታት ታሪክ ያጠናው ዶ/ር ሬይዝነር ደግሞ ታርሃክ ብሎታል። ይህን መሰሉ የስም እና የአገር ስያሜም ለብዙ መደናገሮች በር መክፈቱን ሁሉም የታሪክ መርማሪዎችና ፀሃፊዎች የሚማረሩበት ጉዳይ መሆኑ ይታወቃል።

በዚሁ መጠንም የቲሃርቃ ምንም እንኳን ይዘቱን ባይለቅም ተሐርቃ፣ ታሩቃህ፣ ተሐርቁ፣ ቲሃርቃ፣ ታሐርቆስ፣ ቲርሐቅ እያሉ ይጠሩታል። አሶራውያኑ ደግሞ ታርኩ ብለውታል። ባሁኑ ዘመን ግን ከሁሉ የበለጠውም የተለመደውም መጠሪያው ቲሃርቃ የሚለው ነው። ወይም ቲርሀቅ። ይህም 'ክ' በ 'ቅ' በኛው ንግግር ተለውጦ እንገኘዋለን። እኛም ቲሃርቃ እያልን በመጥራት ታሪኩን እንቀጥል።

ቲሃርቃ ከንግስተ ሳባ ጀምሮ በተዘረዘረው የነገስታት ዝርዝር ውስጥ በ14ኛ ላይ ያየነው ነው። ቲሃርቃ ከኒካንታ ህንዳኬ ቀጥሎ የፈርኦንነት ዘውዱን ከጫነ በኋላ አንዳንድ አመፀኛ ርዝራዦችን ከግብፅ ከደመሰሰ በኋላ የሊብያን ከዚያም አልፎ ዛሬ ድረስ ጂባራልታ እየተባለ የሚጠራውን የአፍሪካን ሰሜን በሙሉ በጦር ሃይሉ እንዳስገበረ ይታወቃል። እስከ አውሮፓ ድረስ ተሻግሯል የሚሉም አሉ።

በቴብ በካርናቅ ከተማ ላይ የራሱ ሃውልት በትልቁ ተሠርቶ የተገኘ ሲሆን፤ በእርሱ ሃውልት አጠገብም እየተዋጋ የማረካቸው የእስያና የአፍሪካ፤ ከእስያ 14፣ ከአፍሪካ 14 ነገስታቶች እንደሆኑ የሚያሳይ ሃውልት ቆሞ ይታያል።

በነገሰ ጊዜም የአባይ ወንዝ ከመቸውም ጊዜ በላይ ሞልቶ ስለተትረፈረፈ የጻድቅነቱ እና የደግነቱ ምልክት ነው ብለው ህዝቡ ሁሉ ያከብሩትና በልዩ አይን ይመለከቱት ጀመር።

ያለ አንዳች ስጋት በተደላደለ አገዛዙ ሃያ አመት ከቆየ በኋላ ግን አንድ ጠላት ተነሳበት። እርሱም የአሶር ንጉስ የሰናክሬም ልጅ አሳርሐዶን የተባለው ንጉስ ነው።

የአሶር መንግስት በዚህ ዘመንና ከዚህም ዘመን ቀደም ባሉት ጊዚያቶች እየገነነ ሔዶ ነበርና አሁን ደግሞ በአጠገቡ ያሉትን ባቢሎንን፣ ጢሮስን፣ ሲዶናን፣ እስራኤልንም ሁሉ ከወረረና ከገዛ በኋላ በንጉስ ሰናክሬም ሞት ቀዝቀዝ ብሎ ታየና ወዲያው የሰናክሬም ልጅ አሳርሐዶን ሲነግስ ደግሞ፤ አባቱ ሲሞት ተዋግተው ነፃነታቸውን ያወጁትን የቀድሞ ተገዢዎች በድጋሚ ለማሸነፍና ለማስገበር ንጉስ አሳርሐዶን የሸፈቱበትን ለመዋጋት ሲሯሯጥ ስለቆየ ቀደም ሲል እንደተፈራው በግብፅ ላይ ለመነሳት ጊዜ አላገኘም ነበር።

አሁን ግን በ600ኛው ዓመት ገደማ ጢሮስንም፣ ሲዶንንም ተዋግቶ እንደአባቱ ተገዢ ሊያደርጋቸው ቻለ።

እነዚህ አገሮች ደግሞ ተስፋ ያደረጉት ኢትዮጵያዊውን ንጉስና የግብፅ የፈርኦንነትን ስልጣን ደርቦ የያዘውን ቲሃርቃን ሆነ። የአሶራውያን ንጉስ አሳርሖዶንም ይህንኑ በመረዳት የግብፅን ፈርኦን ቲሃርቃን ለመዋጋት ጉዞውን በሲና ተራራ በኩል ጀመረ። በመንገድ ላይ እያለም በሲና በርሐ ጥንት እስራኤሎችን ይፈጅ የነበረው መንታ ጭንቅላት ያለው የበርሐ እባብ የአሳርሖዶንን ሠራዊት እየነደፈ ጨረሰበት። ይሁን እንጂ በሲና አውራጃ የሚኖሩ የዘላን ህዝብ ሹማምንት ከነተከታዮቻቸው እየመጡ እርሱን ለማገዝ ተቀሳቀሱት።

በእነርሱ እየተረዳም ከግብፅ ዋና ከተማ መምፊስ ደረሰ። ከዚህም በተጨማሪ በሠሜናዊ ግብፅ የሚገኙት የግብፅ መሳፍንቶች በኢትዮጵያዊው በቲሃርቃ ፈርኦንነት ይቀኑበት ስለነበር ከአሶሩ ንጉስ ጋር በመተባበራቸው በቲሃርቃ ላይ ያንዣበበው ጦርነት ከባድ እየሆነ መሄዱ ታወቀ። ቢሆንም በመምፊስ ሆኖ 15 ቀናትን በደንብ ተዋጋ። ከዚያም መቋቋም ስላቃተው ከመምፊስ ሸሽቶ ወደ ቴብ፣ ቀጥሎ ወደ አገሩ ወደ ናፓታ የተረፈውን ጦር ይዞ ሸሸ። ሚስቶቹና ልጆቹ፣ ስፍር ቁጥር የሌለው መሳሪያና በመምፊስ የሚገኘው ሃብቱ ሁሉ በአሶራውያን እጅ ገባ። አሶራውያንም ከመምፊስ ወደ ቴብ በመጓዝ በዚያም በመምፊስ ያደረጉትን አይነት ብዝበዛ አደረጉ። የቤተመንግስቱንም፣ የቤተ መቅደሱንም ሐብት ሠብስበው ወደ አገራቸው ወደ አሶር ላኩት። የአማልክቶቻቸውን ምስል እያፈረሱ የራሳቸውን የአማልክት ምስል ተኩበት።

የግብፅ መሳፍንቶችም ለአሶሩ ንጉስ ለአሳርሖዶን መታያቸውን እየያዙ እየመጡ ሰገዱለት። አሳርሖዶንም ሁሉም እንዲገብሩ አድርጎ ሃያ



አምስት የግብፅ መሳፍንት በየአውራጃቸው ሾሞ አነገሳቸውና የራሱን ሹማምንትና ሠራዊት ትቶ በደስታ ወደ አገሩ ተመለሠ።

ወደ ከተማው ወደ ነነዌ ሲመለስም ሃውልት አሰርቶ የራሱን ምስል በማቆም ከጎኑ ደግሞ የቲሃርቃን በአንድ ትንሽ ጥቁር አፍሪካዊ መልክ አድርጎ በማሰራት ቲሃርቃ ተንበርክኮ እንደሚለምነው አስመስሎ አሰራው። እውነታው ግን ቲሃርቃ እንኳን ተንበርክኮ ምህረት ሊለምነው ከአሶሩ ንጉስ ጋር በፍፁም በአካል ተያይተው አለማወቃቸው ነው።

ቢገናኙ ደግሞ እንደ አሶራውያን የጦርነት ደንብ የተማረከው ንጉስ እስከነሕይወቱ በቁሙ ቆዳው ይገፈፍ ነበር እንጅ አይለቀቅም። ስለዚህ በሐውልቱ ላይ አሳርሖዶን ያሰራው የቲሃርቃ ሃውልት ሐሰት መሆኑን ፀሃፊው ሁሉ ተገንዝቦታል።

ቲሃርቃ ከሽሽቱ በኋላ ወደ ናፓታ ተመልሶ ግብፅን /ታህታይ ግብፅን/ እንደገና ከአሶራውያን አስጥሎ ለመያዝ ይዘጋጅ ነበር።
በዚህ መካከልም ግብፃውያኑ ራሳቸው ከአሶራውያኑ ግዛት በሃይማኖት፣ በልማድ፣ በቋንቋና በፅሁፍ የሚመሳሰሏቸውና አማልክታቸውን የማያንቋሽሹባቸው ኢትዮጵያውያኑ እንደሚሻሏቸው ተረዱ። ስለዚህም የአሶራውያኑ ግዛት 5 አመት ያህል እንደቆየ "ናና በላያችን ላይ መሪ ሆነህ ከአሶራውያኑ ቀንበር አድነን።" ብለው ወደ ቲሃርቃ ላኩበት። እርሱም ይህን መልዕክት ሲሰማ በደስታ ገስግሶ ከአሶራውያኑ ጋር ተዋግቶ አሸነፈና የመምፊስን ከተማ ይዞ እንደቀድሞው ማስተዳደሩን ቀጠለ።

ከዚያም መዲኔ ሐቡ በተባለው ቦታ ላይ የድል አድራጊነት ሐውልቱን ሲተክል እርሱም በፋንታው በሐውልቱ ግርጌ "የሁለቱ አገር የኢትዮጵያና የግብፅ ንጉስ" ተብሎ በሚፃፍበት ላይ "የአሶርም ንጉስ" የሚል አስጨምሮ አስቀረፀ።

ይህም አሳርሖዶን ቲሃርቃ ተንበርክኮ ሲለምነው አስመስሎ ካሰራው ሃውልት ጋር የሚመሳሰል እንጅ እውነታው አይደለም። ምክንያቱም ቲሃርቃ አሶርን አልገዛም። አሳርሖዶን በግብፅ ትቷቸው የሄደውና ውጊያውና ሽሽቱ መሯቸውና ሰልችቷቸው አሶራውያኑ /በግብፅ ያሉት/ ተገዝተውለት ቢሆንም እንኳ የአሶር ንጉስ አያሰኘውም።

ቲሃርቃ ከናፓታ ወደ መምፊስ ተጉዞ ድል ካደረገና ፈርኦንነቱን እንደቀጠለ አሳርሖዶን በሠማ ጊዜ ከነነዌ ተነስቶ ወደ ግብፅ ጉዞ ጀመረ። ነገር ግን በመንገድ ላይ ሳለ ስለሞተ ንግስናውን ልጁ አሱርባኒፓል /አሱር ባን ሐባል/ ተረከበ።

ቲሃርቃ ፈርኦንነቱን እንዳፀና በመምፊስ 3 አመታት ሲያሣልፍ፣ የአሶሩ ንጉስም 3 አመት በከተማው በነነዌ መንግስቱን ካጠናከረ በኋላ ብዙ

የጦር ሠራዊት ወደ ግብፅ ላከ። የተላከውም ጦር ቲሃርቃን አሸንፎ እንደገና መምፊስን ተቆጣጠረ።

ቲሃርቃም በድጋሚ ወደ ቴብ መሸሽ ግድ ሆነበት። የግብፅ መሳፍንትም ስላልቻሉ በድጋሚ ለአሶራውያን ገቡ /ተገዙላቸው/።

የአሶራውያን ጦር የማረካቸውን ሹሞች ወደ ንጉሳቸው ወደ ነነዌ ልከው በጭካኔ እንዲሠቃዩና እንዲሞቱ ሲደረግ፤ ቲሃርቃንም እንዲይዙት የታዘዙት አሶራውያን ከቴብ አስወጥተው ዓባይ ለዓባይ እያሳደዱ ከቴብም ወጥቶ ወደ አባቶቹ አገር ወደ ናፓታ እንዲሸሽ አስገደዱት። ቲሃርቃም መቀመጫውን በአገሩ በናፓታ ለማድረግ ተገደደ።

አሶራውያንም በግብፅ ላይ ሹም ሽር አድርገው ለረጅም ጊዜ ገዥነታቸውን ሊያቆዩ ቻሉ። በአጠቃላይ ሃያላን ከነበሩ ከኑብያ ኢትዮጵያውያን ነገስታት ተርታ በጀግንነቱ የሚሰለፈውና ብዙ የተባለለት ንጉስ ቲሃርቃ በአሶራውያን ጫና ወደ ናፓታ ከተመለሰ በኋላ ፍፃሜውም በዚሁ በናፓታ ሊሆን ችሏል።

እናም ይህ ታላቅ ፈርኦን ግብፅንና ኢትዮጵያን በአንድነት ደርቦ በመግዛት 26 አመት፣ በናፓታ ብቻ በተወሰነው ግዛቱ 23 አመታትን በመግዛት በድምሩ 49 አመት በገዥነት ስልጣን ላይ ቆይቷል። ይህ ሁሉ ሲሆንም በጦርነት እየሸሹ መልሰው ተደራጅተው ሔደው እየተዋጉ ስለቆዩ የግብፅን የፈርኦንነት ስልጣን ገና ሙሉ ለሙሉ አልተቀሙም ነበር።

ከቲሃርቃ ሞት በኋላ የነገሰው አርድ አሚን አውስያ የሚባል ሲሆን፤ የግዛት ዘመኑም 6 ዓመታት ብቻ መሆኑ ነው የሚታወቀው።

ብላቴን ጌታ ህሩይ በዋዜማ መፅሃፋቸው እንዲሁም ሌሎች ከቲሃርቃ ቀጥሎ የነገሰው አርድ አሜን እንደሆነ በመግለፅ፣ ከነግስናው በኋላም ወዲያው ሠራዊቱን ሠብስቦና አደራጅቶ እስከሠሜናዊ ግብፅ በመንዝ አሶራውያንን ለመዋጋት እንደሞከረና፤ አሶራውያን ያለ አንዳች ጭንቀት መልሰው እንዳባረሩት፤ ከዚያም ከዘመቻው በኋላ ወደ ናፓታ ተመልሶ መጥቶ እንደሞተ ነው የተጻፈለት። አርድ አሚን ከ671-665 ከገዛ በኋላም ተከታዩ ንጉሰነገስት ገስዮ ሲሆን እርሱም 6 ሰአታትን ብቻ በዙፋን አሳልፏል። ንጉስ ገስዮ ለምን 6 ሰዓታት ብቻ እንደቆየና በምን መልኩ ታንታሙን እንደተረከበው አይታወቅም።









The Rise of Taharqa: Ruler of Nubia and Egypt

## ምዕራፍ ፳
## የንጉስ ታንታሙን ዘመነ መንግስት
## ከ665-661 ቅ.ል.ክ

ንጉስ ታንታሙን የቲሃርቃ የልጅ ልጅ ነው:: ማለትም የሴት ልጁ ልጅ:: ታንታሙን ልክ እንደ አባቱ የተለያዩ መጠሪያ ስሞች ነበሩት:: አሚንሚሪነት፣ ኑአትሚይሙን፣ ሚያአሙን፣ ታንታሙን ይሉታል:: እኛም ተብሎ ተብሎ በመጨረሻ በሰደቀው ስሙ ታንታሙን በሚለው እየጠራን በ4 ዓመት አጭር የግዛት ዘመኑ የፈፀማቸውን ታሪኮች እንይለት::

በጀበል ባርካ እነሙሴ ማርዮት፣ ሙሴ ሩገር፣ ሙሴ ሌፒስየስ ካገኙትና ከተረጎሙት የአምስት የኢትዮጵያ ነገስታት ሐውልቶች ውስጥ አንዱ የዚሁ የንጉስ ታንታሙን ሐውልት ነው:: ዜና መዋዕሉን ጨምሮ ብዙ የተፃፈለት ይህ የኢትዮጵያ ንጉስ የተገኘለት ሐውልቱ "የህልም ሐውልት" የሚል ስያሜ አለው::

የሐውልቱ ርዝመት 1 ሜትር ከ32፣ ስፋቱ 72 ሴ.ሜ ሆኖ ዕሁፉ የሠፈረባቸው መስመሮች ላይ "የፀሃይ ልጅ፣ የአሞን ልጅ፣ ዘላለም የሚኖረው የሁለቱ አገሮች /የኢትዮጵያና የግብፅ/ ንጉስ....." የሚለው የተለመደ መግቢያ ይታያል::

ከዚያ ቀጥሎ "በህልሜ አንድ እባብ በቀኝ አንድ እባብ በግራ በኩል ሲወጣ አየሁ:: ይህንን ተርጉሙልኝ" እንዳለና በማግስቱ በርካታ ህልም ፈችዎችና አዋቂዎች ተጠርተው እንደተረጎሙለት፤ እነርሱም ሁለቱ እባቦች ደቡብ ኢትዮጵያንና ሰሜናዊ ግብፅን ወደፊት እንደምትገዛ የሚያሳዩ ምልክት ነው:: ባሉት ጊዜ በህልም አፈታታቸው ተደስቶ ለተገኙት ካህናትና አዋቂ መኳንንት ግብር አብልቶ ለአምላኩ ለአሞን መስዋዕቱን ያቀረበበት ታሪክ ይቀጥላል::

ታንታሙን ከመንገሱ በፊት ቲሃርቃ በነበረበትና በሞተበት ዘመንም ጭምር ስልጣንና ግዛት ሲከፈል የቆየ የነጋሲ ዘር ነው:: በናፓታ ከነገሰ በኋላም ከህልሙ ትርጓሜ በኋላ ጉዞውን ወደ ኤሌፋንቲን ቀጥሎ ወደ ቴብ አድርጓል:: እነዚህ አገሮች ደግሞ ለብዙ ጊዜ የኢትዮጵያ ነገስታትና የአምላካቸው የአሞን ርስት ስለሆኑ፤ ታንታሙን ቴብ እስኪደርስ ድረስ የሚዋጋውም የሚቃወመውም አላገኘም::

ይልቁንም በየመንገዱ "በሰላም ግባ ለግብፅ ህይወት ስጥ የወደቁትን ቤተመቅደሶች አንሳ፣ ሐውልቶችንና ምስሎችን አቃና፣ ለአማልክቱ መስዋዕታቸውን አቅርብ፣ ስለታቸውን ስጥ፣ በዓላቸው ይከበሩ ዘንድ ካህናቶችን በየቤተ መቅደሳቸው አስማራ..." እንዳሉት ተፅፏል::

ታንታሙን ከቴብ ተነስቶ መምፊስ ሲደርስ ግን በአሶር መንግስት ስልጣን ስር የነገሱት ሃያ አምስት የሚሆኑት የሠሜናዊ ግብፅ ነገስታት ከነዋሪው ከአሶር ወታደሮች ጋር ሆነው ተዋጉት:: ነገር ግን በብዙ መስዋዕትነት ድል አድርጓቸው ሸሽተው ስለሔዱና ስለተደበቁ ክትትሉን ትቶ ወደ መምፊስ ተመለሰ::

በመምፊስ ሳለም ሸሽተው የመሸጉት ነገስታቶች በአንድ መስፍን እየተመሩ መጥተው ምህረትን ለመኑት:: በፊቱም ሆነው "የሕይወት መንፈስ ስጠን፤ አንተን የካደ ህይወት የለውምና:: በንግስናህ ቀን እንደተናገርከው የበታችህ እንሆናለን...." አሉት:: ንጉስ ታንታሙን ጥያቄያቸውን በደስታ ተቀብሎ ግብዣ አደረገላቸው::

የአሶሩ ንጉስ ያልነው አሱርባኒፓል ከነነዌ በግብፅ ላይ ሾሞ በንጉስነት ማዕረግ የሳከው ኒካዎ ግን እልገዛም ብሎ ታንታሙንን ስለተዋጋው ታንታሙን ሠራዊቱን አሸንፎ ኒካዎንም ማርኮ ገደለው:: ኒካዎ ከሞተ በኋላም ልጁ ፕሳሜቲክ ከመምፊስ ሸሽቶ ወደ ነነዌ ሄዶ ከአሶሩ ንጉስ ከአሱርባኒፓል ጋር ተገናኝቶ የሆነውን ሁሉ ተረከለት:: ሃይለኛው አሱርባኒፓል ይህን ሲሰማ ተናዶ ራሱ ጦሩን እየመራ ወደ ግብፅ መጣ፣ በዚያን ጊዜ ታንታሙን ቀደም ብሎ ምርኮውን ሁሉ ሰብስቦ ወደ ቴብ ተመልሶ ነበርና ከአሱርባኒፓል ጋር አልተገናኙም ነበር::

እናም ሳያስበው ቴብ ላይ ስለደረሰበት ቴብን ለቆ ወደ ናፓታ መጣ:: ታንታሙን ከነሠራዊቱ የለቀቀውንና ስመጥር የሆነችውን የቴብ ከተማ የአሞንን ቤተመቅደስና የሚያምረውን ቤተመንግስት ሁሉ የአሶር ወታደሮች ክፉኛ በዘበዙት:: ከቤተ መንግስትና ከቤተመቅደስ የተገኘው ማናቸውም እቃ ወርቅ፣ ብር፤ ልብስ፣ መሳሪያ እየተዘረፈ ከሃውልቱ ጋር ወደ ነነዌ ተጓዘ::

በዚያ ዘመን ማለትም ከክርስቶስ ልደት በፊት በ6 መቶኛው አጋማሽ ዓመታት ቴብ ላይ የደረሰው እልቂትና ዘረፋ እስከ ብዙ ዘመን ድረስ እንዳታንሠራራ አድርጓት ነበር:: የሚገርመው ይህ ከመሆኑ ከ50 አመት በፊት በእስራኤል የተነሳው ናሆም የተባለው ነብይ በዘመኑ በራሷ በነነዌ ከተማ ወደ ፊት የሚደርስባትን ውድቀት ሲገልፅ፤ በአሁኑ ሠዓት በቴብ የደረሰውንም አንስቶ እንዲህ ብሎ ነበር::

"እነሆ እኔ ባንች /በነነዌ/ ላይ ነኝ ይላል እግዚአብሔር የሠራዊት ጌታ፤ ልብስሽንም በፊትሽ እገልጣለሁ፤ ለአህዛብም ራቁትሽን አሳየሁ፤ ለመንግስትም ነውርሽን .... የሚያይሽም ሁሉ ካንች አየሸሸ ነነዌ ተፈታች ይላል ..... አንች ከነአሞን ከተማ ትበልጫለሽን? በፈሳሾች መካከል

ከተቀመጠችው፤ ውሃም በዙሪያዋ ነበራት፤ ቅጥርዋም በባህር ውስጥ ነበር። ኩሽና ምስር /ኢትዮጵያና ግብፅ/ የማይቆጠሩ ሃይሏ ነበሩ። ፉጥ /ግብፅ/ የማይቆጠሩ፤ ሊቡም /ሊቢያም/ የሚረዱሽ ነበሩ። ነገር ግን እርስዋ ተጋዘች። ምርኮም ተማረከች። ህፃናትዋም በመንገድ ሁሉ ራስ ተፈጠፈጡ። በጌታዎቿም ላይ እጣ ተጣጣሉ። ታላላቆዎቿም ሁሉ በሠንሠለት ታሠሩ ....." ትንቢተ ናሆም ምዕ 3 ቁ 5-10.

ነብዩ ናሆም እንዳለውም የአሞን ቤተ መቅደስ ያለባት ይች የቴብ ከተማ ከቀድሞ ጀምሮ ሃያላኑ ፈርኦኖች በልዩ ልዩ ሐውልት ያስጌጧት ታላቅ ከተማ የማትፈርስ ትመስል ነበር።


ነገር ግን ፊተኛው ኋላ ኋላኛው ፊት እንደሚሆን ሁሉ፤ የደመቀ ከተማ ፈርሶ የደበዘዘው የበለጠ እንደሚደምቅ ይታወቃልና፤ ቴብን ይህ መሰሉ ውድቀት ሲገጥማት ነብዩ ናሆም እንዳለውም የቴብን አፍራሾች የአሶራውያንን ከተማ ነነዌን ደግሞ በተራዋ ሲአክሳር የሚደን ንጉስ ከ50 አመት በኋላ አፈራርሶ እራሱን የአሶርን መንግስት ሊጥለው ችሏል። በዚህም የትንቢተኛውን የናሆምን ትንቢያ መፈፀሙን በዚያ ዘመን ዓለም አረጋግጣለች።

በመጨረሻም ኢትዮጵያዊው ንጉስ ታንታሙን ከአሶራውያን ጥቃት ለመዳን እየሸሸ ከመምፊስ ወደ ቴብ ከተጓዘ በኋላ ከቴብ ወደ ናፓታ ሔዶ ሊቀመጥ ችሏል። ምንም እንኳን የመጀመሪያው ጉዞው ማለትም ከመምፊስ ወደ ቴብ ያመራው በሽሽት ባይሆንም አሶራውያን እየተከታተሉት መሆኑን ሲያረጋግጥ ግን ጉዞውን ወደ ናፓታ አድርጎ በዚያው በናፓታ ፍፃሜው ሆኗል።

ኢትዮጵያዊው ንጉስ ታንታሙን በናፓታ እንዳለ በ661 ቅ.ል.ክ ከ4 አመት የንግስና ቆይታው በኋላ ሲሞትም የኢትዮጵያ የግብፅ ግዛትም በእርሱ ዘመን ተቋጭቷል። ከዚያ ጊዜ በኋላም በግብፅ ላይ የኢትዮጵያውያን ገዢነት ተወግዶ ሌሎች ሃያላን አገራት ባቢሎን፣ ፋርስ፣ ግሪክ፣ ሮማ፣ ዓረብ... ቱርክ ይፈራረቁባት ጀመር።

በአጠቃላይ እስከአሁን ባየነውና ከፒያንኪ 2ኛ ጀምሮ እስከ ታንታሙን ድረስ የኢትዮጵያ ግዛት በግብፅ ላይ የቆየበት ዘመን 127 ዓመታት ሲሆን፤ ይህም ከ810-661 ቅ.ል.ክ ያለውን ጊዜ ይሸፍናል። የፒያንኪ 22 አመት ሳይቆጠር።





Statues of Nubian kings up toten feet high
Were found buried at the
Nubian capital of Kerma, in Sudan.
Smashdduring Egyptian king pasamtek
II's incursion southaround 593B.C., they were
recntly reassembled. (National Geography Feb. 2008).

## ምዕራፍ ፳፩

## የመናገሻ ከተማ ለውጥ ከናፓታ ወደ መርዌ

የኢትዮጵያ ግዛት በግብፅ ካከተመ በኋላ ከታንታሙን ቀጥሎ ፒያንኪ 3ኛ፣ ከፒያንኪ 3ኛ፣ አማኒን አሳሮ 2ኛ፣ ቀጥሎም ፒያንኪ አፀጥዮ 4ኛ፣ ከዚያም ዙዋሬ ንብረት አስፑርታ፣ ቀጥሎም ሐርሲአተው የተባሉ ነገስታቶች በተከታታይ በኢትዮጵያ ናፓታ ከነገሱ በኋላ ራምሐይ ናስቶስኔን የተባለውና በዝርዝሩ 23ኛ ላይ በሠፈረው ንጉስ ጊዜ የኢትዮጵያ መናገሻ ከተማ ከናፓታ ወደ መርዌ ሊዞር ችሏል።

በእነዚህ ጊዜያቶች ሁሉ ኢትዮጵያውያን ምንም እንኳን የግብፅ ጎረቤት ቢሆኑም እስከ ራምሐይ ናስቶስኔን ድረስ በግብፅ ላይ የተፈራረቁት ሃያላን አገራት ለመውረር አልደፈሩም።

በእነዚህ ከላይ በተዘረዘሩት ኢትዮጵያዊ ነገስታት ጊዜም መንግስታቸውን በናፓታ አደላድለው ከመቆየታቸው ያለፈ የተከሰተው ታሪካዊ ክንውን አይታወቅም። ስለዚህ የኢትዮጵያ መናገሻ ከናፓታ ወደ መርዌ በምን መልኩ እንደተዛወረ በአጭሩ እንመልከትና ከዚያ በኋላ ደግሞ በእነዚህ ዘመናት የግብፅ ዕጣ ፋንታ ምን ይመስል እንደነበር የሚያሳይ አጭር ሐተታ እናስከትል። ለቀጣዩ ምዕራፍም ማለትም ለመርዌ ነገስታት ታሪክ እንደመንደርደሪያም ይሆነናል።

የመናገሻ ከተማ ለውጡ የተደረገው የናፓታው የመጨረሻ ንጉስ ሳይፋይ አርሲአተው በተባለው ጊዜ ሲሆን፣ ይህ ንጉስ በሚገዛበት ጊዜ ከ558-546 ቅ.ል.ክ 12 አመት እንደገዛ ከመርዌ ውስጥ ናስቶስኔን የሚባለው የአውራጃ ሹም ተነስቶ የሐርሲአተውን መንግስት ገልብጦ ወደ መርዌ ወሠደው። የመናገሻ ከተማውም በመርዌ ሆኖ በናፓታ ነጋሲዎች እግር ተተክቶ የምስራቁንና የምዕራቡን ኢትዮጵያ፣ በልዩ ልዩ ነገድ የተከፈለውን ህዝብ ጠቅልሎ መግዛት ጀመረ። ስለዚህ የኢትዮጵያውያን ነስታት ከናፓታ ወደ መርዌ መቀመጫቸው ሊዛወር የቻለው በናስቶስኔን ንግስና ጊዜ በ546 ነው ማለት ነው። ስለሆነም የፋርስ ንጉስ ከኢትዮጵያዊው ንጉስ ከናስቶስኔን ጋር የገጠመው ግጭት በመርዌ የነበረ መሆኑን ከወዲሁ ተገንዝበን ወደ መንደርደሪያችን እናምራ።

አሱርባኒፓል ኢትዮጵያውያንን አባሮ መምፊስንም ቴብንም በጦር ሃይል ይዞ በዘረፋም በምርኮም እያስጨነቀ ካስገበረ በኋላ በሰፊው ግዛቱ ያሉ የከለዳውያንና የኤላም ህዝቦች

ሸፍተዋልና ቶሎ ድረስ የሚል መልዕክት ስለመጣለት በፍጥነት ወደ አገሩ ተመለሰ። በዚያም ሳለ ሞተ።

በዚህ ጊዜ ግብጻውያን ከኢትዮጵያውያኑም ከአሶራውያኑም ግዛት ክፍት የነፃነት ጊዜ ሲያገኙ ፕሳሜቲክ 1ኛ የተባለውን የሳይሱን ንጉስ አነገሱ።



ከአርሱም ጋር አሶራውያን የደለደሏቸው የአውራጃ ሹሞች አብረው ማስተዳደር ጀመሩ።

ንጉስ ፕሳሜቲክም ግብፅን መልሶ ለመገንባት እንቅስቃሴ ያደርግ ጀመር። ይሄው እንደ ፈርኦን የሚቆጠረው ንጉስ ፕሳሜቲክ ከአሶር ግዛት በኋላ የግብፅን ገናናነት ለመመለስ በሚጥርበት ጊዜም ከአሶር በኋላ የተነሳው የባቢሎንን ወራሪነት መቋቋም አቃተው።

የባቢሎን መንግስት በዚህ ጊዜ ተነስቶ ብዙ አገሮችን ከወረረ በኋላ ወደ ግብፅ መጣ። ባቢሎን ቀደም ሲል የአሶር አንድ ግዛት ሆና በአሶር ስር የነበረች ሲሆን፣ አሱርባኒፓል ሲሞት የአሶርን የአገዛዝ ቀንበር ከላያቸው ላይ ጥለው የራሳቸውን መንግስት ለመመለስና እንደቀድሞዋ ሃያል የሆነችን ባቢሎን ለመመስረት ያደረጉት ጥረትም ተሳካላቸው።

በዚህም በጥንታዊቷ በሐሙራቢ ዘመን የነበረችው ገናናዋ ባቢሎን ወድቃ በድጋሚ በመነሳቷ የባቢሎናውያን ዳግም ትንሳኤ ተሰኘ። እናም በዚህ ጊዜ ነው በርካቶችን ለመግዛት የቻሉትና አሁንም ወደ ግብፅ የመጡት። ከባቢሎን ጋር አብረው ነፃ ከወጡ አገሮች ውስጥም ሜዶን አንዷ የነበረች ሲሆን በሜዶናውያን ጦርነትም የባቢሎን ዋና ከተማ ነነዌ ከቴብና ከመምፊስ የበለጠ ተበዘበዘች። በእነዚህ ጊዜያቶች ሁሉ ኢትዮጵያውያን ነገስታቶች በዚያው በናፓታ አገራቸውን እያስተዳደሩ ይገኙ ነበር።

እናም በመጀመሪያ አሶር ቀጥሎ ባቢሎን ግብፅን ካስጨነቁ በኋላ ተከታዩ የፋርስ መንግስት ሆነ። ባቢሎንንም ስትገዛት የቆየችው ፋርስ መልሳ ገዛቻት።

ቂሮስ የተባለው የዚህ ዘመን የፋርስ ንጉስ በአባቱ የፋርስ፣ በእናቱ የሜዶን ተወላጅ ነው። አባቱም ካምቤዝ 1ኛ ገናና ነበር። ቂሮስ የአባቱን መንግስት ወርሶ በባቢሎን መንግስት ላይ ተነሳ። ድል አድርጎ የፋርስን መንግስት አግንኖ 31 ዓመት ገዝቶ ሲሞት ልጁ ካምቤዝ 2ኛ ስልጣኑን ተረከበ።

ካምቤዝ 2ኛ ከአባቱ ከቂሮስ የበለጠ የፋርስን መንግስት አስፋፋ። 4 አመት ያህል የፋርስን፣ የባቢሎንን፣ የሶርያን፣ የፓለስታይንን ግዛቱን እያደላደለ ከቆየ በኋላ በ5ኛው አመት ላይ

ሠራዊቱን ይዞ የፈረደባትን ግብፅን ለማስገበር መጣ። መጥቶም መምፊስን ይዞ ንጉሱንም ገድሎ ግብፅን በሙሉ ያዘ። የፋርስ መንግስት አሶራውያን እንዳደረጉት ወደ ግብፅ መጥቶ አስገብሮ አልተመለሰም። ይልቁንም በግብፅ ግዛት ሆና 27ኛውን ሥርወ መንግሥት ተቀመጠ።

በጊዜ ሂደትም ከግሪክ ጋር እየወገኑም ራሳቸውም እየተፋለሙ ፋርሶችን ለማባረር ቢችሉም መልሰው እየተወረሩና እየተሸነፉ ቆይተው ከሁለተኛው የፋርስ ግዛት በኋላ በ300ኛው ዓመት ቅ.ል.ክ ታላቁ እስክንድር እስኪነሳ ድረስ ቆይተዋል። ከዚህ በኋላ ባለውም ጊዜ ነፃነታቸውን እንዳጡ ነው ግብፆች ያሳለፉት።

## ምዕራፍ ፳፪
## የንጉስ ናስቶስኔን ዘመነ መንግስት
## ከ546-532

የቂሮስ ልጅ ካምቤዝ 2ኛ ጦሩን እየመራ ሠቶቶ የግብፅ መንግስት በወረረውና ባሸነፈው ጊዜ /በ5 መቶኛው ዕጋማሽ አመታት/ እስካሁን ያስገበረው የባቢሎን፣ የአሶር፣ የእስራኤል፣ የጢሮስ፣ የሲዶና፣ የግብፅ፣ የሲና፣ የዓረብ ግዛት ሁሉ ሳይበቃው በግብፅ ከተደላደለ በኋላ የኑብያ ኢትዮጵያን መንግስት ለመውረር አሰበ።

ከመውረሩ በፊትም የኢትዮጵያ ንጉስ ሐይሉ ምን ያህል መሆኑንና፣ አደረጃጀቱ ምን እንደሚመስል ለመረዳት ሰላዮችን ወደ ኢትዮጵያ ላከ። የላካቸውም ሰዎች የመርዌን ቋንቋ የሚችሉ ተብለው የተመረጡ ነበሩ።

የሠጀመሪያው የመርዌ ንጉስ ናስቶስኔን በመርዌ በነገሰበት ዘመን ካምቤዝ /የፋርስ ንጉስ/ መልዕክተኞችን ማለትም ሠላዮችን ልዩ ልዩ የመቃያ ስጦታ አስይዞ ወደ ኢትዮጵያው ንጉስ ላካቸው። እነርሱም መጥተው "እነሆ ወዳጅነትህን የሚፈልገው ታላቁ የፋርስ ንጉስ ካምቤዝ የላከልህ ገፀ በረከት" ብለው ልብስ፣ የአንገትና የእጅ ጌጥ፣ ሽቶና መጠጥ አቀረቡለት።

የኢትዮጵያው ንጉስ ናስቶስኔንም ስጦታውን በዝርዝር አይቶ ከተቀበለ በኋላ ለመልዕክተኞች እንዲህ የሚል ምላሽ ሰጣቸው። "የፋርስ ንጉስ ይህንን ገፀ በረከት አስይዞ የላካችሁ የመንግስቴን ሐይል መርምራችሁ ተመልሳችሁ እንድትነግሩት ነው እንጂ በእውነት የኔን ወዳጅነት ፈልጎ አይደለም። ... አሁንም ከኔ ዘንድ ይህን ቀስት ወስዳችሁ ለፋርስ ንጉስ ስጡት። ልክ እንደኔ ይህን ቀስት የሚዘረጋ ከፋርስ ውስጥ ጎበዝ የተገኘ እንደሆን ከዚያ በኋላ መጥተው ይውጉኝ" በማለት እርሱ ራሱ በመልዕክተኞች ፊት ቀስቱን አጥፎ መልሶ አቃንቶ አሳያቸው።

በተጨማሪም ያመጡለትን ልብስና ወርቅ እያሳያቸው "ይሄ በኔ ዘንድ ርካሽ ነው። እስረኞቹን እንኳን በወርቅ እግር ብረትና በወርቅ ሰንሰለት ነው የማስረው" በማለት ወደ እስር ቤቱ መልዕክተኞችን ወስዶ አሳያቸው።

ከዚያም መልዕክተኞቹ ተሠናብተው ወደ አገራቸው ተመለሱ። ያዩትንና የሠሙትን ሁሉ ለፋርሱ ንጉስ ለካምቤዝ ነገሩት። በተለይ የቀስቱ ሁኔታ አበሳጨው። ቀስቱን ሞክሮም አቃተው። ንጉስ ካምቤዝ እጅግ ከመናደዱ የተነሳ ጦሩን በደንብ ሳያደራጅ በአጠገቡ ያሉትን ወታደሮች ብቻ ይዞ ኢትዮጵያን ለመውጋት ወደ መርዌ ጉዞ ጀመረ።

ግማሹን ጦር በአባይ በኩል ልኮ ግማሹን ደግሞ ራሡ እየመራ ውሃ በሌለበት በኮረስኮ በርሐ በኩል መጣ። ሆኖም እራሱ የሚመራው ሠራዊት በበርሃው ሲጓዝ በውሃ ጥም የተነሳ መጓዝ አቃተው። ስንቅም አለቀባቸው። የፋርሱ ንጉስ ካምቤዝ ሊያበረታታቸው ቢሞክርም የጦር ሠራዊቱ ችግሩን መቋቋም አልቻለም።



ይህንንም ራሱ ካምቤዝ ስለተረዳው እንደተናደደ ሳይወድ በግድ ተመልሶ ወደ ቴብ ከተማ ሄደ። ሐሳቡ ስላልተሳካለትና ኢትዮጵያን ሳይወጋና ሳያስገብር በመቅረቱ ብስጭት አድሮበት ስለነበር እስኪሞት ድረስ በግብፃውያንም በፋርሳውያንም ላይ ብዙ ጭካኔ አደረሠባቸው።

ከኢትዮጵያ ንጉስ ተልኮ የነበረውን ቀስት ማጠፍ መዘርጋት ሁሉ አቅቶት ስለነበርና አንድ ዘመዱ ብቻ አጥፎ ስለዘረጋው ይህንኑ ዘመዱን ገደለው። የግብፅ ንጉስ ሆኖ የነበረውን ፕሳሜቲክን አስገድሎ የግብፅን ግዛት ለእህቱ ባል ለአርአንደስ ሠጠው። እንዲህ እያደረገ በብስጭትና በጭካኔ ደም በማፍሰስ ከኢትዮጵያ መልስ አንድ አመት ተኩል ያህል እንደቆየ ሞተና ልጁ ዳርዮስ 1ኛ በመንግስቱ ተተካ።

ከዚህ በኋላ ባለው ጊዜም የፋርስ ግዛት ከመቸውም ጊዜ የበለጠ ሠፍቶ ከህንድ ጀምሮ እስከ ሊቢያ፣ በደቡብ እስከ ናፓታ ወሠን ሊደርስ ችሏል። በአጠቃላይም በፋርስ ስር የሆኑ 31 ግዛቶች እስከ ዳርዮስ 2ኛ ድረስ ለፋርስ ገብረዋል።

እነዚህ ሁሉ ግዛቶች እንደ ዳርዮስ ላለው ንጉስ በቀጥታ እየገበሩ በሚገዙበት ጊዜ ከ31ዱ የግዛት ክፍል ውስጥ ግብፅ አንዷዋ ናትና በካምቤዝ የተሾመው አርአንዲስ በፋርስ መንግስት ስር ሆኖ ግብፅን በሚገዛበት ጊዜ እንደ አማቹ እንደ ካምቤዝ ሃይለኛ በመሆን በግብፆች ላይ ከህግ ውጭ የሆነ ጫና ያደርግባቸው ጀመር።

ልክ በዚህ ጊዜም የመርዌዎቹ /የኢትዮጵያውያን / ንጉስ ናስቶስኔን መሞቱንና ወንድሙ ሐንዲው አብራ መንግስቱን ተረክቦ ራሱን ችሎ ማስተዳደር መጀመሩን ሠማ።

እናም በካምቤዝ ጊዜ የከሸፈውን አሁን አርአንዲስ የግብፁ ንጉስ በተተኪው ንጉስ በሐንዲው አብራ ላይ ሊፈፅመው አሠበ።

እንግዲህ በንጉስ ናስቶስኔንና በካምቤዝ መካከል ሊካሄድ የታሰበው ጦርነት ባየነው መልኩ በስነ-ልቦና ድል ተጠናቆ ጦር ሳይማዘዙ አልፏል። ይሁን እንጂ በቀጣዩ ምዕራፍ ኢትዮጵያውያንና ፋርሶች ከሽፎ ያልቀረ ጦርነት ማድረጋቸውን የምንመለከተው ይሆናል።

እናም ከላይ ባየነው መልኩ መርዌን የቀረቀረት ኢትዮጵያዊ ንጉስ ናስቶስኔን 14 አመት በቆየው ግዛቱ ካምቤዝን በቃላት አሸንፎ የኢትዮጵያን መናገሻ ከናፓታ ወደ መርዌ አዛውሮ ስልጣኑን ለወንድሙ ለሐንዲው አብራ አስረክቦ አልፏል።

# ምዕራፍ ፳፫

# የንጉስ ሐንዲው አብራ ዘመነ መንግስት

# ከ532-521

በግብፁ ንጉስ በአርአንዲስ ጀማሪነት በፋርስና በመርዌ /በኢትዮጵያ/ መካከል የተደረገውን የጦርነት ታሪክ የፃፈው የግሪክ ተወላጅ የሆነው ሄሊዮዶር የሚባለው ሲሆን፤ 'ኢትዮፒክ' የተሠኘውን ይህን መጽሃፍ ሲፅፍም ጦርነቱ የተተረከበትን የዚያን ጊዜውን መረጃ ተጠቅሞ ነው።

የሄሊዮዶርንና የሌሎችን ፀሃፍት ስምምነት መሠረት በማድረግም የፋርስና የኢትዮጵያ ጦርነት ምን መልክ እንደነበረው አጠር ባለ መልኩ እናየዋለን። ይህን ጦርነት ያስነሳው ሁለት ምክንያት ሲሆን፤ የመጀመሪያው የፋርሱ ንጉስ ካምቤዝ የኢትዮጵያን ንጉስ መውጋት አቅቶት ከመንገድ በመመለሡና የካምቤዝን ሽንፈት የግብፁ ንጉስ ከናስቶስኔን ሞት በኋላ ለመበቀል በማሰቡና ከዚህ ጊዜ ቀደም ብሎም ፋርሶች ኢትዮጵያን መውጋትና ማስገበር ህልማቸው ስለነበር ነው።

ሁለተኛው ደግሞ አንድ ማእድን ያሰበት ስፍራ እንደሆነ የሚታወቀው የኢትዮጵያ ግዛት በዚህ በንጉስ ሐንዲው አብራ የግዛት ዘመን ድንገት ፋርሶች ስለያዙት ነው።

ፋርሶች ምንም እንኳን ኢትዮጵያን /ናፓታንና መርዌን/ እንደሌሎች አገሮች ወግተው ማስገበርና መጠቅለል ባይችሉም፤ ከግብፅ በደቡብ በኩል የሚገኘውንና በቀይ ባህር አቅራቢያ የሚገኙ አንዳንድ የኢትዮጵያ ግዛቶችን ለመያዝ ችለው የነበረ ሲሆን፤ አሁን ግን የበለጠ ለግጭት የዳረገው አንድ ምክንያት ወርቅና ማዕድን የሚገኝበት 'ፊላዬ' በተባለው ከተማ ዙሪያ ያለው አገር ነው።

ይህ ቦታ ከጥንት ጀምሮ በኢትዮጵያውያን እጅ ነበር የሚገኘው። ከላይ በተጠቀሰው ዘመን ግን በፋርሶች እጅ ገብቶ ከተማው በፋርስ ወታደሮች መጠበቅ ጀመረ። ስለዚህ የኢትዮጵያው ንጉስ ሐንዲው አብራ የፋርስን ወታደሮች አባሮ ይችን ከተማ አርአንዲስ ወደ ኢትዮጵያ ከመዝመቱ በፊት በእጁ አስገባት።

በካምቤዝ የተሾመው የግብፅ ንጉስ አርአንዲስም ይህን ሲሰማ ወታደሮቹን ይዞ ከቴብ ከተማ ተነስቶ መጣ። ኢትዮጵያውያኑም ወደዚያው ሔደው ውጊያ ገጠሙ። ነገር ግን ግብፆች አስቀድመው በከተማው ውስጥ ገብተው ስለነበር ኢትዮጵያውያኑ ማጥቃት ከበዳቸው።

ጥረቱ ሁሉ ያልተሳካለት የኢትዮጵያዊው ንጉስም አማራጭ ሲያጣ የአባይን ውሃ መሬት እያስቆፈረ በቦይ አውጥቶ ከተማውን



እንዲያጥለቀልቅና የአርአንዲስ ጦር ከከተማው ቅጥር እንዲወጣ የሚያደርግ ዘዴ ቀየሠ።

ይህ ድርጊት ከተፈፀመ በኋላም አርአንዲስ ከከተማዋ ጦሩን ይዞ ወጥቶ ለመዋጋት ወሠነ። አርአንዲስን ከተከተሉት ሠራዊቶች ውስጥም የፋርስ፣ የሜዶን፣ የሊቢያ፣ የግብፅና የሌሎች በፋርስ ስር ካሉ አገሮች የተውጣጡ ሠራዊቶች ይገኛሉ። በርካታ ፈረሠኛና እግረኛ ወታደሮች ከተሟላ ትጥቅ ጋር ከአርአንዲስ ጎን ተሠልፈዋል።

ከኢትዮጵያው ንጉስ ከሐንዲው አብራ ጎን የተሠለፉት ደግሞ በዋሻና በበርሃ ነዋሪ የሚባሉት የበጃ የብሌማይ ተወላጆች የሆኑና እራሱ ንጉሱ አስከትሎ ያመጣቸው ቋሚ ሠራዊቶች ናቸው። ከበጃዎችና ከብሌማዮች ወገንም በቀስት አደጋገንና በጦር አወራወር በእግር ሩጫና በዝሆንና በግመል ግልቢያ የተካኑ ይገኙባቸዋል።

እነዚህ በርካታ ወታደሮች ከተቀራረቡ በኋላ የፋርስ የፈረሰኛ ጦር ቀድሞ እንዲዋጋ ተደረገ። ኢትዮጵያውያን በንጉሳቸው እየተመሩ ፈረሠኛው ከፈረሠኛው፣ እግረኛው ከእግረኛው፣ ዝሆን ተቀማጩም ባለጦሩም ባለቀስቱም ሁሉም ተደባልቆ ይዋጋ ጀመር።

ፋርሶች ከሁሉም በላይ የተማመኑት በፈረሰኛው ጦር ነበር። ይህንንም ኢትዮጵያውያኑ ስላወቁት በተለይ የብሌማይ ተወላጆች ፈረሠኛ ተዋጊውን ትተው በጎራዴያቸው ውጊያው መሃል ገብተው የፈረሶችን እግርና ሆድ በመቁረጥና በመውጋት ሁሉም የፋርስ ተዋጊ እግረኛ እንዲሆን አደረጉት።

አባረው የሚመቱበትን፣ ጋልበው የሚያመልጡበትን ፈረስ ኢትዮጵያውያኑ ጨረሷቸው። የፋርስ ወታደሮችም ከፈረሳቸው ላይ ከወደቁ በኋላ የለበሱት የብረት ልብስና የራሳቸው ጥሩር ለውጊያውም ለሩጫውም ስለከለከላቸው ብሌማዮቹ እንደልባቸው እየተዋጉ ፈጇቸው።

የቀሩትን የፋርስ እግረኛ ወታደሮችንም ኢትዮጵያውያኑ በተቀመጡባቸው ዝሆኖች እያስረገጡ ጨረሷቸው። ቀስትና ጦሩንም የፋርስ ሠራዊት የሚቋቋመው አልሆነም። የፋርሶችና በፋርስ

ስር ያሉት የግብፅ መሪዎች ውጊያውን እንደማይወጡት ስለተረዱ በወርቅ ሠረገላ ላይ ተቀምጠው ያዙና ይመስኩቱ ከነበሩበት ወርደው ወደ ፈረሶቻቸው በመሔድ በሽምጥ ግልቢያ ሸሹ።

የተረፉት የፋርስና የግብፅ ወታደሮች የንጉሳቸውን መሸሽ ሲመለከቱ ጥቂቶች አብረው ሲሸሹ የቀሩት ተማረኩ። የኢትዮጵያው ንጉስ ሐንዲው አብራ ገና በውጊያው መጀመሪያ ድሉ የኢትዮጵያ መሆኑን በአይያዛቸው ተረድቶ ስለነበር "ግማሻችሁ እዚህ ከምትዋጉ ሂዱና ሌሎች የሚሸሹበትን መንገድ ያዙ" ብሎ አዞ ስለነበር እነዚህ ታዘው የሄዱት

በአባይ ዳር ያለውን መሸሻ ቦታ ዘግተው ይጠብቁ ስለነበር የሸሹት ሁሉ በመንገዱ ቀድሞ መያዝ ተስፋ ስለቆረጡ ግማሾቹ ወደ ባህርና ወደ ገደል እየዘለሉ ሲሞቱ፣ በፈረስ የሸሸው ንጉስ አርአንዴስ ተመትቶ እንደተማረከ ደሙን እያዘራ ከድል አድራጊው ንጉስ ከሐንዲው አብራ ፊት ቀረበ።

የኢትዮጵያው ንጉስ ሐንዲው አብራም ባየው ጊዜ አዘነለት። ብዙ የማፅናኛ ቃላትንም ሠነዘረለት። ቁስሉን እንዲያክሙለትም ለመድሃኒት አዋቂዎች ነገሩለት። ከዚህ በኋላ ምርጥ በሆነው በወርቅ እቃ በተጫነው ዝሆን ላይ ተቀምጦ በጦር ሠራዊቱ እንደታጀበ በየመንገዱ እልልታና ደስታ እየተፈራረቁለት ወደ ሲዬን ከተማ ገባ።
እንደ ዘመኑ ልማድም ለአባይ አምላክ ነጭ በሬ አርዶ የምስጋና መስዋዕት አቀረበ። የኢትዮጵያው ንጉስ የድሉን በዓል በመስዋዕት ስኑስርዓት ከፈፀመ በኋላ ከምርኮኞቹ ውስጥ ባሪያዎቹን ለወታደሩና ለሹማምንቱ በባርነት እንዲያገለግሏቸው አከፋፈላቸው።

የጨዋ ወገን የሚባሉትን ምርኮኞች ደግሞ በነፃነት ለቀቃቸው። ቆስሎ ለተኛው ለግብፅ ንጉስ ለአርአንዴስ እንዲህ ሲል ላከበት። "ለዚህ ጦርነት ምክንያት የሆነውን የፊላዬን ከተማና የማእድኑን ስፍራ በእጄ አደርጋለሁ። ከዚህ የበለጠ ከንቱ የግዛት ፍላጎት የለኝም። ራሱ በፀባዩ በአባይ የተከለለው የጥንቱ አገሬ ይበቃኛል። ፍርድንና ህግንም ለማክበር ስል አንተንም በነፃነት ለቅቄሃለሁ። ነገር ግን ለወደፊቱ ከወሠንህ አትለፍ። ለፋርስ ንጉስም እንዲህ ብለህ ፃፍለት።

ወንድምህ ሐንዲው አብራ ድልን በጨበጣ ውጊያ አግኝቷል፤ ነገር ግን የራስህን አገር መልሶ ለቆልሃል። ይህንንም ማድረጉ ወዳጅነትህን ፈልጎ ነው። ምክንያቱም ፍቅር ለሠው ልጅ ከአንቱ የበለጠ ነገር ነውና። ይሁን እንጂ የጦርነት ምልክት በምትሠጥበት ቀን ለመዋጋት እምቢ አልልም።"

ንጉስ ሐንዲው አብራ ይህንን ሁሉ አድርጎ ሲጨርስ ወደ ዋና ከተማው ወደ መርዌ በደስታ ተመለሠ። ከተመለሰ በኋላም የተለመደውን የአገር ባህልና ልማድ በመከተል ለሀሃይ አምላክ አራት ነጭ ፈረሶችና አንድ ክሴት ያልደረሰ የሠው ወጣት ወንድ፣ ለጨረቃ አምላክም ሁለት ነጫጭ በሬዎችና አንዲት ከወንድ ያልደረሰች ሴት ልጃገረድ ሠዋ።

ይህን መሠሉ ሠው የመሠዋት ልማድ በአፍሪካና በእስያ፣ በምስራቅ አውሮፓና በሌሎችም የተለመደ ነበር። የመርዌዎም፣ የግብፃውያንም፣ የአሶራውያንና የፍልስጤማውያን ካህናትም ጠንከር ያለ



ትግርና ጦርነት ሲገጥማቸው ከድል በፊትና በኋላ ለአማልክቶቻቸው የሚሠውት ሠውን ነበር።

የኢትዮጵያው ንጉስ ሐንዲው አብራ በመርዌ ከተማ የድሉን በዓል የመስዋዕቱን ስነ ስርዓት ከፈፀመ በኋላም በኢትዮጵያ ግዛት ስር የሚጠቃለሉ አገሮች ውስጥ የሚኖሩት ሁሉ እንኳን ደስ አለህ ለማለት የሴሮን ሠዎች፣ የቀይ ባህር፣ የየመን፣ በዋሻ የሚኖሩና ከኤርትራ ባህር ዳር ያሉት ሁሉ ወርቅና ጥንድ አንበሶች፣ ብሌማዮች ቀስትና ወስፈንጥር፣ አክሱሞች ቀጭኔ አመጡለት።እርሱም የድሉን በዓል ለማክበር መታያ እየያዙለት ለመጡት ሁሉ ሽልማትና ስጦታ እየሠጠ አስደስቶ በያገራቸው ሸኛቸው። በዚሁ ጊዜም ታስረው ለነበሩ እስረኞችና ወንጀለኞች ሁሉ ምህረት አድርጎ ሁሉንም አስደሰተ።

የዚህ ንጉስ ታሪክ ሲታተትም በዘመኑ በቅን ፍርድ የሚታወቅ እየተባለ ተፅፎለታል። ኢትዮጵያዊው ንጉስ ሃንዲው አብራ ባየነው መልኩ የፋርስን ጦር ተዋግቶ ድል አድርጎ፣ የተወረረ ቦታሁን አስመልሶ፣ የጦርነትን ሳይሆን የፍቅርን አስፈላጊነት ለፋርሱ ንጉስ ገልፃለት አልፏል።

# ምዕራፍ ፳፩

## የመርዌ መዳከም

መርዌ ከ546 ቅ.ል.ክ እስከ 154 ዓ.ም ድረስ ለ700 አመታት የኢትዮጵያ የመናገሻ ከተማ ሆና አገልግላለች። አክሱማውያኑም በግዛታቸው ላይ በራሳቸው ንጉስ እየተገዙ ቆዩ እንጂ የንጉስ ነገስቱ መቀመጫ መርዌ ነበረች።

ከሐንዲው አብራ በኋላም በመርዌ በርካታ ነገስታቶች ተፈራርቀዋል። ከእነዚህ በመርዌ ከተፈራረቁት የኢትዮጵያ ነገስታት ውስጥም ኒካውላ ህንዳኬ 3ኛ አንዷ ናት። በእርሱዋ ዘመን ደግሞ ታላቁ እስክንድር ታላቅ የተባለበት ዘመን ነበር።

ታላቁ እስክንድር ግዙፉን የፋርስ መንግስት ጥሎ የራሱን ግዛት በግብፅ ሲመሰርትና የዓለም ንጉስ ተብሎ ሲሠየም፤ ከዚያም ከአሶር ወደ ፋርስ፣ ከፋርስ ወደ ህንድ አገር ሳገር እየዞረ ግዛቱን ሲያሰፋ ኖሮ በኋላ ወደ ባቢሎን ተመልሶ በ323 ቅ.ል.ክ ሲሞት የኢትዮጵያ ገዥ የነበረችው ኒካውላህንዳኬ 3ኛ ለታላቁ እስክንድር በመልዕክተኛ እንደገበረች ይነገራል።

"ወእምድኅረ ዝንቱ ገረረ ሎቱ ሀበሻ" "ከዚህ በኋላ ሀበሾች ተገዙለት" ይላል የዮሃንስ መደብር መፅሀፍ። እስክንድር በመልዕክተኛው የአባይን መነሻ እንዳስመረመረና ከህንዳኬ 3ኛ ጋርም ልዩ ወዳጅነት እንደነበረው በርካቶች ፅፈዋል።

እናም እስክንድር ከሞተ በኋላ ግዛቱን የጦር አለቆቹ ሲከፋፈሉት የግብፅ ግዛት የደረሰው ለፕቶሎሚ ሶተር ነበር። ፕቶሎሚ በግብፅ ላይ ነግሶ በሚያስተዳድርበት ዘመንም የኢትዮጵያዋ ንግስት ኒካውላ ህንዳኬ 3ኛ የሞተችበት ዘመን ሲሆን፤ ፕቶሎሚ ሶተር እንዲሁም ከእርሱ ቀጥሎ የግብፅ ገዢ የሆነው ፕቶሎሚ ፊላደልፍ በኢትዮጵያ የሰሜን ጠረፍ ወታደርና ሠዎቹን መላክ ጀመረ። የኢትዮጵያ እጣ ፋንታም ከግብፅ ጋር አንድ አይነት እየሆነ የሚሄድ መሰለ።

ፕቶሎሚ ፊላደልፍ በምዕዋ አጠገብ አንድ የባህር ወደብ አሠርቶ በስሙ ፕቶሎማይስ ብሎ ሠየሚል። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የሠሜኑ ኢትዮጵያ የንግድ ማዕከል መሆን ጀመረ። እንዲሁም ከቀድሞ ጀምሮ የነበረው የአዶሊስ ከተማ መደብ ከጊዜ ወደ ጊዜ የበለጠ እየደመቀ የግብፅና የኢትዮጵያ ዋና የሸቀጥ ማመላለሻ ሆኖ ነበር። ............

የግብፅ መንግስት ከፕቶሎሚ ሶተር/በየሊሞስ/ እንዲሁም ከተከታዩ ፕቶሎሚ ፊላደልፍ በኋላ የተከታተሉት ገዥዎች የእነርሱው ተከታዮች ሲሆኑ፤ እስከ ፕቶሎሚ 15ኛ ድረስ ማለትም ከ.ክ ልደት በፊት ከ330-30 ዓ.ም ድረስ የራሳቸው ግዛት አድርገዋት ቆዩ።



ከዚያም ጁልዩስ ቄሳር የሮማን ግዛት ከሌሎች ይበልጥ አስፋፍቶ ተቀናቃኙን ፖምፔን ካባረረ በኋላ ወደ ግብፅ መጥቶ ግብፅን በግዛቱ ስር አደረገ። ጁልዩስ ቄሳር የግብፅን ግዛት በስሩ ካደረገ በኋላ ኑብያንም ለመያዝ ሲያስብ የጦር አለቆቹና አማካሪዎቹ "በማንም ተገዝታ የማታውቅ የጎበዝ አገር፤ ትልቁ የፋርስ ንጉስ ካምቤዝ ተሸንፎ የተመለሰባት አገር ናት" ብለው አስጠነቀቁት።

ከግብፅ እስክንድርያ ወደ ሮማ ተመልሶ ጁሊየስ ቄሳር ሲሞትም አወግስጦስ /አውግስቲን/ ተተክቶ ወደ ግብፅ በመምጣት ከግብፅም አልፎ ኑብያን ወረረ። ከኢትዮጵያውያን ጋር ተዋግቶም ጦርነቱ በእርቅ እንዲቆም ተደረገ። እናም ከዚያ ጊዜ በኋላ በተለያዩ ጫናዎች የኑብያው ኢትዮጵያ ወደ ግብፅ በሚመጡ ወራሪዎች እየተነካካ በየጊዜው ሲዳከም፤ ከጎኑ ያሉት የአክሱም ኢትዮጵያውያን አክሱምን እያገነኑ ሲሔዱ ችለዋል። መርዌ ተዳክሞ አክሱም ሊገን የቻለበት ምክንያትም በግሪኮች አማካኝነት በአዶሊስና በአካባቢው ባሉ ወደቦች ንግድ እየተስፋፋ በመሄዱ ሲሆን፤ በተቃራኒው ደግሞ መርዌ እየተዳከመች ነበር። ሆኖም እስከ 2 መቶኛው ዓ.ም ድረስ የመናገሻ ከተማነቷ አልቀረም።

መርዌ የኢትዮጵያ መናገሻ ከተማ በነበረችበት ጊዜ ምንም እንኳ በክርስትና ዘመን የንግስት ህንዳኬ ጃንደረባ በፊሊጶስ እጅ ተጠምቆ ወደ መርዌ ቢመጣም በመርዌ ክርስትና ሊስፋፋ አልቻለም። በዚያ ዘመን ማለትም ከ.ክ. ልደት በኋላ የኑብያ መንግስት ግንኙነቱን ከእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ጋር አጥብቆ ክርስትናን ለማስፋፋት ቢታሠብም የታሰበውን ያህል ሳይስፋፋ ቆይቷል። ነገር ግን ቀጥሎ ባለው ጊዜ ነብዩ መሐመድ ተነስተው የእርሳቸው ተከታዮች ግብፅን ይዘው ወደ ሙስሊምነት ሲለውጡት የኑብያ ክርስቲያኖች ሊዋጉ ቢሞክሩም አረቦች ከግብፅ እየመጡ በጦርነትም በስብከትም በየጊዜው ስላየሉባቸው ወደ ሙስሊምነት ሊቀየሩ ችለዋል።

ይህ የሆነው ከ.ክ ልደት በኋላ ከ800-1ሺ ዓ.ም ገደማ ቢሆንም፤ ከዚያ በፊት ግን አክሱማውያን አካባቢያቸው ላይ በተለያየ ጊዜ የገቡ የግሪክ፣ የሮማና የሌሎች ሃያላን አገራት ዜጎች ስለሠፈሩ ከመርዌ ይልቅ አክሱማውያኑ ሊገኑ ችለዋል። እንደተባለውም ለወደብ ቅርብ ስለሆኑ በንግድና በሌሎች ነገሮች ሳቢያ አክሱም የመናገሻ ከተማ ለመሆን ችላለች። የቀረውን ተያያዥ ታሪክም በአክሱም ታሪክ ውስጥ እናገኘዋለን........።

ንግዱ እንዲካሔድ አዘዝኳቸው። ከሌውኮ እስከ ሳቤይ ድረስ ያሉትን ህዝቦች ከኔ በፊት የነበሩት ነገስታት ያላስገበሯቸውን አስገበርኩ።

ስለዚህ ለትልቁ አምላኬ ለወለደኝ፤ ከምስራቅ እጣን እስከሚገኝበት፣ ከምዕራብ እስከ ኑብያ፣ እስከ ሳሱ ያሉትን ህዝቦች ሁሉ በእርዳታው ስላዝሀኝ ለአሬስ ምስጋና አቀርባለሁ። እኔም ራሴ ሔጄ፣ የጦር መኮንን ልኬ በውስጤ የሚገዛውን ህዝብ ሠላማዊ ካደረግኩ በኋላ ለመርከበኞች ደህንነት ይሆን ዘንድ ለዜውስ፣ ለአሬስ፣ ለፖሲዶን፣ መስዋዕት ለማቅረብ እወርዳለሁ። በዚሁ ስፍራ የጦር ሠራዊቴን ሠብስቤ በሠልፍ በነገስኩ በ27ኛው ዓመት ይሄን ዙፋን አምጥቼ ለአሬስ ሰጠሁ።" ይላል።

እንግዲህ አክሱማውያን አክሱምን ከመከተማቸው በፊትና በኋላ ጥብቅ ቁርኝት የፈጠሩት ከግሪክ ጋር መሆኑን በአማልክቶቻቸው መረዳት ይቻላል። እንዲሁም በፅሁፋቸው። ስለዚህ የቀድሞዎቹ ነገስታት በግብፆች በነአሞን ሲያመልኩ የነበረ ሲሆን፤ አክሱማውያን ደግሞ በግሪኮች አማልክት እያመለኩ ነው የቀጠሉት።

ከላይ ባየነው ፅሁፍ መሠረትም ቀደም ሲል መርዌ መናገሻ በነበረች ጊዜ ንጉስ ሐንዲው ኡብራ ፋርሶችን ባሸነፈ ጊዜ አክሱሞች መታያ ይዘው ሄደው እንካን ደስ ያለህ እንዳሉት አይተናል። አሁን ደግሞ ክርስትና ከገባ በኋላ፤ ይህ ንጉስ ከአክሱም ተነስቶ ብዙ አገሮችን ማስገበሩን ስናይ የኢትዮጵያ መናገሻ ከተማ ከመርዌ ወደ አክሱም የተዛወረው በዚሁ ንጉስ ጊዜ ማለትም ክርስትና ከገባ ከጥቂት ጊዜ ጀምሮ መሆኑን እንረዳለን።

ይህ የአክሱም ንጉስ እነዚያ የጠራቸው አገሮች አዋ ያለው አድዋ ወይም የዩሃ አውራጃ፣ ዜንጋቤንና አንጋቤ ያለው ደግሞ ኮስማስ እንደገለፀው በአዶሊስ ዙሪያ ያለው የትግሬ አገር፣ ቲያሞ /ጪያሞ/ ያለው የጋምቤላን ህዝብ ፣አታልሞ ያለው የኩናማን አገር፣ ቤጋ፣ ታንጋይቲ፣ አታቢቲ የሚላቸውም ከአክስም ምዕራብ ሠሜን እስከ ግብፅ ግዛት /ወሠን/ የሚገኙትን ሲሆን፤ የበጅያ /ብሌማይ/ ህዝቦችን ነው። ራውዚ የሚለው ሱማሊን፣ ሳሱ የሚለው ወርቅ የሚገኝበትን የወሊጋን አገር እንደሆነ ታውቋል።

ሎውኮሚ፣ አራቢት፣ ኪናይዶክልፒት የተባሉት ደግሞ በዓረብ ማዕከላዊና ሠሜን፣ በኤርትራ ባህር ዳር በደቡብ በኩል ያሉትን ህዝቦች እንደሆነ ተገምቷል።

ኮስማስ የተባለው ግሪካዊ በ500ኛው ዓ.ም የመጀመሪያው አመታት ላይ በአክሱም በሚመላለስበት ጊዜ በዚያ ዘመን የአክሱም ንጉስ የነበረውና



ወደፊት ሙሉ ታሪኩን የምናይለትን ንጉስ ካሌብን ወደ አረብ ለመዝመት ሲዘጋጅ እንዳየም ምስክርነቱን ሠጥቷል።

ከላይ ያየነውና ኮስማስ የገለበጠው የአዶሊስ የእብነበረድ ዙፋንና በሐውልቱ ላይ የተፃፈው ፅሁፍ ከወደ መጀመሪያው ላይ ተቆርጦ ስለጠፋ ከአክሱም ነገስታት ውስጥ የየትኛው ንጉስ ታሪክ እንደሆነ በትክክል ሊታወቅ ባይችልም፤ ክክርስትና በኋላ በመጀመሪያው ምዕተ አመት እንደሆነ ግን የብዙዎቹ ግምት ነው። ምናልባትም የዚህን ንጉስነገስት ማንነት ለማወቅ ቀላል መንገድ ሳይኖር አይቀርም። ይኸውም ከ154 እስከ 184 ዓ.ም የነገሠውና በቀጣዩ ክፍል በምናየው የነገስታት ዝርዝር ውስጥ በተራ ቁጥር 18 ላይ የሠፈረው አ ዶ ገርን አሠግድ የተባለው ንጉስ ይመስላል። ምክንያቱም ከሐውልቱ ፅሁፍ ላይ እንደተገኘው ራሱ ንጉሱ ታሪኩንና ያስገበራቸውን አገሮች ሲዘረዝር 'በነገስኩ በ27ኛ አመቴ' የሚል ፅሁፍ በታሪኩ ውስጥ አካቷል። ከንጉስ ባዚን ጀምሮ ከተከታተሉት ውስጥ ደግሞ 27 አመት የገዛ ንጉስ የለም።

እስከ አፄ ካሌብ ድረስ ሁለት ንጉሶች ብቻ 30 አመት የገዙ ሲሆን፤ እነርሱም አውዶ ገርን አሠግድ እና እራሱ ንጉስ ካሌብ ናቸው። ስለዚህ በታሪክ ነገስቱ የነገስታት ዝርዝር ውስጥ ይህን ያህል አመት የገዙት እስከ ካሌብ ድረስ ሁለቱ ብቻ ስለሆኑ አክሱምን የቆረቆረው ንጉስ አውዶ ገርን አሠግድ መሆኑን መገመት ይቻላል፤ ማረጋገጥ ባይቻልም።

ከዚህ ቀጥለን ከምናያቸው ስለአክሱም ከሚዘክሩ የታሪክ ማስረጃዎች በመነሳትም ከጥንታዊቷ ከሣባ ከተማ /ንግስተ ሣባና ልጇ እንዲሁም ጥቂት ተከታታይ ነገስታቶች ከነገሱባትና በአክሱም አካባቢ ትገኝ ከነበረችው መናገሻ ከተማ በኋላ/ ናፓታና መርዌ ቀጥለው፤ ከዚያ በኋላ ባለው ጊዜ መርዌ ስትቀዘቅዝ አክሱማውያኑ እንደ አዲስ አክሱምን የቆረቆሯት ክክ.ልደት በኋላ በመጀመሪው ምዕተ አመት አቅራቢያ ሊሆን እንደሚችል እያሠብን፤ አለዚያም እንደተባለው 154 ዓ.ም እንደሆነ ገምተን፤ ከዚያ በኋላ ባለው ጊዜ ግን በኢዛናና በካሌብ ጊዜ የበለጠ አክሱም እየገነነችና እየደመቀች እንደሔደች እንረዳለን ማለት ነው።

ሌላው መረጃ ደግሞ 'በኤርትራ ባህር ላይ ጉዞ' የሚል ትርጉም ያለው 'ዘ ፔሪፕለስ ኦፍ ዘ ኤርትሪያን ሲ' በመባል የሚታወቀውና በ2ኛው መቶ ዓ.ምህረት በግሪክ ተወላጅ የተፃፈው ነው።

በ4ኛው ምዕተ አመትም በግዕዝና በግሪክ ቋንቋዎች የተፃፉ የንጉስ ኢዛና ዜና መዋዕሎችና፣ እንዲሁም በንጉስ ካሌብ ጊዜ በግዕዝ ብቻ የተፃፈው የአፄ ካሌብ ዜና መዋዕል፣ በተጨማሪም ወደፊት የምናገኛቸው አክሱማውያን ነገስታቶች ከወርቅ፣ ከብርና ከነሃስ ያስቀረጿቸው የመገበያያ ገንዘቦች ስለ አክሱምና ስለ አክሱማውያን ታሪክ ከሚዘክሩ መረጃዎች

ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፤ በአካባቢው በተለያዩ ጊዜያቶችና በተለያዩ ነገስታቶች የተተከሉት ሐውልቶችም ተጨማሪ ማስረጃዎች ናቸው።

በዚህ መሠረት በ1ኛው ምዕተ አመት የአክሱም ጥንካሬ ምንጩ መርዌ በመዳከምና በመፈራረስ ላይ በነበረችበት ከላይ በተጠቀሰው ጊዜ የክልሉን የንግድ እንቅስቃሴ በመጠቅለል በቀይ ባህርና በአፍሪካ ቀንድ ተወዳዳሪ የማይገኝለት ሐይልና ስርዓት አክሱማውያኑ ለመገንባት በቅተዋል።

በቀይ ባህር አማካኝነት በንግድ ላይ የተመሰረተው ይህ የአክሱም መንግስት ከመርዌ፣ ከግብፅ፣ ከግሪክና ከሮማ ስልጣኔ፤ እንዲሁም ከአረቢያና ከህንድ ጋር ሠፊ የባህል ግንኙነት ነበራቸው።

ከላይ ከተጠቀሱት አገሮች ወደ አክሱም ይገቡ የነበሩት እቃዎችም ብረት፣ ብር፣ ወርቅና ከወርቅ የተሠሩ የቤት ቁሳቁሶች፣ መስታወት፣ የሸክላ ውጤቶችና ልብሶች፣ የወይን መጠጦች፣ ዘይት፣ የጥጥ ውጤቶችና ሌሎች ሸቀጦች በንግድ ወደ አክሱም ይገቡ ነበር።

አክሱማውያኑ ወደ ተለያዩ አገሮች ይልኩ ከነበሩት የንግድ እቃዎች መካከልም የዝሆን ጥርስ፣ የአውራሪስ ቀንድ፣ የጉማሬ ቆዳ፣ የኤሊ ድንጋይ፣ ልዩ ልዩ እንስሶች፣ ማራኪ ሽታ ያላቸው ቅጠሎች፣ ወርቅና የመሳሰሉት ነበሩ። ለንግድ ልውውጥ አገልግሎት ይውሉ ዘንድም የነሃስ፣ የመዳብ፣ የብርና የወርቅ ሣንቲሞችን አስቀርፀው ይጠቀሙ ነበር።

የገቢና የወጪ ንግድ አስተናጋጅ ወደቦች ደግሞ አዶሊስ፣ ድሬ፣ /ራስ ሳይን/ አዋልት፣ /ዘይላ/ እና በርበራ ነበሩ።

ወደቦችንና የመሐሉን አገር ስፊ አካባቢዎች የሚያገናኙት የሲራራ የንግድ መስመሮች መርዌን በከመአልኬ በኩል እስከ ላይኛው የአባይ ሸለቆ /ነጭ አባይ/ ፣በደቡብ ምዕራብ የሳሱ ወርቅ ማእድኖች የሚገኙበት ድረስ ይዘልቁ ነበር።

በተጨማሪም ከመጀመሪያው ምዕተ አመት ጀምሮ እስከ 6ኛው መቶ ዓ.ምህረት የክርስትና መስፋፋት ለአክሱም ስልጣኔ አንድ ራሡን የቻለ ጠንካራ አስተዋፅኦ አበርክቷል።

"የግዕዝ ቋንቋ ፊደል አናባቢዎችና የንግግር እንዝሮች መገኘት ደግሞ ታላቅ የባህላዊ ፈጠራ ዘመን ከማብሠሩ በላይ፤ ለዛሬዎቹ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እድገት ታላቅ እመርታ ያበሠረ ግኝት ነበር።" በማለትም ኮቢሽካናቪን ጠቅሰው በፃፉትና የኢትዮጵያ የታሪክ መነሻ በተሠኘው ፅሁፋቸው የአገራችን የታሪክ ተመራማሪ ፕ/ር ላጵሶ ሁኔታውን ይገልፁታል።በአጠቃላይ ለአክሱም መነሳትና መመስረት እንዲሁም ለተከታታይ እድገቶቹ መሠረት ከሆኑት ዋና ዋና ጉዳዮች



ውስጥ ከክርስትና መስፋፋት ጋር የተያያዘና ከወቅቱ ሃያላን ክርስቲያን አገሮች ጋር የተፈጠረው ግንኙነት እንደሆነ ታውቋል።

ምንም እንኳ ይህ የሆነው ከ3ኛው መቶ አመት መጀመሪያ አካባቢ ጀምሮ ቢሆንም ከዚያ በፊት በነበሩት ጊዜያቶችም አክሱማውያን ከግሪክ፣ ከሮምና ከቆስጠንጥንያ ጋር የፈጠሩት የንግድ ትስስር ለእድገታቸው በር እንደከፈተላቸው መረዳት ይቻላል።

<u>**የኢትዮጵያ ነገስታት ዝርዝር ከክ.ልደት በኋላ**</u>

| ተ.ቁ | የነገስታቱ ስም | በስልጣን ላይ የቆዩበት ጊዜ በዓመት | የነገሱበት ዘመን ከክ.ልደት በኋላ |
|---|---|---|---|
| 1 | ባዚን | 9 | ከ1-9 ዓ.ም |
| 2 | ሠርጡ ፅንፈ አሰግድ | 21 | ከ9-30 |
| 3 | አካጥታህ ፅንፈ አሰግድ | 2 | ከ30-32 |
| 4 | ሆርኤምትኩ 2ኛ | 2 | ከ32-34 |
| 5 | ንግስት ህንዳኬ 7ኛ /ጌር ሳምት/ | 12 | ከ34-46 |
| 6 | ሐታዝ ባህር አሰግድ /ዞስቃለስ/ | 24 | 46-70 |
| 7 | ምንሴህ ግርማ ሠር | 7 | 70-77 |
| 8 | ሰጥዋ ግርማ አስፋር | 9 | 77-86 |
| 9 | አድገለ | 10 አመት ከ6 ወር | 86-96 |
| 10 | አግባ | 6 ወር | 96-97 |
| 11 | ሠርዓዳ | 16 | 97-113 |
| 12 | መሊስ አላሚዳ | 4 | 113-117 |
| 13 | ሀቃቤ ከሎፅዮን | 6 | 117-123 |
| 14 | ሐቅሌ ሠርጓይ | 12 | 123-135 |
| 15 | ድድሜ ዘርዓይ | 10 | 135-145 |
| 16 | አውጥፓ | 2 | 145-147 |
| 17 | አልአዶ በጋማይ | 7 | 147-154 |
| 18 | ዓውዶ ዣን አሠግድ | 30 | 154-184 |
| 19 | ዛግን ፅዮን ሕገዛ | 5 | 184-189 |
| 20 | ሬፅዮን ሕግዛ | 3 | 189-192 |
| 21 | አዚጋን መዓልባጋድ | 7 | 192-199 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 22 | ገፈሌ ሰብዓ አሠግድ | 1 | 199-200 |
| 23 | ፅጋዮን ብእሴ ወርቅ | 4 | 200-204 |
| 24 | ጋዛ አግድ | 9 | 204-213 |
| 25 | አግዱር አስጓጓ | 8 | 213-221 |
| 26 | ደዊዛ | 1 | 221-222 |
| 27 | ዋከና ንግስት | 2ቀን | 222-222 |
| 28 | ሀውዶስ | 4 ወር | 222-222 |
| 29 | አዕላል ሰንሠገል | 3 | 222-225 |
| 30 | አስፍሐ | 14 | 225-239 |
| 31 | አድገቦ ሠይፈ አርእድ | 6 | 239-245 |
| 32 | አይባ /አይላ/ | 17 | 245-262 |
| 33 | ፀሐመ ለክዱን | 9 | 262-271 |
| 34 | ድጋብ | 10 | 271-281 |
| 35 | ታዜር /ታዜና/ | 10 | 281-291 |
| 36 | አህየዋሶፍያ ንግስት | 7 | 291-298 |
| 37 | /ኢዛናና ሲዛና በአንድነት/ አብርሃና አፅባሃ በአንድነት/ | 26 | 298-324 |
| 38 | አፅባሐ ብቻውን | 12 | 324-336 |
| 39 | አስፋሐ ደለዝ | 7 | 336-343 |
| 40 | ሳህል /ስሁል 1ኛ/ | 14 | 343-357 |
| 41 | አርፍድ ገ/ቀል | 4 | 357-361 |
| 42 | አፅሃን ንግስት | 5 | 361-366 |
| 43 | ርትዕ | 1 | 366-367 |
| 44 | አስፋሐ 2ኛ | 1 | 367-368 |
| 45 | አፅብሐ 2ኛ | 5 | 368-373 |
| 46 | አሜደ | 15 | 373-388 |
| 47 | አብርሐ 2ኛ | 7 ወር | 388-388 |
| 48 | እለ ሳህል | 2 ወር | 388-389 |
| 49 | እለ ገበዝ | 2 | 389-391 |
| 50 | ሳህል /ስሁል 2ኛ/ | 4 | 391-395 |
| 51 | አብርሐ 3ኛ | 10 | 395-405 |
| 52 | አድሃን ንግስት 2ኛ | 6 | 405-411 |
| 53 | ኢዮአብ | 10 | 411-421 |
| 54 | ፀሀም 2ኛ | 2 | 421-423 |
| 55 | አሜደ 2ኛ | 1 | 423-424 |



| | | | |
|---|---|---|---|
| 56 | ሳህል /ሳህለ አህዛብ/ | 2 | 424-426 |
| 57 | ፅባህ መሀረነ ክርስቶስ | 3 | 426-429 |
| 58 | ፀሃም 3ኛ | 2 | 429-431 |
| 59 | እለገበዝ 2ኛ | 6 | 431-437 |
| 60 | አጋሲ /አጋቢ/ | 1 | 437-438 |
| 61 | ሊዊ | 2 | 438-440 |
| 62 | አሜደ 3ኛ /ያዕቆብ/ | 3 | 440-443 |
| 63 | እርማህ /ዳዊት 1ኛ/ | 14 | 443-457 |
| 64 | እምሲ | 5 | 457-462 |
| 65 | ሰልአዮባ | 9 | 462-471 |
| 66 | እልአሜዳ | 8 | 471-479 |
| 67 | ታዚና /ዋዜና/ | 6 | 479-485 |
| 68 | ካሌብ | 30 | 485-515 |
| 69 | ዘእስራኤል | 1ወር | 515-515 |
| 70 | ገብሩ | 1 ወር | 515-515 |
| 71 | ገብረ መስቀል | 14 | 515-529 |
| 72 | ቆስጠንጢኖስ ሳህል | 28 | 529-557 |
| 73 | ወሠን ሠገድ መሐረነ ክርስቶስ | 15 | 557-572 |
| 74 | ፍሬ ሠናይ | 23 | 572-595 |
| 75 | አድርአዝ | 20 | 595-615 |
| 76 | አካለወድም | 8 | 615-623 |
| 77 | ግርማ አስፈር /እርማህ/ 2ኛ | 15 | 623-638 |
| 78 | ዝርጋዝ | 10 | 638-648 |
| 79 | ድግና ሚካኤል | 26 | 648-674 |
| 80 | ባህር ኤክላ | 19 | 674-693 |
| 81 | ጉም /አፄ ገርስም/ | 24 | 693-717 |
| 82 | አስጎምጉም /አፄ ባካላ/ | 5 | 717-722 |
| 83 | ለትም ኢዮኤል | 16 | 722-738 |
| 84 | ተላትም /አፄ እንደቢስ/ | 21 | 738-759 |
| 85 | ዓደጉሽ /አፄ ማህየዊ/ | 13 | 759-772 |
| 86 | አይዙር | 6 ሰዓት | 772-772 |
| 87 | ድድም /አፄ አስፈሪ/ | 5 | 772-777 |
| 88 | ውድድም /አፄ ዳንኤል/ | 10 | 777-787 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 89 | ውድም አስፈሬ | 30 | 787-817 |
| 90 | አርማህ 3ኛ /አፄ እለቆስጠንጢኖስ/ | 5 | 817-822 |
| 91 | ደግናዥን /አፄ ደግነዥን/ | 19 | 822-841 |
| 92 | ግዳዝን /አፄ ህዝበናኝ/ | 1 | 841-842 |
| 93 | ዮዲት ጉዲት | 40 | 842-882 |
| 94 | አንበሳ ወድም /አፄ አንበሳ ሰገድ/ | 20 | 882-902 |
| 95 | ድልነአድ | 10 | 902-912 |

( ተ. የ.መ1951 ዓ.ም )

ይህ ከባዚን ጀምሮ እስከ ንጉስ ድልነአድ ድረስ ያለው ዝርዝር ሲሆን፤ ከድልነአድ በኋላ ደግሞ የመናገሻ ከተማ ለውጥ ተደርጎ አጠቃላይ መንግስቱ፣ በታውም፣ የንግስና የዘር ሐረጉም ከአክሱማውያን ወጥቶ የዛግዌ ስርወ መንግስት ስልጣኑን ተረክቧል። ይህንንም ዘመኑ ላይ ስንደርስ አጠቃላይ ክንውኑን የምናየው ይሆናል።



# ምዕራፍ ፳፮
## የአክሱማውያን /የኢትዮጵያውያን/ የፊደል አመጣጥ

በኢትዮጵያ ባለፉት ምዕራፎች እነዳየነው ቀደም ሲል ናፓታና መርዌ ከግብፅ እንደመዋሠናቸው መጠን ቋንቋቸው፣ ፊደላቸው፣ ሃይማኖታቸው ከግብፅ ጋር ተወራርሶ የቀረ ሆኗል። አክሱም ደግሞ ከዓረብ አገር ጋር ጎረቤት ስለሆነ እንዲሁም ከደቡብ አረብ መጥተው በአክሱምና በአካባቢው ሰፈሩ ያልናቸው የሴም ዘሮች ይዘውት የመጡት ቋንቋና ፊደል ስለነበር ያ ቋንቋ ነው ተወራርሶ እዚህ የደረሠው። እናም አክሱሞች ይጠቀሙበት የነበረውንና ለዛሬው ፊደላችን እንደ አባት የሚቆጠረውን የሳባ ፊደልና የሳባ ቋንቋን መነሻ በማድረግ የፊደላችን ሁኔታ በሚከተለው መልኩ እንየው።

ከሴም ወገን የወረዱትና ከክ. ልደት በፊት ከደቡብ አረብ መጥተው የህንዱን ንጉስ ራማን አሸንፈው አጋዝያን ተሠኙ ያልናቸው ህዝቦች ከዚያ ጊዜ ጀምሮ አክሱምንና አካባቢውን ይዘው ኖረዋል።

እነዚህ ነገደ ዮቅጣን የተባሉት ዮቅጣን ከወለዳቸው ልጆች ውስጥ በ4ኛው ልጁ በሳባ ስም የሚጠሩትና ነገደ ሳባ የሚባሉት ናቸው። እናም ቋንቋቸው ያኔ ይዘውት የመጡት ከግዕዝ ጋር የሚቀራኝ /የሚመሳሰል/ የነበረውና እየቆየ ደግሞ የሳባውያን ቋንቋ፣ የሳባውያን ፊደል እየተባለ ሲጠራ የኖረው ቋንቋ ለዛሬው ቋንቋችንና ፊደላችን አባት መሆኑ ታውቋል።

እነዚህ የሴም ዘሮችም ሀበሳት፣ ሂሚያሪት፣ ሳባውያን,.... እየተባሉ በተለያዩ መጠሪያ እየተጠሩ፤ በተለያዩ በኢትዮጵያ መሬቶች ሠፍረው የነበረ ሲሆን፤ ከእነርሱ ጋርም የኩሽ ዘሮች አብረዋቸው ይኖሩ የነበረ ቢሆንም፤ ፊደላቸው ግን ሳባውያን በሚለው መጠሪያ ተጠቃሎ ነው የሚገኘው። ይህ የሳባውያንና የሂሚያሪት ፊደልም ከሴም ዘር የመነጨ ነው ተብሏል። የጢግሮስና የኤፍራጠስ ወንዝ በሚፈስበት አገር በባቢሎንና በአካድ፣ በአሶር የሚኖሩ የነበሩ የመጀመሪያዎቹ የሴም ዘሮች የሠሜናዊ ወገኖች ለአራማይክ፣ አራማይክ ለእብራውያን፣ እብራውያን ለፊንቄ፣ ፊንቄ ለግሪክ ሲያቀብል፤ በደቡብ በኩል ያሉት ሴማውያን ደግሞ ለነገዳቸው ክፍል ለሆኑት ለሣባውያን ፊደልን አቀበሏቸው።

ሳባውያን ደግሞ ወደ ኢትዮጵያ ከተሻገሩ በኋላ ይዘው የመጡትና እዚህ ለነበረው ህዝብ ያወረሱት ፊደል እስከዚህ ጊዜ ሊደርስ ችሏል። ወራሽ ከአውራሽ በሚቀባበሉበት ጊዜም ከዘሚን ብዛት የተነሳ እየተሻሻለ መጥቶ የጥንቱ የሳባውያን ፊደል ወደ አክሱሞች፣ ከአክሱሞች ወደ ዛሬው ፊደላችን እየቀጠለ ሲመጣ ጥቂት መለያየት ብቻ የሚታይበት ሊሆን

ችሏል። የሳባውያን ፊደል የሚጀምረው እንደመሠሎቹ እንደ አራማይክ፣ እንደ ፊንቄ፣ እንደ እብራውያንና እንደ ፅርአውያን አ በ ገ ደ እያለ ነው።


ሲፅፉ ደግሞ ከቀኝ ወደ ግራ ፅፈው ከዚያም በጨረሠበት መስመር ግርጌ ላይ በመቀጠል ከግራ ወደ ቀኝ ከቀኝ ወደ ግራ ይመለሳሉ። በዚህ ምክንያት ግሪኮች የሳባውያንን ፊደል "BOUSTROPHEDON" ወይም 'የበሬ እርሻ' በማለት ሠይመውታል። በበሬ ሲታረስ መጀመሪያ ከተተለመ በኋላ በዚያው በጨረሱበት ጎን ጀምሮ እርሻውን መቀጠል እንጅ ሁለተኛውን ትልም ለማረስ ወይም ለመቀጠል ወደጀመረበት አይመለስምና ነው። የቆዩትም ሆነ የቅርብ ጊዜ የታሪክ መርማሪ የሆኑ አውሮፓውያን ፊደልንና ልማድን በማጥናት የታወቁት እነ ኤ ቴለር፣ እነ ፒ ቤርጅ፣ እነ ዴ.ሐ ሙለር በሐውልት ላይና በየቋጥኙ የተፃፉትን ጥንታዊ ፅሁፎች እየገለበጡ ፍችውን እያጠኑ የጥናታቸውን ውጤት ይፋ ሲያደርጉ ኖረዋል። ሌሎች ሊቃውንትም ከመረመሩት በኋላ አምነውበት በየፅሁፋቸው ከሚያካትቱት ውስጥ የእነዚህ የመካከለኛው ምስራቅ አገሮችና ለኛ ለዛሬው ፊደላችን አባት የሆነውን የሳባውያን ፊደል አመጣጥ ሲተርኩ ቆይተዋል።

የሆነ ሆኖ ጥንታዊው የሳባ ፊደል ከግራ ወደ ቀኝ ከቀኝ ወደ ግራ በምልልስ ያለማቋረጥ ሲፃፍ ኖሯል። ቀጥሎ ደግሞ አክሡሞች ይህንኑ የአባቶቻቸውን የሳባውያንን የፊደል ዘር ሳይለቁ አፃፃፉን ግን ከግራ ወደ ቀኝ እንዲሆን አድርገው አሻሽለው እንደተጠቀሙበት በየሃውልቱ ላይ በአክሱም፣ በዬሃ፣እንዲሁም በጥንታዊ የኢትዮጵያ ከተሞች ይገኛል። ይህን መሻሻል ደግሞ ከክርስትና በፊት ከ2 መቶ ዓመት ጀምሮ የግሪክ ስልጣኔ በአክሱምና በአካባቢው ይገባ ስለነበር በሐይማኖት፣ በንግድና በሌሎች ነገሮች በወደብ አማካኝነት ጠንክሮ ስለነበር ከግራ ወደ ቀኝ ብቻ መፃፍን አክሱማውያን ከግሪክ እንደወሠዱት ይነገራል።

በተጨማሪም አክሱማውያን ያኔ የተዘቀዘቀ ወይም በጎኑ የተኛውን ፅሁፍ በመገለባበጥና በማዘዋወር የሳባውያንን ፊደል ለዋውጠውታል።

በአጠቃላይ የሳባውያንን ፊደል አክሱማውያን እንዴት እንደለዋወጡትና እንዳሻሻሉት ከሠንጠረዡ እንረዳ።





ሲወርድ ሲዋረድ መጥቶ የዛሬው የአማርኛ ፊደላችን የደረሰው ባየነው መልኩ እየተለዋወጠና እየተሻሻለ ነው። የአሐዝ ቁጥሮቻችን በተመለከተም ከግሪክ ፊደል ለመወሠዳቸው ወይም መሠረታቸው ከግሪክ ፊደላት መሆኑን በመጨረሻው ሰንጠረዥ መረዳት ይቻላል። ............. ሳባውያን ምንም እንኳን ከመካከለኛው ምስራቅ ቢመጡም በኋለኛው ዘመን ከተስፋፋው የአረብኛ ፊደል ጋር ቁርኝት አልፈጠሩም።

ከዚህ በፊት እንዳልነውም የኢትዮጵያ መናገሻ ናፓታና መርዌ በነበሩበት ዘመን አክሱማውያኑ ቋንቋቸው፣ ባህላቸውና ልማዳቸው ሳይበረዝ በግዛታቸው ላይ ሠፍረው ሳይደፈሩ ኖረው የመርዌ መንግስት ሲዳከምና አክሱማውያኑ አክሱምን ሲያቀኑ ያንኑ ቋንቋ፣ ፊደል፣ ባህልና ልማዳቸውን ነው እያስፋፉ የቀጠሉት።

የውጭ ሃገርና የአገር ውስጥ ሊቃውንትም አክሱማውያኑ ከሌሎች አገሮች ፊደል ይልቅ ለአሐዝ ቁጥሮቻቸው የግሪክን ፊደል መርጠው የወሠዱበትን ምክንያት ሲገልፁ የአክሱም መንግስት ከክርስቶስ ልደት በፊት ጥቂት ጊዜ ቀደም ብሎ እንዲሁም ከክ.ልደት በኋላ የዕሑፍና የሐይማኖት እንዲሁም የስልጣኔ ግንኙነት አድርገው የነበሩት ከግሪክ መንግስትና የእነርሱን ቋንቋና ስልጣኔ በላቲን ቋንቋው ላይ ደርቦ ከወረሰው ከሮማ መንግስት ጋር ስለነበር ነው። በነዚያ ጊዜያቶች ደግሞ የግሪክ ፊደልና ቋንቋ እንደዛሬው እንግሊዘኛ በሠለጠነው ዓለም ተስፋፍቶ ነበር።

..................................

ጥንታዊው የሳባ ፊደል በተለያዩ የአክሱም ነገስታቶች እየተሻሻለና እየተለዋወጠ ኖሮ ያለ ሳድስ ሀ.ለ.ሐ.መ እያለ ቀጥሎ፤ እንደገናም ሳድሶች እንዲካተቱ እየተደረገ ቆየና ከአክሱማውያኑ እጅ መንግስቱ ሲወጣ አካባቢ በግዕዙ ቦታ አማርኛ እየተተካ በመጨረሻ ግዕዙ እየቀረ አማርኛ በመንግስት ደረጃ እውቅና የተሠጠው ቋንቋ ሊሆን ችሏል። ይህንንም በታሪክ ውስጥ፣ በሃውልቱ ዕሁፍና በሌሎች ታሪኮች ጣልቃ እየገባ ወደ ፊት የምናገኘው ይሆናል።



## ምዕራፍ ፲፮
## የአክሱማውያን ቀደምት አምልኮና የክርስትና ወደ ኢትዮጵያ መግባት

ሐይማኖትን በተመለከተ ቀዳማዊ ምኒልክ ከአባቱ ከሠለሞን ኦሪት ህግን ይዞ መጥቶ ስለነበር ከክርስትና በፊት በአክሱምና በአካባቢው የነበሩት፤ እንዲሁም በዛሬዋ ኢትዮጵያ ልዩ ልዩ ቦታዎች ሠፍረው የነበሩት ህዝቦች የኦሪትን ሐይማኖት ተቀብለው በእግዚአብሄር ሲያመልኩ ነበር። ሆኖም ሁሉም ህዝቦች ኦሪትን የተቀበሉ ነበሩ ማለት አይደለም።

ከቀዳማዊ ምኒልክ በኋላ የተከታተሉት ጥቂት ነገስታትም በኦሪት ሲመሩ ቆይተው የኢትዮጵያ መናገሻ ናፓታ ሲሆንና የነገስታቱ ሃይማኖት በግብፅ አማልክት ሲመራ፤ በአክሱምና በአካባቢው የነበሩት ህዝቦች ግን የግብፅን አማልክት አልነበረም የሚያመልኩት። ከኦሪት መግባት በፊት የተለያዩ ጣኦታትን ነበር የሚያመልኩት። በተለይ እባብ በዋናነት ይመለክ ነበር። ይህንኑ ጉዳይ በተመለከተ ታሪክነገስቱ ሳይቀር በግዕዝ እንዲህ በማለት ይገልፀዋል።

“ወመጽአ አባ ሰላማ ምስለ አቡሁ ወህዝበ ኢትዮጵያስ እለ ሀለው በህገ ኦሪት ወቦ እለ ነበሩ እንዘ ያመልኩ በአርዌ ...” በማለት ባጭሩ “ከኦሪት በቀር ሌሎች በእባብ የሚያመልኩ” እንደነበሩ ይገልፃል።

ሰዎች ህግና ስርዓት ከእውነተኛው አምላክ ባልተሠጠበት ጊዜ ነገዱ ሁሉ ልቡ ያሠበውን እየመረጠ ያመልክ እንደነበር ይታወቃል። ሌላው ቀርቶ ከጥፋት ውሃ በኋላ የዘር መነሻ የሆነው ኖኅ አምላኩን አውቆ ይኖር የነበረ ቢሆንም፤ ተከታይ ልጆቹ ግን የኖኅን አምላክ ትተው ትኩረታቸውን ያደረጉት ወደ ጣኦት እንደነበር በተደጋጋሚ አይተናል።

በኢትዮጵያ ልዩ ልዩ አውራጃዎችም የተለያዩ የጣኦት አምልኮዎች ነበሩ። ስለዚህ በመጀመሪያው ዘመን ገና ነገደ ዮቅጣን ድንበር ተሻግረው ሳይመጡ ገሚሱ የኢትዮጵያ ነገድ እንደ ጉረቤቱ እንደ ግብፅ በእንስሳና በፍጥረት /በተፈጥሮ/ በተለይም በእባብ ያመልክ ነበር። የቀረው ነገድ ደግሞ በየአውራጃው በወንዝ፣ በተራራ፣ በዛፍ ያመልክ ነበር። ነባሩ ህዝብ ይህን በመሠለ አምልኮ ሲኖር አጋዝያን፣ ሃበሣን የተባሉት ደግሞ ጥንት በአሶርና በባቢሎን ሲኖሩ፤ ከዚያም በደቡብ አረብ ብዙ ዘመን ኖረው ወደ ኢትዮጵያ ሲሻገሩና ባላባትም ነዋሪ ህዝብም ሆነው ዘራቸውን ከካምና ከኩሽ ዘር ሲደባልቁ ሐይማኖታቸውንም ደባልቀዋል።

በእነርሱ ሐይማኖት በተለይ በተራው ህዝብ ዘንድ እባብ፣ አሞራ ይመለክ የነበረ ቢሆንም የሳባውያን አማልክት ተብለው የሚጠሩት ጨረቃ፣

ፀሃይ፣ ባህር፣ ምድር ናቸው። በተጨማሪም አስታር /ሠማይ/፣ መህርም /ጨረቃ/ የሚባሉት ግማሾቹ የሳባውያን፣ የቀሩት የሂሚያሪት፣ የካታባን አማልክት አግዓዚና ሀበሳን ይዘው የመጡትን አምልኮ በአክሱም ቤተ መንግስት እስከ ኢዛና /አብርሐ/ ዘመን ድረስ ይመለክባቸው ነበር። ከዚህ በፊት እንደተባለውም ከአክሱም መቆርቆር በፊት በነበሩት ከተማዎች በየሃ፣ በደቀመሀሪ፣ በከስከሴ ምልክታቸው ተገኝቷል። ብሔርና ምድር፣ አስታር እና መህርም ደግሞ የአክሱም ነገስታት ባስቀረፁት ሐውልት ላይ ብዙ ጊዜ በአምላክነት ጠቅሰዋቸው ስለተገኙ እሱንም ወደ ፊት እንደጠረደ የምናየው ይሆናል።

አብርሐ ከክርስትና በፊት ባስቀረፀው ሃውልት ላይ በግሪክና በግዕዝ ቋንቋ "ዒዛና ወልደ እለ ዓሚዳ ብእስየ ሐሌን ንጉስ አክሱም ወዘሀሜር ወዘራይዳን ወልደ መህርም ዘይአይትመዋፅ ለፀር ...." እያለ የጨረቃን አምላክ እየደጋገመ ያነሳል። ስለዚህ በአክሱም ቤተ መንግስትና ነገስታት ዘንድ እስከ ክርስትና መግባት ድረስ መህርም ዋነኛ አምላክ ነበር ማለት ነው።

በተጨማሪም የአዶሊስን ሀውልት በግሪክ ቋንቋ ያስቀረፀው ንጉስ የግሪኮችን አማልክት ዜውስን፣ ፓሲዶን ፣አሬስን ሲያነሳና የዙፋኑን መታሰቢያ ለአሬስ ሲሰጥ አይተናል። በሳባና በግሪክ እንዲሁም በግዕዝ ቋንቋና አነጋገር መጠሪያው ይለያይ እንጅ አሬስና መህርም አንድ ናቸው። ምድርና አገር፣ ምድርና ብሄር የሚል ፍችም አላቸው።

በዚህ መልኩም በየቤተመቅደሱ መሠዊያና በሚቀረፁት ሃውልቶች ላይ እንዲሁም ወደፊት በምናያቸው ነገስታቶች በሚያስቀርጿቸው ገንዘቦች ላይ ክርስትና ከመግባቱ በፊት የግማሽ ጨረቃና የመሳሰሉ ምስሎች ተካተውበት ይቀረፁ የነበረ ሲሆን፤ ክርስትና ከገባ በኋላ ደግሞ ይህ ምስል በመስቀል ቅርፅ ሊለወጥ ችሏል።

በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ህዝቦች እስከ ክርስትናና እስልምና መግባት ድረስ ባየናቸው ጣኦታት፣ ቀጥሎ በኦሪተ ህግ፣ እንደገናም በቀድሞዎቹ ጣኦታት እያመለኩ ኖረው፤ እስከ ኢዛና/አብርሐ/ ድረስ ግማሹ ከአሶራውያንና ከፊንቂ በመነጨው አምልኮ፣ የቀረው በግሪክ አማልክት፣ ከእስራኤል የመጣው ስርወ መንግስት ደግሞ በእግዚአብሔር ሲያመልኩ ቢኖሩም አንዱ ሲለወጥ ሁሉም የሚለወጥ፣ አንዱ አንዱን ሲሽረው ሁሉም በግዴታ የሚጠቃለሉበት ሁኔታ አልነበረም።

ሆኖም የመንግስት ሐይማኖት የሆነውን በርካታ ህዝቦች ሲከተሉት እንደኖሩ መረዳት እንችላለን። ከዚያም ዒዛናና ሲዛና በነገሱበት ዘመን በ315 ዓ.ም ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ ሊገባ ቻለ። ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ የገባበትን ጊዜ አንዳንድ ፀሃፍት 302 ዓ.ም ሌሎች 320 ዓ.ም



እያደረጉ ፅፈውታል። ነገር ግን በርካታ መረጃዎች በ315 ዓ.ም መግባቱን ያመለክታሉ። ምንም ቢሆን ግን ክርስትና በዒዛናና በሲዛና ጊዜ በ300ኛው ዓ.ም መግቢያ ላይ እንደገባ የሚያጠራጥር አይደለም። የአገባቡም ሁኔታ አባ ፍሬምናጦስ በተባለ ግሪካዊ ነጋዴ አማካኝነት ሲሆን፤ ዝርዝር ታሪኩ ባጭሩ የሚከተለውን ይመስላል።

ክርስትና ወደ ዓለም የመጣው ኢየሱስ ከተወለደ ጀምሮ የነበረ ቢሆንም በመላው አለም ለመስፋፋት ግን ረጅም ጊዜ ወስዷል። የቆስጠንጥንያ ግዛት ንጉስ የነበረው ታላቁ ቆስጠንጢኖስ ደግሞ ክርስትና በሠሜን አፍሪካ እስዲስፋፋ ጥረት ያደረገና መሰረት የጣለ ንጉስ ነበር። ወደ ኢትዮጵያም እንዲገባ፤ ከዚያም አልፎ በመላው አፍሪካ እንዲስፋፋ ፍላጎት ነበረው። ነገር ግን ኢትዮጵያ የቆስጠንጥንያውን ሳይሆን የእስክንድርያውን ተቀበለች።

ፍሬምናጦስ የተባለው የክርስትና እምነት ተከታይ የሆነው ግሪካዊ (ሶሪያዊ ነው የሚሉም አሉ) ወደ አክሱም ቤተ መንግስት ጎራ የማለት ዕድል ገጥሞት በቤተመንግስት ደረጃ የክርስትናን ሐይማኖት ምንነት ለማስረዳትና ለመመስከር የቻለበት አጋጣሚ ተፈጠረ። በዚህ አጋጣሚም ኢዛናና ሲዛና እንዲሁም እናታቸው አህየዋ ሶፍያ ንግስት /ኢዛናና ሲዛና ህፃን በነበሩበት ጊዜ በሞግዚትነት ኢትዮጵያን አስተዳድራለች/ ይህን ግለሰብ አቅርበው በማነጋገርና ስለክርስትና ሐይማኖት ከተነጋገሩ በኋላ ክርስ ያን የመሆን ፍላጎት እንዳላቸው ነገሩት።

ፍሬምናጦስም ስለክርስትና መሠረታዊ ት/ት በአክሱም ቤተ መንግስት በግሉ ካስተማረ በኋላ ራሱ ማጥመቅ ስለማይችል ጳጳስ ለማምጣት ወደ እስክንድርያ አመራ። እዚያም ደርሶ ከሊቀ ጳጳሱ ከአባ አትናቴዎስ ጋር ተገናኝቶ የኢትዮጵያ ህዝብ ክርስትናን መቀበል የሚፈልጉ እንደሆኑ ገለፀላቸው። እናም ወደ አክሱም ጳጳስ እንዲላክ አሳሰበ።

በዚህ ጊዜ ጳጳሱ "የአገሩን ቋንቋና ልማድ የምታውቀው አንተው ትሻላለህ" በማለት የጵጵስና ማእረግ ለፍሬምናጦስ በመስጠትና በመሾም ወደ አክሱም እንዲመለስ ተደረገ። ከዚያም የቤተ መንግስቱን ሹማምንትና ህዝቡን፤ እንዲሁም ዒዛናንና ሲዛናን እናታቸውን ጨምሮ በክርስትና ልማድ መሠረት አጠመቃቸው። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ማለትም ከ315 ዓ.ም ጀምሮ ክርስትና የአክሱም መንግስት ሃይማኖትና የህዝቡ ሃይማኖት መሆን ቻለ።

ዒዛና እና ሲዛናም ስማቸውን ሊወጠው አብርሃ እና አፅብሐ ተባሉ። ፍሬምናጦስም የጵጵሷ ማዕረግ ሲሠጠው ከሳቴ ብርሃን /ብርሃን አምጪ/ የሚል ስያሜ ተሠጥቶት በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ጳጳስ ሆነ።

ከዚያ ጊዜ ጀምሮም ጳጳስ ወደ ኢትዮጵያ በየጊዜው ከእስክንድርያ ይመጣ ጀመር። ይህ ሒደትም እስከ 1951 ዓ.ም ድረስ ቀጥሎ በመጨረሻ በ1951 ዓ.ም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ጳጳስ በመሆን ኢትዮጵያ ከውጭ የምታስመጣው ጳጳስ ቆሞ በዜጎቿ ጵጵስና እንዲቀጥል ሆነ።

ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ ከገባ በኋላም ኢዛና ቀደም ሲል የጦርነት ድል ቀንቶት ሲመጣ ለአማልክቱ መስዋዕት ሲያደርግና የምስጋና ቃሉን ሲያስቀርፅ ከነበረበት የጨረቃ ምስል ወጥቶ የመስቀል ቅርፅ መተካት ጀመረ።

ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ የገባበት ዘመንና አይነት ባየነው መልኩ ሲገለፅ፤ ነገር ግና ከዚህ በፊት እንደተገለፀውም የኢትዮጵያ ንግስት የህንዳኬ ጃንደረባ በ34 ዓ.ም ወደ እየሩሳሌም ሄዶ ወደ ጋዛ ሲመለስ በፊሊጶስ እጅ ተጠመቀ ተብሎ በመፅሃፍ ቅዱስ በሃዋርያት ስራ ምዕ 8 ቁ 27-40 ያለው ማለት ነው፤ ያኔ ንግስት ህንዳኬ በነገሰችበት በመርዌ እንጅ በአክሱም ያልነበረ ከመሆኑም በላይ በዚያ ዘመንም ምንም ያህል ሊስፋፋ አልቻለም ነበር።

እንግዲህ የአክሱም መንግስት የቀድሞ ግንኙነቱ ከአረማውያን ግሪኮች፣ እንዲሁም ወገኖቹ ከነበሩት ከደቡብ አረብ፣ የእነርሱ መፍለቂያ ከሆነው ከአሶርና ከባቢሎን ጋር የነበረው አሁን ደግሞ ከክርስቲያኑ የቆስጠንጥንያ መንግስትና ከእስክንድርያ ጋር ሆነ።

የክርስቲያኑ ስልጣኔም ከእነዚሁ አገራት ወደ አክሱም መሠራጨት ጀመረ። ህንፃው፣ ስዕሉ፣ ቅርፃቅርፁ የቆስጠንጥንያን መልክ መያዝ ጀመረ። መነኮሳትና ቀሳውስት ሲመጡም በርካታ መንፈሳዊ መፃህፍትም እየመጡ ይተረጎሙ ጀመር። ከክርስቲያን አገሮች ጋር በሐይማኖት አማካኝነት የተፈጠረው ትስስርም ለአክሱም ገናናነት ራሱን የቻለ ለውጥ ያስከተለ ነበር። ሆኖም የቆስጠንጥንያ /የሮም/ መንግስት የሚፈልገውን አይነት ክርስትና አልነበረም ኢትዮጵያ የተቀበለችው። ምክንያቱም የቆስጠንጥንያ ክርስትናና የግብፅ እስክንድርያ ክርስትና መሠረታቸው አንድ ቢሆንም ልዩነት ነበራቸውና ነው። በዚህም ሳቢያ ፍሬምናጦስ ከእስክንድርያ የጵጵስና ማእረግ ይዞ በመጣበት ጊዜ የቆስጠንጥንያው ንጉስ ቁንስጣ አደራ እንዳትቀበሉት የሚል ጭብጥ ያለው ደብዳቤ ለዒዛና ልኮ ነበር። ደብዳቤውንም እንደወረደ በኢዛና ታሪክ ውስጥ ወደ ፊት የምናነበው ይሆናል።



## ምዕራፍ ፳፰

## የአክሱማውያን ገንዘቦችና በላያቸው ላይ የሠፈረው ፅሁፍ

በአክሱም ታሪክ ውስጥ ከዋና ዋና የመረጃ ምንጮች ውስጥ አንዱ ነገስታቶች ያስቀረጿቸው የነበሩ የመገበያያ ገንዘቦች /ሳንቲሞች/ ናቸው። እነዚህ ከወርቅ፣ከብር፣ ከነሐስና ከሌሎች ነገሮች የሚቀረፁት ገንዘቦች ተደራጅቶና ተጠብቆ ላልቆየው ወይም ተሟልቶ ላልተገኘው ለአክሱም ታሪክ እንደ አንድ ክፍተት ሞይ የመረጃ ምንጭ ሆነው አገልግለዋል።

በተለያዩ ጊዜያቶች በተለያዩ የኢትዮጵያ /የአክሱም/ ነገስታት የተቀረፁ ገንዘቦች ላይም በላያቸው ላይ የሠፈረው ፅሁፍ ያስቀረጿቸውን የነገስታት ስም፣ የሐይማኖታቸውን ሁኔታ፣ ዓላማቸውንና ሌሎች ተያያዥ ነገሮችን የመግለፅ አዝማሚያ አላቸው።

ጠቅለል ባለ መልኩ የገንዘቦችን ሁኔታ ስናይ ለምሳሌ ክርስትና ከመግባቱ በፊት በአክሱም የነገሰ አንድ ንጉስ ባስቀረፀው ገንዘብ በአንደኛው በኩል ዘውዱን ጭኖ በጆሮው ላይ ሎቲ እንዳንጠለጠለ ካባ ለብሶ ቀኝ እጁን ከካባው አውጥቶ ሠይፍ ይዞ በሁለት የስንዴ እሸት ዘለላ ተከቦ ይታያል። ዙሪያውን በግሪክ ፊደልና ቋንቋ የተፃፉ ፅሑፎች ሲኖሩ፤ በፅሁፎቹ መካከል ደግሞ ከላዩ ላይ ነጥብ ያለበት የሩብ ጨረቃ ምስል ይታያል። ይህም አረማዊነቱን ሲያሳይ፤ በሌላኛው የሳንቲሙ ገፅም የራሱ ምስል እንዳለ ሆኖ በዘውዱ ፋንታ የራስ ቁር ደፍቶ፣ በእጁ ደግሞ ሶስት የዘንባባ ዝንጣፊ ጨብጦ ይታያል። ይህም በአንድ በኩል ሠይፍ ይዞ መታየቱና በሌላኛው በኩል የዘንባባ ዝንጣፊ ይዞ መታየቱ ሊወረው የመጣውን በሠይፉ እንደሚቀጣው፤ ሰላም ፈላጊውን በሠላም እንደሚቀበለው ለመግለፅ እንደፈለገ መገመት ይቻላል።

ሌላው የንጉስ አንዲበስ ገንዘብም ከላይ ያየነውን አይነት ነገሮች የተካተቱበትና ከወርቅና ከብር የተቀረፀ ሲሆን በዘውድ ፋንታ ጥሩር የደፋ ወይም ሻሽ ያሰረ መስሎ ይታያል። በግሪክ ፅሁፍም "የአክሱም ንጉስ ከዳቂ ወገን የሆነ" የሚል ትርጓሜ ያለው ፅሁፍ አስፍሯል።

በተመሳሳይም ሠፊውን ታሪኩን ወደ ፊት የምናይለት የዒዛና /የአብርሃ/ ገንዘብ በግሪክ ፅሁፍ በተከበበው ሣንቲም መካከል እላዩ ላይ ነጥብ ያለበት የሩብ ጨረቃ ምስል እንዲኖረው አድርጎ ያስቀረፀውና ክርስትናን ከተቀበለ በኋላ ደግሞ በጨረቃ ፋንታ መስቀል እንዲኖረው አድርጎ ያስቀረፀው ነው። የፅሁፉ ትርጉምም "ኢዛና የአክሱሞች ንጉስ ከሀሴን ወገን የሆን" የሚል ነው።

እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉ በርካታ ገንዘቦች በግሪክ ፅሁፍ የተፃፈባቸውና የነገስታቱን ሐይማኖት የሚገልፁ መሆናቸው ለምርምር መነሻነት አገልግለዋል። በተመሳሳይም ከግሪክ ፅሁፍ ወጥተው ግዕዝኛ ፅሁፍ የሠፈረባቸው ገንዘቦች በአክሱም ተገኝተዋል፡

ከእነዚህ ውስጥም ንጉስ ኢዩኤል /ለትም/ ያስቀረፀው ገንዘብ የሚገኝ ሲሆን በሁለቱም በኩል የመስቀል ምልክት አድርጎ ባልሁለበነው ጥንታዊ የግዕዝ ፊደል 'ገሀ አየአለ' የሚል ፅሁፍ ሲኖር፤ ትርጓሜው 'ንጉስ ኢዩኤል' የሚል ነው፡፡

በሌላኛው ገንዘብም በአንድ በኩል "ክረስተመሰለነ ነገሥ አየአለ" የሁለቱ ትርጓሜ በአንድ ሲነበብም "ንጉስ ኢዩኤል ክርስቶስ ምስሌ" የሚል ሲሆን፤ ይህ ንጉስ በ700ኛውና በ800ኛው ዓ.ም መካከል የነገሰ ክርስቲያን ንጉስ ነበር፡፡

ሌላው ደግሞ የንጉስ ዋዜና /ታዜና/ ገንዘብ ነው፡፡ በዚህ ገንዘብ በዘውድ ፋንታ ጥሩር ያደረገ ወይም ሻሽ ያሰረ የሚመስል፤ በምስሉ ዙሪያ በአንድ በኩል "ለአሐዘበየ የደለ" የሚል ሲሆን ትርጉሙ "ለአህዛብ ይደሉ" በሁለተኛው ፊት በሁለት በሁለት ፊደል መካከል ጣልቃ የመስቀል ምልክት እያደረጉ +ዘወ+ዘነ+ዘነ+ገሰ ይላል:: ዘዋዜና ዘንጉስ ማለት ነው፡፡

ሚስተር ዋላስ ባጅ 'ዘየደለአሀዘበ' የሚለውን 'ዝይደሉ ለአህዛብ' ብለው በተገቢው መንገድ ተርጉመውታል፡፡ ግዕዙን በቀጥታ ለማይተረጉመው የውጭ አገር ፀሃፊም ማስቸገሩ አይቀርምና ወደ እንግሊዝኛ ሲተረጉሙ "May this be useful to the peoples" "ይህ ለህዝብ ጠቃሚ ይሁን" በሚል ተርጉመውታል፡፡ ሌላኛው ደግሞ የንጉስ አርማህ ገንዘብ ነው፡፡ በዚህ ገንዘብ ንጉሱ ዘውዱን ደፍቶ ዙፋኑ ላይ ተቀምጦ ይታያል፡፡ ዙፋኑ ዙሪያውን በድቡልቡል ነገር አጊጦ ይታያል፡፡ ንጉሱም በአንገቱ ዙሪያ ድቡልቡል ጌጥ አስሮ ይታያል፡፡ ጫፉ ላይ መስቀል ያለበትን በትረ መንግስቱን በቀኝ እጁ ጨብጧል፡፡ በምስሉ ዙሪያ ከላይ ነገሥአ ከታች ረመሐ የሚል "ንጉስ አርማህ" ብለን ልናነበው የምንችለው ፅሁፍ ሀፍሯል፡፡ በሌላኛው በኩል ደግሞ መሐሉ ላይ መስቀል ተስሎ በሁለት የስንዴ እሸት ወይም በጉበስ ተከቦ በዙሪያው 'ፌስሐለየከነ ለአሀዘበ' የሚል ፅሁፍ ያለው ሲሆን፤ ትርጉሙም 'ፍስሀ ለይኩን ለአህዛብ' የሚል ለህዝቦች ደስታ ይሆን ዘንድ የሚመኝ ጭብጥ ያለው ቃላት ሀፍሮበት ይገኛል፡፡ እንዲህና እንዲያ እያለ የአክሱም ነገስታቶች ያስቀረፁት ገንዘብ የያኔውን ታሪክ እንደ አቅሙ እየዘከረ ይገኛል፡፡ በርካታ ጥንታዊ የአክሱም ገንዘቦችም በፈረንሳይና በሌሎች የአውሮፓ አገራት ቤተመፃህፍትና በየቤተመዘክሩ ውስጥ ከተለያዩ ታላላቅና ጥንታዊ ኒሻኖች ጋር ተደባልቆ እንደሚገኝና እንደሚጎበኝ ያዩት ሁሉ ምስክርነታቸውን ይሰጣሉ፡፡



## ምዕራፍ ፳፱

## የንጉስ ዔዛናና ሲዛና /የአብርሃ ወአፅበሃ/ ዘመነ መንግስት

## ከ298-324 ዓ.ም

የኢትዮጵያ መናገሻ ከተማ አክሱም ከሆነች በኋላ ከአክሱም ነገስታት ውስጥ እጅግ ስመጥርና ገናና የሆኑት ነገስታት ዔዛናና ሲዛና ወይም ክርስትናን ከተቀበሉ በኋላ ስማቸው አብርሃና አፅባሀ የተባሉት ናቸው፡፡ ክርስትና የገባውም በእነዚህ ወንድማማቾች ነገስታት መሆኑን አይተናል፡፡

ይሁን እንጂ እነዚህ ወንድማማቾች በአንድ ላይ ሆነው በአክሱም ነግሰው የነበረ ቢሆንም፤ በብዛት ግን በዘመናቸው የተፈፀሙት ታሪካዊ ክንውኖች በዔዛና /በአብርሃ/ ስም ብቻ ነው የሚታወቁት፡፡ ስለዚህም ከዔዛና ጋር አብሮ ወንድሙ ሲዛና እንዳለ እያሰብን ታሪኩን መቀጠል እንችላለን፡፡ ከታሪኩ ጋርም ንጉስ ዔዛና በዘመነ መንግስቱ ያስቀረፃቸውን ሐውልቶችና በላያቸው ላይ የተፃፈባቸውን ፅሁፎች እንደወረደ እንመለከታለን፡፡

ስለ አፄ ኢዛና የሚያትቱ የታሪክ ሠነዶች ከታሪክ ነገስቱ በላይ የውጭ አገርና የአገር ውስጥ የታሪክ ተመራማሪዎች ከሐውልቱ ላይ ፅሁፍን እየገለበጡ ባጠኑት የጥናት ውጤቶቻቸው በፖለቲካ፣ በጦር ሃይል አደረጃጀት፣ በሐይማኖት፣ በድል አድራጊነቱና በአጠቃላይ ታሪኩ እጅግ ገናና የሆነ ንጉስ እንደነበር መስክረውለታል፡፡

ሔንሪ ሳልት የተባለው የእንግሊዝ ሊቅ በ1809 ዓ.ም ከአክሱም እና ከዩሃ ሐውልቶች ላይ ያገኘውን ፅሁፍ ገልብጦ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲያሳትምና ለሌሎች መነሻ ከሆነ በኋላ፤ /ማለትም ከኮስማስ በኋላ/ ሌሎች ተመራማሪዎች በአክሱምና በአካባቢው ልዩ ትኩረት አደረጉ፡፡ ·

ብዙዎችም የራሳቸውን የጥናት ውጤት ይፋ ማድረግ ጀመሩ፡፡ በመጨረሻ ግን ጀርመናዊው ኢኖ ሊትማን /በኋላ ላይ ፐ/ር/ ከተባባሪዎቹ ጋር በመሆን እ.ኤ.አ በ1906 ዓ.ም ከእርሱ በፊት ከነበሩት የበለጠ በፎቶግራፍ ሃውልቱንና ፅሁፉን እያነሳ ለረጅም ጊዜ መርምሮ ስለአክሱምና በዙሪያው ስላሉት ሃውልቶችና ፅሁፎች፤ እንዲሁም ስለመዝሀያ ገንዘቦቻቸውና ስለሌሎች ተያያዥ ነገሮች የሚያትት መፅሃፍ በጀርመንኛ ፃፈ፡፡ የመፅሃፉ ስም በጀርመንኛ "Deustsche Axum Expedition" ይባላል፡፡ እናም ይህን መፅሃፍ እ.ኤ.አ በ1913 ዓ.ም አሳተመ፡፡ ከዚህ መፅሃፍ በኋላ በርካታ ፀሃፊዎች ስለአክሱም ለመረዳትና ለመፃፍ ቻሉ፡፡ በዚህ በአምስት ቮሊዩም በተከፈለውና፤ 5ኛው ቮሊዩም ምስሎችን ባቀፈው መፅሃፍ መነሻነትም እነ ኮንቲ ሮሲኒ፣ ኢልቤር ካሜረር፣ ዋላስ ባጅና ሌሎች በርካታ የታሪክ ፀሃፊት ብዙ ፅሁፎችን

ስለአክሱም እየገፉ ለዓለም ይፋ አድርገዋል። በዚህ መፅሃፍ ውስጥም የስመጥሩ ንጉሳችን የኢዛና /የአብርሃ/ የሃውልት ፅሁፍ በግሪክኛና በቀድሞው የግዕዝ ፊደል የተፃፈው ይገኛል። በእነዚህ ሃውልቶች ላይም የሰፈሩት ፅሁፎች የሚገልፁት ዘምቶ ድል ማድረጉን፣ ያስገበራቸው ግዛቶች የትኞቹ እንደሆኑ፣ ከድሉ በኋላ ለአማልክቱ መስዋቱን፣ "የማይሸነፈው መህርም" ለሚለው ለቀድሞው አምላኩ መስዋዕት አቅርቦ ሃውልትና ወንበር ማስቀረፁን ይገልፃል። በግዕዝና በሳባ ቋንቋ "አስታር፣ ምድር፣ መህርም" የሚላቸውንም በግሪክኛ ቋንቋ ሲያስቀርፅ አሬስን /የመሬት አምላክን/፣ ፓሲዶንን /የባህርና የቀለያትን/ ፣ዜውስን /የሰማይን አምላክ ወይም የአማልክትን አባት ያነሳል/።

ስለዚህም የኢትዮጵያ መናገሻ ከተማ ናፓታና መርዌ በነበሩ ዘመን የአክሱምና የአካባቢው ነዋሪዎችና ሹማምንት በአንድ ኢትዮጵያ ስር የነበሩ መሆናቸው እንዳለ ሆኖ፤ ነገር ግን አክሱሞች ለዋናው ጠቅላይ ንጉሰነገስት ወይም ለማዕከላዊው መንግስት የሚጠበቅባቸውን ግብር በሠላም ያስገቡ የነበረ የመሆኑን ያህል፤ አሁን ደግሞ አክሱማውያን በገንኑበት በዒዛና ዘመን እነዚያኑ አገሮች በሩንታው ማስገበሩን በሃውልቱ ፅሁፍ አስፍሮት ይገኛል።

ታሪክነገስቱ አብርሃ፣ እራሱ ያስቀረፀው ሐውልት ደግሞ ዒዛና የሚለውን ይህ ታላቅ የአክሱም ንጉሰነገስት ከኢትዮጵያ ምዕራብ ሠሜን እስከ ግብፅ የሚገኙትን የበጀያ ህዝቦች ሸፍተውበት ስለነበር፤ ታሪክ ነገስቱ ሲዛና፤ የሃውልቱ ፅሁፍ አፅባሃ የሚለውን ወንድሙንና ሁለተኛውን ወንድሙን ሐዴፋን ልኮ እንዳስወጋቸው የሚገልፀውን የሐውልት ፅሁፍ ከቀድሞው ከሳባ ፅሁፍ ወደ ግዕዝ ተገልብጦ የተፃፈውንና በዛሬው ፊደል ተለቅሞ፤ ነገር ግን የቀድሞውን ግዕዝኛ አነጋገር የያዘውን የሐውልት ፅሁፍ እንደወረደ እንመልከተው፤



[illegible] ፡ ለብሔ[illegible] ፡ ([illegible]) ፡ ወር[illegible] ።

[illegible]
[illegible]
[illegible]
[illegible]
[illegible]
[illegible]
ዘ | ዐድበቱ | ንገሥት | ፶፻፶
፻፶፯ | ወበጊዜ | ፳፰፻፴፱ | ወእንስሳ | ዐውድ |
እንዘ | ይሴብሕዎሙ | እምአሚረ | አውዐእዎሙ | እብሔርሙ |
ለሰብእቶሙ | ኅብስተ | ዐለበ | ፳፻፳፪ | ወምንጋ |
ዘየኃብሮሙ | እንዘ | ያዕትይዎሙ | ምዋ | ወሠፈን | ሕገ[illegible] |
አርባዕተ | አውፈገ | ወበጺሖሙ | አክሱምሃ |
መንገሌን | አፈበስሆሙ | በስፍሖ | ብብእሙ | ወአበርገው |
ናሆሙ | ለንገሥት | ዕንዊ | ወፈየን | ወእደ | ይከብር | ብሔር
በሙ | ያወስ ብሮሬን | ወኤሎን | ይሴብድዎሙ | ለህየ | ወፈተ
ትናሆሙ | ለለንጉሥ | ለህሙ | ፶፻፶ | . . . . . ያከሙን |
ለዐድበቱ ንገሥት | ፪፻፶፻፶፱ | ለህም | ወአቤ
ን | ለመሕርም | ዘወለደኒ | ዘንተ | ምስለ | ዘወርቅ | ለ
ወዘብሩር | አሐደ | ወዘአሬዊ | ወለበተ | ጸሐፍኩ | ዘተ |
ጽሕፈተ | ወሢምኩ | ወወ . . . . . ለዐስተር | ወ
ለብሔር | ወለመሕርም | ዘወለደኒ | ወለእመቦ | ዘእ
ማስኖ | ለዘአብአኒ | ወነቀሎ | ወነሰቶ | ለይሠውቅ |

ይህን ከላይ ያየነውን የሃውልት ላይ ፅሁፍ የጎደለውን እየሞሉ በደንብ አብራርተው የገፉትንና በየመፅሃፎቻቸው ያካተቱትን ፀሃፍት ማለትም ፕ/ር ኢኖ ሊትማን፣ ኤልቤር ካሜሬርንና ኮንቲ ሮሲኒን ጠቅሰው በእነርሱ መነሻነት ፅሁፉን ወደ አማርኛ የተረጎሙት ደግሞ አቶ ተክለፃዲቅ መኩሪያ ሲሆኑ፤ በአማርኛ እንዲህ የሚል ትርጓሜ እንዳለው ገልፀዋል።

"ዒዛና የአክሱም፣ የሂሚያር፣ የካሱ /የኩሽ/ የሳባ፣ የሃበሳት፣ የራይዳን፣ የሳልሄን፣ የፂያሞ፣ የበጋ /በጀያ/ ንጉሥ፣ ንጉሰነገስት፤ በጠላት የማይሸነፈው የመህርም ልጅ። የበጋ /በጀያ/ ህዝብ በሸፈቱ ጊዜ እንዲዋጉዋቸው ወንድሞቻችንን ሳይዛናን፣ ሐዴፋን ላክናቸው። እነርሱም ወደ በጀያ አገር በደረሱ ጊዜ 6 ነገስታት ከነነገዶቻቸው ተገዝተው

ገቡላቸው። ከዚህ በኋላ 6ቱን ነገስታት ከነልጆቻቸው፣ ከነሚስቶቻቸው፣ ከነከብታቸው፣ ከነነዳቸው ማረኳቸው። የሰዎቻቸው ቁጥር 4 ሺ 4 መቶ፣ ከብት 3112፣ በግና ፍየል 6224 ከጭነት ከብት ጋር።

አገራቸውን ከለቀቁበት ጊዜ ጀምሮ በየቀኑ እስኪጠግቡ ድረስ ዳቦም፣ ጠላም፣ ከስጋ ጋር እየተመገቡ አራት ወር ተጉዘው እኛ ዘንድ አክሱም ደረሱ። እኛም ዘንድ ከደረሱ በኋላ ህዝቡን አልብሰን፣ ነገስታቶቻቸውንም ሽልማት ሸልመን በክብር አድርገን "ደወስ ባይራን" በሚባል አገር እንዲቀመጡ አደረግናቸው።

ለእያንዳንዱ ንጉስም 4.190 በሬ /ለንጋ/ በድምሩ ለ6ቱ ነገስታት 25.140 ሥንጋ እንዲሠጣቸው አደረግን። ይህንንም 1 የወርቅ፣ 1 የብር፣ 1 የነሃስ ፣ 3 ሃውልት ለወሰደን ለመህርም መታሰቢያ አድርገን ሠጥተናል።

ይህን መታሰቢያ ሐውልት ያበላሸ ወይም የጣለ እርሱ ይሙት። ዘሩና ልጆቹም ከአገር ይጥፉ። ያከበረው ግን የተባረከ ይሁን። በደንብ /በክብር/ እንዳስቀመጥነው የኛን ዝና ይዞ በከተማችን እስከ ዘለዓለም ይኑር። ለመህርም 1 የቅጥር ቦታና፣ 1 ሰፊ ሸንጎ ሠጥተናል።" ይላል።

በዚህ መልኩ በጥንቱ ባልሠለጠነው የግዕዝ ፊደልና በግሪክ ቋንቋ በርካታ ሃውልቶችን አስቀርጿል። እዚህ ላይ ደግነቱን የገለፀውን ያህልም በቀጣዩ ዕሁፍ ጭካኔውን ሲገልፅ እናያለን።

በተጨማሪ ደግሞ የአገዛት /አጓዛት/ ህዝብ በሸፈቱበት ጊዜ በሌላ ሐውልት ላይ የአገዛትን ህዝብ እንዴት ድል እንዳደረገ የሚገልፅ ፅሁፍ አፅፏል። አገዛት የሚላቸውም አካለ ጉዛዮችን ነው። አገዛት የሚባሉት በአትባራ እና በተከዜ መካከል የሚኖሩ ናቸው።

"ቀጥለን ከሃውልቱ ፅሁፍ ላይ እንደምንረዳው በጉዞው /በዘመቻው/ ጊዜ ስንቅ የተጫነው በግመል እንደሆነ ፅሁፉ ስለሚገልፅ በርሃማ አካባቢ እንደሆነ ያስረዳል። ይህን ፅሁፍ በቀጥታ የአማርኛውን ትርጉም እንይና ከዚያ በኋላ ያሉትን ግን የሃውልቱን ፅሁፍ እንደወረደ የምናይበት እድል ይኖረናል።

"ዒዛና የእለዓሜዳ ልጅ፣ ከሄለን ወገን፤ የአክሱም፣ የህሜር፣ የራይዳን፣ የሳባ፣ የሳልሄን፣ የጺያሞ፣ የቤጋ፣ የካሱ፣ ንጉስ ንጉሰነገስት በጠላት የማይሸነፈው የመህርም ልጅ፤ አጎዛት አንጋቦ ድረስ መጥተው ስለነበር ንጉሳቸውንም አባአልቁዋን ከነህዝቡ አገኘነው። እርሱም መታያ አቀረበልን። አልያ እሚባለው አገር አታጋው ወሰን ስንደርስ ሠፈር ሆኖ ለሃያ ቀን የሚበቃንን ስንቅ ለማደራጀት ግመሎቻችን፣ የቀንድ /የእርድ/ ከብቶቻችን፣ ወንዶቹም ሴቶቹም እረፍት አደረግን። በ3ኛው ቀን



የንጉሳቸውን ከዳት ባወቅን ጊዜ ከንጉሳቸው ከአባአልቁዎን ጋር የመጡትን አጓዛትን ዘረፍናቸው። የተማረኩትንም እንደ ባሪያ በብረት አሰርናቸው።

ንጉሱንም ከዙፋኑ ተሸካሚው ጋር ራቁቱን አድርገን አሰርነው። ከዚህ በኋላ የመሐዛና የጦር አለቆቹ ሠራዊት ሌትና ቀን ወደፊት እንዲገሰግሱ አዘዝን። አለቆቹም ሠርዌ መሐዛና፣ ሠርዌ መቲን የሚባሉትን ላኩና አጎዛትን እንዲወጉ አዘዟቸው። ከዚያ በጉባኤ ስፍራ ተገናኝተው ወደ አዘላ ከዚያም ወደ ኤረግ ደረሱና ያገኙትን ሁሉ ማረኩ።

በአዛልና በናዱ ወንዝ ደርሰው ያገኙትን ገደሉ። ቀጥሎ ወደ አጋዳ ወሠን ደርሰው ብዙ ገድለው የቀረውን ሠው ከነከብቱ ማረኩ። የዳቁንን ሠራዊት ወደ ሲዞት ወደ ምስራቅ እንዲጓዙ አዘዟቸው።

ሶስቱ ሠራዊት ዳቁን፣ ሐራ፣ መቲን፣ እንዲያቦ ላይ ተገናኙ። ከዚያ የሐራ ክፍል ወደ ዛዋት እንዲሔድ ታዘዘ። ከዚያ 3ኛ ጊዜ የዳቀንን ክፍል ወደ ሐዘቦ እንዲሄድ አዘዙት። ጦሩም በቱተሆ በኩል በወንዙ አድርጎ ላዋ ደርሶ ወደ አገዞ ወረደ። ከዚያም ከሐዘባ ጋር በአንድነት ሆነው ሠፈር አደረጉና አደሩ። ከዚያ ጎህ ሲቀድ አገዛትን እየወጉ መካሮ አለቡት ድረስ አባረሩዋቸው። ሶስቱም ጦር ከፍልሃና ከሠራ /ደራ/ ጋር በወንዝ በኩል ሔደ።" ይላል።

ቀጥለን ደግሞ ንጉስ ኢዛና የስዕኔና የዐወንተ ህዝቦችን ማስገበሩን የገለፀበትን የሃውልት ላይ ፅሁፍ ነው የምንመለከተው። የስዕኔና የዐወንተ ህዝብ ደግሞ ከአክሱም በሠሜን በኩል በሚገኘው አካባቢ የሚኖሩ ናቸው። ይህም የተጻፈው በግዕዝ ነው።

፩ [ኄ] ዘና| ወልደ| (እለ) ፩ በሚዳ| [illegible]|
፪ [ሐ] ሉን| ንጉሠ| አክሱም| ወዘ| ሕምየር፡
፫ [ወ] ዘ| ረይዳን| ወዘ| ሰበእ ወዘ| ሰል
፬ ሔን| ወጸ| ጽያም| ወዘ| ብጋ| ወዘ| ካሱ|
፭ [ወ| ልደ| መሕርም| ዘኢይትመዋእ ለ
፮ [ፀ] ር| ፀብአ| ጸረ| ወንግሥቶሙ እ
፯ [ፋ] ን ሶቤ ገፍዐ(ነ)| ወቀተ(ሉ) ፫ | ነገዳ
፰ [ተ] [ወእምዝ| ሰበእናሁ ወእምቀ [ሚ] ፬ [፩]
፱ ፈነውነ| ሠራዊተ| ሰርዌ| ምሕዘ መ
፲ ሰርዌ ዳኪን| ወሰርዌ ሐለ| ሀበበ.
፲፩ ን| ቀለውነ| ወኀደርነ| ምግባእ| መ
፲፪ ራድ| ዓላ| ወአውረርነ| ሠራዊተ
፲፫ ነ| ወቀተልዎ| ወጼወውዎ| ወመሀረ
፲፬ ክዎ| ወቀተልነ| ሰዐነ| ወጸወንቱ|
፲፭ ወጌም| ወዘሕተነ| አርበዐተ| እን
፲፮ ጋደ| ወአንገዝኦ አሊታሃ| ምስሌሆ ነ
፲፯ ልአ| ደቂ| ወኮነ| ቅትለ| ዕድ| ዘዕ ፋ|
፲፰ ን| ፳፻፹ ወአንስት| ፪፻ ወኮነ| [illegible]|
፲፱ ኄዋ| ዕደ| ወአንስት| [illegible] [illegible]| ዐ
፳ ደ| [illegible]| ወአንስት| ወደቂቅ| [illegible] መ
፳፩ ኮነ| [illegible]| ምህርካ| ለሀም| [illegible]
፳፪ [illegible] እንስሳ| በሙደ| [illegible] ወተ
፳፫ መይጠ| ዳንሃ| ምስለ| እሕዛቢሆሙ|
፳፬ ወተከለ| መንበረ| በዝየ| ዘመ[illegible]| ወ
፳፭ አመ(ሐ) ፱ | ዐንም| ለዐስተር| ወለብሔ
፳፮ ረ| ወለምድር| ለእመ| ቦዘ| ነሠቶ| ወ
፳፯ ንቀሎ| ውእቱ| ወብሔሩ| ወዘመዱ| ለ
፳፰ ይትንቀል| ወይትነሠት| እምብሔሩ|
፳፱ ለይሚእ| ወቀላ| እኩየ| ለሙሕ
፴ ረም| ዘወለደኒ| ለሀም| [illegible] ወጼዋ| [illegible]



ይህ ያየነው ሃውልትም ተመሳሳይ ሃተታ የሰፈረበትና የድሉን ውጤት የሚያበስርበት የስዕኔና የፀወንቱ ህዝቦችን እንዴት እንዳስገበራቸው በተመሳሳይ ሐተታ የገለፀበት ነው። ፅሁፉ የተፃፈው በሠለጠነው የግዕዝ ፊደልና ቋንቋ ሲሆን፣ ለግንዛቤ ያህል ደግሞ ይህንኑ ታሪክ በቀድሞው ባልሠለጠነው ግዕዝ በሐውልቱ ላይ እንዴት እንደፃፈውና የቀድሞው ፊደል ምን እንደሚመስል ለአንባቢያን ለማወቅ ስለሚረዳ መካተት አለበትና ይህን ይመስላል።



የንጉስ ዔዛና የመጨረሻውና ትልቁ ሃውልቱን ቀጥለን ስናይ ደግሞ በዚሁ ሃውልት ላይ ከሠፈረው ፅሁፍ ጋር 1ኛ ራሱ ዘምቶ ኑብያን ማስገበሩን፣ 2ኛ የሀይማኖት ለውጥ ማድረጉን፣ 3ኛ የፊደል ማሻሻልን ተግባር በዘመኑ መፈፀሙን አብረን የምንረዳው ይሆናል።

ንጉስ ኢዛና ከዚህ በፊት ባየናቸው ፅሁፎች ወንድሞቹንና የጦር አለቆቹን እየላከ ሲያስገብር እንጂ ራሱ ዘምቶ እንዳስገበረ አልገለፀም። እነዚያ ወደ ደቡብ እና ወደ ኢትዮጵያ ሠሜን ምዕራብ ወደ በጃ የተደረጉት ሥኬታማ ዘመቻዎች ሁሉ በመልዕክት የተደረጉ ናቸው።

አሁን ደግሞ ንጉስ ዔዛና ራሱ የቀድሞውን የናፓታ ቀጥሎ የመርዌ መንግስት ይባል የነበረውንና በተለያዩ የግብፅ ወራሪዎች በሆኑ ሃያላን ከግብፅ ጋር አብሮ እየተገዛ የቆየውን የቀድሞ ኢትዮጵያ ግዛትና መናገሻ የነበረውን አገር አሁን የአክሱም መንግስት በገነነበት ሠዓት እንዳስገበረ ሊገልፅን ነው።

ይህ ሐውልት የዔዛናን ድል አድራጊነትና ግዛት ማስፋፋት መቻሉን ከመግለፁ ባሻገርም፤ ለአገርና ለህዝብ አስፈላጊ የሆኑ ተጨማሪ ነገሮችን ማሻሻሉን ያመላክታል። በመጀመሪያ የእርሱ ነገድ የሆኑትን የአባቶቹን የሳባውያንን ከደቡብ ዓረብ ይዘው የመጡትን ፊደላቸውንና ከእርሱ በኋላ የተተካውን የግዕዝ ፊደል አናጋሪ ሳይኖረው ሀ ለ ሐ መ … እየተባለ ሲሰራበት የቆየውን ከዚህ በፊት እንዳየነው "አዘን ነገሠ አክሰመ" ይል የነበረውን "ዔዛና ንጉሰ አክሱም" ተብሎ እንዲነበብ በማድረግ ሁ፣ ሂ፣ ሃ፣ ….. ሉ ሊ ላ …… የሚሉትን ተጨማሪ የሆሄያት ዝርዝሮችን እንዲካተቱ ያደረገው ንጉስ ዔዛና እንደሆን የሚያስረዳ ሃውልት ይሄው ቀጥለን የምናየው ሃውልት መሆኑ ነው።

ለመጀመሪያ ጊዜም እነዚህ ነቁጣዎች የተካተቱበት ፊደል በዔዛና ዘመን ስለሆነና ከዚህ በፊት ታይተው ስለማይታወቁ መሻሻል ያደረገው እርሱ ራሱ እንደሆን ማረጋገጥ ቀላል ነው። ይህ ማለት ግን ሃሳቡን ያፈለቀው ራሱ ዔዛና ነበር ለማለት አያስችልም። ምናልባት የዘመኑ ሊቃውንቶች ያፈለቁት ሃሳብ ሊሆን እንደሚችልና ተግባራዊ እንዲሆን ንጉሱ እንደፈቀደላቸው ልናስብም እንችላለን። ያም ሆነ ይህ ግን ይህ የፊደል መሻሻል በዔዛና ዘመነ መንግስት በ300ኛው ዓ.ም ተግባራዊ ተደርጎ ያልሰለጠነ ይባል ከነበረው የግዕዝ ፊደል የሠለጠነ ብለው

የሠየሙት የግዕዝ ፊደል አገልግሎት ላይ ውሏል። በኋለኛው ዘመን ደግሞ ይሄው ዛሬ ለምንጠቀምበት ፊደልና ቋንቋ ለአማርኛሙሉ ግልጋሎት እየሠጠ ይገኛል። ይህም ዔዛና ከፈፀማቸው ድንቅ ተግባራት በዋነኝነት የሚጠቀስ መሆኑ የበርካታ ሊቃውንት ስምምነት ነው።



ሌላው ከዚህ ሃውልት ጋር የተያያዘው ደግሞ በቀድሞዎቹ የሐውልት ላይ ፅሁፎች እንዳየነው በፅሁፉ መግቢያ ላይ "ዔዛና ወልደ እለዓሜዳ ብእስየ ሄለን ንጉሰ አክሱም ….ወልደ መህርም ዘኢትመዋዕ ለፀር ….." እያለ መህርም /በግሪክኛ አሬስ/ እያለ የሚጠራውን አምላኩን በዚህ ቀጥለን በምናየው ሃውልት ላይ ግን በፅሁፉ መግቢያ ላይ "በሃይለ እግዚአ ሠማይ ወምድር መዋዒ ለዘኩነ ዔዛና ወልደ እለዓሜዳ" በማለት መቀጠሉ የሃይማኖት ለውጥ ማድረጉን ይነግረናል።

በአጠቃላይ ንጉስ ዔዛና የፊደልና የፅሁፍ መሻሻል፣ የግዛት ማስፋፋት፣ ከክርስትና በኋላም ከሃያላን ክርስቲያናዊ መንግስታት ጋር ወሳኝ የሆነ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ከሌሎች በተሻለ ሁኔታ መመስረቱና፤ ወደፊት እንደምናገኘው ለጭቁን ክርስቲያኖች ነፃነት በመቆሙ፣ ወደተጨቆኑበት አገር እየዘመተ ነፃ በማውጣት፣ እንዲሁም ተስፋቸው ሊሆን በመቻሉና በዘርፈ ብዙ ነገሮቹ ራሱ ገናና ንጉስ ሆኖ አክሱምም የበለጠች ገናና እንድትሆን አድርጓታል።

በዚህ ሃውልት ላይ የተፃፈው ፅሁፍ ጭብጡ የኖባ /የኑብያ/ ህዝብ ከተከዜ ወዲያ ያሉት በዚያ ዘመን ኖባ፣ ሰባ፣ ባሪያ፣ መንጉርቶን፣ ሃሳን….. እየተባሉ የሚጠሩት ህዝቦች አንገዛም ብለው ስለሸፈቱበት እነዚህን ህዝቦች ራሱ ዘምቶ ተከታትሎ እንደወጋቸው፤ ሠራዊቱን እየላከ በሃይል አሸንፎ ማስገበሩን፤ ድል ባደረገበት በተከዜና በግዶው ድንበር መካከል ባለው ቦታ አንድ ከድንጋይ የተሰራ ዙፋን ለአምላኩ ለእግዚአብሔር መታሰቢያ ይሆን ዘንድ ማሰራቱን ነው የሚገልፀው።

በተጨማሪም የማረካቸው የወንዶችና የሴቶች እንዲሁም የከብቶች ብዛት ይገኛል። በመጨረሻም ያንን ለእግዚአብሄር መታሰቢያ ብሎ ያሰራውን ዙፋን ያፈረሰ ሠው የተረገመ ይሁን ብሎ ይደመድማል። በጊዜ ብዛት አርጅተው የማይነበቡ ፊደሎችንም ሊኖ ሊትማን በክብ ቅንፍ ውስጥ የጎደሉትን አንዳንድ ፊደላት ለማሟላት ችለዋል።

ከዚህም በላይ የተሸራረፉና ሙሉ ታሪካቸው በግልፅ የማይነበቡ የኢትዮጵያ ጎረቤት የሆኑ የአረብ አገራት ውስጥ ስለ ንጉስ ዔዛና የሚገልፁ ሃውልቶች መገኘታቸው ታውቋል።

እነዚህ ሁሉ ያየናቸው ዔዛና በዘመኑ ባስቀረፃቸውና ባሣሬባቸው የሃውልት ላይ ፅሁፎች ውስጥ የተጠቀሱት አገሮች ከፊሎቹ በኢትዮጵያ በአክሱምና በአካባቢው፣ የቀሩት ከኤርትራ ባህር ማዶ በዓረብ አገር ውስጥ የሚገኙ ናቸው። እንዳንዶቹን ቀደም ሲል በየት አቅጣጫ እንደሚገኙ አይተናል። ከቀሩት ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ደግሞ ለምሳሌ ፅያሞ የሚለው ከአክሱም በደቡብ ምስራቅ በኩል የሚኖሩ የነበሩ የልዩ ልዩ ነገዶች መጠሪያ ነው።

በጋ /በጃ/ በኢትዮጵያ ሁሜን ምዕራብ እስከ ግብፅ ድንበር ድረስ የሚገኙ በርካታና በወረራ የሚፈሩ ህዝቦች የነበሩ ናቸው። ካሱ/ኩሽ/ ከበጃ በስተደቡብ ከአትባራ ወዲህና ወዲያ ባለው ቦታ ሰፍረው የሚኖሩ የቀድሞው የናፓታና የመርዌ መንግስት ስር የነበሩት ህዝቦች ናቸው።

ህሜር /ሂሚያሪት/ ሐበሳት፣ ራይዳን፣ ሳባ፣ ስልሔን..... የሚባሉት ደግሞ በደቡብ ዓረብ ለየብቻ ተከፋፍለው የሚኖሩ የነበሩና ዔዛና በዘመኑ የጠቀለላቸው አንድ አይነት ዘር ያላቸው ህዝቦች ናቸው።

በመጨረሻው ሃውልት ላይ ኖባ የሚለውም ኑቢያን መሆኑ ይታወቃል። እንግዲህ የዓረብ አገርን ለመጀመሪያ ጊዜ ያስገበረው በአዶሊስ ሐውልት ላይ ታሪኩን ያየነለትን "አክሱምን እንደቀረቀረ ይነገራል።" ያልነው ንጉስ ቢሆንም፤ ከእርሱ በኋላ ደግሞ በድጋሚ ብዙ አገሮች እየሸፈቱ ነፃነታቸውን ለጥቂት ጊዜ ይዘው ቢቆዩም፤ በዔዛናና በሲዛና ዘመነ መንግስት ደግሞ በድጋሚ ሲገብሩ ችለዋል።

ከዔዛና በኋላ ድጋሚ በዓረብ አገራት የሚኖሩ ህዝቦች የሸፈቱ ሲሆን፤ ቀጥለን ታሪኩን በምናይለት በንጉስ ካሌብ ጊዜ ድጋሚ ሲገበሩ ቴገደዋል።

ምንም እንኳ በዚያ ዘመን ግብፅ በሮም ግዛት ስር የነበረች ቢሆንም፤ የእስክንድርያ እና የቆስጠንጥንያ ቤተክርስቲያን የክርስትናቸው መሰረት አንድ ሆኖ፤ ነገር ግን ልዩነት ነበራቸው። የቆስጠንጥንያው ወልድ ፍጡር ሲል፣ የእስክንድርያው ወልድ ፍጡር የሚለውን የማይቀበል፤ ማለትም ኢየሱስ ፍፁም አምላክ ነው ሲል የእስክንድርያው፤ የቆስጠንጥንው ደግሞ የአብ ልጅ ነው በሚል ዛሬ ድረስ ባለ ልዩነት ውስጥ ነበሩ። ሆኖም የአክሱም ነገስታትና የሮም /የቆስጠንጥንያ/ መንግስታት ይህንን ልዩነት ይዘው ሁላማዊ ግንኙነታቸው እንደቀጠለ ነበር። ነገር ግን የአክሱማውያን ነገስታት ከቆስጠንጥንያው ንጉስ ከንጉስ ቁንስጣ ክርስትናን ከግብፅ እስክንድርያ በተቀበሉ ማግስት የደረሳቸው ደብዳቤ እንዲህ የሚል ነው።

"ቪክቶሪዩስ ኮንስታንስዮስ ማክሲሙስ አውግስጦስ፤ ለዔዛናና ለሲዛና /አብርሃና አፅባሐ/ እግዚአብሄር የሰጠን ትምህርትና ማስተዋል ለሁሉም እውነትንና ፅድቅን ለሚፈልግ ሁሉ እንዲዳረስ ስመኝ በእናንተና በሮማውያን

ክርስቲያን መካከል አንድነት እንዲኖር ይገባል። ከሹመቱ የተሻረው፣ ብዙ ሺ ክስ ቀርቦበት መመለስ ያቃተው የእስክንድርያው ጳጳስ አትናቴዎስ ፍሬምናጦስን ሾሞ ልኳልና በቶሎ ፍሬምናጦስን መልሳችሁ ለተከበረው ጳጳስ ለጊዎርጊስ በዚያም ሳሉት ቀሳውስት ሳኩትና የእርሱን ነገር እነርሱ ይጨርሱት። የአባ አትናቴዎስን ስራ ግን ከእናንተ በቀር አገር ሁሉ አውቆ አሳስበጋ ስላለው ... በእናንተ ዘንድ መጠጊያ ይፈልጋል። ፍሬምናጦስ ከልቡ ጳጳስ መሆን ከፈለገ የህይወቱን ታሪክ ለቀሳውስቱ ገልፆ የቤተክህነትን ህግ እና ስርዓት በደንብ ፈፃሚ መሆኑ በእነዚያ ዘንድ ከታወቀ ተመልሶ እንደ ህጉ ጳጳስ መሆን ይችላል።

እስዚያ እንደ አትናቴዎስ እንደ ለፍላፊው ከህግ የሚሸሽ ሆኖ ወደ አክሱም የመጣና ሹመቱን የያዘ እንደሆነ እናንተንም ቤተክርስቲያናችሁንም እንዳያበላሽትና ሁከት እንዳይፈጥር ያስፈራል። እኔ ግን እንደሚመስለኝ ፍሬምናጦስ ወደ እስክንድርያ ተመልሶ በጣም ከከበረው ጳጳስ ከጊዎርጊስና /በወልድ ፍጡር አማኝ የሆኑትን ጳጳስ ማለት ነው/ ከፍ ካሉት ሲቃውንት ተገናኝቶ የቤተ ክህነትን ህግ እና ትምህርት ከተረዳ በኋላ ወደ ጵጵስና ስፍራው ሊመለስ ይችላል። በጣም የተከበራችሁ ወንድሞቼ ሆይ እግዚአብሄር ይጠብቃችሁ።" ይላል። ይህም ደብዳቤ ከቁንስጣ ወደ ዔዛና የተላከው በአንድ ህንዳዊ በሆነና ቴዎፍሎስ በሚባል በወልድ ፍጡር በሚያምን ሠው አማካኝነት ነበር። ይህም በኮንቲሮሲኒ የኢትዮጵያ ታሪክ በተሠኘው መፅሃፍ በገፅ 150 ላይ እንደሚገኝና እርሱን የጠቀሱ በርካታ ፀሃፊዎች በየታሪክ መፅሃፋቸው አስፍረውታል።

ዔዛና ግን ፍሬምናጦስን አላባረረም። የተባለውንም አልፈፀመም። ከዚህ በኋላ ይመስላል ሃያላኑ ኢትዮጵያን ለማዳከም ቁርጥ ሃሳብ ያደረጉት።

በአጠቃላይ ንጉስ ዔዛና አክሱምን አግንኖ ብዙ አገሮችን አስገብሮ የራሱን ገናና ታሪክ ሠርቶ ከ26 ዓመታት የግዛት ዘመን በኋላ በ324 ዓ.ም ሲሞት መንትያ ወንድሙ ሲዛና ወይም እፅቢሐ የንጉስ ነገስትነቱን ስልጣን ለብቻው በመያዝ ኢትዮጵያን ማስተዳደሩን ቀጠለ።

ከንጉስ ዔዛና በኋላም እስከ ንጉስ እለዓሜዳ ድረስ 28 ያህል ነገስታት ተፈራርቀው በአክሱም ነግሰዋል። በእነዚህ ሁሉ ነገስታት ጊዜም አክሱም የበለጠ እየገነነች መሔዷንና ከስልጡንና ከሃያላን አገሮች ተርታ መሠለፍ መቻሏን ከመረዳት በቀር እያንዳንዱ ንጉስ በዘመኑ ምን እንደፈፀመ በዝርዝር ልክ እንደ ዔዛና የሚገልፅ ታሪክ የለም።



## ምዕራፍ ፴

## የንጉስ እለዓሜዳ ዘመነ መንግስት

## ከ471-479 ዓ.ም

ንጉስ እለዓሜዳ በዘመነ መንግስቱ ከፈፀመው ተግባር ይልቅ፣ በዘመኑ የተፈፀሙ ታሪካዊ ክንውኖች ነው ያሉት። ይህም በዘመኑ 99ኙ ቅዱሳን ወደ ኢትዮጵያ መግባታቸውና፣ ዘጠኙን ተቀብሎ በሠላም ማስተናገድ መቻሉ ሲሆን፣ በዚህ ምዕራፍ የምናየውም ይህንኑ ታሪክ ይሆናል።

በንጉስ እለዓሜዳ ዘመነ መንግስትም አክሱም የበለጠ እየገነነች እንጅ እየቀዘቀዘች አልነበረም። እናም በዘመኑ ከተለያዩ ክርስቲያናዊ ስልጡን አገሮች በሐይማኖት ስም 100 ቅዱሳኖች ወደ አክሱም ተላኩ። ከእነዚህ ውስጥ አንዱ በመንገድ ላይ ሲሞት 99ኙ ወደ አክሱም በሠላም ደረሱ። ከደረሱም በኋላም የ90ዎቹ አቋም ከ9ጠኙ ቅዱሳን የተለየ በመሆኑ ምክንያት 90 ዎቹ ከአገር እንዲባረሩ ሲደረግ 9ኙ ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲቀሩ ተፈቀደላቸው ። ከነዚህ ውስጥም አንዱ አባ ዘሚካኤል/ አረጋዊ/ ነበሩና ለንጉስ እለ ዓሜዳ የመጡበትን ምክንያት አስረድተው ከሌሎች 8 የቡድኑ አባላት ጋር ሆነው

ከመንግስት ጎን በመቆም ገዳም መገደምና ቤተክርስቲያን ማሰራት ጀመሩ። በዚህም 9ኙ ቅዱሳን ወይም ተስዓቱ ቅዱሳን የሚል ቅፅል ስም ሲሰጣቸው፣ ከሐገር እንዲወጡ የተደረጉት 90ዎቹ ግን በቀይ ባህር ወደብ በአዱሊስ ከተማ ከትመው ስውር ተልዕኳቸውን ይወጡ ነበር። ዋኢትዮጵያ የታሪክ ጉዞ' የተሠኘውና በሽፈራው መንገሻ በተፃፈው መፅሐፍ እንዲህ የሚል ነገር ሠፍሮበታል። "9ኙ ቅዱሳን ወደ ኢትዮጵያ የገቡት በንጉስ እለዓሜዳ ዘመነ መንግስት ነው።... የገቡበት ዘመን ደግሞ የኢትዮጵያ ስልጣኔ ከጣሪያ ደርሶ መገታት የጀመረበት ጊዜ ነበር። የዘጠኙ ቅዱሳን ተከታዮችም ለሠማዕታቱና ለቅዱሳኑ ቤተክርስቲያን በማነፅና የበዓላት ቀን በመለየት የዓመቱን 365 ቀናቶች ሞሉት። በበዓል መስራት ግዝት ሆነ። ህዝቡም በግዝት ስለተገደደ ከመስራት ይልቅ ወደ ስንፍና አዘነበለ። ስልጣኔን የሰራው መሳሪያ ወደ የት እንደደረሠ የሚከታተል ሠው ታጣ።" ይላል።

በተረፈ የተስዓቱ ቅዱሳን ገድል እንደሚለው በየአገራቱ ክርስቲያኖች ሲጨቆኑና ሲሰደዱ መጡ የሚል ጭብጥ ያለው ሀተታ ነው የሚያትቱት። የሆነ ሆኖ እዚህ የቀሩት 9ኙ ቅዱሳን የመጡባቸው አገሮችና ከመጡ በኋላ የፈፀሟቸው ተግባሮች፣ እንዲሁም መጠሪያ ስማቸውና የተሠጣቸው ክብር የሚከተለውን ይመስላል።

| ስም | የመጡበት አገር |
|---|---|
| 1. ዘሚካኤል /አረጋዊ/ | ሮም |
| 2. ጽንጠሊዮን | ሮም |
| 3. ገሪማ /ይስሐቅ/ | ሮም |
| 4. ሊቃኖስ | ቆስጠንጥንያ |
| 5. ይምዓታ | ቆስያ /ሲሲሊ ኢጣልያ/ |
| 6. ፅህማ | አንፆኪያ /ሶሪያ/ |
| 7. ጉባ | ኪልቅያ /ግሪክ/ |
| 8. አፍጼ | እስያ |
| 9. አሌፍ | ቂሳርያ |

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱትና ቅዱሳኑ የመጡበት የአገር መጠሪያ ከፊሎቹ አንድ አይነት አገር ሆነው፤ ነገር ግን የስም ልዩነት እንዳለባቸው አድርጎ የተዘረዘረው በወቅቱ አገራቱ በየግዛታቸው ስያሜ እንደ አንድ አገር ተቆጥረው በየራሳቸው ነገስታት የሚገዙ የነበሩ በመሆናቸው ነው።

እነዚህ ዘጠኝ ቅዱሳን ወደ ኢትዮጵያ አክሱም መጥተው ፍሬምናጦስ ያመጣውንና እንደ ባህሪ የሚባለውን የክርስትና አይነት በመከተል በየአውራጃው ተበትነው ገዳም እየገደሙ፣ አብያተ ክርስቲያናት እንዲታነፁ እያደረጉ መኖር ጀመሩ። በዚህም የኢትዮጵያ ህዝብ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ታቦት በስማቸው እያስቀረፀ ቤተክርስቲያን እያሰራ ብፁዓን ቅዱሳን አድርጎ ዛሬ ድረስ ያከብራቸዋል። ከእነዚህ ቅዱሳን መካከልም በህዝብ ዘንድ በደንብ የሚታወቁት አቡነ አረጋዊ /ዘሚካኤል/ ሲሆኑ እርሳቸውም በትልቁ ተራራ በደብረ ዳሞ ገዳም የገደሙ ሲሆን፤ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታዮችም ዛሬ ድረስ እየሄዱ ይሳለሙታል። እንደዚሁም አቡነ ገሪማና አባ ጽንጠሌዎን ልክ እንደ አቡነ አረጋዊ ገዳም በገደሙበት በትግራ አገር ነዋሪዎችና በኦርቶዶክስ ተከታዮች ዘንድ የተከበሩ ሆነዋል። የአባ አረጋዊ፣ የአባ ጽንጠሌዎን፣ የአባ ገሪማ፣ የአባ አሌፍ ገድልና ድርሳናቸውም በየገዳማቸው ይገኛል። ሙሉ ታሪካቸውንም በየገድላቸው ማግኘት ይቻላል።



# ምዕራፍ ፴፩
# የአፄ ካሌብ ዘመነ መንግስት
# ከ485-515 ዓ.ም

ከዚህ በፊት ተደጋግሞ ተፅፎ እንዳየነው ከደቡብ ዓረብ መጡ የተባሉት ነገደ ዮቅጣናች በአክሱምና በአካባቢው፤ እንዲሁም በአሁኗ ኢትዮጵያ ግዛቶች ሠፍረው ሲኖሩና የቀድሞዎቹ ናፓታና መርዌ ቀርተው፤ አክሱም ስትገን ደግሞ አክሱማውያኑ እነዚያን የራሳቸውን ወገን በዓረብ አገር ያሉትን ግዛቶች ለማስገበር ዘምተውባቸው አይተናል።

ከክ.ልደት በኋላ ከአክሱም ነገስታት ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ የዓረብን አገር ያስገበረውን ንጉስም ከአዶሊስ የሃውልት ላይ ፅሁፍ ጋር አብረን አይተናል። ከእርሱ በኋላ ደግሞ ነዓንታቸውን እስመልሰው ከኖሩ በኋላ ንጉስ ዒዛና በድጋሚ ወደ አረብ አገር ሔዶ ማስገበሩን በሠፊው ተመልክተናል።

ከንጉስ ዒዛና በኋላ ግን ለጥቂት ጊዜ በዒዛና ለተተካው ለሲዛና /ለአፅባሐ/ ሲገብሩ ቆይተው፤ ከዚያ በኋላ ግን እስከ አፄ ካሌብ ድረስ መገበራቸውን አቁመው በነፃነት ነበር የቆዩት። ይህም ማለት ከንጉስ ዒዛና በኋላ ቢያንስ ለ150 አመታት በነፃነት ኖረዋል።

ስለዚህም በአክሱም ነገስታት ውስጥ ከዒዛና በኋላ ግዛት የማስፋፋት ፍላጎት የነበረውና ሃይለኛ የሆነ ንጉስ ዒዛናን አልተከተለውም ነበር ልንል እንችላለን። ለአክሱም ተገዥ የነበሩት የዓረብ አገራትም ማለትም ንጉስ ዒዛና የሳባ፣ የሐበሳት፣ የራይዳን ... እያለ የሚጠራቸው ህዝቦች ከገባርነት ለመላቀቅ ያደረጉት ጠንክር ያለ ትግል አልነበረም።

በነዚያ ነፃ ሆነው በቆዩባቸው ጊዜያቶችም በዓረብ አገር በተለይም በየመን ከጥንት ጀምሮ በየጊዜው በፓለስታይን ይደረግ በነበረው ጦርነት፤ አሁንም ከክርስትና በኋላ በቀጠለው ጦርነትና ስደት ምክንያት በርካታ የአይሁድ ተወላጆች አገራቸውን እየተው በየመን ተቀምጠዋል።

በዚህ ጊዜ ደግሞ በሮማውያን ያልተገዙት ፋርሶች ክርስትናን ያልተቀበሉና ለሮማውያን አንገዛም ብለው በነፃነት የኖሩ ነበሩ። እናም አይሁዶች ማለትም ክርስትናን ያልተቀበሉት ከፋርስ ጋር በመወገን የክርስቲያኖች ጠላት ሆኑ። በሌላ ጎራ ደግሞ የተለያዩ የክርስትና ሃይማኖት ተከታይ የሆኑት የሮም /የቆስጠንጥንያ/ እና የአክሱም /የኢትዮጵያ/ መንግስታት

ምንም እንኳ ልዩነት ቢኖራቸውም ያው ዞሮ ዞሮ በአንድ ክርስትና ስር ናቸውና ልክ እንደ ፋርስና እንደ አይሁዳውያኑ ጥምረት ፈጠሩ።

በዚህ መሰረት በዓረብ አገር የሠፈሩትና ከቀድሞ ጀምሮ በዚያው አገር በነበሩት ህዝቦች መካከል የክርስትና እምነት ተከታዮችም፣ የአይሁድ እምነት ተከታዮችም፣ አረማውያን የሚባሉትም በጋራ ይኖሩ ነበርና አይሁዶች

በፋርስ ድጋፍ አማካኝነት ክርስቲያኖቹን በመጨፍጨፍ፣ በማሰቃየትና በመጨቆን አሳኖር አሏቸው።

በወቅቱ የዓረብ አገር ደቡባዊ ክፍል እንደዛሬው አጠራር ሀሚን የመን፣ ደቡብ የመን እየተባለ ሳይሆን የሚጠራው ሂማያሪት፣ ሳባ፣ ካታባን፣ ሐድራሞት፣ ሂራ....... እየተባሉ በየነገዳቸው በተሠየመው የግዛት ስም ሲሆን፤ ከእነዚህ ውስጥ ደግሞ የአክሱም ግዛት የነበሩት ራይዳን፣ ሂሚያሪት፣ ሳባ፣ ሳልሄን .... የሚባሉት ነበሩ። እነዚህ ሁሉ ነገዶችም የየራሳቸውን ንጉስ እያነገሡ መኖር ከጀመሩ ቆይተዋል።.

በአሁኑ በአፄ ካሌብ ዘመነ መንግስትም /ከ485-515/ በዚያው አይነት አኗኗር የቀጠሉ ሲሆን፤ በዚህ ዘመን የየአውራጃውን ንጉሶች ስልጣን በእርሱ ስር አድርጎ የመንን በንጉሰነገስትነት ያስተዳድር የነበረው የአይሁዳውያን ንጉስ መጠሪያ ስሙ በዓረብ ፀሃፊዎች ዱኖዋስ፣ በሮማውያን ፀሃፊት አጠራር ዲመኖስ፣ በኛ በግዕዝ ፊንሐስ በመባል የሚታወቅ ሲሆን፤ ማዕሩቅ ብለው የሚጠሩትም አሉ። ስለዚህ እኛ ፊንሐስ እያልን እንጥራው።

ንጉስ ፊንሐስ ከሚመሩቸው ህዝቦች ውስጥ የአይሁዳውያን እምነት ተከታዮችን ድጋፍ ይዞ፤ እንደዚሁም በፋርሶች እየታገዘ በየመን /በናግራን/ አገር ያሉትን ክርስቲያኖች ማሳደድ ጀመረ። ከእርሱ በፊት ክርስቲያን ንጉስ የነበረውን አሬስታን አሸንፎ የነገሠውም በፋርሶችና በአይሁዳውያን ተከታዮቹ ድጋፍ ነበር። ስልጣን በያዘ ጊዜም ለክርስቲያኖች እንደማይጨቁናቸው ቃል ገብቶላቸው ነበር። ሆኖም በስልጣኑ ከተደላደለ በኋላ በመጀመሪያ በ500ኛው ዓ.ም የመጀመሪያው ዓመታት ላይ ቁጥራቸው እየበረከተ ሄዶ የነበረውን ክርስቲያኖች ለማጥፋት የመጀመሪያውን ግፍ የፈፀመው 4250 /አራት ሺ ሁለት መቶ ሃምሳ/ ክርስቲያኖችን በአንድ ላይ በመፍጀት ነበር። ይህም በደንብ ሳይሰማና ትኩረት ሳይሠጠው ችላ ተብሎ ሳለ፤ የናግራንን ከተማ በሠራዊቱ አስከብቦ አስጨነቃት። በከተማው ውስጥ የክርስቲያን መነኩሳትንና ቀሳውስትን፤ እንዲሁም ምዕመናንን እንደማይነካቸው የገባላቸውን ቃል ጥሶ መሃላውን በማፍረስ ሃብታቸውን ዘርፎ ቤተክርስቲያኖቻቸውን አቃጥሎ እነርሱንም ገደለ።

በጨካኝነቱ የሚታወቀው ፊንሐስ /ዱኖቫስ/ በዚሁ ክርስቲያኖች በሠፈሩበት በናግራን ከተማ ጉድጓድ አስቆፍሮ እሳት እየሰደደ ክርስቶስን እንክድም ያሉትን ክርስቲያኖች ሁሉ ወደ ጉድጓዱ እያስገባ በእሳት አቃጠላቸው። በዚህ ሒደቱም በአንድ ቀን ብቻ 20.000 /ሃያ ሺ/ ክርስቲያኖችን እንዳስፈጀ በርካቶች የፃፉ ሲሆን፤ ይህ ከፍተኛ ቁጥርም በአፄ ካሌብ የግዕዝ ታሪክነገስት ውስጥ ተጠቅሶ ይገኛል።

ንጉስ ፊንሐስ ይህን ሁሉ ካደረገ በኋላ የክርስቲያኖች ንጉስ የነበረውን የ95 ዓመት ሽማግሌ የሆነውን አሬታስን ከነቤተሰቡ አስመጥቶ ከፊቱ በማስቆም "ይህን ሁሉ መከራ ያመጣብህ ክርስቶስን ማመንህ ነውና ካድ" ብሎ ጠየቀው።



ሽማግሌው አሬታስም፡- "የሚክዱት አታላዮች እንጂ ነገስታት ውላቸውንና መሐላቸውን፣ የሃይማኖታቸውን ውል፣ አሁን አንተ ይችን ከተማ እሳጠፋም ብለህ የገባህውን ቃል እንደካድክ አይክዱም። እኔም እንዳንተ እንደካሃዲው ይሁዳ ክርስቶስን አልክድም" ብሎ በድፍረት መለሠለት።

በዚህ ምላሽ በመፅናቱም ሽማግሌው ንጉስ አሬታስ አንገቱ ተቀርጦ ሞተ። በዚህ ጊዜ ቶማስ የተባለው የክርስቲያኖቹ ጳጳስ አምልጦ ወደ አክሱም መጥቶ ለአክሱሙ ንጉስ ለአፄ ካሌብ የተፈፀመውን ግፍ ሁሉ በመናገር አቤቱታውን አቀረበ። አፄ ካሌብም ሁኔታውን እንደሰማ ለዘመቻ መዘጋጀት ጀመረ። በተመሳሳይ ጊዜም በየመን የነበሩ ክርስቲያኖች ይህን መሰሉን ግፍ በመሸሽ ወደ ቆስጠንጥንያና ወደ ሌሎቹ የሮማ ግዛት ወደ ሆኑ የክርስቲያን አገሮች እየሄዱ ነበርና፤ የቆስጠንጥንያው ንጉስም መረጃው ደረሰው። በሠማውም ጉዳይ በእጅጉ አዘነ። ይህ በወቅቱ የቆስጠንጥንያ ንጉስ የነበረው ዩስጢኖስ የተባለው ንጉስ ሁኔታውን ለእስክንድርያው ጳጳስ በመልዕክተኛ ሲገልፅለትም፤ የእስክንድርያው ጳጳስ ለቆስጠንጥንያው ንጉስ የመለሠው ምላሽ "ለአክሱሙ ንጉስ ደብዳቤ ፃፍለት" የሚል ነበርና ንጉስ ዩስጢኖስ ወደ አክሱም ንጉስ ወደ አፄ ካሌብ ደብዳቤ ላከ።

ቀድሞ ሀምቱ በዝግጅት ላይ ለነበረው ለአፄ ካሌብ የደረሠው ደብዳቤም እንዲህ የሚል ነው። "እናንተ የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ወደ አረብ ተሻግራችሁ የሞቱትን የክርስቲያኖች ደም ልትበቀሉ ይገባል። እናንተ የማትችሉ ከሆነ ግን የኔ ጦር በኮንቶስና /በላእላይ ግብፅ/፣ በቤርኒቂ /ቀይ ባህር አጠገብ/ በኩል አድርገው በኢትዮጵያ ላይ አልፈው ሄደው ይበቀላሉ።" የሚል ነው።

የቆስጠንጥንያው ንጉሰነገስት የግብፅና የአካባቢው፤ እንዲሁም የእስያ አገር በሙሉ የበላይ ገዥ ስለነበርና የክርስቲያኖች ተስፋ እንደሆነ ስለሚታመን በላከው ደብዳቤ ውስጥ ሌላ ተጨማሪ መልዕክት ያስተላለፈ ይመስላል። ይኸውም አፄ ካሌብን ሔደህ ተበቀል፤ ካልቻልክ ግን የኔ ጦር ከግብፅ ተነስቶ በአገርህ ሲያልፍ ጎድቶህ እና አስገብሮህ ያልፋል ለማለት የፈለገ ይመስላል። ምክንያቱም ጦሩ የሚያልፍበትን ቦታ መጥቀስ አስፈላጊ አይደለምና ነው።

ይህ በእንዲህ እንዳለም የዓረብ ሃገር እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የአክሱም ግዛት የነበረና በፖለቲካና በሃይማኖት ከጥንት ጀምሮ የተሳሰረ፤ እንዲሁም በናግራን ያሉት ክርስቲያኖች የሚመኩት በቆስጠንጥንያና በአክሱም መንግስት ስለሆነና ጳጳሱም አቤቱታውን በቀጥታ ያቀረበው ለአክሱም ንጉስ ስለሆነ አፄ ካሌብ መልዕክቱ ባይደርሰው እንኳን መዝመቱ የማይቀር የነበረ ከመሆኑም በላይ፤ ደብዳቤው የደረሰውም በሚዘጋጅበት ጊዜ ስለሆነ ከማንም በላይ የሚመለከተው የአክሱምን መንግስት ነው።

ከዚህ በኋላ አፄ ካሌብ 72 ታላላቅ መርከቦችንና 70.000 /ሰባ ሺ/ የሚሆነውን ጦሩን አደራጅቶ ወደ የመን ጉዞ ከመጀመሩ በፊት ለአምልኮ

ፀሎት አደረሠ። የፀሎቱ ቃል ከግዕዝ ወደ አማርኛ ሲተረጎም እንዲህ ይነበባል። ወደ ቤተክርስቲያን ሔዶ ልብሰ መንግስቱን አውልቆ፡-

"እግዚአብሔር ሆይ አቤቱ ሁሉን የፈጠርህ፤ እልፍ አእላፍ መላዕክት የሚገዙልህ፤ ኪሩቤልና ሱራፌል የሚያመሰግኑህ፤ የካህናት ፈጣሪ፣ የጌቶች ጌታ፣ የጌታችን የመድሃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት፣ ብርሃናትን የፈጠርክ፣ ሠውን ሁሉ ከዓሳር ወደ ክብር ይመልሰው ዘንድ ልጅህን ወደኛ የሰደድህ ... አቤቱ የአባቶቻችን ፈጣሪ እኛን ስለማዳን ሠው በሆነው በልጅህ ምክንያት ይህ ከሐዲ /ፊንሐስ/ ያደረገውን ሁሉ እነሆ አይተህዋል።
ወገኖችህን እንደ በግ እንዳረዳቸው ቤተክርስቲያንህንም እንዳቃጠለ ... ከዚህ ወጥቼ ይህን ያነተንና የኛንም ጠላት አይሁዳዊ እጠፋዋለሁ። በልጅህ በክርስቶስ ሐይል ለወንድሞቼ ለምዕመናኑ፣ ሳንተ ለፈጣሪዬ ቅን ሆኛለሁና አታሳፍረኝ። በሐጢያቴ ብዛት ግን ልመናዬን የማትሰማ እንደሆነ ከዚህ ቦታ ግደለኝ። አቤቱ ርስትህን ኢትዮጵያን ስምህን ለማያውቁ ለጠላቶችህ አሳልፈህ አትስጣቸው።"

ከዚህ ፀሎት በኋላ አፄ ካሌብ ከነሠራዊቱ በመርከብ ጉዞ ጀመረ። እንደደረሠም 30 ሺ የአይሁድ ጦር ይዞ ፊንሐስ እየተጠባበቀው ነበርና ውጊያው ተጀመረ። ለጥቂት ጊዜ ውጊያው መርከብ ላይ እንዳለ በጦር፣ በቀስትና መርከቦቻቸው ተጠጋግተው በጨበጣ ሲካሄድ ቆየ። ቀጥሎም በየብስ ላይ በሚዋጉበት ጊዜ ከሁለቱም ወገን ብዙ ሠራዊት አልቆ ድሉ የአፄ ካሌብ ሆነና አይሁዳውያኑ ተበታተኑ። ንጉስ ፊንሐስም ሸሸ።

ከዚያም አፄ ካሌብ ወደ የመን ከተማ ወደ ዛፋር ሔዶ የከተማውን ጠባቂዎች አሸንፎ ከተማውን ያዘ። የአይሁድ ንጉስ ሚስትም በዚች ከተማ ተማረከች። ወዲያውም አፄ ካሌብና ንጉስ ፊንሐስ ፊት ለፊት ተገናኝተው በጨበጣ ፈረሶቻቸው ላይ ሆነው ሲዋጉ ካሌብ ፊንሐስን ወግቶ ከፈረሱ ላይ በመጣል ወደ ባህር ገፍትሮ ወረወረውና ሞተ።

ከፊንሐስ ሞት በኋላም የበታቾቹ ጦርነቱን ለመቀጠል ሞክረው ሳይሆንላቸው ቀረና ተሸነፉ። ከዚህ በኋላ አፄ ካሌብ ከተከታዮቹ ጋር ከተማዋን በሙሉ እየዞረ የፊንሐስን ተባባሪዎች ሁሉ እያስያዘ አስገደለ። በሐገረ ናግራን የተፈጁትን የክርስቲያን ምዕመናንን ደምም ተበቀለ። የሸሹትና የተደበቁት ክርስቲያኖችም ወደየመንደራቸው ተመለሱ።
አፄ ካሌብ ሙሉ ለሙሉ ድል ካደረገ በኋላ ወደ እስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ የድሉን ወሬ በመልዕክተኛ ላከ። እጅግ አዝነውና ተክፍተው የነበሩ የየአገሩ ክርስቲያኖችና ካህናቶቻቸውም ሐዘናቸው በደስታ ተለወጠ።

ከዚህ በኋላም ንጉስ ካሌብ በናግራን የሚቹን ንጉስ የሾማግሌውን የአሬታስን ልጅ ሾመው። ወደ ዛፋርም ሄዶ ለየመን ግዛት ዘመዱን አስ



አይባን እንደራሴ አድርጎ ሾመው። ህዝቡ ግን በአስ አይባ እንደራሴነት አለመደሰቱንና ከእርሱ ይልቅ ትውልዱ ዓረብ፣ ሐይማኖቱ ክርስቲያን የሆነ ንጉስ እንዲነግስለት ጥያቄ አቀረበ።

ንጉስ ካሌብ ጥያቄያቸውን ተቀብሎ የፈለጉትንና ወገናቸው የሆነውን አርያት /አቡ ሔሴም/ የሚባለውን የሰንዓ ንጉስ ብሎ ሾመላቸው። እርያትንም በየዓመቱ ለአክሱም ቤተ መንግስት እንዲገብር ትዕዛዝ ሰጠው።

በሌሎች አውራጃዎችም እንዲሁ ሹምሽር አድርጎ 10 ሺ ሠራዊት ለጠባቂነት እዚያው እንዲቀር አደረገ። /በኋላ ላይ ግን የመጀመሪያው እንደራሴ አስ አይባ ወይም አብርሃ ንጉሱን አርያትን እንዳስገደለና በየመን መንግስት ላይ ተደላድሎ በመቀመጥ በየአመቱ ለአክሱም ቤተ መንግስት ግብሩን ማስገባት እንደቀጠለ ይነገራል።/

ከዚህ ድል በኋላ አፄ ካሌብ ወደ አክሱም ከመመለሱ በፊት የክርስቲያኖች ንጉስ በነበረበት ቦታ ቤተክርስቲያን እንዲሰራ አደረገ። መሠረቱ ሲቆፈርም እራሱ ንጉስ ካሌብ ሀባት ቀን ሙሉ አብሮ ሲቆፍር ቆየ። በተጨማሪም የፈረሡትን ሲያሰራ፣ የቀሩትን ቤተክርስቲያኖች ሲያሳድስ ጥቂት ጊዜ በየመን ተቀመጠ።

የአፄ ካሌብ ድል አድራጊነት ለአክሱም መንግስት የቀድሞ ግዛቱን ከማስመለሱና የአክሱምን ገናናነት መልሶ ከማደሱም በላይ፤ በናግራን /ደቡብ የመን/ በክርስቲያኖች እልቂት ምክንያት በእስክንድርያ፣ በቆስጠንጥንያ፣ በአንፆኪያና በሌሎች አገራትና ህዝቦች ዘንድ የተፈጠረውን ሐዘን በደስታ ለውጧል። በዓረብ አገር ሊጠፋ የነበረውን ክርስትናም መልሶ ሊያቃናው ችሏል።

ለከፍተኛ ጥፋት ተባብረው ለነበሩት በአይሁድና በፋርስ ህዝብ ላይ ድልን አግኝቶ ግዛታቸውንና የአመፅ አገዛዛቸውን አስወግዶ የራሱንና የኢትዮጵያን ክብር ሊተክበት ችሏል።

በዚህ ታላቅ ስራውም በቆስጠንጥንያና በዚያ ዘመን ዓረቦች ዘንድ በቤተመንግስቶቻቸውና በቤተክህነታቸው ዘንድ ስመጥርና ገናና ታሪክ ያለው ንጉስ መሆን መቻሉን በጥንታዊ የውጭ አገራት የነገስታት ታሪክ ውስጥ መካተቱ በራሱ ያስረዳል።

አፄ ካሌብ ድልን ሳቀዳጀው አምላኩ ደስታ ሲል ከዘመቻው መልስ የነገሰበትን ዘውዱን አውልቆ በኢየሱስ ክርስቶስ መቃብር በራፍ ላይ እንዲሰቀልለት ለአየሩሳሌሙ ኤጲስ ቆጶስ ላከ፣ የተደላደለ መንግስቱን በመተው፤ ይህን ዓለም ንቆ በአባ ጰንጠሌዎን ገዳም አበገብ በምትገኝ አንዲት ዋሻ ውስጥ አንዲት ሠሌን ለመኝታው፣ አንዲት ቅል ለውሀ መጠጫብቻ ይዞ ገብቶ ተቀመጠ። ምንም እንኳ እስኪሞት ድረስ ሌላ

ንጉሰነገስት ያልተተካ ቢሆንም፤ በዚያች ዋሻ ውስጥ በፀሎትና በስግደት እየኖረ ግንቦት 20 ቀን 515 ዓ.ም ከዚህ አለም በሞት እስከለይ ድረስ ለዚህ አለምና ለመንግስቱ እንዲሁም ለክብሩ ጓጉቶ አለመመለሱ ብዙዎቹን ያስደንቃል። በዚህ ተግባሩም የንጉሰነገስት መናኒ የሚል ስያሜ ተሠጥቶታል።

አፄ ካሌብ ከዓረብ አገር ዘመቻና ድል መልስ በዚች ዋሻ ለ12 አመታት የቆየ ሲሆን፤ አጠቃላይ የግዛት ዘመኑ 30 አመት ነበር። የሞተውም በ 70 አመቱ ነው። አፄ ካሌብን በዚህ ሁሉ ስራው የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን በፃድቅነቱ ታከብረዋለች። የሮም ቤተክርስቲያንም ከሠማዕታቶች ጋር ቆጥራ የአፄ ካሌብን በዓል በየአመቱ /ኦክቶበር 27/ ቀን ታከብረዋለች።

ከዚህ በኋላ በነበረው ጊዜም የየመን ህዝብ ከካሌብ ጀምሮ ለመቶ አመት ያህል መገበሩቸው ቀጥሎ ነበር። ከዚያ በኋላ ግን ፋርሶች መጥተው የሐበሻዎቹን ሠራዊቶች በጦር አሸንፈው ንጉሶችንና ሹማምንቱን ገድለው ለአክሱም መንግስት ይገብር የነበረውን የመንንና አካባቢውን የራሳቸው አደረጉት። አረማውያን ነበሩና አዲስ የተሠሩትንም፣ የታደሱትንም ቤተክርስቲያኖች አፍርሰው የራሳቸውን የጣኦታት ቤተ መቅደሶች ገነቡ። ከዚያም በ630 ዓ.ም ነብዩ መሐመድ መጥተው ፋርሶችን አሸንፈው የጣኦታቸውን ቤተ መቅደስ በማስፈረስ መስጊድ አስገነቡበት። ይህንንም ወደ ፊት በሠፊው የምናየው ይሆናል።

ከአፄ ካሌብ ፍፃሜ በኋላ የነገሱት ሁለት ነገስታት አፄ ዘእስራኤልና አጼ ገብሩ ሁለቱም አንድ አንድ ወር ብቻ ነግሰው የነበረ ሲሆን፤ ሁለቱም የአፄ ካሌብ ተከታታይ ልጆች ነበሩ። ከዚያም የካሌብ ሶስተኛ ልጅ አፄ ገብረ መስቀል ነግሷል።

የሁለቱ ነገስታት የግዛት ዘመናቸው ለምን እንዳጠረ የሚገልፅ መረጃም የለም። ስለዚህም ከእነርሱ ቀጥሎ ወደ ነገሰው ወደ አፄ ገብረ መስቀል ታሪክ እንሻገራለን።



# ምዕራፍ ፴፪
# የአፄ ገብረመስቀል ዘመነ መንግስት
# ከ 515 - 529 ዓ.ም

የአገራችን ነገስታቶች ታሪክ ወደ ኋላ እየሄድን ስናይ በዘመናቸው ካከናወኗቸው የጦርነት ዘመቻዎችም ሆነ ሌሎች አለማዊ ስራዎቻቸው ሁሉ መንፈሣዊ ይዘት ያላቸው ናቸው።

መንግስታዊ መዋቅራቸው የተዘረጋውም ከሐይማኖት ጋር በተያያዘ መልኩ ነው። እያንዳንዱ ንጉሠነገስት በዘመኑ ከፈፀመው አለማዊ ተግባር ይልቅ መንፈሣዊ ስራው የበለጠ ያመዝናል። ይህም ነገስታቶቻችን ለሐይማኖታቸው የነበራቸውን ፍቅርና አክብሮት ከማሣየቱ ባሻገር፤ ሙሉ ጊዜያቸውንም በመንፈሳዊ ስራ ብቻ እንዳሳለፉ በግልፅ ያስረዳናል።

ከዚህ አንፃር የአፄ ገብረመስቀል ዘመነ መንግስትን የአስተዳደር ቅይታ ስናይ ቤተክርስቲያንንና ገዳማትን በምን መልኩ እንደጎበኘ፣ ለገዳማት ምን ዓይነት ስጦታ እንደሠጠ የሚያትተውን ታሪክ እናገኛለን።

ይህ በእንዲህ እንዳለም በአፄ ገብረ መስቀል የንግስና ዘመን የነበረውና አለምን ዛሬ ድረስ የሚያስደንቀውን ጥበበኛ የቅዱስ ያሬድን ታሪክና፤ ከአቡነ አረጋዊ ጋር ስለነበረው ግንኙነት የምናየው በዚሁ ምዕራፍ ይሆናል።

የአፄ ገብረመስቀል ታሪክ ከተስዓቱ ቅዱሳን ውስጥ ከዋነኛው ከአቡነ አረጋዊና የድጓን ዜማ ከደረሠው ከቅዱስ ያሬድ ጋር የተገናኘ ሲሆን፤ የሶስቱ ግንኙነት ደግሞ በገድለ ያሬድ፣ በገድለ አብርሃ፣ በገድለ አረጋዊና በሌሎች መንፈሣዊ ዕሁፎች ውስጥ ሠፍሮ ይገኛል።

ነገር ግን ከላይ እንደተባለው የአገዛዙና የአስተዳደሩ፤ እንዲሁም ሌሎች ተያያዥ ወግና ስርአቶች ምን መልክ እንደነበራቸው የሚገልፁ መረጃዎች ሳይሆኑ፤ ከእነዚሁ ቅዱሳን ጋር የነበረውን ግንኙነት ነው የሚያሳዩት።

በዚህ በገድለ አረጋዊ ውስጥ ራሳቸው አቡነ አረጋዊ የደብረዳሞን ተራራ ለብትውህትናና ለማስተማሪያ መርጠው እያለ፤ ነገር ግን ተራራው ረጅም ከመሆኑ የተነሳ ለመውጣት ስለቸገራቸው ከስር ሆነው ‹‹ምነው ከንፍ በኖረኝ›› እያሉ እደተመኙና እግዚአብሔር ወደ ተራራው ጫፍ የሚያወጣ አንድ ነገር እንዲልክላቸው ሲፀልዩና በፆም፣ በፀሎት፣በስባኤ ሲለምኑ

መልዓኩ ሚካኤል ቀርቦ "አትፍሩ" እንዳላቸው፤ እግዚአብሔርም በገመድ ፋንታ 60 ክንድ ቁመት ያለው ትልቅ ዘንዶ እንደሚልክላቸው መናገሩና ከዚያም ዘንዶው ከተራራ ወርዶ እንደሰው አፍ አውጥቶ ‹‹ከዚያ ተራራ ላይ ከወፎች በቀር ውሃም፣ ዳቦም የለም። ራስህን የምታስጠጋበት

እንካ የለህም...›› ብሎ እንዳነጋገራቸው፤ እርሳቸውም ‹‹አንተ የታዘዝከውን ፈፅም። እምላክ የፈቀደውን ሁሉ አይነሳንም ... ›› እንዳሉት፤ ከዚያ በኋላ ሚካኤል ሠይፋን መዞ እየጠበቀ ዘንዶው ጭራውን እንዳሉት፤ ከዚያ በኋላ ሚካኤል ሠይፋን መዞ እየጠበቀ ዘንዶው ጭራውን ወደ አቡነአረጋዊ አድርጎ እርሳቸውም ጭራው (ጅራቱ) ላይ ወጥተው ተራራውን እየወጡት እያለ ዘንዶው አቡነአረጋዊን አወናጭፎ እንደወረወራቸውና በድንገት ተራራው ላይ ደርሰው ሀሌሉያ ብለው እንዳመሰገኑ፤ ከዚያም በዚሁ በደብረዳሞ ተራራ ሆነው ለህዝቡ ቡራኬና ትምህርት ይሰጡ እንደነበር ይገለፃል።

ከእለታት አንድ ቀንም አፄ ገብረ መስቀል በሰራዊቱ ታጅበ እንደሔደና ሰራዊቱን ከተራራው ስር ትቶ ከጥቂት ተከታዮቹ ጋር በገመድ ወደ ተራራው ወጥቶ ቡራኬ መቀበሉንና ‹‹ቤተክርስቲያን ልሰራ የምችልበትን ቦታ መርጠው ያመልክቱኝ›› ብሎ እንደጠየቃቸው፤ አቡነ አረጋዊም አካባቢውን ከንጉሱ ጋር እየዞሩ ተመልክተው ቦታ መርጠው እንዳሳዩት፤ ከዚህ በኋላ ንጉሱ በአዋጅና በትዕዛዝ ድንጋዩ፤ እንጨቱ እየተሰበሰበ በክብትና በሰረገላ እየተጫነ ወደ ተራራው እየተጓዘ አፄ ገ/ቀል በነገሰ በሁለተኛው ዓመት ግንባታው እንዳለቀ፤ ለዚች ቤ/ያንም ንጉሱ ልዩ ልዩ አልባሳት፤ የወርቅ እና የብር ሰዋ፤ በወርቅና በብር የተሰበጡ መንፈሳዊ መፃህፍትን እንደሰጡና የማርያምን ታቦት አስገብተ ቅዳሴውን አቡነ አረጋዊ ቀድሰው ንጉሡና ጳጳሱ እንደቆረቡ፤ ከዚያም አፄ ገብረመስቀል በተራራው ላይና ከተራራው ስር ላሉት ሰራዊቱ ግብር አብልቶ፣ ነዳያን ሁሉ በመብል እንደጠገቡና ደስታ እንደሆነ ገድሉ ሰፋ አድርጎ ይገልፃል።

ከጊዜ በኋላም ቅዱስ ያሬድ ወደ ደብረዳሞ ወጥቶ ከአቡነ አረጋዊ ጋር በወጣትነቱ ተገናኝቶ የታነፀውን ቤ/ያን አድንቆ እንደተመለሰ ይነገራል። ስለዚህም እዚህ ቦታ ላይ የቅዱስ ያሬድን ታሪክ ሰፋ አድርገን እናየዋለን። የእርሱን ታሪክ ስናይም እግረ መንገዳችን በአፄ ገብረመስቀል ዘመነ መንግስት ኢትዮጵያውያን ደስታና ምቾት በዝቶባቸው እንዴት ይኖሩ እንደነበር እንረዳለን።

በ505 ዓ.ም በኢትዮጵያ ምድር በአክሱም ከተማ የተወለደው ቅዱስ ያሬድ በአፄ ገብረመስቀል ዘመን ንቁ ወጣት ሆኖ ነበር።

ቅዱስ ያሬድ በመንፈሳዊ ዜማ ቀማሪነቱ ይታወቃል። በዚህም ከአገሩ ባለፈ ለአለም የራሱን አስተዋፅኦ አበርክቷል። መንፈሳዊ ት/ቱን ተምሮ ሲጨርስም ሌሎችን በማስተማር ተግባር ተሰማርቶ ነበር። ያሬድ ማለት ይላሉ የሐይማኖት ሊቃውንት... ርደት ... ከዕርሐ አርያም ማህሌተ መላዕክት ያወረደ ማለት ነው።



በተጨማሪም ያሬድ ማለት ንብ ማለት ነው፡ በማለት ስለቅዱስ ያሬድ ቀደም ብሎ የተተነበየለትን መሰረት በማድረግ ያብራሩታል።

ንብ የማትቀስመው አበባና ጤዛ እንደሌለ ሁሉ ያሬድም ከቅዱሳት መፃህፍት ያልጠቀሰው ቃላት፣ ያልመረመረው ሚስጥር የለም። ንብ የቀሰመችውን አበባ አጣፍጣ ማር አድርጋ ታቀርባለች። ማሩን የሰው ልጅ ጣፍጦት ተመግቦት ለመድሀኒትነትም አውሎት ቅሪቱ /ሰሙ/ ደግሞ ለብርሃን አገልግሎት ይውላል። ቅዱስ ያሬድም ከመፃህፍት የቀሰማቸውን ቃላት አዋህዶና አጣፍጦ በዜማ እየዘመረ የማይናድና የማይፈራርስ፤ ብሎም ከብዙ አቅጣጫ ሲታይ ጠቀሜታው የጎላን ነገር አበርክቶ ነው ያለፈው። በዚህም ያሬድን ታሪክ ሲዘክረው ይኖራል።

በትግራይ ክፍለአገር በደስአ ወረደ ማርያም በተባለች ቤ/ያን በተገኘና በብራና ላይ በተፃፈ ጥንታዊ የመዝሙር መፅሃፍ በመቅድሙ ላይ ግዕዙ በአማርኛ ተተርጉሞ እንዲህ ይነበባል።

‹‹ከአፄ ካሌብ ዘመነመንግስት ጀምሮ እስከ ልጃቸው እስከ አፄ ገብረመስቀል ዘመነመንግስት ድረስ በመላው ኢትዮጵያ ሰላምና ጥጋብ በዝቶ ነበር። ህዝቡ ጠግቦ ሁልጊዜ ቀንና ሌሊት እየዘፈነና እየጨፈረ በስጋ ፍላጎት ከገደብ ባለፈ ሁኔታ እየተደሰተ እግዚአብሔርን ያስቀይመው ነበር። ይልቁንም የከተማው ህዝብ ጥጋቡን አልችለው ብሎ በመሰንቆና በሌላ የዘፈን ማጀቢያ በእልልታ በድምቀት ሲዘፍን ቅዱስ ያሬድ ደግሞ በሚያስተምርበት ቦታ ሆኖ ዘፈኑን ይሰማል።

በዚህ ጊዜ በዘፈኑ ሲያዝንና ሲናደድ አምላክ በጣዕመ ዜማው ዘፈኑን ለውጦ ወደ መንፈሳዊ ዜማ እንዲመልሰው በሰጠው የመላዕክት ዜማ ለዘላለም መታሰቢያ እንዲያቆምለት በወደደ ጊዜ በወጣትነት እድሜው ከገነት ኤዶም አርድዕን የሚባሉ ሶስት ነጭ ወፎች ልኮ ወደ ዕርሐአርያም ነጠቀውና በዚያው የሚመስገንበትን የመላእክት ዜማ ገለፀለት። በዚያም ላይ ስልጣነ ክህነት አደለው።

ከዚያም በማግስቱ ወደ ቀድሞ ቦታው መለሰውና በገለፀለት ጣእመ ዜማ ምድራዊ /አለማዊ/ ዘፈንን መልሶ ህዝቡ በሰማያዊ ማህሌተ መላዕክት ፈጣሪውን እንዲያመሰግንና እንዲያስደስት አደረገው››... እያለ ይቀጥላል። ይህንንና ሌሎች በርካታ ፅሁፎችን መሰረት በማድረግ መሪጌታ ልሳነ ወርቅ ገብረ ጊዮርጊስ "ጥንታዊ ስርዓተ ማህሌት ዘአቡነ ያሬድ" በተሰኘ መፅሃፋቸው

የያሬድን ታሪክና የስራ ውጤት አስፍረውት እናገኛለን። እናም ቅዱስ ያሬድ በአክሱም ፅዮን ‹‹ሃሌሉያ ለአብ›› በማለት ድርሰቱን ጀመረ።

የዛድቁ የአፄ ካሌብ ልጅ አፄ ገብረመስቀል ጥዑሙንና ለየት ያለውን ይህን የቅዱስ ያሬድን ዜማ በሰማ ጊዜ ጣዕማዎቹን ከአገሩ

ሳያጠልቅ ተነሳ። መዝሙርቱ /ባለቤቱ/ ንግስት እሌኒም ገረዶቿን ትታ አብራው ተነሳች። ጳጳሱና መምህራኑ፤ እንዲሁም ካህናቱና የቤተመንግስቱ ታላላቆች ይህን ጥዑመ ዜማ ያደምጡ ዘንድ በአንድነት ወጥተው ወደ አክሱም ቤ/ያን ፈጥነው ሄዱና አዲሱን የያሬድ ዜማ ማድመጥ ጀመሩ። ያሬድም ከእኩለ ቀን ጀምሮ ጣዕመ ዜማውን ከድምፀ ቃናውና ከድምፀ መሰንቆው ጋር እያስማማ ሲዘምር ዋለ።

በዚህ መሳጭ ስራውም የሀይማኖት አባቶችን ጨምሮ የሁሉንም ምዕመን አድናቆት አገኘ። ቅዱስ ያሬድ በጊዜ ሂደት ደጋግሞ በመለማመድ እለት እለት እያሻሻለና እያሳመረ ከአገሩ አልፎ ለአለም የሚተርፈውን ዜማ ለመቀመር ቻለ።

የዜማ ጥበቡም ከመንፈሳዊ አልፎ በጊዜ ሂደት ለአለማዊ ዜማዎችና ዜመኞች ዛሬ ድረስ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል። ቅዱስ ያሬድ ከዚህ በኋላ በአንድ ክልል ተወስኖ አልኖረም። በተለያዩ ክፍላተ አገራት በሚገኙ ቅዱስ ቦታዎች እየተዘዋወረ አስተምሯል። ለአብነትም በጣና ሐይቅ ቤተ ሳህል፣ ዲጋ ምእራፍዬ፣ ደብረ ሸራና ዋድ፣ ምድረ ሐይቅና ክሬብ፣ ደብረ ሀገዘ፣ ደብረ ኤዛር፣ ደብረ አባይ፣ ደብረ ምጥማቅ፣ ደብረ ግሽን፣ ደብረ ዳሞ እንዲሁም ወደ ሌሎች ገዳማትና አድባራት እየተዟዟረ ብዙ ሊቃውንትንና መምህራንን እያስተማረ መርቋቸዋል።

የተለያዩ ሐይማኖታዊ መፃህፍትንም ፅፎ ለተተኪው ትውልድ መማሪያና ማስተማሪያ አበርክቷል። ከቅዱስ ያሬድ መፃህፍት ውስጥ ድጓ፣ ፆመ ድጓ፣ ዝማሬ፣ መዋሲት /መስዋዕት/ እኢጋረ ፀሀይ፣መፅሀፈ ብርሀን፣ መፅሐፈ ቅዳሴ ይገኙበታል።

እንደ መሪ ራስ አማን በላይ መፅሀፈ አብርሂት አገላለፅም፦ ቅዱስ ያሬድ ድጓውን የደረሰበት አገር ለብዙ ዘመናት ብዙ መምህራን የተመረቁበት ቦታ በሆነው በቤተልሄም ነው። /በኢትዮጵያው ቤተልሄም ማለት ነው።/

ቅዱስ ያሬድን ስናነሳ ደግሞ ግዕዝ፣ እዝል፣ አራራይ የተባሉ ሶስቱን የዜማ ስልቶች አብረን እናነሳለን። ከዚህም በላይ 12ቱ የዜማ ምልክቶች በባለቤቱ በራሱ በቅዱስ ያሬድ እንደተቀመሩ በግልፅ ይታወቃልና፤ ትርጓሜያቸውንና መገለጫቸውን ማየቱ ተገቢ ይሆናል። (በየጊዜው መሻሻላቸው እንዳለ ሆኖ) እነዚህን የዜማ ስልቶች ቅዱስ ያሬድ በረቀቀ መልኩ እንደተገለገለባቸው የታሪክ ድርሳናት ከማመላከታቸው ባሻገር፤ ዛሬ ድረስም አገልግሎት እየሰጡ ያሉ ናቸው።

**ግዕዝ፦** ግዕዝና ቅዱስ ያሬድ ከቋንቋ ያለፈ ቁርኝት ነበራቸው። ስለዚህም ቅዱስ ያሬድ ግዕዝን እንዲህ ያብራራዋል። የልዑል እግዚአብሔር ምሳሌ



ሲሆን፤ ትርጉሙም ርቱዕ ወይም አንደኛና የመጀመሪያ ዜማ ማለት ነው። እናም ሃሌሉያ ለአብ ሲል ጀምሮበታል።

**ዕዝል፦** በዜማ ስልትነቱ እጅግ ጠንካራና ብርቱ በመሆኑ ሊቃውንት ‹‹ደረቅ ዜማ›› ይሉታል። ስለሆነም የልዑል እግዚአብሄር ወልድ ወይም የወልድ ምሳሌ ሲሆን፤ በዜማነቱ ከግዕዝ ጋር ታዝሎ የሚዜም ዕዝ እና ጠንካራ የሆነ ምስጋና የሚደረግበት ነው።

**አራራይ፦** የልዑል እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ወይም የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ሲሆን፤ ትርጓሜውም የሚያራራ፣ ጥዑም፣ አሳዛኝ፣ ልብን የሚመስጥ ማለት ነው። ቅዱስ ያሬድ እነዚህን በመሰሉ ሂደቶች ጥረቱን እየጠናከረ፣ በተግባር እየሞከረ ለመንፈሳዊ አገልግሎት ሲወጣና ሲወርድ ኖሯል። በዚህ ተግባሩም እጅግ ስኬታማ ነበር።

እነዚህም ሆነ ሌሎች ነገሮች መሰረታቸው ቅዱስ ያሬድ ሲሆን ለዛሬው ትርዕ እና ይዘት ግን የበርካታ ሊቃውንት የየዕለት ክህሎት ታክሎበት ጠንክሮና ዳብሮ ይገኛል። በመሆኑም ቅዱስ ያሬድ የደረሳቸው የዜማ ምልክቶች ትርጉም የሚከተሉት ናቸው።

1. ቅናት፦ ጌታን በቅናት አይሁዶች ለመያዝ ማሰባቸው፤
2. ይዘት፦ ጌታ /ኢየሱስ/ በአይሁድ ጭፍሮች ስለመያዙ፤
3. አዘር፦ ጌታ ከሀና ወደ ቀያፋ ከጲላጦስ ወደ ሔሮድስ መመላለሱ፤
4. ጭረት፦ ጌታ በግርፋቱ ሰንበር፣ ጭረት ማውጣቱ፤
5. ቁርጥ፦ በጌታ ላይ ቁርጥ የሞት ፍርድ መፍረዳቸውና በጦር ሲወጋ ፈፅሞ እንደሞተ መሆኑ፤

6. ሂደት፦ ጌታ ታስሮ መስቀሉን አሸክመው ከሊቶስጥራ ወደ ቀራኒዮ መወሰዱ፤
7. ድፋት፦ ጌታ አክሊለ ሶክ መድፋቱ፤
8. ደረት፦ ደረቱን ረግጠው ለመቸንከራቸው፤
9. ዘንጥል፦ ልብሱን ከሰውነቱ ቀደው መግፈፋቸው፤
10. ርክርክ፦ ለጌታ ለደሙ ነጠብጣብ አወራረድ፤
11. አንብር፦ ሶስት መአልት፣ ሶስት ሌሊት በመቃብር
12. ስለመቆየቱ፤
13. ድርስ፦ በነቢያት የተነገረው ትንቢት ስለመድረሱ /ስለመፈፀሙ/፤

እነዚህ የዜማ ምልክቶች በተግባር እንደየአገባባቸው ተዋህደውና ተጣምረው ሲዜሙ ተወዳጅ የሆኑና ለዛ ያላቸው ሆነው ይገኛሉ።

ቅዱስ ያሬድ ይህን የመሰለ ረቂቅ ስራ በዘመኑ ከመፈፀሙም በሻገር ለአለም የዜማ ድርሰት መሰረት ጥሏልና በሁሉም ዘንድ ባለውለታነቱ የማይዘነጋ አይደለም። የቅዱስ ያሬድ የምድር ቆይታ ሙሉ በሙሉ ለመንፈሳዊ አገልግሎት የተገዛ እንደነበረና፣ ድንግልናውን ጠብቆ ብዙ አባቶችን አስተምሮ፣ እድሜውን በሙሉ በብትውህትና እንደፈፀመ ነው የሚታወቀው።

ቅዱስ ያሬድ የመጀመሪያ ስራውን የፈፀመው በአፄ ገብረመስቀል ዘመነመንግስት ነበርና ንጉሰ ነገስቱ የሚያስፈልገውን ነገር በማሟላትና ወደሚፈልገው ቦታ እየሔደ እንዲያስተምር እንዛ አድርጎለታል። ስጦታም አበርክቶለታል።

ከዚህ በተረፈ ስለ አፄ ገብረመስቀል በውጭ አገር ሀሃፊዎች ዘንድ በጥቂቱ ስሙ ሲነሳ፣ ይኸውም በቆስጠንጥንያ ንጉስ በዩስጢኖስና በአፄ ካሌብ መካከል ቀደም ሲል ወዳጅነት እንደነበረ ሁሉ፣ አሁንም በአፄ ካሌብ ልጅ በንጉስ ገብረመስቀልና በዩስጢኖስ ልጅ በሆነው ዩስጢንያኖስ መካከል እንደአባቶቻቸው አይነት ወዳጅነት የነበራቸው መሆኑ ተፅፏል።

በዚህ ግንኙነታቸውም በቆስጠንጥንያው ንጉስ በዩስጢንያኖስ ወዳጅነት አማካኝነትና የአንድ ባህርይ ክርስትና አማኝ በነበረችው በሚስቱ በቴዎዶራ ደጋፊነት በግብፅና በእየሩሳሌም ከኢትዮጵያ ለሚሄዱት ምእመናንና መነኮሳት መቀመጫ የሚሆን ቦታና ገዳም በአፄ ገብረመስቀል ጊዜ ያለችግር እንዲገዛና በኢትዮጵያ ባለቤትነት እንዲያዝ ማድረግ ችሎ ነበር ይባላል። ከኢትዮጵያም እየሩሳሌምን ለማየትና ለመሳለም እየሄዱ የሚቀመጡት ምእመናት ቁጥር እየበዛ ስለሄደ ቀድሞ የሮማውያንን አይነት ክርስትና ይከተሉ የነበሩትን ወገኖች አያስለቀቁ የእስክንድርያውን አይነት ክርስትና ለሚከተሉት ለእነዚሁ ኢትዮጵያውያን እንደሰጡዋቸው ይነገራል።

አፄ ገብረመስቀልም በዘመኑ ወደ እየሩሳሌም መሄድ ቢፈልግም በንጉስነቱ ምክንያት ሳይችል ስለቀረ ገና በወጣትነቱ የመነከሰውን አባ ሙሴ የተባለውን ልጁን ወደ እየሩሳሌም ልኮት የአባቱ የአፄ ገብረመስቀል ወኪል ሆኖ ዘመኑን ሁሉ የክርስቶስ መቃብር ባለበት በጎለጎታና በቀራኒዮ አሳለፈ ይባላል።



## ምዕራፍ ፴፫
## የእስልምና መስፋፋት

በፊት የነበሩ ሐይማኖቶች በስፋት እንዳየነው ገሚሱ የአይሁድ ኦሪት ህግ፣ ሌላው ክርስትና፣ የቀረው በጣኦታት ላይ የተመሰረተ ሃይማኖትን ነበር የሚከተለው።
መላው አውሮፓንና አንዳንድ የእስያና የሰሜን አፍሪካ አገራትን በአንድ ጠቅልሎ በስሩ ያስተዳድር የነበረው የቆስጠንጥንያ (የሮም) መንግስት ደግሞ በግዛቱ ስር ባሉ አገሮች ዘንድ ክርስትናን ለማስፋፋት ሞክሮ የነበረ ሲሆን በጥቂቱ ተሳክቶለት ነበር።

ሆኖም ብቸኛው በሮም ያልተገዛው የፋርስ መንግስት ቀደም ሲል እነ አፄ ካሌብ ያስገበሩትን የዓረብ አገር አክሱማውያንን ከየመን አባሮ በፋርስ ስር በማድረግና ከአይሁዶች ጋር በመተባበር እንዲገብሩለት ከማድረጉም በላይ ቤተክርስቲያኖቻቸውን እያፈረሰ የጣኦታት ቤተ መቅደስ ገንብቶበት ቆይቷል። በዚህም ብዙዎችን ወደ ጣኦት አምልኮ እንዲዛወሩ አድርጓል።

አሁን ግን ሁኔታው የተለየ መልክ እየያዘ ሔዶ በአለም አቀፍ ደረጃ አንድ ራሱን የቻለ ለውጥ እንዲከሰት ሆነ ። ይህም ለውጥ የእስልምና ሀይማኖት መምጣት ነበር።

ነብዩ መሐመድ /ሰ.ዐ.ወ/ የእስልምናን ሐይማኖት መስርተው በቅዱስ ቁርዓን በዝርዝር የተገለፈውን የፆም፣ የኑሮ ህግና ስርዓት አፅንተው በመላው የዓረብ አገር ላይ የመንፈሳዊውንና የስጋዊውን አስተዳደር አደላድለው ያዙ።

ለጎረቤታቸው መንግስታትም የእስልምናን ሐይማኖት እንዲቀበሉ መፃፃፍ ጀመሩ። በዚህ ጊዜ በዓለም ያሉ የታወቁ መንግስታት ህንድ፣ ቻይና፣ ሞስኮ፣ ጃፓንና ሌሎችን፣ ማለትም ምዕራብ አውሮፓን ወደ ጎን አድርገን በፖለቲካና በሐይማኖት፣ እንዲሁም በዘር ይገናኙና ይቀራረቡ የነበሩትንና በዓረብ አገራት አካባቢ የሚገኙት ታላላቅ መንግስታት ሁሉ ከነብዩ መሐመድ መልዕክቱ ደርሷቸዋል። ሌሎች እጅግ የታወቁና የገነኑ ታዋቂ መንግስታት የቆስጠንጥንያ (ምስራቃዊ ሮም) ፋርስና አክሱምም የመልዕክቱ ተካፋዮች ነበሩ።

ነገስታቶቹም በቆስጠንጥንያ ሔራቅሊዮስ፣ በፋርስ ኮስሮዊፓርዊስ፣ በኢትዮጵያ አርማህ 2ኛ ወይም ግርማ አስፈር ነበሩ። (አፅሃም ይሉታል አንዳንዶቹ) ነብዩ መሐመድ ለእነዚህ ሶስት ታላላቅ መንግስታት እስልምናን እንዲቀበሉ ደብዳቤ ፅፈውላቸዋል። ለአክሱሙ ንጉስ የፃፉት ደብዳቤ አልተገኘም። ነገር ግን ይህ ደብዳቤ ብቻ አንጅ ያልተገኘው ወዳጃዊ

ግንኙነታቸውን በደንብ የሚያሳይ መረጃ ሞልቷል። ይህንን በቀጣዩ ምዕራፍ ስለምናገኘው አሁን በዚህ ምዕራፍ

ከወቅቱ ከቆስጠንጥንያው ንጉሰነገስት ዜና መዋዕል ላይ የሚገኘውንና ነብዩ መሐመድ ለሄራቅልዮስ የፃፉለትን ደብዳቤ የአማርኛ ትርጉም እንየው።

"ከሐሜት ከአምላክ መልዕክተኛ ለሄራቅልዮስ ለሮማውያን ንጉሰነገስት። ቅንን መንገድ ለሚከተል ሁሉ ሰላም ይሁንለት። ወደ ሙስሊምነት እንድትመጣ እጠራሃለሁ። ሙስሊም የሆንክ እንደሆነ ደህንነትን ታገኛለህ። ወደ ቀናይቱ መንገድ ብትመጣ አምላክ በብዙ ይሸልምሃል። ወደኔ ሐይማኖት መምጣት እምቢ ስትል በምታስተዳድረው ህዝብ ላይ በሚደርሰው ክፉ ነገር ሀላፊ ትሆናለህ።››

ማህተም... ማሆሜት...

የአምላክ መልዕክተኛ" ይላል።

ነብዩ መሐመድ ወደ ሌሎቹም ወደ ክርስቲያኖችም ወደ አረማውያንም ነገስታት መልዕክት ሲልኩ ገሚሱ በክብር እየተቀበለ መልዕክተኞቹን ሲያስተናግድ፤ ሌላው ተቃራኒ ተግባር ሲፈፅም ሃደቱ ቀጠለ። ነብዩም አሉታዊውንም አዎንታዊውንም ምላሽ እንደየአመጣጡ ሲቀበሉ ቆዩ።

በመጨረሻም የእስልምናን ሃይማኖት በመሰረቱ በ11ኛ አመታቸው እ.ኤ.አ በ632 ዓ.ም በ62 አመታቸው ከዚህ አለም በሞት ሲለዩ በታላቅ ሃዘንና በታላቅ ስርዓተ ቀብር በመዲና መቅደስ እንዲያርፉ ተደረገ።

እርሳቸው ባረፉ በ2ኛው አመት አቡበከር የተባሉት ተከታያቸው በመላእክት አማካይነት የወረደውን ቅዱስ ቁርዓንን በ114 ምዕራፍ ከፍለውና በደንብ አፅፈው የእስልምና ተከታዮች ሁሉ እንዲገለገሉበት ተደረገ።

ካየነው መንፈሳዊና ታሪካዊ ክንውን በኋላ እስልምና በጊዜ ሂደትም ሆነ በወቅቱ እየተስፋፋ ሲቀጥል ችሏል። እስልምናን ተከትሰው የተፈጠሩና ከአገራችን ጋር የተያያዙትን ታሪኮችም በቀጣዩ ምእራፍ ከንጉስ አርማህ ታሪክ ጋር የምናገኛቸው ይሆናሉ።



## ምዕራፍ፴፩
## የንጉስ አርማህ 2ኛ ዘመነ መንግስት
## ከ623-638 ዓ.ም

ነብዩ መሐመድ በነበሩበት ዘመን የአክሱም /የኢትዮጵያ/ ንጉሰነገስት የነበረው ንጉስ አርማህ 2ኛ /ገርማ አስፈረ/ የተባለውና በአክሱም የነገስታት ዝርዝር ውስጥ በተራ ቁጥር 77 ላይ የተፃፈው ሲሆን ኢትዮጵያን ለ15 አመታት አስተዳድሯል።

ምንም እንኳን አንዳንድ ፀሃፍት አርማህ 1ኛ፣ አፅሃም፣.... ወዘተ እያሉ ቢገልፁትም ነብዩ መሐመድ ከነበሩበት ዘመን ጋር ተጣጥሞ የሚሔደው ግን ንጉስ አርማህ 2ኛ የገዛበት ዘመን ነው። ተደጋግሞ እደተገለፀውም የአንድ ንጉሰነገስት ስም አንድ ብቻ ስላልሆነ ለውዝግቡ በር ሊከፍት እንደሚችል አንባቢያን ሊረዱት ይችላሉ።

እናም ንጉስ አርማህ 2ኛ በኢትዮጵያ በነገሰበት ዘመን ነብዩ መሐመድ ነብይ ከሆኑ ከ5 አመት በኋላ ወደ መዲና ሸሽተው በድጋሚ ወደ መካ ከመመለሳቸው በፊት ሁኔታው አስጊ ስለነበር ነብዩ ቤተሰቦቻቸውንና ማለትም የቅርብ ዘመዶቻቸውን በመጀመሪያ 16 ወንዶችንና 4 ሴቶችን ወደ ሐቀኛው ንጉስ ወደ አክሱም ሂዱ ብለው እንደላኳቸውና የአክሱሙ ንጉስ በስርዓት ተቀብሎ እንዳስጠጋቸው፤ ከዚያም ሁኔታው የተረጋጋ መስሏቸው ተመልሰው ወደ አገራቸው ሲሄዱ ሁኔታው ያው በመሆኑ በድጋሚ ተመልሰው ወደ አክሱም መጥተዋል።

ለሁለተኛ ጊዜ ሲመጡም ሌሎች ተጨማሪ ወገኖች ታክለው በድምሩ 90 የሚሆኑ 13 ሴቶችና 77 ወንዶች ወደ አክሱም መጥተው ተጠግተዋል።

ነብዩ ወደዚች አገር ሲልኳቸውም፦ ‹‹ወደ ሐበሻ መሬት ሸሹ። በዚያ ፍርዱ ቅን የሆነ ህዝቡን በሰላም የሚገዛ ንጉስ አለ። ኢትዮጵያ የእውነት አገር ናት። ንጉሷም መልካም ሰው ነው። በሱ ዘንድ ማንም ሰው አይበደልምና የአላህ ፈቃድ ሆኖ መከላከያ ሃይል እስክናገኝ ድረስ ወደዚያ ሔዳችሁ ጊዜ ብታሳልፉ መልካም ነውና የዕድቅ አገር ወደ ሆነችው ሒዱ›› በማለት ነበር የላኳቸው።

ንጉስ አርማህም ተቀብሎ እንደፍላጎታቸው አስቀመጣቸው። በዚህ ጊዜም የነብዩ መሐመድ ተቃዋሚ የሆኑ የአረብ ጎሸሮዎች ለንጉስ አርማህ ስደተኞችን አሳልፎ እንዲሰጣቸው

/እንዲመልሳቸው/ ከብዙ ገፀ በረከት ጋር፤ በኢትዮጵያ እጅግ የሚፈለጉ እቃዎችን ካከተተ ስጦታ ጋር አድርገው ደብዳቤ አስይዘው መልዕክት ላኩበት።

የንጉስ አርማህ ምላሽ ግን ቁርጥ ያለ ነበር። ‹‹የወርቅ ተራራ ብትሰጡኝ እንኳን እነዚህን እንዳድናቸው የተማፀኑኝን ሰዎች አሳልፌ አልሰጥም›› የሚል

ሆነ ምላሹ። ይህም በዚህ በሰለጠነው ዘመን እንደ ልዩ ስልጣኔ የሚቆጠረውን የአሁኑን የየአገራት ዘመናዊ ጥገኝነት መስጠትን በዚያ ዘመን ንጉስ አርማህ መተግበሩ ስልጡን፣ እንዲሁም ለቃሉ ታማኝ መሆኑን በግልፅ ያሳያል።

እነዚህ እንግዶችም በደስታ ኖሩ። ነብዩ መሐመድ በድል አድራጊነት /በእርቅ/ ወደ መካ ገቡ፡ በመጨረሻም እንግዶቹን የተለያዩ ስጦታዎችን አበርክቶላቸው በሰላም ወደ አገራቸው ሸኛቸው። አገራቸው ደርሰውም የተደረገላቸውን እንክብካቤ ለወገኖቻቸው ገለፁ።

በንጉሱ ተግባር እጅግ ደስ የተሰኙት ነብዩ መሐመድም ሐበሻንና የሐበሻን ንጉስ በቅዱስ ቁርዓን ሳይቀር በመልካም እያነሱ «ሃበሻን አትንኩ» የሚል ቃል ሳይቀር አፅፈዋል።

እንግዲህ ከአክሱም ነገስታት ውስጥ አንዱ የሆነው ንጉስ አርማህ በዘመኑ ይህን ተግባር መፈፀሙ ሲታወቅ፣ የፍቅርና የስምምነት፣ ብሎም የመተማመንና የመቻቻልን ጥንታዊ ባህል የሚያሳየው በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የሆነው መስጊድ /አል ነጃሺ መስጊድ/ በጥንታዊቷ የኢትዮጵያ መናገሻ በአክሱም መገኘቱ ደግሞ የአክሱሙ ንጉስና የነብዩ መሀመድና የተከታዮቻቸውን ወዳጅነት በደንብ የሚያረጋግጥ ሆኖ ይገኛል።

ከእስልምና መምጣት በኋላ የዓረብ አገራትንና ህዝቦችን ሁሉ በመልዕክትም በስብከትም በሃይልም አንድ ሃይማኖት ያለው በአንድ መንግስት ስር የሚተዳደር አድርጎ ለማቋቋም ብዙ ጊዜ ቢፈጅም ስኬታማ እየሆነ ሄዷል።

ነብዩ በመጨረሻ የሕይወት ዘመናቸው በቆስጠንጥንያ ግዛት ስር ወደነበረቸው ሶርያ ልከውት የነበረው ሰራዊት ሳይሳካላቸው ስለቀረና ስለተመለሱ ከእርሳቸው በኋላ በ632 እ.ኤ.አ አቡበክር የተባለው የአይሻ አባት «ከሊፋ» የሚል የማዕረግ ስም ተሰጥቶት ነበረ። ከሊፋ ማለት እንደራሴ ወይም ተከታይ ማለት ሲሆን፣ እንደራሴነቱም ለነብዩ መሐመድ ነው። «ረሱለላህ የአምላክ መልእክተኛ» የሚለው ስያሜ ግን ለነብዩ ብቻ እንዲሆን ተወስኗል። በተጨማሪም ከሊፋው «አሚረል ሙእሚኒን» ወይም የአማኞች መስፍን የሚባል ተጨማሪ ስም አለው።

ስለዚህ አቡበክር በዓረብ አገር የነበሩትን ሽፍቶች ሁሉ ደምስሶ ሲጨርስ ያኔ ሳይሳካ የቀረውን የሶርያን አገር ለማስገበር ተነዘ። ዘመቻውን ዳር ሳያደርስ ስለሞተም በ634 ኡመር የሚባለው የነብዩ ታማኝና ተከታይ የነበረው ከሊፋ ኡመር ተብሎ ነገሰ። በኡመር ዘመነመንግስት ሙስሊሞች በጣም እየበዙና እየተፈሩ ሄዱ። የጦር አለቆቻቸውም ሃያላን ሆኑ። አረቦች ሲባልም ቀድሞ የአገሩና የህዝቦች መጠሪያ (የመካከለኛው ምስራቅ) ብቻ የነበረ ሲሆን፣ ከዚህ ታሪክ በኋላ ግን የሐይማኖቱን ተከታዮችም መወከል ጀመረ። ኡመርም የጦር ሰራዊቱን እየላከ ከቆስጠንጥንያ መንግስት ጋር እየተዋጋ እያሸነፈ ሶርያን፣ ባቢሎንን፣ እየሩሳሌምን፣ ፋርስን ሲይዝ፣



በተጨማሪም ግብፅንና ሊቢያን ያዘና የዓረብን ግዛት ትልቅ የቄሳር አይነት ግዛት አደረገው።

የግብፅን አገርና ታላቋን የእስክንድሪያ ከተማ የያዘው የጦር አለቃ አመርበዲን ኤል አህሳ ይባላል። የያዙትን አገር ነዋሪ ህዝብም ወደ እስልምና እየመለሱት ቀጠሉ።ከዚያም የዓረቦች ንጉስ ከሊፋ ዑመር ከሞተ በኋላ በ644 ዓ.ም ላይ ከሊፋ ኡስማን፣ ከኡስማን በኋላ በ661 ዓ.ም ከሊፋ ዓሊ፣ ከዓሊ ቀጥሎ በ680 ዓ.ም ከሊፋ ሙአዊያህ ነገሰ። ይህ ሰው የሶሪያ ሀገረ ገዢ ሆኖ ተሹሞ ስለነበር አሁን ከሊፋ ተብሎ ሲነግስ እስከ አሁን ዋና የአረቦች ከተማ የነበረችውን ኤል መዲናን አስቀርቶ ደማስቆን ዋና የአረቦች ከተማ አደረጋት። በኋላ ደግሞ ከሊፋ ኤል መንሱር የተባለው በ762 ዓ.ም ላይ ወደ ባግዳድ (ሞሶፖታሚያ) አዛወረው።

እነዚህ ሁሉ የአረብ መሪዎች ከነብዩ በኋላ እየተከታተሉ በመካከለኛው ምስራቅና በሰሜን አፍሪካ ያለውን አብዛኛውን የቆስጠንጥንያ ግዛት ሁሉ በውጊያ ይዘው ሲጨርሱ፣ ከዚያም ወደ አውሮፓ ደቡብ ተሻግረው የኢጣሊያንና የፈረንሳይን ደቡባዊ ክፍል፣ እንዲሁም ስፔንን በሙሉ ይዘው ያስተዳድሩ ጀመር። በያዙት አገር ሁሉ በክርስትና ፋንታ እስልምናን እያስተማሩ፣ በቤተክርስቲያን ፋንታ መስጊድ እየተከሉ ቀጠሉ።

በነብዩ መሐመድ ዘመን አክብረው ትተውት የነበረውን አገር ሁሉ አሁን ከእርሳቸው በኋላ ሃያል ሲሆኑ አገር መያዝ፣ እስልምናን ማስፋፋት፣ የዓረብኛን ቋንቋና ፅሁፍም በያዙት አገር በሰሜን አፍሪካና በመካከለኛው ምስራቅ እያስፋፉ የየአገሩ ተወላጅ ቋንቋና ፅሁፍ እየከሰመ

ሄደ። በዚህ መሰረት በግብፅ አገር ከግሪኮች ጀምሮ ሰልጥኖ የነበረው የኮፕት ፅሁፍ ከክርስትና ሃይማኖት ጋር ደከመ። በአውሮፓም ሻርል ማርተል ተዋግቶ ባይመልሳቸው የላቲኑ ፅሁፍ ተመሳሳይ እጣ ይገጥመው እንደነበር የብዙዎች ግምት ነው።

ባጠቃላይ ሁኔታው ይህን ሲመስል የእስልምና መስፋፋት ከአክሱም /ከኢትዮጵያ/ ጋር በተያያዘ የተፈጠረው ነገርም የሚከተለውን ይመስላል።

የአክሱም መንግስት ቀደም ሲል እንዳየነው የዓረብን አገር ጭምር እየገዛ እያስገበረ ሃይለኛ የክርስቲያን መንግስት ሆኖ ነበር። በነአብርሃ፣በካሌብና በተከታዮች ጊዜ መርከቦቻቸው በኤርትራ ባህር ላይ እየተንሳፈፉ በጦርነት ስአት ወታደር፣ በሰላም ጊዜ ሸቀጥ እያመላለሱ የአክሱም መንግስት በሌሎች ነገሮችና በንግድ የከበረ ትልቅ መንግስት የነበረና የባህር ወደቦች እንምፅዋ፣ እነአዶሊስ፣ እነዳህላክ በዘመናቸው የታወቁ ነበሩ።

በተጨማሪም የክርስቲያን መንግስት እንደመሆኑ መጠን በሌሎች አገራት ላሉት ክርስቲያኖች ሁሉ መመኪያቸው ነበር። ከእስክንድሪያ፣ ከሶርያ፣ ከእየሩሳሌምም በዓረብ ወረራ ምክንያትም ሆነ ከዚያ በፊት በነበረው ጊዜ በርካታ ምዕመናንና ካህናት ወደ አክሱም ነበር እየመጡ የሚጠጉት።

አሁን ደግሞ ተከታታይ ክሊፋዎች መካከለኛውን ምስራቅና ሰሜን አፍሪካን በያዙበት ሰአት የአክሱም ግዛት በነበረው በቀይ ባህር እንዲሁም በወደቦቹ በምፅዋና በአዱሊስ፤ በደሴቶቹ በዳህላክ ላይ በመስፈራቸው ትልቅ ፀብ ተፈጥሮ በየእለቱ ሲጋጩና አንዱ ሲሸነፍና ሲሸሽ ሌላው እንደገና እየበረታ፤ ሲይዙ፣ ሲያስመልሱ ቆይተው በመጨረሻ የዓረቦች ሃይል በርትቶ የሃበሾቹ ሃይል እየደከመ ሲሄድ በ6ኛው መቶ ዓ.ም ይዋጉበት የነበረውን የኤርትራን ባህርና ወደብ በ7ኛውና በ8ኛው መቶ ዓ.ም ላይ ሙሉ ለሙሉ ዓረቦች አሸንፈው ያዙና ያስተዳድሩት ጀመር።


የአክሱም መንግስትም የባህር በሩ ሲያዝበት ንግዱም፤ ሀብቱም ተዘጋና ከዚያ ጊዜ በኋላ ደካማ መንግስት ሆነ። በምዕራብ በኩልም የበጃ ዘሮች እየተነሱ የብሌማይ፣ የኖባ፣ ነገዶች የየራሳቸውን መንግስት ማቋቋም ጀመሩ። ከሁሉም በላይ የአክሱምን መንግስት የጎዳው የወደቦቹ መያዝ ነው። የቀድሞዋ ኑብያ የዛሬዋ ሱዳንም ከጥቂት መከላከል በኋላ ልክ እንደ ግብፅ ሁሉ በአረቦች ስር ሆና ፊደልና ቋንቋዋ ዓረብኛ ሊሆን ቻለ። ይሁን እንጂ ዓረቦቹ ወደቦቹን ከያዙ በኋላ ወደ መሃል ኢትዮጵያ ድረስ ገብተው በሌላው አገር እንዳደረጉት ኢትዮጵያን ለመያዝ አልፈለጉም።

እናም የአክሱም መንግስት የባህር በሮቹን ተቀምቶ ንግዱንና ዘላቂ ሃብቱን አጥቶ ከወዳጅ ከቆስጠንጥንያው የክርስቲያን መንግስት ጋር ግንኙነቱን አቋርጦ በዚያው በአክሱምና በመካከለኛው ኢትዮጵያ ተወስኖ የደከመ መንግስቱን ሲያስተዳድር እንደቆየ በመጨረሻ አንዳንድ

የአገር ውስጥ ነገዶችና በአክሱም መንግስት ስር የነበሩ ተገዥዎች መንግስቱን ለመገልበጥ መደራጀትና መንቀሳቀስ ጀመሩ።

ከውጭ ጠላት ሲያጠቃ ደግሞ በዘርና በሃይማኖት አንድነትና ወንድማማችነት በጥልቅ የማይለማውና አስተዳደርና ስልጣን እኩል ሳይካፈል እየተገዛ ብቻ የኖረ ህዝብ ምቹ አጋጣሚ ባገኘ ጊዜ የተገዥነቱን ቀም ለመበቀል መነሳቱ የማይቀር ነውና የዓረቦች ሃይል ዙሪያውን ባጠቃበት ጊዜ የሰሜን ፈላሾች በዮዲት ጉዲት፣ እንደዚሁም የአገው ዘሮች በየጉዳዮች መሪዎቻቸው አማካይነት በአክሱም መንግስት ላይ ሊነሱ ቻሉ።





## ምዕራፍ ፴፰

## የዮዲት ጉዲት ዘመነ መንግስት

## ከ842-882 ዓ.ም

ከአፄ ገብረመስቀል በኂላ እስከ ዮዲት መነሳት ድረስ በነበረው 313 አመት ውስጥ በመሐል ከነብዩ መሐመድ ጋር ስሙ የተነሳው የአክሱም ንጉስ የእርማህ 2ኛ መጠነኛ ታሪክ ሲታወቅ፤ ከእርሱ በኂላም በአክሱም ብዙ ነገስታት ተከታትለው መንገሳቸው ግልፅ ሲሆን፤ በዘመናቸው የሰሩትን ስራ የሚገልፅ ፅሁፍ ግን ተሟልቶ አይገኝም። ይህንንም ጊዜ የኢትዮጵያን ታሪክ ሲፅፉ የነበሩት ሁሉ የጨለማ ጊዜ (ዳርክ ኤጅ) ይሉታል።

ሲፅፉ የነበሩት ሁሉ የጨለማ ጊዜ (ዳርክ ኤጅ) ይሉታል።
ነገር ግን ከአክሱም መንግስት ጋር ግንኙነት ያላቸው የቆስጠንጥንያና የዓረብ አገር ፀሃፊዎች አንዳንድ ጊዜ የየራሳቸውን ታሪክ ከመፃፍ አልፈው የአክሱምን መንግስት ታሪክ ብልጭ እያደረጉ ይፅፉታል። ከነዚህ የቅርብ ጊዜ ፀሃፊዎች እነ ሩዶልፍ፤ ጀምስ ብሩስ፤ ኤድዋርድ ግላዳር እና ሌሎችም የሚገኙበት ሲሆን ከአፄ ገብረመስቀል ወዲህ ታሪኩን ያቋረጠው ታሪክ ነገስት ደግሞ አልፎ /ዘሎ/ የዮዲትን መነሳት ይፅፋል።

ሲወርድ ሲዋረድ በመጣው በታሪክ ነገስቱና እርሱንም መሰረት እያደረጉና እያሟሉ የውጭዎቹም የአገራችንም ፀሃፊዎች እነ ብላቴን ጌታ ህሩይ፤ እነ አለቃ ታየና ሌሎች ስለ ዮዲት ወይም ስለ አስቴር ጥቂት ብለዋል።

በቀዳማዊ ምኒልክ ዘመን ብዙ የእስራኤል ወገኖች ጎልማሶችና ሽማግሌዎች እንዲሁም ካህናቶች ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ህዝቡን ህገ ኦሪት እያስተማሩ እንደኖሩና ከዚያ ዘመን በኂላም በነበሩት ጊዜያቶች በየወቅቱ በተለያዩ ምክንያቶች በርካታ አይሁዳውያን ከኢየሩሳሌም ወደ አገራችን መግባታቸውን ቀደም ሲል ባየናቸው ፅሁፎች ተረድተናል።

እነዚህ ህዝቦችም ብዙዎች ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር እየተጋቡ እየተዋለዱና እየተራቡ ብዙ ዘመን ኖረዋል። በአብርሃና በአፅባሐ ጊዜ ደግሞ ፍሬምናጦስ «የማርቆስ ወንበር» ከተሰኘው ከእስክንድርያ ክርስትናን ወደ አክሱም ቤተመንግስት ካመጣ በኂላ የአክሱምም ህዝብ ክርስትናን ተቀብሎ ሲኖር እነዚያ ኦሪት ህግን ሲከተሉ የኖሩት አይሁዳዊያን ደግሞ ክርስትናን እንቀበልም ብለው በዚያው በተድሞው ኦሪት ህግ ብቻ ፀንተው ተቀመጡ።

በዚህም የተነሳ የመንግስት ሃይማኖት ሆኖ የታወጀው የክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች የበላይነት ይዘውና ቁጥራቸውም እጅግ በዝቶ ነበርና የኦሪትን ተከታዮች መጨቆን ማንገላታትና መበዝበዝ ጀመሩ። ጭቆናውን መቋቋም ያቃታቸው የህገ ኦሪት አማኞች በዘመነ አክሱም በመጀመሪያ በአክሱምና በዙሪያው መሰደድ ግድ ሆነባቸው። ከትትሎ ሲበረታባቸውም በጣም እየራቁ በመሸሽ በጎንደር አካባቢ ባሉት በሰሜንና በወገራ፤



በወልቃይት፤ በላስታና በአካባቢው ሰፈሩ። ከእነዚህ ህዝቦች ውስጥም ሙሉ ለሙሉ ዘራቸው አይሁድ የሆኑት ሰፊውን ቁጥር ይያዙ እንጅ፤ ከመካከላቸው የሃበሻና የአይሁድ ድቅል የሆኑ ህዝቦች ነበሩ። ይህንኑ ለመለየትም ፈላሻ እና ሙራ ፈላሽ የሚል መጠሪያ አላቸው። ሙራ ፈላሻ ከሚባሉት ውስጥም ሆነ ፈላሻ ከሆኑት ዘሮች ውስጥም ጥቂት ክርስቲያን አይሁዶች ነበሩ።

እነዚህ ህዝቦች ህገ ኦሪትን የሙጥኝ ብለው የራሳቸውን ባህል እንደያዙ በሽሽት ስለተራወጡ ፈላሻ የሚል ስም ተሰጥቷቸው ኑራቸውን በአጥቂዎች የመልሶ ማጥቃት ሳይሆን በተቻላቸው አቅም በመከላከል ላይ የተመሰረተ አድርገው መግፋት ቀጠሉ።

የመጀመሪያ ስያሜያቸው ፈላሲ በመባል የሚታወቅ ሲሆን፤ ትርጓሜውም አገሩን ትቶ ሄያጅ ማለት ስለሆነ፤ እነዚህም ወደ አክሱም ሰሜንና ወደ ወገራ ስለተሰደዱ ፈላሲያን ወይም ፈላሾች ተብለው ተሰይመዋል። እንጂ ከሌላ አገር በመምጣቸው አይደለም ፈላሻ የተሰኙት። ይህ በመጨረሻ የተሰደዱበት የሰሜን አገር ተራራማ ስለሆነ በዚህ ስፍራ ሆነው በተፈጥሮ ምሽግ እየተጠቀሙ ሲወጋቸው የመጣውን ሁሉ እየተከላከሉ በሚመልሱበት ጊዜ ከጊዜ ብዛት ቁጥራቸው እየበዛ ሃይላቸው እየበረታ ሄደ።

ከዚያም በአንድነት መክረው በበላይነት ሊመራቸው የሚችልና ሊያስተባብራቸው፤ እንዲሁም ሊገዛቸው የሚገባው አንድ ሰው ከወገናቸው ለመሾም ተስማሙ።

በዚህም መሰረት ከመካከላቸው ጠንካራና ጥሩ ግንዛቤ ያለው እንዲሁም በእውቀቱ የበሰለ ነው ያሉትን ጌድዮን የሚባልን ሰው ተስማምተው በንጉስነት ሾሙት። (ይህ ስም የፈላሻ ባለስልጣኖች የማዕረግ ስም ሆኖ ቀጥሎ ነበር።) የፈላሾች ንጉስ የሆነው ጌድዮንም አንዲት እጅግ የተዋበችና መልኳ ያማረ ሴት ልጅ ነበረችው። እሷም በኋላ ላይ ዮዲት ተብላ የተጠራችው ስትሆን፤ ዋና መጠሪያ ስሟ ግን አስቴር የሚለው ነበር። ይችን ወጣትና ቆንጆ የሆነችውን ዮዲትንም ዘርዓ ያዕቆብ የሚባል የቡግና ገዥ (የላስታ ገዥ) ሃይማኖቱ ክርስቲያን

የሆነ ፈላሻነቷን ሳይመረምር የመልኳን ውበትና የቁመናዋን ማማር ብቻ አይቶ ለትዳር ተመኛትና በጋብቻ ተሳስረው በትዳር ለመኖር ቻሉ።

ዮዲት በውበቷና በፍቅሯ እለት እለት እየማረከችው ክርስቲያኑን የላስታ ገዥ አባበላና አሳምና ፈላሻነቷን በግልፅ ከመናገሯም በላይ ያባስ ብላ በእርሷ ሃይማኖት በኦሪት ህግ ወይም በይሁዲ ሃይማኖት ስርዓትና ወግ ካገባችው በኂላ ዘርዓ ያዕቆብ የነበረውን ስሙን ሰለሞን በሚል ስም እንዲለውጥ አደረገችው። እሱም ተስማማ።

በዚያ ዘመን በአክሱም ዙፋን ላይ የተቀመጠው የኢትዮጵያ ንጉስነገስት «ደግናዥን» የተባለው ነበር። ከዚያም ግዳዥን ለ1 አመት ነግሶ በዚያው ወቅት ስለሞተ «አንበሳ ውድም» የሚባለው ህፃን ልጁ በአባቱ ተተክቶ ንግስናውን ያዘ። የአክሱም መንግስትም በዚህ ጊዜ በእጅጉ ተዳክሞ

ነበር። ህፃኑ ንጉስ አንበሳውድም በጣም ህፃን ከመሆኑ የተነሳ ኢትዮጵያን ለማስተዳደር አለመቻሉን ዮዲት ባውቀች ጊዜ በሰሜንና በላስታ አውራጃ የሚኖሩትን ፈላሾች ወገኖቿን ይዛ ወደ አክሱም ገሰገሰች።

ዮዲት ከክርስቲያኑ የላስታ ገዥ ከተጋባች በኋላ በሱዋ ሃሳብና ቁጥጥር ስር በማዋሏ የተለያዩ ተግባሮችን ማለትም ፈላሾች እንደልብ እንዲዘዋወሩና ሲያጠቋቸው የሚመጡትን ከመከላከል ወደ ማጥቃት እንዲሸጋገሩና ለከፊል ነፃነት መሰረት ጣለችላቸው። በይፋ እንዲዋጉም በር ከፍታላቸዋለች። በዚህም መሰረት ፈላሾች ከዮዲት ጋብቻ በኋላ በባሏ ግዛት በላስታና በአካባቢው ብዙ ክርስቲያኖች ፈላሾችን እንዲፈሩ አድርጋለች።

አሁንም ወገኖቿን አስከትላ ወደ ህፃኑ ንጉስ ወደ አክሱም ስትገሰግስ የአክሱም መኳንንትና ሹማምንት ብዙም መከላከል ሳያደርጉ ህፃኑን ንጉሳቸውን እንደያዙ ዮዲትን ፈርተው ከአክሱም ወደ ሸዋ ሸሹ።

በዚህ ጊዜ በ842 ዓ.ም በአክሱም ነገሰችና፤ በአክሱምና በዙሪያው ያሉትን ዛውልቶች እያፈራረሰች፣ አብያተ ክርስቲያናቱን፣ የፅዮን ቤተክርስቲያንን ጨምሮ በአክሱምና በአካባቢው ያሉትን ሁሉ እያቃጠለች በአጠቃላይ የክርስትናን መገለጫዎች ሁሉ አወደመቻቸው ያባላል። ከዚህም አልፋ በዚያ ዘመን ለማድ መሰረት የውስጥ ጦርነት እንዳይቀሰቅሱ ተብሎና ተጠብቀው እንዲኖሩ ታስቦ በደብረዳሞ ተራራ ላይ ቡተጠናከሩ ጠባቂዎች ይጠበቁ የነበሩትን ከነገስታት የሚወለዱትንና የመሳፍንት ወገን /ኒጋሲያንን/ ሁሉ ልጆችንም፣ አዋቂዎችንም

በጭካኔ አሳረደቻቸው። በየገዳማቱና በየአድባራቱ ተጠብቀው ይቆዩ የነበሩትን ታሪካዊ ሀነዶች ሁሉ በእሳት አመድ አደረገቻቸው።

በዚህና በዚህ መሠል ጭካኔዋ መሰረትም ዮዲት የተባለው ስሟ ተለውጦ ጉዲት ስትባል አስቴር የሚለው ስሟ ደግሞ እሳቶ ተባለ። በተለምዶ ስትጠራም ዛሬ ድረስ በምትታወቅበት ዮዲት ጉዲት በሚለው ስሟ ነው።

ወደ ሸዋ ሸሽቶ የመጣው አንበሳውድም ወደ ሸዋ በመጣ ጊዜ የሸዋ ህዝብ በደስታ ተቀበለው። ከህፃንነት ወደ አዋቂነትም ተሻገረ። የሸዋ ህዝብ በደስታ እንደተቀበለው ዮዲት በሰማች ጊዜ ከነገሰች ከብዙ አመት በኋላ ብዙ ሠራዊት ሰብስባ ወደ ሸዋ ላከች።

ወጣቱ አንበሳውድምም የመንገዝን ባላገር ይዞ የዮዲትን ጦር በፅናት ተዋግቶ መለሰው። ከዚህ በኋላ ራሷ ዮዲት የቀረውን ጦሯን ሰብስባ እራሷ እየመራች ወደ ሸዋ ተጓዘች። አንበሳውድም የዮዲትን መምጣት በሠማ ጊዜ ከመንገዝ ወደ ሙራቤቴ በሽሽት መልክ ሄደ።



ዮዲትም እስከመራቤቴ ለመከታተል ሞክራ እያለ፤ የአህያ ፈጅ እና የይባ መንገድ ገደላገደልነቱ ስላስቸገራት በዚህም ላይ አንበሳውድምን በእጅጉ የሚረዳውና የሚያግዘው የሸዋ ህዝብ በደንብ በሚያውቀው አገር ላይ በደፈጣም፣ ፊት ለፊትም እየተዋጋና አደጋ እያደረሰ አስቸገራት። ይህንን ከየአቅጣጫው የሚሠነዘርባትን ጥቃት ለመከላከል ጦሯን ወደተበታተነ አቅጣጫ ማዝመት እንደማያዋጣት ስለተረዳች ሃሳቧን ለውጣ ከሸዋ ወደ አክሱም ወገኖቿን ይዛ የመልስ ጉዞ አደረገች። አክሱምም በሰላም ደረሠች።

ከዚህ ጉዞ በኋላ በአክሱም ተጨማሪ 17 አመታትን ገዝታ በድምሩ ለ40 አመት የአክሱምን ግዛት በበላይነት አስተዳድራ ሞተች። በዚህም መሰረት ከ842 ዓ.ም እስከ 882 ዓ.ም ድረስ ዮዲት ጉዲት የአክሱም ንግስት ነበረች ማለት ነው። በ40 ዓመት የግዛት ዘመኗም በአራት መቶ አመት እንኳን የመልሶ ግንባታ ቢደረግበት የቀድሞ ይዘቱንና ቅርፁን ሙሉ ለሙሉ ሊይዝ የማይችልን ውድመት ፈፅማለች።

የዮዲት ጉዲትን ሞት አንበሳውድም በሠማ ጊዜ ከተከታዮቹ ጋር ከሸዋ ተነስቶ ወደ አክሱም ሔደ።

የትግሬ ህዝብም በደስታ ተቀበለውና በአባቶቹ ዙፋን መልሶ አስቀመጠው። እናም የቀድሞው ንጉስነገስትነቱ እንደፀና በአክሱም ቤተመንግስት ሆኖ ለ20 አመታት ኢትዮጵያን አስተዳደረ። ከ20 አመት የግዛት ዘመኑ በኋላ ንጉስ አንበሳውድም ሲሞትም ልጁ ድልነአድ ነገሰ። ንጉስ ድልነአድም የአክሱም የመጨረሻው ንጉስ ሆነ።

ንጉስ ድልነአድ በአባቱ ተተክቶ የአክሱምን የንጉሰነገስትነት ስልጣን ይዞ ከ902 ዓ.ም እስከ 912 ዓ.ም ለ10 አመት ያህል ኢትዮጵያን ማስተዳደር ቢችልም፤ በዮዲት ጊዜ የተቀሰቀሰው የሠሜንና የላስታ ህዝብ በየጊዜው እየተነሳ በማመፅ አላስገዛ ብሎት ሲያስጨንቀው ነው 10 አመቱን ባልተደላደለ ሁኔታ ያሳለፈው።

መጨረሻም መራ ተክለሃይማኖት የተባለው የድልነአድ የራሱ የጦር አበጋዝ የነበረው የላስታ ተወላጅ ድልነአድን ወጋው። አሁንም ንጉስ ድልነአድ የመከላከል አቅም ስላጣ እንደ አባቱ እንደ አንበሳውድም ከአክሱም ወደ ሸዋ ሸሸ። የመጨረሻው የአክሱም ንጉስም እሱ እንደሆነ ቀረ።

## ምዕራፍ ፴፮
## አክሱምና በአካባቢዋ የሚገኙት ቅርሶች

የአክሱምን አነሳስና ውድቀት እንዲሁም በአክሱም ነገስታት የተፈፀሙ ድርጊቶችንና አጠቃላይ ታሪካዊ ክንውኖችን አይተናል። አሁን ደግሞ የአክሱምን ታሪክ ፊዕመን ወደ ዛግዌ ስርወ መንግስት ከመሸጋገራችን በፊት በአክሱምና በአካባቢው ስለሚገኙት ታሪካዊ ቅርሶች ጥቂት ምልክታ ያስፈልገናል።

አክሱምና አካባቢዋ ከክ.ልደት በፊት 1ሺ. አመት ቀደም ብሎ በንግስተ ሳባና በልጇ በምኒልክ ጊዜ ትታወቅ የነበረ መሆኑንና፤ ከዚያ በኋላ ባለው ጊዜ ናፓታና መርዌ የመንግስት መቀመጫ ሆነው ኖረው፤ ከመርዌ መዳከም በኋላ የመንግስት መቀመጫ ልትሆን መቻሏንም አንብበናል። አክሱም የኢትዮጵያ የመንግስት መቀመጫ /ዋና ከተማ/ ሆና ከክ.ል በኋላ በ2ኛው ክፍለ ዘመን ከመቆርቆሯ በፊትና በኋላም የተለያዩ ታሪካዊ ቅርሶች በተለያዩ ነገስታቶች ተተክለውና ተገንብተው ነበር። ቅ.ል.ክ 500ኛው ላይ የተሠራውና በአሁኑ ሰአት ጣራው ፈርሶ የሚታየው የየሃ ቤተመቅደስም አክሱም በኋለኛው ዘመን በደመቀ ሁኔታ ከመቆርቆሯ በፊትም ቢሆን ለስልጣኔ ደፋ ቀና ትል የነበረች ከተማ መሆኗን አረጋጋጭ ነው ተብሏል።

አክሱማውያን የበለጠ የሚደነቁት የስልጣኔያቸው መገለጫ ተደርገው በተወሰዱላቸው በድንቅ ሃውልቶቻቸው ነው። ከእነዚህ ድንጋይ ጠርበው ካነጿቸው ቤተመንግስቶች፣ መካነ መቃብሮችና ልዩ ልዩ ሃውልቶች ውስጥም በከፍተኛ ደረጃ የሚታወቁና በዩኔስኮ የዓለም ቅርስነት ተመዝግበው የምናገኛቸው የአክሱም ሃውልቶች ዋነኞቹ ናቸው። ለሃውልት ተረባ ምቹ የነበሩ አለታማ ተራራዎችና አስገራሚ ድንጋዮችም በአካባቢው ነበሩ፤ ዛሬም ድረስ አሉ።

አክሱማውያን በዘመናቸው ከበርካታ የዓለም ሃያላን አገራት ጋር ያደርጓቸው ከነበሩ የንግድ ልውውጦች ባሻገርም ድንጋይ በመጥረብ፣ ብረት በማቅለጥና፤ ነሃስ፣ ብርና ወርቅ በማንጠር፣ ገንዘቦችንና ቅርፃ ቅርፆችን በመስራት የታወቁ የእደ ጥበብ ባለሙያዎች እንደነበሩ የአርኪዎሎጂ ጥናቶች ያመለክታሉ።

ለዚህም ነው የአካባቢው ተወላጆች ዛሬ ድረስ ወርቅና ብር በማንጠር ስራዎች ተሰማርተው የምናያቸው። በአክሱም የሸክላ ግንብ፣ ከድንጋይ የተፈለፈለ መቃብር፣ አንድ ወጥ ሃውልት፣ በቀይ በቡናማና በጥቁር ሸክላ የተሰራ ጌጣጌጥ፣ የውብ ግንባታዎች፣ ትላልቅ የድንጋይ ወፍጮዎች፣ ውድ ዋጋ ያላቸው ልዩ ልዩ ጌጣጌጦች በቁፋሮ ተገኝተዋል።

በተጨማሪም አክሱምን ለከተማነት የመረጧት በወቅቱ ለእርሻና ለከብት እርባታ ምቹና ለም የነበረች መሆኗን፣ በአካባቢው ወደ 70 የሚጠጉ የውሃ ምንጮች የነበራትና፤ አየሩ ተስማሚ የነበረ በመሆኑ ሲሆን፤ ዶ/ር



ፊሊፕሰን የተባሉትን ተመራማሪ ጠቅሰው ተክሌ ሃጎስ የተባሉት የአገራችን አርኪዎሎጅስት ጤፍ፣ ገብስ፣ ሁሳ፣ ተልባ፣ ማሽላና የተለያዩ ጥራጥሬዎች ይመረቱ ነበር በማለት ይገልጻሉ።

ለከብት እርባታ ምቹ መሆኗንም በቁፋሮ የተገኙ የከብት፣ የበግ፣ የፍየል አጥንቶች መገኘታቸው እንደ ማስረጃ ተወስዷል። ቀንበር ተሸክመው የተጠመዱ የበሬዎች ምስልም በሸክላ ተቀርፆ ተገኝቷል።

በአክሱምና በአካባቢው ከአዶሊስ የሃውልት ላይ ፅሁፍ ጀምሮ የነጊዛና ሃውልት፣ የነአፄ ካሌብ መቃብርን ጨምሮ በርካታ አነስተኛ፣ መካከለኛና ከፍተኛ ርዝመት ያላቸው ሃውልቶች የነበሩ ሲሆን፤ ብዙዎቹ በዮዲት ጊዜ ያለአንዳች ርህራሄ ወድመዋል። የቀሩት ጥቃቅኖችም በተለያየ ጊዜ የከሰሙ ሲሆን ጥቂቶችን የጣሊያን ፋሽስት እንዳፈራረሳቸው ይነገራል።

በአሁኑ ወቅት ቆመውና መድቀው የሚታዩት ሃውልቶችም በ3ኛውና በ4ኛው ክፍለ ዘመን የተሠሩ ናቸው። አክሱማውያኑ ሐውልቶችን ለመቅረፅ የተጠቀሙበት ድንጋይ ከአክሱም ከተማ 5 ኪ.ሜትር ርቆ ከሚገኘው ጉበ ድራ ከሚባለውና በእሳተ ገሞራ ከተፈጠረው ተራራ ሲሆን፤ ግራናይት የሚባለው ድንጋይ በመሆኑ ለሃውልቱ ስራ ምቹና ጠንካራ ነው። በአካባቢውም የትልልቅ አለቶች ተራራ የሚገኝ ሲሆን ሃውልቶቹ ከአለቱ ላይ ከተቀረፁ በኋላ በብዙ ሰዎች ጉልበትና በዝሆኖች አማካኝነት እንዲሁም የተለያዩ መሰል ጉልበቶችና ዘዴዎችን ተጠቅመው ማጓጓዝና መትከል ችለዋል።


ከእነዚህ ሐውልቶች መካከል አንዱና ትልቁ 33 ሜትር ርዝመትና 515 ቶን ክብደት ያለው ሲሆን ይህ ሐውልት እስካሁን በዓለማችን የሰው ልጅ ሊያቆማቸው ከሞከራቸው አንድ ወጥ የድንጋይ ስራዎች ግዙፍ መሆኑ ተረጋግጧል። ይህም ወይ በዮዲት ጊዜ አሊያም በመጀመሪያው ተከላ ጊዜ ወድቆ እንደቀረ ተገምቷል። ሁለተኛውና ከሮም የተመለሰው 24 ሜትር ርዝመትና 152 ቶን ክብደት ያለው ሐውልት ነው። ሶስተኛው ደግሞ ከተተከለበት ጊዜ ጀምሮ አክሱም ከተማ ውስጥ ቆሞ ዛሬ ድረስ የሚገኘው 21 ሜትር ርዝመት ያለው ሃውልት ሲሆን፤ በነሐሴ 2000 ዓ.ም ኃደኛው ከሮም ተመልሶ መጥቶ አብሮት ሊቆም ችሏል።

ሐውልቶች በተተከሉበት አካባቢ ከስራቸው በባለሙያ ተጠርበው በብረት በተያያዙት ከባለአራት ማእዘን የድንጋይ ግንቦች ስር የመሳፍንቶች መቃብር ይገኛል።

ይህ ሃውልት በዓለም ቅርስነት በዩኔስኮ የቅርስ መዝገብ ላይ በ1972 ዓ.ም ሁፍሯል። ይህ ታላቅ ቅርስ ነው እንግዲህ በኢጣልያ ወረራ ወቅት በሞሶሎኒ ትዕዛዝ ወደ ሮም ተወስዶ የነበረውና በኢህአዴግ ዘመን የተመለሰው።

የአክሱም ስጦታዎች







# ምዕራፍ ፴፯

## የዛግዌ ስርወ መንግስት አመሰራረትና የመስራቹ የንጉስ መራ ተክለሐይማኖት ዘመነ መንግስት ከ 912-925 ዓ.ም

ባለፉት ምዕራፎች በስፋት እንዳየነው የሮማውያን፣ የፋርሳውያንና የአክሱማውያን መንግስታት በመካከለኛው ምስራቅ፣ በአረቢያ፣ በቀይ ባህርና በአባይ ሸለቆ ክልል እርስ በርሳቸው በረጅም የሃይል ሚዛን ትግል ውስጥ ነበሩ። በ7ኛው ምዕተ አመት የእስልምና ሃይማኖት በአረቦች ዘንድ መፈጠርና በመካከለኛው ምስራቅ መስፋፋት የሶስቱን መንግስታት ሃይል አዳክሞታል። ምዕተ ዓመቱ ከመጠናቀቁ በፊት የዓረብና የቱርክ ሙስሊሞች በአረቢያ፣ በመካከለኛው ምስራቅ፣ በግብፅ፣ በሠሜን አፍሪካና፣ በሜዲትራኒያን ባህር አካባቢ ሁሉቱን ጥንታዊ የፋርሳውያንና የሮማውያንን መንግስታት ይዞታ ተክቷል።

የአረቦች ሃይል የማይበገር ሆኖ በክልሉ የፖለቲካ መድረክ ላይ መውጣትና በተለይም በመካከለኛው ምስራቅና በግብፅ የበላይነት መያዝ የአክሱም መንግስት ከመካከለኛው ምስራቅና በሜድትራኒያን ባህር ዙሪያ ከነበረው ከግሪክና ከሮማ ስልጣኔ ጋር የነበረውን የንግድና የባህል ግንኙነት አከስሞታል። ቀይ ባህር፣ መካከለኛው ምስራቅና ግብፅ በአረቦች እጅ መውደቃቸውም በዓለም የንግድ ስርዓትና በአካባቢው ጂኦፖለቲካ ላይ ለተመሠረተው የአክሱማውያን ስልጣኔ መዳከምን ያስከተለ ሆኗል።

በዚህ በአክሱም መዳከም ጊዜም ቀደም ሲል እንዳየነው ከዮዲት ሞት በኋላ ብዙም ያልቆየው የአክሱም ንጉስ ድልነአድ በነገሠ ጊዜ መራ ተክለሐይማኖት የተባለ ሰው የአክሱምን የንጉሰ ነገስት ስልጣን በሃይል በመውሰድ የመንግስቱን መቀመጫም ወደ ላስታ አዛውሮታል። አመሰራረቱም በሚከተለው መልኩ ይገለፃል።

ዛግዌዎች ወይም አገዎች ከኩሽ ዘር የወረዱና የኩሽ ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑ ህዝቦች ናቸው። መኖሪያቸውም በላስታ /በሮሃ/ና በአካባቢው የነበረ ሲሆን፤ ለአክሱሙ መንግስት እየገበሩ በአክሱም መንግስት ስር ሆነው የሚተዳደሩ ህዝቦች ናቸው።

አገዎች ከሶስት ተከፍለው ነገር ግን ቋንቋቸው ስሩ አንድ ሆኖ በየክፍላቸውና በየአገራቸው ጥቂት ጥቂት ልዩነት ይዘው ነበር የሚኖሩት። እነዚህ ህዝቦች በሶስት ተከፍለው በሶስት አገር ስም የሚጠሩ ሲሆን፤ የላስታ አገው፣ የዳሞት አገው፣ የሐልሐል በጎስ አገው /ብሌን/ ተብለው ይከፋፈላሉ። የሁሉም መሠረትና ምንጭ የላስታ አገው ነው።

የላስታ አገዎች በዋግ የሚኖሩ ሲሆን፤ በጥንቱ ጊዜ የያዙትን ቦታ ሳይለቁ አሉ። በዚህም መሰረት የአገው /የዋግ/ ነዋሪዎች ከጥናው የአክሱም

ንጉሰነገስት የማሾምላቸውን ንጉስ አኩበረው በመኖር ከፈላሾች፣ ከገገርዎች ከአጋዚያንና ከሳባውያንም በቋንቋና በባህል አንድነትም ልዩነትም ነበራቸው።

እነዚህ ህዝቦች ደግሞ የአክሱምን መዳከም ካስተዋሉበት ጊዜ ጀምሮ በተለያየ ጊዜ ከተገዥነት ለመላቀቅ እንቅስቃሴ ያደርጉ ነበር። ከፈላሾች ጋርም እየተዋጉ ሲሸፍቱ ቆይተዋል። በዚህ መካከል የአክሱም የመጨረሻ ንጉስ በነበረው በአፄ ድልነአድ ጊዜ የራሱ የድልነአድ የጦር አበጋዝና እንደራሴ የነበረውና የላስታ ተወላጅ የሆነው መራ ተክለሐይማኖት የአፄ ድልነአድን ሴት ልጅ መሶበወርቅ የተባለችውን ይወዳታል። ንጉሱን አግባብቶና እሺንም አሳምኖ ያገባታል። ካገባት በኋላ ግን ይዟት ወደ ላስታ ሸሸ። እዚያም ሄዶ ጦሩን አደራጅቶ ተመልሶ ወደ አክሱም በመምጣት ድልነአድን ወግቶ ድል አደረገው። ተሸናፊው ንጉስም ስልጣኑን መቀማቱን ሲያረጋግጥ እንደ አባቱ ወደ ሸዋ ሸሸ። ወዲያውም መንግስቱን ሙሉ በሙሉ ወስዶ የመንግስት ቦታውን ወደ ላስታ አዛውሮ እራሱ መራ ተክለሐይማኖት ንጉሰነገስት ሆኖ የዛግዌን ስርወ መንግስት መሰረተ።

ንጉሰ ነገስት ለመሆን ደግሞ የግድ በጳጳስ እጅ መቀባት ያስፈልግ ነበርና መራ ተክለሐይማኖት ጳጳስ እንዲቀባቸው ለግብፅ ገዥ አመለከተ። ነገር ግን የተሠጠው ምላሽ "ላንተ ዘውድ ለማይገባው ጳጳስ አንልክም። ሊነግስና ጳጳስ ሊቀባው የሚገባው ከንጉስ ሰሎሞን ዘር የሚወለደው ሸዋ ያለው ነው" የሚል ምላሽ ማግኘቱን ሙሴ ኮንቲሮሲኒ ሲያረጋግጡ፤ በተለይ በዚህ በጳጳስ ጉዳይ የዛግዌ መንግስታት ከፍተኛ ችግር በተለያየ ጊዜ ገጥሟቸው እንደነበር ወደፊት በየታሪኩ የምናገኘው ነው። የሆነ ሆኖ እንደምንም ተብሎ በተላከ ጳጳስ ተቀብቶ መራ ተክለሐይማኖት በላስታ ነገሰና "ወተሐይፀት መንግስተ እስራኤል ኀበ ዛጉ" ብሎ አወጀ።

ስመ መንግስቱን ደግሞ ዛጉዬ አለው። ዛጉዬ የተባለበት ምክንያትም እንደ ግማሾቹ አፃፍ ዘአገው /የአገው ወገን/ ማለት ነው። እንደ ግማሾቹ ደግሞ አፄ ድልነአድን ስላባረረ ዘአጉዩዩ የሚለው የግዕዝ ቃል አማርኛ ትርጉሙ ያባረረ ማለት ስለሆነ ነው ይላሉ።

መራ ተክለሐይማኖት የአክሱምን መንግስት በመቀማቱ ገሚሱ ወገን እንዳይቃወመው ቀደም ብሎ ያሰበበት ይመስላል። ምክንያቱም የድልነአድን ልጅ ይዞ ሸሽቷልና። በተጨማሪም የላስታንና የአካባቢውን ህዝብ ቀደም ብሎ በአክሱሙ መንግስት ላይ ማመፁን ተረድቷልና የህዝቡን አጀንዳ አንስቶ መንግስቱን እንደቀማ በማመን አገዎች ተቀብለውታል።

የተለመደውን የዘር ሃረግና የንጉሰነገስት ስልጣን ባለቤት መሆን ያለበት በቀጥታ ከሠለሞን ዘር የተወለዘ ነው የሚለውን ነገርም ብዙዎቹ አምነውበት ስለኖሩ መንግስተ እስራኤል የሚለውን ቃል ያካተተው ይህንኑ ልምድ ያልጣሠ መሆኑን ለማመላከት እንደሆነ ይነገራል።



ያም ሆነ ይህ ግን የአገው ተወላጆች /የኩሽ ዘሮች/ የዛግዌ ስርወ መንግስትን መመስረታቸውን ነው የአገር ውስጥ ፀሃፍትም የውጭ አገር ፀሃፍትም የሚያረጋግጡት።

እናም ባየነው መልኩ መራ ተክለሐይማኖት የዛግዌን ስርወ መንግስት መስርቶ ለ 13 አመታት ያህል ከ912-925 ዓ.ም ድረስ ገዝቶ ካለፈ በኋላ ተከታታይ የአገው ነገስታቶች በሱ እግር እየተተኩ ነግሰዋል።

ከ330 አመታት በላይ ስልጣኑን ይዘው ኢትዮጵያን ያስተዳደሩት የአገው ነገስታቶችም ከቀይ ባህር መለስ እስከ አባይ ወንዝ ባለው ክልል የሚገኙትን አጎራባች የኩናማ፣ የፈላሻ፣ አማራ፣ ጎጃምና አንጎት ማህበረሰቦችንና አካባቢዎችን ጠቅልለው ይገዙ ነበር። በስልጣናቸው ዘመንም በአክሱማውያኑ እግር ተተክተው ለኢትዮጵያ መንግስትና ህብረተሰብ ለእድገትና ለመስፋፋት ጠንካራ መሠረት ጥለዋል። ከቋጥኝ ድንጋይ አስፈልፍለው ያሠሯቸው አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት እንዲሁም መሠል የጥበብ ስራዎቻቸው ከዓለም ታላላቅ ባህላዊ ቅርሶች የሚመደቡና የአገው ነገስታት አስተዋፅኦ ማስረጃዎች ናቸው።

<u>**የዛግዌ ዘመን መንግስት የነገስታት ዝርዝር**</u>

| ተ.ቁ | የነገስታቱ ስም | በስልጣን ላይ የቆዩበት ጊዜ በአመት | የነገሱበት ዘመን ከክ. ልደት በኋላ |
|---|---|---|---|
| 1 | መራ ተክለሃይማኖት | 13 | 912-925 ዓ.ም |
| 2 | ጠጠውድም | 40 | 925-965 |
| 3 | ጃን ስዩም | 40 | 965-1005 |
| 4 | ግርማ ስዩም | 40 | 1005-1045 |
| 5 | መይራሪ | 15 | 1045-1060 |
| 6 | ሐርቤ 1ኛ | 17 | 1060-1077 |
| 7 | ይምርሐነ ክርስቶስ | 40 | 1077-1117 |
| 8 | ቅዱስ ሐርቤ 2ኛ /ገ/ም/ | 40 | 1117-1157 |
| 9 | ቅዱስ ላሊበላ | 40 | 1157-1197 |
| 10 | ቅዱስ ነአኩቶለአብ | 40 | 1197-1237 |
| 11 | ይትባረክ | 8 | 1237-1245 |

## ምዕራፍ ፴፰

## ከአፄ ጠጠውድም እስከ አፄ ይምርሐነ ክርስቶስ

**ከ925-1117 ዓ.ም**

በዛግዌ ስርወ መንግስት ስር ከነገሱት የአገው ነገስታት ውስጥ ሰፋ ያለ ታሪካቸው ተፅፎ የሚገኘው የቅዱስ ሐርቤ፣ የላሊበላና የነአኩቶለአብ ሲሆን፤ ከአፄ ጠጠውድም እስከ አፄ ይምርሐነ ክርስቶስ ድረስ የተከታተሉት ነገስታት ግን ሠፊ ታሪካቸው ተፅፎ አይገኝም።
ነገር ግን የእስክንድርያን ሊቃነ ጳጳሳት ታሪክ ሙሴ ሬኖዶት የተባለው ሀሃፊ ሲፅፍ ብዙ ጊዜ ለኢትዮጵያ ጳጳስ ስለመላክ በሚያጠነጥነው የፅሁፉ ክፍል የኢትዮጵያን ነገስታት አብሮ እየጠቀሰ ስለሚያልፍ፣ የዛግዌን ነገስታት አንዳንድ ቦታ ላይ ያነሳቸዋል። ከእርሱና ከአገር ተወላጅ ፅሁፍ ተሰቃቅሞ የሚገኘው ታሪክም የሚከተለው ነው።

ንጉስ መራ ተክለሃይማኖት 13 አመት ገዝቶ ሲሞት ጠጠውድም የተባለው ተካው። አፄ ጠጠውድም 40 አመት በቆየ የግዛት ዘመኑ በዮዲት ጊዜ የፈረሱትን ቤተክርስቲያናትና ገዳማት እንደገና እንዲሰሩ /እንዲታደሱ/ አድርጓል። በእርሱ ዘመንም በግብፅ የሚገኙ ክርስቲያኖች ከዓረቦች እየሸሹ ወደ ኢትዮጵያ መምጣታቸው ተፅፏል።

እንደዚሁም በጠጠውድምና በተከታዮቹ በጃን ስዩምና በግርማ ስዩም ዘመነመንግስት ጊዜ የግብፅ ከሊፋዎች በሊቃነ ጳጳሳቱና በክርስቲያኖቹ ላይ ጭቆና ሲያደርሱባቸው ነበር። ከሊፋ ሐኪም የሚባለው የዘመኑ የግብፅ ገዢም የግብፅን አገር በሙሉ ወደ እስልምና ለመመለስ ሲል ክርስቲያኖችን ማሰር መፍታትና ማንገላታት ጀመረ። የዘመኑን የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳስ አባ ዘካርያስንም አሠረ። ከዚህ በኋላ አብያተ ክርስቲያናቱን ሁሉ አቃጥሉ ብሎ አዘዘና ተቃጠሉ።

የግብፅ ክርስቲያኖችም ወደ ምስራቅ ወደ ቆስጠንጥንያ የክርስቲያን አገሮች እንዳይሸሹ የቆስጠንጥንያ ክርስቲያኖች ለክርስቶስ ለሁለታዊና መለኮታዊ፣ ሁለት የተለያዩ ባህሪ አለው ብለው የሚያምኑ ስለሆኑና፤ የእስክንድርያዎቹ ደግሞ አንድ ባህሪ አለው ብለው ስለሚያምኑ በዚህም የቆየ ፀብ ስለነበራቸው ወደ ቆስጠንጥንያ ለመሸሽ አልቻሉም። ወደ ኑብያ እንዳይሸሹ ደግሞ ዓረቦች በዚሁ ዘመን ኑቢያንም ይዘው ባለስልጣን ሆነውበታል። ስለዚህ የነበራቸው ብቸኛ አማራጭ እንደነርሱ ባንድ ባህሪ የሚያምንና ከአረቦች ተገዥነት ነፃ ሆኖ የሚገኘው የኢትዮጵያ መንግስት ብቻ ስለነበር የግብፅ ክርስቲያኖች እየሸሹ ወደ ኢትዮጵያ መጡ።

ከመጡትም ውስጥ የቤተክህነቱ ሰዎች እንዳሉ ሆነው ልዩ ልዩ የእጅ ጥበብና ሙያ ያላቸው ይገኙባቸዋል። ስለዚህ እነዚህን ስደተኞች



የኢትዮጵያ ህዝብና ንጉሱም፣ መኳንንቱም በጥሩ ሁኔታ ተቀብለው በሚችሉት ሙያ አስማርተው ርስትና ቦታ ሠጥተው አስቀመጧቸው።

ይህ ሁሉ ከሆነ በኋላ ከከሊፋ ሐኪም የተከተሉት የዓረብ አገረ ገዢዎች የሃይል አስተዳደራቸውን ለውጠው በክርስቲያኖቹ ላይ የጀመሩትን ጭቆና አቆሙ። በዚህ ጊዜ ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር የተቋረጠው ግንኙነት ንግዱም ሆነ ሌሎች ነገሮች እንደገና ቀጠሉ። በዚህ መካከል በአባ ክርስቶዶሉ የጵጵስና ዘመን ከ1039-1069 ዓ.ም አብዱም የተባለ ሰው ሀሰተኛ ደብዳቤ ይዞ መጥቶ አባ ቄርሎስ ተብሎ በኢትዮጵያ ጳጳስ ሆነ። የዚህን ወሬ ቬዝር ባድር ኤል ገማል የተባለው የአረቦች የወታደር አለቃ ሲሰማ ሊቀ ጳጳሱን ለምን እንዲህ አደረግህ? ብሎ ሲወቅሰውና ሲከራከሩ ሳለ ክርስቶዶሉ ሞቶ አባ ቄርሎስ ተተካ። አባ ቄርሎስ ጵጵስናውን የተረከበው በ1070 ዓ.ም ነበር። በዚያን ጊዜ ቬዝር ባድል ኤል ገማል አባ ሳዊሮስ የሚባለውን ቀብቶ ወደ ኢትዮጵያ ለጵጵስና እንዲልኩ ሊቀ ጳጳሱን በልመናም በትዕዛዝም መልክ አሳሰባቸው። አባ ቄርሎስም እሺ ብለው የአረቦቹ ወዳጅ የሆኑትን አባ ሳዊሮስን ቀብተው ወደ ኢትዮጵያ ላኩ።

አባ ሳዊሮስም የጵጵስና ሹመታቸውን ለመረከብ ወደ ኢትዮጵያ ሲደርሱ በሃሰተኛ ደብዳቤ መጥቶ ጳጳስ ሆኖ የተቀመጠው ቄርሎስ ሃሠተኝነቱ መጋለጡን አውቆና ሸሽቶ ወደ ዳህላክ ሄደ። ዳህላክ በአክሱሞቹ ጊዜ የኢትዮጵያ ግዛት የነበረና በአሁኑ ሠዓት የሙስሊሞች ግዛት ስለሆነ እዚያው እንዲያዝ ተደረገና ወደ ግብፅ ተላከ። በቬዝር ባድል ኤል ገማል ትዕዛዝም በአጭበርባሪነቱ ምክንያት አንገቱ ተቀርጦ ተገደለ ይባላል።

እንግዲህ ይህ ሁሉ ሲሆን ኢትዮጵያውያኑ የሚያውቁት ጉዳይ የለም። የመጣውን ይቀበላሉ የሔደውን ይሸኛሉ። ከዚህ በኋላ በሙስሊሞቹ ሹም ተመርጠው በሊቀ ጳጳሱ በአባ ቄርሎስ እጅ ተቀብተው የመጡት አባ ሳዊሮስ ከንጉሰነገስቱ ጋር ተገናኝተው የክብርና የማእረግ ቦታቸውን ከያዙ በኋላ ሙስሊሞቹን እየደገፉ በኢትዮጵያ እንዲስፋፉና መስጊድም እየሠሩ አምልኳቸውን እንደ ልብ እንዲያከናውኑ ይረዷቸው ነበር።

በዚህ ጊዜ ይምርሐነክርስቶስ ነበር የነገሰው። በወቅቱ ደግሞ እየሩሳሌምን ከአረቦች እጅ ለማስለቀቅ የአውሮፓ የክርስቲያን መንግስታት የመስቀል ጦርነት /ክሩሴድ/ የተባለውን ማህበር አቋቁመው ከ1100-1300 ዓ.ም ድረስ በአረቦቹ ላይ ተነስተውባቸው ነበር።

ስለዚህ በዚሁ በአፄ ይምርሐነክርስቶስ ዘመነ መንግስት የኢትዮጵያና የግብፅ መሪዎች ግንኙነት ከቀድሞው የተሻለ ሆነ። ኢትዮጵያ የክሩሴድ አባል አገራት ተባባሪ አልነበረችምና።

አባ ሳዊሮስ ከታሰሩ በኋላም ይምርሐክርስቶስ በዘመኑ ወደ ግብፅ ሊቀ ጳጳስና ወደ አገረ ገዢው ወደ ሺ.ዝር ልኮ አባ ጊዮርጊስን አስመጣ። ሆኖም አባ ጊዮርጊስ የውስጥ ለውስጥ ንግድ በመጀመራቸውና የቤተክህነቱን ንብረት ለግላቸው ጥቅም ሲያውሉ በመታየታቸው ወደ ግብፅ እንዲመለሱ ተደረገ። ግብፅ እንደደረሱም ሺ.ዝር ስራቸውን ሰምቶ አሣሠራቸው።

በመጨረሻ በይምርሐክርስቶስ ዘመን ወደ ግብፅ የሚወርደው የአባይ ውሃ ስላነሰና በግብፅ የውሃ ችግር ስለተፈጠረ የኢትዮጵያ መንግስት ወደ ግብፅ እንዳይወርድ ገድቦት ነውና ሔደው ተነጋግረው ያስለቅቁልን ብሎ ሺ.ዝር አፍዳል ሊቀ ጳጳሱን አባ ሚካኤል የተባሉትን ወደ ኢትዮጵያ እንደላካቸውና መጥተው ውሃውን ማስለቀቃቸው ተፅፏል።

በጥቅሉ ቀደም ሲል የአክሱም መንግስት ግንኙነት ከቆስጠንጥንያ መንግስት ጋር እንደነበረው ሁሉ አሁን በዛጐዌዎቹ ዘመን መንግስት ደግሞ የኢትዮጵያ ግንኙነት በዘመኑ ከገነኑት ከእነዚሁ የዓረብና የቱርክ ከሊፋዎችና ይልቁንም በእነሱ እየተሾሙ ግብፅን ከሚገዙት ባለስልጣኖች ጋር ሆነ።



## ምዕራፍ ፴፱
## የቅዱስ ሐርቤ 2ኛ ዘመነ መንግስት
## ከ1117-1157

በደንብ እንደሚታወቀው ለዓለምና ለህዝቦቿ መዋደድ፣ መከባበርና መተሳሰብ፤ እንዲሁም ለሰው ልጆች ቅን መሆን ሐይማኖቶች ወሳኝ ሚና ተጫውተዋል። የሐይማኖት ዋና መርህ ደግሞ አይነትና መልኩ ቢለያይም ሰዎች በሰላም ተስማምተው እንዲኖሩና ከክፉ ድርጊት እንዲቆጠቡ ማድረግ ነው። ነገር ግን ይህ እውነታ እንዳለ ሆኖ፤ በጥንቱ ዘመን ሐይማኖት የፀብ የግጭትና የጦርነት መነሻ ሆኖ አልፏል። ይህም ከሐይማኖቱ መመሪያ ደንብ ውጭ አንዳንድ ግለሰቦችና የሃይማኖቱ መሪና አዋቂ ነን ባዮች የሐይማኖቱን መመሪያ እየጣሱ በሚሄዱት ሂደት ውስጥ የሚከሰትን ጥፋትና እልቂት በዓለም አስከትሏል። ከዚህ ጉዳይ ጋር በተያያዘም ኢትዮጵያ የአለም አንድ አካል እንደመሆኗ መጠን በሐይማኖት አማካኝነት የጥቅምም የጉዳትም ተቋዳሽ ሆናለች። ለዚህም ማስረጃው እስካሁን ያየነውና አሁን እያየን ያለነው፣ ወደ ፊት ባሉ ምዕራፎችም የምናያቸው ታሪኮች ናቸው።

የኢትዮጵያ የታሪክ ሰነዶች አገሪቱ የሐይማኖት አገር እንደመሆኗ መጠን ታሪኳ ወደ መንፈሳዊነት አዘንብሎ ቢገኝም ሊገርመን አይገባም። ያለፉት ነገስታቶቿም እጥባቂ ሃይማኖተኛ በመሆናቸው በዘመናቸው የፈፀሙትን አለማዊ ስራ ከማየፍ ይልቅ መንፈሳዊነታቸውን አበክሮ የሚገልፅን ታሪክ ከትበው ወደ ማስቀመጥ ነው ያዘነበሉት። ይህን መነሻ ይዘን የቅዱስ ሐርቤን ታሪክ እንቀጥል።

· አፄ ይምርሐክርስቶስ ሲሞት ወንድ ልጅ ስላልነበረው በመንግስቱ የተተካው ንጉስ የወንድሙ ልጅ የሆነው ሐርቤ /ገብረማርያም/ የተባለው ነው። ሐርቤ 2ኛ የታዋቂው የአፄ ላሊበላ ታላቅ ወንድም ነው። በአገራችን አጠራር ቅዱስ ሐርቤ ወይም ገ/ም በሚል ስሙ ሲታወቅ፤ የዓረብ ፀሃፊዎች ቀኑዳ ይሉታል። ፈረንጆቹ ደግሞ ሲኖዳ ወይም ሽኑዳ ይሉታል። እነዚህ ሁሉ ፀሃፊዎች በዚህ ስም ይጠሩት የነበረውም በዘመኑ ኤጲስ ቆጶስ በማሾም ምክንያት በእርሱና በእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ በአባ ገብርኤል መካከል የተነሳውን ፀብ በሚተርኩበት ጊዜ ነው።

በቅዱስ ሐርቤ ዘመን በግብፅ ካይሮ ዋና ሊቀ ጳጳሳት የነበሩትና ከ1131-1145 ዓ.ም በሹመታቸው የነበሩት አባ ገብርኤል 2ኛ ይባላሉ። በቀድሞው እስክንድርያ /በእርሳቸው ዘመን ካይሮ/ በማርቆስ ወንበር ከተቀመጡት ሊቃ ጳጳሳት 70ኛው ናቸው። በኢትዮጵያም በዚሁ ዘመን የነበሩት ጳጳስ አቡነ ሚካኤል ይባሉ ነበር። ቅዱስ ሐርቤም እሠጥ አገባ ውስጥ ሲገባ የምናየው ከእኚሁ ከአባ ሚካኤል ጋር ነው።

ቅዱስ ሐርቤ ቅዱሳን መፃህፍትን በዘመኑ ከነበሩት ሊቃውንት ጋር በመሆን እየመረመረ የኢትዮጵያን ስሩትና የህዝቡን ብዛት በማጤን እንዲሁም

በሙስሊም ወገኖች የተከበበው የክርስትና ሃይማኖት ከመጥበብ ይልቅ እየሰፋ እንዲሔድ ፍላጎት ነበረው። ስለዚህም ከግብፅ ተመርጠው የሚመጡት ጳጳሳት ሁሉ የማእረግ ቦታቸውን ይዘው ከንጉስ ጋር ተከብረው ከመቀመጥና የአገራቱን ሁኔታ ከማጥናት ባለፈ ወደ ተለያዩ አውራጃዎች እየተዘዋወሩ በማስተማር ክርስትናን ለማስፋፋት አለመቻላቸውን ተመለከተ።

ስለዚህ በኒቅያ ጉባዔ 318 የሚሆኑ ሊቃውንት ስለ ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት አሿሿም የወሰኑትን ህግ የምስራቅ አብያተ ክርስቲያናት የሚተዳደሩበትን ደንብና ስርዓት ተመልክቶ በዚሁ መሰረት ጳጳሱን አባ ሚካኤልን "በኢትዮጵያ አውራጃዎች እየዞሩ ክርስትናን ለህዝቡ የሚያስተምሩ ከኢትዮጵያውያን መካከል ውስጥ ሰባት ኤጲስ ቆጶሳት ይሹሙልን" ብሎ ጠየቃቸው። ጳጳሱ አባ ሚካኤልም "ይህን መሠሉን ጉዳይ የበላዩን ሊቀ ጳጳሳት አባ ገብርኤልን ሳላስፈቅድ ማድረግ አልችልም።" የሚል ምላሽ ሠጡት።

ቅዱስ ሐርቤም ከአገር ውስጥ ሊቃውንት ጋር ተመካክሮ አንድ ደብዳቤ ለሊቃ ጳጳሱ፣ አንድ ደብዳቤ የግብፅ አገረ ገዥ ለነበረው ለከሊፋ አልሐፊዝ ዕፎ የኤጲስ ቆጶሳቱን ሹመት አስፈቅደው እንዲመጡ ወደ ካይሮ መልዕክተኛ ላከ። ሆኖም ከሊፋውና ጳጳሱ በሁኔታው ተመካክረው ከሊፋው ጥያቄው ተፈፃሚ እንዲሆን ሲወስን ሲል ዋናው ሊቀ ጳጳስ "ከኢትዮጵያውያን ተወላጆች ውስጥ ኤጲስ ቆጶሳት ከተሾሙ ቆይተው ራሳችንን እንችላለን ይሉናል። ራሳቸውን ከቻሉ ደግሞ በጳጳስ ሹመት ምክንያት የሚመጣልን ግብር ይቋረጥና የበላይነታችንም ይቀራል።" በማለት ለከሊፋው ሲገልፁለት ከሊፋውም እያዘነ ተስማማ።

ከዚህ በኋላ ሊቀ ጳጳሱ አባ ገብርኤል ከጥንት ሲያያዝ እንደመጣው ደንብ መቀበል እንዳለበትና ከዚህ የሚልከው ጳጳስ በቂ ስለሆነ የኤጲስ ቆጶሳቱ ሹመት አያስፈልግም የሚል ደብዳቤ ላከ።

ንጉስ ቅዱስ ሐርቤም በጣም አዝኖ "በኢትዮጵያ ያሉት ጳጳስ ስላረጁ፤ በእርሳቸው ፋንታ ጳጳስ ተልኮ እስኪመጣ ድረስ የኢትዮጵያን ቤተክርስቲያን የሚያስተዳድር ወይም የእኒሁ የአባ ሚካኤል ረዳት ሆኖ የሚሰራ ከኢትዮጵያውያን ውስጥ አንድ ኤጲስ ቆጶስ እንኳ ይሹሙልን" ብሎ እንደገና ሌላ ደብዳቤ ወደ ግብፅ ካይሮ ላከ። አሁንም አልተፈፀመም።

ከዚህ በኋላ በጳጳሱ በአባ ሚካኤል፣ በንጉስ ቅዱስ ሐርቤና በሊቀ ጳጳሱ በአባ ገብርኤል መካከል የከረረ ሀይና ክርክር ተነሳ። በዚህም ምክንያት ቅዱስ ሐርቤን ገሚሱ የኢትዮጵያ ህዝብ ከሊቀ ጳጳሱ ከአባ ገብርኤል ጋር የተጣላ እርጉም ንጉስ በማለት ፈረጁት። ዛሬ ድረስ የሚነበበው ስንክሳርም አባ ገብርኤልን እያሞገሰ ቅዱስ ሐርቤን የሚተች መንፈሳዊ ፅሁፍ የተካተተበት ሲሆን ሚያዚያ 10 ቀን ዘወትር ይነበባል። ካህናቱ ለምእመናኑ ማንበባቸውም ተገቢ እንዳልሆነ የሚከራከሩ አሉ። ምክንያቱም ምንም እንኳ የዚያ ዘመን



ኢትዮጵያውያን ሊቀ ጳጳስን የተናገረ ብለው ቢያወግዙት፤ ጎላማው ዘመናዊና አገራቱ ራሷን እንድትችል የሚያደርግ ነበርና ነው።

እናም የንጉሱና የጳጳሱ ፀብ እየከረረ ሄደ። አንድ ቀን በዚሁ ጉዳይ ሐርቤ እና አባ ሚካኤል ሲከራከሩ ጳጳሱ "እንዲያውም" መንግስት ላንተ አይገባህም ነበር። የሚገባው በሸዋ ላለው ለሰለሞን ዘር ነው" ብለው በቀጥ በመናገራቸው ቅዱስ ሐርቤ ተናዶ አሰራቸው ይባላል።

ከዚህ አንፃር የፀቡ መነሻ የሆነው ባየናቸው ፍላጎቶች አማካኝነት መሆኑ እንዳለ ሆኖ፤ ነገር ግን የስርወ መንግስት ጉዳይም አንድ ድርሻ ነበረው ማለት ነው።

ምናልባትም የግብፅ ሊቀ ጳጳሳትና የኢትዮጵያው ጳጳስ ለቀድሞው ለሠለሞናዊው የነጋሲ ዘር እያደሉ የዛግዌን ዘር እንደ ባእድ ስለተመለከቱት ቅዱስ ሐርቤም ይህንኑ በማወቅ እንድ ለራሱ ቤተ መንግስት ታማኝ የሆነ ኢትዮጵያዊ መጀመሪያ ኤጲስ ቆጶስነት አሠጥቶ ቀጥሎም ጳጳስ አሠኝቶ የግብፅን ጳጳስ ጨርሶ ለማባረር እንዳሰበ መረዳት ይቻላል።

በተጨማሪም ከዚህ በፊት ማንም ያላነሳውን ጥያቄ በማንሳቱም ጥላቻን ያተረፈ ንጉስ ይመስላል። በዚህ መሰሉ ጥያቄው ነው እንግዲህ ህዝቡና ሊቃውንቱ "ከሊቀ ጳጳሱ ከአባ ገብርኤል ጋር ስለተጣላ በአገሩ በኢትዮጵያ ላይ መቅሰፍት አወረደበት" ተብሎ ታምኖ በኋለኛው ዘመን በተፃፈው ስንክሳር ሁሌ የሚነበበው። መቅሰፍት የሚሉትም መንግስቱን ታናሽ ወንድሙ ላሊበላ ስለተተካበት ነው።

የሚገርመው ግን ይህ መሰሉ ጳጳስ የማስመጣት ሒደት ለኢትዮጵያ እንደማይበጅ ግልፅ ነበር። ቅዱስ ሐርቤ በዘመኑ ያነሳው ይህ ሃሳብ በኢትዮጵያ በ1951 ዓ.ም (በሃይለስላሴ ዘመን) ተግባራዊ የሆነውም አስፈላጊነቱ ታምኖበት ነው።

በነገራችን ላይ በዚሁ በጳጳስ ጉዳይ በርካታ የኋለኛው ዘመን ሊቃውንት የየራሳቸውን ሀሳብና አቋም በየዘመኑ ሲገልፁ ነበር። ከእነዚህ ውስጥ ነጋድራስ ተሰማ እሸቴ እንዲህ ብለው ተቀኝተው ነበር። ‹‹ሰፌድና ወንፊት እያለ በእጃችን፤

ያልተነፋ ዱቄት ምነው መብላታችን።›› ሲሉ፤ አለቃ እምባ አቆም የተባሉት ደግሞ:

‹‹በመርከብ ተጉዞ ምንድነው ቅልውጡ፤

ግብፆች ለሐበሻ ደግሰው ላይሰጡ።›› ብለው ነበር።

የሆነ ሆኖ ቅዱስ ሐርቤ 40 አመት ኢትዮጵያን በንጉሰነገስትነት አስተዳድሮ በመንግስቱ ወንድሙ ላሊበላ ተተክቷል። ቀሪው የቅዱስ ሃርቤ ታሪክም ከወንድሙ ከላሊበላ ጋር የተያያዘ ሲሆን እሱንም ከታላቁ ንጉስ ከቅዱስ ላሊበላ ታሪክ ጋር አብረን የምናየው ይሆናል።

# ምዕራፍ ፶

## የአፄ ላሊበላ ዘመነ መንግስት

## ከ1157- 1197 ዓ.ም.

ስለ አፄ ላሊበላ ታሪክ እንደ አንድ ምስክር ሆኖ የሚገኘው ገድሉ ነው። ገድሉ ለመድሃኒዓለም ቤ/ያን በመሠጠቱም ገድለ ላሊበላ ዘቅዱስ መድሐኒዓለም ይባላል። ከዚህ በተጨማሪ በ14ኛው መቶ ዓ.ም በአፄ ዘርዓያዕቆብ ጊዜ በደንብ ተደራጅቶ የተፃፈው ታሪኩ የሚገኝ ሲሆን ፤ ይህንን ታሪክነገስቱን መነሻ እያደረጉም በርካታ የውጭና ያገር ውስጥ ፀሃፍት ብዙ ፅፈውስታል።

በገድለ ላሊበላ ውስጥ ልደቱ፣ እድገቱ፣ በልደቱና በእድገቱ መካከል የተደረገለት ታዓምራት፣ ወንድሙ ሐርቤ መንግስቱን ይቀማኛል ብሎ እንዴት እንዳሣደደው፣ ከዚያ ተመልሶ ወደ እየሩሳሌም እንደሄደ ከኢየሩሣሌም ተመልሶ ከወንድሙ ጋር እንደታረቀና እንደነገሠ፣ እንዲሁም ሁሉ ያለ መንፈሣዊ ተዓምራት በዘመኑ እንደተፈፀመ ታትቷል።

ላሊበላ የተወለደው እዚያው ላስታ ሮሐ ነው። በተወለደበት እለት ብዙ ንቦች በዙሪያው ከበው ሲያነበንቡ እናቱ ስላየች ወደፊት ብዙ ሠራዊት የሚከተለው ታላቅ ሰው የሚሆን ነው ብላ በመገመት ስሙን ላሊበላ አለችው። ንብ ፀጋውን / ገዥነቱን / አወቀ ማለት ነው ይላሉ። "ላሊበላ ብሒል ንህብ አእመረ ፀጋሁ . ." የሚለውን ግዕዝ ተከትለው።

ላሊበላ ተወልዶ ባደገ ጊዜ በዘመኑ የነበረው ንጉስ ወንድሙ ቅዱስ ሐርቤይ ዙፋን ይቀናቀነኛል በማለት ብዙ ጊዜ ያሣድደው ነበር። ሊያስገድለውም ይፈልግ ነበር። አንድ ቀን የላሊበላ እህት ከንጉሱ / ከሌላኛው ወንድሟ / ጋር ተመሣጥራ በመጠጥ ውስጥ መርዝ ጨምራ ልካለት እንደነበረና የቀመሰው ሌላ ሰው ሲሞት እርሱ ሳይሞት እንደቀረ ከዚያም ሸሽቶ ወደ በርሐ ከገባ በኋላ በወታደር ተይዞ እንደመጣ፣ በሐይማኖታዊ ስርዓት ያገባትን መስቀል ክብራ የተባለችውን ሚስቱን ከሰው ነጥቆ ነው ያገባት የሚል ክሣሽ አስነስቶ ንጉሱ ብዙ ሰዓት እንዳስገረፈውና፤ በድጋሚ ከሚስቱ ጋር ሸሽቶ ወደ በርሐ ሄደው እንደተቀመጡና ከዚያ በኋላ ተመልሰው ከንጉሱ ጋር ታርቀው መኖር እንደጀመሩ እምላክ ለንጉስ ሐርቤ በራዕይ ተገልጦ "መንግስትህን ለላሊበላ ልቀቅለት" ብሎ እንደነገረውና ላሊበላ እንደነገሠ ተፅፏል።

ላሊበላ መንግስቱን ከወንድሙ ተቀብሎ የኢትዮጵያ ንጉስ ነገስት ተብሎ በ1157 ዓ.ም. ሲነግስ ስመ መንግስቱ ገብረ መስቀል ተባለ።

እናም በአክሱም ታሪክ ገናና እንደነበሩት እንደነ ኢዛና እንደነ ካሌብ ሁሉ በላስታ ወይም በዛግዌ ዘመን ደግሞ ላሊበላ ገናና እንዲባል ያስቻለውን ስራ ሰራ፤ ይህም በዘመነ መንግስቱ የሠራቸው አስደናቂ የሆኑ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት ናቸው። ይህንንም ሥራ በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ እየተመራ



እንዳከናወነው ይነገራል። በአፄ ላሊበላ ዘመንም ሆነ ከእርሱ በፊትና በኋላ በነበሩት የዛግዌ ነገስታት ዘመን የግብፅ ባለስልጣኖች ጣልቃ ገብነታቸው እየጎለበተ ሄዶ ነበር። ባለፉት ታሪኮች እንደተመለከትነው ሱልጣን ወይም ከሊፋ የሚባሉት በየጊዜው እየተከታተሉ ግብፅን የሚያስተዳድሩት የሙስሊም ባለስልጣናት በስልጣናቸው ስር የሚገኙትን የእስክንድሪያ ሊቃነ ጳጳሳት ግብር ከፈሉ፣ ያለኛ ፈቃድና ምርጫ ጳጳሥ ወደ ኢትዮጵያ እንዳይሄድ፣ በመካከላችሁ የሃይማኖትና የሹመት ክርክር ቢነሣ የኛ ባለስልጣኖች አብረው እየተቀመጡ ሁኔታውን እንዲመለከቱ፣ ወዘተ .. . . በማለት ያስቸግሯቸው ነበር።

ሁኔታው እየከፋ ሲሄድና የክርስቲያኖች ጭቆና በመካከለኛው ምስራቅና በግብፅ ሲበረታ ከዚህ ቀደም እንደሆነው ሁሉ በላሊበላም ጊዜ በሽሽት አገራቸውንና ንብረታቸውን እየጣሉ የሐይማኖት ወንድሞቻቸውን ፈልገው ለመጠጋት ወደ ኢትዮጵያ በርካታ ግብፃውያን የመጡ ሲሆን፤ ያረፉትም የንጉሠነገስቱ መቀመጫ በሆነው በላስታና በአካባቢው ነው። ላሊበላም ስደተኞችን ተቀብሎ ልዩ ልዩ ስፍራ እየሠጠ አስቀምጧቸዋል።

በዚያ ዘመን ለ3ኛ ጊዜ / 3ኛው / የመስቀል ጦርነት ተፋፍሞ ቀጥሎ ነበርና የአውሮፖ ተዋጊዎች የጀርመኑ ንጉስ ፍሬዴሪክ ባርባሩስ ፣ የእንግሊዙ ንጉስ ሪቫርኬርደሊዮን ፣ የፈረንሣዩ ንጉስ ፍሊፕ አውግስቲኒ ዋነኛ ተፋላሚዎች ነበሩ። የዓረቡ ዓለም ንጉስ ሱልጣን ሣላዲን የሚባለው እነዚህን ሁሉ በጀግንነት እየተዋጋ አሸንፎ የኢየሩሣሌምን ከተማ መልሶ በእጁ አደረጋት። / የመስቀል ጦርነት 8ጊዜ ያህል የተካሄደ ሲሆን እየሩሳሌም ስትለቀቅ መልሳ ስትያዝ ከ1096 — 1300 እ.ኤ.አ ዘልቆ እንደነበር ይታወሣል።/ ስለዚህ በዚህ ጦርነት እየተበሣጩ በግብፅ ያሉ ባለሥልጣናት ጭቆና ሲያበዙ ብቸኛ መጠጊያ ኢትዮጵያ ነበረች።

አፄ ላሊበላ ግን ወደዚህጦርነት ሣይገባ ከግብፅ ባለሥልጣኖች ጋርም ሣይጋጭ ስደተኞችን መቀበልና ማስጠጋቱን ቀጠለ። ስደተኞችን ተቀብሎ ጥገኝነት በመስጠቱም ዓረቦች "ለምን አስጠጋኃቸው? አሣልፈህ ስጠን" የሚል ተቃውሞ አላሠሙም።

አንዳንድ የውጭ አገርና የአገር ውስጥ ፀሃፍት እነዚህን ከግብፅና ከኢየሩሣሌም እየተሠደዱ የመጡትን በህንፃው ግንባታ ተሣታፊ እንደነበሩና ሠራውን ሚና እንደተጫወቱ ፅፈዋል።

ነገር ግን ቡተስይ በአገው ተወላጆች ዘንድ ጭንጫ እየፈለፈሉ፣ አለትና ድንጋይ እየጠረቡ ዋሻ መሰል መኖሪያ ቤት በመስራት የታወቁ ነበሩ። በሁቆጣ የብልብላ ጊዮርጊስ ሥራ ፣ በትግራይ ምስራቃዊ ክፍል ደግሞ በሐውዜን ውቅሮ የሚባለው ሥራ የላሊበላን አብያተ ክርስቲያናት ሥራ ስለሚመስሉ ከግብጾች መምጣት በፊት በኢትዮጵያውያን ዘንድ የዋሻ ውስጥ ቤቶችንና አለትን ጠርቦና ፈልፍሎ አብያተክርስቲያናትን ማነፅና ገዳምን መገደም የተለመዱ ነበሩ።

በተጨማሪም የላሊበላን አይነት ውቅር አብያተክርስቲያናት በዓለም በየትኛውም አገር ተፈልጐ አልተገኘም። ከዚህ አንፃር በኢትዮጵያዊያን ብቻ ነው የተሰሩት ብለው የሚከራከሩ አሉ።

ምናልባት አመዛዘኑን ወደ አንድ እውነታ እንድረስ ካልን ሰደተኞቹ በማስዋቡ ሥራ ሁሌ ድርሻ እንደነበራቸው ማመን ይኖርብናል። ምክንያቱም ቀደም ሲል የተሠሩት መሠል ሥራዎች ውበት የሌላቸውና አባጣ ጎርባጣ የነበሩ ናቸውና።

አፄ ላሊበላ በዘመኑ የፅድቅና የመንፈሣዊነት ባህሪ የተላበሠ እንደነበር ነው የሚታወቀው። አስራ አንዱን ውቅር አብያተ ክርስቲያናት ከማሠራቱ በፊትም የእግዚአብሔር አብን ቤ/ያን በግሸን አምባ አሠርቷል። በተጨማሪም በሸዋ በጎንደርና በላስታ ዙሪያ 181 የሚደርሱ መቅደሶችን አሠርቷል። ቀጥሎም ከግብፅ እየተሠደዱ ከመጡት ክርስቲያኖች መካከል ልዩ ልዩ የእጅ ሙያ ያላቸውን ገንዚዎችን ፣ አናጺዎችን ፣ ድንጋይ ጠራቢዎችን ከስደተኞቹ ውስጥ መኖራቸውን ሲሠማ ራሱ አስጠርቶ እየጠየቀ እውቀታቸውን አረጋገጠ።

በዚያው በላስታ ወይም ገዳመ ሮሐ በሚባለው ስፍራ ድንጋያማ የሆነ ቦታ አስመርምሮ አንዱን ትልቁን ቋጥኝ ውስጡን እያስፈለፈለ ልዩ ልዩ ክፍሎች በር፣ መስኮት፣ ጣራ ፣ ግድግዳ እያስወጣ በልዩ ልዩ ቴፕ እያሣመረ አሠነፀው።

ከዋና ዋና ከተማዎች ከእስክንድርያ ፣ ከካይሮ ፣ ከጥንት ግብፃውያን ሲወራረስ የመጣውን ከግሪክና ከቆስጠንጥንያ ተደባልቆ ዘመናዊ የሆነውን ስራ የለመዱትና ባጠቃላይ ከኢየሩሣሌምና ከግብፅ ለመጡት 500 ልዩ ልዩ ሠራተኞች በግንባታው ጊዜ የበላይ አለቃ ሆኖ ከአፄ ላሊበላ ጋር በቅርበት እየተመካከረ ሥራውን ያሠራ የነበረው ሲዲ መስቀል የሚባለው የግብፅ ባለሙያ ሲሆን ፤ ሌሎች ኢትዮጵያዊ ባለሙያዎች ደግሞ በተመሣሣይ "አበይተ ቡግና " በሚባሉ የበላይ አለቃ እየተመሩ እንደሠሩትም ተፅፏል።

ሥራው ይሠራ በነበረበት ጊዜ አፄ ላሊበላ ተጨማሪ ሰው እንደሚያስፈልግ አወቀ። እናም ለግብፁ ሱልጣን "ሌሎች የእጅ ጥበብ የሚያውቁና የጎደለውን ጥበባዊ የማስዋብ ሥራ የሚሠሩልኝ ባለሙያዎች ላክልኝ" ብሎ ተልኮለታልም ይባላል። ልዩ ልዩ የቤተመንግስትና የቤተክህነት ሹማምንት ከላይ ከተጠቀሱት ባለሙያዎች ጋር ሆነው በጋራ ተሣትፈውበታል። ይህን መሠሉን አገላለፅ የውጭ አገር ፀሃፊዎች ይወዱታል ይመርጡታልም። እነሱን መሠረት ያደረጉ የአገር ውስጥ ፀሃፍትም አይክዱም። እኛም በማስዋቡ ሥራ መሣተፋቸውን መካድ አንችልም።

እናም ሥራው በብዙዎች ተሣትፎ ተከናውኖ ድፍን 20 ዓመት ፈጅቶ ሊጠናቀቅ ችሏል።



*የ11ዱ አብያተ ክርስቲያናት ዝርዝርም፡-*

*1. ቤተ ደናግል*
*2. ቤተ ማርያም*
*3. ቤተ መድሃኒዓለም*
*4. ቤተ መስቀል*
*5. ቤተ ጎለጎታ*
*6. ቤተ ቅዱስ ሚካኤል*
*7. ቤተ ገብርኤል*
*8. ቤተ አባሊባኖስ*
*9.ቤተመርቆሬዎስ*
*10. ቤተ አባ አማኑኤል*
*11. ቤተ ጊዮርጊስ*

በሚል የተሠየሙ ናቸው።

ከነዚህ ውስጥ እጅግ የተዋበውና በብዙዎች ዘንድ የሚደነቀው ቤተ መድሃኒዓለም ነው። ቤተ መድሃኒዓለም 10 ሜትር ወርድ ፣ 38 ሜትር ስፋት ፣ 43 ሜትር ርዝመት አለው።
ቤተ አባሊባኖስን ያሠራቸው የላሊበላ ባለቤት መስቀል ክብራ ስትሆን ያሠራቸውም ለባለቤቷ ክብር ስትል ነው። በዚህ ምክንያት በሌሎቹ / በአስሩ/ አብያተ ክርስቲያናት የየስያሜያቸውን የዛድቃኑና የመላዕክቱ እንዲሁም የማርያምና የመድሃኒዓለም ምስል ሲታይ በቤተ አባ ሊባኖስ ግን መሐከል ላይ የፃድቁ የአባ ሊባኖስ በቀኝ በኩልና፣ በግራ በኩል ደግሞ የአፄ ላሊበላና የመስቀል ክብራ ምስል ነው የሚታየው።

የእነዚህን አብያተክርስቲያናት ሥራ በተመለከተ በገድለ ላሊበላ ሠፋ ያለ ሐተታ የሠፈረ ሲሆን፣ ፀሃፊው የሥራውን አስደናቂነት ለመግለፅ ቃል እንዳጠረው ፤ ላሊበላ ከአንድ ቋጥኝ ያሠራቸው እነዚህ ህንፃዎች ንጉስ ሠለሞን በጢሮስ ንጉስ በኪራም እየተረዳ በኢየሩሳሌምካሠራው ቤተ መቅደስ እንደሚበልጥ ፤ የላሊበላ ጥበብም ከሠለሞን የሚበልጥ መሆኑን ያትታል።

አፄ ላሊበላ እነዚህን አብያተክርስትያናት አሣንፆ ውስጣቸውንም አስጊጦ ቀገቢውን መንፈሣዊ አገልግሎት እንዲሠጡ በማድረግ በዘመኑ የነበሩትን ብቻ ሣይሆን እኛንም የወደፊቱንም ትውልድ ሲያኮራ የሚችል ታላቅ ስራ ሠርቷል። በዚህም ክፃግዊ ነገስታት ውስጥ ገናና ሊሆን ችሏል። በዘመኑ የተሠራው የሥራ ውጤትም ከዓለም አስደናቂ ቅርሶች አንዱ ነውና በ1978 ዓ.ም. በዩኔስኮ መዝገብ ሊሠፍር ችሏል።

እነዚህን አስደናቂ ህንፃዎች ቦታው ድረስ እየሄዱ የተመለከቱ የውጭ አገር ታሪክ መርማሪዎችና ጎብኚዎች ተደንቀዋል። ከተመለከቱት ውስጥም ይህን መሠል ከአንድ ቋጥኝ ተፈልፍሎ የተሠራ ህንፃ በዓለም ላይ እንደሌለ ያረጋገጡ ብዙዎች ናቸው። ተጨማሪ ታሪክ ያካተቱ አስተያየቶች ስለሚበረክቱም ከብዙዎች የጥቂቱን እንይ።

" እናንተ ኢትዮጵያውያን የኢየሩሳሌም ለማያዩት / መንግስተ ሠማያት/ ባላገሮች ናችሁ። በእኔ እምነት ገነት ማለት ይች አገራችሁ ናት። ብዙ አገሮችን በጉብኝት አይቻለሁ። የግብፅ ፒራሚዶችን ፣ የባቲካን ቤተ እምላኮችን ፣ የግሪክ ቤተ ጣኦቶችን ፣ ምድረ እስራኤልን ወዘተ . ... ነገር ግን እንደ ላሊበላ ህንፃዎች ያስደነቀኝ የለም። ዛሬ ዓለም በጥበብ ይምጠቅ ፣ ጨረቃን ይጎብኝ ፣ ህዋውን ይፈትሽ እንጂ የእናንተን አባቶች ሠማያዊ ጥበብ

ሊደርስበት አልቻለም፣ በዚህ ልትመኩ ይገባችኋል"፡፡ /ቢል ግርሃም የተባለ አሜሪካዊ ተንቫር 0ሃፊ /

"እጅግ በጣም አስደናቂና ከፍተኛ የጥበብ ችሎታ የሚታይበት እፁብ ድንቅ ሥራ በመሆኑ የተሠማኝን አድናቆት ዘርዝሬ ብፅፍ የሚያምነኝ ስለማይኖር በጥቅሉ ለገብኝትና የዓይን ምስክርነት ለሚሠጡ ትቸዋለሁ" /ፍራንሲስ አልባሬዝ የተባለ አውሮፖዊ ከ1513 - 1517 ዓ.ም. በኢትዮጵያ የቆየ/

ጀራርድ ሮልፍ ይባላል፡፡ የጀርመን ተወላጅ ነው፡፡ በኢትዮጵያና በአፍሪካ ከ1825 — 1870 ዓ.ም. ቆይቶ በፃፈው መፃህፍ ውስጥ የላሊበላን ታሪክ አካቷል፡፡ ይህ ሰው ወደ ላስታ አቅንቶ አብዱራሀማን የተባለ አስተርጓሚውን ይዞ ከአብያተ ክርስቲያናቱ አለቆችና መምህሮች ጋር ተገናኝቶ ውጪውንም ውስጡንም በደንብ እያሰረዱ እንዳስጎበኙት ይገልፃል፡፡ በእርሱ አስተያየት አስራ አንዱ ወይም አስሩ /አንዱን መስቀል ክብሬ ስላሠራቸው/ ሁሉም አብያተ ክርስቲያናት ሲሰሩ ላሊበላ ከእየሩሣሌም ያስመጣቸውን ሀባቱን የወይራ አፀድ ማየቱን ይገልፅና፤ እነዚህን መሠል ስራ በዓለም እንደሌለ ያረጋግጣል፡፡

አችለ. ራፍሬይ የተባለው ደግሞ በኢትዮጵያ / በምፅዋ/ የፈረንሣይ ቆንሲል የነበረ ሲሆን፤ ስለ ስራውና ስለሠሩት ሠዎች የሚገልጽ የብሩና ፅሁፍ ያገኘ ነው፡፡ ይህ ሰው በ1882 ዓ.ም. "የላሊበላ በአንድ ድንጋይ የተሠሩ ሀንፃዎች" በሚል ርዕስ ከህንፃው ጉብኝቱ በኋላ መፅሃፍ ፅፏል፡፡ እርሱም ሆነ ከእርሱ በፊት ስለ ላሊበላ የፃፉትን ዓይነት ተመሳሳይ ሃሳብ የሰፈረበት መጽሐፍም ከሁሉም በላይ ቤተመድሐኒዓለም እንደሚያምር ፣ 5ቱ ባንድ ቦታ ፣ 4ቱ ባንድ ቦታ ፣ 1 ዱ በሌላ ቦታ ሆኖ ከአንድ ወጥ አለት በ3 ተከፍለው መሠራታቸውን ይገልፃል፡፡ ህንፃዎቹን ከመረመረ በኋላም ከቀሣውስቱ የብራና መፅሃፍ በግዕዝ ፣ በዓረብኛ ፣ በግሪክኛ የተፃፈ ፅሁፍ ማግኘቱን፤ ይህንንም የፃፈው የህንፃዎቹ ዋና ሠሪና አሠሪ የነበረው ሲዲ መስቀል የተባለው ግብፃዊ መሆኑን ፣ ፅሁፋም የሚገልፀው በዋናነት አፄ ላሊበላ ለነዚህ አብያተ ክርስቲያናት መነኮሳትና ቀሣውስት መተዳደሪያ እንዲሆን ርስትና ጉልት መስጠቱን የሚያስረዳ ነው፡፡

ገብርኤል ስምአን የተባለ መርማሪ ደግሞ "በእነዚህ አብያተ ክርስቲያናት አጠገብ የሚያልፍ ከሌላ ወንዝ በቦይ ተስቦ የሚተላለፍ ውሃ አለ"፡፡ ይልና "ስሙንም ዮርዳኖስ ብለው ሠይመውታል" ይላል፡፡ "ኢትዮጵያዊያን እነዚህን አብያተክርስቲያናት የሠሩት በጥንታዊቷ የይሁዳ ከተማ በኢየሩሣሌም የሚገኙትን 11 ዱን ቤተ መቅደስ በአገራቸው እንዲገኝ ለማድረግ አስበው ነው…." እያለ ይቀጥላል፡፡

በዘመነ ዛግዌ የኢትዮጵያ ሰፋት እንደቀድሞው እንደ አክሱሞቹ አልነበረም፡፡ በኤርትራ ባህር አጠገብ የሚገኙት ደሴቶች እንዳህላክ፣ እንምፅዋ፣ እንዲሁም በታችኛው ወደብ አቅራቢያ በአዳል አካባቢ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን



ሁሉ በዓረቦች እርዳታ እስልምናን ተቀብለው የየራሣቸውን ባላባት አንግሠው መኖር የጀመሩበት ጊዜ ሆኗል፡፡ ከላሊበላ በፊትና በኋላም አንዳንድ የኢትዮጵያ ነገስታት ላሊበላን ጨምሮ ጦር እየላኩ ሊያስገብሯቸው ሞክረዋል፡፡ ሆኖም ፈፅሞ መጠቅለል አልቻሉም፡፡

አፄ ላሊበላ ደግሞ ከምፅዋ ጀምሮ እስከ ዘይላ የአዳልን አገር በሙሉ በግዛት ዘመኑ ጦርልኮ ሊያስገብራቸው ችሏል፡፡ የላሊበላ ጦር አስገብሯቸው ከተመለሰ በኋላም ለጥቂት ዘመን ገብረው አብዛኛውን ጊዜ ግን በባላባቶቻቸው እየተመሩ የዓረቦችን ሃይል ተደግፈው እንደገና ለየብቻቸው መኖራቸውን ቀጥለዋል፡፡ ስለዚህ በአፄ ላሊበላ ዘመንም ሆነ በአባቶቹ ዘመን የተጣራው ግዛታቸው ትግራይ ፣ በጌምድር /ጎንደር/ ጎጃም ፣ ሠሜናዊው ሸዋ ፣ እንዲሁም በእነዚህ አገሮች መካከል የሚገኘው የወሎ ፣ የየጁና የመሣሠሉት ነበሩ፡፡ ንጉስ ላሊበላን በላሥታ የሚኖሩት ያልናቸው ከግብፅ ተሠደው የመጡት ክርስቲያኖች በግብፅ ያሉት የዓረብ አስተዳዳሪዎች በፊት በእነሱ ፣ አሁን ደግሞ ግብፅ ውስጥ በቀሩት ክርስቲያኖችና ካህናቶች ላይ እስራትና ጭቆና እያደረሱ ነው በሚል ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት ስደተኞች እንዲህ የሚል ምክር እንደሠጡት ይነገራል፡፡

" የግብፅ አረቦች የአባይን ውሃ ካላገኙ መኖር አይችሉምና የአባይን ውሃ ከመንገዱ አውጥተህ ወደ በረሃ እንዲፈስ አድርግ፤ በዚህ ጊዜ አረቦቹ በውሃ ጥም የተነሣ አገራችን ግብፅን ለቀው ይሔዳሉ" ብለው አመለከቱ፡፡

አፄ ላሊበላም የእነሱን ሃሣብ ለመፈፀም የአባይን ውሃ ከመንገዱ አስወጥቶ ወደ በርሃ እንዲፈስ ለማድረግ ወይም ከአዋሽ ጋር ለማገናኘት አስቦ ነበር፡፡ ነገር ግን አድካሚ ስራ መሆኑን ተገንዝቦ በዚህ ምትክ ለአባይ ወንዝ የሚገብሩትን በርካታ ወንዞች እንዳይገብሩ አቅጣጫቸውን እየቀየሱ ወደ ሌላ ቦታ እንዲፈሱ የሚያደርግ ሥራ አስጀምሮ ነበር፡፡ ሆኖም ወደ ፍፃሜ ሊደርስ አልቻለም፡፡

እንደ ብዙዎቹ ግምትም ምናልባት ይህን ያላደረገው ከዓረቦች ጋር ወደ ከረረ ፀብ ሊከተውና ኢትዮጵያንም ወደ አደጋ ላለማስገባት አስቦ እንደሆነ ፤ እንደ ሌሎቹ ግምት ደግሞ ይህ ሃሣብ ከመንፈሣዊነቱ አንፃር ስላልተጣጣመለት እንደተወው ነው፡፡

በተረፈ ላሊበላ ገድሉ እንደሚለው አምላክን በመፍራትና "ስልጣኑን ወደ ሠለሞን ዘር መመለስ አለብህ" የሚለው የካህናቱና የቀሣውስቱ ጭቅጨቃ ስለበረከተ መንግስቱን ለሠለሞናዊው ዘር ሊመልስ አስቦ እንደነበር ነው፡፡


በመጨረሻም አፄ ላሊበላ ወደ ፍፃሜው ሲቃረብ የወንድሙን ልጅ ነአኩቶለአብን አስጠርቶ ባረከው ይባላል፡፡ መንግስቱንም ያወረሰው ለነአኩቶለአብ ሲሆን፤ ላሊበላ ኢትዮጵያን ለ40 አመታት አስተዳድሮ በ1197 ዓ.ም. ሰኔ 12 ቀን አረፈ፡፡ የሞተበትን እለት ለማሠብም በዘወትር ሰኔ 12

የሚነበበስት ክፍል ስንክሳር በተባለው መፅሃፍ ውስጥ ይገኛል። አጽሙም ራሱ ባሠራው በቤተ ጎለጎታ አርፎ ይገኛል።









## ምዕራፍ ፺፩
## የስልጣን ሽግግር ከላሥታ ወደ ሸዋ
## በአፄ ነአኩቶለአብ ዘመነ መንግስት
## ከ1197 — 1237 ዓ.ም.

ከንጉስ ላሊበላ ቀጥሎ የተተካው የመጨረሻው የዛግዌ ስርወ መንግስት ንጉሰነገስት ነአኩቶለአብ ነው። የስልጣን ሽግግር የተከናወነውም በእርሱ ዘመን ነበር። ነገር ግን ከእርሱ በኋላ የላሊበላ ልጅ ይትባረክ በላስታ ዙፋን በንጉስነት የተቀመጠበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ነአኩቶለአብ የቅዱስ ሃርቤ ልጅ ነው። አርባ አመት በቆየ ግዛቱ ላሊበላ የጀመራቸውን ስራዎች ወደ ፍፃሜ ማድረሱ፣ በልዩ ልዩ የኢትዮጵያ ከተሞች አብያተ ክርስቲያናት ማሠራቱ፣ እንዲሁም በአልገብርም ባይነት ሲሸፍቱ የኖሩትን ወገኖች ድል እያደረገ ማስገበሩ ሲታወቅ፤ ከዚህ ያለፈ ዝርዝር ታሪክ አይገኝም።

በዛግዌ ታሪክ ውስጥ በተደጋጋሚ ከየአቅጣጫው የሚሠነዘር ተቃውሞ ነበር። ይህም መንግስቱን ወደ ቀድሞው ወደ ሠለሞናዊው ዘር መልሱት የሚል ነው።

ይሁን እንጂ እስከ ነአኩቶለአብ ድረስ በዚህ ጉዳይ የእርስ በርስ ጦርነት አልተካሄደም። ዛግዌዎችም በዘመናቸው እንደወንድሞቻቸው እንደ አክሱም ነገስታት ለአገራቸውና ለህዝባቸው እድገት ሲጥሩ ነው የኖሩት። ይልቁንም ወደ መሐልና ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ እየተስፋፉ የሄዱበት ሁኔታ የነበረ ሲሆን፤ የፖለቲካ፣ የሃይማኖትና የባህል ተወራራሽነት እየተፈጠረ አሃዳዊ መንግስቱን በፅኑ መሠረት ላይ ለመጣል የተጠናከረ እንቅስቃሴ ያደረጉበት ዘመን ነበር።

በመጨረሻ ግን በአቡነ ተክለሃይማኖት አግባቢነት ሠላማዊ የስልጣን ሽግግር እንዲደረግ ሆኗል። ይህ የስልጣን ሽግግር በሽምግልና ይተገበር ዘንድም ብዙ ጥረቶች ተደርገዋል። ረዘም ያለ ጊዜ ከወሰደ በኋላም ስልጣኑን በተዓፈ ውል ሊለቁ ተገደዋል።

ምንም እንኳ ርክክቡ ወረድ ስንል እንደምናገኘው በሰላማዊ መንገድ ከነአኩቶለአብ ወደ ይኩኖ አምላክ ቢሸገርም ፤ በላስታ ዙፋን "ንጉስ" ሆነው የሚቀመጡ የአገው ንጉሶች እንዲኖሩ ከተደረገ በኋላ ንጉስነታቸውን ትተው ንጉሰነገስት ሆነው ለመቀጠል ያሰቡ ነበሩ። ለምሳሌ ሽግግሩ ከተከናወነ በኋላ በላስታ ዙፋን ንጉስ ሆኖ የተቀመጠው የላሊበላ ልጅ ይትባረክ /ከነአኩቶለአብ በኋላ/ እራሱን እንደ ንጉሠ ነገስት እየቆጠረና እውቅና አልሠጥም በማለት ለ8 አመታት ያህል ያላቋረጠ ውዝግብ ተፈጥሮ ነበር። ሆኖም ወዲያው የሸዋው የመጀመሪያ ንጉስ



ነገስት ይኩኖ አምላክ በሙሉ እውቅና ስልጣኑን ከተረከበ በኋላ ውዝግቡን በሃይል ሊያበርደው ችሏል። የ8 ዓመት ክፍተት የተፈጠረውም በዚህ ምክንያት ነበር። የሆነ ሆኖ ግን ርክክቡ የተከናወነው በነአኩቶለአብና በይኩኖ አምላክ መካከል ነው።

ከዚህ አንፃር የዛግዌ ስርወ መንግስት ለ333 ዓመት እንደቆየ እንረዳለን። ላስታ የኢትዮጵያ ማዕከላዊ መንግስት መቀመጫ ሆና የቆየችውም ከ912-1245 የነበረ ሲሆን፤ የሸዋው ንጉሠ ነገስት ይኩኖ አምላክ የተደላደለ መንግስቱን የያዘው ግን በ1253 ዓ.ም. ነው።

አጠቃላይ የርክክቡ ሂደትና ውጤትም ባጭሩ በሚከተለው መልኩ ይገለፃል።

የዛግዌ ስርወ መንግስት በተመሠረተ ጊዜ የመጨረሻው የአክሱም ንጉስ አፄ ድልነአድ ወደ ሸዋ ሸሽቶ መሔዱን አይተናል። ከእርሱ በኋላ የተወለዱት ዘሮቹም የዛግዌ ስርወ መንግስት እስኪያበቃ ድረስ በዚያው በሸዋ ነው የኖሩት።

በዛግዌ ነገስታት ተይዘው እንዳይታሠሩ በመስጋትም ዘመናቸውን ሙሉ በየዋሻዎች እየሸሹና እየተደበቁ ነበር ያሣለፉት። ዛግዌዎች ግን ይህን መሰል ሙከራ አላደረጉም። እናም ከድልነአድ ጀምሮ ሲዘረዘሩ ድልነአድ ፣ አንበዓፅዮን፣ ፅንፈ አርእድ ፣ ነጋሽ ዞሬ ፣ አስፍሐ ፣ ያዕቆብ ፣ ባህር አሠግድ ፣ አድም አሠግድና ይኩኖ አምላክ ናቸው።

ከእነዚህ ውስጥ የመጀመሪያው ድልነአድና የመጨረሻው ይኩኖ አምላክ፡ በዙፋን ሲቀመጡ እድሜያቸውን ሙሉ በሽሽትና በመደበቅ ያሣለፉት የድልነአድ ተከታዮች /ዘሮች/ ሰባቱ መሆናቸው ነው።

የዛግዌ ንጉስ ነአኩቶለአብ በላስታ በነገሰበት ዘመን ይኩኖአምላክ የተባለው ከሠለሞን ዘር የወረደ ወጣት በሸዋ ይኖር ነበር። እንደዚሁም በመላው ኢትዮጵያ የታወቁት አቡነ ተክለሐይማኖት ይኩኖአምላክ በነበረበት ዘመን ይኖሩ ነበር።

ይኩኖአምላክ/ ተስፋ እየሱስ/ ተወለዶ ባደገ ጊዜ አባቱ እንዳይገደልበት ፈርቶ ወደ አንድ ገዳም ወስዶ አደራ ሠጠው። ይኩኖ አምላክም በሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳም / ከደሴ ወጣ ብሎ/ መንፈሣዊ ትምህርትን እየተከታተለ አደገ።

አቡነ ተክለሐይማኖትም ወደዚህ ገዳም እየሔዱ ይኩኖአምላክን ይጎበኙት ነበር። ከዚያም መምህሩን አስፈቅደው ይኩኖአምላክን ወደ ሸዋ ይዘውት እንዲሔዱ ተፈቅዶላቸው ይዘውት መጡ። በሸዋም በይፋት ፣ በመንዝ፣ በተጉለት ፣ በመራቤቴ እያዞሩ ከባላባቶች ጋር አስተዋወቁት። ይሁን እንጂ ይኩኖአምላክ አብዛኛውን ጊዜውን ያሣለፈው በተጉለት ነው። አንዳንድ ጊዜ ይኩኖ አምላክ መሆኑን ሳይገልፅ በስውር ላሥታ ድረስ

እየሄደ አሽከርነት እየተቀጠረ የቤተመንግስትን ስርዓትና ህግ ያጠና የነበረ ሲሆን ፤ መካሪውም አቡነ ተክለሐይማኖት ነበሩ ይባላል፡፡

እናም አቡነ ተክለሐይማኖት በማናቸውም ረገድ እርሱን ለማንገስ ስለወሰኑ ባላባቱን ሁሉ ወደዚህ ሐሣብ እንዲያዘነብሉ ማድረግ ጀምረዋል፡፡ ይኩኑአምላክም "የአባቶቼ መንግስት በእርስዎ ሀሎት የተመለሰልኝ እንደሆነ ለእርስዎም የአባትዎን የአቡርያስን ሊቀ ካህንነት እመልስልዎታለሁ፡፡ ከመንግስቴም ከሦስት እጅ አንዱን እጅ እሰጥዎታለሁ" ብሎ ቃል ገባላቸው፡፡

ከዚህ በኋላ አቡነ ተክለሐይማኖት የተገባላቸውን ቃል ብቻ ሳይሆን ስልጣኑን ወደ ቀድሞው ሠለሞናዊ ዘር እንዲመለስ ይሹ ነበርና በየአውራጃው እየተዘዋወሩ ማስተማርና ማሣመናቸውን ቀጠሉ፡፡

" ዛጉዬዎች ከሠለሞን ዘር ዙፋኑን አሳግባብ ነው የወሰዱት፡፡ አሁንም ለይኩኑአምላክ በሠላም ሊመልሱ ይገባል" እያሉ መስበክ ጀመሩ፡፡ ከእለታት አንድ ቀንም ወደ ላስታ ሔደው ነአኩቶለአብን / የመጨረሻውን የዛጉዬ ንጉስ/ ተገናኝተው "የኢትዮጵያን መንግስት የወሰዳችሁት በማይገባ መልክ ነውና አሁንም ለሚገባው ለይኩኑአምላክ መልሱ" በማለት በግልፅ ነገሩት፡፡

እርሱም መንፈሣዊ ሰው ስለነበር የአቡነ ተክለሐይማኖትን ቃል እንዳይተላለፍ ፈርቶ ምክራቸውን ሰምቶ "እሺ እለቃለሁ፤ ነገር ግን የኔ ዘመን ካለቀ በኋላ በውል ነው የምለቀው፡፡" ብሎ ገለፀላቸው፡፡ / እዚህ ላይ ምናልባት " የኔ ዘመን ካለቀ" የሚለው የዛግዌ ነገስታት ከጥቂት ንጉሶች በቀር አርባ አርባ አመት እንደገዙ ነውና የሚታወቀው ምናልባት ሞት ካልወሰዳቸው በስተቀር የአንድ ንጉስ የግዛት ዘመን 40 አመት እንዲሆን የተስማሙ ይመስላል/ የሆነ ሆኖ ነአኩቶለአብ እሺታውን ገለፀ፡፡ ጀምስ ብሩስ የሚባለው እንግሊዛዊ ፀሃፊ ኢትዮጵያ መጥቶ ብዙ ፅሁፎችን ሰብስቦ ከሔደ በኋላ የኢትዮጵያን ታሪክ በፃፈበት መፅሃፉ የውሉን አይነትና ዝርዝር አስፍሮታል፡፡ እርሱን መሠረት አድርገው የፃፉ ፀሐፍትም በተመሣሣይ ውሉን በሚከተለው መልኩ አካትተውት ይገኛል፡፡

1ኛ. የነአኩቶለአብ ዘመን እስኪያልቅ ድረስ ይኩኑአምላክ ንጉስ መባል እንዳይጀምርና ንጉስ መባሉ እንዲረጋ ፣ የነአኩቶለአብ ዘመን ሲያልቅ ይኩኑ አምላክ በሙሉ ኢትዮጵያ እንዲነግስ፣

2ኛ. ይኩኑ አምላክ መንግስቱን ከተቀበለ በኋላ ከዛጉዬ ዘር አንድ መስፍን እየተመረጠ በላስታ አልጋ /ዙፋን / እንዲሾም ፣ የላስታም ግዛት ከዛጉዬ ወገኖች እንዳይወጣ፣



3ኛ. ላስታን የሚገዛው መስፍን የዛጉዬ ዘር ለመሆኑ ምልክት ይሆነው ዘንድ ሁለት የብር ነጋሪት እንዲያስጭን ፣ የዘበኞቹ ጦር ባለ ብር ሽቦ ፣ የሠንደቅ አላማው መያዥ ጫፉ የብር እንዲሆን፣

4ኛ. የቀዳማዊ ምኒልክ ዘር የሆነው ንጉስ በወርቅ ዙፋን ሲቀመጥ የላስታው መስፍን በብር ወንበር እንዲቀመጥ፣

5ኛ. የላስታው መስፍን ከንጉሱ ጋር በተገናኘ ጊዜ ወንድም ከወንድሙ ጋር በተገናኘ ጊዜ እንደሚያደርገው እንዲሳሳሙ እንጂ፤ የላስታው መስፍን እንደሌሎች መሣፍንት መሬት እንዳይስም፡፡

6ኛ. እንደ ሌሎች መሣፍንትና መኳንንት ግብር እንዳይገብር፣ መጥን ፣ አሁጣ ተብሎም እንዳይታዘዝ የሚሉ የውል ስምምነቶች ሰፍረው ይገኛሉ፡፡

አቡነተክለሃይማኖት ይህን ውል አዋውለው መንግስቱን ከላስታ ወደ ሸዋ ፣ ከዛጉዬ ወገን ወደ ሠለሞናዊው ዘር ፣ ከነአኩቶለአብ ወደ ይኩኑአምላክ እንዲዘዋወር አድርገዋል፡፡ እናም በዚህ በእርቁና በውሉ መሠረት ይኩኑአምላክ በመላው ኢትዮጵያ ሲነግስ ከነአኩቶለአብ በኋላ በውሉ መሠረት በላስታ አልጋ የተቀመጠው የአፄ ላሊበላ ልጅ ቀደም ሲል እንዳየነው ይትባረክ ነበር፡፡ ከእርሱ በኋላም በተመሣሣይ መልኩ ላስታን ብቻ በመግዛት ተወስነው መቀጠል የቻሉት ሁኔታውን ስላልተቀበሉት ሁሉም በየዘመናቸው ጦርነት እየቀሰቀሱ ተዋግተዋል፡፡ ነገር ግን ይኩኑአምላክና ተከታዮቹ ወደ ፊት ባለው ጊዜ ህዝቡና መኳንንቱ፣ የቤተክህነት አለቆች ስላበሩለትና ስላገዙት የሸዋዎቹ ሐይልና ስልጣን እየበረታ ፣ መንግስታቸውም እየደረጀ ሲሄድ፤ የላስታዎቹ ተዳክመው ሊቀሩ ቻሉ፡፡ ስለዚህ ባየነው መልኩ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ስልጣን በሽማግሌ አማካይነት በሰላማዊ መንገድ ከአንዱ ወደ አንዱ የተላለፈበት ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር ማለት ነው፡፡

ከዚህ ዘመን በኋላ ላለው ታሪክ ማለትም በሸዋ ነገስታት ዘመን የተፈፀሙ ታሪካዊ ክንውኖች ሁሉ በጦርነት የታጀቡ ሆነው ነው የምናገኛቸው፡፡ ይህም ሲባል ግጭቱ የውስጥ ግጭት ሆኖ አንዳንድ ጊዜ ከበስተጀርባ የሌሎች እገዛ እየታከለበት ተቀጣጥሎ ሲቀጥል ልናይ እንገደዳለን፡፡ ስለዚህ ወደ ሸዋ ነገስታት ታሪክ ከማለፋችን በፊት በደቡባዊው የኢትዮጵያ ክፍል ይኖሩ ስለነበሩ ወገኖችና ስለ አካባቢው ግንዛቤ ለመያዝ አንድ አጭር ምዕራፍ እናስቀድምና ወደ ሸዋ ነገስታት ታሪክ እናልፋለን፡፡

## ምዕራፍ ፵፪

## የደብቡና የደቡብ ምሥራቅ ማህበረሰቦች

በዚህ ምዕራፍ ስር ለምናየው አጭር ሃተታ ዋና መነሻችን የኘ/ር ላጵሶ ጌ.ድሌቦ ስራ ነው፡፡ የኢትዮጵያ የታሪክ መነሻ በሚለው ስራቸው የደቡብ ኢትዮጵያ አካባቢዎችና ጥንታዊ ማህበረሰቦች በሚል ንዑስ ርዕስ ስር የጥናት ውጤታቸውን አስፍረዋል፡፡ " የቅድመ ታሪክና የዘመን ታሪክ መሰያ ምልክትና ሚዛን የተፃፉና ከዘመን አቆጣጠር ጋር የተገናዘቡ የሰነድ መረጃዎች መገኘት ነው"፡፡ ይሉናል፡፡ ሲቀጥሉ "በዚህ ረገድ በጥንታዊት ግብፅ የተገኙ መረጃዎች በአፍሪካ ቀንድና በሰሜኑ ክፍል የኢትዮጵያን ጥንታዊ የፑንትና የሃበሻ ነባር ማህበረሰቦችን ማንነትና በሶስተኛው ሺ ዓመተ ዓለም አጋማሽ እንዴት እንደነበሩ ማስተዋወቃቸው ይታወሣል፡፡ በተጨማሪም በጥንታዊ የግሪክ ፣ የሮማውያንና የዓረብ የሰነድ መረጃዎች መሠረት በግምት ከ3ሺ. /ቅ.ል.ክ/ እስከ 1400 ዓመተ ምህረት ድረስ ላሰው የታሪክ ወቅት ስለ አፍሪካ ቀንድ ምስራቃዊ ጠረፍና በህንድ ውቅያኖስ ዳርቻ ስለሚገኙት የጠረፍ ቀበሌዎች የተመዘገበ ታሪክ እስካሁን አልተገኘም፡፡" በማለት የአካባቢው ማህበረሰቦች ከ800 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 14ኛው ክፍለ ዘመን በመጠኑ መታወቅ መጀመራቸውን ይነግሩናል፡፡

የግሪክ ፣ የሮማውያንና የዓረብ ፀሃፊዎች ኢትዮጵያና አዛንያ / ዘንጅ / የተሠኙ ሁለት ሉዓላዊ መንግስታት በሰሜን ምስራቅ የአፍሪካ ክፍለ ሃገር መኖራቸውን አረጋግጠዋል፡፡ ፀሃፊዎቹ በአፍሪካ ቀንድ ምስራቃዊ ጠረፍ የነበሩትንና በማእከላዊ አስተዳደር ስር ያልተሠባሰቡትን አያሌ ቀደምት ማህበረሰቦችን በጥቅሉ "ትሮጀሌዳውያንና በርበራዊያን" በሚል ስያሜ ይጠሯቸው ነበር፡፡ እነዚህ የግሪክና የሮማ ፀሃፊዎች በአፍሪካ ቀንድ የተለያዩ ነባር ጎሣዎችንና ማህበረሰቦችን መሠረታዊ የጎሣ፣ የስም፣ የቋንቋ፣ የመልክና የዘር ገፅታዎችን በውል ለይተው አለመግለፃቸውም ይታወቃል፡፡

ከዚህ ይልቅ የመረጡት አጠቃላይ የህ/ቡን የአኗኗር ባህልን መግለፅና አካባቢውን መጠቆም ብቻ ነው፡፡ ይህም በሚመዝቡት የምግብ አይነትና የአሠፋፈራቸውን ሁኔታ በመግለፅ የተወሰነ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ በኋለኛው ዘመን ግን ማለትም በመካከለኛው ዘመን የነበሩ የዓረብ ፀሃፊዎች ከአዛንያ / ዘንጅ/ በስተቀር በዚህ ክፍለ አህጉር ተበታትነው የሚገኙት ነገዶችና ጎሣዎች የኢትዮጵያ ማዕከላዊ መንግስት ገባሪዎች መሆናቸውን በስፋት ፅፈዋል፡፡

" የግብፅ ፈርኦኖች የግሪክና የሮማውያን እንዲሁም የመካከለኛው ዘመን የዓረብ ፀሃፊዎች የእውቀት አድማስ በሰሜኑ ኢትዮጵያና ጠረፍ አካባቢዎች ላይ ብቻ የተወሰነ በመሆኑ ያቀረቡት መረጃ ከአስራ አራተኛው ምዕተ ዓመት በኋላ ማህበረሰቦቹ ከማዕከላዊው የአፄ መንግስት ግዛት ጋር እስከ ተጠቃለሉበት ጊዜ ድረስ ስላለው ባህላቸውና የእድገት ደረጃቸው ለማወቅ አይረዳም" የሚሉት ኘ/ር ላጵሶ " በአንፃሩ በቅድመ ታሪክ ሳይንሣዊ



ጥናት በደቡቡ ኢትዮጵያ የሰውን ልጅ የመማሪያ ፣ የምርት ፣ የአስተሣሰብ ፣ የባህልና ፣ የአደረጃጀት ዕድገት የሚያስረዱ መረጃዎች ገኝተዋል፡፡ ብዙ ከድንጋይ የተሰሩ ጥንታዊ የዋሻ ውስጥ ስዕሎችና የመቃብር ላይ ሃውልቶች በደቡብ ምስራቅ ማለትም በአዋሽ ጨርጨር አካባቢ / በድሬዳዋ አጠገብ/ በአርኪዮሎጂ ምርምር ተገኝተዋል፡፡

ዘመኑም እስከ 3700 አመታት ይገመታል፡፡ ለምሣሌ በሃረርጌ በለገኦዳ ዋሻ ድንጋይ ላይ የተቀረፀውና 3500 እድሜ እንዳለው የሚገመተው ጥንታዊ የእንስሣትና የሰዎች ስዕል እንዲሁም በሲዳሞ በ "ሻቤ ዋሻ" ድንጋይ ላይ የተቀረፀውና 3000 ዓመት እድሜ እንዳለው የሚገመተው ተመሣሣይ የእንስሣት ስዕል በሰሜን ኢትዮጵያ እንደተገኙት ታሪካዊ ማስረጃዎች በዚህ አካባቢ ላለን ረጅም ባህልና ታሪክ እንዲሁም የጋራ እድገት ቋሚና ጉልህ ማስረጃዎች ናቸው፡፡

"በዚህ በ14ኛው ምዕተ ዓመት በኢትዮጵያ የአፄ ማእከላዊ መንግስት ግዛት ውስጥ ከመቀላቀላቸው አስቀድሞ የሀርላ፣ ሸዋ፣ ይፋት ፣ እርጎባ፣ ወርጅ ፣ አዳል ፣ ሀድያ፣ ሲዳሞ ፣ ደዋሮ ፣ ፈጠጋር ፣ አራብቢኒ ፣ ሻርካ ፣ ባሌ ፣ ደራ ፣ ወጅ ፣ ጉራጌ ፣ ዳሞት ፣ገንዝና እሞ ልዩ ልዩ ማህበረሰቦች እስከ 1000 ዓመተ ምህረት ድረስ የራሣቸውን አስተዳደራዊ ስርዓት ፈጥረው ይኖሩ እንደነበር ይገመታል፡፡ " በማለት ይገልፃሉ፡፡

በጥቅሉ የኢትዮጵያ የመንግስትነት ስልጣን ከአክሱም ወደ ላስታ ሲዛወር ወደ ደቡብና ወደ ደቡብ ምስራቅ መስፋፋታቸው ቀጥሎ፣ ከላስታ ወደ ሸዋ ሲዛወር ደግሞ የበለጠ ግዛት የማስፋቱን / የመጠቅለልና የማስገበር / ተግባሩን የሸዋ ነገስታታ አጠናክረው እንደቀጠሉበት እንረዳለን፡፡ የተጠቀሱትን የኢትዮጵያ ግዛቶች ይዘው ይኖሩ የነበሩት ዜጎችንና አጎራባች ክልሎችንም የሸዋ ነገስታታ በተለይ በንጉስ አምደ ፅዮን ጊዜ በአንድ አሃዳዊ መንግስት ስር አጠቃሎ ለመግዛት የተቻለበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡

በሸዋ ነገስታት ጊዜ የኢትዮጵያ የግዛት ክልል ቀይ ባህር ፣የኤደን ባህረሰላጤ፣ ህንድ ውቅያኖስና ላይኛው የዓባይ ሸለቆ /ነጭ አባይ / እንደሚያዋስኑት የታወቀ ሲሆን፣ በውስጧ ያሉት የእስልምናና የክርስትና እንዲሁም የሌሎች ሃይማኖት ተከታይ ህዝቦች በማዕከላዊው መንግስት ስር ተጠቃለው የሚተዳደሩ፣ ነገር ግን በየጊዜው ላለመገበርና ራስ ገዝ ለመሆን የንጉሰ ነገስት መንግስቱን ሲወጉ የነበሩ መሆናቸውንም ነው ወደፊት የምናየው፡፡

## ምዕራፍ ፶፫

### የሸዋ ነገስታት

| ተ.ቁ | የነገስታቱ ስምና ስመ መንግስት | በስልጣን ላይ የቆዩበት ጊዜ በዓመት | የገዙበት ዘመን ከ.ክ.ል በኋላ |
|---|---|---|---|
| 1 | ይኩኑ አምላክ /ተስፋ እየሱስ/ | 15 | 1253 — 1268 |
| 2 | እግብዓ ፅዮን /ሠለሞን/ | 9 | 1268 — 1277 |
| 3 | ፅንፌ አርዕድ | 1 | 1277 — 1278 |
| 4 | ህዝበ አሠግድ | 1 | 1278 — 1279 |
| 5 | ቅድመ አሠግድ | 1 | 1279 — 1280 |
| 6 | ጃን አሰግድ | 1 | 1280 — 1281 |
| 7 | ሰብዓ አሠግድ | 1 | 1281 — 1282 |
| 8 | ውድም አርዕድ | 15 | 1282 — 1297 |
| 9 | ዓምደ ፅዮን 1ኛ/ገብረመስቀል/ | 30 | 1297 — 1327 |
| 10 | ሰይፈ አርዕድ/ንዋየ ክርስቶስ/ | 28 | 1327 — 1355 |
| 11 | ውድም አስፈሬ/ንዋዩ ማርያም/ | 10 | 1355 — 1365 |
| 12 | ዳዊት | 30 | 1365 — 1395 |
| 13 | ቴዎድሮስ 1ኛ | 4 | 1395 — 1399 |
| 14 | ይስሐቅ /ገ/ቀል/ | 15 | 1399 — 1414 |
| 15 | እንድርያስ/እስክንድር/ | 6 ወር | 1414 — 1414 |
| 16 | ህዝበናኝ /ተክለማርያም/ | 4 | 1414 — 1418 |
| 17 | በድልናኝ /ሰርወኢየሱስ/ | 1 | 1418 — 1419 |
| 18 | አምደእያሱ/ /ዳዊት/ | 7 | 1419 — 1426 |
| 19 | ዘርዓ ያዕቆብ/ ቆስጠንጢኖስ/ | 34 | 1426 — 1460 |
| 20 | በእደማርያም | 10 | 1460 — 1470 |
| 21 | እስክንድር | 16 | 1470 — 1486 |
| 22 | አምደፅዮን 2ኛ | 1 | 1486 —1487 |
| 23 | ናኦድ / እንበሣ በፀር/ | 13 | 1487 — 1500 |
| 24 | ልብነ ድንግል / ወናግ ሠገድ/ | 32 | 1500 — 1532 |
| 25 | ገላውዴዎስ /አፅናፍ ሠገድ / | 19 | 1532 — 1551 |
| 26 | ሚናስ / አድማስ ሠገድ/ | 4 | 1551 — 1555 |



## ከይኩኑአምላክ እስከ ውድማርዕድ

## ከ1253 — 1297

የመጀመሪያው የሸዋ ንጉሰ ነገስት አፄ ይኩኑ አምላክ ስልጣኑን በአቡነ ተክለሃይማኖት አማካኝነት ስላገኘ በተገባው ቃል መሠረት ውለታውን ሊፈጽም ችሏል። ይህም በጠቅላላው ቤተክህነት በዝርዝር በየአውራጃው ያሉትን ገዳማትና አብያተ ክርስቲያናት፣ መነኮሳትና ቀላውስት ካህናቱን የሚያስተዳድሩበት በማለት አፄ ይኩኑአምላክ የመንግስቱን ሲሶ / ከሦስት አንድ እጁን/ በመሃላ ሰጣቸው።

እዚህ ላይ ስለ አቡነ ተክለሃይማኖት ታሪክ አጠር ባለ መልኩ ማካተት አስፈላጊ ይመስለኛል። ስለራሳቸው ታሪክ የሚገልጸውም ገድለ ተክለሃይማኖት የሚባለው ጽሁፍ ነው።

አቡነ ተክለሃይማኖት በቡልጋ አውራጃ ሀጋ ዘአብ ከተባሉት አባታቸው እና እግዚ አርእያ ከተባሉ እናታቸው የተወለዱ ናቸው። በዘመኑ ሐይማኖታዊ ትምህርት አድገው የዲቁና ማዕረግ ፣ ከዚያም የምንኩስና ማዕረግ ተቀብለው በሸዋ በዳሞትና በአካባቢው እየተዘዋወሩ ወንጌልን እየሰበኩ ኖረዋል።

በዚሁ በ12ኛው ክ/ዘመን አጋማሽ ዓመታትም በኢትዮጵያ የሸዋ ክርስቲያኖች ከአዳሎች ሙስሊሞች ጋር ተጣልተው ስለተዋጉና ስላጠቋቸው ይህን ጉዳይ የግብጽ ሡልጣን ሰምቶ ከግብፅ ወደ ኢትዮጵያ ጳጳስ እንዳይመጣ ከለከለ። ስለዚህ የጵጵስናው ቦታ ለዓመታት ባዶ በመሆኑ ቅስናም ዲቁናም የሚሰጥ በመጥፋቱ በኢትዮጵያ ቤ/ን ላይ ችግር ተፈጠረ። በዚህ ምክንያት ክርስትና ጨርሶ እንዳይጠፋ ተባለና ሊቃውንቱም ከየገዳማቱ እና አድባራቱ ተሰብስበው "ከግብፅ ጳጳስ የምናስመጣበት ጊዜ እስኪገኝ አንድ ኢትዮጵያዊ ጥሩ ስነምግባር ያለው እና በሃይማኖቱ የፀና፣ ቀና የሆነ ሰው እንምረጥ" ብለው ወሰኑ። በዚህ ጊዜ የአቡነ ተክለሃይማኖት ምግባርና እየዞሩ ማስተማራቸው በሁሉም ዘንድ ስለሚታወቅ መረጧቸው። ከዚህ በኋላ ከቀድሞ ክብራቸው ላይ የጵጵስና ስልጣን ሲጨምሩ መንፈሳዊ ስልጣናቸው በመላ ኢትዮጵያ ተዘረጋና ተወዳጅ መንፈሳዊ ሰው መሆን ቻሉ።

የኢትዮጵያን ዘውድና ዙፋንም ከዛግዌ ዘር ከነአኩቶለአብ ወደ ሰለሞን ዘር ወደ ይኩኑአምላክ እንዲዛወር ያደረጉት በዚሁ ጊዜ ነው። ይኩኑ ዓምላክን በጵጵስናቸው ቀብተው ያነገሷቸውም እራሳቸው ናቸው። ከዚያም በጵጵስና ዓመታትን አሳልፈው ይኩኑአምላክ ከሞተ በኋላ በአፄ ያግብዓ ዘመን በግብፅ ክሲፋ ፊታድ ጳጳስ ተሾሞ አባ ዮሐንስ የሚባሉት ወደ ኢትዮጵያ ስለመጡ አቡነ ተክለሃይማኖት የጵጵስና ስራቸውን ያለ

እንዳች ማንገራገር ለአዲሱ ጳጳስ አስረክበው እራሳቸው ወዳሰሩት ገዳም ወደ ደብረ አስቦ /በአሁኑ አጠራር ወደ ደብረሊባኖስ/ ሄደው ሲኖሩ በነሐሴ 24 ቀን 1269 ዓ.ም. አረፉና በዚያው በራሳቸው ገዳም ተቀበሩ። የኖሩትም 110 ዓመት ነው። በዘመናቸው የፈጸሟቸው በርካታ መንፈሳዊ ሥራዎች በመኖራቸውም የኢትዮጵያ ተዋህዶ ቤ/ን አንድ ዕለተ በዓል በመስጠት በ24 አስባቸው ስትውል፤ የቆስጠንጥንያ ቤ/ን ሳይቀር ከዓዲቆቿ ተርታ አሰልፋ ታከብራቸዋለች። አብያተ ክርስቲያናት በብዙ ቦታዎች ታንጸው ጽላትም ተቀርጾላቸው ሲታሰቡ ሲኖሩ የቻሉትም እጅግ በርካታ መንፈሳዊ ሥራ በመስራታቸው መሆኑን በቀላሉ መገንዘብ ይቻላል። አቡነ ተክለሃይማኖት ከመንግስት ግዛት ከሦስት እጅ አንዱ ለቤ/ን እንዲሆን የሚያደርገውን አሰራር ተክለው ከይኩኑአምላክ ጀምረው ባሉት ጊዜያቶች እንዲቀጥሉ አድርገዋል።

አፄ ይኩኑአምላክ የተደላደለ መንግስቱን በ1253 ዓ.ም. በመያዝ ኢትዮጵያን ለ15 ዓመታት አስተዳድሯል። ከሰለሞን ዘር የተረፈ ብቸኛው ሰው እንደነበረም ይታወቃል። በዚህ ምክንያት ተስፋ እየሰሰ የነበረውን ስሙን ይኩኑአምላክ ያሉትም አምላክ ይሁንህ ለማለት ነው ይባላል።

የኢትዮጵያ መንግስት መቀመጫ ከላስታ ወደ ሸዋ ሲዛወርም ይኩኑአምላክ የመንግስቱን መቀመጫ ያደረገው በተጉለት አውራጃ /በአንኮበር/ ነው።

ወደ አባቶች ወደ ጥንታዊቷ ከተማ ወደ አክሱም ሳይመለስ የቀረበት ምክንያትም በሁለት ተከፍሎ የሚታይ ሲሆን፤ በሰሜን ኢትዮጵያ ዙፋኑ ወደ ሸዋ መዞሩ ቅር ያላቸው የአገው ወገኖች ወይም ዙፋን ለመውሰድ የሚመኙና የሚፈልጉ ፈላጊዎችን በመፍራት፤ በሌላ በኩልም ንጉስ ይኩኑአምላክ እኔንም አባቶቼንም በስደትና በመከራችን ጊዜ በደስታ ተቀብሎ ያስተናገደንን ፤ እሁንም የአባቶቻችን ዙፋን ለማግኘት ያበቃንን የሸዋን አገር ለቅቄ አልሄድም ብሎ እንደሆነ ይገመታል። አንኮበርን የቆረቆረው ይህ ንጉስ ከአዳሎች ጋር በመዋጋቱና ከግብጽ ሱልጣኖች ጋር በመቀያየሙ ሳቢያ ፊቱን ወደ እየሩሳሌም ለማዞር ተገዶ ነበር። ከኢየሩሳሌም ጳጳስ ጋርም የደብዳቤ ልውውጥ አድርጓል። ሆኖም ጉዳዩን ዳር ሳያደርሰው በ1268 ዓ.ም. ስላረፈ ልጁ አግብአፅዮን ተተክቷል። እንግዲህ የመጀመሪያው የሸዋ ንጉስ ይኩኑአምላክ መሆኑን ካየን ከእሱ በኋላ ከተተካው ከንጉስ አግብዓጽዮን እስከ አምደፅዮን ያሉትን በዚሁ ምዕራፍ አጠቃለናቸው ማለፍ ግድ ይለናል። ምክንያቱም ተከታታይ 5 ነገስታቶች አንድ አንድ ዓመት የገዙና ስፊ ታሪክ የሌላቸው በመሆኑ ነው።



አፄ አግብአጽዮን /ስመ መንግስቱ ሰለሞን/ የአፄ ይኩኑአምላክ ልጅ ነው። አባቱ ይኩኑ ዓምላክ ከአዳል ሙስሊሞች ጋር በመዋጋቱ ከግብፅ ባለስልጣናት ጋር የነበረውን ጥሩ ያልሆነ ግንኙነት አድሶ ሙስሊሞችን በጥሩ አመለካከት ያያቸው ጀመር።

በዚህ አቋሙ በአባቱ ጊዜ የተከለከሰውን ጳጳስ ሊልኩለት ችለዋል። በዘመኑ ከእርስ በርስ ግጭት ነፃ የሆነ 9 ዓመታትን ገዝቶ ከመሞቱ በፊት በተናዘዘው መሠረት 5ቱን ልጆቹን አንድ አንድ ዓመት ብቻ እንዲነግሱ አድርጓል።

በዚህ መሠረት ጽንፈ አርእድ አንድ ዓመት፣ ህዝበ አሰግድ 1 ዓመት፣ ቅድመ አሰግድ 1 ዓመት ፣ ጃን አሰግድ 1 ዓመት፣ ሰብዓአሰግድ 1 ዓመት ኢትዮጵያን አስተዳድረዋል።

ከዚያም የይኩኑአምላክ ሌላ ልጅ የአግብዓጽዮን ወንድም አጎታቸው ውድማ አርዕድ ነግሶ ኢትዮጵያን ለ15 ዓመታት ሊያስተዳድር ችሏል።

## ምዕራፍ ፵፩

## የአፄ አምደፅዮን ዘመነ መንግስት

## ከ1297 — 1327 ዓ.ም

አፄ አምደፅዮን የአፄ ውድማርዕድ ልጅ / የይኩኑአምላክ የልጅ ልጅ / ሲሆን፤ ኢትዮጵያን ለ30 ዓመታት ያስተዳደረ ንጉስ ነገስት ነው። ስመ መንግስቱ ገ/መስቀል ይባላል።

ይህ ንጉሰነገስት የጠፋውንና የተበታተነውን የኢትዮጵያን ታሪክ እንደገና በማደራጀት ለትውልድ እንዲተላለፍ የተቻለውን ያህል የጣረ ንጉስ ነው። በዚህና በድል አድራጊነቱ ስመ ጥር የሸዋ ንጉስ ሆኗል። የመጀመሪያ ስራው ያደረገውም ይህንኑ ታሪካዊ መረጃዎችን መሰብሰብ ፣ በአረብ ፀሐፊዎች እና በሌሎች የውጭ አገር ሰዎች የተፃፉትን ሁሉ እያስተረጐመ ፣ የተገኙትን እያደሰ ፣ ሙሉ በሙሉ የጠፉትን እያጠያየቀ ክምላ ጐደል የኢትዮጵያ ታሪክ እንዲጻፍ አድርጓል።

እንደበርካቶች የታሪክ ፀሐፍት ስምምነትም የዚች አገር ታሪክ ተሸራርፎም ቢሆን መገኙቱ እና ለትውልድ መቅረት መቻሉ በአፄ አምደ ፅዮንና በአፄ ዘርዓያዕቆብ ብርታት ነው።

አፄ አምደ ጽዮን በዘመኑ ረጅም የተባለውን ጦርነትም አካሂዷል።

ከይኩኑአምላክ ጀምሮ አንገዛም እያሉ እየሸፈቱ ይዋጉ የነበሩት የይፋት ወላስሞች ሲሆኑ፤ እነሱም ምንጫቸው እና አቋማቸው እንዲህ ይገለፃል።

የሚኖሩበት ቦታ ይፋት ፣ ሃድያ ፣ ደዋሮ ፣ አዳል . . . የሚባለው ነው። እነዚህ ህዝቦች በዛግዌ ዘመነ መንግስት ጊዜ የሚኖሩበት ቦታ ከላስታ ይርቅ ስለነበር የዛግዌ ነገስታቶች አንዳንድ ጊዜ ጦር እየላኩ ያስገብሯቸው ነበር። እንዲሁም ተዋግተው እየመለሱ ሳይገብሩ በየራሳቸው ባላባት እየተመሩ ነበር የሚኖሩት።

አሁን ደግሞ የኢትዮጵያ ነገስታት መናገሻ ከተማ ሸዋ ስለሆነና ለነዚህ አገሮች ቅርብ ስለሆነ የይፋት የደዋሮ የአዳል ህዝቦችን በቅርብ ሆኖ ማስገበር ግድ ሆነ። እነሱም በእምቢታቸው ገፉበት። እራስ ገዝ መሆን እንደሚፈልጉም ገለጹ። ሆኖም የኢትዮጵያ ግዛት በአንድ ማዕከላዊ መንግስት ስር መጠቃለል አለበት የሚሉት ነገስታት አቋማቸውን ሊቀበሏቸው አልቻሉም።

እነዚህ ኢትዮጵያዊያን የአዳል ፣ የይፋት ፣ የደዋሮ እንዲሁም የባሌ እና የሐድያ ነገዶች ከጥንት ጀምሮ የራሳቸውን ልዩ ልዩ አምልኮና ባህል ይዘው ይኖሩ የነበሩና የአክሱምና የዛግዌ ነገስታቶች በሩቅ ስለሚገኙ አንድ አንድ ግዜ ምቹ ጊዜ ሲገኝ ብቻ የማዕከላዊው መንግስት እያስገበራቸው ኖረው፤ የአረቦቹ ሃይል በምስራቅ በኩል በየመን እና በሳውዲ አረቢያ፤ በሰሜን በኩል በግብፅና በመካከለኛው ምስራቅ በገነነበት ጊዜ ከአረቦች የመጣ



የሙስሊም መምህር መሪ ባላባቶቻቸውን እያስተማረ ወደ እስልምና የመለሳቸው እንደሆኑ እና ከፊሎቹም ከአረብ ነዥዎች ጋር ሳይጣጣሙ ቀርተው የመጡ እንደሆኑ ነው የሚታወቀው።

ስለዚህ ሃይማኖቱን ተቀብለዋልና ከአረቦቹ በሚያገኙት እርዳታ እየታገዙና በራሳቸው ባላባት እየተመሩ ሊያስገብራቸው የሚመጣውን የንጉሱን ጦር እየመለሱ ቆይተዋል። ባላባታቸውም ወላስማ የሚል መጠሪያ አለው። ባጠቃላይ ግን በጥንቱ አጠራር የይፋት፣ የደዋሮ፣ የባሌ፣ የፈጠጋር፣ የደንከል፣ የአዳል ባላባትና ነገዶች በመባል ነው የሚታወቁት። ወላስማ በሚለው የነገዱ ባላባት መጠሪያ መነሻነትም የይፋት ነዋሪዎች ወላስሞች እየተባሉ ይጠሩ ነበር። ከነዚህ ውስጥም የይፋቱ የወላስማ ነገድ፤ በአፄ አምደ ፅዮን ዘመን እጅግ የበረታ ሆኖ ነበር። እነዚህ የኢትዮጵያ አውራጃ ነገዶች በደቡብና በምስራቅ ከሚገኘው ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ልዩነት የላቸውም። ስለዚህ ጦርነቱ የርስ በርስ ጦርነት ነው። ሲጀመርም የ"ገብር" "አልገብርም" ግጭት እንጂ ሐይማኖታዊ ይዘት አልነበረውም። ነገር ግን የሌሎቹ የአረብ አገራት ተወላጆች ቀስ በቀስ እየመጡ በሃይማኖት ሽፋን የበላይ መሪና አማካሪ እየሆኑ እርዳታም እየሰጡ አንድ ህዝቦችን ማዋጋት ጀመሩ።

የይፋት ባላባት ሌሎችን ባላባቶች በስሩ አድርጎ በማዛቱ በይፋት እንደ ንጉስ እየተቆጠረ ይገዛ ጀመር። የይፋት ወላስማ የሚባለው በኋላ ላይ ወደ ሐረርጌ ከመዛሩ በፊት በዚያው በይፋት የነበረ ሲሆን፤ የመጀመሪያው ባላባት ዑመር ወላስማ አራት ልጆች ነበሩት። እነሱም ባዚዩ ሐቅ አድዲን ፣ ሁሴን ፣ ናስር -እና አድዲን ደራደር የሚባሉት ናቸው። ከነዚህ ውስጥ ባዚዩ- መንሱርንና ገማል አድዲንን ሲወልድ ፣ መንሱር ዳልሁይን ፣ ዳልሁይን ሰብረዲንን ይወልዳል። እነዚህ ሁሉ የወላስማ ባላባትነትን እየያዙ የየራሳቸውን ጦር እያደራጁ ለረጅም ምዕተ ዓመት ከሸዋ ነገስታት ጋር የተዋጉ ናቸው። አንዱ ሲሞት አንዱ እየተተካ የመሪነቱን ስልጣን እየያዘ የቀጠለ ሲሆን፤ መሪዎቹና ሹማምንቱ ከኢትዮጵያ ወደ ዓረብ ሐገራት ወደ መካ መዲና እየሄዱ ከሐይማኖት ወንድሞቻቸው ጋር እየተመካከሩ እርዳታም እያገኙ ነው ሲታገሉ የኖሩት። በይፋት የሚኖሩት በወላስማ የሚመሩት ሙስሊሞች ከአፄ አምደፅዮን በፊት እንብዛም የገነኑ አልነበሩም። ዑመር ወላስማ መሪያቸው ከሆነ በኋላ ግን ጠንካራ መደራጀት ያደረጉበት ወቅት ሆኗል። የይፋቱ ወላስማ የዑመር ተከታይ ሃቅ አድዲን የተባለው ልጅ ነው አሁን ከንጉሱ ጋር የተፋጠጠው። አፄ አምደ ፅዮን ደግሞ ከነዚህ ህዝቦች ጋር ልክ እንደ አባቱ እንደ አፄ እግብዓፅዮን ተስማምቶ ሊተዋቸው አልቻለም። በተለይም አፄ ይኩኑአምላክ ደፋቶችንና አዳሎችን ለማስገበር ሲል ሃይል ተጠቅሞ ስለነበር ከዓረብ ነጋዎች ጋር ፀብ ተፈጥሮ የነበረ ሲሆን፤ ቀጥሎ ደግሞ ስምምነት ነበርና አሁን በአምደ ፅዮን ጊዜ ደግሞ መልሶ ግጭቱ በማገርሸቱ እነዚህ ህዝቦች የበለጠ እርዳታ ከአረቦቹ ሊያገኙ የቻሉበት

አጋጣሚ ተፈጠረ። አፄ አምደፅዮን የአረቦቹን እርዳታ በተመለከተ በተደጋጋሚ ደብዳቤ የፃፈ ሲሆን፤ ከነዚህ ውስጥም አንዱ እንዲህ የሚል ነው፡ "ሸፍተቹን መርዳት ካላቆማችሁ እና በግብፅ የሚኖሩትን ክርስቲያኖች ከመጫን ካልተቆጠባችሁ የአባይን ውሃ አስገድቤ ወደ ግብፅ እንዳይወርድ አደርገዋለሁ" የሚለው ይገኝበታል። ሆኖም ለውጥ አልነበረም። ይልቁንም ግጭቱ እየተባባሰ ሄዶ ከአምደ ፅዮን ተልከው ወደ እየሩሳሌም የሚጓዙትን መልዕክተኞችም እየያዙ ያጉላሏቸው ጀመር።

ከአፄ አምደፅዮን ጋር የተደረገው የመጀመሪያው ጦርነት መነሻም በዚሁ በመልዕክተኛ እገታ የተነሳ ሲሆን ታሪኩ እንዲህ ይገለፃል።

የአፄ አምደፅዮን ዋና መልዕክተኛ ከኢትዮጵያ በዘይላ በኩል አድርጎ ለማለፍ ሲሞክር የአዳሉ ባላባት ይዞ አስሮ ካቆየው በኋላ ለይፋቱ ባላባት ለሐቅ አድዲን አሳልፎ ላከለት።

ሃቅ አድዲንም መልክተኛውን ተቀብሎ ሲያንገላታው ከቆየ በኋላ እንዲገደል አደረገ። ይህን ጉዳይ ሲሰማ አምደፅዮን እጅግ ስለተናደደ በየአገሩ ያለውን ዋናውን ጦር ሳይሰበስብ ለጊዜው አጠገቡ ያለውን ጦር ብቻ ይዞ በ1300 ዓ.ም. ላይ ከተጉለት ተነስቶ ወደ ይፋት ተጓዘ።

አምደፅዮን የመጀመሪያውን ጦርነት በይፋት ሲያደርግ ሰራዊቱ ያገኙትን የይፋት ተዋጊ ጦር እየተዋጉ መንደራቸውን እያቃጠሉ ዘረፋም ፈጸሙባቸው። በዚህ ድንገተኛ ጦርነትም የይፋትና የአዳል ጦር በአንድነት ሆኖ በዋናው ባላባት በሃቅ አድዲን እና በተከታይ ወንድሙ በደራደር እየተመሩ ከንጉሱ ጦር ጋር ውጊያ ገጠሙ።

ንጉስ አምደፅዮን ፈረሱ ላይ ሆኖ ሲዋጋ ደራደር የተባለውን የሐቅ አድዲን ወንድም ጦር ወርውሮ ስለወጋው፤ ዋና መሪያቸው ተወግቶ ያዩት ተከታዮቹ ሽሽት ጀመሩ። ብዙዎቹን እየተከተሉ ሲወጓቸው፣ የቀሩት እየሸሹ ሲያመልጡ፣ ገሚሱ እጁን ሲሰጥ ፣ ዋናው አዝማችና መሪያቸው የሆነው ባላባት ሐቅ አድዲን ተማርኮ ንጉሱ ዘንድ ቀረበ። ከዚህ በኋላ ግድያውና ዘረፋው ቆሞ ሃቅ አድዲንም ታሰረ። አምደ ፅዮንም በሐቅ አድዲን ምትክ ለይፋትና ለፈጠጋር ግዛት ሰበንአድ የሚባለውን ሾመላቸው። ሰበንአድ ማለት ወገኖቹ እንገብርም ብለው በሚዋጉበት ጊዜ ለንጉሱ ታማኝ ሆኖ የቆየ እና የሐቅ አድዲን የወንድሙ ልጅ የነበረ ነው። የይፋት እና የፈጠጋር ህዝብም የተሾመው ገዥ ከዚያው ከዑመር ወላስማ ስለወረደ ተቃውሞ ሳያሰሙ ተስማሙ።

አምደፅዮን ይህን መሰሉን ዘዴ ተጠቅሞ አልገብርም ያለውን አገር በጦር አሳምኖ ሹመቱን አደላድሎ ከጨረሰ በኋላ በደስታ ወደ ዋና ከተማው ወደ ተጉለት ተመለሰ። ይህን የመጀመሪያውን የአፄ አምደፅዮን የጦርነት ታሪክ እንማርኮ ፖሎ ፣ አልማቅሪዝ ፣ ጀምስ ብሩስ ፣ ሬኔ ባሴት ፣ ሞሪዮ ኩልቦና ሌሎች የአገር ውስጥ ፀሐፍት እንተክለፃዲቅ መኩሪያ ፣ አለቃ ታዬ



እንዲሁም በግእዝና በአረብ በተፃፈ የኢትዮጵያ ታሪኮች ውስጥ በስፋት ተዘርዝሮ የሚገኝ ነው።

እናም ሐቅ አድዲን በእስር ቤት እንዳለ ሞተ። ይህ ጦርነት ፍፃሜ እንዳገኘ ቆይቶ ደግሞ "በይፋት ወላስሞች ላይ ነግሻለሁ" በማለት ቀደም ሲል ከጠቀስናቸው የዑመር ወላስማ አንዱ የሆነው ሰብረዲን ተነሳ።

የሰብረዲን አነሳስም እንዲሁ ነፃ ለመሆን እና ላለመገበር ሳይሆን፤ ከዚያ ባለፈ አፄ አምደፅዮንን ጥሎ በመላ ኢትዮጵያ ውስጥ ለመንገስ ሆነ። ከእርሱ ጋርም የደዋሮው የአዳሉ ፣ የሐድያው ባላባቶች ያበሩለት ሲሆን፤ በተጨማሪም የደራ ፣ የሞራ፣የሻርቃ፣ የእስቴ ፣ የበስላ ፣ የሐገራ ፣ የፈድሌ ባላባቶች ሁሉ አብረውት ሆነው ነበር። የነዚህ ሁሉ ግዛቶች መጠሪያ ስም የብዙዎቹ በዚህ ዘመን የተለወጠ ሲሆን፤ ጥቂት አውራጃዎች ብቻ በቀድሞ መጠሪያቸው የሚጠሩ ናቸው። ነገር ግን በአሁኗ ኢትዮጵያ ግዛት ስር የሚገኙና ከሸዋ በስተምስራቅና በስተደቡብ የሚገኙ አውራጃዎች ናቸው። አንዳንዶቹ በዛሬው አጠራር በደንከል ፣ በአውሳ ፣ በአዳል /አፋር/ ፣ በዑጋዴን ፣በባሌ ፣ በአሩሲ፣ በሲዳሞና በቦረና አካባቢዎች የሚገኙ ነገዶች ናቸው።

ሰብረዲን በደንብ ተደራጅቶ ይባስ ብሎ በአካባቢው በሚገኙ አገሮች መሳፍንት እና መኳንንት እየደለደለ ሹም ሽር ያደርግ ጀመር። በተጨማሪም ሰብረዲን ኢትዮጵያን በሙሉ ይገዛ መስጊዶችን እተክላለሁ ፣ ህዝቡን ወደ እስልምና እመልሳለሁ ፣ ከዚያም በቅዱስ ቁርዓን ሕግ ሕዝቡን አስተዳድራለሁ በማለት አወጀ።

አፄ አመደፅዮንም የዚህን አወጃ ወሬ ሲሰማ በንዴት እንዲህ ብሎ ላከበት "ይህ የምሰማው ነገር እውነት ነውን? ከዚህ ቀደም ሐቅአድዲን አንድ መልዕክተኛችንን ስለገደለ ያደረኩትን አይተሃል። ዘርህን ደራደርንም መግደሌን ታውቃለህ፤ አሁንም አንተ የኔን ወገን አንድ ብትገድል እኔ ያንተን ወገን 10 እገድላለሁ ፣መቶ ብትገድል ሺህ እገላለሁ" ብሎ ላከበት።

ሰብረዲን ይህን ሲሰማ እንዲህ የሚል ምላሽ ላከ "አንተ ዘንድ መጥቼ በፊትህ አልቆምም፤ አንተ እኔ ዘንድ ብትመጣ ግን አልፈራህም። በጦር በጎራዴ በቀስት በሰይፍ የሚዋጋ ካንተ የበለጠ ሰራዊት አለኝ፤ ስለዚህ መንገዱ ክፍት ነውና ናና ጦርነት እንግጠም፤ አንተ ያልመጣህ እንደሆን ግን እኔ እመጣለሁ"።

ሰብረዲን ይህን ምላሽ ከላከ በኋላ የጦር ሰራዊቱን እና ሹማምንቱን እያደላደለ ዝግጅት ያደርግ ጀመር። ከዚያም ሰራዊቱን በሦስት ክፍሎ ሁለቱን ወደ ሌላ አቅጣጫ እንዲሄዱና እንዲዋጉ ላከ። እራሱ ግን ወደ ንጉሱ አምደፅዮን ወደ ሸዋ /ተጉለት / አመራ።

አምደፅዮንም በ :መሳሳይ ለጦርነቱ መዘጋጀት ጀመረ። ጦር ሰራዊቱን እንዲዘጋጁ ካዘዛቸው በኋላ ከቤተ መንግስቱ ግምጃ ቤት ወርቆችንና ብሮችን

እያወጣ ከተራ ወታደር እስከ ታላላቅ የጦር አዝማቾች ድረስ በሽልማትና በስጦታ አስደሰታቸው።

የካቲት 24 ቀን 1315 ዓ.ም. ጥቂቶቹን ሰራዊት ወደ ሰብረዲን ልኮ ዋናውን ጦር ወደ ኋላ በማስቀረት ቆይተው እንዲከተሉ አድርጎ ላካቸው። ቀድሞ የተላከው ጦር የሰብረዲንን ጦር አሸንፎ ጠበቀው፤ ዘግይቶ የሄደው ዋናው ጦር ሲደርስም የሸሹት የሰብረዲን ሰራዊቶች በድጋሚ ተደራጅተው ድጋሚ ውጊያው ቀጠለ። ምሽት ላይ የንጉሱ ጦር አሸንፎ ሰብረዲንን ሲማርክ ሲልም ሸሽቶ አመለጣቸው። የንጉሱ ጦርም ከተማውን አፈራርሰው የቤተ መንግስቱን ግምጃ ቤት በመበርበር በርካታ የከበሩ ጌጣ ጌጦችን ዘርፈው ወደ ንጉሣቸው ወደ አምደፅዮን መልዕክት ላኩ "ንጉስ ሆይ ደስ ይበልህ በመንግስትህና በሰራዊትህ ላይ የተነሳውን ጠላትህን አሸነፍነው፤ ከሸሸው በቀር ሁሉንም ፈጀነው፤ እቁባቱንና ሴቱን ምንም ሳናስተርፍ ማረክናቸው ፤ በቤቱ / በቤተ መንግስቱ / የተገኘውን የከበረ ድንጋይ ፣ እንቁ ፣ አልማዝ ፣ ወርቅና ብር የጦር መሣሪያ እና ልብስ ሌላም መቁጠር የማይቻል ነገር ሁሉ ዘርፈናል። ሰብረዲን ግን አምልጦን ሸሸ" የሚል መልዕክት የደረሰው አምደፅዮን ተከታዮቹን ይዞ በመጀመሪያ ሰብረዲን በሦስት ክፍሎ ሁለቱን በሌላ አቅጣጫ ልኳቸው ስለነበር እነዚህን ሰራዊቶች ደምስሶ፣ ወደ አሸነፉት ሰራዊቶቹ ሄዶ ተገናኝቶ ድሉን በሚተርኩለት ጊዜ ሸሽቶ ከሄደው ከሰብረዲን መልዕክት ተላከ "በጌታዬ በንጉሱ ላይ በደልኩ ፣ ክፉ ሰራሁ ፣አሁን ግን በሌላ በባዕድ እጅ ከምወድቅ በንጉሱ እጅ ብወድቅ ይሻለኛልና የፈቀደውን ያድርግብኝ ስለዚህ መምጣቴ ነው . . ." የሚል መልዕክት ላከ። አምደፅዮን መልዕክቱ ሲደርሰውም "ብትመጣም ብትቀርም አያሳዝነንም የትም አገር ብትሄድ እከተልሃለሁ አንተን ሳልይዝ ወደ አገሬ አልመለስም" ብሎ አስላከበት። ሰብረዲንም መጥቶ ንጉሱ ፊት ቀረበ። የአምደፅዮን የወቀሳ ቃል እንዲህ የሚል ነበር። "ለምንድን ነው እንዲህ ያለ ሥራ መስራትህ? ለእኔ የሚገባውን ግብር እና ገፀበረከት ለሌሎች ባዕድ ወገኖች አደልከው ፣ የኔንም የራሴን ገንዘብ ለድሆች የሰጠሁትን ብርና ወርቅ ቀማህ ፣ ከእኔ ጋር/ ከመንግስቴ ጋር/ የማነግዱትን አሰርክ። ከሁሉ የበለጠ ደግሞ ዙፋኔን ተመኘህ።" ብሎ ሲጠይቀው "የፈለከውን አድርግብኝ" የሚል ምላሽ ሰብረዲን ሲሰጥ፤ ከብዙ ሰራዊቶች ዘንድ የ "ግደለው" ድምፅ ቢሰማም አምደፅዮን እንዲታሰር አዘዘና ታሰረ። ከእርሱ ጋርም በመጀመሪያው ጦርነት በንጉሱ ታማኝ ተብለው የተሾሙት ከሰብረዲን ጋር ተባብረው ነበርና አብረው እንዲታሰሩ ተደረገ።

የሰብረዲን ግዛት የነበረው ሁሉ ለራሱ ለሰብረዲን ወንድ ለገማልአዲን ተሰጠው። አምደፅዮን ይህን ድል እንዳገኘም ሆነ ከማግኘቱ በፊት ብጥብጡ ያመቻቸው በሰሜን እና በወገራ፣ በሀስምት ያሉ ፈላሾች ተነስተው በመሸፈታቸው አምደፅዮን በዘመኑ የነበረውን ታዋቂ የጦር አበጋዙን ፀጋ ክርስቶስን ልኮ ሊያሸንፋቸው ችሏል።



የይፋትና የደዋሮ አመጽ ረግቦ ባላባቶቹ ከታሰሩ በኋላ አሁንም ንጉሱ እረፍት አላገኘም። ይልቁንም አምደፅዮን በዘመኑ ፈታኝ ሆኖበት ያለፈው የአዳል ጦርነት ተጀመረ እንጂ።

የአዳሎች ጦርነት አስቸጋሪ የሆነውና ከይፋትና ከደዋሮው የበለጠውም፤ ይፋትና ደዋሮ ለሸዋ ቅርብ ስለነበሩና የህዝቡ ፀባይም ሆነ የከተማው መውጫ መግቢያ በደንብ ይታወቅ ስለነበር ብዙ አለማስቸገሩ ሲሆን ፤ አዳልና ሞራ የሚባሉት አገሮች ግን ከደዋሮ እና ከፈጠጋር ጀምሮ እስከ ህንድ ውቅያኖስ ድረስ የሚደርሰው ሰፊው ግዛትና የአዳል ፣ የአውሳ ፣ የዑጋዴን ፣ የሱማሌ አገር ስለሆነ በህዝቡ ብዛት በአገሩ ስፋትና በርሐማነት ሳቢያ የዚህን አካባቢ ጦርነት አክብዶታል።

የአዳል እና የሞራ ህዝቦች የሚባሉት ከላይ በተጠቀሱት አገሮች የሚኖሩት ኢትዮጵያዊያን አንድነት በመመስረት የክርስቲያኑን ንጉስ አገሩ ድረስ ሄደን ካልወጋነው እዚህ መምጣቱ አይቀርም በሚል መነሻ በመዘመትና ወደ ይፋት በመምጣት የንጉሱ ወታደሮች በተኙበት ደርሰው ጥቃት አደረሱ። ብዙ የቀንድ ከብቶችንም ማርከው አሸሹ። በሁለተኛው እና በሦስተኛው ቀንም ዋናው የንጉሱ ጦር ወዳለበት በማምራት ተመሳሳይ ጥቃት ፈጽመው ድንኳናቸውን አፈራርሰው ብዙ ሃብት ከዘረፉና ከሸሹ በኋላ የንጉሱ ወታደሮች ተከታትለው የተዘረፉትን ንብረቶች ለማስመለስ ቻሉ።

በዚያ ግዛት በሰብረዲን ምትክ የተሾመው ገማል ዲንም "አገሩ ሁሉ ፈራርሶብኛልና በድጋሚ እገነባዋለሁ፤ አንተ ግን ወደ አገርህ ተመለስ" ሲለው አምደፅዮን ደግሞ "አዳሎችን ድል ሳላደርግ መመለስ ክብሬ አይፈቅድልኝም" በማለት ሰኔ 6 ቀን 1315 ዓ.ም. አዳሎችን ለመውጋት ዘመተ። የሰባት አገር ባላባቶችም ተሰብስበው ጠበቁት። የአዳል ፣ የሞራ ፣ የጢቆ ፣ የጳጉማ ፣ የበከላ ፣ የወርገር ፣ የገበላ ባላባቶች ናቸው። ንጉሱ ከነሰራዊቱ እረፍት ባደረገበት ቦታ በሌሊት ሲመጡ ትርምሱ በዛ። የሰባቱ አገሮች ጦር ከመብዛቱ የተነሳ የንጉሱ ሰራዊቶች ፍርሃት አደረባቸው። በሌሊት የተጀመረው ውጊያ በጨረቃ ብርሃን የታገዘ ነበርና የትኛው ጦር የማን እንደሆነ በማይለይበት ሁኔታ በተደረገው በዚህ ውጊያ በርካታ ህዝቦች ከሁለቱም ወገን አለቁ።

አምደፅዮንም ሙሉ የጦር ልብሱ በጉራዴ ተገፎ የወለቀበት ውጊያ የነበረ ሲሆን፤ ለጥቂት በመትረፉ ወደ ሽንፈት ተጠግተው የነበሩት ወታደሮቹ ሁሉ የንጉሳቸውን ወድቆ መነሳት ሲያዩ ብርታት አግኝተው በደስታ ተዋግተው ከሽንፈት ዳኑ። የተቃራኒው ወገን ሰራዊትም ሸሸ። ንጉሱ ተከታትለው እንዲወጓቸው ጥቂት ወታደሮች ልኮ ነበርና የተላኩት የሸሹትን ወታደሮች እና መሣሪያዎቻቸውን ማርከው ተመለሱ። አምደፅዮን በደስታ እየዘለለ ሁሉንም ሰራዊቶች አሰልፎ እጅግ የረዘመና ረጅም ሰዓት የፈጀ ንግግር አደረገ።

ከዚህ በኋላ በተጠቀሰው ዓ.ም በሐምሌ 1 ቀን ከሰራዊቱ ጋር ተነስቶ በመንገዝ ሞራ የተባለ አገር ደርሶ ሰፈረ። አሁንም በሌሊት ሊያጠቁት መጡ።

ሰራዊቶቹም ጥሩንባ እየነፉ እየተጯጯሁ ወደ ንጉሱ በመሄድ "አድነን መጡብን" የሚል ልመናቸውን ሲያሰሙ አምደፅዮን ከድንኳኑ ወጥቶ "አትፍሩ ፀንታችሁ ተዋጉ ብዬ ከዚህ ቀደም ነገርኳችሁ፤ አሁንም እነዚህን አመፀኞች በጽናት ተዋጓቸው። ንጉስ ሰራዊቱን እየጠራ ወደ ጦርነቱ ሂዱ ይላል እንጂ እኔን ወደ ጦርነት ትጠሩኝ ጀመር? ያለኔ መዋጋት አይቻላችሁምን?" ብሎ ተቆጣቸው እና ወደ ጦርነቱ እየመራቸው ከፊት ተሰለፈ። አሁንም ድል ቀንቶት አባረራቸው። ጥቂት ቀናቶች አለፉ፤ ንጉሱም ታመመ "እንግዲህ በንጉሱ እና በሰራዊቱ ላይ የደረሰውን ጦርነት ልነግራችሁ ነውና ስሙ" እኔ አይደለሁም የዘመኑ የዓምደ ፅዮን ዜና መዋዕል ፀሐፊ ነው የሚነግራችሁ ስለዚህ ስሙት።

"ከግንቦት ወር እስከ ሐምሌ ወር ሌሊትም ቀንም እረፍት አልነበረም። ከወገቡም ትጥቁን የፈታ የለም። ንጉሱ አምደፅዮን እንደሌሎቹ ነገስታት ሰራዊቱን ብቻ ወደ ጦርነት ሳይሰድ እራሱ ቀንና ሌሊት ሳይተኛ ትጥቁንም ሳይፈታ ጠንክሮ እየተዋጋ በእግዚአብሔር ሃይል አሸንፎ ከዚህ ቀደም የነበሩት ነገስታት ወደ አልደረሱበት አዳል ወደሚባል አገር ይህን በመሰለ ብርታት ደረሰ። በዚህም አገር ምስራቁና ምዕራቡ አይታወቅም . . . . በዚህም ሳሉ የታቦቱ ድንኳን በተተከለበት ስፍራ ምስራቁ በዚህ ነው ፤ የለም ! ምዕራቡ ነው እንጂ ምስራቁ በዚህ በኩል አይደለም! እየተባባሉ ካህናቱ ይጣሉ ነበር። በዚሁ በክረምቱ መካከል በርሃው እንደእሳት ሰውንም እንስሳትንም ያቃጥል ነበር። ውሃም የለም ቢኖርም በሰው እጅ የተቆፈረ በጉድጓድ የሚገኝ የቆሸሸ ውሃ ነው እንጂ የጠራ የሚወርድ ምንጭ የለም። ይኸውም ሆኖ ያው የሚጠጣው እንደ እርጎ በልክ እየተሰጠ ነው።

ድንጋዩም እንደእሾህ ይዋጋል። የዚህ አገር ሰዎች እግራቸውን ወደ ላይ፣ እራሳቸውን ወደታች ዘቅዝቀው እንደ እግር በእጃቸው ይሮጣሉ። (እንስሳ መስለው ለመቅረብ እና ለማጥቃት?) እንደዚህም እየሆነ ሁል ጊዜ ሌሊት እየመጡ የንጉሱን ጦር ይወጉ ነበር። ነገር ግን እየተሸነፉ ይመለሳሉ። ደግሞ ንጉስ አምደፅዮንን የወጉትን የነዚህን ሰዎች ጦርነት የምነግራችሁን ስሙኝ፤ የእነርሱም ነገስታትና መኳንንት ሰራዊቱን በአንድነት አሰድሞ የተነሳው ነገስታቱም / ባላባቱም/ መኳንንቱም በሲቀ ጳጳስ አምሳል እንደ እግዚአብሄር የሚያከብሩት መጠሪያ ስሙ ሰልህ /ሳልህ/ የሹመት ስሙ ቃዚ /ሳልህ ቃዲ ማለቱ ነው/ የሚባለው ነው። ከእነሱም ጋር ለዚህ ጦርነት የተሰለፉት . . . ." ይልና ፀሐፊው የባላባቱን ስም ዝርዝር ከነግዛት አገራቸው በመቶዎች የሚቆጠሩ ስሞችን ይዘረዝራል። የዋና ዋና መኳንንቱ ብቻ ብዛት 2725 ሲሆን መስጊዳቸው ደግሞ በብዙ ሺዎች የሚቆጠር ነው።

እነዚህ በሰው ሃይል ተቆጥረው እንደማያልቁ ከተነገረላቸውና ተደጋግሞ ብዛታቸው አስገራሚ ስለመሆኑ ከተጻፈላቸው ውስጥም በአምደፅዮን የተሸመው ገማልዲን አብሮ ወግኖላቸው ተሰልፎ ይገኛል።



የተቀሳቀሳቸውም በብዙ ማስፈራራት እና ንጉሱ እንደማያዋጣው በተለያዩ ማስረጃዎች ለማስፈራሩትና ተስፋ ስላስቆረጡት ነው።

በተመሳሳይም የአምደፅዮን ጦር የቀኝ እና የግራ ፣ የፊትና የኋላ ተብሎው የተከፈሉ እንደ አዳሎች ባይሆንም በርካታ ቁጥር ያለው ሰራዊት የአምሐራ ፣ የሸዋ ፣ የጎጃም ፣ የዳሞትና የሁሉም አውራጃዎች ጦር የተሰባሰበበት ነበር።

አዳሎች ገስግሰው መምጣታቸውንና መላው የኢትዮጵ ሰራዊት ፊፅሞ ሊቋቋማቸው እንደማይችል አንድ መልዕክተኛ ገለጸ። ይህንን ንግግር አምደፅዮን ሲሰማ ከመኝታው ተነስቶ ሲወጣ ፈለገ። ሆኖም ህመሙ አላራምድ አለው። አሽከሮቹ እንደምንም የጦር ልብሱን አለበሱት። "ፈረስ ላይ እንኳ በቅጡ መውጣት አትችልምና ይቅርብህ . . ." የሚል የሐዘን ጩኸት ከሚስቱ /ከሁሉቱ ሚስቶቹ/ ተሁነሁረ። አልሰማም። "ድንኳን ውስጥ ተኝቼ ከምሞት ተዋግቼ ብሞት ይሻላል" ብሎ ለጦርነት ተዘጋጀ። ሚስቶቹም በሐሣቡ ተስማሙ።

እዚህ ላይ ያን የቅድመን ተራኪ /በናታችሁ ስሙኝ/ ያለውን የሁራዊቱን ብዛት በምን መልኩ እንደገለፀው የሚያሣየውንና የተጠቀመበትን ቃላት እያየን ታሪኩን እንቀጥላለን።

"እንደ ሁማይ ከዋክብት ፣ እንደ አንበጣ ፣ እንደ ባህር አሸዋ በርክተው በክረምት ሁማይን እንደሚሸፍኑ ደመና መስለው፣ ድምፃቸው ነፋስ እንዳወከው የባህር ማዕበል፣ ቃላቸው በዝናብ ጊዜ እንደሚጮህ መብረቅና ነጎድጓድ ሆኖ በጩኸታቸው መሬትን ፣ ተራራን እየነቃነቁ መጡ።

.አንባቢ ሆይ የምነግርህን ሁሉ ከንቱ /ተረት/ ሳታስመስልብኝ ስማኝ። ለኔ እንደመሁለኝ እነርሱ ሲሮጡ ከነርሱ ጋር ዛፉም ፣ ተራራውም ፣ ጫሬቃውም ፣ ኮከቡም አብሮ የሚሮጥ ነው የሚመስለው። . . . . የብዛታቸውን ነገር የሰው አንደበት ተናግሮ ሊጨርሰው አይችልም። እንኳን ሰው አራዊት የሚሸሽበት ቦታ አጥተው ወደ ንጉስ ሰፈር መጡ።" እያለ ይቀጥላል።

አፄ አምደፅዮን ወደ ጦርነቱ ቦታ በህመም በተዳከመ መንፈስ ሲያመራም ወታደሮቹና ታማኝ ሸማምንቱ እየሸሹ ነበር። ንጉሱንም በትክክል እንዳበደ አድርገው እንጅ በጤነኛ አይምሮ ከዚህ ሁሉ ሁራዊት ጋር እዋጋለሁ የሚል ሰው እንደሌለ ደምድመዋል። የአፄ አምደፅዮን ሚስትም /ሉቴን ሞገሳ/ እንዲሁም ሌላኛይቱ ሚስቱ ፣ እቁባቶቹና አብረውት የተጓዙት ሁሉ በማልቀስ ላይ ናቸው።

የተወለዱትን የንጉሱን ልጅም አይኔ እያየ ከሚታረዱ በማለት ታቦቱ ወደተቀመጠበት ድንኳን ውስጥ ጥላቸዋለች።

አፄ አምደፅዮንን ለማስመለስና አብሮዋቸው እንዲሸሽ ታማኝ ባለሟሎቹ ለምነውት አይሆንም ስላለ እቅፈው እየጎመ ለቀቁትና ትተውት ሲሸሹ ንጉሱ "ትንሽ ቆማችሁ እንደምን እየተጋደልኩ እንደምሞት

ተመልከቱ። አምላክ በእጄ የሚሰራውን ተመልከቱ።" አላቸው። እነርሱ ግን ሽሽታቸውን ቀጠሉ። ከዚያም በከፍተኛ ጩኸት " ወዴት ትሸሻላችሁ ግን ? ዛሬ አገራችሁ በሽሽት የምትደርሱ ይመስላችኋልን? እኔን በጠጅና በሙማ ያሣደግኋችሁን ፣ በወርቅና በሽልማት ያከበርኳችሁን እኔን አታስቡምን?. . ." ይህን ተናግሮ "ዓረብ አስፈሪ" በተባለው ፈረሱ ሽምጥ ጋልቦ ለመሞት ሲሄድ ፈረሠኞች ተከተሉት።

ከሸሹት ውስጥ ግማሽ ያህሉ ተመለሱ። ሌሎቹ በሽሽታቸው ቀጠሉበት።

ንጉሱ ወደ አስፈሪው ጦር ገብቶ በጀግንነት ተዋግቶ ተከታዮችም በተመሣሣይ አግዘውት በእነስተኛ ጦር 6 ሰዓት በፈጀ ጦርነት ንጉሱና ተከታዮቹ አሸንፈው አዳሎች ለመሸሽ ተገደዱ።

ጦርነቱን በተመለከተ ይሔው አስገራሚ ሰው /ስሙ በትክክል አይታወቅም/ "ስሙኝ" ሲለን ነውና የጦርነቱን መደምደሚያ እንስማው።

"አምደፅዮን በእጁ የገደለውን ወታደር ብዛት ብዘረዝርላችሁ ይህ የማይቻል ነው ብላችሁ ነገሬን እንደተረት እንዳትቆጥሩብኝ ትቸዋለሁ።" ይላችኋል።

የሆነ ሆኖ አፄ አምደፅዮን ይህን ድል ማግኘቱን ዜና መዋዕሉ አበክሮ ሲገልፅ፤ ከጦርነቱ ፍፃሜ በኋላ ሲዋጋበት የዋለው እጁ በደም ከጦሩ ጋር ተጣብቆ በግድ መላቀቁን ይገልፃል። ሚስቶቹም ባለማመን ፣ ሠራዊቱም በመደመም ድሉን በቅፅበት አስተጋቡ። አምደፅዮንም ወደ ድንኳኑ ሄዶ ለአምላኩ የምስጋና ስግደቱን ፈፀመ።

ከዚህ በኋላ አምደፅዮን የአዳሉ ባላባት መቀመጫ ወደነበረችው "ሃገረ ተለግ" ወደ ተባለችው ከተማ ከቀናት ጉዞ በኋላ ከጦሩ ጋር ደረሰ። እንደደረሰም ከጦርነቱ ያመለጡት የአዳሉ ንጉስ ወንድምና 3ቱ ልጆቹ "ተገዝንልህ በአገሩ የቀረነው ጥቂት ነንና ተወን አታጥፋን" አሉት። "እንሸነፋለን የሚል ግምት አልነበረንም ይቅር በለን" ሲሉት፤ አፄ አምደፅዮንም መክሮና አስፈራርቶ ለወደፊት እንዲገብሩ ሲያዝ፤ እነዚሁ መሣፍንቶች ለየግዛቱ ባላባት "በሠላም ገብሩ" የሚል ደብዳቤ ፅፈው ቢልኩም ዋናው የአዳሉ ንጉስ ለሌሎቹ እሺ እንዳይሉ አስጠንቅቆ "የሸሹት ሁሉ ተሰባስበው ሌላ ጦርነት ይጀመራል እንጂ አንገብርም" የሚል አቋም የያዘ የ99 መሣፍንት አቋም ይፋ አደረገ። አምደፅዮን አሁንም በብስጭት ወዳሉበት በመሄድ ሌላ አደገኛ ጦርነት ከፈተ። በዚህም በአዳሎቹ ብርታት ንጉሱ ብዙ ሠራዊቱን አጣ። በመጨረሻም ራሱ አምደፅዮን ዋናውን ንጉስ በርቀት ጦር ወርውሮ ወግቶ ገደለውና ይህም ጦርነት በእርሱ አሸናፊነት ተጠናቆ



ራሱ የመረጠውን አስተዳዳሪ ሾሞ ተመልሷል። የይፋትን ፣ የደዋሮንና የአዳልን አካባቢ በጦር ያሣመነው ይህ ንጉስ ከነዚህም በላይ የሆኑ የውስጥ ጦርነቶችን ያስተናገደና በድል የተወጣ መሆኑ በስፋት ይነገርለታል። 30 ዓመት በቆየ ግዛቱም እንደ ሌሎች አባቶቹ ሁሉ በመንፈሣዊ ስራዎች ማለትም ቤ/ያን ማሠራቱንና ሌሎች መሰል ተግባራትን ማከናወኑ ተፅፎለታል።

እኛም "ሰው እንዳይደነግጥና ነገሩ እንዳይበዛ ብለን ብዙ ከመናገርና ከመጨመር ባንታገድ ኖሮ በአዳሎቹና በንጉሱ ሠራዊት ላይ ሌትና ቀን የተደረገውን ጦርነት በብዙ ሲፃፍ በተቻለ ነበር።. . ." በማለት ያ ፀሃፊ እንደገለፀው ሁሉ ፤ የአፄ አምደፅዮን ጀብድ ከዚህም በላይ እንደነበር ነው የሚነገረው።

ከአዳል መልስም በተጉለት ተደላድሎ ቀሪ ዘመኑን በመፈፀም ከዚህ አለም በ1337 ዓ.ም. ሲለይ ልጁ ሀይፈ አርዕድ በመንግስቱ ተተክቷል።

ኢትዮጵያን አንድ ግዛት ሆና እንድትዘልቅና እንዳትከፋፈል ጥግ ድረስ ዘምቶ ጀብድ ስለፈፀመው ስለዚህ ንጉስ የሚያስቃኘውን ታሪክ ከመደምደማችን በፊትም በዘመኑ ስለተገጠመለት ግጥም ጥቂቱን እንየው። ይህም ግጥም በዘመኑ ቋንቋ በግዕዝና በአማርኛ ቅልቅል የተፃፈ ሲሆን፤ የዘመኑን የግጥም አይነት ከማሣየት አልፎ ስለሌሎች ተያያዥ ታሪኮች የሚያመላክተው ነገር ይኖራልና እነሆ።

- "ሐርበኛ አምደፅዮን ፣ መላላሽ የወሰን ፣
  ወሐ እንደመሰን መላላሽ የወሰን ፣
  ከወጅ ዜብደናን ከገንዝ ጠጦን
  ምን ቀረህ በወሰን ከድያ አመኖን
  ምን ቀረህ በወሰን ከባሌ አሲን
  ከደዋሮ ሄደራን ከፈጠጋር ዜላርድን
  ከኢፋት አምበል አቦከርን
  ከግድም የዊሠይን
  ከአንጎት ጎርን አሞራን
  ከአገው ቤተ አጉርርን።
  ከትግሬ ነገደ ክርስቶስ ይውረድ
  አደረግኸው ገንዙን
  እንዲሠራ ደውጀውን
  ማን ቀረህ በወሰን

አላፀፋህው ፊቱን
አልአስማረክሽው ልጅ ሚስቱን፣
ከጎጃም ጃን ከምርን
ከጋፋት አወላሞን
በዳሞት ሞት ለሚን
ማን ቀረህ ከወሰን
ያላፀፋህው ፊቱን
ያላስማረክሽው ልጅ ሚስቱን
ሐርበኛ አምደፅዮን
መላላሽ የወሰን፡፡
ዓምደፅዮን ስም የዘራ
በወጅ እስከ በጥር አሞራ
ቃራ ይነስንስ ቃራ እንደ ጭራ
በወንዶች ገራገራ
በሐድያ እስከ ጉዴላ
በባህር እስከ ኤርትራ
ዓምደፅዮን ስም የዘራ፡፡" ይላል፡፡



## ምዕራፍ ፺፫
## የአፄ ሠይፈ አርእድ ዘመነ መንግሥት
## ከ1327—1355 ዓ.ም

ከአፄ እምደ ፅዮን ቀጥሎ በመላው ኢትዮጵያ የነገሠው አፄ ሠይፈ አርእድ ወይም በስመ መንግሥቱ ንዋዩ ክርስቶስ ሲሆን ለ28 አመታትም ኢትዮጵያን አስተዳድራል፡፡

ሠይፈ አርእድ የአፄ አምደ ጽዮን ልጅ ነው፡፡

የዚህ ንጉሠ ነገስት ታሪክ ነገስት እንደሚለው በግዛት ዘመኑ ወደ ላእላይ ግብጽ ሔዶ በግብር ምክንያት በግብጽ የታሰሩትን ጳጳሳት ተዋግቶ እንዳስፈታቸው ይገልፃል፡፡ ሙሴ ሬኔ ባሴት እና አል ማቅሪዝ /የዓረብ ፀሃፊ/ ከፃፉት ውስጥ በአፄ ሠይፈ አርእድ ዘመን የኢትዮጵያና የግብጽ ሁኔታ ምን ይመስል እንደነበር አጠር አድርገው በየመጽሐፎቻቸው አካተው ይገኛል፡፡

በተደጋጋሚ እንዳየነው የግብጽ ሱልጣኖች በሲቃን ጳጳሳቱ ምክንያት የሚያገኙት ግብር ከፍተኛ ነበርና ሁሉም ዐብ እና ግጭት ጠፍቶ አያውቅም፡፡ አሁን በአፄ ሠይፈ አርእድ ጊዜ ደግሞ ሌላ ተጨማሪ ግብር ስለተጣለባቸው እምቢ ያሉት ለእስር ተዳረጉ፡፡

በዚህ ዘመን የነበሩት  የግብጽ ሱልጣኖች መሊክ ኤስ ሳሊህ እና ሞግዚቱ አሚርሺኩም ነበሩ፡፡ እነዚህም በሊቀ ጳጳሱ ላይ ብቻ ሳይሆን በክርስቲያኖቹና በአይሁዳውያኑ ላይ ቀረጥና ግብር ከመጨመር አልፈው እስራት ስለጀመሩ ከአጼ ሠይፈ አርእድ ጋር መጠነኛ ግጭት ሊፈጠር ቻለ፡፡

በዚህም ምክንያት አጼ ሰይፈ አርእድ ሁኔታውን ለመረዳት ወደ ላእላይ ግብጽ ሠራዊቱን አስከትሎ እስከ ግብጽ ወሰን ድረስ እንደደረሰ ከግብጾች ጋር ውጊያ ተደርጎ ውዲያው እንዲቆም መደረጉ ተጽፏል፡፡

ውጊያው እንደቆመም የግብጽ ሡልጣን በሞግዚቱ መካሪነት እስረኞች እንዲፈቱ አስደርጎ ግጭቱ ምንም ያህል ሳይቆይ ሊቆም ችሏል፡፡ አጼ ሠይፈ አርእድ እንደ ግዛት ዘመኑ ርዝመት ታሪኩ ሠፋ ብሎ ባይገኝም በጥቂቱ ተጽፎ ከተገኘው ውስጥ እንደ አባቱ እንደ አምደጽዮን ከይፋት ወላስሞች ጋር ተዋግቷል፡፡ ከሠብረዲን ሞት በኋላ ልጁ አሊ በአባቱ ስልጣን ተተክቶ ይፋትን ይገዛ ነበርና እርሱም ልክ እንደ አባቱ በአጼ ሠይፈ አርእድ ላይ ሸፍቶ ሲዋጋ ተሸንፎ ተማረከና ግዛቱ ለልጁ ለአህመድ ሐርብ አራድ ተሰጠ፡፡ ይህም የተደረገው አባቱ ከተማረከ በኋላ ልጁ ወደ ንጉሱ መጥቶ እንደማይሸፍት ቃል በመግባቱ ነው፡፡

ከዚያም በምርኮ ተይዞ በንጉሱ ቤት መንግስት በግዞት ይኖር የነበረው አባቱ አሊ ምህረት አግኝቶ ሹመቱን አስመልሶ ወደ ይፋት ሔዶ ሥልጣኑን ከልጁ እንዲረከብ ተነገረው።

ነገር ግን አባትና ልጅ ስላልተስማሙ አጼ ሠይፈ አርእድ ባልቃ ገብቶ ለመሐመድ አንድ ሌላ ትንሽ ግዛት ሰጥቶ አስቀመጠው።

መሐመድ ሲሞትም አባቱ አሊ ዋና ሥልጣኑ ተመልሶለት ስለነበር በልጁ ግዛት ላይ ሌላ ሰው ሾመበት። በዚህ ጊዜ ሁለተኛው ልጁ በወንድሙ ግዛት ባለመተካቱ ከአባቱ ጋር ሌላ ግጭት ፈጠረ።

በዚህ መልኩ እርስ በእርስ ሲናቆሩ ቆይተው በመጨረሻ ወደ ንጉሱ መልዕክት መጣ። ዋናው የይፋት ገዥ የገዛ ልጁን /እንደ ጥቂት ፀሐፍቶች የልጅ ልጁን/ ማሸነፍ ስላቃተው ወደ አጼ ሠይፈ አርእድ የጦር ሰራዊት እርዳታ ይሰጠኝ ብሎ ስላመለከተ ንጉሱ 35 ሺ ጦር ሠራዊት ላከለት። ይህን 35ሺ ጦር የአሊ ልጅ ባልተጠበቀ ሁኔታ አሸንፎ ስለመለሳቸው ሌላ ጦር በድጋሚ ተላከ። ሁሉንም መለሳቸው። አባቱም በጦርነቱ ላይ ሞተ። ከዚሁ በኋላ የአሊ ልጅ ወደ አባቱ ግዛት ወደ ይፋት ገስገሰና የመሪነቱን ቦታ በኃይል ያዘ። በዚያ ዘመን የኢትዮጵያ ሁኔታ ይህን መሰል የእርስ በእርስ ግጭትና ጦርነት፣ የሥልጣን ሽኩቻ፣ የገብር አልገብርም ፀብ፣ ወዘተ... የሚስተናገድባት ፋታ የሌላት ሀገር ነበረች። የእያንዳንዱ ንጉሰ ነገስት የግዛት ዘመን ላይም ጦርነት የግድ የነበረ እስኪመስለን ድረስ ያለጦርነት የግዛት ዘመናቸውን ያጠናቀቁት በጣም ውስን ናቸው። ውድመቱንና እልቂቱንም መገመት ይቻላል። ለስራ ምቹ ጊዜ ያልነበረ መሆኑንም እንደዚያው።

በተረፈ አጭሩ የአጼ ሠይፈ አርእድ ታሪክ ያየነውን ሲመስል በ1355 ዓ.ም ሲሞት ልጁ ውድም አስፈሬ ነግሶ ኢትዮጵያን ለ10 ዓመት ያህል አስተዳድሯል። የአጼ ውድም አስፈሬ የግዛት ዘመን ምን ይመስል እንደነበር የሚዳስስ ሰፋ ያለ ታሪክ ባለመገኘቱ "እሙተ ጠፍ" ወይም ታሪክ ጠፍ /ታሪክ የሌለው/ በማለት ታሪክ ነገስቱ ይገልጸዋል። ሌሎች በርካታ የውጭ እና የአገር ውስጥ ጸሐፍትም ለጽሁፍ የሚበቃ ታሪክ እንደሌለው ገልጸውት ነው የሚያልፉት። የሆነ ሆኖ ከ1355 ዓ.ም - 1365 ዓ.ም ነግሶ ከእርሱ በኋላ አጼ ዳዊት ነውና የነገሰው የአጼ ዳዊትን ታሪክ እና የዘመኑን ሁኔታ ወደማየት እንለፍ።



## ምዕራፍ ፵፮
## የአፄ ዳዊት ዘመነ መንግሥት
## ከ1365 -1395 ዓ.ም

አጼ ዳዊት ሥልጣኑን የተረከበው ከወንድሙ ከአጼ ውድም አስፈሬ ነው።

በመላው ኢትዮጵያ ነግሶ 30 ዓመታትን ስላሳለፈው ስለ አጼ ዳዊት "HISTORIA RERUM ISL AMITCARUMIN ABISSINIA" /በሐበሻ የእስላም ነገስታት ታሪክ/ በሚለው መጽሐፉ አልማቅሪዝ የተባለው ግብፃዊ ጸሐፊ ፣ እነ ሬኔ ባሴት፣ እነ ሞሪዮ ኩልቦ እና ሌሎች፣ ከፃፉት የተውጣጣው ታሪክ አጠር ባለ መልኩ ሲገለጽ የሚከተለውን ይመስላል።

እንደተለመደው በአጼ ዳዊት ዘመነ መንግስት ከግብጽ ጋር ከዚህ ቀደም የተደረገው ስምምነት ደብዛው እየጠፋ ሄዶ የግብጽና የኢትዮጵያ ግንኙነት መልሶ የሻከረበት ጊዜ ነበር። ሆኖም ቀደም ሲል ተጀምሮ የነበረውን ዲፕሎማሲያዊ ጥረት አጼ ዳዊት የበለጠ አጠናክሮ ቀጠለበት። አጼ ዳዊት ከአባቱ ዘመን ጀምሮ በሽምግልና ይመጡ የነበሩትን የሀይማኖት ሊቃውንት ወደ ወደብ ድረስ ሄዶ ነበር የሚቀበላቸው። ወንድሙ በነገሰበት ጊዜ ጉዞ ጀምረው የነበሩት የግብጽ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ወደ ኢትዮጵያ ሲደርሱም ውድም አስፈሬ ሞቶ ዳዊት ነበርና የተተካው ወደ አክሱም ሄዶ ተገናኛቸውና በማናቸውም ጉዳይ የመጡበትን ፈጽመው በሰላም እንዲመለሱ አደረገ። ሰላማዊ ንግድ እንዲካሄድ፣ በግብጽ ያሉ ክርስቲያኖች እንዳይበደሉ፣ በኢትዮጵያ ሙስሊሞችም እንዳይጉላሉ በሚል እና በሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ ስምምነት ላይ ተደረሰ። ይህ መሰሉ ስምምነት በግብጽ ሱልጣኖች እና በአጼ ዳዊት መካከል የነገሰ ሰሞን የተደረገ ሲሆን፤ መልዕክተኞችም በታላቅ ክብር ተሸኝተው ተመለሱ።

ከዚያም አጼ ዳዊት የራሱን መልዕክተኞች ወደ ካይሮ ላከ። መልዕክተኞችም ለግብጽ ሱልጣን የሚሰጥ በ20 ግመሎች የተጫነ ዕቃ ይዘው ጉዞ ጀመሩ። ለገጸ በረከት /ለስጦታ/ ከተያዘው እቃ ውስጥም በሽንብራ መልክና ቅርጽ የተሰሩ ወርቆች የሞሉበት በርካታ ከረጢት፣ በወርቅ የተሰሩ ማሰሮዎች፣ /እንስራዎች/ ይገኙበታል።

ከኢትዮጵያው ንጉሰ ነገስት ከአጼ ዳዊት የተላኩት መልዕክተኞችም የጫኑትን እቃ ወስደው ከግብፁ ሱልጣን ጋር ተገናኝተው ገፀበረከቱን አስረከቡ።

በዚህ ጊዜ በአጼ ዳዊትና በግብጹ ሡልጣን መካከል ከቃላት ስምምነት ያለፈ እርቀ-ሠላም ወረደ፤ ወይም የወረደ መሠለ።

ይህን አይነት ስምምነት ስለተደረገም የግብጹ ሡልጣን ተደስቶ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወደ ግብጽም፣ ወደ ኢየሩሳሌምም ሲጓዙ በየመንገዱ ችግር እንዳይገጥማቸው፣ በኢየሩሳሌም የሚገኙ መነኮሣትና ምእመናንም ያለ ችግር እንዲንቀሣቀሱና በሠላም እንዲኖሩ አዘዘ።

በዚህ ምክንያት አጼ ዳዊት የግብጽን ሡልጣን ድጋፍ ካገኙ ወዲህ የኢየሩሳሌም ፓትሪያሪክ ወደ ኢትዮጵያ መጥተው በተመለሱ ጊዜ ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበትንና ንግስት እሌኒ አገኝችው ከሚባለው ከእውነተኛው የመስቀል እንጨት አንድ ጉማጅ እንዲልኩለት ለኢየሩሳሌም ገዳም ባለሥልጣናት ጥያቄ አቀረበ።

ከጥያቄው ጋርም በርካታ የወርቅ ስጦታ ጨምሮ ላከ። የንጉሱን መልእክተኞች በደስታ ተቀብለው ከአፄ ዳዊት የተላከውን የወርቅ ስጦታ ግማሹን የኢየሱስ መቃብር በሚገኝበት በጎለጎታ አስቀምጠው በግማሹ ቅዱስ ሉቃስ የሳለው የሚባለውን የማርያምንና የኢየሱስን ስዕል በአንድነት ያለበትን ምስል /ምስለ ፍቁር ወልዳ/ የሚባለውንና በተጨማሪም አክሊለ ሶክ እንዳደረገ የሚያሳየውን ምስል /ኡርዓተ ርዕሱ/ የሚባለውን ገዝተው ከግማደ መስቀሉ ጉማጅ ጋር ጨምረው ሰጧቸው።

መልእክተኞቹም በተሰጣቸው ነገር ሁሉ ተደስተውና አመስግነው ያለአንዳች የጉዞ መሰናክል ወደ ኢትዮጵያ የመልስ ጉዞ ጀመሩ። እነዚህ የንጉስ ዳዊት መልዕክተኞች ይህን እቃ ይዘው ከኢየሩሳሌም ወደ አገራቸው ሲመጡ የቀድሞው ስጋት ባለመኖሩና እንደልብ መጓዝ መቻላቸው ለስምምነቱ ተግባራዊነት አንዱ አመላካችና አረጋጋጭ ጉዞ ነበር። እናም በሠላማዊ ጉዞ በስናር በኩል አድርገው ወደ ኢትዮጵያ እቃውን ይዘው ደረሱ። ንጉስ አጼ ዳዊትም በፍጥነት ሩቅ ቦታ ድረስ ሄዶ ተቀበላቸውና ህዝቡም ወንዱም ሴቱም በሆታና በእልልታ፣ በዘፈን በጭፈራ፣ ካህናቱም በዜማ በማህሌት በታላቅ ክብረ በአል ተቀበሏቸው።

የግማደ መስቀሉ አንድ አካል ኢትዮጵያ የገባውም በመስከረም 10 ቀን በ1380 ዓ.ም እንደሆነ ነው የሚታወቀው። አጼ ዳዊት ከሸዋ ነገስታት አንዱ እንደመሆኑ መጠንም በዚሁ እለት ተጉለት ገባና በቤተመንግስቱ አጠገብ ቤ/ን አሳንጾ ግማደ መስቀሉ በክብር እንዲቀመጥ አደረገ። በኋላ ግን በአጼ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመን ወደ ደብረ ግሸን እንዲዛወር ተደርጓል። ከዚያ ጊዜ ጀምሮም ሊቃውንቱ እንደወሰኑት መስከረም 10 ቀን በየአመቱ የአጼ መስቀል በዓል ተብሎ መታሰቢያ እንዲሆንና እንዲከበር አደረጉ። /መስከረም 17 ዋናው የመስቀል በዓል መሆኑ ይታወቃል።/

በአጼ ዳዊት ዘመነ መንግስት በውስጥ አስተዳደርና በአገር ውስጥ ያለው ሁኔታ ደግሞ የይፋቶችና የአዳሎችን ጦርነት ያስተናገደ ነበር።



ምንም እንኳን በሠሜንና በወገራ ፈላሾችና የበለው ዘሮች የሚባሉት አንዳንድ ጊዜ ማመፃቸው ባይቀርም ሌላው አውራጃ ግን በአንድ ኢትዮጵያና በንጉስ ነገስቱ ስር ሲተዳደር ነው የኖረው። ይፋቶችና አዳሎችን ግን ለዘለቄታው አስገብሮ ማሳመን የማይቻል ሆኖ ቀርቷል።

እስካሁን እንዳየነውም ለግጭቱ መባባስ ዋና ምክንያት የሆነው የሐይማኖት ልዩነት ብቻ ሳይሆን፤ ከጀርባቸው ያለው የየመን መንግስት ነው። በተለይም በአጼ ዳዊት ዘመን የተነሳውና ኤደንን ቀይባህርን እያስተዳደረ ስልጣኑን እስከ ዘይላ ድረስ ያሰፋው የዘቢዱ ሹም በእነዚህ በኢትዮጵያ ነገስታት ላይ ለሚሸፍቱትና ለሚያምጹት የሃዲያ የይፋትና የአዳል... ባለባቶች ሲዋጉ መሣሪያም፣ ወታደርም፣ በእርዳታ መልክ እየላከ ሲሸነፉ መሸሸያና መጠጊያ ስፍራ እየሰጠ ዋና ደጋፊ ስለሆናቸው ከእርሱ ጀርባ ደግሞ የአውሮፓን ነገስታት ሁሉ ያሸነፈው የግብጹ ማምሉክ እና የግብጽ ሱልጣኞች ስላሉ የይፋትና የአዳል ሁኔታ ከቀን ወደ ቀን አስጊ እየሆነ ሊሄድ ችሏል። የኢትዮጵያ ነገስታት ለእነዚህ ለተገዥዎቹ መሣሪያ እየሰጠ ድጋፍ የሆነውን የየመኑን እና የዘቢዱን ገዥዎች ለመምታት ብቁ የሆነ አቅምና የባህር ኃይል ስላልነበረው ዘመኑን ሁሉ እነዚሁን የሚሸፍቱትን ተገዥዎቹን ብቻ ሊያሳምን ሲሾም፣ ሲሽር፣ ሲያስር፣ ሲፈታ፣ አንዳንዴም ወታደሮቹን በጦርነት ሲያስጨርስ ለመኖር ተገዷል።

በአጼ ዳዊት ዘመንም ሁኔታው ቀጠለና መሐመድ አቡል ባራካት፤ ሳድ እድ ዲን በሚባለው ወንድሙ እግር ተተክቶ እየመራ በአጼ ዳዊት ላይ ተነሳ።

አልማቅሪዝን ጠቅሰው ሙሴ ረኔ ባሴት የፃፉትን ስንመለከት "ሳድ እድዲን አህባዛህ የተባለ አገር ላይ ሲዋጋ የንጉሱ ወታደሮች ማርከውት ነበር። በኋላ ግን የራሱ ወታደሮች አስጣሉት። ከዚያም ጦርነቱን ቀጥሎ የአጼ ዳዊትን ሹም አማን ሞርፋ የሚባለውን በጦርነት አሸነፈና የዘላንን አገር ወሰደ፣ምርኮም አገኘ። ነገር ግን በዚያው ጊዜ ሳሲም ቤን አያድ የተባለው ተባባሪውና አማቹ በጦርነት ተገድሎበታል" ይላል።

ይህ በእንዲህ እንዳለም የንጉሱ ጦር መልሶ ባካሄደው ጦርነት ሸንፈት ገጥሞት አማድ የሚባለው መሪ አንድም የንጉሱን ወታደር ሳያስተርፍ ጨርሶ ድል አድርጓቸዋል።

ከዚህ በኋላም ቦኑካ የሚባል የንጉሱ የጦር መሪ ከሳድ ዲን ጋር ተዋጋና ድል አደረገው። ሳድአዲንም ከጦርነቱ ቦታ ሸሽቶ ዘይላ ከተማ ሲገባ እዚያው ድረስ ተከታትሎ ሄዶ ከተማዋን በማስከበብ የአካባቢውን ሕዝብ በውሃ ጥምና በጦርነት ፈጅቷቸው ተመለሰ።

ይህ ሁሉ ሲሆንም አጼ ዳዊት ልክ እንደአባቶቹና ከእርሱ በፊት እንደነበሩት ነገስታት ራሱ ወደ ጦር ሜዳ ዘምቶ ተዋግቶ አያውቅም።

ሁሉም ጦርነቶች በበታች ሹሞች መሪነትና አዝማችነት የተካሄዱ ነበሩ። የአጼ ዳዊት ስራና ተግባር ግን ዲፕሎማሲያዊ ጥረቱ ላይ ብቻ ያተኮረ ነበር። ይልቁንም ትኩረቱ ሁሉ የዞረው ወደ መንፈሳዊ ሕይወት ነበር ይባላል።

የሆነ ሆኖ በአጼ ዳዊት ዘመንም ኢትዮጵያ በእርስ በርስ የውስጥ ጦርነት ስትናጥ መቆየቷና በውጭ ረጅዎች አማካይነት ብዙ እልቂት መድረሱ ታውቋል። በመጨረሻም አጼ ዳዊት ከ30 አመት የንግስና ቆይታ በኋላ በ1395 ዓ.ም ጥቅምት 9 ቀን በባዝራ ፈረስ ተረግጦ ከዚህ አለም በሞት ተለይቷል። ቀብሩም በጣና ሐይቅ በደሴተ ዳጋ እስጢፋኖስ ቤተክርስቲያን ተፈጽሟል።

እንደአገራችን ፀሃፍት አገላለጽም በፈረስ እርግጫ ግንባሩን የተመታበት ዛሬ ድረስ አጽሙ ላይ ምልክቱ ይታያል ባዮች ናቸው። አጼ ዳዊትን ለማሰብም በየዓመቱ በሞተበት እለት በጥቅምት 9 ቀን ከስንክሳር ላይ መንፈሳዊ ንባባ ይነበብለታል።

ከዚህ በፊት እንዳየነው የዘመኑ የውደሣ ግጥምም ለአጼ ዳዊት ተገጥሞለታል። ግጥሙ ደጃዝማች ኃይሉ እሸቴ አዘጋጅት ከሚባለው ታሪክ ነገስት ውስጥ የተገኘ ሲሆን፤ ሙሉውን ሳይሆን በጣም ጥቂቱን የዘመኑን ቋንቋ ለማመላከት፣ ግዕዝና አማርኛ ተቀላቅሎ ይፃፍና ይነጋገሩበት የነበረ መሆኑን ለማሳየት፣ አማርኛ ቋንቋ ገና በደንብ አለመሰልጠኑን ለመገንዘብ ይረዳን ይሆናል። ስለዚህ በአጼ ዳዊት ዘመን የነበረው የግጥም አፃፃፍ ይህን ይመስል ነበር።

"..ፈርስን ናቀብል
በቅሎህን ናቀብል
አንጥሩ ለዘር እንበሣ ዳዊት ተኲር
በዳበናኽ መገን፣ በፈረስህ መገን
በሪምህ መገን፣ በጽናትህ መገን
አማስለህ አትፍጀን
እኛስ ፈቃደኛህ ነን
እንስጥ መንግስትህን
ፈረስኽ የተፈተን፣ ወርቅ የተመዘን
ሐበጥ ቂራጥ ብለን
ናድርስ መንግስትህን
አማስለህ አትፍጀን።
ገርን በደል አሳት



ፅርሐ ንግስት ታቦት
እንደተከስዋት በእሳት
አሳረሩዋቸው እርሱም በእሳት።
ሐመል ወፍራ የዳዊት
የግራ የቀኝ ባልታት
በደብር ያላችሁ መነኮሳት
በከተማ ያላችሁ ህፃናት
ማን ተዋጋችሁ አቂት
አላስፈታንም ወገረት
ፅለ ጌታ ንግር መኾት
ምንም አልሆንም በልዋት
አንበሳ ዳዊት ፅርሐ ንግስትን ታቦት
እንደተኮስዋት በእሳት
አሣረርዋቸው በእሳት"... እያል ይቀጥላል።

# ምዕራፍ ፵፮

## የአጼ ቴዎድሮስ 1ኛ ዘመነ መንግስት

## ከ1395-1399 ዓ.ም

አጼ ቴዎድሮስ 1ኛ የአጼ ዳዊት ልጅ ነው። የንግስና ስሙ ዣን ሠበር ራስ በመባል ይታወቃል። እንደሚታወቀው ወደፊት በዚህ መጽሐፍ የምናገኘው የቴዎድሮስ 2ኛ ታሪክ በብዛት በየቲያትሩና በተለያዩ ታሪክን በማዘከሩ መድረኮች ታሪኩ በደንብ ይታወቅ እንጂ "ዳግማዊ ቴዎድሮስ" ሲባል ግን ብዙሃኑ የሚረዳው ከእርሱ በፊት ሌላ ቴዎድሮስ ነግሶ እንደነበር በማሰብ ብቻ ነው። ይህም የሆነው ተደራጅቶ ከማይገኘው ታሪካችን አንፃር የቴዎድሮስ 1ኛ ታሪክ የግዛት ዘመኑ ከማጠሩ ጋር ተደማምሮ ሊታወቅ አልቻለም። ነገር ግን "ስምን መልአክ ያወጣዋል።" እንዲሉ የአጼ ቴዎድሮስ 1ኛ እና የአጼ ቴዎድሮስ 2ኛ ተመሳሳይ ባህሪይ ያስደንቃል። እናም የዚህን ኢትዮጵያዊ ንጉስ ካለው አጭር ታሪክ በመነሳት ስለፈጸማቸው ተግባራቶችና ስለግዛት ዘመኑ አጠቃላይ ቆይታ፤ እንዲሁም ከአጼ ቴዎድሮስ 2ኛ ጋር ስለሚመሳሰለው ባህሪው የተመለከተውን ታሪክ እንይ።

አጼ ቴዎድሮስ 1ኛ ከአባቱ ከአጼ ዳዊት ቀጥሎ በኢትዮጵያ የነገሰው በ1395 ዓ.ም ሲሆን፤ የዘርዓያዕቆብ ታላቅ ወንድምም ነው። ስለ አጼ ቴዎድሮስ 1ኛ ጀምስ ብሩስ የፃፈውን ከአገራችን ስንክሳር ጋር አሰናስለን ስናየው ልክ እንደቴዎድሮስ 2ኛ ለሥልጣኔና ለሕዝቦች ጥቅም የቆመ ንጉሰ ንጉስ ነገስት ሆኖ እናገኘዋለን።

አጼ ቴዎድሮስ 1ኛ እንደነገሰ በመጀመሪያው ዓመት የፈጸመው ተግባር በአጼ ይኩኑአምላክና በአቡነ ተክለሃይማኖት መካከል የተደረገውን የሰላም ውል ስምምነትን መጣስ ነበር። ይህም አጼ ይኩኑአምላክ የሲሶ መንግስት ለመንፈሳዊ ግልጋሎት የመስጠት ቃል ኪዳንን አፍርሶ፤ በምትኩ የቤተክርስቲያኑን ከገደብ ያለፈ ርስትና ጉልት በጉልበት ነጥቆ ባልተለመደ ሁኔታ ለሕዝብ አከፋፈለ። ከአባቶቹም ከተከታዮቹም የተለየ ሃሳብ አምጥቶ ወደ ተግባር ከመለወጡ በፊትም ቀደም ሲል ለአባቶቹ በዚህ ድርጊት ደስተኛ እንዳልሆነ መግለጽ ጀምሮ ነበር። በመጨረሻ ግን በአባቱ በአጼ ዳዊት እንደተተካ የመጀመሪያ እርምጃ ያደረገው ይሄንኑ ተግባር ሆነ። በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ የመንግስት ሲሶ ለቤተክህነት ተላልፎ ጸንቶ እየተሰራበት የነበረ ሕግ ነበርና፤ ይህን በመጣሱ ቴዎድሮስ 1ኛ ብዙ ተቃውሞዎች እንደሚደርስበት ጠንቅቆ ያውቀዋል። 1ኛውና ዋናው አባቶቹ የሸዋ ነገስታት ያላፈረሱትን ሕግ በዘመኑ መናዱ እንደካሃዲ ከመቆጠሩም በላይ፤ በታሪኩ ላይ ጥቁር ነጥብን ጥሎ በማለፉ ነውረኛ ንጉስ ሲያሰኘው፤ በሌላ በኩልም ከቤተክህነት የሚነሳው ተቃውሞ



ወደሕዝቡም ሰርጾ ለአመጽ በር መክፈት መቻሉ ነው። ከዚህም ባለፈ እንደንቀት እንደሚቆጠርበት ያውቃል።

ሆኖም ቴዎድሮስ 1ኛ ለስልጣንና ለምስጋና አልጓጓም። "የቤተክህነትን ሀሜትና ወቀሳን አልፈራም፤ ከዚህም በላይ የሕዝቤ ጥቅም ይቅናለት" በሚል አዋጅ በውሳኔው ጸና። ደፋር ንጉስ ነገስት መሆኑንም በዚህ መልኩ ገለጸ። በተመሳሳይም ቴዎድሮስ 2ኛ በቤተክህነት ዙሪያ በነበራቸው አቋም ለአንድ ደብር ይህን ያህል አገልጋይ ወዘተ.. . በማለት እንዲሁም ወታደሩን በደሞዝ መልክ የማስተዳደርና ከቴዎድሮስ 1ኛ ጋር ተመሳሳይ አዋጅ በማወጅ ይታወቃሉ። ይህም ለተለያዩ ተቃውሞችና ለዙፋናቸው መነቃነቅ ሰፊ ሚና የነበረው መሆኑን ዘመኑ ላይ ስንደርስ የምናየው ነው። ሁለቱ ቴዎድሮሶች አላማችን ግቡን ይምታ እንጂ ለሚከተሰው ተቋውሞ ቦታ የለንም ያሉ ይመስላል።

አጼ ቴዎድሮስ 1ኛ ይህን አቋሙን ወደ ተግባር ሲለውጥም የፈራው አይነት ተቃውሞ አልገጠመውም። ይልቁንም ተወዳጅ እንዲሆን አደረገው። ለዚህም ማስረጃው ለቴዎድሮስ 1ኛ የቤተክህነት ታላላቆች ከሁሉም ነገስታት በላይ አክብሮት ማሳየታቸውና ወዲያው መስማማታቸው ነው። አጼ ቴዎድሮስ 1ኛ ከልጅነቱ ጀምሮ አምላኩን የሚፈራና የሚያከብር መሆኑ እንዳለ ሆኖ፤ እንደአባቶቹ በርካታ ሚስቶችና እቁባቶች ያልነበሩትና በአንድ ሚስት ብቻ የተወሰነ ነበር። ይህ አይነቱ የትዳር ሂወት ካለመለመዱ የተነሳም ተአምረኛ ንጉስ ነገስት ሲባል ቾሏል። ቴዎድሮስ 2ኛም እንዲህ አይነት እንደነበር ይታወሳል። አጼ ቴዎድሮስ 1ኛ በነበራቸው ጥቂት የግዛት አመታት ውስጥ ብዙ መንፈሳዊ ስራዎችን ሰርቷል። አብያተ ክርስቲያናትን አሰርቶ ገዳማትን ገድሟል። ከአባቶቹ ከወረሰውና ከራሱ የቤተመንግስት ሃብት ውስጥም ከግማሽ በላዩን ለድሆች አከፋፍሏል። በተመሳሳይ ቴዎድሮስ 2ኛ ለዝቅተኛው መደብ ቀና ምልክታ የነበረው መሆኑ ይታወቃል። የሚገርመው "ፍካሬ ኢየሱስ" የሚለው መጽሐፍ የተፃፈው በአጼ ቴዎድሮስ 1ኛ ዘመን ሲሆን፤ በዚህ መንፈሳዊ መጽሐፍ ውስጥ ደግሞ "ቴዎድሮስ የተባለ ንጉስ በኢትዮጵያ ላይ ወደፊት ይነግሳል" ተብሎ የተተነበየበት መጽሃፍ መሆኑ ነው። ይህን ትንበያ መሠረት በማድረግም ካሳ ኃይሉ የንግስና ስማቸውን ቴዎድሮስ 2ኛ ብለው ለመሰየም ችለዋል።

በአጼ ቴዎድሮስ 1ኛ ዘመን የኢትዮጵያ ሁኔታ ሰላም የሰፈነበት ይምሰል እንጂ፤ የአዳልና የይፋት ተዋጊዎች መልሶ ድርጅት ላይ የነበሩበት ሰዓት ስለነበረ ነው። የውስጥ አመጹም ረግቦ ነበር። በቤተክህነት በኩል የነበረው የስልጣን ሽኩቻና የሃብት ዘረፋም እንደመቆም ያለው በዚሁ በቴዎድሮስ 1ኛ ዘመን እንደነበር ይነገራል። እንደሚታወቀው

አንዳንድ ከፉ ካህናት መንፈሳዊነታቸውን ዘንግተው ወደስጋዊ ሕይወት በማዘንበል የየአድባራቱንና የገዳማቱን ወርቅ እና ልዩ ልዩ ሃብት ይዘርፉ እንደነበር ይታወቃል። ከአቅም በላይ ሐብት መብዛቱም በርካታ ካህናትን ሲያናቁር ከርሟል። ዛሬም እንዲህ አይነት ሁኔታዎች መበርከታቸው ግልጽ ነው። ከዚህ እንፃር አጼ ቴዎድሮስ 1ኛ የወሰደውን እርምጃ የዚያ ዘመን ኢትዮጵያውያን በሙሉ ድምጽ መደገፋቸው አግባብ እንደነበር እንረዳለን። በመጨረሻም በደሃው ህዝብ ዘንድ እጅግ ይወደድ የነበረው ንጉሰ ነገስት አጼ ቴዎድሮስ 1ኛ ከ4 ዓመት የግዛት ዘመን በኋላ በ1399 ዓ.ም በህመም ምክንያት ሰኔ 29 ቀን አርፎ በአማራ ሣይንት ተቀብሯል። የንግስና ሥልጣኑንም ወንድሙ አጼ ይስሐቅ ተረክቦ ኢትዮጵያን ማስተዳደር ጀምሮዋል። የአጼ ቴዎድሮስ 1ኛ የግዛት ዘመን በዚህ መልኩ ከተፈጸመ በኋላ ግን ቀጣይ ወንድሞቹ በቀድሞው አይነት አካሔድ እንደተጓዙ ነው የሚታወቀው።



## ምዕራፍ ሳድ
## የአፄ ይስሐቅ ዘመነ መንግስት
## ከ1399-1414 ዓ.ም

አጼ ይስሐቅ የአጼ ዳዊት ልጅ የአፄ ቴዎድሮስ 1ኛ ወንድም ነው። ይህ ንጉሠ ነገስት 15 ዓመት በቆየው የግዛት ዘመኑ ወደ ሰሜኑ የአገራችን ክፍል አካባቢ ወደወገራ ሄዶ ከፈላሾች ጋር ተዋግቷል። በዘመኑ ደብረ ይስሐቅ የሚባል ደብርም አሰርቷል።

እንደተለመደው ፈላሾች በአሪታዊ ሃይማኖታቸው፣ ሙስሊሞች በእስልምና ሐይማኖታቸው ፀንተው በሚኖሩ ጊዜ ያኔ የመንግስት ሀይማኖት ክርስትና ነበርና በየዕለቱ ግጭት ጠፍቶ አያውቁም። ስለዚህ በአጼ ይስሐቅ ጊዜም ፈላሾች ስለሸፈቱና ዘምቶ ስለወጋቸው ተቋውሞ መጣበት።

የተቃውሞውን መነሻ ምን እንደነበር ጀምስ ብሩሥ የተባለው እንግሊዛዊ ሲገልጸው በአጼ ይስሐቅ ዘመን በትግሬ 12፣ በሸዋ 12፡ በድምሩ 24 የሚሆኑ ዳኞች /የተከበሩ ያገር ሽማግሌዎች/ በፈላሾች ላይ ንጉሱ የፈጸመውን ለየት ያለ በደል በማየታቸው እንዳወገዙት ይገልፃል። በዚህ ጊዜ አጼ ይስሐቅ ሁሉንም ዳኞች ሽሮ በ24ቱ ካህናተ ሠማይ /ዳኞች/ ምትክ በሸዋና በትግሬ ሌሎች የቤተክህነት ሰዎችን እንደሾመ ተጽፏል።

ይህ በእንዲህ እንዳለም ስለ አጼ ይስሐቅ ከታሪክ ነገሱ ሌላ የዓረብ ፀሃፊዎች እነ ታግሪቢሪዲ፣ እነ ማቅሪዝ የፃፉትን ነው የአውሮፓ ሊቃውንት ተስማምተው የሚደግሙት። በዚህ መሰረት:-

በአጼ ይስሐቅ ጊዜ የግብጹ ሱልጣን ሁሉንም ሽማምንት ሰብስቦ የክርስቲያኖችን ጳጳሳትም አስጠርቶ "በኢትዮጵያ እስላሞች ሲጠቁ ለምን ዝም አላችሁ?" በማለ እንደወቀሳቸውና እንደተጣቸው ታግሪቢሪድ ይገልፃል።

በአል ማቅሪዝ መጽሃፍ ደግሞ በአጼ ይስሐቅ ዘመን አልቱም ቦጋ የሚባል የሳይድ አገረ ገዥ የነበረ የጦር መኮንን ከግብጽ ሡልጣን ጋር ተጣልቶ ሸሽቶ ወደ ኢትዮጵያ ሄዶ ለንጉሱ አደረ። ለንጉሱ እየሰራም ለንጉሱ ሠራዊት ወታደራዊ ስልጠና መስጠት ጀመረ። ሌሎችም ከእርሱ ጋር ሸሽተው የመጡት ለአፄ ይስሐቅ ምክር በመስገስና አብረው በመሰለፍ በሙስሊሞች ላይ እንዲዘምት ተባብረውታል። ሙስሊሞችን ለማጥፋትም ወደ ፍራንኮች ንጉስ ደብደቤ መላላክ ጀምሮ ነበር። እያለ ይቀጥላል።

በዚህ መልኩ አጼ ይስሐቅ ከፍተኛ ዘመቻ በሙስሊሞች ላይ ሲያደርግ ሳድአዲን ከሞተ በኋላ አስር ልጆች ነበሩትና ወደ አረብ አገር ሸሽተው በናስር አህመድ ቤን አሽራፍ ኢስማኤል ቤተመንግስት ጥቂት

ኖረው እርዳታ ተደርጎላቸው ዕርዳታውን ይዘው ወደ ኢትዮጵያ መጡ። ከጦርነቱ የተረፉት የመሐመድ አቡል ባራካት ተከታይ ወታደሮች የነበሩት ሁሉ ከያሉ ት ተሰባስበው ተቀላቀሏቸው። ከመሐላቸው አንድ ወንድማቸውን መሪ በማድረግም በክርስቲያናዊው መንግስት ላይ ጦርነት አነሱ።

ብዙ ግዛቶችን ከተቆጣጠሩ በኋላ የንግሱ ወታደሮች መልሰው አባረሯቸው። መሪ ወንድማቸውም በጦርነቱ ስለሞተ ሌላ ተክተው የዳግም ማጥቃት ሙከራ አደረጉ። አሁንም አጼ ይስሐቅ አሸንፎ ሁሉቱን ወንድማማች ማርኮ እስኪሞቱ ድረስ እስር ቤት ውስጥ አግቶ አቆያቸው። እንደገና ከሸሹት ውስጥ ከአስሩ ወንድማማቾች አንዱ ጋማልአዲን የመሪነቱን ቦታ ይዞ ክርስቲያኖችን ለመውጋት ተነሱ። የእርሱ የጦር አለቃ ሐርብጃዊሽ በያጅዛህ በባሌና ባካባቢው እየተዋጋ ብዙ ክርስቲያኖችን ከነመሳሪያቸው ሲማርክ፣ ቤተክርስቲያናቸውን ሁሉ ሲያቃጥል፣ ደዋሮንም ሲዘርፍ፣ ማርኮ ያመጣቸውን ሰዎችም በርካሽ ዋጋ ሲሸጣቸው፣ ራሱ ጋማልአዲን ደግሞ ከአጼ ይስሐቅ ጋር ይዋጋ ነበር። ንጉሱንም እያባረረ እስከ አባይ ወንዝ እንዲሸሽ አድርጎት ነበር። በኋላ ግን በመልሶ ድርጅት እየተከላከለ ከምሽሽ ወደ መልሶ ማጥቃት ተሸጋግሮ ድል በማድረግ ወደ ከተማው ወደ ሸዋ ለመመለስ ቻለ።

አጼ ይስሐቅ በ1414 ዓ.ም. 15 ዓመት ገዝቶ ሲሞትም አጼ ሕዝበናኝ 3 አመት ከ6 ወር /ከ1414-1418/ ድረስ ገዝቷል። ከዚያም በድልናኝ 1 አመት፣ ቀጥሎም አፄ አምደ እያሱ ከ1419 እስከ 1426 ዓ.ም 7 አመታትን በንግስና ቆይቷል። በነዚህ ሁለት አስርት ውስጥም የተለመደው የውስጥ ግጭት እንደቀጠለ ነበር። የነገስታቱ የግዛት ዘመን ከማጠሩ በላይም ሁሉም ከአጼ ይስሐቅ ጀምሮ እስከ አጼ ዘርዓያዕቆብ ድረስ የተፈራረቁት አራት ወንድማማች ነገስታት በእርስ በርስ የዙፋን ሹኩቻ እንዳሳለፉ ነው የሚታወቀው። ነገር ግን ከእነርሱ በኋላ የነገሰው አጼ ዘርዓያዕቆብ ገናናና ስመጥር ንጉስ ሲሆን፣ ሰፋ ያለ ታሪክም አለው። ስለዚህ ወደዚሁ ታላቅ የሸዋ ንጉስ ነገስት ታሪክ ከማለፋችን በፊት ለአጼ ይስሐቅ ከተገጠመው እጅግ ረጅም ግጥም ውስጥ ጥቂት ስንኞችን እንይ። ቤት እንዴት እንደሚመታና እንዴት እንደሚደፋም ሳያስተምረን አይቀርም።

"ገጽ ዣን ይስሐስ ገጽ
በአርያም ይመስል አንቀጽ
እሳት ይመስል ብቀጽ
ከመ መዳልው ልፅሉፅ



ገጹ እንዲያስደነግጽ
እስራኤላዊ መደንግጽ
ዓይነ ቁራንብሁን ቢገልጽ
ማን አየህ ገጽ በገጽ
ዓይነ እንደሎሚ ይፍረጽ
ገላው እንደሸንኩርት ይላጽ
እሳት ይመስል ዣን ተራራ እህዞ ሲልጽ
ማእበሉ ሲቆረጽ
እንዲያስደነግጽ
ማእከለ አገዳውን ሲፈጸፍፅ
እንዲያስደነግጽ
እንዴት ታስደነግጽ
ጎሽ ከፊላው ሲወፅ
ዱር በቀንድ ሲገለጽ
እስትንፋሱ ሲቆረጽ
ድንጊያ በእግሩ ሲፈለጽ
እንዲያስደነግጽ፣ ....." እያለ ይቀጥላል
እኛም ተከታዩን ገጽ እንግለጽ።

## ምዕራፍ ፵፱
## የአፄ ዘርዓያዕቆብ ዘመነ መንግስት
## ከ1426-1460 ዓ.ም

አፄ ዘርዓያዕቆብ በደካማ ነገስታት ስር የነበረውን የኢትዮጵያ ሁኔታ እንደ አዲስ እንዲደራጅና የተለየ መልክ እንዲኖረው ጥረዋል።

በናጋታ እነ ፒያንኪ 2ኛ፣ እነተሃርቃ፣ እነሻባካ፣ በመርዌ እነ ናስቶስኔን፣ እነ ሀንዲው አብራ፣ እነ ህንዳኪ፣ በአክሱም፣ እነ ኢዛና፣ እነ ካሌብ ፣በላስታ እነ ላሊበለ ስመጥርና ገናና እንደሆኑት ሁሉ በሸዋ ነገስታት ደግሞ አጼ አምደጽዮንና በተለይ አጼ ዘርዓ ያዕቆብ ከፍተኛ ቦታ የሚሰጣቸው ነገስታት ናቸው።

ስለ አጼ ዘርዓ ያዕቆብ የኢትዮጵያን አጠቃላይ ታሪክ በደንብ የመረመሩት ታላላቅ ፀሃፊዎች እነ ኮንቲሮሲኒ ፣ እነሙሴ ዲልማን ወደየቋንቋቸው እየተረጎሙ ብዙ ብለውላቸዋል። ኮንቲሮሲኒ "ተዓቅቦ ሚስጥር" የሚለውን የዘርዓያዕቆብ መጽሃፍ ግዕዙን ወደ ጣሊያንኛ በመተርጎም በፃፉት መጽሐፍ "ዘርዓ ያዕቆብ በመካከለኛው ዘመን ከነበሩት የኢትዮጵያ ነገስታት እስከ አጼ ምኒልክ ድረስ ዋነኛው ንጉሠ ነገስት" ብለዋቸዋል።

የዘርዓያዕቆብ ታሪክ የሰፈረበት ዜናመዋዕላቸው የዉስጥ አስተደደራቸውን ፣ የሕግ አወጣጣቸውን፣ የጨካኝነት ተግባራቸውን ወዘተ .. አጠቃሎ የሚገልጽ ነው። በዚህ መጽሐፍ መነሻነትም ፖርቹጋላዊው ዳልሜይዳ፣ እንግሊዛዊው ጀምስ ብሩስ በፖርቹጋል ቋንቋና በእንግሊዝኛ የየራሳቸውን መጽሐፍ ሲጽፉ በደንብ ተጠቅመውበታል።

በኋለኛው ዘመን በአጼ ቴዎድሮስ 2ኛ ጊዜ በእንግሊዞች ተዘርፎ ከሄደው 5 መቶ ያህል የእጅ ጽሁፍ ጥራዝ መጽሐፎች ውስጥም የዘርዓያዕቆብ ዜና መዋዕል የሚገኝ ሲሆን እንግሊዞች ወስደው በክብር በብሪቲሽ ሙዚየም አስቀምጠው ማንም ፀሃፊ እየገባ እንደልቡ እንዲያጠናው ፈቅደዋል ይባላል። የጀርመኑ ሙሴ አውግስቶ ዲልማን፣ የእንግሊዙ ዊሊያም ራይት፣ የፈረንሣዩ ጁሌስ ፔሪሶ እየተመለከቱ በየቋንቋቸው ተርጉመው በማሳተም ለአንባቢ እንዲሰራጭ አድርገዋል። ያገራችን ፀሃፍትም ከዚሁ በመነሳት ስለ ዘርዓያዕቆብ በሰፊው ጽፈዋል።

ለምን እንደሆነ በውል ባልረዳውም፣ ብዙዎችን ጠይቄ ምላሽ ላገኝ ባልችልም በርካታ ፀሃፍት ስለአገራችን ነገስታት ሲጽፉ ከአጼ ዘርዓያዕቆብ በኋላ ያሉትን ነገስታት "አንቱ" እያሉ በመጥራት ነው የሚቀጥሉት። እኔም ከዚህ በፊት በነበሩ ታሪኮች በአንተ መጥቸ ከዚህ ከዘርዓያዕቆብ በኋላ በአንቱታ መቀጠሌ ነው። ምናልባትም አንቱታ የዘርዓያዕቆብ ግኝት ሳይሆን አይቀርም። ወይም ለኋለኛው ዘመን ታሪክ ያመች ዘንድ ከወዲሁ ለመልመድ



አስበው አንቱታውን ከዚሁ የጀመሩበት ሁኔታ ተፈጥሮ ይሆናል። እንጂ ብቻ፣ የአንቱታ አመጣጥ መች እንደሆነ በታሪክ በውል አይታወቅም።

አጼ ዘርዓ ያዕቆብ በ1426 ዓ.ም ንጉሠ ነገስት ሆነው የተሾሙ ቢሆንም የንግስና ስርዓታቸውን ግን ለየት ባለ መልኩ ከጥቂት አመታት በኋላ በአክሱም ጽዮን ነው ያከበሩት።

መንበረ ስልጣኑን በጨበጡ የመጀመሪያው አመትም የፈጸሙት ተግባር ልዩ ልዩ የባእድ አምልኮ ስርዓትን የሚከተሉ ለነበሩ ኢትዮጵያውያን የሚሆን የቅጣት አዋጅ ማወጅን ነበር።

በዚያ ዘመን በኢትዮጵያ የነበሩ ዜጎች አራት ህግ፣ እስልምናና ክርስትናን የሚከተሉ የነበሩ መሆናቸው እንዳለ ሆኖ፣ የጣዖት አምልኮ የሚያመልኩም ነበሩ።

በአጼ ዘርዓ ያዕቆብ ጊዜ ደግሞ ደስክ የሚባል የጣኦት ምስል ነበር። ምስል ብቻም ሳይሆን ዛር፣ ቆሉ ወይም ሌላ ባእድ አምልኮ በከፍተኛ ደረጃ መሠራጨቱ ታውቆ ነበር። ዜናመዋዕላቸው በመጀመሪያው ክፍል "ደስክ የሚባል የጣኦት ምስል ይሁን ጋኔን በውል አይታወቅም፣ ነበረ። ለእርሱና ለዲያብሎስ ሠግድን ብለው አምነው ሌሎችም ከኛ ጋር ሰግደዋል በማለት በግልጽ ስለተናገሩ ተቀጡ" እያለ ይቀጥላል።

አጼ ዘርዓ ያዕቆብ የመጀመሪያውን እደገኛ ቅጣታቸውን የጀመሩትም ከዚህ ጉዳይ ጋር በተያያዘው ሁኔታ መነሻነት ነው። ስለዚህ ስለ ደስክ ጥቂት ነገሮችን እንረዳ።

ደስክ እና ዲኖ በመባል ይታወቃሉ። በተለይ ከዲኖ የበለጠ ደስክ በጣም ተመልኳል። አለቃ ታዬ ለህትመት ባልበቃው ጽሁፋቸው እንዲህ ይሉናል።

"ሸዋ ቅንበቢት አጠገብ ሀንጋ ቦካ በላይ ብለት የምትባል ትንሽ ኮረብታ አለች። ዛሬ የአቡነ ተክለሐይማኖት ታቦት ተተክሎባታል። ጥንት በዚያች ስፍራ ታላቅ ቤተጣኦት፣ ቤተደስክ የሚባል የዛር መቅደስ ነበር። የክርስቲያን ነገስታት፣ መኳንንቱም ዘመቻ ሲነሱ ከርሱ ይሰናኑና ከዛሩ አለቃ ምክር ተቀብለው ይዘምቱ ነበር። በሀገሩም የነበሩ የጋፋት ሕዝብ አምልኳቸው በቤተ ደስክ ነበር። ይህንንም ቤተደስክ በኋላ አቡነ ተክለሃይማኖት አፈረሱት" በማለት ይገልፃሉ።

ይህ ደስክ የተባለ ጣኦት አገር በቀል ይሁን ከውጭ አገር ይግባ በውል ባይታወቅም ብዙ ኢትዮጵያውያንን እንዳሳተ ግን በደንብ የሚታወቅ ነው። በአፄ ዘርዓያዕቆብ ጊዜም በቀጣዮቹ ጊዜም ሙሉ ለሙሉ አልቀረም።

የሆነ ሆኖ አፄ ዘርዓያዕቆብ በዚህ ጠንከር ያለ አቋም ወሰዱ። ብዙዎቹን በሞት እንዲቀጡ አደረጉ። በቅጣቱም የገዛ ልጆቻቸውን ገላውዲዎስን፣ አምደማርያምን፣ ዘርዓአብርሃምን፣ በትረጽዮንን ከሴት ልጆቻቸውም ድል ሀምራን፣ ሮምነገላዔን፣ አዳል መንገሳን፣ ሊምሯቸው አልቻሉም። በዚህ ጊዜ በተደረገው ቅጣት ብዙዎች አለቁ። ጥቂቶችም

ማምለካቸው በደንብ ስላልተረጋገጠ ሳይገደሉ ቀሩ፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞም አንዱ ሌላውን ጠላቱን ሁግዲል እያለ በመጠቀም ያለሀጥያቱ ለበቀል አሳማ ማዋል ሲጀምር "በሀሰት የመሰከረው ደሙ በራሱ ላይ ይሁን" እያሉ ንጉስ ዘርዓያዕቆብ ብዙዎችን በሞት ቀጡ፡፡

ከዚህ ባለፈ እንዲህ የሚል አዋጅ በአደባባይ አወጁ፡- "የክርስቲያን ሕዝብ ሆይ ብዙዎችን ሰዎች ከአምልኮ ጣኦት ለደስክና ለዲኖ ከመስገድ ካዳናቸው በኋላ አሁን ሰይጣን እቤታችን ድረስ ገብቶ ልጆቻችንን አስቶ ገዛቸው፡፡ ህዝቡም የሞቱትንና የተገረፋትን ሰዎች ቁስላቸውን ባየ ጊዜ፤ የደረሰባቸዉን በሰማ ጊዜ አለቀሰ ተጨነቀ፡፡ ቀጥሉም በየሕዝቡ ግንባር ላይ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ የሚል፤ ክህድክዎ ለዲያብሎስ በክርስቶስ አምላክ የሚል በቀኝ እጃቸው ላይ፣ ክህድዎ ለደስክ ርጉም እንተብራ ለማርያም እሙስፈጣሬ ኩሉ አለም የሚል በግራ ክንዳቸው ላይ ይፃፉል፡፡" ተብሎ ታወጀ፡፡ ይህን ጽሁፍ በንቅሳትም ይሁን በምን ሳይጽፍ የተገኘ ቤቱ እንዲበረበር በስጋው እንዲቀጣ በንጉሱ ታዘዘ፡፡ ሕዝቡም የዘርዓያዕቆብን ለልጆቻቸው ሳይቀር መጨከናቸውን ሲያይ በፍርሃት እንደራደና በሐይል ብዙዎችም እንደተመለሱ ታውቋል፡፡ አጼ ዘርዓያዕቆብ ደስክና ዲኖን በአጭሩ ባየነው መልኩ ከዘመቱባቸው በኋላ ቀጣይ ሥራቸው ያደረጉት ሹም ሽርና የማዕረግ አሰጣጥን በተመለከተ ልዩ ልዩ መሻሻል ማድረግን ነው፡፡

የኢትዮጵያን የቤተመንግስት የሹም ሽር አወቃቀር በተመለከተ ከጥንት ጀምሮ የነበረውን ሥርዓት አጼ ዘርዓያዕቆብ እንዳሻሻሉት ይነገራል፡፡ ደጅ አዝማች ኃይሉ እሸቴ የተባሉ የኋለኛው ዘመን ሊቅ ከግራኝ አህመድ የተረፋትን ሰነዶች በየደሴቱ ሰብስበው ያዘጋጁትንና አሉቃ ታዬ በፃፉት የእጅ ጽሁፍ ተመስርተው ስለአንዳንድ የቤተመንግስት የማዕረግ ስያሜዎችና አወቃቀሮች ተክለፃድቅ መኩሪያ በ2ኛው የታሪክ መጽሐፋቸው ያኑተቱት ሐተታ የሚያስረዳውም ይህንኑ ነው፡፡ የሥርዓተ ንግሱን ሁኔታም ለመለወጥ እንደቻሉ ታውቋል፡፡

የቅብአ መንግስቱን /አፈዋተመንግስት/ የሚባሉትንና ክልዩ ልዩ ነገር የሚቀመሙትንም አጼ ዘርአያዕቆብ ቁጥራቸውን ወደ 17 ዝቅ አድርገው በአዲስ መልክ እንዲሰሩ አድርገዋል፡፡ ከሎሚ፣ ከከርቤ፣ ከኮረሪማና ከሌሎች በርካታ ነገሮች እንደሚሰራም ይታወቃል፡፡

ፊት አውራሪ /ቀድሞ የሚጓዝ-የሚዘምት/ ቀኝ አዝማች /በቀኝ የሚዘምት/ ግራ አዝማች /በግራ የሚዘምት/ ደጅ አዝማች /ደጅን አዝማች፣ ከኋላ የደጅን ጦር መሪ/ በጅሮንድ /የመንግስትን ሚስጢር በጆሮ ነጋሪ፣ የግምጃ ቤት ቁልፍ ያዥ/ ባላምባራስ/ ባለአምባል፣ ራስ አምባ ጠባቂ/ ነጋድራስ /የንግድ ወኪል/ ባልደራስ ወዘተ... የሚሉ ከነበሩት የተጨመሩ የማዕረግ ስሞች በአጼ ዘርዓያዕቆብ እንደተጨመሩና በአፄ ዳዊት /በአባታቸው/ ጊዜ ጀምሮ ዘርዓ ያዕቆብ ከመንገሳቸው በፊት የፈለሰፏቸው እንደሆኑ ይነገራል፡፡ መቶ አለቃ /መቶ መሪ/ ሺ አለቃ /ሺ መሪ/ ሀምሳ አለቃ፣ ገበዝ፣



መኮንን፣ ጭቃ ሹም ወዘተ... የሚሉና ለመዘርዘር የበዙ የወታደራዊ የማዕረግ ስያሜዎችን ጨምሮ ጸሐፌ ትዕዛዝ፣ ከንቲባና ወዘተ እያሉ ብዙ ነገሮች መፈልሰፍ መቻላቸውን ታሪካቸው በታተቱባቸው ሰነዶች ሁሉ እንረዳለን፡፡

የፍርድ ሥርዓቱንም ሆነ አጠቃላይ የማዕረግ ስሞችንና መንግስታዊ አወቃቀሮችን ዘመናዊ ለማድረግ የቻሉት ታላቁ የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት ዘርዓያዕቆብ የመንግስት አወቃቀራቸው ሁሉ ከቀደሙት ነገስታት የተለየ ነበር፡፡

አጼ ዘርዓያዕቆብ ከብዙ እጣዎች የተመረጠላቸውና የወጣላቸው ስመ መንግስት ቆስጠንጢኖስ የሚለው ነው፡፡

የሚስቶቻቸው ስምና የማዕረግ ስምም የአንዷ ንግስት እሌኒ ቀኝ ባንልቲት የሁለተኛይቱ ንግስት ፍሬ ማር ግራ ባኅልቲት የሚል ሲሆን፤ በውስጥ ጦርነቱ ፖለቲካዊ ግጭቱን ለማብረድና ጦርነቱን ለማቆም ሲሉም ማንም ያልሄደበትን መንገድ ተጉዘው በአዲስ ስልት በመጠቀም ከሙስሊም ወገን /ከይፋት ወላስማ/ ሴት ልጅ ጋር ጋብቻ ፈጽመው ነበር፡፡ ንግስት እሌኒ /ቀኝዓ ባልቲት/ የወላስማ ዘር ስትሆን ክርስትና አስነስተው ነበር ያገቧት፡፡ በኋለኛው ዘመን በእነ አጼ ናአድ ጊዜ እነ ብህት ወድድ አምዱ፣ በጎንደር ነገስታት ዘንድ በእነ አጼ እያሱ ጊዜ እነ ብሀት ወደድ መላእከ ክርስቶስ "ብሀት ወደድ" በሚለው ስልጣናቸው የአሁኑን የጠቅላይ ሚኒስቴርነት አይነት ስልጣን ይዘው ያገለግሉ ነበር፡፡ አጼ ዘርዓያዕቆብ ግን ወንዶችን ብሀት ወደዶች በመሻር ለሴት ልጆቻቸው ሥልጣን ሰጡ፡፡ በዚህም ሙሉውን ስልጣን በራሳቸው እጅ እንዲይዙና ከወንድ ሹሞች ከሹክቻ ነፃ የሆነ መንግስት ለመመስረት ሞክረው ወንዶችን በሴቶች ተክተዋል፡፡

በዚህም ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ ታሪክ /ብዙ ንግስቶች መኖራቸውን ሳይዘነጋ/ ሴቶች የከፍተኛ ሥልጣን ባለቤት የሆኑበት ጊዜ ሆነ፡፡ ነገር ግን እንዳሰቡት ሳይሆን ቀረና ሴት ልጆቻቸውም ሸፍተውባቸው ነበር፡፡ ሆኖም እንደገና ስልጣኑን በኃይል ሲነጥቋቸው ችለዋል፡፡

ብዙዎች በክህደት ውስጥ የሚሽከረከሩ ሲሆኑባቸው ጊዜም የንጉስ ባለሟል የሆነውን አቃቤ ሰዓቱንና የቤተመንግስት ታማኝ አገልጋዮች /የእልፍኝ አሽከሮች/ ከሴቶች ጋር ወሲባዊ ግንኙነት እንዳያደርጉ፣ ሰው ቤት ገብተው እህል ውሃ እንዳይቀምሱ አዘዙ፡፡ ምክንያታቸውም ወንድ ከሴት ከተገናኘና ቤት ውስጥ ገብቶ ከበላ፣ ከጠጣ፣ መወዳጀቱ ስለማይቀር ሚስጢር እንደሚያወጣ፣ የተወዳጃቸውን ሰዎች ሀሳብ እንደሚፈጽምና መጠቀሚያ ሊሆን እንደሚችል በማሰብ ነው፡፡

አጼ ዘርዓያዕቆብ ታሪካቸውን በየዘርፉ ቀጥለን እንደምናየው በአንድ በኩል እጅግ ሲበዛ ክርስቲያንና ለሃይማኖታቸው ቀናዒ የነበሩ ሲሆኑ፤ ሌላኛው ገጽታቸው ደግሞ አደገኛ፣ ቅጣታቸው የመረረና የከበደ ጨካኝ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ ህግ አወጣጣቸውና የዘመናዊ አስተሳሰብ ባለቤት መሆናቸውን እናይና፤ እንደገና መልሰው በሚወስዱት እርምጃ ኋላ ቀር ይመስሉናል፡፡

አስተሳሰባቸውና አላማቸው ለአገራቸው እድገት፣ አንድነት፣ እንዲሁም ነፃነት ሆኖ ሳለ፤ ነገር ግን ስልጣናቸውን ለማጽናት ሲሉ አሽከሮቻቸውን ከሰውኛ ፍላጎታቸው ሲገድቡ እናያለን፡፡ በተጨማሪም ብዙ ሚስቶችና ብዙ ልጆች መውለዳቸው እንዳለ ሆኖ በርካታ አብያተ ክርስቲያናትን አሰርተዋል፡፡ ደብረ ብርሃንን የቆረቆሯት እኒህ ንጉሰ ነገስት ቁጥር ስፍር የሌላቸው መጽሐፍትን ጽፈዋል፡፡ እጅግ ሲበዛም የጦር ሜዳ ጀግና ነበሩ፡፡ ይህንና ይህን መሰሉ እጅግ አወዛጋቢ አካሄዳቸውን የመረመሩ የውጭ አገር ጸሐፍትም በጥበባቸው ተደንቀው "ታላቅ ንጉስ ነገስት" ብለዋቸዋል፡፡ በዜና መዋዕላቸው መሰረት ከላይ ካየናቸው ተግባራቶች ቀጥሎ ወረድ ሲል የሚያትተው የማሂኮን ሽፍትነት ነው፡፡

አጼ ዘርዓያዕቆብ ከፊሉን ሹም ሽር ካደረጉ በኋላ የተለያዩ ቅጣቶችን ከፈጸሙና ሕጎችን በአዋጅ ከደነገጉ በኋላ ህዝቡ ሁሉ እየተንቀጠቀጠ እንደተገዛላቸው ለመግለጽ "ወርአዩ ኩሉ ሰብእመግርማ መንግስቱ ወእምብዕየ ኃይሉ" ይላል፡፡

ጥቂት ቆይቶ የሃድያው ሹም ለኢትዮጵያ ማዕከላዊ መንግስት የሚገባውን ግብር እንዳያስገባ ሲጠየቅ "ከሀገሬም አልወጣም ወደ ቤተመንግስትህም አልመጣም" ብሎ ላከ፡፡ ይህ የሃድያ ገራድ /ሹም/ መጠሪያ ስሙ ማሂኮ ይባላል፡፡ ይህ ሰው የንግስት እሌኒ /የዘርዓ ያዕቆብ አንደኛዋ ሚስቱ/ ወንድም ነው፡፡ አባታቸውም ገራድ መሐመድ ይባላል፡፡ ማሂኮ ለጦርነት መዘጋጀቱን ደዋሮንና ባሌን ለማጥፋት /ለመወረርና ለመዝረፍ/ ይረዳው ዘንድም ከአዳል ባላባቶች ጋር ለጥምረት መላላኩን መልዕክተኛው ነገራቸው፡፡ አጼ ዘርዓያዕቆብም "የሃድያ ሕዝብ ሙሉ በሙሉ ወይስ በከፊል ነው ያበረለት?" ብለው በመጠየቅ ምክር እንዲለግስ መልዕክተኛውን ሲያዙት "ብዙዎች አብረውለታል፤ የሚሻለውም የአባቱን ወንድም ገራድ ባሞን ጠርተው በሃድያ ይሹሙትና የራሱ ዘመድ ይውጋው" የሚል ምክሩን ለገሰ፡፡ በዚህ ምክር ተስማምተው ገራድ ባሞን ከነጦሩ ካለበት ከዴገን ምድር አስጠርተው የሃድያ ንጉስ ብለው በመሾምና በመሸለም የወንድሙን ልጅ እንዲወጋ ላኩት፡፡ ሌሎች በዳሞት የሚገኙ ጦር ሰራዊቶችንም ጨመሩለት፡፡

ለባሌና ለደዋሮ ሹማምንቶች "ማሂኮ እንዳያመልጥ" የሚል መልዕክት ላኩባቸውና ገዢ ከደብረ ብርሃን ወደ ሃድያ ጀመሩ፡፡ መነኮሳትና ሹማምንቱም በጸሎትና በምርቃት ጦሩን ሸኙት፡፡ ገራድ ባሞ የተሰጠውን ሰራዊት ይዞ ሃድያ ደረሰ፡፡ በዚህ ጊዜ ቀደም ሲል ሸፍተው የነበሩት ሁሉ ጥቂት ተዋግተው ስላልቻሉ እየመጡ ገቡለት፡፡ የግዛት ሹሞች ለገራድባሞ መግባታቸውን የሰማው ዋናው የሃድያ ሹም ገራድ ማሂኮም ለመሸሽ ጉዞ ሲጀምር ስጋ ምድር በሚባል ቦታ ላይ ደረሱበትና ተያዘ፡፡

ከዚያም ገደሉትና እጆቹንና ጭቅላቱን ቆረጡት፡፡ የዚህ የድል ወሬ ለዘርዓ ያዕቆብ ሲደርስ በማህሌት፣ በዘፈንና በጭፈራ የድሉ በዓል ተከበረ፡፡



የሃድያው ገራድ ባሞ እና ተባባሪዎቹ የማሂኮን የተቆረጠ አንገት እጅና እግር ይዘው መጥተው በአጼ ዘርዓያዕቆብ ፊት ቆመው የጦርነቱን ሁኔታ ተረኩ፡፡ ሽልማትና ሹመት ለሚገባው ሁሉ ተሰጠና ተሸኙ፡፡

ከዚህ ጦርነት በኋላ ቀደም ሲል መርጠዋት የነበረችውን ከተማ ደብረ ብርሃንን ወደ ማሳመርና ቤተመንግስታቸውን በአዲስ መልክ ወደማሳነፅ ነው ያመሩት፡፡ የደብረ ብርሃንን ከተማ ሲቆረቁሯትም የስላሴን ቤተክርስቲያን አብረው አሰርተዋል፡፡

በሸዋ ነገስታታ ዘንድ ባልታየ ሁኔታ እጅግ የሚያምርና በውስጡ ይዘት እጅግ ያጌጠ፣ መውጫና መግቢያው በልዩ ሁኔታ የተሰራ ቤተመንግስት ያስገነቡት አጼ ዘርዓያዕቆብ የቤተመንግስቱን ሕግና ሥርዓትም ለዋውጠውታል፡፡ ከቤተመንግስታቸው ወደ ቤ/ያን ሲሄዱም ሆነ ሲወጡና ሲገቡ ማንም እንዳያያቸው አድርገዋል፡፡ በአጠቃላይ የቤተመንግስቱን ሚስጥርና የንጉሱን መውጣት መግባት የሚያውቁት የእልፍኝ አገልጋዮች ብቻ ሲሆኑ፤ እነሱም ወደ ውጭ የማይወጡና ከማንም ጋር ግንኙነት የማያደርጉ ናቸው፡፡ ካህናትና ሹማምንቱም በልዩና ሚስጥራዊነት በተሞላበት ሁኔታ ብቻ ነበር ከንጉሰነገስቱ ጋር ግንኙነት የሚያደርጉት፡፡ ከዚህ ቤተመንግስት ግንባታ መጠናቀቅ በኋላም ሥርዓተ ንግሳቸውን /የንግስ በዓላቸውን/ ወደ ማክበር ነበር የተሸጋገሩት፡፡

የቀድሞው የሰለሞን ዘር ስርዓት በደንብ መመለሱን ህዝቡ ያረጋግጥ ዘንድም የንግስና በዓላቸውን አክሱም ጽዮን ሄደው ለማክበር መወሰናቸው ብዙዎችን አስደስቶ፣ ብዙዎችን አስገርሞ ተቀባይነት እንዲኖራቸው ያደረገና፣ በሸዋ ነገስታት ዘንድ ያልተለመደ ነበር፡፡ አጼ ዘርዓያዕቆብ ወደ አክሱም ከማምራታቸው በፊትም የጨዋ ዘር የሚባሉትንና በመንግስት ዘንድ መሾም የሚገባቸውን ሰዎች መርጠው በአዳል፣ በደዋሮ ፣በሃድያና በሌሎች ግዛቶች በተቆጣጣሪነትና በታዛቢነት በመካሪነትም ሆነ በበላይነት እየሾሙ ሲልኩ እንዲህ የሚል መልዕክትም አብረው ላኩ፡፡

"የስጠናችሁ አዝማች እየገረፈ ቢያስለጥናችሁ እየተቆጣችሁ ወደ ሸፍቶች አገር ሄዳችሁ በእኛና በአዝማቹ ላይ ትመኩበት /ታምፁበት/ ነበር፡፡ አሁን ግን በእናንተ ላይ ሌሎች አዲሶች ጨዋዎች እግዚአብሔር እንዳዘዘን ልከንላችኋል፡፡ የቀድሞውን ክፋታችሁን ትታችሁ በስርዓትና በሕግ ኑሩ፡፡ እምቢ ያላችሁ እንደሆን በእናንተ ላይ እንዳሰብነው ቅጣት እንፈርድባችኋለን" ከደዋሮም ሌላ በሃድያ፣ በባሌ፣ በበጌምድር ፣በጎጃም፣ በፈጠጋር፣በይፋት፣ በግድም፣ በአንጎት፣ በትግሬ፣ ባህር አምባ፣ በሰራዬ በጸርዋጀት፣በእነዚህ ሁሉ አገሮች ለእያንዳንዳቸው ለሀገራቸው ክፍልና ስም እየሰጡ "ጨዋዎች" የሚባሉትን ደልድለው ላኩላቸው፡፡

ከሁሉ በላይም "ባህር ነጋሽ" የሚለውን ማዕረግ ከሁሉ ማዕረጎች እንደሚበልጥ ገለጹ፡፡ በዚህ ሥልጣን ስርም የሽሬን፣ የሰራዬን፣ የሀማሴን ክንቲባዎችን በበላይነት እንዲገዛቸው ስልጣንን ሰጡት፡፡ ይህ ስያሜ እስከ

ቀረብ ጊዜ ድረስ በባህር ነጋሽ በአካባቢው ያሉትን ግዛቶች በበላይነት ለሚያስተዳድር ሹም የሚሰጥ የማዕረግ ስም መሆኑ ይታወቃል፡፡

እናም በዚህ መሰል አሿሿምና አደረጃጀት ቅጥ ያጣውን የመንግስት አወቃቀር ባየናቸው እና ባላየናቸው መልኩ እንደገና አደሱት፡፡ ከዚያም ወደ አክሱም ለንግስ በዓላቸው ተጓዙ፤ ሥርዓቱን ለመፈጸም አክሱም በደረሱ ጊዜ የአገሩ ህዝብና ካህናት በደስታ ተቀበላቸው፡፡

የትግሬ ሹማምንትና ወታደሩ በፈረስ ሆነው ጋሻና ጦራቸውን ይዘው፣ ሴቶች እንደቀድሞ ልማዳቸው እየዘፈኑ ሲቀበሏቸው፤ የአክሱም ንቡረዕድ በግራና በቀኝ ሆነው እንደልማዳቸው የወይራ ዝንጣፊ ይዘው ተቀበሏቸው፡፡

አጼ ዘርዓያዕቆብ ወደ አክሱም ቅጥር ሲገቡ እየረገጡ የሚያልፉበት ልዩ ምንጣፍ ተዘርግቶ ሲጠብቃቸው፤ ልክ ምንጣፉን መርገጥ እንደጀመሩ ይዘውት የሄዱትን መቶ ወቄት ወርቅ (አንድ ወቄት 28 ግራም ነው) 2.800 ግራም ወርቅ ግራና ቀኝ እበተኑ ወደ ውስጥ ገቡ፡፡

ጥር 21 ቀን 14 33 ዓ.ም በተዘጋጀው የድንጋይ ዙፋን ላይ ተቀምጠው ስርዓተ ንግሳቸውን ፈጸሙ፡፡ ለብዙ መነኮሳትም ልዩ ልዩ ማዕረግ ሰጡ፡፡ አስፈላጊው መንፈሳዊ ተግባር ተከናውኖም ለቤ/ያን ርስትና ጉልት ሰጥተው፤ለገዳማትና ለአድባራት ግልግሎት የሚውል ልዩ ልዩ ገጸ በረከቶችን አበረከቱ፡፡ ገዳም እንዲገደምና ከነበረው የቅዳሴ ስርዓት በተጨማሪ «የሳታት» ጸሎት እንዲጀመር አዘውና አስፈላጊውን ነገር ሁሉ አደላድለው ወደ ሸዋ የመልስ ጉዞ ጀመሩ፡፡ በጉዞ ላይ ሳሉም በአማራ አገር ጸሐያ በሚባል ቦታ ሲደርሱ አባታቸው ያሥጀመሩትን የቤ/ያን ግንብ ተመለከቱ፡፡ ወዲያውም የአከባቢውን ሰዎችና የራሳቸውን አሽከሮች አስተባብረው በፍጥነት ቤ/ያን አስገነቡ፡፡ ያሠሯቸውን ሁለት ቤ/ያን አንዱን መካነ ጎል፤ሌላውን ደብረነጎድጓድ ብለው ሠይመው ፅላት እንዲገባ አስደረጉ፡፡ በተመሳሳይ መልኩም በየመንገዱ አዳዲስ ቤ/ያኖችን እያሰሩ አስፈላጊ ካህናትን እየመደቡና ርስት እየሰጡ ብዙ ቆይተው ነበር ወደ ቤተመንግስታቸው የደረሱት፡፡

ንጉሱ በጉዞ ላይ ያሳለፉት ረጅም ጊዜ ነበርና በእነዚያ ጊዜያቶች የይፋትና የአዳል፤ እንዲሁም ሌሎች ባላባቶች በከፍተኛ ሁኔታ ሲደልቱና ሲዘገጃጁ ነበር፡፡

አሕመድ በድላይ የይፋትን የወላስማ ዘር ለመሠረተው ለዑመር ወላስማ አስረኛ ትውልድ ነው፡፡ መላው የዘር ሐረጋቸውም የይፋት ንጉስ ሲባሉ የኖሩ ናቸው፡፡ አሕመድ በድላይ አጼ ዘርዓያዕቆብ የንግስ በዓላቸውን ለማክበር አክሱም በሔደበት ጊዜ ጦሩን ሲያዘጋጅ ነበር የቆየው፡፡

የአህመድ በድላይን ገስግሶ መምጣት የሰሙት ዘርዓያዕቆብ ጦራቸውን ሠብስበው ወደ ደዋሮ ተጓዙ፡፡ በዚህ ጊዜ የሀድያው ገራድ «መጥቼ እንድረዳህ ከፈለግህ ቃልህን ላክብኝ» ብሎ ላከባቸውና በተመሳሳይ ለአህመድ በድላይ «ህብረቴ ካንተ ጋር ነውና እርዳታ ካስፈለገህ ላክብኝ» ብሎ ላከ፡፡ አጼ



ዘርዓያዕቆብ «እስክንጠራህ ድረስ ጦርህን አዘጋጅተህ ጠብቅ» ብለው ላኩበት፡፡ ይህ መሐመድ የተባለው የሐድያው ገራድ በንጉሱ የተሾመና የሚስታቸው የንግስት ዕሌኒ (ቅኝዓ ባልቲት) ወላጅ አባት ነው፡፡

ዘርዓያዕቆብ የአህመድ በድላይን የጦር ብዛት አይተው ተደነቁ፡፡ የንጉሱ ጦር አነስተኛ በመሆኑም ካህናትና ሹማምንት ስጋታቸውን ገለጹ፡፡ "በሰራዊት ብዛት አትመኑ" በሚል የሌሎችን ቃል ሳይሰሙ ቀሩ፡፡

ጥሩንባ እንዲነፋ፣ ነጋሪት እንዲጎሰም፣ ግራ ቀኝ ባንዲራ እንዲተከል አዘዙ፡፡ አህመድ በድላይም «ንጉሱ ለይመጣም አላላችሁኝም ነበር?» የሚል ጥያቄ አቅርቦ ከወታደሮቹ ጋር ሲነጋገር ድንገት ጦርነቱ ተጀመረ፡፡ ከፍተኛ እልቂትም ደረሰ፡፡ አህመድ በድላይ እና ዘርዓያዕቆብም ብቻ ለብቻ የፊልሚያ ውጊያ ጀመሩ፡፡ የንጉሱ አንድ ወታደር ጦር ወርውሮ አህመድን ግንባሩን ሲወጋው ነቅሎ በመስበር በጅግንነት ንጉሱን ተፋለማቸው፡፡ እጅግ ተጠጋግተው ነበርና አጼ ዘርዓያዕቆብ በጦር አንገቱን ከወጉት በኋላ ጭንቅላቱን ቆረጡት፡፡ የተረፈ ወታደር እንዳይኖር በማለትም አስፈጁቸው፡፡

ከድል በኋላም የሐድያውን ገራድና የሌሎች ተባባሪዎችን ሹማምንት ጠርተው አሳዩዋቸው፡፡ የተለመደው የድል በዓል በስጋዊና በመንፈሳዊ ዝማሬና ጭፈራ ተከበረ፡፡

አጼ ዘርዓያዕቆብ አህመድ በድላይን አሸንፈው በተለመደ ቅጣታቸው ጭንቅላቱንም፣ እጁንም፣ እግሩንም ሌላውንም አካሉን እንዲቆረጥ አደረጉና በየአገሩ ተልኮ በየአደባባዩ እንዲዘዋወር ተደረገ፡፡ የማዕረግ ልብሱ ሌላው ንብረቱ ሁሉ ለቤተ ክርስቲያንና ለገዳማት ተሰጠ፡፡ በተጨማሪም በሬት የብረ አስቦ ይባል የነበረውና በዘርዓያዕቆብ ትዕዛዝ ደብረ ሊባኖስ ተብሎ በተሰየመው ገዳም የነበሩ መነኮሳት ከጦርነቱ በፊት «ታሸንፋለህ» ብለው መልዕክት ይልኩ ስለነበር ከድሉ በኋላ 150 ወቄት ወርቅና ሌሎች በርካታ ውድ ቅርሶች ለገዳሙ በስጦታ ተበረከተ፡፡

አጼ ዘርዓያዕቆብ ከዚህ ጦርነት በኋላ የተለመደውን ስራቸውን በመቀጠል ወደ ትውልድ አገራቸው ወደ ፈጠጋር ተመለሰው፤ እንዲሁም በየመንገዱ በዚህ ፅሁፍ ለመዘርዘር የማይቻል በርካታ ቤተ ክርስቲያንና ገዳማት እንዲሰራ በማድረግ ካህናትና መዘምራን በመመደብ ለአንዳንዱ ቤተ መቅደስ ተዘግኖ የማያልቅ ወርቅ እየሠጡ ቀጠሉ፡፡

ይህን ያህል አገራቱን ቤተክርስቲያን በቤተክርስቲያንና እያደረጉ፤ ነገር ግን የመረረ ቅጣታቸውና ጭካኔያቸው ግን ከአንድ ክርስቲያን የሚጠበቅ እንዳልነበረ ሁሉም የሚወዛገብበት ጉዳይ ሆኗል፡፡

ሌላው ቀርቶ ዜና መዋዕላቸው እንደሚለው "በክርስቲያኖች መካከል ክርክር ተካሔዳ ለማርያም ይሰገዳል፤ አይሰገድም በሚለው ክርክር "አይሰገድም" ያሉትን በየካቲት 2 ቀን አፍንጫቸውና ምላሳቸው እንዲ ፈ ረርደው ተቆረጠና በድንጋይ ተወገሩና ሞቱ"... እያለ ያትታል፡፡ ሲቀጥልም "እነዚህ ሰዎች በተወገሩና በሞቱ ከ38ኛው ቀን ጀምሮ ለብዙ ቀን በአከባቢው

ብርሃን ስለታየ ያችን ስፍራ ደብረ ብርሃን ብለው ሀየሟት ..." እያለ ይቀጥላል።

አጼ ዘርዓያዕቆብ ቅዳሜና እሁድ እኩል እንዲከበሩ፣የተለያዩ ሃይማኖታዊ በዓላት ከቀድሞው የበለጠ እንደጨመሩና ወዘተ... በርካታ መንፈሳዊ ሕጉችን ይደነግጉ ጀመር።

ንጉስ በደብረ ብርሃን 14 አመታትን ሲያሳልፉ ካወጇቸው መንፈሳዊ ድንጋጌዎች ውስጥ በአንድ ቤተክርስቲያን አንድ ፅላት ብቻ ሳይሆን ሁለትና ድርብ ወይም ከዛ በላይ እንዲሆን ማዘዛቸው ይጠቀሳል። ብዙዎችን ካህናትን ያስቆጣውና ለቅጣትም የዳረጋቸው የቅዳሜ ሰንበት ሆኖ መታወጅ ሲሆን፤ ይህም የአይሁድና የኦሪት ሕግ እንጂ የእኛ አይደለም በማለት እምፀው ነበር። ሆኖም በዘርዓያዕቆብ ዘንድ ተቀባይነት አልነበረውም። ባጠቃላይ የአጼ ዘርዓያዕቆብ መንፈሳዊ ሥራ እሁን ላለው የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ብዙ ዓይነት መሻሻሎችና አዳዲስ ሕጉችን እንዲቀበልና እንዲቀጥል የሚያደርግ ሆኖ ነው የሚታየው።

አጼ ዘርዓያዕቆብ ወደደረሷቸው መጽሀፍት ስናልፍ ደግሞ በየመጽሐፍቶቻቸው ልዩ ልዩ የስጋዊና የመንፈሳዊ ሕጎችን የደነገጉ ሆነው እናገኛቸዋለን።

ለምሳሌ ሙሴ ኮንቲሮሲኒ በተረጎሙት "ተዓቅቦ ሚስጥር" በሚለው በዘርዓያዕቆብ መጽሃፍ ውስጥ ከሚገኙት በርካታ ህጎች ስለ ቁርባን ሕግ የሚያትት ይገኝበታል። በዚህ ህግ መሰረት "ቆራቢው ካህንም ይሁን መሐይም አቁራቢው ተጠንቅቆ ማቁረብ (ስጋወ ደሙን) መስጠት አለበት።" ይልና በቆራቢውም በአቁራቢውም ዘንድ አምልጦ ቢወድቅ የጣለው 153 ጊዜ እንዲገረፍ ይላል።

"መጽሐፈ ሚለድ" የሚለው ስለ ወርሐዊ ክብረበዓላት ሲተነትን አያይዞም ስለ ጣኦት አምልኮ እና ስለ ቅጣቱ ይደነግጋል።

"መጽሐፈ ባህርይ" የሚለው ደግሞ ስለኑዛዜና ስለተያያዥ ነገሮች የተደነገገውን ያትታል። ዘርዓያዕቆብ ከአገር ውስጥም አልፈው በብራና እያስጠረዙ በእየሩሳሌም ለሚገኘው የኢትዮጵያ ገዳማት ቤተክርስቲያን መተዳደሪያ ሕግና ደንብ እየጻፉ ልከውላቸው ዛሬ ድረስ ግልጋሎት እየሰጠ ይገኛል። እነዚህንና እነዚህን መሰል ሥራዎቻቸውን እያዩም ነው፤ የውጭ ሀገር ፀሀፍት "ኢትዮጵያዊው ሊቅ" የሚል ቅጽል ስም የሰጧቸው። በቫቲካን የካቶሊክ ቤተ መጽሐፍት ውስጥም የጻፉት መጽሐፍትና የላኩት ደብዳቤ ዛሬ ድረስ ይገኛል።

አፄ ዘርዓ ያዕቆብ ይህን ሁሉ ሥራ ከመስራት ጎን ለጎን የይፋትና የአዳል የሀድያና የደዋሮ ባላባቶች ሲሸፍቱ እንዳንዴ ራሳቸው እየዘመቱ፣ ሌላ ጊዜ በመልእክተኞች ተዋግተው ድል እያደረጉ ነው። በተጨማሪም በጥንቱ ዘመን ከግሪክ እና ከሮማ ጋር ብቻ የነበረው የኢትዮጵያ ግንኙነት በዘርዓያዕቆብ ጊዜ ግን ከሌሎች የአውሮፓ አገራት ጋር ሰፋ ያለ ግንኙነት



ለመጀመሪያ ጊዜ ተጀምሯል። ዋናው የሃይማኖት አጀንዳ ቢሆንም፤ በዚህ አጋጣሚ ስለሌሎች ጉዳዮች የመወያየት እድል ነበራቸው። በርካታ ነጮችም ወደ ኢትዮጵያ መምጣት የጀመሩት በዘርዓያዕቆብ ጊዜ ነው።

የቱርኮችና የመካከለኛው ምስራቅ አገሮች እያየሉ በመሄዳቸው ኢትዮጵያ ከካቶሊክና ከኮፕቲክ ቤተክርስቲያን ጋር ህብረት ለመፍጠርና በሰሜን አፍሪካ እየበረታ የሄደውን የዓረብ ሃይል ለመመከት ስለሚችሉበት ሁኔታም ይወያዩ ነበር።

ሆኖም አንድነቱ ሊሳካ አልቻለም። ባለፉት ምዕራፎች እንዳየነው የኃይል ሚዛኑ ወደ እነርሱ ያደላው የቱርክ መንግስት ሱልጣኖች መቀመጫቸውን ባግዳድ አድርገው በክርስቲያኖች ዘንደ ልዩ ትኩረት የሚሰጣትን እየሩሳሌምን ይዘው ስለነበር አውሮፓውያኑ ተባብረው ቅድስቲቱን ከተማ ለማስለቀቅ መዋጋት ከጀመሩበት ከ11ኛው መቶ ዓ.ም ጀምሮ የቀጠለው ጦርነት እስከዚህ እስከ ዘርዓያዕቆብ ድረስ ሙሉ ለሙሉ ባለመቆሙ በላይ፤ በሰሜን አፍሪካ የበለጠ እየተጠናከሩ ነበር። ስለዚህ የክርስቲያን አገሮች ጥምረት ወሳኝ ነበርና ዘርዓያዕቆብም በዚሁ ጉዳይ ዙሪያ ከአውሮፓ ክርስትያናዊ ሀገሮች ጋር ተወያይተዋል። መልዕክተኞችንም ልከው እንደነበር ይነገራል፡ ይሁን እንጂ በአንድነት የመተባበሩ ጉዳይ ለአጼ ዘርዓያዕቆብ የሚዋጥ አልነበረም። ምክንያቱም እጅግ እያየሉ የሄዱትን ኦቶማን ቱርኮችን ከሌሎች የአውሮፓና የላቲን ሀገሮች ጋር ተባብሮ መፋለም ማለት ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የይፋት የአዳልና ሌሎች ተቃዋሚ ወገኖችን አመጽ የበለጠ ማቀጣጠል እንደማለት ነው።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የኦርቶዶክስና የካቶሊክ ሃይማኖት ተከታዮች እርስ በርስ ይጣሉ ነበርና ህብረቱ ሳይሠምር በመቅረቱ ለቱርኮች ሰርግና ምላሽ ሆነላቸው።

በዚያ በፍሎራንስ ጉባኤ ወደ ጣሊያን አጼ ዘርዓያዕቆብ ያልሄዱበትና መልክተኛ (ወኪል) የላኩበትን ምክንያት በደብዳቤ ሲገልጹ "የቱርክ ስልጣኖች እንዳያውቁና ሀገሬ የበለጠ ችግር ውስጥ እንዳትገባ ሁኔታ ነው።" የሚል ቃል እንዳካተቱ ሔንሪኮ ቼሩሌ የተባለ ፀሀፊ "የኢትዮጵያ ስነ ሁፍ ታሪክ" በሚለው መፅሀፉ ወደ ጣሊያን ተርጉሞ የዘርዓያዕቆብን ደብዳቤ ባሰፈረበት ገጽ (143 -144) ይታያል።

አጼ ዘርዓያዕቆብ ብልህነታቸውና አዋቂነታቸው እንዳ ሆኖ፣ ጭካኔ የተሞላበት ቅጣታቸውም እንደቀጠለ ነው። የቅጣት አዋጃቸውን የሚመለከትም ፅኑነቱን ለማስገንዘብ ቤተሰቦቻቸው ሳይቀር ክስ ከቀረበባቸው ጭካኔ እንዲቀጡ ያደርጋሉ።

በዚህም ከበርካታ ሚስቶቻቸው ውስጥ አንዷ የነበሩት ፅዮን ሞገሳን እንዴት እንደቀጧቸው እንይና ታሪኳቸውን ወደ ማጠቃለል እንለፍ።

ፅዮን ሞገሳ የአጼ ዘርዓያዕቆብ ሚስት ሲሆኑ፤ ከዘርዓ ያዕቆብ ቀጥሎ የነገሱትን አጼ በእደ ማርያምን ወልደዋል። ዘርዓያዕቆብ ስልጣን ላይ

እያሱ ጽዮን ሞገሳ ልጃቸውን ሊያነግሱ ከካህናትና ከሹማምንቱ ጋር እየተሳሳኩና እየዶለቱ ነው። የሚል ክስ ቀረበባቸው።

ዜና መዋዕሉ እንደሚለውም "አንች እኔ በመንግስቴ ሳለሁ ልጅሽ እንዲነግስ በየአድባራቱ ካሉት ቅዱሳን ጋር ተላልከሻል" ተብለው ሲጠየቁ "እንዲህ ያለ ስራ በአፌም በህሊናየም አልሞከርኩም አልሠራሁም" የሚል ምላሽ ቢሠጡም ተቀባይነት አጡና በግርፋትና በድብደባ እንዲቀጡ ተወስኖ በዚያው ምክንያት ሞቱ። ልጃቸው በዕደ ማርያምም ታስሮ ጥቂት ከተሰቃየ በኋላ ንፁህ መሆኑ ታምኖ እንዲፈታ ተደረገ።

አጼ ዘርዓ ያዕቆብ 34 አመት በቆየ የስልጣን ዘመናቸው ከይፋት፣ ከሐድያ፣ ከአዳልና ከሦሜን ፈላሾችና ከፀለምት ሹሞች ጋር የተደረገውን ጦርነት ብልህነት በታከለበት አካሄድ እያሸነፉ የቆዩ፣ ባዕድ አምልኮን ከኢትዮጵያ ለማጥፋት የጣሩ፣ ግጭትን በጋብቻ ለማርገብ የሞከሩ፣ የቤተክህነትና የቤተመንግስት ህግ እንዲሁም የስጋዊ አስተዳደር አዋጆችን ከቀድሞው የበለጠ ያሻሻሉና አዳዲሶችን የጨመሩ፣ በርካታ ገዳማትና ቤተክርስቲያን ያሰሩ፣ ብዙ መጽሃፎች የጻፉና ረጅሙን የስልጣን ቆይታቸውን በልዩ ልዩ ስራ ያሳለፉ ንጉሰነገስት ናቸው። ጭካኔያቸውም የበረታ ነበር።

ንጉስ አጼ ዘርዓ ያዕቆብ ከመንገሳቸው በፊት በአንባ ግሸን ሰፊ የመማሪያና የመመራመሪያ ጊዜ ነበራቸው። ሲኖዶስን እና ህጉን እጅግ የመረመሩና ያሻሻሉ ናቸው። ለዚህ መጽሀፍ ከፍተኛ ግምት እንደነበራቸውም ከነገሱ ከጥቂት ዓመታት በኋላ ይህንኑ መፅሀፍ በብራና ጽፈው ወደ እየሩሳሌም ገዳማት መላካቸውና፤ ህግና ስርዓቱ በኢትዮጵያ እንዲፈጸም ከልብ መጣራቸው ያሳያል። ከመንፈሳዊ ሥራቸው ባሻገርም በፖለቲካ አስተዳደር የተሳካላቸው ነበሩ። ከቀድሞ ጀምሮ የነበረውን የአገር ባላባትና (ባለጉልት) ወደ ጎን በማድረግ የቅርብ ሹሞቻቸውን ብቻ በባላባትነት ሳይሆን በወኪልነት እንዲሰሩ በማድረግ በየጊዜው የሚከሰተውን የየግዛቱን ንጉሶች ሽፍታነት አርቀዋል። "ጭዋ" የሚባሉና በራሳቸው ጦር የተደራጁ ሹማምንትን በየክልሉ እየላኩም እንደጠባቂም እንደተቆጣጣሪም ሆነው እንዲያገለግሉ በማድረግ የአከባቢ ሹሞች ሊያምጹ ቢሞክሩ በ "ጭዋ" ው አማካይነት እዚያው እንዲከሽፍ አድርገዋል።

እኒህ ንጉሰነገስት አዳዲስ የፍልስፍናና የምርምር ግኝታቸውን ለአገራቸው ህግና አስተዳደር እንዲውል በማድረግ ህዝቡን መንገድ ለመምራት የሞከሩ ናቸው። ዛሬ ድረስ እየተሰራባቸው የሚገኙ ስጋዊና መንፈሳዊ ህግጋቶች ብዙዎች የዘርዓያዕቆብ ግኝቶች ናቸው። ንጉሱ ከበርካታ ሚስቶቻቸውና እቁባቶቻቸው ከ18 በላይ ልጆች ወልደዋል። ጥቂቶቹን ልጆቻቸውን በባዕድ አምልኮ ሳቢያ እንዲገደሉ ማድረጋቸውንም አይተናል። በመጨረሻም ኢትዮጵያዊው ንጉሰነገስት አጼ ዘርዓያዕቆብ በርካታ ተግባራቶችን በዘመናቸው ካከናወኑ በኋላ ጳጉሜ 3ቀን 1460 ዓ.ም ከዚህ



ዓለም በሞት ተለይተው በኋላ ላይ አስክሬናቸው በጣና ሀይቅ ደሴተ ዳጋ እንዲያርፍ ተደርጓል።

እንደሌሎቹ ሁሉ ለአጼ ዘርዓያዕቆብም በዘመኑ ባለቅኔዎች ስንኝ ተቋጥሮላቸው የነበረ ሲሆን፤ ይህንኑ ረዘም ያለ የሙገሳ ግጥም አጠር አድርገን እንየው።

"ዣን ዘርዓያዕቆብ በድል ጸሐይ
አንኾሮት የዚከብራይ
ባሏ የባርዜላይ
ዣን በደበና ቢታይ
በእልፉት ያዘለቸው ይመስል ሰርናይ
ገ'ን በደበና ቢታይ
አበባ ቢመስል ገላጋይ
የመስከረም ይመስል ዕገይ
ሠይጣን አርዌ በድላይ
የሰመደው በአርጋይ
የለመደው በግዳይ
ዣን ዘርዓ ያዕቆብ በድል ጸሐይ
ቀለበው እንደ እንቧይ።
አፈረጸው እንደሎሚ አልዋልቶ ዋጋ ይታይ
በትግሬ በነገደ ዘእየወሰ ጋይ
ግብጽ የሙጻ ፈርዘነይ የከመሩበት ደንጋይ
ሰማ ዘርዓያዕቆብ እንደይቤይ
በቅድ ሐሊታይ በለሽርጌታ በአንሳት አለይታይ
በሐመበል አቦከር ጋይ በኢይፈት አለ ይታይ
ምሽቱ ዜነባ እንድታይ
ታንጉት እንደ መረዌይ
ትደቁስ እንደበርበሬይ።
በፈጠጋር አለ ይታይ በሴዘርድ ገይ
ስመ ዘርዓያዕቆብ እንደ ይዕበይ
በደዋሮ አለ ይታይ በለአደ ይታይ
በሔድራ ገይ በባሊ አለ ይታይ
አርቿ በድለይ ግዴታ በተአይ ዳኛይ
ምሽት ወይዘሮ ባልሆነም ለዋይ
አካል ሐመር ባልሆነም ለዋይ
ጠርቅ አምባር አልሆነም ለዋይ
ኪዳን ይሆነህ በሠማይ
ጉልትህን አልሰጥ ለሾይ
ይላል ኻን ዘርዓ ያዕቆብ"

## ምዕራፍ ፱

# የአፄ በእደ ማርያም ዘመነ መንግስት

## ከ1460-1470 ዓ.ም

"በጠሀኒ ቤትም በግዞትም ያላችሁ እስረኞች ስለእመቤታችን ስንል አባቴም እኔም ምህረት አድርገንላችኋልና በደስታ ወደየቤታችሁ ተመለሱ።" አፄ በእደማርያም በ1460 ዓ.ም የተናገሩት አዋጅ ነበር።

አፄ በእደማርያም በአባታቸው ዙፋን ሲቀመጡ የ20 አመት ወጣት ነበሩ። ቀደም ሲል ዘርዓያዕቆብ ባለቤታቸውን (የአፄ በእደማርያምን እናት) "እኔ በህይወት እያለሁ ልጅሽን በእደማርያምን ለማንገስ ከሹማምንት ጋር ተላልከሻል" በማለት ንግስት ፅዮን ሞገሳን ተገርፈው እንዲሞቱ ማድረጋቸውን አይተናል። ልጃቸውን በእደማርያምንም አስረውት ነበር። ሆኖም በመጨረሻ የግዛት ዘመናቸው አባትና ልጅ ለመስማማት ችለዋል።

በብዙ እማላጅ የወረደው ስምምነትም አባት ልጃቸውን ከእስር ፈትተው ሹመት እንዲሰጡት አድርጓል። በእደማርያም በአባታቸው ሹመት ሲሰጣቸውም በምንም አይነት ሁኔታ ጉቦ እንዳይቀበሉ አስምለዋቸው ነበር። በተለይ የንግስና ወራሽ እንዲሆኑ የግድ አረማመዳቸውን ማስተካከል እንዳለባቸው የተነገራቸው አባትየው በህይወት እያሉ ነበር። ከዚህ በኋላ አፄ ዘርዓያዕቆብ ሲሞቱ የነጋሲ ልጆች በሙሉ ታስረው በእደማርያም ጳጉሜ 3 ቀን 1460 ዓ.ም በእለተ እሁድ ዙፋን ላይ እንዲቀመጡ ተደረገ። ያየነውን አዋጅም በነገሱ ማግስት ለኛ ማለዳ ነበር።

ቀጥለው የወሰዱት እርምጃ በአባታቸው ዘመን በጥቅል ተይዘው የነበሩትን ስልጣኖች በተለየ መልኩ መቀየር ሲሆን፣ በየግዛቱ በርካታ ሹማምንትን በመሾም የሥልጣን ክፍፍል ማድረግ ነበር።

ቄና መዋዕላቸው እንደሚለው ከሆነ ደግሞ በመጀመሪያ የስልጣን ዘመናቸው ወቅት ለጣኦት ይሰግዳሉ የተባሉትን ዜጎች እንደአባታቸው በአደባባይ እንዲገረፉ ፈርደውባቸዋል። ከዚህ ፍርድ በኋላም እንደ አባታቸው ሁሉ ራሳቸውም በተከታታይ በተለያዩ ቦታዎች መንፈሳዊ ተቋማትን በመገንባት ተግባር ተሳትፈዋል።

ዳዊት በሚለው ስመ መንግስታቸው የሚታወቁት አፄ በእደማርያም1ኛ ከደብረብርሐን ራቅ ወደ ሚል ቦታ ሄደው በአጭር ጊዜ ውስጥ ባስገነቡት ቤተክርስቲያን ስርዓተ ንግሳቸውን ሲፈፅሙ እንደተለመደው ንጉሱ በእጃቸው ወግተው እንዲገድሏቸው ጎሽ እና አንበሳ ቢቀርብላቸውም ጎሹን ሌላ ሰው እንዲገድለው በማዘዝ አንበሳውን ደግሞ እንዲለቁት አደረጉ።

ስርዓተ ንግሱን ሲፈጽሙም ከልጅነት ሚስታቸው ከእሌኒ (እድማስ ሞገሳ) ጋር በመሆን ነው። ጥቂት ቆይተው አፄ በእደማርያም የባህሪ ለውጥ ማሳየት ጀመሩ። ምክንያቱም "ልጅ ናቸው ዘወትር ፈረስ ይጋልባሉ እንጂ



የመንግስትን ስርዓት መፈፀምን ትተዋል"... ወዘተ የሚል ሀሜት ስለሰሙና ስለተበሳጩ ነው የባህሪ ለውጡን ያሳዩት።

ይህን ሐሜት እንደሰሙም "የመንግስት ስርዓት አይፈፅምም ተቀምጦ ፍርድ ሲሰማ አይውልም ብላችሁ አምታችሁኛል። በአባቶቼ ጊዜ ፈረስ መጋለብ፣ ቀስት መወርወር ልምድ አልነበረምን? እንዲህ እያሉ ያሙኝን ሁሉ ይዛችሁ አምጡልኝ" በማለት የበታቾቻቸውን አዘዙ። እነዚህ ሐሜተኞች ተሰቅመው ካልወጡ እነዚህ የበታች ሹማምንት እንደሚገደሉ ተዛተባቸው። ከዚያም ብዙ መንከሳት ተይዘው ቀረቡ። ተጠይቀው ስለካዱ እግራቸውን ከስር እየቆረጡ በጎንደር አካባቢዎች ማለትም ወደ ደቅ፣ ወደ ጉንድ፣ ወደ ጉሽአሮ እና ወደ ደራ እንዲሁም ወደ ሌሎች ገዳማት በግዞት እንደላኳቸው ይነገራል።

በዚህ ጊዜ ህዝቡ ሁሉ "ይህስ ከአባቱ ይበልጥ ጨካኝ ነው" ለማለት ተገደደ። ይህ በእንዲህ እንዳለም አንገዛም እያሉ ዘወትር ይሸፍቱ የነበሩት የአዳል እና የይፋት ባለባቶች በአፄ በእደማርያም ጊዜ ባላባታቸው መሐመድ ቤን በድላይ "እንግዲህ በመካከላችን ሰላም ይሁን። እኔም በየአመቱ ግብሬን ይዤ እመጣለሁ፤ አስገባለሁ። ልገዛልህም ዝግጁ ነኝ። አንተም ወታደሮችህን ወደ አገሬ አትላክብኝ።" የሚል መልእክት ላከ። ይህ መልዕክትም ንጉሱ ንግስናቸውን በፈፀሙበት በወረኢሉ እና በአማራ ሳይንት መካከል በሚገኘው ማረፊያ ቦታቸው ሆነው ሲደርሳቸው መልዕክቱን በሰላምና በደስታ ተቀብለው መልእክተኞቹንም ሸልመው ነበር የመለሷቸው።

በዚህ መልዕክት የአዳልና የይፋት ጉዳይ በመረጋጋቱ ንጉሱ ደስ ቢሰኙም ወዲያው ግን በዋጅራት በራያ እና አዘቦ በኩል አመፅ ተነሳባቸው። እነዚህን ህዝቦች (አገሩን ዶብአ፣ ስዎቹን ሰብዓ፣ ዶብአ ይላቸዋል የታሪክ መዛግብት) ቦታው ከሁብል እና ከየጁ በስተምስራቅ ከአውሳ እና ከደንከል በስተምዕራብ የሚገኝ ሲሆን ህዝቦቹም የራያ እና የአዘቦ ነገዶች ናቸው። እናም ዘወትር ያደርጉት እንደነበረው ያን ጊዜም ያመፁት ነጋዴን በመዝረፍ ግብር በመከልከል እና በሌሎች መሰል ተግባራቶች ነው።

አፄ በእደማርያምም በደብረነጎድጓድ በአትሮንስ ማርያም በርካታ የመንፈሳዊና አስተዳደራዊ ጉዳይ ከፈፀሙ በኋላ ለዘመቻ መዘጋጀት ጀመሩ። ጦርነቱ ተጀምሮ ብዙ እልቂት ካስከተለ በኋላ በንጉሰነገስቱ ወታደሮች የበላይነት ሊጠናቀቅ ቻለ። ከዚያም በዶብአ፣ በአንጎት በኩል አድርገው ከመመለሳቸው በፊት ሹምሽሩንና ድልድሉን በአዲስ መልክ አዋቅረው የንግስናቸውን 1ኛ አመት ወደ አክሱም ሄደው ለማክበርና ለማደስ ሲዘጋጁ ሌላ አዲስ የውስጥ ግጭት ተከሰተ።

ከላይ እንዳየነው ከመሐመድ ቤን በድላይ ጋር ባደረጉት ስምምነት መሰረት ከአዳሎች ጋር ሰላም ወርዶ የነበረ ቢሆንም፤ ከጥቂት ጊዜ በኋላ በመሐመድ ቤን በድላይ እግር የተተካው ኡስማን ቤይ ሱሌይማን "ለውጊያ ተዘጋጅቶ ከአዳል ተነስቶ መጣ" የሚል ወሬ ደረሳቸው። ስለዚህ አፄ

በእደማርያም ወደ አክሱም ለንግስ በዓላቸው በመሔድ ፊንታ ወደ ሸዋ ለመመለስ ተገደዱ።

ወታደሮቻቸውንና ፈረሰኞችን አዘጋጅተው ጉዟቸውን ጀመሩ። የሸዋና የይፋት ህዝብም ተቀበላቸው። ይፋት ደርሰውም ጊዜያዊ ድንኳናቸውን አስተከሉ።

በጉዟቸው ወቅትም የተለያዩ አሉባልታዎች ከበታች ሹማምንቶቻቸው ይደርሳቸው ነበርና ባረፉበት ቦታ ሁሉ ሀሜተኞችና ጥፋተኞች የተባሉትን ሁሉ እያስጠሩ የጭካኔ ቅጣታቸውን በድጋሚ ይሰነዝሩባቸው ጀመር። በዚህ ሳቢያም ሁክቱ እየተጋጋለ ሄደ።

ከዚህ በኋላ የደዋሮ፣ የዳሞትንና የሌሎችን ግዛቶች ወታደሮች ወደ አዳል አገር ሔደው እንዲዋጉ በመላክ፤ ራሳቸው ንጉሱ ደግሞ ከቀሪ ተከታዮቻቸው ጋር ወደ ደዋሮ ገሰገሱ። እነዚያ የተላኩት ወታደሮችም የአዳልን አገር አሸንፈው ተመልሰው ደዋሮ ላይ ከንጉሰ ነገስታቸው ጋር ተገናኙ። ሆኖም ወታደሮቹ አሸንፈን መጣን ይበሉ እንጂ ድላቸው ሙሉ ለሙሉ በማሸነፍ የተጠናቀቀ እንዳልነበር ከጊዜ በኋላ ተደረሰበት።

የአዳሉ ጦርነት አንድ እርግጠኛ የሆነ ውሳኔ ሳያገኝ በውስጥ በየአውራጃው የተለያዩ አድማዎች በንጉሱ ላይ እየተደረጉና ጥፋተኛውም እየበረከተ በመሔዱ በጠቅላላው የአፄ በእደማርያም መንግስት በሁከት የታጀበ መሆኑ ቀጠለ። አሸነፍን ያሉት ወታደሮችም አንዱን የአዳል ክፍል ብቻ ነበርና ያሸነፉት ጦርነቱ እንደገና በአዲስ መልክ ተጋግሎ ሊቀጥል ግድ ሆነ። የአዳሎች መሪ ኡስማን ቤይ ሱሌይማንም አልተገደለም፣ አልተማረም። እናም ንጉሰነገስቱ እንደ አባታቸው ድል ሳይቀናቸው ተሸነፉ። በድጋሚ የተላኩት በርካታ ወታደሮችም ለወሬ ነጋሪ ሸሽተው ካመለጡት በቀር በሙሉ በተጋጋለው ጦርነት አለቁ።

አፄ በእደማርያም የላኩት ጦር ሲሸነፍና መልእክት ከመጣላቸው በኋላ ነገሩን ዳር ሳያደርሱት ሊተውት ተገደዋል።

በአፄ ዘርዓያዕቆብ ጊዜ ተዳክመው የነበሩት አዳሎች በ1460ዎቹ በአፄ በእደማርያም ጊዜ መልሰው ሃይል በመሆን የቀኝ እና የግራ የጦር መሪዎችን (ብህት ወደዶችን) ከነጦር ሠራዊቶቻቸው ሊያሸንፉ ችለዋል።

በሁለቱ ከፍተኛ የጦር አለቆች መካከል ደግሞ በግዛት ስፋትና በሹመት የእርስ በርስ ፀብ የመኖሩ ጉዳይ ለሽንፈታቸው ምክንያት እንደሆነ ተገልጿል። ሁለቱ የሚናናቁ አዝማቾች ደረጃቸው ተመጣጣኝ የሆነ ባለሥልጣኖች ሆነው ሳለ፤ በጦርነቱ ጊዜ ግን አንዱ ሌላውን እያዘዘ እንዲዘምት ስልጣን ተሰጥቶት ነበርና ሌላኛው ተቀይሞ ውጊያውን ችል እንዳለም ይነገራል። ንጉሱም ሁለቱን ብህትወደዶች ቅራኔ እንዳለባቸው እያወቁ በአንድነት መላካቸው እንደ ትልቅ ስህተት ተቆጥሮባቸዋል።

በአፄ በእደማርያም የግዛት ዘመን ውስጥ ሰፊ ታሪካቸውን ይዞ የሚገኘው ከአትሮንስ ቤተክርስቲያን ጋር የነበራቸው ቆይታ ነው።



እንደ ጀምስ ብሩስ አገላለፅ "በአፄ በእደማርያም ዘመን በራሳቸው ትዕዛዝ በአትሮንስ ማርያም ቤተክርስቲያን ውስጥ የማርያምን እና የኢየሱስን ምስል የሳለው ፍራንቸስኮ ደ ብራንካ ሌዎን የተባለ ጣሊያናዊ ነው። ኢትዮጵያውያን ካህናት በዚህ ስዕል የተነሳ ከሰአሊው ጋር ፀብ እና ክርክር ፈጥረዋል።

የክርክራቸው መነሻም በሰአሊው ነጭ መሆንና ካቶሊክ በመሆኑ አልነበረም፤ ይልቁንም በካቶሊክ ደንብ ማርያም ኢየሱስን አቅፋ የያዘችው በግራ እጅዋ ስለሆነ "እንደ ምስራቅ እና እንደ እስክንድሪያ ቤተክርስቲያን ደንብ በቀኝ እጅዋ እንዳቀፈችው አድርጎ ለምን አልሳለውም በማለት ነው" በሚል የግጭቱን መነሻና የአፄ በእደማርያምን ተግባር እየተነተነ ይቀጥላል። ሆኖም ምስሉ ለረጅም ጊዜ ሳይነሳ ቆይቷል።

አፄ በእደማርያም ጫካ አስመንጥረው ቤተክርስቲያን በማሰራት አትሮንስ ማርያም ብለው በመሰየም ፅላት እንዲገባ አስደርገዋል። አትሮንስ ማርያምን አሰርተው በአሉን አክብረው ከጨረሱ በኋላ ለካህናቱ መተዳደሪያ ከአባይ ወንዝ ጀምሮ እስከ ጅማ ድረስ ያለውን ምድር በርስትነት ሰጥተዋል።

ቀጣይ ስራቸው ያደረጉትም የአፄ ቴዎድሮስ 1ኛን አፅም ከአሰሮ፣ የይኩኑ አምላክንና የሌሎችን የኢትዮጵያ ነገስታት የነበሩትን (18 የሚሆኑ የነገስታትና የጳጳሳትን) አፅም ከያሉበት አስለቅመው እዚሁ አትሮንስ ማርያም ቤተክርስቲያን እንዲቀመጡ ማድረግን ነው።

የአፄ በእደማርያምን የትዳር ሁኔታ ስናይም አንድ ለአንድ የሚለውን የወንጌል ቃል ችል በማለት እንደሌሎች ነገስታት ከአንድ በላይ ሚስት የነበራቸው ሆነው እናገኛቸዋለን። በዘመናቸውም ሁለት ሚስት በአንድ ጊዜ ያገቡ ሲሆን፤ ከአንዷ አንድ ወንድ ልጅ ወልደዋል።

ከአንዷ ህጋዊ ሚስታቸው እስክንድርን ሲወልዱ፣ ከእቁባታቸው ደግሞ ሌላ ልጅ ወልደዋል። በ1440 ዓ.ም የተወለዱትና በ1460 ዓ.ም በ20 አመታቸው የነገሱት አፄ በእደማርያም ከ10 ዓመት የንግስና ቆይታ በኋላ በምን እንደሆነ ባልታወቀበት ሁኔታ ሲሞቱም የተኳቸው ንጉስ ልጃቸው አፄ እስክንድር ነበሩ።

የአፄ በእደማርያምን አሟሟት በተመለከተ ጀምስ ብሩስ በመርዝ ተገድለው ይሆናል ቢልም በደንብ በማስረጃ ማረጋገጥ እንዳልተቻለ ግን ሳይገልፅ አላለፍም።

# <u>ምዕራፍ ፵፩</u>
# <u>የአፄ እስክንድር ዘመነ መንግስት</u>
# <u>ከ1470-1486 ዓ.ም</u>

በኢትዮጵያ ነገስታት ታሪክ ውስጥ አንድ ንጉሠነገስት ወንድ ልጅ ካለው አገር ለመምራት ብቁ የሚያደርገው የእድሜ ደረጃ ላይ ባይደርስም መንገሱ አይቀርም። አፄ በእደማርያም በወጣትነት ጊዜያቸው በ30 አመታቸው ነበርና የሞቱት በ20ዎቹ የእድሜ ክልል ውስጥ እያሉ ከዋና ሚስታቸው የወለዱት ልጃቸው አፄ እስክንድር ነበሩ። እናም አፄ በእደ ማርያም ከሞቱ በኋላ የንጉሠነገስትነት ስልጣኑን የ6 አመቱ ህፃን አፄ እስክንድር ተረከቡ።

በስርዓተ ንግስናቸው ጊዜም እናታቸው እመቤት ሮማን ወርቅ እንደ ሞግዚት ሲሆኑ፤ ግራ ብህትወደድ አምደሚካኤል፣ ቀኝ ብህትወደድ በድላርእድ ሆነው በእንደራሴነትና በአማካሪነት ተሾሙላቸው።

አፄ እስክንድር ዙፋን ላይ ከተቀመጡበት ጊዜ ጀምሮ የግራ እና የቀኝ ብህትወደዶች እርስ በርስ የስልጣን ሹክቻ ውስጥ በመግባታቸው የውስጥ ብጥብጡ እየተባባሰ ሄዶ ነበር።

ወዲያውም ብህትወደድ አምደሚካኤል ወታደሩንም አጠቃላይ የአገሪቱን ፖለቲካዊ ጉዳዮች ሁሉ ጠቅልሎ በሙሉ እንደራሴነት በመያዝ ዋና የስራ አስፈጻሚ ሆነ።

የንግስት ሮማንወርቅና የቀኝ ብህትወደድ በድላርዕድ ስልጣንና ተሰሚነት እየከሰመ በመሄዱም ክፍፍል ተፈጠረ።

ይህ ሁሉ እየሆነ ባለበት ጊዜም ብህትወደድ አምደሚካኤል ህፃኑ ንጉሰነገስት ትኩረቱን ወደ መንፈሳዊ ነገር እንዲያደርግ በመገፋፋት በመንግስቱ ውስጥ እንደልቡ የሚያዝበትን ሁኔታ አመቻቸ።

አፄ እስክንድርም በዚሁ የልጅነት ጊዜያቸው አባቶቻቸው የጀመሯቸውን እድባራት እያሳደሱ፣ አገሪቱን እየዞሩ ሲጎበኙ ጥቂት አመታትን አሳለፉ። የወጣትነት እድሜ ላይም ደረሱ። እንደ ዜና መዋዕላቸው አገላለፅ "አፄ እስክንድር ውጊያ የሚያውቁና ሃይል የተሞሉ ነበሩ። ፈረስ መጋለብ፣ በጋሻ በጦርና በቀስት የመዋጋትን ደንብ በደንብ ተምረዋል። ባንድ ወገን ደግሞ መሐሪና ይቅር ባይ ልባቸው ሩህሩህ በቀልን የሚጠሉ መልካምን የሚወዱ ናቸው። ዳሩ ግን ወታደሮቹ አገር እያጠፉ ደሐን ሲያስለቅሱ አልተቆጧቸውም ነበር። ቅዱሳኑ ወደ አዳል አገር አትሂዱ ቢሏቸውም ንጉሱ ግን ሰራዊታቸውን አሰባስበው ምክራቸውን ጥሰው ለውጊያ ወደ አዳል ሔዱ። ዳካ የሚባለው ቦታ ደርሰው ቤቱንም ሁሉንም አፈራርሰው ሲመለሱ የአዳል ሽፍቶች ትንሽ



ሆነው ተከትለው ጦርነት ገጠሟቸው። አፄ እስክንድርም ጦርነቱን ገጥመው ሲዋጉ መቋቋም አቅቷቸው ግማሹ ሰራዊታቸው ሲሞት የቀረው ሲሸሽ ሌላው ተማረከባቸው..." እያለ በመቀጠል ንጉሱ ግን በአምላክ እርዳታ አምልጠው ወደ ከተማቸው በሰላም መመለሳቸውን ይገልፃል።

የአፄ እስክንድር የመጀመሪያ የአዳል ዘመቻ በሽንፈት ከተጠናቀቀ በኋላም አዳሎችን ማስገበር ባለመቻላቸው እየተቆጩ ጦራቸውን እያደራጁና እያጠናከሩ ጥቂት ቆዩ። የእንደራሴዎቻቸውን ስልጣንም ወደ ራሳቸው አዙረው ወደ መጠቅለል አመሩ።

በዚህ ጊዜ አፄ እክንደር የ15 አመት ልጅ የነበሩ ቢሆንም፤ ስልጣን በየጊዜው እየቀነሱባቸው የነበሩ ባለስልጣናት ቂም ያዙባቸውና በየጊዜው እየከዱ አስቸገሩዋቸው። በዚህም ዋናው የጦር አበጋዛቸው ዘስሉስ የተባለው ሳይቀር ከነሠራዊቱ ከዳቸው። ይህን አጋጣሚም የአዳል ባላባቶች ሲጠቀሙበት ፈለጉ። እንደ ጀምስ ብሩስ አገላለፅ "ከበእደ ማርያም ጀምሮ የኢትዮጵያን የታወቀውን ግዛት እየወረሩ አሁንም በአፄ እስክንድር ጊዜ በየጊዜው ጦርነቱን የሚያነሱት የወላስማ ዘሮች (የአዳል ባላባቶች) ናቸው። አፄ እስክንድርም በሁለተኛው ዘመቻው ጊዜ የተዋጋው አሚር ማህፉዝ ከተባለው ጋር ነው።" ምንም እንኳን በመጀመሪያው ጦርነት ንጉሱ ተሸንፈው ቢመለሱም ከዚያ በኋላ ባደረጉት ውጊያ ግን የአዳሉን ንጉስ ልጅ ገድለው ብዙዎችን ማርከው ለማስገበር ችለዋል።

ከዚህ ድል በኋላ ዘስሉስ የተባለው የጦር መሪ ከድቶ በአፋር እና በትግሬ አገር መካከል የሚገኙ ከአሱብ እና ከአንጎት ጨው እያመላለሱ የሚነግዱ ሰዎችን እያስተባበረና እያሳመፀ በኢትዮጵያ መንግስት ላይ ተነሳ።

አፄ እስክንድር ዘስሉስን ወግቶ የሚማርክ ጦር አዘጋጅተው ተክላይ የተባለ ታማኝ አገልጋያቸውን ከብዙ ሰራዊት ጋር ላኩበት። ታማኙ አገልጋይ ተክላይ በዘስሉስ መገደሉን መልእክተኞች መጥተው ሲያረዷቸውም እጅግ አዝነው ራሳቸው ለመዝመት ተነሱ።

እነዚህ የአርኖ ሰዎች የሚባሉት አመፀኞችም በሌሊት ጠብቀው በዘስሉስ ትእዛዝ አፄ እስክንድርን በጨለማ ወግተው ገደሏቸው። አፄ እስክንድር ከተገደሉ በኋላም ዘስሉስ እስከሬናቸው ወደ አገራቸው እንዳያልፍ፡ (እንዳይመለስ) አሳገደና የሚፈልገውን የነጋሲ ዘር ለማንገስ መዘጋጀት ጀመረ። የእስክንድር ወታደሮች ግን በአንድነት ሆነው ዘስሉስንና ተከታዮቻቸውን ገደሏቸው።

አፄ እስክንድር ሁሉንም ስልጣን በልጅነቱ ጠቅልዬ እይዛለሁ በማለታቸው በዚህ መሰሉ ሁኔታ ሕይወታቸው ሲያልፍ የ22 አመት ወጣት ነበሩ። በ6 አመታቸው ነግሰው ከ16 አመታት የግዛት ዘመን በኋላ በ1486 ዓ.ም ያለፉት ንጉሰነገስት አፄ እስክንድር ልክ እንደ አባቶቻቸው ሁሉ ረፍት በሌለበት የውስጥ እመፅ ነበር ያለፉት።

በዚህ በአፄ እስክንድር ዘመነመንግስት ጊዜም ፖርቱጋሎች ለመጀመሪያ ጊዜ መልእክተኛ ልከው ከክርስቲያናዊቷ አገር ከኢትዮጵያ ጋር ወዳጅ ለመሆን መፈለጋቸውን ያሳወቁበት ጊዜ ነበር። መልእክተኞቻቸውም ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ከፖርቱጋል ንጉስ የተላከው ደብዳቤ የተሰጠው ለአፄ እስክንድር የነበረ ሲሆን፣ ከዚህ ጊዜ በኋላ ባሉት ተከታታይ አመታትም የኢትዮጵያ እና የፖርቱጋል ግንኙነት እየጠነከረ ሄዶ አንድ ራሱን የቻለ ታሪካዊ ትስስር የተፈጠረበት ሁኔታ እንዲከሰት በር ከፍቷል።



# ምዕራፍ ፶፱
# ቱርክ፣ ፖርቱጋል እና ኢትዮጵያ

በዚህ ምዕራፍ ለዘመናት ስለተፋጠጡት ሁለት አገሮች ስለ ፖርቱጋል እና ስለ ቱርክ አጠቃላይ ሁኔታ የተመለከተውን ታሪክ እናያለን። ምክንያቱም ታሪኩ በቀጥታ ከኢትዮጵያ ጋር የተያየዘ በመሆኑ ሲሆን፣ በተጨማሪም ለቀጣይ ታሪኮች ግልፅ መሆን መሰረታዊ መነሻችን ይሆናል።

ከጥንት ጀምሮ ከክርስትና በፊት በነበረው ከ3ሺ እስከ 700 አመት ድረስ ገብፅ ተወዳዳሪ ያልነበራት ገናና እና ሃያል አገር ነበረች። ተፎካካሪዎቿም አሶር ባቢሎን እና ፋርሶች ነበሩ። እነዚህ አገሮች እጅግ ስልጡን በነበሩበት ዘመን ሃያላን ነገስታቶቻቸው ቱትሞሲስ፣ ራምሲስ፣ አሱርባኒፖል፣ አሳርሐደን፣ ሰናክሬም፣ ናቡከደናፆር፣ ቂሮስ፣ ካምቤዝና ሌሎች ከቦታ ቦታ እየተዘዋወሩ ግዛት ለማስፋፋት ሲጥሩ፣ ግሪኮች ገና ኋላ ቀሮች ነበሩ። ሮማውያውን ደግሞ ተራ ገበሬዎች ሲሆኑ፣ አረቦችም በበረሐ ግመል እየነዱ የሚዞሩ ዘላኖች ነበሩ።

በነዚያ ጊዜያቶች ቱርክና ፖርቱጋልም ሆነ ሌላው የአውሮፓ አገር ህዝቦች ፈፅሞ ድምፃቸው ተሰምቶ አያውቅም። በአጠቃላይ ስልጣኔ ከኢትዮጵያ ወደ ግብፅ፣ ከግብፅ ወደ አሶር፣ ከአሶር ወደ ባቢሎን፣ ከባቢሎን ወደ ፋርስ፣ ከፋርስ ወደ ግሪክ፣ ከግሪክ ወደ ሮማውያን፣ ከሮማውያን ወደ አረቦች ሲተላለፍ ቆይቶ በዚህ በመካከለኛው ዘመን የአረብን ስልጣኔና ሐይማኖት የያዙት ቱርኮች በአንደ በኩል ሲገኑ፣ የሮማውያንን ስልጣኔና የሮማ ካቶሊክ ሃይማኖትን የወረሱት የፖርቱጋል ተወላጆች ደግሞ በሌላ በኩል ስልጡንና ገናና ሊሆኑ ቻሉ።

የፖርቱጋል መገኛ ቦታ በምዕራብና በደቡብ ከአትላንቲክ ውቅያኖስ፣ በምስራቅ ከእስፔን የሚዋሰን ሆኖ፣ ህዝቦቿም ሳልቶ ሃቤሪክ የሚባሉ የህንድ ዝርያ ያላቸው አውሮፓውያን ነበሩ። ከዚያም በየጊዜው በደረሳባቸው ወረራ በሮማውያንና በአረቦች በጀርመንና በኖርማንዲ እንዲሁም ከአፍሪካ/ከሰሜን አፍሪካ/ በሔዱ ህዝቦች የተዳቀለ ዘር ነው በፖርቱጋል የሰፈረው። ሆኖም ረጅሙን ዘመን የገዟቸው ሮማውያን ስለነበሩ በዘር፣ በልማድ፣ በሐይማኖትና በሌሎች ዘርፈ ብዙ ነገራቸው ወደ ሮማውያንነት ያዘነብላሉ። ወይም ወደ ላቲንነት ተለውጠዋል።

የጀርመን፣ የሮማውያንንና የሌሎችን ወረራ ካሳለፉ በኋላ ከ10ኛው መቶ ዓ.ም ጀምረው የራሳቸውን መንግስት አቋቁመው ቆዩና በዚህ በ14ኛው መቶ ዓ.ም ላይ ግን ያገኙትን የነፃነት ጊዜ በመጠቀም በእግረኛ ጦር፣ በባህር ሃይልና በሌሎች አደረጃጀቶች እየበረቱ ሄዱ።

የአውሮፓ መንግስታት በዚህ በመካከለኛው ዘመን እንግሊዝ፣ ፈረንሳይ፣ ጀርመን፣ ስፔን፣ ጣሊያን በየግዛታቸው በዘውድ በዙፋንና በሃይማኖት እርስ በርስ ሲባሉ የፖርቹጋል መንግስት ምርጥ ምርጥ መርከቦች እየሰሩ የአሜሪካንን፣ የእስያን፣ የአፍሪካንና የሌሎችን የአለም አገራት እያስመረመሩና እየሰለሉ ግዛታቸውን ማስፋፋት ተያያዙት። በ1500 ዓ.ም ገደማ ብራዚልን፣ ህንድንና ፊሊፒንስን ጨምሮ በርካታ አገሮችን በቅኝ ግዛት ያዙ።
በሌላ በኩል ቱርኮች ከ11ኛው መቶ ዓመተ ምህረት ጀምሮ ከቱርኪስታን ተነስተው መካከለኛው ምስራቅን ሁሉ ይዘው ታላቁን የቆስጠንጥንያ መንግስት አሸንፈው ባቢሎንን፣ ፓለስታይንን ሶርያን ያዙ። እየሩሳሌምንም ተቆጣጠሩ። በዚህም የፈረንሳይ፣ የእንግሊዝ፣ የጀርመን ክርስቲያናዊ አገሮች ተባብረው ከዚህ ቀደም እንዳየነው እየሩሳሌምን ለማስለቀቅ ቢዋጉም አልቻሉም። በመጨረሻም የቱርክ መንግስት ከየመን አልፎ ወደ አፍሪካ ድንበር ተሻገረና ግብፅንም አሸንፎ በመያዝ ከዚያም በኤርትራ ባህር ጉብቶ ምፅዋን በ1310 ዓ.ም ያዘ። በያዘው አገርም የአረቦችን ሃይማኖት እያፀና ቀጠለ።

የፖርቹጋል መንግስትም ከግዛቱ ከህንድ የተነሳ ጦር በመላክ ዘይላን በ1516 እ.ኤ.አ ያዘና በቀይ ባህር ላይም ወዲያ ወዲህ ሲል ቆይቶ ከቱርክ ጋር ግጭት ፈጥሮ የነበረ ቢሆንም ቱርኮች ስላየሉ መልሰው ዘይላን ያዙ። ቱርኮች ዘይላን መያዛቸውም የሐረርና የአዳልን ባላባቶችን ደስ አሰኛቸው። የመሳሪያ እርዳታም በገፍ ያገኙ ጀመር።

ፖርቹጋሎች ደግሞ በምስራቅ አፍሪካና በቀይ ባህር ላይ እየተመላለሱ ቀይ ባህርን አስቀድመው ከያዙት ከቱርክ መንግስት ጋር በክፉ አይን እየተያዩ ያሉበት ሁኔታ ተጠናክሮ ቀጥሎ ነበር። ስለዚህም ፖርቹጋል ቱርክን ለመፋለም ይረዳት ዘንድ ከክርስቲያኑ ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር መወዳጀትና ግንኙት መመስረት ጠቃሚ ሆኖ ታያት።
ስለዚህ ንጉስ ጆን የሚባለው የፖርቹጋል ንጉስ ፔድሮ ደ ኮቪልሐኦ የሚባል እና ደ ፓይቫ የሚባል ፖርቹጋላዊ ወደ ኢትዮጵያ ሄደው ከንጉስ ጋር እንዲገናኙ ደብዳቤ አስይዞ ላካቸው።
እነዚህ ሁለት መልእክተኞች እ.ኤ.አ በ1486 ዓ.ም ከፖርቹጋል ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ በቱርክ ይጠበቅ በነበረው ወደብ እንዳይያዙ በመስጋት የነጋዴ ልብስ ለብሰው ወደ ኢትዮጵያ ሲገቡ ደ ፓይቫ የተባለው በርበራ ወደብ ላይ ሲሞት፣ ፔድሮ ደ ከቪልሐኦ በሰላም ደረሰ። መልዕክቱን ለአፄ እስክንድር አድርሶ አፄ እስክንድርም በሰላም ተቀብለው ሲያስተናግዱት ቆይተዋል።



አፄ እስክንደር ከሞቱ በኋላም በቀጣዮቹ ጊዜ ይህ መልእክተኛ እዚሁ ኢትዮጵያ ውስጥ ቀረ። ከአፄ እስክንድር በኋላ ከነገሱት ከአፄ ናኦድም ከአፄ ልብነድንግል ጋርም ወዳጅ ሆኖ ቀጠለ። ይባስ ብሎም ከአንዲት ሴት ወይዘሮ ኢትዮጵያዊ ጋር ትዳር እንዲመሰርት የአፄ በእደማርያም ሚስት የነበሩት ግራት አድርገው ቆንጆ ሴት አጋብተውት መኖር ጀመረ። የቤተመንግስት ባለሟል እስከመሆንም ደረሰ።
በኋላም በዚሁ መልእክተኛ ሃሳብ አቅራቢነት በአፄ ልብነድንግል ጊዜ ከንግስት እሌኒ የወዳጅነት ደብዳቤ ወደ ፖርቹጋል ንጉስ እንዲላክ ሆነ።

ንግስት እሌኒ በክርስቲያኑ የኢትዮጵያ መንግስት ላይ ሙስሊሞቹ የወረራ ስሜት እንዳላቸው ስለሚያውቁና እነዚህን ባላጋራዎች ለመመለስ ከክርስቲያኑ የፖርቹጋል ንጉስ እርዳታ ለማግኘት መፈለጋቸው ግልፅ ሲሆን፣ በተመሳሳይም ፖርቹጋሎች ከተፎካካሪያቸው ቱርክ ጋር ያለባቸውን ስጋት ከኢትዮጵያ ጋር በመወገን ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ ይፈልጋሉ።
ስለዚህም በዚህ በ15ኛው ክ/ዘ ቱርክና ፖርቹጋል ሃያላን አገር ሆነው ለየራሳቸው ጥቅም እንዱ እንዱን ለመርዳት ይራኮቱ የነበረበት ጊዜ ነበርና የኢትዮጵያ የእርስ በርስ ግጭት ካልተማከለና በደንብ ካልተደራጀ ከነበረው አካሔድ በማፈንገጥ ወደ ጠንካራና ወደተደራጀ ሃይለኛ የእርስ በርስ ጦርነት ሊሸጋገር ችሏል።

# ምዕራፍ ፶፫
# የአፄ ናኦድ ዘመነ መንግስት
# ከ1487-1500 ዓ.ም

አፄ ናኦድ በነገሱበት ዘመን ዙፋኑን የሚመለከቱ ውዝግቦች በስፋት ታይተው ነበር። አፄ እስክንድር ከሞቱ በኋላ ህፃን ልጃቸው ልዑል እንድርያስ የ7 አመት ህፃን የነበረና በ15 አመታቸው የወለዱት ልጅ ነበር።

በዘመኑ እንዳይሸፍቱ በመስጋት የነገስታት ልጆች /ዘሮች/ በአምባግሸን በልዩ ጥበቃ ስር ሆነው ይቀመጡ ነበር። ከዚያም የቤተክህነቱና የቤተመንግስቱ ባለሥልጣኖች ተመካክረው የመረጡትን በአዋጅ ያነግሳሉ። ይህም የሚሆነው የበፊቱ ንጉስነገስት ሳይናዘዝ ከሞተ ነው። አፄ እስክንድር ደግሞ ሳይናዘዙ ነበር ድንገት የሞቱት።

በዚህ መሰረት አፄ እስክንድር በሞቱ ጊዜ በአንዱ ወገን ስምምነት አፄ ናኦድን ከአምባ ግሸን አስመጥተው አነገሱዋቸው። ሆኖም ሌላው ወገን ስራ ተቃውሞ አነሳ። ይህም የሆነበት ምክንያት ከአፄ እስክንድር ጀምሮ በእደራሴነት አገሪቱን ሲያስተዳድር የነበረው ሹም ብህትወደድ አምደሚካኤል የአፄ ናኦድን መንገስ ተቃውሞ ሌላ እንደ ልቡ የሚያሽከረክረው የነገስታት ዘር ለማንገስ በማሰቡ ነበር።

ይህ የታሰበው ንጉስም የአፄ እስክንድር ልጅ ሲሆን፤ በእድሜ ያልበሰለ የ7 አመት ህፃን ልጅ ነው። ራስ ብህትወደድ አምደሚካኤል ባሰበው መሰረት የ7 አመቱን ህፃን ልዑል እንድርያስን ከአምባ ግሸን አስመጥቶ "አምደ ፅዮን 2ኛ" በሚል ስመ መንግስት አነገሰው። አፄ ናኦድም በደጋፊዎቻቸው ድጋፍ ቀደም ብለው ከነገሱ በኋላ ክላይ ባየነው መሰረት በራስ ብህትወደድ አምደሚካኤል ተቃዋሚነት ብቻ ተመልሰው ንግስናውንም ዘውዱንም ተገፈው ወደ ቀድሞ መኖሪያቸው ወደ ግሸን አምባ ተመለሱ።

በዚህም አፄ ናኦድ በራስ ብህትወደድ አምደሚካኤል ላይ አደገኛ ቂም ቢይዙም ምቹ ሁኔታን ከመጠበቅና ነገሩን የተቀበሉት መስለው ከመታየት ውጭ አማራጭ አልነበራቸውም። ነገር ግን ንጉስ እንድርያስ ወይም አምደፅዮን 2ኛ 7ወር ኢትዮጵያን እንደገዙ በድንገት በሰባት ዓመት ከሰባት ወራቸው ስለሞቱ የእንደራሴነቱ ሃሳብ ከሸፈ።

ህዝቡም ንጉሱ በልጅነታቸው የተቀጨት በፈጣሪ ቁጣ ነው ብሎ አመነ። ቀጥሎም በቤተመንግስቱ ጥቂት ሁከት ከሆነ በኋላ አምደፅዮን 2ኛ በሞቱ በ3ኛው ቀን ናኦድን እንደገና አምጥተው አነገሱዋቸውና ስመ መንግስታቸውን "አንበሳ በፀር" ብለው ሰየሙላቸው።



ራስ ብህትወደድ አምደሚካኤልም የአፄ ናኦድን መንገስ አምኖ የተቀበለው ፈልጎት ሳይሆን በወቅቱ ሌላ የሚቀርብ ልዑል ባለመኖሩ ብቻ ነው።

አፄ ናኦድ የአፄ እስክንድር ታናሽ ወንድም ናቸው። ሆኖም አባታቸው አፄ በእደማርያም እነዚህን ሁለት ልጆች የወለዱት ከተለያዩ ሴቶች ሲሆን፤ አፄ እስክንድርን ከዋና ሚስታቸው፤ አፄ ናኦድን ከእቁባታቸው ነበር የወለዷቸው። ቀደም ሲል ያየነው የ7 አመት ልሁል ግን በቀጥታ ከአፄ እስክንድር የሚወለድ ነው። ስለዚህ አፄ ናኦድ ከእቁባት፤ አፄ እስክንድር ከዋና ሚስት በመወለዳቸው ሳቢያ ተፈላጊነት የነበረው ዘር /ለዙፋን የሚቀርብ/ ከዋና ሚስት የተወለደው ነበርና አፄ እስክንድር ነግሰው ከዚያም ልጃቸው እንድርያስ ተከትለው አፄ ናኦድ ላይ ደግሞ ውዝግብ መፈጠሩ የዘር ቆጠራውን ባህል ግልፅ ያደርገዋል። ሆኖም ይህን መሰሉን የዘር አወራረድ የሚያተኩሩበት በዙሪያው ያሉ ሹማምንት ለገዛ ጥቅማቸው ሊጠቀሙበት ሲፈልጉ እንጂ ዘር በአባት ስለሆነ ብዙ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ አልነበርም።

የሆነ ሆኖ አፄ ናኦድ በ22 አመታቸው የኢትዮጵያ ንጉስ ነገስት ሆነው ኢትዮጵያን ማስተዳደር የጀመሩት በ1487 ዓ.ም ነበር።

የአፄ ናኦድን ታሪክና የዚያ ዘመኗን ኢትዮጵያ ታሪክ በተመለከተ ዜና መዋዕሉ የአፄ ናኦድን ደግነታቸውንና ሩህሩህነታቸውን ሲገልፅ፤ የአገር ውስጥና የውጭ አገር ፀሃፍት ደግሞ በደግነታቸውና በደትር ባይነታቸው አምነው፤ ነገር ግን የበቀል እርምጃቸው የከፋ እንደነበርና አንዳንዴ ደግ፣ ሌላ ጊዜ ሃይለኛና ፍርደ ገምድል እያደረጉ ታሪካቸውን ፅፈውላቸዋል።

አፄ ናኦድ መንግስታቸውን ካደላደሉ በኋላ ራስ ብህትወደድ አምዱን አስይዘው ከአንገቱ በስተቀር መላ ሰውነቱን መሬት አስቆፍረው በማስቀበር በላዩ ላይ የደለቡ ከብቶች እንዲረማመዱበት በማድረግ እንዲሞት አደረጉት።

ንጉስ ናኦድ ይህን ያደረጉበት ምክንያት ግልፅ መነሻው በቀል ሲሆን፤ በተጨማሪም በይትርታ ቢያልፉት ወደፊት የስልጣናቸው ስጋት ሆኖ እንደሚቀጥል በማሰብ ነው።

ካየነው ጠንካራ የቅጣት እርምጃ በኋላም አንድ ህግ ደነገጉና ህዝቡ በጨካኝነት እንዳይፈርጃቸው ስማቸውን ወደ ማደስ አመሩ። ይህ ህግ ይቅር ባይነትን የሚያውጅ ድንጋጌ ሲሆን፤ እርስ በርስ መካሰስንና በህዝቦች ዘንድ የቂም በቀል ድርጊት መፈፀም ወንጀል መሆኑንና ከፉ ቅጣት እንደሚያስከትል አወጁ።

ከዚህ አንፃር አንዱ ክፉ አድርጎ ሲስላቸው፤ ሌላው ደግና ሩህሩህ እያለ ቢያሞግሳቸው ሳያስገርም ይችላል። የደነገጉትን ህግም ራሳቸው ተግባራዊ አድርገው የሚያሳዩበትንና አርአያ ሆነው ለመታየት ያስቻላቸው አጋጣሚ ተፈጠረላቸው።

ይህም አጋጣሚ አፄ ናኦድ ወደ አንድ መንፈሳዊ ቦታ አምርተው ወደ ሸዋ ስመመለስ ጉዞ በጀመሩበት ጊዜ በመንገዳቸው ላይ "ተካ ክርቶስ" የተባለ የታወቀ አመፀኛ ሽፍታ በመንግስታቸው ላይ ጥብቅ ሴራ ጠንስሶ ጠበቃቸው።

ይህን አመፅ ሰምተው በዝምታ ካለፉት በኋላ ተካ ክርስቶስ የአፄ ናኦድን ትዕግስት እንደፍርሃት ቆጥሮና በወታደሮቹ ተማምኖ ደጋፊዎቹን አደራጅቶ አመፁን አስፋፋው።

በዚህ ጊዜ አፄ ናኦድ "ምኞቱን ይፈፅም ዘንደ ዝም በሉት። እኛ በርቀት እንከታተለዋለን። በእርሱ ላይ ክፉ መስራት እምላክ የሚደግፈው ተግባር አይደለምና ተውት" በማለት ዝም አሉ። በዚህ አቋማቸውም ህዝቡን አስደመሙት።

ተካ ክርስቶስ ወታደሮቹን፣ ፈረሰኞቹን አዘጋጅቶ ለጦርነት ወደ ደሩት ጉዞ ጀመረ። የራሱ ወታደሮች ግን አላማባዘ ያመፀ ሽፍታ መሆኑን ተረድተው ሳያስበው በቁጥጥር ስር አውለው አስረው ወደ ንጉሱ ወስደው አስረከቡት።

በዚህ ጊዜ ህዝቡ ሁሉ በዚህ ሽፍታ ብዙ በደል ደርሶበት ነበርና በተካ ክርስቶስ መያዝ በደስታ ሲዘልና እፎይ ሲል፤ እንዲሁም የሚጠብቀውን ከባድ ቅጣት እያሰበ ሲደሰት አፄ ናኦድ ግን ይህን ሽፍታ መግደል አልፈለጉም። ይልቁንም በግዞት እንዲቀመጥ ብቻ ፈረዱበትና ተውት።

ህዝቡም የንጉሱን ባህሪ በቀጥታ ማወቅ ተሣነው። ይህን ለዙፋን አስጊ የሆነን ሽፍታ እንዴት ግዞት ብቻ ይፈርዱበታል የሚል ተቃውሞ ተስተጋባ። አፄ ናኦድ ግን ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ ከዚህ ጊዜ ጀምረው የይቅር ባይነት አቀንቃኝ ሆነው ተገኙ። ይሁን እንጂ በግዞት ያለውን ተካ ክርስቶስን ከጥቂት ወራት በኋላ ጠባቂዎቹ አይኑን አጠፉት። ወታደሮቹ ይህንን ድርጊት የፈፀሙት በራሳቸው ፍላጎትና ስልጣን ወይም በንጉሱ ልዩ እና ሚስጥራዊ ትዕዛዝ በግልፅ አይታወቅም። ሆኖም ያለንጉሱ ትዕዛዝ ይህን የድፍረት ሃሳብ የሚፈፅም አለመኖሩን ስንረዳ ንጉሱ ራሳቸው በእጅ አዙር እንደፈፀሙት መገመት እንችላለን።

በዘመናቸው ህዝቡ ሁሉ በደለኞች መቀጣት አለባቸው በሚል መነሻ አንዱ ሌላውን "በአፄ እስክንድር ዘመን እንኳ ይህን ሰርቷል እንዲህ ያለ በደል ፈፅሟል..." ወዘተ እያለ እርስ በርሱ በመካሰስ ሁከት ይፈጥር



ጀምሮ ነበርና፤ የሁከቱን መበርከትና መጋነን ያስተዋሉት ብልጣ ብልጡ አፄ ናኦድ ቀደም ሲል ያየነውን አዋጅ ማለትም ባለፈው ጊዜ እንኳ ይሄን ሰርቷል እያላችሁ ባለፈ ነገር አትካሰሱ። አንዱ በሌላው ላይ ይህን የመሰለ ክስ ያቀረበ እንደሆነ የመጀመሪያው አዋጅ "ክፉ ቅጣት" የሚለው "በሞት" መለወጡን አወጁ።

በዚህም በርስት ጉዳይ ካልሆነ በቀር በቂም በቀል ሳቢያ የሚቀርቡ ክሶች ተቀባይነት ካለመኖራቸውም በላይ በሞት እንደሚያስቀጣ መወሰኑ ከአፄ እስክንድር ጊዜ ጀምሮ በተፈጠረው የሹማምንቱ ክፍፍል ምክንያት እስከዚህ ድረስ ተባብሶ ቀጥሎ ነበርና፤ አሁን ግን ሙሉ ለሙሉ ተረጋግቶ ሰላም ሰፈነ። ህዝቡም በዚህ ውሳኔ ደስታውን ገለፀ። በጎራ ተከፍሎ መናቆሩም ተገታ።

የደሩት ወላስሞች /ባላባቶች/ መቀመጫቸውን በደሩት ድንበር አድርገው፣ ሳይመቻቸው ሲቀር ደግሞ ወደ አዳልና ወደ ዘይላ እየተዘዋወሩ ይኖሩ የነበረ ሲሆን፤ በአፄ ናኦድ የግዛት ዘመን ላይ ግን መቀመጫቸውን ወደ ሐረርጌ አዛውረዋል።

ጥቂቶች ደግሞ በዚያው በወላስማ ዘር እየተመሩ በአዳልና በአካባቢው እንደተቀመጡ ነበሩ። ስለዚህም በዚያው ዘመን ወደ ኢትዮጵያ ማዕከላዊ መንግስት ግዛቶች እየመጡ ግዛት በማስፋፋት ተግባራቸው እንደተጠመዱ ነበሩ።

በዚህ በአፄ ናኦድ ጊዜ ግዛት በማስፋፋት ስማቸው የሚጠራው አቡበክር እና ማህፉዝ ናቸው። የወላስሞችን ግዛት መቀመጫ ከአዳል ወደ ሐረርጌ ለመጀመሪያ ጊዜ ያዛወሩትም አቡበክር የተባሉትና ስመ ጥር የሆኑት መሪያቸው ናቸው።

ማህፉዝ የተባሉት ደግሞ የአቡበክርን እህት አግብተው በኋለኛው ዘመን ስመ ጥር የሆኑትንና በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ሰፊ ቦታ የተሰጣቸውን የግራኝ አህመድን ባለቤት ባቲድል ወንበራን ወልደዋል።

አፄ ናኦድም በዘመናቸው እንደአባቶቻቸው ሁሉ ኢትዮጵያንና ግዛቶቿን በአንድ መንግስት ስር ለማድረግና ለመጠቅለል እየተዋጉ የበላይነታቸውን ለማረጋገጥ ብዙ ጥረዋል።

ሁኔታው እየተካረረና በእርስ በርስ ግጭቱ መላዋ ኢትዮጵያ እንዳትረበሽ ለማድረግ ሲሉም ነገሩ በሰላማዊ መንገድ የሚቋጭበትን የመፍትሄ ሃሳብ ከአያቶቻቸው ከእንዘርዓያዕቆብ ከአባታቸው ከአፄ በእደማርያም በመኮረጅ የደዋሮውን ገራድ ልጅ አግብተው ህጋዊ ሚስታቸው በማድረግ ክርስትና አስነስተው እንደ እያትና አባታቸው ሁሉ ስማቸውን እሌኒ አሰኙተዋል። እኒህ ሰስተኛዋ እሌኒም የኢትዮጵያ ንግስት

ሆነው የንግስና በዓላቸው እለት "ናኦድ ሞገሳ" የሚል ስመ መንግስት ተሰይሞላቸዋል።

አፄ ናኦድ ያገቧቸው ንግስት እሌኒ /ናኦድ ሞገሳ/ በቀጣዩ የአፄ ልብነድንግል ዘመን ሞግዚትም፣ መሪም፣ መካሪም ሆነው ኢትዮጵያን ያገለገሉና ስመ ጥር የሆኑ ንግስት እንደነበሩም ወደ ፊት ባለው ታሪካቸው እንረዳለን።

ይህ ሁሉ ሆኖ ግን የጋብቻ ትስስሩ የታሰበውን ለውጥ ለማምጣት አልቻለም። በአፄ ናኦድ ጊዜ የደዋሮዎቹና የሐድያዎቹ ባላባቶች በሰላም ሲቀጥሉ፤ ሌሎች በሐረርጌና በአዳል የሚገኙት መስፍኖች ግን እየሸፈቱ አስቸገሩ። እነዚህ ወገኖች ለመሸፈታቸው ምክንያት የሆናቸው ይፋት፣ ደዋሮ፣ ሐድያና ባሌ ላይ ስልጣናቸውን ለማጥበቅና ለማእከላዊ መንግስት ላለመገበር እንደነበረም ተደጋግሞ ተገልጿል። የቱርክ እርዳታ እንዳጠነከራቸውም እንዲሁ።

አልባሬዝ የተባለ ፀሐፊ ክጥንታዊ ፅሁፎች ላይ ቃርሞ በፃፈውና እርሱንሃ" እየጠቀሱ በፃፉት ጀምስ ብሩስ፣ ባብቲስት ኩልቦ፣ እንዲሁም ሌሎች እንዳሰፈሩት "የአዳሉ ንጉስ በያለበት አገር እየዘረፈ ባስቸገረ ጊዜ አፄ ናኦድ ከእርሳቸው ጋር የነበሩትን የአዳል ወገኖች እየሰለሉ ወሬ ከማቀበልና እኔን ከመጉዳት በቀር ሲጠቅሙኝ አልቻሉም በማለት ሁሉንም ወደየአገራቸው አሰናብተው የራሳቸውን ጦር አደራጅተው ማህፉዝን ለመውጋት ንጉሱ ጉዞ የጀመሩትም የተለያዩ ዲፕሎማሲያዊ ጥረታቸው ባሰቡት መንገድ ባለመሳካቱ ነበር" ይሉናል።

ይህን ወቅት ደግሞ ለየት የሚያደርገው የፆም ወቅት መሆኑ ነው። ቢሆንም የማህፉዝን ገስግሶ መምጣት የሰሙት አፄ ናኦድ " በጦርነት ሰአት ወታደር አይፆምምና ብሉ" ብለው ፈቀዱ።

የዚያ ዘመን መንፈሳዊ መሪም (ጉብረ እንድሪያስ) ወታደሩ በዚህ ጦርነት ሰዓት በልቶ በሰላሙ ጊዜ ንስሐ ገብቶ ለመፆም እንደሚችል አስገነዘቡና ሁሉም ወታደሮች በልተው ተሰለፉ። ጦርነቱ ከመጀመሩ በፊት አፄ ናኦድ ብዙውን ጦር ወደ ኋላ አስቀርተው በአነስተኛ ጦር ለመዋጋት እራሳቸው እየመሩ ሄዱ።

የማህፉዝ ወታደሮችም ከኋላ የቀረ ጦር መኖሩን አላወቁም ነበርና፤ ከመጣባቸው ሰራዊት ጋር በሙሉ ሃይላቸው እየተዋጉ ባለበት ሰዓት ድንገት ከኋላ የቀሩት ወታደሮች መጥተው አጠቋቸው።

እናም ማህፉዝ ባሉበት ሆነው የጠሩን መመታትና መሸሽ፣ መማረክና መሞት፤ ከሸሹት ጥቂት ወታደሮች ስምተው ተመለሱ። እስከዚህ ጊዜ ድረስ የማይበገሩ ጀግና ስለነበሩ፤ በሁሉም ዘንድ ክፍ ያለ



ግምት ስለነበራቸው ተሸንፈው መመለሳቸው በበርካቶች ዘንድ መገረምንና ፍርሐትን አሳደረ።

ከዚህ በኋላ የአዳሉ ሱልጣን አፄ ናኦድ ጀግናውን ማህፉዝን ካሸነፉ ወደ እኔ መምጣታቸው አይቀርም በማለት በመልእክተኞች በኩል "እንኳን ደስ ያለህ" የሚል ቃል ላኩ።

ቀጥሎም በአፄ ናኦድ እና በአዳሉ ሱልጣን መካከል የተደረገውን የሰላም ቃል አስታውሰው ወደ አገራቸው እንዳይመጡ አሳሰቧቸው።

አፄ ናኦድም "በአንተ ዘንድ ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ያሉትን ወገኖች ስጠኝና አልመጣብህም" ብለው ላኩ።

ምርኮኞችን የሚረካከቡበት ቀን የ15 ቀን የጊዜ ገደብ ሰጧቸው። የአዳሉ ሱልጣንም ይህንን በሰሙ ጊዜ ከወገኖቻቸው ጋር ተመካክረው በሌሎች ቀደምት ነገስታት ከ30 ዓመታት ጊዜ ያህል ጀምሮ በየጦርነቱ እየተማረኩ በዘረፋም፣ በሽያጭም፣ በሸፍትነትም እየሄዱ በግዛታቸው ይኖሩ የነበሩትን ክርስቲያኖች ሰብስበው ወደ ንጉሱ ወደ አፄ ናኦድ ላኳቸው።

ንጉሱም እነዚህን ሰዎች ተረክበው በድል አድራጊነት በወታደሮቻቸው ታጅበው በታላቅ ክብር እና ደስታ ወደ ቤተመንግስታቸው ተመለሱ።

ይህንን ድል የፖርቹጋል ተወላጅ የሆኑ የታሪክ ፀሃፊዎች ሲገልፁት "ይህ የአፄ ናኦድ ድል አድራጊነት የኢትዮጵያ ማእከላዊ መንግስት የመጨረሻ ድል ነው" ይሉታል። ምክንያቱም ከአፄ ናኦድ በኋላ በተከታተሉት ነገስታቶች ዘንድ የተፈጠሩ ተመሳሳይ ግጭቶች እጅግ ከባድና ነገስታቱ ሲቋቋሙት የከበዳቸው መሆኑን ለመግለፅ ነው። ሁኔታው ሳይረጋጋ ተባብሶ በመቀጠሉም እስከ ግራኝ አህመድ ድረስ ቆይቶ በግራኝ አህመድ ጊዜ ግን ሙሉ ኢትዮጵያን መቆጣጠር እስከመቻል ደርሰዋል።

አፄ ናኦድ ባየነው መልኩ ኢትዮጵያን ከ1487 እስከ 1500 ዓ.ም ድረስ ለ13 ዓመታት ያህል አስተዳድረው በ35 አመታቸው በሞት ተለይተዋል።

በዘመናቸውም በመንፈሳዊ ስራቸው ይታወቁ እንጂ "ማርያም ኢየሱስን አልወለደችም" የሚሉትን ፈላሾች በሰይፍ እንዲፈጁ አድርገዋል።

አፄ ናኦድ የሞቱበትን ዘመን የቤተመንግስትና የቤተክህነት ሊቃውንት አስልተው የሰው ልጅ በተፈጠረ በ7ኛው ሺ አመት ያረፈ ፃድቅ ንጉስ ነበሩ ሲሉ ያወድሷቸዋል። ከክርስቶስ ልደት በፊት 5 ሺ 500 ዓመታትንና ከልደት በኋላ 1ሺ 500ውን በመደመር ማለት ነው።

አፄ ናኦድ በመጨረሻው ዘመናቸው በመንፈሳዊ ስራ ተጠምደው ከ30 የሚበልጡ መንፈሳዊ መፅሃፍትን በእጃቸው ፅፈው ለየአድባራቱ እንዳበረከቱም ይታወቃል። ስልጣኑንም ከአባታቸው የተረከቡት ብቸኛ ወንድ ልጃቸው ልብነ ድንግል ናቸው።

# ምዕራፍ ፶፬

## የአፄ ልብነ-ድንግል ዘመነ መንግስት

### ከ1500-1532 ዓ.ም

ከይኩኖ አምላክ ጀምሮ እስከ አፄ ልብነ-ድንግል ድረስ የኢትዮጵያ ማዕከላዊ መንግስት መቀመጫ መንዝና ተጉለት (ደብረብርሃን) እንዲሁም፤ በቡልጋ ውስጥ የሚገኘው ፈጠጋር (ያኔ ፈጠጋር አሁን ቡልጋ).. ወዘተ... ሆኖ በዚያው በሸዋ የሚጠቃለለው ቦታ ነበር።

እነዚያ ሁሉ የክርስቲያን ነገስታት መንግስታቸውን ከይፋት፣ ከአዳልና ከሌሎች እንዲሁም ከሐረር ወላስሞችና አሚሮች ጋር እየተዋጉ፣ እየተከላከሉ እያጠቁ እስከዚህ ዘመን ድረስ ለመድረስ ችለዋል።

ክርስቲያን ነገስታቶች ከሸዋ፣ ከትግሬ፣ከወሎ፣ከየጁ፣ከጎጃም፣ከጎንደርና ከሌሎች ግዛቶች የተሠበሠቡ ሠራዊታቸውን ይዘው ሲቀጥሉ፤ አሚሮችና ወላስሞቹ ደግሞ ከሐረር እስከ ህንድ ውቅያኖስ ድንበር ከሐረር እስከ ኤደን ጠረፍ ድረስ የሚገኘውን ህዝብ በሃይማኖትና በዘር ትስስር እየሣመኑ የሱማሌ፣የአዳልና የአክባቢውን ሕዝብ እያደራጁ ነበር የቀጠሉት። ሲመቻቸውም በደዋሮና በፈጠጋር ስም ይጠራ የነበረውን ግዛት እየወረሩ፣ እየዘረፉ፣እየማረኩ፣ ሳይገብሩ በእንቢታ ፀንተው ሲቆዩ፤ ሳይመች ደግሞ እየገበሩ በሠላም ሲኖሩ መቆየታቸውንም ቀደም ባሉት ምዕራፎች ተረድተናል።

በዚህ በአፄ ልብነ-ድንግል ዘመነ መንግስት ጊዜ ግን ሁኔታው የበለጠ ተባብሶ የቀጠለበት ሁኔታ ከመኖሩም በላይ፤ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገስቶች መቀመጫ ከተማም ወደ ሌላ ቦታ እስከመዛወር የተደረሠበት ሁኔታ ሲፈጠር እናያለን።

አፄ ልብነ-ድንግል የአፄ ናኦድ ልጅ ናቸው። አፄ ናኦድ 13 አመት ገዝተው በ1500 ዓ.ም ሲሞቱና ልጃቸው ልብነ ድንግል ስልጣናቸውን ሲረከቡ ገና የ12 ዓመት ልጅ ነበሩ። ስለዚህም እናታቸው እቴጌ ናኦድ ሞገሣ እና የአያታቸው የአፄ በእደማርያም ባለቤት የነበሩት እቴጌ እሌኒ እንዲሁም ዘመዶቻቸውና ታላላቅ ሹማምንት እንደሞግዚት ሆነው ያስተዳደሩን ስራ እንዲያግዟቸው ተደረገ። እንደማንኛውም ንጉሠነገስት የልጅነት ጊዜያቸውን አደን፣ዋና፣ፈረስ ግልቢያና ሌሎች የዘመኑን አስፈላጊ ነገሮች ሲለማመዱ አደጉ። በስልጣናቸው ዘመንም ኢትዮጵያ ከሌላው ጊዜ የተሻለ የእርሻና የተለያዩ የአገር ውስጥ ስራዎች ተስፋፍተው የታዩበትና ህዝቡ የተሻለ ኑሮ መምራት የቻለበት ጊዜ ሆነ።

በአፄ ልብነ-ድንግል ዘመን 60 የሚሆኑ የውጭ ዜጎች ባልተለመደ ሁኔታ ኢትዮጵያ ውስጥ ይኖሩ ነበር።



ከእነዚህም ውስጥ ፖርቹጋሎች ይበረክቱ ነበርና የፖርቹጋልን ታላቅነት ደጋግመው ለንጉስ ነገስቱና ለሹማምንቱ ሲገልፁ እቴጌ እሌኒ ወደ ፖርቹጋል ንጉስ የወዳጅነት ደብዳቤ ለመላክ አሠቡ።

ደብዳቤውን የሚያደርስ የውጭ ዜጋ ሲመረጥም ማቴዎስ የተባለው የአርመን ተወላጅ እንዲላክ ተወሠነ። እቴጌ እሌኒ ደብዳቤና የወርቅ መስቀል አስይዘው በ1502 ዓ.ም ሸኙት። በመጀመሪያ ወደ ህንድ፣ ከዚያም በፖርቹጋሎች መርከብ ተሣፍሮ ከ3 ዓመት በኋላ ፖርቹጋል ደረሰ። የተላከውን ደብዳቤና የወርቅ መስቀል ለንጉሱ ኢማኑኤል አበረከተ።

የደብዳቤው ይዘትም ሁለት ነገሮችን የሚያመላክት ሲሆን፤ በአንድ በኩል ቀደም ሲል በንጉሱ ጆን ተልኮ የመጣው ፔድሮ ኢትዮጵያ ውስጥ ኑሮውን በመመስረቱ ዘራችሁ ከዘራችን ተደባልቆ ዝምድና ተመሥርቷል። የሚል ይዘት ሲኖረው በሌላ በኩል የፖርቹጋል መንግስት በየብስና በባህር ላይ ሃያል ስለሆነ ሃይሉ ከኢትዮጵያ ሃይል ጋር ጥምረት ፈጥሮ በቀይ ባህር ላይ የተሠማራውንና የሙስሊሞች ረዳት የሆነውን ገናናውን የቱርክ መንግስት ሃይል ተባብረን እንስበር የሚል ጭብጥ ያለው መልእክት ነው የላኩት።

የፖርቹጋል መንግስትም ከኢትዮጵያ ጋር ቢወዳጅ በተይ ባህርና በህንድ ውቅያኖስ ድንበር፣ እንዲሁም በየወደቦቹ ላይ ጥቅም እንደሚያገኝ መልእክተኛው ጨምሮ ገለፀ። መልእክተኛውን ወደ ሮማው ጳጳስ ወደ ሉዊ 10ኛ ላከው። ጳጳሱም ማቴዎስን ተቀብሎ አነጋገረው። ንጉሡና ጳጳሱ ተመካክረው የካቶሊክ ሃይማኖትን ለመስበክ ዶም ፍራንሲ አልቫሬዝ፣ ጆን ፈርናንዴዝ፣ ፒየር አልፎንሦ የሚባሉ የቤተክህነት ሠዎች ወደ ኢትዮጵያ እንዲሔዱ ሲያደርጉ ጳጳሱ፣ ንጉሡ ደግሞ ለዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ዶም ኤድዋርድ ጋልቫም የተባለና ሌሎች የቤተመንግስት ሠዎችን በ1507 ዓ.ም ተላኩና ከ6 ዓመታት በኋላ ገሚሶቹ በመንገድ ሞተው የቀሩት ከሊገዘበን ሸዋ ደረሡ።

መልእክተኞቹ አፄ ልብነ-ድንግል ወደ ነበሩበት ወደ ይፋት ሔደው በጥቅምት ወር 1513 ዓ.ም ላይ ደብዳቤውንና ገፀበረከቱን ቢያስረክቡም፤ ነገር ግን ኢትዮጵያውያኑ የጠበቁትን ዘመናዊ መሳሪያ ይዘው ባለመምጣታቸውና የቤተክህነት ሠዎች መብርከታቸውን ሲያዩ አቀባበላቸው የቀዘቀዘ ሆነ።

በብዙ ደጅ ጥናት የተገናኟቸውን ንጉሡንም ቸል መባላቸውን በማንሳት "ታዲያ ለምን መጣን?" የሚል ጥያቄ ሲያቀርቡላቸው አፄ ልብነ-ድንግል "እናንተ እንድትመጡ በቃልም, በደብዳቤም ማቴዎስን

አላዘዝንም" የሚል ምላሽ ሠጧቸው። በጊዜ ሂደት ግን ስምምነት ተፈጥሮ የመጡት የውጭ ዜጎችም ልዩ እንክብካቤ እየተደረገላቸው 6 አመት በሸዋ ተቀመጡ። በዚህ መካከል ንጉስ ኢማኑኤል ሞቶ ልጁ ጆን ተተካ።

ከ6 ዓመት ቆይታ በኋላም የመጡትን መልእክተኞች እንደገና ወደ ፖርቹጋል እንዲመለሡ ስንቅ ተዘጋጀና አንድ የወርቅ መስቀል ለጳጳሱ፣ አንድ የወርቅ ዘውድ ለንጉስ ጆን 2ኛ አስይዘው በታላቅ ክብር ሸኟቸው። ፀጋዘአብ የሚባል ኢትዮጵያዊም አብሮ ተላከ።

የተላኩትም የተጀመረው ወዳጅነት ተጠናክሮ እንዲቀጥልና በተጨማሪም የእጅ ሙያ አስተማሪዎችን፣ አናፂና ግንበኞች ከፖርቹጋል ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡ ንጉስ ጆንን ለማስፈቀድ ነበር። ቀድመው ከመጡት አንድ ሠዓሊና ዮሃንስ ቤርሙዴዝ የተባለው ሃኪም ሲቀሩ፤ ሌሎች ፖርቹጊዞች እንዲመለሡ ተደረገ። በ1518 ዓ.ም ተነስተው በምፅዋ አድርገው የሔዱት መልእክተኞች የደረሡበት ጠፍቶ 10 አመት አለፈ። በነዚህ ጊዜያቶች ደግሞ የሙስሊም ወገኖች ወረራ እየተስፋፋና እየተጠናከረ ቀጠለ። ስለዚህ ሐኪሙ ዮሃንስ ቤርሙዴዝ ለእርዳታ ጥያቄ ተላከ።

አፄ ልብነ-ድንግል የውጭ አገር ባለሙያዎች መጥተው ኢትዮጵያውያኑን በልዩ ልዩ ሙያ እንዲያሰለጥኑላቸው ተደጋጋሚ መልእክት ቢልኩም አልሆነም። ምክንያቱም ፖርቹጋሎች ባለሙያ ሲጠየቁ ጥያቄውን ወደ ጎን አድርገው ከዚህ ይልቅ የካቶሊክን ሃይማኖት የሚያስፋፉበትን እድል መናፈቅ ጀመሩ። ኢትዮጵያውያኑ ደግሞ የኦርቶዶክስን ሃይማኖት የማይለቁ ናቸውና በጊዜው የታሠበው ሣይሆን ቀረ። ነገር ግን በኋለኛው ጊዜ 400 ፖርቹጋሎች ዘመናዊ መሣሪያ ታጥቀው የኢትዮጵያን ክርስቲያናዊ መንግስት ለመታደግ የቻሉበት ሁኔታ ሊፈጠር ችሏል። ይህንንም ወደ ፊት እናገኘዋለን።

ይህ በእንዲህ እንዳለም የውስጥ ግጭቱ በርትቶ ነበርና አፄ ልብነ-ድንግልም እንደአባቶቻቸው ከአዳል ባላባቶች ጋር ትግል ውስጥ ነበሩ።

የሐረርና የአዳል ባላባት የነበሩት አሚር ማህፉዝ ከአፄ ናኦድ ጊዜ ጀምሮ የይፋትን ግዛት እየወጉ ከብትም፣ሠውም እየዘረፉ በመውሰድ የአፄ ልብነ-ድንግልን መንግስት አስጨንቀዉ። የቱርኮችን ድጋፍም አገኙ። ቱርኮች ሃይማኖትና ግዛታቸውን ለማስፋፋት ስለሚጠቀሟቸውም ዘመናዊ መሳሪያ ከመስጠት ባለፈ በሐረር ባላባትነታቸው ላይ "የዘይላ አገረ ገዥ" ብለው ሾሟቸው። አዳዲስ መሣሪያም አስታጠቋቸው።

ከዘመናዊ መሳሪያ በተጨማሪም ሌሎች ስጦታዎች ሠጧቸው። የጎረቡ አለም ሙስሊሞች መገለጫ የነበረውን አረንጓዴ የሐር ሠንደቅ ዓላማም ላኩላቸው። አሚር ማህፉዝም /ማህፉድ/ በፋንታቸው ወርቅ፣ ብር፣ የዝሆን ጥርስና ባሪያ በስጦታ ይሠጧቸው ጀመር።

ዘመናዊ መሳሪያ በመታጠቃቸው አዳሎችን ወደ ይፋት እየላኩ ብዙ ህዝብ አስጨርሰው ቤትና ንብረት አዘርፈው ቤተክርስቲያናትን አቃጥለው ከፍተኛ ኪሳራ አደረሱ። የዚህ ወሬም በአፄ ልብነ-ድንግል ቤተመንግስት ሲሠማ ንጉሡ እድሜያቸው 20 ሞልቶ ነበርና ጦራቸውን አደራጅተው በማስከተል ወደ ይፋት ተጓዙ። አሚር ማህፉዝም የአዳሎችን ጦር ሠብሥበው ጠበቋቸው።

በ1508 ዓ.ም በሃምሌ ወር በይፋት አቅራቢያ ጦርነት ተጀመረና የጨበጣ ውጊያ ደራ። ዋናው አዝማች አሚር ማህፉዝም አባ ገብረእንድርያስ ከተባሉ መነኩሴ ጋር በጨበጣ ተዋግተው መነኩሴው ማህፉዝን በሠይፍ ጥለው ራሣቸውን ቆረጡና ለንጉሡ ለአፄ ልብነ-ድንግል አስረከቡ።

እናም አዳሎች የዋና መሪያቸውን መሞትና ከወገናቸው ውስጥ በርካቶች ማለቃቸውን ሲያዩ ሸሽት ጀመሩ። ክርስቲያኖችም እስከ አዳል ድረስ ዘልቀው በመግባት "ዘከሬ" በሚል መጠሪያ የሚታወቀውን የአሚር ማህፉዝን ከተማ አቃጥለውና ዘርፈው ተመለሡ።

ከዚህ ጦርነት በኋላም ከ1508 እስከ 1518 ድረስ 10 ዓመት ሙሉ ኢትዮጵያ ውስጥ አንፃራዊ ሠላምና ዕፎታ ሠፍኖ ቆየ።

አፄ ልብነ-ድንግል እድሜያቸው ለአስተዳደር ሥራ ስለደረሠ ሞግዚቶቹ ቀርተው ብቻቸውን ማስተዳደር ቀጠሉ።

ያልተለመደ ሠላምና ደስታ ከመታየቱም በላይ በየጊዜው ይከሰት የነበረው የሽፍቶች ዘረፋም ሆነ አጠቃላይ የሌብነት ተግባር የማይፈፀምበት ዘመን በመሆኑም አፄ ልብነ-ድንግል ሠፊ ጊዜያቸውን መንፈሳዊ መፅሃፍትን በመመርመርና ሊቃውንትን በማከራከር ያሣልፉ ነበርም ይባላል።

# ምዕራፍ ፶፮
# የግራኝ አህመድ የበላይነት
# (ከ1519-1534 ዓ.ም)

ስለ ግራኝ አህመድ አነሣስ በርካቶች ብዙ የፃፉ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥም ግራኝ በተሠለፈበት የጦር ግንባር አብሮ እየተጓዘ፣ ባደረበት አብሮ እያደረና ጦርነቱን ካየው ሁሉ እንደበት እየሠማ ታሪኩን የፃፈው ሽህ ሙዲን አህመድ ቤን አብዱልቃድር (ዓረብ ፋቂህ) የሚባለው ፀሃፊ ይገኝበታል። የዚህ ሠው "ፍቱህ አል ሐበሻ" የተሠኘ መፅሃፍ እየጠቀሱም ብዙዎች ስለ ግራኝ አህመድ ታሪክ ለመፃፍ ችለዋል።

ከዚህም በተጨማሪ ከፖርቹጋል ተልከው ንጉሡን ለመርዳት ከመጡት 400 የፖርቹጋል ወታደሮች አንዱ የነበረውና በሕይወት ተርፎ ወደ አገሩ ለመመለስ የቻለው ሚጉኤል ዲካስታንሆዞ አጠቃላይ የወቅቱን ሁኔታ በፖርቹጋል ቋንቋ ፅፎ የነበረ ሲሆን፣ ይህ የፖርቹጋሎች ጀግንነት" የሚለው መፅሃፍም በልዩ ልዩ ቋንቋዎች ተተርጉሞ የዚያን ወቅት ታሪክ እየዘከረ ይገኛል።

በአገራችን ታሪክ ነገስትም ስለ ግራኝ አህመድ የታተቱ መጠነኛ ፅሁፍ ይገኛል። አህመድ ኢብን ኢብራሂም አልጋዚ ይባላል። አባቱ ገራድ ኢብራሂም የሚባሉ ሲሆን እናቱ ሽምሺያ የተባሉ የሐረር ሙስሊም እንደነበሩ ይታወቃል።

አህመድ ኢብን ኢብራሂም አልጋዚ በ1498 ዓ.ም የተወለደ መሆኑ ሲታወቅ፤ከባላባት ዘር ለመገኘቱ ግን ቁርጥ ያለ ድምዳሜ ላይ ሊደረስ አልቻለም። ሁሉም ፀሃፍት በራሱ ጥረት ታላቅ መሆን እንደቻለ ነው የሚጠቁሙት። ነገር ግን አባቱ "ገራድ" የሚለውን መጠሪያ ስላገኙ ከመካከለኛው መደብ መገኘቱን መረዳት ይቻላል። ሱማሌዎች ጉራይ ሲሉት፤ ኢትዮጵያውያኑ ደግሞ ግራኝ ይሉታል። ግራኝ የተባለበት ምክንያት ጦር ሲወረውርም ሆነ ሲዋጋ በግራ እጁ በመሆኑ ነው።

ግራኝ አህመድ የልጅነት ጊዜውን በዘላይ (ሁባት) ነው ያሳለፈው። በማህፉዝ ቤትም እንደአገልጋይ ሆኖ ሲኖር በፈረስ ግልቢያ፣ በጦር ውርወራና በአተኳኮስ ልዩ ብቃት እንዳለው ያዩ ሁሉ አድናቆታቸውን ይቸሩት ነበር።

አባቱን ገራድ ኢብራሒም የገደለበት የዘይላው ሱልጣን አቡ በክር ነበር። ከአባቱ ሞት በኋላም የአባቱን ሐብት ወርሶ ተከታዮችን አፈራ። ከዚያም የማህፉድን ልጅ (በመነኩሴው እጅ ሲዋጉ የሞቱትን ልጅ) ባቲ ድል ወንበራን አገባ። እርሷን ካገባ በኋላም የሐረር ወላስሞች ቤተመንግስትን በይገባኛል፣አይገባህም ክርክር እና ጦርነት አሸንፎ ቤተመንግስቱን ወረሠ። ገና እድሜው 20 ያልሞላው ግራኝ በወጣትነቱ የወላስሞችን ከፍተኛ ሥልጣንና



ቤተመንግስቱን በሐይል መውረሱ እንዳለ ሆኖ፤ ሠውነቱ የገዘፈ ጠንካራና አስፈሪ እንደበር ይነገርለታል።

ቀደም ሲል ስራቸውን የጀመሩት ቱርኮችም ወዳይው "የዘይላ ሼህ" ብለው ሾሙት። ቀጥሎም በሃይለኛነቱና በጋብቻው ምክንያት የሐረርና የአዳሎች (የአፋሮች) ሁሉ ዋና መሪ ተባለ። የማእረግ ስሙም "ኢማም መሐመድ" ተሠኘ።

ሚስቱም "የአባቴን ደም ተበቀልልኝ" ትለው እንደነበር ይነገራል። የሆነ ሆኖ በጣም እየተደራጀና ጥቃቅኑን የአከባቢውን አመፅ በቁጥጥር ስር እያደረገ ታላቅነቱን አስመስክሮ ታዋቂነትንም አተረፈ።

ዘውትር ከፖርቹጋሎች ጋር በምዕዋና በቀይ ባህር ዳር በግዛት የሚጋጩት ቱርኮችም ለማህፉድ ከሠጡት የበለጠ አዳዲስ የጦር መሳሪያ ለግራኝ አህመድ ሠጡት። ሁለት ዘመናዊ የወቅቱን መድፎችም ተረከበ።

የአዳል ሡልጣን ወይም የሐረር ወላስሞች ያደርጉት እንደነበረው ሁሉ ግራኝ አህመድም በማእከላዊው የኢትዮጵያ መንግስት ላይ ለመነሣት በቂ ዝግጅት አደረገ።

ሲመቻቸው እንዝዘርም ይሉ የነበሩት፣ ሳይመቻቸው ይገብሩ የነበሩት የዚያ ወቅት የአዳልና የሐረር ህዝቦችም ከተከላካይነት ወደ አጥቂነት የሚያሸጋግራቸውን ሃይል በግራኝ አህመድ አማካይነት መገንባት ጀመሩ። ግራኝም ሙሉ ኢትዮጵያን ለመውረር፣ የክርስቲያኑን መንግስት ገልብጦ የሙስሊም መንግስት ለመመስረት፣ በቤተክርስትያናት ምትክ መስጊዶችን ለማቆም፣ በወንጌል ፋንታ፣ ቁርዓንን ለማስፋፋት ተዘጋጀና ዓላማውንም ለሐረር፣ ለሡማሌ፣ ለአዳልና ለአካባቢው ህዝብ አሣወቀ።

አፄ ልብነ ድንግልም የማህፉድን ጦር ድል ካደረጉ በኋላ አገሩ ሠላም ሆኖ ነበርና ይህን ዝግጅት ሲሠሙ በ1518 ዓ.ም ፋኑኤል የተባለውን የዋግ አገረ ገዥ ሠራዊቱን አስከትሎ ወደ አዳል እንዲዘምት ላኩት።፡ ፋኑኤልም ወደ አዳል ዘምቶ አንድ ክፍል የግራኝን ጦር ድል አድርጎ አካባቢውን ዘርፎ ሊሔድ ሲል ግራኝ ሌላ ጦር ይዞ መጥቶ ተዋጋና አሸንፎ የዘረፈውን ሀብት ሁሉ አስመልሶ በድል አድራጊነት ወደ ቦታው ተመለሠ።

ከዚያም እንደገና ተደራጅቶ ከአዳል ወደ ደዋሮ በመምጣት ከአፄ ልብነድንግል ሠራዊት ጋር ውጊያ ገጠሙ። ሆኖም የንጉሡ ጦር በፅኑ ተዋግቶ ስላሸነፈው ለመሸሽ ተገደደ።

በዚህ ጦርነትም አብረው ተሠልፈው የነበሩት የጦር አለቆች 6 አሚሮችና አጎቱ መሐመድ ዜሐርቡይ ተማረኩ። ንጉሡም ጊዜያዊ ደስታ ተሰማቸው።

ከዚህ ጦርነት በኋላም የግራኝ አህመድ አባት ገዳይ የሆነው ሱልጣን አቡበክር ከግራኝ ጋር ሲታረቁና ሲጣሉ ቆይተው ነበርና አሁን ደግሞ ሡልጣን አቡበከር ግራኝን ከነሠራዊቱ ወግቶ አሸንፈና ከሐረር አባሮ እስከ

ዘይላ አደረሠው። ወዲያው ግን ግራኝ እንደገና ተዋግቶ አሸነፈና ሐረርን በድጋሚ በመያዝ የበላይነቱን አረጋገጠ።

በዚህም አፄ ልብነ-ድንግልና ተከታዮቻቸው በአቡበክር ላይ ተስፋ ጥለው ነበርና መሸነፉን ሲሠሙ ስጋታቸው ቀለለ።

አንድ አመት አለፈ። ራስ ደገልሐን የተባለው የንጉሡ ዋና የጦር አለቃና የእህታቸው ባል የነበረውን፣ እንዲሁም የባሌ አውራጃ ገዥ የሆነውን በ1519 ዓ.ም ወደ አዳል እንዲዘምት የተደረገውም የግራኝ አህመድ ጦር በመገስገስ ላይ መሆኑ ስለታወቀ ነበር። እናም ጦርነቱ ተጀመረ። ሦስት ቀን ከፈጀ ሃይለኛ ጦርነት በኋላ የግራኝ ተከታዮች አሸነፉ። በርካታ መኳንንት ከነመሳሪያቸው፣ ከነፈረሳቸው ተማረኩ።

ግራኝ አህመድ ከምርኮው ውስጥ ጥሩ ጥሩውን መርጦ አሚር ሁሴማን ለሚባለው ለየመኑ ዘቢድ ልኮ የቀረውን ለራሁና ለሰራዊቱ አከፋፈለ። ሠራዊቱም በደስታ ለቀጣዩ ጦርነት በወኔ ተዘጋጀ።

ከአንድ አመት በኋላ በ1520 ላይም የግራኝ ጦር ወደ ደፋት መጣና ወናግ ጃን የተባለው የንጉሡ አዝማች ከሚመራው ጦር ጋር ውጊያ ተደረገ። በመጀመሪያው ቀን በክርስቲያኑ ጦር የበላይነት ታየና በቀጣዩ ቀን የግራኝ ጦር ድል ቀናው። አዝማች ወናግ ጃንም ተገደለ። ይህ ድል እና የተገኘው ምርኮም ግራኝና ተከታዮችን በዝና ላይ ዝና በድል ላይ ድል አጎናፀፋቸው።

ግራኝም ከነተከታዮቹ ወደ መሃል ደፋት ገብቶ ቤተክርስቲያን አቃጥሎ በአካባቢው ሲዘዋወር ለመውለድ ቀኗ የደረሠው ባለቤቱ ባቲ ድል ወንበራም አብራው ነበረች። ከጥቂት ጊዜ በኋላም ዋናውና ታላቅ እልቂት ያስከተለው ጦርነት በአፄ ልብነ-ድንግልና በአህመድ ኢብን ኢብራሒም አል ጋዚ መካከል ተካሄደ። ይህ ጦርነት "የሽንብራ ኩሬ ጦርነት" በመባል የሚታወቅ ሲሆን ቦታውም በዝቋላና በሞጆ አቅራቢያ የሚገኝ ነው።

አዝማቹ ራሣቸው አፄ ልብነ-ድንግል ሆነው ሽንብራ ኩሬ ላይ ከግራኝ አህመድ ጋር ያደረጉት ይህ የእርስ በርስ ውጊያ በርካታ ወገኖች ያለቁበት ሆኖ አልፏል። በዚህ ጊዜ ንጉሡ 16 ሺ ፈረሰኛ 200 ሺ እግረኛ ወታደር ያሠለፉ ሲሆን፤ አጠቃላይ የጦራቸው ብዛት በአማካይ 250 ሺ (እሩብ ሚሊየን) ጦር የሚደርሁ ነበሩ። በተቃራኒው ደግሞ የግራኝ አህመድ የሠራዊት ብዛት 12 ሺ ብቻ ነበር።

ይህን ሠፊ ቁጥር ያለው ሠራዊት ይዘው የተሠለፉት ንጉሡ በሠባት የውጊያ ረድፎች አሰልፈው ሲያዋጉ በድርጅትና በአመራር ጉደለት በኋላ ቀር የጦር አሠላለፍና በኋላ ቀር መሣሪያ የነበረ ሲሆን፤ ከፍተኛ የውጊያ ስልትና ልምድ በነበረው በግራኝ አህመድ ጦር ለመሸነፍ ተገደዋል።

መጋቢት 13 ቀን 1521 ዓ.ም ሙሉ ቀን በተደረገው እልህ አስጨራሽ ውጊያ ምሽት ላይ ሙሉ ለሙሉ በግራኝ አህመድ የበላይነት ተደመደመ። ከ200 ሺ በላይ ኢትዮጵያውያን በአንድ ጊዜ ያለቁበት ትልቅና ከባድ ጦርነትም ነበር።



ከዚህ በኋላ ባሉት ተከታታይ ጊዜያቶች በየጊዜው ጦርነቶች ቢካሔዱም ንጉሡና ሠራዊቶቻቸው የሚቋቋሙት አልሆነም።

ስለዚህም በምስራቅ፣ በደቡብና በመሐል ሸዋ የሚገኙ ግዛቶች ሁሉ በግራኝ አህመድ ቁጥጥር ስር ሆኑ። እርሁም የያዘውን አገር እያስጠበቀ ወልዳተያዙ ግዛቶች እየዘመተና ድል እያደረገ ህዝቦችን እያሰለመ ቤተክርስቲያኖችን እያቃጠለ ሲገሠግሥ አፄ ልብነ-ድንግል ደግሞ በሽሽት ከቦታ ቦታ መዘዋወራቸውን ቀጠሉበት።

"ጎጃም ንጋሽ" በሚለው ሥሙ የሚታወቀውና ወሰን ሠገድ የተባለው የጎጃም ገዥ የተደረጉትን ጦርነቶችና የንጉሡን ሽንፈት ካየ በኋላ ያለውን ጦር ይዞ መጥቶ " እስከ አሁን እንደተዋጉት መኳንንቶች አልምሠልህ፣ እኔ ወሠን ሠገድ ነኝና ተመልሠህ አገርህ ብትገባ ይሻልሃል" የሚል መልዕክት ለግራኝ አህመድ ላከበት።

የወሠን ሠገድ ስም ደግሞ በመላው የኢትዮጵያ ህዝብ የታወቀና ገናና ነበርና ክዳሞት ወደ ሸዋ መድረሱ ሲሠማ በንጉሡ ዘንድ ተስፋ ሲያሳድር በግራኝ ዘንድ ስጋትን አሣደረ።

ግራኝ የወሰን ሠገድን መልእክት ቢሠማም ወደ ግዛቱ ከመመለስ ይልቅ ሰራዊቱን እያበረታታና እየመከረ ወደ አንኮበር፣ ወደ ደብረሊባኖስ እየሔዱ እንዲያጠቁና እንዲዘርፉ ይልካቸው ጀመር። የተላኩትም በየደረሱበት እየዘረፉና እያቃጠሉ ትዕዛዙን ይፈፅማሉ።

በዚህ ጊዜ ነበር ደብረሊባኖስ፣ አስቴት ኪዳንምህረት ምስአለማርያም ወዘተ.. የተቃጠሉት።

ግራኝ ከፊል ጦሩን ልኮ እርሱ ደግሞ ከሚተማመንባቸው ጀግና ተከታዮቹ ጋር ሆኖ የጎጃሙን ወሠን ሠገድን ይጠባበቅ ጀመር።

በ1523 ዓ.ም ከወሠን ሠገድ ጋር የተደረገው ጦርነት 3 ጊዜ ግራኝንና ተከታዮቹን እንዲሸሹ ያደረገ ነበር። በአራተኛው ውጊያ ግን ገራድ አቡዱ የተባለው የግራኝ የጦር አለቃና ወሰን ሠገድ ፈረሳቸው ላይ ሆነው ሰረጅም ሠአት ሲዋጉ ከቆዩ በኋላ ገራድ አቡዲ የወሰን ሠገድን ጦር ከእጁ አስጥሎ ባዶ እጁን እንዲቀር በማድረግ ወሠን ሠገድን በጎራዴ መትቶ በመጣል ከወደቀም በኋላ ደጋግሞ በመምታት ቆራርጦ ጣለውና ድሉ የእነ ግራኝ ሆነ።

በእነዚህ ጊዜያቶች የግራኝ ስም እየገነነ ነበርና ጥቂቶች የንጉሡ ሹማምንት ወደ ግራኝ እየከዱ የተቀላቀሉበት ሁኔታ ተፈጥሯል።

ሁኔታው በዚህ ቀጥሎ አፄ ልብነ-ድንግል ከሸዋ፣ ከትግሬ፣ ከጎጃም፣ ከላስታ፣ ከጎንደር እና ከሌሎች ግዛቶች ሹማምንትና ወታደሮችን እያስመጡ ቢዋጉ፣ ራሣቸውም ዘምተው ቢያዋጉ የግራኝን ጦር ድል ማድረግ የማይቻልበት ሆነ።

ግራኝ አህመድ ተሸንፎ ሸሸ ሲባልም ድምፁን አጥፍቶ ቆይቶ በአዲስ መልክ ተደራጅቶ በመምጣት ያሸንፋቸዋል። ስለዚህ አፄ ልብነ-ድንግል ከጦርነቱ የተረፉትን ጥቂት ታማኝ ወታደሮቻቸውን አስከትለው ከቤተሰቦቻቸው

ጋር በመሆን፣ በአማራ ሣይንት፣ በኩል አድርገው ወደ ጎጃምና ወደ ጎንደር ለመሆድ ተገደዱ፡፡ ከሸዋ ተነስተውም ሸሽታቸውን ተያያዙት፡፡

ግራኝም ክትትሉን ቀጠለ፡፡ በየቦታው የግራኝን ጦር እየተፋለሙ ንጉስ ነገስቱን ሳያስማርኩ ብዙ መከላከል አደረጉ ታማኞቻቸው፡፡ ግራኝና ተከታዮቹም ንጉሡን ለመማረክ ክትትል በሚያደርጉበት ጊዜና ቦታ የሚያገኙትን ቤተክርስቲያን እየዘረፉና እያቃጠሉ ተጓዙ፡፡ ግራኝ የመካነ ስላሴን ቤተክርስቲያን አቃጥሎ አማራ ሣይንት ውስጥ ያሉትን አድባራት ዘርፎና አዘርፎ የአትሮንስ ማርያምን ቤተክርስቲያን አቃጥሎ ካህናቱንም ወደ እሣቱ ውስጥ እንዲጨመሩ አድርጓል፡፡ ይህን ያደረገውም ካህናቱ የቤተክርስቲያኑን ፅላትና ልዩ ልዩ ጌጣ ጌጥ ደብቀው አውጡ ሲባሉ አምቢ በማለታቸው ነው፡፡ ከዚያም ንጉሡ አምባ ግሸን ተራራ ላይ አርፈው ነበርና የግራኝ ጦር ወደ ተራራው ለመውጣት ሲል ከላይ ሆነው ናዳ እያወረዱ በርካታ ሠራዊቶችን ጨረሡበት፡፡ በዚህ ጊዜም የግራኝ አማችና ብዙ ሹማምንቶች አለቁበት፡፡ ዋናው የጦር አዝማች ገራድ አህምሹም ተማረከና ንጉሡ ፊት ቀርቦ በጥይት ተደብድቦ ተገደለ፡፡

ይህን ግራኝ ሲሠማ እጅግ አዝኖ ሸሽተው የመጡትን ወታደሮቹን አሠራቸው፡፡ ወዲያው ግን ተፈቱ፡፡

ንጉሡ በአማራ አገር በስደት እየተንከራተቱ ባለበትና የመከላከል ውጊያ እያደረጉ በሚሸሹበት ጊዜ ምንም እንኳ ግራኝ አህመድ ሠፊውን የኢትዮጵያ ግዛት ተቆጣጥሮ የነበረ ቢሆንም፤ ንጉሡን ካልማረኩ በሚል ከመከታተል አልቦዘነም፡፡ በየሄደበትም የተለመደውን ተግባር ይፈጽም ነበር፡፡

አፄ ልብነ-ድንግል ከበጌምድር /ከጎንደር/ ወደ ወገራ፣ ከወገራ በሠሜን አልፈው ወደ አክሡም፣ ከአክሡም ተመልሠው ወደ ወልቃይት ጠገዴ፣ ከዚያም ወደ ደንቢያ እየተዘዋወሩ እከመጨረሻው ተከላከሉ፡፡ የየግዛቱ ሹማምንትም ግራኝን መመከት ሳይችሉ ቀሩ፡፡

ስለዚህም ወደ ፖርቱጋል መንግስት ጆን ቤርሙዴዝን ልከው የእርዳታ ጥያቄ አደረጉ፡፡ ባየነው የሽሽት አይነትም 10 አመት አለፈ፡፡ በእነዚህ ጊዜያትም ግራኝ አህመድ የበላይነትን እንደያዘ ነበር፡፡

አፄ ልብነ-ድንግልም ከባለቤታቸው ከንግሥት ሠብለወንጌልና ከልጆቻቸው ጋር ሆነው ከአገር አገር፣ ከዋሻ ዋሻ፣ ከተራራ ወደ ተራራ በሚባክኑበት ሠአት የፖርቱጋሎች እርዳታም ሣይደርስ ሞቱ፡፡ በአገሩም በሽታና ረሀብ በዝቶ ነበርና አፄ ልብነ-ድንግል በበሽታ ነበር በ1532 ዓ.ም ያረፉት፡፡

ኢማም አህመድ ኢብን ኢብራሒም አል-ጋዚ (ግራኝ አህመድ) በጣም በተጠናከረ ሃይል የኢትዮጵያን አብዛኛውን ክፍል በቁጥጥር ስር አድርጓል፡፡

በ17 አመቱ ከዘይላ፣ ከአዳል፣ ከሐረርና ከአካባቢው ተከታዮችን እየመለመለ ተደራጅቶ በመነሳት በፍጥነት ተቀባይነት በማግኘትና የሐረርን ወንበር በወጣትነቱ በመያዝ ከሐረር፣ ከደብረ ብርሐን፣ ከዋጅ፣ ከደዋሮ እና



ከአክሡም በተከታታይ በመነሳት አገር አቀፍ የሆነውን የወረራ ሒደት በደቡብ ምስራቅ ከዘይላ ወደብ ጀምሮ በሠሜን ምዕራብ እስከ ፋንጂ፣ ከሠላና ኑብያ ድረስ፣ በደቡብ ምዕራብ ከጋሞ ደጋማ አካባቢ አንስቶ በስሜን እስከ ምፅዋ ድረስ ግዛቱን አስፋፍቷል፡፡

ከ1526 ዓ.ም እስከ 1534 ዓ.ም ድረስ ደግሞ ኢማም አህመድ ማእከሉን ደንቢያ ላይ በጣና ሐይቅ አካባቢ አድርጎ የሠሜን ምስራቅ አፍሪካን መለስተኛኙሏል፡፡ ከ1534 እስከ 1535 ዓ.ም ድረስ ግን ከፊሉን ግዛቱን በጦርነት እያጣ ሄደ፡፡

ይህን ሁሉ ሰፊ እና የማይታመን የግዛት ክልል በራሱ ስር ማድረግ በመቻሉ ከፍተኛ የሆነ ወኔ እና ጀግንነት እንደነበረው ለአንባቢ አይሰወርም፡፡ አጥፊነቱም እንደዚያው፡፡ ከደብረ ብርሐንና ከአክሱም በመቻ ማዕከላት በመነሳትም በሰሜን የአንጎት፣ የቄዳ፣ የትግራይ፣ የሲሐርት፣ የአበርገሌ፣ የእንደርታ፣ የተምቤን፣ የሽሬ፣ የአጋሜ፣ የስራዬ፣ የሀማሴንና ሌሎችም የጠረፍ አካባቢ ማህበረሰቦችን በሙሉ ለማስገበር ችሏል፡፡ በተጨማሪም በቀይ ባህር የዳህላክ ደሴት ነዋሪዎችና በከሰላ አካባቢ መዘጋ ተብሎ የሚጠራው የቤጃ ማህበረሰብ ለግራኝ ገብረዋል፡፡ ከሚያዝያ 1427 ዓ.ም ጀምሮ የኢማሙ የጦር አለቆችና አገረ ገዥዎች ከትግራይ፣ ከሃማሴንና ከስራዬ በኩል ወደ ሰሜን ምዕራብ በመሄድ የፀለምት የወገራ፣ የበጌ ምድር፣ የላስታና የደምቢያ አካባቢዎችንና ማህበረሰቦችን በጦር ሃይል አስገብረው ይዘዋል፡፡

ከ1527-1534 ዓ.ም ድረስ ደምቢያ የኢማም አህመድ ግራኝ የፖለቲካ እና የሐይማኖት ማዕከል ሆነች፡፡ ይህ ሁኔታም የኢማም አህመድ ግራኝ ሱልጣናዊ መንግስት እስከተንኮታኮተበት ጊዜ ድረስ እንደቀጠለ ቆይቷል፡፡ ይህ ወቅት የአገሪቱ ሠሜን ምዕራባዊ ድንበር የአባይ ወንዝ መፋሰሻን ተከትሎ ጉምዝና ፋንጂ እስከሚባሉት የኑብያ ግዛቶች ድረስ የተስፋፋበትና ያደገበት ወቅት ነበር፡፡

ከዚህ ሁሉ ከፍተኛ ድልና ውጣ ውረድ በኋላ በደንቢያ አካባቢ በተደረገው ውጊያ የቀድሞ ድሉ እየደበዘዘ ሔደ፡፡ እናም በጣና ሃይቅ አካባቢ ደንቢያ ላይ በተደረገው በመጨረሻው ፊታኝ ውጊያ በጥይት ተመትቶ በ1535 ዓ.ም ወደቀ፡፡ ህይወቱ ሲያልፍ የ37 ዓመት ጎልማሳ የነበረ ሲሆን እሱ የተመታበት ስፍራም ዛሬ ድረስ ግራኝ በር እየተባለ ይጠራል፡፡ የተቀበረውም በዚያው አካባቢ ሲሆን፤ በጎንደር ዙሪያ ወረዳ ዘንተራ እየሱስ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ልዩ ስሙ አለቅት ወንዝ በተባለ ስፍራ መቃብሩ ይገኛል፡፡

ኢማም አህመድ ከ1519-1534 ዓ.ም ኢትዮጵያን በበላይነት ይዞ ቆይቷል፡፡ በመጨረሻ ግን የፖርቱጋሎች እርዳታ ደርሶ የአፄ ልብነድንግል ልጅ አፄ ገላውዴዎስ እና ሰራዊታቸው ከ400 ፖርቱጋላዊ ወታደሮች ጋር ተባብረው ድል ሊያደርጉት ችለዋል፡፡ የሞተው ከፖርቱጋሎች በተተኮሰ ጥይት መሆኑና አጠቃላይ የውጊያውንም ሆነ የአሚሚቱን እንዲሁም ከእርሱ

በኋላ ስለተከሰቱ ተያያዥ ክንውኖች የሚያወሱትን ታሪኮችም በአፄ ገላውዲዎስ ዘመነ መንግስት ስር ተካተው እናገኛቸዋለን፡፡

ከዚያ በፊት ግን ኢማም አህመድ ካቃጠላቸው አድባራት ውስጥ በሙሉ የሚታወቁትን የቤተክርስቲያን ስሞችንና ዝርዝራቸውን አይተን ይሆናል የምናልፈው፡፡

1.ተድባበ ማርያም
2.መካነ ሰማዕት
3.ደብረ ወርቅ ቤ/ያን
4.አትሮንስ ማርያም
5.ደብረ ብርሐን
6.ደብረ ሊባኖስ
7.ምስአለ ማርያም
8.ገነተ ጊዮርጊስ
9.ደብረ ህንፀተን
10.ደብረ ዱማህን
11.መካነስላሴ
13.ወልደ ነጎድጓድ
14.ደብረ ኪሩቤል
14. ኤንድሮስማርያም
15. ታዕከ መንግስት
16.ደብረፅርሐማርያም
17 . ገነተ ማርያም
18.ጊዮርጊስ/ዘጋስመን/
19. ደብረ ቤተል
20. እግዚአብሔር አብ
21. ደብረ እስጢፋኖስ
22. መርጡለ ማርያም
23. ደብረዘይት
24. ናዝሬት
25 .አምበር ቂርቆስ
26 . ገሊላ
27. አጥሲሳን
28 .ደብረመሲህ
29. ጎለታ ማርያም
30. ጓሐ ፅዮን
31 . ዋሻ ሚካኤል
32.ደብረከርቤ

መዘተ ሲሆኑ እነዚህም በአፄ ገላውዲዎስ ዘመንና በሌሎች ተከታዮቻቸው እንደገና እንዲሰሩና እንዲታደሱ የተደረጉ አብያተክርስቲያናትና ገዳማት ናቸው፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለም ግራኝ አህመድ ከአድባራቱ ቃጠሎ ጋር ስፍር ቁጥር የሌላቸውን መንፈሳዊ መፃህፍት አመድ እንዲሆኑ አድርጓል፡፡ ባጠቃላይ በኢትዮጵያ ታሪክ ላይ ጥቁር ነጥብ ጥሎ ማለፉንም የሚክድ የለም፡፡

እንደ በርካታ ቀደምት ፀሃፍት አገላለፅም በኢትዮጵያ ላይ ሃይለኛ የጥፋት ክንዳቸውን በማሳረፍ ከፍተኛና ታሪካዊ ውድመት የፈጸሙ ተብለው ዮዲት ጉዲትና ግራኝ አህመድን ሳይጠቅሱ አያልፉም፡፡



## ምዕራፍ ፶፮
## የአፄ ገላውዴዎስ ዘመነ መንግስት
## ከ1532-1551ዓ.ም

አፄ ልብነ ድንግል በ1532 ዓ.ም ሲሞቱ ልጃቸው አፄ ገላውዲዎስ አፅናፍ ሰገድ በሚል ስመ መንግስት ተሰፋ ቢስ የተባለውን ዙፋን ወረሱ፡፡

በነገሡ በአንድ ወራቸው ከግራኝ አህመድ ጦር ጋር ተዋግተው በቀላሉ የማይታይ ጀብድ ስለፈጸሙ መኳንንቱና ወታደሩ በወጣቱ ንጉሰነገስት ጀግንነት ደስ ተሠኙ፡፡

አፄ ገላውዲዎስ በእድሜ የበሰሉ ስላልነበሩም እናታቸው እቴጌ ሰብለወንጌል እንደሞግዚት ሆነው ያግዟቸው ነበር፡፡

እቴጌ ሰብለ ወንጌል የትውልድ አገራቸው ሰሜናዊ ትግራይ ነበርና በቀደሙት ጊዜያቶች እየሸፈቱ ያስቸግሩ የነበሩት የሰሜን አውራጃ ህዝቦች እቴጌ ሰብለወንጌልን አክብረው ለአፄ ገላውዲዎስ ተባባሪ እንጂ ተቃዋሚ አልሆኑም፡፡ አፄ ገላውዲዎስ በነገሱ ጊዜም ዋና መቀመጫ ተብሎ የተወሰነ ቤተመንግስት አልነበረም፡፡ ስለዚህም አፄ ልብነ ድንግልና ቤተሰቦቻቸው ከቦታ ቦታ በሽሽት ሲዘዋወሩ ስለነበር በዚህ ጊዜ ደግሞ ሸሽተው ያረፉበት አካባቢ ትግሬ አገር ውስጥ ስለነበረ እዚያው ባሉበት ሆነው ነው ዘውድ የጫኑት፡፡ ስለሆነም አፄ ገላውዲዎስ በተንቤንና በሽሬ የነበረውን የግራኝን ጦር በነበራቸው ወታደር አሸንፈው፣ ለግራኝ የወገነውንና የአካባቢው የጦር አዝማች የነበረውን ዮናታን ከነሰራዊቱ በማሸነፍ ራሱን ዮናታንን ገድለው የትግራይንና የሰሜኑን ግዛታቸውን አደላደሉ፡፡ በአካባቢውም መደራጀታቸውን ቀጠሉ፡፡

በዚሁ ጊዜም ከወራት በኋላ በ1533 ዓ.ም በጉጉት ይጠበቁ የነበሩት 400 የፖርቱጋል ወታደሮች ከህንድ ተነስተው በቤርሙዴዝ እየተመሩ ምፅዋ ደረሱ፡፡

ከፖርቱጋል መንግስት ተልከው የኢትዮጵያን ማእከላዊ መንግስት ለመታደግ የመጡትን 400 ወታደሮች እየመራ የመጣውና ዋና አዛዣቸው የነበረው የታዋቂው የቫስኮ ደጋማ ልጅ ዶም ክሪስቶፍ ነበር፡፡ ከተለያዩ ከዚያ ወቅት ዘመናዊ መሳሪያዎች ባሻገር 26 መድፎችንም ይዞ መጥቷል፡፡

ምፅዋ እንደደረሱም የቱርኮችን ሹም ገድለው ተከታዮቹን አባረው ኑር ኤደን የሚባለውን የወደቡን የበላይ አለቃ አንገቱን ቆርጠው ለእቴጌ ሰብለ ወንጌል በመላክ መምጣታቸውን አበሰሩ፡፡

የአፄ ልብነ ድንግል ባለቤት እና የአፄ ገላውዲዎስ እናት ንግስት ሰብለ ወንጌል ከደንገጡሮቻቸውና ከጥቂት አሽከሮቻቸው ጋር እንዳይማረኩ

ፈርተው የተደበቁበትን አምባ ዶም ክርስቶፍ በአካባቢው ነዋሪ ስለተነገረው 100 ወታደሮች ሔደው አጅበው እዲያመጧቸው አደረገ።

እቴጌ ሰብለ ወንጌል ከፖርቹጋሎች ጋር ተገናኝተው እዚያው በምዕዋ ወደብ እንደሰፈሩ ስለ አጠቃላዩ ሁኔታ በአስተርጓሚ አስረዱ። እስከ መጨረሻቸውም እቴጌ ከፖርቹጋሎች ጋር እየተዘዋወሩ ቁስለኛ በመርዳትና በማማከር ተግባር ተጠምደው የዘለቁ ፅኑ ሴት እንደነበሩ ታውቋል። የፖርቹጋሎች መምጣት በንጉሡ ዘንድ ሲሰማ ታላቅ ደስታን ፈጠረ። ለግራኝ አህመድና ለተከታዮች እንዲሁም ለቱርኮች ግን ስጋት ነበር። ቱርኮቹም ከየመንና ከሌሎች ግዛቶቻቸው የተውጣጡ 2 ሺ የሚደርሱ ወታደሮችን ከግራኝ ጎን እንዲሰለፉ አደረጉ።

እቴጌ ሰብለ ወንጌልም እንግዶችን በልዩ አቀባበል ተቀብለው ምግባቸውን እያዘጋጁ መኝታቸውን እያሳመሩ በደስታ እንዲያርፉና ለመጡበት ጉዳይ እንዲዘጋጁ አስፈላጊውን ነገር ሁሉ አሟሉላቸው።

ግራኝም ህብረት ከመፍጠራቸው በፊት ነጣጥሎ ለማጥቃት ፈለገና ወደ ሐማሴን በፍጥነት ተጉዞ አካለ ጉዛይ ደረሠ። በ1533 ዓ.ም በመጋቢት ወር አናሳ በሚባል ተራራማ ቦታ ላይ ግራኝ አህመድ ሲሰፍር ህብረት ፈጥረው ጠበቁት። በዚሁ በሰሜናዊው የኢትዮጵያ ክፍል ጦርነቱ ቀጠለ።

ፖርቹጋሎች ይዘውት የመጡትን መድፍ በግራኝ ሰራዊት ላይ ሲያዘንቡት ድንጋጤ ተፈጠረ። ሆኖም ግራኝ አህመድ በወኔ የተሞላ ጀግና ነበረና በርትቶ እየተዋጋ፣ ተከታዮቹንም አይዟችሁ እያለ ያደፋፍራቸው ነበር። ጦርነቱ ተጋግሎ በቀጠለበት ሁኔታም በግራኝ ላይ አነጣጥረው ተኮሱበትና በጥይት እግሩን ተመቶ ቆሰለ፤ ፈረሱም በጥይት ተመታና ይዞት ወደቀ።

እንዳይማረኩም ጭፍሮቹ በፍጥነት አንስተው ወሰዱት። የግራኝ ተከታዮች ከሐማሴን ወደ ዮብል ተመለሱ። ወዲያው ለየመን ሱልጣን "መሳሪያና ወታደር ላክልኝ" ብሎ ግራኝ ሲልክበት 2 ሺ ዓረቦችን ከመሳሪያ ጋር ላኩለት።

ፖርቹጋሎችና ኢትዮጵያውያኑ ከአካለ ጉዛይ ወደ አሸንጌ መጡ። የመጀመሪያውን ጦርነትም በድል በመወጣታቸው በወኔ ተሞልተው ለቀጣዩ ውጊያ ሲዘጋጁ ቆዩ። ግራኝም የቱርኮችን እርዳታ ሲጠብቅ ቆየና ሳይዘገዩ ደረሱለት። ከቱርክ መንግስት የተላኩትም ግራኝን ለማስደሰትና ለመሸለም እየተሯሯጡ በድፍረት መዋጋታቸውን ቀጠሉ።

የፖርቹጋሎች መሪ ክሪስቶፍ ደጋማም የታወቀ ጀግና ነበርና ተከታዮቹን እየመራ እራሱ ከፊት ቀድሞ በታላቅ ጀግንነት ሲዋጋ



በእሩምታ ተኩስ ቆሰለና ወደቀ። ተከታዮቹ በመሪያቸው መውደቅ ተደናግጠው እንደምንም ውጊያውን ቢቀጥሉም ሃይላቸው እየደከመ በመሄዱና በመምሸቱ አፈገፈጉ። ክሪስቶፍ ደጋማንም እቴጌ ሰበለ ወንጌል የመጀመሪያ እርዳታ ካደረጉለት በኋላ ሌሎች ተከታዮች በታላቅ ሃዘን አሸሽተው ጫካ ውስጥ በመደበቅ ቁስሉን ሲጠጋግኑለት ቆዩ። በኋላ ግን የተደበቀበት ቦታ በጠቋሚ ተደረሰበትና ተማረከ። ወደ ግራኝ አህመድ ወሰደውም በፊቱ ጣሉት።

ሲተፉበትም ሆነ ሲሰድቡት በፍፁም ወታደራዊ ጀግንነት በዝምታ ይመለከታቸው ነበር እንጂ የምህረት ልመና አላቀረበም። ወዲያውም የግራኝ አህመድ እኅትና የወንድሙ ልጅ ቆስለው ስለነበር ቁስላቸውን እንዲያክም ሲጠየቅ "አላደርገውም።" የሚል ምላሽ ሰጠ። ፖርቹጋሎችና ኢትዮጵያውያኖች የሸሹበትን ቦታ ጠቁም ሲሉትም በንቀት ከማየት ውጭ መልስ አልሰጠም ይባላል።

ግራኝ አህመድ ስለምን ልማርህ ሲለው ዝም በማለቱ ጠጋ ብሎ "ሐይማኖትህን ለውጥና ወደ እኔ ተቀላቀል ልማርህ" ሲለው የፊጥኝ ታስሮ ነበረና ግራኝ ላይ ተፋበት ይባላል። ከዚያም የአይን ሽፋሉንና ቅንድቡን ግራኝ በሙቀስ ቆረጠው። ከዚህ በኋላ በአሰቃቂ ሁኔታ እየተፈራረቁ ከደበደቡት በኋላ፤ በመጨረሻም ምንም አልናገር ስላለ ግራኝ አህመድ በመጥረቢያ ራሱን ፈለጠው፤ አንገቱንም ቆርጦ ወደ ኮንስታንትኖፕል (ኢስታንቡል) ለቱርኩ ሱልጣን ላከ፤ ሌሎች የተማረኩ 160 ፖርቹጋሎችም አንገታቸው ተቆረጠ።

የክሪስቶፍ ደጋማ ሞት ለክርስቲያኑ ጦር የስነ ልቦና ፍርሐት አሳድሮ ጥንካሬያቸውን ያላላዋል ተብሎ ቢታሰብም በተቃራኒው ሆነና የሚወዱትን መሪያቸውን ደም ለመበቀል በብርቱ ይዋጉ ጀመር። ወዲያውም ከንጉሱ እናት ከሰብለ ወንጌል ሰራዊት ጋር ተገናኙና ህብረት ፈጠሩ። አፄ ገላውዴዎስ ከሞት ለተረፉ ፖርቹጋሎች ብዙ የወርቅ ስጦታ በሽልማት መልክ በመስጠት በዶም ክሪስቶፍ ደጋማ ሞት የተሰማቸውን ሃዘንም ገለፁ

በዚህ ጊዜ ከሐማሴን፣ ከትግራይ፣ ከጎጃም፣ ከጎንደር ብዙዎች እየመጡ ተሰብስበው ከንጉሡ ጎን ተሰለፉ። ቀደም ሲል ከንጉሱ ልብነ ድንግል እየከዱ ወደ ግራኝ የተቀላቀሉትም ይቅርታ እየጠየቁ ከእቴጌ ሰብለ ወንጌል ጎን እንሰለፋለን አሉ።

ንጉሱም ለቀጣዩ ዘመቻ ዝግጅት ሲደረግ "የግራኝን ጭንቅላት ቆርጦ ለሚያመጣልኝ እህቴን እድርለታለሁ፤ ነገር ግን ፖርቹጋሎች ከሆኑ በጋብቻ ምትክ ልዩና ታላቅ ሽልማት አበርክታለሁ።" የሚል ቃላቸውን ተናገሩ። የተረፉትን 120 የፖርቹጋል ወታደሮች ከጎናቸው

አስልፈው በግራኝ ቁጥጥር ስር የነበረውን የሰሜኑን ክፍል ተዋግተው አስመለሱ። ግራኝ በ1534 ግማሹን ግዛት አጣ እንጂ ፍፃሜው የሆነው በ1535 ዓ.ም ነው።

በ1534 ዓ.ም ወገራ በተባለው በጎንደር ሰሜናዊ ክፍል ከግራኝ ሰራዊት ጋር ከባድ ጦርነት ተደረገና የግራኝ የበታቾች አነሲድ አህመድ፣ አዝገራዱ ዑስማንና ሌሎች ታላላቅ የጦር አበጋዞች በዚህ ጦርነት ተገደሉ። የተረፉትም ሸሹ፣ ጥቂቶችም ተማረኩ። ከዚያም ከ6 ወር በኋላ በየካቲት ወር በ1535 ዓ.ም ወደ ደንቢያ ተጉዘው በአካባቢው ላይ ግራኝ አህመድ የሰራቸውን ቤቶችና መስጊዶች የንጉሱ ሰዎች መልሰው አፈረሷቸው።

በወቅቱ ግራኝ ወደ ዞብል ሔዶ ነበርና ይህን ሁሉ ሲሰማ በቁጣ ተነስቶ ወደ ደንቢያ ገሰገሰ። ደንቢያ አካባቢ ደርሶ ያለውን ሃይል አሟጦ ተጠቅሞ ለመዋጋት ተዘጋጀና በጣና ሃይቅ አጠገብ በሚገኘው ግዛት ከፖርቹጋሎችና ከንጉሡ ሰራዊት ጋር ለመዋጋት ተሰለፈ።

ንጉሡ 8 ሺ ሰራዊት፣ ግራኝ 13 ሺ ሰራዊት አሰልፈው ጥቂት ቀናት ቆዩና ጉዳዩን ጀመሩት። ዘንተራ በተባለው ተራራ ስር የተጧጧፈ ውጊያ ተደረገ።

በዚህ ጦርነት ጊዜ በዶም ክሪስቶፍ ደጋማ ምትክ ዳን አልፎንዝ ካልዶራይ ተሾሞ ነበር። ውጊያው ላይ ተመቶ ከሞተ በኋላም ምክትሉ አሪየስ ዲያዝ የአልፎንዝን ቦታ ሸፍኖ አመራር እየሰጠ በጀግንነት ሲዋጋ፣ ግራኝም እሱን አይተው ተከታዮቹ እንዲበረታቱ በጀግንነት ይዋጋ ነበር። በዚህ ጊዜ ፔድሮስ ሊዎን የተባለው የክሪስቶፍ ደጋማ አሽከር ግራኝ አህመድን አየውና አነጣጥሮ ተኩሶ ክፉኛ አቆሰለው። ግራኝ በፅኑ መቁሰሉን ይብቅ ተከታዮቹን "በርቱ" የሚል ቃል ተናገረና እንደምንም ዞር ብሎ ቁጥቋጦ ውስጥ ተደበቀ። በኋላም ራሱ ያቆሰለው ፖርቹጋላዊ ተከታትሎ ሔዶ ተኩሶ ገደለው። "የጌታህን ደም የተበቀልክ ጀግና" በማለት ሲዮንን አመሰገኑት። ወዲያውም የግራኝን ጭንቅላት ቆርጦ በፈረስ እየጋለበ አንድ ኢትዮጵያዊ ንጉሱ ፊት ቀረበ። ሆኖም እሱ እንዳልገደለው በመረጋገጡና ፔድሮስ ሊዮን የግራኝን ጆሮ ቆርጦ ይዞ ነበርና አውጥቶ ስላሳዩ ለኢትዮጵያዊው ጋብቻው ሳይጸናለት ቀረ። በምትኩ የወርቅ ስጦታ ተሠጠው። ለፖርቹጋሎችም በተመሣሣይ ብዙ ወቄት ወርቅ ሸለሙት።

የግራኝ አህመድ ሕይወትም በዚህ መልኩ ተደመደመ። ባለቤቱ ድል ወንበራ እና የተረፉት ወታደሮች አገር አቋርጠው ወደ ሐረር ሸሹ። ከዚህ ድል በኋላ በአፄ ልብነድንግል ጊዜ ተልኮ በአፄ ገላውዲዎስ ጊዜ ምላሹን ይዞ የተመለሰው ቤርሙዴዝ "ከኢትዮጵያ ላይ ግማሽ ግዛት ለፖርቹጋል መንግስት ይሰጥ። የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን አቡን ከእስክንድርያ መምጣቱ ቀርቶ ከሮማ ይምጣ እኔም የመጀመሪያው አቡን /ጳጳስ/ ልሁን" የሚል ሃሳብ አነሳ።

ይህ ሰው አፄ ገላውዴዎስ ሲልኩት "በኢትዮጵያ ወደብ በምፅዋና በኤርትራ ባህር ላይ የፖርቹጋል መንግስት ጥቅምን ያገኛል" የሚል ቃል ከንጉሡ ተነግሮት ይሁን ራሱ ፈጥሮ ሲዝበን በሔደ ጊዜ ገልፆ ነበርና አሁን ከድል በኋላ ያንኑ ሃሳብ አንስቶ በጣም በመከራከሩ ንጉሱ "የፖርቹጋል መንግስት ክርስቲያኑን የኢትዮጵያ መንግስት ረዳ እንጂ በዚህ እገዛ ምክንያት የኢትዮጵያ መንግስት ኦርቶዶክሳዊ ሃይማኖቱን በካቶሊክ አይለውጥም፤ ከግዛቱም ገሚሱን አይሰጥም" በማለት ቁርጥ ያለ ምላሽ ሰጡ።

ከሴላ ወገን የበረታ ግፊት ባለመኖሩም የራሱ የግለሰቡ አቋምና ሃሳብ ብቻ መሆኑ ታወቀ። ብዙ በመጨቃጨቁና በንጉሱ ላይ ሃይለ ቃል በመናገሩም ወደከፋ በግዞት ተልኮ በፖርቹጋሎች ልመና ተለቆ ወደ አገራቸው ከተመለሱት 6 ፖርቹጋሎች ጋር አብሮ ሔደ።

ከመጡት የፖርቹጋል ወታደሮች ውስጥ በፍላጎታቸው ጥቂቶች ሲመለሱ፤ የቀሩት ደግሞ እዚሁ መኖርን በመምረጣቸው እንዲኖሩ ተፈቀደላቸውና መሬት በነፍስ ወከፍ ተሰጧቸው በግብር እና በበአልም ጊዜ የባለ ማእረግ ቦታ ላይ እንዲቀመጡ ተደረገ። ከግራኝ አህመድ የተማረከውን ወርቅ እና ልዩ ልዩ ሐብት ለሔዱትና ለቀሩት ተሰጣቸው፤ የቀሩትም ኢትዮጵያዊ ሴቶችን እየመረጡ አግብተው በደስታ መኖር ጀመሩ።

ምንም እንኳን ውለታቸውን ሃይማኖት በማስለወጥ እንዲመልስላቸው ፖርቹጋሎች ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር እሰጥአገባ ውስጥ ባይገቡም፤ በሰላማዊ መንገድ ግን የሮማ ካቶሊክ ጳጳሳት ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ሚሲዮናውያን መላክ መጀመራቸው ግልፅ ነው።

የፖርቹጋል መንግስትና የሮማ ሊቀ ጳጳሳት ተመካክረው ሚሲዮናውያንን ወደ ኢትዮጵያ ለማስገባት ያመቻ ዘንድ ሮም ውስጥ ቅዱስ እስጢፋኖስ ቤተክርስቲያን አጠገብ የኢትዮጵያ ቋንቋና የቤተክህነት ጉዳይ እንዲሁም የኢትዮጵያ ባህልና ልማድ የሚጠናበት ት/ቤት ከፍተው በዚህ ት/ቤት ውስጥም የሮማ የቤተክህነት ሰዎች እየተመረጡ ገብተው ስለኢትዮጵያ ያጠኑና ይማሩ ነበር።

እነዚህ የተማሩት ሰዎችም በኋላ ላይ ከሌሎች ሚስዮኖች ጋር ወደ ኢትዮጵያ ከሮም ተልከው በመምጣት ወንጌልን እንዲሰብኩ ተደርጓል።

ሲልኳቸውም አንዱን በትሪያሬክ ብለው የኢትዮጵያ ፓትርያሪክ አድርገው በመሾም ከሞተም ሌሎች ተከታዮች ሹመቱን እንዲወርሱ

የሌጺስ ቆጶስነት ማእረግ ሰጥተው ነበር የሸኟቸው። እነዚህ ሚሲዮኖች በ1548 ዓ.ም ከሮም ተነስተው ብዙ ገፀ በረከት ይዘው ከረጅም ጊዜ የመንገድ ቆይታ በኋላ ኢትዮጵያ ደርሰው ለንጉሱ የተላከውን ስጦታ ሲያስረክቡም አፄ ገላውዲዎስ በጥሩ ሁኔታ ተቀብለዋቸዋል። ነገር ግን ወንጌልን እንዲሰብኩ ፈቀዱላቸው እንጂ የሐይማኖት ለውጥ አላደረጉም (ጥቂት ኢትዮጵያውያን አፄ ገላውዲዎስ መልዕክተኞችን በጥሩ ሁኔታ ስለተቀበሏቸው ካቶሊክ ሆኑ እያሉ አምተዋቸው ነበር።)

የተላኩት ሚሲዮናውያንም ጥቂት እንደቆዩ ከግብፅ ከመጡት ከዋናው የኦርቶዶክስ ጳጳስ ከአቡነ ዮሴፍ እና ከኢትዮጵያ ሊቃውንት ጋር የሃይማኖት ክርክር አነሡ። ንጉሡ በተገኙበት የጦፈ ክርክር ተደርጎ መግባባት ስላልተቻለ በመቶዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊ ካህናት "ከአባቶቻችን ሃይማኖት በፍፁም አንወጣም" ብለው ለሚሲዮኖች ቁርጥ ሃሳባቸውን አሳወቁ።

ሚሲዮናውያኑም ለጊዜው ክርክሩን አቁመው ስብከታቸውን ብቻ እንዲቀጥሉ አስፈቅደው ጉባዔው ተበተነ። ይህ በእንዲህ እንዳለም አፄ ገላውዲዎስ የግራኝ አህመድን ጦር ድል አድርገው መንግስታቸውን ካደላደሉ በኋላ ሁሉም ዜጋ ወደ ሰላማዊው ስራው እንዲመለስ አዘዋል። ዋናው ጦርም የግራኝን የቀረ ጦር ተከታትለው እንዲጨርሱ ትዕዛዝ ሠጥተዋል። በግራኝ ጊዜ የፈረሱና የተቃጠሉ አድባራትና ገዳማትን እንደገና እንዲገነቡም ባለሙያዎችን አሰማርተዋል።

ይሁን እንጂ ለጥቂት ጊዜያቶች ሰፍኖ የቆየው ሰላም ሌላ ድባብ ረበበት። ይኸውም የግራኝ አህመድ መሞት የጦርነቱን ሁኔታ ጨርሶ ሊያከስመው ባለመቻሉና ይልቁንም የግራኝ ሽንፈትና ሞት በአዳሎችና በሐረርጌዎች ዘንድ ቁጭትንና በቀልን አስከትሎ ሌላ የጦርነት ምዕራፍ እንዲከፈት አደረገ።

በ1550 ዓ.ም ገራድ አሊ የተባለው የግራኝ አህመድ ልጅ እና፣ ዑመር ዲንባራሳት በተባለው ሱልጣን የሚመሩ ሙስሊም ወገኖች ወደ ደዋሮ መጥተው ከንጉሡ ሰራዊት ጋር ጦርነት ገጠሙ። ነገር ግን ድል ሳይቀናቸው ቀረና በክርስቲያኑ ሃይል ተማረኩ። ብዙ ዝግጅት የተደረገበት ዘመቻ ነበርና ሽንፈታቸው በሐረርጌዎች ዘንድ ሲሰማ ድንጋጤን ፈጠረ። በተለይ የግራኝ አህመድ ባለቤት ባቲ ድል ወንበራ ልጅዋ ገራድ አሊ ስለተማረከ ይገድሉብኛል የሚል ስጋት ውስጥ ገባች። ስለዚህ ምዕዋ ለሚገኙት ለቱርክ ባለስልጣኖች "እባካችሁ ከአፄ ገላውዲዎስ ጋር ተነጋግራችሁ በእርቅ ልጄ እንዲመለስ አድርጉልኝ።" ብላ ላከች። እነርሱም ከንጉሱ ጋር ተነጋግረው በአንድ መደራደሪያ ተስማሙ። ይህም ግራኝ አህመድ በነበረበት ጊዜ ማርኮ የሸጣቸውን አቤቶሚናስንና እህቱን



ሮማንወርቅን ከተሸጡበት አገር ከየመን መጥተው ለወንድማቸው ለአፄ ገላውዴዎስ እንዲሰጡ ተደረገና በምትኩ አሊ ገራድ እና ሱልጣን ኡመር ዲን ተለቀው በሰላም ወደ ዘመዶቻቸው ሔደው ተቀላቀሉ።

በ1551 ዓ.ም ኑር አህመድ (ኑር ኢብን ሙቃሒድ) የተባለው የግራኝ አህመድ የእህት ልጅ ተነስቶ የሐረር እና የአካባቢው አሊቃ ሆነ። ኑር አህመድ በዘመኑ የሀረርን ግንብ ስላስገነባ የጎላ ተቀባይነት እንዲኖረው አደረገው።

ባቲ ድል ወንበራም ሽሽታ ሐረር ከገባች በኋላ የባሏን ደም የሚበቀልላት ታላቅ ሰው ትፈልግ ነበር። የአባቷን የማህፉድን ጠላት ልብነድንግልን በመጀመሪያ ባሏ በግራኝ አህመድ እንደተበቀለችው ሁሉ፣ አሁንም የባሏን ደም በወጣቱ በኑር ለመበቀል ፈለገችና በፍቅር ወጥመድ ጣለችው።

ኑርም በፍቅሯ ወደቀ። ቀጥሎም ለጋብቻ ጠየቃት። በዚህ ጊዜ ድል ወንበራ "የአፄ ገላውዴዎስን አንገት ቆርጠህ ልታመጣልኝ ማልና ላግባህ" አለችው፡

ኑር በአንድ በኩል የአጎቱን የግራኝ አህመድን ደም ለመበቀል፣ በሌላ በኩል ቆንጆዋን ድል ወንበራን (የጎቱን ሚስት) ለማግባት፣ እንዲሁም ለዘመናት የዘለቀውን የነገድና የሀይማኖት ፀብ መሰረት በማድረግ ማለላት፣ እናም በጋብቻ ሚስቱ አደረጋት።

እርሷም በምትችለው መንገድ ሁሉ አዘጋጀችውና ኑር ለጦርነት ተዘጋጅቶ ወደ ሸዋ ገስግሶ በመምጣት በመጀመሪያ በንጉሡ በተሾመው በሸዋው እንደራሴ ላይ ጥቃት ሰንዝሮ አሸንፎ ተመለሰና፣ ተመልሶ ተደራጅቶ የበለጠ ሰራዊት አስከትሎ ባለቤቱም አብራው ተከትላ ከሐረር ወደ ሸዋ መጥቶ ፈጠጋርን (ቡልጋን) ወረረ።

አፄ ገላውዲዎስ በዚህ ጊዜ ጎጃም የደብረወርቅን ቤተክርስቲያን እንደገና እያሰሩ ነበረና ወረራውን ሰምተው በንዴት ከጎጃም ገስግሰው ሸዋ ደረሱ። ወደ ፈጠጋር ተጠግተውም ከኑር ሰራዊት ጋር ፊት ለፊት ለውጊያ ተፋጠጡ። ሙሉውን ሰራዊታቸውን አስከትለው ባለመምጣታቸውም ሹማምንቱ "ያለው ጦር አነስተኛ ስለሆነ የፋሲካን በአል አሳልፈን ጦር ጨምረን ብንዋጋ ይሻላል" የሚል ምክር ለገሡ።

ካህናቱም "ፋሲካን አብረን ብንውል ይሻላል" ሲሉ ንጉሡ "ፋሲካን በሠማይ ከጌታዬ ከእየሱስ ክርስቶስ ጋር እውላለሁ" የሚል ምላሽ በመስጠት የስቅለት ቀን ወደ ኋላ ሳይሉ ከፊት እየመሩ መዋጋት ጀመሩ። በተጋጋለው ውጊያ ውስጥ ገብተው ሲፋለሙ ከተፋላሚው ወገን በተተኮሠ ጥይት ተመቱ። እንደተመቱም ወታደሮቹ እንዳይደናገጡ ቁስላቸውን

አስረው ውጊያውን ቀጠሉ። ወዲያው ግን የኑር ተከታይ የሆኑ ፈረሰኞች ተጠግተው በጦር ወግተው ጨረሷቸው።

አፄ ገላውዲዎስ ከተገደሉ በኋላም በኑር ትዕዛዝ ከራሳቸው ላይ ጭንቅላታቸው ተቆርጦ ተወስደና በትልቁ ሐረር በር ላይ እንዲሰቀል ተደረገ። ሆኖም ንጉሡ ከሞቱ በኋላ በቀሩት ወታደሮች የኑር ሰራዊት ተሸንፎ ስለሸሸ የቀረው የንጉሡ አካል ከጦር ሜዳው ላይ በሶስተኛው ቀን ተገኝቶ ራሳቸው ወዳሰሩት ወደ ተድባበ ማርያም ቤ/ን ወስደው ቀበሯቸው። እዚህ ላይ ዜና መዋዕሉ ያሰፈረውን ብሉፍ እንይ።

"በዚህ አመት በሀረርና በአውራጃው ታላቅ ረሐብና በሽታ ተነሳ፤ ምክንያቱን ባቲ ድል ወንበራ ከአዋቂዎች ስትጠይቅ የአፄ ገላውዴዎስን ጭንቅላት በሐረር በር ስለሰቀልሽ ፈጣሪ ተቆጥቶ ነው ብለው ስለመለሱላት ጭንቅላታቸውን አስወርዳ በነጋዴዎች እጅ አንፆኪያ (ሸዋ) ላከችውና በክብር ተቀመጠ" ይላል።

ለማንኛውም ኑር ድል ቀንቶት የባለቤቱን ፈቃድና መሐላውን ፈፅመ፤ የአጎቱን ደም በመበቀሉም የሀረርና የአዳል ህዝቦች በጉብዝናው አደነቁት።

አፄ ገላውዲዎስ "ደቅርብዎት" እየተባሉ አሻፈረኝ ብለው ውጊያ ገጥመው በእለተ አርብ በስቅለት ቀን በፈቃዳቸው በመሞታቸው ቀጥሎ ያለው ግጥም ተገጠመላቸው

"አፄ ገላውዲዎስ ጌታን ተከተለ፣
ፋሲካውን ሳይውል አርብ ተሰቀለ።
ጌታውም ሳይረሳው የፋሲካ ለታ፣
አስጠርቶ አበላው ከሚት እስከ ማታ።
አፄ ገላውዲዎስ እንደ ዮሐንስ፣
ባህር ዳርን ዞሮ ሸዋ ሲመለስ፣
አንፆኪያ ታዬ ብርሐን ሲሰበስ።"



## ምዕራፍ ፶፯
## የአፄ ሚናስ ዘመነ መንግስት
## ከ1551-1555 ዓ.ም

አፄ ሚናስ የአፄ ገላውዴዎስ ወንድም ናቸው። አፄ ሚናስ በአፄ ልብነድንግል ጊዜ ጦርነት ላይ ተማርከው ለየመኑ ገዥ ለዘቢዱ ፓሻ እንደባሪያ ተሸጠው የነበሩትና በኋላም በአፄ ገላውዴዎስ ጊዜ በእንገራድ እሊ ተለውጠው የተመለሱ ናቸው።

ወንድማቸው ሲሞቱ ስልጣኑን እንደያዙና ገና አድማስ ሰገድ በሚል ስመ መንግስት በኢትዮጵያ ዙፋን በተቀመጡ ማግስት የእናታቸውን የእቴጌ ሠብለወንጌልን የእቴጌነት ማዕረግ ሽረው፤ ለባለቤታቸው ለእቴጌ ሰሉስ ኃይላ (ለአድማስ ሞገሳ) ማዕረጉን ሰጧቸው። በዚህም መላው ህዝብ ተገረመ።

እቴጌ ሠብለወንጌል የአፄ ልብነድንግል ባለቤት የአፄ ገላውዴዎስና የራሳቸው የአፄ ሚናስ ወላጅ እናት ከመሆናቸውም በላይ፤ ከባለቤታቸው ዘመነ መንግስት ጀምሮ በግራኝም ጊዜ በስደትና በመከራ ያሳለፉ፤ በልጃቸው በገላውዴዎስ ዘመንም እንደ ንግስት ተከብረው ሲኖሩና ለአገራቸው ብዙ ሲደክሙ መኖራቸው በሌላው ህብረተሰብ ሳይዘነጋና ሳይረሳ በገዛ ልጃቸው ውለታቸው ተዘንግቶ ይህን የመሰለ የልታሰበ ሽረት ሲገጥማቸው ብዙሃኑ አዘኑላቸው። እቴጌዋም ከመገረም ውጭ የተናገሩት አልነበረም። ስለዚህ ሁለት ቀሳውስት ወደ አፄ ሚናስ ሔደው "እናትን አዋርዶ ሚስትን ማክበር ተገቢ አይደለምና ታረቅልን" ቢሏቸው፤ ንጉሱም "ለእናቴ ከኔ ይልቅ እናንተ አትቅርቧትም፤ በዘመኗ ነግሳለች፤ ከዚህ በኋላ ለእሷ አክሊሏ ቆቧ ነው" የሚል ምላሽ ሰጡ። ቢገዘቷቸው ቢያወግዟቸው ሊሰሙ አልቻሉም። እንዲያውም የሚያወግዟቸውን ሰዎች ማሰር ማንገላታት ጀመሩ።

አፄ ልብነድንግል በግራኝ ወረራ ጊዜ ሸዋን ለቀው ከተሰደዱ በኋላ ከዚህ በፊት እንደተገለፀው፤ ወደፊትም እንደምናየው፤ የኢትዮጵያ ንጉስነገስቶች መቀመጫ ወደ ሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል ዞሮ ቋሚ እና ራሱን የቻለ የመንግስት መቀመጫ አልነበረም። ሆኖም እስከዚህ እስከ አፄ ሚናስ ጊዜ ነገስታቱ የሸዋ ነገስታት ተብለው ከመዘርዘር ውጭ ሌላ ስያሜ ገና አልያዙም። ስለዚህ አፄ ሚናስ በዘመናቸው የሰፈሩት በዚያው በእናታቸው አገር በሰሜን ነው።

እናም በአፄ ሚናስ የግዛት ዘመን የሰሜን ፈላሾችና አንዳንድ የአካባቢው ነዋሪዎች ተባብረው ሸፈቱባቸው። ፈላሾቹም ከንጉሱ ዘበኞች ጋር ተመሳጥረው በሌሊት ገብተው ድንኳናቸዉ ውስጥ ሊገድሏቸው ሲሉ ተደርሶባቸው እንዲገደሉ ተደረገ።

ምናልባትም የሠሜን ሰዎች በአፄ ሚናስ ላይ የሸፈቱት ከዚህ በፊት (በገላውዴዎስ) ጊዜ እናታቸውን እቴጌ ሠብለወንጌልን አክብረው በሰላም ተገዝተውላቸው ነበርና አሁን ግን የእቴጌኒቱን ስልጣን ስለሻሩባቸው ይመስላል።

የሆነ ሆኖ የአካባቢው ባላባቶች ከየአቅጣጫው ከመሸፈታቸው በላይ፤ የትግሬ እና የሐማሴን ገዥ የነበረው ባህርነጋሽ ይስሐቅ የተባለው የአፄ ሚናስን ወንድም የአቤቶ ያዕቆብን ልጅ ተዝካሮ የሚባለውን አነግሳለሁ ብሎ በአፄ ሚናስ ላይ ተነሳ። አፄ ሚናስም ዘርዓ ዮሐንስ የሚባል የጦር አለቃቸውን አዘው ከብዙ ሰራዊት ጋር ሆኖ ባህርነጋሽ ይስሐቅን እንዲወጋ አዘመቱት።

በዚህ ጦርነት ባህርነጋሽ ይስሐቅ ዘርዓዮሐንስን ገድሎ፣ ጦሩንም አሸንፎ፣ አባረረውና ተዝካሮ ንጉስ መሆኑን አወጀ።

ንጉስ የተባለው ተዝካርም ጦር ይዞ መጥቶ አጎቱን አፄ ሚናስን ለመውጋት ሲገሰግስ መጣና ንጉሱ የሰፈረበት አካባቢ ደርሶ ሁለቱም ለውጊያ ተሰለፉ። ቦታውም ወገራ የሚባል ቦታ ሲሆን፤ ሰሜን ጎንደር ውስጥ ነው። በዚህ ውጊያ አፄ ሚናስ ድል አድርገው የወንድማቸውን ልጅ ተዝካሮን ከማረኩት በኋላም በሲማሲሞ ገደል ውስጥ ተወርውሮ እንዲገደል አደረጉት።

ባህር ነጋሽ ይስሐቅም የተዝካሮን መማረክና መገደል ሲሰማ ከቱርኮች ጋር በመወገን አፄ ሚናስን ለመጉዳት አሰበ። ቱርኮችም ከምፅዋና ከአርቂኮ ጀምሮ በዚያ ዘመን የትግሬና የሐማሴን ዋና ከተማ የነበረውን ደባሩአ ድረስ ያለውን ግዛት በመያዝ ባህርነጋሽ ይስሐቅን በመርዳት ይዞታቸውን ለማስፋፋት ቻሉ። ለባህር ነጋሽም አፄ ሚናስን የሚከላከልበት የሰው ሃይልና ዘመናዊ መሳሪያ ሰጡት።

ሁኔታው በዚሁ ቀጥሎ ባለበት ጊዜ ፖርቱጋሎች ባለውለታነታቸው ገና በትኩሱ ነበርና አገሪቱ ውስጥ በካቶሊክ ሃይማኖት ስብከታቸው ውስጥ የአፄ ሚናስን አገዛዝም እያነሱ መጥፎነታቸውን በመግለፅ እና ህዝቡን ለማሳመፅ በመንቀሳቀሳቸው፤ እንዲሁም የሐይማኖት ክርክሩ እየተጋጋለ ግጭትን በማስከተሉ አፄ ሚናስ ብዙ ሚስዮናውያንን ማሰርና ማንገላታት ጀመሩ። ይባስ ብለው ፖርቱጋሎች ኢትዮጵያዊ ሴት እንዳያገቡና ስብከታቸውንም እንዲያቆሙ አዘዙ።

ሚስዮኖችም ባህርነጋሽን ተማምነው የአፄ ሚናስን ትዕዛዝ ሳይፈፅሙ ቀሩ። ብዙዎች ሚስዮናውያን በግዞት እንዲኖሩ ስለተፈረደባቸውም ጥበቃውን ጥሰው አመልጠው ወደ ባህር ነጋሽ ይስሐቅ ሄደው ተቀላቀሉ። በዚህም የካቶሊክን ሐይማኖት ካልሰበክን በሚል መነሻ ከጠላታቸው ከቱርክ ጋር እንደወገኑ ይቆጠራል። የኦርቶዶክስን ሐይማኖት



በካቶሊክ ካልቀየርን የሚል ጠንካራ አቋምም ነበራቸው። በዚህ ጊዜ አፄ ሚናስ ወደ ባህር ነጋሽ ይስሐቅ ዘምተው ድል ቢያደርጉም፤ ድል የተደረጉት ወገኖች ወደ ጠረፍ ሸሽተው ስላመለጡ የተማረከ አልነበረም።

ከዚያም ወደ ሸዋ ተመልሰው በዳባ በኩል ኦሮሞዎች ሸፈቱ ስለተባለ እነሱን ሲያሳድዱ በወባ ተነድፈው ታመሙና ሞቱ። አስከሬናቸውም በተድባበ ማርያም እንዲቀበር ተደረገ።

ከ1551 እስከ 1555 ዓ.ም በቆየው በ4 አመት የግዛት ዘመናቸውም ከወገኖቻቸው ጋር፣ ከሚስዮኖችም፣ ራሳቸው ከሾሟቸው ሹማምንትም ሆነ ከእናታቸው ጋር ሳይግባቡ ነበር ያሳለፉት። ከአፄ ሚናስ ሞት በኋላም በየቦታው የዙሩን ፍጭቶች እየተደረጉ ቆይተው በመጨረሻ የአፄ ሚናስ ልጅ ሠርፀ ድንግል ነገሡ።

የሸዋ ነገስታት ተብለው የሚዘረዘሩት ከይኩኖ አምላክ ጀምሮ እስከ አፄ ሚናስ ድረስ ያሉት ሲሆኑ፤ ከሰርፀ ድንግል ጀምሮ ደግሞ በጎንደር ዙሪያ በሚገኙ ጥቃትን አውራጃዎች ጥቂት ነገስታት መቀመጫቸውን አድርገው ቆይተው፤ በኋላ በአፄ ፋሲል ጊዜ ግን ደምበኛ ቤተመንግስት ተገንብቶ የነገስታቱ ቋሚ ቤተመንግስት ሲሆን ችሏል።

እንግዲህ በአፄ ሚናስ አጭር የግዛት ዘመን ውስጥ የተከናወኑትን ነገሮችም ሆነ ከእርሳቸው በፊት በነበሩት ጊዜያቶች የስልጣን ጥያቄ ጠንካራ ልዩነት እየፈጠረ ነገስታትን ከነገስታት፣ ሹማምንትን ከሹማምንት እያዋጋ ለበርካታ ዜጎች እልቂት መንስኤ ሆኖ መዝለቁን እንረዳለን። በጦርነት የደቀቀች፣ ሰላም ሰፍኖ ለሥልጣኔ ደፋ ቀና የሚባልበት ጊዜ ጉልበትና ገንዘቧ ባክኖ፣ አምራች ዜጎቿ እየተፈጁባት የኖረች አገር መሆኗንም እንገነዘባለን። በተጨማሪም በወንድማማቾች ፀብ ጣልቃ እየገቡ አገር ለሚያራቁቱ ባእዳን እንድትጋለጥ አድርጓታል።

## ምዕራፍ ፶፰

## የጎንደር ነገስታት ዘመን

የኢትዮጵያ ነገስታት ከጥንታዊው የሳባ ከተማ ናፓታ እና መርዌ፣ ቀጥሎ አክሱም፣ ከዚያም ሮሃ/ላስታ/ እንደገና ሸዋ ዋና መቀመጫቸውን እያደረጉ እንደገዙ አይተናል። አሁን ደግሞ የነገስታቱ መቀመጫ ከተማ ጎንደር ሆነ። ይህም ሲባል ከግራኝ ወረራ በኋላ ከአፄ ልብነድንግል ሽሽት ጀምሮ ወደ ሰሜኑ የኢትዮጵያ ግዛት ሔደው ከቦታ ቦታ እየተዘዋወሩ መግዛት በመጀመራቸው ነው።

በዚህ በ1555 ዓ.ም ደግሞ ከአፄ ሰርፀድንግል ጀምሮ ማለትም አፄ ሠርፀድንግል፣ አፄ ያዕቆብ፣ አፄ ዘድንግል፣ አፄ ሱስኒዮስ ተከታትለው በነገሱበት ዘመን መቀመጫቸውን በጣና ሐይቅ ዙሪያ በዋጅ፣ በጉዛራ፣ በደንቀዝ፣ በደብሳን፣ በጎርጎራ፣ በጎመንጌ፣ በአዘዞ እና በአካባቢው አድርገው ኢትዮጵያን ሲያስተዳድሩ ነበር። ሆኖም በ1624 ዓ.ም አፄ ፋሲል ዋናውን የጎንደር ቤተመንግስት በአሁኗ የጎንደር ከተማ /ፋሲል ግንብን/ አስገንብተው የተከታይ ነገስታቶች ዋና ቤተመንግስት ሆኖ ቀይቷል።

ይሁን እንጂ የመጀመሪያው የጎንደር ቆርቋሪ ተብለው የሚጠሩትና የሚታወቁት አፄ ሰርፀድንግል ናቸው። በመሆኑም ከአፄ ሠርፀ ድንግል በመነሳት ይሆናል የጎንደር ነገስታትን ታሪክ ማየት የምንጀምረው።

ይህ ከመሆኑ በፊትም እስካሁን ያየናቸው ታሪካዊ ክንውኖች ምን አይነት አገር አቀፍ ለውጥ እንዳስከተሉ ከወዲሁ ባጭሩ አይተን ማለፉ ለቀጣይ ታሪኮች ግልፅ መሆን አስተዋፅኦ ይኖረዋልና ጥቂት ነጥቦችን እናንሳለን። አንደኛው ነጥብ፡-

ቀደም ሲል በዋቢ ሸበሌና በጁባ ወንዝ፣ በሲዳሞ እና በቦረና፣ በአሩሲ እና በባሌ እንዲሁም በኢትዮጵያ ደቡባዊ ክፍል ይኖሩ የነበሩ ኦሮሞዎች በአፄ ልብነድንግልና በግራኝ አህመድ መካከል በተደረገው ውጊያ የሰፈሩበትን ግዛት እየለቀቁ ግራኝን እየተከተሉ በቁጥጥሩ ስር ባደረጋቸው አገሮች ውስጥ መኖሩ ጀመሩ። በሌላ አገላለፅ የኦሮሞ ተወላጆች ከግራኝ ጊዜ በፊት በመጠኑ፣ በግራኝ ጊዜ ደግሞ በከፍተኛ ደረጃ ከቀድሞ መኖሪያቸው ወደ መሃል አገር ወደ ሸዋ፣ ወደ ዳሞት፣ ወደ ጎጃምና ወደ ጎንደር ገብተዋል።

የጎንደርን ነገስታትም ወደ ፊት ባለው ጊዜ በየጊዜው ተደራጅተው በመነሳት ሲዋጉዋቸው ቆይተዋል፡ የግራኝ አህመድ ወረራ ታላቅ ፍልሰትን አስከትሎ ነበርና።

ሌላው ነጥባችን ዳር ሳናደርስ የተውነውን የሐረር ሱልጣኖችን ጉዳይ የሚመለከት ነው። ከግራኝ አህመድ በኋላ በተነሱት ሡልጣኖችና አሚሮች አማካይነት ሸዋንና አካባቢውን ለ7 አመታት ያህል ይዘው የቆዩ ቢሆንም፣ ከአፄ ሚናስ በኋላ በነገሱት በአፄ ሰርፀድንግል ጊዜ ግን መቀጠል አልተቻላቸውም።



ከኑር መሐመድ በኋላ የተነሱት ሡልጣኖችና አሚሮች በሐረር፣ በኦጋዴንና በአውሳ እየተዘዋወሩ አካባቢውን ሲያስተዳድሩ ቢቆዩም፣ በወላስማ ቤተመንግስት ዙፋን እርስ በርስ ይጋፉ ነበር እንጂ ወደ ኢትዮጵያ ሰሜን ለመስፋፋት የሚያስችል ጊዜ አላገኙም።

ቀጥሎ ባለው ጊዜ በሐረርጌ፣ በአዳል /በአፋር/ በሱማሌና በኦጋዴን ህዝብ ላይ የኦሮሞ ህዝቦች ተደባልቀው መኖር በመጀመራቸውና፣ የሥልጣን ቃጋፊ ስለሆኑባቸው የአካባቢው ሱልጣኖች የተደላደለ ዙፋን አልነበራቸውም። ቀጥለን በምናየው የአፄ ሠርፀድንግል ዘመንም የሐረርና የአካባቢው ዙፋን እየከሰመ መሄዱን የምንገነዘበው ይሆናል።

### የጎንደር ነገስታት ዝርዝር

| ተ.ቁ | የንገስታቱ ስም | ስመ መንግስታቸው | በሥልጣን ላይ የቆዩበት ጊዜ በዓመት | የገዙበት ዘመን |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ሠርፀድንግል | መላክ ሠገድ | 34 | ከ1555-1589 ዓ.ም |
| 2 | ያዕቆብ | ----- | 5 | ከ1589-1594 ዓ.ም |
| 3 | ዘድንግል | አጥናፍ ሠገድ | 2 | ከ1594-1596 ዓ.ም |
| 4 | ሱስኒዮስ | ስልጣን ሠገድ | 28 | ከ1596-1624 ዓ.ም |
| 5 | ፋሲል | ዓለም ሠገድ | 35 | ከ1624-1659 ዓ.ም |
| 6 | ዮሐንስ 1ኛ | አእላፍ ሠገድ | 15 | ከ1659-1674 ዓ.ም |
| 7 | እያሱ 1ኛ | አድያም ሠገድ | 24 | ከ1674-1698 ዓ.ም |
| 8 | ተክለሐይማኖት | ልዑል ሠገድ | 2 | ከ1698-1700 ዓ.ም |
| 9 | ቴዎፍሎስ | አፅራር ሠገድ | 3 | ከ1700-1703 ዓ.ም |
| 10 | ዮስጦስ | ፀሐይ ሠገድ | 5 | ከ1703-1708 ዓ.ም |
| 11 | ዳዊት 3ኛ | አድባር ሠገድ | 5 | ከ1708-1713 ዓ.ም |
| 12 | በካፋ | መሲህ ሠገድ | 10 | ከ1713-1723 ዓ.ም |
| 13 | እያሱ 2ኛ | ብርሃን ሠገድ | 25 | ከ1723-1748 ዓ.ም |
| 14 | ኢዮአስ | --- | 14 | ከ1748-1762 ዓ.ም |
| 15 | ዮሐንስ 2ኛ | አድማስ ሠገድ | 1 | ከ1762-1763 ዓ.ም |
| 16 | ተክለሐይማኖት 2ኛ | ሃያል ሠገድ | 7 | ከ1763-1770 ዓ.ም |
| 17 | ሠለሞን | ጥበብ ሠገድ | 3 | ከ1770-1773 ዓ.ም |
| 18 | ተክለጊዮርጊስ | ፍቁር ሠገድ | 4 | ከ1773-1777 ዓ.ም |

(የጎንደር ታሪክ 1999 ዓ.ም)

## ምዕራፍ ፺፰

## የአፄ ሠርፀድንግል ዘመነ መንግስት

## ከ1555-1589 ዓ.ም

አፄ ሚናስ በ1555 ዓ.ም ከሞቱ በኋላ ከተለመደው ሰፊ የመኳንንቱ ክርክር እና ጉባኤ በኋላ ልጃቸው ሰርፀድንግል ይንገሱ በሚል ተስማሙና "መላክ ሠገድ" በሚል ስመ መንግስት የ13 አመቱን ልጅ በማንገስ "አፄ ሚናስ ስለሞቱ ልጃቸውን ሠርፀድንግልን አንግሰናል" በማለት በነጋሪት ለህዝቡና ለወታደሩ አሳወቁ።

አፄ ሠርፀድንግል የአፄ ልብነድንግል ባለቤት በነበሩት፣ ሰፊ የአስተዳደር ተሞክሮ በነበራቸው በእቴን ስብለወንጌልና በአፄ ሚናስ ባለቤት በእናታቸው በእቴጌ ስሉስ ሃይላ /አድማስ ሞገሳ/ አማካይነት በሞግዚት ጥቂት ጊዜ ሲያስተዳድሩ ከቆዩ በኋላ መላውን ስልጣን መያዝ የሚችሉበት የእድሜ ደረጃ ላይ ደረሱና ራሳቸውን ችለው ማስተዳደር ቀጠሉ።

አፄ ሠርሀድንግል ሥልጣን በያዙ ማግስት የአፄ ልብነድንግል የእህት ልጅ ሐመልማል የተባለው የቤተመንግስት ተወላጅ በመሆኑ ዙፋን ለመቀናቀን ተነሳ። የጎጃሙን ገዥ ዘርዓ ዮሃንስ፣ የደንቢያውን ሐርቦ፣ እንዲሁም አዝማች ተክሉ፣ ሮም ሰገድ፣ እስላም ሰገድ፣ የሚባሉትን ከጎኑ አድርጎ ለጦርነት ተነሳ።

በዚህም እልቂት፣ ስደት፣ መከራ ደረሰ። አፄ ሠርሀድንግልም የሥልጣን አጀማመራቸው በመከራ የታጀበ ሆነ። ሆኖም ብዙዎች ከእርሳቸው ጎን በመሰለፋቸው ድል አድርገው ገሚሶቹ በምርኮ፣ የቀሩት በእርቅ ተመልሰው ገቡላቸው። መከራው አልፎ ሰላም ከወረደ በኋላም የሾሙት ድልድል ሲደረግ ለሐመልማል ጎጃምን፣ ለሮም ሰገድ ሸዋን ሠጧቸው።

እነዚህ ሁለት ተሿሚዎች፣ ሮም ሰገድ ሸዋን በሚያስተዳድር ጊዜ አፄ ገራድ ከተባለው የሙስሊም ባላባት ጋር በተደረገ ውጊያ አብረው ተሰልፈው ነበርና በዚሁ ጦርነት ስለተገደሉ፣ የስልጣን ተቀናቃኝ ጠፍቶ በተደላደለ ዙፋን ተቀምጠው የየግዛቱን ባላባት በውድም በግድም ለማሳመን ይዘጋጁ ጀመር።

ከዚያም ከጎንደር ተነስተው ወደ እናሪያ፣ ወደ ጉራጌ አገር በመንገዘ ያልገበረውን የኦሮሚያንም ክልል እያስገበሩ፣ ከቀድሞ ገባሪዎችም ግብር እየተቀበሉ መዘዋወር ጀመሩ።

ከጉራጌ አገር በስተደቡብ፣ ከእናሪያ በስተምስራቅ በኩል ያለውን የከምባታና፣ የኮሎን አገርና አካባቢውን እየተዘዋወሩ በማቅናትና በማስገበር



ላይ ሳሉ የከምባታና የአካባቢው ህዝብ በባላባቶቹ እየተመራ ወደ ጫካ ገብቶ ንጉሱን መዋጋት ጀመረ። ከብዙ ፍልሚያ በኋላ ተሸንፈውና ሊገብሩ ተስማምተው ሲገቡ፣ የሐድያ ህዝብ ደግሞ የበለጠ በርትቶ በመዋጋት አላስጠጋ አላቸው።

በወቅቱ የሐድያን ህዝብ ይዞ ይዋጋ የነበረው አፄ ገራድ የተባለውና ሮም ሰገድን ሸዋ ላይ በጦርነት የገደለው የሙስሊም ባላባት ነው። በኋላ ግን ተሸንፎ በይቅርታ ታልፎ ገበረ። ንጉሱም ታማኝነቱን በመጠራጠር ደጃዝማች ተክለጊዮርጊስን ሾመው ገራድን በመሻር ወደ ጎንደር ተመለሱ። ይህም ገራድ ወዲያው ሸፍቶ ግዛቱን ለማስመለስ ከደጃዝማች ተክለጊዮርጊስ ጋር ሲዋጋ በመሞቱ የከንባታ፣ የሐድያና የአካባቢው ግዛቶች ሁሉ ገባሪ ሊሆኑ ቻሉ።

በ1562 ዓ.ም ከደቡብ ተነስተው ወደ ሸዋ በመምጣት ኦሮሞዎች ብዙ ዘረፋ ፈፀሙ። ንጉሱ ይህን ሲሰሙ ወዲያው ወደ ዝዋይ ሐይቅ ደርሰው ዘርፈው በመሸሽ ላይ የነበሩትን ደረሱባቸው። በዚህም ታላቅ የተባለውና ለአንድ አመት ያህል የዘለቀው የኦሮሞዎቹ ውጊያ በዝዋይና በአካባቢው ተደረገ።

ከብዙ እልቂት በኋላ ኦሮሞዎቹ ተሸንፈው ሸሹ። የዘረፉትን ቁጥር ስፍር የሌለው ከብትም ትተው ሸሹ። በዚህም ታላላቅ የጦር አዝማቾቻቸውን ያጡት ንጉሡ በተገደሉት አዝማቾች ሃዘን ምክንያት በሰፈሩበት ቦታ ጥቂት ቆዩ። ከዚህ ረጅም ጦርነት በኋላ አፄ ሰርፀድንግል የሰሜኑ አካባቢ ፀጥታ የተከበረ ስለሆነና፣ ነገር ግን ከሸዋ በታች ያሉ አገሮች ወደ ፊትም ስጋት ስለሚሆኑ ችግሩን ከስሩ ለማስወገድ በሸዋ አካባቢ ጥቂት አመታት አሳለፉ።

በእነዚህ አመታት የሐረርና የአካባቢው ሡልጣኖች እርስ በርስ የሚጋጩበትና ከኦሮሞዎቹ ጋር የሥልጣን ሽሚያ የሚያደርጉበት ወቅት ነበር። የሐረሩ ባላባት አሚር ኡስማንና የአውሳው ኢማም ገራድ ጂብሪል በግዛት ተጣልተው እርስ በርስ ይዋጉ ነበር።

ከዚያም የሐረሩ የአውሳውን አሸንፎ ገደለው። ከአሚር ኡስማን በኋላ ልጁ ናስር ለጥቂት ጊዜ በሐረር የበላይነትን ይዞ ቆይቶ መሐመድ ኢብን ኢብራሒም የሚባለው ከግራኝ አህመድ ዘር የሚወለደው ከብዙ ክርክርና ውጊያ በኋላ በ1568 ዓ.ም በሐረር ዙፋን ላይ ተቀመጠ። የማዕረግ ስሙም ኢማም መሐመድ ተባለ።

ኢማም መሐመድ በአፄ ሠርፀድንግል ላይ ለመነሳት ምፅዋ ካለው ከባህር ነጋሽ ይስሐቅ ጋር እየተላላከ መዶለት ጀመረ።

አፄ ሰርፀድንግል ጉዳዩን ቢደርሱበትም ባህርነጋሽን ደስ የሚያሰኝ መልዕክት እየላኩ በዘዴ ሲያባብሉት ቆዩና የሐረርጌን ሙስሊሞች ለመዋጋት ተዘጋጁ።

በ1568 ዓ.ም መገባደጃ ላይ ጉዞ ጀመሩ። ኢማም መሐመድም የንጉሱን መምጣት ሲሰማ ሐረርን እንዲጠብቅ ወንደሙን ቢዘር አህመድን ከብዙ ወታደር ጋር ትቶ በ1569 ዓ.ም ለጦርነት ተሰልፎ ጠበቃቸው። ተሰልፎ በሚጠብቅበት ጊዜም አስ አድ ዲን የተባለው አንድ አዝማቹ ከድቶ ወደ ንጉሱ ተቀላቀለ። ኢማም መሐመድም ከዚህ በኋላ ከቆየ ብዙ ተከታዮቹ እንደሚከዱት በማሰብ በፍጥነት ጦርነቱን ጀመረው።

ሙሉ ቀን በዋለ ውጊያ ሳይሸናነፉ አድረው በማግስቱ በተደረገ ውጊያ የኢማሙ ጦር "ደክሞናል" ብለው ማጉረምረም ጀመሩ። ጦርነቱን በግድ ቢያስጀምራቸውም ከልባቸው ሊዋጉ አልቻሉምና ድል ተደረጉ። በተለይም የአስአድዲን ከድቶ ወደ ንጉሱ መሄድና ተሹሞ ተሸልሞ በማየታቸው ብዙዎች ወደ ንጉሱ ተቀላቀሉ። ኢማም መሐመድ በሠራዊቱ ዘንድ ፍቅር እንዳልነበረው ይነገራል። በመጨረሻም ኢማሙ ከ50 ፈረሰኞቹ ጋር ሸሽቶ ሊያመልጥ ሲል ተያዘና ንጉሱ ፊት ቀርቦ ተገደለ።

ሐረር ቀርቶ የነበረው ቢዘርና ተከታዩ መንሱርንም ኦሮሞዎች ሔደው ስለገደሏቸው የሃረር የሱልጣኖች ባላባትነት ፈፅሞ ወደቀ። የሙስሊሞቹ ዋና መደብም ከሐረር ወደ አውሳ ዞረ። አውሳም የሡልጣኖች መቀመጫ ሆነና ሐረር በአውሳ ሡልጣኖች ወኪል እየተገዛ ዙሪያውን የከበቡትን ኦሮሞዎች እየተከላከለ እስከ ግብፆች መምጣት ድረስ ቆየ።

ከዚህ ድል በኋላ አፄ ሠርፀድንግል ወደ በጌምድር /ጎንደር/ ተመልሰው ጥቂት ካረፉ በኋላ የባህርነጋሽ ይስሐቅ ጉዳይ እስኒ ደረጃ ላይ መድረሱን ስላወቁና በግልፅ ስለሸፈተ ከጎንደር ተነስተው ወደ ትግራይ ሲጓዙ ሲሉ ጥቂት ታላላቅ መኳንንት ይህን ዘመቻ ለማስቀረትና ጉዳዩን በሠላማዊ መንገድ ለመጨረስ ፈለጉ። ንጉሱም "ታርቆ ከገባ ግዛቱን አልወስድበትም ከሹመቱም አልሽረውም" አሉ። የእርቅ ደብዳቤ ወደ ባህር ነጋሹ ሲላክ "እኔ ንጉሱን ከማመን እና ታርቄ ከመግባት ይልቅ የቱርኩን ፓሻ ባምን ይሻለኛልና በአንድ ስጋጃ ላይ ተቀምጬ ከቱርኩ ፓሻ ጋር ታርቄያለሁ" የሚል የእምቢታ ምላሽ ሰጥቶ በአፄ ሚናስ ጊዜ እንዳደረገው አሁንም ተመልሶ ከቱርክ ጋር ወገነ። ከቱርክ ብዙ መድፎች መቀበሉን ለመግለጽም የእምቢታ ደብዳቤውን ከአንድ የመድፍ ጥይት ጋር ነበር የላከው።



ንጉሱም "አንተ በቱርኮች ትመካለህ፤ እኔ ግን ሃይለኞችን በሚጥል በኢየሱስ ክርስቶስ ተመክቼ እመጣብሃለሁ" የሚል መልዕክት ልከው ሠራዊቶቻቸውን አስከትለው ዘመቱ። ሁሉም ከያለበት እየመጣ ከጎናቸው ተሰለፈ። እንትጮ ላይ ሲደርሱ በሐበሾች ወታደሮቹ ብቻ ሊዋጋ የነበረው ይስሐቅ ሁኔታው አላምር ስላለው ወደ ከተማው ወደ ደባሩአ ሔዶ ቱርኮች እንዲያግዙት ጠየቀ። የቱርኮችና የባህርነጋሽ ጦር በህዳር ወር 1570 ዓ.ም እንትጮ ላይ ጦርነቱን ለመጀመር ተሰለፈ። የንጉሱ ጦርም ለውጊያ ተዘጋጁ።
አፄ ሠርፀድንግል ጦሩን በሶስት ከፍለው የመሐሉ አዝማች ራሳቸው ሆነው ዘመናዊ መሳሪያ ከታጠቀ ዘመናዊ ሰራዊት ጋር ይፋለሙ ገቡ። ያልተለመደው የመድፍ ተኩስ ሲደመጥ የንጉሱ ሠራዊት ተደናግጠው ሊሸሹ ቢሞክሩም፣ ንጉሱ ወታደሮቹን እያበረታቱ እግረኛው ከኋላ እንዲከተልና ፈረሰኛው ወደ መድፉ ጋልቦ ሔዶ በጨበጣ እንዲዋጋ በማዘዛቸው፤ ተንጋግተው የሔዱት ፈረሰኞች በመድፍ አልቀው የቀሩት ጥቂቶቹ ተርፈው ወደ መድፉ ተጠግተው ቱርኮችን በጨበጣ ተዋግተው አሸነፉ።

ባህር ነጋሹም እርቅ ጠየቀ። ንጉሱም "ናና ታሪቅ አብረን ሆነን ቱርኮችን እንዋጋ" ሲሉት፣ "ቱርኮቹንማ እንዴት አድርጌ እክዳለሁ" ብሎ እርቁን ተወው። የቆመው ጦርነት በታህሳስ ወር እንደገና ቀጠለ። በዚህ ጦርነትም ባህር ነጋሽ ይስሐቅ በጦር ተወግቶ ወደቀና ሞተ። የቱርኩ ፓሻ ከድር ከወርቅ የተሰራ የራስ ቁር ደፍቶ፣ የወርቅ ሰይፍ በጎኑ ታጥቆ፣ የወርቅ ጦር በቀኝ እጁ እንደጨበጠ፣ ፈረሱ ላይ ሆኖ ድል እየሆነ ያለውን ጦር በመመልከት ላይ ሳለ፤ የንጉሱ ታማኝ ዘመድ ዮናኤል ጦር ወርውሮ ወግቶ ከጣለው በኋላ በራሱ የወርቅ ሰይፍ የፓሻውን አንገት ቆርጦ አመጣና ለአፄ ሠርፀድንግል አስረክቦ ፎከረ።

"የንጉሱ ሎሌ ዮናኤል፤ ፓሻውን ገደለው በራሱ ሾተል" እየተባለ ዛሬ ድረስ ይነገርለታል። ከዚህ ድል በኋላ ብዙዎቹ ተመልሰው ወደ ንጉሱ ገቡ። በቱርኮች ሰፈርም በርካታ ገንዘብና ልዩ ልዩ እቃዎች፣ ጌጣጌጦች፣ መድፍና ዘመናዊ መሳሪያዎች ተማረኩ። የምፅዋ ወደብም ተመልሶ ወደ ንጉሠነገስቱ ግዛትነት ተለወጠ።

የፓሻውንና የተቆረጠውን ጭንቅላት በአንድ ስጋጃ ምንጣፍ ላይ ጎን ለጎን አስቀምጠው፤ ንጉሱ እየጠሩ ለታላላቅ ሹማምንት አሳዩዋቸው። የሁለቱን የስጋጃ ላይ ስምምነት ለማስታወስ መሆኑ ነው። የቀሩት ቱርኮችም ባሉበት ሆነው "እኛ የንጉሱ ሀብት ነን፤ አሁንም ታማኝ ሰው ይላኩና በእጃችን ያለውን ሀብት፣ መሳሪያና ንብረት ሁሉ ይውሰዱ።" ብለው ላኩና ሰው ተመድቦ ብዙ ንብረቶች ለንጉሱ ተሰጡ። መሳሪያውንም

ለወታደሮቻቸው አከፋፈሉ። የድሉን በዓል አስመልክተው በዚህ አጋጣሚ ስርዓተ ንግሳቸውን እንደአባቶቻቸው በጥንታዊቷ በአክሱም ፅዮን ለማክበር በ1570 ዓ.ም በጥር 15 ቀን አክሱም ገቡ። ከፍተኛ ድምቀት የታየበት አቀባበልም ጠበቃቸው። የድሉንና የንግስናውን በዓል አክብረው ሹመትና ሽልማት ሰጥተው በታላቅ ደስታ ወደ እንፍራንዝ /ጎንደር ዙሪያ/ ተመለሱ። ሹማምንቱንም ወደየ ግዛቶቻቸው ሸኙዋቸው።

ይህ ሁሉ ሆኖ አፄ ሰርፀድንግል እረፍት አላገኙም። በሌሎች ነገስታት የግዛት ዘመን እንዳየነው ሁሉ፣ አሁንም ከየአቅጣጫው የሚያምፁ አልጠፉም። በአንድ በኩልም የነገስታት ዝርያ ያላቸው ዙፋኑ ይገባናል ብለው ሲነሱ፣ በሌላ በኩልም የፈላሻ እንዲሁም የዛጉዌ ዘሮች፣ ቡተጨማሪም የየግዛቱ ባላባት አልገብርም ማለትና አሁን ደግሞ የኦሮሞ ተወላጆች ገሚሱ ከንጉሱ ጋር በወታደርነት ተሰልፈው ቢዋጉም፣ የቀሩት በየነገዶቻቸው ሆነው መነሳታቸው አልቀረም። በዚህም ሳቢያ ፈጣን የትራንስፖርት ዘዴ ባለመኖሩና በመሰል ችግሮች ምክንያት አንዱን ሲሉ አንዱን እየሆነባቸው በየጊዜው ከቦታ ቦታ እየተዘዋወሩ መግዛት ግዴታቸው ነበር። ስለዚህም አፄ ሰርፀድንግል ከአክሱም መልስ የፈላሾችን ጥቃት ለመመከት ወደ ጦር ሜዳ ማምራታቸው ነው። በ1571 ዓ.ም "ፈላሾች ከሰሜንና ከወገራ መንደሮች እያሰፉ የወገራን አውራጃ ዘረፉት፣ ቤቱንም አቃጠሉት፣ ህዝቡንም ወንዱንም ሴቱንም እንደ ባሪያ ያጉላሉት ጀመር የሚል መልእክት መጣላቸው።" ይልና "ንጉሱ ይሄን ሲሰሙ በንዴት ተቃጠሉ።" ይላል ታሪክ ነገስታቸው።

ወታደሮቻቸውን ሰብስበው ከ20 ቀን ጉዞ በኂላ ወገራ ደረሱ። የፈላሾች መሪ ጎሽ ከመሽገበት ተራራ ደርሰው የተራራውን ዙሪያ ከበቡት። ሆኖም ወደ ላይ ለመውጣት ችግር ነበርና ፈላሻቹ ከላይ ሆነው የቋጥኝ ናዳ እያወረዱ ብዙ የንጉሱን ሰራዊቶች ፈጁባቸው። ታላላቅ የጦር አዝማቾቻቸው በድንጋይ እየተጨፈለቁ አለቁ። ጥቂት ጀግና አዝማቾች ወደ ተራራው ወጥተው ውሃ የሚገኝበትን አካባቢ በቁጥጥር ስር አድርገው ብዙ ፈላሾችን ሲገድሉ፣ ይህን ተራራ ለቀው ወደ ዋናው ተራራማ መንደር ሸሹ።

ይሄኛው መንደራቸው ደግሞ ከቀድሞው የበለጠ ነበርና በተመሳሳይ ተከበበ። ሰፊ ጊዜ አግኝተው ተራራው ላይ የወጡት ፈላሶች መከበባቸውን ሲያውቁ ጌዲዮን የተባለው የፈላሾች ዋና መሪ " ወገኖቼ ሆይ ስሙኝ፣ ተማርከን በክርስቲያኖች ባሪያ ከምንሆን ለኛ ሞት ይሻለናል። የሮማው ቄሳር ልጅ ጢሮስ እየሩሳሌምን በጦርነት ከቦ ባስጨነቀ ጊዜ አባቶቻችን እስራኤሎች በሀፍረት ከመኖር በክብር መሞት ይሻላል ያሉትን አልሰማችሁም?" ሲላቸው ብዙዎቹ በጌዲዮን፣ የቀሩት



በጎሽ አዝማችነት በቁርጠኝነት ሊዋጉ ተዘጋጁ። ዋናው ጦርነት ተጀመረና የንጉሱ ወገኖች ከታች ወደ ላይ እየተኮሱ ሲገድሏቸው እነሱም የድንጋይ ናዳ ሲያወርዱባቸው ብዙ ሰው አለቀ። ወደ ተራራው መውጣት የማይታሰብ ነበርና፣ ንጉሱ ከቱርክ የማረኩትን መድፍ አስጠምደው ወደ ላይ ሲያስተኩሱ ከፈላሾች ብዙዎች ተመተው ሲወድቁ ስለታየና ለመድፍ እንግዳ ስለነበሩ መብረቅ ነው ብለው ይራወጡ ጀመር። በዚህ ክፍተት ተጠቅመው የንጉሱ ወታደሮች በገመድና በሌሎች ዘዴዎች ተንጠልጥለው ወደ ተራራው በመውጣት በመሳሪያ ተኩስና በጨበጣ ውጊያ ጨረሷቸው። መሸነፋቸውን ሲያውቁ ጥቂቶች በገዛ ፍቃዳቸው ወደ ገደል እየተወረወሩ ሲሞቱ፣ አዝማቻቸው ጎሽም አልማረክም ብሎ ወደ ገደል በመውደቁ የንጉሱ ድንኳን አጠገብ ወድቆ ተገኘ። ጌዲዮን ግን አመለጠ።

በብዙ ትግል ፈላሾችን አሸንፈው ቀደም ሲል ሄደውበት ወደነበረው ወደ እናሪያ ነበር የተጓዙት። በጎንደርና በጎጃም አልፈው ሲጓዙ ሌላውን ሰራዊት ወደ ወሰጋ እና ሊሙ፣ ወደ ጅማ፣ ወደ ከንባታ... እያሰራጩ ያልገበረው እንዲገብር እያስደረጉ እናሪያ ደረሱ። የእናሪያ (ከፋ) ባላባትም ባንደቾ የሚባለው ሲሆን፣ እርሱም እንደአባቱ በታማኝነት ተቀብሎ አስተናግዶ ገበረላቸው። ፈቃደኛ በመሆኑም ንጉሱን ተከትለው በሄዱት ቀሳውስት አማካኝነት ክርስትናን ተቀብሎ የተጠመቀ ሲሆን፣ ሹማምንቱ እና ህዝቡ በቂ ቀሳውስት ባለመኖሩ በየወንዙ እየተጠመቁ ክርስትናን የተቀበሉት ካህናቱ ስለሰበኩላቸው ነው። ባንደቾም ክርስትና ተነስቶ ዘማርያም የሚል ስም ተሰጥቶት የወርቅ መስቀል በአንገቱ ንጉሱ እራሳቸው አስረውለት ግብሩንም በግማሽ ቀንሰውለት በደስታ ጥቂት ጊዜ አሳልፈው በአካባቢው የቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን እንዲሰራ ተደረገና፣ በዚሁ አካባቢ ባላባቶችና ህዝቦች ክርስቲያን መሆን ጀመሩ። .

አፄ ሰርፀድንግል ከእናሪያ ተመልሰው እንደመጡ ቱርኮች ከምሽጋቸው ከአርቂኮ ወጥተው ደባሩአን ያዙ። ከዚያም አልፈው ከሃማሴን ከንቲባ ጋር ጦርነት አድርገው ቱርኮች አሸነፉ። በጦርነቱም ብዙ መኳንንትና ወታደር አለቀ የሚል መልዕክት ደረሳቸው። እዚህ ላይ የምንረዳው የቱርኮችን ብልጠት ሲሆን ይኸውም ከዚህ በፊት በተደረገ ጦርነት ታማኝ መስለው ንብረታቸውን አስረክበው ከንጉሱ ጋር የተስማሙ በመምሰል አዘናግተው ንጉሱ ራቅ ብለው እስኪሄዱ ጠብቀው ድጋሚ መውረር ማሰባቸውን ነው።

የሆነ ሆኖ አፄ ሰርፀድንግል ይህን ሲሰሙ "ምታ ነጋሪት ክተት ሰራዊት" ብለው ሁሉም ወታደር እንዲሰበሰብ ያልተሰበሰበውንም ቤት ንብረቱን እንደሚዘርፉ አወጁ። ሁሉም ሲሰባሰብ ወደ ሽሬ ተጓዙና ለዋናው ጦር የበላይ አዛዥ የአክሱምን ንቡረ ዕድ ተማስን፣ ከተማስ ጋር ወሰኖ

መሐመድ (የክርስትና ስሙ ወ/ክርስቶስ) የሚባለውን በውስጡ የሚታዘዙትን የኦሮሞ ተወላጆች ይዞ እንዲዘምት አደረገ። ቱርኮችም እስከመሪብ ድረስ መጥተው ነበርና፤ ጥቂት ተዋግተው የማረኩትንና የዘረፉትን ይዘው ሸሹ። እቁበ ሚካኤል የተባለው ዘዴኛ ተዋጊ ቀድሞ አልፎ የመሸሻ መንገዶቻቸው ላይ አድፍጦ ነበርና ሳያስቡት አጥቅቷቸው የዘረፉትንና የማረኩትን አስመልሶ ድል ስላደረጋቸው ንጉሱ ደስ ተሰኝተው ባህር ነጋሽ ብለው ሾሙት። የራስ ወርቅም ታሰረለት። ቱርኮች ከኢትዮጵያ ወደብ ግዛት ካልጠፉ ኢትዮጵያ መቼም ሰላም እንደማታገኝ ዘግይተው የተረዱት አፄ ሰርጸድንግል በዚህ ጊዜ በ1581 ዓ.ም እስከ ባህር ጠረፍ ድረስ ሄደው ተዋጓቸው።

ንጉሱ በየብስ ጠረፍ፣ ቱርኮች በባህሩ ላይ በመርከብ ሆነው በርቀት ሲታኮሱ ቱርኮች በኢትዮጵያ ጦር ላይ ብዙ እልቂት አድርሰው የነበረ ቢሆንም፤ እስከመጨረሻው እነሱን ለማጥፋት በወሰኑት ንጉሰነገስት የሚመራው ጦር በፅኑ ስለተዋጋቸውና ስላልቻሉ በጀልባ እና በመርከብ እየሸሹ ወደ ዳህላክ ደሴት ሄደው ሰፈሩባቸው። የኢትዮጵያ ጦርም ቱርኮችን ጠራርጎ ለማስወጣት፣ ተከታትሎ ለመደምሰስ የሚችልበት መርከብ አልበረውም። እዚያ ጠረፍ ላይ ረጅም ጊዜ ለመቆየት የሚያስችል ስንቅ ባለመኖሩም ወታደሩ የአካባቢውን ህዝብ እየዘረፈ በመብላቱ የአካባቢው ነዋሪዎች ለንጉሱ አቤቱታ ሲያቀርቡ " ምን ይደረግ ስንቅ ሲያልቅ፤ ደግሞስ ከጠላቶቻችሁ ከቱርክ ወታደሮች የአገራችሁ ወታደር ቢዘርፋችሁ አይሻልም?" እስከማለት ያደረሳቸው የስንቅ እጥረት ነበር። በአካባቢው እህል የማይበቅል ለከብት፣ ለፈረስ ለበቅሎ የሚሆን ሳር እንኳ የሌለበት ነበር። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ሃማሴንና ጠረፉ በአፄ ሠርፀ ድንግል እጅ ሆነ። ሆኖም ደባሩአ፣ ምፅዋ፣ አርቂኮ ላይና በአካባቢው ሁሉ ሰራዊት ማስቀመጥና ማስጠበቅ አልተቻለም። ይሁን እንጂ እስከ ዘመነ መሳፍንት ጊዜ ድረስ መሳው ሃማሴንና ጠረፉ ጠንካራ ንጉስ ሲነሳ በኢትዮጵያ እጅ፤ ደካማ ንጉስ ሲነግስም በቱርኮች እጅ፤ እየሆነ ሲዘልቅ ቢችልም፤ አፄ ሠርፀድንግል ግን በዘመናቸው በስራቸው አድርገውት ሲቆዩ መቻላቸውም ሆነ መሞከራቸው ያስመሰግናቸዋል። እናም ባየነው መልኩ አፄ ሰርፀድንግል ቱርክን ሁለት ጊዜ ድል አድርገው ድንበራቸውን በማስከበር፤ በግራኝ ጊዜ የተከፈለውን ሀገር በአንድ መንግስት ስር በማጠቃለል፣ እራቅ ባሉ ግዛቶች ክርስትናን በመዘርጋትና በሌሎች የአስተዳደር ስራዎች ያለ እረፍት ሲጥሩ 34 ዓመቱን የስልጣን ዘመናቸውን አጠናቀው ለህልፈት የደረሱት በ1589 ዓ.ም በ47 ዓመታቸው ነው።



## ምዕራፍ ፷

## የአፄ ያዕቆብ ዘመነ መንግስት

## ከ1589-1594 ዓ.ም

አፄ ሠርፀድንግል ከሞቱ በኋላ ከዋናዋ ባለቤታቸው የወለዷቸው ልጆች ሁሉ ሴቶች ነበሩና ከእቁባታቸው የወለዱት ልጅ አቤቶ ያዕቆብ (በነገራችን ላይ አቤቶ የሚለው ቅፅል ስም የህፃናት የነጋሲ ዘሮች መጠሪያ ነው) ነበሩ ለንግስና የተመረጡት። ይህም የሆነው የአፄ ሠርፀ ድንግል ዋናዋ ባለቤታቸው እቴጌ ማርያምሥና ወንድ ልጅ ስለሌላቸው ነበር። ስለዚህ የሴት ልጆቻቸውን ባሎች ከጎናቸው አድርገው በመምከር የ7 ዓመቱን ህፃን አቤቶ ያዕቆብን በማንገስ በራስ አትናስዮስ ሞግዚትነት እንዲያስተዳድር አደረጉ።

ራስ አትናስዮስ የእቴጌዋ ሴት ልጅ ባል ነበርና አማቱ ያዘዙትን ለመፈፀም የአፄ ሚናስ የልጅ ልጅ የሆኑትን ዘድንግልን ዙፋን እንዳይቀናቀኑ አስረው ህፃኑን ንጉስ እንደፈለጉ የሚያሽከረክሩበትን መንገድ አመቻቹ።

በወቅቱ አገር ለማስተዳደር የሚያስችል ዕድሜ የነበራቸው ዘድንግል እና ሱስንዮስ የነበሩ ሲሆን፤ ዘድንግልን በጣና ደሴት ወስደው ሲያስሯቸው ያዩት ሱስንዮስም ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ ሸሽተው አመለጡ።

ከዚያም እቴጌ ማርያምስና፣ ራስ አትናስዮስ፣ ራስ ክፍለ ዋህድ፣ ደጀዝማች ዘስላሴ የኢትዮጵያን ግዛት ተከፋፍለው በሙሉ ስልጣን ያሻቸውን እየሾሙ እየሻሩ ይገዙ ጀመር። (አሁንም የ7 ዓመቱን ህጻን "እንቴ" ልንል ነው) አፄ ያዕቆብ በ7 አመታቸው ነግሠው 5 አመታትን በስልጣን ስለቆዩ አጠቃላይ ታሪካቸው በዚያው በልጅነት እድሜ በ12 አመታቸው የሚቋጭ ነው። ስለዚህ በዚህ እድሜያቸው እንዲህ እንዲህ አደረጉ ሲባል አንባቢን ግራ ሊያጋባ ይችል ይሆናል። ሆኖም የነጋሲ ዘሮች ከልጅነታቸው ጀምሮ በየግል መምህራኖቻቸው በልዩ ሁኔታ መንፈሳዊውንም ዓላማዊውንም ትምህርት በበቂ ሁኔታ ስለሚማሩ ስለአሿሿም አሻሻር ...... ወዘተ በደንብ ማወቃቸው ሊያስገርመን አይገባም። በተጨማሪም በዙሪያቸው ያሉ ሹማምንት በግልዕም በድብቅም ያማክሯቸዋል አፄ ያዕቆብ ስልጣናቸው በሰው እጅ መሆኑን ስላልወደዱት እነዚህን ባለሥልጣኖች ወደ ጎን አድርገው ሙሉውን ስልጣን ለመጠቅለል ፈለጉ። እናም ሹምሽር ማድረግ ጀመሩ። በመጀመሪያ ደጃዝማች ዘስላሴን በቀጥተኛው አሿሿም በግዛት፤ ውስጥ ለውስጥ በግዞት ዓይነት አካሄድ በመሔድ ወደ እናሪያ ላኳቸው። በዚህ ጊዜ እነ ራስ አትናስዮስ "ነግ በኔ" በሚል መነሻ ንጉሡ ላይ ተነሡባቸው። ወዲያውም እራሳቸው እንዳላነገሡዋቸው "ይህ ንጉስ ህፃን ነውና, ለማስተዳደር አይበቃም።

እንዲያውም እንደ ማበድ እያደረገው ነው" ወዘተ እያሉ ለህዝቡ ያልሆነ ነገር እየተናገሩ አሣደሙባቸው። እድሜው መበራከቱን ባዩ ጊዜ ያዕቆብ እንዳያስሯቸው በመፍራት ሸሽተው ወደ እናታቸው አገር ወደ ሠሜን ተራራ ሲሔዱ በመንገድ ላይ ሳሉ ተያዙና በግዞት ወደ እናሪያ ተላኩ።

በዚህ ጊዜ መኳንንቱና እቴጌ ማርያም ስና ያለ ንጉስ ህዝቡ እንደማይገዛ ያውቃሉና ራሳቸው ያሠሯቸውን ዘድንግልን አስመጥተው በአፄ ያዕቆብ ስፍራ "አጥናፍ ሰገድ" አሠኝተው አነገሡዋቸው። አፄ ያዕቆብ በግዞት ባሉበት እዚያው እናሪያ ይቆዩንና የቀረውን ቀጥለን ታሪካቸውን ከምናይላቸው ከአፄ ዘድንግል ታሪክ ጋር ተያይዞ እንገኘዋልን።



## ምዕራፍ ፷፩

## የአፄ ዘድንግል ዘመነ መንግስት

## ከ1494-1596 ዓ.ም

አፄ ዘድንግል በአፄ ያዕቆብ ዙፋን በተቀመጡ ጊዜ የውጭ አገር ሚስዮናውያን ቀደም ሲል ለአፄ ያዕቆብ አንድ ጥያቄ አቅርበው በእንጥልጥል የቀረባቸውን ጉዳይ ለአፄ ዘድንግል አቀረቡ። ይህም ጥያቄ "ትምህርት ቤት ከፍተን ብዙ የኢትዮጵያ ልጆች ከፖርቱጋል ህፃናት ልጆች ጋር ደባልቀን እያስተማርን ለቤተ መንግስቱ አገልጋይ የሚሆኑ ልጆች እናዘጋጅ" የሚል ሲሆን፣ አፄ ዘድንግል "ጥቂት ጊዜ ወስደን እንምከርበት" የሚል ምላሽ ሠጧቸውና እነዚሁኑ ጥያቄ አቅራቢዎች መልዕክተኛ በማድረግ ወደ ሮማ ጳጳስና በወቅቱ ገናና ሆና ወደ ነበረችው ስፔን የወዳጅነት ደብዳቤ እንዲወስዱ አደረጓቸው።

ሃሳባቸውም የእጅ ሙያ የሚያስተምሩ ስፔናውያንና ፖርቱጋሎች ወደ ኢትዮጵያ እንዲልኩላቸው መጠየቅ ሲሆን፣ አባቶቻቸውን ፖርቱጋል እንደረዳቻቸው ሁሉ፣ አሁንም ችግር ቢነሣ ሃያሏ ስፔን ከጎኔ ትሆናች ብለው በማሠብ እንደነበር ይነገራል። ሆኖም ምላሹ አጥጋቢ አልነበረም። ሚሲዮናቹ ግን ጥያቄያቸው ምላሽ እንደሚያገኝ ተስፋ በማድረግ ትዕዛዛቸውን ይፈፅሙ ነበር። በጣም ከመዋደዳቸው የተነሣም ካቶሊኮችንና ኮፕቶችን (ኦርቶዶክሶችን) አከራክረው ከካቶሊኮቹ ወገን በመሆን ከጦር አለቃቸው ከደጃች ላእከ ማርያም ጋር ተስማምተው ከኦርቶዶክስ ወደ ካቶሊክ ሃይማኖት በማምራታቸው ከእስክንደሪያ የመጡት የዘመኑ ጳጳስ "ለንጉስ ዘድንግል የሚታዘዘውን ገዝቻለሁ" ብለው ህዝቡንም መኳንንቱንም አወገዙ።

ወድያውም ከእናሪያ ተመልሶ በራስነት ማዕረግ ጎጃምን ይገዛ የነበረው ዘስላሴ የጎጃምን ህዝብ ይዞ በንጉሡ ላይ ተነሣ። ብዙዎቹም ካቶሊክ የሆኑትን ንጉስ ተቃውመው ከጎኑ ተሰለፉና ደንቢያ ላይ ጦርነት ተደረገ። ሁለት መቶ የሚሆኑ የታጠቁ ፖርቱጋሎችና ሚሲዮኖችም "ከእርስዎ ጋር እንሞታለን" ብለው ከአፄ ዘድንግል ጋር ተሠለፉ። ሆኖም ጦርነቱ እንደተጀመረ የንጉሡ ወታደሮች እየከዱ ራስ ዘስላሴን ማገዝ ጀመሩ። በዚህ ጦርነት ንጉሡም፣ አዝማቻቸው ደጃች ላእከማርያምም በጦር ተወግተው ሞቱ። አፄ ዘድንግል ከሞቱ በኋላም የእጣታቸውን አልማዝ ለመውሰድ እጃቸውን ቆርጠው አይናቸውንም አጥፍተው በዚሁ በካቶሊክነታቸው ማቢያ በሬሳቸው ላይ እንስሣ እንዲራመድበት አደረጉና የንጉስ ክብር በመንፈግ ሬሳቸውን ዛፍ ስር ጥለውት ሔዱ። በኋላም የአካባቢው ባላገሮች አንስተው ቀብረዋቸው ነበርና በኋላ ላይ የነገሡት

ሱስንዮስ ራሳቸውን አስመጥተው በጣና ሃይቅ በደሴተ ዳጋ በክብር እዲያርፉ፡ አደረጉ።

የአፄ ዘድንግል ታሪክ ባየነው መልኩ በ1596 ዓ.ም ከሁለት ዓመት የግዛት ቆይታ በኋላ ተፈፀመ።

ከዙፋን ወርደው ወደ እናሪያ የተላኩት አፄ ያዕቆብ እዚያው እናሪያ ስለነበሩና፤ ሸሽተው ወደ መሐል ሀገር ሔደው የነበሩት ሱስንዮስም በአቅራቢያው ስለማይገኙ ራስ ዘስላሴ የመንግስቱን ስልጣን በበላይነት ይዘው ቆዩ። ራሣቸው ለመንገስ ቢያስቡም ከነገስታት ዘር ስላልሆኑ በሸማግሌ ምክር ሃሣቡን በመተው አፄ ያዕቆብን አስመጥተው ለሁለተኛ ጊዜ በዙፋን ላይ አስቀመጧቸው።

በዚሁ ጊዜም ሱስንዮስ የዘድንግልን ሞት በሠሙ ጊዜ የሸዋና የአካባቢው ተወላጆች ጦራቸውን አስከትለው ወደ ጎንደር ተጓዙ። የየግዛቱን ሹማምንትም ከያሉበት በመልዕክተኛ ሲያስጠሩ የነጋሲ ዘር እንደመሆናቸው መጠን ገሚሉ በጥሪው መሠረት እየመጣ ከጎናቸው ሆነ። ይህ በእንዲህ እንዳለም በአፄ ያዕቆብና በራስ ዘስላሴ መካከል ቅያሜ መኖሩ ለሱስንዮስ ተመቻቸላቸው። የሁለቱን ሠራዊት ለየብቻ ተዋግተው ጎጃም ወስጥ አፄ ያዕቆብ ድል ሲሆኑ፤ ራስ ዘስላሴ መሸነፉን ሲያውቅ እርቅ ጠይቆ ወደ ሱስንዮስ ተቀላቀለ።

ከዚህ ድል በኋላም ሱስኒዮስ የንጉሠነገስትነቱን ስልጣን ለመያዝ ቻሉ።



## ምዕራፍ ፳፱

## የአፄ ሱስኒዮስ ዘመነ መንግስት

## ከ 1596-1624 ዓ.ም

አፄ ሱስኒዮስ ስልጣን በያዙ ማግስት ለስፔን ንጉስ ለፍሊፕ 3ኛ የወዳጅነት ደብዳቤ ዕፈው የወታደር፣ የዘመናዊ መሣሪያ እና የአጠቃላይ እርዳታ ጥያቄ ፓኤዝ በተባለ ኢትዮጵያ ውስጥ በሚኖር ሚሲዮናዊ አማካይነት ላኩ። በተመሣሣይም ለሮማው ጳጳስ ይህንኑ ሐሳብ የያዘ ደብደቤ ላኩ። ስለዚህም የሮማው ጳጳስና የስፔኑ ንጉስ ተመካክረው ለአፄ ሱስኒዮስ የላኩት ምላሽ "ኢትዮጵያ በቅድሚያ የኦርቶዶክስ ሃይማኖቷን በሮማ ካቶሊክ ትለውጥ እንጂ የጠየቁት ጥያቄ ሁሉ ይፈፀማል" የሚል መልዕክት ላኩባቸው።

አፄ ሱስኒዮስም አገራቸውን ለማሰልጠን ካላቸው ጉጉት የተነሳ በስፔን፣ በፖርቹጋል ሚሲዮናዊያንና በሮማ ጳጳሳት ግፊት ለብዙ ዘመናት ፀንቶ ከነበረው ከእስክንድሪያ ኮፕቲክስ ቤ/ን ህግ በመውጣት ለሮማው የካቶሊክ ቤተ ክርስትያን ራሳቸውን ቤተሰቦቻቸውንና ህዝባቸውን አሳልፈው ሠጡ።

በዚህ ምክንያት አገሪቱ ውስጥ የከፋ ብጥብጥ ተከተለ። ያሬድ ግርማ ሐይሌ የጎንደር ታሪክ በሚለው መፅሐፉ "ካቶሊክን የመንግስት ሐይማኖት ለማድረግ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ በወሰዱት የሃይል እርምጃ ብዙ ህዝብና በርካታ ቀሳውስት፣ መነኮሳትን በጭካኔና በግፍ ማስገደላቸው ለተከታዩ ትውልድ ጠባሣ ታሪክ ጥለው አልፈዋል" በማለት ይገልፀዋል ሲቀጥልም ይሁን እንጂ አፄ ሱስኒዮስ በዘመናቸው የስልጣኔ ፈ ለመቅደድ በርካታ ጥረቶችን አድርገዋል። ከነዚህም ውስጥ በሃገሪቱ ታሪክ የመጀመሪያ የሆነውን የአባይን ወንዝ ድልድይና ሌሎችንም ድንቅ ስራዎች ሠርተዋል።

ተክለፃድቅ መኩሪያ በ3ኛው ክፍል መፅሃፋቸው "ሱስኒዮስ አፄ ያዕቆብንና ደጃዝማች ዘስላሴን ካሸነፉ በኋላ ጎጃም ቀራኒዮ መድሐኒአለም ቤ/ን ስልጣን ሠገድ ተብለው ነገሡ። አፄ ሱስኒዮስም ከደብረ ታቦር ጋር 20 የሚሆኑ ከተሞችን ቆርቁረዋል" ይሉና "ዋና ከተማቸውን ደንቀዝ አደረጉ። ረጅም ግንብ አሠርተው አማካይ ቦታ ስለሆነ ወደ ሠሜን ትግሬ፣ ወደ ደቡብ ጎጃም፣ ወደ ምዕራብ የመተማ አፋፍ ጭልጋ ይታያል።" እያሉ ይቀጥላሉ። በእርግጥም እነዚህን መሰል ድልድይ፣ አዳዲስ ከተሞችን መቆርቆራቸውና የመሣሰሉት ጀምሮቻቸው ለሥልጣኔና ለእድገት የነበራቸውን ጉጉት ሊያመለክቱ ይችላሉ። የሆነ ሆኖ ፈቃደኝነታቸውን ገልፀው ሃይማኖቱን ከተቀበሉ በኋላ ሚሲዮኖቹም እንደልባቸው በዋና ዋና ከተሞች በትግራይ፣ በደንቢያና በጎርጎራ

እንዲሁም በሌሎች የገዢዎ ስፍራዎችና በሁሉም ቦታ እየሰበኩ በካቶሊክ ሃይማኖት ህግ ህዝቡንም መኳንንቱንም ያጠምቁ ጀመር። በተለይም ፖኤዝ የተባለው ሚሲዮናዊ ረጅም ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ በመኖሩ ግዕዝና አማርኛ አቀላጥፎ ይናገር ነበርና በየቦታው እየሰበከ በርካቶችን መለሠ። አውሮፓውያኑም የዘመናት ህልማቸው ስለተሳካ ደስተኛ ሆኑ።

ሆኖም የአገር ውስጡ ካህናትና ቀሳውስት ውግዘታቸውን አጠናከሩት። በንጉሡ ላይም ተነሱባቸው። ሁኔታውም በየጊዜው ለሚሸፍቱት ልዩ ልዩ የህ/ሰብ ክፍሎች ምቹ ሆነላቸውና አመፁ በረከተ።

ሜንዴዝ አልፎንሡ የተባሉት ጳጳስም ከሮም መጥተው የካቶሊኩን ህግ በኦርቶዶክስ ህግ ላይ ተኩት። ንጉሡም የሁሉም አብያተ ክርስትያናት ህግ እንዲለወጥና በካቶሊክ ደንብ እንዲተካ በአዋጅ አስነገሩ። ንጉሡንና ቤተሰባቸውን ያዩ በርካታ ኢትዮጵያውያንም ሐይማኖቱን ተቀበሉ።

በአጠቃላይ 1ሺ 300 አመት እድሜ ያለው የእስክንድሪያ ኮፕቲክስ መንበረማርቆስ ከሆነው የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ህግ በመውጣት በሮማው መንበረ ጴጥሮስ ሲተካ ሊከሰት የሚችለውን አገር አቀፍ አመፅና ውግዘት ለአንባቢ መዘርዘር ሳያስፈልግ ሁሉም በቀላሉ ሊረዳው ይችላልና የአፄ ሱስንዮስ መንግስት ምን ያህል አጣብቂኝ ውስጥ እንደሚገባ ግልፅ ነው።

ጉልበታሙ ካህናት ንጉሡን ተቃውመው ለውጊያ ከተዘጋጁ ወገኖች ጎን ሲሰለፉ፣ የኦርቶዶክሱ ጳጳስ አቡነ ስምኦንም ከሸፈቱት ካህናት ጋር ሆነው "ከሱስኒዮስ ጎን ተሰልፎ የወጋን ውጉዝ ከመአርዮስ" እያሉ ሲያወግዙ፣ ሌላው በግርግሩ ከብትና ገንዘብ ለመዝረፍ፣ወዘተ... ሲራኮቱ ከ1611 ዓ.ም እስከ 1618 ዓ.ም ድረስ በአገሩ ዘረፋና እልቂት በረከተ። ንጉሡም ወዲያ ወዲህ እየተሯሯጡ ሲዋጉና ሲያዋጉ ሠላም ጠፋ።

መነኮሣት "ውግዝ ሮማዊት ትፍለሥ፣ ካቶሊክ ይርከስ፣ተዋህዶ ይንገሥ" የሚል ተቃውሞ በንጉሡ ፊት በድፍረት ሲያሰሙ 100 ያህል መነኮሳት፣ 300 የቤተ ክህነት ሊቃውንት በሠይፍ ሲሠየፉ በርካታ ቀሳውስትም በስቅላት ተገደሉ። ጥቂቶቹም ምላሳቸው እንዲቆረጥ ተደረገ።

በዚህ ጊዜ በትግሬ፣ በላስታ፣ በበጌ ምድር/ጎንደር/ በጎጃምና በሌሎች ግዛቶች ያሉ ሊቃውንት "ሠማዕትነት አያምልጥህ ቶሎ ድረስ" እየተባባሉ እየተጠራሩ ወደ ደንቀዝ እየመጡ አንገታቸውን ለሰለት መስጠት ጀመሩ። የማይታሰብ የዕድቅ መሸመቻ አደረጉት ሊባልም ይችላል።



የተዋህዶ ሐይማኖት ተቆርቋሪዎች ተባብረው በመሠረቱት የጦር ግንባር በኩል በተደረገውና ጳጳሡ አቡነ ስምኦን ከሚገኙበት ክፍል ጋር በተደረገው ጦርነትም የንጉሡ ወታደሮች ብዙዎችን ፈጅተው ድል ስላደረጉ ንጉሡ ድል ላደረጉ ወታደሮቻቸው በደንቀዝ ላይ ሹመትና ሽልማት በሚሠጡበት ጊዜ አዝማሪ ተነስቶ "አበባ አበባ የመስከረም ፣ አፄ ሱስኒዮስ ንጉሰ ሮም" ብሎ ገጠመላቸው።
ይህ ሁሉ ሆኖ ግን የጠበቁት እርዳታም ሆነ ፍላጎታቸው የተፈፀመበት ሁኔታ አልነበረም።

አፄ ሱስኒዮስ ከአውሮፓውያኑ ጋር ተዛዕፈው ይህን መሰሉን ስምምነት ከማድረጋቸው በፊት በነበረው ጊዜ (በቀድሞው ሃይማኖታቸው እያሉ) የገነተ ኢየሱስ ቤተ ክርስትያንን ፣ የአዘዞ ተክለሃይማኖትንና ሌሎች አብያተ ክርስትያናትን አሳንፀው ነበር። የአዘዞ ተክለሃይማኖትን ቤተክርስቲያን በአስደናቂ ጥበብ እንዲሰራ ካደረጉ በኋላም ከዋናው ከደብረ ሊባኖስ ገዳም የሚገኘውን የፃድቁ አቡነ ተክለሃይማኖትን ፅላትና 50 ቁሶች፣ ተጨማሪ ሊቃውንትና መዘምራንን ከቤተልሔምና ከዙር አምባ አስመጥተው "ርዕሰ አድባራት ዳግሚት ደብረ ሊባኖስ" ብለው ሰይመዋል።

የፃድቁ ተክለሃይማኖት ዋናው ፅላት ለረጅም አመታት በአዘዞ ተክለሃይማኖት ከኖረ በኋላ በዳግማዊ አፄ ምኒልክ ጊዜ በሸዋ ካህናት ግፊት ወደ አዲስ አበባ መጥቶ በተክለሃይማኖት ቤ/ን በሐምሌ 12 1898 ዓ.ም እንዲገባ ተደርጎ ዛሬም ድረስ በዚያው ቤተክርስቲያን ይገኛል።

በተጨማሪም በሸንታ ወንዝ አጠገብ በአባ ሳሙኤል ስም ቤተክርስቲያን ያሠሩ ሲሆን፤ ይህን ቤተክርስቲያን ያሰሩትም የአዘዞ ተክለሃይማኖትና የአባ ሳሙኤል ዘዋልድባ ገዳም መነኮሳት በየጊዜው እየተገናኙ መንፈሳዊ ልውውጥ ያደርጉ ስለነበር ለእንግዶች ማረፊያና መፀለያ እንዲሆን ነው። ይህም ቤተክርስቲያን በኋለኛው ዘመን የሡዳን መሐዲስቶች /ድርቡሾች/ አፈራርሰውት ነበርና ፍርስራሹ ዛሬ ድረስ በቦታው ሲታይ፤ ነገር ግን የአካባቢው ሰዎች ተባብረው እዚያው ቦታ ላይ በቅዱስ ሚካኤል ስም ቤተክርስቲያን አሠርተው መንፈሳዊ አገልግሎት እየሠጠ ይገኛል። ሸንታ ወንዝ አጠገብ ሲባልም በአሁኑ የጎንደር ከተማና በአዘዞ መካከል በሚገኝ ቦታ ላይ ነው።

አፄ ሱስኒዮስ ከ1596-1624 ዓ.ም ድረስ ኢትዮጵያን በንጉሰነገስትነት ለ28 አመታት ሲያስተዳድሩ ያየናቸውን ክንውኖች ከፈፀሙ በኋላ አንገደበታቸው ተዘግቶ ጆሯቸው ደነቆረ። እግራቸውም ሽባ ሆነ። በዚህ ጊዜ ልጃቸው ልጅ ፋሲል ከዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም ተጠርተው መጡ።

ልጅ ፋሲል በጣም ሲጨንቁ አባ እምደ ስላሴ የሚባሉ በመተማ ቋራ በስማቸው የሰየሙትን ማህበረ ስላሴ ገዳምን የቆረቆሩ የበቁ መነኩሴ ስልጆ ፋሲል "አባትህን ብፈውስ ምን ታደርግልኛለህ?" ብለው ሲጠይቁ "ሲሶ መንግስት እሰጥዎታለሁ" አሏቸው። "በረሐ ላይ የሰራሁት ቤ/ን ስላሰ ጉልት ስጠኝ" ሲሏቸው ጥያቄያቸውን እንደሚፈፅሙ በመልእክተኛ አሣወቋቸውና ከቋራ ተነስተው መነኮሳትን አስከትለው ወደ ደንቀዝ ሄዱ። ደርሠውም 3 ሱባኤ ቀን በፀሎት ሌሊት በሳታት ፀልየው ፈወሷቸው። መነኩሴውም የተገባላቸው ቃል 44 ጉልት ፀናላቸው።

አፄ ሱስኒዮስ የተዘጋው እንደበታቸው ተከፍቶ ጥቂት ከቆዩ በኋላ ግን በዚሁ በ1624 ዓ.ም በታህሳስ ወር አረፉ። የተዘጋው እንደበታቸው ከተከፈተ በኋላ እንደ ታሪክ ነገስታቸው አገላለፅ "የእስክንድሪያ ሃይማኖት ትመለስ፣ የሮም ሃይማኖት ትርከስ፣ ፋሲል ይንገስ" ብለው ተናግረው ንስሐ ገብተው ወደ ኦርቶዶክስ ተመልሰው አረፉ።" ይላል። ሆኖም ከካቶሊክ ወገን የሆኑ ፀሃፍት በካቶሊክነታቸው እንደፀኑ ሞቱ እያሉ ይፅፋሉ።

በመጨረሻም ከጥቂት ቀናት በኋላ የቀብራቸው ስነ-ስርዓት በእዘዞ ተክለሃይማኖት ተፈፀመና እንደገና ወጥቶ በደቅ ደሴት ዳጋ እስጢፋኖስ በአንድነት ገዳም በክብር ተቀመጡ። የንጉሡ ነገስትነቱን ስልጣንም ልጅ ፋሲል ተረከቡ።



## ምዕራፍ ፳፫

## የአፄ ፋሲል ዘመነ መንግስት

## ከ1624-1659 ዓ.ም

አፄ ፋሲል ከአፄ ሱስንዮስ እና ወልደ ሰዓላ ከተባሉት በደብረ ታቦር ቆማ ፋሲለደስ አካባቢ ከተወለዱት እናታቸው የተገኙ ናቸው።

የልጅነት ጊዜያቸውንም በጣና ሐይቅ ደቅ ደሴት ዳጋ እስጢፋኖስና በሌሎች ጥንታዊ የትምህርት መስጫ ቦታዎች መንፈሳዊና አለማዊ ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ያሳለፉ ሲሆን፤ በቆይታቸውም ስለመንግስት አወቃቀር፣ ስለህዝብ አስተዳደር፣ ስለፍርድ አሠጣጥና ስለሌሎች ጉዳዮች በሚገባ አጥንተዋል።

አፄ ፋሲል የንጉስነገስትነቱን ስልጣን ዓለም ሆገድ /ዓለም የሰገደልህ/ በሚል ስመመንግስት ተረክበው በአባታቸው ዙፋን በ1624 ዓ.ም እንደተቀመጡ "ፋሲል ይንገስ፣ ተዋህዶ ይመለሥ፣ የሮም ሀይማኖት ይጥፋስ" በሚለው ቃል መሠረት የመንግስት ሐይማኖት የቀድሞው ኦርቶዶክስ እንዲሆን ስላደረጉ በርካቶች ንግስናቸውን በደስታ ነበር የተቀበሉት።

ስልጣን በያዙ ማግስትም ከቤተክህነት ሊቃውንት በኩል "ከካቶሊኩ ጳጳስ ከአልፎንሱ ጋር የሐይማኖት ክርክር እናደርጋለንና ጉባኤ ይጠራልን" የሚል ጥያቄ ስላቀረቡላቸው ጉባኤው እንዲካሄድ ፈቀዱና የክርክር ጉባኤው ንጉሡ በተገኙበት ተካሄደ።

እጨጌ በትረጊዮርጊስ የተባሉ ኢትዮጵያዊ ሊቅ ተመረጡና ከአልፎንሱ ጋር ክርክር አድርገው አልፎንሡ ተሸነፈ። ከዚህ በኋላ አፄ ፋሲልን ሊቃውንቱ "በሮማው ጳጳስ በአልፎንሱ ስብከት ሳቢያ የብዙ ምዕመናን ደም በከንቱ ፈሷልና እንበቀል" አሏቸው። ንጉሡም "የሞቱት ሰዎች የሠማዕታት ዋጋ አግኝተዋል። አሁን የእነዚህ ደም ቢፈስ ምንም አይጠቅማችሁም። ደግሞም አባቱ ሱስኒዮስ ይህን ሠው /አልፎንሱን/ ምዕዋ ድረስ ሸኝተህ ወደ አገሩ ስደድልኝ ብለው ተናዘዋልና አልችልም" አሏቸው። ከዚህ በኋላ አንድም የሮማ ካቶሊካዊ ሃይማኖት ተከታይ ወደ አገሪቱ እንዳይገባ የሚል ትእዛዝ አስተላለፉ። ጳጳሱ አልፎንሱና 8 ተከታዮቻቸውም ከኢትዮጵያ እንዲባረሩ ተደረገ። ወዲያውም ሮዝቅላ የተባለ ጳጳስ ሳይሾም ተሾሞ ከግብፅ የመጣ በመምሰል ታቦቱንና ቤተክርስትያኑን ባርኮ የዲቁናና የቅስና ማዕረግ ሠጠ። ሆኖም ሃሠተኝነቱ ተደርሶበት ተዋርዶ ተመለሠ።

አፄ ፋሲል/ፋሲለደስ/ በነገሱ በሦስተኛው ዓመት መልአከ ክርስቶስ የተባለ የላስታ ባላባት ተነሳባቸውና ጥቂት ተዋግተው አፄ ፋሲል ጊዜያዊ ሽንፈት ደርሶባቸው ሲሸሹ፤ መልአከ ክርስቶስ ወደ ቤተ መንግስታቸው ገብቶ ዙፋናቸው ላይ ተቀመጠ። ነገር ግን አፄ ፋሲል ወዲያው የሠሜን፣ የዳሞትና የበጌ ምድር አገረ ገገርዎችን አስጠርተው ከጎናቸው በማሰለፍ ተዋግተው አሸነፉና መልአከ ክርስቶስም ተነድሎ ወደ ዙፋናቸው ተመለሱ።

ልጅ ፋሲል በጣም ሲጨነቁ አባ አምደ ስላሴ የሚባሉ በመተማ ቋራ በስማቸው የሰየሙትን ማህበረ ስላሴ ገዳምን የቆረቆሩ የበቁ መነኩሴ ለልጅ ፋሲል "አባትህን ብፈውስ ምን ታደርግልኛለህ?" ብለው ሲጠይቁ "ሲሶ መንግስት እሰጥዎታለሁ" አሏቸው። "በረሐ ላይ የሰራሁት ቤ/ን ሰላሰ ጉልት ስጠኝ" ሲሏቸው ጥያቄያቸውን እንደሚፈፅሙ በመልእክተኛ አሣወቋቸውና ከቋራ ተነስተው መነኮሳትን አስከትለው ወደ ደንቀዝ ሄዱ። ደርሠውም 3 ሱባኤ ቀን በፀሎት ሌሊት በሳታት ፀልየው ፈወሷቸው። መነኩሴውም የተገባላቸው ቃል 44 ጉልት ፀናላቸው።

አፄ ሱስኒዮስ የተዘጋው እንደበታቸው ተከፍቶ ጥቂት ከቆዩ በኋላ ግን በዚሁ በ1624 ዓ.ም በታህሳስ ወር አረፉ። የተዘጋው አንደበታቸው ከተከፈተ በኋላ እንደ ታሪክ ነገስታቸው አገላለፅ "የእስክንድሪያ ሃይማኖት ትመለስ፣ የሮም ሃይማኖት ትርከስ፣ ፋሲል ይንገስ" ብለው ተናግረው ንስሐ ገብተው ወደ ኦርቶዶክስ ተመልሰው አረፉ።" ይላል። ሆኖም ከካቶሊክ ወገን የሆኑ ፀሃፍት በካቶሊክነታቸው እንደፀኑ ሞቱ እያሉ ይፅፋሉ።

በመጨረሻም ከጥቂት ቀናት በኋላ የቀብራቸው ስነ-ስርዓት በአዘዞ ተክለሃይማኖት ተፈፀመና እንደገና ወጥቶ በደቅ ደሴት ዳጋ እስጢፋኖስ በአንድነት ገዳም በክብር ተቀመጠ። የንጉሡ ነገስትነቱን ስልጣንም ልጅ ፋሲል ተረከቡ።



# ምዕራፍ ፷፫

# የአፄ ፋሲል ዘመነ መንግስት

# ከ1624-1659 ዓ.ም

አፄ ፋሲል ከአፄ ሱስንዮስ እና ወልደ ሰዓላ ከተባሉት በደብረ ታቦር ቆማ ፋሲለደስ አካባቢ ከተወለዱት እናታቸው የተገኙ ናቸው።

የልጅነት ጊዜያቸውንም በጣና ሐይቅ ደቅ ደሴት ዳጋ እስጢፋኖስና በሌሎች ጥንታዊ የትምህርት መስጫ ቦታዎች መንፈሳዊና አለማዊ ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ያሳለፉ ሲሆን፤ በቆይታቸውም ስለመንግስት አወቃቀር፣ ስለህዝብ አስተዳደር፣ ስለፍርድ አሠጣጥና ስለሌሎች ጉዳዮች በሚገባ አጥንተዋል።

አፄ ፋሲል የንጉስነገስትነቱን ስልጣን ዓለም ሠገድ /ዓለም የሰገደልህ/ በሚል ሰመመንግስት ተረክበው በአባታቸው ዙፋን በ1624 ዓ.ም እንደተቀመጡ "ፋሲል ይንገስ፣ ተዋህዶ ይመለሥ፣ የሮም ሀይማኖት ይፍለስ" በሚለው ቃል መሠረት የመንግስት ሐይማኖት የቀድሞው ኦርቶዶክስ እንዲሆን ስላደረጉ በርካቶች ንግስናቸውን በደስታ ነበር የተቀበሉት።

ስልጣን በያዙ ማግስትም ከቤተክህነት ሊቃውንት በኩል "ከካቶሊኩ ጳጳስ ከአልፎንሱ ጋር የሐይማኖት ክርክር እናደርጋለንና ጉባኤ ይጠራልን የሚል ጥያቄ ስላቀረቡላቸው ጉባኤው እንዲካሄድ ፈቀዱና የክርክር ጉባኤው ንጉሡ በተገኙበት ተካሄደ።

እጨጌ በትረጊዎርጊስ የተባሉ ኢትዮጵያዊ ሊቅ ተመረጡና ከአልፎንሱ ጋር ክርክር አድርገው አልፎንሡ ተሸነፈ። ከዚህ በኋላ አፄ ፋሲልን ሊቃውንቱ "በሮማው ጳጳስ በአልፎንሱ ሰብከት ሳቢያ የብዙ ምዕመናን ደም በከንቱ ፈሷልና እንበቀል" አሏቸው። ንጉሡም "የሞቱት ሰዎች የሠማዕታት ዋጋ አግኝተዋል። አሁን የእነዚህ ደም ቢፈስ ምንም አይጠቅማችሁም። ደግሞም አባቴ ሱስኒዮስ ይህን ሠው /አልፎንሱን/ ምዕዋ ድረስ ሸኝተህ ወደ አገሩ ስደድልኝ ብለው ተናዘዋልና አልችልም" አሏቸው። ከዚህ በኋላ አንድም የሮማ ካቶሊካዊ ሃይማኖት ተከታይ ወደ አገራቱ እንዳይገባ የሚል ትእዛዝ አስተላለፉ። ጳጳሱ አልፎንሱና 8 ተከታዮቻቸውም ከኢትዮጵያ እንዲባረሩ ተደረገ። ወዲያውም ሮዝቅላ የተባለ ጳጳስ ሳይሾም ተሾሞ ከግብፅ የመጣ በመምሰል ታቦቱንና ቤተክርስትያኑን ባርኮ የዲቁናና የቅስና ማዕረግ ሆነ። ሆኖም ሃሠተኝነቱ ተደርሶበት ተዋርዶ ተመለሠ።

እፄ ፋሲል/ፋሲለደስ/ በነገሱ በሦስተኛው ዓመት መልአከ ክርስቶስ የተባለ የላስታ ባላባት ተነሳባቸውና ጥቂት ተዋግተው አፄ ፋሲል ጊዜያዊ ሽንፈት ደርሶባቸው ሲሸሹ፤ መልአከ ክርስቶስ ወደ ቤተ መንግስታቸው ገብቶ ዙፋናቸው ላይ ተቀመጠ። ነገር ግን አፄ ፋሲል ወዲያው የሠሜን፣ የዳሞትና የበጌ ምድር አገረ ገገርዎችን አስጠርተው ከጎናቸው በማሰለፍ ተዋግተው አሸነፉና መልአከ ክርስቶስም ተነድሎ ወደ ዙፋናቸው ተመለሱ።

በ5ኛ አመት በ1629 ዓ.ም አቡነ ማርቆስ የተባሉ ጳጳሥ ከእስክንድርያ መጡ። አገሩም ህዝቡም ሰላም ሆነ። አፄ ፋሲልም የአስተዳደር ስራቸውን ከመስራት ጎን ለጎን እጅግ የሚወዱትን አውሬ የማደን ተግባራቸውን ቀጠሉ።

ከአባታቸው ዘመን ጀምሮም "ጎ ይነገስ" የሚል ንግርት ከአንድ ከበቁ ባህታዊ ተሠንዝሮ እንደነበር ይነገራል። አፄ ሱስንዮስ ይህ ንግርት ለኔ ነው በሚል መነሻ በ "ጎ" በሚጀምሩ አገሮች ጎርጎራ፣ ጎጃም... ወዘተ.. እያሉ ቤተመንግስታቸውን በዚያ አገር ለመመስረት ሲኳትኑ ነበር። ሆኖም ንግርቱን ተግባራዊ ሳያደርጉ ሞቱ። ልጃቸው አፄ ፋሲል ስልጣን ከያዙ ጊዜ ጀምሮ ንግርቱን እውን ለማድረግ ጎ.. ጎርጎራ ጎ.. ጎጃም ጎ.. ጎመንጌ እያሉ በማሠስ ሲጥሩና መቀመጫቸውን ጎመንጌ ላይ አድርገው ሲያስተዳድሩ ከቆዩ በኋላ ትክክለኛውን ቦታ ጎንደርን አገኙ።

ይህ ከመሆኑ በፊት የአፄ ፋሲል በቅሎ የታሠረችበትን ገመድ በጥሣ በመጥፋት የአሁኑ ጎንደር ከተማ ደርሳ ፋሲል ግንብ ከታነፀበት ቦታ ላይ ደርሣ ቦታው ላይ ይፈልቅ ከነበረው ምንጭ ውሃ ጠጥታ እዚያው ቆማ ቀረች።

የንጉሡ አሽከሮች ለፍለጋ ተልከው ከብዙ ድካም በኋላ አገኟትና ወደ ጎመንጌ ቤተመንግስታቸው ወሠዷት። የተገኘችበትን ቦታም ለአፄ ፋሲል ነገሯቸው። ንጉሡም ተገረሙ።

ይህ ከሆነ በኋላም አፄ ፋሲል አውሬ ለማደን ጫካ ሔደው የዱር እንስሳ ሲፈልጉ ጎሽ ያገኛሉ። በጦር ወርውረው ሊወጉት ሲሉም ጎሹ አይታቸው ሸሸ። ንጉሡም ጎሹን ተከትለው በፈረሳቸው ሲጋልቡ በቅሎዋ ውሃ የጠጣችበት ቦታ ላይ ደረሡ። ከምንጩም አንድ መነኩሴ ነበሩና ጎሹ ከመነኩሴው ተጠግቶ ቆመ ይባላል። ንጉሡም ከፈረስ ወርደው መነኩሴውን እጅ ነስተው ሠላምታ አቀረቡላቸው። መነኩሴውም " ወደዚህ ቦታ ለምን መጣህ?" ሲሏቸው "ይህንን ጎሽ ለመውጋት" ብለው መለሡ። መነኩሴውም "ስለ እግዚአብሔር ስትል ማርልኝ። ከኔ ተጠግቶ በመማፀን እንደ ሠው አደራ ብሎኛልና" አሏቸው።

አፄ ፋሲልም "እሺ ይባርኩኝ እንጂ እተዋለሁ። ወደ ቦታየ በሠላም እንድመለስም ይፀልዩልኝ" አሏቸው። ባህታዊው መነኩሴም ባርከውና ፀልየው "በከመ ይደሉ ወይ ቤሎ ብሔረ መንግስት ከሳ ነያ ይእቲ ሀገረ ጎንደር እንታ ታውጋዘ ሐሰስ ወመዓረ። ዘውዕቱ ሠላም ወፍቅር ወበውስቴታ ይትረከብ ብዙኃ መዝገብ ወርቅ ዐብሩር። ዘውዕቱ ትርጓሜ ብሉይ ወሐዲስ። ወይሰማዕ በላዕሊሃ ማህሌተ መላዕክት ዘዓርያም" አሏቸው። ትርጓሜውም " ቤተመንግስትህ ይች ጎንደር ናት። ማር እና ወተት የምታፈስ፣ ሠላምና ፍቅር በውስጧ የሚገኝባት፣ በክርሠ ምድሯም ብዙ የወርቅና የብር መዝገብ ያለባት። ይኸውም ትርጓሜ ብሉያትና ሃዲሳት ማህሌተ መላዕክት የሚሰማባት ናት። የውሐው ምንጭ ባለበት አጠገብ ታላቅ ቤተመንግስት



ታንፃለህ። ዳግመኛም ብዙ አብያተ ክርስትያናትን ትሠራለህ" የሚል ነው። አፄ ፋሲለደስም "ከዚህ ውሃ ከሚፈልቅበት ቦታ ላይ ቤተመንግስት እንዴት ልሰራ እችላለሁ?" አሉ። መነኩሴውም "በትግሬ፣ በአማራ ገዳማት ያሉ መነኮሳት መጥተው ቢፀልዩበት ውሃው ይደርቃል። ከዚያም ልዩ ልዩ መልክ ያለው የከበረ ድንጋይ ታገኛለህ። በዚያ ቤተመንግስትህን ትሰራለህ" አሏቸው።

አፄ ፋሲል ይህንን ሰምተው ደስ እያላቸው ወደ መጡበት ወደ ጎመንጌ ተመለሡ። ከዚያም "ከአዋቂ ጥበበኞች ባህታዊያን የሠማሁት ትንቢት ዛሬ ተፈፀመልኝ" በማለት የቤተመንግስት ማረፊያ የሚሆናቸውን ጎንደርን ማግኘታቸውን ለቤተመንግስቱ ሹማምንት ገለፁ። ለደስታቸው ሲሉም 7 ቀን ግብዣ አድርገው ከዚያም ወደ ጎንደር በመምጣት ድንኳን ተከሉ።

እኒህ ባህታዊ መነኩሴም በኋላ ላይ ሲሞቱ በቤተመንግስቱ አጠገብ በሚገኘው በበዓለ እግዚአብሔር ቤ/ን ነበር የተቀበሩት።

ይህ መሰሉ ክስተት ለዛሬ አንባቢያን ተረትተረት ሊመስለው ይችላል። ሆኖም በእምነት ውስጥ ላለ ሠው ከዚህም በላይ የሆነ ታአምራዊ ክስተት ሊያስገርመው አይችልም።

ይህን ሁኔታ በተመለከተ የ"አዋልድ" መፅሃፍንና ሌሎችን ሰነዶች መሠረት በማድረግ ያሬድ ግርማ ያሰፈረውን ጥቂት ሐተታ እንይ። "እንዲህ አይነቱ መንፈሳዊ ሂደት ኢህአድጋ ለሐገር ዘእንበለ ኢሐዱሔር /ፈጣሪ አገርን ያለ ጠባቂ አይተዋትም/ እንደሚል ወንጌል፣ ቅጠል ለብሰው ዳዋ ጥሰው፣ ድንጋይ ተንተርሠው የሚያድሩ የልዑል እግዚአብሔር ሃይልና መንፈስ ያደረባቸው ለከዋኜ እሳት የበቁ እልፍ አእላፋት የሆኑ ታላላቅ ባህታዊያን በስውር እንደነበሩና እንዳሉ ወደፊትም እንደሚኖሩ ታላላቅ አባቶችና አዋልድ መፅሐፍት ይዘረዝራሉ /ይተርካሉ/ እነኚህ ሁብዕ ባህታዊያን ልክ እንደ እሳት ስለሆኑ ትንኝም ሆነ ማንኛውም ነገሮች አይጠጋቸውም፡፡ በአካለ ስጋ ተከስተው የሚታዩትም በልቡ ደግነት የተሞላበት፣ ፆም፣ ፀሎት፣ ስግደት ያዘወተረ፣ ከዝሙት ተከልሎ ንፅህናውን የጠበቀ፣ ለሰው የማይመቀኝ፣ በሳ አድራጎት ያለውና የልዑል እግዚአብሄርን ፈቃድ ለፈፀመ ተገልጸው ያነጋግሩታል፡፡ እስከ ዘመን ፍፃሜም እንደሚኖሩ ይታመናል" ይለናል፡፡ ከዚያም አፄ ፋሲል ቦታው ላይ ካረፉ በኋላ በአካባቢው ለነበሩ ባለ ርስቶች ለወይኑ እና ለሠይኑ 1,500 ወቄት ወርቅና በደረስጌ መሬት ሰጥተው ቦታውን ተረከቧቸው ፡፡

በፆም በጸሎት የተጠመዱ 24 መነኮሳት ከትግሬ፣ ከአማራ ማለትም ከደብረ ጉንድ ተክለ ሃይማኖት /በለሣ/ ከአዘዞ ተክለሃይማኖት፣ ከደብረ ቢዘን (ባህረ ነጋሽ) ከዋልድባ (ወልቃይት ጠገዴ) ከደብረ አባይ (ሽሬ) ከደብረ ማኅበረ ስላሴ /በመተማ አፋፍ ተንከል በርሃ/ ከደብረ መንዳባ/ ጎርጎራ/ ከደብረ ዳጋ እስጢፋኖስ፣ ከደብረ ናርጋ ስላሴ /ጣና ሐይቅ ደሴት/ ከደብረ ሰደቦ ገዳም፣ ከመልዛ ደብር /ደብረ ታቦር/ ደብረ ሀገዘ አምባ/በለሳ/ ከደብረ ቤተልሄም፣

ከደብረ ሳሊባ /ሮሃ/ አስመጥተው ከሚፈልቀው ውሃ ላይ እንዲጸልዩ አደረጉ፡፡

እነዚህ መነኮሳት 40 ቀንና 40 ሌሊት ከጸለዩ በኋላ ሞልቶ የነበረው ውሃ ምንጩ ደረቀ፡፡ እኒያ ባህታዊ እንደተናገሩትም በውስጡ የከበረ ድንጋይ፣ እብነበረድ፣ ልዩ ልዩ ነገሮች ተገኙ፡፡ አፄ ፋሲልም እጅግ ተደስተው ለመነኮሳቱ የሚገባቸውን ስጦታ ሰጥተው አሰናበቷቸው ፡፡

በአባታቸው ጊዜ የታነፁትን ፅላቶችም ወደዚሁ ቦታ እንዲመጡ አደረጉ፡፡ ከዚያም የተለያዩ የእደጥበብ ባለሙያዎችን የግንብ ስራ፣ የብረታብረት ስራ፣ የአንጥረኝነት ስራ የሚያውቁትን፣ ኖራ አቡኪ፣ ሸክላ ሰሪዎችንና ወዘተ--- ከያሉበት አስጠርተው በማሰባሰብ በቤተመንግስቱ ዙሪያ እዲሰፍሩ አደረጉ፡፡

ስለቤተመንግስቱ አሰራርና ረቂቃዊ ሚስጥሩ የተመለከተውን ታሪክ ከመቀጣላችን በፊት ስለ ጎንደር ስም ስያሜ የሚመለከተውን ታሪክ እናስቀድም፡፡

ስለ ጎንደር ስያሜ የተሰነዘሩ በርካታ መላምቶች ቢኖሩም ተጨባጭነት የሌላቸው የሚመስሉት ይበረክታሉና ዋና ስያሜዋን የገኘችበት ተብሎ የሚታመነውን ብቻ እንይ፡፡ "ጎንደር" የሚለው ቃል መሰረታዊ ምንጩ "ጉንደ ሀገር" ከሚለው የግዕዝ ቃል የተገኘ ሲሆን፤ ትርጉሙም የሃገር ግንድ፣ የሀገር መሰረት፣ርዕሰ ሃገር ወይም የሀገር ራስ ማለት ነው፡፡

ይኸውም የአዲሱ ትውልድ የዓለም አባት የሆነው ፃድቁ ኖኅ ከጥፋት ውሃ በኋላ የተቀመጠባት በእንተላ፣ በአይዋርካ፣ በሸሌ፣ በአይከል በኩል አድርጎ ጎንደር ላይ ብዙ ዘመን ፈጣሪውን እያመሰገነ እየቀደሰ የኖረባትና የተቀበረባት ቦታ በመሆኗ የሃገር መጀመሪያ ዋና ግንድ ተባለች፡፡ በማለት እነዚህን አረፍተ ነገሮች ለማስፈር የተጠቀመባቸውን ምንጮች ያሬድ ግርማ ሲያሰፍር መፅሃፈ ሰዋሰው ወግስ መዝገበ ቃላት ሐዲስ (በአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ) እንዲሁም የእለቃ አያሌው ታምሩን ስለ ግዕዝ ትንታኔ የሠጡበትን ፅሁፍ መሰረት አድርጎ ነው፡፡

አፄ ፋሲለደስ በህንፃ ጥበብ የተካኑ በነበሩት በኢትዮጵያዊው በአባ ገብረክርስቶስ ለሚመራውና ለአማካሪዎቹ ለግብፃዊው ሳዲቅ ናስር፣ ለህንዳዊው አብዱልከሪም እና ለፖርቱጋላውያኖቹ "የኖኅን መርከብ የሚመስል ረጅምና ከፍተኛ የሆነ ህንፃ ስሩልኝ" አሏቸው፡፡

እነርሱም ቀደም ሲል የተሰሩትን የጉዛራውን እና የደንቀዙን ቤተመንግስታት መሰረት በማድረግ ከአማራዎች፣ ከፈላሻዎች፣ ከቅማንትና ከአካባቢው ነዋሪዎች ጋር ተባብረው በኖኅ መርከብ አምሳል ቤተመንግስቱን የማነጽ ስራቸውን ጀመሩ፡፡

ድንጋይ ማያያዣ ኖራ ከእርማጭሆ፣ ከጭልጋና ከኖራ ኢየሱስ፣ ቀይ ሸክላ ድንጋይ ከቁስቋምና ከጅብ ዋሻ፣ እንጨቱን ያምበቃ ከሚባል ቦታ አስመጡ፡፡ አፄ ፋሲል ይህንን ቃል በመለኮታዊ መንፈስ ይናገሩት እንጂ፤ ኖኅ



ሚስቱን እሜቴ አይከልን ይዞ ወደ አገራችን ምድር መጥቶ ለዘመናት እንደቆየ፣ ሚስቱ እሜቴ አይከል ስትሞትበት በጭልጋ ምድር እንደቀበራት፣ በመቃብሯ ላይም ትልቅ ዛፍ በቅሉበት እስከ ዛሬ ድረስ በህገ ልቦና የሚያምኑ የቅማንት ብሔረሰቦች ጸሎት እንደሚያደርሱበት፣ በዚህም የጭልጋ ዋና ከተማ በስሟ አይከል እንደተባለ በኖኅ ታሪክ ውስጥ ያየነው ነው፡፡

‹‹ኖኅም ከሚስቱ ተለይቶ ከኖረ በኋላ በአሁኗ የጎንደር ከተማ ሲሞት በመቃብሩ ላይ ምንጭ ፈልቆ በርካታ ሰዎችን ይፈውስ ነበር፡፡ ሆኖም ፈጣሪ ለኖኅ መታሰቢያ ይሆን ዘንድ በቤተመንግስት አሳቦ የኖኅ መቃብር ሐውልት እንዲታነፅ ፈቀደ፡፡" ( የጎንደር ታሪክ 1999 ዓ.ም ) ስለዚህም በሚያምርና በሚያስደንቅ መልኩ የቤተመንግስቱ ታላቅ መሰረት ተጣለ፡፡ ሆኖም ግን 3 ጊዜ ከስሩ ተመንግሎ ታላቅ አወዳደቅ ወደቀ፡፡ በዚህም በጎንደር ከተማ ከፍተኛ ሃዘንና ለቅሶ ሲሆን አፄ ፋሲልም በጣም አዝነው ፈጣሪያቸውን ለመለመን ሱባዔ ገቡ፡፡

በጸሎት ላይ ሳሉም በደብረ አባይ ገዳም የሚኖሩ አባ ተስፋ ማርያም የተባሉ ባህታዊ መነኩሴ መጡና "ቤተመንግስትህ ይጸናልህ ዘንድ አስቀድመህ በቅዱስ ሚካኤል ስም በምዕራብ በኩል ቤተክርስቲያን ስራ ብለው አዘዟቸው፡፡

በታዘዙት መሰረትም ቤተክርስቲያን ሰሩ፡፡ በውስጡም 24 ካህናትና ሊቀ ዲያቆናትን መደቡ፡፡ ርስት ይሆናቸው ዘንድ በደንቢያ ምድር አዳጊ የተባለች ቦታ፣ ጉራምባ ሚካኤልና ደስማርያምን ሰጧቸው፡፡

ለሁለተኛ ጊዜም በአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ስም ሰራ፡፡ ሲኗቸው እንደታዘዙት አደረጉ፡፡ 24 ካህናትና ሊቀ ዲያቆናትንም እንዲያገለግሉ አድርገው በተመሳሳይ ዘንጋጅ ቡተባለ ቦታ ርስት ሰጧቸው፡፡

ከዚህ በኋላ አፄ ፋሲል ቤተመንግስቱን እንደ አዲስ ማሳነጽ ጀመሩ፡፡ ማዕዘኑንም በግብረ ግንፋል (በጥሩ ኖራ) ሲሰሩ እየተስተካከለና እያደገ ሔደ፡፡ በዚህ መሰሉ ሂደት በሌላው ዓለም መሠል የሌለው ውብና ማራኪ ቤተመንግስት በሚያስደንቅ ሁኔታ አሳነፁ፡፡ አፄ ፋሲል ስልጣን ከያዙ ከ6 ወይም ከ7 ዓመት በኋላ ማሳነፅ የጀመሩት ይህ ቤተመንግስት /ፋሲል ግንብ/ ግንባታው ተጠናቆ፣ የውጭና የውስጥ ቅርፁ የኖኅን መርከብ መስሎ፣ ቁመቱም 32 ሜትር ሆነ፡፡ ፋሲል ግንብና የኖኅ መርከብ በስፋት፣ በርዝመት፣ በወርድ፣ በቅርፅ፣ በመልክ፣ በውጫዊና በውስጣዊ አሰራሩ... በአጠቃላይ መርከቡን መስሎ ነው የተሰራው፡፡ ግንቡ በከተማው እማካይ ቦታ ላይ በመሆኑ በሰሜን የወገራና የእርማጭሆን፣ በደቡብ ደምቢያን፤ በምስራቅ የበለሳን ምድር አሻግሮ ለመመልከት የሚያስችል ሆነ፡፡

የውስጥ ይዘቱን በተመለከተም ምድር ቤቱ ታላላቅ አዳራሾችን ጨምሮ ከ20 ክፍሎች በላይ ሲኖሩት፤ በመጀመሪያው ፎቅ መግቢያ ህዝባዊ ጉዳዮችን የሚያከናውኑበት፤ የወንዶችና የሴቶች የግብር ማብያ ክፍሎች ሲኖሩት፤ ለብርሀን መስጫ የሚሆን እሳት ማንደጃና (ጭሱ ውስጥ ለውስጥ

ኬዶ ወደ ላይ ይወጣል) የተንዲል መስቀመጫዎች አሉት። ሁለተኛው ፎቅ የቄሶች መወረቢያ፣ የታቦት ማስቀመጫና የራሳቸው ማረፊያ፤ እንዲሁም በዘውድ ቅርፅ በተሰራው ቦታ ቆመው በህዝብ ፊት ንግግር የሚያደርጉበት ነበር።

በዚህ ፎቅ ዙሪያ በአራቱም ማዕዘን የፀሎት ቤቶች ሲኖሩ በየመስኮታቸው በከተማው ያሉትን አድባራት በግልፅ ያሳያሉ።

3ኛው ፎቅ የንጉሰንገስቱ ክፍል ሲሆን፤ 4ኛው የቤተመንግስቱ ሰገነት ነው። ከዚህም በላይ ለልዩ ልዩ ግልጋሎት የሚውሉ ክፍሎች የተካተቱበት አስደናቂ ቤተመንግስት ሆነ።

አፄ ፋሲል የንጉሰነገስት ዙፋን አስቀምጠው በየመስኮቶቹና በየክፍሎቹ ደማቅና አንፀባራቂ የሆኑ የሀር መጋረጃዎች ዘረጉ ለማቋረጥ ብርሐን ሰጭ መብራቶች እንዲበሩም አደረጉ። ስለዚህ ቤተመንግስት አካላዊ ቅርፅ አስመልክቶ አቶ ገሪማ ታፈረ የተባሉ ፀሃፍት ባልታተመው "ጎንደርና ነገስታቷ" በሚለው ጽሁፋቸው ሲገልጹ፦ "የዚህን ቤተመንግስት አቋም በተመለከተ የአገሪቱ (ኢትዮጵያ) ጥንታዊያን ደራሲያን ስሜታቸውን ሲገልፁ በኖህ መርከብ እየመሰሉ ተርከዋል፤ በምሳሌያቸውም የተገኘው ፍሬ ነገር እንዲህ የሚል ነበር፦

1. የግንቡ ምድር ቤት ግዙፋን አራዊት የነበሩበት፣
2. ከመጀመሪያው ፎቅ በስተሰሜን ያለው ክፍል የኖኅ ወንዶች ልጆች የነበሩበት፣
3. በስተደቡብ ያለው ክፍል ሴቶች ልጆች የኖሩበት ሲሆን፤ በመካከሉም አራሱ ኖኅ ከነሚስቱ የነበረበትን ክፍል ተመልክቶ የተነደፈ ነው።
4. ከአንደኛው ፎቅ ወደ ላይ ፤ ከሁለተኛው ፎቅ ወደ ታች ባለው ህንፃ ወገብ ዙሮ የገጠመው የግንብ ቀፀላ በኑሄ ሞትሊዋታን እየተባሉ የሚጠሩት ዓለምን ዞረው የገጠሙት አራዊት (ዘንዶዎች) ምሳሌ ነው።
5. ከሁለተኛው ፎቅ መካከል ያለው ኮርቻ ግንብ ኖኅ አቅመ አዳምን አስቀምጦበት ለነበረው ክፍል ምሳሌ ነው።
6. ከሁለተኛው ፎቅ መካከል ያለው ኮርቻ ግንብ ኖኅ አቅመ አዳምን አስቀምጦበት ለነበረው ክፍል ምሳሌ ነው።
7. በዚህ ክፍል ወደ ምዕራብ ከ3ኛው ፎቅ ተያይዞ የሚታየው ህንፃ የአንበሳ ምሳሌ ነው። የአንበሳው ግራ ቀኝ ጆሮዎች ቀጥ ብለው፤ ከራሱ ላይ ዘውድ ጭኖ፣ አይኖቹን አፍጥጦ ወደ ምዕራብ እየተመለከተ የሚያጉረጠርጥ ይመስላል።
8. በ3ኛውና በ4ኛው ፎቅ ቀሲሳን እና ረቂቃን ፍጡራን ለነበሩበት ክፍል ምሳሌ ሆኖታል። ባጠቃላይ የቤተመንግስቱ አሰራር የኖኅን መርከብ ይመስላል።



ግንቡ ተሰርቶ ሲያልቅ ከወርቅ የተሰራ መንበረ ዳዊት አስቀመጡበት። እንዲሁም በየክፍሉና በየመስኮቶቹ የሚታጠል እሳት የመሰለ የሀር መጋረጃ ዘረጋበት" በማለት ገልጸውታል።

አፄ ፋሲል ግንባታው ከተጠናቀቀ በኋላ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አደባባይ ኢየሱስን አሰርተው 32 ካህናት መደቡ። ቀጥሎም በቅድስት ማርያም ስም ግምጃ ቤት ማርያምን አሰሩና 32 ካህናት እንዲያገለግሉ አደረጉ። ከዚያም በቅዱስ ጊዮርጊስ ስም እልፍኝ ጊዮርጊስን አሰርተው 24 ካህናት እንዲያገለግሉ ሲያደርጉ፤ እንደገናም የመድሀኒያለምንና የቅዱስ ገብርኤልን ቤ/ያ አሰርተውና አገልጋዮችን መድበው ለሁሉም ርስትና ጉልት ከየአውራጃው እየመረጡ ሰጧቸው፤

ከላይ ከተጠቀሱት አብያተ ክርስቲያናት ውስጥም ገብርኤልና መድሃኒአለም ከቤተመንግስቱ ጥቂት ራቅ ብለው ሲገኙ ሌሎች በአሁኑ ሰአት የሚገኙት በፋሲል ግንብ ዙሪያ ነው።

ከዚህ በኋላም አፄ ፋሲል ከቤተመንግስቱ አጠገብ ለቤመዛግብት የሚሆን ባለ 2 ፎቅ ህንፃ አስገነቡተዋል፤ ይህም ወረቀት ግንብ በመባል የሚታወቅ ሲሆን፤ እንደ አቶ ገሪማ ታፈረ አነላለፅ ወረቀት ግንብ ማለት የፅህፈት ሚኒስትሩ ወይም የፀሃፌ ትዕዛዙ ስራውን የሚያከናውንበት ቤተመዘክር ነው። እንዲሁም ምድር ቤቱ ግምጃ ቤት ስለሆነ ለቤተመንግስቱ በጅሮንድ አገልግሎት አበርክቷል። ይላሉ።

በዚህ ቤተመዛግብት መንፈሳዊ መፃህፍት የመጻፍ፣ የማርቀቅና የመተርጎም ስራዎች ሲሰሩበት፤ ልዩ ልዩ መፅሐፍት እየተዛፉም ለአድባራትና ገዳማት ይሰራጩ ነበር። በቤተመንግስት ደረጃ ይህን መሰሉ ቤተመዛግብት በዘመናዊ መልክ የተቋቋመውም ለመጀመሪያ ጊዜ በአፄ ፋሲለደስ ዘመን መሆኑ ነው።

የቤተመንግስቱን ቅጥርም በተመሳሳይ የግንባታ ግብዓቶች በማሰራት 12 በሮች እንዲኖሩት አደረጉ። እነዚህ በሮች የቤተመንግስቱ ሹማምንት በየወገናቸው የሚወጡበት የሚገቡበት ሲሆን፤ የ12 ቱ በሮች ስም ደግሞ በሚከተለው መልኩ ይዘረዘራሉ።

1. ፊት በር /ጃንተከል በር/፦ ንጉስ ነገስቱ የሚወጡበትና የሚገቡበት፣
2. ወንበር በር፦ የንጉሱ የቅርብ አማካሪዎች የሚወጡበትና የሚገቡበት፣
3. አዛዥ ጥቁሬ በር፦ የጦር አዝጋጅና የአገር ግዛት ሹሞች ከነሰራዊታቸው የሚወጡበት የሚገቡበት፣
4. እቃ ግምጃ ቤት በር፦ ማንኛውም የቤተመንግስቱ እቃ የሚወጣ የሚገባበት በር፣
5. ቀጭን አሸዋበር፦ ለህንፃዎችም ሆነ በግቢው ውስጥ ለሚገነቡ ግንባታዎች አሸዋ በፈረስ ተጭኖ የሚገባበት፣
6. ፈረስ ባልደራስ በር፦ ነጋዴዎች በፈረስ እቃ ጭነው የሚገቡ የሚወጡበት፣

7. እምቢልታ በር፡- ሹመት ሽልማት ሲሰጥ እምቢልታ እያስነፉ የሚገቡ የሚወጡበት፣
8. ኳሊበር፡- ሴት ወይዛዝርት እየኳኳሉ ፣ እየተቆነጃጁ የሚወጡበትና የሚገቡበት፣
9. እንኮዬ በር ፡- የእንኮይ ዛፍ በበሩ አካባቢ ስለነበረች? (እንኮይ በተባሉ ቆንጆ ሴት የተሰየመ)፣
10. ተዝካሮ በር፡- የነጋሲያን ዘር ሲሞቱና ተዝካራቸው ሲወጣ ታዳሚዎች የሚወጡ የሚገቡበት፣
11. አደናግር በር፡- ድንገተኛ ግርግር ሲነሳ ሰዎች የሚወጡ የሚገቡበት፣
12. ርግብ በር፡- (የዋሃን) ደናግላን የሚገቡበት የሚወጡበት ናቸው።

በእያንዳንዱ በር ላይም በደንብ የሰለጠኑ ወታደሮች ተመድበው ያለንጉሱ ትዕዛዝ ማንም እንዳይገባ የሚያግዱ ሆነው እንዲቆሙ ተደረገ።

በዚህ ቤተመንግስት ከንጉሰነገስቱ ጋር አብረው የሚያስተዳድሩ 12 ከፍተኛ ባለስልጣናት የነበሩ ሲሆን 4 አለቆች (ሊቃውንት) 4 ወንበሮች (ፍትሀነገስት ገልጠው የሚዳኙ) 4 አዛገች 1ኛ የወልቃይት አዛዥ ፣ 2ኛ የፋርጣ አዛዥ 3ኛ የደምቢያ አዛዥ 4ኛ የአገው ምድር አዛዥ ሆነው በቤተመንግስቱ ተሾመው ነበር።

ከዚህ በኋላ አጼ ፋሲል ቀጣይ ሥራ ያደረጉት በዚሁ ቤተመንግስት አምሳል የተሠራውንና ዛሬ ድረስ የቱሪስት መናህሪያ የሆነውን ህንፃ ማሰራት ነበር። በቀሐ ወንዝ አጠገብ ያስገነቡት ይህ ህንፃ ማንኪት ይባላል፡ ከህንፃው ስር የተሰራው ሰፊው የመዋኛ ገንዳ ዛሬ ድረስ የጥምቀት በኣል የሚከበርበት ሲሆን፣ አፄ ፋሲል ቦታውን ካሰሩት በኋላ ከቀሃ ወንዝ ውሃ ተጠልፎ እንዲገባ በማድረግ የነገስታት ልጆች ዋና እንዲማሩበትና በጥምቀት በዓል ለመጠመቂያነት እንዲያገለግል ያሰሩት ነው። የጥምቀት በዓል ከሌሎች የኢትዮጵያ ግዛቶች የበለጠ አጅግ ደምቆ ሲከበር የሚታየው በጎንደር ሲሆን፣ ታቦታቱ ወጥተው በአንድ ላይ የሚያድሩትም በዚሁ በፋሲለደስ ህንፃ ነው። ነገሥታትም ውበቱን ለመግለጽ ቃላት ያጥራቸዋል።

አፄ ፋሲለደስ እነዚህን ሁሉ ስራዎች ከሰሩ በኋላ አምላካቸውን አመሰገኑ። ተንበርክከው ሲያመሰግኑና ሲጸልዩም የፀለዩበት ቦታ በብርሐን ተሞላ። ብርሐኑን ባዩት ጊዜም እጅግ ደስ አላቸው። ደስታቸውንም መላው ህዝብና የቤተክህነት ሰዎች እንዲሁም ሹማምንቱ የታደሙበት የ7 ቀናት ግብዣ አደረጉ።ከስነ ህንፃ ግንባታዎች ጎን ለጎንም ታላቅ ንጉሰነገስት የሚያሰኛቸውን ተግባራት አከናውነዋል።

አፄ ፋሲል ከነገሱበት ጊዜ ጀምሮ ከአውሮፓውያን ጋር የነበረውን ግንኙነት አቋርጠው ነበር። ሆኖም የፖርቱጋል ፣ የስፔን እና የሮማ ካቶሊክ ጳጳሳት ህልማቸው እውን ሳይሆን በመቅረቱ ተበሳጭተው በኢትዮጵያ መንግስት ላይ ባልታሰበ ጊዜ ችግር ሊፈጥሩ እንደሚችሉ በማሰብ የአባቶቻቸው ጠላት ከነበረው ከቱርክ ፓሻ ጋር ግንኙነት መሰረቱ።



እንደዚሁም ወደ የመን ተሻልክው ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ጀመሩ። ከቱርኩ ፓሻ ጋር የወዳጅነት ስምምነት ካደረጉ በኋላም በስምምነታቸው ውስጥ ንጉሱ ያልፈቀዱለትን የውጭ አገር ሰው በምፅዋ ወደብ በኩል ሳያስገባ ቃላ ገባላቸው ። ከዚህም በላይ በስምምነቱ አማካይነት በወደብ በኩል ከውጭ አገራት ወርቅ የዝሆን ጥርስ፣ ቆዳናሌጦ፣ የእርሻ ውጤቶችንና ሌሎችንም እያቀረቡ የንግድ ልውውጦችን ማካሔድ ጀመሩ።

ሚሲዮኖችም ተደጋጋሚ ሙከራቸውን ቀጠሉ። ሆኖም በቱርኩ ፓሻ እየተያዙ ይታሰሩ ይገደሉ ነበርና የምፅዋውን ወደብ ትተው በሱማሊያ በኩል ለመግባት ሲሞክሩም ተመሳሳይ እጣ በአካባቢው ነዋሪዎች ይገጥማቸው ነበር። የአገር ውስጥ ጥቂት ባላባቶች ሲሸፍቱባቸውም በየጊዜው አመጹን እያፈራረሁ በቁጥጥራቸው ስር አድርገዋል።

አፄ ፋሲል የኢትዮጵያ ግዛታቸውን ካደላደሉ በኋላም በኢትዮጵያ ምዕራብ በኩል ያለውን የሱዳን ግዛት የሆነውን ሰናርን ከድንበራቸው አልፈው ሔደው ለማስገበር ችለዋል። እንደራሴያቸውን ንጉስ ጊዮርጊስን በሚያስገብሩት አገር ላይ ሾመውት ተመልሰዋል።ሱዳንን ማስገበራቸውን በተመለከተም አዝማሪ እንዲህ ተቀኝቶላቸው ነበር።

“ጎንደር ቢያትረመርም ፋሲል ፈረስህ፣
ኑብያና ሰናር ወርቁን ጫኑልህ።
ሳሩን ተጠየፈ የፋሲል ፈረሱ፣
ከምር የሱዳን ወርቅ ገፈራው ነው ለሱ።”

ቀደም ባለው በአፄ ሱስኒዮስ ጊዜ ሱስኒዮስ ክሮማ ከተማ ያስመጧቸው ሮማዊት ዘሊያን እና ሊንዳ የሚባሉ ሁለት ቆንጆ ሴቶች ነበሩ። ዘሊያን የአፄ ሱስኒዮስ እጮኛ ነበረች። እነዚህ ሴቶች እህትማማቾች ናቸው። ዘሊያንን አፄ ፋሲል አግብተዋት ነበር። ከዚያም እህቷን ሊንዳንም በጭን ገረድነት /በእቁባትነት/ አብረው ስለተጠቀሙ “ዋርሳ አታርክሱ ድንበር አታፍርሱ” የሚለውን የአበው ብሒል ሳቱ ተብሎ ብዙ ጭቅጭቅ ተፈጠረ። በቤተመንግስቱ ዙሪያ ያሉት ሊቃውንትም አጼ ፋሲል ሊንዳን ጨምረው መያዛቸውን ሲሰሙ ታላቅ ሃዘን አደረባቸው።

የደብረ ሞጊና መነኮሳት ይህንን ነገር ሲሰሙ ወደ አፄ ፋሲል ሔደው “ከአንድ እናት ከአንድ አባት የተወለዱትን እንዴት አገባሃቸው?” ብለው ጠየቋቸው። ቀጥሎም “ንስሐ ግባ ከስንፍናህ ተመለስ” አሏቸው። አጼ ፋሲልም ከደብረ ሞጊና የመጡትን የእነዚህን መነኮሳት ውግዘት በመናቅ አጣጣሉት።

በተከታታይም ሁለቱን እህታማቾች እንዳያገቡ ደጋግመው አወገዟቸው በዚህ ጊዜ አፄ ፋሲል በጣም ተቆጥተው ጃዊ የተባለ የቅርብ ባለቤታቸውን አዘው አንገታቸውን በሰይፍ አስቀሏቸው።
ጭንቅላታቸውን በቤተመንግስቱ በስተሰሜን በኩል ባለው በር፣ ካንገት በታች ያለውን አካላቸውን በደቡብ በኩል ባለው በር አስጣሉት።

ይህ የሚሆነኤ ተግባራቸው በመላው ኢትዮጵያ ባሉት ግዛቶች ተሰማ። ሁኔታው የበለጠ ተባባሰና ዳግመኛም ሌሎች በርካታ መነኮሳት መጥተው ንጉስ ነገስቱን በፅኑ አወገዟቸው።

እነሱንም እንደፊተኞቹ በሰይፍ አስገደሏቸው። ደማቸውም እንደ ጎርፍ ሆነ። በዚያን ጊዜ ታላቅ የመሬት መናወጥ በአካባቢው እንደደረሰ ይነገራል። መነኮሳት ወደ ቤተመንግስቱ እንዳይገቡ ጠባቂ ቢቀመጥም ቆባቸውን እያወለቁ ተደብቀው በመግባት ንጉሱን ሲያወግዙ ራሳቸውን ለሰለት አሳልፈው በመስጠት ሰማዕትነት ተቀበሉ።

በርካቶች ከሞቱ በኋላ አንድ ባህታዊ መነኩሴ መጥቶ ተመሳሳይ ግዝቱን ሲያሰማ "ይህን መነኩሴ ወደ ውጭ አውጡልኝ" ሲሉ ጠባቂዎች እየደበደቡ ሲያስወጡት በድብደባው ብዛት ሲወድቅ በወገቡ ስለት ያለው ነገር ዙሪያውን ታጥቆ ነበርና አካሉ ከሁለት ተቆረጠ። አፄ ፋሲለደስ በመነኩሴው ላይ የሆነውን ነገር ሲያዩ ደነገጡ እጅግም ፈሩ።

ወዲያውም ታላቅ ለቅሶ አለቀሱ። የተቀደሱ መነኮሳትን ስላስገደሉም ተጸጸቱ።ከዚያም የመነኮሳቱ በድን ወደተጣለበት ፈጥነው ሄዱና በጥሩ ልብስ ተገንዘው እንዲቀበሩ አስደረጉ።

በፋሲል ግንብ አጠገብ በቖንተክል ዋርካና በአደባባይ ኢየሱስ ቤተክርስቲያን መካከል ባለው ቦታ በአዲስ መቃብር ተቀበሩ። ይህ ቦታ ዛሬ ድረስ በጎንደር ህዝብ ዘንድ ቅዱስ ቦታ ተብሎ ስለሚታመን ምዕመናን እዚሁ ቦታ እየቆሙ ይጸልዩበታል።

አጼ ፋሲል ያስገደሏቸውን የመነኮሳት ብዛት ጥቂቶች 9999 እንደሆኑ ይታመናል ሲሉ፤ ሌሎች ዝቅ ያደርጉታል። አጼ ፋሲል በጣም ከተፀፀቱ በኋላ በሌሊት ብቻቸውን ወደ ደብረ ሞጊና ገዳም ሄዱ። 3 ቀን ተጉዘው እንደደረሱ በገዳሙ ያሉትን ቅዱሳን አባቶች "እንደደቅርታችሁ መጠን ይቅር ባሉኝ፣ ማሩኝ" አሏቸው። ቀጥለውም "የበዛየውን የፊተኛውን ሃጢያት በመነኮሳቱ ላይ የፈጸምኩትን በደል ሁሉ ይቅር በሉኝ ነብሴን ከስቃይ የሚያድናት መድሀኒት ፈልጉልኝ" በማለት ተማጸኑ።

አንድ መነኩሴ "ለነብስህ ደህንነትን ከፈለግህ በዋሻ፣ በተራራው፣ በጉድጓዱ በየቦታው ዙር" በማለት መለሱላቸው።

አፄ ፋሲልም እንደተነገራቸው በየቦታው ተዘዋውረው ምንም ሳያገኙ ቀሩ። ከዚያም ባህርን በእሳት ያቃጠሉ ከሚባሉት ከአቡነ ፊሊጶስ ገዳም ከሆነቸው ከደብረቢዘን ገዳም ሄዱ እዚያም ደርሰው ተመሳሳይ ተማዕኖዋቸውን አቀረቡ።

ያገኙትም ምላሽ "ንጉስነገስት ሆይ ወደ ቤተመንግስትህ በሰላም ተመለስ፤ የፍየል ሌጦ የምትለብስ ስሟ ፍኖተ ህይወት የተባለች አካሏ የነጣ አንዲት መበለት በዚያ ታገኛለህ። እሷ ነብስህ የምትድንበትን ነገር ትነግርሃለች" የሚል ነበር።



ይቺ መበለት ከጥዋት እስከ ማታ የቤተመንግስቱን ስራ ከሚሰሩት ሴቶች ጋር ሆና እየሰራች የምትውልና ደሞዟን ተቀብላ ለድሆች እየሰጠች ሌሊት ደግሞ ወንዝ ውስጥ ስትፀልይ የምታድር ናት።

አፄ ፋሲልም ከ3 ቀን በኋላ ወደ ቤተመንግስታቸው ተመልሰው አካሏ የነጣ መበለት እያሉ ይፈልጉ ያፈላልጉ ጀመር። ከብዙ ፍለጋ በኋላም አገኙዋት።

ፈጥነው እግሯ ስር በመውደቅ "በልዑል እግዚአብሄር ስም ይገፈሻለሁ። አንቺ እውነተኛ የእግዚአብሄር አገልጋይ ሆይ ነብሴ የምትድንበትን ነገር በልዑል እግዚአብሄር ስም አደራ እልሻለሁ! በስላሴ ስም አማጽንሻለሁ ንገሪኝ" አሏትና ስራቸውን ሁሉ ነገሯት። ያቺ መበለትም " በመንግስትህ/በግዛትህ/ ሁሉ በየወንዞቹ ላይ መሸጋገሪያ ድልድይ ስራ፤ በዚህ ነገር ልዑል እግዚአብሄር ሃጢያትህን ሁሉ አስተሰርዮ ይቅር ይልሃል። ህዝቡም ሁሉ በክረምትም ሆነ በበጋ ሁል ጊዜ በተሻገሩ ቁጥር ጌታ ሆይ የንጉስነገስቱን ሐጢያት ይቅር በለው እያሉ ይፀልዩልሀልና" አለቻቸው።

አፄ ፋሲለደስም ይሄን ቃል ሲሰሙ እጅግ ተደሰቱ፤ በሚገዙት ግዛትም በወንዞች ላይ ድልድይ አሰሩ።

ከእነዚህም ውስጥ በአንገረብ፣ በመገጭ፣ በትክል ድንጋይ (ባምብሎ) ቆራጣ ድልድይ በአንገረብና በቀሃ ወንዞች መገናኛ (ጎባጢት) እንዲሁም በአባታቸው ጊዜ በአንድ አቅጣጫ ብቻ የነበረውን ብቸኛ የአባይ ድልድይ እንዳለ ሆኖ የአባይን ድልድይ አንዱን በአፈረ ዋናት በኩል አንዱን በእንዳ ቤት በኩል ያሰሩት ድልድይ ይገኙበታል። ባጠቃላይ ያንን የመሰለ ግፍ ከፈጸሙበት ከ1648 ዓ.ም ጀምሮ በነበሩት ተከታታይ አመታት አስከፍፃሜያቸው ድረስ በርካታ ድልድዮችን አሰርተዋል

ህዝቡም ድልድዮች በተሻገረ ቁጥር "የፋሲልን ነፍስ ይማር" እያለ ይሻገር ነበር። ዋና ዋናና ታላላቅ ድልድዮችን ዛሬ ድረስ ግልጋሎት እየሰጡ ሲሆን፤ ከመካከለኛና ጥቃቅን ድልድዮች ውስጥ ጥቂቱ ዛሬ ድረስ ፈራርሰው ይታያሉ።


ከዚህ በኋላ አፄ ፋሲል በጳጳሱ በአቡነ ክርስቶስ አማካኝነት ከውግዘቱ ሁሉ ተፈቱ። ከዚያም በነገሱ በ35 አመታቸው በተወለዱ በ78 አመታቸው መስከረም 15 ቀን በ1659 ዓ.ም አረፉ። አፄ ፋሲል ካረፉ በኋላም ብጥብጥ እንዳይነሳ በሚል ስጋት እረፍታቸው ተደብቆ በበላቴን ጌታ መልዓከ ክርስቶስ ትዕዛዝ የነጋሲ ዘሮች እንዲታሰሩ ተደረገ። ከዚያም ጥቅምት 10 ቀን በሰሉተ ማክሰኞ ማለዳ ላይ ዳግማዊት ደብረ ሊባኖስ ተብሎ በሚጠራው በአዘዞ ተክለሃይማኖት የቀብር ስነ-ስርዓታቸው ተፈጸመ። አፅማቸው በኋላ ላይ ከዚያ ወጥቶ በጣና ሐይቅ ዳጋ እስጢፋኖስ ገዳም በክብር ተቀመጠ።

አፄ ፋሲል ከእቴጌ እህተጊዮርጊስ ዛድቁ ዮሃንስን፣ ከእቴጌ ዘሊያን ወንጌላዊትን፣ ከወይዘሮ አመተ ድንግል ራስ አንስጣቴዎስንና ሌሎች ልጆችን ወልደዋል።


የአፄ ፋሲልን ታሪክ እና በዘመናቸው በኢትዮጵያ ምድር የተፈፀመውን ታሪካዊ ክንውን ያየንበትን ምዕራፍ ከመደምደማችን በፊትም ባሰሯቸው ድልድዮች ምክንያት በዘመኑ ዘፋኝ የተዜመላቸውን ዜማ ግጥሙን ለታሪኩ መደምደሚያ እንጠቀምበት።

"ርብ እና አባይ መንጠቅ የለመዱ
እንደልማዳቸው ሰውን እንዳይጎዱ
በፋሲል ዳኝነት ተፈጥመው ሔዱ፤
ርብና አባይ ሽፍተው ሲኖሩ
አላፊ አግዳሚውን ከጎራ እያሰሩ
በትላልቅ ድንጋይ ተደብድበው ቀሩ።"

በተባበሩት መንግስታት የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል ድርጅት እ.ኤ.አ በ1959 ዓ.ም ባወጣው ዓለም አቀፍ የትርሶች ጥናት ጥበቃና ህግ መሰረት የጎንደር ግንብ እ.ኤ.አ በ1980 ዓ.ም በዩኔስኮ ቅርስነት ሊመዘገብ ችሏል። በተጨማሪም ፋሲል ግንብ የበርካታ ቱሪስቶች መናኸሪያ ሆኖ ራሱን የቻለ አገራዊ ጥቅም ከማስገኘቱ ጎን ለጎን የአፄ ፋሲልን ታሪክ እየዘከረ ይገኛል።









## ምዕራፍ ፴፬

## የአፄ ዮሐንስ 1ኛ ዘመነ መንግስት

## ከ 1659-1674 ዓ.ም

አፄ ዮሐንስ በሚለው መጠሪያ ስም ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ የነገሡት እኒሁ የአፄ ፋሲል ልጅ የሆኑት ናቸው።

የአፄ ፋሲል እረፍት ለህዝብ ሳይጠጣ እስከ ልጃቸው ንግስና ድረስ ተደብቆ ነበር። ይህውም በዙፋን ምክንያት አመፅ እንዳይቀሰቀስ ተሰግቶ የተደረገ ነበር። የአፄ ፋሲል ታማኝ የነበረው ብላቴን ጌታ መልዓከ ክርስቶስ ብዙዎችን አሣምኖ ያኔ የነገስታቱ ዘር ታጉረው ከሚኖሩበት አምባ ዮሃንስን በማስመጣት እንዲነግሡ አደረጓቸው።

በዚያው ጊዜም ሹማምንቱ ወደ አደባባይ በመውጣት "ንጉሣችን አፄ ፋሲለደስ አርፈዋል። ልጃቸውን ዮሃንስን አንግሰናል። የሞትንም እኛ ያሰነም እኛ። ጠላታችን ይዘን፤ ወዳጃችን ደስ ይበለው" ተብሎ በነጋሪት አዋጅ ተገለፀ። ከዚህ በኋላ ስለሟቹ ንጉሥ ሐዘን፣ ስለ ነጋሚውም ክብረ በዓል በይፋ ተደረገ። አፄ ዮሃንስ1ኛ በ1659 ዓ.ም የንግስና ስማቸውን "አእላፍ ሰገድ" አሠኝተው የአባታቸውን መንግስት ይዘው ስራቸውን ማካሄድ ጀመሩ።

የመጀመሪያ ስራቸው ያደረጉትም የነገስታቱ ልጆች ብቻ በወህኒ አምባ እንደከዚህ ቀደሙ ባሉበት እንዲቆዩ አድርገው፤ ለቀሪው መሳፍንት እስረኛ ሁሉ ሙሉ ምህረት ማድረግን ነበር። ይህም ወዲያው ተግባራዊ ሆነ።

አፄ ዮሃንስ 1ኛ ለንግስና የተመረጡበት ምክንያት ከልጅነታቸው ጀምሮ መንፈሳዊ ትምህርት ላይ ያተኮሩና ለጸሎ አዛኝ መሆናቸውን በደንብ ይታወቅ ስለነበር ነው። በዚያው በነገሡበት አመትም "የፍቅር አደራሽ"ተብሎ የሚጠራ ቤተመንግስት በቀድሞው ቤተመንግስት ጊቢ ውስጥ አሳነፁ።

ለእንደራሴያቸው ለመላእከ ክርስቶስም የርዕሠ መኳንንትነት ሙሉ ስልጣን ሠጡት። በወህኒ አምባ በለመዱት ስራቸው ስሌን እየሠሩ ለድሆች በነፃ ይሠጣሉ።በርካታ መንፈሳዊ ተግባራትን መከወንም የእለት ተለት ተግባራቸው አደረጉ። እጅግ ደግ ከመሆናቸው የተነሣ "ፃድቁ ዮሃንስ" በሚል መጠሪያቸው ነበር የሚታወቁት። አፄ ዮሃንስ በዘመናቸው ከፈፀሟቸው ተግባራት ውስጥም የተለያዩ ነገዶችን ለየግላቸው መንደራቸውን ለይተው በየራሣቸው ባህል፣ ወግ እና ልማድ እንዲኖሩ ማድረጋቸው ይጠቀሣል።

የውጭ አገር ዜጎችን በተመለከተም በኢትዮጵያውያን ወግ እና ባህል፤ እንዲሁም ሃይማኖት ስር ሆነው መኖር የሚፈልጉትን በነፃነት



መኖር እንዲችሉ በመግለፅና በዚህ ካልተስማሙ ግን ሁሉም ወደየመጡበት አገራቸው እንዲመለሱ አውጀዋል።

ይህን መሠሉ አዋጅ ሲታወጅ በኢትዮጵያ ምድር የነበሩ የውጭ ዜጎች በአሪንጎ ሰፍረው ይኖሩ ነበር። ወደ አገራቸው ሳይሄዱ በያሉበት የነበሩትም ይገድሉናል ብለው ፈርተው ነበር። ወዲያውም "ሲይዙን የመጡ እንደሆነ ሳንወጋ እጃችንን አንሠጥም ብለዋል" የሚል ወሬ በቤተመንግስቱ ተሰማ።

ስለዚህ ንግግር አዋቂና የዲፕሎማሲ ሰው ግራዝማች ሚካኤል ነው፤ ተባለና ተመረጦ ፈረንጆቹ ወዳሉበት ሄዶ የንጉሡን ትዕዛዝ አስረዳቸው። "በቆላ ወይም በደጋ በፈለጋችሁት በኩል ወደ አገራችሁ እንድትመለሱ ታዟችኋል" ሲባሉ እነሱም "በቆላ በኩል አድርገን በሰናር በኩል ተጉዘን ወደ አገራችን እንገባለን" የሚል ምላሽ ሠጡ። በዚህ ተስማምተው እነርሡ ከአሪንጎ ወደ ሰናር/ ሱዳን ሲጓዙ ግራዝማች ከአሪንጎ ወደ ጎንደር ተመለሠ።

ከአፄ ፋሲልና ከእቴጌ እህተክርስቶስ የተወለዱት አፄ ዮሃንስ 1ኛ በዘመናቸው በአባታቸው ጊዜ ይሸፍቱ የነበሩትን የሻንቅላ፣ የሀንጋዝ፣ የባንጋ፣ የዋጅራት ነገዶችን አመፅ አስተናግደዋል።

በየክፍሉ እንደራሴያቸውን መልዓከ ክርስቶስን፣ የጦር አለቃቸውን ብላቴን ጌታ ገብረልዑልን፣ ሹማምንቶቻቸውን እና ደጃዝማች ዘማሪያምን ልከው እያዋጉ፣ እራሳቸውም እነ አቤቶ ዮስጦስን፣ እነ ፊትአውራሪ ወልደ ብሩክን እያስከተሉ ሄደው ከአገር ወደ አገር እየተዘዋወሩ ሲያዋጉና ሲዋጉ ቆይተው፤ የየግዛቱን አመፆች አርግበው በድል አድራጊነት ወደ ጎንደር ለመመለስ ችለዋል።

ከጦር ሜዳ መልስ በቤተመንግስታቸው ተቀምጠው በሠላም አገራቸውን በሚያስተዳድሩበት ወቅትም "ከህዝብ ከፍተኛ ቀረጥና ግብር አልወስድም" በማለት ራሳቸው በሚሠሩት ሠሌን ይተዳደሩ ጀመር። የተረፈውንም ለድሆች መመፅወታቸውን ቀጠሉ እንጂ የተንደላቀቀ ሕይወትን ንቀውት ነበር ጊዜያቸውን ያሣለፉት።

ሆኖም ሠፊ የሠላም ጊዜ እንዳይኖራቸው የአገር ውስጥ አመፁ መበራከት አገዳቸው። በ1667 ዓ.ም በአገው ምድር ያመፁትን ተዋግተው ያስገብሯቸው ዘንድ ጉዞ ጀመሩ።

በዚያ ወቅት ደግሞ በላስታና ዋገቢው ልዩ ልዩ ተላላፊ በሽታዎች በርክተው ህዝቡ ማለቅ ጀምሮ ነበር። ንጉሡ እንደደረሡም ሠባቱ የአገው ምድር ነዋሪዎች የሸፈቱት ሁሉ ለንጉሡ ነገስቱ ሰገዱላቸው። ሳጥናቸውንም እየከፈቱ ወርቅ ብርና የዝሆን ጥርስ እጅ

መንሺያና ይቅርታ መጠየቂያ ሠጡዋቸው፡፡ ፀሁፊያውም ቀርቶ ሁኔታው በሠላም ተፈታ፡፡

አፄ ዮሃንስ 1ኛ በተለያዩ አገሮች ለጦርነትም፣ ለሌላም ጉዳይ በሚጓዙበት ጊዜ በየደረሡበት አገር ሁሉ የህዝቡን መሻት እየጠየቁ፣ ህዝቡ የፈለገውን ነገር እየሠሩ፣ ችግራችን ነው ያሉትን ነገር ሁሉ መፍትሔ እየሠጡ ነበር የሚጓዙት፡፡

በርካታ ስራቸውም ዛሬ ድረስ እንደ ቅርስነት ተቀምጦ ሲገኝ፤ የገነቧቸው ግንባታዎችም እስከ አሁን ተጠብቀው ለህዝብና ለምዕመኑ ግልጋሎት እየሰጡ ይገኛሉ፡

ከእነዚህ ውስጥም ከአገው ምድር በሚመላለሡበት ጊዜ በህዝቡ ጥያቄ መሰረት "ምን ልስራላችሁ?" ሲሏቸው "በእግዚአብሔር ስም ቤተክርስቲያን" የሚል ምላሽ ባገኙበት ቦታ በጠዳ የ"ጠዳልዕል እግዚአብሔር አብ ቤተክርስቲያን ይጠቀሣል፡፡ የአገው ግምጃ ቤት ማርያምንና ሌሎች አብያተክርስትያናትንም አስገንብተዋል፡፡

እኒህ ንጉሠ ነገስት በጦር ሜዳ ውሎ ስኬትን፣ በደግ ተግባራቸው በህዝቡ ዘንድ ተወዳጅነትን፣ በመንፈሣዊ ስራቸው ፅድቅን እንደገበዩ ይነገርላቸዋል፡፡

በተለይም መንፈሣዊነታቸው "ወደር የለሽ" የተባለለት ነበር፡፡ሌሎችን ትተን አንዱን እንይላቸው፡፡

ባለቤታቸው እቴጌ ሡብለወንጌል ከንጉሥሐ አባታቸው(አንዳንድ ፀሃፍት ከመልከኛው ምግብ አብሣያቸው ጋር ነው ይላሉ) ፍቅር እንደ ጀመሩ በሡፊው ይነገር ነበር፡፡ አፄ ዮሃንስም ጉዳዩን በደንብ አውቀውታል፡፡ ከእለታት አንድ ቀን ንስሀ አባታቸው፣ እቴጌ ሰብለወንጌልና አፄ ዮሃንስ1ኛ በአንድ ማዕድ ቀርበው የተጠበሠ ዓሳ ይመገባሉ፡፡ አፄ ዮሃንስ በቤተመንግስታቸው ውስጥ በሚገኘው የመኖሪያ ክፍላቸው በር ላይ እንደ ጠቢቡ ሰሎሞን ሰው ሠራሽ ባህር አስበጅተው፣ በባህሩም ውስጥ ዓሳ አስረብተው፣ከዚህም ዓሳ ውስጥ ተመርጦ እየተሠራ ለምግብነት ይውል ነበር፡፡ አሁንም ይሄ ሊበላ የቀረበው ዓሣ ከዚሁ ባህር የተገኘ ነው፡፡ እናም በዚህ ጊዜ ንጉሡ "ሶሥታችን እውነት ብንናገር ይህ የተጠበሠ ዓሣ በህያውነት ተነስቶ አባህሩ ውስጥ ይገባ ነበር" ብለው ተናገሩ፡፡ ከዚህ በኋላ እቴጌይቱ "ቄሱን አግብቼ ብኖር እወዳለሁ" ብለው በግልፅ ተናገሩ፡፡ ቄሱም "እቴጌን አግብቼ ብኖር እመርጣለሁ" ሲሉ ንጉሡ ግን "ይችን ከንቱ ዓለም ንቄ ብመነን እወዳለሁ" ብለው ሶሥቱም እውነት ተናግረው የየፍላጎታቸውን ተግባር እንደፈፀሙት በርካታ የታሪክ መዛግብት ያስረዳሉ፡፡ ባሉት መሠረትም የተጠበሰው ዓሣ ነብስ ዘርቶ ወደ ባህሩ ገባ ይባላል፡፡ ዛሬ ድረስም በጣና ሃይቅ ይህን አይነት አሣ በመረብ



ተይዞ ከተገኘ "የፃድቁ ዮሃንስ አሣ ነው መልሡት አይበላም" እየተባለ ይመለሣል፡፡

ቀዳማዊ አፄ ዮሃንስ ቀደም ሲል በመንፈሳዊነታቸውና በፀሎታቸው ይታወቁ የነበሩትን የመደባይን ባላባት የገብረመስቀል ጃታማን ልጅ ሡብለወንጌልን አግብተው ይኖሩ በነበረ ጊዜ አቤቶ ዮስጦስን፣ አቤቶ እያሡን፣ ልእልት ኢሌኒን፣ አቤቶሁን ቴዎፍሎስን እና አቤቶ ቆላዥን ወልደው ነበር፡፡ ስለሆነም አፄ ዮሃንስ1ኛ አእላፍ ሠገድ ንጉሠነገስት ዘኢትዮጵያ ተብለው በነገሡ በ15ኛ አመታቸው የዚህን ዓለም ደስታ ትተው ልጃቸውን አቤቶ ኢያሡን ለትምህርት ከተላከበት ገዳም አስመጥተው በመመረቅ ብላቴን ጌታ ገብረቃል፣ ብላቴን ጌታ አካለክርስቶስ፣ ፀሃፌ ትዕዛዝ ወልደሐይማኖት እንዲሁም ሌሎች ባሉበት ልጃቸውን አድያም ሠገድ እያሡን ንጉስ ነገስት ዘኢትዮጵያ አሠኝተው በመሸም መነኑ፡፡

ከዚህም በኋላ የፃድቁ ዮሃንስ መመነን ለማንም እንዳይነገር ራሣቸው ስለከለከሉና ስላወገዟቸው አቤቶ ቴዎፍሎስንና አቤቶ ቆላዥን ወደ ወህኒ አምባ አስወስደው ስርዓተ ንግሱን አስፈፅመው ደጃዝማች አስጠንጣንዮስ "ንጉሣችን አፄ ዮሃንስ አርፈዋልና ልጃቸውን አዲያም ሠገድ እያሱን ንጉሠ ነገስት ዘኢትዮጵያ ብለን አንግሰናል" ብለው አሣወጁ፡፡

ከዚያ በኋላም ፃድቁ ዮሃንስ በ1674 ዓ.ም ሐምሌ 15 ቀን በእለተ እሁድ ሞተው ቀደም ሲል ባሠሩት በጠዳ እግዚአብሔር አብ ቤተክርስቲያን ተቀበሩ፡፡ ቆይቶም አፅማቸው ተቆፍሮ ወጥቶ በጣና ደሴት በፅርሀ ፅዮን ገዳም እንዲቀመጥ ተደረገ፡፡

አፄ ዮሃንስ1ኛ በዘመናቸው ምንም አይነት 'የባእድ' ወረራና ውጊያ ሳይኖባቸው ነበር የግዛት ዘመናቸው የተጠናቀቀው፡፡ የእኒህን ንጉሠነገስት መንፈሣዊ ተአምራት በተመለከተ ከዓሣው ጋር በተያያዘ የተገጠመላቸውን ግጥም አይተን እናብቃ፡፡

"የደጉ ዮሃንስ ደግነት ቢነሳ፤
ዘሎ ገባ እባህር የተጠበሰ ዓሣ፡፡
ዓለምን ቢመኙ ንጉሥ ጠርተውት፤
ያ የሞተ ዓሣ ተነሣ ከሞት፡፡
ፃድቁ ዮሃንስ ዘውድ ይዞ ብቃት፤
ልበ አምላክ ሆነ ደግሞ እንደ ዳዊት፡፡

## ምዕራፍ ፰፫

## የአፄ እያሡ 1ኛ ዘመነ መንግስት

## ከ 1674-1698 ዓ.ም

አፄ እያሡ 1ኛ /አድያም ሠገድ/ በአባታቸው ዙፋን ከተቀመጡ በኋላ በ3ኛው ቀን ወደ ወህኒ አምባ ሔደው ሁሉንም የነጋሲ ዘር እስረኞች ፈትተው በማስወጣት ታላቅ ግብዣ አደረጉላቸውና በሰላም ወደየቤታቸው ላኳቸው። "መንግስትህን ከልጅ ልጅ እያውጣው" እያሉ አመሠገኗቸው። እጅግ ደስ ስላላቸው የተፈቱት ሁሉ ንጉሡ እግር ስር ወድቀው ሠገዱላቸው።

ወዲያውም የአባታቸውን ፈለግ በመከተል እልፍኝ የተባለ ቤተመንግስት በአባወልደጊዮርጊስ የበላይ አስገንቢነት አስገነቡ።

በነገሡ በ2ኛው ዓመትም በጳጳሱ በአባሲኖዳ እና በእጨጌው አባ ሀርያቆስ አማካኝነት ከሀማሴን ወገን የሆነችውን ወለተፅዮን ሃብተየሡሥ የተባለችውን ልጃገረድ በስርዓተ ተክሊል አገቡ።

በነገሡ በ3ኛው ዓመት በጎጃም ግዛት የሚኖሩ የነበሩ የቱለማ ኦሮሞዎች፣ በወሎ ደግሞ የውጫሴና የከረዩ ዘሮች ሸፍተው የሌሎችን ግዛቶች ንብረት መዝረፍ ጀመሩ።

አፄ እያሡም የዳሞት ገዥ የነበሩትን ራስ አንስጣስዮስን ወደ ወሎ እንዲዘምቱ በማድረግ ራሣቸው ደግሞ ወደ ጎጃም ዘመቱ። የቱለማ ኦሮሞዎችም የዘረፉትን ይዘው ሸሹ። አፄ እያሁ ተከታትለው በመዋጋት አሸንፈው የተዘረፈውን ሁሉ አስመልሠው ከብዙ ምርኮ ጋር ወደ ጎንደር ተመለሡ።

ቀጥሎም ደጃዝማች ወሴ የተባለው ሹም የጎጃምን፣ የሜጫን፣ የጉድሩን፣ የጃዊን... ተወላጆች አሣምኖ በንጉሠነገስቱ ላይ ተነሣ። ተነስተም ይስሀሐቅ የሚባለውን የአፄ ሱስኒዮስ የልጅ ልጅ ነኝ የሚለውን ንጉሥ አሠኝቶ በማንገስ በጋራ ሽምሽር አድርገው የጎጃምን ግዛት ለአመፀኛው እንዲከፋፈል አደረጉ። አፄ እያሡም ይህን ሲሰሙ በርካታ ሠራታቸውን አስከትለው በሠንተራ ሜዳ አሠልፈው ለውጊያ ተዘጋጁ። አመፀኞችም ጥቂት ተዋግተው የሠራዊቱን ብዛት ከተሟላ ትጥቅ ጋር ሲያዩና ጦርነቱን እንደማይቋቋሙት ሲያውቁ ሸሹ።

የጎጃም ገዥ የነበረው ደጃዝማች ጣሚ ተከታትሎ በርካታ አመፀኞችን ፈጃቸው። ንጉስ የተባለው ይሰሐቅም አምልጦ ሸዋ መግባቱ ሲሰማ አፄ እያሱ ለሸዋው ገዥ ደጃዝማች ድሜጥሮስን መልዕክት ልከው ይዞ እንዲያመጣላቸው አስደረጉ። ደጃዝማች ድሜጥሮስም ከኦሮሞዎች ዘንድ በዘዴ ቀርቦ 80 ከሚሆኑ ከቱለማ ወገኖች ጋር ሆኖ ይሰሐቅን ወስዶ ለንጉሡ አስረከበ። ይህ ሠው በፍርድ ሸንጎ ፊት ቀርቦ ሲጠየቅ "እኔ በደብረ ወርቅ አውራጃ በብር አንጥረኞችና በብረት ቀጥቃጮች ቤት ውስጥ ተቀጥሬ እሠራ የነበርኩኝ ነኝ" ብሎ እውነቱን ተናገረ። ሆኖም የሱስኒዮስ የልጅ ልጅ ነኝ ብሎ በሃሣዊ



ስልጣን ሁከት ፈጥሮ ብዙዎችን ስላስጨረሰ ህዝቡ ሁሉ በአንድ ቃል "ይሠቀል" ስላለ ስቅላት ተፈረደበትና በስቅላት ተቀጣ።

አፄ እያሡ እነዚህን የውስጥ አመፆች በቁጥጥራቸው ስር ካደረጉ በኋላ ወደ አክሱም አቀኑ። በየመንገዱም ያልገበረውን እያስገበሩ የሌላውን ግብር እየተቀበሉ በመንዝ የቀረውን ሠራዊታቸውን ወደ ስናር እየላኩ ግዛታቸውን በምዕራብ እስከ ስናር፣ በሠሜን የከረንን የሃባብንና የአከባቢውን ግዛት ሁሉ እያስገበሩ ጨርሠው እስከ ላይኛው የባርካ ወንዝ ድረስ ተቆጣጥረው ሽምሽር እያደረጉና ግብር እየጣሉ ሲዘዋወሩ ቆይተው አክሱም ደረሱ።

በአክሱም ነዋሪው ህዝብና ካህናቱ ደማቅ አቀባበል አደረጉላቸው። በታቦተ ፅዮን ፊት ለፊት ሆነውም ሠገዱ። በእለተ ሠንበትም ቅዳሴ አስቀድሰው ስጋወደሙ ተቀበሉ።

ከቀዳማዊ ምኒልክ ጀምሮ እስከ እርሣቸው ድረስ ይሠራበት የነበረውን ህግ ሁሉ በአዲስ መልክ እያዘጋጁና እያሻሻሉ ፍትሀ ነገስት በመባል የሚታወቀውን የሃገሪቱን ህገ መንግስት እንደገና ተሻሽሎ እንዲፃፍ አስደረጉ። ከአክሱም ቆይታቸው በኋላም ወደ አካባቢው ሔደው አጠቃላይ ሁኔታውን ቃኝተው ወደ ጎንደር ተመለሁ።

በአፄ እያሁ 1ኛ ጊዜ ሙራድ የተባለ የግብፅ ተወላጅ በንጉሠ ነገስቱ ትዕዛዝና መልካም ፈቃድ ከግብፅ ወደ ኢትዮጵያ፣ ከኢትዮጵያ ወደ ህንድ እየተመላለሠ ይነግድ ነበር። አንዳንድ እቃዎች እያመጣ ከቤተመንግስቱ ሹማምንትና ከንጉሁ ጋር ያደርገው በነበረው የንግድ ልውውጦች ሣቢያም ብዙዎች ደስ ስለተሠኙበት ዋና ባለሟል እስከመሆን ደርሶ ነበር። አንድ ቀን የንጉሰነገስቱንና የራሡንም ገንዘብ ይዞ ወደ ምፅዋ ለመሔድ በጉዞ ላይ ሳለ በምፅዋና በአርኪቆ መካከል ያለው የቱርኮች ሹም ናይብ የያዘውን ንብረትና ገንዘብ ቀምቶ አሠረው።

አድያም ሠገድ እያሡም ይህንን የሽፍትነት ስራ እንደሠሙ እጅግ ተቆጥተው በዙሪያው ያለውን ድንበር ይጠብቁ ዘንድ በትግሬ አገር ያሉ ሹማምንቶችን አዘዟቸው። ወደ ምፅዋም ማር፣ ቅቤና ሌሎች ነገሮች እንዳያልፍ አዘዙ።

ናይብ ይህንን ማዕቀብ ሲሠማ በታላቅ ድንጋጤ ሙራድ የተባለውን ነጋዴ ፈትቶ ከወሰደበት ገንዘብ ሌላ ጨምሮ ሸኘው። ከዚያም ነጋዴውን ተከትሎ ወደ ንጉሠ ነገስቱ በመምጣት እግራቸው ሥር ወድቆ ብዙ ወርቅ ሠጥቶ ይቅርታ ጠየቀ። ንጉሱም ይቅርታውን ተቀብለው በሠላም ሸኙት።

ከዚህ በኋላ አፄ እያሁ በነጋዴዎች ላይ የሚደርሰውን ልዩ ልዩ ጫና በመረዳታቸው አንድ ህግ ደነገጉ።

"የንጉሠነገስት ቀረጥ በሃገር ውስጥ በአንድ አውራጃ አንድ ኬላ ብቻ ሆኖ ከ 5 በቅሎ የጫነው ጭነት አንድ በቅሎ ጭነት ጨው፣ ከአስር አህዮች ጭነት አንድ አህያ ጭነት፣ በትከሻው የሚሸከም አግረኛ እንዳይነካ፣ የበግና

የፍየል ነጋዴዎች ቀረጥ እንዳይከፍሉ፣ ይህንን ህግ የተላለፈ ቤቱ ይበርበር ንብረቱ ይዘረፍ፣ ገንዘቡም ይቀማ" የሚል ህግ ወጥቶ ተግባራዊ ሆነ።

ይህም ህግ ተፅፎ በቤተመንግስት እንዲቀመጥ ተደረገ፡፡ በቀይ ባህር በኩል ከየመንና ከህንድ ጋር ለሚደረጉ የንግድ ልውውጦች ግብፃዊው ሙራድ እንዲቆጣጠር ሲሾም፣ ከግብፅና ከሱዳን ለሚመጣ ሸቀጥ ደግሞ ሐጂ አሊ የተባለ ሌላ ግብፃዊ ተሾሞ እህል፣ ቅቤ፣ ማር፣ ቡና፣ ቆዳ፣ የቀንድ ከብት ወደ ውጭ እየላከ እንዲሸጥም ተፈቀደለት፡፡
በጳጳሱ በአቡነ ማርቆስ /አቡነ ሲኖዳን የተኳቸው ናቸው/አማካይነት እስከ አለም መጨረሻ ይህንን ህግ ማንም እንዳያፈርስ ተወገዘ፡፡
ኢትዮጵያውያኑም ይህ ህግ (ቀረጥን የሚመለከተውን) መውጣቱን በሰሙ ጊዜ ንጉሡን እጅግ በማመስገን መረቋቸው፡፡ በህዝቡ ደስታም አፄ እያሱ ተደሠቱ፡፡

አፄ እያሱ ከዚህ በኋላ ያሠሩት በቤተመንግስታቸው አጠገብ በአቡነ ተክለሐይማኖት ስም አደባባይ ተክለሐይማኖትን በአዛዥ ጥቂሬ በር በኩል አሰርተው 147 ካህናትና መዘምራንን መመደብና በበለግ ምድር በርስትነት ቦታ ወደ መስጠት ነበር፡፡ ቀጥሎ ደግሞ አስደናቂውን ስራ ወደማሰራት ነበር ያመሩት፡፡

የአድባራት ሁሉ ንግስት በማለት ደብረ ብርሐን ስላሴ ብለው የሠየሙትን ቤ/ያን ለየት ባለ መልኩ አሳነፁ የህንፃ አዋቂ የሆኑ ታላላቅ ባለሙያዎችን መርጠው በማስማራት ፣በጥሩ ሁኔታ የተጠረቡ ድንጋዮችን፣ ለረጅም ዘመናት በጥንካሬ የሚቆዩትን እንጨቶች እያስመጡ በጎንደር ከሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ተወዳዳሪ የሌለው ሆኖ እንዲታነፅ አስደረጉ፡፤

የወርቅ ጉልላት በላዩ ላይ አሰርተው ከወርቅ የተሰራ መስቀልም እንዲኖረው አድርገው፤ በቀን እንደ ጸሃይ በሌሊት እንደ ጨረቃ ያንፀባርቅ ነበር። በማይነቅዝ እንጨትም በአዋቂዎች እጅ አስጠርበው የታቦቱን መንበር አሰሩ። በገዘፈን ጥርስ አስጊጠውም አሳመሩት። ከዚያም የቅድስት ስላሴ ፅላት እንዲገባ አስደረጉ።

አባ ሐይለ መስቀል ወልዱ በተባሉ ሣዓሊ አማካይነትም ሁሉንም አይነት መንፈሳዊ ስዕሎች እንዲሳል ተደረገ፤ ውስጡ በመንፈሳዊ ስእሎች ከማሸብረቁም በላይ ጣራው ሁሉ በተመሳሳይ ስእል ያጌጠ ነበር።

ከዚያም ጊቢውን በማስፋት አደ ኢያሪኮ ቅጥር ታላቅ እንዲሆን በጥሩ ኖራ ዙሪያው ረጅምና ሰፊ ሆኖ ታጠረ፡፡ በፊት ለፊቱም መግቢያና መውጫ 2 በር አሰሩ፡፡ በእነዚህ በሮች ላይ ትልቅ የአንበሳ ራስ ቅርፅ ያለው ባለግርማ ግንብም ተሠራ፡፡ በዙሪያውም 12 እንቁላል ግንቦች አሳነፁ፡፡

ቀጥሎም ግዙፍና ታላላቅ የሆኑ 2 ደውሎች በጠንካራ ገመድ ታስረው እንዲንጠለጠሉ ሆነ፡፡



ከእነዚህ ደውሎች የሚወጣው ድምፅ ከጎንደር አልፎ ከአካባቢው ወጣ ብለው ወደሚገኙ ሌሎች ግዛቶች ሳይቀር ይሰሙ የነበረ ሲሆን፣ እንዳ ደወል ከሮም ንጉስ በስጦታ የተበረከተ ነበር፡፡

ይቺ የበርካታ ቱሪስቶች መናሃሪያ የሆነች ደብር ተሰርታ እንደተጠናቀቀች በዙሪያዋ ልዩ ልዩ አትክልቶች እንዲተከሉና ዛፎች እንዲከቧት ስለተደረገ ዛሬ ታላላቅ ዛፎች አጥረዋት ይገኛሉ፡፡

በመጨረሻም አፄ እያሡ የቤተክርስቲያን ንዋዬ ቅድሳት ከቤተመንግስታቸው አዘጋጅተው ፣ ከወርቅ የተሠሩ ልዩ ልዩ መገልገያዎችንና መንፈሳዊ አልባሳትን አስይዘው በታላቅ ደስታ ከቤተመንግስቱ ሹማምንትና ሊቃውንት ጋር ተጓዙ፡፡

ያን ጊዜ ታቦቱን ብፁእ አቡነ ማርቆስ ባርከውና ቀድሰው፤ በሜሮን አክብረው እጨጌ አባ ጸጋ ክርስቶስ ለተባሉት ሰጧቸው፡፡ እጨጌውም ተቀብለው ተሸከሙት፡፡ መሰንቆ፣ እምቢልታ፣ እንዚራ እያሰሙ፤ ከበሮ እየመቱ፣ ቃለ ቀርን እየነፉ የራሳቸው ሰራዊቶች ይከተሏቸው የነበሩት ንጉሡ ከነጭ ፈረሳቸው ወርደው ካህናትና መዘምራን በምስጋናና በማህሌት ከተቀበሏቸው በኋላ ደብረ ብርሐን ስላሴ በር ላይ ሲደርሱ አፄ እያሡ ታቦቱን ከእጨጌው ተቀብለው ራሳቸው ተሸክመው ወደ መቅደሱ አደረሡት በዚህ ጊዜ አገሩን ሁሉ ጉድ አሠኙት፡፡ ከዚያም እንዲህ የሚል ትርጉም ያለው ቅኔ በግዕዝ ተቀኙላቸው

"የእዝያንና የቆሬ ልጆች ካህናት ለመሆን አስበው አምላክ ያልፈቀደውን የወርቅ ማዕጠንት በያዙ ጊዜ ተቀሰፈው እሳት ፈጃቸው፡፡ አንተን የሚፈሩህ ሰዎች ግን በሰጠሐቸው ምልክት ተመርተው፤ ዳዊት ቢራብ መሰዋዕትነት በላ፣ እያሡም ፅላትን አነሳ፡፡" ሲባልላቸው የአማርኛ ገጣሚ ደግሞ እንዲህ ብሎ ገጠመላቸው፡፡

"ወዴት ሄዶ ኖሯል ሰሞንኛ ቄሡ፣
ታቦት ተሸከመ ዘውዱን ጥሎ እያሡ፡፡
የተሸሸገውን ያባቱን ቅስና፣
ገለጠው እያሡ ታቦት አነሳና፡፡
አየነው እያሡ ደብረብርሐን ቆሞ፣
ልክ እንደ ኪሩቤል ሶስቱን ተሸክሞ፡፡
ስላሴን ቢሸከም እያሡ ገነነ፣
ለአራቱ ኪሩቤል አምስተኛ ሆነ፡፡"

ከዚያም ቡራኬ ተደርጎ፣ በታላቅ ክብር ታቦቱ ገብቶ በተዘጋጀለት ልዩ ቦታ ተቀመጠ፡፡

"ደጋግ ነገስታት የልዑል እግዚአብሄር ወዳጆች የሆኑ እንደ ቆስጠንጢኖስ አኖሪዎስ፣ አርቃዴዎስ... ነገስታት ሁሉ ታላቅ በረከት ያሣድርብዎ" በማለትም ህዝቡና ካህናቱ አመሰግነው ባረኳቸው።

አፄ እያሡ 1ኛ ወደ ቤተመንግስታቸው ተመልሰው ለ3 ቀንና ሌሊት ታላቅ ግብዣ አደረጉ።ይህም የሆነው ጥር 7 ቀን ስለነበር የጥር ወር በገባ በ7ኛው ቀን ሁሌም በዓሉ እንዲከበር ተደረገ።ቀጥሎም 170 ካህናት እንዲያገለግሉ ተደርጎ ብዛት ያለው ቦታ በርስትነት እንዲያገኙ ተደረገ። በዚህም ካህናቱ ሁሉ በዘመናቸው እጅግ ይወዷቸውና ያከብሯቸው ነበር።"ሺ አመት ያንገስህ አድሜህን ያርዝመው፡ አንተ የካህናት ሁሉ ጌጥ፣ የዘመናችን ተድላ የልቦናችንም ደስታ፣ የኃለማችን ጸሃይ ነህና" እያሉ ይጸልዩላቸውም ነበር።ከጊዜ በኋላ በቤተመንግስቱ አካባቢ ታላቅ አውሎ ንፋስ ተነስቶ ሻንተከል የተባለውን የቤተመንግስቱን መግቢያ በር አፈረሰው ። በዚያ የነበሩት ብዙ ሰዎችም ሞቱ።

ከ5 ወራት በኋላ ደግሞ በእርግብ በር በኩል እሳት ተነስቶ ብዙ የከተማ ቤቶችን፣ የአቡነተክለሐይማኖትንና የቅዱስ ጊዮርጊስን ቤተክርስቲያን አቃጠለ። አፄ እያሱን ከልጅነታቸው ጀምሮ እያስተማሩ ያሳደጓቸውና ሰይፈ መለኮትንና መልክዓ ስላሴን የደረሱት አባ ስብሐት ለአብ የተባሉትም ሞቱ። ይህ ሁሉ ሲሆንም አፄ ኢያሡ በጣና ሃይቅ ደሴት ጨቅላ መንዝ በምትባል ቦታ ጸሎት ላይ ነበሩ። ፀሎታቸውን ጨርሰው ሲወጡ ታላቅ ሐዘን አደረባቸው።

ወዲያውም አስደንጋጭ መርዶዎች ሁሉ አልፈው ሰላም ወረደና ህዝቡም ንጉሱም ሐዘናቸውን ረስተው በሰላምና በደስታ ኑሯቸውን ቀጠሉ።በአፄ እያሡ 1ኛ ዘመነ መንግስት ጊዜም ሆነ በቀጣዮቹ የጎንደር ነገስታት ዘንድ ባጠቃላይ ከጎንደር ሊቃውንት ውስጥ ስሙ ገኖ በየታሪኩ ውስጥ ተካቶ የሚገኝ ክፍለ ዮሐንስ የተባለ ባለ ቅኔ ነበር።ይህ ሰው ቅኔ በመቀኘት ወደር ያልተገኘለት ሰው ነው። አፄ እያሱ ባሰሩት ደብረ ብርሀን ውስጥም ያስተምር ነበር። አንድ ቀን አፄ ኢያሱ የክፍለ ዮሃንስን ት/ት እስጣጥ ለመታዘብ ይሔዳሉ። በቅኔ ተመስጦ ስለነበር ደበሎውን ለብሶ አቀርቅሮ ስላላያቸው በሎሚ ቅርፅ በተሠራ የወርቅ ሉል ወርውረው ሲመቱት ወዲያው ቅኔ ዘርፎ፦

"በእስጢፋኖስ አእባን እመ ኀልቁ ዘበጠኒ እያሡ በወርቁ" ሲል ተቀኘ። ትርጓሜው የመጀመሪያ የክርስቲያን ሰማዕታት የሆነው እስጢፋኖስ አይሁዶች በድንጋይ ደብድበው ሲገድሉት ድንጋዮቹ በእርሱ ገላ ላይ ስላላቁ እያሡ የሚመታበት ቢያጣ በወርቅ ያበደበኝ ማለት ነው። (ቃል በቃል ሳይሆን በሰፊው ተተንትኖ ሲተረጎም ማለት ነው)

ሊቁ ክፍለ ዮሐንስ ነቢይ፣ ሃዋርያ፣ መምህር ወመገስፅ፣ መናኝ ባህታዊ፣ የቅኔና የመፅሃፍ መድብል፣ የ4ቱ ጉባኤ መምህር ነበር።
አድያም ሰገድ እያሡ ሹመትና ሽልማት በሚሰጡበት ጊዜ ለዚህ ሊቅ የወርቅ ካባ ቢሸልሙት አልፈልግም ለቤ/ን ይስጡት፤ ለኔና



ለደቀመዛሙርቶቹ የሚሆን ገንዘብ ይስጡኝ ብሎ እህልና ልብስ ገዝቶ አከፋፍሎ ደብሎውን እንደለበሰ ነበር ማስተማሩን የቀጠለው። ይህ ሰው እጅግ መንፈሳዊ ከመሆኑ የተነሳ ሸዋ የሚገኘው የደብረ ብርሃን ስላሴ ቤ/ያን እና ጎንደር የሚገኘው ደብረ ብርሐን ስላሴ በአንድ ቀን በሚከበሩበት ጊዜ እየተመላለሰ ሁለቱም ጋርስለሚውል የሸዋና የጎንደር ካህናት እኛ ዘንድ ነው የዋለው እየተባባሉ ይከራከሩ ነበር። ክፍለ ዮሐንስ በደመና እየተመላለሰ ነበር ሁለቱም ጋር የሚውለው ይባላል። ለዚህ ክርክር ሊቁ ሲመልስ፦
"እነሂ ወግብረ ቅኔ ዘበሆሳ እና
እምዕደ ገፉኢ ወተገፋኢ ንትመሰጥ በደመና" በሆሣእና ያለን የቅኔ ጥበብና እኔ ከገፊውና ከተገፊው እጅ በደመና እንናጠቃለን። እንደማለት።

ከደብረ ብርሐን ስላሴ ሌላ አፄ እያሡ በዘመናቸው በወገራ ኮረንኮ ማርያምን፣ በቆላድባ ጉቢያ ኢየሱስንና በዳባት ዳቋ ኪዳነምህረትን አሳንፀዋል።
በአፄ አምደ ፅዮንና በአፄ ዳዊት ተሰርቶ የነበረውን ክብራን ቅዱስ ገብርኤል አሳድሰዋል። በአፄ አምደ ፅዮን ዘመነመንግስት ለተሰራው ለባህር ዳር ፊለገ ገነት ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያንም ለእቃ ቤት የሚሆን ባለ ሁለት ፎቅ ግንብ እንዲሰራ አድርገዋል።

በጣና ሐይቅ በዘጌ በአራራት ተራራ አካባቢም ይጋንዳ ተክለሐይማኖትን ያሰሩት እኒሁ መንፈሳዊ ንጉሰነገስት አድያም ሰገድ እያሡ ናቸው።እንደ አዲስ ባሰሩት ክብራን ቅዱስ ገብርኤል ግምጃ ቤት ውስጥም ዛሬ ድረስ በሐዋርያው በቅዱስ ሉቃስ የተሳለች የቅ/ማርያም ስዕል፣ ከብረት የተሰራ የአቡነ ዘ ዮሃንስ ልብስ፣ የእኒሁ ንጉስ አልጋና ሰይፍ፣ የንጉስ ተክለሃይማኖት አልጋና ሌሎችም ውድ ቅርሶች ይገኛሉ።

በአፄ እያሱ 1ኛ ዘመን ሸዋን ተከፋፍለው ይገዙ የነበሩ ባላባቶች እርስ በርሳቸው በግዛት ይጋጩ ነበርና አፄ እያሱ መጥተው እንዲያስማሟቸው መልዕክት ላኩ።ንጉሱም ጎንደርንና አካባቢውን ለራስ ፋሬስ እዲጠብቁ በማዘዝ ወደ ሸዋ ተጓዙ።

የሸዋ ካህናትና ህዝቡ፣ ወታደሮችና ሹማምንቱ በታላቅ ደስታ ተቀብለው የእነ አፄ ቴዎድሮስ 1ኛን፣ የእነ አፄ ይስሐቅን ፣ የአፄ ገላውዴዎስንና የአፄ ሚናስን መቃብር በተድባበ ማርያም ቤ/ን እንዲጎበኙ አደረጉ። ንጉሱም ለዚህ ደብር የለበሱትን የወርቅ ካባ አውልቀው በስጦታ ሰጡ።

ከሸዋ ሊቃውንት መካከልም መርዕድ አዝማች ዘሚካኤል የተባሉት ባለቅኔ በግዕዝ ለአፄ እያሡ የተቀኙላቸው ቅኔ የአማርኛ ትርጉም እንዲህ የሚል ይዘት ነበረው። "ከወገኑ የተወለደው አምላክ በደብረ ሲና በወረደ

ጊዜ በሙሴና በአሮን ፊት ከእኔ በቀር ሌላ አምላክ አታምልክ ብሎ በግልፅ ባይናገር ኖሮ አንተን አድያም ሀገድ እያሱን አምላክ አድርገን በሰገድንልህ ነበር።”

አጼ እያሱ 1ኛ በሸዋ ውስጥ የግድምን፣ የግሼንን፣ የመራቤቴን ፣ የተጉለትን ባላባቶች አስማምተው ለሁሉም የበላይ መስፍን አቤቶ ነጋሲን ሾመው ወደ ጎንደር ተመለሱ።እንደተመለሱም በራሳቸውና በዙፋኑ ላይ ዶልተው የጠበቋቸውን በመርዝ ንጉሱን ለመግደል ማሴራቸው ሲረጋገጥ በፍርድ ሸንጎ ተገቢውን ቅጣት እንዲያገኙ ተወስኖባቸው አድመኞቹ ወደ ወህኒ ተወረወሩ።

ከዚህ በኋላ ከጎንደር ተነስተው በርካታ ኦሮሞዎች ይኖሩበት ወደነበረው ወደ እናርያ በጉራጌ አገር አቅራቢያ ወደሚገኘው ወደ ጊቤ ተጓዙ። በዚህ ግዛት ሃብትና ንብረት እየዘረፉ ህዝቡንም የሚያሰቃዩ የተደራጁ ሽፍቶች ነበሩና አለቃቸውን ዲላሞ የተባለውን አመፀኛ ውጊያ ገጥመው ድል ካደረጉ በኋላ ህዝቡን እፎይ አስባሉት። ለብዙ ጊዜያት በምርኮኝነት ይሰቃዩ የነበሩና በፈላጭ ቆራጩ ዲላሞ ይሰቃዩ የነበሩትን በርካታ ክርስቲያኖች አስለቅቀው ወደየመጡበት በሰላም እንዲሔዱ አደረጉ።እንደገናም በሰላም ወደ ጎንደር ተመልሰው ህዝቡ በደስታ ተቀባላቸው።

አድያም ሰገድ እያሱ በሸዋ፣ በትግሬ፣ በጎጃምና በኦሮሞ አገሮችና ህዝቦች ዘንድ እጅግ ተወዳጅ የነበሩና ገናና የሆኑ ንጉሰነገስት ይባሉም ነበር።የግዛት ወሰናቸውም ከሰሜን ኤርትራን አልፈው ከሰላን፣ ከምዕራብ እስከ ሰናር ድረስ አስፍተው ይገዙ ነበር፤ በዘመናቸውም ከግብፅና ከህንድ ጋር እንዲሁም ከሌሎች አገሮች ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት በማድረግ የስልጣኔ ጮራ በመፈንጠቃቸው በመላው ኢትዮጵያውያን ዘንድ ታላቁ እያሱ እየተባሉ ነበር የሚጠሩት። ኩልበ የተባለው ፈረንሳዊ ተጓዥ ፀሃፊ አፄ እያሱ 1ኛን በሚመለከት "በኢትዮጵያ ረጅም ዘመን ታሪክ ዘመነ መንግስቱ ወርቃማ ዘመን ከሚባሉት በጣም ጥቂቶች አንዱ ነበር።ተክለ ቁመናው ግርማ ሞገስ ያለውና ሰውየው ራሱ የደስደስ የተጎናጸፈ በመሆኑ ቤጋዎቹ ትልቁ የሚለውን ቅዕል ስም ሸልመውታል" ይላል።

አፄ ኢያሱ በዘመናቸው ከፈጸሟቸው ተግባራቶች ውስጥም ወሽባ ግንብ መገንባቱ አብሮ ሲጠቀስ ይህ ግንብ የአሁኑ ዘመን አይነት የሳውና ባዝ አገልግሎት የሚሰጥ ነበር። በወሽባ ግንብ ህሙማን ገብተው በእንፋሎት ታጥበው ይፈወሱ ነበር። የህክምና ክፍል በሚልም ይጠራ ነበር።

አድያም ሰገድ እያሱ ድንገተኛ ህመም ሲደርስባቸው በግብፃዊው ሃጂ አሊ አማካይነት ዶክተር ፓንሴት የተባለ ፈረንሳዊ ሃኪም እንዲመጣ ተደረገና



ዶ/ሩ ጎንደር መጥተ አክሞ አዳናቸው። ፈረንሳዊው ሀኪም ፓንሴት የተመለከተውን ሁኔታ ሲገልጽ "ንጉሰነገስቱ በወርቅ የተለጠፈ ባለ ረጅም እጅጌና ሰደርያ ለብሰው ነበር። መቀነታቸው በዚያው ስልት የተለጠፈ ነው። ባርኔጣ አላደረጉም ጸጉራቸው በሚያምር መልኩ ሹሩባ ተሰርቷል።

ግንባራቸው ላይ እንቁ ስለነበር ግርማቸውን አድምቆታል። ጫማቸው የህንዶችን አይነት ሆኖ በአበባ ምስል ላይ ሱል አለበት" ብሏል።

ከዚህ ዶ/ር ጋር ወዳጅ ሆነው ሲወያዩም ከፈረንሳዩ ንጉስ ከሉዊ 14ኛ ጋር ተፃፅፈው ወዳጅነት ቢመሰረቱ መልካም እንደሆነ ነግሯቸው ተስማምተው እንቅስቃሴ ጀምረው ነበር። ሆኖም የቱርክ ፓሻዎች መልዕክተኞቹን እያጉላሉ ጅምሩን አጨናገፉት።

አፄ እያሱ 1ኛ በነገሱ በ24ኛ አመታቸው ታላላቅ ሹማምንትንና ሊቃውንትን ጠርተው በመሰብሰብ በራሳቸው ላይ የደፉትን ዘውድ አውልቀው "ይህ ዘውድ የህዝብ በመሆኑ ህዝቡ የመረጠውን ያንግስ" ብለው ዙፋናቸው ላይ በማስቀመጥ የዚህን ከንቱ ዓለም መንግስታቸውን ትተው ጩቅሳ ወንዝ ከምትባለው ገዳም ሔደው ገቡ። በምንኩስናም ኑሯቸውን ቀጠሉ።ከዚያ በኋላ ምን እንደተከሰተና ፍፃሜያቸው ምን እንደሚመስል በተከታዩ "ርጉም" ንጉሰነገስት ታሪክ ውስጥ የምናገኘው ይሆናል።

## ምዕራፍ ፳፯

## የአፄ ተክለሐይማኖት /ርጉም/ ዘመነ መንግሥት

## ከ1698-1700 ዓ.ም

ከአጼ ፋሲል ዘመነ መንግስት ጀምሮ የጎንደር ነገስታትና ካህናትን እንዲሁም ህዝቡን ይንጥ የነበረው የሐይማኖት ክርክር ነበር። ይህም በየነገስታቱ የግዛት ዘመን በየጊዜው ይደረግ የነበረበት ሁኔታ ነበር።

ኦርቶዶክሶች በ3 የተከፈለ አቋም ያዙ። በዚህም ተዋህዶ፣ ቅብዓት እና የጸጋ ልጆች/ጸጋ/ በሚል ተከፋፈሉ።

"ፍሬውን ያፈራው ዛፍ አንድም ቃል ሳይናገር ፍሬውን የሚበሉት ወፎች ይንጫጫሉ" እንደሚባለው አባባል መሆኑ ነው።

ተዋህዶዎች "ክርስቶስ በተዋህዶ የባህርይ አምላክ ነው፤ ተዋህዶ ማለትም የልኡል እግዚአብሔር አብ ልጅ የኛን ስጋ በእኩሉ ከፍሎ ቢዋሀደው በሰውነቱ እንደ አብና እንደ መንፈስ ቅዱስ ያለ ፍጹም አምላክ ሆነ" ሲሉ

ቅብዓቶች፣ "የስጋና የቃል መዋሃድ ሁለትነትን አጠፋ እንጂ፤ ቃል የለበሰውን ስጋ የባህርይ አምላክነት ክብር፤ ያከበረው መንፈስ ቅዱስ ነው" አሉ።በሌላ በኩልም "ቃል በለበሰው ስጋ በመንፈስ ቅዱስ እንደኛ የጸጋ ክብር አግኝቶ ክርስቶስ ተባለ" የሚሉት ደግሞ የጸጋ ልጆች ነበሩ።

ተዋህዶዎች አሸንፈው የአገሪቱ ሃይማኖት– ተዋህዶ እንዲሆን የተወሰነበት ሁኔታ በአጼ ፈሲል ጊዜ ተፈጥሮ የነበረ ቢሆንም፤ ልዩነቱ ግን እስካሁንም እንደቀጠለ ነበር። በዚህም በቅብዓት አማኞች በጎጃም ሊቃውንትና ሹማምንት እየታገዙ አጼ ተክለሐይማኖት በራሳቸው ፈቃድ የአባታቸውን የአድያም ሀገድ እያሱን ዙፋን ያለ ህዝቡ ምርጫ ተቀመጡበት።

ስመ መንግስታቸውን ልኡል ሰገድ አሰኝተውም በእናታቸው በወ/ሮ መለኮታዊት፣ በራስ ፋሬስና በደጃዝማች ፍስሐ ክርስቶስ፣ እንዲሁም በእናታቸው ወንድሞች ጳውሎስና ዳርመን በተባሉት አጎቶቻቸው ተጨማሪ እገዛ የኢትዮጵያ ንጉሠነገስት ሆኑ።

ይህን ጉዳይ መናኔ መንግስት አድያም ሰገድ እያሱ ሲሰሙም እጅግ በማዘን በመልእክተኞቻቸው በደጃዝማች ዮስጦስ አማካይነት እንዲህ የሚል መልዕክት ላኩ።

"ልጄ ሆይ ይህን መንግስት የያዝከው በእኔ? በቤተመንግስቱ ሹማምንት? ወይስ በማን ፈቃድ ነው? አሁንም ልጄ ሆይ ይህን ተንኮል ተው! በከንቱ ነገር እንዳትጠፋ ይቅርብህ" ብለው ላኩ።

(በነገራችን ላይ መናኔ መንግስት ሲባል ዙፋኑ እንዳለ ተጠብቆ ንጉሰነገስቱ ከሞቱ በኋላ በህዝቡና በሹማምንቱ ምርጫ ሌላ ንጉስ ይተካል እንጂ፤ አንድ ንጉሰነገስት መነነ ማለት ያሻው ይግዛ ብሎ ጥሎ ሄደ ማለት



አይደለም። ንጉሰነገስቱ እስኪያልፍ ድረስም አገሪቱ በታማኝ እንደራሴዎች ትተዳደራለች፤ ሳይሞት እንደሞተ አድርጎ አዋጅ ካላስነገረ በቀር) ሆኖም መንግስቱን በሐይል ቀምተው የያዙት አጼ ተክለሐይማኖት ይህን ደብዳቤ አይተው በቃላቅ ቁጣ መልዕክተኛውን ደጃዝማች ዮስጦስን አሰሩ። አጼ እያሱ በድጋሚ "ተው" የሚል መልእክት ቢልኩም ሰሚ አላገኙም። ለሦስተኛ ጊዜ በአባ፟ር ገላውዴዎስ እጅ "ልጄ ከሆንክ ቤቱን ልቀቅ፣ ከአልጋውም ውረድና ወደ ነበርክበት ቤት ሒደህ ቆይ፣ የሌሎች ምክር አይጠቅምህም፣ ከእኔ ፍቃድና ሃይማኖት የወጣህ እንደሆነ ግን እንኳን የመሬቱን ርስት የሰማዩንም ርስት አታገኝም" አሉት።

አጼ ተክለሐይማኖት ግን "ቤትዎንም አለቅም፣ ከዙፋንዎም አልወርድም። የመነነ ሰው አልጋ ምኑ ነው? የመነነ፣ በዱር የሞተ፣ ከመቃብር ይመሰላልን? ዛሬ በእርስዎ እንደተጀመረ ሁሉ ለምን መነንኩ ብለው ተፀፅተው እንደሆነ ከመነኑበት ደሴት ይውጡና እንዋጋ፤ ፈረስዎ ፈረሴ ሰራዊትዎም ሰራዊቱ ነው። ማንም ሊያድንዎት አይችልም" በማለት ልጅ አባቱን መናገር የሌለበትን አይነት ንግግር ተናገራቸው።

ከዚያም በመናኔ መንግስት እያሱ ዙሪያ ያሉት ሹማምንትና ካህናት "ከደሴቱ ይውጡና እናዋጋ" የሚል ሀሳብ ቢያቀርቡም መናኔ መንግስት አድያም ሰገድ እያሱ ግን (እንዲህ እንዲሆን የአምላክ ፍቃድ ቢሆናልና ተውኝ" የሚል ምላሽ ሰጡ። ቀጥለውም አብረዋቸው በዙሪያቸው የነበሩትን መኳንንትና ቀሳውስት አመስግነው ወደየቦታቸው እንዲሄዱ አሰናበቷቸው። ልጃቸውንም "በአባትህ ላይ ክፉ እንደመከርክ ክፉ መካሪ ይውረድብህ፣ ሹመትህም ለባእድ ይሰጥ፣ ሰውም አይገዛልህ። ዋትህ፣ ባክነህ በጠላት እጅ ሙት" ብለው ረገሙት።

አፄ ተክለሐይማኖትና መካሪዎቹ ሹማምንቱም መጥፎ ምክር በመመካከር ደጃዝማች ፍስሃ ክርስቶስን፣ የእናቱን ወንድሞች ጳውሎስንና ዳርመንን፣ እልባተ ተስፋን፣ አባ ሰይፈ ሚካኤልንና አባ ዘማርያምን ልከው ካሉበት ደሴት አስወጥተው ወደ ሌላ ቦታ እንዲወስዷቸው፤ እልሄድም ካሉም እንዲገድሏቸው ተላኩ። የተላኩትም መናኔ መንግስት እያሱን ካሉበት ደሴት አስወጥተው ወደ ሌላ ገዳም ሊወስዷቸው ሲሉ፣ ደጋፊዎቻቸው ሊዋጉ ቢሉም አፄ እያሱ አልፈለጉምና "እንዳትመጡ" አሏቸው። እያንገላቱ ወደ ማይፈልጉት ቦታ ወሰዷቸው። በዱላና በሌላ ነገር መጫወቻ አደረጓቸው።

አድያም ሰገድ እያሱ እጅግ አዝነው "ጌታ ሆይ አይሁድ በሙቱህ ጊዜ አላመመህምን? እጥንትህ እስኪታይ በገረፉህ ጊዜስ ልብህ አላዘነምን? በጦር በወጉህ ጊዜስ፣ 5 ቦታ በቸነከሩህ ጊዜስ ልብህ አላዘነምን?

በመንግስተ ሰማያት በቀኝህ የተሰቀለውን ሽፍታ እንዳሰብከው እኔንም አስበኝ ብለው ጸለዩ"

ቀጠሉና "እኔ የማያልፈውን መንግስት በሚያልፈው ለውጫለሁ። በእኔ ሞት ተክለሐይማኖት የሚጠቀመው ምንድን ነው? በአጥንቴ ቤት አይሠራበት፣ በደሜ ሳር አያበቅልበት፣ ሥጋዬም ለትል ነው፤ የግፍ ብዛት ምን ይረባዋል?" ብለው ሲናገሩ እልባተ ተስፋ የተባለው እጅግ ተሰምቶት "እኔ በአፄ እያሱ ላይ ምንም መጥፎ ነገር አላደርግም" ብሎ ተወ። ጳውሎስ፣ ዳርመንና ሌሎች ግን እያፌዙ እንደገና ልናነግስዎ ነው የመጣነው" እያሉ በመዘበት ብዙ በደል ፈጸሙባቸው። አፄ እያሡም "እርግጥ በሰማይ ቤት ልታነግሱኝ እንደመጣችሁ አውቃለሁ" ብለው መለሱላቸው። ወደ ቅብአት ሐይማኖት እንዲገቡ ሲጠይቋቸውም አወገዟቸው። ከዚያም ጳውሎስ የተባለው ለሌሎቹ ትእዛዝ ሰጥቶ በጥይት እንዲመቱ አደረገ። አፄ እያሱ ጣር በዝቶባቸው በሚያቃስቱበት ጊዜ ዳርመን የተባለው "ይህ ካህዲ ቶሎ አይሞትም" በማለት እራሱ በሁለት ጦር ወግቶ ጨረሳቸው። ሬሳቸውም ወንዝ ውስጥ ይጣል፣ አሞራ ይብላው፣ ወዘተ.... እየተባባሉ ተከራክረው የቀበረ ይቅበራቸው ብለው ጥለዋቸው ሄዱ። በዚህ ምክንያት አፄ ተክለሐይማኖት "እርጉም" ተክለሐይማኖት እያተባሉ መጠራት ጀመሩ።

በኋላም በጣና ደሴት ይኖሩ የነበሩ ነዋሪዎችና ካህናት በታላቅ ሃዘን እያለቀሱ ወድቆ ያገኙትን አስከሬን በጥሩ ሁኔታ ገንዘው ስርአተ ፀሎቱና ፍትሀት አድርገው በጽርሃ ጽዮን ደሴት ቀበሯቸው። የተቀበሩትም በእለት ቅዳሜ ጥቅምት 5 ቀን 1698ዓ.ም ነበር።

የእድያም ስገድ እያሡ ሞት በየቦታው በተሰማ ጊዜ ሃዘን፣ ጸጸትና ቂም በቀልን ቀሰቀሰ። የጎንደር ከተማ ካህናት፣ መዘምራን፣ ሕዝቡ በቤተመንግስቱ ዙሪያ ተሰብስቦ እያለቀሰ እየጮኸ እርስ በርስ አንገት ለአንገት ተያይዘው ሀዘናቸውን ይገልጹ ነበር።በዚያን ጊዜም የጎንደር ምድር ታወከች፤ ሰማይና ምድር ጨለማ መሰለ። በተለይም ሀዘኑ የበረታባቸው የንግስት አድባራት ደብረ ብርሃን ሥላሴ ካህናትና የሌሎች አድባራት ካህናት ልብሳቸውን ቀደው ማቅ ለበሱ፤ እስከ አርባ ቀን ድረስም ሥርአተ ቅዳሴ እያደረሱ ፍትሃት እየፈቱ የለቅሶ ጊዜያቸውን አራዘሙ።

"ዬ ዬ ዬ እያሡ ፀሃየ አሰምን ዬ ዬ ዬ እያሡ ሰርጉ ካህናቲነ፣ ዬ ዬ ዬ እያሱ ፍቁረ ዚአነ" ወይም አዬ አዬ አዬ የዓለማችን ፀሐይ፣ "አዬ አዬ አዬ የክህነታችን ሽልማት፣ አዬ አዬ አዬ የሁላችን ወዳጅ" እያሉ ሀዘናቸውንና የነበራቸውን ፍቅር ገለጹ።

ይህ አይነቱ የአለቃቀስ ስርአት አዳም ልጁ አባል በሞተበት ጊዜ ምርር ብሎ ሲያዝን እግዚአብሔር በመንፈስ ተገልጦ ቀኝ እጁን ትከሻው ላይ



በማሳረፍ አጽናናው ተብሎ ስለሚታመን ዛሬም ድረስ በጎንደርና በአካባቢው ብቻ ሳይሆን፤ በመላው ኢትዮጵያ ሰው ሲሞት ለቀስተኛው ሁሉ እየሄደ የሟች ቅርብ ዘመድ ትከሻ ላይ ቀኝ እጁን አሳርፎ ማጽናናት የተለመደ ነው።

ከዛም በኋላ የጎጃም መኳንንትና ሲታውንት አፄ ተክለሐይማኖት ሸፍተው በነበረ ጊዜ እገዛ አድርገውላቸዋልና በውለታነት "ክርስቶስ በተዋህዶ የባህሪ አምላክ መሆኑ ቀርቶ በቅብአት የባህሪ አምላክ ሆነ ብለው ያውጁልን" አሏቸው። እርጉም ተክለሐይማኖትም "ከተዋህዶዎች ጋር አከራክሬ ነው እንዲህ የማደርገው" ሲሏቸው ተቀየሙ።

ወዲያውም እርጉም ተክለሐይማኖት የንጉስነገስትነቱን ስልጣን አደላድሎ መያዙን ሲያረጋግጥ ለእናቱ ለመለኮታዊት የእቴጌነት ማእረግ፣ ለራስ ፋሬስ የእንደራሴነት ሹመት፣ ለዳርመን የጎጃምን ግዛት፣ ለጳውሎስ የበጌ ምድርን ግዛት፣ ለሌሎችም ተመሳሳይ ሹመት ሰጥተው ሀገሪቱን ለማስተዳደር ሞከሩ።

ሆኖም ጦርነት፣ የሐይማኖት ክርክር፣ ርሃብና በሽታ በየቦታው መከሰቱ ስልጣናቸውን ተፈታተነው።

በሌላ በኩልም ጎጃሞች አምደ ጽዮን የተባለ ሰው አንግሰው መዋጋት ጀመሩ። የአፄ እያሱ አንደኛ ደጋፊ የነበሩትም ሁሉንም የሕብረተሰብ ክፍል አሳድመው ይህንን ጦርነት ማገዝ ጀመሩ። የዳርመን ጦር ግን በጽናት ተዋግቶ አሸነፈ።

አፄ ተክለሐይማኖትን በጦርነት ማስወገድ ስላልተቻለም ሌላ አይነት ዘዴ ተዘየደ። እርጉሙ ተክለሐይማኖት አውሬ ማደን ይወዱ ነበርና ጎጃሜዎች በጫካ ውስጥ ለአንድ ሰው መሳሪያ ሰጥተው መሽጐ እንዲቀመጥ አደረጉ።

ተኳሹ ተደብቆ ከተዘጋጀ በኋላም በሌላ ወገን አስመስለው "በአገራችን በአገው ምድር ልዩ ልዩ አውሬ በግፍ ይገኛልና መጥተው ቢያድኑ ጥሩ ነው" የሚል የወዳጅ መልእክት አስላኩባቸው።

እርጉም ተክለሐይማኖትም በተደረገላቸው ጥሪ መሠረት በበቅሏቸው ሆነው ተጓዙና ጫካ ውስጥ ለአደን ሲዘጋጁ በተዘጋጀው ወጥመድ አማካኝነት ተነጣጥሮ በተተኮሰው ጥይት ተመተው ወደቁ። አሽከሮቻቸው በቃሬዛ ወስደው አንድ ሰው ቤት አስገብተው ቢያስተኟቸውም ሊተርፉ አልቻሉም። "ፈጣሪ የእጁን ሰጠው" እያለ ሕዝቡ ሁሉ ተደሰተ። ስለዚህ አፄ እርጉም ተክለሐይማኖት በነገሱ በሁለተኛ አመታቸው በ1700ዓ.ም ሞቱ።

## ምዕራፍ ፳፯
## የአፄ ቴዎፍሎስ ዘመነ መንግስት
## ከ1700 - 1703 ዓ.ም

በጆሮንድ ዮስጦስ፣ ደጃዝማች ህዝቅያስ፣ ዳጃዝማች ወልደ አቢብ የተባሉ ሹማምንት አፄ ቴዎፍሎስን ከወህኒ አምባ አምጥተው "አጽራር ሰገድ" አሰኝተው አነገሷቸው።

አፄ ቴዎፍሎስ የጻዲቁ ዮሐንስ ልጅ፤ የአድያም ሰገድ እያሱ ወንድም ሲሆኑ፤ የንግስና ዘመናቸው የቆየው ለሦስት አመታት ብቻ ነው።

ለንግስና የረዷቸው በጆሮንድ ዮስጦስን በራስነት ማእረግ የሰሜን የትግራይ ገዢ፣ ደጃዝማች ሕዝቅያስን የበጌምድር ገዢ፣ ደጃዝማች ወልደ አቢብን የጎጃም ገዢ አድርገው ሾሟቸው።

በነገሱ በመጀመሪያው አመትም ስልጣን በሀይል ወስደው የነበሩትን የርጉም ተክለሐይማኖትን እናት እትጌ መለኮታዊትንና አጋዥ የነበሩትን እልባተ ተስፋን ጳውሎስንና ሎሎቹን ከየአሉበት አስለቅመው በቤተመንግስታቸው አደባባይ አስገደሏቸው። በዚህም የወንድማቸውን ደም ተበቀሉ።

ደጃዝማች ዳርመን ግን ከጎጃምና ከዳሞት ግብራበሮቹ ጋር ሆኖ በመሸፈት እጅ አልሰጥም አለ። ሆኖም ፈታኝ ውጊያ ተደርጎ በጦርነቱ ቆስሎ ተማረከና እንዳደረገው ጭካኔ ሁሉ እርሱም በጦር ተወግቶ እንዲገደል ተደረገ። ከዚህ መሰል እርምጃ በኋላ በ318ቱ ርቱእነ ሊቃነ ጳጳሳት ስም ቤተክርስቲያን አሰርተው "ሀመረ ኖህ" የሚል ስያሜ ሰጧት። 318ቱ ብሉያትንና ሀዲሳትን የሚያውቁ መምህራንና መዘምራንንም በውስጧ እንዲያገለግሉ በማድረግ በርስትነት ቦታ ሰጧቸው። ይህቺን ቤተክርስቲያን በኋላ ላይ የአፄ ዮሐንስ ሦስተኛ ባለቤት አድሰው በተደራቢነት በቅዱስ ላሊበላ ስም የተባረከተ ታቦት አስገብተውባታል። 150 ካህናትና መዘምራን በመመደብም በሰቀልት ሰንበት ደብር፤ ክልል ቅዱስ ሩፋኤል፣ ድርማራ የተባሉትን ቦታዎች በርስትነት ሰጥተው ነበር። በኋላ ግን በድርቡሾች ቃጠሎ ፈርሳለች።

አፄ ቴዎፍሎስ በቀጣይነት ደፈጫ በተባለች ቦታ በኪዳነምህረት ስም ቤ/ያን አሰርተው በውስጧ 150 ካህናት እንዲያገለግሉ በማድረግ በርስትነት



ከአንገረብ እስከ ግልገል መገጭ ያለውን ቦታ ሰጧቸው። ቀጥለውም በአፄ እያሡ ጊዜ የተቃጠለውን እልፍኝ ጊዎርጊስን አሳደሱ።

በነገሱ በሁለተኛ አመታቸውም ይባባ ወደሚባል ቦታ ሄዱ። በዚህ አካባቢ በምትገኘው ደብረ መዊ የተባለች ደብር ቱጂ የተባለ የአካባቢው ነዎሪዎች ሹም በአቅራቢያው በምትገኝ አትሮንስ ማርያም በተባለች ቤ/ያን ካህናቱን አስገድሎ፣ የቤ/ያኗን ልዩ ልዩ አልባሳትና መንፈሳዊ ስእሎችን አቃጥሎ፣ 500 የሚሆኑ ተከታዮችን ይዞ መሽጎ ይኖር ነበር። አጼ ቴዎፍሎስ ወደዚህ ቦታ የሄዱትም ይህንኑ ጉዳይ ሰምተው ነበር። ውጊያ ተደረገና ቱጂ አምልጦ ሊሸሽ ሲል የአካባቢው ነዋሪዎች ከነሁለት ልጆቹ አግኝተው በመግደል እራሳቸውን ቆርጠው ወደ ንጉሱ ላኩላቸው። በዚህም እጅግ ተደስተው በድል አድራጊነት ወደ ቤተመንግስታቸው ተመለሱ።በሦስተኛው አመታቸው በወባ ተነድፈው ጥቅምት 5 ቀን 1703ዓ.ም አረፉና በእግዚአብሔር አብ ቤ/ያን ተቀበሩ።

## ምዕራፍ ፺፰
## የአፄ ዮስጦስ ዘመነ መንግስት
## ከ1703- 1708 ዓ.ም

አጼ ዮስጦስ የአፄ ቴዎፍሎስ እንደራሴ የነበሩና የራስነት ማእረግ የነበራቸው ናቸው። ከአፄ ቴዎፍሎስ እረፍት በኋላ የመንግስታቸውን ሥም ፀሐይ ሰገድ አሰኝተው ነገሱ።አፄ ዮስጦስ እንዳለፉት ነገስታት ሁሉ ጥቂት አመታት በቆየ የሥልጣናቸው ጊዜ የልደታ ቤ/ያንን አሰርተው፣ 150 ካህናትን መድበው፣ በደንቢያ ርስት መስጠታቸው ሲታወቅ፤ በነገሱ በ4ኛ አመታቸው በ1707 ዓ.ም በፀና ህመም ተይዘው ከቦታ ቦታ፣ ከገዳማት ወደ ገዳማት እየተዘዋወሩ ቢጸልዩ፤ መንፈሳዊ አባቶችን ጸልዩልኝ እያሉ ቢንተጉቱም ፈወስ ራቃቸው።

እንደታመሙ በአልጋ ላይ ሆነው ወደ ቤተመንግታቸው ተመለሱ። የአገሬው ህዝብም "የነገስታትነት ዘር የላቸውም" እያለ ውስጥ ውስጡን ከማማት አልፎ፤ አፄ ቴዎፍሎስን በመድሃኒት ገድለው ይሆናል የነገሱት" ወደሚል ሀሜት በመሸጋገር ህመማቸውን ከግፍ ጋር አይይዘው ተረጎሙት።

እውነት ይሁን ሀሰት በውል በይታወቅም አፄ ዮስጦስ የካቲት 12 ቀን 17089.ም አረፉ። አንዳንድ ጊዜ 5 አመትም እንዲህ አጭር የሚሆንበት ጊዜ አለ።



## ምዕራፍ ፺፱
## የአፄ ዳዊት 3ኛ ዘመነ መንግስት
## ከ1708- 1713 ዓ.ም

አድባር ሰገድ በሚለው ስመ መንግስታቸው የሚታወቁት አፄ ዳዊት /ሣልሣዊው ዳዊት/ ወይም ሶስተኛው ዳዊት በሚለው መጠሪያቸውም ይታወቃሉ።

በአቡነ ማርቆስና በእጨጌ ዘሚካኤል አማካኝነት ተቀብተው ዘውድ የጫኑት አጼ ዳዊት በመጀመሪያው ዓመት እጅግ የሚደነቅ ቤተ ተውኔት ነበር ያሰሩት።

ሳልሳዊው ዳዊት በገና በመደርደር ይታወቃሉ። ለኪነ ጥበብ ልዩ ፍቅርም ነበራቸው። ይህን ጉዳይ በተመለከተ የአገራችን አንጋፋ ፀሀፊ ተውኔት አያልነህ ሙላቱ ቴያትር ወደ ኢትዮጵያ መቼ እደገባ ለመግለጽ ሲሞክር "ቴአትር/ድራማ/ በዘመነ ዛግዌ ብልጭ ሳይል እንዳልቀረ" ይጠቅስና ምክንያቱንም ሲያስቀምጥ "የዛግዌ ነገስታት በቤተመንግስታቸው አጫዋቾች እንደነበሯቸውና በተለያዩ ሙዚቃዊ ድራማዎች ይዝናኑ እንደነበር" በመጠቆም፤ ነገር ግን በዋናነት በጎንደር ንጉስ በሳልሳዊው ዳዊት ጊዜ ዘመናዊ ቴአትር/ድራማ/ መሰረቱ እንደተጣለ ለመረዳት የሚያሥችል ፍንጭ እንዳለ ይገልጻል።

አፄ ዳዊት የአፄ አድያም ሰገድ እያሡ ልጅ ናቸው። በነገሱ በዓመታቸው በ1709 ዓ.ም እጅግ ያማረች ደብር የምትባለውና "ንግስተ አድባር" እየተባለች የምትጠራው የደብረ ብርሀን ስላሴ ቤ/ያን በመብረቅ ተመትታ ፈረሰች። ይህ የሆነበት ምክንያት ተብሎ በይፋ የሚታወቀው ታሪክም "አንዲት ዘማዊት ሴት በቤተመንግስት ሽቶ ተበጥብጦ የተሳለውን መንፈሳዊ ስዕል ሳትነጻ ገብታ በልብሷ (በዝሙት መንፈስ) ስታሻሻቸው መብረቅ እርሷንም ጨምሮ አቃጠላቸው" የሚል ነው።

አፄ ዳዊት ይህን ሰምተው እያዘኑ በታላቅ ለቅሶ ወደ ቤ/ን ሔዱ። አባታቸው አድያም ሰገድ እጅግ ተጠንቅቀውና አሳምረው ያሠሯት ደብር ነበረችና እንደማይሆን ሆና ሲያዩ አዝነው በ3ኛው ቀን እንደ አዲስ በሌላ መሰረት ወይም በሰቀላ ግንቡን አስጀመሩት። ከአንድ አመት በኋላም ተሰርቶ አልቆ ስርአቱ ሁሉ እንደቀድሞው ሆኖ እንዲቀጥል አስደረጉ።

በዚህም ንጉስ ብቻ ሳይሆን ህዝቡም ካህናቱም እጅግ ተደሰቱ።
ይህን ያጤነው ሊቁ ክፍለ ዮሐንስ "ዮም ኮነ ብዙኅ ትፍስሕት
እስመ ደብረታቦር ቆመ ፈጣሪ ዐዘ ደብረ ብርሀን ዳዊት"

"የዛሬዋ ቀን የብዙ ደስታዎች እለት ናት። በደብረታቦር ፈጣሪ የታየባት ሲሆን፤ አንተም ዳዊት በእለቷ በደብረታቦር ቆመህ አየንህ"

ማለት ነው። ሊቁ ክፍለ ዮሐንስ ወጣ ያለ ባህሪ ያለውና ከሌሎች ካህናት ጋር ስምምነት የሌለው ነው። እናም ይነቅፉታል። ይሉኝታ አያውቅም፤ በራሱ ይተማመናል። በፍጥነት በሚቀኛቸው ቅኔዎች አማኒይነትም ብዙ ሽልማት ስለሚያገኝ የጎንደር ሊቃውንት አይወዱትም።

አንድ ቀን አጼ ዳዊት ካህናትና ሊቃውንቱን ሁሉ ጠርተዋቸው ነበርና ሁሉም በፈረስ፣ በበቅሎ ወደ ቤተመንግስቱ ሲጓዙ ሊቁ ክፍለ ዮሐንስ ግን በእግሩ ነበር የሚሄደው። በዚህ ጊዜ በእግሩ በመሄዱ ሳቢያ ሲያፌዙበት እንዲህ አላቸው

"ብዙሃን አይዱግ በላእለ አይዱግ ሆሩ፣
ክፍለ ዮሃንስ ሊቅ እነዘ ይሐውር በእግሩ።"

ሲተረጎም "ሊቁ ክፍለ ዮሃንስ በእግሩ ሲሄድ፤ ብዙ አህዮች ግን በአህዮች ላይ ይሄዳሉ" ማለት ነው።

አንድ ቀን አጼ ዳዊት የአባታቸውን የአጼ እያሡን የሙት አሙት /13ኛ የመታሰቢያ ሙት አመት/ በአደባባይ ተክለሐይማኖትና በደብረ ብርሀን ስላሴ በማክበር ላይ ሳሉ ሊቃውንቱ ተሰብስበው ሊቁ ክፍለ ዮሃንስን አላሥጠጋው አሉ።

ይህን የታዘቡት አጼ ዳዊት "ሊቁ ክፍለ ዮሃንስ የት ነው?" ሲሉ ካህናቱ "የለም አላደረም" አሏቸው። አጼ ዳዊት ግን የካህናቱን መጠማመድ ስለሚያውቁ ብቻውን ካለበት ፈልገው አገኙትና "ሊቁ ሰው የሚኖረው መስሎ ተመሳስሎ ነው፤ ካህናት እንደ መላዕክት ናቸው፤ ስለዚህ አብሮ ተከባብሮ መኖር ይሻላል" አሉት። እርሱም እንዲህ አለ፡-
"ሰመልአክ ኢናክብሮ ለእመ አስረጸ ቆጽለ በመጠን ነዊኀ ቆሙ
ለእፍ ወለትንንያ እስመ ክንፍ ፀሙ
ወበሲበቱ ለስብዕ ኢናክብሮ ቀዲሙ
ፀዓዳ ሲበት እስመ ሀለወሙ
ለዕፀው ወአዕባን ኩሎሙ"

ማለትም "በረጅም ቁመቱ ክንፍን ቢያክልና በክንፍ ቢሸፈን መልአክን አናከብረውም፤ ወፎችና ትንኞም ክንፍ አላቸውና። ሰውን በሽበት አናከብረውም ድንጋይና እንጨትም ነጭ ሽበት አላቸውና። ሰውን በእውቀቱ እንጂ በሽበቱ አናከብረውም" ማለት ነው።

በዚህ ንግግሩ ካህናቱ ደንግጠው ክው አሉ። አጼ ዳዊት ግን ወደ ቤተመንግስታቸው ሄደው ይህ ንግግር በክብር መዝገብ እንዲመዘገብ አደረጉ። ወርቃማ ንግግር በራሱ ጥበብ ነው። ይህን መሰል ነገር ደግሞ ለአጼ ዳዊት ልዩ ነበር። አጼ ዳዊትን ዜና መዋዕላቸው ጥበብ አፍቃሪ እደሆኑ ሲገልጽ፤ የሌሎች ነገስታት ደግሞ አደን አፍቃሪ መሆናቸውን ነው የሚገልጸው።



ከዚያም አጼ ዳዊት በቅድስት ማርያም ስም እና በቅዱስ ሚካኤል ስም /አጣጣሚ ሚካኤልን/ አሰርተው 150 ካህናትን ለሁለቱም አድባራት መድበው ርስት ሰጡ።በነገሱ በ5ኛ አመታቸው ቀደም ሲል አናታቸውን የቅብዓት እማኞች "ልጅሽ ከነገሰ የቅብዓት እማኝ እንዲሆን አድርጊልን" ብለው በመሀላ ቃል አስነብተዋቸው ነበርና ከጎጃም ወደ ጎንደር መጥተው "ሳንተ የሚሻልህ ይሄ የእኛ እምነት ነው" ብለው አፄ ዳዊትን ወደ ቅብዓት እምነት መለሱዋቸው።

በዚህም ጉዳይ ካህናቱና ሊቃውንቱ ሁሉ ተበሣጭተው በአቡነ ማርቆስ የተተከሉትን አቡነ ክርስቶዶሉን ይዘው ወደ ቤተመንግስቱ ገቡ። በንጉሱ ፊት ቆመውም ተዋህዶዎችና ቅብዓቶች ለክርክር ተዘጋጁ።

በክርክሩም ተዋህዶዎች "ወልድ ክብርን ከመንፈስ ቅዱስ አይሻም። ክብሩ የባህሪው ነው" በሚለው አቋማቸው ቅብዓቶችን አሸነፉ። በዚህ ጊዜ ቅብዓት በመንግስት እውቅና አለማግኘቱን ከተረዱት ተከራካሪዎች ውስጥ አንዱ ቀድሞ ከቤተመንግስቱ በመውጣት ጃዊ የተባለውን ሃይለኛ የንጉሰነገስቱ የዘብ አለቃን ጠርቶ "ንጉሰነገስቱ እነዚህን የተዋህዶ ካህናት ሊቃውንት ሁሉንም ሲወጡ ጠብቀህ አንገት አንገታቸውን ቁረጥልኝ ብለውሀል" ብሎ ያልታዘዘውን ትእዛዝ አስተላለፈ። ይህ ሰው ዲዮስቆሮስ ይባላል።

ፈላጭ ቆራጩ ጃዊም የበታቾቹን ሁሉ አዘጋጅቶ መጠባበቅ ጀመረ። ምክንያቱም አጼ ዳዊት ቀደም ብለው ወደ ቅብዓት መግባታቸውን ያውቅ ስለነበር፣ አሁንም በዚያው የቀጠሉና ተዋህዶዎች የተሸነፉ ነበርና የመሰለው ትእዛዙን የሚጠራጠርበት ምክንያት አልነበረውም፤ መጠራጠርም አይፈልግም።

ጃዊ ካህናቱና መነኮሳቱ ሲወጡ ጠብቆ ሁሉንም በሰይፍ ተቀበላቸው። እንደተባለውም አንገት አንገታቸውን ይቆርጥ ጀመር። አይ ጃዊ እንዴት ያለ የጦር ሰው መሰላችሁ፤ በሰው ከተባለ ደስታው ነበር ይባላል። ሰይፍና ጎራዴው ስራ ከፈታ አኩርፎ ይውል ነበርም ይባላል። ያን ጊዜ በአጣጣሚ ሚካኤል መንገድ የካህናቱ ደም እየፈሰሰ ወደ አርባይቱ እንስሳ በሚወስደው መንገድ እንደ ጎርፍ ወረደ። የደሙ ጎርፍ ሄዶ የቆመበት ስፍራ ፈውስ የሚሰጥ የህይወት ጠበል ፈለቀበለት። ደመ ሰማያት ተሰኘ። ዛሬ ድረስ በአካባቢው ሰዎች ዘንድ "ዋሸ ሚዳ" እየተባለ ይጠራል። በቀድሞ ጊዜ ፍል ውሃ፣ በኋላም ቀዝቃዛ እየሆነ እንደ ፈውስ ጸበል ብዙዎችን የፈወሰ፤ የአደባባይ ተክለሐይማኖት የሀበል ቦታ ማስጥራዊ ግኝትም ሆኖ ነበር ይባላል። በኋላ ላይም ጣሊያኖች በሲሚንቶ አስገንብተው ይጠቀሙበት ነበር። አሁን ግን ተራ ምንጭ ሆኖ የቆሻሻ

ክምር ተጭኖት ይገኛል።ፈላጭ ቆራጩ ጃዊ ሁሉንም ፈጅቶ እጨጌውንም በሰይፍ ቆራርጦ ወደ አቡነ ክርስቶዶሉ ሲያመራ ጠፋበት። በዚህም አቡኑ ብቻ ተረፉ።

እንደ አንበሳ እያገሳ እየፎከረ ወደ ንጉሡ ሲሄድም ምንም የማያውቁት ንጉሡ ጩኸቱን ሰምተው ሲወጡ ነበር ሁሉንም ነገር የተረዱት። በዚህም እጅግ ተቆጥተው ዲዮስቆሮስ የተባለውን ዋሾ አስይዘው በዕኑ ስቃይ አሰቃይተው እንዲገድሉት አዘዙ። በአሰቃቂ ሞትም ሞተ።

ከዚህ በኋላም ከሞት የተረፉት የቅብዓት አማኞች በንጉስ ነገስቱ ትእዛዝ ከከተማዋ እንዲወጡ ተደረገ። አፄ ዳዊትም በሆነው ነገር እጅግ ተጸጽተውና አዝነው ራሳቸውን እንደጥፋተኛ በመቁጠር ንስሐ ገቡ።ከዚያም ንጉሠነገስቱና ህዝቡ ሁሉ 318ቱ ሊቃውንት በጉባኤ በወሰኑት በቀደሙቱ የተዋህዶ ሐይማኖት ፀንቶ እንዲኖር በአዋጅ አስነገሩ። ቀጥሎም በጽኑ ታመሙና ግንቦት 12 ቀን 1713ዓ.ም በእለተ እሁድ ህይወታቸው አለፈ።



## ምዕራፍ ፫
## የአፄ በካፋ ዘመነ መንግስት
## ከ 1713–1723 ዓ.ም

አፄ በካፋ ወይም መሲህ ሰገድ የልጅነት ቆይታቸውን ቅዱሳት መፃህፍትን በማጥናትና በመመርመር ነበር ያሳለፉት።

አፄ በካፋ የአድያም ሰገድ እያሱ ልጅ የአፄ ዳዊት ወንድም ናቸው። ቀደም ሲል በወህኒ አምባ የነበሩትን የነጋሲ ልጆች አፄ ዮሃንስ 1ኛ እንዲለቀቁ አድርገው የነበረ ቢሆንም በቀጣይ ጊዜያቶች ተመስሳዩ ልማድ ቀጥሎ ነበርና አጼ በካፋም እዚያው ወህኒ አምባ እያሉ ነበር የንጉሰ ነገስት ዘውድ እንዲጭኑ የተደረገው። ከወህኒ አምባ ሲመጡም ጳጳሱ አቡነ ክርስቶዶሉና ሊቃውንቱ፣ እንዲሁም ህዝቡ በታላቅ ደስታ ነበር ተቀብሎ ወደ ቤተመንግስቱ ያስገባቸው።

አፄ በካፋ ወዲያው እንደነገሱ "አራሽ ይረስ፣ ነጋዴ ይነግድ፣ የእጅ ሙያተኛው በጥበቡ ይስራ ... ከዚህ ወልከፍ ያለ ግን ቤቱ ይዘረፍ፣ ገንዘቡ ይቀማ" የሚል አዋጅ አወጁ።

ሐሜተኛና አሉባልተኛ በዘመኔ በሕይወት አይኖርም አይነት አቋም መያዛቸውን ለህዝቡ ይፋ ከማድረግ አልፈው፤ በቤተመንግስቱ ዙሪያ አሉባልታ ሲነዛ የተገኘን አንድ ሰው በአደባባይ እንዲሰቀል በማድረጋቸው ህዝቡ ሁሉ ወሬውን ትቶ ሥራውን ብቻ ይከውን ጀመር።

እንዳባቶቻቸው ሁሉ የራሳቸውን ቤተመንግስትም በጊቢው ውስጥ አስገነቡ። ጥቂት ቆይተውም የእጅ ጥበበኞችን ከግብፅ አገር አስመጥተው ዲሜጥሮስ እና ጊዎርጊስ ከተባሉ ሰዎች ጋር ሆነው ዘመናዊ መካከለኛ መርከብ እንዲሰራ አድርገው መርከቡ ተሰርቶ በንጉሰ ነገስቱ ተመርቆ በጣና ሃይቅ ላይ አገልግሎት እንዲሰጥ አደረጉ።

ሆኖም በዚህ መሰሉ ወሳኝ አገራዊ ስራ ሊቀጥሉ አልቻሉም። ይልቁንም እይምሯቸው መጥፎ መጥፎውን ማሰብ ጀመረ።

አፄ በካፋ ወ/ሮ አዋልደ ከተባለች ወጣት ልጃገረድ ጋር በስርዓተ ተክሊል ጋብቻቸውን ፈፅመው የንግስትነት ማዕረግ ቢያሰጧትም ባልታወቀ ምክንያት የጋብቻቸው እለት ታመው ወዲያው ስላረፉ ህዝቡና ሹማምንቱ ደነገጡ። ንጉሱም ግራ ገባቸው።

የነገስታት ልጆችንም ያለጥፋታቸው በግፍ ማስገደሉን ተያያዙት። ጥሩ ማሰብ ተሳናቸው። ወዲያውም ምንም ያላደረጉትን እህቶቻቸውን ወለተ እሩፋኤልንና ወለተ ኪዳንን አሲራችሁብኛል ብለው ገደሏቸው።

ቀጥለውም ለአደን በሄዱበት አገር በወባ ተነድፈው ታመሙና ለማገገም በአንድ ባላባት ቤት ተኝተው ሳለ•በቋራው ባላባት ሴት ልጅ

በምንትዋብ ላይ አይናቸውን ጣሉ። ይችኑ ከደጃዝማች መንበር እና ከወ/ሮ እንኮዬ የተወለደችውን ምንትዋብንም ወደ ቤተመንግስታቸው ከተመለሱ በኋላ አስመጥተው ታላቅ ድግስ ደግሰው አገቧት።

"እቴጌ ብርሃን ሞገሳ" አሰኝተው የንግስትነት ማዕረጉን እንዲይዙ አደረጉ። ከጋብቻው በኋላ እየተረጋጉ ሄዱና የእህቶቻቸው ሞት ስለፀፀታቸው፤ እንዲሁም ያለበደላቸው የቀጧቸው የነገስታት ዘሮች ሞት ከነከናቸው። ስለዚህም ያም ፀሎት አዘውታሪ ሆኑ። ንስሐም ገቡ። ከእቴጌ ምንትዋብም እያሱ የተባለ ወንድ ልጅ ወለዱ። ከዚህ በኋላ "በቅዱስ ሩፋኤል ስም ቤ/ያን እንዳሰራ የሚያዝ ራዕይ አይቻለሁ" በማለት በእህታቸው በወለተ ሩፋኤል መኖሪያ ቤት ላይ የቅዱስ ሩፋኤልን ቤተክርስቲያን በጥሩ ሁኔታ አሰሩ። 150 ካህናትንም መደቡና ለርስት ቦታ ሰጥተው በሰላም አገሪቱን መምራት ቀጠሉ። የደፈጫ ኪዳነምህረትን ቤ/ያንም አሳደሱ። ከዚህ ጊዜ በኋላ ግን ድጋሚ መጥፎ ነገር በልባቸው አደረና በተለይም የደብረብርሃን ስላሴን ካህናት በሆነ ባልሆነው አልቅሱ፤ እዘኑ እያሉ ማዘዝ ጀመሩ። ሌትም ቀንም ያለ ምክንያት ሱባኤ ግቡ፤ ወዘተ... እያሉ ያጉላሉዋቸው ገቡ። ከመጥፎ መናፍስት ትምህርት እንደቀሰመ ከሚነገርለት ከደብተራ ተዋናይ ጋርም ገጠሙ። ልዩ ልዩ የመናፍስት ጥበብን ለማወቅና ለመማርም ተጉ። በመሐልም የደብረ ብርሃን ስላሴ ካህናት ሌት ተቀን ሱባዔ ገብተው እየተላቀሱ በነበረበት ጊዜ ድንገት የአጼ በካፋ ሞት ተሰማ።

አፄ በካፋ 10 ዓመት በቆየው የግዛት ዘመናቸው ረጅሙን ጊዜያቸውን ያሳለፉት በመጥፎ ሃሳብ እንደተከበቡ ነበር። በ1723 ዓ.ም የሞቱበት ምክንያት ተብሎ የሚነገረውም የአስማተኞችን ጥበብ ለማድነቅና ለመተግበር ሲሉ በደብተራ ተዋናይ ጥበብ በአየር ላይ ሲሄዱ ድንገት የተሰጣቸውን ትዕዛዝ ተላልፈው ኖሮ አለት ላይ ተፈጥፍጠው እንደሞቱ ነው። በ37 አመታቸው የሞቱት አፄ በካፋ አፅማቸው በጣና ሃይቅ በደሴተ ቅዱስ ጊዮርጊስ ይገኛል። ባለቤታቸው እቴጌ ምንትዋብም ሞታቸው ይፋ ከመውጣቱ በፊት ከቋራ ወንድሞቻቸውን ደጃዝማች ወልደ ልዑል እሹቴን፣ ጌታ ኢውሳብዮስ ነሙና ባጠቃላይ አምስት የሚሆኑ ወንድሞቻቸውን አስጠሩ። ወገኖቻቸውን በዙሪያቸው ካደረጉ በኋላ ግን የአፄ በካፋ ሞት ለሁሉም በይፋ ተገለፀ።



## <u>ምዕራፍ ፸፩</u>
## <u>የአፄ እያሱ 2ኛ ዘመነ መንግስት</u>
## <u>ከ1723–1748 ዓ.ም</u>

አፄ በካፋ ከሞቱ በኋላ ዙፋኑን የሚወርስ እድሜው የደረሰ ልጅ አልነበረም። ስለዚህም የአፄ በካፋ ባለቤት እቴጌ ምንትዋብ የወርቅ አክሊል ደፍተውና የወርቅ ጫማ ተጫምተው "ንግስተ ነገስታት" ለመባል ተነሱ። ነገር ግን የነገስታት ዘር የለም ትም ተባሉና ከሹማምንቱና ከካህናቱ በኩል ተቃውሞ ገጠማቸው።

ስለዚህ የ8 ዓመት እድሜ የነበራቸውን እያሱን "ንጉሰ ነገስት" አሰኝተው በሞግዚትነት ማስተዳደር ጀመሩ።

የአፄ እያሱ 2ኛ ስመ መንግስት ብርሐን ሰገድ ቋረኛ እያሱ ይባላል። ቋረኛው እያሱ በእናታቸው አጋዥነት ስልጣን እንደያዙ ወዲያው ከአባታቸው ቤተመንግስት ፊት ለፊት ያለውን የተዋበ ቤተ መንግስት አስገነቡ።

ቀጥለውም በቅዱስ ፋሲለደስ ስም ተሰርቶ የነበረውን ቤተ መቅደስ አሳደሱ። ከዚያም በቀሐ ወንዝ ዳር የተሰራውን የቀሀ ኢየሱስ ቤተክርስቲያንን አደሱ። እንደገናም የመድሐኒአለምን ቤተክርስቲያን በተመሳሳይ አድሰው ተጨማሪ አገልጋዩችን መደቡ። ከነበራቸው ርስት ላይም ጨመሩላቸው።

እቴጌ ምንትዋብም ይፋ ባልሆነ መንገድ የባለቤታቸውን የአፄ በካፋን ወንድም አግብተው 3 ልጆች ወልደው ነበርና ህዝቡ፣ ካህናቱ፣ ሹማምንቱ በነቀፌታ ማጉረምረም ጀመረ። የኋለኛው ዘመን ንጉሰ ነገስት አፄ ዮሃንስ 4ኛ ከዚህ ዘር የሚመዘዙ ናቸው። በምኒልክ ጊዜ የጎጃም ንጉስ የነበሩት ተክለሃይማኖትም በተመሳሳይ የዘር ሃረጋቸው ከዚህ ከበካፋ ወንድምና ከእቴጌ ምንትዋብ ጋብቻ ጋር በተያያዘ የተወራረደ ነው። ልጃቸው ቋረኛው እያሱም ሁኔታውን ሰምተው አወገዟቸው። እቴጌም "ከዚህ በኋላ የዚህን አለም ደስታ አልፈልግም" አሉና "ንጉስ ሔሮድስ ህፃናትን እያሳረደ ሲገድል ድንግል ማርያም ኢየሱስን ይዛ በግብፅ አገር ቁስቋም በተባለ ቦታ ተሰዳ እንደቆየች ሁሉ እኔም ከከተማው ወጣ ብዬ መቀመጥ እፈልጋለሁ" አሉና ከቤተ መንግስቱ 5 ኪ. ሜትር ርቀው የጎንደር ቁስቋም ቤተክርስቲያን አሰርተው እዚያው ተቀመጡ።

እዚያም ሆነው የአፄ እያሱን መንግስት በርቀት መቆጣጠራቸውንና ማገዛቸውን ቀጠሉ። የቁስቋም ቤተክርስቲያን እንደ ሌሎቹ ታላላቅ የጎንደር አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የበርካታ ቱሪስት መናሃሪያ ሆና ዛሬ ድረስ ያለች መሆኗ እንዳለ ሆኖ፤ 1ሺ ኢትዮጵያውያን የግንባታ

ባለሙያዎች ሲገነቡ 500 ኢትዮጵያውያን ደግሞ ቆመው እያዩ ስህተቶችን ይጠቁሙ ነበር።

ግንባታው 15 አመታትን ሲፈጅ በጊቢው ውስጥ በርካታ እንቁላል ግንቦችም አብረው እንዲገነቡ ተደርጓል። እነዚህ ግንቦች የባህታውያን መኖሪያ፣ የእንግዶች ማረፊያ፣ መኝታ ቤቶች፣ ምግብ ቤቶች፣ የእቴጌዋ ልዩ የፀሎት ቦታ እና ወዘተ... የተለያዩ አገልግሎቶች የሚሰጡ ሲሆን፤ ከእነዚህ ውስጥ አንዱ ጀምስ ብሩስ የተባለው እንግሊዛዊ የታሪክ አጥኚ በ1760ዎቹ የመጀመሪያ አመታት ነበርና ወደ ኢትዮጵያ የመጣው ለ7 አመታት ያህል መኝታ ቤቱ የነበረው በቁስቋም ቤ/ያን ጊቢ ውስጥ በሚገኘው በአንዱ እንቁላል ግንብ ውስጥ ነበር። የቤ/ያኗ የውስጥ ይዘትም በልዩ ልዩ የከበሩ ንብረቶች የተሞላችና ያጌጠች ነበረች። ለዚች ቤ/ያን ግንባታ ኖራው ከከች ባጀና፣ ድንጋዩ ከአካባቢው ቋጥኞች እየተፈነቀለ፣ እንጨቱ ከአርማጭሆ ደምበቃ የመጣ ሲሆን፤ ግንባታው ተጠናቆ ፅላት እንዲገባ ተደረገና እቴጌ ምንትዋብ "ድንግል ማርያም ሔሮድስ ሞቷል" ስትባል ከቁስቋም ተነስታ ቤተልሔም የደረሰችበትን ቀን በማሰብ ህዳር 6 ቀን በየአመቱ እንዲከበር አደረጉ። በየወሩም ይከበራል።

ከዚያም 150 ካህናት ብሉያትንና ሐዲሳትን የሚያውቁ እንዲያገለግሉ ተደርገው ለሊፈ ቦታ በርስትነት ተሰጥቷቸው መንፈሳዊ ተግባራቸውን እንዲቀጥሉ ተደረገ።

እቴጌ ምንትዋብ /ብርሐን ሞገሳ/ በዚች ደብር ሆነው በርካታ ተማሪዎች እንዲማሩ በማድረግ ለፊደል ቆጣሪ እንጀራ በወጥ፣ ለዜማ ተማሪ እንጀራ በወጥ፣ አንድ ብርሌ ጠላና አንድ ብርሌ ጠጅ፣ ለቅኔ ተማሪ እንጀራ በወጥ 1 ብርሌ ጠላና 1 ብርሌ ጠጅ፣ ለትርጓሜ ተማሪ እንጀራ በወጥ 2 ብርሌ ጠላና 2 ብርሌ ጠጅ እየሰጡ፣ ልብሳቸውን በእንዶድ እያሳጠቡ አስተምረው በማስመረቅ ከከፍተኛ ሽልማትና ሹመት ጋር በተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት እንዲያገለግሉ ያደርጉ ጀመር። 365ቱን ቀናት ቤተክርስቲያኗን የሚያገለግሉ አገልጋዮችም እንዲመደቡ አድርገው ትምህርቱ ቀጣይነት እንዲኖረው አስችለዋል።

ይች ልዩ የህንፃ ጥበብ የተንፀባረቀባት ቤተክርስቲያን በ1880ዎቹ ድርቡሾች ጎንደር ገብተው ቤተክርስቲያናቱን በሚያቃጥሉበት ጊዜ ተመሳሳይ እጣ ቢገጥማትም የተረፈችውን ፍራሽ ደግሞ በዳግም የኢጣልያ ወረራ ጊዜ እንግሊዞች ጣሊያንን ለማስወጣት በየአገሩ የአውሮኘላን ድብደባ ይፈፅሙ ነበርና በዚያ ጊዜ ጣሊያኖች እንደምሽግ የሚጠቀሙት በግንብ የተሰሩትን ቤተክርስትያናት ስለነበር አንዷ ምሽጋቸው ቁስቋም ነበረችና በአውሮኘላን ተደበደበች።



በዚህ ድብደባም የተዋበው ህንፃ ብቻ ሳይሆን በውስጧ የሚገኙ ንብረቶችም በከፊል ወድመውና ተዘርፈዋል። ሆኖም ዛሬ ድረስ ቤተክርስቲያኗ አገልግሎቷ እንደቀጠለ ነው። ዛሬ ድረስም የእቴጌ ምንትዋብ አፅም በውስጧ ሲገኝ፤ በተጨማሪም በርካታ መንፈሳዊ መፃህፍትና ቅርሶች ተመናምነውም ቢሆን ተጠብቀው ይገኛሉ።

እቴጌዋም በዘመናቸው መኖሪያቸውን በዚችው ደብር አድርገው ለካህናቱ አስፈላጊውን ነገር ሁሉ እያሟሉ ነበር የቆዩት።

የወይን፣ የጠጅ፣ የስጋና የሌሎች የምግብና የመጠጥ ማቆያ ቤቶችም ሁሌ ሙሉ እንደሆኑና ካህናቱ ዘወትር ሳይጎድልባቸው በደስታ ነበርና የሚኖሩት የሌሎች አድባራት ካህናት የእቴጌዋ ልዩ እንክብካቤ ምን ይሆን ሚስጥሩ? እያሉም ይደነቁ ነበር።

ከዚህ በኋላ በአፄ እያሱና በእቴጌ ምንትዋብ መልካም ፈቃድ የእቴጌዋ ወንድም በሆነውና ከደጃዝማችነት ወደ ራስነት በተሻገረው በራስ ወልደልዑል እሸቴ አማካይነት በመጥምቁ ዮሃንስ ስም ተጨማሪ ቤ/ያን ተሰራ። ይህም የመፈራረስ አደጋው ሰለባ የነበረ ሲሆን፤ በወቅቱ 99 የሚሆኑ ካህናት ተመድበውበት ነበር። ዛሬ ድረስም ታሪካዊነቱን በግንቡ እያንፀባረቀ ውስጡን የአካባቢው ነዋሪዎች እንደገና ጠጋግነውት መንፈሳዊ አገልግሎቱን እየሰጠ ይገኛል።

አፄ እያሱ 2ኛ ወደ ወጣትነት እድሜ ተሸጋግረዋል። ስለዚህም ሰራዊታቸውን "ኑ ተከተሉኝ" በማለት ወደ ሰናር ተጓዙ። የሰናር አገረ ገዥዎች በጎንደር ዘመነ መንግስት ጊዜ ጠንካራ ንጉሰ ነገስት ሲዘምትባቸው እየገበሩ፤ አንዳንዴም በነፃነት ሳይገብሩ ነበር የሚኖሩት። አፄ እያሱ 2ኛ ሰናር ሲደርሱ የሰናሩ አገረ ገዥ አብዱ ኢብን ሻሉክ "የኢትዮጵያው ንጉሰ ነገስት ጦሩን አስከትሎ መጣ" የሚል ወሬ ሲሰማ በታላቅ ፍርሐት ፈጥኖ ያሉበት ድረስ በመምጣት በፊታቸው ሰግዶ ወርቅና ብር እጅ መንሻ አቅርቦ ያለጦርነት ሊገብር ተስማማ። በዚህም እጅግ የተደሰቱት ቋረኛው እያሱ የእንኳን ደስ ያለሽ መልዕክት ለእናታቸው ላኩ። ለቁስቋም ካህናትም እንዲሁ። በዚህም ታላቅ ደስታ በሁሉም ዘንድ ሆነ።

ሰናርን አስገብረው ወደ ጎንደር ተመልሰው አገራቱን በሰላም፣ በደስታ፤ በፍቅር ማስተዳደራቸውን ቀጠሉ።

ሆኖም በ2ኛው ዓመት የሰናሩ ንጉስ ይገብር የነበረውን ግብር ትቶ አልገብርም ብሎ ማመፁን ሰሙ። በቁጣ ሰራዊታቸውን አስከትለው ሄደው በመዋጋትም ብዙውን የኢትዮጵያ ወታደር አስጨረሱት። በታላቅ ሃዘንም የተረፉትን ጥቂት ወታደሮች አስከትለው ወደ አገራቸው ተመለሱ።

ቀጥሎ ባለው ጊዜ ደግሞ አስከፊ የውስጥ አመፅ ተነሳና አጼ እያሱና እቴጌ ምንትዋብ አጣብቂኝ ውስጥ ገቡ። የአመፁ መነሻም በአፄ በካፋ ዘመን ትልቅ ስልጣን የነበረውና በአጼ እያሱ 2ኛ የተሻረው ተንሴ ማሞ የተባለው ሰው ስልጣኑን ከተቀማበት ጊዜ ጀምሮ ወንጀለኞችንና የየአገሩን ሽፍቶች አስተባብሮ የበላይ መሪያቸው ሆኖ መነሳቱ ነው።

በርካታ ግዛቶችንም ቀስ በቀስ ይዞ "ከዚህ በኋላ ለእያሱ እንገዛም" እያለ እሳመሀና አገር ላገር እየዞረ ወረራውን ቀጠለበት። ወደ ወህኒ አምባ በሃይል ገብቶም ህዝቅያስ የሚባል ወጣት የነጋሲ ዘር አምጥቶ "አነግሳለሁ" አለ። ቀጠለናም "ወህኒ አምባን ሰብሬ እንደገባሁ ይህን ቤተመንግስትም ሰብሬ ገብቼ ድል አደርጋለሁ" እያለ ቤተመንግስቱን በተከታዮቹ ለማስከበብ እንቅስቃሴውን ቀጠለ።

በማግስቱም አፄ እያሱ 2ኛ ጳጳሱን ክርስቶዶሉንና እጨጌውን፣ እንዲሁም ልዩ ልዩ መኳንንትና ሹማምንቱን፣ እናታቸውንም ጭምር አስጠሯቸው። የተጠሩትም ወደ ቤተመንግስቱ ፈጥነው መጡ።

ንጉስ እያሱ ራስ ኤልያስ የተባለ ታማኛቸውን ሲያስጠሩት ከተንሴ ማሞ ጋር ወግኖ አልመጣም አሉቸው። ራስ ወልደልዑል የንጉሱን ጦር አስተባብረው ወደ ቤተመንግስቱ በማስገባት የጃንተከልን በር ዘግተው የገባው እንዳይወጣ፣ የወጣው እንዳይገባ ብለው በማዘዝ ዙፋኑን ለመታደግ ዝግጅት ያደርጉ ጀመር።

አፄ እያሱ የጎጃሙን ገዥ ደጃዝማች ዋሉን እና የሌሎች ግዛቶችን ሹማምንት ሰራዊታቸውን አስከትለው እንዲመጡ መልእክት ላኩ። ብዙዎች ሲመጡ ጥቂቶች ከራስ ኤልያስና ከተንሴ ማሞ ጋር ወገኑ። የቤተመንግስቱ ሁሉም በሮች ተዘጉ። "ንጉስ ነገስት ህዝቅያስ ነው" እያሉ ተንሴ ማሞና ራስ ኤልያስ ቤተመንግስቱን አስከብበው መሪሎህ ጀመሩ። ጦርነቱ አይቀሬ መሆኑ እየታወቀ ሄደ።

የአፄ እያሱ 2ኛ ሰራዊት በጃንተከር በር ተሰለፉ። ብላቴን ጌታ ኤፍሬም፣ ባላምባራስ አደሩ፣ አዛዥ ፍስሐ፣ በጅሮንድ ማሞ ከነተከታዮቻቸው አንዳንድ በር ዘግተው ያዙ። የቤተመንግስቱ አንጋቾች በአደናግር በር፣ ፊትአውራሪ ኤፍሬም በኳሊ በር፣ ደጃዝማች አረከሌድስ በአዲሱ ግንብ በር፣ ለዙፋኑ ቅርብ የሆኑ ታማኞች በተዝካሮ በር፣ ሌሎችም በሌሎች በሮች ተሰለፉ።

የአካባቢው አብያተ ክርስቲያናት አገልጋይ የሆኑ ካህናትም በያሉበት ለሀሎት ተሰማሩ። ቤተ መንግስቱ ውስጥ ምግብና መጠጥ በገፍ ተዘጋጅቶ ወታደሩ እስኪጠግብ እንዲበላ ተደረገ። እቴጌ ምንትዋብ ጥቁር ለብሰው አምላካቸውን ይለማመናሉ።



የቤተመንግስቱ ሹማምንት መስኮቶችን ከፍተው ያለውን ሁኔታ ሲያዩ ተከበዋል። ስለዚህ በጊቢው ውስጥ ያሉ ዛፎች የጠላት መመሸጊያና መንጠላጠያ እንዳይሆን በማለት ቅርንጫፎችን አስቆረጡዋቸው።

አማፅያኑም ከበባቸውን አጠናከሩት። የጎንደር ከተማ ታወከች። የመጀመሪያውን ሙከራ በሌሊት በተዝካሮ በር በኩል አደረጉ። ራስ ወልደልዑል ድል አድርገው መለሷቸው። ቀጥለው በአደናግር በር ሲሄዱ ደግሞ ባላምባራስ አደሩ ድል አድርገው መለሷቸው። ከዚያም ጠንከር ያለው ጦርነት በሁሉም በሮች በኩል ተካሔደና ብዙዎች አለቁ። የንጉሱ ጦርም ተዳከመ።

በተለይ በአደናግር በር እና በቀጭን አሸዋ በር የተሰለፉት ወታደሮች ረሐብና ጥም ፀናባቸው። ተንሴ ማሞ እና ራስ ኤልያስም በአንድ በኩል እያዋጉ በሌላ በኩል እያስጨፈሩ በእቴጌዋና በንጉስ ነገስቱ ላይ መዘባበት ያዙ።

ለተከታታይ ቀናት ያለማቋረጥ በተደረገው በዚህ ጦርነትም ህዝቡ ሁሉ በረሐብና በጥም እየተሰቃየ ያለቅስ ነበር። አማፅያኑ በጃንተከል በር በኩል ግር ብለው ሲሔዱ የተሻለ መሳሪያ የታጠቀው የንጉሱ ጦር የጥይት መአት አወረዱባቸውና ብዙዎችን ፈጁ። ሆኖም የበለጠ እየተጋጋለ እንጅ እየቀነሰ አልሄደም። በጦርነቱ መካከልም ቤተ መንግስቱ በእሳት ተቃጠለ። ቀጥሎም የቅዱስ እሩፋኤል ቤ/ያን ተቃጠለ። ብዙ እልቂት እየደረሰ መሆኑን የተገነዘቡት አፄ እያሱ ደጃዝማች ወረኛ የተባለውን ጦረኛ አስላኩበት። ደጃዝማች ወረኛ ጦሩን አስከትሎ ከጠዳ ገስግሶ መጣና ወደ ቤተመንግስቱ ተቃረበ። በዚህ ጊዜ ሁሉም በረቱ።

ካህናቱ ሊያስታርቁ ቢሞክሩ ሳይሳካ ቀረ፤ል፣ ተዋጊውም ፈረሶችም የሚበሉት ምግብ ጠፍቷል፣ አካባቢው በአማፅያኑ እየተዘረፈ እየተቃጠለ ነው፣ የቤተመንግስቱ ግንብ እየፈረሰ ነው። ስለዚህም ከውጭ በኩል የሚያጠቃ ጦር የግድ ያስፈልግ ነበርና ደጃዝማች ወረኛ ሁኔታውን ቀየረው። ከእርሱ ጋር ደግሞ የአፄ በካፋ ታማኝ የነበረው ጃዊ ነበር። በዚህ ጊዜ ከውጭና ከውስጥ የሚሰነዘረውን ጥቃት መቋቋም የተሳናቸው አማፅያን ከሐሰት ንጉሳቸው ጋር ደንግጠው ሸሹ። ጦራቸውም ያለቀው አልቆ የቀረው ተበታተነ።

ደጃዝማች ወረኛና ተከታዮቹ የሸሹትን የአመፁ አስተባባሪዎችን ተከታትለው በመክበብ ፈንጠር ላይ ከብዙ ደም መፋሰስ በኋላ ድል አደረጓቸው። ለ16 ቀናት የቆየው ይህ የከተማ ጦርነት ከተማዋን በደም አበላ ያጠበና ብዙ ኪሳራ ያደረሰ ነበር። የጦርነቱን አስከፊነት በወቅቱ የተመለከቱት ሰዎችም "ዓለም ከተፈጠረ፣ ዘመን ከተቆረ እንዲህ ያለ

ጦርነት ሆኖ አያውቅም ወደፊትም አይሆንም" ለማለት የተገደዱትም እንዲህ ያለ ደም መፋሰስ አይተው ባለማወቃቸው ነው፡፡

ደጃዝማች ወረኛ አማፅያኑ ዘርፈው የወሰዱትን ንብረት አስመልሶ ወደ ቤተመንግስቱ መጥቶ ለአፄ እያሱ እጅ መንሻ አስረከበ፡፡ የከዱተኞችንም ጭንቅላት ቆርጦ በማምጣቱ ንጉሱ እጅግ ደስ አላቸው፡፡ ህዝቡም ደስታውን ባደባባይ ሲገልፅ፤ ካህናቱ በዝማሬ አምላካቸውን አመሰገኑ፡፡ ንጉሱ ህዝቅያስም ተይዞ በእቴጌ ምንትዋብና በአፄ እያሱ ፊት ቀረበ፡፡ ጥፋቱም በዕሁፍ ተነበ አዛገሮች የሞት ፍርድ ቢፈርዱበትም ንጉሱና እቴጌዋ ምህረት እንዲያገኝ በማድረግ አስጠንቅቀው ወደ ወህኒ አምባ መለሱት፡፡ ሳይያዝ የቀረው ተንሴ ማሞ ነበርና እሱንም የወገሬ ሰዎች በሽሽት ላይ ሳለ አግኝተው ያዙትና "ኑ ውሰዱት" ብለው መልዕክት ላኩ፡፡ ባላምባራስ አደሩ ሔደው አምጥተውት በሞት ተቀጣ፡፡ አመፁ ሙሉ በሙሉ በቁጥጥር ስር ውሎ፣ የተቃጠሉት ቦታዎች ተጠግነው፣ የተዘረፉት ንብረቶች ተመልሰው በአገሪቱ ሰላም ሰፈነ፡፡ አጼ እያሱም ሁሉንም ከሽልማት ጋር ወደየመጡበት አሰናበቷቸው፡፡

ከዚህ በኋላ በነበረው ጊዜም እቴጌ ምንትዋብ የተለመደውን መንፈሳዊ ተግባራቸውን በመቀጠል በርካታ አብያተክርስቲያናትንና ገዳማትን እያደሱና እያሳነፁ፤ ጎን ለጎን ደግሞ የተዋጣለትን አለማዊ ስራ ይሰሩ ጀመር፡፡ ይኸውም በቤተመንግስቱ አጠገብ ስፊ ግንብ አስገንብተው የአገሪቱ ሴቶች በባልትና ሙያ እንዲሰማሩ ማድረጋቸው ነው፡፡ ፈትል እንዲፈትሉ፣ ጥልፍ እንዲጠልፉ፣ ሹሩባ፣ ውቅራት፣ ንቅሳት ወዘተ... የሚችሉት ለማይችሉት እንዲያስተምሩና ሁሉም በጋራ የሚሰሩትን ልዩ ልዩ ባህላዊ ጌጣጌጥም ሆነ ማናቸውንም ነገር ለቤተመንግስቱ ሹማምንትና ለህዝቡ እየሸጡ ኑሯቸውን እንዲያሻሽሉ አሰማርተዋቸዋል፡፡ ይህን ሲያደርጉም ራሳቸው አስተማሪ ሆነው ከወሃ አሰራር ጀምሮ እስከ ልዩ ልዩ የእጅ ሙያ ድረስ ተምረው ራሳቸውን እንዲችሉ አድርገዋል፡፡ በዚህም የሴቶችን የዚያ ዘመን አመለካከት በመለወጥና ወደ አደባባይ እንዲወጡ በማድረግ ረገድ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ማበርከት መቻላቸው ያስደንቃቸዋል፡፡

በ1737 ዓ.ም አቡነ ክርስቶዶሉ ስላረፉ ሌላ ጳጳስ እንዲመጣ ወደ ግብፅ መልዕክተኛ ተላከ፡፡ መልዕክተኞቹን ቱርኮች ዘርፈው ከሰደቻቸው በኋላ ሲመለሱ ደግሞ ጳጳሱንም መልእክተኞችንም አስረው አንገላቱዋቸው፡፡

ብርሐን ሰገድ እያሱ ይህን ሲሰሙ ተበሳጭተው ለተንቤኑ ገዥ ለስዑል ሚካኤል "ሔደህ የምዕዋውን ገዥ ናይብን ተበቀል" ብለው ላኩበት፡፡ ስሁል ሚካኤል ግን ከናይብ ጋር በጥቅም ተደልሎ ወግኖ ስለነበር አሻፈረኝ አለ፡፡ ስለዚህ አጼ እያሱ ራሳቸው ሰራዊታቸውን አስከትለው ወደ ትግሬ አገር ተጓዙ፡፡



ደጃዝማች ስዑል ሚካኤል የንጉሱን መምጣት አይቶ ውጊያ ለመግጠም ቢያስብም የሰራዊቱ ብዛት ስላሰጋው ሰማያት በሚባለው ተራራ ላይ ሰፈረ፡፡

አፄ እያሱም ጦራቸውን በአራት ከፍለው ተራራውን አስከበው ተኩስ አስጀመሩ፡፡ በዚህ ጊዜ እንደማይወጣው የተረዳው ስዑል ሚካኤል ለራስ ልዑል መልዕክት ልኮ ንጉሱን ይቅርታ መጠየቅ እንደሚፈልግ ገለፀ፡፡ ወዲያውም ድንጋይ በአንገቱ አስሮ መጣና ወደፊት ታዛዥ ሊሆን ቃል ገብቶ ይቅርታ ጠየቀ፡፡

አፄ እያሱ 2ኛም ምንም እንኳን ሹማምንቶቻቸው ይገደል ቢሉም "ምህረት ተደርጎለት ቢገባ በጀግንነቱ ኢትዮጵያን ይጠቅማታል" የሚል ሃሳብ ስንዝረው ወደ ጎንደር ወስደው ጥቂት አስረው ይቅርታውን ተቀብለው ፈቱት፡፡ የታሰሩት ጳጳስና መልዕክተኞችም ተለቀቁ፡፡ ቀጥሎ ባለው ጊዜ ራስ ወልደ ልዑል ሲሞት በምትኩ "ራስ" ተብሎ ተሾሞ ባለሙሉ ስልጣን እንደራሴ ሆነ፡፡ በኋላም የእቴጌ ምንትዋብን ልጅ አስቴርን /ከአጼ በካፋ ወንድም/ ከወለዷቸው ሶስት ሴት ልጆች አንዷን አግብቶ ተቀመጠ፡፡

አፄ እያሱ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ወደ ወሎ አቀኑ፡፡ ከወሎ ባላባት የተወለዱትን ውቢት የተባሉ ቆንጆ ሴት አምጥተውም ክርስትና አስነስተው ወለተ ቤርሳቤህ አሰኝተው አገቧቸውና ኢዮአስ የተባለ ወንድ ልጅ ወለዱ፡፡

በዚህም ምክንያት ከወሎና ከየጁ ባላባቶች መጥተው ሹመት እየተሰጣቸው ማገልገል ጀመሩ፡፡ ወለተ ቤርሳቤህ ግን የእቴጌነት ማዕረግ ሳይጠይቁ ለጊዜው አርፈው ተቀመጡ፡፡ አጼ እያሱ 2ኛ ባየነው መልኩ ከእናታቸው ከእቴጌ ምንትዋብ ጋር በመሆን ኢትዮጵያን ለ25 አመታት አስተዳድረው በ1748 ዓ.ም ህልፈተ ሕወታቸው ሆነና እናታቸው ባሰሯት ቁስቋም ማርያም ቤ/ያን ተቀበሩ፡፡

# ምዕራፍ ፳፪
# የአፄ ኢዮአስ ዘመነ መንግስት
# ከ1748 –1762 ዓ.ም

አፄ እያሱ 2ኛ ከሞቱ በኋላ ከወለተ ቤርሳቤህ የተወለዱት ልጅ ኢዮአስ በመንግስቱ መተካት ነበረባቸው፡፡ ቀደም ሲል እንገታቸውን ደፍተው የነበሩት ወለተ ቤርሳቤህም "የንግስትነት ማእረግ ይሰጠኝና ከልጁ ጋር ልግባ" የሚል ሐሳብ አቀረቡ፡፡ ይህ ሃሳባቸውም ከቀደምቷ እቴጌ ተዋበች ጋር አጋጫቸው፡፡

በሁለቱ ሴቶች መካከልም ክርክሩ እየበረታ በአፄ ኢዮአስ መንግስት ላይ የጎላ ተፅእኖ አሳደረ፡፡ በተጨማሪም ውዝግቡ እየተካረረ የሁለት ግለሰቦች ሀብ ከመሆን አልፎ የኢትዮጵያን ማእከላዊ መንግስት ወደመፈታተን አመራ፡፡ የወለተ ቤርሳቤህ ሃሳብ ደጋፊዎች የወሎ፣ የየጁ፣ የራያ፣ኦሮሞዎች ሉብ እና ብርሌ በተባሉ ሹማምንት እየተመሩ 1ሺ ፈረሰኛ አስከትለው ጎንደር ገቡ፡፡ ያጀቧቸው በርካታ ሰዎችም ጎንደርን አጥለቀለቋት፡፡

በዚህ ምክንያት በጎንደር በተለይም በቤተመንግስቱ ዙሪያ የኦሮምኛ ቋንቋ መነጋገሪያ እየሆነ አማርኛው ላይ ተፅእኖ አሳደረ፡፡

አፄ ኢዮአስም በኦሮምኛ ቋንቋ መናገር ጀመሩ፡፡ ሐይማኖታቸውም ላይ ተመሳሳይ ሁኔታ መንፀባረቅ ሲጀምር የጎንደር፣ የጎጃም፣ የሰሜንና የትግሬ መኳንንት እንዲሁም ካህናት በአፄ ኢዮአስ ላይ ማጉረምረም ጀመሩ፡፡

በቋረኞችና በወሎየዎች መካከልም አለመግባባቱ እየጠነከረ ሔደ፡፡ ሆኖም ከሁለቱም ወገን ውጭ የሆነው ራስ ስዑል ሚካኤል የእንደራሴነቱን ባለሙሉ ስልጣን ስለያዘው በስርዓት ማስተዳደሩን ቀጥሎ ነበር፡፡

አፄ ኢዮአስ ደግሞ የእንደራሴነቱን ስልጣን በያዘው ሰው ደስተኛ አልነበሩም፡፡ በዚህ ጊዜ ራስ ማርያም የተባለ መኳንንት በንጉሱ ላይ ሸፈተ፡፡ አጼ ኢዮአስም ይህን ሰው ራስ ስዑል ሚካኤል ብቻውን ሔዶ እንዲወጋው አዘዙትና በጎን ደግሞ ራስ ዘ ማርያምን የሚያግዝ ጦር ልከው ራስ ስዑል ድል እንዲሆን ፈለጉና የሸፈተባቸውን ሰው መርዳት ጀመሩ፡፡ ይህ ያልተለመደ አካሔዳቸው ውጤት አላስገኘም፡፡ ይልቁንም ራስ ስዑል ሚካኤል ሁሉንም ደምስሶ ድል አደረገ፡፡ የሰሩትን ስራ ግን አውቆታልና ቅሬታውን በውስጡ ይዞ ዝም አለ፡፡

ከዚያም ራስ አስራት የሚባል ሹም አመሀና ራማቸው ንጉሱ ዘምተው ወደ አማራ ሳይንት ተጓዙ፡፡ በዚህ ዘመቻም ራስ ስዑል ሠራዊቱን አስከትሎ ከንጉሡ ጎን ተሠለፈ፡፡ ሆኖም የአማራ ሣይንት ካህናት በሽምግልና ገብተና "ራስ አስራትን ይማሩልን፡፡ አይውጉትም" አሏቸው፡፡

አፄ ኢዮአስም በደስታ እሺ አሉና ለቀጣዩ በቀል ይዘጋጁ ጀመር፡፡ ራስ አስራት ንጉሡ ፊት ወድቆ ይቅርታ ጠየቀ፡፡ ካህናቱም ጥርጣሬ ስላደረባቸው



"በራስ ስዑል ሚካኤል ፊት በማሐላ ቃል ይግቡልን" አሏቸውና በራስ አስራትና በንጉሱ መካከል አንድነትና ፍቅር እንደሚኖር በመሐላ ቃል ገቡላቸው፡፡ ካህናቱም በእርቁ ተደሰቱ፡፡

ነገር ግን በ3ኛው ቀን አፄ ኢዮአስ ራስ አስራትን ሰቀሏቸውና ራሳቸውን ወደ አባይ ወንዝ አስወስደው አስጣሉት፡፡ በዚህ ጉዳይም ራስ ስዑል ሚካኤል እጅግ አዘነ፡፡ እህል አልበላም ውሃም አልጠጣም ብሎ ሰስት ቀን ሲያለቅስ ቆየ፡፡ ካህናቱም በጣም አዘኑ፡፡ ከአማራ ሳይንት ወደ ጎንደር አፄ ኢዮአስ ሲጓዙ ራስ ስዑልም ተከትሎ አብረው ጎንደር ገቡ፡፡ ከዚያም የእንደራሴዎች ካምፕ ተብሎ በተሰራው ቦታ ራስ ስዑል ከነሰራዊቱ ሔዶ ተቀመጠ፡፡

ከጥቂት ቀናት በኋላም የራስ ስዑል ወታደሮች በንጉሱ ወታደሮች ይጠበቅ ወደነበረው ወደ ማንኪት ግንብ ገብተው የጊቢውን ሳር ሲያጭዱ የንጉሱ ወታደሮች እረፉ ቢሏቸውም በንቀት ስራቸውን ቀጠሉ፡፡ እርስ በርስ ተዋግተውም የራስ ስዑል ወታደሮች አሸነፉ፡፡ ይህም ሆን ተብሎ የተደረገ ግጭት መሆኑ ግልፅ ይመስላል፡፡

አፄ ኢዮአስ ይህን ነገር ሲሰሙ በጣም ተቆጥተው ሰራዊታቸውን ማዘጋጀት ጀመሩ፡፡ ራስ ስዑልም የንጉሱን መዘጋጀት ሲሰማ ጦሩን ሰብስቦ ወደ ቤተመንግስቱ ሔደና በሩን ሰብሮ ገብቶ መዋጋት ጀመረ፡፡ በፅኑ ውጊያ ድል አደረገና አፄ ኢዮአስን ማረካቸው፡፡ ብማግስቱም ካህናቱን፣ ሊቃውንቱን የቤተመንግስቱን ሹማምንት ሁሉ ሰብስቦ "ቃል ኪዳኑን ትቶ ማሐላውን አፍርሶ ነብስ ያጠፋውን ይህን ንጉስ ምን እንደሚገባው ፍረዱ" አላቸው፡፡ "የሞት ሞት ይገባዋል" ብለው መለሱ፡፡ ሆኖም የርጉም ተክለሐይማኖት እጣ እንዳይደርሰው በማሰብ ከሁሉም ጋር ተነጋግሮ "ንጉስ በጥይት ተደብድቦ መሞት የለበትም" የሚል ስምምነት ተደረሰና በሻሽ አንቀው ገደሏቸው፡፡

እቴጌ ምንትዋብ ይህን ሲሰሙ በጣም አዘኑ፡፡ ቀብራቸውም በቅዱስ እሩፋኤል ቤተክርስቲያን በስርዓቱ ተፈፀመ፡፡ በኋላ ላይ ግን አፅማቸው ወጥቶ በቁስቋም እንዲቀመጥ ተደረገ፡፡ ዛሬ ድረስም የአባታቸው የአፄ እያሱ 2ኛ፣ የእማታቸው የእቴጌ ምንትዋብና የራሳቸው የአፄ ኢዮአስ አፅም በመስታወት ውስጥ ሆኖ ይገኛል፡፡

## ምዕራፍ ፸፫

## የአፄ ዮሐንስ 2ኛ ዘመን መንግስት

## ከ1762-1763 ዓ.ም

ራስ ስዑል ሚካኤል አፄ ኢዮአስን ካስገደሉ በኋላ ለራሱ የሚስማማውን በወህኒ አምባ ከሚቀመጡት ነጋሲያን ውስጥ የአፄ እያሱ 1ኛ/የአድያም ሰገድ እያሱ/ ልጅ የአፄ በካፋ ወንድም የሆኑትን ዮሐንስን "አድማስ ሰገድ" አሰኝቶ አነገሳቸው። አፄ ዮሐንስ 2ኛ ተባሉ።

አፄ ዮሀንስ 2ኛ ከወህኒ አምባ መጥተው ሲነግሱ ባልተለመደ ሁኔታ እድሜያቸው 70 አመት ነበር። በዚህም ላይ አንድ እጃቸው ቆራጣ ነበር፡

ስለዚህም ስማቸው በሰፊው የሚጠራው "አንድ እጁ" ዮሐንስ እየተባሉ ነው እጃቸውን ያስቆረጧቸው ደግሞ ወንድማቸው አፄ በካፋ ናቸው። አፄ በካፋ በፈጸሙት ግፍ በተጸጸቱበት ጊዜም "እኔ ከሞትኩ ይነግሣል" ብለው ከወህኒ አምባ አስመጥተው አጠገባቸው አድርገዋቸው የነበረ ቢሆንም፤ በሌሎች ተተኪዎች ከበካፋ ሞት በኋላ ወደወህኒ አምባ እንዲመለሱ ተደርጓል። አሁን ግን ነገሱ። በአንድ እጃቸው ኢትዮጵያን ሲመሩ።

በአፄ ዮሐንስ 2ኛ መንገስ ሳቢያ ህዝቡና መኳንንቱ "እንደዚህ ያለው ሰው ሊነግስ አይገባም" በማለት ከፍተኛ ክርክር ፈጥረው ነበር። ሆኖም ሰሚ አልነበረም።

አንድ እጁ አጼ ዮሐንስ በወህኒ አምባ ሲኖሩ እድሜያቸውን ሙሉ ማለትም 70 አመት ሙሉ ያሳለፉት መንፈሳዊ መጻህፍትን በመመርመርና በማጥናት ስለነበር እንደ አንድ ሊቅ የሚቆጠሩ የነገስታት ዘር ናቸው። በቅኔም የሚያክላቸው የለም።

ስለዚህ በ1762ዓ.ም በሕዳር ወር በተከበረው የአመቱ ሚካኤል እለት በአጣጣሚ ሚካኤል ቤተክርስቲያን ውስጥ ተገኝተው ቀጥሎ ያለውን ቅኔ ተቀኙ። አጠቃላይ የታሪኩን ሂደት በውስጠ ወይራ በመግለጻቸውም ብዙ ሊቃውንት ተደነቁባቸው።

ይህን ቅኔያቸውን ከግዕዝ ወደ አማርኛ መልሰን ስንተነትነው እንዲህ ይነበባል።

"የግብፅን ድንቅ ነገሮች ሙሴ እንደወደደ አደረገ፤ ለሙሴ መልዕክተኛውና የፊቱ አንጻ የኤርትራ በር ሚካኤል ነውና። የተግሳጽ ልብስ የኤርትራ ባህር መቀደዱና መሰፋቱ በእንጨት በተደረገ ጊዜ የግብጽ በትር መቀሱ ናት፤ መቀሲቱም መርፌው ናት።"

ደብልቀ ሲተነተን ደግሞ ፍሬ ነገሩ የአምላክ መልእክተኛ የሆነው ሙሴ የኤርትራን ባህር ከፍሎ ሙሴን እንዳሻገረውና የእስራኤል መሪ



እንዳደረገው፤ ራስ ስዑል ሚካኤልም ወህኒ አምባን ከፍቶ አፄ ዮሐንስ 2ኛን ንጉስ ማድረጉን ያሳያል። በተጨማሪም ሁለቱም የተለቀቁት ከባርነት መሆኑን ይገልጻል።

"የግብጽ በትር መቀሱ ናት፤ መቀሲቱም መርፌው ናት" ሲሉም የራስ ሚካኤልን ስራ መጠቀማቸው ነው።

በተጨማሪም አጼ ዮሐንስ 2ኛ አንድ እጅ ስለሌላቸው ህዝቡ ይንገስ አይንገስ እያለ ሲጨቃጨቅ በተመለከቱ ጊዜ እንዲህ ሲሉ ተቀኙ

"ጊዜ የተሐ አእላፈ እመ መክሩ እእላፈ

አንተ ዘለይኩ ወዘወሠንኩ አይታርፍ"

"ብዙ ሺህ የመከረውን ቢመክር አንተ ካሰብከውና ከወሰንከው አያልፍም" ማለት ነው።

አጼ ዮሀንስ 2ኛ እንዳሉትም ህዝቡ አንድ እጅ፤ በዚያ ላይ የ70 አመት አዛውንት ንጉስ አንፈልግም ቢልም፤ ራስ ስዑል ሚካኤልን በመፍራት የዮሀንስ 2ኛን ንግስና "ይሁን ብለናል" ብሎ ተቀበለ። ራስ ስዑል ሚካኤል እህቱን ወ/ሮ ወለተ ሥላሴን ለንጉሰነገስቱ ለአፄ ዮሐንስ 2ኛ ዳረላቸውና በማናቸውም ረገድ እራሱ ባለሙሉ ስልጣን ሆኖ አጼ ዮሃንስ "አሻንጉሊት ንጉስ" የሚባለውን ስልጣን ይዘው በዙፋኑ ተቀመጡ።

ይህ በእንዲህ እንዳለም ከአጼ በካፋ ጀምሮ ስልጣናቸው ገኖ ይኖር የነበረው ቋራቴ ምንትዋብ ስልጣንም ተወሰነ። የቀደሙት ነገስታት ይሰሩት የነበረው አይነት አሰራርም ቀረና እንደራሴው ራስ ስዑል ሚካኤል አዛዥም አስፈጻሚም ሆኖ በየአገሩ ታማኞቹንና ዘመዶቹን ብቻ እየመረጠ መሾም ጀመረ። ለልጁም ጎጃምን ሰጠው።

እቴጌ ምንትዋብም በዚሁ ጊዜ ስልጣናቸው ሲያጥር፤ እድሜያቸውም ገፋ። በራስ ስዑል አገዛዝም ተስፋ ቆረጡ፤ ስለዚህም ወደ ቁስቋማቸው ተመልሰው በፀሎትና በስግደት መኖራቸውን ቀጠሉ።

በዚህ ዘመን የነበረው ጀምስ ብሩስ የእቴጌዋን እሳዛኝ ፍጻሜም ጽፎ ነበር። እያይዞም ራስ ስዑል ሚካኤልን አውግዟል። ይህ ሰው አጼ ዮሀንስ 2ኛንም፣ ራስ ስዑል ሚካኤልንም፣ እቴጌ ምንትዋብንም በቅርበት ያነጋግራቸው ነበርና ወደ አገሩ ከተመለሰ በኋላ የአመታት የጎንደር /የኢትዮጵያ/ ቆይታውንና የጥናቱን ውጤት "BRUCE TRAVEL" በሚል ርዕስ በ5 ቮሊዩም ከፍሎ ስለ ኢትዮጵያ አጠቃላይ ሁኔታ ፅፏል። ኢትዮጵያ ውስጥ የነበረበትን ዘመን አስመልክቶም የነበረውን የስልጣን ሹክቻ ሳይጠቅስ አላለፈም። ጀምስ ብሩስ "የአባይን መነሻ ምንጭ ለመጀመሪያ ጊዜ ያገኘሁት እኔ ነኝ" ብሎም ነበር፤ ሙሉ በሙሉ ተቀባይነት ባያገኝም።

ወደ አጼ ዮሀንስ 2ኛ ታሪክ ስንመለስ፤ አንድ ፋሲል የተባለ መኳንንት በዳሞት ሸፍቶ አስቸገረ። ይህ መኳንንት ከሸፈተ ብዙ ጊዜው ነበር። አሁንም ይገባል፣ ይገብራል ተብሎ ሲጠበቅ በእምቢታው ገፋበት። ራስ ስዑል ሚካኤልም የዳሞቱን ሸፊታ ፋሲልን ለመዋጋት መዘጋጀት ጀመረ። ዝግጅቱ ከተጠናቀቀ በኋላም ንጉሱን አጼ ዮሀንስ 2ኛን "አብረን እንሄድና ፋሲልን እንዋጋው" በማለት አማከራቸው።

አጼ ዮሀንስ 2ኛ ግን በወህኒ አምባ ሲኖሩ ፀሎትና ስግደት በማዘወተር ኖሩ እንጂ የጦርነትን ነገር ፈጽሞ ሞክረውት አያውቁም ነበርና "አልችልም፤ በዚህም ላይ ሽምግያለሁ፤ ደግሞም አላውቅበትም" ብለው እምቢ አሉት። ቢያባብላቸውም በእምቢታቸው ጸኑ። ይባስ ብለውም "ብትፈልግ ወደ ወህኒ አምባየ መልሠኝ እንጂ አልሄድም" ብለው መለሱ።

በዚህም ስልጣን አልባ ባለሥልጣን መሆናቸውን ገሀድ አወጡት። ራስ ስዑል ሚካኤል የንጉሱን እምቢ ማለት በሌላ ተረጎመው። ይኸውም ለእኔ እምቢ ማለታቸው እኔ አልፍ ስል ሌላ እንደራሴ ሊሾሙብኝ አስበዋል ማለት ነው። በሚል ተርጉሞት አረፈ። ሆኖም አጼ ዮሀንስ 2ኛ እንዲህ ያለው ሃሳብ ፈጽሞ በልባቸው አልነበረም ይባላል። በአጉል ጥርጣሬ የከፋ ስጋት ላይ የወደቀው ራስ ስዑል ሚካኤልም በእጅ አዙር ንጉሱን ከምግብ ጋር ገዳይ መርዝ ቀላቅለው እንዲሰጧቸው አድርጎ አስገደላቸው። አጼ ዮሀንስ 2ኛ በነገሱ በ1ኛ አመታቸው በ71 አመታቸው በ1763ዓ.ም ነበር የተገደሉት። በዘመናቸውም እንዳችም ስራ አላከናወኑም።



## ምዕራፍ ፳፬

## የአፄ ተክለሐይማኖት 2ኛ ዘመነ መንግስት

## ከ1763-1770ዓ.ም

አጼ ዮሃንስ 2ኛ ከተገደሉ በኋላ ቀደም ባለው ጊዜ የወለዱት ልጅ 15 አመት ሞልቶት ነበርና ራስ ስዑል ሚካኤል አምጥቶ በአባቱ ዙፋን እንዲቀመጥ አደረገ።

የአጼ ዮሀንስ 2ኛ ልጅ ተክለሐይማኖት ሐያል ሰገድ ተብለው የንጉሠነገስተነቱን ስልጣን ይዘው ኢትዮጵያን ለ7 አመታት ቢያስተዳድሩም አጠቃላይ ፖለቲካዊ ጉዳዩ የሚከናወነው ግን በራስ ስዑል ሚካኤል አማካኝነት መሆኑ እንደቀጠለ ነበር።

አጼ ተክለሐይማኖት በነገሱ በመጀመሪያው አመት ባዕታ ማርያም የተባለችውን ቤተክርስቲያን በጥሩ ሁኔታ አስገነቡ። በውስጧም 277 አገልጋዮችን መድበው ርስት ሰጡ።

ቀጥለው ደግሞ በቅዱስ ቂርቆስ ስም ተጨማሪ ቤ/ያን አሰርተው 150 ካህናትን መድበው የተለመደውን ርስት ሰጡ።

ከዚያም በንጉሱ በአጼ ተክለሐይማኖት ትዕዛዝና መልካም ፈቃድ በራስ ፋረስ አማኝነት የወልደ ነጎድጓድ ዮሐንስን ቤተ ክርስቲያ በሸንተከልዋልኳ አጠገብ አሠሩ። 150 ካህናት ተደልድለው ርስትም ተሠጣቸው።

እንደገና ደጃዝማች ወንድወሰን የተባሉት የላስታ ገዢ በንጉሡ ትዕዛዝ በጻድቁ በአቡነ ተክለሐይማኖት ስም ተጨማሪ ቤ/ያ አስገነቡና ስያሜውም የላሥታው ገዢ የፈረስ ስም "ጃሌ" ይባል ስለነበር ከንጉስነገስቱ ስም ጋር አጣምረው "አባ ጃሌ ተክለሐይማኖት" ብለው ሰየሙት። "እረ በአባ ጃሌው" የሚሉ የዜማ ስንኞች መሠረታቸው ይሄ ነው። በተጨማሪም አብ እናት የሚገኘው ቅዱስ ገብርኤል ቤ/ያን በአጼ ተክለሐይማኖት ጊዜ የተሰራ ሲሆን፤ በርካታ አብያተክርስቲያናትንም በዘመናቸው አሳድሰዋል።

ራስ ስዑል ሚካኤል በእንጥልጥል የቀረውን የፋሲልን ሽፍትነት ጉዳይ አሁን እልባት ለመስጠት ፈለገና አፄ ተክለሐይማኖትን አስከትሎ ወደ ዳሞት ተጓዘ።

ፋሲልም የዳሞትንና የአገውን ጦር ይዞ ፈጊት በምትባለው ቦታ ሆኖ ይጠባበቅ ነበር። ፋጊት ላይ ሁለቱም ተገናኙና አደገኛ ጦርነት ተካሄደ።

በዚህ ጦርነት ከሁለቱም ወገን 10ሺ ወታደሮች አለቁ። ድሉ ግን የራስ ስዑል ሚካኤል ሆነ። ፋሲልም የተረፉትን ጥቂት ወታደሮች አስከትሎ ሸሸ።

ራስ ስዑል ሚካኤል ምርኮኞችን በጭካኔ አስጨፈጨፋቸው። ምህረት ጠይቀው የገቡትን ወታደሮችም የራስ ስዑል ሚካኤል ወታደሮች ባልተለመደ

ጭካኔ ቆዳቸውን ገፈው በውስጡ ጭድ እየሞሉ ለራስ ስሑል ሲያሳዩት አሳወግዛቸውም ነበር፡፡

በዚህ ጭካኔ ሳቢያ የአማራ ሳይንቱ ራስ ጎሹ እና ደጃዝማች ወንድወሰን የተባሉት ከዱት፡፡ ህዝቡም በጣም አዘነበት፡፡ ራስ ስዑል ሚካኤል አጼ ተክለሐይማኖትን ይዞ ወደ አክሱም አቀና፡፡ እዚያም ደርሶ በራሱ ትዕዛዝ ለንጉሡ የአንገሬው መኳንንት ግጸ በረከት እንዲያስገቡ አደረገ፡፡

በዚህ ጊዜ እቴጌ ምንትዋብ ከነበሩበት ቁስቋም መጥተው "የአጼ እያሱ ብርሃን ሰገድን ልጅ አንግሸለሁ" ብለው ቢያውጁም ሰሚ አልነበራቸውም፡፡

ፋሲልም የራስ ስሑልን ወደ አክሱም መሄድ ሲሰማ ሸሽቶ ከሄደበት ተነስቶ ወደ ጎንደር መጣና ወደ ቤተመንግስቱ በሃይል ሲገባ ሲል በቤተመንግስት ሹማምንትና ወታደሮች ተሸንፎ ተመለሰ፡፡

በዚህ ጊዜ ራስ ስዑል ሚካኤል ከአጼ ተክለሐይማኖት 2ኛ ጋር ተጨማሪ ሰራዊት አስከትሎ ከትውልድ አገሩ ከትግሬ አገር ወደ ጎንደር ተመለሰ፡፡ ሲደርሱም የእርሱ ታማኞች "አባሴ እንዲህ አድርጓል፤ አባሴ ይህን ሰርቷል" በሚል ነገር ሰራት ብዙዎች በጭካኔ እንዲታረዱና በጥይት እንዲደበደቡ ተደረገ፡፡

ራስ ጎሹም ከሌሎች ሹሞች ጋር ህብረት በመፍጠር በራስ ስዑል ላይ ተነሳበት፡፡ ብዙዎችም በጭካኔው ምክንያት ከእሱ እየወጡ ከጠላቶቹ ጋር ወገኑ፡፡ ስለዚህም ከነራስ ጎሹ ጋር 8 ቀን የፈጀ ሃይለኛ ጦርነት አደረገና ለመጀመሪያ ጊዜ ሽንፈት ደረሰበት፡፡ ራስ ስዑል ሚካኤልም ተማርኮ ወደ እስር ቤት ገባ፡፡ ከእርሱ ጋር ሆነው አጼ ኢዮአስ ላይ ሞት የፈረዱባቸውን ሁሉ ሰብስበውም በሞት ቀጧቸው፡፡

ግንቦት 26 ቀን 1765ዓ.ም እቴጌ ምንትዋብ ከረጅሙ የፖለቲካ ሕይወታቸውና ከረጅሙ መንፈሳዊ ሕይወታቸው፤ እንዲሁም ከእጨቃሳዩ ምድራዊ ውጣ ውረድ ተገላግለው አረፉ፡፡ ሬሳቸው ባሰሩት ቁስቋም ማርያም ቤ/ያንም ተቀበሩ፡፡

ስንመለስም ራስ ስዑል ሚካኤል ከ7 አመታት የእስር ቆይታ በኋላ እጅግ ስላረጀ ተፈትቶ ጥቂት እንደቆየ በ1772ዓ.ም በአድዋ ከተማ ሞተ፡፡

አጼ ተክለሐይማኖ 2ኛ ከ7 አመት የግዛት ዘመን ቆይታቸው በኋላ "ይህን የሚያልፍ መንግስት ትቻለሁ" ብለው መንኑና ዋልድባ ገዳም ገብተው ተቀመጡ፡፡ ገዳም ከገቡ ከ6 ወራት ቆይታ በኋላም እዚያው አርፈው በአባ ሚናስ ገዳም ተቀበሩ፡፡

አሁን ዘመነ መሳፍንት እየተቃረበ ነው፡፡ የቀሩንም ሁለት ያህል ንጉሠነገስቶች ናቸው፡፡ ለዘመነ መሳፍንት መከሰት ደግሞ በሩውን በር ከፍቶ ያሰፈው ራስ ስዑል ሚካኤል ነው፡፡ እስካሁን ያየነው እንቅስቃሴው፤ ሒደቱና ውጤቱም ይህንኑ እውነት ነው የሚያረጋግጠው፡፡ "አንድ ሹም እንዳሻው ማንገስ መሻር ከቻለማ... እኛስ....." የሚል ሃሳብ በበርካታ ምናልባትም በሁሉም መሳፍንት በንደ እንዲጸነስ ማድረጉንም በቀላሉ መረዳ ይቻላል፡፡



# ምዕራፍ ፸፫
# የአጼ ሰለሞን ዘመነ መንግስት
# ከ1770-1773 ዓ.ም

የቤተመንግስቱ ሹማምንት እንደ ደንቡ የተሸለሙትና በወርቅ ያጌጡት የንጉሰነገስት መንጎዣ የሆነችውን ውድ በቅሎ ይዘው ወደ ወህኒ አምባ ሔዱ፡፡ ሰለሞን የተባሉትን የኒጋሲ ዘር መርጠው አወጡ፡፡ እድሜ ልካቸውን በዚህ የግዞት ቦታ በሆነው በወህኒ አምባ ሥላሳለፉም "በቅሎዋ አትወጋኝም?" የሚል ጥያቄ አቅርበው እንደነበር ይነገራል፡፡ በዚህ ጊዜ ሹማምንቱ ሽማግሌውን ሰለሞንን እንደምንም ይጋግሬው በቅሎዋ ላይ አስቀመጧቸውና ወደ ቤተመንግሥቱ ይዘዋቸው ሔዱ፡፡

ህዝቡና ካህናቱም እንደ ደንቡ በዝማሬና በእልልታ ተቀበሏቸው፡፡ ጥበብ ሰገድ አሉና የወርቅ ዘውድ አቀዳጅተው በዙፋኑ ላይ አስቀመጧቸው፡፡ በቤተመንግስቱ ዙሪያ የሚገኙትን አብያተክርስቲያናት እንዲታደሱ አስደረጉ፡፡ ከከተማው ወጣ እያሉም ተመሳሳይ ተግባር ፈጸሙ፡፡

ቀጥሎም በፋሲለደስ ቤተክርስቲያን ውስጥ የነበረው የቅዱስ ፋሲለደስን ታቦት ከመጥኛው ጋር በተገነባው ህንጻ እንዲገባ አደረጉ፡፡ በዚህና በዚህ መሰል ስራቸው ህዝቡንና ካህናቱን እጅግ ደስ አሰኙ፡፡

ከ3 አመት የግዛት ዘመን በኋላም በእርጅና ምክንያት አረፉ፡፡ እድሜያቸው በውል ባይታወቅም ከ70-80 ይገመታል፡፡

## ምዕራፍ ፴፮

## የአፄ ተክለጊዮርጊስ ዘመነ መንግስት

## ከ1773-1777 ዓ.ም

የጎንደር ነገስታት ታሪካቸውን ማሳመር ካለባቸው የሚጠበቅባቸው ስራ በዘመናቸው አብያተክርስቲያናትን ማሰራት ነው። የጎንደር ነገስታት ብቻም ሳይሆን ሰፊ የነፃነት ጊዜ ያገኙት የኢትዮጵያ ነገስታት ሁሉ በግልጽ እንዳስተዋልነው ታላቅ ተግባር ከወኑ የሚባለው ይህንኑ መሰል ስራ ከሰሩ ነው።

ስለዚህም አጼ ተክለጊዮርጊስ ፍቁር ሰገድ በሚል ስመ መንግሥት የንጉሰነገስትነቱን ስልጣን ይዘው በአባቶቻቸው ዙፋን ቡተቀመጡ ማግስት ደብረ ምጥማቅ የምትባለውን በድንግል ማርያም ስም በማሰራት 500 ካህናት መድበውና ርስት ሰጥተው የፈንጠር ልደታን አሳድሰው ሲያበቁ፤ ኪዳነምህረት ተብላ የምትጠራውን ቤ/ያንም አሰርተው፤ ህዝቡን አስደሰቱ። በዘመናቸውም አቡነ ቄርሎስ የተባሉ ሌላ ጳጳስ መጡ። በ1776 ዓ.ም ግን የገንዘብና የማር ቀረጥ በህዝቡ ላይ ጣሉ። ቢዚህም ህዝቡ አጉረመረመ። ይህንንም የተመለከቱ የቤተመንግስቱ ታዛዦች በመንግስታቸው ላይ ተነሱና አመጹባቸው። በየግዛቱ ያሉትን መኳንንትም ማነሣሣት ጀመሩ። ክንፈ አዳም የተባለ ሹም ከሰሜን እንዲመጣ ተሳከበት። ክንፈ አዳም ሰራዊቱን ሰብስቦ ተጉዞ ወገራ ደረሰ። መስፈሩን በሰሙ ጊዜ አፄ ተክለጊዮርጊስ ፈርተው ወደ ጠዳ ሸሹ።

ደጃዝማች ብሌ በውቀቱ የተባለው ዘዴኛ ከክንፈ አዳም ጋር የወገነ መስሎ ሳይታሰብ ማረከውና ለአጼ ተክለጊዮርጊስ "ንጉሰ ነገስት ሆይ የምስራች፤ ጠላትህ ክንፋ ማሞ ተይዞልሃልና ፈጥነህ መጥተህ በዙፋንህ ተቀመጥ" የሚል መልእክት ለከ።

አጼ ተክለጊዮርጊስ ተመልሰው መጥተው ወደ ቤተመንግስታቸው ገቡና ለደጃዝማች ብሌ በውቀቱ ራስ ቢትወደድ የሚባለውን ሹመት ሰጡት።

ወዲያው ደግሞ ሳቡር የተባለ አገልጋያቸው ከበጌ ምድር አዛዥ ከእሸቱ ሀይሉ ጋር ወገኑና ሁለቱ ተባብረው ለየጁው መስፍን ለትልቁ ራስ አሊ እንዲህ የሚል መልእክት ላኩ "የተክለጊዮርጊስ መንግስት እዚህ ላይ ማብቃት አለበት፤ እኛም ላንተ እንገዛልሀለን፤ ከጎንህም እንሆናለን፤ እንኳን እኛ ጎንደር ያሉ ሴቶች በግጥም እየዘፈኑ "ዓሊና ዓሊና ዓሊና በሞቴ

የአማራን ማተብ ሰለችው አንገቴ" እያሉ ነው" በማለት ወዳጅነትን በሚያሳይ ቀልድ አዘል አነጋገር ሲሉክበት የየጁዉ መስፍን ትልቁ ራስ አሊ /ትንሹ ራስ አሊ የሚባል ስላለ ነው ትልቁ የተባለው/ሰራዊቱን ሰብስቦ ገሰገሰና ጎንደር ገባ።

እነ እሸቴ ሀይሉም መምጣቱን ሲሰሙ ለበጌምድር ሰዎች "ራስ አሊን እንቀበለው የሚል ሃሳብ ሲያቀርቡ ጥቂቶች ሃሳባቸውን ቀየሩ።



እሸቱ ሃይሉ በጣም ቅር አለውና "እግዚአብሔር ከልፈቀደ እንኳን ሰው እጅና እግር አይታዘዝም" በማለት ወደ ትግሬ አገር ትቶ ሲሄድ፤ራስ ወልደ ሥላሴ ራስ አሊን ፈጥኖ በደስታ ተቀበለው። እሸቴ ሀይሉም የጉዳዩ ተካፋይ ሳይሆን ጥቂት ቆይቶ ሞተ።

አጼ ተክለጊዮርጊስም ይህን ጉዳይ ሲሰሙ ከሰራዊታቸው ጋር ሆነው ከመሩለም ይልቅ የለመዱትን ሽሽት ነበር የመረጡት። ይህም ሲባል ሰራዊቱ ሁሉ በየግዛቱ መኳንንት ስር የተሰገሰገበት ሁኔታ እንጂ የነበረው፤ እንደተደመጡት ነገስታት ብዛት ያለው ወታደር በንጉሰነገስቱ ስር አልነበረም። ይህ ሁኔታም ጎልቶ መንጸባረቅ የጀመረው ከራስ ስዑል ሚካኤል እንደራሴነት ጀምሮ ነው። ስለዚህ አጼ ተክለጊዮርጊስ ጉልበቱም ወኔውም አልነበራቸውምና ሸሹ።

በዚህ ጊዜ በየግዛቱ ያሉ መሳፍንቶች "እንዴት ንጉሠነገስቱን ያባርራል?" በሚል ቁጭት ከያሉበት ተሰባሰበው ራስ አሊን ለመዋጋት ተስማሙ።

በዚህም የትግሬው ደጃዝማች ወልደ ገብርኤል፣ የሰሜኑ ራስ ገብሬ፣ የላስታው ዋግ ራስ ስዩም፣ የቆማው ራስ ደመ ክርስቶስ፣ የጎጃሙ ራስ ሃይሉ፣ የአለፋጣቁሳው ደጃዝማች ዘክርስቶስ፣ የቋራው መስፍን አዛዥ ልደት፣ ሁሉም ተሰባስበው ህብረት ፈጠሩና ጦራቸውን ይዘው ወደ ዘሰሳ ተጉዘው መደብ ተብላ በምትጠራው ቦታ ሠፈሩ።

ባጠቃላይ ከትግራይ እስከ ሸዋ ያሉት መኳንንት ሁሉ ተባምረው በምድረ መደብ ትልቁን ወጊያ አካሄዱ።

ትልቁ ራስ አሊም በዚህ ጦርነት በርትቶ ተዋግቶ ሁሉንም ድል አደረጋቸው። ራስ ደመ ክርስቶስ በውጊያው ላይ ሲሞት ደጃዝማች ወልደ ገብርኤል እና ሌሎች መኳንንቶች ወታደሮቻቸውን አስፈጅተው በየቦታው ሸሹ።

ትልቁ ራስ አሊም ከድሉ በኋላ ወደ ቤተመንግስቱ ሄዶ በቁጥጥሩ ስር አደረገው። ሆኖም ከነጋሲያን ዘር መርጦ አምጥቶ በዙፋኑ እንዲቀመጥ አደረገ እንጂ፤ ዘሎ ገብቶ ራሱን ንጉሠነገስት አድርጎ ዙፋኑ ላይ ዘፍ ለማለት አልደፈረም። ስለዚህም የአጼ ተክለጊዮርጊስ ዘመነ መንግስት ከ1773-1777 ዓ.ም ድረስ ለ4 አመታት ያህል ዘልቆ፤ ፍጻሜያቸውም በዚህ መልኩ በሽሽት ሲጠናቀቅ የኢትዮጵያ አጣፋንታም የተለየ ገጽታ ሲኖረው ግድ ሆነ።

ምክንያቱም የኢትዮጵያ ዋናው ማእከላዊ መንግስት ያስአንዳች የውጭ ወረራ በእርስ በርስ ፍጭት ብቻ አከርካሪው ተሰብሮ፤ የየግዛቱ መሳፍንት እርስ በርስ እየተናቆሩና የበላይነቱን የያዘው አሸናፊነት ንጉስ ዙፋኑ ላይ እያስቀመጠ ሲገዛ፤ ተከፋፍለው በድንበር አለፍክ ሳቢያ የብዙ ዜጎች ደም በከንቱ የሚፈስባት ምድር እንድትሆን አድርገዋታልና ነው።

ይህም ዘመን ዘመነ መሳፍንት በመባል የሚታወቀው ነው።

## ምዕራፍ ፳፯

## ዘመነ መሣፍንት፤ ከትልቁ ራስ ዓሊ እስከ ትንሹ ራስ ዓሊ ከ1777-1845 ዓ.ም

በተለምዶ ዘመነ መሳፍንት ከ1777-1845ዓ.ም ለ68 አመታት የቆየ ነበር ተብሎ ይገለፅ እንጂ፤ አጠቃላይ ጊዜውን ስናሰላው ለ86 አመታት ያህል የቆየ መሆኑን ነው የምንረዳው። ይህም ሲባል ራስ ስዑል ሚካኤል አፄ ኢዮአስን ማርኮ በሞት እንዲቀጡ ካስደረገበት ጊዜ ጀምሮ ካሣ ሀይሉ ዘውድ እስከደፋበት ጊዜ ድረስ የሚቆጠር በመሆኑ ነው። ስለዚህም የዘመነ መሳፍንት ጊዜ ከ1761-1847 ዓ.ም የቆየ ነበር። ነገር ግን ከራስ ስዑል ሚካኤል ህልፈት በኋላ በተለመደው የአነጋገስ ስርዓት ሁለት ንጉስ ነገስቶች ተከታትለው ስለነገሱ እና በነዚያ ጊዜያቶችም የመሳፍንቱ የበላይነት ገሀድ ያልወጣ በመሆኑ ምክንያት የዘመነ መሳፍንት ጊዜ ከትልቁ ራስ ዓሊ የበላይነት ዘመን ከ1777 ጀምሮ እስከ ትንሹ ራስ ዓሊ ዘመን እስከ 1845 ዓ.ም ተብሎ ሊገለጽ ችሏል።

በዘመነ መሳፍንት ጊዜ በየጊዜው የበላይነቱን ይይዙ የነበሩ መሳፍንትን የነጋሲ ዘሮችን እያመጡ በንጉሰ ነገስትነት ያነግሷቸው ነበር። በዚህ ረጅም ዘመን ውስጥም 14 ያህል ንጉሰነገስቶች ተከታትለው ነግሰዋል ባይባልም ግንብ ጠብቀዋል።

የእነዚህ ነገስታት መለዋወጥም መነሻው የመሳፍንቱ ድል ወይም ሽንፈት እንጂ ሌላ አይደለም። በሌላ አገላለጽ የስልጣናቸው እድሜ የሚወሰነው በመሳፍንቱ የትግል /የጦርነት/ ውጤት ነው። አንዱ ያነገሰውን ሌላው ያሸነፈው ያወርደውና ሌላ ንጉስ ይተካል። በመሀል ከሞቱም የበላይነቱን ያየዘው መሳፍንት የመረጠውን ያነግሣል። ስለዚህ ቀጥሰው የተዘረዘሩት ነገስታት በየዘመናቸው ምንም የፈጸሙት አገራዊ ስራ የለም፤ ሊኖርም አይችልም።

1. አጽቀ ኢያሱ 3አመት
2. ህዝቅያስ 7አመት
3. ዮናስ 1አመት
4. በእደ ማርያም 8 ወር
5. ሰለሞን 2 ወር
6. ድሚጥሮስ 3 አመት
7. ዕጓለ ፅዮን 2 አመት
8. ኢዮአስ 4 አመት
9. ጊጋር 9 አመት
10. ገብረክረስቶስ 10 አመት
11. በእደ ማርያም 1 አመት
12. ኢያሱ 4 አመት
13. ዮሃንስ 3ኛ 1 አመት
14. ሳህለ ድንግል 22 አመት



የነገስታቱ ስም እና በግንብ ግዛታ የቆዩበት ጊዜ ያየነውን ሲመስል፤ የተፈራረቁት መሳፍንት ደግሞ የበላይነቱን ይዘው የኖሩበት ዘመን በሚከተለው መልኩ ይዘረዘራል።

1. ትልቁ ራስ አሊ ከ1777-1782 ለ6 አመታት /የየጁ መኳንንት/
2. ራስ አሊጋዝ ከ 1782-1786 ለ4 አመታት
3. ራስ አስራት እና ራስ ወልደ ገብርኤል ከ1786-1792 ለ6 አመታት /የበጌ ምድር መኳንንት/
4. ራስ ጉግሣ ከ1792-1818 ለ26 አመታት /የየጁ መኳንንት/
5. የራስ ጉግሣ ልጅ ራስ ይማም ከ1818-1820 ለ2 አመታት /የጁ/
6. የራስ ይማም ልጅ ራስ ማርዬ ከ1820-1823 ለ3 አመታት
7. ራስ ዱሬ 3 ወር ገዝቶ ሲሞት፤ በምትኩ የራስ ማርየ ልጅ ትንሹ ራስ አሊ ተተኩ።
8. ትንሹ ራስ አሊ ከ1823-1845 ለ22 አመታት እንደገዛ እዚህ ዘመን ላይ የዘመነ መሳፍንት ጊዜ ተገታ። ከ1845-1847 ዓ.ም ያለው ጊዜ አፄ ቴዎድሮስ የየግዛቱን መሣፍንት እየተዋጉ ሲያሣምኑ ያለፈ ሲሆን፤ በዚህም ስኬታማ ሆነው በ1847 ዓ.ም የንጉሠነገስትነት ስልጣንን ሊይዙ ችለዋል።

በመሳፍንቱ ዘመን ሁሉም የየራሱን ወታደር ይዞ ግዛቱን ሲያስተዳድር፤ ሐይል የተሰማው ድንገት ተነስቶ ጦር ይገጥምና ካሸነፈ የሌላውን ግዛት ጠቅልሎ ይይዛል። የበለጠ ተደጋጋሚ ድል ከገጠመውም የዋናው መሳፍንት የበላይ ሆኖ ከተሿሚነት ወደ ሿሚነት ይሸጋገራል።

ባጠቃላይ በእነዚህ ዘመናት በእርስ በርስ ፍጭታቸው በርካታ ቁጥር ያለው ወታደር ያለቀ ሲሆን፤ ኢትዮጵያ ቅጥ ባጣ ሁኔታ ፍልስልሷ ወጥቶና ሰላም እርቋት ያለፈችበት ዘመን ነበር። ድፍን 68 አመቱም ያለቀው ሙሉ ለሙሉ በጦርነት ታጅቦ ነው። በእነዚህ ጊዜያቶች አንዲት ኢትዮጵያ የምትባል አገር ፈጽሞ አልነበረችም።

ይህን እስከፊ የኢትዮጵያ ገጽታ ለመለወጥ ከባድ ስራ ይጠይቅ የነበረ ሲሆን፤ አፄ ቴዎድሮስ 2ኛ ብቻ እንጂ ማንም ሊያስበውና ሊተገብረው አልሞከረም። በጽንኑነታቸው ዘመነ መሳፍንት እንዲያበቃለት ያደረጉትን ታላቅ ኢትዮጵያዊ ጀግና ታሪክም በተከታዩ ምዕራፍ ብቻ ለማጠናቀቅ ስሞክር ቅር እያለኝ ነው።

# ምዕራፍ ፪፰
# የአፄ ቴዎድሮስ 2ኛ ዘመነ መንግስት
# ከ1847 – 1860 ዓ.ም

ካሳ ሐይሉ / አፄ ቴዎድሮስ/ "ጀግና፣ እውነተኛ፣ ታማኝ፣ የማያወላውል፣ ቆራጥ፣ ደፋር፣ የራሳቸውንና የአገራቸውን ክብር የማያስደፍሩ፣ ማንንም የማይለማመጡ፣ ይቅርታን ለሚጠይቅ ምህረት የሚያደርጉ፣ ከዳተኞችን ፍዳቸውን የሚያሳዩ፣ ለኑበላቸው የማይሰስቱ፣ ትንጦት የማይወዱ፣ ራሳቸውን ከተራ ወታደር ለይተው የማያዩ፣ ከሰው ይልቅ በአምላክ የሚተማመኑ" ... ተብለው ተገልፀዋል። (ዋለልኝ እምሩ1997 ዓ.ም)

በሌላ በኩልም "ጠቢብ፣ ዕጉ፣ ፈላስፋ፣ ቆራጥ፣ ጀግና፣ ነብይ፣ ደፋር፣ ባለቅኔ፣ ባለራዕይ፣ የሃገር መሪ፣ የጦር መሪ፣ ፈረሰኛ፣ እግረኛ፣ ሰላይ፣ አይረኔ፣ ዲፕሎማት፣ ሐቀኛ፣ ሃገር ወዳድ፣ ፋና ወጊ፣ ሐይማኖተኛ፣ ሩህሩህ፣ ጨካኝ፣ ቁጡ፣ ልዩ ፍጡር፣ አልሸኛ፣ የተግባር ሰው፣ አመፀኛ፣ አይተኬ ናቸውም" ተብለዋቸዋል። ይህን ሁሉ ባህርይ አጣምረው መያዛቸውም አስደናቂ ነው።

ስለ ታላቁ ንጉስ ነገስት፣ አገርና ህዝብ ወዳድ ስለሆኑትና፣ አፍቃሪ ስለነበሩት ቴዎድሮስ ብዙዎች ብዙ ያሉላቸው ቢሆንም አጠቃላይ አካላዊ አቋማቸውንና የውስጥ ማንነታቸውን አጠገባቸው ሆኖ በደንብ የተመለከተውን ሰው ገለፃ ከወዲሁ አይተን ወደ ታሪካቸው እናልፋለን። ይህ ሰው በአፄ ቴዎድሮስ ዘመን ታስረው ከነበሩት እንግሊዛውያን ውስጥ አንዱ የነበረ ሲሆን ዶክተር ሔንሪ ብላንክ ይባላል።

"ለመጀመሪያ ጊዜ በ1852 ዓ.ም አፄ ቴዎድሮስን ሳገኛቸው እድሜያቸው 48 ይሆን ነበር። መልካቸውም ከብዙዎች ሐበሾች ጠቆር ያሉና ጠይም የሚባሉ ናቸው። አፍንጫቸው ደፍጠጥ ያለ፣ አፋቸው ሰፋ ያለ፣ ከንፈሮቻቸው ስስና ቀጠን ያሉ ነበሩ።

በፈረሰኛነታቸው፣ በጦር አወራወር ስልታቸውና በወታደርነታቸው የተመሰገኑ፣ ጠንካራ የሆነውን ጠላታቸውን ለማሸነፍ ችሎታ ያላቸው ሰው ነበሩ። ጎድጎድ ያሉት የጥቋቁር አይኖቻቸው አገላለጥ አስደንጋጭ ሲሆን፣ በሰላም ጊዜ ለስላሳ ሆነው ደስ የሚያሰኙ፣ በተቆጡ ጊዜ ደግሞ በርበሬ መስለው የሚያስደነግጡና የሚያሸብሩ እሳተ ገሞራ የሚወረውሩ ነበሩ። በድንገት ሲቆጡ መላ አካላቸው የሰውን ልጅ ክፍ ካለ ድንጋጤ ላይ ይጥላል። ጠይሙ ገላቸው ሲክስክስ፣ ስሱ ከንፈራቸው ሲንቀሳቀስና ሆራቸው ሲዘናፈል በጠቅላላው ሰውነታቸው የአንበሳነት ፀባይ የያዘ አስደንጋጭ ይሆናል" ብሏል።
(Dr. henry blank 1886)



ልጅ ካሳ ጥር 6 ቀን 1811 ዓ.ም ከቋራው ተወላጅ ከሐይሉ ወልደጊዮርጊስና ከእንፍራዟ እመቤት ከወ/ሮ አትጠገብ ወንድወሰን ነበር የተወለዱት። ምንም እንኳን አባታቸው ባላባትነት እንደነበራቸውና እናታቸው ባላባትነት ያልነበራቸው ተደርጎ ብዙ ጊዜ ቢነገርም፣ እውነታው ግን ከባላባት ዘር የተገኙት እናታቸው ወ/ሮ አትጠገብ እንጅ አባታቸው አይደሉም። ጥቂት ፀሃፊት ለዚህ መነሻ የሆናቸው የእናታቸው ኮሶ ሸጦ ልጃቸውን ማሳደግ መቻላቸው ነው። ይህም የባላባት ዘር እንዴት ኮሶ ሊሸጥ ይችላል? የሚል ጥያቄ አስነስቶ እናታቸውን ከስረኛው መደብ፣ አባታቸውን የቋራ ገዥ የነበሩና ራስ ሃይሉ ወልደጊዮርጊስ የሚባሉ እንደነበሩ ተደርጎ የተፃፈበት ሁኔታ አለ።

ሆኖም የኮሶን መድሐኒት መቀመምና የታመሙትን መፈወስ የተራው ሰው ተግባር ብቻ አይደለም። የሚሰጠውም በሽያጭ መልክ ብቻ አይደለም። በነፃም ይሰጣል። በሂደት ግን የልጅ ካሳ እናት የደኸዩበት ሁኔታ ሲፈጠር ቢችልና የሙያቸውን ውጤት ወደ ገንዘብ ማስገኛ ለውጠው ልጃቸውን ቢያሳድጉ የሚገርም አይሆንም። በተጨማሪም የባላባት ዘር ሆኖ የሚደኸይ፣ የሐብታም ልጅ ሆኖ ደሐ የሆነ ሰው ያጋጥማል። የሆነ ሆኖ ልጅ ካሳ ከእንፍራዟ/ከደንቢያ ባላባት ከተገኙት/ ከወ/ሮ አትጠገብ እና ከቋራው ተወላጅ ከሐይሉ ወልደ ጊዮርጊስ አብራክ ከፍለው ወደ ምድር መጥተዋል።

በተወለዱ በ1 አመታቸው አባታቸው ስለሞቱ እናታቸው ወ/ሮ አትጠገብ ተምረው ለወግ ማዕረግ ይበቁ ዘንድ ወደ አንድ ገዳም ወስደው ለመነኮሳቱ ሰጧቸው። በመጀመሪያ በማህበረ ስላሴ ገዳም፣ ቀጥለው በቸንክር ተክለሐይማኖት ገዳም መንፈሳዊ ትምህርትንና ዓለማዊ ትምህርታቸውን ሲከታተሉ አደጉ።

ወደ ወጣትነት ሲሸጋገሩም ከደምቢያው ባላባት ከእናታቸው ወንድም ከደጃች ክንፉ ጋር ሆነው እያገለገሉ ሳለ ገለስኝ እንግዳ ከተባለች ልጃገረድ ጋር ተጋብተው መሸሻን እና አልጣሽን ወለዱ። ትዳራቸው ግን ብዙ አልቆየም። ከዚያም ከአጎታቸው ጋር ወደጎንደር ቤተመንግስት መጡ። በቤተመንግስቱ ውስጥም ማገልገል ጀመሩ።

በአጭር ጊዜ ውስጥም በሚፈፅሟቸው የድፍረትና የጀግንነት ስራ ተወዳጅ እየሆኑ ሄዱ። በልዩ ልዩ ግዛቶች ለዘመቻ ሲሔዱም በታላቅ ጅብድ ድል እያደረጉ ምርኮም እያመጡ ለትንሹ ራስ አሊ እና ለራስ አሊ እናት ለእቴጌ መነን ልብን አመዱ በማስረከብ ታማኝ አገልጋይ ሆኑ። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ግን የኢትዮጵያ ሁኔታ በእጅጉ ያሳስባቸው ጀመር። በየመሳፍንቱ ውዝግብ የሚደርሰውን እልቂት ሲያዩም የኢትዮጵያ ተከፋፍላ መቅረት ማብቃት እንዳለበት ተገነዘቡ።

በ1830ዎቹ የግብፅ ጦር በሱዳን በኩል ኢትዮጵያን ለማጥቃትና ለመውረር ከመቸውም ጊዜ በላይ ተጠናክሮ የመጣበት ወቅት ነበር። ይህንን

ጦር ልጅ ካሳ በከፍተኛ ጀግንነት ተከላክለው በተደጋጋሚ ድል መመከት ቻሉ። በተለይ ስናር ድረስ ዘልቀው ገብተው የግብፅን ወራሪ ሃይል ድምጥማጡን አጥፍተው በመመለሳቸው እጅግ ገናና መሆናቸውን በሁሉም ዘንድ አሳወቀላቸው። ሆኖም በጦርነቱ ብዙ ጀግና ወታደሮቻቸው አለቁ። በዚህም ዘመናዊ መሳሪያ ወሳኝ መሆኑን ከመረዳታቸውም በላይ በኢትዮጵያ ኋላ ቀርነት እጅግ አዘኑ። ራስ አሊና እቴጌ መነንም ከመኳንንቱ ተወላጆች የበለጠ ወደዱዋቸው። ነገር ግን የሃይላቸው ብርታት ብዙም አላስደሰታቸውም። የልጅ ካሳ ጀግንነት ለራሳቸውም ስጋት ሆናቸው። ስለዚህ በዘዴ መያዙን መረጡና በጋብቻ ገመድ ጠፍረው ለማሰር ሲሉ የራስ ዓሊን ልጅ የእቴጌ መነንን የልጅ ልጅ ተዋበችን በሚስትነት ሰጥተው አጋቧቸውና 40 ቀን ድረስ የዘለቀ ግብግር ተካሄደ።

የደጃዝማችነት ማዕረጉንም በዚህ ጊዜ ነበር ያገኙት።

በመሐመድ አሊ ከሚመራው ከግብፅ ጦር ጋር ባደረጉት ከባድ ውጊያ በርካታ ሰራዊት ከማለቁም በላይ እራሳቸውም ቆስለው ነበር። ሆኖም ድሉ የደጃዝማች ካሳ ከመሆን አላመለጠም። ከደጃዝማች ካሳ ጋርም የባለቤታቸው ወንድም ዘምቶ እሱም ቆስሎ ነበርና ሁለቱም እንዲያገግሙ እቴጌ መነን ቁስለኛ ለሆነው ወገናቸው ጥሩ ወይፈን ሲልኩ ለደጃዝማች ካሳ አንድ አግር ወርች ስጋ ላኩላቸው።

እቴጌዋ ደጃዝማች ካሳን ዝቅ አድርገው በማየታቸው ያዘኑት ጀግናም ባለቤታቸውን ተዋበችን "ተመልከች የእናትሽን ግፍ" አሏት በምሬት። ተዋበችም በእናቷ እጅግ አዘነች። በተለይም በበርካቶች ዘንድ "ከደሐ ጋር የተጋባች" እየተባለች ትወቀስ ነበርና በንዴት ተውጣ ዝም ባለች ጊዜ "ምን ትያለሽ ተዋበች?" ብለው ሲጠይቋት "ተነሳ ነዋ የምልህ! ታጠቅ ነዋ የምልህ" የሚል መልስ ሰጠች። መልስ ሰጠች።

ይህ አጋጣሚ በውስጣቸው የተፀነሰውን ኢትዮጵያን አንድ የማድረግ ፍላጎትና ዓላማ የማሳኪያ የመጀመሪያው መንገድ ስለሆነላቸው እየተደሰቱ የዚያኑ ሊሊት የሚመሩትን ጦር አስከትለው ተዋበችንም ይዘው ሸፈቱ። ወደ ቋራ አቅንተውም በአካባቢው ባለው በርሐ ሰፈሩ። ያሸፈታቸው ግን የግል ቂም በቀል አለመሆኑን ልብ ማለት ያስፈልጋል። ይልቁንም የውጭ አገርን ወራሪ በከፍተኛ ጀብድ የመለሱ ሆነው ሳለ ገና ለገና የባላባት ዘር አይደሉምና ሁሌም ዝቅ ያለ ክብር እንደሚጠብቃቸው ከመረዳታቸውም በላይ፣ ይህ የቆየ ልማድና ባህል መቅረት እንዳለበትና ክብር በስራ እንጂ በዘር መሆኑ ያከትም ዘንድ ነው።

ወዲያውም ከእቴጌ መነን ጋር ተጣልቶ የሸፈተውን ይልማ ወሰንን አገኙትና በከፍተኛ ደስታ ተቀብሉ ክንኑ አደረጋቸው። የመረንቱን በታም ለጀግናው ካሳ ሃይሉ ለቀቀላቸው። ሀብረት ፈጥረውም የአካባቢውን ግዛት ሹማምንት ድል እያደረጉ አንዳንድ ቦታዎችን ተቆጣጠሩ።



እቴጌ መነን የደጃዝማች ካሳን መሸፈት ሲሰሙም ሄደው እንዲወጉቸው ቀኝ አዝማች ነጋሽን እና አቶ አቡየን ከብዙ ሰራዊት ጋር ላኳቸው። ደጃዝማች ካሳ በቅፅበት ድል አደረጓቸው። ራስ ዓሊና እቴጌ መነንም በፈጣኑ ሽንፈታቸው ተበሳጩ። በቤተመንግስቱ ስጋት በነገሰ ጊዜ ደጃዝማች ወንድይራድ ለትንሹ ራስ ዓሊ እና ለእቴጌ መነን ታማኝነቱንና ጀግንነቱን ለማሳየት በንቀት "ይሄን የኮሶ ሻጭ ልጅ አንጠልጥየ አመጣዋለሁ" ብሎ ፎከረና ሰራዊቱን ይዞ ተጓዘ። ወዲያውም ድል ሆኖ ተማረከ።

ደጃዝማች ካሳም ምርኮኛውን ወንድይራድን ይዘው "እናቱ ሳይሸጥላት ቀርቶ ከገበያ የተመለሰ የኮሶ መድሐኒት ስላለ፣ ላንተ የሚሆን ምግብ ስለሌለን ፈጭተህ ውሰድ" አሉና አስገንብለው እያስፈጩት "የእንቶቶ ልጅ እንቶቶ፣ የኮሶ ልጅ ኮሶ፣

,,በሽታው ያሽራል እንኳንስ ተቀምሶ።"... እያሉ የፈጨውን እያስበጠበጡ ጋቱት። ይህን የሰሙት የአገሬው ሰዎችም፦

"እንቶቶና ኮሶ ሲጠጣ ለውሶ፣
አየነው ወንድይራድ ሲፈጭ ተገንብሶ።
ወዳጁ ወንድይራድ ምነው የማይከራ
ነውር አይደለም ወይ መግባት በሰው ስራ።
ወዳጄ ወንድይራድ የሚመክረው ጠፍቶ፣
ሲፈጭ አደረ አሉ በሴት ስራ ገብቶ" እያሉ

አፌዙበት።

ወዲያውም ክልክ በላይ ጠጥቶ ነበርና ሞተ። (መድሃኒት ሲበዛ ገዳይ ነው።) እቴጌ መነን ትዕግስታቸው አልቆ ሰራዊታቸውን ሰብስበው ደጃዝማች ካሳን ለመውጋት ተነሱ። ብዙ ሰራዊት አለቀ። በውጊያውም እቴጌ ጭናቸው ላይ በጦር ተወግተው ቆስለው ተማረኩ። የመረያቸውን መማረክ አይተው የደነገጡት ተከታዮችም ሙሉ በሙሉ ድል ሆኑ። ደጃዝማች ካሳ ሃይሉ እቴጌዋን ባሳዩት ንቀት ብሰው አሳሰሯቸው።

የዚህን ጉድ ትንሹ ራስ አሊና ሹማምንቱ ሲሰሙ የካሳን እናት ወ/ሮ አትጠገብን ይዘው አሰሯቸው። በዚህ ጊዜ በሀዘኑና በካህናቱ ልመና እንዲሁም በእቴጌዋ መታሰር ስጋት ምክንያት ራስ አሊ የካህናቱን ልመና ተቀብሉ ወ/ሮ አትጠገብን ፈታቸው።

ደጃዝማች ካሳም በዚህ ተደሰቱ። በተመሳሳይም ካህናቱ ከራስ አሊ ተልከው ወደ ካሳ ሔዱ። "የአትቴ የደጃዝማች ክንፋ ግዛት ይሰጠኝና መነንን ልልቀቅ" በሚል መደራደሪያ አቀረቡ። ይህን ያሉት ያጎታቸው ግዛት ለሌላ ተሰጥቶ ስለነበር ነው።

ትንሹ ራስ አሊ ግን ከደጃዝማች ውሉ ጋር ሆኖ ካሳን መሪ እንደሚያደርግ ስለተማመነ ወዲያው እሽ አላሰም። ነገር ግን እቴጌ መነን

"የጠየቀውን ሰጥተህ ቶሎ ከዚህ መጥፎ ቦታ ካላስወጣከኝ በጦርነት አሸንፌህ ልታስፈታኝ አትችልም" የሚል መልዕክት በመላክ በተዛዋሪ የካሳን አይደፈሬነት አረጋገጡ።

ራስ አሊ መወሰን አቅቶት ባለበት ሰዓት ደጃዝማች ካሳ የጠየቁትን ግዛት ሳይቀበሉ በነፃ እቴጌ መነንን ለቀቋቸው። ነገር ግን በራሳቸው ጊዜ ከቋራ እስከደንቢያ ያለውን ግዛት ተቆጣጠሩ። እቴጌ መነንም ወደ ዋድላ ሔዱ። ካሳ ሃይሉ ቀስ በቀስ ወሰናቸውን ማስፋት ቀጠሉ። ከዚያም የጎጃሙ ገዥ ደጃዝማች ጎሹ "ወሰን ገፋህ" በሚል ካሳን ለመውጋት ልጁን ደጃዝማች ብሩን አስከትሎ ለውጊያ ወደ ጉራምባ ሄደ።

ጉራምባ ላይ ሐይለኛ ውጊያ ተደርጎ ድሉ የደጃዝማች ካሳ ሃይሉ ሆነና እነ ደጃች ጎሹ ሸሹ። የካሳ አዝማሪ በጦሩ መሐል ሆኖ ይህን ድል በተመለከተ እንዲህ ብሎ ገጠመ።

"ጎሹ አረደና ልቡ ቢዘናጋ
ጉራምባ ወረደ አንበሳን ሊወጋ
ጎሹ እስከነ ልጁ ጉራምባ ላይ ወርዶ
ያንበሳን ፊት ቢያይ ወደቀ ተዋርዶ።"

ራስ አሊ ግራ በተጋባበት ጊዜ ከጎኑ የነበሩት ደጃዝማች ውቤና የጎጃም መኳንንቶች አመፁበትና ራስ አሊ አባይን ተሻግሮ ወደ ጎጃም ተጓዘ። የእርዳታ ጥያቄውንም በየግዛቱ ላሉ ታማኞቹ ቢያቀርብ ውጤት አልባ ሆነ። ራስ አሊ በዙሪያው ያሉትን ሰብስቦ ከነበረው ሰራዊት ላይ የወረሒመኑን መኳንንት ጨምሮ ካሳ ሃይሉን ሊወጋ ተዘጋጀ።

"አይሻል" በተባለ ሜዳ ላይ ትልቅ ጦርነት አካሔደ።
ሽንፈት የማይነካቸው ጀግና ይህንንም በድል ተወጡት። ራስ ዓሊም ከመማረክ ለጥቂት ተረፈና ሸሸ።

ከዚህ ድል በኋላ ከአባቱ ጋር ሸሽቶ አምልጦ የነበረውን ደጃዝማች ብሩ ጎሹን "አዋጦ" በተባለ ቦታ ላይ ጦርነት ገጥመው ድል በማድረግ ግዛቱን ጎጃምን ወሰዱበትና ፊጥነው ወደ በጌምድር ሄዱ። ጥቂት እረፍት ባደረጉበት በዚህ ቦታ ህዝቡ "ያለ ንጉስ የቀረች አገር" እያለ ሲያጉረመርም ሰምተው "ህዝቤ ሆይ በምድረ ሰሜን "ስሜን" እስክነግርህ ድረስ ቅን ፈራጅ ንጉስ እያልክ ጥራኝ" በማለት ጮክ ብለው ተናገሩ።

ቀጥለውም በኢትዮጵያ ግዛቶች እየተዘዋወሩ፣ መኳንንቱን ሁሉ ነጣጥለው ድል እያደረጉ በቁጥጥር ስር ባደረጉት ግዛት ላይም ፍርድ እየሰጡ፣ ተከታዮቻቸውን እያበዙ ያለ ረፍት ከቦታ ቦታ ሲዘዋወሩ ቆዩ።

ከዚህ ሁሉ መኳንንት አንድ ደጃዝማች ውቤ ብቻ ነበር የቀራቸው። ደጃዝማች ውቤ በግዛቱ በሰሜን ሆኖ ለውጊያ ተዘጋጀ። ደጃዝማች ካሳም በከፍተኛ ወኔ ወደ ሰሜኑ የኢትዮጵያ ግዛት ሔደው "እንጨት ካብ" ከተባለ



ቦታ ላይ ሰፈሩ። ደጃዝማች ውቤም ደጃዝማች እሸቱ ውቤ እና ደጃዝማች ጓንጉል ውቤ የተባሉ ልጆቻቸውን ከጎናቸው አሰልፈው "መከሁ" በተባለች ስፍራ ተዘጋጅተው መጠባበቅ ጀመሩ። ሁለቱ ወገኖች ተጠጋግተው በ ዋሐት" በሚባለው ቦታ ከባድ ውጊያ አካሔዱ።

በዚህ ጦርነት ደጃዝማች እሸቱ በከፍተኛ ቁራጥነት ሲዋጋና ሲያዋጋ በጥይት ተመትቶ ሲሞት፣ ደጃዝማች ውቤና ደጃዝማች ጓንጉል ተማረኩ። ስለዚህም ድሉ ሙሉ በሙሉ የደጃዝማች ካሳ ሐይሉ ሆነና አባትና ልጁ በግዞት በጭለማ ቤት እንዲታሰሩ ተደረገ። በሚያስገርም ሁኔታም የደጃዝማች ውቤ ንብረት ተማርኮ ሲቆጠር 40 ሺ የማሪያትሬዛ ብር፣ 7 ሺ ጠመንጃ፣ ቡበኑ ጋን የተቀመጠ ወርቅ፣ ቁጥር ስፍር የሌለው ፈረስ፣ አህያ፣ ግመል፣ ላም፣ በግ፣ ፍየል፣ በወርቅ የተለበጡ አልባሳት፣ ልዩ ልዩ የከበሩ ጌጣጌጦችና የዘመኑ ውድ ምንጣፎች ወዘተ... ተገኙ። የብዛቱ ሁኔታ ያስገረማቸው ደጃዝማች ካሳም ደጃዝማች ውቤን አስጠርተው "ይህን ሁሉ ሐብት የሰበሰብከው ለምንህ ነው?" ብለው ሲጠይቁ "ለክፉ ቀኔ ብዬ" የሚል ምላሽ አገኙ። "ሰው ያለውን ከተጠቀመ ምን ክፉ ቀን አለ?" በማለት መለሱና ወደ እስር ቤቱ እንዲወስዱት አዘዙ። ደጃች ውቤ እስር ቤት እያለ ሲሞት፣ ልጁ በኋላ ላይ እንግሊዞች ሲገቡ ነበር የተፈታው። የደጃዝማች ውቤ ሬሳም ከእስር ቤት የወጣው እንግሊዞች ከመጡ በኋላ ነበር።

በድል ላይ ድል እየተጎናፀፉ እዚህ የደረሱት ጀግና ይህንን ተጨማሪ ታላቅ ድል ከተቀዳጁ በኋላ ወደ ጎንደር ቤተመንግስት በሰላም ተመለሱና ህዝቡንና ካህናቱን ሰብስበው "የመንግስት ስልጣን ይገባኛል። ምን ትላላችሁ?" ብለው ጠየቁ። ተሰብሳቢዎች ጥቂት መከሩና የዘር ሐረጋቸውን መረመሩ።

በዚህ ምርመራ በእናታቸው በኩል ከአፄ ፋሲል የሚመዘዝ የባላባትነት ሐረግ መኖሩ ተረጋገጠ። በአባታቸው በኩል ግን ፈፅሞ የባላባትነት ዘር አልተገኘም። ስለዚህ በርካታ ሊቃውንት እየተነሱ የምርመራቸውን ውጤት ለተሰብሳቢው ይፋ በሚያደርጉ ጊዜ "ለመንግስትነት የሚያበቃው በአባት በኩል ያለው የዘር ሃረግ እንጂ፣ በእናት በኩል ያለው ስላልሆነ መንግስት አይገባውም" የሚለው በረከተ። ከመጠነኛ ክርክር በኋላ መምህር አካለወልድ የተባሉ ሊቅ ተነሱና ለተሰበሰበው ሊቃውንትና መኳንንት፣ እንዲሁም ለህዝቡና ለወታደሩ እንዲህ የሚል ንግግር አደረጉ።

"ደጃዝማች ካሳ በእናቱ ሐረግ መንግስትነት ካለው መንግስት ይገባዋል። ለምሳሌ ጌታችን መድሐኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለምን ለማዳን የቻለው ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም በነሳው ስጋ አይደለምን? በአባቱማ መንግስቱም ሆነ መወለዱ በባህሪዩ የረቀቀ ነው። እንደ እውነቱ ከሆነ ከአፄ ፋሲል በእናቱ ከተወለደ መንግስት ይገባዋል ብየ ቃሌን ለጉባኤው እሰጣለሁ" ሲሉ፣ በእኒህ 81ን ብሉያትና ሐዲሳት በቃላቸው በያዙት ሊቅ ሁሉም ተገርሞ የሚመልሰው አጣ። በዚህ ጊዜ "ውድቅ ሊደረግ የማይችል

ቃል ነው እዎ መንግስት ይገባቸዋል" አሉ ሁሉም። በጣም የተደነቁት ደጃች ካሳም "ይማሯል እንደ አካልዬ፣ ይዋጋል እንደ ጉብርዬ!" በማለት ጉባኤውን መሐል ለመሐል ሰንጥቀው አልፈው መምህር አካለወልድን እትፍ አድርገው እያገላበጡ ሳሟቸው። ከዚህ በኋላ በእለተ እሁድ የካቲት 5 ቀን 1847 ዓ.ም በደረስጌ ማርያም ቤ/ያን በታላቅ ስነ-ስርዓት የንጉሰ ነገስትነት ዘውዱን ተቀዳጁ።

ስመ መንግስታቸውንም በራሳቸው ምርጫ የከዚህ ቀደሙን ትንቢያ መሰረት አድርገው "ዳግማዊ ቴዎድሮስ" አሰኙ። ጀግናው ደጃዝማች ካሳ ሃይሉ ጀግናው አፄ ቴዎድሮስ 2ኛ እየተባሉ መጠራት ጀመሩ።

አፄ ቴዎድሮስ የየግዛቱን ባላባት ስልጣን ገድበው ኢትዮጵያን በአንድ ማዕከላዊ መንግስት ስር የምትተዳደር አገር ለማድረግና የእርስ በርስ ጦርነቱን ተከትሎ የሚፈሰውን ደም ለማስቆም፣ ይልቁንም ኢትዮጵያን ስልጡንና ዘመናዊ አገር ለማድረግ ቆርጠው ተነሱ።

ለዚህ አይነቱ ጉዳይ መሳካት ሲባልም የሚጠይቀውን መስዋዕትነት መክፈል የግድ ነበር። ስልጣን በያዙ ማግስት የሚከተለውን ህግ በአዋጅ አስነገሩ። በመጀመሪያ "ግዛትና አባት ያለህ በየግዛትህና በየአባትህ ግባ። ግዛትና አባት የሌለህ ግን የእኔ አባት እሆንሃለሁ፣ ግዛትም እሰጥሃለሁ" አሉ። ቀጥለውም:-

1ኛ. ክርስትያን በክርስቲያንነቱ፣ እስላም በእስላምነቱ ሆነቶ ይቀመጥ። ነገር ግን አንዱ ከቀድሞው ሃይማኖት ወጥቶ ወደ ሌላ ሃይማኖት የገባ እንደሆነ ሰባኪውም ተሰባኪውም አንገቱ በሰይፍ ይቀረጣል። ደረቱ በጦር ይወጋል።

2ኛ. ክርስቲያን የሆነ ሁሉ ከአንዲት ሴት በቀር ሌላ አግብቶ ቢገኝ ሀብቱን ሁሉ እንዳለ ለመጀመሪያ ሚስቱ ጥሎ እንዲወጣና ርስትም ሆነ ሹመት እንዳይሰጠው።

3ኛ. ከጥንት ጀምሮ የነበረው የቁስና የደብተራ የመሬት ግብር እንደነበረ ሆኖ ይቀያል። (ይቀያል እንጅ ይሆናል አላሉም)

4ኛ. የቤተመንግስቱ ባለስልጣኖች በእለት ተግባራቸው በደሞዝ እንዲሰሩ እንጅ ባሪያ መግዛትና መሸጥ እንዳይፈፅሙ፣ ሲሸጡና ሲገዙ ቢገኙ እንደነብሰ ገዳይ በአደባባይ እንዲሰቀሉ ወይም በግዞት እንዲኖሩ፣

5ኛ. የቤት ሰራተኞች ገረድና አሽከሮች በደሞዝ ቢያገለግሉና ከአሰሪያቸው ጋር ተጣልተው ቢወጡ በውላቸው መሰረት ነገሩ ይሁድቃል፣

6ኛ. ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በሙያው እንዲሰለፍ፤ ገበሬም በግብርናው ነጋዴም በንግዱ እንዲተዳደር።

7ኛ. ገበሬው ከጥንድ በሬ በላይ የሚያርስ ከሆነና ነጋዴው ከአጋሰስ ጭነት በላይ የሚነግድ ከሆነ ግብር እንዲከፍል፤ ነገር ግን በትክሻው ተሸክሞ



የሚነግድና ቆፍሮ የሚዘራ ገበሬ ግብር ከፈል፣ መዋጮ አውጣ፣ ተብሎ እንዳይገደድና እንዳይከፍል..." የሚል አዋጅ አስነገሩ።

ከዚያም አገሬ ገኸርዎችና ዳኞች ባጠቃላይ ሹማምንቱ ደሞዝ እየተከፈላቸው እንዲሰሩ አደረጉ። 150 ሺ የሚደርሰውን ሰራዊታቸውንም በመልካም ስነ ምግባር የታነፀ እንዲሆኑና በሚከፈላቸው ደሞዝ አገራቸውን እንዲያገለግሉ በማድረግ ራሳቸውን ምሳሌ አድርገው መልካም እንቅስቃሴያቸውን ገፉበት።

ኢትዮጵያ ከነበረችበት አዘቅት ወጥታ ልዩ ገፅታ እንዲኖራት በማሰብም ማንም ደፍሮት ያልተነሳውን ዓላማ አንግበው መንግስታዊ አወቃቀሩንም፣ የጦር አደረጃጀቱንም ሆነ መኳንንቱ በፈላጭ ቆራጭነት ደሐውን ህዝብ እንዳይጫኑው በማሰብ የራስ ወዳዶችን መንግድ ሁሉ ዘጉባቸው። ጉርምርምታውንም ተቋቋሙት።

ኢትዮጵያ ከዓለም ታላላቅ አገሮች ተርታ ትሰለፍ ዘንድም ከስልጡን አገሮች ምሁራን እየመጡ ህዝባቸውን እንዲያስተምርላቸውና የቴክኒክ ድጋፍ እንዲደረግላቸው ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ከተለያዩ አገሮች ጋር ለመመስረት ሞከሩ።

በተለይም የቱርኮችን የተስፋፊነት ውጥን ለማክሸፍ የዘመናዊ መሳሪያ ባለቤት መሆንን ይመኙ ነበርና በዋናነት ከአውሮፓውያን ጋር ነበር ይጣፉ የነበረው።

ስልጣን ከያዙበት ጊዜ ጀምሮ በነበሩት ጥቂት ተከታታይ አመታትም ህዝቡን በፍቅርና በአንድነት እያስተዳደሩ፤ በሐቅ ፍርዳቸውም ድሆችን ያስደስቱ ነበር።

አፄ ቴድሮስ መንግስታቸውን አደላድለው ከያዙ በኋላ በአገሪቱ ላይ ሰላም ሰፍኖ የነበረ ቢሆንም ብዙም ሳይቆይ ግን የወሎ ህዝቦች በአህመድ በሽር መሪነት አንገዛም፣ አንገብርም ብለው አመፁ።

በዚህ ጊዜ አፄ ቴድሮስ ከጎንደር ተነስተው ወደ ወሎ ሄዱና አመፀኞችን እጅና እግራቸውን እየቆረጡ በግድ አሳምነው አስገበሯቸው። ከዚያም ወደ ሸዋ አቀኑ። በመንገድ ላይ ሳሉም የሸዋውን ንጉስ የሐይለመለኮትን ዜና እረፍት ሰሙ። እንደደረሱም የንጉስ ሃይለመለኮትን መቃብር ጎብኝተው ሃዘናቸውን ገለፁ።

የሸዋ መኳንንትም ከልጅ ምኒልክ ጋር ሆነው ሲቀበሏቸው በታላቅ ፍርሐትና አክብሮት ነበር። ቤተመንግስቱንም ከፍተው የንጉስ ሐይለመለኮትን ወርቅ፣ ብር እና ሌሎች ነገሮችን እጅ መንሻ አቀረቡ።

አፄ ቴዎድሮስም በደስታ ተቀብለው የንጉስ ሐይለመለኮትን ወንድም ሃይሌን የሸዋ መስፍን አድርገው ሾመው በሰላም አስገብረው ተመለሱ። ሲመለሱም በርካታ የሸዋ መኳንንትን አስከትለው ልጅ ምኒልክንም ይዘው ነበር ወደ ጎንደር የተመለሱት። እንደደረሱም ልጅ ምኒልክን በታላቅ ክብር

እንዲያድጉ በማድረግ፣ የደጃዝማችነት ማእረግ በመስጠትና ልጃቸውን በሚስትነት በመዳር ወደ ሉዛ ማርያም ሔደው /አዘዞ/ እንዲቀመጡና በዙሪያቸውም አብረው የመጡት የሸዋ መኳንንት እንዲያጅቧቸው አደረጉ።

ቀጥለውም ወደ ደብረታቦር ሔደው በመድሐኒአለም ስም ቤ/ያን አሰሩ። ስልጣን በያዙ በመጀመሪያው አመትም የጎንደሩን መድሐኒአለም ቤ/ያን አሳድሰውት ነበር።

ከዚያም ወደ ጎንደር ከተማ ተመልሰው በሳሙና በር አካባቢ ሰፈሩና ጥቂት ተቀምጠው ለአገሬው ህዝብ ፍርድ ሲሰጡ ቆዩ። ከዚሁ ጊዜም በወታደሮቻቸው መካከል ግጭት ተፈጥሮ ኖሮ የጥቂት ሰዎች ህይወት ጠፍቷል ተባለና ለዚህም ጥፋተኛው ራሳቸው ንጉሱ ናቸው ሲባል በሌሎች ዳኞች ፍርድ ሰጭነት ተከሰው ቅመው 500 ብር ተወስኖባቸው ካሳ ለመክፈል ችለዋል።

አፄ ቴዎድሮስ የአገሬውን ቀኝጅት ሰብስበው በኢትዮጵያ የመጀመሪያውን የቀንጅና ውድድር ያካሔዱትም በዚሁ ጊዜና ቦታ ላይ ሲሆን አንደኛ የወጣችውም ባለቤታቸው እቴጌ ተዋበች ናት።

ከዚያም ወደ አዘዞ ሉዛ ማርያም ሄደው ጥቂት ወራት ካሳለፉ በኋላ አገሪቱ ውስጥ ከፍተኛ የንሮ ውድነት ተከሰተ። በዚህም ላይ አገሬውን ገበሬ ሰብስበው ለወታደሩ ቀለብና ለተመሳሳይ መሰረታዊ ፍላጎት ማዋል መቻሉ ፈተና እየሆነባቸው ሔደ። በዚህ ጊዜ መፍትሄ ያሉትን እርምጃ ሁሉ ለመውሰድ ተገደዱ። ወዲያውም በ1851 ዓ.ም የማያፈቅሯት ባለቤታቸው ተዋበች ድንገት አረፈችና መሪር ሐዘን ውስጥ ገቡ። መሃን ነበረችና ልጅ አልወለደችላቸውም። ሆኖም ቀደም ሲል ከተጠቀሱት ሁለት ልጆች ሌላ ተጨማሪ ሁለት ልጆች አፍርተው ነበር። ከተዋበች ሞት በኋላም ሃዘናቸውን ረስተው ወዲያው እቴጌ ጥሩ ወርቅን በጋብቻ ስርዓት ቢያገቡም ፈፅሞ እንደተዋበች ሊሆኑላቸው አልቻሉም።

ብቸኛውን ልዑል አለማየሁንም ከእኒሁ ንግስት ነበር ማፍራት የቻሉት። የሆነ ሆኖ የተዋበች ሃዘን ከውስጣቸው ሊወጣ አልቻለም። እንደምንም ተረጋግተውና ብስጭታቸውን ረስተው የማስተዳደር ስራቸውን ቀጠሉ። ስለዚህም ለተከሰተው አገራዊ የኢኮኖሚ ቀውስ መፍትሔ ይሆን ዘንድ የሚከተለውን አይነት ህግ አውጥተው ተግባራዊ አደረጉ።

በመጀመሪያ ከጥንት ጀምሮ ከ24 እስከ 500 የሚደርሱ ካህናት ለየአድባራቱ አገልግሎት ይመደቡ የነበረውን የቆየ ልማድ በመሻር ለአንድ ቤተ ክርስቲያን 2 ቄስና 3 ዲያቆን ብቻ እንዲያገለግል ሲያደርጉ፤ የቀረው አገልጋይ ከምርት ተግባር ላይ ተሰማርቶ እንዲተዳደር ደነገጉ።

የየአድባራቱ በርስትነት የተሰጠው መሬት ተነጥቆ ለወታደሩ እንዲከፋፈል ተብሎ ሲታወጅም ቀደም ሲል በወጣው ህግ ይደመጥ የነበረው ጉርምርምታ ተባባሰ።



በተለይ የቤተክህነት ሰዎች ክፉኛ ተቆጡ። ከጳጳሱ ከአቡነ ሰላማ ጋርም ሃይለኛ ግጭት ውስጥ ገቡ። አፄ ቴዎድሮስም "ለኢትዮጵያና ለህዝቧ አስፈላጊ እስከሆነ ድረስ ከዚህም ያለፈ ተግባር ልፈፅም እችላለሁ" የሚል አቋማቸውን ሲገልፁ ጳጳሱና ካህናቱ አወገዟቸው። በወቅቱ ደግሞ የካህናት አመፅና ግዝት በቀላሉ የሚታይ አልነበረም። የቃላት ምልልሱ ከጳጳሱ ጋር እየተደረገ እየተካረረ በመሔዱም ተሰዳደቡ። አፄ ቴዎድሮስም እጅግ ተቆጥተው "ከሴቶች ጋር በስውር ሲወስልት አይቸዋለሁ" በማለት ራሳቸውን ምስክር አድርገው ቀረቡ። በዚህ ጊዜ ጳጳሱ እጅግ ተበሳጭተው "ልዑል እግዚአብሔር በሚያመጣው መቅሰፍት ይቅሰፍህ፣ ከከዳተኛው ይሁዳ ጋር እድል ፈንታህ ይሁን" ብለው ተራገሙ ይባላል።

እኒህን ጳጳስ በተመለከተ እንግሊዛዊው ሚስተር ሆርሙዝ ራሳም ሲገልፅ "ጳጳሱ ተንኮለኛ፣ አወናባጅ፣ የሐይማኖት ጉዳዮችን እየተወ በአገሪቱ የፖለቲካ ጉዳይ ጣልቃ እየገባ የሚያውክ ጠማማ ሰውና ለገንዘብ ሲል ተገዝቶ የመጣ ተራ ባሪያ ነበር" ብሏል።

የሆነ ሆኖ አፄ ቴዎድሮስ በዚህ እርግማን እጅግ ተናደው አቡነ ሰላማን አሰሩና እድባራቱንና ገዳማቱን ማፍረስ ጀመሩ። ካህናቱም አመፁን ሲያቀጣጥሉት በየግዛቱ ያሉና ስልጣናቸው የተገደበባቸው መኳንንቶች ደግሞ ምቹ ሁኔታ ተፈጠረላቸው።

ባጠቃላይ ንጉሰ ነገስቱ ለአገርና ለህዝብ ብለው የቀየሱት ዘዴ ከየአቅጣጫው ተቃውሞ አስነሳባቸው። የተረጋጉ የነበሩት ቴዎድሮስ ቁጡው ማንነታቸው ገንፍሎ ወጣ። ካህናቱን እጣን ጠባሽ፣ ፈሳ መሪ፣ ራሱን ታጣቂ፣ ወገቡን ሰባቂ... እያሉ ይዘልፏቸው ጀመር።

ብዙዎችንም ወደ እስር ወስደው አጎሯቸው። አንዳንዶችን ወደ ገደል አስወረወሩዋቸው። ሩቅ እያሰቡ ቅርብ እንዲያድሩ የሚያስገድዷቸውን ሁሉ እሳት እንድደው ወደ እሳት ጨመሯቸው። የቀሩትን በጦር አስወጓቸው።

ካህናቱን "አርሳችሁ ብሉ" ብለው መወሰን በወቅቱ በእርግጥም ከባድ ነበርና ይህን ሁሉ በካህናቱ ላይ ፈፅመው እንኳ ከማመፅ ወደ ኋላ ያለ የለም። ስለዚህም አፄ ቴዎድሮስ የካህናቱን አመፅ መቋቋም ተሳናቸውና የጎንደርን መናገሻነት ትተው ደብረታቦርን አጠናከሩ።

ከአራት አመት በኋላም ወደ ጎንደር ተመልሰው የየቤተመቅደሱን ንዋየ ቅድሳትና መፃህፍቱን ሁሉ ጠቅልለው ወደ ደብረታቦር አጋዙት። የደብረብርሃን ስላሴን ደወል ሳይቀር አያስንቱ ወሰዱት። የጎንደርን ከተማ ጭር እንድትል አደረጓት። ካህናቱንም ሁሉ ሰብስበው ከደብረታቦር 112 ኪሎ ሜትር በምትርቀው መቅደላ በግዞት አስቀመጡዋቸው። ደጃዝማች ምኒልክም ከወገኖቻቸው ጋር ወደ መቅደላ ተወስደው ነበርና በሌሊት ወጥተው አብረዋቸው ከነበሩት ከሸዋ መኳንንት ጋር በፈረስ አመለጡ።

ንጉሱ በዚህም እጅግ ተበሳጭተና ምኒልክ እንዲያመልጥ ረድታችኋል ያሏቸውን 24 የወሎ መኳንንት ወደ ገደል ወርውረው ገደሏቸው።

ፋታ ባልነበረው ሁኔታ ከየአቅጣጫው የቀድሞ ሹማምንት ሲሸፍቱም በየቦታው እየሄዱ መዋጋት የለት ተለት ተግባራቸው ሆነ። "ወደ ደቡብ ብሔድ በሰሜን ያለው ህዝብ ያምፃል፣ ወደ ምዕራብ ብሔድ የምስራቁ ይሸፍታል። በየጊዜው ይቅርታ ባደርግላቸውም በአመፃቸው እየገፉ አሻፈረኝ ይሉኛል። አሁን ግን በየአቅጣጫው እያሳደድኩ ስጋቸውን ወደ መቃብር ነብሳቸውን ወደ ሲኦል ለመላክ ቆርጫለሁ" በማለት በየቦታው እየተዘዋወሩ አመፀኞችን እየያዙ የግፍ አገዳደል ይፈፅሙባቸው ጀመር።

የህዝቡ፣ የካህናቱና የሹማምንቱ አመለካከት ፈፅሞ ከአፄ ቴዎድሮስ ራዕይ ጋር ሊቀራረብ አልቻለም። በርካቶችም ይዘውት የተነሱትን ዓላማ በውል ሊረዱላቸው አልቻሉም። ይህ ሰፊ ክፍተትም ለቴዎድሮስ ከማበሳጨትም በላይ መሆኑን በቀላሉ መረዳት ይቻላል።

ሁኔታው በዚሁ ቀጥሎ በነበረበት ጊዜም የትግራዩ ባላባት ደጃዝማች ንጉሴ ወልደሚካኤል ከጣልያንና ከፈረንሳይ መንግስት ጋር 20 አመታት የፈጀበትን አገር ቆርሶ የመሸጥ ውል ተዋውሎ ወደ ፍፃሜ መድረሱን ሰሙ።

አፄ ቴዎድሮስ በታላቅ ቁጣ ከደብረታቦር ተነስተው ሲገሰግሱ ደጃዝማች ንጉሴ ለፈረንሳይ እውቅና ለመስጠት የፈረንሳይን ባንዲራ በአድዋ ከተማ ሲያውለበልብ ደረሱበት። ውሉ የጣሊያን መልዕክተኞች በቀይ ባህር ዳርቻ ያለውን "እንዱዳ" የተባለውን ቦታ እንዲሰጣቸው የሚጠይቅ ሲሆን፤ የፈረንሳይ መንግስት ዙላንና የዲሲን ደሴቶች ጨምሮ ከዊን እስከ ዘይላ ድረስ ያለውን የኢትዮጵያን የቀይ ባህር በር በመልዕክተኞቹ አማካይነት እንዲይዝ የሚል ነው።

በዚህ የውል ስምምነት አንቀፅ 5 ላይ "ይህ የሰጠኋችሁ ስጦታ ለፈረንሳይ ንጉስ እስከ ልጅ ልጅ ድረስ ፀንቶ ይቆያል" የሚል ነበር። ነገር ግን ኢትዮጵያን ከራሳቸው በላይ የሚወዷት አፄ ቴዎድሮስ ቶሎ ደርሰው ደጃዝማች ንጉሴ ወልደሚካኤልን ከነጭፍሮቹ በመደምሰስ ውሉን አጨናግፈው ጣሊያንንና ፈረንሳይን የሐፍረት ሸማ አከናነቧቸው።

ሁሉን አረጋግተው ለመቀበል መታተራቸውን ቢቀጥሉም በስተምዕራብ በኩል ደግሞ ግብፆች መጡባቸው። ዕንው ንጉስ ነገስት በጠንካራ ክንዳቸው ተፋልመው መለሱት። ጥቂት ዘመናዊ መሳሪያም ለመማረክ ቻሉ።

አፄ ቴዎድሮስ ከበርካታ አገሮች ጋር ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነታቸውን እንደቀጠሉ ነበር። በዘመናቸውም ኢትዮጵያ ውስጥ የተለያዩ አገሮች በሚስዮናዊነትና በቆንሲልነት የላኳቸው ቤቶች ይገኙ የነበረ ሲሆን። ከእነዚህ ውስጥም እንግሊዛውያኑ ይበረክቱ ነበር።



የአፄ ቴዎድሮስ መሻት ደግሞ ስልጣኔ ነው። ኢትዮጵያ አንድነት፣ እኩልነት፣ ሰላምና ስልጣኔ እንዲኖራት ብቻ በመመኘትና ምኞታቸውንም ተግባራዊ ለማድረግ ብዙ ድንጋይ ፈንቅለዋል። ሆኖም እነዚህ ሚሲዮኖች ከፍላጎታቸው አንዱንም ሊፈፅሙላቸው የቻሉ አልነበሩም። በዚህም ተበሳጭተው ለአውሮፓውያኑ ያላቸው አመለካከት ተለወጠና "የአውሮፓውያን ሃሳብ ስውር አይደለም። አገር ለመያዝ ሲፈልጉ መጀመሪያ ወንጌላዊ ተብሎ ሰላይ ይላካል፣ ሰላዩን ለመርዳት ቆንሲል ይሾማል፣ ከዚያም የሰላይ ዘር ይበዛል፣ ቆንሲሉንና ዝርያውን የሚጠብቅ ጦር ይከተላል። እንዲህ ያለ ነገር በአገሬ እንዲካሄድ አልፈቅድም። እኔ የሂንዱስታን ራጃ አይደለሁም። ቆንሲል ከሚላክብኝ ይልቅ ጦር ቢላክብኝ እመርጣለሁ" እስከማለት ደረሱ።

ነገር ግን ከእንግሊዝ በኩል ጥሩ ተስፋ ጥለው ነበር። ተደጋጋሚ ጉትጎታቸውም ዘመናዊ መሳሪያ ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ የእደ ጥበብ ባለሙያ ከሰለጠነው ዓለም እንዲመጣላቸው ነው።

ስለዚህም በወቅቱ የእንግሊዝ ንግስት ለነበሩት ለንግስት ቪክቶሪያ ደብዳቤ ፃፉ። የወቅቱን ቆንሲል ዳንካን ካሜሩንን መርጠው "... ለመንገድ ስራ መሐንዲስ፣ የጦር መሳሪያ እርዳታ፣ እንዲሁም ለኢትዮጵያ ስልጣኔ የሚያገለግሉ የእደ ጥበብ ባለሙያዎች ... ይላኩልኝ..." በማለት በዲፕሎማሲያዊ ቃላት የታጀበ ደብዳቤ አስይዘው ላኩት። አፄ ቴዎድሮስ የላኩት ሰው የውሃ ሽታ ሆነባቸው። ምላሽ ሲጠፋ "ምላሽ የነፈጉኝ ቢንቁኝ አይደል?" በሚል መነሻ ምድረ ቆንሲልን ከያለበት ለቃቅመው 72 የሚደርሱ አጠቃላይ የውጭ ዜጎችን በመቅደላ አምባ ከሚገኘው እስር ቤት አጎሯቸው።

- በዲፕሎማሲ ጥረት ማግኘት ያልቻሉትን የዘመናዊ መሳሪያ ጥማት ሙያው በሌላቸው ሰዎች በግድ ለማግኘት "እንደምንም መድፍ ስሩ" ብለው እስረኞቹን አስገደዱ። ደብዳቤው ምላሽ ያላገኘበትን ሁኔታ በርካታ ፀሃፍት ሲያብራሩትም "ንጉሰ ነገስቱ ዘመናዊ መሳሪያ ያስፈለጋቸው ቱርክን ሊወጉበት ነው። ይህ ማለት ደግሞ ቱርክ ከሌላ ወገን ጋር አብራ እንግሊዝን በቂም በቀል ትፈታተናለች ... ወዘተ" የሚል እሳቤ ውስጥ ገብተው ነው በማለት ይገልፃሉ።

በዚህ ጊዜ አፄ ቴዎድሮስ በእንግሊዛውያኑ ቆንሲሎችና ሚሲዮኖች ላይ መረር ያለ እርምጃ በመውሰድ በጅራፍ ያስገርፏቸው ገቡ። ሄንሪ ስተርን የተባለው እንግሊዛዊም በጅራፍ ግርፋት ምክንያት ስቃይ በዝቶበት ሲሞት መቃረቡን እንግሊዛውያኑ ሲሰሙ እጅግ አዘኑ።

የስምምነት ደብዳቤ አስይዘው ሌላ እንግሊዛዊ ወደ ኢትዮጵያ ቢልኩም እሱም ተይዞ ታሰረ። በዚህ መካከል ሴባስቶፖል የተባለው መድፍ በእስረኞቹ ትብብር ተሰራ። ሁሉም በደስታ ከመፈንደቃቸው ባሻገር አፄ ቴዎድሮስም በደስታ በግድ ያሰሩትን መድፍ አቅፈው ሳሙት። መድፉን በመስራትና በማሰራት ላይ የነበረው ተሳታፊ የአውሮፓውያኑ መሪ ቴዎፍሎስ

ቫልዲሚየር ከመሰሉቹ ጋር ስለሰራው መድፍ ሲፅፍ "ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ሙከራችን ተሳካ። ሲያሳግጡብን የነበሩ ኢትዮጵያውያን ሁሉ በአግራሞት ተደሰቱ። ንጉሱም መድፉን በትክሉ አቅፈው ሳሙት ..." በማለት ፅፏል።

ንጉሱ አክለውም "ከዚህ በኋላ ማንኛውም ነገር ይሳካል!" አሉ። ከዚያም እንግሊዞች በስምምነታቸው ለመቀጠል ሲሉ የእደ ጥበብ ባለሙያዎችን ወደ ኢትዮጵያ ላኩ። ከለንደን ተልከው የመጡት ባለሙያዎች ግን በቀይ ባህር ዳርቻ ከሚገኘው የምፅዋ ወደብ ከደረሱ በኋላ "የታሰሩት እንግሊዛውያን ካልተፈቱ ወደ መሐል አገር አንገባም" ብለው ላኩ። ቢፈቱላቸውም እንኳ ኢትዮጵያን ለማሰልጠን እንቅስቃሴ እንደማይጀምሩ ከግልፅም በላይ ግልፅ ነው። ሲጀመርም የተላኩት የእደጥበብ ባለሙያ አልነበሩም።

አፄ ቴዎድሮስም "እስረኞቹን የምለቀው ባለሙያዎቹ ደብረታቦር ሲደርሱ ብቻ ነው" በማለት ውሳኔያቸውን አሳወቁ። ብዙ ድርድሮች ተካሔዱ። በማባበያ ቃላትና በገፀ በረከት ዜጎችን ለማስለቀቅ እንግሊዞች ብዙ ጣሩ። ቴዎድሮስ ግን ኢትዮጵያን ካላሰለጠናችሁልኝ በቀር በቃላት አልሸነገልም ብለው ድርቅ አሉ።

የእንግሊዞች ትዕግስት ተሟጠጠ። የተጠየቁትን ጥያቄ መመለስም ሽንፈት ሆኖ ታያቸው። ስለዚህ የለንደን ምክር ቤት እስቸኳይ ጉባኤ ጠርቶ "ጦር ተልኮ እስረኞቹ በሃይል እንዲፈቱ" የሚል ውሳኔ አሳለፈ። የአፄ ቴዎድሮስን ጀግንነት ግንዛቤ ውስጥ በማስገባትም ጠንካራ ሃይል ተደራጀ።

4,330,285 ፓውንድ ለመርከብ ኪራይ የሚውል ገንዘብ ተመድቦ 10,231 እግረኛ ወታደሮች፣ 983 መድፈኛ ወታደሮች 2,064 ፈረሰኛ ወታደሮች 2,306 ረዳት እቃ ያዥ ወታደሮች በድምሩ 16 ሺ 189 ተዋጊ ወታደሮች፣ 12,640 ከብት ነጅና ጠባቂዎች፣ 3,233 ሰራተኞች፣ 4,189 ፈረሶች፣ 1,759 አህያዎች፣ 16,022 በቅሎዎች፣ 5,733 ግመሎች፣ 44 ዝሆኖች፣ ለምግብነት የሚውሉ 7,071 በሬዎችና 12,839 በጎች በ 669 መርከቦች ተጭነው ወደ ኢትዮጵያ ተላኩ። እጠቃላይ የሰው ሃይሉ ሰራተኞችንና ከብት ጠባቂዎችን ጨምሮ 32 ሺ እንግሊዛውያን በጀኔራል ናፒየር ዋና መሪነት ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡም "እስረኞችን ለማስፈታት እንጅ አገር ለመውረር አልመጣንም" እያሉ ህዝቡን በፈገግታ ያሳምኑ ነበር።

በዚህ ጊዜ የትግራዩ ደጃዝማች ካሳ ምርጫ /በኋላ አፄ ዮሃንስ/ የእንግሊዝ ጦር ወደሰፈረበት ቦታ ሔደው "እንኳን ደህና መጣችሁ" በማለት አቀባበል አድርገውላቸዋል። ለዋናው መሪ ለጀኔራል ናፒየርም በድንኳናቸው ጠርተው ታላቅ ግብዣ በማድረግ የአንበሳ ጎፈር በራሱ ላይ በመጫን የተሸለመች በቅሎዋቸውን ሰጥተው መልካም ምኞት ተመኝተው ጎራዴና ጦር አስጨብጠው ነበር የሸኙት።



አፄ ቴዎድሮስ የእንግሊዞችን ሁኔታ ሲሰሙ እጅግ ተቆጡ። እንግሊዞችም ከወደብ ወደ ወደብ ተንንዘው ወደሰንአፌ፣ ከሰንአፌ ወደ አሸንጌ፣ ከአሸንጌ ወደ መቅደላ በሚገቡ ጊዜ በቴዎድሮስ ቅር የተሰኙ መኳንንት መንገድ እየመሩ ነበር አልጋ ባልጋ በሆነ የጉዞ አይነት ያደረሷቸው።

አፄ ቴዎድሮስ ማንም ሊተካው የማይችል ራዕያቸው መደብዘዝ እንደሌለበት በማሰብ የተቻላቸውን ሊጥሩ፣ ህልማቸውን ሊታደጉት ተዘጋጁ። ሩቅ አስበው ሁሌም ቅርብ ያድራሉ። ለዚህም ነው ሎሬቱ "ተስፋ ባባ ምድረ በዳ

ያንድ እውነት ይሆናል እዳ፣
እና ትንፋሼ አለሆነሽም
ሆኚብሽ መራር መካሪ
ሩቅ አሳቢ ቅርብ አዳሪ
እውነት ላንች መች ተስፋ ናት?
ቁስቁል ልሳንሽን ነክሳሽ ...
ክንድሽን ካዘለ ቅርስሽ
መጠላለፍ ሲሆን እጣሽ
ከእንግሊዝ የሞት እማልክት
ሙተናኘቅ ሲሆን ድርሻሽ
መልመጥመጡ መሽቆጥቆጡ
መስሉሽ ድንገት የሚያዋጣሽ
የኔ እውነት ሆነብሽ እዳሽ!..." እያለ በትንቱ

የቴዎድሮስን ሁኔታ በምናቡ እያየ፣ በቴዎድሮስ ውስጥ ኢትዮጵያን እያስተዋለ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ወቅቱን እያሰበ፣ በሐሳቡ ውስጥ ትዝታውን እየተዘተ፣ በትዝታው ውስጥ እውነትን እያብላላ "የቴዎድሮስ ስንብት ከመቅደላ" ብሎ እውነቱን መፃፉ የንጉሱ ጥረት ቢነካው አይደል?

በእርግጥም አፄ ቴዎድሮስ ጉጉታቸው ስልጣኔና ስልጣኔ ብቻ ነበር። ለኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት ብቸኛው አስተንፋሿ ደግሞ ስልጣኔና አንድነት ለመሆኑ የእሁኑ ፍላጎታችን መሆኑ በራሱ ያስረዳናል። ይህን ለማምጣት ደግሞ በመጀመሪያ ሰላም ያስፈልጋል። እናም የተጋረጠባቸውን ፀረ ስልጣኔ ለማስወገድ ሰላምን ማስፈን ነበረባቸው። ይህን ለማግኘት ደግሞ ከፊል ሳይሆን ሙሉ ድል ማግኘት ነበረባቸው። ለዚህ ሲባልም ዘመናዊ መሳሪያ የመጨረሻው አማራጫቸው ሆኖ አገኙት። በጦርነት ድል በማድረግ ብቻ ደግሞ ስልጣኔ እንደማይመጣ በመገንዘባቸው "ስልጡን የሰው ሃይል እርዱኝ" አሉ "እምቢ" አሏቸው፣ አስገደዱ አልሆነም። ይልቁንም ፍፃሜያቸውን አሳጠረው።

ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ "የኢትዮጵያ" ታሪክ ከ1947 – 1983" በሚለው መፃሃፋቸው ውስጥ በአፄ ቴዎድሮስ ግምጃ ቤት ውስጥ በወቅቱ የነበረውን መሳሪያና አይነታቸውን ዘርዝረዋል። በዚህም 15 መድፎች፣ 7 ሞርታሮች፣ /መንጀኒቆች/ 11,063 ልዩ ልዩ ጠመንጃዎች፣ 875 ሽጉጦችና 481 ሳንጃዎች እንዲሁም 555 የመድፍ እና 83,565 የቀላል መሳሪያ ጥይቶች ይገኙ ነበር።

በዚህ መልኩ ፈፅሞ ሊመጣበኑት ከማይችሉት ጠላት ጋር መፋጠጣቸው ሳይበቃ፤ ቄሶች "ከቴዎድሮስ ጎን የተሰለፈ የተረገመ ነው!" ብለው በመገዘት ህዝቡ ከጎናቸው እንዳይቆም አደረጉ።

በሰላም ኢትዮጵያን መምራት ያልታደሉት፣ ከቦታ ቦታ እየተንከራተቱ አዲስ የአስተዳደር ስርዓት የዘረጉት፣ ፊት ለፊት የሚመጣባቸው ጦር ሳያስጨንቃቸው ፈረሳቸው ላይ ሆነው ህግ የሚያወጡት፣ መመሪያ የሚያስተላልፉት፣ አስልጥኑን እያሉ መልዕክት የሚልኩት ጀግናው መይሳው ካሳ አሁን ውስብስብ ባለ ሁኔታ ላይ ነው ያሉት። በመጨረሻም ለኢትዮጵያ ህዝብ የመጨረሻ ንግግራቸውን እንዲህ በማለት ነበር የተናገሩት። የዚህ ንግግር ታዳሚዎችም ወታደሩ፣ ውግዙን ንቀው ከጎናቸው የተሰለፉ አገር ወዳዶችና የቴዎድሮስ ራዕይ በውል የገባቸው ወገኖች ነበሩ። ለዚህ ትውልድ ብቻም ሳይሆን ለሁሉም የሚያገለግል ከታላቅ ኢትዮጵያዊ ጀግና አንደበት የፈለቀ ታላቅ ንግግርም ነውና ልብ ያለው ልብ ብሎ ሊማርበት ይችላል።

"በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ፤ ልዑል እግዚአብሔር መርጦ ያነገሰውን ንጉሰ ነገስት ቴዎድሮስ ዘኢትዮጵያ በዛሬ እለት በአሁኑ ሰዓት በጎኔ የተሰለፋችሁ ጀግኖች፣ አንድነትን የምትወዱና የምትከተሉ ተከታይ ትውልዶች ልነግራችሁና ላስተምራችሁ የምፈቅደው ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቃል ነው።

የእንግሊዝ መንግስት ጦር ሰራዊት አንድነታችን ለማፍረስ፣ ሃይላችን ለማድከም በቱርክ መንግስት እየተረዳ ወደ ኢትዮጵያ ምድር ባህር ተሻግሮ ገባ። የተረፉት መሳፍንት ተገናኝተው እጅና ብትር ሆነው መጡብን። አሁን ባጠገቤ ያላችሁ ወገኖች፣ የኢትዮጵያ ሰራዊት፣ ለአንድነት የቆማችሁ፣ ያለፈውን የመሳፍንት አመራር በማጥፋትና የቀና አስተዳደር በቦታው በመተካት መልካም ስራ እና ዘመናዊ ጥረት እንዲስፋፋ ለማድረግ ላደረግሁት ድካሜ የኢትዮጵያ ምድር በስሜ ላይ ትመስክር።

መቾም እድሜያቸውን ሙሉ በወገኖቼ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ክፉ ሲያደርጉ የኖሩ መሳፍንትና የነገስታት ቅምጥል ዘሮች ደግ ስራ መስራት ስለማይችሉ እንዲሁም መልካም ትምህርትና ጥበብ ማስተማር ቀርቶ በቅን ልቦና የሚሰሩትን፣ የሚጠበቡትን ሁሉ ተከታይ ትውልድ እንዳይኖራቸው ለማድረግ ስለሚያጠፏቸው እናንተ የኢትዮጵያ ጀግኖች ለቆማችሁለትና



ለደከማችሁለት አንድነት ታማኝ ሆናችሁ እነሱን ለማዳን መገኘት የአንድነት ጥሪ ነው።

ነገር ግን አንድነታችሁና ሃይላችሁ እንዲጠፋ ከተሰለፈባችሁ ጠላቶች ፊት መሸሽ ወይም በግዴለሽነት ማለፍ ወገንን አታሎ፣ ህሊናን በድሎ፣ ሳይሞቱ ሞቶ፣ በውርደት መቃብር ታፍኖ መኖር ሲሆን፤ በሌላም በኩል ደግሞ በአገሩ ላይ የመልካም ስራና ደግ ስራው አንድነቱ፤ ነፃነቱና ዓላማው በተግባር እንዲፈፀም መጣር ለትውልድ መንገድ መሪ ነው።

ማንኛውም ትውልድ በወረደ ልማድና በተበታተነ ስርዓት ታፍኖ፣ በክፉ ስራት ተዋርዶ ሺ ዘመን ተንቆ ከመኖር ለከፍተኛ አንድነት፣ ለመልካም ስራ በታማኝነት ለሃገሩ ክብር ሲል የሞተ ጀግናው ወታደር በክብር ይበልጠዋል። ለተከታዩ ትውልድም የመልካም ስራው መስዋዕትነት መታሰቢያ ሆኖ ይኖራል። ይህ ትውልድ ቢያፍነው እንኳ ሌላ ትውልድ ይገልጠዋል።

ለዚህ ታዛቢና መስካሪ የአገርህ የኢትዮጵያ ምድር ነው። እነዚህ አሁን የከበቡህ የመሳፍንት ጭፍራዎችና አጃቢዎች የውጩን አገር የእንግሊዙን የጦር ሃይል ይዘው ቢመጡብህ አትፍራቸው፤ ለክብርህ ብትሞት በህይወት አለህ። ባትሞት ግን የሞትክና የተዋረድክ ነህ። ስለዚህ አሁን ለቀረበልህ ክብር ተነሳ። ታጠቅ! ተቀበለው! ጠላቶችህ መሳፍንት ደስ ይበላቸው፤ የዛሬ ደስታቸው የነገ ሃዘናቸውና ለቅሷቸው ነው።

በየጊዜው ትውልድ ሁሉ የራሱ መብትና ምርጫ መኖሩን ያለፉት ነገስታት ቢያውቁ ኖሮ ህዝባቸውን በከንቱ ባልገደሉት ባላጠፉት ነበር። ለጊዜው ግዛታቸውና ታሪካቸው የሚኖር መስሏቸው ያከመውበት በከንቱ ጊዜያቸው አለፈ።

እኛ ግን ከእነርሱ የተለየን የዛሬ ትውልድ ባለቤቶች ነን፣ የነገም፣ የከነገወዲያም ባለቤቶች ነን።

ይኸውም መልካም ስረንና ስራውን ስለምንመኝ፤ ለአንድነትና ለተግባር ሐይል ለማቆም ስንደክም፣ ስንታገል ነው እንጅ፤ የነገው ትውልድ ባለቤት ለመሆን መልካም ስራንና አንድነትን ለይቶ የመምረጥ መብት የነገው ትውልድ ነው።

አሁን እናንተ ለህዝባችሁ አንድነት ምንድነው የምትሰሩለት? የህዝባችሁ አንድነትስ ለእናንተ ምን ያህል ክብር ነው የሚያስቀምጥላችሁ?

አንድነት ከሌለ ህዝብ የለም። ህዝብ ከሌለ ደግሞ ሃገር የለም። ሃገር ለባዕድ ይሆናል። ህዝብ በአንድነት ከቆመ ግን ሃገር አለ።

ሃገርን የሚሰራት የህዝብ አንድነት እንጅ ሃገር የህዝብ አንድነትን አይሰራውም። አያቆመውም። ነገር ግን ሐገር ታኖረዋለች። ታስመሰግነዋለች፤ መኖሪያና ሰፈሩ ሆና እውነተኛ ትውልድ ታስተላልፋለች። እናንተም ሆናችሁ እኔ ለምን ደከምን? ለምን እንደምንሞትም ማወቅ የራሳችን መብት ነው።

ነገር ግን መብታችን የራሳችን ቢሆን፣ ሞታችን ደግሞ በታሪክ የሚኖር፣ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ ህይወት ነው። ስለዚህ በህይወታችን እንደምንኖር ቁጠሩት እንጅ ሳይሞቱ ከሞቱት ጋር ያለን እንዳይመስላችሁ። የእኛ ሞት ለተከታዩ ትውልድ ክብር ነው። ስለዚህ ሞታችን ጣፋጭ ማር እንጅ መራራ ሬት አይምሰላችሁ።" ( የጎንደር ታሪክ 1999 ዓ.ም)

በማለት አንዳችም ተቀርጣ የምትጣል ቃል ሳያነቱ የውስጣቸውን እውነት በሐቀኛ ኢትዮጵያዊ አንደበታቸው ተናገሩ። እውነት ዘላለማዊ ናትና የአፄ ቴዎድሮስ ንግግር እስከመጨረሻው በሚኖረው ተከታታይ ትውልድ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ሊሰጠው የሚገባው ልዩ ስፍራ እንዳለ ለማንም አይሰወርበትም። ዘመን አይሽሬ ንግግርም ነው።

ከዚህ በኋላ አፄ ቴዎድሮስ ሁሉ ነገራቸውን ሰብስበው በተራራ ወደ ተከበበችው ወደ መቅደላ አምባ አመሩ። የእንግሊዝን ጦርም እንዲወጉ ሰራዊታቸውን አዘዙ። በጀግናው ንጉስ ነገስት ስር የተሰባሰበው ጀግና ኢትዮጵያዊ ወታደር ሁሉ በከፍተኛ ወኔ ከመቅደላ አምባ ወርደው ተዋጉ።

የእንግሊዝ ጦር ወሳኝ ቦታዎችን በኢትዮጵያውያን ተባባሪዎቹ አማካይነት ይዞ በታጠቀው ዘመናዊ መሳሪያ የቴዎድሮስን ጦር ፈጀው። ሴባስቶፖሉም የረባ ውጤት ሳያስገኝ ቀረ። ፊት አውራሪ ገብርዬና ራስ እንግዳ እንዲሁም ሌሎች ታላላቅ መኳንንቶች ሁሉ ተራ ወታደሮችን ጨምሮ በእንግሊዝ ወታደሮች ተገደሉባቸው።

በዚህ ጊዜ አፄ ቴዎድሮስ በጥልቅ ሐዘን አለቀሱ። በተለይ የፊት አውራሪ ገብርዬ ሞት ተስፋቸውን አጨለመባቸው። በፉላና በሰላምጌ በኩል በተደረገው ጦርነትም ተመሳሳይ እጣ ገጠማቸው።

ድል እንጅ ሽንፈት ባጠገባቸው አልፎ የማያውቀው ታላቁ ንጉስ ነገስት ለአንደኛና ለመጨረሻ ጊዜ ሙሉ በሙሉ ድል ሆኑ። ይህንን ሲያውቁም አስረኞቹን ፈትተው ለቀቋቸው። እንግሊዞችም ለመማረክ ሞክረው ሳይሳካላቸው ሲቀር "እጅዎን በሰላም ይስጡና በምርኮ በክብር እንይዝዎታለን" የሚል ቃል ተናገሯቸው።

መይሳው ካሳ ይህን ቃል ሲሰሙ አበዱ። "የተማረከው የኢትዮጵያ ንጉስ ልባል? በትውልድ ሊፌዝብኝ? የአገሬን ክብር አላዋርድም። ምንም የመጨረሻ ቀኔ ቢሆን በጠላት እጅ መያዝ ቀርቶ እጅህን ስጥ ተብዬ መጠየቄ እንኳን ንቀት ነው። ደግሞም ለህዝቤ ስል ብናቅ እይገደኝም" ነበር ያሉት። "ለቴዎድሮስ ከአምላክ ሌላ አለቃ የለውም።" ሲሉ አከሉበት። ልዑል አለማየሁን የወለዱላቸው እቴጌ ጥሩ ወርቅም ሽጉጣቸውን መዘው ራሳቸውን ለመግደል ሲዘጋጁ አይተው "እባክዎን ለልዑል አለማየሁ ሲሉ እንኳን



ይቆዩለት" ሲሏቸው "ልጅ አለማየሁ ቴዎድሮስ እንዲት ኢትዮጵያ በአይኑ እንደዞረች ሞቶ ብለሽ ንገሪው" አሏቸው። (ዝኒ ከማሁ)

የደቂቃዎች እድሜ ቀራቸው። ያንን ጥረታቸውን ሁሉ ለአፍታ አስታወሱት። በዘመናቸው የሽንፈትን ስሙን እንጅ ተግባሩን አያውቁትም። አሁንም ማወቅ አልፈለጉም። በያዙት ሽጉጥ ራሳቸውን ገደሉ። ሚያዝያ 7 ቀን 1860 ዓ.ም ከ13 አመታት የንግስና ዘመን ቆይታ በኋላ ሲያልፉ እድሜያቸው 49 ሞልቶ ነበር። የተቀበሩትም መቅደላ ነው። ነብሳቸው ልትወጣ ጣር ላይ በነበሩ ጊዜ ነበርና እንግሊዞች የደረሱት ከፊታቸው ለቆመው ጄኔራል ናፒየር በጣር ድምፅ "አደራ አሁንም አገሬን አሠልጥኑልኝ።" ብለውታል። (ዝኒ ከማሁ)

የስምንት አመት እድሜ የነበረው ልዑል አለማየሁ ከእናቱ ጋር ቀረ። ከዚች እለት ጀምሮም በእንግሊዞች እጅ ወደቀ። የልዑሉን አሳዛኝ ታሪክ ወደ መጨረሻ እንመለስበታለን። አሁን ስለ ቴዎድሮስ የተገጠሙትን ጥቂት ስንኞች አይተን የእንግሊዞችን አደገኛ ዘረፋ እናስከትል።

ኢትዮጵያዊው ባለቅኔ ሎሬት ፀጋዬ ገ/መድህን መታሰቢያነቱ ለአለማየሁ ቴዎድሮስ በማለት ቀደም ሲል ካየነው ግጥም መሐል የንጉሱን አሟሟት በኋለኛው ዘመን በበሳል ስንኝ እንዲህ ገጠመ፦

“... ሆኖም ጎስቋላ አልምሰልሽ የሚያዝንልኝ አልፈልግም
ጠላትሽን በክንድሽ እንጅ በእንባሽ ወዝ ባላሸንፍም
የልቤን ፍቅር በስተቀር የማወርስሽም ውሏ የለኝ
የክብ ሻጭ ልጅ ደሐ ነኝ።
ደሞም ያላንች የለኝና...
ድሌም የተስፋ ጎህ ባይሆን ከሞት ጋር ትግል ነውና!
ከዚህ ሌላ ትዝብት ውረሽ ...
ሳይነጋ እንዳስመሸሽብኝ፣
ጊዜና ትውልድ ይፍረደን
ሳልነቃ እንዳስረፈድሽብኝ።
ያም ሆኖ ለራስሽ እንጂ ለኔ ከቶም አታልቅሽ፣
አንች ነሽ እንባ እምትሺ...
የእምነትሽ መተሳሰሪያ ውልሽ ለተላቀቀብሽ
ላንች ነው እንባ ሚያስፈልግሽ።
አዎን! ይህንን እወቂልኝ ምስክር
ሁኑኝ ሰማዕታት
ለሱዋ ነው እንባ ሚያስፈልጋት።
ከጠላቶች ጭብጥ ውስጥ ትንፋሼን በጄ ስነጥቃት፣
ሞቴን ከመንጋጋቸው ውስጥ መንጭቄ እኔው ስሞታት
ለሕገሬ ብድሬ ልከፍላት

የነፈገችኝን ፍቅር በራሴ ሞት ልለግሳት
ዳግም ከሞቴ ባገኜ በመንፈስ ጣር ስሞግታት!
ያኔ ነው እንባዋ የሚያጥራት፡፡
ስለዚህ ለራስሽ እንጅ ልቅሶሽ ለኔ ምን ሊረባ?
ብቸኛ ምሬት ነው ሐይሉ ወኔ መስለቢያ ነው እንባ፡፡
እና ለራስሽ አዘኝ ...
እንጂ ከቶ ለኔ አትባክኝ፡፡ ..........." እያለ ይሔድና
"ይልቅስ ተረት ልንገርሽ" ብሎ ይቀጥላል፡፡ "ይልቅስ ተረት ልንገርሽ
የተላከ ከእንግሊዝ ዘንድ
እጅህን ስጥ አለኝ ፈረንጅ
እጅ ተይዞ ሊወሰድ
ምን እጅ አለው የእሳት ሰደድ
አያውቅም ክንዱ እንደሚያነድ!" በማለት
የተከበረው ያገሩ ባለቅኔ የተከበረውን ንጉስ ነገስት ገፅታ በግጥሙ ገልፆት አልፏል፡፡
በወቅቱም የአገሬው ሰዎች "መቅደላ አፋፉ ላይ ጩኸት በረከረ
የሴቱን አናውቅም አንድ ወንድ ግን ሞተ"
ተባለላቸው፡፡
"የሰው ልጅ መሞትን ነውር አድርጎት፣
እዩት ተመልከቱት ያንበሳውን ሞት፡፡
ወላቶቹን ሁሉ አጭዶ እንደ ገብስ
መቅደላ ላይ ጣለው ራሱን በራስ፡፡"
በዚህ ጊዜ እንግሊዞች በጣም ተበሳጩ፡፡ ባለመማረካቸውም አዘኑ፡፡
"ገደልን እንዳይሉ ሞተው አገኟቸው
ማረክን እንዳይሉ ሰው የለ በእጃቸው
ምን አሉ እንግሊዞች ሲገቡ አገራቸው?
ለወሬ አይመቹም ተንኮለኞች ናቸው፡፡"
አንድ የመሳፍንት ወገን የሆነና የቴዎድሮስ ዓላማ ፈፅሞ ያልገባው አዝማሪ ደግሞ "እኔ ብቻ ልግዛ ነውና ነገሩ
ሰማይ ቤትም ሄደው እንዳያስቸግሩ" ብሎ ገጠመ፡፡

መቅደላ አምባ ጭር ብላለች፡፡ እንግሊዞች በንጉስ ነገስቱ ላይ ሳይሆን በድናቸው ላይ ነውር የሆነ ተግባር ፈፀሙ፡፡ ሬሳቸውን እየጎተቱ አንገላቱት፡፡ ሽጉጣቸውን፣ የአንገት ሐብላቸውን፣ የጣት ወርቃቸውን ከመውሰድ አልፈው ልብሳቸውን አወላልቀው ወስደው እርቃናቸውን ከማድረግ ባለፈ ሹሩባ ፀጉራቸውንም ላጭተው ወሰዱት፡፡

በአሁኑ ሰዓት museum of man kind ሹሩባቸው ሲገኝ፣ የጣት ቀለበታቸው Colget church Lancaster ይገኛል፡፡ ሽሚዛቸው ደግሞ Bank



field museum ውስጥ ይገኛል፡፡ የአንገት ሐብላቸውን ግን ከ80 አመት በኋላ በሃይለስላሴ ዘመን ከጥቂት እቃዎች ጋር ማስመለስ ተችሎ የነበረ ቢሆንም ከአገራችን ሙዚየም በ1966 ዓ.ም ከ 140 ግራም ወርቅ ጋር ተሰርቆ ጠፍቷል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለም በጄኔራል ሮቤርቶ ናፒየር የተመራው የእንግሊዝ ጦር ሰራዊት አፄ ቴዎድሮስ ከጎንደር አድባራት ሰብስበው የወሰዷቸውንና ታላቅ ሙዚየም አሰርተው በክብር ሊያስቀምጧቸው ያዘጋጇቸውን ውድ ቅርሶች በርካታ መፃህፍትን ጨምሮ ከያሉበት በማውጣት በደላንታ ሜዳ ለእንግሊዝ ዜጎች ጨረታ አቅርበው ተቀራመቷቸው፡፡ የእንግሊዝ የቅርስ ባለሙያ የሆነውን ሪቻርድ ሆልምስን አስመጥተው አዘረፏቸው፡፡ በተጨማሪም የቴዎድሮስን የወርቅ ዘውድ፣ የወርቅ ዕዋ፣ የእቴጌ ተዋበችን የወርቅ እክሊል፣ ተቀብረው የተቀመጡትን በሳጥን የተሞሉ ወርቆች፣ በወርቅ የተለበጡ ጋሻዎች፣ ጦሮች፣ ጽናፅሎችና በርካታ ልዩ ልዩ ውድ ቅርሶችን ወደ አገራቸው አጋዙ፡፡

በአንድ ወቅት የእንግሊዝ ጋዜጣ "ፋይናንሻል ታይምስ" ከመቅደላ አምባ በእንግሊዝ ወታደሮች ተዘርፎ ወደ አውሮፓ የሔደውን የኢትዮጵያ ሐብት በገንዘብ ተምኖ አውጥቶት ነበር፡፡ ፅሁፉ እንዳተተው 2 ቢሊዮን ዶላር እንደሚያወጣ ነው፡፡ ነገር ግን የተጠቀሰው ጋዜጣ የራሳቸው ስለሆነ ቁጥሩን በጣም ዝቅ አድርገው ማቅረባቸው እንጂ እንደ እውነቱ ከሆነ ... በመቶ ቢሊዮኖች ሊገመት እንደሚችል በቀላሉ ይታወቃል፡፡ ስንት መርከብ ወርቅ ነው 2 ቢሊዮን ዶላር የሚያወጣው? የኢትዮጵያን ባዶ መሬት ብቻ አስተርፈው የሄዱበት ዘመን ነው፡፡ ነገር ግን ..... ብዙ ተቆርቋሪ ስላላቸው ራሳቸው ያሉትን ለማድመጥ እንገደዳለን፡፡ ስለዚህ 2 ቢሊዮን ዶላር ነው እሺ፡፡

በአፄ ቴዎድሮስ ጊዜ እንግሊዞች በርካታ ቅርሶችና መፃህፍት መውሰዳቸው እንዳለ ሆኖ፣ በተለያየ ጊዜም ብዙ የኢትዮጵያ ቀደምት መፃህፍትና ቅርሶች በተለያዩ ሚሲዮናውያን፣ ቆንሲሎች፣ ጎብኝዎችና የታሪክ ተመራማሪና ተመራማሪ ተብየዎች ተወስደዋል፡፡ በዘረፋ፣ በስርቆት፣ በስጦታ፣ በውሰት፣ በጥቂት ራስ ወዳድ ዜጎች አማካኝነት በሽያጭ ... ወዘተ... ከኢትዮጵያ ወደ በርካታ የአለም አገሮች የተጋዙት አጠቃላይ መፃህፍት ቁጥራቸው 4,051/አራት ሺ ሃምሳ አንድ/ ናቸው፡፡ "ኢትዮጵያንም አምላክ የወራሪ ቀኝ ገዥዎችን አይን ጋርዶ አተረፋት እንጅ በዚህ ጊዜ የተጋለጠች ነበረች፡፡" ይባላል፡፡ ምን ያደርጋል ቅኝ ግዛት? ምን ቀረና እዚሁ ሆነው ኢትዮጵያን ቅኝ ያደርጋሉ? ... ስለዚህ ቅኝ ማድረግ እየቻሉ አዝነውልን ትተውን ሄዱ፡፡...

በ1999 ዓ.ም እ.ኤ.አ. አዲስ ቲሪቡን ጋዜጣ ኘ/ር ሪቻርድ ፓንክረስትን ጠቅሶ ባወጣው ፅሁፍ እንደገናም በአውሮፓ ቤተመፃህፍት እየተዘዋወሩ የአገራቸውን ፅሁፍና ቅርስ በየሙዚየሙ እየዞሩ ለማየትና ለማጥናት እድሉን

ያገኙት ተክለሃይማኖት መኩሪያ በአይናቸው እንዳረጋገጡት፣ የኢትዮጵያ ልዩ ልዩ መጻሕፍት በተለያዩ የአለም አገሮች ቤተ መዘክር ተከፋፍለው መቀመጣቸውን እንረዳለን።

ከእነዚህም ውስጥ በእንግሊዝ 850, በጀርመን 734, በፈረንሳይ 700, በቫቲካን 600, በአሜሪካን 400, በኔዘርላንድ 60፣ በእስራኤል 50፣ በአውስትራሊያ 50, በአርመንያ 30፣ በቤልጂየም 14፣ በካናዳ 11, በስዊዘርላንድ 6፣ በፖርቹጋል 4፣ በስፔን 3፣ በኒውዝላንድ 3፣ የሚገኙ ሲሆን፤ እነዚህ በይፋ የሚታዩና ተጠብቀው የቆዩት ናቸው። ስለዚህም ከዚህ የሚበልጡ የኢትዮጵያ ሐብቶች ሌላው አለም እንደ ቅርጫ ተከፋፍሏቸው መገኘቱ ያሳዝናል። ከወርቅ የተሰሩ ፅላቶችን ጨምሮ በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ ውድ የኢትዮጵያ ቅርሶች እንደወጡ ቀርተዋል። ለማንኛውም ግን እነዚህ መፃህፍት ተራ ፅሁፍ የታጨቀባቸው አይደሉም። ቀደምት አባቶች ቆዳ ፍቀው ቀለም፣ አበክተው የፃፉት ነው። እድሜልካቸውን ደክመውበታል። ዓላማቸውም ዘርፈ ብዙና የተለያየ ነው። ለትውልድ ታስበው ነው። መንፈሳዊ መፃህፍት ብቻም አይደሉም። ስለሰው ዘር፣ ስለክዋክብት፣ ስለፀሀይ ጥጥረት፣ ስለህክምና ጥበብ፣ ስለተፈጥሮ ... ወዘተ ... ተዘርዝረው ስለማያልቁ ጥበቦች የሚያትቱ ናቸው። የዘመናዊ ፍልስፍና ምንጮች! ከመትበኘት ያለፈ ሚና አላቸው! ጥበብ፣ እውቀት፣ ስልጣኔ ከዚህ ተወስደው ነው ከዚያ እስኪመጣ የምንናፍቀው። ፍሬውን ወስደዋል፤ ምናለ ልጣጩን እንኳ ቢመልሱልን! ኤዲያ! ወደ ቴዎድሮሳችን እንመለስ።

አፄ ቴዎድሮስ በዘመናቸው ራስ መሸሻ ቴዎድሮስን፣ ቀኛዝማች ሃይሉ ቴዎድሮስን፣ ወ/ሮ አልጣሽ ቴዎድሮስን፣ ይማም ቴዎድሮስን ወልደው ነበር።

አሁን በመጨረሻቸው ዘመን አካበቢ ደግሞ ከመጨረሻዋ ባለቤታቸው ከእቴጌ ጥሩወርቅ ውቤ ልዑል አለማየሁን ወልደው ነበር።

የጀግናው ንጉስ ነገስት የዳግማዊ ቴዎድሮስ /የካሳ ሃይሉ/ የመይሳው ካሳ/ ታሪክ በጀግንነት ከተደመደመ በኋላ፤ ያየነው ነገር ሁሉ ተከናውኖ ሌላ የታሪክ ምዕራፍ ተከፈተ። የልዑል አለማየሁ።

ፕሮፌሰር ሪቻርድ ፓንክረስት ልዑሉን በተመለከተ መረጃዎችን አሰባስበው "Ethiopian Observer" በሚል መፅሄት ላይ እንዳሰፈሩት "እንግሊዞች መቅደላ በመሸገው የንጉሱ ጥቂት ታማኝ ጦር ላይ የመጨረሻውን የማጥቃት እርምጃ ከመውሰዳቸው ጥቂት ጊዜ ቀደም ብሎ መቶ አለቃ ራንሳም በንጉሱ አማካኝነት ልዑሉን ተዋውቆት ነበር። ጤናማና ንቁ የ8 አመት ልጅ ነበር" በማለት ገልፀውታል።

ሆኖም ከጦርነቱ በኋላ አባቱን ለሚያውቃቸውና አማርኛን አቀላጥፎ ለሚናገረው ለሻምበል ስፒድ ሲተላለፍ ግን ልዑሉ ፈዛዛና ጤነኛነቱ የሚያጠራጥር ሆኖ ነበር። ልዑል ከስፒድ ጋር ወደ እንግሊዝ እንዲሄድ



የተደረገው አባቱ ሃገሩን እንዲጎበኝላቸው ይፈልጉ ነበር በሚል ሰበብ ነው። ልዑሉ ከእናቱ፣ ከመምህሩ አለቃ ዘነብ/ይህ ሰው የዘመኑ ሊቅ፣ መፅሃፍ ቅዱስን ወደ ኦሮምኛ የተረጎመ፣ የአፄ ቴዎድሮስ ታሪክ ፀሃፊና ፈላስፋ ሲሆን፤ መፅሃፈ ጨዎታ ስጋዊ ወመንፈሳዊን ጨምሮ በርካታ የፍልስፍና መፃህፍትን የደረሰ ነው።/ ከአልባሹ ገብረመድህን ጋር በመሆን ወደ ወደቡ ተጓዘ።

በዚህ ጉዞ እናቱ እቴጌ ጥሩወርቅ ውቤ ትግራይ ውስጥ "ሸለንቆት ስላሴ" ከተባለ ቦታ ሲደርሱ በጠና ታመሙና፤ ልጃቸውን ለስፒድ አደራ በመስጠትና "የመንፈስ አባቱ" በማድረግ አረፉ። ቀብራቸውም በዚሁ ቤተክርስቲያን በከፍተኛ ሐዘንና በደመቀ ስነ–ስርዓት ተፈፀመ።
ከዚህ በኋላ የልዑሉ ሕይወት መረጋጋት የሌለበትና ጭንቀት የሰፈነበት ሆነ። እናትና አባቱን በተከታታይ በሞት መነጠቁና ነጮች ይበቀሉኛል በሚል ስጋት ፈዛዛ ሆኖ ነበር። ልዑሉ ቀን እረፍት፣ ሌት እንቅልፍ አልነበረውም። ከስፒድ ውጭ ማንንም አይቀርብም ነበር። መምህሩንና አልባሹንም ጠልቷቸው እንደነበር ተገልጿል። በጉዞ ላይ እያሉ ለከፍተኛ የአይምሮ መናወጥ የዳረገውን አጋጣሚ ሻምበሉ እንዲህ ይተርከዋል። "ብዙ ጊዜ ከኔ ጋር ያሳልፍ ነበር። በባህር ላይ እንዳለን ሰኔ 15 ቀን የልዑሉን የድረሱልኝ ጥሪ በአማርኛ አዳመጥኩ። ከነፍሱ ስደርስ ልዑሉን ሎርድ ናፒየር ሲያባብሉት ደረስኩ። በመባነንና በከፍተኛ ጭንቀት ላይ ነበር። በኋላ ስናረጋግጥ መንስዔው የመምህሩ ቁጣ እና ተግሳፅ መሆኑን ደረስንበት።" በማለት ይገልፃል። (አለቃ ዘነብ ለንደን ሳይደርስ ከመንገድ እንዲመለስ ተደርጎ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ነበር በ67 አመቱ 1867 ዓ.ም የሞተው።)

ስፒድ ይቀጥልና፡– "ልዑሉ ለመረጋጋት ሶስት ወር ያህል ወስዶበት ነበር።" ይላል። ልዑል አለማየሁ በሽታው በሚነሳበት ወቅት ስፒድን ቀስቅሶ እንቅልፍ እስኪወስደው እንዲጠብቀው ይማፀነው ነበር። ጉዞው አልቆ እንግሊዝ ገብተውም ከስፒድ መነጠል አይፈልግም ነበር።

ንግስት ቪክቶሪያ እንዲጎበኛቸው ሲልኩበት ስፒድን አስከትሎ ነበር የሔደው። ንግስቲቱን ለመጎብኘት ልዑሉ የሔደ ጊዜ የንግስቲቷ ታማኝ ባለሟል ሚስስ ናንሳይን በማስታወሻ ደብተሯ እንዲህ ብላ አስፍራለች።

"የሐበሻው ንጉስ ልጅ አሳዛኙ አለማየሁ ከስፒድ ጋር መጥቶ ነበር። ከምሳ በኋላ የሐበሻ ልብሱን እንደለበሰ ንግስቲቱ ፊት ቀረበ። ንግስቲቱም ለተወዳጁ ልዑል ሰዓትና የወርቅ ሰንሰለት አበረከቱለት።" ይላል ማስታወሻዋ።

ንግስት ቪክቶሪያም በማስታወሻ ደብተራቸው "ተወዳጅ ልጅ ነው" በሚል ዘወትር ቢያዩት እንደማይሰለቹ አስፍረዋል ይባላል።

የልዑሉ የትምህርት ጉዳይም እንዲታሰብበት ለስፒድ በአመት 300 ፓውንድ፣ ለሞግዚት 400 ፓውንድና ለልዩ ልዩ ወጪም ተጨማሪ ገንዘብ መድበውለታል። ስፒድ ትዳር ከያዘ በኋላም ልዑሉ ለ3 አመታት አብሮት

ኖሯል። በኋላ ግን የመንግስቱ ባለስልጣናት በልዑል አለማየሁ ምክንያት መወዛገብ ጀመሩ።



(ልዑል አለማየሁ ቴዎድሮስ)

"እናት አባቱ የሞቱበት ወጣት ልዑል ወደዚች አገር በመምጣቱ የንትርክና የጭቅጭቅ መነሻ ሆነ" ተባለ። ይህ የሆነው ከመሞቱ አንድ አመት ቀደም ብሎ ነው። ልዑል አለማየሁ ካሳ በባእድ አገርና በባእድ እጅ 11 አመታትን አሳለፎ በ1879 ዓ.ም በ19 አመቱ ሞተ። የሞተውም በህመም ምክንያት ነው ተብሎ ተገለፀ። የቀብር ስርዓቱም እንግሊዝ ውስጥ ዊንድሰር በሚገኘው የቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ውስጥ ተፈፀመ። ስለልዑሉ አሟሟት ንግስት ቪክቶሪያ በማስታወሻቸው ላይ እንዲህ ብለው ፅፈዋል "በዛሬዋ እለት ማለዳ መልካሙ ልጃችን ልዑል አለማየሁ ከዚህ አለም በሞት መለየቱን ስንሰማ ያደረብን ሐዘን እጅግ መሪር ነው። እጅግ በጣም አሳዛኝ! እስከዛች ዕለት ድረስ ልዑሉ የወገኑን እና የአገሩን ናፍቆት በልቡናው አምቆ በባእድ አገር፣ በባዕድ መካከል ኖረ። ህይወቱ በሙሉ ከደስታ የራቀ ነበር።
በቀለሙ ልዩነት ሰዎች አተኩረው ሲመለከቱት ደስታ ይርቀዋል የሚል ግምት አድሮብኝ ነበር። በእርግጥም በሁሉም ነገሮች ከፍተኛ ሃዘን እንደተሰማው አረፈ።"




ለልዑሉ የተገነባለት የነሐስ መቃብር ላይም ከምስሉ ስር ከመፅሐፍ ቅዱስ የወጣ ጥቅስ ሰፍሯል። "እንግዳ ነበርኩ፤ ተቀበላችሁኝን?" ከዚህ ግርጌ ደግሞ "እናት አባቱ የሞቱበት የሐበሻው ወጣት ልዑል እዚህ አርፏል" ይላል። ይህም አፅም ከተዘረፉት ቅርሶቻችን አንዱ መሆኑ ነው።

የሚገርመው በአፄ ቴዎድሮስ ዘመን የንጉሱ ባለሟል የነበረው እንግሊዛዊው ቆንስል ፕላውዴን በአመፀኞች በእነጋረድ ተገድሎ በጎንደር ከተማ ግምጃ ቤት ማርያም ቤተክርስቲያን መቀበሩ ነው። በወቅቱምአፄ ቴዎድሮስ የፕላውዴንን ገዳዮች ተበቅለውለታል።

የአፄ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግስት ያየነውን አይነት ታሪካዊ ክንውን ያሳለፈ ሲሆን ዛሬ ድረስም ገጣሚያን፣ ፀሃፊ ተውኔቶች፣ ደራሲያንና ታሪክ ፀሃፊዎች በቴዎድሮስ ስብዕናና ጀግንነት ተማርከው ደጋግመው ሲዘክሩት ኖረዋል፣ እየዘከሩትም ነው፣ ወደፊትም ሲያወሱት ይኖራሉ። ጥቂቶችን ለአንባብያን ለመግለፅ ያህል በወቅቱ አብሮ የነበረው ዜና መዋዕል አለቃ ዘነብ ታሪካቸውን ሁሉ ተንትኖ የፃፈ ሲሆን ይህን ዕሁፍ ጀርመናዊው ሊቅ ኘ/ር ኢኖሊትማን አሳትመውታል። /the chronicle of king Theodre of Abyssinia/ የቻምበር ማተሚያ ቤት ባለቤት አቶ አስፋው ተፈራም ይህንኑ ታሪክ አሳትመው እንዲሰራጭ አድርገዋል።

አለቃ ወልደማርያም የፃፉት የቴዎድሮስ ታሪክ፣ ሄንሪ ብላንክ በ1868 የፃፉት "Narrative of Captivity in Abyssinia፣ ሄንሪ ሆዚየር በ1925 ዓ.ም ያሳተመው "Record of Expedition to Abyssinia፣ ኘ/ር ሪቻርድ ፓንክረስት "The Emperor Theodore and the Question of foreign Artisans in Ethiopiā ክቡር አቶ ተክለፃድቅ መኩሪያ "አፄ ቴዎድሮስና የኢትዮጵያ አንድነት" ጳውሎስ ኞኞ "አጤ ቴዎድሮስ" ገሪማ ታፈረ "አባ ታጠቅ ካሳ የቋራው አንበሳ"
ሰብ ሩብንስ "The survival of Ethiopian Independence" አቤ ጉበኛ "አንድ ለናቱ"፣ ብርሃኑ ዘሪሁን "የታንጉት ምስጢር ወዘተ ሲጠቀሱ ከገጣሚያንና ከፀሃፊ ተውኔቶች ውስጥም ሎሬት ፀጋዬ ገብረመድህን "ቴዎድሮስ" ቴያትር፣ ጌትነት እንየው "የቴዎድሮስ ራዕይ" ቴያትር ይገኙበታል። ሙዚቀኞችና ሰዓሊያንም ደጋግመው ቴዎድሮስን እያወደሱ ዘፍነዋል፣ ስለዋል። ሌሎችም ያልተዘረዘሩ ስለቴዎድሮስ ታሪክ የሚያትቱ ምልተዋል።









# ምዕራፍ ፩፱

## የአፄ ተክለጊዮርጊስ ዘመነ መንግስት

## ከ 1860-1863 ዓ.ም

እንግሊዞች ጉዳያቸውን ሁሉ ፈፅመው "ተስማምታችሁ ኑሩ" ብለው ሔዱ። በዚህ ጊዜ የቴዎድሮስን መውደቅ ይፈልጉ የነበሩ መሣፍንት ሁሉ ካያሉበት ተደራጅተው የንጉሰ ነገስቱን ስልጣን ለመያዝ ተዘጋጁ።
በወቅቱ 60ሺ. ጦር ሠራዊት የነበራቸው የላስታው ተወላጅ ከአፄ ይትባረክ የዘር ሐረግ የወረዱት ዋግ ስዩም ጎበዜ (ዋግ ሹም ጎበዜ) በፍጥነት ተነስና ለመንገስ ሲሉ ጳጳስ የለም። አቡነ ሰላማ በቴዎድሮስ ጊዜ ስለሞቱና የጳጳስ ማስመጫው ወደብ ምፅዋ በግብፆች ስለተያዘ ዋግ ስዩም ጎበዜ በኢትዮጵያዊው እጨጌ ገብረ ኢየሱስ እጅ ተቀብተው በሚያዝያ ወር 1860 ዓ.ም ነገሡ።ስማቸውም አፄ ተክለጊዮርጊስ ተባለና ንጉሠ ነገስት ዘኢትዮጵያ በማለት ስልጣኑን ያዙ።

በአፄ ቴዎድሮስ ጊዜ የፈራረሱትን አድባራት እያደሱ፣ ለቤተ-ክህነት ሠዎች የቀድሞውን ስርዓት ስለመለሱላቸው ወዲያው ተቀባይነትን አገኙ። ወደ ፋሲለደስ ቤተመንግስት ገብተውም በህንፃው ማማር እየተደነቁ እድሣት የሚያስፈልገውን እያደሱ ጥቂት ወራት እንደቆዩ ደጃዝማች ጉበዜ ሸፈተባቸውና በፋሲለደስ ሜዳ ውጊያ አድርገው በፍጥነት ድል አደረጉት።ያም ቢሆን በየግዛቱ ያሉት መሣፍንትም ለመንገስ ስለሚፈልጉ አፄ ተክለጊዮርጊስ የተረጋጋ መንግስት እንደማይኖራቸው ያውቁታል። በተለይ የትግራዩ ደጃዝማች ካሣ ምርጫ የእንግሊዝ ልዩ ባለውለታ ነበሩና የመሣሪያ እርዳታ አግኝተው ድል ያደርጉኝ ይሆናል በሚል ስጋት አፄ ተክለጊዮርጊስ ከደጃዝማች ካሣ የበለጠ ተቀባይነትን ለማግኘት በርካታ ደብዳቤዎች ለእንግሊዝ ፅፈዋል።

ከዚህ በኋላ በሚኖሩት ታሪኮችም የወቅቱን ሁኔታ ቁልጭ አድርገው የሚያሣዩንና የነበረውን ፍትጊያ የሚያስረዱን በየነገስታቱ የተፃፉት ደብዳቤዎች ናቸውና እንዳስፈላጊነታቸው እንጠቀምባቸዋለን። ተክለፃድቅ መኩሪያ ከንማህተማቸው እንደወረዱ በመፃህፎቻቸው አካተዋቸዋል።

የአፄ ተክለጊዮርጊስን ስጋት እንመልከት። « በስመ አብ..... መልዕክተ አፄ ተክለጊዮርጊስ ትብፃህ ሀበ ንግስተ እንግሊዝ....... አምናም እናንተ ብትመጡ ከሠው በፊት እኔ ተቀብየ መንገድ መርቸ፣ እህልም፣ ማርም፣ቅቤም፣ በግ፣ ፍየል፣ ይዘህ ከሠፈራቸው ግባ ብዬ አዋጅ ነገርሁ። ሽፍታው ጥሶ ጎበዜ (ከነገሁ በኋላ በፋሲለደስ ሜዳ ድል ያደረጉትን ደጃዝማች ጉበዜን ማለታቸው ነው።) ስለተነሣብኝ ወደ እርሱ ሔድኩ። እኔ ስሄን፣ የእንግሊዝ ጦር መቅደላ ሆኑ። የደጃች ካሣ ነገርም (ካሳ ምርጫን ነው።)

ፊትም ትግራይ ስገባ ከሠው በፊት ሎሌነት (አሽከርነት) ገብተልኝ ሹሜ ሽልሜ ባኖረው የትግራይ ሎሌየን አባብሎ ከዳኝ።

ከሠሜን ከወገራ የሾምሁትን ሎሌየን ሐይለማርያምን አስከድቶና አልፎ ተርፎ እስከ ጎንደር ሹሞ ሽልሞ ሰደደው። ይህ ሁሉ መደረጉ የእናንተን ቃል ጠብቄ ብሠነብት ነው እንጅ ለእርሱ የሚሆን ጉልበት አጥቸ አይደለም። ክርስቶስ መንፋቴን አይቶ ጉልበት ቢሠጠኝና በአገሩ ብሾምበት አታድሉብኝ። (እንዳትረዱብኝ)" ይላል። ሁሉንም መሣፍንት "ሎሌ" በማለት የበላይነታቸውን መጠቆማቸው ነው። ይህ ማለት አፄ ቴዎድሮስ በወደቁ በአመቱ መሆኑ ነው። እናም ካሣ ምርጫን (በኋላ አፄ ዮሃንስን) ለመገርሠስ ስላሠቡኩ እንዳትረዱት ማለታቸው ነው። «የእናንተን ቃል ጠብቄ እንጅ ጉልበት አጥቼ አይደለም» ያሉት። እንግሊዞች መቅደላን ለቀው ሲወጡ «ተስማምታችሁ ኑሩ» ብለው በመሄዳቸው ነው።ነገር ግን እንዳሠቡት ሳይሆን ቀርቶ እንግሊዞች ወደ አፄ ዮሃንስ ማድላታቸውን ሲያጤኑም እጅግ ተናደዱና ለፈረንሣይ ንጉስ እንዲህ ብለው ፃፉ።

«ይድረስ እግዜር መርጦ ካነገሠዎ ንጉሠ ነገስት ናፖሊዮን፣ እኔ የእርስዎን ወዳጅነት እጅግ እፈልጋለሁ። አፄ ቴዎድሮስ ያከፉትን (ያበላሹትን) ነገር ሁሉ ከምክርዎና ከፍቅርዎ ጋር በእግዚአብሔር ሃይል አቀናዋለሁ። ደጃች ካሣ ምርጫ እያቱ ላያቴ፣ አባቱ ለአባቴ ተገዝቶ ይኖር ነበር።

እርሱንም እኔ ሹሜ አገር ጠብቅ ብየ ብተወው ሽፍቶ አልታዘዝም አለ። አሁን ግን የምጠይቀው ግባ አለዚያ መጣሁብህ ብየ ነኝና አይፍረዱብኝ......» ይላል። ብዙ ብዙ ሞከሩ። ሆኖም ያመጡት ውጤት አልነበረም። የትግራዩን ደጃዝማች ካሣ ለማስገባት (ለማስገበር) አፄ ተክለጊዎርጊስ የቀራቸው ተዋግቶ እድልን መሞከር ብቻ ሆነ።ከዚያም በመጀመሪያ በስነ-ልቦና ጦርነት ለማሰበርገግ በመልዕክተኛ ዛቻቸውን ማኸጎድጎድ ጀመሩ። ካሣ ምርጫ ድምፃቸውን አጥፍተው የንግስና መንገዳቸውን እዚያው አድዋ ሆነው እያመቻቹ፣ እየተደራጁ፣ እየተዘጋጁ ነው።

አፄ ተክለጊዎርጊስ የሠራዊታቸውን ብዛት ለማስረዳትና ነገሩ በዛቻ የሚከናወን መስሏቸው አንድ ስልቻ ጤፍ አስሞልተው «ወታደሬ በዚህ ልክ ነው» በማለት መልዕክተኛ ይልካሉ።ስልቻ ሙሉ ጤፍ የተላከላቸውን ደጃኸርማች ካሳ የተላከላቸው ጤፍ ተቀብለው ያስቆሉታል። ከዚያም ለመልዕክተኛው የተቆላውን ጤፍ አሸክመው «ወታደርህ እንዲህ ቢበዛ በጥይት ቆልቸ ነው የምሠደው።» ብለው መልሠው ላኩላቸው።

በመጨረሻም በ1863 ዓ.ም ከስልቻው ጤፍ ጋር ያመሣሠሉትን 60ሺ ወታደር አስከትለው ያረጀ መሣሪያና ጋሻ፣ጦር፣ጎራዴ አስታጥቀው ወደ አድዋ ተጓዙ። ደጃዝማች ካሣም በእነዚህ ጊዜያቶች በተመሣሣይ ከእንግሊዝ ጋር ይፃፃፉና እርዳታ ይቀበሉ ነበርና 12 ሺ ሠራዊታቸውን ስድስትና አምስት



እንች ውፍረት ያለውን ሞርታር፣12 መድፍና ብዙ ዘመናዊ መሣሪያ አስታጥቀው በእንግሊዛውያኑ በእነ ኪርክሐም እና በእነ ሉዊ ስልጠና የወሠዱ ወታደሮቻቸውን ጥሩ ምሽግ አስይዘው ጠበቋቸው።

"አሳም" ላይ ውጊያው ተካሔደ። አፄ ተክለጊዎርጊስ ፈረሣቸው ላይ ሆነው «ግፋ በለው» እያሉ ሲያዋጉ ፈረሣቸው በመድፍ ጥይት ይመታና ይወድቃሉ። ወድቀው ከቆሠሉ በኋላ ተማረኩ። በዚህ ጊዜ ያ ሁሉ ወታደራቸው የንጉሱን መማረክ ሲያይ ተደናግጦ ውጊያውን መቀጠል ሳይችል ቀረና ድሉ የደጃች ካሣ ሆነ። 60 ሺ ጦር በ12 ሺ ጦር ድል ተደርጎ 24 ሺ ወታደር ተማርኮ 500 ሲሞት 1ሺ ወታደሮች ቆስለው ብዙ እልቂት ሣይደርስ ጦርነቱ በፍጥነት ተጠናቀቀ። የቀሩትም ሸሹ።

ሐምሌ 5 ቀን 1863 ዓ.ም ደጃች ካሣ ይህን ድል ካገኙ በኋላ አፄ ተክለጊዎርጊስን «አምባ ሠላማ» በተባለ እስር ቤት አጎሯቸውና ጥቂት ጊዜ ቆይተው እዚያው ሞቱ። አፄ ተክለጊዎርጊስ 3 ዓመት በቆየው የስልጣን ዘመናቸው በየአገሩ እየዞሩ ሁሉንም አስገብረው ለመንገስ ቢችሉም፤ ደጃች ካሣን መቋቋም አቅቷቸው ድል መሆናቸውንና ወዲያው መሞታቸውን ሲሠሙም ካህናቱ ከባድ ሐዘን ላይ ወደቁ። የጎንደር፣ የጎጃም፣ የላስታ፣ የአካባቢውን ህዝብ ለማስደሠት ጥረው ነበርና "ባለውለታችን" እያሉ አለቀሠላቸው።

ከዚህ በኋላ አፄ ዮሃንስ ያለ ጠንካራ ተቀናቃኝ የበላይነታቸውን አረጋገጡ። በዚህ ታሪክ ውስጥም ሆነ ወደ ፊት ባሉት ምዕራፎች የምንረዳው ለስልጣን ሲባል ለሚካሄደው ውጊያ የዘመናዊ መሣሪያ እርዳታ ለማግኘትና ለአጠቃላይ የቴክኒክ ድጋፍ መሟላት ሲባል ኢትዮጵያውያኑ የሚመሠርቱት የወዳጅነት ስምምነት ለጣልቃ ገቦች ባእዳን ሠፊ በር መክፈታቸውን ነው። አውሮፓውያኑም ይጠቅመናል ያሉትን ወገን ለማንገስ የሚችሉትን ድጋፍ ከሠጡ በኋላ ባለውለታነታቸውን ተገን አድርገው የተለያዩ ጥቅሞችን ለማግኘት ይራኮታሉ። በውስጥ ጉዳይ ጣልቃ እየገቡ ይፈተፍታሉ። ከሁሉም በላይ የአገሪቱ ሚስጥር መባከኑ ለበርካታ ችግሮች መንስኤ ሆኗል፤ በውጤቱም ኢትዮጵያ ተጎድታለች።

የሆነው ቢሆን ግን እያንዳንዱ ንጉሠነገስት ተቀናቃኙን አጥፍቶ ስልጣኑን ከያዘ በኋላ ድጋፍ ያደረገለትን አገር እንኳ ሊወር ከመጣ ድባቅ መትቶ መመለስን ኢትዮጵያውያኑ ያውቁበታል። በተደጋጋሚም ተግብረውታል። ስለዚህ ሹክቻው ሁሉ ለዚያች ወንበር ሲባል እንጂ ኢትዮጵያን ለባእድ አሳልፎ የመስጠት ሒደት በማናቸውም ንጉሠነገስት ልብ ውስጥ ፈፅሞ አልነበረም።

# ምዕራፍ ፸

## የአፄ ዮሃንስ 4ኛ ዘመነ መንግስት

## ከ1864-1881 ዓ.ም

ከ1860ዎቹ ጀምሮ የአውሮፓ ካፒታሊዝም ወደ ኢምፔሪያሊዝም ለመሸጋገር እንቅስቃሴ የጀመሩበትና አፍሪካን ለመቀራመት እቅድ ያወጡበት ጊዜ ነው። በተጠቀሰው ዘመን ደግሞ እንግሊዝና ፈረንሳይ ሀያል አገራት ነበሩ። ይህ በእንዲህ እንዳለም ከ10ኛው እስከ 15ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ የዓለም ሃያል አገር የነበረችው ቱርክ ነች። ሲቀጥልም ስፔንና ፖርቱጋል። ቱርክ ከግዙፉ የቄሳር ግዛቷ ውስጥ አንዷ ግብፅ ነበረች። ምንም እንኳ ናፖሊዮን ከ1794-1797 በእጁ አድርጓት ቢቆይም ገዥነቱን አጠንክሮ መቀጠል ሳይችል ቀርቶ ከግብፅ ተባሯል።

የግብፅ ገዥዎች (ፓሻዎች) ሹመት የሚያገኙትና ሹመታቸው የሚፀድቀው በቱርክ ሱልጣኖች አማካይነት የነበረ ሲሆን ስልጣናቸውን ለማፀደቀ ደግሞ ወደ ኢስታንቡል መጓዝ ግዴታቸው ነበር። ከ1797-1840 ዓ.ም ድረስ የግብፅ ፖሻ የነበረው መሐመድ አሊ የነበረ ሲሆን፤ እርሡም የናፖሊዮንን ጦር ከግብፅ ለማባረር በተደረገው ዘመቻ ጀግንነቱን ያሣየና በሁሉም ዘንድ ተፈሪና ተከባሪ መሆን የቻለ ነው። የዘመናዊት ግብፅ መስራች እያሉም ይጠሩታል። ስለዚህም የግብፃውያን ሕይወት የሆነውን የአባይን ምንጭ ለመያዝ አስቦ በሙቶማ በኩል ኢትዮጵያን ወሮ በቴዎድሮስ የሽፍትነት ዘመን ተሸንፎ ተመልሷል። ቀጣዩ ፓሻ ደግሞ ልጁ አባስ ነበርና ከአፄ ቴዎድሮስ ጋር ሠላማዊ ግንኙነት ለመመስረት ችሎ ነበር። ሆኖም አባስ ወዲያው ስለሞተ ስልጣኑን የመሐመድ ዓሊ 4ኛ ልጁ ሠይድ ፓሻ ተረከበ።

ሠይድ ፓሻ ስልጣን እንደያዘ የበላይ ጌታውን የቱርክን ሡልጣን አስፈቅዶ የስዊዝን ቦይ በፈረንሣዊው መሐንዲስ በዴሊሠንስ አማካይነት አስቀደደ። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ግብፅ በአውሮፓውያን ዘንድ ክበሬታን አገኘች። በስዊዝ ቦይ መከፈት የተነሣ በተቋቋመው ማህበር ውስጥም አክሲዮኖች መሸጥ ጀመሩ።ሠይድ ፓሻ የስዊዝ ቦይ አገልግሎት መስጠት ከመጀመሩ በፊት በ1855 ዓ.ም ስለሞተ ልጁ ስልጣኑን ይዞ የነበረ ቢሆንም፤ እሱም ወዲያው በባቡር አደጋ ስለሞተ የመሐመድ ዓሊ የልጅ ልጅ ኢስማኤል ስልጣኑን ተረከበ።ኢስማኤል የቱርኩን ሱልጣን እንደምንም ወደ ካይሮ ጋብዞ አገሩን አስጎበኘና የተለየ የመንግስት አወቃቀር ቢኖር መልካም መሆኑን ገለፀለት። እቅዱንም ነገረው። በዚህ ጊዜ "ፓሻ" የሚለው ውክልናን የሚገልፀው የሹመት ቃል ቀርቶ "ከዲቭ" ወይም "ጌታው" በሚል ተለወጠና ግብፅ ለቱርክ አመታዊ ግብር ሳታጓድል መስጠት እንዳለባት፤ ነገር ግን ነፃ መንግስት እንደሆነች ለኢስማኤል ተነገረው። ከዲቭ ኢስማኤል ነፃ



ያልሆነችውን ነፃ አገር ግብፅን በከዲቭነት ማስተዳደር ቻለና ከቱርክ ንጉስ ቀጥሎ ሁለተኛው ንጉስ ሆነ።በእያቱ የተቀደደው ቦይ በኩባንያ መልክ ተቋቁሞ በትክክል ስራ የጀመረው 0186 ዓ.ም በእርሱ ጊዜ ሆነ። ለቱርክም አመታዊ ግብሩን ማስገባት ቀጠለ።

የስዊዝ ቦይ ከተከፈተ በኂላ በደቡብ አፍሪካ እየተዞረ፣ ወይም በመካከለኛው ምስራቅ በባህርና በየብስ በብዙ ድካም ተጉዘው አውሮፓ እና ሩቅ ምስራቅ ያደርጉት የነበረው የንግድ ልውውጥ ተቀየረ። ባጠቃላይ ለአውሮፓ፣ ለእስያ፣ ለአፍሪካ ወሣኝ የመተላለፊያ በር በመሆኑ አውሮፓና ሩቅ ምስራቆች በቀላሉ የንግድም የፖለቲካም ግንኙነት ማድረግ ቻሉ። በዚህም የግብፅ መንግስት በአክሲዮን ሽያጩ፣ ከቀረጥ በሚገኘው ገንዘብ ኢኮኖሚውን ገነባ። የጦር ሐይሉንም ከዲቭ ኢስማኤል አጠናከረው።በእነዚህ ጊዜያቶች ስፔንና ፖርቱጋል እየወረዱ እንግሊዝና ፈረንሣይ እየገኑ የሔዱበት ሁኔታ ነበር። እንግሊዝ አይኗን ግብፅ ላይ ጣለች። ልዩ ወዳጅነትም መሠረተች።

ከዲቭ ኢስማኤል ግብፅ በኢኮኖሚ ማንሠራራቷን መሠረት በማድረግ የተስፋፊነት አላማውን ሠነቆ ተነሣ። ዋናው ዓላማው የአባይ ምንጭ የሆነችው ኢትዮጵያ ነበረች። ቱርክም ይዛው የቆየችውን ምፅዋንና ሡአኪምን በ1863 ዓ.ም ለግብፅ በፊርማ ለቀቀች። አሁንም ግብፅ ሡዳንን እንድትይዝ ተደረገ። ከሡዳን አልፋም ኡጋንዳን፣ ..... እያለች እስከ ኒያንዛ ባህር ዘልቃ በርካታ የአፍሪካ አገሮችን መያዝ ቻለች። ብልጣ ብልጦቹ እንግሊዝና ፈረንሣይ ክስር ከስር ይከተሏትና "አይዞሽ" ይሏት ነበር።

ከዲቭ እስማኤልም በርካታ የአውሮፓ አገራት ዜጎችን እየመለመለ የ"ፓሻ"ነት ማእረግ እየሠጠ በሚይዛቸው ግዛቶቹ ላይ እንዲያስተዳድሩ ይሾማቸው ጀመር። ተሿሚዎቹ አውሮፓውያንም ለየአገራቸው ሁኔታዎችን ያመቻቹ ነበር።ይሔ ሁሉ ሲሆን የቱርክ ሱልጣኖች በአካባቢያቸው ያሉትን ግዛቶች ይቆጣጠሩ ነበር እንጅ በቀይ ባህርና በህንድ ውቅያኖስ ያሉ ወደቦችን በግብፅ አማካይነት ነው የሚቆጣጠሩት። ቱርክ የግብፅ የበላይ ስለሆነች ሃሣቧን ጥላ ቁጭ ስትል እንግሊዝና ፈረንሣይ ለግብፅ አጋዥ ሆነው በግብፅ ላይ ይዶልቱ ነበር።

አፍሪካውያንን በአፍሪካውያን እያስወረሩ፤ በግብፅ በሚሾሙ ዜጎቻቸው አማካይነት የወደፊት ዓላማቸውን ለማሳካት እቅድ እያወጡ፣ በጎን ሐይላቸውን እያጠናከሩ፣ የአገራቸውን ጥቅም ይገነቡ ነበር። በተለይም ከቀድሞዋ ገናና አገር ከቱርክ ጋር ጦርነት ከመግጠም ይልቅ የቱርክ ሐይል እንደበሰለ ፍሬ በራሱ ጊዜ "ጧ" ብሎ ሲወድቅ በየግዛቱ ለመተካት ከፍተኛ የቤት ስራቸውን አጠናቀዋል።

በወቅቱ ጀርመን፣ ሩሲያና ኦስትሪያ ስጋት አልነበሩም። ጣሊያንም ብትሆን ከፊል ግዛቷ በፈረንሳይ፤ የቀረው በኦስትሪያ ተወስዶ ኖሮ በ1853

ዓ.ም ነው አንድ አገር ሆና የኢጣሊያ መንግስት የተመሠረተው፡፡ ስለዚህ ፈረንሣይና እንግሊዝ ናቸው የበለጠ ፉክክር ውስጥ የነበሩት፡፡ በተለይ እንግሊዝ በቱርክ ግዛት እንደምትተካ አውቃለችና ከተተኩ በኋላ ነጭና ጥቁር አባይ የሚተሳሰሩበትን የሡዳንን ግዛት ከያዘች በአባይ ውሃ ህልውናዋ የተመሠረተውን ግብፅን መያዝ ቀላል ሲሆንላት፤ ከሡዳን በስተደቡብ ያሉትን እነ ዩጋንዳን ከታላላቅ ሐይቆች ጋር ስትይዝ፣ በታንጋኒካና በካሜሮን የሚገቡትን ጀርመኖች፣ በኮንጎ የተሠማሩትን ፈረንሣይና ቤልጅየምን በንቃት መቆጣጠር እንደሚያስችላት ቀድማ አውቃዋለች፡፡ባጠቃላይ በ1884 እ.ኤ.አ አውሮፓውያኑ አፍሪካን ለመቀራመት የስምምነት ውሣኔ ላይ ሲደርሡ የስዊዝ ቦይ መከፈትን እንደ ልዩ አጋጣሚ በመውሠድ ሲሆን፤ በዚህ ትልቅ ስራም ከገናናዎቹ ቱርክ፣ ስፔንና ፖርቱጋል ጋር ከመወዳደር አልፈው መበለጥ የቻሉበት ሁኔታ ተመቻችቶላቸዋል፡፡ይሔ ሁሉ ሲሆንና ሲባል የኢትዮጵያ ነገስታት ከአውሮፓውያኑ የሚሹት ጥቂት ዘመናዊ መሣሪያና ወዳጅነትን እንጅ በውስጣቸው አንዳች ነገር አልነበረም፡፡አውሮፖውያኑ ግን ግብፅን ተጠቅመው ከመጣል አልፈው በግዛታቸው ስር ለማድረግ ችለዋል፡፡ ለእነዚህ ክንውኖች ይረዳቸው ዘንድም በየአገሩ ቆንስሲሎቻቸውን ያሠማሩ ሲሆን፤ በሐይማኖት፣ በንግድ፣በፖለቲካ ግንኙነት ሠበብ የአውሮፓ ዜጎች ወደ ኢትዮጵያና ወደ ሌሎች አገሮች በየጊዜው እየገቡ ይሠልሉ ነበር፡፡

ከርቀት ሆነውም ወዳጅና አጋዥ በመምሠል በርካታ ቅድመ ስራዎችን አከናውነዋል፡፡ ይህን መነሻ ይዘን ወደ ኢትዮጵያ ስንመጣ ደግሞ በወቅቱ የነበረው የመሣፍንቱ ክፍፍልና አለመግባባት ለሰረኞች ምቹ ሁኔታን ፈጥሮላቸው እናገኛለን፡፡ በዚህም አንዱን መኳንንት እየረዱ ሌላውን እንዲያጠቃና እርስ በርስ እንዲፋጅ ከማድረግ ባለፈ፤ አሸናፊውን በዋሉለት ውለታ መጠቀሚያ ሲያደርጉት መኖራቸው አዲስ ነገር አይደለም፡፡

ወደ ታሪኩ ስንመለስ፡፡ ደጃዝማች ካሣ ምርጫ አፄ ተክለ ጊዮርጊስን ድል ካደረጉ በኋላ ነበር የንግስና ስልጣኑን የያዙት፡፡ ነገር ግን ከመንገሣቸው በፊት የነበሩበትን ሁኔታ እናስቀድም፡፡

ደጃዝማች ካሣ የተወለዱት በትግራይ ግዛት አድዋ ውስጥ በ1825 ዓ.ም ሲሆን በትግራይ መኳንንት እግር ተተክተውም የአካባቢው ገዥ ሆነው ቆይተዋል፡፡ በወደቡ አቅራቢያ መገኘታቸውም ከአውሮፓውያን ቆንሲሎች ጋር ወዳጅነት እየመሠረቱ መጠነኛ የትጥቅ ድጋፍ አግኝተዋል፡፡ እንደሚነግሡ እርግጠኛ ነበሩና ደጃዝማች ከነበሩበት ጊዜ ጀምሮ ራሣቸውን ለየአገሩ መንግስታት በደብዳቤ ያስተዋውቁ ነበር፡፡ለምሣሌ ካሣ ምርጫ ከመንገሣቸው በፊት ነሃሴ 30 ቀን 1863 ዓ.ም ለፈረንሣይ ንጉስ እንዲህ ብለው ፅፈዋል፡፡

‹‹በስመ አብ............ መልዕክተ እመሐበ ደጃዝማች ካሣ፡፡ ርዕሠ መኳንንት ዘኢትዮጵያ፡፡ ትድረስ ለንጉሱ ናፖሊዮን (ቦናፖርትን አይደለም እሡ ቀዳማዊ ናፖሊዮን ነበር የሚባለው) ንጉስ ፈረንሳይ እግዚአብሔር



የሾመኝ በመስከረም ነው፡፡ በመስከረም ወረቀት እንዳልሠድ እንግሊዞች በእንግድነት ወደ አገሬ መጥተውብኝ ነበር፡፡ የበካፋ እና የፋሲል የእነዚህ የነገስታቱ ልጅ ነኝ፡፡ ከመሣፍንት የሚካኤል (የራስ ስዑል ሚካኤል እና የራስ ወልደስላሴ ማለታቸው ነው) ልጅ ነኝ፡፡›› በማለት እራሳቸውን አስተዋወቁ፡፡ ደጃዝማች ካሣ ወዳጅነት ከመመስረቱ ጎን ለጎን ግን ድንበራቸውን አጥብቀው የሚጠብቁና ለኢትዮጵያ አይበጅም ብለው ካሠቡ ማንንም ወደ መሐል አገር አያሳልፉም ነበር፡፡ ለዚህም በራሣቸው እጅች ተፅፈው የተላኩ አንድ ሁለት አዝናኝና አስገራሚ ደብዳቤዎች እንመለከትላቸዋለን፡፡

ደጃች ካሣ ሃይላቸውን እያጠናከሩ በነበረበት ጊዜ በፈረንሣዩ ቆንሲል በሙሲንጅር አማካኝነት ችግር ውስጥ ገቡ፡፡ ይኸውም በሐይማኖት ዙሪያ ሲሆን፤ የካቶሊክ እምነትን አላስገባም በማለት ብዙ አታካራ ውስጥ ገቡ፡፡ይህን በተመለከተ ከመንገሣቸው በፊትም በኋላም ደጋግመው ፅፈዋል፡፡ ከመንገሣቸው በፊት፡-

‹‹በስመ አብ ......... የተላከ ከደጃዝማች ካሣ የሠደዱት ወረቀት ደረሠኝ፡፡ አንድ ነገር አለምንዎታለሁ፡፡ የካቶሊክ ካህናቶች እኔ አስተምሩ ሳልላቸው ቤተ-ክርስቲያኑ የኛ ነው፣ ካህናቱም የኛ ናቸው እያሉ አስቸገሩኝ፡፡ በዚህ ነገር የመጣ አይሆንልኝም፡፡ ጥንትም በሴትና በካህን ነው ጠብ የሚመጣው፡፡ አሁንም ከእርስዎ ጋር እንዳያጣሉኝ፡፡ የካቶሊክ ሐይማኖት ክፉ ነው ብዬ አይደለም፡፡ ነገር ግን እጣዬ የማርቆስ የእስክንድርያ ሐይማኖት ነው፡፡ አሁንም እነዚህን ካህናት ቢከለክሉልኝ ስለ ብዙ ገንዘብ እቆጥረዋለሁ፡፡ ነጋዴ ቢመጣ እጠብቃለሁ፣ አገር የሚያይ ቢመጣ እቀበላለሁ፡፡ የክርስቲያን አገር ነው አልከለክልም፡፡ ከእርስዎ ጋር ፍቅር (ወዳጅነት) አጥብቼ ፈልጌያለሁ፡፡ ተፅህፈተ በ2 ቀን በመጋቢት 1862 ዓ.ም አድመንነቲ ላይ ›› ይላል፡፡ በዚህ ደብዳቤ ምላሽ ሲያጡም ከነገሡ በኋላ ተመሣሣይ ይዘት ያለው ደብዳቤ የፃፉ ሲሆን፣ ይህንኑ ደብዳቤም ከነገሡ በኋላ ባለው ታሪካቸው እናገኘዋለን፡፡

ደጃዝማች ካሣ አሁንም የመንገስ ፍላጎታቸውን እውን ለማድረግ የሚጠበቅባቸውን ሁሉ እያከናወኑ ነው፡፡ በ1862 ዓ.ም ለእንግሊዝ ውጭ ጉዳይ ሚ/ር ለግራንቪልም እንዲህ ብለው ፅፈዋል፡፡ ‹‹እጅግ ደስ ብሎኛል፡፡ እርስዎን ያህል ወኪል በለንደን አድርጌአለሁና፡፡ የማምናችውን ርዕሠ መማክርት ወርቄ ምርጫን ጭምር ልኬ ሠድጃለሁ፡፡ ገፀ በረከት ለእንግሊዝ ንግስት ሊሠጡ በመልካም እንዲገቡ ቢያደርጉልኝ እጅግ ደስ ይለኛል፡፡

የፍቅር ምልክት ነው፡፡ ደግሞም የጥበብ ነገር ስራ የሚያስተምር ወደ ሐበሻ ቢመጣልኝ እወዳለሁ፡፡ ...›› ይላል፡፡ በዚህ መልዕክት ለንግስት ቪክቶሪያ የላኩት ገፀ በረከት አንድ የወርቅ ድሪ፣24 ባምራ ጦር፣ አንድ የወርቅ ኮርቻ፣ አንድ የወርቅ ልባ ልባ፣ አንድ በወርቅ የተከፈፈ በርኖስ፣ አንድ የወርቅ ጫማ እና ሌሎች ውድ እቃዎች ይገኙበት እንደነበር በጥር 6 ቀን 1863 ዓ.ም የስጦታው ተቀባይ የሆኑት ንግስቷ በፃፉት የምስጋና ደብዳቤ ተረጋግጧል፡፡

እንዲህና እንዲያ እያሉ አገር ውስጥ እየተዘዋወሩ ለስልጣን የሚራኮቱትን መኳንንት ድል እያደረጉ ቆዩና በመጨረሻ ከአፄ ተክለጊዮርጊስ ጋር ያደረጉትን ውጊያ ድል ካደረጉ በኋላ የቀራቸው ነገር ጳጳስ ማስመጣት ብቻ ሆነ። እናም ለግብፅ ገዥ ለከዲብ ኢስማኤልና ለፓትሪያሪኩ ለአባ ዲሜጥሮስ 20 ሺ የማር ትሬዛ ብር ገፀ በረከት ልከው አቡነ አትናቴዎስን ከግብፅ አስመጡ።

አፄ ተክለጊዮርጊስን ሐምሌ 5 ቀን 1863 ዓም ነበርና ያሸነፉት በሐምሌ 22 ቀን በድላቸው ማግስት ለንግስት ቪክቶሪያ እንዲህ ብለው ፅፈው ላኩ። ይህንን ደብዳቤ ሲልኩት ገና ያልነገሡ ቢሆንም የቀራቸው ነገር ስለሌለ እርግጠኛ ሆነው "ርዕሰ መኳንንት" የሚለውን ንጉሥ ነገስት ብለው ነበር የፃፉት።‹‹በስመ አብ .........መልእክት ዘ ስዩመ እግዚአብሔር ካሣ ንጉሠነገስት ዘኢትዮጵያ። ይድረስ ከክበሩት ንግስት ቪክቶሪያ ዘ አገረ እንግልጣር (እንግሊዝ) በእርስዎ ምክር በእርስዎ ፍቅር ፀንቻለሁ። እጅግ ደስ ብሎኛል። አሁንም ጠላቴ ዋግሹም ጎበዜ አፄ ተክለጊዮርጊስ የተባለው ከአድዋ ከከተማየ መጥቶ ተዋጋና ድል አደረግሁት። ከሠራዊቱ ጋር እርሁንም ያዝኩት። ከጠላቴ ሁሉ አንድ እንኳን ያመለጠ የለም። ሁሉ ተለቅመው ከእጀ ገቡ። ከሸዋው ምኒልክ በቀር። የኢትዮጵያን መንግስት ሁሉ በእግዚአብሔር ሃይል ከእጀ አደረግሁት። እንደ ጥንት ፍቅራችን አይርሁኝ። ይዘኑልኝ። እኔም የእንግሊዝን መንግስት ፍቅር አልረሣሁም። እንደ ጥንቴ ነኝ። አባቶቼና አባቶችዎ፣ እኔና እርስዎ እንደተፋቀርን ከአውሮፓ ነገስታት ጋር ሁሉ እንዲያፋቅሩኝ እለምንዎታለሁ። ተፅሀፈ በ22 ቀን ሐምሌ 1863 ዓ.ም በዓድዋ ከተማ .......›› በማለት ድላቸውን አበሠሩ።

ከዚያም ደጃዝማች ካሳ ምርጫ (በዝብዝ ካሳ) ጥር 13 ቀን በ1864 ዓ.ም በእለተ እሁድ በአክሱም ፅዮን ቤተ-ክርስቲያን በጳጳሱ አትናቴዎስ እጅ ተቀብተው "ዮሃንስ 4ኛ" ተብለው የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት ሆኑ።

አፄ ዮሃንስ በዚህ በንግስና በዓላቸው ላይ 3 ቀን ሙሉ ሙሉ ያደረ ግብዣ ያደረጉ ሲሆን፤ለዚህም 4ሺ የደለቡ ሠንጋዎች፣ 150 ሺ እንስራ ጠጅ ቀርቦ ተበላ፣ ተጠጣ።

አፄ ዮሃንስ 4ኛ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ኩተቻለ ኢትዮጵያን አንድ የማድረግና በአንድ ማዕከላዊ መንግስት ስር ተጠቃልላ የምትተዳደር አገር እንድትሆን፣ ካልተቻለ የልዩ ልዩ ግዛቶች ንጉሶች እንዳሉ ሆነው እሣቸው ደግሞ የሁሉም ንጉሳ የበላይ ንጉሠነገስት ሆነው ለማስተዳደር መጣር ጀመሩ። ስለዚህም ከስመው ሊቀሩ የማይችሉትን የየግዛቱን መኳንንት ከቦታ ቦታ እየተዘዋወሩ ማስገበርን የመጀመሪያ ስራቸው አደረጉት። በዚህም ከሞላ ጎደል ስኬታማ መሆን ችለዋል። ሆኖም አፄ ቴዎድሮስ የየግዛቱን መሣፍንት ለማጥፋት እርምጃ እንደወሰዱትና፤ የቤተ-ክርስቲያንን የኢኮኖሚና የፖለቲካ መሠረት በማፍረስ ማእከላዊውን መንግስት በዘመናዊ ጦርና አስተዳደር



ለማጠናከር እንደሞከሩት ሁሉ፤ አፄ ዮሃንስ ደግሞ የየግዛቱን መሣፍንት በስራቸው ካደረጉ በኋላ በተቃራኒ መልኩ ሐይማኖትን ዋና የፖለቲካ መሣሪያ አድርገው ማእከላዊውን መንግስት ለማጠናከርና ለመገንባት ሞከሩ። እነዚህ የተለያዩ ሁለት አካሄዶችም የየራሣቸውን ችግር ማስከተላቸው አልቀረም።

አፄ ዮሃንስ 4ኛ ኢትዮጵያን አንድ ለማድረግና በአንድ ንጉሠነገስት ስር የምትተዳደር አገር እንድትሆን ማይሆን የፈለጉት፤አንድ አይነት ሐይማኖት የሚከተል ህዝብ ጭምር ነበር የፈለጉት። በዚህ አካሄድም መንግስታቸውን ለማጠናከር ሻቱ። እናም በተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ዘንድ እምነትን በሐይል የማስቀየር ጫና አደረጉ።ይህን ከማድረጋቸው በፊትም ከቀድሞ ጀምሮ የፀጋ፣የቅብዓት፣የተዋህዶ እየተባለ ክርክር ይደረግበት የነበረውን ለመጨረሻ ጊዜ እልባት ለመስጠት ካህናቱን ሠብስበው ካከራከሩ በኋላ ተዋህዶ እንዲሆንና የመንግስት ሃይማኖት ሆኖ እንዲቀጥል አውጀዋል። በዚሁ ጊዜም ከሸዋው ምኒልክ ጋር ድርድር አድርገው ምኒልክ የሸዋ ንጉስ እየተባሉ እንዲቀጥሉና ዮሃንስ ንጉሰነገስት ሆነው እንዲያስተዳድሩ፤ ምኒልክም ለማእከላዊው መንግስት ሊገብሩ፣ ጠላት ቢመጣ በህብረት ሊመልሁ የተስማሙበት ወቅት ነበር። የሐይማኖትን ጉዳይ በተመለከተ የወሠዱትን እርምጃ በአውሮፖውያን ዘንድ ጠላትነት እንዳይፈጥር በማለትም ለንግስት ቪክቶሪያ እንዲህ ብለው ፅፈዋል። ‹‹ሸዋ ዘምቼ ሳለሁ እኛ በእኛ ክርስቲያኖች በሐይማኖት ተከራክረን ረትተን በእስክንድሪያ ሐይማኖት አገባናቸው። (ፀጋዎችን) እስላሙ ሁሉ ይህን አይቶ ሠምቶ ለካ ለኛስ አባት የለንም? ብሎ ያጥምቁኝ፤ክርስትና ያስነሱን ብሎ ስለለመነኝ እሽ ከፈቀድህስ ክርስትና ግባ ብየው የኢትዮጵያ እስላም ሁሉ ወዶ በፈቃዱ ክርስቲያን ሆነ። አንድም ነገር በሐይል ያደረግሁት የለኝም። ወዶ በፈቃዱ ገባ እንጂ። ተፅህፈ ህዳር 12 አስመራ››ይላል።

አፄ ዮሃንስ ወደ ሸዋ በዘመቱበት ጊዜም በወሎና በአካባቢው ተመሣሣይ ስራ እየሠሩ በነበረ ጊዜ ነው ራስ ሚካኤልን ክርስትና እንዲነሱ አድርገው እራሣቸው የክርስትና አባት ሆነው ሹመት በመስጠት የስም ለውጥ እንዲያደርጉ በውዴታ የመከሯቸው። ይህን መሠሉ ሁኔታ የሡዳንና የግብፅ ጋዜጦች እየተቀባበሉ ሲያስተጋቡት፣ እንዲሁም ቁጣን ሲቀሰቅስባቸው፤ በሌላ ወገን ደግሞ አውሮፖውያኑ የካቶሊክ እምነት ተከታዮቻቸው የሚደርስባቸውን ጫና ሲያዩ የአፄ ዮሃንስ መንገስ አልዋጥላቸው አለ።ይህን መሠሉ ጫናም በተለይ የእስልምና ተከታዮችን ወደ ሡዳን እንዲሸሹ ያደረገበት ሁኔታ ከመፍጠሩም ,በላይ፤ በኋላም ለሡዳን ድርቡሾች (መሐዲስቶች) መነሳት እንደ አንድ ግብዓት ሆኖ ሲያነሣሣቸው ችሏል። (መሐዲስቶች ማለት የሡዳኑ ነፃ አውጭ የአል ማህዲ (የመሪው) ስም ሲሆን ተከታዮቹ አርበኞች ሁሉ መሐዲስቶች ይባላሉ።) ባጠቃላይ ሁሉም ቢጋ የመንግስት ሐይማኖት በሆነው በክርስትና ስር እንዲሆን አዘዙ። ምንም እንኳ የቀድሞው ስርዓት

የተመሰሁሳቸው የቤተክህነት ሁምችን, ድጋፍ ቢያገኙም ሁኔታው ያስቆጣቸውም አልጠፋም።ሌላው ቀርቶ ከተወዳጁት ከፈረንሣይ መንግስት በኩል ካቶሊኮች ወደ ኢትዮጵያ እየተላኩ በሚመጡ ጊዜ ስልጣኑን በያዙበት አመት መረር ያለ መልዕክት ነበር የላኩት። ለዳግማዊ ናፖሊዮን« አንድ ነገር ልንገርዎ ይስሙኝ። የካቶሊኮችን ነገር። ባገርህ የካቶሊኮችን ሃይማኖት እናስተምር አሉኝ። እኔ ግን መለስሁላቸው። በስላሴ ስም ተጠምቄያለሁ። ክርስቶስን በወንጌል አምናለሁ። የሚያስተምረኝም በማርቆስ ወንበር የተቀመጠ የማርቆስን እጣ (ተዋህዶ) የያዘ ከእስክንድሪያ እርሡ ነው። ለህዝቤም የሚያስተምር እርሡ የእስክንድሪያው ፓትሪያርክ ወይም ጳጳሱ የሾሚችሁ ቀሣወስት ኡሉኝ።ደግሞ አልኳቸው ማስተማር ብትፈልጉ ዓለም ላይ በስላሴ ስም ያልተጠመቁ ክርስቶስን በወንጌል የማያምኑ ብዙ አህዛብ አሉ፤ እነዚያን አስተምሩ አልኳቸው። እነዚህ ካቶሊኮች ናቸው የህዝበ ክርስቲያንን ደም ያፈሠሡ። ደግሞ ካስፈታደ ቤተክርስቲያን ሠሩ። የአገሬን ህዝብ ሁሉ ኑ ወደኛ ግብር እንዳትገብሩ አሏቸው።እኔም አንድ ሹሜን ሂድ ግብር አውጣ ብየ ሠደድሁት። እነዚያም ተሠብስበው ኖር እንገብርም አሉ። አዝገር የሠደድሁት ሹም ቤታቸውን ሲያቃጥል አብሮ ተከሠባቸው። የእነርሡንም ቤተ-ክርስቲያን አቃጠለባቸው። የእኔን ስም ሊያስከፉት ነው። ይህን ሁሉ ግፍ ይጡልኝ። ይህን ሁሉ የሚያደርገኝ ሙሲንጀር (ቆንስሉ) ነው። ተርኩ መርቼ መጥቼ አስገድልሐለሁ ብሎ ፈከረብኝ። ግፌን ይዩት።የካቶሊኮችን ክፋታቸውን ሁሉ ዕፈ ወደ እናንተ ብሠድ ሙሲንጀር ቀምቶ ምፅዋ ላይ ከባህር አገባው። ተፅሀፈ በ8 ቀን ነሃሴ 1864 ዓ.ም አድዋ ከተማ።›› በማለት በሐይማኖት ዙሪያ እንኳ የቀረው ይቅር እንጅ ......... አይነት አቋም ይዘው እንዳይቀየሙ ቀድመው በማሣሠብ መረር ያለ እርምጃ ወስደዋል።

አፄ ዮሃንስ በየወደቡ አሠፍስፈው ያሉ ኢትዮጵያን የመውረር እቅድ ያላቸው ወገኖች መበርከታቸውን ባዩ ጊዜም ከተለያዩ የአውሮፓ ነገስታት ጋር ወዳጅነታቸውን ለማጠናከር እንደተጉ ናቸው። ያሉበትን አጣብቂኝም በደብዳቤያቸው ጠቆም እያደረጉ ነው የሚልኩት። ቀጥለን የምናየው ለኢጣሊያ ንጉስ ለኡምቤርቶ የፃፉትም የዚሁ አንድ አካል ነው።

‹‹መልዕክተ ስዩመ እግዚአብሔር ዮሃንስ ንጉሠ ነገስት ይድረስ ከንጉስ ኡምቤርቶ ፊተኛው ዘኢጣሊያን። (ቀዳማዊ ማለታቸው ነው።) እንዴት ነዎ። እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ። ከዚህ በፊት ደብዳቤ ያልፃፍሁልዎ መንገዱ በእስላም እጅ ተዘግቶብኝ ነው። አሁን እንኳን ይህን ወረቀት የፃፍሁልዎ ከኢጣሊያ በመጡ ነጋዴዎች ምክንያት ነው። ሌላ ጉዳይም እንዳልፅፍልዎ በፊት ወዳጅነትዎን ሳገኘው ብየ ነው። አሁንም የፍቅር ምልክት ይሆን ዘንድ አንድ ተባእት እና አንድ እንስት የአንበሣ ጉችላ (ግልገል) ሠድጃለሁ። ተፅሀፈ በጎንደር ከተማ ሰኔ 14 ቀን›› ብለው ለየት ያለ



ገፀ በረከትም ጨምረው በመላክ እግረ መንገዳቸውንም የጠያቡ በግብፆች መያዝ መሆናከል እንደሆነባቸው ገልፀዋል።

ግብፅ በመሪዋ በከዲቭ ኢስማኤል አማካኝነት ከምፅዋ አልፋ ኢትዮጵያን ለመውረርና ለመያዝ ተነሣች። አፄ ዮሃንስ ይህን አደገኛ የሆነ የወረራ ሐሣብ እና የግብፅን እንቅስቃሴ እንዳዩ ጉዳዩን በሠላማዊ መንገድ ለመፍታት ቢጥሩም የአውሮፓ አገሮች ፊታቸውን ከኢትዮጵያ አዙረው ውስጥ ውስጡን ለግብፅ ማድላት ጀመሩ።

በዚህ ጊዜ አፄ ዮሃንስ ለእንግሊዝ ንግስት እንዲህ ብለው ላኩ።

‹‹.......... የግብፅ መንግስት በያለበት ከቦኛል። የአውሮፓ ክርስቲያን ነገስታት መሣሪያ ይዘው መጥተው የኢትዮጵያን ንጉስ ይጠብቁ አልልም። ነገር ግን ሐቀኞች ገላጋዮች ልከው በእኔና በኢስማኤል መካከል ነገሩን በትክክል መርምረው ማናችን ጥፋተኛ እንደሆንን፣ ማናችን ወራሪ መሆናችን ለይተው እንዲረዱ ነው።››

ለዚህ ደብዳቤ ምላሽ ከንግስት ቪክቶሪያ የተላከላቸው ሲሆን፤ የንግስቷ ምላሽም እንዲህ የሚል ነበር። ‹‹ በአገልጋይዎ በጄኔራል ኪርክሐም እጅ የላኩልን ደብዳቤ ደርሶናል። በከዲቭ ኢስማኤል አድራጎት የደረሠብዎን ስለነገሡልን ጉዳዩ አስግቶናል። እርስዎም ወዳጃችን ስለሆኑ እውነተኛውን ነገር ለመረዳት በቆንሲላችን በኩሎኔል ስታንቶን በኩል ጠይቀነው በሠጠን መልስ ላይ የግዛቱን ፀጥታ በድንበር ላይ ከሽፍቶችና ከቀማኞች ለመጠበቅ የወታደሮቹ ንቅናቄ ከማግኘት በቀር አገርዎን ለመውረር ምንም ሐሣብ እንደሌለው አረጋግጦልናል። ከዚህም የተረፈውን የውጭ ጉዳይ ሚንስትራችን በዝርዝር እሚልኩ እንዲልክልዎ አዘነዋል። ይህ ደብዳቤ ሲደርስዎ ከከዲቭ ኢስማኤል በኩል በግዛትዎ ላይ ያሠጋዎ ጉዳይ በፍፁም እንደሚወገድ ተስፋ እናደርጋለን።›› ይላል።ነገር ግን የአፄ ዮሃንስ ስጋት እንኳን ሊወገድ ጭራሽ ተባባሠና ወዲያው ጊሐድ የጠጣው ወረራ ተካሔደ። ግብፆች በመጀመሪያ ከምፅዋ አልፈው የቦጎስ ከረንን ክልል ተቆጣጥረው ማስፋፋት ጀመሩ።

‹‹ የኢትዮጵያ ልጅ ሆይ ልብ አድርገህ ተመልከት። ኢትዮጵያ የተባለች አንደኛ እናትህ ናት፣ ሁለተኛ ዘውድህ ናት፣ ሶስተኛ ሚስትህ ናት፣ አራተኛ ልጅህ ናት፣አምስተኛ መቃብርህ ናት። እንግዲህ የእናት ፍቅር፣ የዘውድ ክብር፣ የሚስት ደግነት፣ የልጅ ደስታ፣ የመቃብር ከባድነት እንደዚህ መሆኑን አውቀህ ተነሣ።›› (አፄ ዮሃንስ 4ኛ የተናገሩት የቅስቀሣ ንግግር ነው (ወይም አዋጅ)

1866 ዓ.ም የግብፁ መሪ ከዲቭ ኢስማኤል ኢትዮጵያን ለመውረር በሠሜንና በምስራቅ በኩል ሠራዊት አዘጋጀ። በሠሜን ለሚዘምተው ሠራዊት መሪዎቹ ራውፍ ፖሻ እና የዴንማርኩ ቅጥረኛ ኩሎኔል አሬንድሩፕ ሲሆኑ፤ በምስራቅ በኩል ለሚዘምተው ሠራዊት ደግሞ የስዊዝ ተወላጅ የሆነውና ፈረንሣይ ዜግነት የሠጠችው ግብፅ ቦጎስን እንድትቆጣጠር ያስቻለው፤ ከዚህ

በፊትም አፄ ቴዎድሮስን ለማጥቃት ጄኔራል ናፒየር ሲመጣ ከሌሎች ሐበሾች ጋር መንገድ መሪና አማካሪ ሆኖ በመስራት ቀንደኛ የኢትዮጵያ ጠላት የሆነው ሙሲንጀር ፓሻ ነው። (ፓሻ የሚለውን ማዕረግ ያገኘው በግብፆች ሲሆን ዜግነቱ ፈረንሣዊ ነው)። በሠሜን ሰዘመተው የግብፅ ወራሪ ጦር ሙሉ በሙሉ አመራሩን አሬንድሩፕ ከያዘው በኋላ ከምፅዋ በመንቀሣቀስ ዶጋሊን፣ ከዚያም ሐማሴንን ወረሩ።

አፄ ዮሃንስ 70 ሺ ጦር የሚደርስ ጦር ሠራዊታቸውን ባልተጠበቀ ፍጥነት በማሠባሠብ ወደ ወራሪው በመገስገስ ጉንደት ላይ ገጠሙት። ሠራዊታቸው በእነ ራስ አሉላ እና በእነ ደጃዝማች ሐጎስ መሪነት ጠላትን በማጥቃት ግብፆችን ብትንትናቸውን አውጥተው ድል አደረጉ። አዝማቹ አሬንድረፕም ተገደለ።

በምስራቅ በኩል በሙሲንጀር ፓሻ መሪነት የተደረገው ወረራም በኢትዮጵያውያኑ የደፈጣ ውጊያ የግብፅ ጦር ተሸነፈ። ጥቂቶች ብቻ ሲተርፉ ሙሲንጀር ፓሻን ጨምሮ አብዛኛው የግብፅ ወታደር አውሣ በተባለው ቦታ በደንከል /አፋር ውስጥ ነው/ አለቁ። ግብፆች በዚህና በጉንደቱ ጦርነት በኢትዮጵያውያን በመሸነፋቸው ከፍተኛ ውርደት ስለተሠማቸው ይህን ሽንፈት ሳይበቀሉት ቢቀሩ ደግሞ የባሠ ሃፍረት ስለሚሆንባቸው ኢትዮጵያን እንደገና ለመውረር ከፍተኛ ዝግጅት ጀመሩ።

20ሺ የሚደርስ ሠራሪ ጦር በመሐመድ ራቲብ ፓሻ፣ በረዳቱ በአሜሪካዊው ጄኔራል ሎረን ከአርሁም በታች በኮሎኔል ማክዳይ እና በኮሎኔል ቻርልስ ፊልድ ከእነዚህም ጋር ከጀርመን የጦር ት/ቤት የሠለጠነው የከዲቭ ኢስማኤል ልጅ ልዑል ሃሠን አመራሩን በመጋራት በ1868 ዓ.ም ኢትዮጵያን በድጋሚ ወረሩ።

ይህ በከፍተኛ ዝግጅት በዘመናዊ የጦር መሣሪያና በአስተማማኝ አመራር የተደራጀው የግብፅ ጦር አፄ ዮሃንስ 4ኛን እንደሚያስፈራራ ግብፆች ስላመኑ ንጉሡ ጦርነት የመግጠሙን ሃሣብ ይታውታል ወይም ሣይዋጉ ይሸሻሉ ብለው በማሠብ ዋና ከተማቸው አድዋ ድረስ ዘልቀው ገብተው እንዲወሩ ከዲቭ ኢስማኤል ጦሩን አዘዙ።

የግብፅ ወራሪ ጦርም ከምፅዋ ወደ አስመራ፣ ከዚያም አስመራን አልፈው ጉራዕ ላይ በመስፈር ጠንካራ ምሽግ ገነቡ።አፄ ዮሃንስም "ምታ ነጋሪት፣ ክተት ሠራዊት" ብለው ከአስሩ አንዱ ብቻ መሣሪያ የታጠቀ 70ሺ ጦር ሠራዊታቸውን አስከትለው ዘመቱ።ከአድዋ የተንቀሣቀሠው የኢትዮጵያ ጦር እየተመመ በጉንደትና በአዲኳላ አድርጎ ወደ ጉራዕ አመራ። ጉራዕ ላይ የመሸገው የግብፅ ጦር 40 መድፍ እና 10 ሮኬት ደግኖ ኢትዮጵያውያኑን ተጠባበቀ። የሁለቱ ሠራዊት ምሽጋቸውን ተገን አድርገው ለሣምንት መቆየታቸው የጦርነቱን ጊዜ አራዘመው።



ልዑል ሜጀር ሐሠን የግብፅ ጦር ከምሽጉ ወጥቶ እንዲዋጋ በማድረጉ በሁለቱም መካከል ባለው ረባዳና ሜዳማ ቦታ በተደረገው የመጀመሪያ ምዕራፍ የጉራዕ ጦርነት የኢትዮጵያ ጀግና ወታደሮች የግብፅን ወታደሮች እያሣደዱ ማጥቃት በመጀመራቸው ግብፆች ተመልሠው ወደ ምሽጋቸው መግባት ግድ ሆነባቸው።

ኢትዮጵያውያኑ ጠላት ከገባበት ምሽግ ውስጥ ተከታታለው እየገቡ መዋጋታቸውን ቀጠሉ። ግብፆች አስቀድመው በምሽጋቸው ውስጥ አስቀምጠዋቸው የነበሩትን መድፎች እየተኮሱ ብዙ የኢትዮጵያ ጀግና ተዋጊዎችን መፍጀት ቢችሉም፣ ጦርነቱ በማግስቱም ቀጠለና በሁለተኛው ቀን የንጉሡ ነገስቱ ወታደሮች ምሽጉን ሙሉ በሙሉ በማጥለቅለቅ ተቆጣጠሩት። ግብፆች ከነዘመናዊ መሣሪያዎቻቸው ተማረኩ። ጥቂቶቹም አመለጡ። በዚህ ድል 20 መድፍና በርካታ ዘመናዊ መሣሪያ ኢትዮጵያውያኑ ማረኩ።

"የጉራዕ ድል በአፄ ዮሃንስ ዘመነ መንግስት ኢትዮጵያውያኖች በወራሪው ጠላት ላይ ካስመዘገቧቸው ድሎች ከፍተኛው ነው።" ብሏል ዋለልኝ እምሩ የዓለም ጀግኖችን ታሪክ በፃፈበት መፅሃፉ። ለዚህ ድል መገኘት አፄ ዮሃንስ ከተራው ወታደር ሳይለዩ ደፋር ተዋጊና አዋጊ በመሆን ያበረከቱት አስተዋፅኦ ከፍተኛ ድርሻ ነበረው። ሠራዊቱ በፅናት ለአገሩ ነፃነት እንዲዋጋ አድርገዋል። ከዚህ በኋላም አፄ ዮሃንስ በአገር ውስጥና በውጭው አለም የተፈሩ እና የተከበሩ ንጉሠ ነገስት ሆኑ።

ከ1866-68 ዓ.ም በነበረው ጊዜ የግብፅን ጦር ደጋግመው ድል ካደረጉ በኋላ ግብፅ የእርቅ ጥያቄ አቀረበች። በጉዳዩም እንግሊዝ አስታራቂ ሆነችና ማግባባት ጀመረች። የግብፅ ጥያቄ ወደቡን እንደያዘች ልትቀጥል፤ ነገር ግን ሌላ የኢትዮጵያን ግዛት ላትነካ የሚል የነበረ ሲሆን፤ አፄ ዮሃንስ ግን ሁሉም ተመልሶልኝ ካልሆነ አልታረቅም" አሉ፡ ግብፅ በኢትዮጵያ ብቻ ተሸነፈች እንጂ ሌላው የአፍሪካ ዘመቻዋ የተሣካ ነበር። ሆኖም የሡዳንን ግዛት ከያዘች ጀምሮ የግብፅን የበላይነት የሚቀናቀን አመፅ ተቀስቅሶ ነበር። በማህዲ የሚመራው የሡዳን አርበኞች ጦር ሠራዊት ግብፅ በኢትዮጵያ መሸነፏን ሲያይ ቀዝቅዞ የነበረውን ትግሉን እንደገና ጀመረ፡

ግብፆችም በጣም እየተዳከሙ ነበርና እንግሊዝን እንደ ድጋፍ መጠቀም ጀምረዋል፡ በዚህ ጊዜ ግብፅ እንግሊዛዊያኑን ጎርደንን የፓሻነት ማዕረግ ሠጥታ ሡዳንን እንዲገዛ አድርጋው የነበረ ሲሆን፤ ጎርደን ፓሻ ግን ዋና አላማው አድርጎ ይንቀሣቀስ የነበረው በሡዳን ላይ በግብፅ ምትክ እንግሊዝን ለመተካት ነበር። ስለዚህም ግብፅን ለማገዝ የእንግሊዝ ጦር በሡዳን ይገኛል። እል ማህዲ ተከታዮቹን ሠራዊቱን /ማህዲስቶችን/ አጠናክሮ በመዋጋት ግብፅና እንግሊዝን አሠጋ። በአገሩ በሡዳን ውስጥ የሚገኙትን የእንግሊዝ፣ የፈረንሣይ፣ የኢጣሊያ፣ የጀርመንና የሌሎች አገሮች ቆንሲሎችንም በግድ ማስለም ጀመረ። ከፊሉ የአውሮፖ ወታደር የግብፅ

ቅጥረኛ ነበር። ይባሥ ብሎም ማህዲ የሱዳኑን ገዥ ጎርደን ፓሻን ድል አድርጎ አንገቱን አስቆረጠው። የማህዲስቶች የበላይነት እየተጠናከረ ሲሄድ ግብፅ እንኳን ሱዳን ውስጥ የመቆየት ከአካባቢው ለቆ ለመውጣትም ተሣናት። ስለዚህ የእንግሊዝን ድጋፍ አግኝታ ለመውጣት ብታስብም የማህዲ ጦር የግብፅ፣ የቱርክ፣ የእንግሊዝን ጦር እያስወጣ እያባረረ ወደ ኢትዮጵያ ድንበር አስጠጋቸው። አልፈው እንዳይሔዱና እዚያው እንዳያልቁ ስለፈለገም አስከበባቸው። እንግሊዝ ግብፅን "ያለው አማራጭ እንደምንም ለቆ መውጣት ነው" በማለት ራሷን ልትተካ የምትችልበትን ሁኔታ ያመቻቸችው በዚህ ጊዜ ሲሆን፤ በዚህም ስኬታማ ነበረች። እንግሊዝ የጎርደን ፓሻ አንገት መቆረጥን ስትሠማ አዘነች። አልበቃ ብሎ ያ ሁሉ ጦር በኢትዮጵያ ሠሜን በከሠላ በኩል ተከቦ በጭንቀት ላይ መሆኑን ስታውቅ አማራጭ አልነበራትምና ሚያዝያ ቀርቶ የነበረውን ስምምነት እንደ አዲስ አንስታ አፄ ዮሃንስን ማግባባቷን ቀጠለች። ጦሩ ከከሠላ የግድ በሠላም መውጣት ነበረበትና። ስለዚህም ሁኔ 3 ቀን 1876 ዓ.ም የእንግሊዝ የባህር ሃይል ም/ል አዛዥ በነበረው በሬር አድሚራል ሔዊት አማካኝነት አፄ ዮሃንስን የ"ሔዊት ውል" የሚባለውን አስፈረሟቸው። ግብፅና ኢትዮጵያ በእንግሊዝ ሽምጋይነት ተስማሙ። በዚህ ውል ውስጥም ግብፅ ወደቡን ለቃ እንድትወጣ፣ አፄ ዮሃንስ ደግሞ ተከቦ የሚገኘውን የግብፅ ጦር ከአካባቢው አስወጥተው በሠላም የግብፅን ጦር እንዲያሻግሩ የሚል ይገኝበታል። ከዚያ በኋላም በእንግሊዝ ተቆጣጣሪነት የኢትዮጵያ ወደብ በሠላም ስራውን እንዲያከናውን እንደሚያደርግና ኢትዮጵያ ከቀረጥ ነፃ እንድትሆን ወዘተ የሚል የራስን ጥቅም ያማከለ ውል ነበረ ተስማምተው የፈረሙበት።እናም በማህዲስቶች የተከበበውን ጦር አፄ ዮሃንስ ከጀግናው አሉላ አባነጋ ጋር ሆነው ተዋግተው ነፃ አውጥተው በሠላም እንዲሻገሩ አደረጉ።

ስለዚህም ማዲስቶች ለኢትዮጵያ የነበራቸው ጥላቻ የበለጠ ተባብሶና አደገኛ ቂም ያዙ። በዚህ ጊዜ እንግሊዝ በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ ገደለች። አንደኛ በዚህ በግብፅ መውጣት መነሻነት የባሪያ ንግድ ለማጥፋት ወዘተ.. በሚል ምክንያት ሱዳንን ቅኝ ግዛት ለማድረግ ስትችል፤ በሌላ በኩል የምፅዋን ወደብ በበላይነት እየመራች ለማስተዳደር የኢጣሊያን ቡድን ወደ ወደቡ ልካ ያሻትን ለማድረግ አመቻቸች። የሔዊት ውል ግብፆች እንዲወጡ እንጂ ወደቡ ለኢትዮጵያ ይመለስ አይልም። ይህ ሁኔታ ከተከናወነ በኋላ ግብፆች ምፅዋንና አካባቢውን ለቀው ወጡ። ወዲያው ግን እንግሊዝ ጣሊያንን ወደ ምፅዋ ልካ ወደቡን እንዲይዙ ተስማምታ፤ በጎን ደግሞ አፄ ዮሃንስን መሸንገል ማባበል ቀጠለች። ግብፅ ከሱዳን ስትወጣም እንግሊዝ ሱዳን ነፃ እንደሆነች አድርጋ ሊሎችን ሱዳናውያን በመሾም የማህዲን ጦር እንዲወጉ አደረገችና ማህዲ ተገደለ። ሆኖም የማህዲን ሠራዊት ኡስማን ዲግና እየመራው በኢትዮጵያ ላይ ተነሣ። ኢጣሊያም በእንግሊዝ ተልኮ በግብፅ



ተተካችና ምፅዋን ያዘች። ቀስ በቀስም የጦር ሃይሏን ማስገባት ጀመረች። የሔዊት ውልም ተጣሠ። አጠቃላይ ክንውኑንም ከራሣቸው ከአፄ ዮሃንስ እንደበት እንስማው።

"..... የላኩት ደብዳቤ ደርሶኛል። ከፍቅርዎ ላይ ፍቅር ለማብዛትም አንድ ሰኔ፣ አንድ ሰልጂ ለራስ አርአያ የሠደዱልኝን ሁለት የከበረ ጎራዴ ከ ስተር ሃሪሠን ስሚዝ እጅ ተቀበልኩ። ደረሠኝ እግዚአብሔር ይስጥልኝ። በፊትም ቱርኮች /ግብፆች/ ጉልበት ተሠማኝ፣ ጥዑብ አበዛኑ ብለው ጥንተ ነገስታት የኢትዮጵያ አባቶች ሲገዙት የነበረውን አገሬን ቢይዙብኝ ደግሞ የምፅዋን በር የጦር መሣሪያም ሆነ ሌላ ለቤተመንግስት የሚሆን እቃ እንዳይወጣ እንዳይገባ ቢዘጉብኝ ከዚህ በኋላ ቀጥለው በግፍ እቤቴ ድረስ መጥተው ቢወጉኝ ይህን ሁሉ በደሌን ለእርስዎ ፃፍሁልዎ።

እርስዎ ግን አስተውለው አውጥተው አውርደው ከቤተመንግስት ሹማምንቶችዎ ጋር መክረው፣ የምፅዋ በር ይከፈት፣ በእንግሊዝ ጠባቂነት የሐበሻ ነጋዴ ምፅዋ ላይ አይቀረጥ እንደልቡ ይውጣ ይግባ። የጦር መሣሪያም ሌላም ለቤተመንግስተ የሚገባ እቃ ይውጣ አይከልከል፣ ቱርኮችም የነበሩበትን አገር ለቀው ወደ አገራቸው ይመለሡና እነሡ ከነበሩበት የተገኘ የጦር መሣሪያም፣ አገሩም ለንጉሡ ኢትዮጵያ ይሁን ተብሎ ተዋውለው ይህም ቃልኪዳን ተፃፈ ታተመ።

ምፅዋ ግን ቱርኮች ሲለቁ ለሐበሻ ንጉስ ይሁን ተብሎ እውነት ነው ከውል አልገባም። አልተፃፈም አልታተመም። ነገር ግን ከዚህ መሐል ጣሊያኖች መጥተው ምፅዋ ላይ ተቀምጠው ውል አፍርሠው የሐበሻን ነጋዴ ቀረጡ። ደግሞ ከዚያ ተቀምጠው የሆነ ያልሆነውን እየፃፉ እንዳያጣሉኝ፣ በውላችን የሐበሻ ነጋዴም እንዳይቀረጥ የሚጠብቅልኝ፣ በደሌን የምነግረው ከእንግሊዝ ቤተ መንግስት አንድ ሠው ምፅዋ ላይ ይቀመጥልኝ።
ከኢጣሊያ ጋር ተፋቀሩ ብለው የፃፉልኝ ነገርዎ፣ አገሬን እንያዝብህ አይበሉኝ እንጂ እንፋቀር ቢሉኝ አልፋቀርም አላልሁም። ይህ ስለሆነ ግን አላረፉም። የያዙትንም በእጃቸው ይዘዋል፡ ያልያዙትንም እንይዛን ይላሉ። እየተላላኩ የሐበሻን መሬት ሁሉ ይመረምራሉ፡

ከኢጣሊያ ጋር ተፋቀሩ ያሉኝንም ከዚህ በፊት ጠብ አልነበረንም። ደግሞ አገሬን ይዘውብኛል እንጂ እኔ ካገራቸው አልደረስኩም። ነገር ግን የምፋቀርበትን ብልሐቱን አላወቅሁትምና የዚህን ብልሐቱን ገልፀው እንዲልኩብኝ ይሁን። የዚህን ምላሽ ሰምቼ እኔም ምላሹን እፅፍልዎአለሁ።
ተፃፈ ሚያዚያ 18 ቀን 1878 ዓ.ም።"

አፄ ዮሃንስ በውሉ የተደነገገውን የራሣቸውን ስምምነት ሳይክዱ፤ ነገር ግን ጣሊያን ከገባ በኋላ እንኳንስ ያለ ቀረጥ ቀረጥ ተከፍሎበት እንኳን ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ቀደም ሲል የተደነገገውን "የሔዊት ውል" አጭበርባሪ ውል መሆኑን ዘግይተው ይድረሡበት እንጂ ግብፆች ወጥተው ገና ጣሊያን

ሲመጣ ራስ አሉላ አባ ነጋ ከፍተኛ ተቃውሞ አሠምቶ ነበር፡ ሆኖም ሠሚ አላገኙም።

ራስ አሉላ ጀግና ነው። ለአፄ ቴዎድሮስ ጉብርዬ እንደበራቸው ለአፄ ዮሃንስ አሉላ እንግዳ /አሉላ አባነጋ/ ነበር መመኪያቸው። ታላቅ የኢትዮጵያ ባለውለታም ነው። ጀግንነቱ ወደር ያልተገኘለት ሲሆን፤ ባልተለመደ ሁኔታ ከተራ ቤተሠብ ተነስቶ ራስ የሚባለውን ከፍተኛ ስልጣን ማግኘት የቻለ ኢትዮጵያዊ ነው። ነገር ግን በመሣፍንቱ ዘንድ ዝቅ እንዲል የሚያደርጉ ነገር ስራቶች እየተካሔዱበት እንደገናም ጀግንነቱ ስጋትን እያሣደረባቸው ወዘተ ጣል ጣል እየተደረገ የታየበት ሁኔታ ነበር። እስከ ምኒልክ ዘመን ቆይቶም ለኢትዮጵያ ታማኝ፣ ለነገስታቱ ተጠርጣሪ በመሆን ሙሉ እድሜውን ለአገሩ የሠዋ ድንቅ ሠው ነው።እናም ከላይ እንደተገለፀው ጣሊያኖች ከመጡበት ዓላማ በማፈንገጥ ወደ ሌላ አቅጣጫ ፊታቸውን በማዞራቸው "የዶጋሊ ጦርነት" ሲፈጠር ግድ ሆነ።

ጥር 28 ቀን 1878 ዓ.ም ጣሊያኖች የምፅዋን ወደብ ይዘው የእነራስ አሉላን ተቃውሞ በሐሠተኛ ወሬ ለማስተባበል እየሞከሩ ከመጋቢት ወር ጀምሮ አዳዲስ ጦር እየተከታተለ ወደ ምፅዋ በመግባት ምሽጉን መጠባበቅ ያዙ፡ ከምፅዋ ወደብ አልፎም ሌሎች ቦታዎችን እየያዙ የ1878 ዓ.ምን አሣለፉ። በዚህ ጊዜ የጣሊያን መንግስት ለወረራው ክብደት በመስጠት ኮሎኔል ሳሌታን አስነስቶ በምትኩ ጄኔራል ካርሎጄኒን ሾመ። ጣሊያኖች ባልታሠቡና ባልተጠበቀ መንገድና ፍጥነት በምፅዋና ባካባቢው ጌቶች ሆኑ። ከአፄ ዮሃንስና ከራስ አሉላ ጋር ተቀያይመው የሸፈቱትን እየሠበሠቡ ወደራሣቸው ቀላቀሉ። በኮሎኔል ሳሌታ ጊዜ ከወደቡ አጠገብ ያሉት ምንኩሉ እና ዊዓ ከተያዙ ወዲህ በቀጣዩ በጄኔራል ካርሎጄኒ ጊዜ ደግሞ ወረራው ቀጥሎ ከወደቡ19 ኪሎ ሜትር ዘልቆ ሠሐጢን ይዞ መሸጉ።

በጊዜው የሚከላከላቸው አልነበረም። ምክንያቱም ራስ አሉላ ወደ ከሠላ ዘምቶ ነበርና ነው። የሡዳን ማህዲስቶች የግብፅን ጦር ያስመለጡትን የኢትዮጵያ ጦር በእልህ መዋጋታቸውን እንደቀጠሉ ናቸው፡ ስለዚህ አሉላ በከሠላ በኩል ያለውን ድንበር መከላከል ነበረበትና "ኩፊት" በተባለው አውደግንባር በኡስማን ዲግና የሚመራውን የመሐዲን ጦር ድል ካደረገ በኋላ ከኢትዮጵያ ድንበር አባርታል። አፄ ዮሃንስም በተመሣሣይ የኢትዮጵያን አንድነት እያጠናከሩ ከቦታ ቦታ እየተዘዋወሩ ከአገር ውስጥ ተፃራሪዎች ጋር ይዋጉ ነበር።

ራስ አሉላ የጣሊያንን ሁኔታ ሠምቶ የነበረ ቢሆንም፤ ከከሠላው ድል በኋላ ወደ አስመራ መጥቶ የጣሊያንን ወረራ በአይኑ ሲያይ ግን ከጠበቀው በላይ ሆነበት። ቀድሞውንም የጣሊያን አገባብ ያላማረው አሉላ ያኔ ሠሚ በማጣቱ እያዘነ፣ ጦሩን እያበራታና እያጠናከረ ከአስመራ ወደ ጊንዳ በሚጓዝበት ወቅት ይህን ደብዳቤ ፃፈ። የፃፈውም ከጀኔራሉ በኩል የወዳጅነት



ደብዳቤ ከደረሠው በኋላ ነበር። "የተላከ ከራስ አሉላ፡ ይድረስ ለጄኔራል ካርሎጄኒ፡ በናይብ መሐመድ የላኩብኝ ቃል መልካም ነው። እንግዲህ ወዳጅ ከሆንን ሠራዊትዎን ከዊዓ ያስወጡ። ነጋዴውም በአድገዶ (ሀባብ) በኩል መሆኑ ቀርቶ ለመሸጥም ለመግዛትም በጊንዳ በኩል ይመላለስ። ዊዓ ያለው ጦርዎ እስከ ጥር 13 ቀን ድረስ ይልቀቅ። ዞላ ያለው ወታደርዎ ከ ወር በኋላ ይውጣ። ወዳጅነት ከፈለጉ ይሔ መፈፀም አለበት። ያለዚያ ግን ወዳጅነት መቅረቱን ይወቁት። ጥር 5 ቀን 1879 ዓ.ም።" ይህ የራስ አሉላ በራስ መተማመንን የሚገልፅ ደብዳቤ መሆኑ ለማንም አይሠወርም።ይልቁንም በዘመናዊ መሣሪያ የተደራጁና የሠለጠኑ ጦሮች እንደሆኑ እየታወቀ እንዲህ በድፍረት ማስጠንቀቅ ከማንም ባይጠበቅም ከኢትዮጵያዊ ጀግና ግን ይጠበቃል።እናም ጄኔራሉ ይህ ደብዳቤ ሲደርሠው ተከታዩን ምላሽ ፅፎ ላከ።

"ጥር 5 የተፃፈውን ደብዳቤዎን ናይብ መሐመድ ሠጥቶኝ አነበብኩት። ወዳጅነት እንደምፈልግ ዘወትር ነግሬዎታለሁ። ዊዓ ያሉት ወታደሮች ይህን ወዳጅነት አይቃወሙም። እኔ መቼም ቃሌን አልለውጥም። ወታደሮቹ ዊዓ የሚቀመጡት ለአገሩ ፀጥታ ሲባል ነው። እንደውም ከማንኛቸውም ወገን ውጊያ ቢገጥማቸው እንዲቋቋሙ ከቀድሞው የበለጠ አጠናክሬያቸዋለሁ። ይህንንም የምልዎ የኢጣሊያ መንግስት ሌሎችን ሲያከብር ራሡም መከበር እንደሚፈልግ እንዲያውቁት ብዬ ነው። የኛ ወዳጅ እስከሆኑ ድረስ እኔም ወዳጅዎ ነኝ። ምፅዋ ጥር 5 ቀን።"

ይህ የሾርኒ ገፅታ የሚታይበት ደብዳቤ ሲሆን፤ በግልፅ እንደተቀመጠው የገሐድ ጦርነት ለማወጅ እንዳሠቡ ያሣያል። የኢጣሊያና የኢትዮጵያ የመጀመሪያ ግጭትም ይሔው ነው። ከዚህም ባሻገር ጣሊያኖች ለወረራቸው ከሚያረድሯቸው አሣማኝ ካልሆኑ ምክንያቶች ውስጥ ጥቂቱን ብናይ 1ኛ ይሔ ክፍል /ግዛት/ ግብፆች ያስተዳድሩት ስለነበር እኛ በእነርሡ እግር ከተተካን መያዝ አለብን፤ 2ኛ የምፅዋን ወደብ ለማስተዳደር ንግድን ለማስፋፋት ፀጥታን ለማስጠበቅ ቦታዎችን መያዝ ያስፈልገናል፤ 3ኛ በዚህ አካባቢ ያሉት ሙስሊም የሆኑ ጎሣዎች በኛ ጥበቃ ስር መሆንን ስለመረጡ የሚሉት ይገኙባቸዋል። ለዚህም የሚሠጡት ሠበብ "ከላይ የራስ አሉላ ሹማምንት እና የነሻለቃ አርአያ የነ ባላምባራስ ተሠማ ሠዎች ከጊንዳዕ እና ከአይለት እየመጡ ሙስሊሞችን ስላንገላቱዋቸው እነርሡን የመጠበቅ ግዴታ አለብን የሚል ነው።

ለዚህም ራስ አሉላ የሚከተለውን ምላሽ ይሠጣል፡-

"ከምፅዋ ወደብ ጀምሮ ያለው ወረዳ የእስላምም፣ የክርስትያንም ህዝብ የሠፈረበት የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገስት ግዛት ነው ልቀቁ"

ይህም ሆኖ ጣሊያን ጦሩን ማጠናከር እንጂ ለማንኛውም ማስጠንቀቂያ ጆሮውን ሊሠጥ አልቻለም። ከዚህ በኋላ ራስ አሉላ የሚፈልገውና የሚጠብቀው አንድ ነገር ብቻ ነበር። የአፄ ዮሐንስን ትዕዛዝ ብቻ፡ የንጉሡ

ትዕዛዝ ግን እንደመዘግየት አሉ፡ ንጉሡ ከአገር ውስጥ ሹማምንቶች ጋር በስምምነትም፣ በሃይልም የማዛመን ስራቸውን እንደቀጠሉ ናቸው። ሆኖም ይህ የአገር የታሪክና የህልውና ጥያቄ ነበርና ራስ አሉላ በገዛ ፍቃዱ ዳር ድንበሩን ለማስከበር ወሠነ።

አሉላ ሠራዊቱን አስከትሎ በጥር ወር አጋማሽ ላይ 1879 ከጊንዳ ቁልቁል ወደ ሠሐጢ ወርዶ ወደ ጣሊያን ምሽግ ለመድረስ 5 ኪ.ሜ ሲቀረው ሠፈሩ አደረገ። የጣሊያን ጦር በተለያዩ ወረዳዎች በርካታ ሠራዊቶችን አሠማርቷል። አሉላ በሠፈረበት አካባቢ የተመደበው በሜጀር ቦሬቲ የሚመራው ጦር ሲሆን፤ 300፤ ያህል የአካባቢው ተወላጅ የሆኑ ባንዶችና የራሁን ቤጋ አሠማርቷል። አሉላ ተበግቶ የመጀመሪያውን ውጊያ አካሔደ። ጣሊያኖች ቀድመው ምሽግ በመያዛቸው ጉዳት ማድረሣቸውን የተረዳው አሉላ የሠሐጢን ምሽግ ትቶ ወደ ታች ወደ ዶጋሊ ወርዶ ሠፈረና አካባቢውን አጥሮ ተቆጣጠረ።

በዚህ ጊዜ ማጆር ቦሬቲ በጦርነት ላይ እንዳለና እንደተከበበ ገልፆ፤ የጦር እርዳታም ስንቅም በአስቸኳይ እንዲላክለት ወደ ጀነራል ጄኔ ላከ። ጀነራሉም ምንኩሉ ላይ ለሠፈረው ለሌላኛው ጦር ለ3ኛው ባታሊዮን አግረኛ አዛዥ በኮሎኔል ቶማስ ደክሪስቶፍ አዝማችነት የተጠየቀውን የጦር መሣሪያና ሌሎች ነገሮች በበቅሎና በግመል ጭኖ በፍጥነት ወደ ተከበበው ወደ ሠሐጢ ይልካል።

ከዶጋሊ ምንኩሉ ርቀቱ 11 ኪ.ሜ፣ ከምፅዋ ደጋሊ 19 ኪ.ሜ ርቀት ነበረው። ከወደቡ ሠሃጢ ድረስ ግን 24 ኪ.ሜ ይርቅ ነበር። ስለዚህም ኮሎኔል ቶማስ ደክሪስቶፍ ከተሜነው ጭንትና በደንብ ከታጠቀው ሠራዊት 10 ጋር መድፎችንና በርካታ መትረየሶችን አካቶ ሲጓዝ ውሎ ሲጓዝ አድሮ ሌሊት 11 ሠአት ላይ ዶጋሊ ደረሠ።

የአሉላ ጦር ግራ ቀኙን ይዞ ይጠብቅ ነበር። በእነዚህ በተጠቀሁት ቦታዎች መሽገው የነበሩ ሃበሾች በራስ አሉላ አስደናቂ የጦር አቅድና አመራር በመሣሪያ ብቻ ሣይሆን በጨበጣ ውጊያም ጭምር ድሉ የኢትዮጵያ ሆነ።በዚህ ፈታኝ የነበረ ጦርነት ላይ ዋና አዝማቹ ኮ/ል ቶማስ ብዙ ወታደሮቹ ቢያልቁበትም ከቀሩት ከ22 የጦር መኮንኖች ጋር የተረፉትን ወታደሮች ይዞ እስከመጨረሻው ድረስ ተፋለመ። ሽምላውን በቀኝ እጁ ይዞ "ኢጣሊያ ህያው ትሁን! ኢጣሊያ ህያው ትሁን ! ወደፊት ቅደም! በለው! እያለ በጀግነት ሲያዋጋ ቆይቶ በጨበጣ ውጊያው ቆስሎ ወደቀና ከመሞቱ በፊት ለቀሩት ወታደሮቹ በጣር ድምፅ "ለተዋደቁት ዜጎች ከመሞቱ በፊት ቡበረት ሠላምታ ስጡ" እስና አሸለበ። ይህ ሠው በጣሊያናውያን ዘንድ ዛሬ ድረስ ሠፊ ክብር እንደተሠጠው ነው።

ራስ አሉላ ሁሉንም በድል ከተወጣ በኋላ ወደ ዋናው ቦታ ወደ ምፅዋ ለመዝመት አስቦ ተዘጋጀ። ሆኖም ባልተጠበቀው በዶጋሊው ጦርነት



በኢጣሊያና በኢትዮጵያ እንዲሁም በእንግሊዝ መካከል ሠፋ ያለ የፖለቲካ ውዝግብ በመፈጠሩ፤ በአፄ ዮሃንስ ዘንድ ቅሮታ ተፈጥሮ ራስ አሉላ ከጦር ጠቅላይ መሪነቱ ለጊዜው ተገለሰና አልሆነም። ከዚህም በላይ የራስ አሉላ የዶጋሊ ድል ያለ አፄ ዮሃንስ ፈቃድ የተገኘ መሆኑና ከባላባት ዘር ሣይሆን ደሃን የመሠለ ጀብድ መቀዳጀቱ በብዙ መኳንንቶች ዘንድ በስጋት አይን እንዲታይ አደረገው። በነዚህ መሠል ምክንያቶች የምፅዋን ወደብ የማስለቀቅ ሃሣቡ ከንቱ ሆነበት።ይህን ሁኔታ ኤሚሊዮ ዴላቪታ የተባለው የኢጣሊያ የጦር መኮንን በዕሁፍ ሲገልፀው "ከዚህ ከዶጋሊ ድል አድራጊነቱ በኋላ ጠላት በፍፁም ወታደር አልባ የነበረውን ምፅዋን ገስግሶ በመውረር የድል አድራጊነቱን ፍሬ መልቀምን አላወቀበትም።" እያለ የወቅቱን ሁኔታ በዝርዝር አስቀምጦታል። ሆኖም እንደ ሌሎቹ ፀሃፍት አባባል በወደቡ 20ሺ የሚሆን ጦር እንደነበር ተገምቷል። ዞሮ ዞሮ ግን የኤሚሊዮ ዴላቪታ ቃል ይታመናል። ምክንያቱም በወቅቱ ጣሊያኖች ብዙ ጦር ያለ አስመስለው ፕሮፖጋንዳ መንዛታቸው የግድ ነበርና ነው።

ምፅዋ ላይ የነበረው ጀኔራል ካርሎጄኒ የራስ አሉላን ከነጦሩ ወደ አስመራ መመለስ ከሠላዮቹ ካረጋገጠ በኋላ ድንጋጤው በርዶ ወደ ዶጋሊ ሠው ልኮ የወገኖቹን ሬሣ ለማስለቀም ጦር ላከ።ለሬሣ ለቀማ ከተላኩት ሠዎች ውስጥ አንዱ ሃምሣ አለቃ ፊሪኒ ኦታቪዮ ይባላል። ይህ ሠው ወደ ጣሊያን አገር ለወንድሙ ለሉዊጂ ኦታቪዮ የፃፈው ደብዳቤ የተገኘ ሲሆን፤ በደብዳቤው መዝጊያ ላይ የራስ አሉላን የዶጋሊ ድል እና የወቅቱን ሁኔታ ይገልፃልና እኛም ለዶጋሊው ድላችን መዝጊያነት እንጠቀምበት።

"…. ውድ ወንድሜ ከጦርነቱ በኋላ በ3ኛው ቀን በአለቆቼ ትዕዛዝ ጦርነቱ ወደተደረገበት ቦታ የጀግናውን የአገራችንን ተወላጅ የኮሎኔል ቶማስ ደክርስቶፍንና ከእርሁ ጋር የወደቁትን ሬሣ ለማምጣት ሄድን። እንዴት ያለ አስቀያሚ ትርዒት አለው? ሰስቱ ጉብታዎች ራቁታቸውን በሆኑና ገና በሚደሙ ሬሣዎች ተሸፍነዋል። የእነዚህም ሠውነታቸው ከብዙ ቦታ ተቆራርጧል። አንዳንዶችም የተቀሉ አሉ። ጅብ እና አሞራ ምንም ያህል አልጎዳቸውም። ውሎ በማደር ሬሣዎቹ ጠቁረዋል። ከጥቂት ፍለጋ በኋላ የኮሎኔል ክሪስቶፍን ሬሣ አገኘንና በድንኳን ጨርቅ ጠቅለለን በግመል አግዘን ወደ ምንኩሉ ስንደርስ የክብር አቀባበል ተደርጎለት በካቶሊኮች መቃብር ተቀበረ።…" ይላል።

በማናቸውም ጣሊያናዊ ፀሃፊ የተፃፈው የዚያን ወቅት ታሪክ የያዘ መፅሃፍ ሁሉ ልዩ ትኩረትና አድናቆቱ በዶጋሊው ጀግና በራስ አሉላ አባነጋ ላይ ነው። በውጭው ዓለም ብቻም ሳይሆን የአገር ውስጥ ተወላጆችም በስንኞቻቸው እንዲህ አሞግሠውት አልፈዋል።

"መብቱን ዮሃንስ ለሉላ ቢሠጠው፤
እንደ ቀትር እሣት ቱርክን ገላመጠው፤

ጣሊያንም ወደቀ እያንቀጠቀጠው፤
እጭዶና ክምሮ እንደጎብስ አሥጣው፤
"አባ ነጋ አሉላ ካስመራ ቢነሣ
እንደ አንበሣ ሆኖ እሣት እያገሣ
ቢቾግረው ጣሊያን አለ ፎርሣ ፎርሣ።
ጣሊያን በአገርህ አልሠማህም ወሬ፤
የበዝበዞች አሽከር እነሞት አይፈሬ
ዘለው ጉብ ይላሉ እንደ ጎፈር አውሬ፤
አሉላ አባነጋ የዶጋ ላይ ኮሶ፤
በጥላው ያደክማል እንኳንስ ተቀምሶ።
ጣሊያን ሰሐጢ ላይ እግሩን ቢዘረጋ፤
በብረት ምጣዱ በሀሣጢ አደጋ፤
አንገብግቦ ቆላው አሉላ አባ ነጋ፤
ተው ተመከር ጣሊያን ይሻላል ምክር፤
ሠሐጢ ላይ ሆነህ መሬት ብትቆፍር፤
ኋላ ይሆንሐል ላንተው መቃብር።
ይች አገር ኢትዮጵያ የበዝበዝ አገር
ምንም አትቃጣ እንደ እራስ ነብር።"

የዶጋሊ ድል 1879 ዓ.ም ነው የተገኘው።

እስከዚህ ጊዜ ድረስም የኢትዮጵያ አንድነት በውል የተረጋገጠ አልነበረም። ምክንያቱም የየግዛቱ ባላባትን አፄ ዮሃንስ ማሣመን ቢችሉ እንኳን የጎጃሙ ንጉስ ተክለሐማኖትና የሸዋው ንጉስ ምኒልክ ሊስማሙ አልቻሉም።ይህ ደግሞ ለአውሮፓውያኑ የበለጠ እየጠቀማቸው ነበር። ለአፄ ዮሃንስ ደግሞ በተለይ ምኒልክ ሲጋት ሆኑ።

ንጉሠ ነገስት ዮሐንስ በኢትዮጵያ አንድነት በፅኑ የሚያምኑና ለአንድነቷም በጣም ቢጥሩ ከየአቅጣጫው ያለው ነገር ለዚህ ህልማቸው መሠናክል ሆነ።አንድነት ከሌለ ለውጭ ወራሪ መጋለጥ የግድ መሆኑን የተረዱት አፄ ዮሃንስ የጎጃሙ ንጉስ ተክለሐይማኖትና የሸዋው ንጉስ ምኒልክ ከአባይ ወዲያና ከአባይ ወዲህ ባሉ ግዛቶች በይገባኛል ጦር በሚማዘዙ ጊዜ አፄ ዮሃንስ ለማስማማት ብዙ ጥረዋል።

"ከባህር ወዲህ ከባህር ወዲያ ብዙ ጠላት ሣለን እርስ በራሣችን ብንዋጋ የክርስቲያን ደም በከንቱ ቢፈስ ክርስቶስ ደስ አይለውም" ብለዋቸውም ነበር። በተጨማሪም የውስጥ ግጭቱን ለማርገብና ቅድሚያ በውጭ ጠላት ላይ እንዲተኮር በማለት ከጋብቻ ጀምሮ የተለያዩ እርምጃዎች ለመውሠድ ሞክረው ነበር፣ ባጠቃላይ የውስጡ ግጭት፣ የጣሊያን ወረራ፣ የእንግሊዝና የፈረንሣይ ጣልቃ ገብቶ መፈትፈት፣ አንዱ ሳንዱ መሣሪያ እየሠጠ ማናቆርና የፍላጎቱ ማጣኪያ ለማድረግ የሚደረገው ርብርብ፤ በቱርክ ስር የነበረችው



ግብፅና ራሷም ቱርክ በአንድነት ሆነው ጦርነት መክፈታቸው ......ወዘተ ኢትዮጵያን አጣብቂኝ ውስጥ የከተታት ዘመን ሆነና ቂም በቀላቸውን ለመወጣት የተለያየ ዝግጅት ያደርጉ የነበሩትን የሡዳን መሐዲስቶችን (ድርቡሾችን) ምቹ ሁኔታ ፈጠረላቸው።

የአፄ ዮሃንስ ሐይማኖትን ማእከል አድርጎ የተጀመረው መንግስትም ፍፃሜው ተቃረበ።በ1881 ዓ.ም ድርቡሾች በምዕራብ በኩል ወረራ በማድረግ በመተማ አድርገው ጎንደር ድረስ በመዝለቅ ህዝቡን በጭካኔ በመጨፍጨፍ፣ ቤተክርስቲያናትንና ገዳማትን በማፈራረስና በማቃጠል አደገኛ ጥፋት አደረሁ። ዛሬ ድረስ ሊጠገኑ ያልቻሉና ድምጥማጣቸው ጠፍቶ የቀሩ በርካታ ታሪካዊ ቦታዎችም በዚሁ ዘመን ነበር የፈራረሡት።
በዚህ ጊዜ አፄ ዮሃንስ በዘኪ ቱማል የሚመራውን ጦር ለመደምሠስ ከሡሜን ተነሡ። ለዘኪ ቱማልም በድል አድራጊነትና በጀግንነት መንፈስ ተሞልተው ‹‹መጣሁ፣ ታጠቅ፣ እንደ ሌባ በድንገት መጣብኝ እንዳትለኝ...›› የሚል መልዕክት አስቀድመው ላኩበትና፤ ምንም እንኳን ቅር ተሠኝተውበት፣ በመኳንንቱ እና በአውሮፓውያኑ ግፊት ራስ አሉላን ከጠቅላይ ጦር መሪነቱ እንዲገለል አድርገውት የነበረ ቢሆንም በዚህ ውጊያ ያለሡ ተሣትፎ ድል አይገኝም በሚል በሰራቸው አድርገው አብረው ዘመቱ።

የሡዳን 85 ሺ ጦር መተማ ላይ ጠንካራ ምሽጉን ገንብቶ መጠባበቅ የጀመረው ወደ ጎንደር ዝብቶ ከፍተኛ ግፉን ከፈፀመ በኋላ ነበር። በዚህ ቦታ ውጊያው ተጀመረና የኢትዮጵያ ጦር በከፍተኛ ወኔ ምሽጉን እየጣሠ በመግባት ጦርነቱን አፋፋመው። ሡዳኖችም በርትተው ተዋጉ። አፄ ዮሃንስም ከፊት ቀድመው በጀግንነት ሲዋጉና ሲያዋጉ ውለው አመሻሽ ላይ ድሉ የኢትዮጵያ ሊሆን በተቃረበበት ሁኔታ ድንገት አንዲት ተባራሪ ጥይት አፄ ዮሃንስ ደረት ውስጥ ገባች። ሳያቋርጥ ደም ስለፈሠሣቸው ከውጊያው መገለል ግድ ሆነባቸው። የንጉሡን መቁሠል የኢትዮጵያ ሠራዊት ሲሠማ የማረከውን እየያዘ መሸሽ ጀመረ።የሱዳን መሐዲስቶች ይህን ሁኔታ ሲረዱ ከሚሸሹበት ተመልሠው ኢትዮጵያውያንን እየተከታተሉ ማጥቃት ጀመሩ። አፄ ዮሃንስም በዚሁ ሁኔታ አረፉ።

ይህ የጀግንነት አሟሟታቸው እንዳለ ሆኖ፤ በክብር የቀብር ስነ-ስርዓታቸው ሳይፈፀም ሡዳኖች ተከታትለው በማጥቃት የአፄ ዮሃንስን 4ኛ ሬሳ በመማረክ አንገታቸውን ቆርጠው ወሠዱት።ኢትዮጵያውያኑ ንጉሣቸው እንደቆሠሉና እንደሞቱ ተረጋግተው መዋጋትና ድሉን ጨብጠው በጀግንነት ህይወታቸው ያለፈውን አፄ ዮሃንስን እንደመቅበር ወይም በጦርነቱ ላይ ቆስለው ሲዳከሙ የሚቀርቧቸው የጦር መኮንኖች ሁኔታውን ሸፋፍነው ሠራዊቱ እንዳይሠማ አድርገው ውጊያውን ማስቀጠል ሲገባቸው የንጉሡን የመሞት ወሬ በመንዛታቸው ኢትዮጵያ ለዚህ አስቆጭ ሽንፈት ተዳረገች።

ለመተማው ጦርነት ሽንፈት እንደምክንያት ከሚጠቀሱት ውስጥ አንዱ ከላይ ያየነው ሲሆን፤ (ንጉስ ሲቆስልና ሲሞት ሁሉም ወታደሩ ቅስሙ እንደተሰበረና ተስፋ እንደቆረጠ ነው) ሌላኛቹ ደግሞ አፄ ዮሃንስ የሸዋውንና የጎጃሙን ንጉስ ከጎናቸው አድርገው አለመዝመታቸው ነው። ይህን ሁኔታ በሚመለከት አንዳንድ ሀሄፍት ምኒልክ አብረው የመዝመት ሃሣብ አቅርበው ጉዞ የጀመሩና በመሐል አፄ ዮሃንስ በሹማምንቶቻቸው ምክር ሳቢያ ስጋት ውስጥ ገብተው ከመንገድ እንዲመለሱ ማድረጋቸውን ፅፈዋል። የሆነ ሆኖ አፄ ዮሃንስ ብቻቸውን ነበር የዘመቱት።

ለራስ አሉላ የነበራቸው አመለካከት በዮቂቱ ቀንሶ መታየቱንም እንደ አንድ ችግር የሚጠቅሱት አልጠፉም።ራስ አሉላ በዚህ የመጀመሪያው በሆነው ሽንፈቱ ምንም ማድረግ አልቻለም። አፄ ዮሃንስ ከሞቱ በኋላም ወደ ግዛቱ ሲመለስ ጣሊያኖች ዋና ከተማውን አስመራን፣ ከዚያም አልፈው መላ ሐማሴንን በቁጥጥራቸው ስር አድርገው ጠበቁት። አሁንም ምንም ማድረግ ባይችልም የአፄ ዮሃንስ አልጋ ወራሽ ከነበረው ከራስ መንገሻ ጋር ሆኖ በትግራይ መረጋጋትና ስርዓት እንዲሆን አድርጓል።

ግዛቱ የነበረችውን ኤርትራን የወሰዱበትን ጣሊያኖች ለመበቀል ሁሌም ያስብ የነበረው አሉላ፤ ጣሊያኖች ከምኒልክ ጋር ጦርነት በጀመሩ ጊዜ ምቹ ሁኔታ ተፈጠረለትና የረጅም ጊዜ ጠላቱን አድዋ ላይ ከምኒልክ ጎን ሆኖ ድል በማድረግ ተበቀሏቸዋል። ከአድዋ ድል በኋላ አስመራን ከጣሊያኖች ማስመለስ ባይችልም ራስ አሉላ አባነጋ እስከ ሽምግልናው ድረስ ጠላቶቹን ድል በማድረግ ለኢትዮጵያ አኩሪ ታሪክ አስመዝግቦ ያለፈ ጀግና ኢትዮጵያዊ ነው። አፄ ዮሃንስ 4ኛ በ1881ዓ.ም ባየነው መልኩ ፍፃሜያቸው ሆነና የንግስና ዘመናቸው በ17 አመታት ብቻ ተወስኖ ቀረ።

አውሮፓውያንም ከግራ ከቀኝ እየዋከቡና አንዱን ባንዱ እያስወጉ የዜጎቻቸውን ደም ሳያፈሱ ፍላጎታቸውን ለማሟላት ይሯሯጡ ነበርና እቅዳቸው ሙሉ ለሙሉ እየሠመረ የሚሔድበትን መንገድ ጠርገው ጨረሱ። አፄ ዮሃንስና አሉላ ወደ መተማ ሲዘምቱ ጊዜው ምቹ ነበርና በእንግሊዞች ተልካ የመጣችው ጣልያን ከላይ ባየነው መልኩ አስመራን ይዛ ተደላድላ ተቀመጠች። ከመረብ ወዲያ፤ «ምድረ ባህሪ» ተብላ የምትጠራው ግዛትም ከአፄ ዮሃንስ ሞት በኋላ በ1881 ዓ.ም ቀደምት ግሪካውያን ይጠሩበት በነበረው ስም "ኤርትራ" የሚለውን ስያሜ በኢጣሊያኖች አማካይነት ያዘች።
ለአፄ ዮ'ንስ ከተገጠሙላቸው የለቅሶ ግጥም ውስጥ የሚከተው ይገኙበታል።

"አፄ ዮሐንስ ሞኝ ናቸው፤
እናም ሁላችን ናቅናቸው።
ንጉስ ቢላቸው በመሃሉ፣
ወሆን ጠባቂ ልሁን አሉ።
አፄ ዮሃንስ ይዋሻሉ፣



መጠኛ አልጠጣም እያሉ፤
ሲጠጡ አይተናል በርግጥ
ራስ የሚያዞር መጠጥ።
በጎንደር መተክስስ፣
በደንብያ መታረድ አዝኖ ዮሐንስ፣
ደሙን አፈሠሠ እንደ ክርስቶስ።
እንዲያመረው ብሎ ደሐ ወዳጁን፣
መተማ አፈሠሠው ዮሃንስ ጠጁን።
የጎንደር ሐይማኖት ቆማ ስታለቅስ፣
አንገቱን ሠጠላት ደግማይ ዮሃንስ።"







አፄ ዮሐንስ 4ኛ

# ምዕራፍ ፴፩
# የአፄ ምኒልክ 2ኛ ዘመን መንግስት
# ከ1882-1906 ዓ.ም

ልጅ ምኒልክ በ1836 ዓ.ም ነው የተወለዱት። የአፄ ልብነድንግል ልጅ ከሆኑት ከአፄ ያዕቆብ ትውልድ 13ኛ የዘር ሐረግ ላይ ይቀመጣሉ። አያታቸው ሣህለስላሴ የሸዋውን ንጉስ ሐይለመለኮትን ይወልዳሉ። ሐይለመለኮት ወ/ሮ እጅጋየሁን ያገቡና ልጅ ምኒልክን ይወልዳሉ።

ነሐሴ 12 ቀን 1836 ዓ.ም የተወለዱት ልጅ ምኒልክ በ11 አመታቸው አፄ ቴዎድሮስ ወደ ሸዋ በመጡ ጊዜ ይዘዋቸው ወደ ጎንደር ሔደው ነበር። በ1857 ዓ.ም ከወሎና ከሸዋ ባላባቶች ጋር ውስጥ ውስጡን ሲላላኩ ቆይተው ከመቅደላ አምልጠው ሸዋ ገቡ። 10 አመት በግዞት ነበሩ።

ሸዋ መጥተውም በአባታቸው ዙፋን ተቀምጠው ንጉስ ምኒልክ እየተባሉ ሸዋን ብቻ ሲገዙ ቆዩ። በግዞት በነበሩ ጊዜም ሸዋን ይገዛ የነበረው አቶ በዛብህ አፍቅሬ የተባለ ሠው ነበርና ከተባባሪዎቻቸው ጋር ማርከው ዙፋኑን አስለቀቁት። ለ12 አመታት ያህል እስከ 1870 ዓ.ም ተቀናቃኝ ሣይኖርባቸው ሃይላቸውን ሲያጠናክሩ ነበርና አፄ ዮሃንስ ስጋት ገባቸው። እናም ሸዋን ለማስገበር ወደ ደብረብርሐን መጡ። የፈሩት ሣይደርስ ቀረና ንጉስ ምኒልክ ለአፄ ዮሃንስ "እገብራለሁ" የሚል መልዕክታቸውን ላኩ። ደብረሊባኖስ ሔደው በአካል ተገናኝተው ከተስማሙ በኋላ አፄ ዮሃንስ የንጉስ ምኒልክን የሸዋ ንጉስነት ሙሉ እውቅና ሠጡት።

አፄ ዮሃንስ በ1873 ዓ.ም ራስ አዳል የተባሉትን ንጉስ ምኒልክ ባሉበት አስተጠርተው ንጉስ ተክለሐይማኖት ብለው በመሠየም የጎጃም ባላባት "ንጉስ" ተብሎ የማያውቀውን አዲስ ሹመት ሠጥተው አሠናበቱ።

ንጉስ ምኒልክ የሸዋ ግዛታቸውን ወደ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሲያሠፉ፤ ንጉስ ተክለሐይማኖትም ከንጉስ ምኒልክ ቀድመው ለማስፋፋት ሲሻሙ አለመግባባት ተፈጠረ። በ1874 ዓ.ም የሁለቱ ወገኖች ጦርነት ተካሒዶ እምባቦ በተባለ ቦታ ላይ ንጉስ ምኒልክ አሸንፈው ንጉሰ ተክለሐይማኖት ቆስለው ተማረኩ። በዚህ ጊዜ አፄ ዮሃንስ ጉዳዩን ሠምተው ምርኮኛውን ይዘው እንዲመጡ ሲልኩባቸው እንደተባሉት ንጉስ ተክለሐይማኖትን ወስደው ቦሩ ሜዳ ላይ ተገናኝተው አስረከቡ።

አፄ ዮሃንስ "እንዴት ያሰፈታዱ" በሚል ተቆጥተው የወሎን ግዛት ከምኒልክ ቀምተው ሁለት ቦታ በመክፈል አንዱን ለልጃቸው ለራስ አርአያ፣ አንዱን መሐመድ አሊ ሲባሉ ቆይተው በኋላ ሚካኤል አሠኝተው ክርስትና ሳነሲቸው ለራስ ሚካኤል ሠጧቸው። የወሎው ንጉስ ሚካኤል ተባሉ።



በዚህ ጊዜ ንጉስ ምኒልክ ቅር ተሠኙ። አፄ ዮሃንስም የምኒልክን ቅሬታና የጠነከረ ሐይላቸውን ስላልወደዱት ዘላቂ ሠላም እንዲኖር በሚል ልጃቸውን ዘውዲቱን ለልጃቸው ለራስ አርአያ እንዲድሩላቸው ለመኗቸው።

ንጉስ ምኒልክ በ1868 ዓ.ም በ32 አመታቸው 3ኛ ልጃቸውን ከወ/ሮ አብችው ወልደው የነበረ ሲሆን፤ 3ኛ ልጃቸው ዘውዲቱ ነበሩና የአፄ ዮሃንስን ጥያቄ ተቀብለው ለልጃቸው ለራስ አርአያ ዳሩላቸው። ጥቅምት 13 1875 ዓ.ም ሠርጉ ተከናውኖ ዘውዲቱ በ7 አመታቸው ተዳሩ። ከዚህ በኋላ የአፄ ዮሃንስና የንጉስ ምኒልክ ዝምድና ጠንክሮ አፄ ዮሃንስም ደቡቡንና ምዕራቡን ኢትዮጵያ እንደልባቸው ያሠፉ ዘንድ ፈቀዱላቸው።

ንጉስ ምኒልክ ከቦሩ ሜዳ መልስ ግዛት የማስፋፋት ስራቸውን ተያያዙት። ከአባጅፋር ጋር ተላልከው አባ ጅፋርም እንደሚገብሩ ከገለፁ በኋላ፤ ምኒልክ እነ ባሻህ አቦዬን፣ ራስ ጎበናን፣ ራስ ወልደጊዮርጊስን ከነጦራቸው ጀየላኩ ጅማን አልፈው ጌራን፣ ቀጥለው ከፋን፣ እንደገናም በጊቤ ወንዝና በአዋሽ መካከል ያለውን አገር ሁሉ ከየግዛቱ ባላባት ጋር እየተዋጉ አስገበሩ። ወሊሶን፣ አመያን፣ኖኖን፣ ሌቃን፣ ነቀምትንና የወለጋን አገር በሙሉ በራስ ጎበና አማካኝነት አቀኑ። ራስ ወልደ ጊዮርጊስም ሊሙንና ጃንጀሮን ማስገበር ቻሉ።

ከዚያም ራሣቸው ንጉስ ምኒልክ ሔደው የወላይታን አገር አስገበሩ። የጅማው አባጅፋርም ከፋንና አካባቢውን ለማቅናት በተደረገው ዘመቻ ተባብረዋል። በዚህ አይነት ሁኔታ ንጉስ ምኒልክ የኢትዮጵያን ግዛት እያቀኑ፤ እያስገበሩ ቀጠሉ። በተመሣሣይም የሌሎች የገበሩ አገሮች ህዝቦችንና ባላባቶችንም ወደ ሸዋ እየመጡ እንዲሠፍሩና እንዲኖሩ አደረጉ። በዚህም ፀጣ ባለና ባልተለመደ መልኩ የህዝቦችን አንድነት ማጠንከር መቻላቸው ብልህነታቸውን ለማስታወስ አንድ ማስረጃ ነው።

የሩቅ አገር ግዛት ህዝቦችን አምጥተው በክብር እያሣደጉ፣ የተማረኩ ባላባቶችን ግዛትና ሹመት እየሠጡ፣ በነገድ ተለያይቶ የነበረውን ሁሉ በጋብቻ፣በባህልና በሐይማኖቱ ተሣስሮና ተቻችሎ በአንድነትና በፍቅር እንዲኖር፣ አንዱ ያንዱን ጎሣና ሃይማኖት ሣይንቅ አክብሮና አስከብሮ በሠላም ተስማምቶ እንዲኖር አደረጉት። የአንድነቱን ውጤትም ወደ በኋላ ላይ የድል ፍሬ ለቅመውበታል።

ይህን ሁኔታ የበለጠ ግልፅ ለማድረግ ያህል ተክለፃድቅ መኩሪያ "የኢትዮጵያ ታሪክ ከአፄ ቴዎድሮስ እስከ ቀዳማዊ ሃይለስላሴ" በሚለው መፅሃፋቸው ያካተቱትን እንይ።

"በወጣትነታቸው ደጃዝማች ባልቻንና ፊት አውራሪ ሐብተጊዮርጊስን ንጉስ ምኒልክ አምጥተው ካሣደጓቸው በኋላ ለታላቅ ማዕረግ አበቋቸው። ከእለታት አንድ ቀን ሁለቱ መኳንንት መንገድ እየተጓዙ ሳለ የተማረኩበት ቦታ ላይ ሲደርሱ ደጃች ባልቻ "ይሔውልዎ የተማረክንበት ቦታ" ብለው

ለፊት አውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ አስታወሷቸው። ፊት አውራሪም "ይህ ስፍራ የተማረክንበት ሳይሆን የተባረክንበት ነው" አሏቸው" ይባላል።

ንጉስ ምኒልክ ለአፄ ዮሃንስ ታዛዥ ሆነው፤ ነገር ግን የዘር ሀረጋቸውም ከቀዳማዊ ምኒልክ ዘር ከወረደው ከልብነ ድንግል መሆኑን እያንሣሣሡ፤ ንግስናው የሚገባው ለማቸው እንደሆነ እያሀቡ አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅትና የወደፊት መንገዳቸውን በዘዴ ነበር የሚጠርጉት።

እናም ንጉስ ምኒልክ ገና ንጉሠነገስት ሳይባሉ "ንጉሠ ነገስት" የሚል ማህተም አሠርተው ማተም ጀምረው ነበር። በ1880 ዓ.ም የአፄ ዮሃንስ ልጅ የዘውዲቱ ባል የነበሩት ራስ አርአያ ሞቱ። ከዚሁ ጋር ተያይዞም የንጉስ ምኒልክና የንጉሠነገስት ዮሃንስ ወዳጅነት ተቋረጠ።

ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ንጉስ ምኒልክ ከውጭ አገር መንግስታት ጋር ለንግድም ሆነ ለማንኛውም ነገር በቀጥታ እየተፃፃፉ ወዳጅነት ጀመሩ። ይህም ሲባል ለመጀመሪያ ጊዜ ከአውሮፓ ነገስታት ጋር መፃፃፍ የጀመሩት ከ1880 ዓ.ም በኋላ ነበር ማለት አይደለም። መፃፃፍ የጀመሩት ከ1861 ዓ.ም ጀምረው ነው። ከአፄ ተክለጊዮርጊስ ጊዜ ጀምሮ ማለት ነው። ንጉስ ምኒልክ አስቀርፀውት ነበር ያልነው ማህተም "ሞአ አንበሣ ዘእምነገደ ይሁዳ ምኒልክ ንጉሠ ነገስት" ይላል። ንጉሠ ነገስት ብለው "ዘኢትዮጵያን" ያልጨመሩት 1ኛ ሙሉ ኢትዮጵያን አልጠቀለሉም 2ኛ በጳጳስ አልተቀቡም። ይሄንን ግን ቀደም ብለው ለመፈፀም /ገና ከመቅደላ አምልጠው እንደመጡ ጀምሮ/ ፈልገው ነበር። ከእስክንድሪያ ጳጳስ ለማስመጣትም እንደ አፄ ዮሃንስ ከከዲቭ ኢስማኤል ጋር ይፃፃፉ ነበር። ከዚህም ባሻገር የእንግሊዝንና የፈረንሣይን ወዳጅነት ለማግኘት በደብዳቤ ከአፄ ዮሃንስ ጋር ይሻሙ እንደነበር በፓሪስ፣ በሮማና በለንደን የሚገኙት የቤተመፃህፍት ሠነዶች በግልፅ ያመለክታሉ። በፊት በአፄ ተክለጊዮርጊስ ዘመን በ1861 ዓ.ም ለናፖሊዮን በፃፉት ደብዳቤ እንዲህ ብለው ነበር።

"የተላከ ከንጉስ ምኒልክ አገረ ሸዋ። ይድረስ ለንጉሠ ነገስት ናፖሊዮን ዘሐገረ ፈረንሲስ። እንዴት ነዎ እጅጉን። የመልክም ሠውነትዎን ወሬ እየሠማሁ፤ የእርስዎን ወዳጅነት እጅግ እፈልጋለሁ። የፈረንሲስና የሸዋ ፍቅር የተጀመረው በአያቴ በሣህለ ስላሴ ነው። ከሌሎች ክርስቲያን ነገስታት ወዳጆችዎ ጋር እንዲያስተዋውቁኝ።" ብለው ፅፈዋል። በአፄ ዮሃንስ ዘመን ደግሞ በ1866 ዓ.ም ከሙሲንጀር ቀጥሎ በምዕዋ የፈረንሣይ ቆንሲል ለነበረው ዶማርዘክ ሲፅፉ፦ "የተላከ ከንጉሠ ነገስት ምኒልክ። ይድረስ ለቆንሲል ፈረንሣዊ ዶማርዘክ... የእርስዎን ደግነት ሠማሁ። ስለዚህ ነገር ፍቅርዎን ፈለግሁኝ። ከአውሮፓ ነገስታት ሁሉ እንዲያፋቅሩኝ፤ ብርሃን በኢትዮጵያ እንድትገባ እንዲጥሩልኝ" ይላል።



ወደ ዋናው የንጉስ ምኒልክ ደብዳቤ ስናልፍ ለእንግሊዝ ንግስት ለቪክቶሪያ የፃፉትን እናገኛለን። "መልእክት የተላከ ከንጉስ ምኒልክ ሐገረ ሸዋ። ይድረስ ወደ ንግስት ቪክቶሪያ።

እንዴት ነሽ፣ እጅጉን ደህና ነሽ። እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ። ሠዌም አገሬም ደህና ነው። ቀድሞ የሠደድሽልኝ ደብዳቤ ደረሠኝ። እጅግ ደስ አለኝ። መልክተኛዬም ደህና ገባልኝ። ያንችን ወዳጅነትና ምክር እጅግ ሠደድኩ። እኔም ያንችን ፍቅርና ዝምድና ተፈለግሁ ብዙ ቀን ነው። መልክተኛዬ ሣይመለስ ወዳንቺ የላክሁት እኔ ራሴ ወደ መቅደላ ዘምቼ የታሠሩትን ሠዎችሽን ለማስፈታት ነገሩ ባይመቸኝ ተመልሼ አገሬ ገባሁ። ደግሞ ሁለተኛ ሠዌን አዝምቸ የናንተ ወሬ ቢርቀው ያገሬ ሠው ፋሲካን ከዘመቻ መዋል አልለመደምና ተመልሶ ገባ። ሠዌ/ሠዎቼ/ በገቡ በአስር ቀን እንግሊዞች ድል አደረጉ፤ ቴዎድሮስ ሞቱ፤ የሚል የምስራች መጣልኝ።

ይህን ብሠማ እጅግ ደስ አለኝ። እኔም በፍቅር ለመገናኘት ተሠዎችሽ ጋር ስነሣ ቸኩለው ተመለሡ ቢሉኝ ቀረሁ።... እግዚአብሔር ይስጥልኝ። እኔ ስለ ፍቅር ያደረግሁትን ሁሉ ነገር እራስዎም ያውቃሉ። አንድ የብር ካራ፤ አንድ ቢላዋ ሠድጃለሁ። ለንግስት ይጠቅማል ብዬ አይደለም። ለመልክተኛው ምልክት ነው። ሽፍታ እምባ እየያዘ አስቸግሮኛልና ለዚያ መስበሪያ ይፈለግልኝ።" ይላል።

የፍቅር ደብዳቤ አስመስለው ፅፈው ሲያበቁ "ሽፍታ አስቸግሮኛልና መስበሪያው ይፈለግልኝ" ብለዋል። የመሣሪያ እርዳታ መሆኑ ነው። ከቴዎድሮስ ጋርም ያው ፀብ እንደነበሩ ይታወቃል።

"ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ሸዋ... ይድረስ ወደተከበረው የተወደደው ንጉስ ያምቤርቶ። የኢጣሊያ ንጉስ። እጅጉን እንዴት ነዎ እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ። ሠራዊቴም ሁሉ ደህና ነው። ከኮንት አንቶሎኒ ጋር የላክሁት ጉዳይ ሁሉ ቀና ብሎ ኮንት አንቶሎኒ ቢልክብኝ 'እጅግ ደስ ብሎኛል። አሁንም የአሠብን መንገድ ስለመክፈት አሸክሬን ልኬ ብዙ እቃ አስይገፑ ለንጉስ ጥቂት የፍቅር በረከት ከኔ ስዕል ጋር አስይገፑ ልኬዋለሁ። ይህንንም ጥቂቱን የፍቅር ምልክት በረከቴን እንደብዙ አድርገው እንዲቀበሉልኝ እለምናለሁ..." እያሉ ብዙ መሣሪያዎችን በግዥም በስጦታም እየሠበሠቡ ነበር የቆዩት።

ንጉስ ምኒልክ ሶስት ሴቶች ልጆችን ከወለዱ በኋላ ወ/ሮ ባፈናን /ከመርሐቤቴ ባላባት የተወለዱትን/ አግብተው ነበር። ሆኖም ወ/ሮ ባፈና ሀሊያቸው አስቸጋሪ ሆነባቸውና በ1875 ዓ.ም ፈትተው ከየጁ ባላባት የተወለዱትን ወ/ሮ ጣይቱ ብጡልን በ1875 ሚያዚያ 25 ቀን እንደ ደንቡ ሲጋወደሙ ተቀብለው/በአቡነ ማቴዎስ እጅ/ አገቡዋቸው።

ንጉስ ምኒልክ ከ1870ዎቹ ጀምረው የተያያዙትን የግዛት ማስፋፋት ስራ አጠናክረው በመቀጠል በኢትዮጵያ ደቡብ ያለውን ግዛት፤ እንዲሁም

ታላቁን የሐረርን ግዛት ራሳቸው ዘምተው በ1879 ዓ.ም /ከግብፅ ጋር ጦርነቱ ከተካሄደ በኋላ/ አሚር አብዱላሒን አሸንፈው፤ እጁን ስለሠጠ አገሩን በቅንና በትጉህነት ፍርድ እንዲያስተዳድሩ በኋላ ላይ ራስ የተባሉትን የአክስታቸውን ልጅ/ራስ መኮንን/ ደጃዝማች ብለው ሾመው ሐረር ትተዋቸው ተመለሠዋል።

ንጉስ ምኒልክ ከአውሮፓ መንግስታት ጋር ወዳጅነታቸውን እያጠናከሩ፣ ጎን ለጎን ግዛት እያሠፉ ስለነበር ለውጭ አገር ሚስዮናውያን የተመቹ ሆኑ። ሠባኪው ሁሉ እንደ ልቡ መስበክ ጀመረ። በወቅቱ አባ ማስያስ የተባሉ ሚሲዮናዊ ወደ ሸዋ መጥተው ከአገራቸው ከኢጣሊያ መንግስት ጋር ጥብቅ ወዳጅነት እንዲመሠርቱ ይገፋፉዋቸው ነበር። በእርግጥም አማካይነትም ከኢጣሊያ ጋር ቶሎ ቶሎ ይፃፃፉ ነበርና በርከት ያሉ የኢጣሊያ ዜጎች ከአገራቸው መንግስት ተልከው በቆንስልነት ወደ ሸዋ መጡ። ንጉስ ምኒልክ መብዛታቸው ስላልተዋጠላቸው ለአባ ማስያስ "ወደ አገራቸው እንዲመለሡ ይንገሩልኝ" ሲሏቸው አባማስያስ ግን አውሮፓውያን ደግ መሆናቸውንና ክፋት እንደሌለባቸው. የጥንቱን የፖርቹጋልን ወዳጅነት ወዘተ.. እየጠቀሡ "እነዚህም ለግርማዊነትዎ ጥሩ ጥሩ መሣሪያ የሚሠጡ ናቸው እንጂ ተንኮል የለባቸውም። እኔ ዋስ እሆናለሁ" ብለው አሣመኗቸው።

የኢጣሊያ እንግዶችም በአባ ማስያስ አስተርጓሚነት ወደ ንጉስ ምኒልክ ቀርበው እጅ ነስተው በአንኮበር ቦታ ተሠጥቷቸው በሠላም መኖር ጀመሩ። በ1870 ዓ.ም መሆኑ ነው።

ጥቂት ቆይቶ ኮንት ፒየትሮ አንቶሎኒ የተባለው የኢጣሊያ ልዩ መልዕክተኛ መጣ።

ይህ ሁሉ ሲሆን ዋናው ንጉሠነገስት አፄ ዮሃንስ ናቸው። ነገር ግን ከሚሲዮኖችም ጋር ሆነ ከሌሎች የውጭ አገር መንግስታት ጋር የነበራቸው ግንኙነት ተበላሽቶ በራቸውን ዘግተው ስለነበር አውሮፓውያኑ ወደ ሸዋው ንጉስ ወደ ምኒልክ ትኩረታቸውን አደረጉ። አፄ ዮሃንስ በመናገሻቸው በመቀሌ ሆነው ሸዋ ላይ ብዙ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነቶች ይከናወኑ ነበር።

ንጉስ ምኒልክ በመጀመሪያ በአባታቸው ከተማ በአንኮበርና በአካባቢው መኖሪያቸውን አድርገው ሸዋንና አካባቢውን ሲገዙ ቆይተው ለመቀመጫነት ተራራማ የሆነውን ቦታ መረጡ። ዋናውን ታሪክ ከመቀጠላችን በፊትም ንጉሠነገስት ከመሆናቸው በፊት ስለቆረቆሯት አዲስ አበባ ጥቂት እንይ።

ከ1877 ዓ.ም እስከ 1878 ዓ.ም ድረስ ባሉት ጊዜያቶች ንጉስ ምኒልክ እንጦጦ ማርያምንና አጠገቧ የሚገኘውን ደብረሐይል ቅዱስ ራጉኤል አብያተክርስቲያናትን አሠሩ። የመጀመሪያ ቤተመንግስታቸውን የሠሩትም እዚያው እንጦጦ ተራራ ላይ ነበር።

ከእቴጌ ጣይቱ ጋር መቀመጫቸውን እንጦጦ ካደረጉ በኋላም ሹማምንቱን በአካባቢው እንዲሠፍሩ አደረጉ።



በ1879 ዓ.ም አዲስ አበባ በይፋ ተቆረቆረች። ከተማዋ ስትመሠረት በአማካይ ቦታ ላይ የተሠራው ታላቁ ቤተመንግስት/ጊቢ/ ነበር። በኋላ ከፍል ውሐ ከፍ ብሎ በሚገኘው ኮረብታማ ስፍራ ትልቁ ጊቢ ተሠራ። ዙሪያውን ዘበኞች እንዲሠፍሩ ተደረገ። ሹማምንቱም ይህንን መንገድ ተከትለው መኖሪያ ቤታቸውን ገነቡ። በኋላ ላይ ከአድዋ ዘመቻ መልስ ከተማዋ በአዲስ መልክ መስፋፋት ስትጀምር አዲስ አበባ አሏት። በአራት ኪሎና በሌላውም አካባቢ የሹማምንቱና የቆንስሎች መኖሪያ የሆኑ ህንፃዎች እየበረከቱ የተለየ ውበት እየያዘች ሔደች።

ንጉስ ምኒልክ ለባላባቱ ሁሉ በየቦታው አብያተክርስቲያናት እንዲያሣንፁ አዋጅ አስነግረዋል። በዚህ መሠረትም በርከት ያሉ ቤተክርስቲያኖች ሊሠሩ ችለዋል።

ቀደም ባለው ጊዜ ግን በአያታቸው በሣህለ ስላሴ ጊዜ በ1816 ዓ.ም እንደ ቀራኒዮ መድሐኒያለም ያሉ ራቅ ባለ ቦታ የታነፁ አብያተክርስቲያናት ነበሩ። ሆኖም አዲስ አበባ ቤት አልባ ዱር ነበረች።

ንጉስ ምኒልክ በ1881 ዓ.ም የካቲት 28 ቀን ከእንጦጦ ተነስተው መጋቢት 7 ቀን ደብረብርሃን ደርሠው፤ ቀጥለውም ወሎ ሲገቡ በግሸን ሐይቅ የአፄ ዮሃንስን እቃ ይጠብቁ የነበሩት "የንጉስ እቃ ለንጉስ ነውና ይረከቡን" ብለው ላኩ። ንጉስ ምኒልክም መልክተኛ ልከው ተረከቡ።

የአፄ ዮሃንስ መተማ ላይ መሞት ተሠምቶ ነበርና ህዝቡ፣ መኳንንቱ፣ መሣፍንቱ የንጉስ ምኒልክን ተከታይነት ያለተቃውሞ ተቀበለ። የጎጃሙ ንጉስ ተክለሐይማኖት፣ የላስታው ዋግ ስዩም ብሩ፣ የሠሜኑ ደጃዝማች ወልደ ስላሴ፣ የአፄ ቴዎድሮስ ልጅ ራስ መሸሻ... ሁሉም እየመጡ ገቡላቸው። ንጉስ ምኒልክም ለሁሉም ግዛት ሳነሣቸው እየሿሙሩ፣ የቀድሞ ግዛታቸውንም እንዲረጋላቸው እያደረጉ ወደ እንጦጦ ሲመለሡ፤ በረኢሉ ቦሩ ሜዳ አካባቢ ውጫሌ በተባለው ስፍራ ላይ ሠፍረው ሳለ ሚያዝያ 25 ቀን 1881 ዓ.ም ከኢጣሊያ መንግስት ጋር ቀጥሎ ያለውን ውል ተዋዋሉ። በግራዝማች ዮሴፍ አስተርጓሚነት የተዋዋሉትና "የውጫሌ ውል" ተብሎ የሚታወቀውን ታሪካዊ ውል እናይ፦

"... የኢጣሊያ ንጉስ ኡምቤርቶና... የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገስት ዳግማዊ ምኒልክ ለኢትዮጵያ መንግስትና ለኢጣሊያ መንግስት ለልጅ ልጅ የሚኖር ሠላምና እርቅ ለማድረግ የፍቅርና የንግድ ውል ተዋዋሉ።... በኢጣሊያ ንጉስ፤ ኮንት አንቶሎኒ ወደ ንጉሠ ነገስት ምኒልክ ሙሉ ስልጣን ተቀብሎ የተላከ... ንጉሠ ነገስት ምኒልክ የኢትዮጵያን አልጋ የወረሡ እርስዎ ስለሆኑ ይህን ከዚህ ቀጥሎ የተፃፈውን ውል ከኢትዮጵያ ንጉሠ ነገስት ምኒልክ ጋር ተዋዋልን። (ገና ሣይነግሡ በፍጥነት ነበር ያስፈረሟቸው።)

1ኛ በኢጣሊያና በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መካከል በወራሾቻቸውም በህዝባቸውም እነዚህንም በተጠጉ ህዝብ መካከል ሠላምና ፍቅር ሳይጓደል ለዘለቄታ ለልጅ ልጅ ይኖራል።

2ኛ እነዚህን ሁለቱ አሁን የተዋዋሉት ነገስታት በየአገራቸው በየምስለኔያቸው ይነጋገራሉ። አንዱ ከአንዱ አገር ቆንስልም፣ የቆንስልም ወኪል መሾም ይቻላቸዋል። እነዚህም ሹሞች እንደ አውሮፓ ነገስታት ስርዓት መታፈርና መከበር አይጓደልባቸውም።

3ኛ በእነዚህ በሁለቱ ነገስታት ወሰን ጠብና ክርክር እንዳይነሣ በእውቅ የተመረጡ ከሁለቱ ወገኖች ሁለት ሁለት ሽማግሌዎች ልክው በማይጠፋ ምልክት የሚሆን ድንበር ይወስናሉ። ከድንበሩ ወዲህ የሚጨመሩት አገሮች እነዚህ ናቸው። የደጋው አፈር ከኢትዮጵያና ከኢጣሊያ መሐል ወሰን ይሆናል። ከራፋሲ ጀምሮ ሐላይ፣ሠገነይቲ፣አስመራ፣ሰሱ የኢጣሊያ መንግስት መንደር ይሆናሉ። ዳግመኛ በቦጎስ በኩል አዲነፋስ፣ አዲዮገስ በኢጣሊያ ድንበር ውስጥ ይሆናሉ። ከአዲዮገስ ጀምሮ ከምስራቅ ወደ ምዕራብ ባቀና ይከፈላል።

4ኛ የደብረ ቢዘን ገዳም ከእነ ጉልቱ፣ ከእነርስቱ የኢትዮጵያ መንግስት እንደሆነ ይቀራል። የጦር አምባ መሆን ግን አይቻለውም።

5ኛ ከምፅዋ የሚመጣ የንግድ እቃ ከመቶ ስምንት በገቢ እቃ እየተገመገመ በገቢ አንድ ጊዜ ይከፍላሉ።

6ኛ የጦር መሣሪያ ንግድ በምፅዋና በኢትዮጵያ መካከል የሚመላለሠው ለንጉሠነገስት ብቻ ይፈቀድልዎታል። ሲያስመጡም ባለማሁተም ደብዳቤዎን ለኢጣሊያ ሹማምንት እየላኩ ያስመጣሉ። ነፍጡንም የያዘውን ሠፈር ከምፅዋ ጀምሮ እስከ ኢትዮጵያ ድንበር ድረስ የኢጣሊያ መንግስት ወታደሮች ዘበኛ ሆነው ይሸኛሉ።

7ኛ የእነዚህ የሁለቱ ውል ያደረጉ ነገስታት ዜጎች የንግድ እቃውን ይዘው አንዱ ካንድ አገር መሔድ መምጣት ይቻላቸዋል። በየመንግስቱና በየወረዳው ባለው ሹም ጥግነት /ድንበር/ ደስ ብሏቸው ይመላለሣሉ። ነገር ግን ከሁለቱም ወገኖች የጦር መሣሪያ የያዘ ብዙ ሆኖ ካንዱ ድንበር ወደ አንዱ ድንበር መተላለፍ ተከልክሏል። እንዲህም ማለት አንዱ ያንዱን ከብት እንዳይዘርፍ በሁሉም ነገር እንዳይነካካ ተከልክሏል።

8ኛ የኢጣሊያ ሠዎች በኢትዮጵያ፤ የኢትዮጵያ ሠዎች በኢጣሊያና የኢጣሊያ መንግስት በሚገዛው አገር ቢሆን እንደየአገሩ ልማድ መግዛት መሸጥ መከራየት ይቻላቸዋል።

9ኛ የእነዚህ የሁለቱ ነገስታት ዜጎች አንዱ ካንዱ አገር ቢሔድ በሐይማኖታቸው ይኖራሉ።

10ኛ የኢጣሊያ ሠውና የኢጣሊያ ሠው የተካሠሡ እንደሆነ ራሳቸው በመረጡት ዳኛ ያለዚያም ተያይዘው ምፅዋ ወርደው ይዳኛሉ። የኢጣሊያና የኢትዮጵያ ሠው የተጣሉ እንደሆን ግን የኢትዮጵያ መንግስት ወኪልና፣ የኢጣሊያ የምፅዋ ሹም፣ በአንድነት ሆነው ይዳኛሉ።

11ኛ የኢጣሊያ ሠው በኢትዮጵያ የሞተ እንደሆነ፤ የኢትዮጵያም ሠው በኢጣሊያ አገር፣ የኢጣሊያ መንግስት በሚገዛው አገር የሞተ እንደሆነ፣ ከሟቹ መንግስት ወገን ገንዘቡን የሚቀበል ሠው እስኪመጣ ድረስ የሁለቱ ነገስታት ሹማምንት ገንዘቡን ጠብቀው ያስቀምጣሉ።

12ኛ በማናቸውም ሐጢያት ተከሶ የተያዘው የኢጣሊያ ሠው በኢጣሊያ ሹማምንት ይዳኛል። ስለሆነ ግን ታላቅ ሐጢያት ሠርቶ የተገኘ የኢጣሊያን ሠው ፈጥነው ይዘው ለምጽዋ ሹማምንት መስጠት ነው። ደግሞ በኢጣሊያ መንግስት ግዛት የኢትዮጵያ ሠው ታላቅ ሐጢያት ሠርቶ የተገኘ እንደሆን በኢትዮጵያ ዳኛ ይዳኛሉ።

13ኛ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገስት የኢጣሊያ ንጉስ ብርቱ ሃጢያት የሠራ ሠው ካንዱ ግዛት ወደ አንዱ ግዛት ሸሽቶ የሄደ እንደሆን ሁለቱም እያሠሩ ይልካሉ።

14ኛ የባሪያ ንግድ በክርስቲያን ሐይማኖት የተከለከለ ስለሆነ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገስት በሚቻላቸው ነገር ሁሉ ባገራቸው በባሪያ እንዳይነገድ ይከለክላሉ።

15ኛ ይህ አሁን የተፃፈው ውል ለኢትዮጵያ መንግስት ሁሉ ውል ነው።

16ኛ ይህ ውል ከተደረገ ከ5 አመት በኋላ ከሁለቱ መንግስታት አንዳቸው ውል ለመጨመር ወይም ለመለወጥ ያስፈለጋቸው እንደሆነ ካመት በፊት አስቀድሞ መናገር ይገባቸዋል። ነገር ግን የንግድ ውል ብቻ ማረም ማስጠንቀቅ ይገባቸዋል እንጅ ዛሬ የተለየውን የድንበር ወሠን ማፍረስ አይቻላቸውም።

17ኛ የኢትዮጵያ ንጉሠነገስት ከአውሮፓ ነገስታት ለሚፈልጉት ጉዳይ ሁሉ በኢጣሊያ መንግስት አጋዥነት መላላክ ይቻላቸዋል።

18ኛ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገስት ከሌላ መንግስት ሠዎች ጋር የጥበብ፣ የንግድ ነገር ለመዋዋል የፈለጉ እንደሆን ከሁለቱ አማርጠው ሲያበቁ የሁሉቱም ውል አንድ የሆነ እንደሆን ለኢጣሊያ ሠው ይሠጡታል።

19ኛ ይህ አሁን የተደረገው ውል በአማርኛና በኢጣሊያ ቋንቋ ትክክል ሆኖ ተገልብጦ ሲያበቃ የታመነ ምስክር ይሆናል።

20ኛ ይህ አሁን የተፃፈው ውል በሮማ ከተማ ፊርማ ይጠናቀቃል/ተግባራዊ ይሆናል/ ነገር ግን ይህን ውል ኮንት ፒየትሮ አንቶሎኒ በኢጣሊያ ንጉስ ስም ከንጉሠነገስት ምኒልክ ጋር ተዋውለው አትመው ጨርሠዋል። ሚያዚያ 25 ቀን 1881 ዓ.ም በውጫሌ ሠፈር ተፃፈ።" ይላል ውሉ። አይ ጣሊያን!

ሌሎች አንቀፆች ሁሉ የማናቸውም የተለያዩ አገራት ነገሮች ሁሉ የሚዋዋሉዋቸው አይነት ውሎች ይመስላሉ። ነገር ግን አንቀፅ 17 ላይ በአማርኛ ትርጉሙ "የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገስት ከውጭ አገር መንግስታት ጋር የሚያደርገውን ግንኙነት 'ፈቃዱ ከሆነ' በኢጣሊያ መንግስት በኩል ሊያደርግ ይቻለዋል" የሚል ትርጉም የሚሠጠው ዓረፍተ ነገር በጣሊያንኛ አተረጓጎም "የኢትዮጵያ መንግስት ከውጭ አገር መንግስታት ጋር የሚያደርገውን ግንኙነት በኢጣሊያ መንግስት አማካይነት ማድረግ ይገባዋል" የሚል ጭብጥ ያለው ዓረፍተነገር ነበር።

ስለዚህ ንጉስ ምኒልክ ዘውድ መጫናቸውን ለውጭ አገር መንግስታት በቀጥታ ባስተላለፉ ጊዜ የፈቃዱን እንደ ግዴታ ቆጥሮ /የኢጣሊያ መንግስት/ ክርክር ስላነሣና በዚህም ላይ የኢጣሊያና ያማርኛ ትርጉሙ የሚሰጠው ስሜት ለየብቻ በመሆኑ ለ5 አመት እንዲቆይ ተፃፈውት የነበረው ውል በጭራሽ ፈርሶ ነገሩም የአድዋን ጦርነት አስከተለ።

ዞሮ ዞሮ የኢጣሊያ መንግስት ወረራውን በይፋ ላለመፈፀምና ቀስ በቀስ ኢትዮጵያን ቅኝ ለማድረግ አስቦ የተነሣው ቀደም ባሉት ጊዜያቶች ነበርና፤ የዚህ የውጫሌ ውል አንቀፅ 17ትንም አውቆ በስምታች ትርጉም እንደፃፈና እንዳስፈረማቸው ግልፅ ነው። ንጉስ ምኒልክም በማንኛውም ጊዜ ቢነቁ ፈፅሞ ተቀበሉት ማለት አገራቸውን አሣልፈው ሠጡ ማለት እንደሆነ ግልፅ ነውና እቴጌ ጣይቱም ንጉሡም በፅኑ ተቃውመውታል። ነገር ግን በማይቱው "ንጉሠ ነገስት" ከተባሉ በኋላ ነበር የደረሡበት። እናም ንጉስ ምኒልክ ከዚህ በኋላ ነበር ንጉሠነገስት የሆኑት። የትርጉም ስህተት መኖሩን ያወቁትም ንጉሰነገስት ሆነው ሲቀቡ የደስታቸውን መልዕክት በቀጥታ ለአውሮፓ መንግስታት በመልዕክት ሲያሣውቁ "አይቻልም፤ መልዕክትንም ቢሆን እኛ ነን መንገር ያለብን..." የሚል እቋም ያዙባቸው። ባጠቃላይ ኢጣሊያ ሞግዚት መሆን ፈለገች፤ አንቀፅ 17ን መሠረት አድርጋ።

ንጉስ ምኒልክ ከቦሩ ሜዳ/ከውጫሌ/ ተነስተው ሐምሌ 9 ቀን 1881 ዓ.ም እንጦጦ ገቡ። በደረሡ በ4ኛው ወር ጥቅምት 25 ቀን 1882 ዓ.ም በጳጳሱ በአቡነ ማቴዎስ እጅ ተቀብተው "ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠነገስት ዘኢትዮጵያ" ተብለው በእንጦጦ ማርያም ቤተክርስቲያን ነገሡ።

ዳግማዊ ምኒልክ /ምኒልክ 2ኛ/ የተባሉበትም በዚህ ስም የንግስተ ሣባና የሠለሞን ልጅ ምኒልክ ቀድሞ ነግሶ ስለነበር ነው። በሶስተኛውም ቀን ወ/ሮ ጣይቱ ብጡል በጳጳሱ በአቡነ ማቴዎስ እጅ የሚገባቸውን ዘውድ ደፍተው እቴጌ ተባሉ። ከዚያ ቀን ጀምሮም "ጣይቱ ብርሐን ዘኢትዮጵያ" እየተባሉ መጠራት ጀመሩ።

አፄ ምኒልክ በ46 አመታቸው የመላዋ ኢትዮጵያ ንጉሠነገስት ይሁኑ እንጂ፤ ከ22 አመታቸው ጀምሮ ለሁለት አስርት ያህል ኢትዮጵያን ሲያቀኑ የቆዩ ንጉስ ነበሩ። ስለዚህም የሩቁም የቅርቡም መሣፍንት ያለማንገራገር



ተገዙላቸው። ነገር ግን የአፄ ዮሃንስ ልጅና ወራሻቸው የነበረው ራስ መንገሻ ህዳር 29 ቀን 1884 ዓ.ም ከኢጣሊያ መንግስት ጋር በጀኔራል ጋንዶልፊ አማካይነት የወዳጅነት ውል ተፈራርሞ ነበር። በኋላ ግን አፄ ምኒልክ ወደ አዲስ አበባ እንዲመጣ በላኩበት ጊዜ ጥቂት አመንትቶ፤ በመጨረሻ ወደ አዲስ አበባ በ1887 ዓ.ም መጣ። አፄ ምኒልክም ሌላ ግዛት ጨምረው ሠጥተው በሠላም አሠናበቱት።

በዚህ ጊዜ ጣሊያኖች አፄ ዮሃንስንና ንጉስ ምኒልክን ያጣሉ እንደነበሩት ሁሉ አሁንም ራስ መንገሻን መጠቀሚያ ለማድረግ አስበው ሣይሣካላቸው ቀረ።

ወዲያው የኢጣሊያ መንግስት በአፄ ዮሃንስ ጊዜ ይዞት ከነበረው አገር አልፎ ከነራስ አሉላ ጋር እየተጣሉ ከድተው ለጣሊያን በገቡት ሹማምንት እየተመራ ብዙ ግዛቶችን መያዝ ጀመረ። ራስ መንገሻና ራስ አሉላ ከጠላት ጦር ጋር ተዋግተው ድል አድርገው "ኩዓቲትን" አስለቀቁ። በማጀር ቶዘሊ የሚመራው ጦር ድል ከሆነ በኋላ የጀኔራል አርሞንዲ ጦር ተተክቶ አደጋ አደረሠ። የኢትዮጵያ ሠራዊቶችም ወደ ሠንዓፌ አፈገፈጉ። የጣሊያን ጦር ሠንአፌን ድል አድርጎ ተቆጣጠረ። የራስ መንገሻ 1ሺ ወታደሮችም በዚሁ ጦርነት አለቁ። አንድ፤ አንድ እያለ ከአስመራ የቀጠራቸውን ወታደሮች ከፊት እያደረገ አድዋ ድረስ አደረሰው ወረራውን።

ጀኔራል ባራቲሪ አድዋ እንደደረሠ ለወቅቱ የኢጣሊያ ጠቅላይ ሚ/ር የገንዘብ እርዳታ እንዲልክለት ጠይቆ እንዲህ የሚል መልስ ከጠቅላይ ሚ/ር ፍራንቼስኮ ክርስፒ ደርሶታል። "ናፖሊዮን ጦርነቱን ያካሄድ የነበረው በተሸናፊዎች ገንዘብ ነውና አንተም እንደምንም ብለህ እዚያው ፈልገህ ግዳጅህን ተወጣ እንጂ የገንዘብ ችግር ምክንያት አድርገህ ወደፊት ከመግፋት እንዳትቦዝን" ብሎ ላከለት።

አፄ ምኒልክም "ወዳጅነትህን አፍርሠህ የያዝከውን አገር በሠላም ለቀህ ውጣ" ብለው ልከውበት ነበር። ሆኖም ባራቲሪ እንኳን ለቆ ሊወጣ ከአድዋ እስከ መቀሌ፤ ከመቀሌ እስከ አምባላጌ ደረሠ። አፄ ምኒልክ ዋና መገለጫቸው ሆኖ የቀረውን አስደናቂ ታሪክ የሚፈፅሙበት ወቅት ተቃረበ። ዘሩፋቸውን ለአንታቸው ለራስ ዳርጌ አደራ ብለው ለዘመቻ ከመነሣታቸው በፊት ተከታዩን የክተት አዋጅ ለህዝቡ አስተላለፉ።

"ልዑል እግዚአብሔር በቸርነቱ እስካሁን ጠላት አጥፍቶ አገር አስፍቶ አኖረኝ። እኔም እስካሁን በልዑል እግዚአብሔር ቸርነት ገዛሁ። እንግዲህም ብሞት ሞት የሁሉ ነውና ለኔ ሞት አላዝንም። ደግሞ ልዑል እግዚአብሔር አሣፍሮኝ አያውቅም። ከእንግዲህም ያሣፍረኛል ብዬ አልጠረጥረውም። አሁንም አገር የሚያጠፋ፤ሐይማኖት የሚለውጥ ጠላት ልዑል እግዚአብሔር የወሠነልንን ባህር አልፎ መጥቷል። እኔም የአገሬን ከብት ማለቅ የሠውን

መድከም አይቼ፣ እስካሁን ዝም ብለው ደግሞ እያሰፈ እንደፍልፈል መሬት ይቆፍር ጀመር።

እሁን ግን በልዑል እግዚአብሔር ረዳትነት አገሬን አሣልፌ አልሠጠውም። የአገሬ ሠው፣ ከአሁን ቀደም የበደልኩህ አይመስለኝም። አንተም እስካሁን አላስቀየምከኝም። አሁንም ጉልበት ካለህ በጉልበትህ እርዳኝ። ጉልበት የሌለህ ለልጅህ፣ ለሚስትህ፣ ለሐይማኖትህ ስትል በሀዘን እርዳኝ። ወስልተህ የቀረህ ግን ኋላ ትጣላኛለህ አልተውህም። እግዝእትን ማርያምን ለዚህ አማላጅ የለኝም። ዘመቻዬም በጥቅምት ነውና የሸዋ ሠው እስከ ጥቅምት እኩሌታ ድረስ ወረይሉ ከተህ ላግኝህ።"/የአፄ ምኒልክ የክተት አዋጅ መስከረም 7 ቀን 1988 ዓ.ም/ ።

"እኔ ሴት ነኝ፣ ጦርነት አልወድም። ግን እንዲህ መሳዩን ውል ከምቀበል ጦርነት እመርጣለሁ። እኛ ለራሣችን እንበቃለን። የናንተን የበላይ ጠባቂነት አንፈልግም። እናንተን አንፈራችሁም"/እቴጌ ጣይቱ ብርሀን ዘኢትዮጵያ የውጫሌን አንቀፅ 17 ውል በተመለከተ ቀደም ሲል የተናገሩት/።

ጥቅምት 2 ቀን 1888 ዓ.ም ከአዲስ አበባ ሲነሡ እቴጌ ጣይቱም አብረው ተነሡ። ራስ መኮንን/የአፄ ሃይለስላሴ አባት/ የጦር አበጋዝ ሆነው ራስ ወሌን፣ ራስ ሚካኤልን፣ ራስ መንገሻ አቲከምን.... ይዘው ተጉዘው ጣሊያኖች መሽገው በተቀመጡበት አምባላጌ ተራራ አጠገብ ሠፈሩ። አሁንም የእርቅ መልዕክት ተላከ አልተሣካም።

ህዳር 28 ቀን የተደረገው የአምባላጌ ጦርነት 2 ሠአት ፈጅቶ ራስ መኮንን በመሩበት ክፍል የኢጣሊያ ጦር ሸሸ። ከአምባላጌ ለቆ ወደ መቀሌ ሔዶ ሲመሽግም "የተላከ ከራስ መኮንን፣ ይድረስ ከኮ/ል ጁሴፔ ጋሊያኖ። ይህን አሁን መሽገህ ያለህበትን ስፍራ ለቀህ ወደ ኋላ እንድትመለስ በወዳጅነት አሣስብሐለሁ። እሰተም ያልህ እንደሆነ ግን የግድ ጦርነት አድርገን የማጆር ቶዞሊ እድል እንዳያገኝህ።"

"በንጉሴ ታዝዤ የያዝኩትን አገር ለመልቀቅ አልችልም። ጦርነትም ቢፈልጉ እኔ ዘንድ ብዙ መድፍና መሣሪያ እንዳለ ይወቁ" ብሎ ላከ። የአምባላጌውን ጦርነት ኢትዮጵያ ድል አደረገች። የኢጣሊያ ጦር ከአምባላጌ ሸሽቶ መቀሌ ደረሠና የመቀሌውን ምሽግ አጠናክሮ ለዳግም ጦርነት ተዘጋጀ።

ራስ መኮንን ወደፊት እየገፉ መቀሌ ደረሡ። የኢጣሊያ ጦር ከመሸገበት ሆኖ ረጅም ሠአት ቢዋጋም ተከቦ ነበርና በውሃ ጥም ግቢያ ምሽጉን ሊለቅ ተገደደ። ይህም የሆነው መሣሪያውን ሁሉ አስረክበው በሠላም ምሽጉን እንዲለቁ ከራስ መኮንንና ከምኒልክ ጋር ተላልከው በመስማማት ነው። በዚህም በርከት ያለ የጦር መሣሪያና መድፍ መማረክ ተቻለ።

ከአምባላጌና ከመቀሌ ጦርነት በኋላ ዋና የጦር አዝማቹ ባራቲየሪ የቀረውን ሠራዊት በ4 ክፍሎ በአንደኛው ክፍል ጀ/ል አርሞንዲን፣ በ2ኛው ክፍል ጀ/ል ዳቦርሚዳን፣ በ3ኛው ክፍል ጀ/ል አልበርቶኒን፣ በ4ኛው ክፍል



ጀ/ል ኤሌናን አደራጅቶ የጦር ካርታ አዘጋጅቶ በአራቱም አቅጣጫ አሠለፋቸው። አጠቃላይ የኢጣሊያ ጦር ከ20 ሺ. በላይ የነበረ ሲሆን፤ ሁሉም ዘመናዊ መሣሪያ ከበቂ ጥይቶች ጋር፤ እንዲሁም 60 መድፎችን ታጥቀው ነበር።

በዚህ በአድዋው ጦርነት የኢትዮጵያውያን የጦር አደረጃጀትና አሠላለፍም እንዲህ ይገለፃል።

1. እራሣቸው አፄ ምኒልክ አድዋ አጠገብ እዲማህለያ በተባለው ስፍራ ከ30 ሺ. ጦር ሠራዊት ጋር፣
2. እቴጌ ጣይቱ በዚሁ ስፍራ ከ3ሺ. ወታደር ጋር፣
3. ፊታውራሪ ገበየሁ ገቦ የእሁምን ወንዝ ሻገር ብለው በማይ ጓጓአ ከ6 ሺ. ወታደር ጋር፣
4. ንጉስ ተክለሐይማኖት በዚሁ ወንዝ አቅራቢያ ከ3ሺ. ወታደር ጋር፣
5. ንጉስ ሚካኤል በሠናይ ፀባኦና በእንዳ ሚካኤል ከ8ሺ. ወታደር ጋር፣
6. ልዑል ራስ መኮንን በአዲ አቡን ከ8ሺ. ሠራዊት ጋር፣
7. ራስ መንገሻ ዮሃንስ ከራስ አሉላና ከራስ ሐጎስ ጋር በሸዊቶ በኩል ከ3ሺ. ሠራዊት ጋር፣
8. ዋግሹም ጓንጉል በዚሁ ስፍራ ከ6ሺ. ጦር ሠራዊት ጋር፣
9. ራስ ወሌ በማይ ደላእታ ከ3 ሺ. ጦር ጋር፣
10. ራስ መንገሻ አቲከም ከ3ሺ. ወታደር ጋር። በድምሩ 73 ሺ. የጦር ሠራዊት ተሠልፏል።

የተለመደው ባህላዊ መሣሪያና በደህና ጊዜ የተገዙ መድፎች በጥቂቱ፣ ዘመናዊ መሣሪያም እንዲሁ ታጥቀዋል ኢትዮጵያውያኑ። የዚህና የሌሎች ጦር ሠራዊቶች ጠቅላይ አዛዥ ጀግናው ፊት አውራሪ ገበየሁ ገቦ ሆነው የካቲት 23 ቀን 1888 ዓ.ም የአድዋው ጦርነት በኢትዮጵያውያኑ ጀግኖች በድል ተጠናቋል። ሆኖም የአድዋውን የድል ታሪክ "በድል ተጠናቋል" ብለን የምንዘጋው ሳይሆን፣ የድሉ ገፅታ ምን መልክ እንደነበረው አጠር አድርገን መቃኘት ግድ ይለናል።

የዓድዋ ድል ትልቅ ድል ነው። የአፄ ምኒልክና የኢትዮጵያውያን የማንነት ገፅታ ተንፀባርቆበታል። በተራቀቁት የአውሮፓ አገሮችና በቅኝ ግዛት ስር ለሚማቅቁ ህዝቦች ሁለት ተቃራኒ የሆኑ ስሜቶችን ፈጥሯል። ሀፍረትንና ድፍረትን።

ገሐድ የወጣው የኢትዮጵያውያኑ ዝና ለተጨቆኑ ጥቁር ህዝቦች አርአያ ሆኖ ድቅድቁን የጭቆና ዘመን የተስፋ ብርሀን የፈነጠቀበት ነው።

በምኒልክ የንጉሠ ነገስትነት ዘመን በተለይ በአድዋ ጦርነት ዋዜማ ኢትዮጵያውያኑ ሙሉ ለሙሉ አንድነታቸውን ያረጋገጡበት ወቅት ነበር። ይህ አንድነቱን የጠበቀ ሠራዊት ምኒልክ ያሠባሠቡትን ዘመናዊ የጦር

መሣሪያ በመጠቀም በአድዋ ላይ ለዘውትር ጥቁር ህዝቦችን ሲያኮራ የቻለና ሲያኮራ የሚኖር ድል ያስመዘገበበት ወቅት ነበር።

ሠራዊቱ ለአገሩ ውድ ሕይወቱን መስዋዕት ለማድረግ እየተሽቀዳደመ ይዋጋ የነበረው በምኒልክ ዘመን ተፈጥሮ በነበረው የህዝቦች ትስስርና ፍቅር ነው ለማለት ይቻላል። እርግጥ ነው አገር በህዝቦቿ ህዝቦቿም በአገር ይገለፃሉና ሁሉም ኢትዮጵያዊ ለአድዋው ድል ብቻም ሳይሆን ለሙሉ ዘመን ነፃነቷ ተዋድቀዋል። ቢሆንም ልዩ ጥበብ የታከለበትን ድል ያስገኙ ጀግኖች ልዩ ቦታ ይሠጣቸዋል።

የዓድዋ ድል መነሻው የአፄ ምኒልክ አስተዋይነት ነበር። ወረራው እንደማይቀር በማጤን ቀድመው ዘመናዊ መሣሪያ ማከማቻታቸው፣ ለጠላት የተሣሣተ መረጃ እንዲደርሠው ማድረጋቸው፣ ሁሉንም በፍቅርና በነፃነት ወዳጅ ማድረጋቸው ትልቅ አቅም ፈጥሮላቸዋል።

ምኒልክ ቀደም ብለው የሠበሠቡትን ዘመናዊ መሣሪያ ራስ መንገሻ ዮሃንስ "የምኒልክ ሐብት" በማለት ይጠሩት ነበር ይባላል። ይህም ሲባል የዓድዋ ድል በመሣሪያ ብዛት የተገኘ ነው ለማለት አይደለም።

ራስ መንገሻ ዮሃንስ ስለዚህ የምኒልክ ሐብት ስለሚሉት ከአውሮፓ በየጊዜው እያስመጡ ስለሠበሠቡት ዘመናዊ መሣሪያ በተመለከተ ምኒልክ ወደ ዘመቻው እየተጓዙ አላማጣ ሲደርሡ ከራስ መንገሻ የተላከላቸው ደብዳቤ ይገልፃል፡-" ጃንሆይ ጦርነቱ አልታሠበም ነበር። ፊታውራሪ ገበየሁ ሄዶ ገጠመው። እኔም በጀርባው፣ መኳንንቱም በግንባር ገቡበት። ከመኳንንቱ ሠራዊቱ፣ ከሠራዊቱ መኳንንቱ ታይቶ ተሠምቶ አይታወቅም ድሉ። ይህ ሁሉ የሆነው በምኒልክ ሐብት ነው። ፈረንጅ እንኳን መድፍና ወጨፎ ይዞ አምባው ሲሠበር ከጥንት በአባቶቻችን በድንጋይ ይመለስ ነበር። ግን ከዚህ በፊት ተደርጎ የማያውቅ ዛሬ በምኒልክ ሐብት ተደረገ። እንግዲህ የምኒልክ ሐብት ይጠብቀናል።" በማለት በአምባላጌውና በመቀሌው ጦርነት በምኒልክ ዘመናዊ የጦር መሣሪያዎች ያስገኙትን ድል ራስ መንገሻ ገልፀውታል። "እንግዲህ ይህ ጦር አምርሮብን ሣለ ለጌታችን አልጋ መሞት ይገባናል። እንዲህ ተባብለው ጭፍራው እንዳለ አንድ ግዜ ገባበት።" ያሉት ደግሞ ፊት አውራሪ ገበየሁ ገቦ ሲሆኑ፣ ሁሉም ለንጉሠነገስቱ ያለውን ፍቅር ያሣያል። ሲቀጥሉም፡-

"የመድፍ ጥይት ይመታናል፣ የጠመንጃ ጥይት ይመታናል ብሎ በልቡ ፍርሐት ያደረበት የለም። አለቃው ሲወድቅ ወታደር፣ ወንድሙ ሲወድቅ ወንድሙ አያነሣውም። ቁስለኞቹ ራሳቸው ዙፋት ይርጋ እንጂ እኔን ስትመለስ ታነሣኛለህ፣ ስለዚህ እንዳታነሣኝ በማሃይም እንደቡቱ ገዝቸሃለሁ" ይሉና ይባባሉ ነበር። አንዳንድ አርበኞች ደግሞ ብዙ ይፋለሙና ትንሽ ድካም ሲሠማቸው አረፍ ካሉ በኋላ ወዲያውኑ እመር ብለው ተነስተው "ሎሚ ሳበላኝ፣ ጠጅ ሳጠጣኝ ጌታዬ ምኒልክ ብድሩን



እንዴት ነው የምመልሠው!" ይሉና ደንፍተው ጦርነቱን እንደገና ይጀምራሉ። ያ ወቅት ማለት አለመግባባቶች በእኔ እብስ እኔ እብስ ስሜት ተለውጦ ኢትዮጵያውያኑ በፍቅር የተዋደቁበት ወቅት ነበር።

ለምሣሌ በመቀሌው ጦርነት የኢትዮጵያ ወታደሮች ከምኒልክ ትዕዛዝ ውጪ በመሆን ራሣቸው በከፈቱት ውጊያ ብዙዎች በመሞታቸው ምኒልክና ጣይቱ ራስ መኮንንን በግልፅና በሠራዊቱ ፊት ወቀሣ ሠንዘሩባቸው። ወዲያው ምክክር ይያዝ ተባለና ምክክር ተያዘ። ከዚያም አፄ ምኒልክ ታማኛቸውን ራስ መኮንንን ያስጠሯቸዋል "ከኢጣሊያዎች ጋር ተስማምተሃል። ኮሎኔል ጋሊያኖም ምሽጉን እስኪሠራ ጊዜ ሠጠኸው፤ እኔ ከኢትዮጵያ እንዲወጣ ያልኩት ፊልተር የሚባለውን ጠላት በሠፈርህ አስቀምጠህዋል..." ብለው እንደ ከዳተኛ ወቀሷቸው።

ራስ መኮንንም "ታማኝነቴን ለመግለፅ ምን ማድረግ ይገባኛል?" ከማለት በቀር ወቀሣው ተሠምቷቸው አተካራ አልገጠሙም። ንጉሡም "በል አንተው ጊዜ ሠጥተህ የመቀሌን ምሽግ እንዳስመሸግከው አንተው ራስህ አስጠጣ" ብለው ሲናገሯቸው ራስ መኮንንም ወዲያው ያለምንም ማወላወል ግዳጃቸውን ተወጥተው የመቀሌውን ምሽግ ሠበሩ። እናም በዚያን ጊዜ የነበሩ አርበኞች እንዲህ በመነጋገርና በመወቃቀስ አንድነታቸውን መጠበቅ ቻሉ እንጂ "ለምን እንዲህ ተባልኩ" በማለት በንጉሡ ላይ አያኮርፉም አያቄሙም ነበር። ወደ ዋናው የድል ፍሬ አቋዳሾች ታሪክ እንለፍ።

የአፄ ምኒልክ መኩሪያ ነበሩ። ፊት አውራሪ ገበየሁ ገቦ። በቅድመ አድዋ ጦርነቶች አንቱ የተባሉ ጀግና ነበሩ። የአርበኞች ጦር እየተከታተለ ደርሶ ዋናው ጦርነት ስለተጀመረ ጀኔራል አልበርቶኒ በቀረው መድፍና ጠመንጃ በሚዋጋበት ጊዜ ስባለቀበት ሻርገኔል የሚባለው ሃይለኛ ቦምብ እንዲተኮስ አዘዘ። ይህንን ማድረጉ ሀበሾቹ በዚህ ተኩስ እንዲደናገጡና እንዲሸበሩ አስቦ ነው።

በዚህ ጊዜ ሐበሾቹ 1500 ሜትር የሚሆን ቅርበት ያለውን ስፍራ ይዘው አንዳንድ ጊዜ 1ሺ ሜትር ተጠግተው ሲዋጉ በዚሁ ቦምብና መድፍ ብዙ ሠራዊት አለቀባቸው። ወደ ኋላም ማፈግፈግ ሲጀምሩ የአምባላጌን በር የሠበሩት ፊት አውራሪ ገበየሁ ጦራቸውን ይዘው ለወታደሮቹ ምሣሌ በመሆን አፊት ሆነው እየመሩ በግስጋሴ ወደተጋጋለው ተኩስ ገቡ። 5ሺ ያህል ጦር ሆ ብሎ ተከተላቸው። በዚህ ጊዜ በሁለቱ መካከል የሚደረገው ጦርነት ከልክ ያለፈና የተጋገለ ሆነ። የሐበሾቹ ጦር ማየል ያሠጋው ጀ/ል አልበርቶኒ ተጠባባቂው ባታሊዮን እንዲመጣ አዘዘ። በዚሁ ጊዜ የእቴጌ ጣይቱ ጦር "ስድስት ሐኪስ" የሚባሉትን መድፎች ይዞው ከተዋጊው 3ሺ ሜትር ርቀው መድፍ እየተኮሡ ተጠባባቂውን ጦር ገድበው ያዙት። ሆኖም 7ኛው ባታሊዮን ጦር የሀበሾቹን ተኩስ ተቋቁሞ ወደ ኋላ 1ሺ ሜትር

እንዲያፈገፍጉ አስገደዳቸው። በዚህ አይነት ጦሩ ወደፊት ለመግፋት እንዳመነታ ባዩ ጊዜ ፊት አውራሪ ገበየሁ ወደ ጦሩ ፊታቸውን አዙረው "የእምባላጌው አሸናፊ ገበየሁ በምን አኳኋን እንደሞተ ወደ ሸዋ በሕይወት የሚመለሱት ይናገሩ" አሉና እንደ አንበሳ ተወርውረው ወደ ጣሊያኖች ገብተው ሲዋጉና ብዙ ጀብድ ሲፈፅሙ ከቆዩ በኋላ በመትረየስ ተመተው ኪዳነ ምህረት በር ላይ ወደቁ።

ስለ ፊት አውራሪ ገበየሁ አዲስ አበባ ድረስ ተማርኮ መጥቶ የነበረው የኢጣሊያ መኮንን ጆቫኒቴዲኖ የፃፈውን ማስታወሻ ስናይ እንዲህ ይላል።

"በቢያንኪንና በማዘቶ በሚመሩት መድፎች እየተመቱ ሃበሾች ወደ ኋላ ሲያፈገፍጉ አይቶ "ፈሪ ሁሉ እንዴት ትሸሻላችሁ? እኔ እንዴት እንደምሞት ለንጉሡ ሄዳችሁ ንገሩ። በማለት ፈረሱን በአለንጋ አስነስቶ በግልቢያ በሚዘንበው የመድፍ ጥይት መካከል ገባ። እሱን ሲያይ ሁሉም እየሮጠ ተከትሎት ገብቶ ከመድፈኞቹ ጋር ተጨፋጭፎና ገድሎ መድፈኞቹን ማረከ። የገበየሁ ሬሣ ከወደቀበት ቦታ የኛዎቹ ጀግኖች አብረው በመውደቅ የእርሁን እሬሣ አከበሩት።" በማለት ገልፆታል።

በጥቁር ህዝቦች ታሪክ ውስጥ አንፀባራቂ ድል የተመዘገበትን የአድዋን ድል ፊት አውራሪ ገበየሁ ውበት ሠጥተውት እንዳለፉ ሁሉም የሚስማማበት ሆኗል።

ሌላኛው ለአድዋ ድል ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳበረከተ የሚተረክለት ባሻይ አውአሎም ሐረጎት ነው። (በነገራችን ላይ የጥቂቶች ጀግንነት ያስገኘው ድል ነው እየተባለ አይለደም። ተዘርዝረው የማያልቁ ጀግኖች ዋጋ ከፍለዋል። ነገር ግን ስማቸው ጎልቶ ስለተስተጋባው ግለሠቦች ሲተረክ የሁሉም ትብብር አብሮ የሚታይ መሆኑ ግልፅ ስለሆነ ነው።

ባሻይ አውአሎም ሐረጎት ዓድዋ ላይ ታአምር የሠራ ኢትዮጵያዊ ሠላይ ነው።

አፄ ምኒልክ ከአዲስ አበባ ተነስተው አድዋ እንደደረሡ ጣሊያኖችን የሚሠልልላቸው ታማኝ ሠው በከፍተኛ ሚስጥር ሲያፈላልጉ በትግራዩ ገዥ በራስ መንገሻ በኩል የተገኘ ወጣት ነው። ይህ ወጣት አርበኛ ከአድዋ ድል በኋላ ለተጠየቀው ጥያቄ ምላሽ ሲሠጥና ከአፄ ምኒልክ ጋር የነበራቸውን ግንኙነትና ምክራቸውን ሲያብራራ፦ "ከተቀመጡበት በቅሎ ጎን ለጎን እየሄድን ሃሣብ ስሠጣቸው ጠላትን በሠላይ ልንይዘው የሚያስፈልግ መሆኑን ነገሩኝና ተረዳሁ። የባራቴሪ ወዳጅና ታማኝ በመምሠል የበለጠ ታላቅ ጥቅም እንደምሠጥ አፄ ምኒልክ ነገሩኝ።" ይላል።

በዚህ ጊዜ አፄ ምኒልክ ባሻይ አውአሎምን እንዴት አድርጎ የኢጣሊያን ጦር እንደሚሠልልላቸው መልሠው ሲጠይቁት "የአባቱ አገር ማይ ሐማሴን ነው። በዚያ ዘመዶቼ ይኖራሉ። እነርሡን የምጠይቅ መስዬ እሔዳለሁ። ወደ ባሊያን ሔጄ እተዋወቅና የእርስዎን አዚህ መስፈርና



የሠራዊትዎን ሁኔታ ልነግራቸው እንደምችል አስረዳቸዋለሁ። የእነርሡን ሁኔታ አጣርቼ መጥቼ ለእርስዎ ደግሜ እነግርዎታለሁ።" የሚል እቅዱን አቀረበላቸው። አፄ ምኒልክም ይስማሙና ስለላው ይጀመራል።

በዚህ ጊዜ የኢጣሊያው ጠቅላይ የጦር አዛዥ ጀኔራል ባራቴሪም የአፄ ምኒልክን ሠራዊት የሚሠልሉለት ሠዎች እየመረጠ፣በርከት ያለ ገንዘብም እየሠጠ መላክ ጀምሮ ነበር።

ጣሊያኖች ይልኳቸው የነበሩት ሠዎች ግን ሁሉም ተመልሠው አልሄዱላቸውም ነበርና በጣም ተቸግረው ሳለ ባሻይ አውአሎም ወደ ጣሊያን ሠፈር ይሄድና ስለ አፄ ምኒልክ ሠራዊት ሁኔታ ማውራት ሲጀምር የኢጣሊያ ወታደሮች ወደ ጄኔራሉ አቀረቡት። የሃማሴን ተወላጅ መሆኑንና የአፄ ምኒልክን ሠራዊት ሊሠልልላቸው እንደሚችል አረጋገጠ።

ጀ/ል ባራቴሪ ስለተጠራጠረው ከታማኝ የሐበሻ ሠላዮች ጋር መደበው። ሠላይ በሚያስፈልግበት ጉዳይ ላይ ሠላዩ የሚለውን መቀበል ግድ እንደሚል ሁሉ፤ ሠላዩን የላከው ደግሞ በሠላዩ ላይ የአዛዥነት ስልጣን ይኖረዋል። ይህንን የማዘዝና የመታዘዝ ሁኔታ ከጦርነቱ በኋላ ባሻይ አውአሎም ሲገልፀው "እኔ ለጠላት ሠራዊት ለባራቴሪ ስታዘዝ፤ አፄ ምኒልክ ደግሞ እኔን ሲያዙኝ በእኔ ውስጥ ደግሞ ባራቴሪን ያዙት ነበር" ብሏል። ስለ ንጉሡ ፀባይም "አፄ ሚኒልክ ንጉስ ብቻ አልነበሩም። የጦር ስልት አዋቂ እንደ ጄኔራልም ነበሩ" ይላቸዋል።

ስለራሡና ስለፈፀመው ጀብድ ሲናገር "በዚያ በየካቲት 22 ሌሊት የጠላትን ሠራዊት ይገፍ ስገሠግስ አድሬ ንጋት ላይ በአፄ ምኒልክ ሠራዊት እቅፍ ውስጥ ያስተኛሁት እኔ ነኝ..." ማለቱን የዓለም ጀግኖች ታሪክ የሚለው መፅሃፍ ያትታል።

የባሻይ አውአሎም የስለላ ውጤትና፣የአፄ ምኒሊክና በዙሪያቸው ያሉ የጦር መኮንኖች የጥበብ ስራ የሆነውን ጠላትን የሚያሣስቱበትን ብልሐት የፈጠሩት የአድዋ ጦርነት ከመፈንዳቱ አንድ ቀን ቀደም ብሎ ነበር። ጀ/ል ባራቴሪ ከሌሎች ሠላዮች ጋር ቀላቅሎ ልኮታል። ባሻይ አውአሎም ታዛቢዎችን ይዞ ወደ አድዋ ይገባና የኢጣሊያ ሠላዮች ሳያዩትና ሳይጠረጥሩት ወደ ራስ መንገሻና ወደ ራስ አሉላ ሔዶ ሁኔታውን ይናገራል። ወሬውም ለአፄ ምኒልክ ይደርሣል።

በዚህ ጊዜ አፄ ምኒልክ እቴጌ ጣይቱና በዙሪያቸው የነበሩ አማካሪዎቻቸው ድንቅ ሃሣብ አፈለቁ። ዘዴው ጠላትን በትክክል አሣምኖ፣ ነገር ግን አሣስቶ በኢትዮጵያ አርበኞች ወጥመድ ወስጥ የሚያስገባ ነበር። ዘዴውም ለኢጣሊያ እውነተኛ ሠላዮች ሲነገርና ሲሠሙት እውነት እንዲመስላቸውና እነርሡም ያመኑትን ለባራቴሪ አሣምነው እንዲነግሩትና እንዲሣሣቱ የሚያደርግ ነበር።

በዚህም መሠረት የኢጣሊያ ሠላዮች እየሠሙ ለኢትዮጵያ ጦር ሠራዊት አዋጅ ተነገረ። አዋጁም "እንደገና የክተት አዋጅ እስኪታወጅ ድረስ በስንቅና በውሐ እጥረት የተቸገረው ወታደር እንዲበተን" የሚያዝ ነበር። ይህ የማስመሠል አዋጅ ሲነገር ከባሻይ አውአሎም ጋር የነበሩት እውነተኛ የኢጣሊያ ሠላዮች በነገሩ ያምናሉ። እንግዲህ እንደ በርካቶች ፀሃፍት ስምምነት ይህ ዘዴ ነው የኢጣሊያን ወታደሮች እንደሚታረድ በሬ ወደ አራጁ እየጎተተ ያመጣቸው።

ከአዋጁ በኋላ ባሻይ አውአሎምና የኢጣሊያ ሠላዮች ወደ ጦር ሠፈሩ ሲገሠግሡ ይደርሡና አፄ ምኒልክ ሠራዊታቸውን እንደበተኑና ከጥቂት ወታደሮቻቸው ጋር ብቻ አድዋ ስለሚገኙ የኢጣሊያ ጦር በቀላሉ ሊይዛቸው እንደሚችል በደስታ ያስረዳሉ። ጄ/ል ባራቴሪም በዚሁ መረጃ ተማምኖ ሠራዊቱን ያዘምታል። ጦሩም ከኢትዮጵያ ሠራዊት የውጊያ መስመር ከያዘበት መካከል ዘው ብሎ ገባ። ለዚህ ነው ባሻይ አውአሎም "አፄ ምኒልክ እኔን ሲይዙኝ በእኔ ውስጥ ደግሞ ባራቴሪን ያዙት ነበር።... በዚያ በየካቲት 22 ሌሊት የጠላትን ሠራዊት ይገፎ ስገሠግስ አድሬ ንጋት ላይ የካቲት 23 1888 ዓ.ም በአፄ ምኒልክ እቅፍ ውስጥ አስተኛሁት" ለማለት የደፈረው። ይህ ሠላይ የኢጣሊያን ሠራዊት መርቶ ካስመታ በኋላ በሚደንቅ ፍጥነት ወደ ወገን ጦር ተቀላቅሎ ተኩስ በመክፈት ተዋግቷል። አንድ የኢጣሊያ ወታደር ማርኮ ለራስ መንገሻ አስረክቧል። ብዙ ጊዜ ይፈጃል ተብሎ የታሠበው ጦርነት የኢትዮጵያ ጀግኖች ግማሽ ቀን ባልሞላ ጊዜ ውስጥ የተረከቡትን ሠራዊት ጭጭ አድርገውት ጦርነቱ ተፈፀመ።

ከአድዋ ጦርነት የተረፈ አንድ የኢጣሊያ የጦር መሪ እንደተናገረው "የተዋጋነው የወታደር ስርዓት ከሌለውና ከሞት ባህር ዘሎ ከሚገባ ህዝብ ጋር ነበር። እኛ በርቀት የሚመቱ እጅግ ፈጣን የሆኑ መድፎችና መትረይሶች ይዘን ስንዋጋ፣ ሠይፍና ጎራዴ ይዘው እየሮጡ የሚገቡ፣ በመድፍ አፍ ውስጥ በርበሬና ድሪቶ የሚወትፉ፣ ከሞት ጋር ሳለመነካከት የተማማሉ የሚመስሉ ሠዎች ጋር ነው የተዋጋነው። ከሁሉም የበለጠ የጎዳንና የተዋጋን የአገሩ አቀማመጥ ቢሆንም፣ ባሻይ አውአሎም የተባለው መሠሪ የፈፀመብን በደል ከሁሉም ድል አንዱ ነው" ብሏል። ሌላው የጦር መሪ ሲናገር "በተለይ ባሻይ አውአሎም የተባለው ኢትዮጵያዊ ለኛ ጦር የሠለለ እየመሠለ እኛን መንገድ በማሣየትና በመምራት የረዳ እየመሠለ ለካ ለአገሩ ሞራል የሚሠልለው። በኋላ በየዋህነት ወደ ተኩላ መንደር እንደሚሔዱ እሡም እየመራ ወስዶ ከኢትዮጵያውያን ጋር በድንገት አላተመን።" በማለት የባሻይ አውአሎምን ስራ ጠላት ሳይቀር መስክሮለታል።

ከጦርነቱ በኋላ ለአገሩ በፈፀመው አኩሪ ስራ ከአፄ ምኒልክ የሚገባውን ወሮታ ያገኘ ሲሆን፣ በራስ መንገሻ ስር የእንትጮ ወረዳ



አስተዳዳሪነትን አግኝቶ እድሜውን በደስታ ጨርሶ በ78 አመቱ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል።

የዓድዋ ድል በልዩ አንድነትና ቅንጅት፣በከፍተኛ ጥበባዊ የውጊያ ስልትና በታላቅ መስዋዕትነት በኢትዮጵያውያን ጀብደኞች የኢትዮጵያ ሆኗል። የካቲት 23 1988 ዓ.ም። ይህ እለት THE BLACK HISTORY MONTH እየተባለ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚከበር እለት ሆኗል። የመላው ጥቁር ህዝቦች ድል ነበርና።

ጦርነት እንደመሆኑ መጠንም ብዙ ሺ ሠራዊቶች ተረፍርፈው የውጊያ ግንባሩ በሬሣ ክምር ተራራ እንደሠራ መገመት አይከብድም። ድሉ የኢትዮጵያ መሆኑ ሲረጋገጥ ግማሡ የኢጣሊያ ጦር ሲማረክ፣ የተረፉት ሸሹ። እንደበርካቶች አገላለፅ በአድዋ ጦርነት የሞቱ የኢጣሊያ ወታደሮች ብዛት 5ሺ ጣልያናዊ ነጭ ወታደሮች፣ 2ሺ ከኤርትራ የተመለመሉ ወታደሮች ሲሞቱ፣ 2400 የሚሆኑት ደግሞ ከ60 መድፍና ከብዙ ዘመናዊ መሳሪያ ጋር ሲማረኩ፤ የቁስለኞች ቁጥርም 2500 ይደርሣል ይባላል።

ከኢትዮጵያ በኩልም ግማሡ ፀሃፍት ከኢጣሊያ እኩል ሲያደርገው፣ አንዳንዶቹ እጥፍ ነበር ይላሉ። ዞሮ ዞሮ ግን የሐበሻ ወታደር ተኝቶ መተኮስ የፈሪ ነው እያለ ቆሞ በጀግንነት ሲዋጋ ስለነበር ደረቱ ለጥይት የተጋለጠ ነበርና ብዙ ወታደር አልቋል። አጠቃላይ የሟችና የቁስለኛው ቁጥር 10 ሺ እንደነበርም የብዙዎች ግምት ነው።

ጀኔራል አልበርቶኒ በቅሎ ላይ ተቀምጦ ሲዋጋና ሲያዋጋ በቅሎው በጥይት ተመትታ ስትወድቅ እሡም ሊያመልጥ ሲፍጨረጨር ኢትዮጵያውያን ማረኩት። ጄ/ል ዳቦር ሚዳን በጥይት ደረቱን ተመቶ ሞተ። ጄ/ል አርሞንዲም ተገደለ። ጄ/ል ኤሌና ቆስሎ ሸሸ...። ዋናው አዝማች በራቴሪም ከጦርነቱ ፍፃሜ በኋላ የአገሩ መንግስት በወታደር ችሎት በቸልተኝነት ከሶት ከስልጣኑ ተነስቶ ወደ ኢጣሊያ ተመለሠ።

የኢጣሊያ የተረፉ ወታደሮች ከአድዋ እየሸሹ ተበታትነው ወደ አዲ ሐይቅ ሲጓዙ የኢትዮጵያ ወታደሮች ተከታትለው እያሣደዱ ከመረብ ወዲያ አሻገሯቸው።

የዓለም ህዝብ ጉድ አለ። ኢጣሊያም አንገቷን ደፋች። አፄ ምኒልክ ምርኮኞቻቸውን ይዘው ወደ አዲስ አበባ በድል አድራጊነት ገቡ። ሚያዚያ 8 ቀን ሲገቡ ህዝቡ በታላቅ ደስታና እልልታ ተቀበላቸው። ከዚህ ድል በኋላ ነው "ምኒልክ ተወልዶ ባያነሣ ጋሻ

ግብሩ እንቁላል ነበር ይሆን ጊዜ አበሻ..." እየተባለ የተገጠመው። ከዚህ ድል በኋላ ነው "... ገበየሁ ቢሞት ተተካ ባልቻ

መድፍ አገላባጭ ብቻ ለብቻ..."
እየተባለ የተፎከረው።

ጂ.ኦፍ.ኤ ባርክሊይ የተባለ እንግሊዛዊ ፀሃፊ ስለአድዋ ድል የተሠማውን ስሜት ሲገልፅ "ድሉ በአፍሪካ ውስጥ አዲስ ሃይል የመነሣቱ ምልክት ነው። የዚያ ክፍለ አለም ህዝቦች ልናስታውሣቸው የሚገባን የጠታደር ሃይል እንዳላቸው አሣውቆናል። የሚታመን ነገር ባይመስልም እንኳ፣ የጨለማው ክፍለ ዓለም በሃይለኛው አውሮፓ ላይ የሚያደርገው የመጀመሪያው እንቅስቃሴ ምልክት ሆኗል።" በማለት ገልጿል።

ከዚህ ድል በኋላ ፍርድ ተከናወነ። አገራቸውን ከድተው ሰጠላት ወግነው ሲዋጉ የተማረኩትን እንደ ደንቡ እጅ እና እግራቸውን እየቆረጡ ጳጳሱ አቡነ ማቴዎስ ጭምር በተገኙበት ቀጧቸው። የኢጣሊያ ምርኮኞችንም የሮማው ጳጳስ ልዮን 13ኛ ለአፄ ምኒልክ በላኩት ልብ የሚነካ የተማፅኖ ደብዳቤ ሲለቋቸው ቻሉ። ነገር ግን ቀድመው ስለ ወሆኑ አከላለል መደራደር ነበረባቸውና ምርኮኞቹን መያዣ ይዘው የውል ድርድር ጀመሩ።

ህዳር 25 1889 ዓ.ም ዶክተር ኔራስኒ የሚባል መልዕክተኛ ከኢጣሊያ መንግስት ተልኮ ሁለቱ አገሮች በተከታዩ ውል ተስማሙ።

1ኛ ከዚህ ቀደም እንደተደረገው ያለ ጦርነት ቀርቶ በኢትዮጵያ መንግስትና በኢጣሊያ መንግስት መካከል ለልጅ ልጅ የሚቆይ የወዳጅትና የእርቅ ውል ተደርጓል።

2ኛ ከዚህ ቀደም ውጫሌ ላይ ተደርጎ የነበረው ውል በፍፁም ቀርቷል።

3ኛ የኢጣሊያ መንግስት የኢትዮጵያን ሙሉ ነፃነት ያውቃል። /አውቅና ይሠጣል/

4ኛ ምንም እንኳን ከዚህ ቀደም ስለወሰኑ በነገር ቢስማሙ አሁንም ይህ ውል ከተደረገበት ቀን አንስቶ እስከ አንድ አመት ድረስ ሁለቱ መንግስታት የሚካለሉላቸውን ወኪሎቻቸውን አድርገው በስምምነት ይካለላሉ። ይሁን እንጂ እስከዚያ ድረስ የመረብና የበለሣ ወሰን ይሁን ተብሎ ለጊዜው የተወሰነው ከሁለቱም ወገን እንደተከበረ ይቆያል እንጂ አይሻርም።

5ኛ የኢጣሊያ መንግስት ወሰኑን በደንበ ሣይካለል በኤርትራ የያዘውን አገር ወይም ከያዘው አገር ቆርጦ ለመስጠት የፈለገ እንደሆነ ለኢትዮጵያ መንግስት ይሰጣል እንጂ ለሌላ መንግስት አሣልፎ ለመስጠት አይችልም። ይላል። አይ ጣሊያን!

በዚህ ተስማምተው ሁሉንም ምርኮኞች ለቀቁ። ከምርኮኞች አንዱ የነበረው ጀ/ል አልበርቶኒ ሲሔድ ከመነሣቱ በፊት ተጠርቶ ከጀ/ል አርሞንዲ የተማረከውን ሻምላ አፄ ምኒልክ ሠጥተው ለቤተሰቦቹ በክብር እንዲሠጡለት አደራ ብለው ላኩት። በዚህም የኢጣሊያ ህዝብ ለንጉሡ ያለውን አድናቆት/በተለይ ሶሻሊስትን የሚደግፉትና ከመጀመሪያው ጀምሮ ወረራውን ይቃወሙ የነበሩት/ በሮም አደባባይ አድናቆታቸውን ገልፀዋል ይባላል፣ ለምኒልክ። ጣሊያን ከዚህ ድል በኋላ ከዚህ ቀደም እንዳየነው በአፄ ዮሃንስ



ጊዜ የያዘችውን ኤርትራን ብቻ አጠናክራ ይዛ ለመቆየት ተጨማሪ 15 ሺ ጦር ሠራዊት ልካ በኤርትራ ተወሠነች።

እዚህ ነጥብ ላይ ሲደረስ ብዙዎች ይቆጫሉ። አምባላጌን አስለቅቀው፣ መቀሌን አስለቅቀው፣ አድዋን አስለቅቀው ለምን በዚያው ወኔ ኤርትራን አላስለቀቁም? የሚል ነገር ከብዙዎች ይነሣል። መነሣትም አለበት። ወቀሣው ግን ተገቢ ሊሆን አይገባ ይሆናል። ይቻል ነበር? የሚለውም አንድ ሊመለስ የሚከብድ ጥያቄ ነው። 15 ሺ ጦር የመጣው ወዲያው ነው፣ በአድዋ ጦርነት ያለቀው ጦር ብዙ ነው፣ ለረጅም አመት የተጠናከረ ምሽግ ያለበት ነው... ወዘተ።

ኤርትራውያኑ "ለባእድ ተላልፈን ተሠጥተን!" እያሉ ይቆጩ ነበር። ከወንድሞቻቸው ጋር መቀላቀል ይፈልጉ ነበር። ማንኛውም ንጉስ ኤርትራን ግድ ካልሆነበት በቀር አሣልፎ ሊሠጥ አይችልም፣ ቢነጥቁት እንኳ ተጋድሎ ማስመለስ ምርጫው ነው። ነገር ግን የአቅም ጥያቄ አለ። አለመሠልጠንና በእርዳታ መሣሪያ መዋጋት ማለት ምን ማለት መሆኑ ግልፅ ነው። ተዋግቶ መሸነፍም ይኖራል፣ ሲሸነፉ ደግሞ የያዙትንም ማጣት ይኖራል። አፄ ምኒልክ ያን ያላደረጉበት ምክንያት "እንዲህ እንዲህ አስበው ነው" ብሎ መናገር አይቻልም። ነገር ግን ለምን ገፍተው ኤርትራ ድረስ አልሔዱም? የሚለውን ቁጭት አዘል ጥያቄ ስናነሣ፣ አብረን የወቅቱን ሁኔታ ለማስታወስ መዘጋጀት ይኖርብናል ለማለት ነው ጥቂት ማለት ያስፈለገኝ።

አፄ ምኒልክ ከዚህ የስምምነት ውል በኋላ የኢጣሊያን እውቅና መስጠት መሠረት አድርገው ወዳጅ ለሚሏቸው ለፈረንሣይ፣ለሞስኮ፣ለእንግሊዝና ለሌሎች መንግስታት አስታወቁ። ከዚህ ውል በኋላም ኢትዮጵያ ብቸኛዋ ነፃ የአፍሪካ አገር ሆና አገራቱ ባለሙሉ ስልጣን ወኪሎቻቸውን/ዲፕሎማቶቻቸውን/ መላክ ጀመሩ።

ሙሴ ሌዎንስ ላጋርድ ከፈረንሣይ መንግስት፣ ጄኔራል ከላሶውን ከሞስኮ መንግስት፣ ሌተናል ኮሎኔል ጂን ላን ሐሪንግተን ከእንግሊዝ መንግስት፣ ካፒቴን ፍሬደሪኮ ቺኮዲካላን ከኢጣሊያ መንግስት ተልከው መጥተው የሹመት ደብዳቤያቸውን ለአፄ ምኒልክ አቅርበው ሌጋሲዮናቸውን እየከፈቱ ተቀመጡ።

ከአድዋ ድል በኋላ ኢትዮጵያ በፍጥነት ወደ ዘመናዊ አገርነት መራመድ ጀመረች።

ፕሮፌሠር ላጵሶ ጌ.ድሌቦ "የኢትዮጵያ የገባር ስርዓትና ጀምር ካፒታሊዝም" በሚለውና በ1983 ዓ.ም በታተመው መፅሃፋቸው "ከአድዋ ጦርነት በኋላ በአዲስ አበባ መዲና ማእከላዊ መንግስቱን ለማጠናከር በከተማ ስራት፣ በንግድ፣ በኢኮኖሚ፣ በአስተዳደር፣ በውጭ ግንኙነት የተካሄደው የካፒታሊዝም ግንባታ ጀምር ነው" ይሉታል ሒደቱን።

ከዚያ ዘመን ጀምሮ የተከናወኑት አዳዲስ ስራዎች ሁሉ በእርግጥም የዲፕሎማሲ ግንኙቱ ውጤቶች ናቸው። ለዚህ ደግሞ ኢትዮጵያ ሉዓላዊ አገር መሆኗና እውቅና ማግኘቷ ጠቅሟታል። ከአድዋ ድል በኋላ እንግሊዝ፣ ፈረንሣይ፣ ጣሊያን፣ ሞስኮ፣ ጀርመንና ሌሎች የዚያ ዘመን ሃያላን አገራት የኢትዮጵያን መንግስታዊ ሉአላዊነት በመቀበል ከአገራችን ጋር የዲፕሎማሲና የንግድ ግንኙነት ከመመስረታቸው ጋር በተያያዘ፣ ከአዲስ አበባ ጅቡቲ የምድር ባቡር ሃዲድ አማካይነት በኢትዮጵያና በውጭው ዓለም መካከል እያደገ የሚሔድ ንግዳዊና አለም አቀፋዊ የስልጣኔ ትስስር ተፈጥሯል።

በነገራችን ላይ አፄ ምኒልክ ግንኙነቱን ከሁሉም መንግስታት ጋር ያድርጉ እንጂ፤ በዋናነት ፊታቸውን ያዞሩት ወደ ፈረንሣይ ነበር። ፈረንሣዮችም እንደ ዋና አማካሪ ሆነው ብዙ ስራ ሠርተዋል።

ይህም ማለት ከወረራው አስቀድሞ የተጀመረ ልዩ ግንኙነት የነበረ ሲሆን፤ከጦርነቱ በፊት በ1884 ዓ.ም ከስዊዙ ተወላጅ መሀንዲስ ከሙሴ አልፍሬድ ኢልግ ጋር ከጅቡቲ እስከ ሐረረ፣ ከሐረር እስከ እንጦጦ፣ ከእንጦጦ እስከ ከፋ፣ ከዚያም እስከ ነጭ አባይ ድረስ የሐዲድ መንገድ እንዲዘረጋ በውል ፈቅደውለት እንደነበር በዚያው አመት የተዋዋሉት የመጀመሪያው ሆኑድ ያስረዳል። የሃዲድ ዝርጋታውም በፈረንሣይ የምድር ባቡር ኩባንያ ሊከናወን ታስቦ፤ በማህበሩ ስር ሆነው ስራውን ለመምራት የስዊዙ ኢልግ፣የፈረንሣዩ ሙሴ ሽፍኔ፣ የሞስኮው ሊዎንቴፍ፣የጅቡቲ አገረ ገዥ የነበረው ላጋርድ በፈረንሣይ መንግስት ስር ሆነው ተሣትፈዋል። እቅዱ ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ ባይሆንም።

በዚህ ሐዲድ ከሚወጣውና ከሚገባው የሸቀጥ ቀረጥ ላይም ማህበሩ ከመቶ አስር እንዲያገኝ በአንቀፅ 10 ተስማምተው ነበር። ሆኖም ሙሴ ኢልግ ከማህበረተኞቹ ጋር ተመካክሮ ወደ ፈረንሣይ ሔዶ በቂ ገንዘብ ለማምጣት ሞክሮ ስላልተሣካለት ከጅቡቲ አዲስ አበባ ድረስ ብቻ ያለውን ለመስራት ተገደደ። የውሉ አንቀፅ 3 እንደሚለውም ውሉ ለ99 አመት ብቻ የሚቆይ ነበር። ከ99 አመት በኋላ ማህበሩ ስላወጣው ገንዘብም ሆነ ስለሌሎች ቁሣቁሶች ጥያቄ ሳያቀርብ ጥሎ ሊሔድ ነው የተስማሙት። ስራው በ1884 ተጀምሮ በ1909/10/ ዓ.ም ተጠናቆ ተመረቀ።

የሆነ ሆኖ ከዚያ ጊዜ በኋላ በአገር ውስጥ በንግድ አስተዳደርና በግብር፣ በአዲስ አበባ ከተማና በክፍለ አገር ከተሞች መካከል እያደገ የሚሔድ አዲስ የገበያ ስርዓትና የባህል ግንኙነት ተፈጠረ። በአዲስ አበባም ዘመናዊ የመንገድ፣ የመገናኛ፣ የንግድ፣ የገበያ፣የገንዘብ፣ የባንክ፣የትምህርት፣የአስተዳደር ማእከላት ስራዎችና አገልግሎቶች ጅምር ታዩ።

በዘመናዊ የአስተዳዳር ስርዓትና የስራ ጅምርን በሚመለከት ከ1900 ዓ.ም በፊት በአገራችን ሀገረ ትዕዛዝ፣ አፈንጉስ፣ የጊዜ ሊጋባና የጦር አበጋዝ



የተባሉ አራት አማካሪዎችንና ረዳት ሹማምንቶችን ይዞ የመንግስትን ስልጣንና ስራ ማከናወን ነበር የተለመደው።

በአፄ ምኒልክ ጊዜ ግን የመንግስትን የስልጣን ስራ በንጉሡ ስም በውክልና የሚያከናውኑ አዲስ የሚንስትሮች ምክር ቤት በፈረንሣይ አማካሪዎች ምክርና እርዳታ በአዋጅ ተቋቋመ። በምክር ቤቱ የአገሪቱ የመጀመሪያ ቢሮክራሲያዊ የፍርድ፣ የጦር፣ የግቢ፣ የፅህፈት፣የአገር ግዛት፣ የገንዘብ፣ የውጭ ጉዳይ፣ የንግድ፣ የእርሻ፣ የፖስታ፣የቴሌግራፍና የቴሌፎን፣የስራና የትምህርት መስሪያ ቤቶች ተዋቀሩ።

በተጨማሪም ለአስተዳደርና ለግብር ስራ በሚያመች መንገድ የአገሪቱ መላው ህዝብና መሬት በአዲስ አበባ በቤተመንግስት ጊቢ ውስጥ በአዲሁ የፍርድ ሚንስቴር ስር በስድስት የህግ እና የፍርድ ጉባዔዎች ተዋቀሩ። በስድስቱ የህግና የዳኝነት ጉባዔዎች ስር ዘጠና በሚደርሁ የአስተዳደር ክልሎች ተመደቡ። በስድስቱ ጉባዔዎች ስር፣ ክልሎች ለበላይ ውሣኔ በይግባኝ የሚመጡ የአስተዳደር ጉዳዮችን መርምረው የሚወስኑ ከፍተኛ ባለስልጣኖች ተሾሙ።

በ1900 ዓ.ም በሚንስትሮች ምክር ቤት ምስረታና ሹመት የመንግስት ሹማምንቶች ተከታታይ የህግ አዋጆችን እያወጡ ተግባራዊ ማድረግ ጀመሩ። ለምሣሌ የሚንስትሮች ምክር ቤት በተቋቋመ በአራተኛው ቀን በአገሪቱ ረጅም ታሪክ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ በአዲስ አበባ የከተማ መሬት በግለሠቦችና በመንግስት የሚሸጥበትና የሚገዛበት አዲስ ህግ በአዋጅ ወጣ። ቀጥሎም በሐምሌ ወር 1900 ዓ.ም የሚንስትሮች ምክር ቤት በመጀመሪያው ጉባዔው በአገሪቱ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ "አዲስ" የፍርድ፣ የዳኝነት የፍትሐብሔር፣የወንጀል፣ የግል መሬት ይዞታ፣የመንግስት ሐብት፣የግል ሐብትና የውርስ ህጎችን ደነገገ።

" በወንጀል እየተያዘ መሬቱን የሚነቀል ሠው ሁሉ፣ ወንጀልም ቢገኝበት በኩቡቱ እና በሠውነቱ ይቀጣ እንጂ መሬቱን አይነቀል። ነገር ግን ነፍስ ገድሎ የሄደ፣ በመንግስት ክፉ ስራ የሠራ ይነቀል። ርስትም ማለት፤ ያባት የናት መሬት፣ ደግሞ በወርቁ የገዛው መሬት ነው እንጂ የመንግስት መትከያ የሆን አይደለም።

"ደግሞ የመትከያም መሬት ቢሆን መንግስት ርስት ያደረገለት ይረጋል። ሠካንም የሞተ እንደሆን አባቱ እናቱ ገንዘቡንም ርስቱንም ይውሠዱ እንጂ ሹም አይወርስ። እናትም አባትም የሌለው እንደሆን ወንድሙ እህቱ ይውረሁ። እናት አባት እህት ወንድም የሌለው እንደሆን ግን እስከ አራት ትውልድ ላለ ለቅርብ ዘመዱ ይሁን። ደግሞም ከዘመዶቹ ለይቶ ለአንዱ ይሁን ብሎ የተናዘዘ እንደሆን የተናዘዘለት ይውሠድ። ከአራት ትውልድ ወዲያ የሆነ ግን ውርሱ ለሹም ይሁን።" ተብሎ ተደነገገ።

ይህም ህግ በመኳንንቱም፣በሠራዊቱም ተቀባይነት አግኝቶ በንጉሡ ፈቃድ በነጋሪት አዋጅ በአደባባይ ተነገረ።

ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ማህበራዊ... የሚባሉት ቃላቶች በዚሁ ዘመን ነበር አዲስ መልክ ይዘው ብቅ ያሉት። በጥቅሉ ከዚህ ምክር ቤት መቋቋም በኋላ የአስተዳደር ስርዓትን ተከትለው የሚመጡ መሠረታዊ ለውጦች መታየት ጀመሩ።

አፄ ምኒልክ እንደ አውሮፓውያን ደንብ በየክፍሉ የሾሟቸው ሚንስትሮች

1. አፈ ንጉስ ነሲቡ መስቀሉ የፍርድ ሚ/ር
2. ፊት አውራሪ ሐብተ ጊዎርጊስ ዲነግዴ የጦር ሚ/ር
3. ሊቀ መኳስ ከተማ ያገር ግዛት ሚ/ር
4. ነጋ ድራስ ሃይለጊዎርጊስ ወልደሚካኤል የውጭ ጉዳይና የንግድ ሚ/ር
5. በጅሮንድ ሙሉጌታ ይገዙ የገንዘብ ሚ/ር
6. ከንቲባ ወልደ ፃድቅ የእርሻና የመስሪያ ሚ/ር
7. አለቃ ገብረ ስላሴ ወልደ አረጋይ የፅህፈት ሚ/ር (ፀሐፊ ትዕዛዝ)
8. አዛዥ መታፈሪያ የግቢ ሚ/ር
9. ቀኝ አዝማች መኮንን ተወንድ በላይ የስራ ሚ/ር
10. (ጥቂት ቆይቶ) ልጅ በየነ ይመር የስልክ ሚ/ር
11. የትምህርት ሚ/ር ስራው ብቻ ታውጆ የተማረ ስለሌለ ገና ሹም አልተደረገበትም ነበር።

ይህም ሲባል አፄ ምኒልክ የሚንስትሮች ምክር ቤትን በ1900 ካቋቋሙ በኋላ የስርዓቱ ውጤት ወይም የፈረንሣይ ምክርን ተግባራዊ በማድረጋቸው የተገኙ ውጤቶች ብቻ ተደርገው መወሠድ የለባቸውም ቀጥለን የምናያቸው ነገሮች። እድገት መታየት የጀመረውም ሚንስትሮች ከተሾሙ በኋላ ብቻ አይደለም። አፄ ምኒልክ ለሚሲዮኑም፣ለቆንሲሉም፣ ለሁሉም አውሮፓዊ በራቸውን ክፍት ያደረጉና የተመቹ የሆኑት ከአድዋ ድል በፊት ጀምሮ ነው። የሐይማኖት ሠባኪያንን እንኳ አልከለከሏቸውም። ለስልጣኔ የነበራቸውን ጉጉት ከአድዋ ጦርነት በፊት ባሠሯቸው ስራዎች መገንዘብ ይቻላል። እርግጥ ነው ብዙ ተግባራቶች የተከናወኑት ከ1900 ዓ.ም ጀምሮ ነው። ሆኖም የምድር ባቡሩ፣ የፖስታ፣ የቴሌግራምና ቴሌፎንን የመሣሠሉት ከ1887 ዓ.ም ጀምሮ ነው መሠረታቸው የተጣለው።

አፄ ምኒልክ ከላይ ያየነውን ዘመናዊ የሚባል /አንፃራዊ/ የአገዛዝ ስልትና አወቃቀር ተግባራዊ ከማድረጋቸውም በላይ፣ በኢትዮጵያ የመጀመሪያ የሆኑ በርካታ ተግባራቶች በዘመናቸው አከናውነዋል፣ መስርተዋል፣ አቋቁመዋል፣ አስመጥተዋል... ወዘተ። ከብዙ በጥቂቱ የሚከተሉት ናቸው።



ለመጀመሪያ ጊዜ ዘመናዊ ትምህርት ቤት የተከፈተው በ1901 ዓ.ም ሲሆን፤ይህ የመጀመሪያው የመንግስት ዘመናዊ ት/ቤት "የዳግማዊ ምኒልክ ተማሪ ቤት" ነው። የመጀመሪያዎቹ መምህራኖችና የስራ መሪዎች የግብፅ ተወላጆች ነበሩ። የት/ቤቱ ርዕሠ መምህር የግብፅ ዜጋ ሲሆን ሐና ሣሊብ ይባል ነበር። ት/ቤቱ መቶ ተማሪዎች ተቀብሎ የነበረ ሲሆን፣ በየጊዜው ቁጥሩ እያደገ ሄዷል። ጅምሩ አዲስ አበባ ላይ ብቻ የነበረ ቢሆንም፤ በዚያው ዘመን በተከታታይ በሃረር፣በአንኮበር፣በደሴ እንዲከፈቱ ተደረገ። መምህሮችም እንደ ዳግማዊ ምኒልክ ት/ቤት ሁሉ ግብፃውያን ነበሩ። በ1905 ዓ.ም የአሊያንስ ፍራንሲሲ የፈረንሣይ ት/ቤት ተቋቋመ።

ከት/ት መስፋፋት ጋር አብሮ የሚሔደው የህትመት ስራም መሠረቱ የተጣለው በዚሁ ዘመን ነበር። የግሪክ ተወላጅ የሆነው እንድርያስ ካቬዲያስ ነበር የመጀመሪያውን የህትመት ስራ የጀመረው። በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ጋዜጣ "አእምሮ" የተባለው በየሣምንቱ ቅዳሜ ታትሞ መውጣት የጀመረው በእንድርያስ አነስተኛ የማተሚያ ማሽን አማካኝነት ነው። የመጀመሪያው እትም ጥር 17 ቀን 1901 ዓ.ም በገበያ ሲታይ የስርጭት መጠኑ ከ10-15 ጋዜጣ ብቻ ነበር። የጋዜጣውን ስያሜ የሠጡት አፄ ምኒልክ ሲሆኑ፤ የመጀመሪያው ደንበኛም ራሣቸው ነበሩ። ንጉሡ የጋዜጣውን ጥቅም ለመኳንንቱ በማስረዳታቸው የጋዜጣው ደንበኞች እየበዙ ሔዱ።

በ1903 ዓ.ም ከአውሮፓ የህትመት ማሽን አስመጥተው "መርሐ ግብብ" ማተሚያ ቤትን አቋቋሙ።

ለመጀመሪያ ጊዜ ገንዘብ ያተሙና፣ በስማቸውና በመልካቸው ያስቀረፁ መሆናቸውም ይታወቃል። ምንም እንኳን መጠናቸው /ብዛታቸው/ አነስተኛ ቢሆንም የብሮቹ ስሞች አላድ፣ሩብ፣ ትሙን እና ግርሽ" ይባሉ የነበረ ሲሆን፣ ገንዘቡን ያሳተሙት በፓሪስ ነው። ወዲያው የገንዘቡን መቅረጫ በአዲስ አበባ አቋቁመው በ1901 ዓ.ም በሙሉው ግዛታቸው መገበያያ እንዲሆን አወጁ። እንዲህም ተገጥሞላቸዋል፦

"ልማዴ መሸከም፣አሞሌ ማንከብከብ ሲወዘውዙኝ
እምዬ ምኒልክ ብር አሠሩልኝ።
ከገበያ ወጡ ጥይትና ጨው
የፈረንጆችን ብር ሠራ አባዳኘው።"

ከዚህ በኋላ ከግብፅ ባንክ ጋር ስምምነት በማድረግ "የአበሻ ባንክ" የተባለውን አቋቋሙ። የተቋቋመው ባንክ ካፒታሉ 5000 ፓውንድስተርሊንግ የነበረ ሲሆን፤ የግብፅ ባንክ 100 ሺ ፓውንድስተርሊንግ ወዲያው አዋጥቶ መስሪያ ቤቱ በአዲስ አበባ ተቋቋመና እስከ 1928 የዳግም የኢጣሊያ ወረራ ድረስ አገልግሎት ሲሠጥ ቆየ። (በነገራችን ላይ ግብፅ የከዚህ ቀደም ወረራዋና ሠበቅቷ እንዲረሣ ትፈልጋለች ይልቁንም ባገኘችው አጋጣሚ ሁሉ ኢትዮጵያን ወዳጅ ማድረግ የውጭ ግዴታዋ ነበር፣ ነው፣ ይሆናልም።

ቱተሰይ ኢትዮጵያ መሠልጠን ስትጀምርና የሌላውን አለም ወዳጅነት ስታገኝ፣ ስልጣኑ ስትጋራ የአባይ ሁኔታ የበለጠ እያሠጋት ይሄድ ነበርና፤በማስፈራራቱም፣ በማባበሉም፣ በመወዳጀቱም ሆነ በማንኛውም መንገድ ምንም ነገር ብታደርግ ልንደነቅ አይገባም፡፡ አባይ ውሎ ይግባ)፡፡

የትራንስፖርትና መገናኛ መሠረት የተጣለው በእምዬ ምኒልክ ጊዜ ነው ለማለት ይቻላል፡፡

ከስዊዙ ተወላጅ ኢልግ ጋር በመነጋገር በአዲስ አበባ ብዙ መንገዶች ሲሠሩ ከከተማዋ ውጪ ከአዲስ አበባ እስከ አዲስ አለም 45 ኪ.ሜ መንገድ ተሠርቷል፡፡ መንገዱን የሚደለድል ዳምጠው የሚባለው መኪና ከአውስትራሊያ ንጉስ ተልኮላቸው ተጠቅመውበታል፡፡ በመጀመሪያ የአዋሽ ወንዝ ላይ የተሠራው ድልድይ በ1879 ዓ.ም ሲሆን፤ ከኢልግ ጋርም ጣሊያናዊው መሐንዲስ ካፑቺ ተሣትፎበታል፡፡ ይህንን ድልድይ ፈረንሣዮች በኋላ ላይ በብረት ሠርተውታል፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ እስካሁን በአገልግሎት ላይ ያሉት የራስ መኮንንና የቀበና ድልድይም በዚሁ ጊዜ በእነዚሁ መሐንዲሶች የተሠሩ ናቸው፡፡ በ1887 ዓ.ም የፖስታ፣ የቴሌግራምና የቴሌፎን አገልግሎቶች እንዲኖሩ ሆነዋል፡፡ ባህር ዛፍንም ፈሉን ከአውስትራሊያ አስመጥተዋል፡፡

በ1901 ዓ.ም አውቶሞቢል ወደ ኢትዮጵያ ሲገባ ቀደም ሲል በተሠሩት መንገዶች ላይ ነበር አፄ ምኒልክ የተንሸራሸሩት፡፡ ይህ ሁሉ ሲሆንም የአገሬው ሠው አልለምድ ብሎ ንጉሡ ተቸግረው ነበር፡፡ እንዲ የሠይጣን ፈረስ፣ ሌላ ጊዜ መርገምት እያሉ ይተቹ የነበሩም በርካታ ናቸው፡፡ ሁሉንም ነገር እንደ አርአያ ሆነው የሚያሣዩት ንጉሡ ነበሩ፡፡

አፄ ምኒልክ የህዝቡ ጤና አጠባበቅ ላይም አተኩረዋል፡፡ በመጀመሪያ የሩሲያ ሐኪም ቤት ይባል የነበረው ነበረ፡፡ በኋላ በ1901 ዓ.ም የዛሬው ዳግማዊ ምኒልክ ሆስፒታል ተመሠረተ፡፡ በሐረርም ፈረንሣዮች ሆስፒታል እንዲያቋቁሙ ተፈቅዶላቸው አቋቁመው ነበር፡፡

ኢ.ኤ.አ በ1894 ዓ.ም የመጀመሪያው የቧንቧ ውሃ በቤተመንግስቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ በተዘረጋ ጊዜ መኳንንቱ ጉድ አሉ፡፡ አልጣከበም ያለውም ብዙ ነበር፡፡ ከተለመደ በኋላ ግን እንዲህ ተወደሠበት፡-

"ንጉስ አባዳኘው እንዴት ያለ አመጣ
ውሐ በመስኮት ላይ ባየር ላይ ሲወጣ
ያደፈው ሲታጠብ የጠማው ሲጠጣ፡፡
አየት በኛ ጊዜ እንዲህ ያለ መጥቷል፣
ደም ጥቁት ቢቆይ ከፈረንጅ ይበልጣል፡፡"

የስፌት መኪና፣ እንጨት የሚሠነጥቅ ማሽን፣ የእህል ወፍጮ፣ የሣሙና ፋብሪካ.. ወዘተ እያስመጡና እያሠሩ ኢትዮጵያን መስመር የሰያዙ ታላቅ ንጉሠነገስት ነበሩ፡፡



ወታደር ስንቁን ራሡ ይዞ እንዲንቀሣቀስ፣ ደሞዝ ስለሚከፈለው ህዝቡን እንዳያስቸግር፣ የተኩስ ስርአት እንዲያውቅ በማድረግ እጅግ የዘመነ ባይሆንም የሠለጠነ የሃገር መከላከያ ሠራዊት ገንብተው በሚኒስትር እንዲጠቃለል አድርገዋል፡፡

ቤተመንግስታቸውንም አሻሽለውና ሠራተኞችን በደሞዝ ቀጥረው አድሠዋል፡፡ ብዙ ቤቶችና አብያተክርስቲያናትንም አሣንፀዋል፡፡

ከዘመናዊ የኤሌክትሪክ መብራት ጀምሮ ብዙ አይነት የስልጣኔ አይነቶች ብልጭ ያሉበትና በርካታ አገራዊ መሠረቶች የተጣሉበት ዘመን ነው፡፡

እቴጌ ጣይቱ የመጀመሪያዋ ሣይክል ጋላቢ ከመሆን ጀምረው እስከ ዘመናዊው ጣይቱ ሆቴል አመሠራረት ድረስ የተሣተፉበት ዘመን ነበር የአፄ ምኒልክ ዘመን፡፡

አፄ ምኒልክ ከ20 የሚበልጡ ልዩ ልዩ ውሎችን አድርገው እንደነበርም ይነገራል፡፡ ከማዕድን ቁፋሮ ጀምሮ እስከ ሐዲድ ዝርጋታው ድረስ ከፈረንሣይ፣ ከእንግሊዝና ከኢጣሊያ ጋር በተሰይ በርከት ያሉ የስራ እቅዶች ነበሩ፡፡ ሶስቱ አውሮፓዊ አገሮችም በግልፅ የጥቅም ተካፋይነታቸውን ያረጋገጡበትን የውል ስምምነት ግልባጭ ለአፄ ምኒልክ ልከውላቸው ነበር፡፡ እንግሊዝ፣ፈረንሣይና ኢጣሊያ እ.ኤ.አ በ1906 /በኛ አቆጣጠር ታህሣስ 13 1899 ዓ.ም/ ለንደን ላይ "የሶስቱ መንግስታት ስምምነት" ተብሎ የሚጠራውን ውል ተፈራርመዋል፡፡ ውሉ በኢትዮጵያ ለሚካሄደው የልማት ስራ የጥቅም ተጋሪ ለመሆንና "የኢትዮጵያን ነፃነትና የንጉሠነገስቱን ስልጣን፣ የህዝቡንም መብት እንነካም" የሚል አንቀፅ ያካተተ ነው፡፡ እናም እነዚህ ሶስቱ አገሮች በኢትዮጵያ አጎራባች አገራት ያሏቸውን ቅኝ ግዛት አገሮች አስጠብቆ ከመቆየት ጎን ለጎን አንደኛዋ አገር ብቻዋን ከኢትዮጵያ ጋር በወዳጅነት ተሣስራ ብቻዋን ተጠቃሚ እንዳትሆን ትኩረት ላይ ነበሩ፡፡ ኢጣሊያ ኤርትራና ከፊል ሡማሊያ ቅኝ ግዛቷ ነው፣ ፈረንሣይ "የፈረንሣይ ሱማሌላንድ" እንግሊዝ "የእንግሊዝ ሱማሌላንድ" ኢጣሊያ "የኢጣሊያ ሱማሌላንድ" ብለው የሠየሚቸው ግዛቶች ስላሏቸው የኢትዮጵያን ጠረፎች በቀለበት ከበው በኢትዮጵያ ብሔራዊና ማህበራዊ የእድገት አቅጣጫና ጎዳና ላይ በፖለቲካ፣ በስትራቴጂ፣ በኢኮኖሚና በባህል ከባድ ጂኦፖለቲካዊ ተፅእኖ ማሣደራቸው የግድ ነበር፡፡ በዚህም ላይ ወደቦችን ሁሉ ይዘዋል፡፡ ስለዚህም እርስ በርስ መፎካከር ብቻ ሣይሆን መጠባበቅም ነበረባቸው፡፡

የሶስቱን መንግስታታ ስምምነት ለአፄ ምኒልክ ግልባጩን ቢልኩላቸውም "የእኔ አገር ወኪል በሌለበት ውል አልገደድም" የሚል መልስከት ልከውላቸዋል፡፡ ነገር ግን ምንም ለውጥ አልነበረውም፡፡ እነሡም ግልባጩን የላኩት እንዲሁ ለማሣወቅ ያህል እንጅ የማዳከም ስራውን በጊሐድ እንደማይፈፅሙት ያውቃሉ፡፡

እነዚህ አገራት በምኒልክ ጊዜ የወደፊቱን ጥቅም እያሰቡም ቢሆን በወዳጅነትና በነፃ አንዳንድ ጠቃሚ ስራ ሲሠሩ ቢችሉ አያስገርምም።

ከዚህ አንፃር አንዱ ብቻውን ወዳጅ ሆኖ ሌሎቹ እንዳይገለሉ የጋራ ስምምነት ማድረግ ነበረባቸውና አድርገዋል። ሌሎች ከግል ጥቅምና አንዳንድ ጊዜም ከ "ሴራ" ጋር የተቆራኙ ውሉችን ተፈራርመዋል።

አፄ ምኒልክ በፅኑ የታተሙት በ1902 ዓ.ም ነበር። ይሁን እንጂ ባለቤታቸው እቴጌ ጣይቱ የባለቤታቸውን ጅምር እንቅስቃሴ ለማስቀጠል ከመጣር ጎን ለጎን ስልጣኑንም ወደራሣቸው ለመጠቅለል ይጥሩ ነበር።

ንጉሠ ነገስት ምኒልክ ብዙ አገራዊ ተግባራቶችን ከውነው በተጠቀሠው ጊዜ ህመሙ እንደመበርታት ሲል ተከታዩን የኑዛዜ ቃል ይፋ አደረጉ።

"... አፄ ቴዎድሮስ የሞቱ ጊዜ ከነቸው ጋራ የነበረው ሠው ሁሉ ያንዱን አገር አንዱ እደርባለሁ፣ አንዱን ገድዬ እኔ ጌታ እሆናለሁ እያለ ሁሉም ሳይረባ ተላልቆ ቀረ።

ከዚህም በኋላ የአፄ ዮሃንስ ሠው የሆነውን የምታውቁት ነው። ባገር በሽታ ሳይገባበት ሌላ የባእድ ጦር ሣይነግበት በምቀኝነት እርስ በርሡ እንደተላለቀ አይታችኋል። አሁንም ልጆቸ ወዳጆቸ አንዱ ባንዱ ምቀኝነት ይቅር። ያንዱን አገር አንዱ እኔ እደርባለሁ እንዳትሉ። እኔ እስካሁን በፍቅር እንዳኖርሁዋቸሁ እናንተም ተስማምታችሁ በፍቅር እንድትኖሩ እለምናችኋለሁ። እናንተ አንድ ልብ ከሆናችሁ በምቀኝነት እርስ በርሣችሁ ተዋግታችሁ ካላለቃችሁ በቀር አገራችንን ኢትዮጵያን ለሌላ ለባእድ አትሠጧትም። ክፉም ነገር አገራችንን አያገኛትም። ይህንን ምክር ለእናንተ መስጠቴ እኔማ በእግዚአብሔር ቸርነት ይህንን ያህል ዘመን ገዛቼ የለምን። ነገር ግን ሠው ነኝና እንግዲህ እስንት ያህል ዘመን እቆያለሁ ስል ነው።

አሁንም እኔ እንደተመኘሁት እግዚአብሔር የተጨመረበትና ፈቃዱ ሁኖ ልጅን/የልጅ ልጅን ለማለት ነው።/ ቢእቆምላችሁ ክልጁ ጋራ ሁናችሁ አገራችሁን ጠብቁ አደራ ብያችኋለሁ።" ይህ የኑዛዜ ቃል በማህተም እየታተመ በየማዞቱ ተሠራጨ፣ በጃን ሜዳም ተነበበ። ለ4 አመታት ያህል ኑዛዜው በተዋጠላቸውና ባልተዋጠላቸው መካከል ፋክክሩ በረታ።

በተለይ ለልጅ እያሡ በሞግዚትነት በታጩት በራስ ተሠማ ናደውና በእቴጌ ጣይቱ መካከል። እቴጌ ጣይቱ የወንድማቸውን የራስ ወሌ ብጡል ልጅ የሆኑትን ራስ ጉግሣ ወሌንና ዘውዲቱ ምኒልክን በጋብቻ ከማስተሣሠር ጀምረው ተመሣሣይ ጥልፍልፎሽ በመፍጠር ከስልጣኑ ላለመገለል ሲሉ ብዙ ነገር አከናወኑ። እቴጌ ጣይቱ ከልጅ እያሡ ይልቅ ዘውዲቱ ወራሲ መንግስት እንዲሆኑ ነበር ምኞታቸው።

ሆኖም ምኒልክ የኑዛዜውን ቃል ጥቅምት 17 ካሠሙ በኋላ ብዙ ሣይቆይ በየካቲት ወር 1902 ዓ.ም የጦር ሚ/ሩ ፊት አውራሪ ሐብተጊዮርጊስና ሞግዚቱ ራስ ተሠማ ናደው እቴጌዋ ላይ አንድ ውሣኔ አሣለፉ። ይህ ውሣኔም በአደባባይ ስብሠባ ተካሒዶ ብዙሃኑ አምኖበት የተላለፈ ይምሠል እንጅ በዚዱ ተቀነባብሮ፣ የቀድሞ ቂመኞችና በጣይቱ የማይወደዱ የነበሩ ሹማምንት የፈተሉት ነበር። እነፊትአውራሪ ሐብተጊዮርጊስ የእቡኑን ድጋፍ ይዘው ውሣኔውን በጳጳሱ አማካይነት እንዲያውቁት አደረጉ።

ይህም ከአስተዳደር ስራው ውጭ ሆነው ባለቤታቸውን በማስታመም ብቻ እንዲወሠኑ የሚል ነው። እቴጌ ጣይቱ ይህን ውሣኔ ሲሠሙ ኢትዮጵያ ሡልጥና የአውሮፓ ስርዓት አራማጅ ሆናለች ሲባሉ እውነት መስሏቸው ውሣኔው አግባብነት እንደሌለው በመግለፅ ለአውሮፓውያን ቆንሲሎችና ለአዲስ አበባ አድባራት የተማፅኖ ደብዳቤያቸውን አቀረቡ። ወደ አገሬ ልሒድ በሚል።

"እኔም በመሬቱም በምንም ብንባላ ለሐገሬ ስል ነው እንጂ እናንተን ለማስቀየም አይደለም። ይህንንም አገሬን መውደዴን እናንተም አትጠሉትም። ነገር ግን አሁን ንጉሡ ሲታመሙ ጊዜ ህዝቡ እመንግስት ስራ አይግቡብን ብሎ ለአቡን ማቴዎስ ላከብኝ። እኔም እሽ አልገባም ሸኙታችሁ አገሬ ስደዱኝ ብዬ ወደ ህዝቡ ልኪያለሁ። ይህም ደንብ በእናንተም በአውሮፓ አገር ያለ ነው። መንግስቱን ሲለቅ ወደ ርስቱ መሔድ። እንሠድም ያሉኝ እንደሆነ ግን ለመንግስትህ አስታውቅልኝ። እንደ አውሮፓ ስርዓት እናድራለን ብለዋል። ይህ ከአውሮፓ ስርዓት የወጣ ነው።"

-እንደ አውሮፓ ስርዓት እናድራለን ብለዋል የሚሉት የሚንስትሮች ምክር ቤት በመቋቋሙ ነው። ሚንስትሮች ሲሾሙም ሆነ መ/ቤቱ ሲቋቋም "እንደ ኤሮፓ አገር ስርዓት" በሚል ቃል ነው አንቀፁን የሚዘጋው። ስለዚህ እቴጌ ጣይቱ 'ምክር ቤትም ሆነ ህግ አፍራሽ ውስጥ እንደማይሠራ ገና አልደረሡበትም ነበርና አቤቱታቸውን ለእንግሊዙ ዲፕሎማት ነበር ያቀረቡት። የሆነ ሆኖ ከምኒልክ በፊት ሞግዚቱ ራስ ተሠማ ቀድመው ሲሞቱ በ1903 ዓ.ም ሁኔታው ሌላ ሁከት አስተከለ። አፄ ምኒልክም ከ4 አመታት ፅኑ ህመም በኋላ አረፉ። ከ1882-1906 ዓ.ም ኢትዮጵያን በንጉሠ ነገስትነት አስተዳደረውና የስልጣኔ ጮራ ፈንጥቀው በ70 አመታቸው ነበር ያረፉት።

እቴጌ ጣይቱም ወዳገሬ ስደዱኝ ያሉት ከወንድማቸው ጋር ሆነው ሊያምፁ ነው አስባለባቸውና ቤተመንግስቱን ለቀው ወደ እንጦጦ ማርያም ቤተክርስቲያን ሔደው በማዞት እንዲኖሩ ተፈረደባቸውና እስከ እለተ ሞታቸው እስከ 1910 ዓ.ም ድረስ በዚያው አሣልፈው አለፉ።

ዳግማዊ ምኒልክ እንደበታቸው ሣይቀር ታስሮ ስለነበር እቴጌ ጣይቱ ከተገለሉ በኋላ ልጅ እያሡ ማስተዳደሩን ጀምሮ ነበር። ምክንያቱም በ1902 እቴጌዋ ሲገለሉ፣ በ1903 ሞግዚቱ ስላለፉና ምኒልክም ስለተኙ ከ1903 ጀምሮ ልዑሉ

ራሁን ችሎ የአስተዳደር እንቅስቃሴውን ጀምሮዋል። ሆኖም የልጅ እያሱ ዘመን መንግስት ተብሎ የሚታወቀው ከምኒልክ ሞት በኋላ ከ1906-1909 ዓ.ም ነው።
በመጨረሻም አፄ ምኒልክ በህይወት ሣሉ ባሠሩትና ለልዑላኑ ሁሉ መቀበሪያ እንዲሆን

ባዘጋጁትና "የመታሠቢያ ቤት" ብለው በሠየሙት በ4 ኪሎዋ ባእታ ማርያም ቤተክርስቲያን ተቀበሩ። እቴጌ ጣይቱም በተመሣሣይ ከባለቤታቸው ጎን እንዲያርፉ ተደረገ።









ከምኒልክ የግዛት ዘመን በኋላ ያልተዘመረለት ልጅ እያሡ ስልጣኑን ይዞ ከ1906-1909 ዓ.ም ድረስ ኢትዮጵያን አስተዳድሯል። እርሁም በብዙዎች ተቃውሞ ስልጣኑን በኩዴታ ካጣ በኋላ የአፄ ምኒልክ ልጅ ዘውዲቱ "ንግስተ ነገስታት" ተብለው በዙፋን ሲቀመጡ፤ ራስ ተፈሪ መኮንን "አልጋወራሽ" ተብለው ከ1909-1922 ዓ.ም ከቆዩ በኋላ፤ ራስ ተፈሪ መኮንን በ1923 ዓ.ም የንጉሠነገስትነት ስልጣኑን ይዘው እስከ 1966 ዓ.ም ድረስ ኢትዮጵያን አስተዳድረዋል።

መስከረም 2 1967 ዓ.ም ከዙፋን በሃይል ከወረዱ በኋላም ዘወዳዊ ስርዓቱ እስከመጨረሻው አክትሞ ደርግ ስልጣኑን ይዞ 17 አመታትን አሣልፏል።

በዚህ መሠረት የልጅ እያሡ ታሪክ በአፄ ሃይለስላሴ ዘመን እንዲዳፈን ሲደረግ፤ የአፄ ሃይለስላሴ ታሪክም በደርግ ሲጥላላ ከርሟል። የደርግ ታሪክም እንደዚያው። ስለዚህም በቀጣዩ መፃህፍ "የኢትዮጵያ ታሪክ ካልተዘመረለት እያሡ እስከተዘመረለት ኢህአዴግ" በሚል ርዕስ 2ኛውን ታሪክ ሠፋ አድርገን እስከንቃኘው ድረስ የዚህን መጽሀፍ 1ኛውን ክፍል በዚሁ ልንገታው እንገደዳለን።

፠ተፈፀመ፠

<u>ዋቢ መጻህፍት</u>

- መፅሐፍ ቅዱስ - 1962 ዓ.ም ዕትም
- ቅዱስ ቁርዓን - 1964 ዓ.ም ዕትም
- የጎንደር ታሪክ - ያሬድ ግርማ ሐይሉ 1999 ዓ.ም
- የኢትዮጵያ ትንሳኤ ታሪክ - መሪ ራስ ኢም ኢ በላይ 1986 ዓ.ም
- የዓለም ታሪክ - አቶ ዮሐንስ ወልደማርያም 1936 ዓ.ም
- ስለ ቅዱሳት መፃህፍትና ሳይንስ ስምምነት - ዶ/ር ሙሪ ሬመር ትርጉም በንበቤ ማፊጠ 1953 ዓ.ም
- የኢትዮጵያ ታሪክ መነሻ - ፕ/ር ላጰሶ ጌ.ድሌቦ 1983 ዓ.ም
- ዋዜማ - ብላቴን ጌታ ህሩይ ወልደስላሴ 1921 ዓ.ም
- የኢትዮጵያ ታሪክ - አባ ጋስፓሪኒ ገብረማርያም 1948 ዓ.ም
- የኢትዮጵያ ታሪክ - ኑብያ/ናፓታ መርዌ/ 1ኛ መፃህፍ - ተክለፃድቅ መኩሪያ 1965
- መፅሐፈ አብርሂት - መሪ ራስ አማን በላይ 1999 ዓ.ም
- የኢትዮጵያ ህዝብ ታሪክ - አለቃ ታዬ
- ባለታሪክ ኢትዮጵያ - ነጋ ወልደስላሴ 1985 ዓ.ም
- የኢትዮጵያ አንድነትና ኢጣሊያ - ዶ/ር ተወልደ ትኩዕ 1989 ዓ.ም
- የኢትዮጵያ ስልጣኔ - በላይ ግደይ 1983 ዓ.ም
- የኢትዮጵያ አጭር ታሪክ - ብርሐኑ ድንቄ 1952 ዓ.ም
- አክሱም - በላይ ግደይ አምሐ 1995 ዓ.ም
- አክሱም ለምን? ልዩ እትም - ተክሌ ሐጎስ 2000 ዓ.ም
- የኢትዮጵያ ታሪክ አክሱም - ዛጉዬ 2ኛ መፃህፍ - ተክለፃድቅ መኩሪያ 1966 ዓ.ም
- ትቤ አክሱም መኑ አንተ? - አስረስ የኔሰው 1951 ዓ.ም
- የኢትዮጵያ ታሪክ ኑብያ - አክሱም - ዛግዌ - ተክለፃድቅ መኩሪያ 1951 ዓ.ም
- የኢትዮጵያ ታሪክ ጉዞ - ሽፈራው መንገሻ 42ኛው የቀ.ኃ.ስን.ኒ.መ
- የኢትዮጵያ ታሪክ ከንግስት ሣባ እስከ ታላቁ የዓድዋ ድል - ህሩይ ወ/ሰ 1921 ዓ.ም
- ቤተ እስራኤል በኢትዮጵያ - መ/ር አስረስ ያየህ 1989 ዓ.ም
- ጥንታዊ ስርዓተ ማህሌት ዘአቡነ ያሬድ - መሪጌታ ልሳነወርቅ ገ/ጊስ
- የኢትዮጵያ ታሪክ ከይኩኖ አምላክ እስከ ልብነድንግል - ተክለፃድቅ መኩሪያ 1966 ዓ.ም
- የፖርቱጋሎች ጀግንነት - ሚጉኤል ዲ.ካስታንሆህ - ትርጉም መራድ ከማልና ዮና በጋስ 1933 ዓ.ም
- የግራኝ አህመድ ወረራ - ተክለፃድቅ መኩሪያ 1966 ዓ.ም





- የኢትዮጵያ ታሪክ ከአፄ ልብነድንግል እስከ አፄ ቴዎድሮስ - ተክለፃድቅ መኩሪያ 1953 ዓ.ም
- ዝክረ ነገር - ማህተመስላሴ ወልደመስቀል 1962 ዓ.ም
- የኢትዮጵያ ታሪክ ከአፄ ቴዎድሮስ እስከ አፄ ኃይለስላሴ - ተክለፃድቅ መኩሪያ 1936 ዓ.ም
- አፄ ቴዎድሮስና የኢትዮጵያ አንድነት - ተክለፃድቅ መኩሪያ 1981 ዓ.ም
- አፄ ዮሐንስና የኢትዮጵያ አንድነት - ተክለፃድቅ መኩሪያ 1976 ዓ.ም
- አፄ ምኒልክና የኢትዮጵያ አንድነት - ተክለፃድቅ መኩሪያ 1983 ዓ.ም
- የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1847 እስከ 1983 - ፕ/ር ባህሩ ዘውዴ 2002 ዓ.ም
- የኢትዮጵያ የገባር ስርዓትና ጅምር ካፒታሊዝም 1900 እስከ 1966 - ፕ/ር ላጰሶ ጌ.ድሌቦ 1983 ዓ.ም
- አፄ ምኒልክ - ጳውሎስ ኞኞ 1984 ዓ.ም
- ዳግማዊ ምኒልክ - አፈወርቅ ገብረኢየሱስ 1901 ዓ.ም
- ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠነገስት ዘኢትዮጵያ - ፀሐፊ ትዕዛዝ ገ/ሴ 1959 ዓ.ም
- የዓለም ጀግኖች አጫጭር ታሪኮች - ዋለልኝ እምሩ 1997 ዓ.ም
- ክብረ ነገስት - የብራና መፅሐፍ
- አቡሻክር - የብራና መፅሐፍ
- ታሪክ ነገስት - የብራና መፅሐፍ
- የዮሐንስ መደብር - ዮሐንስ የኒቅዩ ኢጳስ ቆጶስ /ዜና እስክንድር/
- Plant and Planiet - Fredrhic T.Botton /Journal/ 1982
- The Arbs – David Lamb 1987
- A credil of Ethiopia History – Lapiso G. dillebo 1989
- A History Of Ethiopia (Nubia and Abssinia) – wall is budge – 1928 V.1
- World Book Encyclopedia V.14 1994
- Reise in Abissinia – Ruppel Edward – 1940
- National Geographic Magazine 1 February 2008
- Ancient Ethiopia – David W. Phillipson 1998
- The Dictionary of Ethiopian Biography V1 AAU 1975
- The Qemant – A pagan Hebraic Peasantry of Ethiopia – by Frederiche c. Gamst 1996
- Deustsche Axum Expedition - Eno Litman 1913
- History For young Ethiopian – 1974
- Ancient and medieval History & Ethiopia to 1270 A.A – Sergew H. Slassie 1972
- Aksumite Sites in Tigray (Ethiopia) The significance of their distribution, mhil dissertation – Tekle hagos 1997
- The periplus maris Erythrai. Princeton –Casson L. 1989

- Environmental History of early Aksum, new trends of Ethiopian studies, proceedings & twelfth international conference, V1.3,5 Bard. K 1994
- The Sign and The Seal – By Grham Hankok 1992
- The Ethiopian Royal Chronicles – edited by Richard K. P Pankhurst 1967
- Ethiopian in Brief – by yohhans petros 1979
- A Narrative Captivity in Abyssinia -- Dr Henry Blank 1868
- Ethiopia the Era of the Princes – By Mordechai Abir.
- Historia Rorum Islamitcar – Al Makires.
- Travels to Discover The Source of the Nile, In the Years 1768, 1769, 1771 and 1773 – James Bruce 1879
- Storia di Abissinia – Luca Deisabelli – 1936/37
- Lizicon Linguae Ethiopicae – A. Dillmann 1865
- Ethiopia through the ages – Nawal Kishore Sazeala 1968
- Etudes Sur Berbers, Ethiopienne etarabes – basset rene 1881
- Histoire'd Ethiopie Vòl.1 Jean morie 1929
- Storia d' Etiopia – conti Rossini 1904

“የጥንት ፈርኦኖች ኢትዮጵያውያንን አስገበርን በማለት ፋንታ ምስኪኖችን አስገበርን ብለው ነበር። አሁን ያ የማኮሰስ ቃል በፒያንኪ 2ኛ ተለውጧል። እናም እናንተ በሞት የምትኖሩ ደካሞች፣ ምስኪኖች፣ የምሽጋችሁን መዝጊያ ሳትከፍቱ ጥቂት ጊዜ ያለፈ እንደሆነ በሚደርሠው እልቂት ኃላፊዎች ትሆናላችሁ፤ ለሕይወት የከፈትኩላችሁን መዝጊያ አትዝጉ.....ሞትን አትምረጡ፣ በአገር ፊት ሕይወትንም አትናቁ።”

“ይህ በኔ ዘንድ ርካሽ ነው። እስረኛየን እንኳን በወርቅ እግር ብረትና በወርቅ ሠንሠለት ነው የማስረው በማለት ወደ እስር ቤቱ መልዕክተኞችን ወሰዶ አሳያቸው።”

“የጁልዩስ ቄሣር አማካሪዎች በማንም ተገዝታ የማታውቅ የኀበዝ አገር፤ ትልቁ የፋርስ ንጉሥ ካምቤዝ ተሸንፎ የተመለሰባት አገር ናት ብለው አስጠነቀቁት።”

ከመጽሐፉ የተወሰደ



ጋዜጠኛ ፍስሐ ያዜ

ሕትመት አልፋ አታሚዎች